# ዐፄ ምኒልክ እና
# የኢትዮጵያ አንድነት



በተክለ ጻድቅ መኩሪያ

# ዐፄ ምኒልክ

# እና

# የኢትዮጵያ አንድነት

444-1144
44-11-69

በ

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፫

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ TEL. 11 27 19
መ. ሣ. ቁ. P. O. x. 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል — ሥዩም ታደሰ (ቦሌ ማተሚያ ቤት)

በቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ

# ማ ው ጫ

አርእስት — ገጽ

መታሰቢያ .............................. 13
ማመልከቻ .............................. 15
መቅድም .............................. 17

ክፍል አንድ

የዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አገማመር

ምዕራፍ 1

የደጃዝማች ምኒልክ ከመቅደላ ማምለጥ—ከአቶ በዛብህ ጋር ተዋግተው ማሸነፋቸው—የሸዋ ንጉሥ መባላቸው .... 23

ምዕራፍ 2

የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ወሎ — ያፄ ዮሐንስ ዕረፍት መሰማት — ለምኒልክ የገቡላቸው መሳፍንትና መኳንንት 31

ምዕራፍ 3

የኢጣልያ መንግሥት ከውጫሌ ውል በፊት ካፄ ምኒልክ ጋር ያደረገው ስምምነት ................ 37

ምዕራፍ 4

የኢጣሊያ ጦር ከረንንና አሥመራን ስለመያዙ—በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ የውጫሌ ውል ..... 41

ምዕራፍ 5

የደጃዝማች መኰንን ጉዞ ወደ ሮማ—ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍራንቼስኮ ክሪስፒ ጋር ያደረጉት ስምምነት ..... 53

ምዕራፍ 6

የሹም ተምቤን ምርጫና የእንደርታው የባልጋዳ አርአያ ቤት 63

ምዕራፍ 7

የንጉሥ ምኒልክ ሥርዓተ ንግሥ — ወደ ትግሬ ያደረጉት ጉዞ — የራስ መንገሻ ላዒ ምኒልክ መግባትና በትግሬ የተደረገ ሹም ሽር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 69

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጠብ

ምዕራፍ 8

ከውጫሌ ውል ውስጥ 17ኛው አንቀጽ ያበቀለው ጠብ. . . 77

ምዕራፍ 9

አንቶኔሊ ያቀረበው የማስፈራሪያና የማባበያ ማስታወሻ ፍሬቢስነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 89

ምዕራፍ 10

ድርጎ በገጸ በረከት አንጻር . . . . . . . . . . . . . . . 97

ምዕራፍ 11

በ17ኛው አንቀጽ አለመሳካት የነአንቶኔሊ ወደ አገራቸው መመለስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 103

ምዕራፍ 12

የውጫሌ ውል በግራዝማች ዮሴፍና በግለኞች ላይ ያደረሰው ችግር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 109

ምዕራፍ 13

ከነአንቶኔሊ መመለስ ወዲህ የኢጣልያኖች አያያዝ — የራስ መንገሻና የዠኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ መስማማት 113

ምዕራፍ 14

የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ለማለያየት የተደረገ የፖለቲካ ዘዴ — ኢጣልያኖች መንገሻን ከድተው ወደ ምኒልክ እንደዞሩ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 125

ምዕራፍ 15

የነፊታውራሪ ጉልባኔ ኡዶሚ — የራስ መንገሻ ምሕረት ጠይቀውና ታርቀው ወደ ዐፄ ምኒልክ መግባት . . . 135

ምዕራፍ 16

የኮሎኔል ፍሬዲሪኮ ፒያኖ መላክና ምንም ፋይዳ ሳያገኝ ወደ መጣበት መመለስ . . . . . . . . . . . . . . . . 145

ምዕራፍ 17

የደጃች ባሕታ ሐጎስ ከኢጣልያኖቹ ጋር በኃይላ ተዋግተው መሞት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 153

ምዕራፍ 18

በኢትዮጵያ የተሠራጨው የኢጣሊያኖች የስለላ ሥራ. . . 161

ምዕራፍ 19

የዠኔራል ባራቲዬሪ ዓድዋ መምጣትና መመለስ — ራስ መንገሻና ኢጣልያኖች ኮዓቲትና ሰንዓፌ ላይ ያደረጉት ጦርነትና የራስ መንገሻ መሸነፍ . . . . . . . . . . . . 171

ምዕራፍ 20

የዤኔራል ባራቲዬሪ ሮማ ደርሶ መመለስ . . . . . . . . 179

ምዕራፍ 21

የደብረ ኃይላ ጦርነት . . . . . . . . . . . . . . . . . 183

ምዕራፍ 22

የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መሳፍንት ከፋፍሎ ለማስነሣት ያደረገው የመጨረሻ ሙከራና ያፄ ምኒልክ ያጸፉ መልስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 189

ምዕራፍ 23

ስለ ዋግሹም ብሩ መያዝ — ስለ መሐንዲሱ ካፑቺ መታሰር .......................... 197

ምዕራፍ 24

የኢትዮጵያና የመስኮብ ግንኙነት .............. 207

ክፍል ሦስት

የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት

ምዕራፍ 25

የክተት ዓዋጅ—የንጉሠ ነገሥቱ ጉዞ ወደ ትግሬ—ወታደራዊ ድርጅትና አቅዋም .................. 223

ምዕራፍ 26

በራስ መኰንን አዝማችነት ግንባር ቀደም የሆነው ጦር አላጌ ስለ መድረሱ—ራስ መኰንን ከጄኔራል ባራቲዬሪና ከማጆር ቶዜሊ ጋር የተጻጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ..... 241

ምዕራፍ 27

የአምባ አላጌ ጦርነትና ድሉ ................ 251

ምዕራፍ 28

የዳግማዊ ምኒልክና የሠራዊታቸው መቀሌ መግባት — የኢትዮጵያ ድርጅትና የጦር ኃይል ............ 265

ምዕራፍ 29

የመቀሌ ምሽግና ማጆር ጋልያኖ—ከኢጣሊያ አገር የሚላከው ጦርና በምክር ቤት የተደረገ ክርክር ...... 273

ምዕራፍ 30

የንጉሠ ነገሥቱ ጦር አሠፋፈር — በመቀሌ ምሽግ የመጀመሪያው ጦርነት ................... 283

ምዕራፍ 31

በመቀሌ ምሽግ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ጦርነት— ምሽጉን በሰላም ለማስለቀቅ የተደረገ ስምምነት ..... 287

ምዕራፍ 32

የመቀሌው ጦርነት በ[illegible] በኩል በ[illegible] ሰነድ — የማጆር ጋልያኖ ጦር ከመቀሌ ወደ አዲግራት መሔድ ...... 297

ክፍል አራት

የዓድዋ ጦርነት

ምዕራፍ 33

የኢትዮጵያ ጦር ከመቀሌ ወደ ዓድዋ መዛወር ስለ እርቅ ጉዳይ ማጆር ሳልሳ ተልኮ ወደ ዐፄ ምኒልክ እንደ መጣ .. 307

ምዕራፍ 34

የነራስ ስብሐት ወደ ኢትዮጵያ ጕራ መመለስ— የአንቶኔሊ ማስጠንቀቂያ — የኢትዮጵያ ጦር በሚዳ ፡ የኢጣሊያ ጦር በምሽግ ስውጊያ ስለ መፈላለጋቸው ............ 319

ምዕራፍ 35

የኢጣልያኖች ተታላይነትና የጄኔራል ዳቦርሚዳ ደብዳቤዎች .............................. 335

ምዕራፍ 36

የመጨረሻው የኢጣሊያኖች ተስፋ ልጅ ጉግሣ ዳርጌ ... 341

ምዕራፍ 37

የአውሳ ጦርነትና የመሐመድ አንፋሪ መሸነፍ ..... 345

ምዕራፍ 38

በኢጣሊያኖች ዘንድ የጦርነት ምክር— በሰላይ ተታለው ከምሽግ ወጥተው ለመዋጋት እንደ ቀረጡ ........ 355

ምዕራፍ 39

የዋናው ጦርነት አጀማመርና ፍጻሜ በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ........................ 365

ምዕራፍ 40

የኢጣሊያኖች የሌሊት ጉዞ—የግራው አዝማች ጦር መደምሰስ—[illegible] ጦር አበጋዝ የፊታውራሪ ገበየሁ አሟሟት—የጄኔራል አልቤርቶኒ መማረክ ............ 377

ምዕራፍ 41

የመጀመሪያው ብርጌድ ጦር ተዋግቶ ስለ መሸነፉ—የጄኔራል አሪሞንዲና የኰሎኔል ጋልያኖ ፍጻሜ ........ 389

ምዕራፍ 42

የቀኝ አዝማቹ የብርጌድ ጦር ተዋግቶ መሸነፍ—የጄኔራል ጕሴፔ ዳቦርሚዳ አሟሟት ................ 397

ምዕራፍ 43

የዳግማዊ ምኒልክ ከጦሩ ግንባር ወደ ሠፈር መመለስ .. 407

ምዕራፍ 44

በዓድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱትና የቆሰሉት 413

ምዕራፍ 45

የኢጣልያ ጦር መፍረስና ቅጥ ያጣ ሽሽት ........ 423

ምዕራፍ 46

ሌተና ጄኔራል አንቶኒዎ ባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ ምጥዋ እንደገባ — ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ስለ ዕርቅ ጉዳይ ወደ ምኒልክ እንደመጣ — ሌተና ሮቬርሲ ባይኑ የተመለከተው የኢትዮጵያ ሠፈር — የዕርቁ ለጊዜው አለመሳካት .... 431

ምዕራፍ 47

የዓድዋ ድል በኢጣልያና በአውሮፓ ተሰምቶ ያደረሰው ስሜትና ረብሻ ..................... 445

ምዕራፍ 48

የጄኔራል ባራቲዬሪ ፍጻሜ ................ 453

ምዕራፍ 49

በምክር ቤት የተነሣው ሁካታ—በሮማ የመንግሥት ለውጥ—ያዲሱ መንግሥት አዲስ ፖለቲካ — የክሪስፒ ፍጻሜ 459

ምዕራፍ 50

ዳግማዊ ምኒልክ መረብን አልፈው ያልሔዱበት ምክንያት ........................ 469

ምዕራፍ 51

የኢጣሊያ ወታደር በሆኑት ያገር ተወላጆች ላይ የተፈጸመው ቅጣት ........................ 477

ምዕራፍ 52

የምሥራች ለሙሴ ሞንዶን—የስሞታ ደብዳቤ ለሮም ጳጳስና ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ............... 485

ምዕራፍ 53

የኢጣሊያ ምርኮኞችና ወደ አዲስ አበባ ጉዟቸው ... 495

ምዕራፍ 54

የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ መመለስ—ያዲስ አበባው አቀባበል ........................ 501

ምዕራፍ 55

የእቴጌ ጣይቱ ምሽግ መለቀቅ ................ 509

ምዕራፍ 56

የመስኮብ የቀይ መስቀል ሐኪሞች አዲስ አበባ መድረስና ያበረከቱት የሕክምና አገልግሎት ............... 517

ምዕራፍ 57

ስለ ምርኮኞች ነጻነት የሮማ ሊቀ ጳጳስ ልዮን 13ኛና
ዳግማዊ ምኒልክ የተለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎች ...... 523

ምዕራፍ 58

ማገሮር ቄዛሬ ኔራሲኒ የመዋዋል ሥልጣን ተቀብሎ ወደ
አዲስ አበባ እንደ መጣ. .................... 531

ምዕራፍ 59

የጦርነቱ ኪሣራ ጥያቄ—በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል
የተደረገው ውል ......................... 537

ምዕራፍ 60

የምርኮኞቹ አኗኗር ፣ ስለነርሱ የተደረገው ስምምነት—ስለ
ወጣው የኪሳራ ገንዘብና የምርኮኞቹ አገራቸው መግባት 541

ምዕራፍ 61

ከዓድዋ በኋላ የኢትዮጵያ ነጻ መንግሥትነት በይፋ መደ
ላደል —የኃያላን መንግሥታት እንደራሴዎች ወደ አዲስ
አበባ መምጣትና ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ....... 549

ምዕራፍ 62

የራስ መንገሻ ዮሐንስ መከዳትና አንኮበር መታሰር .. 559

ምዕራፍ 63

ከውጭ መንግሥታት ጋር የተደረጉት ውሎች—የሦስቱ
መንግሥታት የክፍፍል ስምምነት ............. 565

ምዕራፍ 64

ዓድዋ ያስገኘው ዓለም አቀፋዊ ዕውቂያና የወሰን ስም
ምነት ........................... 571

## ክፍል አምስት

## ከዓድዋ በኋላ የልማት ሥራ አወጣጥን

ምዕራፍ 65

ለልማት ሥራ ተባባሪዎች .................. 575

ምዕራፍ 66

ባለሞያ ንጉሠ ነገሥት —ልዩ ልዩ የሥልጣኔ ውጥን .. 585

ምዕራፍ 67

የመገናኛ መስመር ፣ የምድር ባቡር ፣ የመንገድና የስልክ
ምዘርጋት—የአቶሞቢል መታየት ............. 593

ምዕራፍ 68

ያፄ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የቅርብ ግንኙነት 601

ምዕራፍ 69

የራስ ዳርጌ ፣ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የራስ መኰንን ሞት 607

ምዕራፍ 70

የዓድዋ የሰባተኛው ዓመት የድል በዓል አከባበር .... 615

## ክፍል ስድስት

## የንጉሠ ነገሥቱ መታመም

ምዕራፍ 71

ያፄ ምኒልክ በሕመም መውደቅ — የጀርመን ወኪሎችና
ሐኪሞች ችግር መፍጠር .................. 621

ምዕራፍ 72

የንጉሠ ነገሥቱ ሥጋትና ዝርዝር ምክር—የልጅ ኢያሱ
አልጋ ወራሽነት — የራስ ተሰማ ናደው እንደራሴነት. 629

ምዕራፍ 73

የመለያየት ስሜት—የዋግሹም አባተና የደጃዝማች አብርሃ ጦርነት ........................................ 639

ምዕራፍ 74

የራስ ቢቶደድ ተሰማና የእቴጌ ጣይቱ የሥልጣን ፍልሚያ —የእቴጌይቱ ከሥልጣን መወገድና የራስ ተሰማ ዕረፍት 647

ምዕራፍ 75

በየግዛታቸው ያሉት ባለሥልጣኖች — የወጣቱ የልጅ ኢያሱ ሥልጣን አያያዝ—የራስ አባተ ተቃውሞና እስራት—ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ቀኛዝማች ደቻሳ... 651

ምዕራፍ 76

የደጃዝማች ሥዩምና የራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ጠብ 659

ምዕራፍ 77

ያፄ ምኒልክ ዕረፍት ........................ 665

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የነበሩ መኳንንትና መሳፍንት ........................ 695

ዋቢ መጻሕፍት ..... ................... 705

# መታሰቢያ

ከማሳደግ ጋር የመዠመሪያውን ፊደል ሀሁ...ን በንባብ እንድ ዠምርና በጽሕፈት እንድሠማራ ያደረጉኝን አባቴን ደብተራ መዙሪያ ጉልቴንና የመዠመሪያውን መምህሬን የኔታ ስብሐት ለአብን ፤ (1912—1918)

በሥጋ ሳልወለደው ከአማርኛና ከዜማ ትምህርት ቤት አውጥቶ ዘመናዊውን የመዠመሪያውን የፈረንሳይ ትምህርት ቤት በአሊያንስ እንድዠምር ያደረገኝን በጅሮንድ መንገሻ ገብረየስን ፤ (1919—1920) ከአባቴ ጋር ባላቸው የዝምድና ሰበብ በቤታቸው አስቀምጠው ቀለብ ቆርጠው በጸሐፊነት ሙያ እንድሠለጥን የፈቀዱልኝን ክቡር ቢቶደድ ወልደ ጻድቅ ጉሹን (1921—1926)

ያገር ነጻነት በ1933 ዓ.ም. ከተመለሰ ወዲህ በትምህርት ሚኒስቴር በ1934 ዓ.ም በመንግሥት ሥራ በተሠማራሁበት ወቅት ከደንበኛው ሥራዬ ጐን የደራሲነት ሙያ በፈቃዴ ስወጥን ፣ በቅንነት እርዳታቸው ያልተለየኝን ክቡር ደጃዝማች መኰንን ደስታን ፤ (1944—1949) እያመሰገንሁ ፤ የዚህን መጽሐፍ መታሰቢያነት ሰጥቻለሁ ።

ተ.ጸ.መ.

# ማመልከቻ

ቅኝ አገር ፈላጊዎች አውሮፓውያን፣ ከራሳቸው አልፈው ሌላውን ያልሠለጠነውን አገር በሚወሩበት መስመር ፣ የብዕር ሰዎቹ ደግሞ የራሳቸውን አገር ታሪክ ጽፈው ከአገባደዱ በኋላ ፣ የሌላውን ወደኋላ የቀረውን አገር ታሪክ በየመስኩ እየጻፉ ማራባታቸው ግልጽ ነው ። በኢትዮጵያም በሌላው የሥራ ዘርፍ ወደኋላ እንደ ቀረን ሁሉ ፣ ፊደል እያለን በሥነ ጽሑፍ ረገድ አልተራመድንም ።

ስለዚህ ፈረንጆች የኛን የመሬት መልክዓ ምድር ተራራውን ፣ ወንዛ ወንዙን ፣ ባሕሩንና ደሴቱን ከፖለቲካውና ከጦርነቱ ጋር ፤ የቤተ ክህነቱንና የቤተ መንግሥታችንን ታሪክ እኛ ባለቤቶቹ ያልጻፍነውን ወይም በተወሰኑ ሊቃውንት ባጫጭሩ በግዕዝ ተጽፎ በየገዳማቱ ፣ በየቤተ መንግሥቱ የተቀመጠውን የገዛ ታሪካችንን እነሱ ተፈላልገውና ተመራምረው በየቋንቋቸው ተርጒመው ፣ በጽሑፍ አስፍረውታል ። በማኀተም አራብተው ለዓለም ከማሳወቅ ጋር እኛንም የገዛ ታሪካችንን ያስተምሩናል ። በዚህ የመማር ዕድል ያለው የውጭ አገር ቋንቋ ዐዋቂው ብቻ ነው ። የኛንም ታሪክ በደንብ ለመመርመር የሚችለው ጽሑፋችንን ለማንበብና በቋንቋችን ለመናገር የቻለው ነው።

በዕውቀትና በልማት ልዩነት የተነሣ ፣ አንድ ኢትዮጵያዊ የእንግሊዝን ወይም የአንዱን አውሮፓዊ አገር ታሪክ ለመጻፍ ቢነሣ ያልቀባለ ወይም ያልተገለጸ ነገር ካለማግኘቱ ጐን አነሣሡ እንደ ከንቱ ድፍረት ይቆጠራል ። አንድ የውጭ አገር ሰው ያንዱን የአፍሪካ አገር እንዲሁም የኢትዮጵያን ታሪክ በሙሉ ወይም በከፊል ቢጽፍ አግባብ ሆኖ ይገኛል ። ተወላጆቹም ማንበብና ማድነቅ የሚመርጡት ከራሳቸው ተወላጅ ይልቅ የርሱን ነው ። በዚህ ምክንያት ስለ አፍሪካም በጠቅላላው ፣ በተለይም ስለ አገራችን ታሪክ የፈረንጆችን መጽሐፍ ማንበብና መጥቀስ ውዴታም ግዴታም ከሆነ ጊዜው ሩቅ ነው ። ስለዚህ ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ብንሆንም ፣ እንደ ኢኮኖሚው ሁሉ በሥነ ጽሑፍም ረገድ ከጥገኝነት ነጻ አልወጣንም ማለት ነው ። ባሁኑም ጊዜ ዐውቀን ያገር ፣ የባህል ፣ የወገንነት ተቆርቋሪነትና ፍቅር አድሮብን መከላከሉን ካላወቅንበት ቋንቋቸው ቋንቋችንን ፣ ፊደላቸው ፊደላችንን እያደር ከመጫንና ከማደብዘዝ ላይ ይገኛል ። ወጣቶቻችን የራሳቸው

ቋንቋ ሳያጡ ንግግር በሚለዋወጡበት ጊዜ ቢያንስከ 10 እስከ 20 በመቶው ያህሉ እንግሊዝኛ ነው ። በባንክ ፣ በዩኒቨርስቲ ፣ በመገናኛ ፣ በሐኪሞች አካባቢ ውዴታም ፣ ግዴታም ተጨማምሮ እንግሊዝኛው ጽሑፍ ያማርኛውን ጽሑፍ ከዕለት ወደ ዕለት ሲተካው ይታያል ።

አገራችን ከፋሽስት ወረራ ነጻ ከወጣችበት ጊዜ ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ከዕለት ሥራዬ ጐን የጻፍሑዋቸው መጻሕፍት በእንግሊዝኛው ፋንታ ለትምህርት ቤት ተመድበው አገልግሎት ማበርከታቸው የታወቀ ነው ። አሁን ደግሞ ፣ ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ጡረታ በመገለል የበቃ ጊዜ ስለአገኘሁ ፣ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ በሦስት ቅጽ የተከፈለውን ለማዘጋጀት ረዳኝ ። ከነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ፣ "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" ሁለተኛው ፣ "ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት" በሚል ሥያሜ ታትመው የመሠራጨት ዕድል አግኝተዋል ። በነዚያው ዓይነት ይኸው ያሁኑ መጽሐፍ "ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት" የሚለውን አርእስት እንደያዘ ታትሟል ።

በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር (እ. ኤ. አ.) ተብሎ ከተለየው በቀር ፣ የቀረው ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር መሆኑን አመለከታለሁ ።

መስከረም 30 ቀን 1983 ዓ.ም.

ደራሲው



# መቅድም

በዘመነ መሣፍንት ፣ የሥልጣን ሽሚያ ሲደረግ ማንኛውም በዚህ እድገት ደረጃ ይገኝ የነበረ መንግሥት እንዳጋጠመው ሁሉ ፣ ባገራችን የአንዱ አካባቢ ገዥ ሌላውን ለማስገበር ፣ አንዱ ሁለተኛውን ከዶ ከሌላው ጋር በማበር ሥልጣን በእጁ ለማስገባት ሲል ብዙ ውጣ ውረድና ጦርነቶች አጋጥመዋል ። ይህ የሥልጣን ሽሚያ ያስከተለው የእርስ በርስ ጦርነት የውስጥ መዳከምን ከማስከተሉም ፣ በተጨማሪ የውጭ ወራሪዎች ወዳገራችን አሰፍስፈው ለመግባት ሁኔታው እንዲመቻችላቸው አድርጓል ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በትረ መንግሥት ከመጨበጣቸው በፊትና ከጨበጡም በኋላ ፣ የሹመት አባቶቻቸው የጀመሩትን የተለያዩ አውራጃዎችን መልሶ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማጽናት ብዙ ደከመዋል ። በዚህም ጥረታቸው ተቀናቃኝ የአውራጃ ገዢዎችን ይነስ ይብዛ በሰላማዊ መንገድና አልፎ አልፎም እምቢተኝነት ያሳዩትን ገዢዎች አስገድደው በማስገበር ጅምሩን ከግብ ለማድረስ በቅተዋል ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት ባገራችን ቀደም ብሎ የተጀመረው የሥልጣን ሽሚያ ያስከተለው የእርስ በርስ ጦርነት የማዕከላዊ መንግሥት በመዳከሙ የተነሣ አገሪቱን ቅኝ አድርጎ ለመያዝ ምኞት ለነበራቸው የውጭ ወራሪ ኃይሎች አመቺ አጋጣሚ እንደ ፈጠረላቸው ከነበረው ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል ። የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ለመቀራመት የተነሡበት ዘመን ስለነበር ፣ በኢትዮጵያም እነዚህ ቅኝ ገዢዎች በወኪሎቻቸው አማካይነት አንዱን ወገን ለጊዜው ደግፈው በሌላው ላይ በማስነሣት ፣ በወቅቱ ሥልጣንን ለመያዝ እጅግ ተፈላጊ የሆነውን የጦር መሣሪያ እንደ ገጸ በረከት በማቅረብ አንዱን ሲያነሡ ሌላውን ሲጥሉ ፣ ለአንዱ ሲታመኑ ሌላውን ሲክዱ ፣ በአንዱ አካባቢ ተሰሚነት ሲያጡ ወደሌላው ሲያቃኑ በፈጠሩት ችግር አገራችን ከባድ ፈተና ላይ ወድቃ ነበር ።

አውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች በፈጠሩት ምስቅልቅል ሁኔታ የተነሣ በግዛት አንድነቷና ለረዥም ዘመን ተጠብቆ በቆየው ነጻነቷ ላይ አደጋ ሲያንዣብብበት ታይቷል ። በዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ

እጅግ ረዥም በሆነው ታሪኳ ውስጥ አጋጥሟት የማያውቀው ገሀድ
የሆነ የግዛት መደፈርና የውጭ ኃይል በግዛቷ ሰሜናዊ ክፍል መቆና
ጠጥ የበቃው በዚህ በዘመነ ቅኝ ግዛት ሽሚያ ወቅት ነበር ። ይህም
በኢትዮጵያ ላይ ብቻ የታየ ክስተት አይደለም ።

ያለፈውን የዓለም ታሪክ አገላብጠን ስናነበው የፋርስ ፣ የባቢሎን ፣
የግሪክ ፣ የሮማ ፣ የዓረብ ፣ የቱርክ ፣ የቄሳር ግዛቶች በጦርነቱ ተንኰታ
ኩተው ይዘውት የነበረውን ሰፊ ግዛት አጥተዋል ። እንደዚሁም ጥንት
በብርታቱም ሆነ በግዛቱ ስፋት ገናናነት የነበረው የኢትዮጵያም መን
ግሥት ከመካከለኛው ዘመን ዠምሮ በተስፋፊዎችና በአውሮፓ ቅኝ
ገዢዎች ሤራ መከፋፈልና መዳከም አጋጥሞታል ።

ካፄ ቴዎድሮስ ዠምሮ እስከ ዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ
ባገራችን ለመግባት ካሰፈሰፉት የውጭ ወራሪዎች መካከል ቀንደኞቹ
ግብጾችና ኢጣሊያኖች ናቸው ።

በዐፄ ቴዎድሮስ የተደከመበትና በዐፄ ዮሐንስ የተጣረበት የኢ
ትዮጵያን አንድነት የማጠናከር ዓላማ በዐፄ ምኒልክ ይበልጥ ለፍሬ
በቅቷል ። በዐፄ ምኒልክ ዘመን የኢትዮጵያን አንድነት በማጠናከር
ረገድ ከፍተኛ ውጤት የታየ ቢሆንም ፣ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ዐፄ
ዮሐንስ መተማ ላይ የወደቁበትንና ምኒልክ የተተኩበትን የሽግግር
አጋጣሚ በመጠቀም የሀገሪቱን የቀይ ባሕር ጠረፍ "ኤርትራ" በሚል
ሥያሜ በመያዝ የፈጠሩትን ችግር ማስወገድ በወቅቱ አለመቻሉን
በመጽሐፉ ውስጥ በስፋት ተተንትኗል ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚነበበው ታሪክ ከመቅደላውም
ውጊያ ፣ ከግብጾችም ጦርነት የበለጠ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል
ከዶጋሊ ዠምሮ በኰአቲት ፣ በሰንዓፌ ፣ በደብረ ኃይላ ፣ በአምባ አላጌ ፣
በመቀሌ ፣ በዓድዋ የተካሔደው ጦርነትና ከዚያም ወዲህ የታየውን የሰ
ላም ፣ የዲፕሎማሲ ፣ የልማትና የአንድነት ትግል ነው ። ሁለቱ አገሮች
በአህጉርና በባሕር የተለዩ ፣ በዘር ፣ በባህል ፣ በቋንቋ የማይገናኙ ሆነው
ሳለ አንደኛውን ከሩቅ አገር የግዛት ምኞት ስቦት ፣ ሁለተኛውን የአ
ገሬን ነጻነት እጠብቃለሁ የሚል ቅዱስ ቅናት አነሣሥቶት በመጋጨ
ታቸው ብዙ ደም ተፋሰዋል ። ለሁለቱም አገሮች በባህልና በልማት
መስክ ሊያገለግሉ የሚችሉ ብዙ ተወላጆች በየጦሩ ሜዳ ወድቀው
ቀርተዋል ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሀብት ባክኗል ።

በሁለቱ ወገን ለሞተውም ፣ ለጠፋውም ሀብት ኃላፊዎች ኢጣ
ልያኖች ናቸው ። ኢጣሊያኖች ነጻነታቸውን ከአቋቋሙ በኋላ ፣ ባገራ
ቸው የሚያርሱት ለም መሬት ሳያጡ የሚበላው ፣ የሚለበሰው በገዛ



አገራቸው እያላቸው ፣ ራሳቸው ተሟልተው ሳይሠለጥኑ ኢትዮጵያን እና
ሠለጥናለን በሚል የሐሰት ምክንያት ወዳጅ መስለው እንደ ድመት
ተስበው ከማድባት ጋር በእንግሊዝ ተደግፈው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ።

የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ፡ ምጥዋን ከያዙ ጀምሮ የሚሰጡት ምክ
ንያት ዥጉርጉር ነበር ። አንድ ጊዜ ፣ "የመጣነው በእንግሊዝና
በኢትዮጵያ ፈቃድ ነው" ሲሉ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ደግሞ ፣ "መች ፈቀ
ድሁና" ስለአሉ ፣ "የለም የኛ አመጣጥ ወደቡን ብቻ ይዘን በወዳጅነት
ንግድ ለማስፋፋት ነው" አሉ ። በሚቀጥለው ባፄ ምኒልክ ጊዜ ደግሞ ፣
"የበረሀው ሙቀት ስላስቸገረን ወደ ደጋው ክፍል ለመሥፈርና የበጋ
ውን ጊዜ ለማሳለፍ ይፈቀድልን " ብለው ለመኑ ። በመጨረሻ
ደግሞ ፣ የቅኝ አገር ፍላጎታቸውን መደበቅ ሲያቅታቸው ፣ "የለም እው
ነተኛው ዓላማችን የመላዋ ኢትዮጵያ የበላይ ሆነን ሕዝቡን ለማሠል
ጠን ነው " በማለት ሰበባቸውን ከዕለት ወደ ዕለት እየቀያየሩ ፣ ወደ
ትልቁ ወደ ተዋረዱበት ወደ ዓድዋው ጦርነት ሊደርሱ ቻሉ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቸስኮ ክሪስፒ ፣ ይኸን የመሳሰለውን እያፈ
ራረቀ ሲያቀርብ የራሱ ትውልድ አገር ሲቺሊያ ፣ ፈደል ያልቆጠረ
ባላገር የመላበት ፣ ለም መሬትና በረሀው ክልማት የራቀ የወንጀለኛ
ሠፈር ነበር ። አሁንም እንኳን ከዘጠና ዓመት በኋላ በማፊያ ስም
የሚጠራው የወንጀለኛ ጕሬንነቱ በዓለም የታወቀው ይኸው ሲቺሊያ
ነው ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብዙ የኢጣሊያ ታላላቅ መማክርት በሰው
ልጅ ትክክለኛ መብትና ነጻነት የሚያምኑት ሲመክሩትና ሲያወ
ግዙት ራሱን እንደ አገር አፍቃሪ ፣ እነርሱን ላገራቸው እድገ
ትና ገናናነት እንደማያስቡ እያደረገ ይወነጅል ነበር ።

ወደፊት በየምዕራፉ በዝርዝር እንደምናነበው ፣ ክሪስፒ መንፈሱ
በሙሉ በቅኝ አገር ምኞት ላይ ስለ ተመረዘ ያገሩን ሰዎች ምክር
መስማት አልፈለገም ። ባለፈው ዘመን በብዙ ጦርነት የተዳከመውን
የሕዝባቸውን ሕይወት ከጦርነት ለማዳን አጥብቀው ሰላም የፈለጉት
ዐፄ ምኒልክም በበኩላቸው የሚያቀርቡለትን የሰላም ጥሪ ወደ
ፍርሃት በመተርጐም ከምጥዋ እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ወታደሩ
እንዲገሠግሥ ሲያደርግ ፣ ለጠቅላይ አዛዡ ለጄኔራል ባራቲዬሪ
ቀደም ብሎ የሰጠው መመሪያ ፣ "የትግራይ ግዛት ለኢጣሊያ ክፍት
ነው ፣ ሳንይዘው ብንቀር የኛ ስንፍና ነው" የሚል ነበር ።

ዐፄ ምኒልክ ሙሉ የሕይወታቸው ታሪክ ሲነበብ ፣ አገራቸውን
ለማሠልጠን ከሁሉ በፊት የሥልጣኔ ባለቤት ከሆኑት ፈረንጆች ጋር
መቀራረብ ፣ ባገር ውስጥ ያለውን ልዩ ልዩ ሃይማኖት የያዘውን ክርስ

ቲያኑንም ፤ እስላሙንም ፤ ልዩ ልዩ ነገዶችንም አስተባብረው ባንድ እግር በማቆምና በማሠልጠን ወዳንድ ወደ ታወቀ የሰላም አኗኗር ለመምራት መሆኑ ይታያል ። ስለዚህ ቀደም ብለው ከፈረንሳዮቹም ፤ ከኢጣሊያኖቹም ፤ ከመስኮቦቹም የተወዳጁት ፤ "በነርሱ በኩል መምህራን አግኝቼ አገሬን አሠለጥናለሁ ፤ ከነርሱ የጦር መሣሪያ ገዝቼ በዚህ መስመር የሚነሣብኝን ጠላቴን በመደምሰስ መንግሥቴን አጠናክራለሁ" የሚል ምኞት እንደ ነበራቸው ግልጽ ነው ።

በዚሁ ጊዜ ፤ ካፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዠምሮ ካገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚቀሰቀስ ማናቸውንም ጦርነት የሚያስከትለውን መከራና ፍዳ ፤ ዋይታና ሰቆቃው በመገንዘብ ጦርነት የሚወገድበትን ፤ ሰላም የሚገኝበትን መንገድ አጥብቀው ሳይሹ ፤ ለውጊያ የተዘጋጀውን ባላጋራቸውን ሳይመከሩና ሳያባብሉ ፤ በቀላሉ ለማሸነፍ የሚያስችል ጉልበት እንዳላቸው ቢያውቁትም ፤ በማን አለብኝ ወይም በግልፍታ ፤ በኩራት ወይም በትምክህት ተዋግተው አያውቁም ። ከዚህም የተነሣ ከመቅደላ አምልጠው ከወጡ ዠምሮ (1857 ዓ. ም.) በሕመም ወድቀው እስከ ሞቱበት እስከ 1906 ዓ. ም. ድረስ ዐፄ ምኒልክ በርከት ያሉ ጦርነቶች ሲያደርጉ ዕድላቸው ሆኖ ባንዱም የጦር ግንባር ተሸንፈው አያውቁም ።

የኢጣሊያ መንግሥት ፤ መላ ኢትዮጵያን በበላይነት ካልገዛሁ ብሎ በተነሣበት ሰዓት የጦር መሣሪያውን ራሱ የሚሠራ ያንድ አውሮፓዊ መንግሥት ኃይል ከባድነት እንዳለው ዐፄ ምኒልክ ተረድተውታል ። ኢጣሊያን ከጐበኙት ከራስ መኰንንም ፤ ከየፈረንጁም በደንብ ሁኔታውን አጢነውታል ። ስለዚህም ጦርነቱን ለማስቀረት በብዙ አንጻር ሞክረው ፤ ሙከራቸው ፍሬ ቢስ ሆኖ የኢጣልያ ጦር የራስ መንገሻን ጦር አሸንፎ ፤ ትግሬን በመላ ወርሮ አሸንጌ መድረሱን ሲሰሙ ፤ ወደ ጦሩ ግንባር ጉዞ ከመዠመራቸው በፊት ያደረጉት ቀጥሎ ያለው የክተት ዐዋጅ በራሳቸው መተማመናቸውን ላገራቸው ለመሠዋት መቁረጣቸውን ይገልጻል ።

> "... እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አኖረኝ ... እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና አላዝንም ። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም ። እንግዲህም ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም ..."

እውነትም እንደ ድመት እያደባም ፤ እየተወረወረም እስከ አሸንጌ ሐይቅ በገሠገሠው ጠላታቸው ላይ በእርሳቸው የሚመራው ጦር እንደ አንበሳ ተቆጥቶ በአላጌም ፤ በመቀሌም በተለይ ዓድዋ ላይ የፈጸመው የዠብዱ ሥራ ኢትዮጵያን ያኰራ ፤ ኢጣልያንን ያሳፈረ ፤ ዓለ



ምን ያስደነቀ ፤ የኢጣሊያን የዚያን ጊዜ ወዳጆች ጀርመኖችንና እንግሊዞችን ያስቆጨ ሆኖ ተገኘ ። የኢትዮጵያ ድል አድራጊነት የራሷ ብቻ ሳይሆን ፤ የአፍሪካና የእስያ ተወላጅ ሁሉ ድል እንደ መሰለ ተሸናፊም ኢጣሊያ ብቻ አልሆነችም ። ቅኝ አገር ያላቸውም ፤ የሌላቸውም አውሮፓውያን በዚህ ጦርነት አብረው እንደ ተሸነፉ ቆጥረውታል ። ነጭ የማይሸነፍ ነው ተብሎ እስከዚህ ጊዜ ድረስ የታመነውም በዚህ ጊዜ ተባበለ ።

እላይ እንዳልነው ፤ ከመዠመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ የባልካን አገሮች ፤ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ አፍሪካውያን ነጻነታቸውን አግኝተዋል ። ኢትዮጵያም በሠለጠኑት አውሮፓውያን ዘንድና በዓለም ዘንድ በይበልጥ የታወቀችው ፤ ቀድሞ ገሸሽ እያደረጉዋት በመናቅ ስሜት የቆዩት የአውሮፓ ኃያላን በአዲስ አበባ ሌጋሲዮን ከፍተው ሙሉ የዲፕሎማሲ ዕውቂያ ያደረጉላት ፤ የድሉን ኮከብ በዓለም ሰማይ ላይ ካበራው ከዓድዋ ድል በኋላ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ በጦር ሜዳ ድል ማድረጋቸውና ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ መታወቃቸው ጉልህ የሥራ ውጤት ነው ። ይሁን እንጂ ለነጻነት ዘለቄታ ዋስትና የሚሆነው እንደ ሠለጠኑት አገሮች ሠልጥኖ መገኘት መሆኑን በደንብ ስለተገነዘቡ ፤ ከዓድዋ በፊት የወጠኑትን የልማት ሥራ ከዓድዋ በኋላ እንደ ተመኙት ሳያገባድዱ በመካከሉ እርጅና ፤ ሕመምና ሞት ተከታትለው ቀደሟቸው ። ከዓድዋ ድል በኋላ የሰላምና የጤንነት ዘመን ተጐናጽፈው ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያን ምን ያህል ሊያራምዷት በቻሉ ነበር ።

ዳሩ ግን ፤ በዕድሜያቸው በሁሉ አንጻር የታደሉት ንጉሠ ነገሥት ጠባያቸውን ከነችሎታቸው ወርሶ ምኞታቸውንና የሥራ ውጥናቸውን ወደ ፍጻሜ የሚያደርስ አልጋ ወራሽ በማግኘት ረገድ አልታደሉም ። በዓለም ያሉ አብዛኞቹ የታላላቅ መሪዎች ዕድል በዚህ በኩል ተመሳሳይ ነው ። ነገሥታትና መሪዎች የሞት ሽታ ሲሰማቸው ፤ በሕይወታቸው ዙፋናቸውን ለወደዱት ወይም በዘር ወራሽነት ለሚገባው በኑዛዜ ማውረስ ሲችሉ ፤ የነበራቸውን ገናናነትና ችሎታ ለወራሽ የመተው ዕድል ሳያገኙ በድኑ ሥጋቸው ስሙን ብቻ ለወገኑና ለዓለም አውርሶ ፤ ተመልሶ ለመውጣት ወደማይችልበት ወደ መቃብር ይወርዳል ።

ተ. ጸ. መ.

# ክፍል አንድ

## የዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አጀማመር

## ምዕራፍ አንድ

### የደጃዝማች ምኒልክ ከመቅደላ ማምለጥ — ካቶ በዛብህ ጋር ተዋግተው ማሸነፋቸው — የሸዋ ንጉሥ መባላቸው

ምኒልክ በነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም. አንጐለላ ኪዳነ ምሕረት ተወልደው፣ ካባታቸው ከንጉሥ ኃይለ መለኮትና ከእናታቸው ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር በአንጐለላ ፣ በአንኮበርና በደብረ ብርሃን እየተዘዋወሩ ቆይተው በኋላም የሕፃንነትና የወጣትነት ጊዜያቸውን በጐንደርና በደብረ ታቦር ካፄ ቴዎድሮስ ጋር እንደ ልጅም ፣ እንዳማችም ሆነው አሳልፈዋል ።

ወደኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ፣ ምኒልክ ካፄ ቴዎድሮስ ጋር የአማች ባለሟል ሆነው ከቆዩ ወዲህ በመጨረሻ የመጋዙ ጽዋ ለርሳቸውም ደርሶ ነበር ። ሁኔታው ሲገመገም ግማሽ ግዞት እንጂ እንደ ሌሎች ግዞቱ በርሳቸው ላይ የጠበቀ እንዳልነበረ ይታያል ። ለማምለጥም የረዳቸው ይኸው የግዞቱ መላላት ሳይሆን አይቀርም ። ቢሆንም ፣ ባፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዎቹ ዓመታት (1856—60 ዓ.ም) ሁኔታው እስከፊ እየሆነ ሲሔድ ፣ ከምኒልክ ጋር አብረዋቸው ያሉት የሸዋና የቤጌምድር መኳንንት ለርሳቸው ሕይወት እጅግ በማሰብ በተለይ እነ አቶ ገርማሜ ወልደ ሐዋርያት ፣ አቶ ሀብተ ሥላሴ ደስታ ፣ ሞግዚታቸው አቶ ናደው* (ደጃች) ፣ አቶ ወልደ ገብርኤል** (ደጃች) ከእናታቸው ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር ውስጥ ለውስጥ የሚያመልጡበትን ዘዴ ሲያወጡ ሲያወርዱ በሰነበቱበት ጊዜ፣ የዚህን ምስጢር ለባለቤታቸው ለወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ የደበቋቸው ይመስላል ።

---

* የራስ ተሰማ አባት

** ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን የራስ ብሩ አያት

ስለዚህ ፣ ምቹ ጊዜ ሲመርጡ ቆይተው በሰኔ 24 ቀን 1857 ዓ.ም ቅዳሜ ለት ማታውኑ አቶ ገርማሜ (በኋላ ደጃዝማች) በቴዎድሮስ ትእዛዝ ካገቧቸው ከወይዘሮ ቀጠሮና ከአቶ ሀብተ ሥላሴ ደስታ ጋር ታላቅ የወዳጅነት ግብዣ አድርገው የጥበቃ ሹማምንቱንም ፣ ወታደሩንም በግብዣው ላይ በመጠጥ አሰከሩዋቸው ። ጠባቂዎቹ በጥልቅ እንቅልፍ በተዋጡበት ሌሊት ፣ ጐልማሳውን ምኒልክን ይዘው ከመቅደላ በአሊ በር በኩል አምልጠው ወረሂመኑ ግዛት ገቡ ። ባላባቷ ወይዘሮ ወርቂት ቀደም ብለው ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ጋር ወዳጅነት ወጥነው ስለነበር ፣ "ያባት ወዳጅ ለልጅ ይተርፋልና መጣሁ ተቀባይም ስደጅልኝ" ብለው ላኩባቸው ። እርሳቸውም ባንድ ወገን ወደ ምኒልክ ተቀባይ ልከው በነዚሁ ሰዎቻቸው አማካይነት ምኒልክን እያስጠበቁ ፣ በሌላ ወገን ከይማም አባ ቡላ የወለዱት ዓመዴ ዐሊ የሚባለው ልጃቸው ቀደም ብሎ ዓፄ ቴዎድሮስ ክርስትና አንሥተውት ሳለ ፣ በኋላ እርሱንም እንደ ምኒልክ በጥርጣሬ አስረውት በመቅደላ ነበርና ወርቂት በምኒልክ ለውጥ ልጃቸውን ለማስፈታት አስበው "ምኒልክን አስሬ ላላክልዎትና ልጄን ዓመዴ ዐሊን ይላኩልኝ" ብለው ወደ ቴዎድሮስ ላኩ ። ልጅየው ግን ቀደም ብሎ መገደሉን አልሰሙም ነበር ።

የምኒልክን ማምለጥ ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ሰሙ ፣ "ለምን አልጣሽን ትቷት ሔደ" አሉ ይባላል ። ይኸውም ማለት ከምኒልክ ማምለጥ የልጃቸው አብሮ አለማምለጥ የቆጫቸው ይመስላል ። ምንአልባት ምኒልክ ወደፊት እንደሚነግሡ ታይቷቸው ልጃቸው ከምኒልክ ጋር አብረው እንዲነግሡ በመመኘትም ይሆናል ።

ምኒልክን ተቀብለው የሸኟቸውም የወሎ መኳንንት ናቸው የሚል አስተኛ ወሬ ስለሰሙ ፣ ቴዎድሮስ በብስጭት ቀደም አድርገው ብዙ የወሎን መኳንንት ከወርቂት ልጅ ጋር ገደል እያስገፉ ገድለው ነበር ። የዚህን ጉዳይ በዚያው የነበሩት አለቃ ወልደ ማርያም እንደዚህ ሲሉ ገልጸውታል ። "የሸዋን ሰው እናትዎን* ይዘው ወጡ ። ሲነጋ ኩታማ በሚባል ፈረስዎ ንጉሡ (ቴዎድሮስ) ተቀምጠው ወደ እስር መንደር መጡ ። በዚያም ጊዜ እጅግ ተናደው ነበርና 'እስሩን (እስረኛው) ሁሉ አውጡ' አሉ ፣ 'የወርቂት ልጅ ማናቸው ነው' ብለውም ጠየቁ ። ሰዎቹም የክርስትና ልጅዎ (ልጃቸው) ነበርና ይምሩታል

* ምኒልክን ማለታቸው ነው ። በአክብሮት አነጋገር 'እናትዎን ' ይዘው ወጡ ማለት 'እናታቸውን' ለማለት ነው ። የቀድሞ ጸሐፊዎች የሚያከብሩትን ሰው በሁለተኛ ሰው እንጂ በሦስተኛ ሰው አይናገሩም ።



ብለው ፈጥነው አሳዩዎ (አሳዩዋቸው) ። እርሱም እኔ ልጅዎ ነኝ በነገ ዝምበር (በጧት)ግብርዎን ላግባ ዛሬ ያሳድሩኝ (ግብርዎን ላግባ ልገዛ አይግደሉኝ) አለ ። በዚህ ጊዜ በንጉሡ ልብ ምሕረት አል ነበረምና እርሱን በፊት ለፊት ከርሱም ጋር የነበሩ 24 የኦሮሞ መኳንንት እነ ፋሪስ ቃሲምን ፣ እነ ዐሊ ወዳጆን ራቁታቸውን እያስጎተቱ ከመቅደላ ገደል አቀረቧቸው ። እግርና እጃቸውን በጐራዴ እያስቆረጡ ሁሉንም ገደል ሲያስጥሉ አንዱ ባለመንቆር (የእንጨት እግረሙቅ) ከገደሉ ሲቀርብ ሞተ ። ሰዎችም አይተው 'ይህ ሰው ሞቷል' ቢሉ 'ከንንጨቱ ገፍተህ ጣለው' ብለው ቢጥሉት ከገደሉ ላይ እንጨቱ ይዞት ተንጠለጠለ ። ከዚያም ላይ እንዳይቀር 'በደንጊያ አሶርደው ' ብለው ተሰባብሮ ወረደ[1] ።"

ይህ ከሆነ በኋላ ፣ የወይዘሮ ወርቂት መልክተኞች መቅደላ ደርሰው የዓመዴ ዐሊን ወሬ ቢጠይቁ "ምነው እሱማ ገደል ተጥሎ ሞቶ" ብለው ነገሩዋቸው ። እነሱም ተመልሰው የዚህኑ ወሬ ለእመቤታቸው ቢነግሩ ፣ "ይህን ሰው እግዚአብሔር ቢወደው ነው" ብለው ለምኒልክ ስንቅም ሽኝም ሰጥተው ወደ ሸዋ ሰደዷቸው ። በሸዋም ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ "በዘውዴ እንጂ በገርግንነት አልበልጥህም" ብለው ጉብዝናውን ያደነቁለትና የሾሙት አቶ በዛብህ (በዙ አባ ድክር) በመጨረሻ ጊዜ ካፄ ቴዎድሮስ ሸፍቶ ራሱን እንደ ንጉሥ ቆጥሮ ደብዳቤም ሲጽፍ "ንጉሠ ሸዋ" እያሰኘ ማስተዳደር ዠምሮ ነበርና የምኒልክን መምጣት ሲሰማ ጦሩን በበኩሉ ሰብስቦ ለመዋጋት ተዘጋጀ ። ሲዘጋጅም ለራሱ ሥልጣን ማራዘሚያ መሆኑንና የሸዋ ንጉሥ እያለ መጻፉንም በይፋ ሁሉም እያወቀ ሐሜታ ስለ አበዛበት ፣ በፊተኛው ጊዜ ፣ "እኔ የጌታዬ ልጅ እስኪመጣ ነው አገር የምጠብቀው ፤ የጌታዬ ልጅ ከመጣ በሰላም አስረክባለሁ" እያለ ባንድ ወገን እየሰበከ አሁን ደግሞ ምኒልክ ፣ "መጣሁ ተቀበለኝ" ብለው ሲልኩበትና የሥልጣኑ ፍጻሜ መቃረቡን ቁርጡን ሲያውቀው ፣ "እምቢ" ብሎ ለጦርነት ይዘጋጅ ገመር ። ተዘጋጅቶም ሲጨርስ ወደ ጋዲሎ (ግድም ውስጥ) ለውጊያ ከነጦሩ መጓዙን ያየች አንዲት "እናት ዓዋጁ" የምትባል ነገር ዐዋቂ "እረ ተው" ብላ ዘማቹን በማውገዝ እንደዚህ ብላ ገጠመች ይባላል ።

ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ
ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ

1 ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ሞንዶን ቪዳዬ ያሳተመው ገጽ 30—31

ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መሳሉ
የጌታችሁ(የኃይለ መለኮት) ልጅ ነው ኧረ በስሙ አብ በሉ ። [1]

ሌሎችም በመጀመሪያ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር የመጡ ጊዜ ራሱ በዛብህ ከሌሎቹ መኳንንት ጋር ሆኖ ምኒልክን ይዞ በበረከት ከነራስ እንግዳ ጋር በዠግንነት ሲዋጋ መቁሰሉንና መታሰሩን አሁን ደግሞ ሊወጋቸው መሔዱን በመንቀፍ እንደዚህ ብለው ገጠሙ ።

የበረከት ለታ ከሸንጡ ተወግቶ
ከሻንቅላ ጋር አብሮ ተቆራኝቶ
አገር ለምኒልክ እያለ ቆይቶ
ሊወጋቸው ሔደ የሰው ነገር ሰምቶ
አንተም አደረግኸኝ የመነኩሴ ፈራጅ
የሙት ልጅ ሲቀበል እንዲህ ነወይ ወዳጅ

በዚህም ጊዜ ካህናት ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን ፥ ገርማሜ በዛብህን ይንቁ ስለነበረ ፥ "ከዚህ ከባላገር ጋር ጦር ነት እንጂ ፥ በሰላም የዕርቅ ነገር መደራደር ውርደት ነው" ስላሉና እርሳቸውም ተደማጭነት ስለ ነበራቸው ዕርቁ ቀርቶ የጦርነቱ ጉዳይ የማይቀር ሆነ ።

ምኒልክ ከተከተላቸው በቀር የወሎም ፥ በተለይ የሸዋ ሰውም ከያ ለበት ፥ "የጌታችን ልጅ መጣልን" እያለ ተሰበሰበ ። ከበዛብህም ጋር ከነበረው ግሚሱ እየተከፈለ ወደ ርሳቸው ሲዞር የበዛብህ ጉራ እየመነመነ ሔደ ። ቢሆንም በዛብህ በነሐሴ ወር መዠመሪያ ላይ የሚቻለውን ያህል ተዋግቶ መሸነፉን ሲያውቀው ሸሽቶ ወደ አፍቀራ ምሽግ ገባ ። የርሱ የጦር አለቃ የነበረው አብተየስም እንደዚሁ ተሸንፎ የግድምንና የኤፍራታን ግዛት ለምኒልክ ባለሥልጣኖች አስረከበ ። በኋላ የምኒልክ ዋና የጦር አለቃ የነበሩት ራስ ጐበናም በዚህ ጊዜ አጋፋሪ ጐበና እየተባሉ የበዛብህ ጭፍራ ነበሩና መጥ ተው ለምኒልክ ገቡ ።

ከዚህም በኋላ ምኒልክ ፥ ከጦርነቱ ቦታ ከጋዲሎ (ግድም) ተጉዘው በኩል ወደ ሾላ ሜዳ (ተጉለት) መጡ ። ከዚያም በሸዋ ምሥራቅ በኩል አድርገው ማህል ወንዝ ደረሱ ። ከወይዘሮ ወርቂት ዘንድ ለመሸኘት የተላኩትም መኰንኖች በደጃዝማች ብርዬ መሪነት ከጭፍሮቻቸው ጋር

1 የብላቴን ጌታ ኅሩይ ሳይታተም የቀረው የእጅ ጽሑፍ ገጽ 82
Four Ethiopian Biographies - By Bairu Tafla-Daddaz-mach Garmame Aba - mala - PP 3—10



እንዳሉ ወደ ወሎ አንመለስም ብለው አብረዋቸው ተጓዙ ። በዚህ ዓይ ነት ምኒልክ በሠራዊታቸው እንደ ታጀቡ በ1857 ዓ. ም. በነሐሴ 24 ቀን አንኮበር ከተማ በደስታና በዕልልታ ገብተው የቴዎድሮስ ደጃዝማ ችነታቸው ቀረና ንጉሥ ምኒልክ እየተባሉ ሸዋን ያስተዳድሩ ዠመር ። ትንሽ ቆይተው ወሎንም ደረቡ ።

በዚህ ጊዜ ፥ ከላይ ከመሐመድ ዐሊ አባ ጅቦ ባላባትነት የወረዱት ወይዘሮ መስተዋት የዐመዴ አባ ዋጠው * እናትና ወይዘሮ ወርቂት የሚቹ የዐመዴ ዐሊ እናት በወሎ ግዛት ባላንጣነታቸው የጋለ ነበር ። ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ ለመምጣት ሲሉ ፥ ወርቂት ለልጃቸው ለውጥ ሊያደርጓቸው እንደነበር ምኒልክ ቢሰሙትም ባንድ ወገን ለልጃቸው ሞት ሰበቡ እርሳቸው መሆናቸውን በመረዳት፥ ሁለተኛ የልጃቸውን ሞት ከሰሙ በኋላ ፥ "ይህ ሰው እግዚአብሔር ያልተለየው ነው" ብለው ስንቅም ሸኝም በመስጠት ፥ "የሸዋ ሰው አውራህ መጥቷልና ደስ ይበልህ ተቀበል" የሚል የይፋ መልዕክት ልከው በደስታና በክብር ስለ ሰደዷቸው ፥ ይኸንን እንደ ውለታ ቆጠሩ ላቸው ። ምኒልክም በሸዋ ከተቋቋሙ በኋላ ወደ ወሎ ተመልሰው ሲመጡ ወርቂት ልጃቸውን ካጡ ወዲህ በባላንጣቸው በወይዘሮ መስተዋት ተጠቅተው ነበር ። አሁን ግን ፥ ምኒልክ ወይዘሮ መስተዋትን አጥቅተው ወርቂትን በሥልጣናቸው አደላድለው አስቀመጧቸው ። ንጉሥ ምኒልክ በሸዋ ገብተው ተደላድለው ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ ፥ በዛብህም ውሎ አድሮ ለንጉሥ ምኒልክ ታምኖ ገባላቸው ። ዳሩ ግን ሸጉጥ አጉርሶ ንጉሡን ሊገድል አስቧል ተብሎ በዚሁ ተፈርዶበት ተገድሏል ።

* በኋላ ንጉሥ ምኒልክ ክርስትና አንሥተው ራስ ኃይለ ማርያም የተባሉት



ንጉሥ ምኒልክ

ከቤተ መንግሥት መዝገብ ቤት

# ምዕራፍ ሁለት

## የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ወሎ — ያዔ ዮሐንስ ዕረፍት መሰማት — ለምኒልክ የገቡላቸው መላፍንትና መኳንንት

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፣ ዐፄ ዮሐንስ አንደኛ በጥንት ወዳጃቸው በእንግሊዝ ተገፋፍተው የደርቡሾቹን ጠላቶች ግብጾችን ረድተው ባገራቸው በትግረና በትግራይ እንዲያልፉ ፈቅደውና ሸኝተው ወደ ምጥዋ አደረሱዋቸው ። ሁለተኛ የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ከያዙ ዠምሮ ቅባቶችንና ጸጎችን በቦሩ ሜዳ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባሉበት ከተዋሕዶች ጋር አከራክረው በጉባዔ አስወስነው የተዋሕዶን (ካራ) ሃይማኖት በይፋ አጸደቁ ። ከዚሁ አያይዘው በኢትዮጵያ ያለው የእስልምና እማኝ ሁሉ እንደ ሌላው ክርስቲያን ሕዝብ ተዋህዶ ክርስቲያን መሆን አለበት ብለው ዓውጀው ነበር ። በዚሁ የተነሣ እስላሙን ሁሉ ሹማምንትና መልከኛ በወታደር እየሰበሰበ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ ፣ "ተጠመቅ ፣ ቁረብ" ሲለው የፈራው ያለልቡ ተጠምቆ ቆረበ ። ያልፈራው በመታሰር ተጉላላ ። ከነዚሁ መካከል ጥቂቶቹ ከኢትዮጵያ እየሸሹ ወደ ሱዳን ገብተው ጥቃታቸውንና መጉላላታቸውን ለደርቡሾቹ አስረዱ ። ዐፄ ዮሐንስንም እንዲወጉላቸው ጠይቀው እነርሱም አብረው በውጊያ ለመሞት መቁረጣቸውን እየገለጹ ይወተውቱ ነበር ። ለነዚህም ዋና ቀንደኛው ከወሎ የሔደው ሼከ ጦልሃ ቤን ጃፋር ነበር ። እርሱም ካዔ ዮሐንስ ሞት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከኢጣልያኖች ጋር ሆኖ የአላጌን ጦርነት መካፈሉን ወደፊት እናነባለን ።

ስለዚህ ፣ ያዔ ዮሐንስና የደርቡሾች ጦርነት ከፖለቲካና ከመሬት ፍለጋው ጋር ፣ በኢትዮጵያ የተጠቃውን የእስልምና ተከታይ ጥቃት ለመበቀል የተደረገ የሃይማኖት ጦርነት ነበር ለማለት ይቻላል ። የመተማ ጦርነት ባዔ ዮሐንስ ላይ የተባባሰው በነርሱ ምክንያት መሆኑን እያወቁት እንግሊዞች ላዔ ዮሐንስ ምንም ዓይነት እርዳታና ምክር ሳይሰጧቸው መቅረቱ ያሳዝናል ። በኋላ ግን ፣ ላዔ ዮሐንስ ብሎ ሳይሆን ባንድ ወገን ወገኑን ጐርዶን ባሻን ስለ ገደሉበት ፣ በሌላ ወገን ሱዳንን ቅኝ አገር ለማድረግ ስለፈለገ ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ

ዘጠኝ ዓመት ቆይቶ ኦራሲዮ ሄርበርት ክችነር እ. ኤ. አ. በመስከረም 2 ቀን 1898 ዓ.ም. የእንግሊዝን ጦር ይዞ መጥቶ የከሊፋ አብዱላሂን ጦር ፍርስርሱን አውጥቶ አገሪቱን ይዟል ። ሱዳንም ሙሉ ነጻነቱዋን እስከ አገኘችበት እ.ኤ.አ. እስከ 1956 ድረስ በበላይነት ይዞ ሲያስተዳድር ቆየ ።

ዐፄ ዮሐንስ ፣ ከደርቡሾች ጋር ባደረጉት ጦርነት ቀንቷቸው ቢሆን ኖሮ ፣ በትኩሱ በአዲስ የድል አድራጊነት ግርማ ወደ ሸዋ ይዘምቱ ነበር ። እንዲሁም በውድም በግድም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የወሎው ባላባት ራስ ሚካኤል አብረው መዝመታቸው ስለማይቀር ፣ ንጉሥ ምኒልክም ለመመከት ቆርጠዋልና ታላቅ ጦርነት መደረጉ የማይቀር ነበር ። ነጋድራስ አፈወርቅ ፣ "ዐፄ ዮሐንስ ከንጉሥ ምኒልክ ቢዋጉ እንደሚሸነፉ ስለ ተረዱት ፊታቸውን ወደ መተማ አዞሩ" ብለዋል ። አከታትለውም "...ካጤ ምኒልክ ጋር ተዋግቶ ድል ሆኖ በገዙበት ሥፍራ እንዳይገዙ ፣ ባስገበሩበት ፊንታ እንዳይገብሩ... ከዚያው ለመቅረት ..." የሚል ቃል አስፍረዋል ።[1] ሞታቸውን መርጠው ወደ መተማ ወረዱና ለመመለስ አይደለም

ይኸም ቃል እንደዚሁ በመላ የተወረወረ ነው እንጂ ፣ ወደ መተማ ሲዘምቱ የጦር መሪነቱን ከራስ አሉላ እጅ አውጥተው ለራስ ኃይለ ማርያም ባይሰጡ ኖሮ ፣ ውጊያውንም በእልህ በማድረግ ፊንታ በጥናትና በጥንቃቄ አድርገውት ቢሆን ኖሮ ፣ እንዳጋጣሚም ንጉሠ ነገሥቱ ከፊት ቀድመው በመዋጋትና በማዋጋት በዚያች ጥይት ተመትተው ባይቆስሉ ኖሮ ሊያሸንፉ በቻሉ ነበር ። ደርቡሽንም አሸንፈው ከተመለሱ በዚያው በድል አድራጊነት ግርማ ወደ ሸዋ መዝመታቸው የማይቀር ስለሆነ ፣ ምንም እንኳን በደርቡሽ ውጊያ ጦራቸው ቢዳከምም የአሸናፊ ሞራሉ ከፍ ማለቱ ስለማይቀር ፣ ምናልባት ንጉሥ ምኒልክን ሊያሸንፉ ይችሉ ነበር ብሎ ለማሰብ ይቻላል ።

የሁለቱም ኃይለኛ ውጊያ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ አገሪቱን በጣም አዳክሞ ጦርነቱን አቆብቁቦ ለሚጠብቀው ለኢጣልያ ወረራ ምቹ ይሆንለት ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ ንጉሥ ምኒልክ ከአባይ ዳር ጦራቸውን መልሰው በእንጦጦ ከተማቸው ሆነው የሚሆነውን ይጠባበቁ ነበር ። ከእንቀጥሎም ለማናቸውም ብለው በየካቲት 28 ቀን 1881 ዓ.ም. ከእንጦጦ ተነሥተው በመጋቢት 6 ቀን ደብረ ብርሃን ገቡ ። በመጋቢት 3

1. ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ—ነጋድራስ አፈወርቅ ገጽ 55



ቀን ዐፄ ዮሐንስ መሞታቸውን ሳያውቁ በመጋቢት 11 ቀን ከደብረ ብርሃን ተነሥተው በ17 ቀን ቀወት ደርሰው በሰፈር እንዳሉ ያፄ ዮሐንስ ሞት ወሬው ደረሳቸው ።

ያፄ ዮሐንስን ሞት ሲሰሙ ድንጋጤም ፣ ሐዘንም ደስታም የተደባለቀበት ስሜት እንደሚሰማቸው የታወቀ ነው ። ሐዘኑና ድንጋጤውም ምንም እንኳን ከሥር ጀምሮ ሁለቱም የዘሩትን ባላንጣነታቸው የታወቀ ቢሆን ፣ በ1870 ዓ. ም. ተገናኝተው ልጅ ከልጅ አጋብተው ይነስ ይብዛ በመጨረሻ በ1880 ዓ. ም. ዝምድናው መልሶ እስኪደፈርስ ድረስ ዐሥር ዓመት በፍቅርና በስምምነት ኖረዋል ። ግብጾችና ቱርኮችን ለመቃወም መሣሪያ እርዱን ብለው ንጉሥ ምኒልክ ለኢጣልያ ንጉሥ በ1874 ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ ላይ ፣ "ካባቴ ከወዳጄ ካፄ ዮሐንስ ጋራ ታረቅሁ ፤ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆንን" ያሉትን እናስታውሳለን ። ወደፊት እንደምናነበው ፣ ለኢጣልያ ንጉሥ በጻፉት ሌላ ደብዳቤ ላይ ፡ "በመጋቢት መዠመሪያ ቀን እጅግ የሚያሳዝን ፣ የሚያስደንቅ ብርቱ ነገር መተማ ላይ ተደረገ ። ዓፄ ዮሐንስ ሠራዊታቸውን ሁሉ አስከትተው ወርደው ከደርቡሽ ጋር ተዋግተው ድል ሆነው ቆስለው ሞቱ" ብለዋል ። ነጋድራስ አፈወርቅም "ያጤ ዮሐንስ መሞት ወሬው ከመቅጽበተ ዐይን ላጤ ምኒልክ መጣልዎ ፤ ዐጤ ምኒልክ በብርቱ አዘኑ አለቀሱ[1]" ብለው ጽፈዋል ።

ባንድ ወገን ደግሞ ፣ ያንዱ ሞት ለሌላው ሕይወት እንደ መሆኑ መጠን ያፄ ቴዎድሮስ ሞት ላፄ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሞት ላፄ ዮሐንስ መንግሥት መንገድ እንደ ከፈተ ሁሉ ፣ አሁንም ያፄ ዮሐንስ ሞት ለንጉሥ ምኒልክ ግልጽ የሆነ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ የሚያስጨብጥ መሆኑ አያጠራጥርም ። በመተማ ጦርነት ላይ ዐፄ ዮሐንስ ቢቀናቸው ኖሮ ተመልሰው እንደሚወጉዋቸው ስለሚያምኑ ፣ አሁን ግን ከዚህኛው ሥጋት ስለ ተገላገሉና የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ የሚቀዳጁበት ጊዜ ስለደረሰ ፣ በሐዘኑ ጐን ሌላ ዓይነት ግላዊ ደስታ ይሰማቸዋል ብንል ትክክለኛ አስተያየት ይሆናል ። ይኸን የመሰለ ሁኔታ በማንም ሥጋ ለባሽ ላይ የሚደርስ ድርብ ስሜት ነው ። ከሁለቱ ድርብ ስሜቶች በሰው ልጅ ላይ ራስን መውደድ ስለሚያመዝን ከሐዘኑ ይልቅ የደስታው ወገን ሚዛኑ ከበድ ሊል ይችላል ።

ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን ሞት ከሰሙ በኋላ ከቀወት ወደፊት ተጉዘው ዘቦሩ ሜዳ ላይ እንዳሉ ፡ "ባለህ እርጋ ገዥህ እኔ ነኝ ..." የሚል

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 55—56

ዓዋጅ በነጋሪት እናገሩ ። ከቦሩ ሜዳ ሰገራት* እንደ ደረሱ ያፄ ዮሐንስ
ሹማምንት የግሸንን አምባ ከነዕቃው ይጠብቁ ነበርና ወደ ንጉሥ
ምኒልክ ቀርበው ፣ "...የንጉሥ ዕቃ ለንጉሥ ነውና አምባውን ከነ
ዕቃው የሚረከብ ሰው ያድርጉልን"[1] ብለው አመለከቱ ። በዚህ ጊዜ
ንጉሡ ሹም ሽር ማድረግ ጀመሩ ። ግሸን ያለበትን የአምባሰልን ግዛት
ለባላባቱ ለገንጥራር እስፋው ሰጡ ። በአምባው ያለውን ዕቃ እንዲ
ረከቡ ደጃች ወልዴን ልከው አምባውን ጠባቂ አቶ ወልደ ተክሌን
አድርገው ከዚያ ወደ ሐይቅ ተጉዘው ከጨጨሆ በላይ ያለውን የየጁን
ግዛት የራስነት ማዕረግ ጨምረው ለደጃች ወሌ ብጡል ሰጡ ።

ንጉሥ ምኒልክ ፣ ባሻ ጨሬ ባሉበት ሰዓት ካፄ ዮሐንስ ጋር የመተ
ማን ጦርነት የተካፈሉት ራስ ሚካኤል መጥተው እጅ ነሥተው ገቡ ።
ከዚያ አልፈው ንጉሡ ከወይዘሮ ጣይቱ ጋር ወደ ላሊበላ ሔደው ዋግ
ሹም ብሩ ስለገቡላቸው ያባታቸውን የዋግሹም ገብረ መድኅንን አገር
ዋግን ሰጡዋቸው** ከዚያ ንጉሡ በድብኮ ተጉዘው በገረገራ እል
ፊው በግንቦት 27 ቀን ቋና በሰፈሩበት ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት
መጥተው ገቡላቸው ። ንጉሥ ምኒልክም 31 ጊዜ ስለ ክብራቸው
መድፍ አስተኩሰው በደስታ ተቀበሉዋቸው ። በያዙትም አገር ላይ
ከፋን አከሉላቸው ። ከዚሁ እያይዘው ለስሜኑ ባላባት ለራስ ወልደ
ሥላሴ ያባቶቻቸውን የነራስ ገብሬን ግዛት ስሜንን ፣ ላዬ ቴዎድሮስ
ልጅ ለራስ መሸሻ ደምቢያን ሰጡ ። የደምቢያንና የቤጌምድርን የበላይ
ቆራጭነት ለራስ ወሌ ሰጥተው የቀረውንም የቤጌምድርን መኳንንት
በየአለሀበት ሹመትህን እንደያዝህ ቆይ ብለው ፈቀዱ ። በዚህም ጊዜ
ካፄ ዮሐንስ ጋር የነበሩ መኳንንት ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ
በቀር ብዙዎቹ ከመተማ እየገሠገሡ መጥተው ገቡላቸው ። ራስ መን
ገሻ ግን ፣ አልጋ ወራሽነትን ካፄ ዮሐንስ በኑዛዜ ተቀብለው ስለነበር
ምንም እንኳን ንጉሥ ምኒልክን ለመቋቋም በቂ ኃይል እንደሌላቸው
ቢረዱትም ፣ እንደ ሌሎቹ በቶሎ መጥተው ለምኒልክ መግባቱ ቅር ስለ
አላቸው ሊመጡ አልቻሉም ። ራስ አሉላና ራስ ሐጐስም ከርሳቸው
ጋር ስለሆኑ በዚህ ጊዜ አልመጡም ።[2]

---

* ሰገራት ከወረይሉ በስሜን በኩል የሚገኝ ወረዳ ነው ።

1. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ጸ.ት. ገብረ ሥላሴ — ገጽ 154

** ዋግሹም ብሩ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ወንድምና የዋግሹም ጓንጉል አባት ናቸው ።

2 ገብረ ሥላሴ ፣ ምዕ.39 ፣ ገጽ153—156 Chronique du Regne de Menelik II ....
XXXIX pp. 258-263.



# ምዕራፍ ሦስት

## የኢጣሊያ መንግሥት ከውጫሌ ውል በፊት ካፄ ምኒልክ ጋር ያደረገው ስምምነት

በአንኮበር እነ አንቲኖሪ ፣ እነቼኪ መጥተው የኢጣሊያንና የኢት
ዮጵያን ወዳጅነት ለመመሥረት ካፄ ምኒልክ ጋር ግንኙነት ሲወጥኑ ከአን
ደበታቸው የሚፈልቀው ፣ "በወዳጅነት የንግድን ጉዳይ ከማስፋፋት በቀር
የኢጣልያ መንግሥታችን እንደ ሌሎቹ እንደ እንግሊዝና እንደ ፈረንሳይ
መንግሥታት የሰውን አገር ለመውረር አይመኝም" የሚል ነበር ።
ምኒልክም ፣ ከጐንደር እናኗኗራቸው ዝምሮ የፈረንጆችን ጥበባቸውንና
ዕውቀታቸውን ስለ ተረዱት ፣ የነርሱን ዕውቀት ባገራቸው ለማስገባት
አጥብቀው ይሹ ነበር ። እንዲሁም ጸጥታንም ለመጠበቅና ባላጋራንም
ለመመለስ የጦር መሣሪያ ማግኘት አስፈላጊነቱ ስለ ተሰማቸው ፣ ፈረ
ንጆቹን በተለይ በዚህ ጊዜ (1860—80 ዓ. ም.) ማቅረብና በነርሱም
ወዳጅነት ለመጠቀም ከልብ እንደሚጣጣሩ ፣ "ዐፄ ዮሐንስና የኢት
ዮጵያ አንድነት" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ተወስቷል ።

ኢጣሊያኖች ካፄ ምኒልክ መንግሥት ጋር የወጠኑት ዝምድና
እያደር እየጠበቀ ሔደ ። ፒዬትሮ አንቶኔሊ በኢትዮጵያ ተቀማጭ
ሆኖ የኢጣልያ መንግሥት ንጉሥ ወኪልና ተጠሪ በነበረበት ሰዓት
ይኸው የወዳጅነት ግንኙነት የበለጠ እንዲጠብቅ በ1880 ዓ.ም.
ከዚህ ቀጥሎ የሚነበበውን ውል ተዋዋለ ።

ንጉሥ ምኒልክና የኢጣሊያው ንጉሥ መልእክተኛ ፣ ከኮንት
አንቶኔሊ ጋራ የተነጋገሩት ነገር ይህ ነው ።

መዠመርያ ነገር

— ኢጣሊያና ንጉሥ ምኒልክ የከበረውም መንግሥታቸው በወዳጅ
ነትና በቃል ኪዳን መኖራቸውን ገልጠው ያስታውቃሉ ። ከኒህም

ቃል ኪዳን ያላቸው በሥራት የሚኖሩ ፪ቱ ወገኖች በሚቻላቸው መልካም ነገር ሁሉ ሳይናፈጉ እየተስማሙ ይኖራሉ ።

ሁለተኛ ነገር

— የኢጣሊያ ንጉሥ መንግሥት ፣ ንጉሥ ምኒልክን መሣርያም ሆኑ ሌላም ነገር ሆነ ጉልበትዎን ለማጠንከር ዕርዳታና ማገዝ የፈለጉ እንደሆን ፈጥነው ያደርጉላቸዋል ። ንጉሥ ምኒልክም በበኩልዎ የኢ ጣሊያን መንግሥት በተቻለዎ ነገር ሁሉ ይረዳሉ ።

ሦስተኛ ነገር

— የኢጣሊያ ንጉሥ ከኢትዮጵያ መሬት ፩ም ቦታ እንዳይዙ እን ዳይነኩ ይሆናል ።

አራተኛ ነገር

— የኢጣሊያ ንጉሥ አሰብ ላይ ለንጉሥ ምኒልክ ወኪል ይህ ነገር ከተነ ጋገሩበት ቀን ዠምሮ ፯ ወር ድረስ ፭ ሺ ሬሜንግቶን (ጠበንጃ) ያስረ ክባሉ ።

አምስተኛ ነገር

ንጉሥ ምኒልክም በበኩልዎ ለኢጣሊያ ንጉሥ እኒህ ነፍጦች እኔን ለመጥቀም ይሆናሉ እንጂ ፣ የኢጣሊያ ሰዎችን መውጊያ እንዳይሆኑ እርግጠኛ እውነተኛ ቃል ይሰጣሉ ።

ይህ ነገር በንጉሥ ምኒልክና በኮንት አንቶኔሊ የኢጣሊያ ንጉሥ መልእክተኛ ፊት ታተመ ። በጥቅምት ፲ ቀን በ፲፰፻፹ ባዲስ አበባ ባዲሱ ከተማችን ተጻፈ ።

በዚህ ውል ውስጥ በሦስተኛው አንቀጽ እንደ ተመለከተው ፡ "የኢ ጣሊያ ንጉሥ (የስም ቦታ ክፍት ተደርጓል) ከኢትዮጵያ መሬት አን ድም ቦታ እንዳይነካ ይሆናል" በሚለው ቃል ተረጋግጦ ነበር ። ዳሩ ግን ፣ በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ መንግሥት የምጥዋን ወደብና አካባቢውን ይዟል ። በዚህም ምክንያት ያዶጋሊው ጦርነት ሊነሣ ችሏል ።

ዳሩ ግን ፣ ባንድ ወገን የመንግሥታችን መዳከም ፣ በሌላም ወገን የርስ በርሱም ጦርነት አላቋርጥ ማለቱ አግዟቸው ፣ "ምጥዋን አስቀድሞ ቁርኮችና ግብጾች ይዘውት ነበር ። በኋላም የኢጣሊያ ጦር መጥቶ



በያዘበት ጊዜ የዚህ ክፍል አውራጃና ወደቡ የኢትዮጵያ አይደለም" የሚል ስሜት በእንግሊዞቹም ፡ በኢጣልያኖቹም ዘንድ እንደነበረ የታወቀ ነው ።

አሁን አንቶኔሊ ፡ ይኸን ውል ከምኒልክ ጋር ሲዋዋል ከዚሁ ስሜት ጋር በማያያዝ ፡ "የሸዋው ንጉሥ ስለቀረው እንጂ ስለዚያኛው ክፍለ ሀገርና ወደብ አያገባቸውም" በሚል አስተሳሰብ ነው ። እንደዚሁም ወቅቱ ምኒልክ ካፄ ዮሐንስ ያፈነገጡበት ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ሸዋን ሳይወሩ አይቀሩም የሚባልበት አሥጊ ሰዓት ነበር ። ውሉ በዚህ ውል በአራተኛው አንቀጽ ላይ የተመለከተውን 5000 (አምስት ሺ) የሬሜን ግቶን ጠመንጃ ለማግኘት ሲባል የተደረገ መሆኑ ነው ። ዳሩ ግን ከዚህ ውል በኋላ ባመቱ ውጫሌ ላይ የተደረገው ውል ብዙ ሐተታ ፈጥሮ ወደ ዓድዋው ጦርነት እንዳመራ በየምዕራፉ ወደፊት እናነባለን ።

# ምዕራፍ አራት

## የኢጣሊያ ጦር ፣ ከረንንና አሥመራን ስለ መያዙ—በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ የውጫሌ ውል

ያፄ ዮሐንስ በመተማ መሞት ወሬው ለንጉሥ ምኒልክ ሐዘን ድንጋጤና ደስታ የተደባለቀበት ስሜት ሲያሳድር ፣ በኢጣልያኖች ዘንድ ግን የሰጠው ስሜት ደስታ ብቻ ነበር ። ኢጣሊያኖች ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ የትግሬ መሳፍንት ባንድ እግር መቆም እንደማይችሉ አጠገባቸው ባሉት መሳፍንት በነደጃች ደብብና በነደጃች ስብሐት አቅዋም ያውቁታል ። "ምኒልክም የሸዋ መስፍን ስለሆኑ ፣ ከኛም ጋር ከጥንት ጀምረው ስለ ተወዳጁ ፣ ስለ ኤርትራና ስለ ትግሬ አበክረው ከኛ ጋር በጦርነት አይቋቋሙም ። ራስ መንገሻ ዙፋን ካፄ ዮሐንስ ቢወርሱም ፣ ራስ አሉላም ለርሳቸው ቢታመኑም ፣ ሁለቱን በነደጃች ደብብ ለማፍረስ ደብብ ለንጉሥ ምኒልክ እንዲገባና ምኒልክ የትግሬን ግዛት ለደብብ እንዲሰጡ ማድረግ ነው ። ምኒልክ ይኸን የማይቀበሉ ሲሆን ምኒልክን በዮሐንስ ላይ እንዳስታጠቅን ፣ አሁን ደግሞ ምኒልክ መስፋፋታችንን የሚቃወሙ ከሆነ ፣ ራስ መንገሻንና የትግሬን መሳፍንት በማስማማት አስታጥቀን በምኒልክ ላይ ማስነሣት ፣ በዚህ ዓይነት እርስ በርሳቸው ሲዋጉ ለኛ በቀጥታ ያለምንም ደም ከጊንዳ አሥመራ ፣ ከአሥመራ መረብን አልፈን ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት እንመሠርታለን" የሚል እምነት እንደ አደረባቸው በየመጽሐፋቸው ይነበባል ፣ [1]

ይህ አሳብ ፣ በሮማ ያለው የጠቅላይ ሚኒስትሩና እንደዚሁም በምጥዋ የሚቀመጠው የጦር ጠቅላይ አዛዥ ሲሆን ፣ ሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ዘንድ የኢጣልያ ወኪል ሆነው የተቀመጡት እነ አንቶኔሊ እነትራቨርሲ ግን ፣ ከዚህ ዓይነቱ መከፋፈል በመጠኑ ለየት ይላሉ ። የእነርሱ አስተያየት ፣ "በዚህ ጊዜ የንጉሥ ምኒልክ አቅዋም በማናቸውም የጠነከረ ስለሆነ ፣ የእርሳቸውን ወዳጅነት አጠንክሮ ከርሳቸው የተፈቀደውን መሬት ይዞ በሰላም መቆየት ይሻላል እንጂ ፣ የትግሬ

1 La Prima Guerra d' Africa, Documenti . . . .T. Plamenghi, - Crispi, chap. VI-X

መሳፍንትትን ይዞ በምኒልክ ላይ ለመነሣት የሚወስደው እርምጃ እሩቅ አይሔድም” የሚል ስሜት ስለአላቸው፣ በምጥዋ ባሉት የጦር አለቆችና አዲስ አበባ ባሉት የኢጣሊያ ወኪሎች መካከል ጠብና ክርክር ተፈጥሮ ነበር። ሮማ ያሉት የመንግሥቱ መሪዎችም ከሁለቱም ወገን የሚጎርፈውን ራፖር በጽሞና እያነበቡ የሚሆነውን መካከለኛ ውሳኔ በመውሰድ ይጠቀሙ ነበር።

ዐፄ ዮሐንስ፣ ከሰሐጢ የጦር ግንባር ነቅለው ከነሠራዊታቸው መቀሌ የተመለሱ ጊዜ የኢጣልያ ጦር አዛዥ ሆኖ የመጣው ሌተና ጄኔራል ሳንማርሳኖ ነበር። የጦርነቱ ደመና ስለ ተገፈፈለት፣ እርሱም ካጋማሽ በላይ የሆነውን ጦር ይዞ ተመለሰ። በርሱ ስፍራ ጄኔራል አንቶኒዎ ባልዲሠራ ተሾሞ ነበር። ባልዲሠራ ከርሱ ጋር በቀሩት 6000 ወታደሮች እየተጠቀመ እስከ ጊንዳ ያለውን ወረዳ ይዞ እገዛዙን እያጠነከረ ወደ አሥመራ የሚወስደውን ተራራማና ወጣ ገባ መንገድ እያሠራ ያገር ተወላጅን አለቃና ጭፍራ እየመለመለ ወታደር ያደራጅ ነበር።

በዚህ ጊዜ፣ ባጠገቡ ሆነው ጭፍራቸውን ይዘው ከኢጣልያ የጦር አለቃ ጋር አብረው ይሠሩ የነበሩት ዋነኛው ደጃች ደብብ አርአያ ሲሆኑ፣ እንደዚሁም ሌሎች ሹማምንቶች አብረው በመሆን መሣሪያ ሆነዋል። እነዚህም የራስ ወልደ ሚካኤል አማች ባላምባራስ ከፈል፣ ደጃች አድጎ አምበሳ፣ ቡልቅባሽ አዳም እጋ፣ ወንድሙ ከንቲባ አማን ኡመር፣ አጋር ትኬ የሚባሉ ናቸው። ወደ አሥመራ እንደገቡ የአጋሜው ደጃች ስብሐትና የእከለ ጉዛዩ ደጃች ባሕታ ሐጎስ ለኢጣልያ ታማኝ ሆነው ስለገቡለት፣ በማናቸውም ረገድ የኢጣሊያኖች አቅዋም ለጊዜው እየበረታ የሔደ መስሎ ይታይ ነበር። በሮማ በዋናው ምክር ቤትም ሲድኔይ ሶኒኖ የሚባለው ወደ ማኸል ኢትዮጵያ እንደልብ መጋለብ እንደሚቻል ያስብ ነበር።[1] በመካከሉ ዐፄ ዮሐንስ በመተማ መሞታቸውንና ጦራቸው መፍረሱን፣ ከመተማ የተመለሱት የትግሬ መሳፍንት በግዛት ባላንጣነት እርስ በርስ በውጊያ መፋጀታቸውን ወሬው ካገር ተወላጆቹ ለጄኔራል ባልዲሠራ በመድረሱ፣ የትግሬ ግዛት ከእንግዲህ ለኢጣሊያ አገዛዝ ክፍት መሆኑን ተረዳው። በዚህ ምክንያት ጄኔራል ባልዲሠራ ያፄ ዮሐንስን ሞት ከሁሉም አንደበት ካረጋገጠ በኋላ፣ ከዚህ የሚቀጥለውን በ226 ቁጥር የተጻፈ ቴሌግራም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለጦር ሚኒስትሩ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 2 ቀን 1889 ዓ.ም. አስተላለፈ።

1 La Prima Guerra D'Africa - R. Battaglia pp. 355 - 360



... የንጉሡ ሞት በሁሉም ዘንድ የተረጋገጠ ሆኗል። ሠራዊቱ በሙሉ ፈርሷል። በሁሉም ስፍራ ድብልቅልቅ፣ እርስ በርስ መገዳደልና ድኅነት ሰፍኗል። ይኸውም ያሁኑ የሐበሻ ሁኔታ በዓመታት ለሚቆጠር ጊዜ የሚቀጥል እንጂ በቀላሉ የሚያልፍ አይደለም። እንደዚሁ ብንጠብቅም የምንከስረው ነገር የለም። ምኒልክም ባሁኑ ጊዜ ወደ ዓድዋ ለመምጣት በጣም ይቸግራቸዋል እንጂ፣ ከነጦራቸው ቢመጡ የርስ በርሱ የጦርነት ጊዜ አጠር ሊል ይችላል። በትግሬ ደብብ፣ አሉላ፣ ደጃች ሥዩም፣ ባላምባራስ ከፈል እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ። ሁሉም በቶሎ ወይም ቆየት ብለው የኛን እርዳታ መጠየቃቸው አይቀርም። በኛ በኩል አሥመራንና ከረንን ለመያዝ ምንም ዓይነት አስቸጋሪ ነገር የለም። ሁሉም (የመኖሪያው ሸቀጥ) ከምጥዋ መጋዝ ስላለበት ችግሩ የሚመጣው በኋላ ነው። ....

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ይህ ቴሌግራም ሲደርሰው፣ አንድ ትልቅ ዕድል እንደአገኘ በመቁጠር ለጦር ሚኒስትሩ ለቤርቶሌ ቪያሌ እንደዚህ ሲል ጻፈለት። “ባልዲሠራ በቁጥር 226 ከላከው ቴሌግራም በኋላ ወደ አሥመራ ከመጓዝ የዘገየን እንደሆነ ለጥቅማችን አደገኛ ነው። ከዚህ የበለጠ ዕድል ሊገጥመን አይችልም።”

የጦር ሚኒስትሩ ደግሞ በፋንታው ለባልዲሠራ እንደዚህ ብሎ መልስ አስተላለፈለት።

.... በቁጥር 226 ቴሌግራም የላከኸው ቃል እርግጠኛ እንደሆነ ተስፋ አለኝ። የጉዞ ችግር ካልገጠመህ በቀር በቶሎ ወደ አሥመራ ተጉዘህ መሽገህ ተቀመጥ። ከደብብ ጋር መልካም ግንኙነት በማድረግ ከባላጋራዎቹ ጋር በሚያደርገው ጠብ እንደምታግዘው ተስፋ እየሰጠህ መንፈሱን ቀስቅሰው። አሥመራንም ስትይዝ ኢጣልያ የወሰኗን ጸጥታ ለመጠበቅና ወደርሷ የተጠጉትን ሕዝቦች ለመርዳት ምኞቷ መሆኑን በዓዋጅ አስታውቅ ...[1]

በኢጣልያ መንግሥት በኩል ይኸን የመሰለው የመልእክት ልውውጥ ሲደረግ፣ በወዲህም ንጉሥ ምኒልክ፣ የዮሐንስን ሞት ከሰሙ በኋላ ገና በጉዞ ላይ እንዳሉ፣ ወሎ ሳይገቡ ግድም በነበሩበት ጊዜ፣ በጉዞ ያልተለያቸው ኮንት አንቶኔሊ ስለ መከራቸው ይመስላል፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለኢጣሊያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ ቀዳማዊ ጻፉ።

.... በመጋቢት በመጀመሪያ ቀን 1881 ዓመተ ምሕረት እጅግ የሚያሳዝን፣ የሚያስደንቅ ብርቱ ነገር መተማ ላይ ተደረገ። ዓፄ ዮሐንስ

1 Palamenghi, chap. V. pp. 112-154, Crispi e Menelich, A. Salimbeni, chap. 1-2; L' Italia in Africa, Vol. 1, Tome VIII, PP. 220 - 235.

ሠራዊታቸውን አስከትተው ወርደው ከደርቡሽ ጋር ተዋግተው ድል
ሆነው ቆስለው ሞቱ ። አሁን ግን ፡ ኮንት አንቶኔሊና የኔ መልእክተኞች
ሆነው ቆስለው ሞቱ ። (ወደ ኢጣልያ) ድረስ የልቤን ጉዳይ ሁሉ እነዚያ (መልክ
እስኪመጡ (ወደ ኢጣልያ) ድረስ በትግሬ በኩል ያሉ ሽፍቶች ይኸንን ወሬ
ተኞቹ) እስኪነግሩዎ ድረስ በትግሬ በኩል ያሉ ሽፍቶች ይኸንን ወሬ
(ያፄ ዮሐንስን ሞት) የስሙ እንደሆነ በየበኩሉ መንግሥት ያምረዋ
ልና ፡ ምጥዋ ወዳሉት ሹማምንቶችዎ የተላላኩ እንደሆነ እንዳይሰሙ
ዋቸው ፡ አንድም ነፍጥ እንዳይወጣ ያድርጉልኝ ።

ዳግመኛ የርስዎ ሹማምንት በአሥመራ በኩል ቢጠብቁ እጅግ
መልካም ነውና በጣም ያስጠብቁልኝ ። ይኸንን ማለቴ እስካሁን ድረስ
የጠበቅሁት የኢትዮጵያን ዳኝነት በኔ እጅ እግዚአብሔር ከጠቀለለው
ኢትዮጵያን ከጦርነት አሳርፋታለሁ ብዬ ነው ። በመጋቢት 18 ቀን
በግድም ሰፈር ተጻፈ ።[1]

ንጉሥ ምኒልክ ፡ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፡ "....የርስዎ ሹማምንት
በአሥመራ በኩል ቢጠብቁ እጅግ መልካም ነውና በጣም ያስጠብቁ
ልኝ..." ሲሉ በአንቶኔሊ የፖለቲካ ማወናበድ ፡ ዐውቀውም ሳያው
ቁም ፡ እየተታለሉ ኢጣልያ አሥመራን ስለርሳቸው ከሽፍቶቹ እየተከ
ላከለ የሚያስቀምጥላቸው መስሏቸው ይሆን ? ይኸንን አስበው እንደሆነ
በጌን ጠብቅልኝ ብሎ ተኩላን እንደ መለመን ይቆጠራል ። ዋናው
ያፄ ምኒልክ አሳብ ግን ፡ የጦር መሣሪያን ጥቅሙንና ጉዳቱን በጣም
ለይተው ስለሚያውቁ ራስ መንገሻም ፡ ሌላውም ዞሩን ተቀናቃኝ
በምጥዋ በኩል መሣሪያ እንዳያገኝ ለማድረግ ነው ። ይኸን ደብዳቤ
ጽፈው ከላኩ በኋላ ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው ያደረጉትን ሹም
ሽር ተመልክተናል ። ራስ መንገሻንና ራስ አሉላንም ጠብቀው
ሳይገቡላቸው ስለቀሩ ቅርታቸውን በልባቸው ይዘው ፡ ወደፊትም እንዳ
ይገፉ ካገሩ ከወጣ የቆየው ሠራዊት የሚራብ በመሆኑ ፡ ያሉበትና
ያለፉበት ወረዳም በግብር ስለሚጐዳ ፡ ከዚህም በላይ በዚሁ ጊዜ
ረኃብና የከብት እልቂት በኢትዮጵያ ላይ ገብቶ ስለነበር ወደ አዲስ
አበባ መመለስ ግዴታ ሆነ ።

በዚህ ጉዟቸው ጊዜ ያልተለያቸው ኮንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ
የኢጣልያ መንግሥት ለርሳቸው ፍጹም ወዳጅ መሆኑን ፡ በትግሬ
በኩል ያሉት የኢጣልያን ጦር አዛዦች የርሳቸውን ጥቅም እንደሚጠ
ብቁና በርሳቸው ላይ የሸፈተውን እንደሚያጠቁ በማስመሰል ነገራ
ቸው ። እንደዚሁም ፡ "የብድር ገንዘብም ፡ የጦር መሣሪያም የሚገኘው
በይፋ አንድ የስምምነት ውል ሲያረግና የኢትዮጵያም ዋና መልክተኛ

[1] Archivio Storico del Soppresso Ministero Africa Italiana, pos. 36.6-53. La Prima Guerra D' Africa - R. Battaglia - PP.352- 362



ሮማ ሔዶ ከኢጣልያ ንጉሥ ሲገናኝ ነው" እያለ ደጋግሞ አመለከተ ።
በተለይም ንጉሥ ምኒልክ በንጉሠ ነገሥትነት በደንብ ሳይጸኑ ፡ ራስ
መንገሻና ራስ አሉላም ሳይገቡ ፡ ያሉበትን የውልውል ወቅት በመጠ
ቀም ያለፈውን የወዳጅነትና የንግድ ውል የሚያጠቃልል አዲስ ውል
እንዲደረግ አበክሮ አሳሰበ ።

ከሮማ የተላከለትንም የውል ረቂቅ ይዞ ነበርና ይኸው የውል
ረቂቅ በግራዝማች ዮሴፍ ወደ አማርኛ ተተርጕሞና ለንጉሡ ቀርቦ
በምክር መጠነኛ ጥናት ከተደረገበት በኋላ ፡ ወደ አዲስ አበባ ለመመ
ለስ ውጫሌ በሠፈሩበት ሰዓት በውጫሌ ስም የተሠየመውን ውል ተዋ
ዋሉ ። በዚህም ውል ንጉሥ ምኒልክ ከብዙ ክርክር በኋላ ጠብቁልኝ
ያሉትን የአሥመራን ከተማ ለኢጣልያኖቹ ሲለቁ ይታያል ። በ20
አንቀጽ የተከፈለውን የውሉን ዝርዝር እንደሚከተለው እንመልከት ።

### 1ኛ

በኢጣልያና በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መካከል በወራሾቻቸ
ውም ፡ በሕዝባቸውም እነዚህንም በተጠጉ ሕዝብ መካከል ሰላም ፍቅር
ሳይጐድል ለዘወትር ለልጅ ልጅ ይኖራል ።

### 2ኛ

እነዚህ ሁለቱ አሁን የተዋዋሉት ነገሥታት ፡ በየአገራቸው በም
ስለኔዎቻቸው ይነጋገራሉ ። አንዱ ካንዱ አገር ቆንሲልም ፡ የቆንሲል
ወኪልም መሾም ይቻላቸዋል ። እነዚህም ሹሞች እንደ አውሮፓ
ነገሥታት ሥርዓት መታፈርና መከበር አይጐድልባቸውም ።

### 3ኛ

በነዚህ በሁለቱ ነገሥታት ወሰን ፡ ጠብና ክርክር እንዳይነሣ
በዕውቅ የተመረጡ ከ2ቱ ወገኖች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ልከው
በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድንበር ይወስናሉ ። ከድንበሩ ወዲህ
የሚጨመሩት አገሮች እነዚህ ናቸው ። የደጋው አፋፍ ከኢትዮጵያና
ከኢጣልያ መካከል ወሰን ይሆናል ። ከራፋሊ ጀምሮ ሐላይ ሰገነይቲ
አሥመራ ሦስቱ የኢጣልያ መንግሥት መንደር ይሆናሉ ።

ዳግመኛ በቦገስ በኩል አዲ ነፋስ ፡ አዲ ዮገስ በኢጣልያ ድንበር
ውስጥ ይሆናሉ ። ከአዲ ዮገስ መንደር ጀምሮ ከምሥራቅ ወደ
ምዕራብ ባቀና ይከፈላል ።

4ኛ

የደብረ ቢዘን ገዳሙ ከነጉልቱ ከነርስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት
ርስት እንደሆነ ይቀራል ። የጦር አምባ መሆን ግን አይቻለውም ።

5ኛ

ከምጥዋ የሚወጣ የንግድ ዕቃ የሚገባም የንግድ ዕቃ ከ100፥8
በገቢ ዕቃው እየተገመገመ በገቢ አንድ ጊዜ ይከፍላሉ ።

6ኛ

የጦር መሣሪያ ንግድ በምጥዋና በኢትዮጵያ መካከል የሚመላ
ለሰው ለንጉሠ ነገሥት ብቻ ይፈቀድልዎታል ። ሲያስመጡም ባለ
ማኅተም ደብዳቤዎን ለኢጣልያ ሹማምንት እየላኩ ያስመጣሉ ። ነፍ
ጡንም የያዘውን ሠፈር ከምጥዋ ዠምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድምበር ድረስ
የኢጣልያ መንግሥት ወታደሮች ዘበኛ ሆነው ይሸኛሉ ።

7ኛ

የነዚህ የሁለቱ ውል ያደረጉ ነገሥታት ዜጐች ፡ የንግድ ዕቃቸውን
ይዘው ያንዱ ካንዱ አገር መሔድ ፡ መምጣት ይቻላቸዋል ። በየመንግ
ሥቱና በየወረዳው ባለው ሹም ጥግነት ደስ ብሏቸው ይመላለሳሉ ።
ነገር ግን ፡ ከሁለቱም ወገኖች የጦር መሣሪያ የያዘ ብዙ ሆኖ ካንዱ
ድንበር ወደ አንዱ ድንበር መተላለፍ ተከልክሎአል ።

8ኛ

የኢጣልያ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የኢትዮጵያ ሰዎች በኢጣልያ ፡ የኢ
ጣልያ መንግሥት በሚገዛውም አገር ቢሆን ፡ እንደ አገሩ ልማድ መግ
ዛት መሸጥ መከራየት ይቻላቸዋል ።

9ኛ

የነዚህ የሁለቱ ነገሥታት ዜጐች ፡ አንዱ ካንዱ አገር ቢሔድ
በየሃይማኖታቸው ይኖራሉ ።

10ኛ

የኢጣልያ ሰውና የኢጣልያ ሰው የተካሰሱ እንደሆነ እነዚያ በመ
ረጡት ዳኛ ፡ ያለዚያም ተያይዘው ምጥዋ ወርደው ይዳኛሉ ። የኢጣልያና



የኢትዮጵያ ሰው የተጣላ እንደሆነ ግን ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪ
ልና የኢጣልያ የምጥዋ ሹም አንድነት ሆነው ይዳኛሉ ።

11ኛ

የኢጣልያ ሰው በኢትዮጵያ የሞተ እንደሆነ ፡ የኢትዮጵያ ነው
በኢጣልያ አገር የኢጣልያ መንግሥት በሚገዛው አገር የሞተ እንደ
ሆነ ፡ ከሟቹ መንግሥት ወገን ገንዘቡን የሚቀበል ሰው እስኪመጣ ያ ረስ
የሁለቱ ነገሥታት ሹማምንት ገንዘቡን ጠብቀው ያስቀምጣሉ ፡

12ኛ

በማናቸውም ኃጢአት ተከሶ የተያዘው የኢጣልያ ሰው በኢጣ
ልያ ሹማምንት ይዳኛል ። ስለሆነ ግን ፡ ታላቅ ኃጢአት ሠርቶ የተገኘን
የኢጣልያን ሰው ፈጥነው ይዘው ለምጥዋ ሹማምንት መስጠት ነው ።
ደግሞ በኢጣልያ መንግሥት ግዛት የኢትዮጵያ ሰው ታላቅ ኃጢአት
ሠርቶ የተገኘ እንደሆነ በኢትዮጵያ ዳኛ ይዳኛል ።

13ኛ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣልያ ንጉሥ ፡ ብርቱ ኃጢአት
የሠራ ሰው ካንዱ ግዛት ወደ አንድ ግዛት ሸሽቶ የሔደ እንደሆነ
ሁለቱም እያሰሩ ይልካሉ ።

14ኛ

የባሪያ ንግድ በክርስቲያን ሃይማኖት የተከለከለ ስለሆነ ፡ የኢት
ዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሚቻላቸው ነገር ሁሉ ባገራቸው ባሪያ እንዳይ
ነገድ ይከለክላሉ ።

15ኛ

ይህ አሁን የተጻፈው ውል ለኢትዮጵያ ሁሉ መንግሥት ውል ነው ።

16ኛ

ይህ ውል በተደረገ ከ5ዓመት በኋላ ፡ ከሁለቱ መንግሥት አንዳ
ቸው ውል ለመጨመር ወይም ለመለወጥ የፈለጋቸው እንደሆነ ከዓ
መት በፊት አስቀድሞ መናገር ይገባቸዋል ። ነገር ግን ፡ የንግድን ውል
ብቻ ማረም ፡ ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል እንጂ ዛሬ የተለየውን የድምበር
ወሰን ማፍረስ አይቻላቸውም ።

## 17ኛ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ ፡ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል ።

## 18ኛ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፡ ከሌላ መንግሥት ሰዎች ጋራ የጥበብ ፡ የንግድ ነገር ለመዋዋል የፈለጉ እንደሆነ ከሁለቱ አማርጠው ሲያበቁ የሁለቱም ውል አንድ የሆነ እንደሆነ ለኢጣልያ ሰው ይሰጡታል ።

## 19ኛ

ይህ አሁን የተደረገው ውል ፡ በአምሐርኛና በኢጣልያ ቋንቋ ትክክል ሆኖ ተገልብጦ ሲያበቃ የታመነ ምስክር ይሆናል ።

## 20ኛ

ይህ አሁን የተጻፈው ውል በሮማ ከተማ ፈጥኖ ይጠናቀቃል ። ነገር ግን ፡ ይህን ውል ኮንት ፒትሮ አንቶኔሊ በኢጣልያ ንጉሥ ስም ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተዋውለው አትመው ጨርሰዋል ። በሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓመተ ምሕረት በውጫሌ ሠፈር ተጻፈ ።

የዚህ ውል ረቂቅ ከተዘጋጀ ወዲህ ሲነበብ ፡ አንዳንድ ነገር ሲለወጥ ሲገለበጥ ቆይቷል ። ይልቁንም በ3ኛው አንቀጽ የተጻፈው ያገር መለስ ጉዳይ ስለሆነ ፡ ንጉሥ ምኒልክ ኢጣልያኖቹ ከአሥመራ ወደ ኋላ መለስ እንዲሉ ሲመኙ ፡ ኢጣልያኖቹ ደግሞ እንዲያውም ከሥመራ አልፍ ለማ ለት ሲነጋገሩበት ሰንብተዋል ። ንጉሥ ምኒልክ ፡ ባንድ በኩል የውጭ ተጽዕኖና ወረራ በሰሜንና በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሚያንዣብብ ብ በት ፡ በሌላ ወገን በአጼ ዮሐንስ ሞት ምክንያት በየክልሉ የሚገኙ ተ መሳፍንት የራሳቸውን ግዛት አደላድለው ለመያዝ የሚራኮቱበት ወቅት በመሆኑ ፡ እነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አስገድደዋቸው ለጊ ዜው ውሉን እያንገራገሩ ለመፈረም በቁ ። በእርግጥም ሕሊናቸው ፈቅዶና ሙሉ እምነት አድርገው አለመፈረማቸውን ሊያረጋግጥ የሚ ችለው ፡ የኋላ ኋላ ውሉን መሠረዛቸውና እንዲያውም የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ከምጥዋ አልፎ ሕንድ ውቅያኖስ መድረሱን ማሳወቃቸው ነው ።



እንደዚሁም በ17ኛው አንቀጽ የተጻፈውን ቃል ንጉሥ ምኒልክ ፡ "...መቼም እኔ በአውሮፓ እንደ ንጉሥ ኡምቤርቶ ያለ ወዳጅ ጉዳዬን የሚፈጽም የለኝምና መጻፉ ቢቀር ምን አለበት..." እያሉ ለኮንት አንቶኔሊ ደጋግመው ነግረውት ነበር ፤ ነገር ግን ኮንት አንቶኔሊ በዘዴና በብልሃት ይህ መርዘኛ አንቀጽ እንዲኖር አድርጎታል ። እንዲኖር ሲያደርግም ፡ "...ይህ አንቀጽ መኖሩ ካልታወቀ በአውሮፓ የጃንሆይና የኢትዮጵያ ጥቅም ሲነካ አፋችንን ሞልተን ለመናገርና ለመቃወም አንችልም ..." የሚል በወዳጅነት ሽፋፍኖ አስመሳይ የሆነ መልስ በመስጠት አሳምኗቸዋል ። ስለዚህ እላይ በተዘረዘሩት አንቀጾች ተስማምተው ፡ በመጨረሻ ይህ ውል በኢጣልያ ንጉሥ እንደራሴ በኮንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ ተፈርሞ የንጉሡ ማኅተም ከታተመበት በኋላ ፡ በሁለተኛው ወር ደጃዝማች መኰንን የውሉን ጉዳይ በማጽደቅ እፍጻሜ ለማድረስ የጦር መሣሪያና የብድር ገንዘብ ለማግኘት ወደ ሮማ የዳግማዊ ምኒልክ ዋና መልክተኛ ሆነው እንዲሔዱ ተወሰነ ።[1]

---

1 L 'Italia in Africa, Serie Stroica, Vol. 1: Ethiopia, Mar Rosso, Tome Vol, 328; Crispi e Menelich, Diario Salimbeni, C. Zaghi, pp. 152-153; Italia ed Ethiopia, Dal Trattato ...c Conti — Rossini PP.1-11.



የውጫሌን ውል የተረጐሙት ግራዝማች ዮሴፍ
ክሪስፒና ምኒልክ ከሚባለው ከካርሎ ዛጊ መጽሐፍ



የውጫሌን ውል የተዋዋለው ፒዬትሮ አንቶኔሊ
ከአባ ማስያስ መጽሐፍ

# ምዕራፍ አምስት

## የደጃዝማች መኰንን ጉዞ ወደ ሮማ—ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ክፍራንቼስኮ ክሪስፒ ጋር ያደረጉት ስምምነት

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተገነዘብነው ፤ ዐፄ ምኒልክና ኢጣልያኖች በብዙ ረገድ ወዳጅነታቸውን ሲመሠርቱ የሁለቱ ዓላማና ምኞት በግልጽም በስውርም የተለያየ ነበር ። ዐፄ ምኒልክ በኢጣልያኖች ወዳጅነት መሣሪያ አግኝተው ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ዙፋን ለመውጣት ሲሆን ፤ የኢጣልያኖች ዓላማ ደግሞ በዐፄ ምኒልክ መሣሪያነት በኢትዮጵያ ሰሜን ለመስፋፋት ነው ። ይህ የማይታረቅ ተፃራሪ ዓላማ ወደፊት የአባጌን ፤ የመቀሌንና የዓድዋን ጦርነት ሲያስከትል እንመለከታለን ። እስከዚያ ድረስ ግን ፤ ሁለቱም ወገኖች ውስጣዊ ፍላጐታቸውን ሳይገላለጹ የፖለቲካ ጦርነታቸውን በተሸፈነ የወዳጅነት መልክ ሲቀጥሉ ይታያሉ ። በወዳጅነትና በስምምነት አብሮ ለመሥራት ያላቸውን ፍላጎት በውጫሌ ውል ላይ ገልጸውታል ።

በዚሁ መሠረት ፤ በአንድ ወገን የወዳጅነታቸውን ስሜት ለመግለጽ ፤ በሌላም ወገን ፤ "ኮንት አንቶኔሊና ጓደኞቹ የኢጣልያ መልክተኞች ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ ሲመላለሱ ፤ ከግርማዊነትዎ ዘንድ ግን ፤ ከዐሥራ አምስት ዓመት በፊት አባ ሚካኤል የሚባሉት ከመላካቸው በቀር ዋና መላክተኛ ሔዶ አያውቅም ። ስለዚህ የጃንሆይ መላክተኛ ወደ ኢጣልያ አገር ቢላክ የኢጣልያ ንጉሥና መንግሥቱ ደስ ይላቸው ነበር" እያሉ ብዙ ጊዜ ያሳስቡ ነበር ። የኢጣልያ መንግሥት መሪዎችም "ያፄ ምኒልክ መላክተኛ ወደ ሮማ ቢመጣ በክብር እንቀበለዋለን" በማለት ይገፋፉ ነበር ።

በዚህ ምክንያት ፤ የውጫሌን ውልና ሌላውንም በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ያለውን ጉዳይ ሁሉ በዝርዝር የሚያውቁት የንጉሡ ያክስት ልጅ የሐረርጌው አገረ ገዥ ደጃዝማች መኰንን ወልደ ሚካኤል እንዲሔዱ መወሰኑ ለኮንት አንቶኔሊ በይፋ ተነገረው ። እርሱም በነገሩ በጣም ተደስቶ ወደ ሮማ ለመንግሥቱ መሪ ለክሪስፒ በቴሌግራም አስተላልፎ ስለነበረ ፤ "...በታላቅ ክብር እንቀበላቸዋለንና

አንተው ይዘህቸው እንድትመጣ . . .” የሚል መልስ በቴሌግራም ኳጠቅላይ ሚኒስትሩ መጣለት ።

በዚህ ዓይነት ደጃዝማች መኰንን ወደ ሮማ እንዲሔዱ ከተወሰነ በኋላ ፣ አዲስ አበባ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው በግዛታቸው በሐረር በኩል አድርገው ወደ ኢጣልያ ለመሔድ ተነሡ ። እርሳቸውንም ተከትለው የሔዱት ዋነኞቹ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው ።

1ኛ. አባ ወልደ ሚካኤል—የንስሐ አባት
2ኛ. ቀኛዝማች አባ ናዳ (የደጃዝማች መኰንን የቅርብ ዘመድ)
3ኛ. ፊታውራሪ ቢራቱ *
4ኛ. ግራዝማች ዮሴፍ (አስተርጓሚ)
5ኛ. ግራዝማች ደሳለኝ (በዓድዋ ጊዜ ፊታውራሪ ናቸው)
6ኛ. ባላምባራስ ገነሜ (በኋላ ቀኛዝማች ቀጥሎ ደጃዝማች)
7ኛ. ባሻ ቆለጭ (በኋላ ፊታውራሪ ተብለው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሞግዚት የነበሩት)

ከነዚህ በቀር ዝቅተኛ መኰንኖችና ተራ ተከታዮች ቁጥራቸው እስከ 27 የሚደርስ አብረው ነበሩ ። ከመነሣታቸው በፊት ከነአንቶኔሊ ጋር በመስማማት ለኢጣልያ ንጉሥ እንደ ገጸ በረከት የሚቀርበው የዝሆን ግልገል ፣ ፈረስና በቅሎ ከነሙሉ መሣሪያቸው ቀደም ብሎ ከምጥዋ ወደብ ቬኒዚያ በሚባል መርከብ ተጭኖ ወደ ናፖሊ ተልኳል።

ደጃዝማች መኰንን ፣ ከሐረር እ.ኤ.አ. በሐምሌ 20 ቀን 1889 ተከታዮቻቸውን እንደያዙ ተነሥተው በመጓዝ ነሐሴ 2 ቀን ዘይላ ደረሱ ። ዕለቱን ወደ ማታ ክርስቶፎሮ ኮሎምቦ በሚባለው መርከብ ተሳፍረው በነሐሴ 12 ቀን ፖርት ሳይድ ገቡ ። ከዚያም በነሐሴ 21 በታወቀው የኢጣልያ ወደብ ናፖሊ ሲደርሱ ታላቅ የክብር አቀባበል ተደረገላቸው ።

ደጃዝማች መኰንንንና ተከታዮቻቸውን ለመቀበል ፣ በናፖሊ የከተማው ሕዝብና ያንድ ክፍል ጦር ከጦር መኰንኖችና ከአስተዳዳሪዎች ጋር እንደ ተሰለፈ ሲጠባበቅ እንግዶቹ ከመርከብ ወረዱ ። ከጦር ሚኒስቴር ኃላፊ ሆኖ ለመቀበል የተመደበው ማዦር ዶሚኒኮ ግራንዲ የሚባለው ሙሉ የማዕረግ ልብሱን እንደለበሰ ፣ ከደጃዝማች መኰንን ዠምሮ በጋለ ወዳጅነት ሁሉንም እየጨበጠ ተቀበላቸው ።

* ደጃዝማች ብሩ የተባሉት የራስ መኰንን ወንድም የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ልጅ የደጃዝማች ደስታ አባት ናቸው ።



መልክተኞቹ ፣ በናፖሊ እንዳሉ የዋናውን አስተናጋጃቸውን የአንቶኔሊን አባት ሞት ሰምተው ሐዘንተኛነታቸውን ከገለጹ በኋላ የደስታው አቀባበል ፣ ፋብሪካዎችን የመጐብኘቱ ተግባር ፣ በያለበት ግብዣውና መስተንግዶው ሲቀጥል ቆይቶ በመጨረሻ በነሐሴ 27 ቀን ወደ ሮማ ተጓዙ ። ሮማ ደርሰው ለነርሱ ማረፊያ እንዲሆን በተመደበው ሚራፊዎሪ* በተባለው ሆቴል ዐርፈው በዚያ አዳር ሆነ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከንጉሡ ከኡምቤርቶ የሚገናኙበት ቀን እ.ኤ.አ. ነሐሴ 28 ቀን 1889 ዓ.ም. እንዲሆን ስለ ተወሰነ ፣ በዚሁ ቀን ጧት በአራት ሰዓት የፕሮቶኮሉ ሹም የኖያ መስፍን ወዳረፉበት ሆቴል መጥቶ ወደ ቤተ መንግሥት ይዟቸው ሔደ ። በጉዞውም ጊዜ በጣም ባማረውና በመጀመሪያው ሠረገላ በቀኝ ደጃች መኰንን ፣ በግራ የኖያው መስፍን ተቀመጡ ። ቀጥሎ ባሉት ሠረገሎች ሌሎቹ መኳንንት እንደየማዕረጋቸው ተከታትለው ከቪላ ሚራፊዎሪ በፈረሰኛ ወታደሮች ታጅበው ኩይሪናሌ ወደሚባለው ቤተ መንግሥት ደረሱ ። ሙዚቃው በየዓይነቱ እየተነፋ ፣ ሠረገላዎቹ በድንጉላ ፈረሶች በተቀመጡ ወታደሮች ታጅበው ሲያልፉ ፣ በየመንገዱ ግራና ቀኝ በብዙ ሺ የሚቆጠር የሮማ ሕዝብ በጭብጨባና በሆታ እየተቀበለ ያሳልፋቸው ነበር ። ያቀባበሉን ዕፁብ ድንቅነት በዚያው አገር በትምህርት ላይ የነበሩት ነጋድራስ አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ በዝርዝር ጽፈውታል ። ቤተ መንግሥት ሲደርሱም ፣ የቤተ መንግሥቱ ዋናው የፕሮቶኮል ሹም ኮንቲ ጂአኖቲ ተቀብሎ ወደ ዙፋን አዳራሽ ወሰዳቸው ።

ንጉሡ ኡምቤርቶም ፣ የጄኔራል ልብስ ለብሶ ፣ በወርቅ የተሠራ ላባ የተሰካበት ጥሩር በራሱ ላይ ደፍቶ እንዳማረበት በእልፍኝ ወራሹ ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በክሪስፒና በሌሎች ሚኒስትሮች እንደ ተከበበ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይጠባበቅ ነበር ። በዚህም ያቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ደጃች መኰንንንና ኢትዮጵያን ደህና አድርገው የሚያውቁት እነ አንቶኔሊ ፣ ብራንኪ ፣ ሳሊምቤኒ ፣ ኔራሲኒ ፣ ትራቬርሲ ፣ ካፑቺ አብረው ነበሩና ፣ “እንደዚህ በሏቸው ፤ እንደዚህ አድርጉላቸው” የሚል ምክር ለማቅረብ ሳይሻሙ አልቀሩም ። በዚህ ዓይነት ደጃች መኰንንና ተከታዮቻቸው ወደ አዳራሹ ገብተው በፕሮቶኮሉ ሹም በኮንት ጂያኖቲ እየተመሩ በንጉሡ ፊት ለፊት ሲደርሱ ሁለት ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ንጉሡን እጅ ነሡ ። ንጉሡም ከዙፋኑ ተነሥቶ ለደጃዝማች

* ሚራፊዎሪ አበባ ተመልከት ማለት ነው ።

መኰንን የእጅ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ፣ ደጃዝማቹ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በአማርኛ ሲናገሩ ፣ ግራዝማች ዮሴፍ ወደ ፈረንሳይ ቋንቋ ተረጐሙት ።

ግርማዊ ሆይ

> ግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሥ የወዳጅነታቸውን ስሜት ለግርማዊነትዎ እገልጽ ዘንድ አዘውኛል ። አሁን የመላዋ ኢትዮጵያ ባለቤት የሆኑት ንጉሤ ከግርማዊነትዎ መንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅ ይፈልጋሉ . . , በኢትዮጵያና በኢጣልያ ግዛቶች መካከል ሰላምና ጸጥታ እንዲገኝ የጋራ ንግዳችንም እንዲስፋፋ የግር ማዊነትዎ ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግልን በመንግሥቴ ስም እጠይቃለሁ ። ንጉሤ ሰላምን ይፈልጋሉ ። በማናቸውም ዓይነት የኢጣልያ ጠላቶች የእኛ ጠላቶች እንደሚሆኑ ለግርማዊነትዎ አረጋግጣለሁ ።

ለዚህም መልስ ንጉሡ በኢጣልያንኛ ሲናገር ፣ ኮንት አንቶኔሊ ወደ ፈረንሳይኛ የተረጐመው ወደ አማርኛ ሲመለስ ከዚህ እንደሚ ከተለው ይሆናል ።

> . . . ንግግሮችዎን በብዙ ደስታ እዳመጥሁ ። ተስምተውኛልም ። ንጉሥዎም የመላዋ ኢትዮጵያ ባለቤት መሆናቸውን በመስማቴ ተደስቻለሁ ። ከብዙ ዘመንም ጀምሮ ከንጉሥዎ ጋር ወዳጅ እንደ ነበርን እሁንም እንቀጥላለን ። ለዚህም በሁለቱ መንግሥቶች መሐከል የተደረገው ውል ማረጋገጫ ነው ። የኔና የመንግሥቴም ጥበቃ አይለያችሁም ። ሰላምና ጸጥታም እንዲገኝ ከልብ እንመኛለን ። . . . .

መቼም የኢጣልያን መንግሥት ባሁኑ ጊዜ የሚያማልለው በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነቱ ነገር ነው ። ደጃች መኰንን ያላሉትን ወይም እርሳቸው ያሉትን በመጠምዘዝ እንዳሉ አስመስለው ፣ “የግርማ ዊነትዎ ከፍተኛ ጥበቃ እንዲያደረግልን ” ብለዋል ብለው ጽፈው ይሆናል እንጂ ፣ እንደ ኢጣልያኖቹ አተረጓጐም የኢትዮጵያ መንግሥት በኢጣልያ ጥበቃ ውስጥ እንድትሆን አስበውና አምነው አይናገሩም ። ጥበቃንም ጠቅሰው ቢሆን እንኳ በኢትዮጵያው ስሜት ወዳጅ ወዳጅን “ጠብቀኝ” ሲለው “ባላጋራ ፣ ነገረኛ ሲነሣብኝ እርዳኝ” ለማለት ነው እንጂ ፣ “ግዛኝ ፤ አስተዳድረኝ” ለማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው ። የሆነ ሆኖ ፤ በብሪዞኒ መጽሐፍ እንደ ተመለከተው ፣ በማናቸውም ረገድ ከንግግር ለውጥ በኋላ ዋናው የፕሮቶኮል ሹም ከደጃዝማች መኰንን ፣ ከግራዝማች ዮሴፍና ከጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በቀር ሁሉንም አስወጣና መዝጊያው ተዘግቶ እኩል ሰዓት ያህል የግል ጭውውት



አደረጉ ። ከዚህ በኋላ መዝጊያው ተከፍቶ ከዐፄ ምኒልክ የተላከው ልዩ ልዩ ስጦታ ለንጉሡ መቅረብ ጀመረ ።

ከስጦታዎቹ ውስጥ ሠላሳ የሚሆኑ የዝሆን ጥርሶች ፣ ያጌጡ ኮርቻዎች ፣ የጠጅና የድቁስ ቀንዶች ፣ ከበሮና የወርቅ መስቀል ፣ አክሊል ሙሉ ወታደራዊ የኢትዮጵያ የንጉሥ ልብስ ፣ ጦርና ጋሻ ፣ በወርቅ የተዘመዘመ የአንበሳና የነብር ቆዳ ፣ የዝሆን ግልገል ፣ በቅሎዎችና ፈረሶች ከሙሉ ዕቃዎች ጋር ይገኙበታል ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከንጉሡ በፍቅርና በወዳጅነት ተሰነባብተው ከቤተ መንግሥቱ ወጥተው ፫ ወር ያህል ሚላኖ ፣ ኮሞ ፣ ቶሪኖ ፣ ጀኖቫ ፣ ፒያቸንካ ፣ ቪቼንሳ ፣ ቬኒስያ ፣ ቦሎኛ ፣ ላስፒዚያ ፊሬንሴ ፣ ፒሩጅያ የሚባሉትን የኢጣልያን ዐሥራ አንድ የሚሆኑ ታላላቅ ከተሞች እየተዘዋወሩ በታላቅ ክብር ሲጐበኙ ሰነበቱ ። ለየከተሞቹ ከንቲባዎች “. . . ደህና አድርጋችሁ ፣ ተጠንቅቃችሁና አክብራችሁ ተቀበሉ. . .” የሚል ልዩ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ አስተላልፎ ነበር ። ከደጃች መኰንን ጋር ለነዚህ ከተሞች ጉብኝት የተመረጡት መልክተኞች በየደረሱበት የተደረገላቸው የክብር አቀባበል በከፍተኛ ደረጃ የሚገመት ነበር ።

በተለይ በዚሁ አጋጣሚ ፣ የኢጣልያ መንግሥት የጦር ኃይሉንና ትጥቁን ለደጃዝማቹና ለተከታዮቻቸው በማሳየት ለማስደነቅ ዋና አሳቡ ነበር ። የምድሩን ጦር ፣ የመርከበኛውንና የመድፈኛውን በያይነቱ እያሰለፈ ሲያስጐበኛቸው ሰነበተ ። ይኸንንም ማድረጉ ምናልባት ኢጣልያ በሰሜን ኢትዮጵያ ስትስፋፋ ፣ ኢትዮጵያ ይኸን ኃያል መንግሥት ለመቃወም እንዳትከጅል ወይም ውል ማፍረስ እንዳያምራት ለማስፈራራት መሆኑ አይጠረጠርም ።

ነጋድራስ አፈወርቅ ፣ ስለዚሁ ጉብኝት በመጽሐፋቸው ላይ “ . .ከሐውልት የሚበላልጥ መድፍ ሲተኩሱና በዙሪያው ያለ ሰው መሬቱ እየተንቀጠቀጠበት ሲወድቅ (መልክተኞቹ) አዩ ፤ ተገረሙ ፤ ተደነቁ ። አንድ የመድፍ ጥይት ብቻ ቁመቱ ከፊታውራሪ ቢራቱ ቁመት ስንዝር ተጋት በለጠ ። ወፍሩ ግን ሁለት ፣ ሰው ክንዱን ዘርግቶ ቢጠመጠም ሳይደርስበት ቀረ . . .”[1] ሲሉ ጠቅሰውታል ። የዚህን ዓይነት ጥይት የሚተኩሰው መድፍ መጠኑ ምን ዓይነት እንደሆነ አይታወቅም ። ቀጥለውም “የመድፉ ጥይት ግን ከዚያ ወዲህ አራት እጥፍ እየበለጠ ሔዷል” ብለዋል ።

---

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 68—69

ደጃዝማች መኰንን ፡ በዚህ ዓይነት ክብርና ደስታ ከቆዩ በኋላ ፤ ከከተማዎቹ ጉብኝት ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ በአስተርጓሚው በግራዝማች ዮሴፍ እየተረዱ ስለ ግዛት ፡ ስለ ንግድ ፡ ስለ ገንዘብ ብድር ጉዳይ ደጃዝማች መኰንን ስለዳግማዊ ምኒልክ ፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ስለ ኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ሆነው የውጫሌን ውል በማሟላት ተዋዋሉ ።

ደጃዝማች መኰንን ጉብኝታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ፡ በኅዳር ወር መጨረሻ ላይ ወደ አገራቸው ለመመለስ ከኢጣልያ ተነሡ ። ሲመለሱም እቴጌ ጣይቱ ኢየሩሳሌም ከጌታችን መቃብር ከጎልጎታ አጠገብ መሬት በ8000 ብር እንዲገዙ ቀደም ብለው አዘዋቸው ስለነበረ ፡ ኢየሩሳሌም ሔደው ከዚያ በምጥዋ በኩል አድርገው መጥተው በዚህ ጊዜ መቀሌ ከነበሩት ከንጉሠ ነገሥቱ ካፄ ምኒልክ ጋር ተገናኙ ።

ከርሳቸውም ጋር ከኢጣልያኖች ዘንድ የነበሩት የአጋሜው ደጃች ስብሐት ፡ ሌሎችም ደጃች ወልድዬ ፡ ደጃች ማሩ ፡ ደጃች ብሩ የሚባሉ መኳንንቶች በዚህ ጊዜ አብረው ገቡ ። ደጃዝማች መኰንን ምጥዋ ሲገቡ የጦሩ አዛዥ ጄኔራል ኦሬሮ በውጫሌ ውል የተደረገውን ወሰን አልፎ ወደ ዓድዋ የመንግሥቱን ትእዛዝ በመጣስ ሔዶ ነበር ። ኋላ ደግሞ ወቀሳም ስለ በዛበት ፡ ፍርሃትም ስለ ደረሰበት ምኒልክ ወደ ትግሬ ግዛት ከመግባታቸው በፊት ወደ መረብ ተመለሰ ። የርሱና በምጥዋ ያሉት የጦር ሹማምንቶች ከጠቅላይ ሚኒስትሩና ከፖለቲካ ሰዎች ለየት ብለው ስምምነቱን ሁሉ ወደጐን ትተው ፡ "የትግሬን ግዛት ከኛ ጋር ካሉት ሹማምንት ላንደኛው ለምሳሌ ለደብብ ሰጥተን አውራጃውን በመላ በኢጣልያ ሥር እናደርገዋለን" የሚል ስሜት ነበራቸው ። አንቶኔሊና ጓደኞቹ ፡ "ይኸኛው እርምጃ አደገኛ ነው" በማለት በደብዳቤ እየተጨቃጨቁ ከተጣመዱ ቆይተዋል ። አሁን አንቶኔሊ ከደጃዝማች መኰንን ጋር ምጥዋ ሲገባ ፡ አገረ ገዥዎቹ የጦር መኳንንት እነ አንቶኔሊን ገሸሽ ለማድረግ ፈትነው ነበር ። እንዲያውም በጠብ ከመባሰላቸው የተነሣ ጄኔራል ኦሬሮ በደጃች አድጉ አምበሳ እጅ አንቶኔሊን ለማስገደል እስከ ማሰብ ደርሶ ነበር ይባላል ።

ነገር ግን ይኸንኑ የሚያውቀው ክሪስፒ ፡ ኦሬሮ ወደ ዓድዋ ዘምቶ ስለነበር በርሱ እግር ምጥዋ ለቀረው ለኰሎኔል ኮሳቶ ፡ "መኰንንንና አንቶኔሌን በደንብ ተቀብለህ የሚያስፈልጋቸውን በማቅረብ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላክ" የሚል ቴሌግራም ቀደም ብሎ አስተላለፈለት።

1 Ibid



ደጃዝማች መኰንን ፡ በዚሁ በአንቶኔሊና ለነርሱ ባደሩት በነደጃች ስብሐት እየተመሩ በሰላም መቀሌ ደርሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተገናኝተው የመልእክታቸውን ውጤት በዝርዝር ማስረዳት ቻሉ ።[1] ስለአቀባበሉ አብሮአቸው ያለው ኮንት አንቶኔሊ ወደ ሮማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስተላለፈው ቴሌግራም እንደዚህ ይላል ።

> . . . ጧት በ23 (የካቲት) መቀሌ ስንገባ ምኒልክ መልካም አቀባበል አደረጉልን ። ከመድረሳችን በፊት ባንዲራ የያዙ የክብር ወታደሮች መጥተው ተቀብለው እያጀቡ እግቢ አደረሱን ። እግቢ ስንደርስ ስለ ክብራችን 21 ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ስለ መልክቱ በምኒልክ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቻለሁ . . .

1 Livro Verde . . . XV; Gli Italianai in Africa Orientale . . . A. Del Boca, II, PP 43-357; 3 L' Italia in Africa, Serie Storica, vol. I, Tome VII; C. Giglio, PP. 269-272.



ራስ መኰንንና ተከታዮቻቸው በሮማ
ከአሸል ቢዞኒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ስድስት

## የሹም ተምቤን ምርጫና የእንደርታው የባልጋዳ እርአያ ቤት

ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ባልታወጀበት ፣ ጽኑ ምክር ቤት ባል ተመሠረተበት አገር በኃይሉ የነገሠ አንድ ትልቅ ንጉሥ ሲሞት ልጆች ያሉት እንደሆነ ልጆቹ ፣ የሌሉት እንደሆነ የወንድምና የእህት ልጆች ወይም ወንድሞቹ በሥልጣኑ ለመተካት እርስ በርስ መዋጋት በቤተ መንግሥት የተለመደ ጉዳይ ነው ። በፊተኛው በኢትዮጵያ መንግሥት ፡ እንደ ልማድ ሆኖ ፡ አንዱ ሲነግሥ ወንድሞቹንና የደረሱ ልጆቻቸውን በግሸን አምባና በወህኒ አምባ ያስር የነበረው ፣ ይህን የመሰለውን የርስ በርስ ጦርነት ለማስቀረት ነበር ። ይኸም ቢቸግር ነው እንጂ የሚገባ ሆኖ አይደለም ። አንድ ሰው ከንጉሣዊ ቤተሰብ መወለዱ ብቻ እንደ ኃጢአት ተቆጥሮበት ፣ ሌላ ወንጀል ሳይ ሠራ ያለፈቃዱ ባንድ ቦታ ተወስኖ እስረኛ ሆኖ እንዲኖር የማድረጉ ልምድ ለሕሊና የሚከብድ አሳዛኝ ድርጊት ነው ።

ባንድ ወገን ደግሞ ፣ በአባታቸው በንጉሡ የአገዛዝ ዘመን እንደል ባቸው በነጻነት ባሉበት ጊዜ አባት ሲሞት ሥልጣኑን ለመውረስ የሚያደርጉት የርስ በርስ ጦርነት የብዙውን ሰው ሕይወትና ንብረት ሲያጠፋ መኖሩ እንዲሁ አሳዛኝ ነው ። ምናልባት የጥንት አባቶች የመሳፍንቱን በግዞት መኖር የመረጡት ፣ በጥቂቶቹ እስራት የብዙኀኑን ደም ለማዳን ብለው ይሆናል ። ይኸን ሁኔታ ለማስወገድ ባስተዳደር የበሰሉትና በዕውቀት የሠለጠኑት አገሮች አንድ ንጉሥ ሲሞት ከልጆቹ አንጋፋው ፣ ልጆች የሌሉት እንደሆነ በዝምድና የሚቀርበው እንደሚነግሥ በሕገ መንግሥት ላይ ስለ ተመሠረተ ፣ አንድ ንጉሥ በሞተ ቁጥር የዘውድ ውርስ ለሌላው ያለ ምንም ደም መፋሰስ ፣ ያላንዳች ግርግር ይተላለፋል ። ዘመዶቹም ልዑላን መሳፍንት እየተባሉ በልዩ ልዩ ክብርና ተግባር ተሠማርተው አብረው ይኖራሉ ። ሁሉም ባስተዳደር አይገቡም ። በእንግሊዝ ፣ በሆላንድ ፣ በዴንማርክ ፣ በኖርዌ ፣ በስዊድን ፣ በጃፓን ያለው ያስተዳደር መልክ ይኸው ነው ።

በኢትዮጵያ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ይህ ዓይነቱ ስላማዊ የሥልጣን ርክክብ እንደ ሕልም ይቆጠራል ። ቴዎድሮስም

ዮሐንስም ሁለቱም በኃይልና በጦርነት ዙፋንን እንደ ወረሱ እንብበናል። በዚህ ምክንያት፤ አሁንም ዐፄ ዮሐንስ ሲሞቱ በቀጥታ ከአብራካቸው የተወለዱት ራስ አርአያ ስለሞቱ፤ ለወንድማቸው ልጅ ለራስ መንገሻ ተናዘዙ። ይኸን ኑዛዜ የቀሩት ዘመዶች አልተቀበሉትም። ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም ባሁኑ ጊዜ ኃይልና ድርጅት ያለው በምኒልክ እጅ ስለ ሆነ፤ ያፄ ዮሐንስ ኑዛዜ የውሀ ላይ ኩበት ሆኖ የንጉሠ ነገሥትነቱን ሥልጣን ገና ካፄ ዮሐንስ በፊት ይጠባበቁ የነበሩት ንጉሥ ምኒልክ በቀጥታ በመውሰድ ነገሡ። ይኸን ኃይል ያወቁት ሁሉ ገና የንጉሠ ነገሥትነት በዓላቸውን ሳያከብሩ እየመጡ ገቡላቸው። ራስ መንገሻ ግን፤ ምንም ያቅማቸውን መጠን ቢያውቁት አልጋ ወራሽነትን በኑዛዜ ካፄ ዮሐንስ ተቀብለው ሳለ፤ እንደ ሌሎቹ ከመተማ መልስ መጥተው ለምኒልክ እጅ መንሣት የማይዋጥ መራራ ጉርሻ ሆኖባቸዋል። በዚ ህም ላይ ከዘመዶቻቸው ውስጥ የርሳቸውን አልጋ ወራሽነት ባለመ ቀበል ስለ ሸፈቱባቸው ከነርሱ ጋር መዋጋትም ግዴታ ሆነባቸው።

በዚህ የተነሣ፤ የተደረገውን የርስ በርስ ጦርነትና መከፋፈል ከመጥቀሳችን በፊት ለመከፋፈልም ምክንያት የሆነውን የትውልዳ ቸውን ዘርፍ ማወቅ ይጠቅማልና ከዚህ እንደሚከተለው እናመለ ክታለን።

የተምቤኑ ሹም ተምቤን ምርጫ፤ ወይዘሮ ሥላስን አግብተው ደጃች ሐጐስን ፤ ጉግሣን ፤ ማሩን፤ ድንቅነሽንና ደጃች ካሳን ይወል ዳሉ። ደጃች ጉግሣ ራስ ኃይለ ማርያምንና ራስ መንገሻን፤ እቴጌ ድን ቅነሽ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ከተለያዩ በኋላ፤ ራስ ቢትወደድ ገብረ ኪዳንን አግብተው ደጃች ሥዩምን፤ ዐፄ ዮሐንስ ራስ አርአያን፤ ደጃች ማሩ ደጃች መሸሻን ይወልዳሉ።

ባንድ ወገን ደግሞ፤ ያፄ ዮሐንስ እናት የወይዘሮ ሥላስ ወን ድም ወይም የዐፄ ዮሐንስ አጐት ትልቁ ራስ አርአያ ደጃች ደብብን ደጃች ቦጋለን፤ ደጃች ተድላ አባ ጐበንን ፤ ደጃች አብርሃንና ወይዘሮ አምለሱን ይወልዳሉ። እነዚህም ሁለቱ የዘር ግንዶች ያፄ ዮሐንስ የተምቤን ቤት የራስ አርአያ ደግሞ የእንደርታ ቤት ይባላል። ሁለቱም ብዙ ጊዜ የሥልጣን ባላንጣዎች ናቸው።

ያፄ ዮሐንስ ቀጥታ የባሕርይ ልጃቸው ራስ አርአያ ገና በወ ትነታቸው ጊዜ ስለሞቱ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከመሞታቸው በፊት የወ ድማቸውን የደጃች ጉግሣን ትልቅ ልጅ ራስ ኃይለማርያምን አል ወራሽ ለማድረግ ወስነው ሳለ፤ እሳቸውም በጦርነቱ ስለሞቱ ዙፋና ቸውን ለታናሽ ወንድማቸው ለራስ መንገሻ ጉግሣ በኑዛዜ አውርሰው



ሞቱ። በዚህ ምክንያት፤ ራስ መንገሻ ያባታቸውን ስም ወደ ጎን ትተው ራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ማኅተም አሠርተው በዚሁ ይጠሩ ዠመር።

ይኸን ውርስ አብረው ካፄ ዮሐንስ ጋር የዘመቱት ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ፤ እጨጌ ቴዎፍሎስ፤ መኳንንቱ እነራስ አሉላ፤ እነራስ ሐጐስ ተቀብለው ራስ መንገሻን አቀፉ። የደጃች ማሩ ልጅ ደጃች መሸሻና የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ደጃች ቦጋለ ቀደም ብለው አልጋ ወራሽ ነቱን በየበኩላቸው ይመኙት ነበርና ሁለቱም አኩርፈው ሠራዊታቸውን ከነዚያ ለይተው በየክፍለ ጦራቸው እንደ ታጀቡ ከመተማ ወደ የክፍለ ግዛታቸው ተመለሱ።

ደጃች ደብብ አርአያ፤ ገና ዐፄ ዮሐንስ በሕይወት ሳሉ ጀምረው ከዐፄ ዮሐንስ ከድተው መጀመሪያ ወደ ግብጾች፤ ቀጥሎ ወደ ኢጣልያ ኖች ገብተው ሳለ፤ ዐፄ ዮሐንስ ሰሐጢን በከበቡበት ሰዓት አባታቸው ራስ አርአያ ዐፄ ዮሐንስ አጠገብ ነበሩና መክረውም፤ ወቅሰውም ወደ ኢትዮጵያ ጐራ መልሰዋቸው ነበር። ዳሩ ግን፤ ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ እንደገና ለጣልያኖች ገብተው ባሁኑ ጊዜ በኢጣልያኖች ድጋፍ በኤ ርትራና በትግሬ ጠቅላላ ሥልጣን ለማግኘት የሚመኙበት ሰዓት ነበር። የእቴጌ ድንቅነሽና የራስ ቢትወደድ ገብረኪዳን ልጅ ሥዩም ገና አስቀድሞ ባፄ ዮሐንስ ጊዜ ከራስ አርአያ ጋር ተጣልተው አርአ ያን ስለ ሰደቡዋቸው፤ ዐፄ ዮሐንስ ይኸንኑ ሰምተው ገርፈዋቸው ነበር። በዚሁ ተቀይመው ከትግሬ ወደ ሸዋ ሸሽተው መጥተው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ስለነበሩ፤ አሁን የምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነት ጊዜ ስለ ደረሰ በምኒልክ ድጋፍ ትግሬን ለመግዛት ይጠባበቃሉ።

ሌሎችም በአጋሜ የደጃች ሰባጋዲስ ተወላጆች እነ ደጃች ስብ ሐት፤ በሐጼጋ የራስ ወልደ ሚካኤል ቤት፤ በጼሐዘጋ የደጃች ኃይሉ አባ ሐባል ተወላጆች ቀድሞውኑ የየግል ትውልዳቸውን ከፍ አርጎ በመገመት ለሹም ተምቤን ምርጫ ቤት መገዛቱን የጠሉ ነበሩ። ወይም "የተሰጠን ሹመትና ግዛት አነሰን" በማለት በፊት ወደ ቱርኮች አሁን ደግሞ፤ ወደ ኢጣልያኖች ገብተው ለኢጣልያ ወረራ መሣሪያ በመሆን መንገድ የሚመሩ ፤ ወሬ የሚያቀብሉ ፤ ልብስ፤ መሣሪያ፤ ገንዘብ በመቀበል በወታደርነት እየተደራጁ የጠላትን ወታደራዊ አቅ ዋም የሚያጸኑ አሉባቸው።

ዘመናዊ ትምህርት ባልተሰጠበት ፤ ያገር ፍቅር በስፋት ባልተሰበ ከበት በዚያ ዘመን እንኳን እነርሱ፤ ለዙፋኑ በጣም የቀረቡት ነገሥታት የግል ምኞታቸውን ለማሟላት አገር የሚጎዳ ጠላትን የሚጠቅም

እርምጃ ሲወስዱ ፣ እርምጃቸው አደገኛ መሆኑን አያጤኑትም ። እያንዳንዳቸው የሚመለከቱት የቁጭታቸውን መወጣትና የምኞታቸውን መሳካት ብቻ ነው ። እነዚህም መሳፍንት በነዚያ የምኞት መስመር ላይ ስለሚገኙ ፣ ተራውም ወታደር ላበላውና ላጠጣው ፣ የወር ቀለብ ለሚሰጠው ለውጭ ጠላት ሲዋጋ ቢሞት ያንጊዜ እንደ ዛሬ ከሐዲነት ነው ብሎ እምብዛም አያምንም ። አንዳንድ የሚያምንም ቢኖር በጠቅላላው ሁኔታ ውስጥ ተውጦ እየተጸጸተም ቢሆን የብዙኃኑን እርምጃ ለመከተል ግዴታም ውዴታም ይሆንበታል ። ኢጣልያ ምጥዋ ከገባ ዠምሮ በሰሐጢና በዶጋሊ ከራስ አሉላና ካፄ ዮሐንስ ጋር በተደረገው የጦርነት ሰልፍ ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ላፄ ምኒልክ ከገቡ ወዲህ በኮዓቲትና በደብረ ኃይላ ሲዋጉ ብዙ ያገር ተወላጅ ወታደር ከኢጣልያ ጦር ሠራዊት ጐን ሆኖ ለመዋጋት የተነሣው የዕለት እንጀራው እስገድዶት እንደነበር ወደፊት እናነባለን ።

ራስ መንገሻ ፣ የራስ አሉላንና የራስ ሐጐስን ኃይል እንደያዙ በዚያው በትግሬ ሆነው ምኒልክን በምን አኳኋን ለመከላከል ወይም መግባት እንደሚችሉ በማውጣትና በማውረድ ላይ ነበሩ ። በኢጣልያኖች የተደገፉት ደጃች ደብብ የትግሬን ገዥነት ስለሚመኙ ፣ የኢጣልያኖችን እርዳታ ይዘው መቀሌ አጠገብ ለጦርነት ከተሰለፉና ከተዋጉ በኋላ በእርቅ ድርድር ሰበብ ራስ መንገሻን እማርካለሁ ብለው ሲመኙ ራሳቸው ተማርከው በአምባ ሰላማ ታሰሩ ።

ከዚህ በኋላ ራስ መንገሻ ፣ ከጄኔራል ባልዲሠራ ጋር ተላልከው ወዳጅነት ጠይቀው ቢያስፈልግም እስከ ምጥዋ ድረስ ሔደው ለመገናኘት ልከውበት ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ባልዲሠራ ይኸንኑ ወደ ሮማ አስተላልፎ ሳለ በዚህ ጊዜ በንጉሥ ምኒልክና በኢጣልያ መካከል ወዳጅነቱ የተሟሟቀበት ፣ ደጃዝማች መኰንን ሮማን የሚጐበኙበትና የውጫሌን ውል ለማጽደቅ የሚነጋገሩበት ጊዜ ነበርና ጄኔራል ባልዲሠራ ከሮማ በተቀበለው ትእዛዝ መሠረት ፣ “ . . . ከኛ ጋር ወዳጅ የሚሆኑት በቅድሚያ ለንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ከገቡ በኋላ ነው . . .” የሚል ተስፋ አስቆራጭ መልስ ሰጣቸው ።

በዚሁ መካከል ደጃች ሥዩም አባ ኃያል ፣ ከሸዋ ወደ ትግሬ ዘልቀው ዓድዋ አጠገብ ከራስ መንገሻ ጋር ተዋግተው ተሸንፈው ወደ ጄኔራል ባልዲሠራ ሔዱ ። ባልዲሠራም የትግሬ መሳፍንት እርስ በርሳቸው በተዋጉና በተዳከሙ መጠን ለመስፋፋት እንዲሚመች ስለሚረዳው ፣ በዚህም ላይ ሥዩምን የምኒልክ ወገን አድርጎ በመቁጠር የጦር መሣሪያም ፣ ስንቅም ሰጥቶ እንደገና ወደ ትግሬ መለሳቸው ። ከዚህ በኋላ ባገኙት እርዳታ እንደገና ከራስ መንገሻ ጋር ፍሬምና



(አድዋ አጠገብ) ላይ ተዋግተው አሸነፉ ። ራስ መንገሻም እጃቸውን ለደጃች ሥዩም ሰጡ ። ሥዩምም በማግሥቱ እስራቸዋለሁ ብለው ለጊዜው በመልካም አኳኋን ይዘዋቸው ሳለ ፣ በደጃች አምባዬ እርዳታ እምልጠው እንደገና አክሱም እንዳ አባ ጳንጠሌዎን አጠገብ ከደጃች ሥዩም ጋር ተዋግተው ራስ መንገሻ አሸነፉ ። ሥዩምም እንደገና ወደ ጄኔራል ባልዲሠራ ሔደው ፣ በባልዲሠራ ምክር ወደ አጋሜ ተመልሰው ከባላባቱ ከደጃች ስብሐት ጋር አንድነት ተባብረው ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ለመውጋት ይዘጋጁ ጀመር ።

ይኸን የመሰለው የመሳፍንቱ የርስ በርስ ጦርነት በኢጣልያ መንግሥት ዘንድ እየተደገፈ ፣ የመመሪያው አሳብ ሁሉ ከሮማ ለወኪሎቹ በጽሑፍ ይተላለፍ ነበር ። የመመሪያውም መሠረተ ሐሳብ መንገሻንና አሉላን በደብብ ፣ በስብሐትና በሥዩም ማስመታት ፣ ደከም ላለው መሣሪያ በመስጠት አየል ያለውን እየመቱ ማዳከም ፤ በዚሁ መካከል ግዛት በሰሜን ኢትዮጵያ ማስፋፋት መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ስለዚህ የኢጣልያ የጦር አዛዥ ሥዩምንና ስብሐትን አቅፎ እነዚህ ከራስ መንገሻ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ መሣሪያና እርዳታ በመስጠቱ ሰበብ የአከለ ጉዛይንና የአጋሜን ግዛት በመያዝ የወራሪነት አቅዋሙን ያጠነክራል ።

እንደዚሁም ፣ ደጃች ደብብ ከራስ መንገሻ ተዋግተውና ተሸንፈው በአምባ ሰላማ ታስረው ነበር ። ከዚያ ደግሞ እንደገና አምልጠው ከመተማ ጦርነት የተመለሱትን ወንድማቸውን ደጃች ቦጋለንና የእንደርታን ሰው አስከትለው ፄሀ ላይ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር ተዋጉ ። ዳሩ ግን ፣ በዚህ ቀን ጦርነት በራስ አሉላ ጭፍሮች ተመትተው ወደቁ ። ጎዳያቸው የደጃች ደርሱ ልጅ ደጃች ተስፋዬ ናቸው ይባላል ። የሆነ ሆኖ በደጃች ደብብ ሞት ለራስ መንገሻ በትግሬ ዋና ተቀናቃኝ ጠፋላቸው ማለት ነው[1] ።

1 Crispi e Menelich - Carlo Zacghi - chap .1. PP. 3-23- La Prima Guerra D' Africa - R. Bataglia - PP. 382 -

## ምዕራፍ ሰባት

### የንጉሥ ምኒልክ ሥርዓተ ንግሥ — ወደ ትግሬ ያደረጉት ጉዞ—የራስ መንገሻ ላዩ ምኒልክ መግባትና በትግሬ የተደረገ ሹም ሽር

ንጉሥ ምኒልክ ፣ ወደ ሰሜን የሔዱ ጊዜ የራስ መንገሻን በሰላም መግባት ተስፋ አድርገው ሳይገቡላቸው እንደ ቀሩና ወደ እንጦጦ በሐምሌ ወር መግባታቸውን ባለፈው አመልከተናል ። እንደ ተመለሱም ሥርዓተ ንግሣቸውን ለማከበር ዝግጅት ተዠምሯል ። ነገር ግን ፣ ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ባገር ላይ ታላቅ ረኃብና በሽታ ተነሥቶ ሰውም ከብትም በዚሁ በሽታና ረኃብ ግማሹ የሚሞትበት ፣ ግማሹ የሚሰቃይበት ፣ እናት ልጅዋን የበላችበት ክፉ ጊዜ ነበር ። እንደዚህ ያለው አሳዛኝ ሁኔታ ለንጉሠ ነገሥቱ የቀረበውን ሥርዓተ ንግሥና የደስታ ጊዜ መርዞት ነበር ማለት ይቻላል ። በዚሁ ዓመት ከወይዘሮ ጌጤ የተወለዱት ልጃቸው ደጃች አስፋወሰን ሞተዋል ። እንደዚሁም ስመ ጥሩው የጦር አለቃ ራስ ጎበና ዳጬ በ1881 ዓ.ም ሞተው በወቅቱ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የተደጋገመ ሐዘን ደርሷል ።

ስለዚህም ምኒልክ ከጳጳሱ ከአቡነ ማቴዎስ ፣ ከታላላቆቹም መኳንንትና ሊቃውንት ተመካከረው ምሕላና እግዚኦታ ተያዘ ። በተጨማሪም የሃይማኖት ነገር እንዳፄ ዮሐንስ እምብዛም የማይጫናቸው ምኒልክ በእግዚኦታ ብቻ የእህል ረድኤት እንደማይወርድ በማመን እግዚኦታው ሳይቋረጥ የርሻ ከብት ቢያልቅ በቁፋሮ እህል መዝራትና ማምረት እንደሚቻል አስገነዘቡ ። ራሳቸውም ምሳሌ በመሆን በእጃቸው ዶማ ይዘው እየቆፈሩ ከላይ እስከታች በማናቸውም ደረጃ የሚገኘው ሁሉም በእጁ እንዲቆፍር አዘው በዚህ ዓመት ታላቅ የቁፋሮና የመዝራት ዘመቻ ሆኖአል ።

የጐጃሙ አለቃ ተክለሥላሴ ስለ እህል ማደል እንደዚህ ሲሉ አትተዋል ።

> .....ዳግማዊ ምኒልክ በጉዞው (በየአምራቹ ገበሬ) ቤት ወታደር ሰደደ ። ሰባለ እህሉ በነፍስ ወከፍ የአንድ ዓመት (እህል) እየተወለት ትርፉን በደብዳቤ አግብቶ (ደረሰኝ እየሰጠ?) ተበድሮ ለደሀ ናኘው። ከዚህ በኋላ (የደበቀው ሁሉ) ወታደር ከሚዘርፈንስ ገበያ ብንሸምተው ይሻለናል እያለ ገበያ አወጣው ። ያን ጊዜ እህል በገበያ ተረፈ ። በአንድ ብር 3 ቁና ተሸመተ ።

ይህን ካስገነዘቡ በኋላ ጸሐፊው ስለዐፄ ምኒልክ ትጋት እንደዚህ ሲሉ ይደመድማሉ ።

ዳግማዊ ምኒልክ ለሕዝቡ ትጋትና ትሕትና አስተማረ ። መጥረቢያ አበጅቶ ካንቻ መታ ። ቁፍሮ (ዶማ) አበጅቶ ዳገት ቆፈረ ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ ሲሠራ እያለ ራስ ቢቶደዱ ደጃዝማች . . . የተሾመ የተሸለመ ሁሉ መኳንንት አይረባ (የማይረባ) ኩራቱን እየተወ በየሀገሩ ካንቻ እየመታ ቁፋሮ እየቆፈረ ሎሌ ገረዱን አተጋው. . . . .[1]

ዳሩ ግን ፣ በዚሁ ጊዜ በሰሜን የሚደረገውን የርስ በርስ ጦርነት ሰው ሁሉ እየሰማ ባገር ላይ እግዚአብሔር ቁጣ እንዳወረደ በሁሉም ዘንድ ተገምቶ ምሕላውም ፣ እግዚኦታውም በተያዘበት ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ ወዳጆቻቸውን ሰብስበው ፣ “ . . . . ጊዜው ረኃብ ሆነ ። እንዳ ልቀር እርስ በርሳቸው ትግሮቹ ጪት ማታ እየተዋጉ ሰዉም መኳንንቱም አለቀ ። እንዳልዘምት ላሙ በሬው አልቋል ፣ ድሀው ይጐዳብኛል። ስለዚህ ተጨንቄያለሁ ፣ ምን ይበጃል . . .” ብለው ጠየቋቸው ። በዚያም ያሉት መኳንንት ፣ “. . . እግዚአብሔር ለፍጥረቱ እርስዎን ዳኛ አድርጎ ሾመ ። እንግዲህ አንድ ሰው እንኳ ቢሞት ዕዳው የርስዎ ነው። ሥርዓተ መንግሥት አድርሰው ወደ ትግሬ ይዝመቱ” ብለው መከሩዋቸው ። ከዚህ በኋላ በንጉሠ ነገሥትነት የሚነግሡበት ድርጅት በየመልኩ መዘጋጀት ጀመረ ።

ታላቅ ዳስ እንጦጦ ላይ ተሠርቶ ፣ ድግሡ በያይነቱ ተደግሶ ፣ በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መኳንንቱና መሳፍንቱ ባሉበት በጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተው በታላቅ ሥነ ሥርዓት ፣ “ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ” ተብለው 25 ዓመት ሙሉ የጠበቁትን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ጫኑ ።

ባለቤታቸው ወይዘሮ ጣይቱ ብጡልም ፣ እንደ ደንቡ የንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓተ ንግሥ በተደረገ በሦስተኛው ቀን በጥቅምት 27 ቀን የእቴጌነት ዘውድ ጫኑ ።[2]

ከዚህ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ምኒልክ ጥቅምት 25 ቀን የራሳቸውን ፣ ጥቅምት 27 ቀን የባለቤታቸውን ሥርዓተ ንግሥ ካከበሩ በኋላ ፣ አጎታቸውን ራስ ዳርጌን ላገር ጥበቃ ትተው ባለቤታቸውን አስከትለው በታኅሣሥ 9 ቀን ከእንጦጦ ወደ ትግሬ ለመሔድ ጉዞ ጀምረው

1 አለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 133—137

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ.40—41



በታኅሣሥ 27 ደሴ ገቡ ። በደሴ የልደትንና የጥምቀትን በዓል ካከበሩ በኋላ ደሴ ላይ እቴጌ ጣይቱን ትተው ጉዟቸውን ቀጠሉ ። ከንጉሠ ነገሥቱ በፊት የወሎው ገዥ ራስ ሚካኤል ፣ የየጁና የበጌምድር ገዥ ራስ ወሌ ፣ የራስ ዳርጌ ልጅ ደጃች ደስታ ፣ የራስ መኰንን ወንድም ደጃች ኃይለማርያም ፣ ቱርክ ባሻ ታምሬና ሌሎችም ቀድመው ትግሬ ግዛት ገብተው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሲጠባበቁ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በጥር 29 ቀን ጉሊማ ደርሰው ከዚያ በየካቲት 16 ቀን መቀሌ ገቡ ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ በየካቲት 20 ቀን ከመቀሌ ተነሥተው በማይ መከደን ፣ በእጉላዕ ፣ በገንፈል አልፈው በየካቲት 25 ቀን አብርሃ ወአጽብሃ ገቡ ። ከዚያም በአጽቢ እንዳሥላሴ ፣ በአጽቢ ደራ ፣ በጸዓዳ አምባ አልፈው ሐረማት በተለይ እጐዴ ከሚባለው ቀበሌ ሰፍረው ሳለ ፣ ሲላላኩ የቆዩት ራስ መንገሻና ራስ አሉላ የመቃወሙ ጉዳይ እንደማያዋጣ በመገንዘብ መጥተው እጅ ነሥተው ገቡላቸው ። ንጉሠ ነገሥቱም ስለ ክብራቸው ጠመንጃም ፣ መድፍም እያስተኮሱ በደስታ ተቀበሏቸው ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በመጀመሪያ ጉዟቸው ጊዜ የቀሩት ሲገቡ ራስ መንገሻ የራስ አሉላንና የራስ ሐጎስን ኃይል በመደገፍ ፣ ለምኒልክ እንደ ሌሎቹ ሳይገቡ ቢቀሩ ማንንም ሊያስገርም አይችልም ። በርሳቸው ስፍራ ያለ ማንም ሰው ሊያደርገው የሚችል ነው ። እንዲያውም ነገሩን የማያመዛዝን ግልፍተኛ ሰው ቢሆን ፣ ጦርነት ጀምሮ ብዙ ሰው ሊያስፈጅ በቻለ ነበር ። በዚህም ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግሬ ከመዝመታቸው በፊት አንድ ጊዜ በኢጣልያ ከተደገፉት ከደጃዝማች ደብብ እርአያ ጋር ፣ ባንድ ወገን ከደጃዝማች ሥዩም አባ ኃያል ጋር ሲዋጉ ቆይተው ፣ አሁን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ተጐናጽፈው በታላቅ ግርማ በብዙ ሠራዊት ታጅበው የመጡትን ምኒልክን መውጋቱ ፈጽሞ አደገኛ አቅዋም መሆኑን ይገነዘቡታል ። ዳግማዊ ምኒልክም ፣ ምንም እንኳን እርሳቸውን ደጅ በመጥናት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በሸዋ የኖሩት እንደ መንገሻ ከሹም ተምቤን ምርጫ ልጅ ካፄ ዮሐንስ እህት ከእቴጌ ድንቅነሽ የሚወለዱት ደጃች ሥዩም አባ ኃያል ባጠገባቸው ቢኖሩም ፣ የንጉሠ ነገሥቱን ያፄ ዮሐንስ ደንበኛ ወራሽ የሆኑትን ራስ መንገሻን ጊዜ ሰጠኝ ብለው ሊያጠፉዋቸው የሚወዱ አይመስሉም ። ያለዚያ በደጃች ሥዩም ግንባር ቀደምትነት የነራስ ሚካኤልን ፣ የነራስ ወሌን ጦር ልከው አጣድፈው ሊያስጠቁዋቸው በቻሉ ነበር ።

በዚህ ፈንታ በትዕግሥት እየጠበቁ በሰላም መንገድ ተላልከው እንዲገቡ አደረጉ ። በገቡም ጊዜ ስለ ክብራቸው መድፍ አስተኩሰው

ያለምንም ወቀሳ ተቀበሏቸው ። ከዚህ በኋላ ተመክሮና ተዘክሮ ለራስ
መንገሻ ከተምቤን ወደ ደቡብ እስከ ተከዜ ያለውን የትግሬን ግዛት ፥
ለደጃች ሥዩም ገብረ ኪዳን (አባ ኃያል) አጋሜን ሰጡ ። ተቀማጭ
ነታቸው ዓድዋ ሆና ከመረብ ወዲያ ባለው አገር ላይ ደጃች መሸሻ
ወርቄን ሾሙ ። የደጃች መሸሻ ወርቄ አሿሿም በኢጣልያ ባለሥ
ልጣኖች ዘንድ እንደ ወኪል ሆነው ስለ ወሰኑም ከልል እንዲጨርሱ
በኢጣልያኖቹና በራስ መንገሻ ፥ በደጃች ሥዩምና በራስ መንገሻ መካ
ከል ጠብ እንዳይነሣ የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ሆነው እንዲጠባበቁ ነው።

በዚህም ጊዜ ፥ ደጃች ሥዩም በሹመቱ ስላልተደሰቱ ፥ ግርግር አን
ሥተው ንጉሠ ነገሥቱ ሲመለሱ ራስ መንገሻን ሊወጉ ነው ስለ
ተባለና ይኸው ስለ ተረጋገጠ ፥ እጃቸው ተይዞ ወደ አዲስ አበባ እንዲ
መለሱና ጠቅላላው የትግሬ ገዥነትም በራስ መንገሻ እጅ እንዲ
ረጋ አደረጉ ። ከሹመቱ በቀር በልዩ ልዩ ሽልማት ራስ መንገሻን
አስደስተው ወደ እንጦጦ ለመመለስ በመጋቢት 11 ቀን ወደ ድንግ
ለት መጡ ። ከዚያም አይበቶ በሰፈሩበት ሰዓት ራስ መንገሻ ለመ
ሸኘት አብረው ተጉዘው ነበርና ከአይበቶ ላይ ተሰናብተው ወደ መቀሌ
ተመለሱ ። ንጉሠ ነገሥቱ መቀሌ ባሉበት ሰዓት ከሮማ የተመለሱት
ደጃች መኰንን መልእክታቸውን ፈጽመው በሌላውም ሁሉ አስደስ
ተው ነበርና በሐረርጌ ላይ ጨርጨር ተጨምሮላቸው የራስነት ማዕ
ረግ ተቀበሉ ።

በዚህ ጊዜ ፥ እቴጌ ጣይቱ ከእንጦጦ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብረው
ተነሥተው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግሬ ሲዘልቁ ፥ እርሳቸው ደሴ ላይ ቀር
ተው በግራ በቀኝ የሸፈተውን እያስወጉ ይጠባበቁ ነበር ። አሁን ንጉሠ
ነገሥቱ ከመቀሌ ተመልሰው ደሴ ላይ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በደስታ
ተገናኙ ። ከደሴም አብረው ተነሥተው በአሸንጌ ፥ በሰላድንጋይ ፥ በአን
ኮበር አድርገው ሰኔ 5 ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።





እቴጌ ጣይቱ ብጡል
ከፒዮኒ ምንቴጋዛ መጽሐፍ



ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ፡
ከአሚ ዶ. ላይቴር

# ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጠብ

# ምዕራፍ ስምንት

## ከውጫሌ ውል ውስጥ 17ኛው አንቀጽ ያበቀለው ጠብ

ሁለቱ ወገኖች የውጫሌን ውል ከተፈራረሙ ወዲህ ፣ ኮንት አንቶኔሊ ራስ መኰንንን እየመራ ወደ ኢጣልያ አገር ሔዶ አብሮ በመመለስ በመቀሉ ከንጉሠ ነገሥቱ ከተገናኘ በኋላ ወደ አገሩ ሔዷል ። በርሱ ምትክ ለዘለቄታ አዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ የወሰኑንም ፣ ሌላውንም ጉዳይ እንዲጨርስ ኮንት አውግስቶ ሳሊምቤኒ አዲስ አበባ ገብቶ በውልና በቀጥታ ስምምነት ያልተቻለውን የወሰን ጉዳይ ባንድ ወገን በገጸ በረከትና በስጦታ ፣ በሌላው ወገን በማስጠንቀቂያና በማስፈራሪያ ለማግኘት በመጣጣር ላይ ይገኛል ። ገጸ በረከቱን ከተቀበለውና ከበላው ውስጥ ፣ "የጣልያን መላከተኛ ቸር ነው ። ደግ ነው ። እጁን ቆርጠው ቢበሉት ቅር አይለውም" የሚል ይኖር ይሆናል እንጂ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ፡ "እባክዎ በኤርትራ የኢጣልያ ወሰን እስከ መረብ ይድረስለት" ብሎ ደፍሮ የሚመክርም ፣ የሚያስታውስም እንደ ሌለ የታወቀ ነው ።

የወሰኑ ጉዳይ በዚህ እንዳለ ፡ ከውጫሌ ውል ውስጥ 17ኛው አንቀጽ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ከወሰኑ የበለጠ ኃይለኛ ጠብ አበቀለ ። እንደሚታወሰው ፣ 17ኛው አንቀጽ የአማርኛው ጽሑፍ የሚለው "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል " ነው ። ይኸንንም አንቀጽ በወዳጅነቱ ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ ፣" ከአውሮፓ ከወንድሜ ከኢጣልያ ንጉሥ ወዲያ ማን አለኝና ነው ጉዳዬን የሚፈጽም ፣ ባይጻፍስ ምን ያደርጋል" ብለውት ሳለ ፣ አንቶኔሊ "ይኽ ቃል ካልተጨመረ የኢጣልያ ንጉሥ እርስዎን ለመርዳት አይመቻቸውም" በሚል ዘዴኛና አጭበርባሪ መልስ በማግባባት ይህቺ ነገረኛ አንቀጽ በውሉ ውስጥ እንድትሰፍር አድርጓል ።

ስለዚህ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ይኸ ቃል የሠፈረበትን የውጫሌን ውል ሲፈርሙ የኢጣልያ መንግሥት በዚህ አንቀጽ አሳቦ ፣ "ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጠባቂነት ውስጥ ነች ። ንጉሠ ነገሥቱም በኢጣሊያ ንጉሥ አማካይነት ካልሆነ በቀር ከማንም የመንግሥት መሪ ጋር ሊጻጻፉም ሊዋዋሉም አይችሉም" በሚል ትርጉም ይከራከረኛል ብለው በፍጹም አላሰቡትም ።

ኮንት አንቶኔሊ ፣ ከግራዝማች ዮሴፍና ከነአቶ ገብርኤል ናደው ጋር ሆኖ ኢትዮጵያውያኑን በስጦታም ፣ በብድርም ፣ በግብገርም እያንከባከበ ወደ ኢጣልያ የተረጐመው ቃሉና መንፈሱ ካማርኛው ለየት ብሎ ሱራንና አለቆቹን እነክሪስፒን በሚያስደስት መንገድ ሆኖ እንደዚህ ይላል ።

"Sua Maesta, il Re dei Re d'Etiopia consente di servirsi del Governo di S. M. il Re d' Italia a per tutte le trattazioni di affari che avesse con altre potenze o Governi"

የዚህም የአማርኛው ትክክለኛ ትርጉም ፣ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ኃያላን ወይም መንግሥታት ጋር ለሚዋዋሉት ጉዳይ ሁሉ በግርማዊ የኢጣልያ ንጉሠ ነገሥት (አማካይነት) ለመጠቀም እሺ ብለዋል" የሚል ነው ።

"በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል" ማለትና ፣ "ለመጠቀም እሺ ብለዋል" ማለት ልዩነት አለው ። እሺታ ያለቀለት ሲሆን ፣ ይቻላል ማለት ግን የተንጠለጠለና ሊሆንም የሚችል ነገር እንዳለበት ያሳያል ። "... ለሚዋዋሉት ጉዳይ ሁሉ..." ማለትና "... ለሚፈልጉት ጉዳይ ..." ማለትም እንደዚሁ ልዩነት አለው ።

የሆነ ሆኖ ፣ አንቶኔሊ ገና ንጉሡ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ከመጫናቸው በፊት ይኸን የውል አሳብ ይዞ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብሮ እየተጓዘ ነበር ። እነራስ መንገሻ ተጠብቀው ሳይገቡ ቀርተው ከወሎ

1 Crispi e Menelich C. Zaghi, Chap. VI - La Prima Gueraa d' Cr.spi, Chap. vl - Italia ed Etiopia PP. 1—11



ግዛት ወደ ሸዋ ለመመለስ በውጫሌ ላይ በሠፈሩበት ጊዜ እንደ ምንም ጐትጉቶና አግባብቶ ውሉን ከፈረሙና በንጉሠ ነገሥቱ ማኅተም ካሳተመ በኋላ ፣ ከራስ መኰንን ጋር ወደ ኢጣልያ ሔዶ ይኸን ውል ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፍራንቼስኮ ክሪስፒ ሰጠው ። እርሱም በዚህ ጊዜ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ደርቦ ይሠራ ነበርና በውሉ ተደሰተ ። አንቶኔሊም ይኸን ጉዳይ ወደ ፍጻሜ በማድረሱ ብዙ ክብር ፣ ሹመትና ጥቅም አግኝቶበታል ።

ክሪስፒ ፣ የዚህን ውል በተለይ በ17ኛው አንቀጽ ላይ የተጻፈውን አባሪ አድርጎ በበርሊን እ.ኤ.አ. በ1885 ዓ. ም. አፍሪካን ለመከፋፈል በተደረገው ስምምነት መሠረት በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ ፣ በአሜሪካ ፣ በመስኮብ ፣ በጀርመን ፣ በቱርክ ፣ በነምሳ ፣ በኤስፓኝ በፖርቱጋል ፣ በዴንማርክና በስዊድን አገር ላሉት አምባሳደሮቹና ጉዳይ ፈጻሚዎቹ ደብዳቤ በመላክ ለየተወከሉበት መንግሥታት በይፋ እንዲያስታውቁ አደረገ ። ይኸውም በግልጽ አነጋገር ፣ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጠባቂነት ሥር ለመሆን ፈቅዳለችና ለወደፊቱ ከርሷ ጋር ሌሎች መንግሥታት የሚያደርጉት ማናቸውም ግንኙነት ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት በኩል እየተላለፈ መፈቀድ አለበት የሚል ነው ።

እ.ኤ.አ የካቲት 25 ቀን 1885 ዓ. ም ቅኝ አገር የሌላቸውም ፣ ያላቸውም ኃያላን መንግሥታት በበርሊን ተሰብስበው ስለቅኝ አገዛዝ ንግግር አድርገው ከተስማሙባቸው ጉዳዮች ውስጥ ፫ኛው አንቀጽ ፣ "አንድ ኃያል የራሱን መብት ለመቆጣጠር እንዲመቸው ፣ ሌላው ኃያል መንግሥት በአፍሪካ ውስጥ አንድ አገር በያዘ ጊዜ ይህን ውል ለተፈራረሙት ኃያላን በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት"[1] የሚል ነው ። አሁንም የኢጣልያ መንግሥት በማጭበርበር የደነቀረው ይህ 17ኛው አንቀጽ ፣ በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነት መብት እንደሚፈቅድለት በመቁጠር ለነዚህ ኃያላን በወኪሎቹ በኩል አቅርቦ የመቀበል መልስ እንዲመጣለት ወኪሎቹን በቴሌግራም ያጣድፍ ነበር ። ወኪሎቹም ያሉበትን አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችን ቀጠሮ እየጠየቁ የማወቁ መልስ ለኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቶሎ እንዲላክ ይወተውቱ ዠመር ።[2]

ለኢትዮጵያ ወዳጅነት የሚሰማቸው እንደ ፈረንሳይ ፣ እንደ መስኮብ ያሉትና ሌሎችም እንደ ቱርክ ያሉት አገሮች ፣ "እንደ ኢትዮጵያ ነጻ ሆኖ የኖረ አገር የሌላውን አገር የበላይ ጠባቂነት በፈቃዱ

1 Storia Della Conqusta Dell' Africa - R. Mazzucconi PP. 195 - 196.

2 La prima Guerra d' Africa . . .PP. 320- 254.

እንዴት ሊቀበል ይችላል” የሚል ጥርጣሬ ስለ አደረባቸው ፤ ሁኔታውን ከምንጩ ከአዲስ አበባ ለማጣራት ሲቆዩ በብዙ ውትወታ ከጀርመንና ከአንዳንድ አገሮች የማወቅ መልስ መጣለት ። የእንግሊዝ መንግሥት መልስም ፤ ዘግይቶ ሲመጣለት እርሱም የመለሰው ቃል ባወላዋይ ሁኔታ ነው ።

በዚሁ ጊዜ ፤ ዳግማዊ ምኒልክ በበኩላቸው በእንጦጦ የንጉሠ ነገሥት ሥርዓተ ንግሣቸውን ከፈጸሙ በኋላ ፤ ለፈረንሳይ መንግሥት ፕሬዘዳንት ለሙሴ ሲዲ ካርኖ ፤ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ፤ ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት ጉዮም (ዊልሄልም) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን እንዲያውቁላቸው ደብዳቤ አስተላለፉ ። ከደብዳቤዎቹ ውስጥ ላንድ መሪ የተጻፈው ከሌላው በጥቃቅን ነገር ይለያይ እንጂ በጠቅላላው ተመሳሳይ ነው ። በደብዳቤያቸውም የመለከቷቸው ጉዳዮች ፤

1. ባፄ ዮሐንስ ፈንታ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን እነዚህ መንግሥታት እንዲያውቁላቸው ፤
2. ያገራቸውን ጸጥታ ለመጠበቅ እንዲመቻቸው በብሩክሴል (ቤልዥክ) የተደረገው የጦር መሣሪያው እገዳ እንዲነሣላቸው ፤ *
3. በኃያላኑ መንግሥታትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የወዳጅነትና የንግድ ሥራ እንዲስፋፋ የሚሉ ይገኙባቸዋል ።[1]

በተለይ ወደ ፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ወደ ሙሴ ካርኖ የተጻፈው ከሁሉም ሰፋ ያለ ሲሆን ፤ ደብዳቤውንም ይዞ የሔደው በንግድ ረዥም ጊዜ በኢትዮጵያ የተቀመጠው የኢጣልያንንም ይዞታ ከሚቃወሙት ውስጥ አንደኛው ሙሴ ሳቩሬ አርማን የሚባለው የፈንሳይ ተወላጅ ነው። እርሱም የምኒልክን ደብዳቤ ይዞ ወደ ፓሪስ ከሔደ በኋላ ፤ በዝርዝር ራፖር ለፕሬዚዳንቱ አቅርቦ ያመጣው መልስ ፤ በሙሉ የምኒልክን ምኞት የሚያሟላና የኢጣልያንን ምኞት የሚያግድ ነበር ።

ከእንግሊዝ መንግሥት የመጣው መልስ ፤ የኢጣልያ መንግሥት ያስተላለፈለትን 17ኛውን አንቀጽ ጠቅሶ በጠቅላላ አነጋገሩ ያው የማወቅ

* ኃያላኑ አፍሪካን ያለምንም ተከላካይ እንደ ልባቸው ለመግዛት እንዲመቻቸው ወደ አፍሪካም ፤ ወደ ሌላው ምሥራቅ አገር መሣሪያ እንዳይገባ በብሩክሴል እ.ኤ.አ. በ1889 ዓ.ም. ስምምነት አድርገው ነበር ።

1 Crispi e Menelich . . .pp. 397-406



ያህል ነው ። ዐፄ ምኒልክንና እቴጌ ጣይቱን በተለይ በጣም ያናደዳቸው ግን ፤ ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት የመጣው መልስ ነው ። “ በውጫሌ ከተዋዋሉት ውስጥ 17ኛውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ በኢጣልያ መንግሥት አማካይነት ንጉሠ ነገሥት መሆንዎ ካልተላለፈልን አንቀበልም ” ከማለቱ በቀር አድራሻውን ፤ “ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ” በማለት ፋንታ ፤ “ ለልዑል ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ” የሚል ቃል አለበት ።[1]

የኢጣልያ የውሉ አተረጓጐም በጠቅላላው የአገሪቱን በተለይ የንጉሠ ነገሥቱን ክብር በቀጥታ የሚነካ ስለሆነ ፤ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ (1882 ዓ.ም.) እስከ ዓድዋ ጠርነት ድረስ (1888 ዓ.ም.) በዐፄ ምኒልክና በኢጣልያ መሪዎች መካከል አንድ ጊዜ የላላ ፤ ሌላ ጊዜ የከረረ ጠብና ክርክር ሲካሔድ ቆይቷል ።

ባንድ ወገን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ዐፄ ምኒልክን እንደ ውል አፍራሽ በመቁጠር ፤ “ ውሉን አፍርሰው እንደምን ለውጭ አገር መንግሥታት መሪዎች ጻፉ ” እያለ አዲስ አበባ ያለውን ወኪሉን ይጠይቃል ። ንጉሠ ነገሥቱ በበኩላቸው ደግሞ ፤ ምንም እንኳ የኢጣልያ መንግሥት 17ኛውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ይኸን ያልታሰበ አደገኛ ሁኔታ መፍጠሩ ቢገርማቸውም ፤ ነገሩን በተለመደ ትዕግሥታቸው በሰላም ለመጨረስ አሰቡ ። ስለዚህ ጉዳይ ፤ ለኢጣልያ ንጉሥ አንድ ደብዳቤ በመላክ የኢጣልያ መንግሥት ስለ17ኛው አንቀጽ ለየመንግሥታቱ ያሳለፈውን አተረጓጐም ስሕተት መሆኑን በማሳሰብ ገለጹ ። በደብዳቤያቸው ውስጥ የጠቀሱት ፍሬ ነገር ፤

> የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆኔን ለወዳጆቼ ለውጭ መንግሥታት አስተላልፈው ስለነበረው የመጣልኝ መልስ አዋራጅ ነገር ይገኝበታል ። ሰበቡም 17ኛው አንቀጽ ነው ። ይኸም አንቀጽ የኢጣልያንኛው አባባል ከአማርኛው የተለየ ነው ። ያንንም ውል ሳደርግ በአውሮፓ የምንዋዋለው ምስጢሩ የጠበቀ እንዲሆንና እንዲቃና ስል አደረግሁት እንጂ ፤ ምንም የሚያስገድደኝ ነገር የለም ። አንድ ነጻ የሆነ አገር በወዳጅነት ካልሆነ በቀር ምንም የሚያስገድደው እንደሌለ ግርማዊነትዎ ያውቀዋል . . . ስለዚህ ለወዳጅዎ ክብር ሲሉ ይህ አንቀጽ እንዲታረምና ስላስተላለፉላቸው የወዳጅ አገሮች ይኸንኑ ስሕተት ገልጸው እንደሚጽፉላቸው ተስፋ አለኝ ።

የሚል ነው ። ለዚሁ መልስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከውጭ ጉዳይና ከመከላከያ ሚኒስትሮቹ ጋር ተማክሮ ያቀረበለትን የኢጣልያ ንጉሥም ተስማምቶበት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የደብዳቤ መልስ ላከላቸው ።

1 Italia ed Etiopia - conti - Rossini PP. 9-15

ኡምቤርቶ ቀዳማዊ በጸጋ እግዚአብሔር የኢጣሊያ ንጉሥ ለፍጹም ወዳጅ ለዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ለላምታ ፣ ግርማዊነትዎ በውጫሌ ስለ ተደረገው ውል ስለ 17ኛው አንቀጽ አተረጓጐም ማዘንዎን በ19 ነሐሴ ጽፌውልኛል ። ስለዚህና ስለሌላውም ጉዳይ ሁሉ ከኛ መላከተኛ ከፒዬትሮ አንቶኔሊ ጋር በመነጋገር አከራካሪውንና አወላዋዩን ቃል ወደ ብርሃን ለማምጣት ይቻላል ። ይኸው አንቀጽ ለኃያላኑ የአውሮፓ መንግሥታት ሊተላለፍ የቻለው ከርስዎ መላከተኛ ከራስ መኰንን ጋር ስምምነት ከተደረገ በኋላ ነው ። ይኸም የተደረገው በአውሮፓ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት መብት ለመደገፍ እንዲመቸን ነው ። በአሁኑ ጊዜ አውሮፓ ላይ አፍሪካን ለማደራጀት* በሚታሰብበት ጊዜ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛት አንድነት በሚጠቅመው መንገድ ተነጋግሮ ወደ አንድ ጠቅላላ ስምምነት መድረሱ በግፅማዊነትዎ ዘንድ ጥቅሙ እንደሚታወቅ እርግጠኛ ነኝ ።

ላንድ ክርስቲያንና ወዳጅ ለሆነ አገር የምናደርገው ድጋፍ መከበር እንደሚገባው የኢትዮጵያ መሬትም ፣ መንግሥቱም ንጉሠ ነገሥቱም እንዳይነኩ ለማድረግ እኛና መንግሥታችን በትጋት እንደምንሠራ እያረጋገጥኩልዎ ፣ ግርማዊነትዎ በምናደርገው ሁሉ እምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ተጻፈ በሞንዛ እ. ኤ. አ. ጥቅምት 28 ቀን 1890 [1]

የዚህ ደብዳቤ አሳብ ፣ በአፍሪካ ቅኝ አገር የሚፈልጉት ኃያላን መንግሥታት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ግዛት እንዳይቀሙ ፣ የንጉሠ ነገሥቱን የግዛት መብት እንዳይተናኮሉ እኛ እንጠብቃለንና ይኸንኑ የጠባቂነት መብት የሚፈቅድልንን 17ኛውን አንቀጽ ተቀበሉ የሚል ነው ። የውስጡ አሳብ ደግሞ ፣ ሌሎች ኃያላን የቅኝ አገር ግዛት ጠግበ ዋልና እኛ ምንም ስለሌለን እኛው ግዛታችሁን ወስደንና በበላይ ሆነን እንድናስተዳድራችሁ ተቀበሉ የሚል ነው ። እንደ እውነቱ በዚህ ጊዜ እንግሊዝም ፣ ፈረንሳይም ፣ በጥቅምና በንግድ ከመተሳሰር በቀር ኢትዮጵያን በግልጽ ቅኝ አገር አድርጎ ለመግዛት ምንም ዓይነት ምኞት አልነበራቸውም ።

ይኸ ቢሆን ኖሮ ከ12 ዓመታት በፊት እንግሊዝ መቅደላ ድረስ ገብቶ ለምን ለቆ ይወጣ ነበር ? ፈረንሳይም እንኳን ለመውረር በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ደጋፊነቷ የታወቀ ስለሆነ ፣ ኢጣልያኖችም የእኛን አያያዝ የምታሰናክልብን ፈረንሳይ ናት ይሉ ነበር ።

---

* በኢጣልያንኛ Sulla sistemazione delle questioni Africanj የሚለው ግልጽ ትርጉሙ አፍሪካን ለመከፋፈል ማለት ነው ።

1 Storia diplomatic adurantel regno Ji Menelik -C- Rossetti PP. 78-83



ስለዚህ ፣ በግልጽ አነጋገር ኢጣልያ እረኛ ሆኜ ልጠብቃችሁ ማለት ፣ ሌላ በላተኛ አውሬ ሳይኖር እኔው ጠብቄ እኔው ልብላችሁ የማለት የተኩላ አነጋገር ነው ። ዳሩ ግን ፣ ደግነቱ በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ መሪዎች ለተኩላ እረኛ የሚመቹ ሳይሆኑ እንደ ኢዮብ ታጋሽ ሆነው ፣ ሲቆጡ ደግሞ እንደ ነብር ወይም እንደ አንበሳ የሚዋጉ ነበሩ ። ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ቅኝ ግዛት ለመመሥረት የተነሣችበት ዓላማ ባለመሳካቱ ዕድለቢስ ሆናለች ማለት ይቻላል ።

የኢጣልያ ንጉሥ በላከው ደብዳቤ ላይ ፣ “ 17ኛው አንቀጽ ለኃያላኑ ለመተላለፍ የቻለው ከመልክተኛዎ ከራስ መኰንን ጋር ስምምነት ከተደረገ በኋላ ነው ” የሚል ቃል ይገኝበታል ። ሌሎችም ጣልያኖች ይኸንኑ ጉዳይ በመጽሐፍ ሲያስፍሩ ፣ ራስ መኰንንም ግራዝማች ዮሴፍም ሮማ በጉብኝት ላይ በነበሩበት ጊዜ ቃሉ ወደ ኃያላኑ ከመተላለፉ በፊት በየጋዜጣው ሲጻፍ ሰምተውና አንብበው ሳለ ፣ በምንም አኳኋን አልተቃወሙም እያሉ አመካኝተዋል ። እነራስ መኰንን ሮማ በነበሩበት ጊዜ ፣ “ በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ መሠረት በኢትዮጵያ ላይ የጠባቂነታችን መብት ይታወቅ ዘንድ ለኃያላኑ መንግሥታት ልናስተላልፍ ነው ። ይኸንንም ካስተላለፍን በኋላ ፣ በኛ አማካይነት ካልሆነ በቀር ለወደፊቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ መንግሥታት ጋር እየተጻጻፈ ጉዳዩን ሊጨርስ አይችልም ” ብለው በግልጽ እንዳልነገሯቸው የታወቀ ነው ። ይኸንንም ቢነግሯቸው እንደ ማይቀበሏቸው ኢጣልያኖቹ ራሳቸው ያውቁታል ። ነገር ግን ፣ በማጭበርበር መንገድ ነገሩን እንደ ተቀበሉ አስመስለው ተከራክረውበታል ማለት ነው ።

በኢጣልያንኛ የተጻፈውን ግን ቢያስተላልፉም ፣ በጋዜጣ ቢጽፉትም ፣ ይኸንኑ ቃል ልናስተላልፈው ነው ብለው ቢነግሯቸውም ፣ የግራዝማች ዮሴፍም ዕውቀት በመጠኑ ፈረንሳይኛ እንጂ ጣልያንኛ ስላልሆነ ፣ በምንም አኳኋን ቃሉንም መንፈሱንም ራሳቸው ተረድተው ምንም የውጭ አገር ቋንቋ ለማያውቁት ለራስ መኰንን አስረድተው እሺ ይሁን ሊያሰኟቸው አይችሉም ። በሮማ የሚታተመውንም የፈረንሳይ ጋዜጣ አፈላልገው ማንበቡን ፣ የአንቀጹንም ስሜትና ተንኰሉን በግልጽ ሊረዱት አይችሉም ።

በዚህም ላይ ፣ ራስ መኰንን ከነተከታዮቻቸው ሮማ ከደረሱ ዠምሮ እስኪመለሱ ድረስ የተደረገላቸው አቀባበልና መተስተንግዶ ፣ የመጠጡና የመብሉ ዓይነት ፣ ያረፉበት የቪላ ሚራፊዮሪ ሕንፃ ፣ የተመደበላቸው ክፍል በሥጋጃና በከፋይ የተንቆጠቆጠ ፣ ጣራና ግድግዳው

በወርቅና በብር ቅብ የሚያብረቀርቅ ፣ አልጋው የሚያረገርግ ፣ ፍራሹና የውስጥ ልብሱ ከነብርድ ልብሱ የሚያማምርና ከኢትዮጵያ ኑሮና ምቾት ጋር በፍጹም የተራራቀ ነበር ። ከኢትዮጵያ ወጥቶ የፈረንጅን አገር ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላልቀመሰ ሁሉ በደስታና በሽብር የተበረዘ ስሜትን መስጠቱ የታወቀ ነው ። ይኸን በመሰለ አዋካቢ መስተንግዶና አዘናጊ ማቀማጠል መካከል የራሱን ጥቅም የሚደነቅር ጋባዥም አጭበርባሪ እንጂ ፣ እውነተኛ ጋባዥና ሐቀኛ ወዳጅ አይባልም ። ከመስተንግዶውም ጋር ከተሞችን ፣ ፋብሪካዎችን ፣ ድርጅቶችን በማስጐብኘት የዕረፍት ጊዜ አግኝተው በጽሞና ለማሰብ እንደማይችሉ ያደረጉዋቸው ይመስላል ።

ይኸውም ሆኖ ፣ በጉብኝቱ ወቅት የዚሁ አንቀጽ ጉዳይ በጋዜጣ መጻፉን ለትምህርት የተላኩትና ኢጣልያንኛ ደህና አድርገው የሚያውቁት የዘጌው ወጣት አፈወርቅ እንብበው ፣ "ምነው እንደዚህ ያለ ከፉ ነገር ተደረገ" ብለው ለራስ መኰንን አስረድተዋል ። ራስ መኰንንም ከኮንት አንቶኔሊ ጋር በዚህ ነገር ተጣልተዋል ። የዚህን ነገር አፈወርቅ እንዳይናገሩ አንቶኔሊ በገንዘብ አባብሏቸው እንደ ነበርና ላገራቸው ሲሉ ተቆርቁረው በመናገራቸው ሮማ ላይ ብዙ ውርደትና ግፍ እንደ ደረሰባቸው ይገልጻሉ[1] ። በጉዳዩ ራስ መኰንን ትንሽ የጽሑፍ ማስታወሻ ትተዉልን ቢሆን ኖሮ ፣ ሁኔታውን በግልጽ ለመመልከት ይረዳን ነበር ። ራሳቸውም ለመጻፍ ባይችሉም በዚያን ዘመን ያልተለመደ ሆኖ ነው እንጂ ሊያጽፉት በቻሉ ነበር ።

ዋናው ፍሬ ነገር የአፈ ወርቅ ማስታወስ ፣ የራስ መኰንን ማወቅና መከራከር ሳይሆን ኢጣልያ በዚህ ወቅት ቅኝ አገር ለማግኘት ቆርጣ መነሣቷ ፣ የርሷ በኃያላን የውል ጓደኞቿ በእንግሊዝና በጀርመን መንግሥታት መደገፏ ፣ ከሠለጠኑት መንግሥታት መቆጠሯና የጦር መሣሪያዋን ራሷ ለመሥራት በመቻሏ ነው ። በዚህ ቁርጠኛ ምኞቷ ዝርባ የምታቀርበው የማወናበድና የማጭበርበር ምክንያት ግን ፣ ለሰበብ እንዲረዳ "አታደፍርሽብኝ" ነው እንጂ ፣ "የበላይ ጠባቂ ሆኛለሁ" ለማለት የውጫሌው ውል አንቀጹም ፣ ትርጒሙም እንደማያስሔድ ራሳቸው ኢጣልያኖቹ ያውቃታል ።

አውግስቶ ሳሊምቤኒ ፣ አዲስ አበባ ሆኖ ላንድ በኢጣልያ አገር ለሚገኘው ጄኔራል ሉቻኖ ዳል ቬርሜ ለሚባለው ወዳጁ በግል ሲጽፍ እንደዚህ ብሎታል *።

---

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 70—71

* ሳሊምቤኒ አማርኛ ማንበብ መጻፍም ይችላል ።



. . . . በበርሊኑ ስምምነት መሠረት ለኃያላኑ የተላለፈው 17ኛው አንቀጽ የውጫሌ ውል በውስጡ ዝብርቅ ነገር አለበት ። ከአውሮፓ ጋር ለሚያደርጉት ነገር በኢጣልያ በኩል ለማድረግ ምኒልክ ግዴታ አለባቸው የተባለው በፍጹም ሐሰት ነው ። ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ መኰንን ፣ ከዳጃች መሸሻ ወርቄና ከግራዝማች ዮሴፍ ጋር ሆነው አንብበው እርመው ወደ ኢጣልያ እንዲተረጐም ያደረጉት ያማርኛው ጽሑፍ በኢጣልያ ድጋፍ ለማድረግ ይቻላቸዋል ይላል እንጂ ግዴታ የለበትም ። ይቻላቸዋል ሲልም ትርጒሙ ቢፈቅድ ማለትን በውስጡ የሚያስገነዝብ ነው ። በኋላ ግን ፣ ወደ ኢጣልያንኛ ሲተረጐም ከእውነተኛ ቃል ወጣ ብሎ የኢጣልያን መንግሥት ሊያስደስት በሚችል መንገድ ተተርጒሞ ተላለፈ . . .[1]

ሲል ሐቁን ጽፎታል ። ሳሊምቤኒ በዐይኑ ያየውን ጽሑፍና የተረዳውን ትርጒም ለወዳጁ በግል ሲጽፍ ፣ ከሌላው ወዳጁ ከአንቶኔሊ ላለመቀያየም የበላይ ባለሥልጣኖቹ በጋለ ምኞት የጨበጡትን ክርክር አቃውሶ ከደረጃው ላለመዋረድ ሲል ይኸን እውነተኛ አሳቡን በግልጽ በጋዜጣ አልጻፈም ። አብራርቶ በገሃድ መናገርም አልቻለም ። ለጠቅላይ ሚኒስትሩም በዚህ ዓይነት አልገለጸለትም ።

የኢጣልያ መሪዎች ፣ ቅኝ አገር መያዝ ስለ አማራቸው ጥቁር የተባለውን ሁሉ በመናቅና በጦር ኃይላቸው በመመካት በኤርትራ የሚገኙ የጦር አለቆች ፣ "ግማሹን ወርረን ቅኝ አገር እናድርገው ፣ በተረፈው ላይ ባላባቶቹን እንዳሉ ትተን እርስ በርስ እያዋጋን የበላይ ጠባቂ ሆነን እናስተዳድረው" የሚለውን አሳብ ተቀብለዋል ።

በመሆኑም ንጉሡ ኡምቤርቶ ፣ "በዘመኔ ካባቶቼ የበለጠ የኢጣልያን ግዛት አስፋፋለሁ" በማለት ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒም ፣ "በኔ መሪነት ለኢጣልያ ይኸን አውራጃ አስገኘሁ ! ይኸን የመሰለውን ለኢጣልያ የሚጠቅም ውል አስፈጸምሁ" እያለ በፖለቲካ ባላጋራዎቹ ፊት ለፓርላማው ለመፎከርና በሚጥመው በጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ሥልጣን ለመቆየት ፣ አንቶኔሊም ወደ ካቢኔ ሚኒስትር ደረጃ ለመድረስ የሆነውንም ያልሆነውንም ፣ ሊሆን የማይችለውንም እርስ በርስ በመተላለል ሌላውንም ለማታለል በመሞከር ምኞታቸውን ለማርካት ይመኛሉ ። ያን ጊዜ የተጻጻፉት ሰነድ ሁሉ ዛሬ ሲነበብ የሚያሳየን ሥዕል ይኸንን ዓይነት መልክ ያለው ነው ።

በእውነትም ከውጫሌ ውል በኋላ ፣ ምንም እንኳን ገና ጉዳዩ በብዙ ውዝግብ የታጠረ ቢሆን ፣ በርሱ እግር ሳሊምቤኒ ተልኮና አንቶኔሊ ከኢትዮጵያ ወደ ሮማ ተጠርቶ ከሔደ በኋላ እስካሁን ላከናወነው

---

2 Crispi e Menelich . . .p. 18[illegible]

ዋጋ በመስጠት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የምክትል ሚኒስት
ርነት ደረጃ ተሰጠው ። ምኞቱም ይኸው ነበር ። ያለዚያ ግን ፣ የነጻነት
ዘመኑን ከሦስት ሺ ዓመት ዠምሮ የሚቆጥር ሕዝብ ትውልዱን
ከዳዊት ከሰሎሞን የዘር ግንድ የሚስብ ንጉሠ ነገሥት በጦር ሜዳ
ተዋግቶ ሳይሸነፍ የሳቮያ ኢጣልያዊ ነጋሢ ከበላዬ ሆኖ በጠባቂነት
ያስተዳድረኝ ብሎ በፈቃዱ ነጻነቱን ትቶ ተገዥ ልሁን ብሎ እንደ
ምን ይዋዋላል? እርሱስ ቢፈቅድ መሳፍንቱና መኳንንቱ እንደምን
ይቀበሉታል?

የሆነ ሆኖ ፣ በዚህ አንቀጽ ሰበብ በኢትዮጵያ ላይ የበላይነቱን
ለማስታወቅ ለየመንግሥታቱ ስለ አስተላለፈ ፣ መላክተኞቹ እነሳሊም
ቤኒ ያላመኑበትን እንዳመኑበት መስለው ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን አን
ቀጽ እንዲቀበሉ ማባበልም ማስፈራራትም ባለበት መንገድ ሲጣጣሩ
ይታያል ። ባንድ ወገን ፣ "ይኸን አንቀጽ ካልተቀበሉ በትግሬ በኩል
እነራስ መንገሻ ፣ እነራስ አሉላ ቢሸፍቱ ፣ በጐንደር ደርቡሽ ብቅ ብሎ
ቢወጋዎ ፣ በዘይላ በኩል እንግሊዞች ቢነሡብዎና ሐረርጌን ቢወሩ ፣
የኢጣልያ መንግሥት እርስዎን በመደገፍ ወረራውን ማገድ አይሆ
ንለትምና ቢቀበሉ ይሻላል" እያሉ በልሰላሴ እንዲመክሩና በወዳጅ
በኩል እንዲያስመክሩ ሲታዘዙ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ በዚያው ሰዓት
ኤርትራ ያሉት የጦር አለቆችና በያለበት የተሠራጩት የኢጣልያ
ወኪሎች በምኒልክ ላይ የሚነሡ መሳፍንትና መኳንንትን በማነፍነፍና
በመገፋፋት ላይ ይገኛሉ ።

በዚህም ጊዜ ፣ ባዬ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ከብዙ ጊዜ ዠም
ረው ከንጉሠ ነገሥቱ ተዋውቀው የተላመዱ ፈረንሳዮችና መስኮቦች ፣
በፊተኛው ጊዜ ኢጣልያኖቹ የምኒልክ ባለሟል ሆነው ሽር ጉድ ሲሉ ፣
በቅርብም በሩቅም ሆነው በቅናት ይመለከቱ ነበር ። ባሁኑ ጊዜ ደግሞ
የኢጣልያ መንግሥት በዚህ በአንቀጽ 17 የተነሣ ፣ ከኢትዮጵያ መንግ
ሥት ጋር ሲጣላ እነርሱ በተራቸው ባለሟል ሆነው በኢጣልያ በኩል
የቀረበውን የውሉን ጥያቄ አደገኛነቱን በማብራራት ጭምር ከነራስ
መኰንን ፣ ከነደጃች መሸሻ ፣ ከነግራዝማች ዮሴፍ ጋር በመተባበር
ኢጣልያኖችን ይቃወሙ ዠመር ። ቀድሞ ከኢጣልያ ወኪሎች ጋር
በስጦታና በግብዣ የተወዳጀው ግሪኩም ፣ አርመኑም ሁሉ ባሁኑ
ጊዜ ጐራውን ለውጦ ስለ ኢትዮጵያ ተከራካሪና መካር ሆኗል ።
በዚህ ዓይነት ፣ ኢትዮጵያ በጠላቷ ጐን ወዳጅ አላጣችም ማለት ነው ።
በተለይ በፈረንሳይና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል ባለው ፉክክ
ርና ባላንጣነት የምኒልክ መንግሥት ደህና አድርጎ ተጠቅሞበታል
ማለት ይቻላል ።



በ1887 እ.ኤ.አ. ጀርመን ፣ ነምሳ (አውስትሪያ) ፣ ኢጣልያ
ሦስቱ የቃል ኪዳን ዝምድና መሥርተው ጠላት ቢነሣ አንድነት ሊመ
ልሱ ተዋውለው ነበር ። ይኸን ውል እንግሊዝ በመልካም ዐይን
ተመልክቶ ከቀድሞ ዠምሮ የኢጣልያን ወደ ምጥዋ መግባቱንም
መስፋፋቱንም እንደ ደገፈ ፣ በዚህ አንቀጽ የተነሣውንም ክርክር እንደ
ጀርመን ባይሆንም በመጠኑ ደግፏል ። የፈረንሳይ መንግሥት ግን
እንግሊዝ ኢጣልያንን የሚደግፈው ፣ የፈረንሳይን ኃይል ለማዳከም
መሆኑንና የሦስቱም አገሮች የቃል ኪዳን ጓደኝነት ምንም እንኳን
በግልጽ ባይጠቀስ በፈረንሣይ ላይ መሆኑን ስለሚያውቅ ፣ አሁን
ምኒልክና የኢጣልያ መንግሥት በዚህ ዓይነት ሲቀያየሙ ፣ ምኒልክን
ለመርዳት የኢጣልያንን በኢትዮጵያ ላይ መስፋፋት ለመቃወም አመቺ
ሆነለት ።

ሙሴ ሳቩሬ ፣ ወደ ፕሬዚዳንት ካርኖ ተልከው ከሔዱ በኋላ ባዬ
ምኒልክ ዘንድ የታወቁት በአሰብ የሳሊኒን የጨው ማዕድን ለማስኬድ
ፈቃድ ያገኙት ሙሴ ሸፍኔ ሌዎ ከፈረንሳዊ ፕሬዚዳንት ዘንድ የወ
ዳጅነትና የድጋፍ መልስ ከመጣ በኋላ ፣ ታላቁን የፈረንሳይን የሌዥ
ዎን ዶነር የኮርዶን ኒሻን ለንጉሠ ነገሥቱ በፕሬዚዳንቱ ስም ባን
ገታቸው ሲያጠልቁና በካባቸው ላይ ሲያደርጉላቸው ፣ ይህ ታላቅ ኒሻን
ነጻ ለሆኑ አገሮች መሪዎች ብቻ የሚሰጥ መሆኑን ባንደበታቸው
ገልጸውላቸዋል ። እንደዚሁም በ23,000 ማሪያቴሬዛ ብር ከኢጣልያ
ኖቹ በተሻለ ዋጋ ዐሥር * ዘመናዊና ፈጣን የሆነ ሆችኪስ የሚ
ባል መድፍ አምጥተው ሸጡላቸው ።[1] በዚህ ዓይነት ፣ ከፖለቲካው
ክርክር ጐን ምኒልክ የጦር ሠራዊታቸውን በዘመናዊ የጦር መሣ
ሪያ የማስታጠቁን ጉዳይ እንዳልዘነጉት ለማወቅ ይቻላል ።

በዚህ ጊዜ የኢጣልያ ጋዜጦች ፣ "ዳግማዊ ምኒልክ ውል የማያ
ከብሩ ፣ አገሪቱ ሥርዓት የማታውቅ ፣ ሕዝቡ ገና ካረመኔነት ያልተላ
ቀቀ ፣ ሽፍታና የባሪያ ንግድ የሚያዘወትር ነውና ልናሠለጥነው ይገ
ባል" በሚል መንፈስ እየጻፉ በአውሮፓ ፕሮፓጋንዳ ያደርጉ ነበር ።
አዲስ አበባ የሚቀመጠው ሞንዶን ቪዳዬ የሚባለው ሌላው የፈረን
ሣይ ተወላጅ 'ለታ' ለሚባለው የፈረንሳይ ጋዜጣ ወኪል ሆኖ ለንጉሠ
ነገሥቱ መካርም ወዳጅም ነበር ። በአውሮፓ የተደረገውን ፣ በኢጣልያ
መንግሥትና በምክር ቤቱ የተባለውን ወደ አማርኛ እየተረጐመ
ለንጉሠ ነገሥቱ ከማቅረብና ከማስረዳት ጋር በፈረንሣይኛ ቋንቋ

* የመድፎቹን ቁጥር ዴልቦካ 15 አድርጓቸዋል ።
Italiani in Africa P.396.

1 Italia ed Etiopia - ,Rossin, P.86

ደግሞ የንጉሡ ነገሥቱን ብልህ መሪነት ፣ የኢትዮጵያን ደንበኛ መንግሥትነት ፣ የኢጣልያን አጥቂነት እየዘረዘረ በመጻፍ በጋዜጣ እያሳተመ የኢጣልያን ፕሮፓጋንዳ በመቃወም ለዓለም ያስታውቅ ነበር ። ይኸ የፈረንሳይ ተወላጅ እዚሁ አዲስ አበባ ተምሮ በአማርኛ መናገርም መጻፍም ይችል ነበር ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በባሕርያቸው ከአስተዳደር ዘዴ ጋር የፖለቲካ ጥበብ የተሰጣቸው ፣ ትዕግሥትና ብልህነት የተዋሐዳቸው ፣ በዐዋቂ መካር መከበብን የሚያውቁ ፣ ችሎታ ያለውን ሰው መምረጥ የሚችሉ ነበሩ ። የጦር መሣሪያ መሰብሰብን ሳያቋርጡ በመስኮብ ይልቁንም በፈረንሳይ መንግሥትና በተወላጆቹ ይጠቀሙ ነበር ። እስካሁን ደግሞ በወዳጅነት የቆዩትን የኢጣልያ ወኪሎች ባንድ ጊዜ እርግፍ አድርገው ሳይተዉና ፊት ሳይነሡ ፣ ጠቅለውም ለፈረንሳይ መንግሥት መሣሪያም ሳይሆኑ ፣ በሁሉም መካከል ሆነው ሁኔታውን እያመዛዘኑ ላገራቸውና ለሕዝባቸው የሚጠቅመውን በዙሪያቸው ካሉት መሳፍንትና መኳንንት ጋር እየተመካከሩ ይሠሩ ነበር ። በተቻለ መጠንም ለዓለም የሚቻለውን ያህል ስሞታ በማሰማት ፣ ሐቀኛውን መንገድ በመውሰድ ፣ ኢጣልያኖቹ አገር አልፈው የመስፋፋትን ነገር እንዲተዉ ፣ ይኸን ያገር ክብር የሚነካውን አንቀጽ ኢጣልያኖች ራሳቸው ዐውቀው እንዲተዉና ወደ ቀድሞው የወዳጅነት መንፈስ እንዲመለሱ ለማድረግ በተቻለ መጠን ተጣጥረው ነበር ። ይኸንንም ሁሉ የሚያደርጉት ድንገተኛ ጦርነት ተነሥቶ በጥንካሬና በትጋት ያስፋፉት የኢትዮጵያ ግዛት እንዳይናጋ ፣ ባገርና በአውራጃዎች መካከል እንደ ፊተኛው ጊዜ መከፋፈል እንዳይኖር መሆኑ አይጠረጠርም ። በመከፋፈልም ኢትዮጵያ ተመልሳ በውስጥ ጦርነት እንዳትዳከም ፣ በዚህ ድካመትም ኢጣልያም ፣ ሌላውም ጠላት እንዳይጠቀም ነው ።

በዚህ ዓይነት ፣ ለሰላም ደከመው የሰላሙ መንገድ በኢጣልያኖች እምቢታ የሳተ እንደሆነ በማለት የጦር መሣሪያ ከያለበት የመሰብሰቡንና ወታደሩን ከነሹማምንቱ በየክፍሉ የማደራጀቱን ጉዳይ ችላ አላሉትም ።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## አንቶኔሊ ያቀረበው የማስፈራሪያና የማባበያ ማስታወሻ ፍሬ ቢስነት

ሳሊምቤኒ ፣ በአንቶኔሊ እግር በአዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ ባንድ ወገን 17ኛው አንቀጽ እንዲረጋና የኢጣልያ የቅኝ ግዛት ወሰኑ በኤርትራ እስከ መረብ እንዲደርስ በማናቸውም ረገድ ቢጨቃጨቅም ፣ ቢያባብልም ፣ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት ቢበትንም ፣ ጉዳዩ ስላልተሳካለት አንኮበር አጠገብ በልጥ ማረፊያ ተቀማጭ የሆነውን ሊዎፖልድ ትራቬርሲን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ “እዚህ በማባበል አልሆነልኝም ፣ አበሾች እሺ እንዲሉ በመድፍ በትር ብቻ ካልሆነ በቀር አልተቻለም” የሚል ማስታወሻ ጭምር አሲዞ ወደ ሮማ ላከው ። ቴራቬርሲ አሰብ እንደ ደረሰ መምጣቱን ወደ ሮማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ ቴሌግራም አስተላለፈ ። ክሪስፒ በዚህ ጊዜ የውጫሌውን ውል አንድ የፖለቲካ ውጤት እንዳገኘ በመቁጠር ምክር ቤቱን ከማጭበርበር ጋር ፣ “እንዲያውም የግራ ክፍሎች መቃወሚያ እያበጁ የእርምጃ እግሬን በከርከር እግረ ሙቅ ባያስሩኝ ኖሮ ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ለመስፋፋት ነገሩ ሁሉ ቀላል ነበር” እያለ የሚደነፋበት ሰዓት ነበር ። የምኒልክን የ17ኛውን አንቀጽ አለመቀበልና የመረቡንም ወሰን በግልጽ እምቢ ማለታቸውን ትራቬርሲ ሮማ ደርሶ እንዳያወራ ሲል በቁጣ ቃል ፣ “አንተ ወደ መጣህበት ወደ አዲስ አበባ ተመለስ ። ለማናቸውም ነገሩን ለማቃናት አንቶኔሊ መጥቷል” የሚል ቃል ስለ አስተላለፈለት ፣ ትራቬርሲ ከአሰብ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። እንደ ተባለው ኮንት አንቶኔሊም ከሮማ ወደ አዲስ አበባ መጣ ። እሱም ታዞ ይምጣ እንጂ በጉዳዩ አልተማመነበትም ።

ዳሩ ግን ፣ ሳሊምቤኒ በብዙ መንገድ እንደ ተረዳው ፣ በዚህ ጊዜ የኢጣልያ መንግሥትም ፣ በጠቅላላው ጣልያኖችም በአዲስ አበባ ተጠልተዋል ። በተለይ ደግሞ ቀድሞ ያፄ ምኒልክም ፣ የእቴጌ ጣይቱም ፣ የመኳንንቱም ፣ ያስተርጓሚዎቹ ሁሉ ወዳጅ የነበረው አንቶኔሊ በዚህ ጊዜ ፣ “አታላይ ፣ ተንኮለኛ ፣ አዘንግቶ የሚነክስ የመስክ እባብ” እየተባለ ከመሰደብ ላይ ይገኝ ነበር ። የርሱ አመጣጥ ምንም የሚለውጠው ነገር እንደሌለ ሳሊምቤኒ ራሱ በጥልቅ ስለ ተረዳው

ለአንቶኔሊ ፣ "እውነት የ17ኛውን አንቀጽና የመረብን ወሰን የኢጣልያ መንግሥት በሚፈልገው ዓይነት ምኒልክ እንዲቀበል ያደረግህ እንደ ሆነ የካርዲናል ጃኮሞ አንቶኔሊ የወንድም ልጅ ሳትሆን ፣ እራሱ ካርዲናሉ ከሞት ተነሥቶ እንደ ፈጸመው እቆጥራለሁ" ብሎ በማፌዝ እንደ ነገረው ያስረዳል ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ አንቶኔሊ እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ ወር 1891 ዓ.ም. ከደረስ በኋላ ፣ ስለ አከራካሪው 17ኛው አንቀጽ ሰፋ ያለ ማስታወሻ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚቀርብ በፈረንሳይ ቋንቋ አዘጋጅቶ ሲጨርስ ይኸንኑ ወደ አማርኛ እንዲተረጐም በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ አቶ ገብርኤል ታዘዙ ። ለርሳቸውም ረዥሙን ማስታወሻ ወደ አማርኛ ስለ መተርጐማቸው አንድ መቶ ብር ጉርሻ እንዳገኙ ሳሊምቤኒ ባሠፈረው ማስታወሻ ላይ ተጠቅሷል ።[2]

ማስታወሻው ያለፈ ውለታን ከመጥቀሱና ከማጭበርበር ጋር ከፊል ልመና ፣ ከፊል ማባበል ፣ ከፊል ማስፈራራት ያለበት መሆኑን አንባቢ ከዚህ እንደሚከተለው ሊረዳው ይችላል ።

ከቡር ወልዑል ጃንሆይ ብሎ ይዠምርና ከዚህ እንደሚከተለው ያትታል ።

> የውጫሌ ውል የተዠመረበትን ነገር ባጭሩ እንዳሳይዎ ይልቅስ ዛሬ በኢጣልያና በጃንሆይ መኻል ያለውን ወዳጅነት መፍረስ የሚፈልጉት ሰዎች የተደገፉበትን የውሉን 17ኛውን ክፍል እንዳመለክትዎ ይፍቀዱልኝ ።
>
> የዚህ ውል ረቂቅ ቃል ፣ በ1881 ዓመተ ምሕረት በየካቲት ወር ለጃንሆይ ቀረበ ። አዲስ አበባ ከተማ በክቡር ወልዑል ንጉሥ ኢጣልያ መንግሥት ስም ።
>
> የዚያን ጊዜ የንጉሥ ዮሐንስ ጠብ ጃንሆይን ማስፈራራት አስቦ ነበርና ስለዚህ የኢጣልያ መንግሥት ለርስዎ ለመርዳት ብሎ 5ሺ የረሚግቶን ነፍጥ 5ሺ ባለ ክምሱር ጠመንጃ ፣ 70ሺ አረር (ጥይት) አንድ መትረየስ ፣ 12 ሳጥን ባሩድ ፣ 100ሺ ብር ደግሞ ሌላ ልዩ ልዩ በረከት አድርጎ ላከልዎ እውነትም ይኸ ነፍጥ ሁሉ የደረሰ ጊዜ ንጉሥ ዮሐንስ እሸዋ ገብቶ ለመዝረፍ ተሰናድቶ እምሁሩ ላይ ተቀምጦ ነበር ።
>
> ጊዜያቱ ምንም የጦር ጊዜ ቢሆን ውሉ በጃንሆይ ትእዛዝ በግራዝማች ዮሴፍ እጅ ባማርኛ ተተርጉሞ ተነበበልዎ ። ጃንሆይም እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት መባል ሲያበቃኝ ፣ ይኸንን ውል አትም ዘንድ የሚቸግረኝ ነገር የለም አሉ ።

---

1 Gli Italiani in Africa Orientale - Angelo de Boca P.399

2 Crispi e Menelich, P. 281.



> የኢጣልያ መንግሥት ከርስዎ ጋር ያለው ቃሉ እንዳይታበል ብሎ ዐፄ ዮሐንስ በእርቅ ነገር የላከበትን መልእክት ሁሉ እይሻኝም ብሎ መልሶለት ሲያቆም ፤ ወደ ትግሬ የሚወጣ ጦር እንኳ ደግሶ ነበር ። ንጉሥ ዮሐንስም ወደ ሸዋ የጦር መሣሪያ እንደ መጣ ዐውቆ ባሥመራ በኩል ደግሞ የኢጣልያን ጦር መውጣት ወሬ ሰምቶ ነው ። ሸዋን ለመውጋት ያሰበ አሳቡን ትቶ ከስላሞች ጋር ለመዋጋት እስከ መተማ ድረስ ወረደ ። በዚህ ዘመቻ ግን ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሀብታም ሳይሆኑ ቀርቶ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን ለራስ መንገሻ ትቶ ወድቆ ለመሞት በቃ ።
>
> ኢጣልያ ግን ፣ ራስ መንገሻን አላወቀም ፤ ለምኒልክ የሰጠውን ቃል አላሳበለም ። ንጉሡ ዮሐንስ ድል ተመቶ ሞተ የሚል ወሬ ግድም ላይ የተሰማ ጊዜ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መሐል ተዠምሮ የነበረው ውል ደግሞ ተነሥቶ ብዙ ቀን ተነጋግረንበት የውሉ ቃል እንደገና ተነቦ ሲያበቃ ንጉሥ ምኒልክ ከሚል ቃል ፋንታ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ቃል ተጻፈ ።
>
> ጃንሆይ እያሌ ቃል አሳረሙ ። 4ኛውን ክፍል ጨመሩበት ። ደብረ ቢዘኑንም ወደርሶ አደረጉት ። ሌላ ክፍሎችም ታረሙ ። 3ኛ ፣ 10ኛ ፣ 12ኛ ፣ 16ኛም ክፍል ማለቴ ነው ።
>
> ጃንሆይ ባረሙት ቁጥር የታረመውን እንጽፍ ነበር እኔና አነጋጋሪዎ (ግራዝማች ዮሴፍ) ። እኔ በኢጣልያን ቋንቋ ጻፍሁ ። እርሱም ባማርኛ ።
>
> ኋላ ግን ፣ መታረሙ እጅግ በብዙ በኢጣልያን ቋንቋም ባማርኛም የተጻፈ ሁሉ እንደገና ታድሶ ይጻፍ ተባለ ። ባማርኛ የታረመው ግን በኢጣልያን ጽፈት ከታረመው ጋር ባንድነት ይኖራል ዛሬ በሮማ ከተማ ።
>
> ባማርኛ ሆነ ወይም በኢጣልያን ቋንቋ ከ17ኛው ክፍል አንድ ቃል ብቻ ነው የታረመ ። ንጉሥ ምኒልክ የሚል ቃል ቀርቶ ስለርሱ ፋንታ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ቃል ተጻፈ ማለቴ ነው ።
>
> ይኸው ውል እንደገና በ2ቱም ቋንቋ ተጽፎ ሲያቆም ፤ ቃላቱ ሁሉ ከመዠመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ዳግመኛ በራስ መኰንንና በደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ፊት ቢነበብ ፣ በእበላ ወይም በወንጀል ነገር በተጻፈው 12ኛው ክፍል ላይ ለጃንሆይ ሌላ ቃል አርመው ሲያበቁ 17ኛውም ክፍል ተነበበ ። የዚያን ጊዜ ጃንሆይም ይህ 17 ክፍል ባይጻፍም ነገር የለበትም ፤ ስለምን ብትሉ ከእንግዲህ ወዲህ መቸም የቸገረኝን ጉዳይ በሌላ መንግሥት እጅ የማልክ ነኝ በኢጣልያ እጅ ነው እንጂ አሉ ። እንዲህ ተሆነ ጃንሆይም የዚህን ክፍል መሰረዝ ከፈቀዱ መሰረዙን እንችላለን አልሁዎ ። ዳሩ ግን ፣ በየውሮፓ ስለርስዎ የሚቆምልዎ አንድ ወዳጅ ንጉሥ ቢገኝልዎ ይሻላል ይመስለኛል ብዬ ነገርሁዎ ። ጃንሆይም የዚያን ጊዜ ይሁን ይህ 17ኛውም ክፍል በውሉ ውስጥ ይጻፍ ብለው ውሉም እንደገና እምሮ ተጽፎ ባማርኛም በኢጣልያም ቋንቋ ሆኖ ፣ በ1881 ዓመተ ምሕረት በሚያዝያ በ25 ቀን ውጫሌ ላይ ተዋውለን ጨርሰን ፣ በ2ቱም ቋንቋ ለየብቻው የተጻፈውን ውል ጃንሆይ በማኅተምዎ አሳተሙት ።

ከዚያ ወዲያ ራስ መኰንን ወደ ኢጣልያ መጡ ። ሚኒስትር ክሬስፒም በመስከረም በ16 ቀን ሒድና የውላችን 17ኛ ክፍል ቃሉ ወደ ነገሥታት የሚላክ ነውና ከራስ አስፈቅድልን ብሎ ላከኝ ።

ኢጣልያ ግን ፥ ያ17ኛውን ክፍል ቃል ወደ ነገሥታት ማሰማት መፈለጉ እንግሊዞች በሱማሌ አገር የውሀ ጉድጓድ ማስቆፈር ይሹ ነበሩና ስለዚህ ምክንያት ለኢትዮጵያ የተገባ ጥቅም እንዳይነካ ለማድረግ ጉልበት ለማግኘት ነበር ።

ራስ መኰንን ፥ ግራዝማች ዮሴፍን ጠርተው የ17ኛውን ክፍል ትርጓሜ ከርሱ አፍ ሰምተው ሲያቆሙ ፥ ከእንግሊዞች ጋር ባለው ጉዳይ ለመላላክ እንዲመች ይህ ክፍል ቃሉ ከነገሥታት ቢታወቅ መጥቀሙን ዐውቀውት ወደ ነገሥታት ይላክ ዘንድ ፈቃድ ሰጡ እንዲህ ሲሉ ። ይህ ክፍል መኖሩን እንኳ አላወቅሁትም ነበር ። ዳሩ ግን ጃንሆይ ከወደዱት በላይ ምናለ ይላክ ለነገሥታት ብለው ፈቀዱለት ።

ይህ 17ኛ ክፍል ቃሉ ወደ ነገሥታት ከተላከ ወዲያ ግን ፥ ወደ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ እንዲያልፍልኝ ፍቀዱልኝ የሚል ደብዳቤዎ ከየአውሮፓ መንግሥቶች ዘንድ ተልኮ ተገኘ ።

በዚያን ጊዜ የታተመ ጋዜጣ ሁሉ ፡ ዐጤ ምኒልክ እያታለሉት ርእሰ መማክርት ሚኒስትር ክሪስፒ እንዴት የለም ይላል ብሎ እነርሱንም የቀሩት ሚኒስትሮችንም ያሙ ገርመሩ ። ጥንቱውንም የሸዋን ነገር ያልወደዱት ጠላቶች ደግሞ ፥ ይህንን ነገር ምክንያት አድርገው ዓድዋን አለመልቀቅ ነው ከራስ መንገሻም ጋር እንስማማ ማለት ፈለጉ ።

ከራስ መኰንን ጋር ነገሩን ጨርሰን ነበር ። ወደ መቀሌ የመጣን ጊዜ ግን ታዝዤ ከመጣሁ መናገር ይገባል ብዬ ነገሩን ባነሣብዎ ወደ ሌላ ነገሥታት የምልከው ጉዳዬን በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላኬ በወዳጅነት ነው ወይስ በግድ ነው ብለው ጠየቁኝ ። እኔም እንዲህ ብዬ መለስሁልዎ ። በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላክዎ ስለ ወዳጅነትም ስለ መከበርም ነው እልሁዎ ። ይህ ሁለት ነገር ቢጎድል ግን ጃንሆይ የፈቀደዎን ማድረግ ይችላሉ ብዬ ነገርሁዎ ።

ከዚያ ወዲያ ይህ ነገር ዳግመኛ አልተነሣም ። ጃንሆይ የኢጣልያ ንጉሥ እጅግ ያዘኑበት አንድ ደብዳቤ ወደ ኢጣልያ አስቲልኩ ድረስ በዚህ ደብዳቤዎ ግን ፥ ምነው የውሉ 17ኛ ክፍል ቃል ባማርኛ እንደ ተጻፈ ትክክል ሆኖ በኢጣልያ ቋንቋ ሳይጻፍ ቀረ ብለው ተከፍተው ላኩባቸው ።

በፊት በኢጣልያ ቋንቋ የተጻፈውን ቃል የኢትዮጵያ መንግሥት አስተርጓሚ አማርኛ ትርጓሜው ላይ አጥፍቶ ቢተረጒመው ይህ ጥፋት ከኢጣልያን መንግሥት አይጠየቅም ፤ 17ኛው ክፍል ግን ከቶ አልታረመም ። ስለምን ቢሉ በላይም እንዳሳየሁዎ በዚህ ክፍል የተለወጠ ቃል አንድ ብቻ ነው ። ንጉሥ ምኒልክ የሚል ቃል ተሰርዞ ንጉሠ ነገሥት የሚል ቃል ተጻፈ ማለቴ ነው ።

ኢጣልያ ግን ፥ ሁልጊዜ እርስዎን ደስ አሰኝቶዎት በሰላም በእርቅ



መኖር ይመኛልና ስለዚህ የተነሣውን ነገር በወዳጅነት ለመጨረስ ብሎ ምሉ ሥልጣን ሰጥቶኝ ወደ ርስዎ ላከኝ ።

በርስዎም ዘንድ ከደረስሁ አንድ ወር በኋላ ጃንሆይ ስለ መጨረሻ ይህንን 3 ቃላት ነገሩኝ ።

መዠመሪያ ቃል ፡ ወይ የውሉን 17ተኛ ክፍል መሰረዝ ።

ሁለተኛ ቃል ፥ ወይ ይህ 17ኛ ክፍል ውሉ ላይ ባማርኛ እንደ ተጻፈ መቀበል ።

ሦስተኛ ቃል ፡ ወይም ጃንሆይ በዚህ ነገር ተናግረው ፈቃድዎን ሳያስታውቁ በ2ቱም ቋንቋ የተጻፈውን ቃል እንዳለ መተው ነው አሉኝ ።

እኔ ግን ፡ ያገሬ መንግሥት እዞኝ የተላክሁበትን ጉዳይ እንሥተው ሲያቆም አሁን ጃንሆይ ከነገሩኝ ከ3ቱ ቃላት አንዳቸውንም መቀበል አልችልምና ስለዚህ በዚህ ነገር የኢጣልያ ንጉሥ መንግሥት በሮማ ከተማ የሚለውን አዳምጣለሁ እንጂ ብዬ መለስሁልዎ ።

ነገር ግን እኔም ይህን ነገር ለኢትዮጵያም ፥ ለኢጣልያም በሚጠቅም ወግ አልቆ ስምም እንዲሆን እመኛለሁና ስለዚህ ምክንያት ለመስማማት ከዚህ ቀደም ባመለከትሁዎ ብዙ ብልሀት ሌላ ደግሞ አያሌ ብልሀት ባሳይዎ የማይሆን ሆነ ።

በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ ፡ እነጋጋሪዎ እኔ የተላኩበት ጉዳይ እንዳይቃና ለማድረግ ብሎ የኢትዮጵያን መንግሥት በብዙ የሚጐዳ ወሬ ያወራል ይሉኛል ። እንደዚህ ማድረጉ ግን ወይ አለማወቁ እንዳይገለጥ ወይም ተንኰሉ እንዲሰወርለት ብሎ ነው ።

ነገሥታት ዘንድ የተላከ ቃል ግራዝማች ዮሴፍ ከሮማ ሳይነሣ 50 ቀን በፊት ተልኮ በጋዜጣ ሁሉ ላይ ታትሞ ሲያቆም ፥ እንዴት ግራዝማች ዮሴፍ ይህ ቃል እኔ ከሮማ ከተማ ከተነሣሁ በኋላ ነው የተላከ ማለት ይቻላል ።

ዳሩ ግን ፥ ግራዝማች ዮሴፍ ዕለት ዕለት ከኢጣልያን ጋዜጦች ጋር በፈረንሣዊ ቋንቋ ደግሞ በሮማ የሚታተም ስሙም ሲታሊ የሚባል አንድ የፈረንሲስ ጋዜጣ መቀበሉ የታወቀ ነው ። ይህም ጋዜጣ እንደሌላ ጋዜጣ ሁሉ ወደ ነገሥታት የተላከውን 17ኛውን ክፍል ቃል በቃል አትሞት ነበር ።

በውሉ 19ኛ ክፍል ውል በኢጣሊያና ባማርኛ ቋንቋ ነው የተጻፈ ሲባል ፥ ግራዝማች ዮሴፍ እንዴት አድርጎ የጃንሆይ ማኅተም ባማርኛ ከተጻፈ ላይ ብቻ ነው የታተመ ማለት ይደፍራል ።

ለኢጣልያን መንግሥትስ በየውሮፓ ከቶ ባልታወቀ ቋንቋ ውል መዋዋል እንደምን ይመቻል ።

ጃንሆይ እንኳ በነሐሴ በ19 ቀን በተጻፈ ደብዳቤዎ 19ነኛ ክፍል የ2ቱም ቋንቋ ትክክል ሆኖ ይስማማ ዘንድ ይገባል ይላል ብለው ጽፈዋል ።

እንደዚህ ሆኖ በትርፍ ነገር ጉዳይ ሲበላሽ በብርቱ ወዳጅ የሆኑ ለዎች እንኳ ተስፋ መቁረጥ ይጀምራሉ ። ስውም በሐሰት ከማማትና ነገር ከመሥራት በቀር ሌላ ምላሽ ያጣ ጊዜ እንግዲህ የቂም ነገር ምላሽ አያገኝምና እስከ መጨረሻ አረሩንም (ጥይቱንም) ተኩሶ አር ፎአል እንደሚል ተረት ነው ።

ጃንሆይ

ይህንን ሁሉ መናገሬ ከርስዎ ጋር የተነጋገርን ጊዜ ፣ ምናልባት አስተርጓሚዎ ቃሌን ለውጦ አበላሽቶ ነግሮዎ እንደሆነ ብዬ ጠርጥሬ ነው ።

ለ2ቱም ሕዝብ የሚጠቅመውን አንድ ብልሀት ጃንሆይ ይፈልጉትና ተስማምተን ጨርሰን እርስዎ ያሉኝን ለማተም የተሰናዳሁ ነኝ ።

ኢጣልያ ስለኢትዮጵያ መሬት ጥቅም ቆሞ ከብዙ ወር ዠምሮ ከየውሮፓ ጋራ መሟገቱን ጃንሆይ ያስተውሉት ።

ግን የምኒልክ ንጉሠ ነገሥትነት ግዛት እንዳይነካ ሆኖ በትልቅነት በኃይል እንዲኖር ብመኝ ነው ። ኢትዮጵያ በፈረንሣዎች ወይም በእንግሊዞች እጅ ቢገባ አንወድም ። ኢትዮጵያ በኢትዮጵያውያን እጅ ሆኖ ቢኖር ነው እንጂ ደስ የሚለን ።[1]

በዚህ ክርክር የሚገቡ ባለሥልጣኖች ፣ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ በቀር ራስ መንገሻ አቲከም ፣ ራስ መኰንን ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄ ፣ ዋናው አስተርጓሚ ግራዝማች የሴፍ ንጉሤ ናቸው ። ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እነሊቀ መኳስ አባተም ፣ እነአቶ ገብርኤልም ይገባሉ ።

ቀድሞውኑ ውሉ ሲዘጋጅ ዐፄ ምኒልክ የኢጣልያ እርዳታ "እውል ውስጥ ባይገባስ ምን አለበት" ሲሉት አንቶኔሊ በተንኮለኛ አባባል ፣ "እውል ውስጥ ካልገባ የኢጣልያ ንጉሥ እንደልቡ ሊረዳዎት አይችልም" ብሎ እውል ውስጥ በ17ኛው አንቀጽ እንዲሠፍር ሲያስፈቅድ ፣ አባባሉን ያሠፈረው የሮማ ባለሥልጣኖች በሚደሰቱበት እነርሱም ሲደሰቱ የርሱ ሥልጣን በሚያድግበት ዓይነት ነው ።

በዚህ ዓይነት መዘጋጀቱን አንቶኔሊ ልቡ እያወቀው በደፈናው ሲከራከር ፣ ኮንት ሳሊምቤኒና ትራቬርሲ ነገሩን ተረድተው ሁኔታውን የያዙት ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ነበር ። ከሁለቱም የበለጠ ሳሊምቤኒ ፣ አንቶኔሊ በፎከረበትና አሁንም በሚከራከርበት ፣ ምኒልክ ባልተቀበሉት አሳብ ለክርክሩ መተባበሩን ሳይተው ትዝብት አድሮበታል ።

1 Archivio Storico del Soppresso Ministreo Africa Italiana - pos. 36, 37, 38.



ስለዚህም ለሚስቱ ለአማሊያ ኤሊዚ * እ.ኤ.አ. በጥቅምት ወር 1891 በጻፈላት የግል ደብዳቤ ላይ ፣ የነአንቶኔሊን ማታለል ፣ በራሱ ላይ የደረሰውን ችግር ደህና አድርጎ እንደዚህ ሲል አብራርቶታል ።

> . . .ከመዳከም የተነሣ እኔ ዘቀጥታ ሳልጽፍልሽ ስለቀረሁ በሥራ ምክንያት ለምጽፍላቸው ለፒዛኒና ለማዬር ሰላም እንዲሉሽ ነግሬያቸው ነበር . . . ከጤንነት ማጣቴ ጋር እዚህ (አዲስ አበባ) ያለው ብጥብጥና ችግር እውነቱንም በግልጽ የልቤን ለመናገር እያቃተኝ የቁጣ (ብስጭት) መንፈስ አድርብኛል ። . . . በቀላሉ ጉዳዩን በሚያስደንቅ አኳኋን ለማከናወን አሁን ነው የገባኝ ። ይኸውም በኢጣልያንኛ ቋንቋ የኢጣልያ (ባለሥልጣኖች) እንደሚፈልጉት ባማርኛው ፣ ምኒልክ የሚፈልገውን ጽሑፍ አስፍሮ ሁለቱ ቃላት ባይስማሙም መጭው ያስብበታል ። የኔው አሚሊያ እንዴት ያለ ችግር እንዴት ያለ ማጭበርበር እንዴት ያለ ውሸት ይመስልሻል?. . .[1]

በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ ላይ ፣ የአንቶኔሊንና በርሱም አማካይነት የኢጣልያኖችን አጭበርባሪነት ከዚህ ከሳሊምቤኒ አባባል የበለጠ የሐቅ ምስክርነት አይገኝም ። አንቶኔሊ ከኢጣልያ እንደመጣ ቀድሞ በወዳጅነቱ ዘመን ፣ በተለይ ዐፄ ዮሐንስ ከጐጃም ወረራ በኋላ ወደ ሸዋ ሊመጡ ነው ተብሎ በሚያስፈራሩበት ሰዓት ፣ የሁለቱ መዋጋት ለኢጣልያ ጥቅም መሆኑን በማሰብ ፣ በግሥጋሤ አምጥቶ ያውም በብድር የሰጠውን የጦር መሣሪያ እንደ ትልቅ ውለታ በመቁጠር ፣ በ17ኛው አንቀጽ እርሱ በኢጣልያ ቋንቋ ያሠፈረውን እንደማይቀበሉት እያወቀ በከንቱ ሲጨቃጨቅ ጊዜውን አጠፋ ። ከርሱ ጋር ያሉት ኮንት ሳሊምቤኒና ዶክተር ትራቬርሲ ባላመኑት ጉዳይ መከራከር ቢጠሉም ፣ ለይስሙላ ብቻ ከርሱ ጋር ኅብረት ማሳየት ግዴታቸው ነበር ። ያለዚያ ባሁኑ ጊዜ አንቶኔሊ በኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የምክትል ሚኒስትርነት ሥልጣንና የምክር ቤት አባል ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የክሪስፒ ባለሟል ስለሆነ ልዩነታቸውን በግልጽ ቢያሳዩ ለበላይ ነግሮ ሊያዋርዳቸው ይችላል ። ሆኖም ሦስቱ በሚወያዩበት ጊዜ ፣ ሁለቱ የመለየት መንፈስ ስለሚያሳዩት በአንቶኔሊ ዘንድ ቅርታ መፈጠሩ[2] አልቀረም ። አንዳንድ ጊዜ ሳሊምቤኒ በአንቶኔሊ ማሾፍ ሲያምረው ለሰዎች ሲጽፍ ኮንት አንቶኔሊ በማለት ፈንታ ካርዲናሊኖ (ቲንሹ ካርዲናል) ይለዋል ። ይኸውም አንቶኔሊ የካርዲናል ጃኮሞ አንቶኔሊ ተወላጅ ነኝ እያለ መመካቱን ለማስታወስ ነው ።[3]

* Êelisi Amalia

1 Crispi e Menelich - Nel Diario Inedito del conte Augusto Salimbeni. C. Zaghi, PP. 185 - 185.

2 Crispi e Menelich - p. 362

3 Crispi e Menelich - P. 372

# ምዕራፍ ዐሥር

## ድርጎ በገጸ በረከት አንጻር

በኢትዮጵያ ከቀድሞ ዝምሮ አንድ የውጭ መልክተኛ ሲመጣ ባገሪቱ እንግዳ የሚቀመጥበትና የሚመገብበት ሆቴል ስለሌለ ፣ የመንግሥት መሪዎች እንግዳውን ተቀብለው ማረፊያ ቤት ሰጥተው የማስተናገዱ ጉዳይ የነርሱ ነው ። እንዲቀመጥበት በተዘጋጀው ቤት በየቀኑ ፣ የሚዘገይም ሲሆንና ወይም ነዋሪ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ እመኖሪያ ቤቱ ድረስ እንጀራው ፣ ወጡ ፣ ሰንጋው ፣ በሬው ፣ ሙክቱ ፣ ጠቦቱ ፣ ጠጅና ጠላው ወደ አገሩ እስኪ ተመለስ ድረስ ከቤተ መንግሥት ይላክለታል ። የድርጎው ዓይነትና ብዛት እንደ እንግዳው አቀዋምና እንደ ላኪው መንግሥት ኃያልነት መጠን ነው ። ለማብሰያም እንጨት ፣ ለጉዝጓዝና ለክብት ሣር ሳይቀር ይላካል ። ይኸም ድርጎ እንዳይቋረጥ የሚቆጣጠር የመልክተኛውን ፍላጎት የሚፈጽም ባልደረባ ተብሎ የሚጠራ አንድ ባለሥልጣን ይመደባል ።

ፖርቱጋሎች ፣ እ.ኤ.አ. በ1520 ዓ.ም. ወዳዬ ልብነ ድንግል የመጡ ጊዜ ለፖርቱጋሎች ባልደረባ እንዲሆን የተመደበው ሕዱግ (ራስ) መሆኑን ከጠቀሰ በኋላ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ ፣ "እንዳረፍን ሦስት ነጭ* እንጀራ ፣ ብዙ ገምቦ ጠጅ ፣ አንድ ፍሪዳ (ሠንጋ በሬ) ተላከልን" ካለ በኋላ ፣ እልፍ ብሎ "በማግሥቱ ቅዳሜ . . .በደንብ ሆኖ የተዘጋጀ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥጋና እንጀራም መጣልን. . .ከተላከልን ምግብ አንደኛው በደንብ ሆኖ የተዘጋጀ ያንድ ጊደር (መሲና) ሥጋ በሙሉ ነበር ። በተለይም ይህ ምግብ በጣም ጣፍጦ ስለነበር የተሠራው ሳንጠግብ አለቀ. . ."[1] ሲል ያወሳል ።

ባዬ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ከፕሎውዴን ሞት በኋላ ሻርል ደንካን ካሜሮንን ቆንሲልነት ሾሞ ላከው ። ቆንሲሉ እ.ኤ.አ በ1862 ዓ. ም. መጥቶ ካዬ ቴዎድሮስ ጋር ተገናኝቶ

---

* ሦስት መሶብ ማለቱ ይሆን ?

1 ኢትዮጵያ ፖርቱጊዞች እንዳዩዋት የጻፈው ፍራንቼስኮ አልባሬዝ ፣ የተረጐመው ግርማ በሻህ ፣ ምዕ. 70-71 ፣ የግራኝ አህመድ ወረራ ፣ ተ.ጻ.መ ፣ ምዕ.19—20

ስለ ሁለቱ አገሮች ግንኙነት ከተነጋገረ በኋላ ፣ ወደ ተዘጋጀለት ሠፈር ሔዶ እንዳረፈ ከቤተ መንግሥት አዛዡ ሃምሳ ላም* ፣ መቶ በግ ፣ ሁለት ሺ እንጀራ ፣ ሠላሳ ጋን ጠጅ ፣ ዐሥር ገምቦ ማሰፊያ ጠጅ ፣ ዐሥር ገምቦ አዋዜ ተላከለት ። ቆንሲሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ የሚል ምስጋና አስቀድሞ ፣ "ይኸን ሁሉ የሚፈጅ ሠራዊት የለኝም ። አምስት ላም ፣ ዐሥር በግ ይበቃኛል" ብሎ ቢመልስ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ "... ሰወጉ ነው እንጂ እንኳን እንዳንተ ያለ በንግሥት የከበረ ሹም፣ የቤተ መንግሥት ደብዳቤ ይዞ የመጣውን እንደ ንጉሥ አክብሮ መቀበል ይገባል" ብለው ከቅርታ ጋር መልሰው ቢልኩለት ካሜሩንም በዝምታ ተቀበለው ።[1]

የዚህ የድርጎ አሰጣጥ ጉዳይ ባፄ ዮሐንስም ፣ ባፄ ምኒልክም ዘመነ መንግሥት ሁኔታው ተመሳሳይ ነው ። ዐፄ ምኒልክ ወደ መጨረሻው ዘመናቸው በኢትዮጵያ አዲሱን የአውሮፓ ሥልጣኔ ለማስገባት በወጠኑበት ሰዓት ፣ እቴጌ ጣይቱ ዛሬ በስማቸው ጣይቱ ሆቴል የሚባለውን በ1900 ዓ. ም.[2] ከፍተው እንግዳ እንዲቀመጥበት ከማለማመዳቸው በፊት የነበረው የእንግዳ አቀባበልና መስተንግዶ እንግዳው ወደ ሠፈረበት በያይነቱ ድርጎ የመላኩ ጉዳይ ከጥንት ከመጣው ልማድ ጋር የተያያዘና ተመሳሳይ ነበር ።

ኢጣልያኖች ፣ አንኮበርና ልጥ ማረፊያ የነበሩ ጊዜ ፣ በኋላም እንጦጦና አዲስ አበባ በተቀመጡበት ሰዓት ለኢጣልያ ወኪሎች ለነአንቶኔሊ የወር ድርጎ በአዛዦቹ በነአዛዥ ዘአማኑኤል ፣ በነአዛዥ ስንቄ አማካይነት ይላከላቸው ነበር ። የኢጣልያ ወኪሎችም ብዙ ዘመን ከመቆየት የተነሣ ፣ በይፋም ባይሆን ከሴቶች ውስጥ ቆንጆዎቹን እየመረጡ እንደ ሚስት በማስቀመጥ ጸሐፊም ፣ አስተርጓሚም ፣ አሽከርም ፣ አትክልተኛም እየቀጠሩ እንደ ኢትዮጵያ መኰንን በብዙ ሰው መከበብን እነሱም አልጠሉትም ።

ስለዚህ ፣ ከቤተ መንግሥት በየቀኑ ወይም በሳምንት አለዚያም በወር የሚላከላቸው ድርጎ እንደ ወር ቀለብ የሚቆጠር ስለሆነ ፣ ራሳቸው ከመመገብ ጋር በነርሱ ሥር ለሚተዳደሩት ማትረፋቸው የታወቀ ነው ። አንቶኔሊ ብዙ ጊዜ በአንኮበርና በእንጦጦ ቆይቶ በመጨረሻ የውጫሌን ውል አስፈጽሞ ወደ አገሩ እንደገባ በርሱ እግር ተተክቶ የመጣው ሳሊምቤኒ ከመጣ ዠምሮ እንደ አንቶኔሊ በዘመኑ

* ሠንጋ ማለቱ ይሆናል ።

1 ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ፋዚላ ያሳተመው ገጽ 28—29 ።

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 336



ካሉት መሳፍንትና መኳንንት በተለይ ከቤተ መንግሥቱ የቅርብ የሥራ ረዳቶችና አስተርጓሚዎች ጋር በስጦታም ፣ በንግግርም ተወዳጅቷል ። በአማርኛ ቋንቋ ለመናገርም ለመጻፍም ይሞክራል ።

ሳሊምቤኒ ፣ በአንቶኔሊ እግር እንደ መጣ የተመደበለት የወር ድርጎ ስምንት ዳውላ እህል ፣* አራት ጉንዶ ማር ፣ ሁለት ዳውላ ጌሾ ፣ አንድ ዳውላ በርበሬ ፣ አምስት ቁራጭ ጨው ፣ ስምንት ሙክት ፣ አንድ ቁና ቡና መሆኑን ራሱ በጻፈው ማስታወሻ ያረጋግጣል ።[1] ይኸንንም በየወሩ የሚያቀርቡለት የቤተ መንግሥቱ የምግብና የመጠጥ ኃላፊ አዛዥ ስንቄ ናቸው ።

አዛዡ ባንደኛው የጊዜ ወቅት በእንጦጦ ቤተ መንግሥት እንዳሉ ለግብር የሚሆን አንሷቸው ከተለመደው አነስ አድርገው ልከውለት ኖሮ ፣ ሳሊምቤኒ በቁጣ ተቀንሶ የመጣለትን ድርጎ መልሶ ላከላቸው ። አዛዡም ለዋናው አስተርጓሚና ለፈረንጆቹ ባልደረባ ለግራዝማች ዮሴፍ ችግራቸውን ሲያዋዩ ግራዝማቹ ለኮንት ሳሊምቤኒ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጻፉ ።

> ይድረስ ከኮንት ሳሊምቤኒ የተላከ ከግራዝማች ዮሴፍ እንዴት ዋሉ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። አዛዥ ስንቄ አሁን አንድ ነገር ላኩብኝ ። ድርጎ ብልክ አልቀበል ብሰው መለሱት ። ውነት እንደ መዠመሪያ ቀን አይደለም ። ነገር ግን ነገ ሙሉ ግብር** ቢሆንብኝ አሳንሸዋለሁ አሉኝ ።
>
> እርስዎ የመጡ ስለ ኢጣሊያና ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ለማጥናት ስለ ሆነ ስርሶ ድርጎ ቁም ነገር የለውም ። ደግሞ እስካሁን ድረስ ጃንሆይ የሰደዱልዎ መስተንግዶ ነው እንጂ ድርጎ አይደለም ። የቀለብዎን ነገር ከጃንሆይ ጋራ ትላንት መድበነዋል ነገ ይቀበሉታል ። እኔም ዛሬ አለመምጣቴ ነገ ከግብር መጠራትዎን ብሰማ ፣ ነገ እንነጋገራለን ብዬ ነው ። አሁንም ጃንሆይ የሰሙ እንደሆነ ያዝናሉና እባክዎ ስለ ዛሬ ይቀበሉ አይቆጡ ።
>
> ወዳጅዎ ግራዝማች ዮሴፍ
>
> ፊርማ በፈረንሣይኛ ንጉሜ[2]

* እህል ሲል ስንዴና ጤፉን አይለይም ።

Crispie Menelich, Nel Diario del conte A. Salimbeni. C Zaghi, PP. 106,176

ሙሉ ግብር ማለት በትልቁ አዳራሽ ንጉሠ ነገሥቱ በመንበረ ዳዊታቸው እንደተገኙ መሳፍንትና መኳንንት ፣ ሹማምንትና የጦር ሠራዊት ካህናትም የሚካፈሉበት ትልቅ ግብዣ ነው ።

Archivio Storico, Etiopia, Pos. 36/8 -66.

አንድ የውጭ አገር መልከተኛ በነዋሪነትም ፥ በጊዜያዊነትም በመልእክት ወይም ለጉብኝት መጥቶ በኢትዮጵያ በሚቆይበት ጊዜ ይኸን የመሰለ መስተንግዶና ድርጎ ለጊዜያዊው በየቀኑ መስተንግዶ ፥ ለነዋሪው በየወሩ እንደ ቀለብ በድርጎ ስም ይሰጠዋል ። አውራጃ ሊጐበኝ በሚሔድበት ጊዜ ሳይቀር ይኸንኑ የመሰለ መስተንግዶ እንዲያደርጉ አገረ ገዥዎች እየታዘዙ ባይታዘዙም ዐውቀው ያደርጉታል ። ወዳገሩ ሲመለስ ደግሞ የወርቅ ፥ የብር ፥ የጋሻ ፥ የጦር ፥ የሰይፍ ፥ የጎራዴ ፥ የልብስና የመጽሐፍ ስጦታ እንደ እንግዳው ዝንባሌና ደረጃ ይሰጠዋል ። ይኸ ሁሉ በጥሬ ገንዘብ ሲተመን ወጭው ብዙ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፥ ፈረንጆቹ ሲመጡ ለንጉሠ ነገሥቱ ፥ ለእቴጌ ይቱ ፥ ለመኳንንቱ ፥ ለባለሟሉና ላስተርጓሚው ከሚሰጡት ጠመንጃና ሽጉጥ ፥ ሥጋጃና ካሊም ፥ ሽቱና ጌጣጌጥ ወይም ጥሬ ገንዘብ እንደ ገጸ በረከትና እንደ ጉቦ ከሚያቀርቡት ሒሳብ ጋር ቢታሰብ እነሱ የሚቀበሉት የሚያመዝን ይሆናል ። የነርሱ ላንድ ጊዜ ሲሆን የኛዎቹ የሚሰጡት በወራትና በዓመታት በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ነው ።

ብዙ ዘመን አንኮበርና እንጦጦ የተቀመጠው ኮንት አንቶኔሊ ወዳገሩ ሲመለስ ከቤተ መንግሥት ጥሩዋ ተመርጣ የመረሻት* ዕቃ የተሜነች በቅሎ ቢሰጠው ላመጣለት አሽከር 50 ብር እንደ ጉርሻም ፥ እንደ በቅሎ ዋጋም አድርጎ ቢሰጠው ገንዘቡ ስለበረከተ በት አሽከሩ እምሳውን ብር አምጥቶ ለንጉሠ ነገሥቱ ቢያቀርብ "ለጉርሻ ይበዛል ለዋጋም ያንሣል ። የሆነ ሆኖ እንደ ጉርሻ የሚቆጠር ነውና ውሰደው"[1] ብለው ላሽከሩ መረቁለት ።

ዶክተር ሜራብ የሚባሉ ያፄ ምኒልክ ሐኪም ፥ እ.ኤ.አ. በ1900 ዓ.ም. አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የገበያ ዋጋ በዘረዘሩት መጠን ለኮንት ላሊምቤኒ በየወሩ የሚሰጠው የድርጎ ዋጋ ስምንት ዳውላ** እህል አንዱ ዳውላ 2 የማሪያ ቴሬዛ ብር ፥ አራት ጉንዶ ማር አንዱ 7 ብር ፥ 2 ዳውላ ጌሾ ፥ አንዱ ዳውላ 4 ብር ፥ 8 የበግ ሙክት አንዱ 4 ብር ፥ አንድ ዳውላ በርበሬ 4 ብር ፥ 5 አሞሌ ጨው 1 ብር ፥ አንድ ቁና *** ቡና 3 ብር የሁሉም ድምር 92 ማሪያ ቴሬዛ ብር

* መረሻት ማለት የበቅሎው ኮርቻ ከልባቡና ከልጓሙ ባንገቱ ከሚያደርገው ጋር ያለው የጠፍር ጌጥ ብርማ ወይም ወርቅማ ሥራ ሲሆን ነው ።

**አንድ ዳውላ 80 ኪሎ ግራም ?

***አንዱ ቁና 16 ኪሎ ከ800 ግራም

1 Impression d' Ethiopie, Tome II, PP. 142 - 144



ይሆናል ። ይኸ ደግሞ ባመት ቢታሰብ 1.104 ብር ይሆናል ። አንድ ነዋሪ መልከተኛ እስከ 5 ዓመት ቢቆይ 5,520 ብር ይፈጃል ማለት ነው ።[1]

ይህ ላንድ ሰው የታሰበው የመብል ጉዳይ ሰውዬው መልእክቱን ጨርሶ ሲሰናበት አሁንም እንደ ሰውየው ደረጃ የሚሰጠውን የወርቅ ፥ የብር ፥ የዝሆን ጥርስ ሥራ ፤ የሚቀበለውን ጐራዴውን ፥ ሰይፉን ፥ ጋሻውን ፥ ጦሩን ፥ መስቀሉን ፥ መጽሐፉን ፥ ልብሱን አይጨምርም ። አንዳንድ ጊዜ ራሱ ወርቁ በወቄት ተለክቶ ወይም የዝሆን ጥርሱ በፈረሱላ ታስቦ የሚሰጥበት ጊዜ አለ ። ያንዱ ወቄት ወርቅ ዋጋ በዚህ ዘመን (1900 ዓ.ም.) 37 ብር አንዱ ፈረሱላ የዝሆን ጥርስ 180 ብር ይሆናል ።

ይኸ ሁሉ የውጭ አገር ነገሥታት ወይም መልእክተኞች ፥ አገር ጐብኝዎች በገጸ በረከት ስም ከሚያቀርቡት አውሮፓዊ ሥራ ሥጋጃ ምንጣፍ ፥ ጠመንጃ ፥ ሽጉጥ ፥ ጐራዴ ፥ ካፖርት ፥ ጨርቃ ጨርቅና ሽቶ . . . የኛዎቹ በረዥም ጊዜና ባንድ ጊዜ የሚሰጡት ይበልጣል ማለት ነው ።

በዚህ ዓይነት ፥ ጣልያኖቹ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ ዠምሮ የሚሰጡት ስጦታ በነርሱ በኩል እንደ ጉቦና እንደ ማባበያ ሲቆጥሩት ምንአልባት አንዳንዱ አንባቢ የኛዎቹ እውነትም ጉቦ የተቀበሉና ተቀብለውም ነገር የሚያበላሹ ሊመስለው ይችላል ። ነገሩ በትክክል ሲታይ የስጦታ ልውውጥ እንጂ ጉቦ የለበትም ። የስጦታውም ዋጋ ቢገመገም ከእንግዶቹ ስጦታ ይልቅ እነርሱ የሚቀበሉት ዋጋ የሚበልጥ ይመስላል ።

1 Italia ed Etiopia P. 51

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## በ17ኛው አንቀጽ አለመሳካት የነአንቶኔሊ ወደ አገራቸው መመለስ

ኮንት አንቶኔሊ ፣ የኢጣልያን ንጉሥ ደብዳቤ ይዞ ከመጣ ወዲህ ቀድሞ ከነበሩት ከኮንት አውጉስቶ ሳሊምቤኒና ልጥ ማረፊያ ከሚቀመጠው ከዶክተር ሊዎፖልድ ትራቬርሲ ጋር እየተመካከረ ከላይ የተመለከትነውን ማስታወሻ በዝርዝር አቅርቦ በማግባባትም ፣ በማስፈራራትም ፣ በማባበልም የ17ኛው አንቀጽ ቃል እንዲረጋ ምንም ቢጣጣር አልሆነለትም ። የሚጣጣረውም ከራሱ መንግሥት የተሰጠውን መመሪያ እግብ ለማድረስ እንጂ ፣ በነገሩ ራሱ ያመነበት አይመስልም ። ስለዚህ አንቶኔሊ በዚህ ጊዜ በሁለት ወገን ተቸግሮ እንደ ተወጠረ ይታያል ።

ባንድ ወገን ያፄ ምኒልክንና የእቴጌ ጣይቱን ፣ የሌሎቹንም በዚህ ጉዳይ የሚያገባቸውን መኳንንት ቁጣና ክርክር በመመልከት 17ኛው አንቀጽ የገባው በወዳጅነትና በፈቃድ እንጂ ፣ በእውነትም በግዴታ ወይም በበላይ ጠባቂነት መንፈስ የተጻፈ አለመሆኑን በመጥቀስ ፣ "ይልቅስ ይኸንን በመሰረዝ ምኒልክን አስደስተን ስለ ወሰኑ ጉዳይ ብንከራከር ይሻላል" እያለ ላለቆቹ ወደ ሮማ ሲጽፍ ፣ "አንድ ጊዜ ለየመንግሥታቱ አስተላልፈን የበላይ ጠባቂነታችን ከታወቀልን በኋላ መሰረዙ ክብራችንን ስለሚነካ ፣ እዚያው እንደ ምንም በርትተህ አንቀጹ እንዲረጋ አድርግ" የሚል የትእዛዝ መልስ ይደርሰዋል ። በዚህም ረገድ ፣ የበላይ አለቃውን ክሪስፒን ማስደሰት እንጂ ፣ ማስቀየም ስለማይፈልግ ከአቅሙ በላይ በሆነው ጉዳይ ገትሮ ሲከራከር ይገኛል ።

በሌላ ወገን ደግሞ ፣ ያገር ተወላጆቹ ዐዋቂዎቹና የውጭ ተወላጆቹ ፈረንሳዮቹም ፣ መስኮቦቹም ሁሉ ፣ "ይህ ቃል የረጋ እንደሆነ ልክ የኢጣልያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እንደ በላይ ጠባቂ (ፕሮቴክቶሬት) መሆኑን ስለሚያስገነዝብ መሰረዝ አለበት" እያሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ያስረዳሉ ። ንጉሠ ነገሥቱም እየጠሩ ፣ "ድሮውንም ይኸ ቃል ባይገባስ ቢቀርስ ብዬህ ነበር ። አሁንም ይኸን ቃል የሚናገረው

አንቀጽ ይሰረዝና ሌላው ይርጋ ፤ ወይም ውሉ እንደ ግዴታ እንዳይ ቆጠር የሚያስችል ሌላ ቃል ይግባና ወዳጅነታችን ይቀጥል ። ከሁ ሉም ይልቅ አንቀጹ ፈጽሞ ይቅር" እያሉ ሲያዋክቡት ፣ እርሱም "ማናቸውንም ለመንግሥቴ ሳላስታውቅ በራሴ ፈቃድ የምችለው ነገር የለም" እያለ መልስ በመስጠት ሰፋ ያለ የክርክር ውዝግብ ከተፈ ጠረ በኋላ ፣ በመጨረሻ አንድ ጽሑፍ በደብዳቤ መልክ ተዘጋጅቶ የንጉሠ ነገሥቱ ማኅተም ፣ የአንቶኔሊ ፊርማና ማኅተም ታትሞበት ለኢጣልያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ እንዲላክና መልሱ ከዚያ እንዲጠበቅ ስምምነት ተደረገ ።

ጽሑፉ እንደ ተለመደው ፡ በደብዳቤ መልክ....ሞዓ አንበሳ ዘእ ምነገደ ይሁዳ . . . ይድረስ ከወዳጃችን ከኡምቤርቶ 1ኛ የኢጣልያ ንጉሥ. . . ብሎ ይጀምርና ፣ ሀ/በፊተኛው ደብዳቤ የኢጣልያንኛው አነ ጋገር ቀርቶ ያማርኛው ብቻ እንዲሆን ብለው አንቶኔሊን ቢጠይቁት ከንጉሤና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳላስፈቅድ አልችልም ማለቱ ፤ ለ/ አሁን ግን ይህ 17ኛው አንቀጽ ቃል በፍጹም እንዲቀር ከአንቶኔሊ ጋር ተስማምተናል ። ይህንንም በወዳጅነት ስናደርግ መቼም ወደፊትም ቢሆን ፣ በወዳጅነት ከውጭ አገር የምፈልገውን በግርማዊነትዎ እር ዳታ ለማድረግ መፍቀዴን በደብዳቤ ስገልጽልዎ ይኸውም በወዳጅ ነት ነው ። እንደኔ ያለ የነጻ አገር (መሪ) በወዳጅነት ካልሆነ በቀር የሚረባ ነገር የለውም የሚልና ሌላም የወዳጅነት አነጋገር ያለበት ነው ። በዚህ ጽሑፍ እላይ እንደ ተባለው ሁለቱም ወገኖች አት መውበት አንዳንድ ግልባጭ ከተለዋወጡ በኋላ እርሱም አንዱን ግል ባጭ ይዞ ሔደ ። እርሱ ግን ፣ ". . . 17ኛው አንቀጽ ይቅር" ሲባል የተረዳው ፣ "እንዳለ ይቅር ፣ ይኸውም ማለት እንዳለ ይርጋ" የተባለ መስሎት ኖሯል ።

ስለዚህ ፡ በአማርኛ የተጻፈውንና የፈረመበትን ከቤቱ ወስዶ በራሱ አስተርጓሚ ባቶ ዮሴፍ (ሌላ ዮሴፍ የልዋ ማረፊያው) ቃል በቃል እያስተረጐመ ሲረዳው ፣ የ17ኛው አንቀጽ መሰረዙን እንደ ተስማማበት ሆኖ መጻፉን የሚያረጋግጥ መሆኑን ተገነዘበው ። በዚህ ጊዜ በንዴት በማግሥቱ ተመልሶ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ፣ ራስ መኰንንና ግራ ዝማች ዮሴፍ ወዳሉበት እልፍኝ ገብቶ ፣ "እኔ የውጫሌ ውል የተ ደረገው ለ5 ዓመታት ነው ፤ ከዚሁ 2 ዓመታት ተቀንሶለታል ። ስለዚህ የ17ኛው አንቀጽ ጉዳይ እንዳለ ይርጋ ፣ ነገሩም መነሣቱ ይቅር አልሁ እንጂ አንቀጹ ይቅር ፤ ይሰረዝ አላልሁም ። አሁንም 'ይሰረዝ' ያላልሁ ትና ያልተናገርሁት ቃል ነውና የተጻፈው ይለወጥ" ብሎ አመለከተ ።



ዐፄ ምኒልክም ፣ "በግልጽ ባስተርጓሚ ተነጋግረን ተስማምተን የተጻፈውና የታተመው አሁን ቢጸጽትህ አይለወጥም" ብለው መለሱ ለት ። በዚህ ጊዜ ፊቱን ወዳስተርጓሚው ወደ ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ መልሶ ፣ "ይኸን ሁሉ የምትዘባርቅ አንተ ነህ" ብሎ ተሳደበ ። በዚህ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ ፣ "ቢያጠፋስ አሽከራችንን እኛ እንቀጣዋለን እንጂ አንተ መሳደብ የለብህም" ብለው በተግሣጽ መልክ መለሱ ለት ። ከዚያ እርሱ ፣ "ውጫሌ ላይ የተዋዋልንበት የፈረንሳዩ ቃል ይታይ" ሲል ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ ፣ "እኛ የምናውቀው አማርኛውን እንጂ የፈረንጅ ቋንቋ አናውቅም" ብለው ሲመልሱለት በጣም ተበሳጭቶ "ተሰርዟል" የሚለው ቃል ያለበትንና እርሱም የፈረመበትን የንጉሠ ነገሥቱም ማኅተም ያለበትን ጽሑፍ ከፊታ ቸው በጫጭቆ ፣ "እንግዲህ ወዳጅነት ቀርቷል ። ጦርነት ብቻ ነው" የሚል ቃል ወርውሮ በድፍረት ደንፍቶ ለመሔድ ሲወጣ ፣ እቴጌ ጣይቱ ከት ብለው በመሳቅ ፣ "ጦርነቱን የዛሬ ሳምንት አድርገው ፣ በዚህ የሚ ደነግጥልህ የለም" ብለው በታላቅ ቁጣ መለሱለት ።[1]

ሁኔታው ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ በቀር እዚያ ያሉትን እነራስ መኰንንና እነግራዝማች ዮሴፍን ሁሉንም አስገረማቸው ። ሁሉም አድራጎቱን እንደ ብልግና ቆጠሩበት ። እውነትም ቀድሞውኑ ያማ ርኛውን ጽሑፍ ከመፈረሙ በፊት ማስተርጐምና መረዳት ፣ ከተረዳ በኋላ መፈረም ወይም እምቢ ማለት ነበረበት እንጂ ፣ ተመልሶ "ቃሌ አይደለም" ብሎ ጽሑፉን ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት መቅደድ ፣ የራሱ ዜጋ ያልሆነውን አስተርጓሚ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት መገሠፅ ከየትም አገር ሥነ ሥርዓት ውጭ መሆኑ የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ በእጁ ያለውን ቀዳዶ በንጉሠ ነገሥቱ እጅ ያለው ንም ለማስመለስ ፈትኖ ሳይሆንለት ከቀረ በኋላ ፣ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሔዶ ጉዳዩን ለሥራ ጓደኞቹ ለኮንት ሳሊምቤኒና ለዶክተር ትራቬርሲ ነግሮ ከተመካከሩ በኋላ ፣ "ከእንግዲህ ወዲህ ምንም ለመሥራት አንች ልምና ወደ አገራችን እንመለስ" ብለው ወሰኑ ። ቢሆንም ፣ "ይኸን ያህል ዘመን የቆየንበትን አገር እንደዚሁ ትተን ዝም ብለን መሔድ አይገባንምና በደብዳቤ ንጉሠ ነገሥቱን እንሰናበት" ብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በኢጣልያንኛ ጽፈው ሦስቱም ፈርመው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ።

---

1 አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ ስለ አወጣጡ ሲጽፉ ፡ "ሰላምታ ነፍጎ እንደ ቡኸር በንጉሦች ፊት ዘሎ ገና ተልፍኙ ቆቡን ተራሱ አድርጎ እንደ ዘላን ከበርቱ እያፎጫጨ ቢሔድ..." በማለት በራሳቸው ልዩ አነጋገር ገልጸውታል ። ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 66—79 Let - -Marefia, L. Traversi, Cap. XXXVII

ለግርማዊ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። በሁለት አገሮች መካከል ክርክር ሲፈጠርና ክርክሩ መንገድ ሳይገኝለት ሲቀር የዚያ መንግሥት መላክተኞች በያገራቸው መመለስ በሠለጠኑት የክርስቲያን አገሮች የተለመደ ነው ። ዛሬ እነሆ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል በወዳጅነት ለመሥራት የፈተንነው ሥራ ፍሬ ቢስ ሆኗል ። በዚህ ዓይነት የኛ በግርማዊነትዎ ግዛት መቆየት ከንቱ ነው ። ለንጉሣችን ትእዛዝ ታማኞች ሠራተኞች እንደ መሆናችን በሐረር በኩል አድርገን ወደ አገራችን እንድንመለስ እንዲፈቀድልን እንለምናለን ። በምንሰናበትበት ጊዜ ፥ እዚህ አገር በደግነት ስለ ተስተናገድንበት ለግርማዊነትዎ ምስጋና እያቀረብን ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ለግርማዊነትዎና ለቤተሰቡ ለሠራዊቱም ደስታና ዕድል እንዲሰጥ እንለምናለን ።

ተጻፈ አዲስ አበባ የካቲት 9 ቀን 1891 ዓ. ም. እ.ኤ.አ

ፊርማ አንቶኔሊ
ሳሊምቤኒ
ትራቬርሲ

ለዚህ መልስ ፥ ዐፄ ምኒልክ እንደዚህ ብለው ጻፉለት ።
"ይድረስ ከኮንት አንቶኔሊ የተለመደ ሰላምታ ፥

እዚህ አገር ከመጣህ ዠምሮ እስካሁን በኔ መንግሥትና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለው ጉዳይ ስምምነት እንዲያገኝ በትእግሥት ስደክም ቆየሁ ። አንተንም እንደ ልብ ወዳጄ እንጂ እንደ አንድ የመንግሥት መላክተኛ አልመለከትህም ነበር ። አንተም እንደ ተቻለህ ወዳጅነትህን አሳይተኸኛል ።

አንድ የመንግሥት መላክተኛ እንኳን ንጉሠ ነገሥቱን ያገሩንም ሕዝብ ሊያከብር ይገባል እንጂ ፥ ትናንት እንደ ሠራኸው ያለ ሊሠራ አይገባም ። ጉዳዩ ያለቀ መስሎኝ የውሉን አሳብና ንጉሡ ኡምቤርቶ ለጻፉልኝ መልስ የተዘጋጀውንና ሁለታችንም ያተምንባቸውን ደብዳቤዎች እኔን በፍጹም ሳትጠይቀኝ ላንድ ንጉሥ የሚገባውን ክብር አጓድለህ በመቅደድህ አሳዝነኸኛል ። በዚህ በሠራኸው አስበህ የተጸጸትህ ሲመስለኝ አንተና ኮንት ሳሊምቤኒ ዶክተር ትራቬርሲም ወደ አገራችን እንድንሔድ ብላችሁ ጠየቃችሁኝ ። በፊት ይኸ ነገር ሳይደርስ የስምምነቱን ነገር ስንነጋገር ያልተስማማንበትን ወገን ንጉሡ ኡምቤርቶና ክሪስፒ ካልፈቀዱ አይሆንም ብለህ ለዚሁ ተመካክረን ጽፈን መልሱን እመጠበቅ ላይ ነበርህ ። አሁን መልሱ ሳይመጣ ያለፈቃዳችን ብትሔድ ደስ አይለኝም ፤ እንሒድ ብላችሁ ከቆረጣችሁ ደግሞ አልከለክላችሁም ። እናንተ እምቢ ብትሉና ብትሔዱም በእናንተ ምክንያት በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ያለው ወዳጅነት የሚጠፋ አይመስለኝም ።

ተጻፈ የካቲት 3 ቀን 1883 ዓ.ም. [1]

1 እነዚህ ደብዳቤዎች ካርሎ ሮሴቲ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ትርጉማቸው በኢጣልያንኛ ይገኛል ። Storia Diplomatica . . .C. Rossetti; P. P. 102 - 103



አንቶኔሊ ፥ ከኢጣሊያ አገር መልስ መጠበቅ እንደማይጠቅመው በመገንዘብ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ወደ አገሩ ለመመለስ ተነሣ ። ንጉሠ ነገሥቱም በጥሩ ዐይነት የተጫኑች በቅሎ ስጦታ በቀር በየአደረበት ፍሪዳው ፥ እንጀራው እንዳይጐድልበት ትእዛዝ ለየሹማምንቱ አስተላልፈው ነበር ። ኢጣልያኖቹም ከአዲስ አበባ ልጥ ማረፊያ (አንኮበር) ደርሰው የልጥ ማረፊያ ጣቢያቸውን ፥ "እስክንመለስ ድረስ ጠብቅ" ብለው ገመዳ ለሚባል ሰው አደራ ብለው ከልጥ ማረፊያ ወደ ሐረር ሔዱ ከሐረርም እንደዚሁ ቺዛሬ ኔራሲንና በርሱ እግር ተሾሞ ሐረር ራስ መኰንን ዘንድ ለመቀመጥ የመጣውን ካርሎ ዲሩዲን ጨማምረው በዘይላ በኩል አድርገው ወደ አገራቸው ተመለሱ ። እንደ ተመለሱም አንቶኔሊ በምኒልክ ፊት ያሳየውን የብልግና አቅዋም በመገንዘብ ፥ በኢጣልያ አገር ወቀሳ ዠምረውት ነበርና ላለቆቹ ሁኔታውን በራፖር በገለጸበት ላይ ራሱን ከጥፋተኛነት ለማዳን ሲል ፥ "ጽሑፉ በስሕተት ነውና የተጻፈው እመልስልሃለሁ ብለው በኋላ ከዱኝ" በማለት ጥፋቱን ሁሉ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለመላከክ ሞከሯል ። በኢጣልያም አገር የርሱን አባባል የሚያስተባብል ወኪል ስለሌለ ፥ ዐፄ ምኒልክ አንቶኔሊ እንደሔደ ወዲያው አከታትለው የርሳቸውን አቅዋም ለኢጣልያ ንጉሥ ዝርዝር ጉዳዩን በፈረንሳይኛ ቋንቋ አጽፈው በመላክ ለማስተባበል ሞክረዋል ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፥ ከሥልጣን ላይ ከወጡ ዠምሮ ያለፈውን በኢትዮጵያ የደረሰውን የጦርነት ዘመን በመገንዘብ ፥ በዚህ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ በጫኑበት ወቅት ባገር ላይ የተነሣውን የክብትና የሰው እልቂት በማሰብ ፥ በቅርብ ጊዜ በእርሳቸው ቀጥተኛ አመራር ሥር የተጠቃለሉትን ታላላቅ አውራጃዎች ለማጠናከር በማናቸውም ረገድ ባገር ላይ ትልቅ ጦርነት ከውስጥም ፥ ከውጭም እንዳይቀሰቀስ አጥብቀው ከመጣር ላይ እንደሆኑ ሁኔታው ያስገነዝበናል ። በየምክንያቱ ለውጭ አገር መንግሥታት መሪዎች በጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ሕዝቡን ከጦርነት ለማሳረፍ ፥ ወዳገር ውስጥ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት ያላቸውን ምኞት ደጋግመው መግለጻቸው ተጠቅሷል ። ከኢጣልያም ጋር ጦርነት እንዳይነሣ በበኩላቸው አጥብቀው የሚጣጣሩት ለዚህ ነው ። በየደብዳቤያቸውም ፥ ባነጋገራቸውም ላይ የሚታየው ይኸው ሰላምና ዕረፍት ፈላጊ መሆናቸው ነው ።

ኢጣልያኖቹ ፥ በአውሮፓውያንነታቸው ፥ በሥልጣኔያቸውና በኃይላቸው ተማምነው የሚመኩ እንደ እንግሊዝ ፥ እንደ ፈረንሳይ ፥ እንደ ጀርመንና ቤልዥክ በአፍሪካ ሰፊ ቅኝ አገር ለማግኘት በምኞት ተውጠውና ቆርጠው የተነሡ በመሆናቸው ፥ ባፄ ምኒልክ በኩል የሚደረገውን ሰላማዊ መንገድ ሁሉ ከምንም አልቆጠሩትም ። በፊተኛው

ዘመን ምኒልክን ባዬ ዮሐንስ ላይ ለማስታጠቅና ለማዋጋት ተነሥተው በምኒልክም ፣ በዮሐንስም መቻቻል የሳተውን የውስጥ ጦርነት አሁን አንቶኔሊ ከነጓደኞቹ 17ኛውን አንቀጽ ለማስቀበል ፈትኖና ሳይሳካለት ቀርቶ ወዳገሩ ከተመለሰ በኋላ ፣ ራስ መንገሻን አስታጥቀው ባዬ ምኒልክ ላይ ለማስነሣትና ለማዋጋት ፣ ከዚህም ውጊያ መካከል የነርሱ የመስፋፋት ዓላማ ግቡን እንዲመታ ይጣጣሩ ዠመር ። ይኸን የመሰለውንም የከፋፍለህ ግዛ ዓላማ ጣልያኖቹ በምኒልክ ላይ ለመፈጸም ሲመኙ ፣ ይልቅስ ምኒልክ ኢጣልያንና መንገሻን እርስ በእርሳቸው ከፋፍለው እንደምን እንደ አዋጉዋቸው ወደፊት ስንመለከት ፣ በፖለቲካ ዘዴ ትምህርት ካገኙት ኢጣልያኖች ይልቅ ፣ ምንም አውሮፓዊ ትምህርት ያልቀሰሙት ምኒልክ በልጠዋል ። ስለዚህ ነው አንጀሎ ዴልቦካ የሚባለው የኢጣሊያ ጸሐፊ ፣ "... መንግሥቱን ለመገንባት ምኒልክ ምንም ዓይነት አጋጣሚ ጊዜና ሁኔታ አያመልጠውም ። በሚያምኑቱት ወገኖች ላይ ይጠቀማል ። የርሱ መዘግየት በምቹው ጊዜ ላይ ለመጠቀም ነው ። ይኸም በፍጥረቱ ያለውን የፖለቲካ ባሕርያዊ ስጦታ ያሳያል"[1] ሲል አትቷል ።

---

1. Gli Italia in Africa Orientale, P. 222.



# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

## የውጫሌ ውል በግራዝማች ዮሴፍና በግለኞች ላይ ያደረሰው ችግር

የውጫሌው ውል ፣ 17ኛው አንቀጽ ያስከተለው ችግር በዝርዝር ሆኖ በየመልኩ ቢጻፍ ራሱ አንድ መጽሐፍ ይወጣዋል ። አሁን በመጨረሻ ዘመን ጉዳዩን በዝርዝር ያጠኑት የኢጣልያ ጸሐፊዎች ነገሩን ከበላይ ሆኖ በሐሰት ፣ በአጠራጣሪና በተጭበረበረ መንገድ አንቶኔሊ ያቀረበለትን ውል በመቀበል ፣ ምክር ቤቱን በማታለል ወደ ዓድዋ አዋራጅ ጦርነት የመራው ራሱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ መሆኑን ተገንዝበውታል ። ከነዚህም ውስጥ ካርሎ ጁሊዮና አንጀሎ ዴልቦካ ፣ ናፖሊዎኒ ኮላጃኒ ፣ ቢዘኒ አኪለ ይገኛሉ ።[1]

ዮሴፍ ንጉሤ ፣ የትግራይ ተወላጅ ናቸው ። በምጥዋ በካቶሊክ ሚሲዮን ተምረዋል ። በኋላም ሙሴ አርኑ ከሚባሉት የፈረንሳይ ነጋዴ ዘንድ ተቀምጠው በአስተርጓሚነት ሠርተዋል ። ቀጥሎም ከጓደኛቸው ከገብረ ተክሌ ጋር ሆነው ወደ ምኒልክ ገብተው በማስተርጐምም ፣ ወደ ኤደንና ወደ ጅቡቲም በመላክ ንጉሥ ምኒልክን አገልግለዋል ። ገብረ ተክሌ ኤደን ሆነው ምኒልክ አገራቸውን ለማሠልጠን ያላቸውን ምኞት ከመግለጽ ጋር ከፈረንሳይ መሪዎች ከነማጀንታ ጋር እንዲወዳጁ ከመጣጣር አልፎ ፣ በነአቡበከርና በነአንፋሪ አማካይነት የጦር መሣሪያ ለምኒልክ እንዲደርስ ያደርጉ ነበር ።[2]

በምኒልክ ቤተመንግሥት በአነጋጋሪነት ከገብረ ተክሌ ፣ ካቶ ዮሴፍ (የልጥ ማረፊያው) ፣ ካቶ ገብርኤልም ፣ ካቶ ሚካኤልም ፣ ከማንም ኢትዮጵያዊ የበለጠ የታወቁት ዮሴፍ ንጉሤ ናቸው ። እርሳቸውም በዚሁ አገልግሎታቸው የግራዝማችነት ማዕረግ አግኝተው የታወቁ ሆነዋል ። ከውጫሌ ውል በኋላ ፣ ራስ መኰንንን ተከትለው ሮማ መሔዳቸውን በምዕራፍ አምስት ላይ አውስተናል ። ከጠቡ በፊት

---

1 Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca,, PP. 352 - 353

2 በሰኔ 11 ቀን በ1870 ዓ.ም. ከኤደን ለማጀንታ የጻፈው ደብዳቤ ቁ. 361 ፣ ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ።

በነአንቶኔሊ አማካይነት ልጃቸው አበራ ዮሴፍ ሮማ ላይ እየተማረ አድጓል ይባላል ።

ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ ፤ ባስተርጓሚነታቸው የተነሣ በውጫሌው ውልና በ17ኛው አንቀጽ ምክንያት ከሁሉ የበለጠ ከችግር ላይ የተገኙ ናቸው ። ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌይቱ ፊት ፤ "ይኸን ሁሉ የምትዘባርቅ አንተ ነህ" ብሎ አንቶኔሊ እንደ ሰደባቸው ተመልክተናል ። ከኢጣልያኖቹ ዘንድ አስተርጓሚዎቹ ሁሉ በብድርም ፤ ያለብድርም ገንዘብ ተቀብለዋል የሚል ወሬ ስለነፈሰ ፤ በእቴጌይቱና በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ጥርጣሬ አድሮ ላጭር ጊዜ ፊት የመነሣት ዕድል የገጠማቸው ይመስላል ። የዚህን ጉዳይ ሳሊምቤኒ በጻፈው ማስታወሻ ላይ ፤ "... በ17ኛው አንቀጽ አተረጓጐም ተንኮል እንዳለበት በንጉሡ ልብ ላይ ጥርጣሬ አድሮበታል" ካለ በኋላ ፤ "በዚህ ነገር የታመመ የከሳ ዐይኑ ጐድጉዶ የሚታየው ግራዝማች ዮሴፍ ነው " ሲል ጠቅሷል ።[1]

ጠቅላላው ሁኔታ ሲታይ ከዐሥር ዓመት በላይ ዮሴፍ ከአንቶኔሊ ጋር ሲተዋወቁ ፤ እነ አንቶኔሊ ለየመኳንንቱ ገጸ በረከት በማቅረብ አስተርጓሚውን ሁሉ በገንዘብ ስጦታ ስበን የምኒልክን መንግሥት ቦርቡረን እንገባለን ብለው በተያያዙበት ሰዓት እንደ ሌላው ሁሉ ፤ ግራዝማች ዮሴፍ ልዩ ልዩ ስጦታ መቀበላቸውና ገንዘብ ችገር ባላቸው ወይም ጥሬ ብር በአማራቸው ጊዜ በብድርም በጉርሻም ሳይቀበሉ አልቀረም ። ብድር ብለው የተቀበሉትንም ፤ ጣሊያኖቹ እንደ ጉቦ ሆኖ ለመሳብ እንዲመቻቸው ሲሉ መልሰው አይቀበሉም ። ዮሴፍም ጕትጕተው አይሰጡም ይሆናል ። ይሁን እንጂ ፤ ግራዝማች ዮሴፍ በገንዘብ ተደልለው በክዳት መልክ የ17ኛው አንቀጽ ቃል እንዲገባ ያደረጉበት መንገድ አይታይም ።

በዚህም ላይ ፤ የፈረንሳይኛ ዕውቀታቸው በንግግር ላይ የተመሠረተ እንጂ ጠለቅ አድርገው በክፍል ያልተማሩት ይመስላል ። ለፈረንጆቹ በተለይም ስለማናቸውም ጉዳይ ደብዳቤ ሲጽፉ በአማርኛ ነው እንጂ በፈረንሳይኛ ሲጽፉ አልታየም ። ምናልባት ባለፈው ምዕራፍ በእርሳቸው አስተርጓሚነት ምኒልክና አንቶኔሊ በመጨረሻ ሲከራከሩ ንጉሠ ነገሥቱ ፤ "ይህ 17ኛ አንቀጽ ቀድሞውንም እንዲያው ነውና የገባው አሁንም ይቅር ፤ ይኸውም ማለት ይሠረዝ" ሲሉ ግራዝማች ዮሴፍ ለአንቶኒሊ "qu'il reste" ብለው ተርጕመውለት ይሆናል ። ቃል በቃል "rester" የሚባለው ግሥ ፤ በአማርኛ መቅረትን ሲያሰማ በፈረንሳይ ይርጋን ያሰማል ። ይህ አተረጓጐም ይሆናል

1 C. Zaghi, Crispi e Menelich P. 258



ኮንት አንቶኔሊን ያስቆጣና ከመሳደብ ያደረሰው ። በግራዝማች ዮሴፍ በኩል ደግሞ ፤ አንቶኔሊን ከተዋወቁበት ጊዜ ዠምሮ ከልብ በወዳጅነት ሲያገለግሉት ኖረው ሳለ ፤ እርሳቸው ባማርኛ የጻፉትን "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል" የሚለውንና ንጉሠ ነገሥቱም የተቀበሉትን ቃል ወዳገሩ ቋንቋ ሲገለብጥ በተንኮልና በማጭበርበር ፤ "S. M. il re dei re d'Etiopia consente di Servirsi del governo di S. M. il re d'Italia" የሚለውን ቃል ጨምሮ ይኸንኑ መንግሥቱ ለየመንግሥታቱ በማስተላፍና ፤ "የኢትዮጵያ የበላይ ጠባቂ ሆነናል" በማሰኘት ፤ እኔን በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ አስወጋኝ የሚል ቅሬታ ሳይሰማቸው አልቀረም ።

ስለዚህ ፤ እነአንቶኔሊ ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ እንደ ተመለሱ አከታትለው ለአልቤርቶ ጆሴፒ ፒዛኒ አሁንም በአማርኛ አንድ የስሞታ ደብዳቤ ጽፈዋል ። ፒዛኒ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ የቅርብ ረዳትና የካቢኔ ዲሬክተር ሆኖ የሚያገለግል ከፍተኛ ባለሥልጣን ነበር ። ግራዝማች ዮሴፍ ከደብዳቤው ግንኙነት በቀር ሮማ ከራስ መኰንን ጋር የሔዱ ጊዜ የተዋወቁትና የተላመዱት ይመስላል ። የደብዳቤውን ቃል ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

" ... የተላከ ከግራዝማች ዮሴፍ ይድረስ ከካባሊዬሬ ፒሳኒ ደሲዬ እጅጉን እንዴት ነህ ። እኔ ከአንተ ከተለየሁ ከጤናዬ በቀር በሌላው የመንግሥት ጉዳይ ሁሉ በጦርነት ተቀምጫለሁ ። ይህ ሁሉ መሆኑ በኮንት አንቶኔሊ ሥራ የተነሣ ነው ። ኮንት አንቶኔሊን ካወቅኋቸው ከ14 ዓመት ይበልጣል ። ይህን ያህል ዓመት ስንኖር ከማገልገል በቀር ያሳዘንኋቸው ነገር ያለ አይመስለኝም ። ደግሞ ወዳጁን በማይታይ ጦር መግደል የጥሩ ሰው ሥራ አይደለም ። እውነተኛ ሰው ሲጣላ በጦር በጎራዴ ፤ በጠመንጃ ይጣላል እንጂ ወዳጁን በመርዝ አይገድልም ። ኮንት አንቶኔሊ ግን ፤ በተወለድሁበት አገር እንኳን አገልግዬ ለምኜ እንዳልበላ አድርገውኝ ሔዱ ። ከመንግሥት የመጣ ሰው ቢሆንም ባይሆንም ፊት ለፊት ተናግሮ የተገሰጠ ሥራ ሠርቶ ባገሩም በተላከበትም አገር ይመሰገን ዘንድ ያደርጋል እንጂ ፤ ንጉሠ ነገሥትን እስከ ሠራዊቱ ለማታለል የቄሶች ዘር መሆን ያስፈልጋል ።* የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐጤ ምኒልክ የፈለጉት ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የሚቀር ፍቅር ለማድረግ ነበር እንጂ ፤ ዐጤ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ጉዳያቸው ሲሞላ ወንድማቸውን ወደናንተ አይልኩም ነበር ። ነገር ግን ምስጋና ቢስ እሆናለሁ ብለው የኢጣልያ መንግሥት ፍቅር ለመጨረስ ፤ በቤተ መንግሥቱ ብዙ ትልልቅ ሰው ሞልቶ ሳለ የሚወዱትን ወንድማቸውን (ራስ መኰንንን) ልከው የኢጣልያን መንግሥት

* የካርዲናል ጃኮሞ አንቶኔሊ ተወላጅ መሆኑን አሹፈው ለመጥቀስ ነው ።

ማክበራቸውን ገለጡት እንጂ ዐጼ ዮሐንስ ሳሉ የችግራቸው ጊዜ ያለመኗችሁን (ያልጠየቋችሁን) ጥግነት ዛሬ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲባሉ ምን ቢቸግራቸው የኢጣልያ መንግሥትን ጥግነት ይለምናሉ ። ነገር ግን 30 ምልዮን ነፍስ (ሕዝብ) ባለበት አገር አንድ መከረ ይጠፋና በ31 ዓመት ሙሉ ደከማችሁ ከኢትዮጵያ ጋር ያደረጋችሁት ፍቅር ይፈርሳል አይመስለኝም ።”

ይኸን ካመለከቱ በኋላ ፣ በጠቅላላው በኮንት አንቶኔሊ ምክንያት የተበላሸው የኢትዮጵያና የኢጣልያ ግንኙነት ከሳሊምቤኒና ከትራቬርሲ ጋር ሆነው እንደገና እንደሚቃና ለመግለጥ ያላቸውን ምኞት በማውሳት ፤

“ላይረባ ይህ 17ኛ ክፍላችሁ (አንቀጽ) ነገሩን ሁሉ አበላሸብን ይህ ነገር (አንቀጽ) ባይኖር እኔና ኮንት ሳሊምቤኒ ብዙ ጉዳይ እንሞላ ነበር ። ደግሞ ሁሉን ነገር በደብዳቤ ዛሬ መጻፍ አይቻለኝም ። የኔንና የኮንት ሳሊምቤኒን ኑሮ የነገሩን መጨረሻ ከሐኪም ትራቬርሲ ታገኙታላችሁ ።[1] ” የሚል ቃል አስፍረዋል ።

በዚህ ዓይነት ፣ ትራቬርሲና ሳሊምቤኒ የበላያቸው ከሆነው ከአንቶኔሊ ጋር በከርከሩና አገር ለቆ በመሔዱ የተባበሩ ቢመስልም ፣ ከልባቸው የውጫሌውን ውል እንዳልተቀበሉትና ማጭበርበር እንዳለበት ተረድተው ይህ አንቀጽ ቀርቶ ከምኒልክ ጋር ያላቸው የቆየ ወዳጅነት እንዲረጋ ተመኝተዋል ማለት ነው ።

ነገር ግን ፣ በአንቶኔሊ ዐውቆ ማጭበርበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ፣ “አንድ ጊዜ ለዘለቄታ በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነትን ለኢጣልያ አስገኘሁ” ብሎ በምክር ቤቱ ፊት የፎከረበትና ለመንግሥታቱ ያስተላለፈበት ጉዳይ ስለሆነ ፣ የሁለቱ ባለሥልጣኖች ከግራዝማች ዮሴፍ ጋር መተባበር በምንም ዓይነት ሊጠቅም አልቻለም ። እነሱም በልባቸው የራሳቸውን መንግሥት እየታዘቡ ለእንጀራቸውና ለእድገታቸው ሲሉ ባላመኑበት ነገር ከአንቶኔሊ ጋር ተባብረዋል ማለት ነው ።

1 Archivio Storico dei Soppressi . . .(Etiopia) XV 1857 - 1895) ROMA.



# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## ከነአንቶኔሊ መመለስ ወዲህ የኢጣልያኖች አያያዝ የራስ መንገሻና የዠኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ መስማማት

በኢጣልያ አገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ተሽሮ ማርኪዜ ዲሩዲኒ አንቶኒዎ* ስታራባ ተሾሞ ነበር ። እርሱም አጭር ጊዜ እንደሠራ ተሽሮ እ. ኤ. አ. ግንቦት 15 ቀን 1892 ዓ. ም. ጆዎቫኒ ጂዎሊቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ ብረ ቤኔዲቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ ። እነአንቶኔሊ ከተመለሱ ወዲህ የኢጣልያ ባለሥልጣኖችና በኤርትራ የሚገኙ ወኪሎቻቸው ፣ “ምኒልክ በፊት የሸዋ ንጉሥ የነበሩ ጊዜ ገራገር ፣ የዋህና ጣልያኖችን ወዳድ የነበሩት አሁን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ሲጭኑ ተለውጠው ጥብቅና ክፉ ሆኑ ። የቀድሞውን የኛን ወዳጅነት ትተው ፣ ጉዳያቸው ከተሟላና የጦር መሣሪያ ከሰበሰቡ በኋላ ፣ ከፈረንሳይና ከመስኮብ መንግሥታት ጋር ይወዳጁ ዠመር ። ይኸን ለማድረግ የሚገፋፉ የኛ ጠላቶች የሆኑትና አዲስ አበባ የሚቀመጡት የፈረንሳይ ፣ የስዊስና የመስኮብ ተወላጆች ናቸው” እያሉ ያሙ ዠመር ።

ዶክተር ትራቬርሲ ፣ “. . . ሁል ጊዜ የሸዋን ሐቀኝነት እጠራጠር ነበር ። ምኒልክ አሁን የፈለጉትን አግኝተዋል ። ለኛ የመልክ ውበት ሲል የሐበሻ ጠባይ የሚለወጥበት ምክንያት የለም ። በሚቴ ንጉሠ ነገሥትና ባሁኑ ንጉሠ ነገሥት መካከል ልዩነት የለም ። በመካከላቸው ያለው ልዩነት ያኛው ዮሐንስ ፣ ይኸኛው ምኒልክ በመባል የሥያሜ ልዩነት ብቻ ነው”[1] ሲል ጽፏል ።

በኢጣልያኖቹ ፊት የሁለቱም ነገሥታት ኃጢአት የኢትዮጵያን ወደብና አውራጃ ስንወር ፣ ወሰናችን እስከ መረብ ይድረስ ስንል ፣ ለምን ዝም ብለው አይመለከቱም? ለምንስ ይከራከራሉ ነው ። ባለሥልጣኖቹ ያን ጊዜ እርስ በርሳቸው የተጻጻፉበት ሰነድ ዛሬ ሲነበብ

* ሐረር የመጣው ዲሩዲኒ ዘመዱ ነው ።
1 Let - Marefia - L. Traversi, P. 386.

በነርሱ ዘንድ ፡ “እገሌ የሚባለው ራስ ወይም ደጃዝማች ኢጣል
ያንን ይወዳልን ”ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ያለውን አን
ዱን ወኪሉን ሲጠይቅ ፡ ወኪሉም አዎን ብሎ ሲመልስ ትርጓሜው
ይህ ራስ ወይም ደጃዝማች ኢጣልያ ከኢትዮጵያ አንዱን አውራጃ
ቆርሳ ብትወስድ ፡ መላውንም አገር ብትወር ዝም ይላል ፤ በዚህ የተ
ነሣ የኢጣልያ መንግሥት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቢዋጋ ወደኛ ዞሮ
ሊሰለፍ ይችላል የሚል የቂል ስሜት ነው ። እገሌ ጣልያንን አይወ
ድም ሲሉ አገሩን ብንወር ሊዋጋን ይችላል ነው ። በዚህ ዓይነት አገ
ሩን ከድቶ ለነርሱ የሚያደላውን ፡ ወሬ የሚያቀባብለውን ፡ “ብልህ ፡
ሥልጣኔ ወዳድ” እያሉ ሲያሞጋግሱ ፡ ያኛውን አገር አፍቃሪ ፡ “ግትር
(ፋናቲክ) ሞኝ” እያሉ ሲጠሉ ሲያጥላሉ ይታያሉ ። ነገሩን ሁሉ እንደ
ራሳቸው በመገመት ፈንታ የአፍሪካዊውን መልክ የሚመለከቱት
በተዋረደ ዓይነት ነው ። በነርሱ ዘንድ በዚያን ጊዜ ያገር አፍቃሪነት
ስሜቱም ፡ መብቱም የተሰጠው ለአውሮፓዊ ብቻ እንደሆነ አድር
ገው ነው የሚገምቱት ።

መቼም ሁሉም ቢሆን ፡ “ጥቁር ፡ አገርና የራሱ ነጻ መንግሥት
አይገባውም” ብሎ የመናቅ ፡ የነጭን ዘር የማኩራት ጉዳይ ነው እንጂ
ያለዚያ በንጹሕ ወዳጅነትና ባገር ጉዳይ ያለውን ግልጽ ልዩነት ሳያ
ውቁት ቀርተው አይደለም ። እነርሱ ራሳቸው በቅርብ ጊዜ ከአው
ስትሪያ የቄሣር ግዛት ተዋግተው ደማቸውን አፍስሰው ነጻነታቸውን
ያቋቋሙ ስለሆነ ፡ በነጻነትና በተራ ወዳጅነት መካከል ያለው ልዩነት
እስኪደናገራቸው ድረስ ይኸን ያህል ሞኞች አይደሉም ። ይኸውም
ሆኖ አገሩን ከዶ ለነርሱ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግላቸውን በልብ እየ
ታዘቡ ፡ አበክሮ የሚጠላቸውንና የሚዋጋቸውን ግን ፡ በልባቸው ማከ
በር የሚወዱ ከመካከላቸው እንደማይጠፉ የታወቀ ነው ።

በጠቅላላው አብዛኞቹ ኢጣልያኖቹ ግን ፡ በአውሮፓና በአፍሪካ
መካከል ያለውን ሁኔታ ሁሉ ባንድ ዓይነት አይመለከቱም ። ቢማርም
ባይማርም ፡ በጠባዩ ወይም በትምህርቱ ከነሱ የተሻለ የሞራል ከፍታ
ቢያሳይም ፡ ባያሳይም አፍሪካዊውን የሚመለከቱበት የዚህ ዘመን
ዐይናቸውና የሚመዝኑበት አእምሮአቸው ከአውሮፓዊው ጋር የተለ
ያየ ነው ። “አውሮፓዊው ለገዥነት የተመደበ አገሩን አፍቃሪ ፡ ጥቁር
ግን ላበላው ብቻ የሚሞት ፡ የነጻነትን ጣዕም ያላጣጣመ ፡ የወገን
ፍቅር የሌለው ነው” ብለው ያምናሉ ። ይኸ ከሆነ ደግሞ ያልሠለጠ
ነው አፍሪካዊ በሠለጠነው አውሮፓዊ መገዛት አለበት የሚሉና እም
ነታቸውን ሁሉ በዚህ መስመር ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው ።



በተለይ ደግሞ ፡ ይህ ዘመን አውሮፓውያን ፡ አፍሪካን ተከፋፍለው
የሚገዙበት ጊዜ ነበር ። ከዚህም አልፎ የቤልዥክ ንጉሥ ፡ ዳግማዊ
ሊዎፖልድ ፡ ኮንጎን (ዛየርን) የሚያህል ታላቅ አገር ለግሉ ይዞና አቆይቶ፡
በኋላ እንደ ጉርሻ ሳገሩ ፡ ለቤልዥክ በስጦታ መልክ እ.ኤ.አ. በ1906
ዓ. ም እስኪያስተላልፈው ድረስ እንደግል ንብረት ይዞ በወኪሉ የሚ
ያስተዳድርበት ጊዜ ስለነበረ ፡ ጣልያኖቹም የኢትዮጵያን ነጻ መንግ
ሥትነት መቀበሉ ይቀፋቸው ነበር ። የነርሱው ተወላጅ የሆነው ፖላሚ
ንጊ የሚባለው ኢጣልያዊ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የዚህን ጉዳይ
ሲያብራራ ፡ “የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታዊ
መንግሥት መኖሩን እንደማያውቅ ይመስል ነበር”[1] ሲል አመልክ
ቷል ። እውነትም ከዓድዋ ድል ወዲህ ኢጣልያኖች በጽሑፍም
በቃልም ምኒልክን ፡ “ንጉሠ ነገሥት እያሉ በውጫዊ መልክ ለማከ
በር ቢገደዱም ፡ እርስ በርሳቸው በሚጻጻፉበት ጊዜ አንዳንዶቹ ንቀታ
ቸውን አይሰውሩም ። ይህ አገር በሺ የሚቆጠር ዘመን ነጻነቱን ጠብቆ
የኖረ ፡ በታሪኩም ፡ በዠግንነቱም የሚኮራ ፡ በቅርቡ ባፄ ዮሐንስ ጊዜ
ግብጾችን ሁለት ጊዜ ተዋግቶ የመለሰና ነጻነቱን ያጠነከረ መሆኑ
በቅኝ አገር ምኞት የተሸፈነው አእምሮአቸው በትክክል ሊመለከ
ተው አይችልም ነበር ። ሊመለከቱ የሚችሉት ወገኖች በጣት የሚ
ቆጠሩ ናቸው ። እነሱም በዚህ ጊዜ ቢናገሩም ፡ ቢጽፉም አድማጭም
የላቸውም ። እንደ ከሐዲም እየተቆጠሩ በምክር ቤትም በጋዜጣም
ይዘለፉ ነበር ።

ስለዚህ ስለ ወሰኑም ፡ ስለ አንቀጹም አዲስ አበባ ላይ ገንዘባቸውን
ረጭተው ፡ አባብለውም ፡ አስፈራርተውም ጉዳዩ ሁልጊዜ ጥሬ በመ
ሆኑ ተስፋ ቆረጡ ። እነአንቶኔሊ ወደ አገራቸው እንደ ተመለሱ አስ
ቀድሞ ፡ “አንቀጹ ካልጸደቀ መንገሻና አሉላ ቢሸፍቱብዎት ፡ እንግሊ
ዞች ቢነሡብዎት መደገፍ አይቻለንም . . ,” እያሉ ያስፈራሩበትን
አሳብ እነርሱው ራሳቸው መሳፍንቱን በማሸፈት በሥራ ለመግለጽ
ተነሣሡ ። በነዚሁ ከኢትዮጵያ በተመለሱት ወኪሎችና በጠቅላይ
ሚኒስትሩ ተመርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ባፄ ምኒልክ ላይ
ለማስነሣት ከመደባቸው ውስጥ ለዋናውና ለቀንደኛው ለራስ መን
ገሻ ፡ “ማናቸውንም የሚያስፈልግዎትን ነገር ምጥዋ ወዳለው የበላይ
ኃላፊያችን ቢልኩ ይከናወንልዎታል” የሚል ደብዳቤ በሰው እጅ
በመላክ ራስ መንገሻን ለማሸፈት መቀስቀስ ዠመረ ። እርሳቸውም
ያፄ ዮሐንስ አልጋ ወራሽነት ከልባቸው ስለ አልጠፋ ፡ ነገሩን በደስታ
ተቀብለው መልስ ሰጡ ።

---

1 Palamenghi. Crispi e Menelich, . . p. 307.

ይሁን እንጂ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ከነአንቶኔሊ ጋር በተጣሉ ጊዜ ጠቡን በማባባስ እራዝመው ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ፈጽሞ ላለመቆራረጥ ይጠነቀቁ እንደ ነበርና እንደዚሁም የኢጣልያ ንጉሥና ራስ መንገሻ በሚጻጻፉበት ጊዜ ፡ ውስጡን ልብ ለልብ እየተዋወቁ ወይም በመልክተኛ አማካይነት በምስጢር ግልጹን እየተነጋገሩ በጽሑፍ ላይ በሚያሰፍሩት ቃል ግን ፡ የኢጣልያ ንጉሥም ራስ መንገሻም እንደሚጠነቀቁ በየደብዳቤዎቹ ላይ ይታወቃል ።

በዚህ ምክንያት ፡ እነአንቶኔሊ በየካቲት ወር የስንብት ደብዳቤ ጽፈው ወዳገራቸው እንደ ተመለሱ ፡ ራስ መንገሻ ፡ ቀድሞ ምኒልክ ባዬ ዮሐንስና በኢጣሊያኖች ጠብ የተጠቀሙትን መጠን አሁን ደግሞ በፋንታቸው በምኒልክና በኢጣልያኖች ጠብ ለመጠቀም ሲሉ ፡ በሐምሌ ወር መዠመሪያ ላይ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ፡ ካዬ ምኒልክ ደብቀው ፡ ከኢጣልያ ንጉሥ ለመጣላቸው ደብዳቤ መልስ ሰጡ ።

> በእግዚአብሔር ቸርነት በአገር ፈቃድ የነገሠ 1ኛ ኡምቤርቶ የኢጣልያን ንጉሥ . . . እኔ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ደህና ነኝ ። ባለፈው መልክታችሁ አንድ ነገር ከኔ ብትፈልጉ ምጽዋ ወዳለው ወደኔ ሹምና ጸሐፊ እመልክቱ ብላችሁ ጽፋችሁልኛል ። ልዑል ሆይ እኔ ከናንተ ፍቅር ለማድረግ ነው እንጂ ፡ ሌላ ነገር የምፈልገው የለኝም ። ፍቅራችሁንም ለዘለዓለማዊ ፍቅር እንድትሆን በልቤ ያለ ቅን አሳቤን በዚሁ ደብዳቤ እገልጽላችኋለሁ ። ነገር ግን እኔ የምፈልገው ፍቅራችን ለጊዜው ብቻ አይደለም ። ለትውልደ ትውልዳችን እንድትሆን ነው ። እንደ አሳቤ ሊሆንልኝም ተስፋ አለኝ ። ሐምሌ 6 ቀን 1882 ዓ.ም.

ለዚህ ደብዳቤ የኢጣልያ ንጉሥ እንደዚህ ሲል ይመልሳል ።

> ራስ መንገሻ ፡ የንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ልጅ ጤና ይስጥልኝ ። የጻፉልኝ ደብዳቤ ደረሰኝ ። እጅግም ደስ አለኝ ። እኔም ደግሞ ከናንተ ጋር ወዳጅነት ለማድረግ ብዙ ምኞት አለኝ ። በኢትዮጵያ ሁሉ በዳግማዊ ምኒልክ የናንተ ንጉሠ ነገሥት ብዙ ተስፋ አለኝ ። ነገር ግን አሳቤና የናንተ አሳብ ይስማማ እንደሆነ ለመመርመርና ለማስረገጥ የኔ እሙን አሽከር ዶክተር ነራዚኒ ከወዳጃችሁ ከዶክተር ዴማርቲኖ ጋር ከናንተ ሊዋዋሉ እስድላችኋለሁ ። ሁሉንም ነገር እንደ አሳቤ ልትስማሙ ተስፋ አለኝ ። የበለጠ ነገር ግን ፡ ከጄኔራል ጋንዶልፊ የምጥዋ ገዥ ጋር አንድ ትልቅ ጉባኤ አድርጋችሁ እንድትገናኙ ለሁላችሁም የሚጠቅም ውል ተስማምታችሁ እንድትዋዋሉ ። ፍቅራችንም በሁለታችን ተጠብቃ ረዥም ዘመን እንድትኖር እግዜርን እለምናለሁ ። ተጻፈ በኢጣልያ መንግሥት ቤት 15 መስከረም 1891 (መስከረም 5 ቀን 1884 ዓ.ም.)
>
> ፊ ፡ ኡምቤርቶ[1]

1 አቶ ገብረ ሚካኤል ጉርሙ ያጠናቀሩት በዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ክፍል ፡ ቁ. 324 ።



በዚህ ደብዳቤ ላይ የተጠቀሱት ፡ 1ኛ ኔራዚኒ የተባለው ዶክተር ቺዛሬ ኔራሲኒ የተባለው ነው ። ስለርሱ ጉዳይ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ስሙን ጠቅሰናል ። ተቀማጭነቱ በሐረር ሆኖ ራስ መኰንንንና የሐረርጌን ሁኔታ የሚሰልል ነው ። በዚያ በኩል የዘይላን ሁኔታ እያጠና ፡ ቢያስፈልግ ወደፊት በሐረር በኩል የጦር ግንባር ለመክፈት የሚያስችለውን መንገድ የሚመረምርና ራስ መኰንንም ካዬ ምኒልክ የሚለዩበትን መንገድ ሲያውጠነጥን የቆየ ነው ። አሁንም በመጨረሻ የራስ መኰንን ለከዳት አለመበገር ሲታወቅ ፡ ከሐረር ወደ ሮማ ከተመለሰ ወዲህ ራስ መንገሻን ካዬ ምኒልክ ለማስከዳት የታቀደውን ዓላማ ከፍጻሜ ለማድረስ ተመርጦ የመጣ ነው ።

2ኛው የርሱ ጓደኛ ደማርቲኖ (ዶክተር ደማርቲኖ አንጀሎ) በፊት በአውሳ ሆኖ ከመሐመድ እንፋሪ ዘንድ አራት ዓመታት ተቀምጦ ባላባቱን ለማስከዳት ብዙ ሠርቷል ። ቀጥሎ በአንቶኔሊ አሳሳቢነት ከአሰብ ተዛውሮ ዓድዋ ላይ የኢጣልያ ወኪል ሆኖ በፊት ከንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ከደጃች መሸሻ ወርቄ ፡ ቀጥሎ ከራስ መንገሻ ጋር ተዋውቆ በጣም የተለማመደና ከዚያም አልፎ በልዩ ልዩ ሰበብ የተወዳጀ ነው ። በኋላ ግን ፡ በሴተና አርቱሮ ሙላዚኒ ተለውጦ ወደ ኢጣልያ አገር ተመልሶ ነበር ። አሁን የኢጣልያ መንግሥትና የምኒልክ ወዳጅነት ወደ ጠብ ተለውጦ መንገሻን በምኒልክ ላይ ለማስነሣት በሚፈለግበት ጊዜ ደማርቲኖ ለራስ መንገሻ እንደግል ወዳጅ በመቆጠርና የትግሬዎቹን ጠባይ ያውቃል ተብሎ እንደ ኔራሲኒ ተመረጠ ። ራሳቸው ራስ መንገሻ ፡ "እሱ ይምጣልኝ" ብለው ቀደም አድርገው ጽፈው ነበር ። በሁለቱም ወገን የርሱ ምርጫ የተስማማ ሆኖዋል ። ለዚሁ የመለያየትና ምኒልክን የማዳከም ተግባር መመሪያ ተቀብሎ ወደ መቀሌ መጣ ።

ደማርቲኖና ኔራሲኒ ፡ ከኢጣልያ አገር መጥተው በስፍራው ካለው ከሙላዚኒ ጋር እ.ኤ.አ. ጥቅምት 20 ቀን 1891 ዓ.ም. (ጥቅምት 13 ቀን 1884 ዓ.ም.) ዓድዋ ላይ ተገናኙ ። በኅብረት ከተነጋገሩና ከተስማሙ በኋላ ፡ ወደ ራስ መንገሻ ሔደው እስከ መረብ ያለው የኢጣልያ ይዞታ እንዲጸና ፡ ስለ አከለ ጉዛይና ስለ ሠራዬ የወደፊት ሁኔታ ተወያይተው ስምምነት አደረጉ ። ይሁን እንጂ ፡ በዚያው በትግሬ የንጉሠ ነገሥቱ ያዬ ምኒልክ አንዳንድ ወዳጅና ወሬ አቀባይ እንደማይጠፋ በመገመት ፡ በተቻለ ሁኔታውን በዝርዝር እንዳይሰሙ ለማድረግና ቢሰሙም የራስ መንገሻና የኢጣልያኖች ግንኙነት ወዳጅነትንና ንግድን ለማስፋፋት ፡ የመልካም ጉርብትና ግንኙነት እንዲመስል ይጣጣሩ ነበር ። ወሬውን ቢሰሙና ደብዳቤው ቢገኝም ፡ ዐፄ ምኒልክን የሚያስቆጣ እንዳይሆን ራስ መንገሻ ፡ "ከወዳጅነት በቀር

ምንም አልፈልግም'' የሚል ዐረፍተ ነገር በማከል ፣ የኢጣልያ ንጉሥም ''ከዳግማዊ ምኒልክ ከናንተ ንጉሠ ነገሥት ጋር ወዳጅነት ለማድረግ ተስፋ አለኝ'' በሚል አነጋገር ለመሸፋፈን ሞክረዋል ።

እነዚሁ የፖለቲካ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ብለው ከራስ መንገሻ ጋር ተስማምተው ሲጨርሱ ፣ በመጨረሻ ምጥዋ የሚቀመጠው ዋናው አገረ ገዥ ጄኔራል ዦሴፔ ጋንዶልፊና ራስ መንገሻ በንጉሥ ኡምቤርቶ ደብዳቤ ላይ እንደ ተጠቀሰው ተገናኝተው እንዲዋዋሉ አደረጉ ። ግንኙነቱ በመጀመሪያ የታሰበው ዓድዋ ላይ ነበር ። በኋላ ግን ፣ ባንድ ወገን ምስጢሩ እንዲጠበቅ ፣ በሌላም ወገን ጄኔራል ጋንዶልፊ ከመረብ ወንዝ እጠገብ እዲ ኳላ እጠገብ እንዲሆንለት ስለጠየቀ ፣ ራስ መንገሻ በራስ አሉላም በሌሎቹም መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ወደ መረብ ሔዱ ። በዚያም ሁለቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በወዳጅነት መልክ ተገናኝተው አሳባቸውን ከተለዋወጡ በኋላ ፣ ከዚያው ላይ እንደ ዘለዓለማዊ የኢጣልያኖች ጠላት ይቆጠሩ የነበሩት ራስ አሉላ በራስ መንገሻ አማካይነት ከጄኔራሉ ጋር እጅ ለእጅ ተጨባብጠው በኢጣልያኖችና በነራስ መንገሻ መካከል ጠቡ ቆሞ ፍቅር መተካቱ ተነገረ ።[1]

ቀጥሎ ወንጌልና መስቀል ቀርቦ ፣ ራስ መንገሻና ጄኔራል ጋንዶልፊ ከዚህ እንደሚከተለው በመሐላ ስምምነት አደረጉ ።

1ኛ ራስ መንገሻን የሚጠላ ለኢጣልያ መንግሥት ጠላቱ ነው ። ራስ መንገሻን የሚወድ ወዳጅ ነው ። የኢጣልያ መንግሥት ራስ መንገሻን ይወደዋል 1 ያከብረዋል ። የኢትዮጵያም ንጉሥ ልጅ እንደ መሆኑም ያውቀዋል ። ራስ መንገሻን የሚያሳዝን ትንሽ ነገር በቅኳ ምንም ነገር እንዳያደርግ ምኳል ።

2ኛ የኢጣልያን መንግሥት የሚጠላ ለራስ መንገሻ ጠላት ነው ። የኢጣልያን መንግሥት የሚወድ ወዳጅ ነው ። ራስ መንገሻ የኢጣልያ መንግሥት ይወደዋልና ያከብረዋል ። ኅዳር 29 ቀን 1884 ዓ. ም.[2]

የራስ አሉላ መሐላ ፣ ከሌሎች መኳንንት ለየት ይላል ። የቀሩት ለኢጣሊያ ወዳጅነታቸውን በመሐላ ሲያጸኑ ፣ የእርሳቸው አማማል ግን ፣ ''ለራስ መንገሻ ታማኝ አገልጋይ ነኝ'' ብቻ የሚል ነው ይባላል ። መሐላው የተደረገው ጋንዶልፊ ለራስ መንገሻ ፣ ራስ መንገሻ ለኢጣልያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ በመጻፍ በደብዳቤ መልክ ነው ። ውሉን በተለይ ወዲያና ወዲህ እያለ እንዲከናወን ያደረገው እላይ

1 Italia ed Etiopia p. 62, No. 1.
2 Storia Diplomatica . . . Rossetti PP. 108 -111



እንዳልነው ፣ ከሮማ ከንጉሡ ዘንድ ለራስ መንገሻ ደብዳቤ ይዞ የመጣው ቼዛሬ ኔራሲኒ ነው ።[1]

የስምምነቱ ዓይነት ፣ ምንም ባይገለጽ ዘወር ባለ አባባል በንጉሠ ነገሥቱ በዳግማዊ ምኒልክ ላይ መሆኑ ለማንም የተሰወረ ሊሆን አይችልም ። ደንበኛው ትርጉም ኢጣልያ ከምኒልክ አሁን እንደ ተጀመረው ቢጣሉ ፣ መንገሻ ከኢጣልያኖች ጋር ሆነው ከምኒልክ መጣላት አለባቸው ። መንገሻም ከምኒልክ ጋር ቢጣሉ በኢጣልያኖቹ በኩል የሚደረገው ይኸው ነው ። እንዲያውም ኢጣልያኖቹ ከምኒልክ ተጣልተው መንገሻ ከሚደረቡ ፣ መንገሻ ከምኒልክ ቢጣሉና ቢዋጉ መንገሻን በመደገፍ ኢጣልያኖቹ ከምኒልክ ጋር መዋጋትን ይመርጣሉ ። የኢጣልያ መንግሥት ምኞትና የውሉም መሠረተ ሐሳብ ይኸው ነው ። በተረፈ ኔራሲኒ በጽሑፍ ይዞ በመጣው መመሪያ መሠረት ፤

1ኛ ለእከለ ጉዛይና ሠራዬ አስተዳዳሪዎቹ የሚሾሙት በራስ መንገሻና በምጥዋው ገዥ ስምምነት እንዲሆን ፤

2ኛ እነዚህ ሁለቱ አውራጃዎች በውስጥ አስተዳደር ነጻ ሆነው ግብር ለኢጣልያም ለኢትዮጵያም እንዳይከፍሉ ፤

3ኛ በሁለቱ አውራጃዎች ሹማምንት ዘንድ ተቀማጭ የሚሆኑ የጦር መሣሪያ የያዙ የኢጣልያ ሹማምንትን ለመሾም የኢጣልያ መንግሥት መብቱ እንዲታወቅለት ፤

4ኛ በሁለቱ አውራጃዎች ላይ ምንም ዓይነት ዘረፋ እንዳይደረግ የሚል ነው ።[2]

ከዚህ ሁሉ ስምምነት በኋላ ፣ ራሳቸው ራስ ሆነው የንጉሥነት ማዕረግ ሳያገኙ ውሉን ተዋውለው ከጨረሱ በኋላ ፣ ራስ መንገሻ ለጄኔራል ጋንዶልፊ የራስነት ማዕረግ ለዶክተር ኔራሲኒ የቀኛዝማችነት ማዕረግ ከልዩ የኒሻን ሽልማት ጋር ስለሰጡ ፣ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ መሸፈታቸውን ራሳቸው አስታወቁ ማለት ነው ። ይኸንንም አድርገው ከተለያዩ በኋላ ፣ ከመረብ ወዲያ ከእሥመራ ወዲህ በሁለቱ መካከል ከንጉሠ ነገሥቱ ተሹመው የነበሩትን ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን ሁለቱም ወገኖች ጠብ እየቀሰቀሱ አላስቀምጥ አሉዋቸው ። በፊተኛው ጊዜ ከወዲህ የራስ መንገሻ ሰዎች ባስቸገሯቸው ጊዜ ወደ እሥመራ ሲሔዱ ፣ የእሥመራ ገዥዎች እነጄኔራል ባልዲሠራ ፣ እነጄኔራል አሬሮ እንከባክበው ያስቀምጧቸው ነበር ። አሁን ጄኔራል

1 Crispi e Menelich . . ,P. 293. No. 8
2 Ibid.

ጋንዶልፊ ከራስ መንገሻ ጋር ከተስማማ ወዲህ ፣ ስንቅ ለራሳቸውም ለሰዎቻቸውም ካገር ላይ እንዳያገኙ በማድረግ እየከለከለና ፊት እየነሣ ፣ "ሰዎችህ አገር አጠፉ ያንተ ጭፍሮች ባላገር ዘረፉ" በማለት እያወገዘ ፣ በመጨረሻ እንዲያውም ፣ "ግዛቴን ለቀህ ውጣ" ብሎ የጦር መሣሪያቸውን ቀምቶ አስወጣቸው ።[1] በፊት አንከባክበው ይዘዋቸው የነበሩት ራስ መንገሻም ፣ ተመሳሳይ እርምጃ በመሸሻ ላይ ስለወሰዱ ፣ መሸሻ ሁሉንም ትተው ወደ አዲስ አበባ ፣ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ተመልሰው የሚያውቁትን ሁሉ በዝርዝር ገለጹ ።

ራስ መንገሻ ፣ ራስ አሉላን ፣ ራስ ሐጎስንና የአክሱሙን እጨጌ ቴዎፍሎስን ይዘው በስብሰባ ምክር እየተደረገ ለሸዋ ያደላሉ የሚባሉትን እንፊታውራሪ ለውጤን እያገለሉ ለቀረው ሹመት ሽልማት ይሰጡ ዠመር ። ምናልባት ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግሬ መዝመታቸው አይቀርም በሚል ሥጋት ካሁኑ ጀምሮ የወታደር ድርጅት ያደርጉ ዠመር ። ለዚህም ከጄኔራል ጋንዶልፊ 35,000 ጥይት ተቀበሉ ። የአጋሜው ደጃዝማች ስብሐት ከራስ መንገሻ ጠበኛ ሆነው በአሁኑ ጊዜ ከኢጣልያኖች ጋር ነበሩ ። በኢጣልያኖች አሳሳቢነትና በአማቻቸው በራስ አሉላ አማካይነትም ተላልከው ገብተው ፣ ድንጋይ ተሸክመው ራስ መንገሻን ላለፈው ጥፋታቸው ምሕረት ጠይቀው በመሐላ ታረቁ ። ራስ መንገሻም ለርሳቸው የራስነት ማዕረግ ፣ ለልጃቸው ለደስታ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጧቸው ። ራስ መንገሻም በዚህ ጊዜ ወዲያና ወዲህ ሲሉ ልክ እንደ ንጉሥ ቀይ ጃንጥላ ያስይዙ ዠመር ። ሐውዜን ላይም ታላቅ ስብሰባ አድርገው ለመንግሥ ማሰባቸውንና ካፄ ምኒልክ መከዳታቸውን የሚገልጽ ዲስኩር ለሕዝቡ በይፋ ተናገሩ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ዋና ባላንጣቸው የነበሩት ደጃች ደብብ አርአያ ፣ በራስ መንገሻ ትእዛዝ አምባ ስላማ ላይ ታስረው ይኖሩ ነበርና ከዚያ አምልጠው ወንድማቸውን ደጃች ቦጋለን ይዘው ዩሃ ላይ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጦር ጋር ተዋግተው በጦርነቱ ሲሞቱ መላው ትግሬ በራስ መንገሻ ሥር ይነስ ይብዛ ተጠቀለለ ። የእንደርታዎቹም እነደጃች ተድላ ዋህድ ገቡላቸው ። ይኸም ሳይበቃ ቀርቶ ወጣቱ ደጃች ውብነህ የራስ ሐጎስ የልጅ ልጅ ፣ ከአያቱ ከራስ ሐጎስ ግዛት ከጸለምት ጦር እያሳበረ የራስ ወሌ ግዛት የሆነውን ሰሜንና ወገራን ፣ የሸሬው ደጃች አብርሃ ደግሞ ፣ ከራስ ወሌ ሹሞች ከነደጃች ወርቅነህ ጋር በራስ መንገሻ ስም እየተዋጉ በወልቃይትና በጸገዴ በኩል ግዛት ያስፋፉ ዠመር ።

1 Archivio Stroico (Etiopia) XV 1857 - 1895 (Roma)



በዚህ ዓይነት ራስ መንገሻ ፣ ያፄ ዮሐንስን ዙፋን በኢጣልያኖቹ እርዳታ ከዐፄ ምኒልክ ላይ መልሰው ለመውሰድ እንደ ቀረቡ ተማመኑ። በበኩላቸው ኢጣልያኖቹ ደግሞ የኤርትራ የቅኝ ግዛት ወሰናቸው ከምጥዋ ዠምሮ እስከ መረብ ወንዝ እንዲደርስ የተመኙትንና ምኒልክ በልመና እምቢ ያሉትን ፣ መንገሻን ከምኒልክ በማሸፈት በቀላሉ እንደሚያገኙት ብቻ ሳይሆን ወደፊትም በሰሜን ኢትዮጵያ እንደልብ ለመስፋፋት እንደሚችሉ ቆጠሩት ።

በ1884 ዓ. ም. ላይ መንገሻና ጋንዶልፊ መረብ ላይ ከመዋዋላቸው በፊት ቀደም ባሉት ወራት በንጉሥ ኡምቤርቶና በራስ መንገሻ መካከል የወዳጅነት ግንኙነት ፣ የስጦታው ልውውጥ ለጊዜው እየተሟሟቀ ሔዶ ነበር ። ራስ መንገሻ ከደጃች ደብብ ጋር ተዋግተው የገደሉበትን ሰበብ የኢጣልያን ወዳጅነት ለመጠበቅ መሆኑን ገልጸው ፤

> ደጃች ደብብ ኢጣልያኖች ወዳጆቼ ናቸውና ውደዱልኝ ብዬ ብላቸው እንቢ ብለው ስጓዝ ካንገት (መዋጊያ በር ይዘው) ላይ ቆይተው ተሰልፈው ተዋጉኝ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት በርስዎ ጸሎት ድል አደረግኋቸው እርሳቸውም ሞቱ . . . .

የሚል የምሥራች ደብዳቤ ለኢጣሊያ ንጉሥ ጻፉ ።

ይኸን ደብዳቤ ከጻፉበት ከመስከረም 13 ቀን 1884 ዓ.ም. ቀደም ብሎ፣

> ይድረስ ኃበ ዓቢይ ወክቡር ንጉሥ ኡበርቶ (ኡምቤርቶ) . . . ገጸ በረከት ያባቴ የጃንሆይ (ያጼ ዮሐንስ) የነበረ የወርቅ ኮርቻ ለፍቅር ምልክት እንዲሆን ስድጄልዎታለሁ . . .[1]

ከሚል ደብዳቤ ጋር የወርቁን ኮርቻ በመላክ ወዳጅነታቸውን ለማጠንካከር ጥረት ማድረጋቸው ይታያል ።

ይሁን እንጂ ፣ ወደፊት ያሉት ምዕራፎች እንደሚያስረዱን ፣ በምኒልክና በአማካሪዎቻቸው የፖለቲካ ዘዴ ፣ በጦር ኃይላቸው ብዛት፣ በመንግሥታዊ ድርጅታቸው ክብደት የመንገሻ ምኞት ሳይሳካ ይቀራል። ኢጣልያኖቹ ራስ መንገሻን ከድተው እንደገና ወደ ምኒልክ ተለጥፈው ምኞታቸውን ከግብ ለማድረስ ይፈትናሉ ። ራስ መንገሻ የኢጣልያኖቹ ክደት ገርሟቸው ካፄ ምኒልክ ምሕረት ጠይቀው ከታረቁና ግዛታቸውን ካስመረቁ በኋላ ከኢጣልያኖቹ ጋር ይዋጋሉ ። የሁለቱም ውጊያ ተከታትሎ መጨረሻው ዓድዋ ጦርነት ላይ ይወድቃል ።

1 Archivio Storico (Etiopia) XV 1857 - 1895 (Roma)



ባዬ ምኒልክ ላይ ከራስ መንገሻ ጋር በመረብ የተዋዋለው ጄኔራል ጋንዶልፊ

ሊኢ.ታሊያ ኢን አፍሪካ

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ለማለያየት የተደረገ የፖለቲካ ዘዴ
## ኢጣልያኖች መንገሻን ከድተው ወደ ምኒልክ እንደዞሩ

ንጉሠ ነገሥቱ ከመጀመሪያው ወቅት ላይ፣ የራስ መንገሻን ከዳት በትክክል አያውቁም ነበር። ነገር ግን የኢጣልያ ወኪል አንቶኔሊ፣ "...ከእንግዲህ ወዲህ ከናንተ ጋር ጦርነት እንጂ ሰላም የለም" ብሎ ፎክሮ ከሔደ በኋላ፣ እንደ ራስ መንገሻ ያሉትን ለማስነሣት እንደሚ ይመለስ ያውቃሉ። ራስ መንገሻም፣ "እኔን ደግፋችሁና እስከ መረብ ድረስ ያለውን ግዛት ልፍቀድላችሁ ብለው አጎታቸውን ግራዝማች ሳዶርን ልከውብን እኛ ሳንቀበላቸው ቀረን" ብለው ኢጣልያኖቹ ከዚህ በፊት የተናገሩትን ላይጠራጠሩት ይችላሉ። ራስ መንገሻን በመጠርጠርና በማመን መካከል ሆነው ለማናቸውም ወደ ወሎ ብቅ ብለው ሁኔታውን ለመጠባበቅ ምኒልክ ቦሩ ሜዳ ላይ ሰፍረው ነበር።

የአካሔዳቸውም ዓላማ፣ የራስ መንገሻን ክዳት አምነውም ይሁን ሳያምኑ፣ ቦሩ ሜዳ ድረስ ራስ መንገሻን ጠርተው፣ በልዩ ልዩ ሽልማት አስደስተውና የትግሬን ግዛት በሙሉ ሰጥተው ከኢጣልያኖች ደባ እንዲጠበቁ ለማድረግ ነበር። በዚህ ምክንያት ከአዲስ አበባ ሔደው ቦሩ ሜዳ ከደረሱ ጀምሮ ራስ መንገሻ ይመጣሉ ተብሎ ሽልማቱ ሲዘጋጅ ድግሱ ሲደገስ ሰነበተ። በዚህም ጊዜ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ወይዘሮ ሸዋረጋ አብረው ነበሩ። በሰው ሁሉ ዘንድ፣ "ልጃቸውን ድረው ራስ መንገሻን ስማቸውን ገብረ መስቀል አሰኝተው በትግሬ ሊያነግሷቸው ነው" ተብሎ ተወራ። ይሁን እንጂ፣ ቦሩ ሜዳ ድረስ እንዲመጡ ተልኮባቸው ሳለ፣ በየምክንያቱ ከዘገዩ በኋላ በመጨረሻ የከዳታቸው ወሬ በይፋ እየተወራ ሔዶ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ለመታመን ቻለ።

በዚህ ጊዜ፣ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ ጋር አቡነ ማቴዎስ፣ እጨጌ ገብረ ሥላሴ፣ ራስ ሚካኤል፣ ራስ ወሌ፣ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ፣ ደጃች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን፣ ደጃች ገርማሜና ሌሎችም አብረው በቦሩ ሜዳ ነበሩ። ከራስ መንገሻ ግዛት ጋር

ከሚወሰኑትና ጠበኛ ከሆኑት ከነዋግሹም ብሩ ፣ ከአንደርታው ከነደጃች ተድላ ዋህድ ዘንድ ፣ "ራስ መንገሻ ከኢጣልያኖች ጋር ተማምለው ከድተዋልና አይመጡም" የሚሉ ወሬ ሲነፍስ ቆይቶ ነበር ። አንዳንዶቹ ደግሞ ፣ "የመጡ እንደሆነ ይታሰራሉ" እያሉ ወደ ራስ መንገሻ በሐቅም ፣ በተንኮልም ይልኩባቸው ነበር ይባላል ። ዐፄ ምኒልክም በራስ መንገሻና በዋግሹም ብሩ መካከል ያለውን ጠብ ያውቃሉና ወሬውን በሙሉ ለመቀበል አጠራጥሯቸው ነበር ።

ስለዚህ ፣ ዐፄ ምኒልክ የሰሙትን እንዳልሰሙ እየመሰሉ ፣ ከዳታቸውን ለሚነግሯቸውም "እያደርገውም" እያሉ ብዙ ቀን ሲጠባበቁ ቆይተው ፣ በመጨረሻ የራስ መንገሻ በተባለው ቀን አለመግባት ከተወራው ወሬ ጋር ስለ ገጠመ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዝርዝሩን ጉዳይ ከትግሬ ተባረው ከመጡት ከደጃች መሸሻ ወርቄና ከሌላውም ካዳመጡ በኋላ በነገሩ አዝነው ለራስ መንገሻና ለትግሬ መኳንንት የተዘጋጀውን ሽልማት ለራስ ሚካኤልና ለወሎ መኳንንት ሸልመው ፣ ግብሩንም አብልተው እንዳበቁ ፣ ብዙ መኳንንት "አሁኑኑ ጉዟችንን ቀጥለን ወደ ትግሬ እንዝመት" ብለው ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱም አሳቡን ለጊዜው ተቀብለው ፣ ራስ መኰንንም ከሐረር ወደ ወሎ ሠራዊታቸውን ይዘው እንዲመጡ መልእክት ሔዶ ነበር ።

ነገር ግን ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ማናቸውም የሰላም መንገድ ሳይሞክር ፣ ማናቸውም የፖለቲካ ዘዴ ሳይሠራበት በችኮላ ነገር ማባባስ ፣ ሁከት ማስነሣትና ሊድን የሚችለውን ችግር አጋነው የጦርነት ውሳኔ ማድረግ እንደማይወዱ ባለፈው አመልክተናል ። "ራስ መንገሻ መረብ ወንዝ ላይ ከጄኔራል ጋንዶልፊ ጋር በርስዎ ላይ ተዋዋሉ ፣ ለጄኔራሉና ለደጃች ስብሐት የራስነት ማዕረግ ሰጡ ። ሐውዜን ላይ የትግሬን ሕዝብ ሰብስበው ለመንገሥ ማሰባቸውን አስታወቁ ። እንዲ ንጉሥ ቀይ ጃንጥላ አሲዘው ወዲያና ወዲህ ይላሉ" የሚባለውን ወሬ ሰምተው ። ምንም በልባቸው ቢናደዱ ፣ ንዴታቸውን በትእግሥት ውጠው ታላቅ ስብሰባ ተደረገና ፣ "አሁን ሠራዊቱም ስለሚራብ ፣ ያለፈውም በሽታና ረኃብ ገና ከአገር ላይ ስለ አልተወገደ ወደ አዲስ አበባ ሔደን ትንሽ ዐርፈን በአዲስ ኃይል ተዘጋጅተን እንደገና መመለሱ ይሻላል" ተብሎ በምክር ተወሰነ ።

ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ በሚዘጋጁበት ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ወይዘሮ ሸዋረጋን ፣ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ሆነው ሁልጊዜ የሚያዩዋቸው ራስ ሚካኤል "ላግባ" ብለው አማላጅ እቴጌ ጣይቱን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ። ንጉሠ ነገሥቱም ፣ "ሚካኤልን እንደ ልጅ ነውና የማየው ልጄን ለወዳጄ ፣ ለልጄ እንደምን አስጣለሁ ፣



ከሆነም አሁን ሁዳዴ ነውና አዲስ አበባ ገብተን ከተፈሰከ በኋላ መጥቶ ይውሰዳት" ሲሉ ተግደረደሩ ። ራስ ሚካኤል ግን ፣ ካሁን ዠምሮ ሚስቴ ናትና ትሰጠኝ ብለው ጥያቄያቸውን ስለአጸኑ ልመናቸውም በእቴጌ ጣይቱ ስለተደገፈ ፣ እዚያው ደሴ ላይ በጥር ወር 1884 ዓ. ም. ሠርጉ ተደግሶ አጋቡዋቸውና ንጉሠ ነገሥቱ ከነሠራዊታቸው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ። ሲመለሱም ፣ "መቼም እንደገና ወደ ትግሬ መዘመቱ የማይቀር ይሆናል ብለው በመገመት የያዙትን መድፍ አህያ ፈጅ ላይ ትተውት መጡ ። አዲስ አበባ እንደገቡ የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ለማለያየት የሚችሉበትን ዘዴና መንገድ አጥብቀው ይፈልጉ ዠመር ። በዚሁ ጐን ጦር የመሰብሰቡም ጉዳይ አልተዘነጋም።

ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተመለሱ ፣ ኢጣልያኖች ውል እያፈረሱ ከአሥመራ አልፈው እስከ መረብ ያለውን አገር መውረራቸው ፣ በቤተ መንግሥቱ ያልታሰበውን የውጫሌ ውል ልዩ ትርጒም እየሰጡ ፣ ጠባቂ እንሁን ማለታቸው ፣ አሁን ደግሞ ራስ መንገሻን ማስከዳታቸው እየተጠቀሰ የኢጣልያኖች ተንኮል ፣ የራስ መንገሻ ከዳት ፣ በሁሉም ዘንድ በርክቶ እየተወራ ቁጭትንና ንዴትን አሳደረ ። በዚህም ጊዜ አዲስ አበባ ያሉት ፈረንሳዮቹም ፣ አርመኖቹም ፣ ግሪኩና ስዊሱ ሁሉ ፣ "የኢጣልያንን ተንኮል ቀድሞም ተናግረናል" እያሉ ራሳቸው በመቆጨት ኢትዮጵያውያኑንም ያስቆጪቸው ነበር ይባላል ።

ባለፈው ዓመት ፣ ከነአንቶኔሊ ጋር ወደ ኢጣልያ ለመመለስ ተሰናብቶ የነበረው ዶክተር ትራቬርሲ እነአንቶኔሊ ያበላሹትን የወዳጅነት ፖለቲካ እንዲያቃና እንደገና ተመልሶ መጥቶ በዚህ ጊዜ አዲስ አበባ ነበር ። ወደ ደሴም ፣ ወደ ሐረርም ፣ ወደ እንጦጦም እየተመላለሰ ፣ "ራስ መንገሻና ጄኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ የተስማሙት ሁለቱም የኢጣልያና የኢትዮጵያ ነገሥታት ወኪሎች እንደ መሆናቸው መጠን በስምምነት የየክፍል አገራቸውን በሰላም ለማስተዳደር እንዲመች ነው እንጂ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ራስ መንገሻን ከግርማዊነትዎ አስከድቶ ለመስማማት በፍጹም አሳብም ምኞትም የለውም" እያለ ንዴታቸውንም ፣ ሐዘናቸውንም ለማረጋጋት ሞከረ ። እነራስ መኰንንም ፣ "ይኸ ከሆነ የንጉሥነት ማዕረግ ከሌለው ከራሱ ከራስ መንገሻ የራስነት ማዕረግና ኒሻን የናንተ ጄኔራል ጋንዶልፊ እንደ ምን ተቀበለ? ራሱስ ማዕረጉ ራስ ሆኖ እንደምን የራስነት ማዕረግ ለነራስ ስብሐት ይሰጣል?" እያሉ ተከራከሩት ። ፈረንሳዮቹ እነ ሙሴ ሸፍነ ፣ እነ ሙሴ ሞንዶን ፣ ዋናው አማካሪያቸው ሙሴ ኢልግ ከፈረንሳይ 'ለታ' እና 'ሲዬክል' ከሚባሉ ጋዜጦችና በኢጣልያ አገር ከሚታተሙት ጋዜጦች በራስ መንገሻና በጋንዶልፊ መካከል የተደ

ረገውን የውሉን ግልባጭና የተሰጠውን ሐተታ ፣ በኢጣልያ የባሕር መዝገብ በደንብ ከተመዘገበው ላይ እየቀዱ እያመጡ ፣ የመረቡን የቃል መሐላ ስምምነት ቃሉንም ፣ መንፈሱንም አሳዩ ። በቃልም ጉዳዩን የኢጣልያ መንግሥት መቀበሉን እያስረዱ የትራቬርሲን አባባል ያስተባብሉ ዠመር ።[1]

በዚህ መካከል ፣ ቀድሞ ከነበረው የወረርሽኝ በሽታ ያገገመውን ሕዝብ እንደገና ከወደ ጅቡቲ የመጣ አዲስ በሽታ 'ኮሌራ' ተነሥቶ ብዙ ሰው ፈጀ ። ንጉሠ ነገሥቱም ከዚሁ በሽታ ለመከለል አንኮበር ሔደው በሽታው ከበረደ በኋላ ፣ በመስከረም ወር 1885 ዓ.ም. ተመልሰው አዲስ አበባ መጡ ። ቀጥሎ ባዲስ አበባ ትልቅ ቃጠሎ ተነሥቶ የንጉሠ ነገሥቱ እልፍኝ ሳይቀር በመቃጠሉ አንድ ዓይነት ሐዘን ባገር ላይ ጥሎ ነበር ።

በተለይ ደግሞ ዐፄ ምኒልክ የሠጉት ፣ ራስ መኰንን ከኢጣልያ አገር ገዝተው ያመጡት 2 ሚሊዮን ጥይት በአሰብ በኢጣልያኖቹ እጅ እንደተያዘ ነበርና አሁን ኢጣልያኖቹ ከራስ መንገሻ ጋር በተስማሙበት ሰዓት እንደዚህ ቁጥሩ የበረከተው ጥይት እንዳይቀርባቸው ነው ። ባሁኑ ሰዓት አሳባቸው በጥብቅ ያተኮረው ኢጣልያኖችን እንዳልጠሉ በመምሰል ፣ በፖለቲካ ዘዴ ኢጣልያኖቹንና ራስ መንገሻን ከማለያየቱ ላይ ነው ። ለዚህ ጉዳይ ዋና መሣሪያ ይሆነኛል ብለው የመደቡት የመረቡ ስምምነት ውሸት ነው እያለ ለማስተባበል የሚሞክረውን ራሱን ሊዎፖልድ ትራቬርሲን ነው ። እርሳቸውም የሚያምኑትን በልባቸው ይዘው ፣ በአንደበታቸው እኔም የኢጣልያ ንጉሥ ይኸን የመሰለውን ተንኮል ያደርገዋል ብዬ አልጠረጥርም እያሉ የርሱን አባባል ለማጽደቅ ይሞክሩ ነበር ። ይኸውም ዓይነቱ አነጋገራቸው ባንድ ወገን ለፖለቲካ እርምጃቸው መሣሪያ ሲሆን ፣ ትራቬርሲንም መንገሻን ከኢጣልያ ለመለየት ይገፋፋዋል ፣ ወይም ይረዳዋል በሚል መንፈስ ነው ።

ስለዚህ ፣ አንድ ደብዳቤ ለኢጣልያ ንጉሥ በተለመደ አነጋገራቸው ሰላም ፈላጊነታቸውን ፣ ወዳጅነት አጥባቂነታቸውን የሚገልጥ አዘጋጅተው ከጨረሱ በኋላ ዶክተር ትራቬርሲ ወደ ግቢ ተጠራ ። ወደ እልፍኝም ገብቶ የአክብሮት ሰላምታውን አቅርቦ ከተጨባበጡ በኋላ ፣

“ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ወዳጅነታችን በዳግማዊ ቪክቶር አማኑኤል ዠምሮ ነው ። ያሁኑም ንጉሥ ኡምቤርቶ ለኔ ወዳጄ ወንድሜ

1 Let - Marefia - L. Traversi, PP. 278 - 381; Italia ed Etiopia .,PP. 70-72.



ነውና ምናልባት እንደዚህ ያለውን መጥፎ ሥራ የምጥዋ አስተዳዳሪዎች (እነ ዤኔራል ጋንዶልፊ) ይሠሩት ይሆናል እንጂ ፣ የኢጣልያ መንግሥትና ወዳጄ ኡምቤርቶ ይሠሩታል ብዬ አልጠረጥርም ። የቀረውንም ክርክራችንን ሁሉ በሰላምና በወዳጅነት እንፈጽመዋለን እንጂ የሚያጣላን የለም ። አሁንም ይኸን የጻፍሁትን ደብዳቤ ለወዳጄ ለኡምቤርቶ ወስደህ አስረክብና አንተው ራስህ ነገሩን ሁሉ አስረድተህ ጨርስ ። ይኸን በመረብ የሆነውን ስምምነት ምጥዋ ያሉት ሹሞች ሠርተውት እንደሆነ እነሱ ይቀጣሉ ። የኢጣልያ መንግሥት ዐውቆ አድርጎት እንደሆነ መቼስ ምን ይደረጋል ። ወዳጅነቱ ቀርቶ ጠብ መሆኑን ከዚያ ወዲያ እናውቀዋለን” አሉት ።

ለንጉሥ ኡምቤርቶ የጻፉት ደብዳቤ ይዘት ፣ የምጥዋ ባለሥልጣኖች ስምምነታችንን እየጣሱ ለራስ መንገሻ መሣሪያ ማቀበላቸው በማንም ዘንድ የተገለጸ ስለሆነ ፣ እንዲህ ያለው ሥራ የክፉ ሰዎች ሥራ መሆኑን ፡ ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ የሸፈቱባቸውን መሳፍንት እነራስ መንገሻን ለማሳመን በሚያደርጉት ዘመቻ በመካከሉ የኢጣልያ ዜጎች ተገኝተው ቢሞቱ በርሳቸው እንዳይፈረድ የሚያስጠነቅቅ ሲሆን ፣ የቀረው ስለ ውጫሌው ውል አተረጓጐምና አሰብ ስለተያዘው ጥይት መለቀቅ የሚያሳስብ ነው ። ለሁሉም ትራቬርሲ መላኩን ይገልጻል ።[1] ስለዚህ ትራቬርሲ ይኸን ለኢጣልያ ንጉሥ የተጻፈውን ደብዳቤ ተቀብሎ ሲያበቃ ፣ “የኢጣልያ ንጉሥ እንደዚህ ያለውን ዝቅተኛ አድራጎት አይፈጽምም . . . አሁንም ሁሉንም እኔ ጨርሼ እስክመለስ ድረስ ግርማዊነትዎ ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳይወስድ ፣ በአሰብ ያለውንም 2 ሚሊዮን ጥይት እኔው ራሴ እንዲመጣ አደርጋለሁ ። ነገር ግን ፣ ወደ አዲስ አበባ እስኪደርስ ያምስት ወራት ጊዜ መፍጀቱ አይቀርም ብሎ መለሰላቸው ።

በዚህ ጊዜ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አነጋገሩ ስለ አስደሰታቸው፣ እርሳቸውም በበኩላቸው በስጦታም ፣ በንግግርም አስደስተው አሰናበቱት ። በዚያም የነበሩት ራስ መኰንን ለኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትርና ለዥዎግራፊያ የኢጣልያ ማኅበር ፕሬዚዳንት የተጻፉ የወዳጅነት ደብዳቤዎች ሰጥተውና ከንጉሠ ነገሥቱ የተረፈውን አሟልተው አስረድተውት ፣ በመልካም ስሜት አሰናበቱት ። ከግቢ ሲወጣ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዞ በጥሩ ዕቃ የተጫነች የምታምር ሰጋር በቅሎ በስጦታ ቀረበችለት ።

በዚህ ዓይነት ዶክተር ሊዎፖልድ ትራቬርሲ ፣ በግንቦት ወር ላይ ከአዲስ አበባ በሐረርና በዘይላ አድርጎ አሰብ ደረሰ ። ከአሰብ በመርከብ ተሳፍሮ በሐምሌ ወር ሮማ ደረሰ ። በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት

1 Italia ed Etiopia . . .p. 55

እንዳመለከትነው ፣ ክሪስፒ ተሽሮ ጂዎሊቲ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ፣ በዲሩዲኒ ፋንታ በኔዴቶ ብረ የሚባለው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ይዘው ነበረ ። እነዚህ አዳዲሶቹ ባለሥልጣኖች ቅኝ አገር ማስፋፋትንና ለዚህም ብዙ ገንዘብ ማውጣትን እምብዛም የማይፈልጉ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በስምምነት መቀጠልን የሚመኙና የቀድሞዎቹ ባለሥልጣኖች እነክሪስፒ የሠሩትን በመጠኑም ቢሆን የሚቃረኑ ናቸው ። ስለዚህም የምኒልክ መልክተኛ ሌዎፖልድ ትራቬርሲ መልክቱን እንደልቡ ለማከናወን በሮማ የተደለደለ ሜዳ አጋጠመው ። በዚህም ለውጥ ትራቬርሲ ሲቀናው ፣ የመጨረሻውና ዋናው ተጠቃሚ ያፄ ምኒልክ መንግሥት ሲሆን የሚጐዱት ደግሞ በሌላው አንጻር ራስ መንገሻ መሆናቸው ነው ።

ትራቬርሲ ይዞ የሔደውን ደብዳቤ ለንጉሡና ለየባለሥልጣኖቹ አድሎ ከጨረሰ በኋላ ለንጉሡም ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በመረብ ከራስ መንገሻ ጋር የተደረገው ውል ለኢጣልያ በፍጹም የማይጠቅማት መሆኑን ገለጸ ። ራስ መንገሻ ባሁኑ ጊዜ ጠንካራ የወታደር እቅዋምና ብዙም ተከታይ የሌላቸው ሲሆኑ ፣ ዐፄ ምኒልክ ግን ምንም እንኳን ባንዳንድ ቦታ ሽፍታ ባይጠፉም ፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተገዛላቸውና ለከፋም ፣ ለደጉም ሕዝቡ የሚከተላቸው መሆኑን በዝርዝር አስረድቶ ከራስ መንገሻ ጋር የተወጠነው የወዳጅነት ፖለቲካ በፍጹም እንዲለወጥና በማናቸውም ረገድ የወዳጅነቱ ጉዳይ ከምኒልክ ጋር እንዲጸና አጥብቆ አሳሰበ ። አዳዲሶቹ ባለሥልጣኖችም የርሱን አባባል እያጤኑ ወደ መቀበል አዘነበሉ ።

እንደዚሁም በአሰብ የተቀመጠው 2 ሚሊዮን ጥይት አንድ ቀን ጠላት ሊሆነን ለሚችለው ለምኒልክ አይሰጥ የሚሉ ነበሩ ። ለነዚህም መልስ ዶክተር ትራቬርሲ ፣ “ራሳቸው የገዙትን ጥይት ስንከለክላቸው ትርፉ ቅያሜና ጠብ ነው ። የፈለጉትን ያህል ጠመንጃና ጥይት እኛ ብንከለክላቸው በጅቡቲ በኩል ከፈረንሳዮቹ በቀጥታ ሊያገኙ ይችላሉ” ብሎ አስረድቶ አሳመነ ። ከራስ መንገሻ ጋር መረብ ላይ “ወዳጅህ ወዳጄ ፣ ጠላትህ ጠላቴ ነው” ተባብሎ የተዋዋለውን ጄኔራል ጋንዶልፊን አሽሮ ፣ በርሱ እግር ጄኔራል ኦሬስቲ ባራቲዬሪን አሾመ ። ባራቲዬሪ እስካሁን ምክትል ገዥ ሆኖ ሲሠራ አለቃው ጋንዶልፊ የወጠነውን አዲስ ፖለቲካ የሚቃወም ነበር ።

የኢጣልያ መንግሥት ፣ በምንም ዓይነት መንገሻን እንደማይረዳ ለምኒልክ እንዲያረጋግጥ ሊዎፖልዶ ትራቬርሲ ከመንግሥቱ መሪዎች ቃል ተቀብሎና በዚህ ዓይነት ጉዳዩ ሁሉ ቀንቶት ተመለሰ ።



እርሱም ከሮማ ወደ አሰብ መጥቶ 2 ሚሊዮን ጥይት በስድስት መቶ ግመል አስጭኖ እስከ አንኮበር አመጣ ። ከአንኮበር ደግሞ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ አደረሱ ። ትራቬርሲም ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሰ ለንጉሠ ነገሥቱ ፣ “ቀድሞውንም እንደተናገርሁት ስምምነቱ ለጉርብትና ጉዳይ ነበር እንጂ ፣ የኢጣልያ መንግሥት የለበትም” ብሎ በመንግሥቱ ስም በማረጋገጥ አንድ ታላቅ ጉዳይ እንዳከናወነ ተሰምቶት በመመካት ገለጸላቸው ።[1]

እንደ እውነቱ ፣ የኢጣልያ መንግሥት መሪዎች ከፋፍለህ ግዛ ተብሎ ካባቶቻቸው ከሮማውያን የወረሱትን ፍልስፍና በመጠቀም ራስ መንገሻን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለማስነሣት ከልብ አቅደው እንደ ተነሡበት ሰነዱ ሁሉ በግልጽ አመልክቷል ። አሁን የተሻረው ጄኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ ከራስ መንገሻ ጋር የተዋዋለው የዚህኑ መሪ ትእዛዝ ኔራሲኒ ከሮማ ከንጉሡ ከኡምቤርቶና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ዘንድ ካመጣለት በኋላ መሆኑን ባለፈው አመልክተናል ።

ኢጣሊያኖች ፣ ንጉሠ ነገሥታዊው መንግሥት መጽናቱን ፣ የራስ መንገሻንና የራሳቸውን አቅም ደካማነት አመዛዝነው ከራስ መንገሻ ጋር የዶለቱት ውለታ ሩቅ መንገድ እንደማያዘልቅ ሲረዱት ፣ ወንጌልና መስቀል አቅርበው ፣ “የራስ መንገሻ ጠላት ጠላታችን ነው” ብለው በመሐላ ያረጋገጡትን በቀላሉ ክደውና ወዳፄ ምኒልክ ዞረው ራሳቸው የራስ መንገሻ ጠላት ለመሆን በቁ ። ለጄኔራል ባራቲዬሪም ከዚህ በፊት እንደ ተባለው ፣ “እኛ በቂ ገንዘብ ስለሌለን ወደ አፍሪካ አዲስ ወታደር ለመላክም ሆነ ጦርነት ለማድረግ ፣ ካለው በቀር ግዛት ማስፋፋትም አንፈልግምና በተቻለ መጠን ከንጉሠ ነገሥቱ ከምኒልክ ጋር በወዳጅነት ስምምነት ለማድረግ ሞክር ። ለራስ መንገሻ በሩቅ የወዳጅነት ስሜት ከማሳየት በቀር ማናቸውንም የጦር እርዳታ አታድርግ ። የጦር መሣሪያም በፍጹም አትስጥ” የሚል ዝርዝር መሪ ትእዛዝ ባዲስ ዓይነት ከመንግሥቱ ደረሰው ። ምኒልክም የራስ መንገሻንና የኢጣልያን ወዳጅነት በትራቬርሴ በኩል ካስፈረሱ በኋላ ራስ መንገሻ እንዲገቡላቸው ጥሪያቸውን አጠነከሩ ።

ራስ መንገሻም ፣ ራስ አሉላም ፣ ይኸን ሁሉ የተደረገባቸውን ከዳት ስለ አልተረዱት ፣ ከሸዋ የሚደርሳቸውን ጥሪ ችላ እያሉ ፣ በዚያው በወንጌልና በመስቀል መሐላ በተዋዋሉት ውላቸው ተማመኑ ። ተጠርተን

1 Let - Marefia . . p. 382; Italia ed Etiopia . . „Conti Rossini, p. 75 - 76

ስንቀር ከሸዋ ጦር መምጣቱ አይቀርም በሚል ግንጋቤ ፤ "ማናቸውንም ለመመካከር እንገናኝ" ብለው ቀጠሮ ቢጠይቁት ፤ ባራቲዬሪ የፖለቲካውን ለውጥ ሳይገልጥ ምክንያት ብቻ እየፈጠረ ገሸሽ አደረጋቸው ። ቢሆንም ፤ በዚያው ሰሞን ባራቲዬሪ ሠራዊን ሲጎበኝ እርሳቸው ካሉበት ሩቅ ስላልነበረ ፤ "ራስ አሉላ መጥቼ ልገናኝህ" ብለው ቢልኩበት የማይችል መሆኑን ስለ ገለጸላቸው ፤ የኢጣልያ መንግሥት እንደ ከዳቸው ተረዱት ። በዚህ ጊዜ ፤ ሹም አጋሜ ተሰፋዬ የሚባሉት የራስ መንገሻ ባለሟል ከበፊቱ ሁኔታውን ይጠራጠሩ ኖሮ ፤ "ጣልያኖች ለማንም የማይታመኑ ለሁሉም በሐሰት ወዳጅ የሚመስሉ አታላዮች ናቸው" ሲሉ በራስ መንገሻ ፊት ተናገሩ ይባላል ።

ከዚህ በኋላ ነገሩን ለብዙ ጊዜ መደበቅ ስለ አልተቻለ ፤ "ከእንግዲህ ወዲያ እኛ አንረዳዎትም ፤ ወደ ንጉሠ ነገሥትዎ ገብተው ይታረቁ" እያሉ በመልእክት በይፋ ይገፋፉዋቸው ዠመር ። ይኸውም አንሶ ባንድ ወገን የኢጣልያን ንጉሥ እንደ በላይ አድርጎ ለማስከበር ፤ በሌላው ወገን ምኒልክ በሙሉ ተደስተው ፤ "እንግዲህስ የመረብን ወሰንና 17ኛውን አንቀጽ ልቀበል" ወደ ማለት እንዲያዘነብሉ ለማድረግ ጄኔራል ባራቲዬሪ ያንኑ የራስ መንገሻ ወዳጅ የተባለውንና ከንጉሡ ከኡምቤርቶ ተልኮ በመረብ ከጋንዶልፊ ጋር እንዲዋዋሉ ያደረጋቸውን ካፒታኖ ደማርቲኖን ልኮ ፤ "ለግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ፈቃድ በመታዘዝ ያጼ ምኒልክን ንጉሠ ነገሥትነት እቀበላለሁ" ብለው ራሳቸው ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ቢጽፉና ቢታረቁ ይሻላል ብሎ ላከባቸው ። በራስ መንገሻ በኩል ነገሩ በጣም አናዳጅ መሆኑ አይጠረጠርም ። በዚህ ጊዜ በራስ መንገሻም ፤ በራስ አሉላም ዘንድ የሚያድረውን የሐዘንም የጸጸትም ይልቁንም የትዝብት ስሜት ለመረዳት ቀላል ነው ። ሹም አጋሜ ተሰፋዬም ፤ "ጣልያን አታላይ ነው" የሚለውን ቃል የወረወሩት እዚህ ላይ ሳይሆን አይቀርም ። የዚህ ዓይነቱም አታላይነት በግልጽ በአድራጎት የታየ ስለሆነ ነጋሪም አያሻውም ። "ለግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ፈቃድ መታዘዝ" የሚለው ቃል እንዲጨመር የፈለጉት ፤ ዐፄ ምኒልክ የኢጣልያ ንጉሥ ለካ ሥልጣን አለው ብለው እንዲያምኑ ሆን ተብሎ የተደረገ የቂልነት ዘዴ ነው ።

ቢሆንም ፤ ራስ መንገሻ ትዝብትና ጸጸታቸውን በልባቸው እንደያዙ ፤ "ደህና ነው እንዳላችሁት በናንተው አስታራቂነት የምኒልክን የበላይነት ዐውቃለሁ ! ወደ ሸዋም ሔጄ ከምኒልክ ጋር እገናኛለሁ" የሚል የቃል መልእክት ጨምረው በደብዳቤ ግን ፤ "ዓድዋ ድረስ መጥቼ ከእርስዎ እንገናኝና ሐሳቤን ገልጬልዎት ወዳጅነታችንን እናጽና ። ማናቸውም ነገር በደብዳቤ አያልቅምና ሁለታችን ተገናኝተን እርስዎም አሳብዎን ይንገሩኝ ። እኔም በልቤ ያለውን ሁሉ ቃል በቃል



ልገልጽልዎት" ብለው በጽሑፍ አስፍረው ያንኑ ደ ማርቲኖን መልሰው ወደ ጄኔራል ባራቲ ፡ ላኩት ።

ጄኔራል ባራቲዬሪም ፤ ይኸ ደብዳቤ ሲደርሰው ሁኔታውን ትንሽ ስለሚያፍርበት እሺ ማለት አልፈቀደም ። በዚህ ጊዜ ሌዎፖልዶ ትራቬርሲ ለጥይቱ ጉዳይ አሰብ ነበርና ወደ ምጥዋ በቶሎ ተጠርቶ ከምክሩ ውስጥ ገባ ። በምክሩ ጊዜ ፤ "የዚህ ቀደሙ የጋንዶልፊ አንሶ አሁን ደግሞ አገረ ገዥው ባራቲዬሪ ዓድዋ ሔዶ ከመንገሻ ተገናኘ ሲባል ወሬው በቶሎ ሸዋ ደርሶ የምኒልክን ቁጣ በመቀስቀስ የተዠመረው የሰላም መንገድ ስለሚበላሽ አይሆንም" ብሎ ስለ ተናገረ ፤ በዚሁ ተወስኖ ባራቲዬሪ አሁንም ግንኙነቱን እንደማይፈልግ ገሰጠላቸው ።[1]

እንግዲህ ራስ መንገሻም ፤ ራስ አሉላም ቢወዱም ቢጠሉም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ተላልከው ከመግባት በቀር ሌላ ምርጫ እንደሌላቸው ተረዱት ። ራስ መንገሻ በዚህ ዓለም ብዙ ጊዜ በሕይወት ላይ የሰው ልጅ ሊቀበለው የማይፈልገውን ፤ የመቀበል ግዴታ እንደሚያጋጥመውና ስለ ሕዝብም ኃላፊነት እንዳለበት በመገንዘብ ፤ ያለ አንድ የውጭ ኃይልም ድጋፍ የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ አለመቻሉንና የማይቻለውንም እንደሚቻል አድርጎ በእልህ ጦርነት መዠመር ሕዝብንና የተከተላቸውን የንጹሑን ወታደራቸውን ደም በከንቱ ማፍሰስ ፤ የራሳቸውንም ሕይወት አደገኛ ሁኔታ ላይ መጣል መሆኑን ይረዱታል ።

ስለዚህ ፤ ልባዊ ጉብዝና የሚሰማቸው ራስ አሉላ ቀድሞም የመረቡን ውል ከልብ እንዳልተቀበሉት አሁንም የራስ መንገሻ በቶሎ ወደ ሰላም ማዘንበል ቅር ብሏቸው ሲያፈነግጡ ፤ መንገሻ ግን የመንገሡ ተስፋ በኢጣልያኖቹ ግልጽ ክዳት ፈጽሞ ስለጠፋ በሰላም ለመግባት ወዳጄ ምኒልክ መላላክ ዠመሩ ። ምኒልክ ደግሞ ለውጊያ እንደማይቸኩሉ ሁሉ ፤ ያለውዴታውም ቢሆን በሰላም ገብቶ በሚገዛላቸው ፊት የፉከራና የድንፋታ ስሜት አያሰሙም ። በዚህ ፈንታ ጥፋቱን ሸፍነውና አረሳስተው ሸፍቶ ቆይቶና ተመልሶ የገባላቸውን ሳይቆጡ በደስታ በመቀበል ፤ መልሶም ከልቡ የጥቃቱና የመሸነፉ መንፈስ እንዲጠፋለት ማድረጉን ያውቁበታል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ባንድ እግር አቁመው ባንድ ሥልጣን አስተባብረው በዓድዋ ከኃያሉ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ለመዋጋትም ለማሸነፍም የረዳቸው የዚህ ዓይነቱ አቅዋም ነው ።

1 Memoire d' Afrique -O.- Baratieri pp. 39 - 43 ; Italia ed Etiopia - C. Rossini PP. 76 - 81; Let - Marefia -L. Traversi, Cap. XLIII - PP. 391 - 399

ባጠገባቸው በመቆየት የምኒልክን ጠባይ የገመገመው ሲልቪ ቪኘራስ የሚባለው የፈረንሳይ ተወላጅ ከኢትዮጵያ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ እንደዚህ ይላል ።

> "...ምኒልክ በጠባዩ መሐሪ ነው ። ደግሞም የጭካኔ ቅጣት ጥላ ቻን እንደሚወልድ ያውቃል ። ከጠባዩ ሁሉ በላይ ደግነቱ ጐልቶ ይታያል ። ሕዝቡም ከልብ ይወደዋል ። አሸንፎ የያዛቸው እንኳን ቀድሞ እርስ በርሳችን በየነገዳችን ያስዕረፍት እንዋጋ ነበር እያሉ አሁን ግን ፣ ይኸን በመሰለ መሪ ውስጥ በጸጥታ በመተዳደራቸው ተደ ስተዋል ። .....[1]

---

1 Sylvian Vigneras, Une Mission Française en Abyssinie, p.191.



# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## የነፊታውራሪ ጉልላቴ አድማ—የራስ መንገሻ ምሕረት ጠይቀውና ታርቀው ወደ ዐፄ ምኒልክ መግባት

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በራስ መንገሻ ላይ ደም ሳያፈሱ ሁለት ጊዜ የሰላ ምና የፖለቲካ ድል አግኝተዋል ። አንደኛው በ1881 ዓ.ም. እነ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሲገቡ ፣ እርሳቸው እምቢ ብለው ራስ አሉላን ይዘው ባመፁ ጊዜ ፣ እንጦጦ ላይ በ1882 ዓ.ም. የንጉሠ ነገሥትነት ዘውዳቸ ውን ከደፉ በኋላ ፣ ወደ ትግሬ ራስ መንገሻን ለማስገበር ዘምተው ያለ ጦርነት ራስ መንገሻን አሳምነው ተመልሰዋል ።

አሁን ደግሞ ፣ በ1884 ዓ. ም. ላይ ራስ መንገሻና የኢጣልያ መንግሥት በመሐላ መረብ ላይ መዋዋላቸው በመንግሥታቸው ላይ ከፍ ያለ አደገኛ ሁኔታ እንደ ፈጠረ ንጉሠ ነገሥቱ አልተዘነጋቸውም ። አንድ የሠለጠነ አውሮፓዊ መንግሥት አንድን ከፍተኛ መስፍን እስከሚበቃው ድረስ በጦር መሣሪያ አስታጥቆ ራሱ ከኋላ ድጋፍ ሆኖ ቢነሣ ምናልባት ማሸነፉ እንኳን ቢያጠራጥር ፣ ላንድ አዲስ ዠማሪ ንጉሠ ነገሥት ምን ያህል ከባድና አደገኛ እንደሚሆንበት ግልጽ ነው ። ኢጣልያ አንደኛ በራሷ ፋብሪካ ማናቸውንም የጦር መሣሪያ ከተራ አልቤን እስከ መድፍ ድረስ እንደልቧ የሠራችውን ያለምንም ገደብ ከኢጣልያ አገር ወደ ምጥዋ አግዛ በማራገፍ ያገሯንም ፣ ያገር ተወላጅንም ወታደር ስታስታጥቅ ፣ በርሷ አንጻር የምትገኘው ኢት ጵያ በዚህ ጊዜ ምንም ዓይነት ዘመናዊ መሣሪያ ከመሥራት ደረጃ ላይ አልደረሰችም ። በዚህም ላይ የአውሮፓ መንግሥታት አፍሪካን እንደ ልብ ለመግዛት እንዲመቻቸው ብሩክሴል ላይ በ1890 ዓ. ም. እ.ኤ.አ. በባሪያ ንግድ እገዳ አስመስለው የጦር መሣሪያ ለአፍሪካ (ለኢትዮ ጵያ ጭምር) እንዳይሸጥ ስምምነት ማድረጋቸው ይታወሳል ።

ስለዚህ ፣ በዚህ የቅኝ አገዛዝ በተስፋፋበት ዘመን ፣ ካንድ ከሠለጠነ መንግሥት ጋር መጣላት አደገኛ ከመሆኑም በላይ ፣ በተለይ ይህ መንግሥት ራስ መንገሻን ከመሰለ የታወቀ መስፍንና ራስ አሉላን ከመሰለ ስመ ጥሩ ዠግና ጋር ተስማምቶ ሲነሣ አደገኛነቱ የበለጠ የሰፋ ነው ። በዚህ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፣ ኢጣልያንንና መንገሻን ለማለ

ያየት ረቂቁን የፖለቲካ ዘዴ ባላቸው ሙሉ ኃይል ተጠቅመው በሚሠሩበት ወቅት ሥጋት በሕሊናቸው ውስጥ እንደሚመላለስ አይጠረጠርም ። ስለዚህም ፣ በኢጣልያ ግንባር ጫለፈው የተመለከትነውን የማለያየት ፖለቲካ እየሠሩ ባገር ውስጥ ደግሞ ፣ ራስ መንገሻን ለማጋለጥና ደጋፊ ለማሳጣት ሌላ ዓይነት የፕሮፓጋንዳ ዘዴ በትግሬ ይነዛሉ ።

በዚህ ምክንያት ፣ የራስ መንገሻን ክዳት እንደሰሙ ትራቬርሲን ወደ ሮማ በላኩበት ወቅት ፣ "የመንገሻን ነገር እዩልኝ መሐላና ግዝቱን አፍርሶ እኔን አባቱን ከድቶ ከማያውቃቸው ሰዎች ጋር ሆኖ ጠላት ሲሆነኝ ነው ። እኔም እንግዲህ ወደናንተ መዝመቴ ነው ። ካህናቱ ቢበድሉ ፣ ቤተ እግዚአብሔር ቢጠፋ ነጻ ነኝ"[1] የሚል የኃይል እርምጃ እንደሚወሰዱ ወደ ትግሬ አድባራት እየላኩ በማስፈራራት በፖለቲካው ዘዴ ጐን ኃይላቸውን ለማሳየት ይጣጣሩ ነበር ።

ዳግማዊ ምኒልክና ራስ መንገሻ ፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚገኙበት ጊዜ ሁለቱም በየቤታቸው የውስጥ አድማ አጋጥሟቸው ነበር ። በ1885 ዓ. ም. የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የመርዕድ አዝማች ኃይሌ ልጅ ፊታውራሪ ጉልላቴ (ተክለ ማርያም) እስከ አሁን በመልካም አገልግሎት የቆዩትን የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ሆነው በትግሬ ተሾመው የነበሩትንና የመረቡ ስምምነት ወደ አዲስ አበባ ያባረራቸውን ደጃች መሸሻ ወርቄንና አለቃ አድማሱን ጨምረው ንጉሠ ነገሥቱን አስገድለው ጉላልቴ ንጉሠ ነገሥት ፣ መሸሻ ወርቄ ራስ ቢትወደድ ሊባሉ ማደማቸው ተገለጸና ተያዙ ። በዚህም ጊዜ እነዚህ ሁሉ ከራስ መንገሻና ከኢጣልያኖች ጋር ስምምነት አድርገዋል ተብሎ ተወራ ።

ደጃች መሸሻ ወርቄ ፣ ኢጣልያኖችና ራስ መንገሻ በምኒልክ ላይ መስማማታቸውን በዝርዝር ስለሚያውቁ ፣ ምናልባትም ፈረንጅ በዚህ ዓይነት ሲነሣ አበሻ አይመልሰውም በሚል ግምት የምኒልክ ዕድል እንዳለቀ ቆጥረው አዲስ የኑሮ ቤት ለማሰናዳት አስበው ይሆናል ። በዚህም ላይ ላፄ ምኒልክ አገልግሎታቸውን ያበረከቱት ከመዠመሪያው ዠምሮ ስለሆነ እነራስ ወሌ ፣ እነራስ መንገሻ አቲከም ፣ እነራስ መኰንን ራስ ሲባሉ ፣ እኔስ ለምን ቀረብኝ የሚል ውስጠ ንዴት እንዳላቸውም አይታወቅም ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እንደሚሉት ምኒልክ የአድማውን ወሬ እንደሰሙ እውነተኛነቱን በመጠራጠር

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 212 ።



ብዙ ጊዜ ቆይተው ሳለ ፣ እያደር እውነትነቱን ስለ ተገነዘቡት እንዲያዙ አድርገዋቸዋል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ሊባኖስ ሳሉ ፣ ጳጳሳቱ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ማቴዎስ ፣ እጨጌ ገብረ ሥላሴ ፣ ራስ ዳርጌ ፣ ራስ ሚካኤልና ራስ ወሌ ሌሎችም ባሉበት አድመኞቹ እንደ ተያዙ ቀርበው በአደባባይ ሲመረመሩ ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ለመግደል ማደማቸውን አመኑ ። የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ለመደብደብ ሊሔዱ ሲሉ ጳጳሳቱም ፣ መሳፍንቱም ከተቀመጡበት ተነሥተው የሞቱ ፍርድ እንዲቀርላቸው ልመና አቀረቡ ። በዚያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "እነዚህ ካልተቀጡ በነዚህ ምን መጣባቸው እያለ ሌላው ሁሉ እንዲህ ያደርግ የለምን" ቢሉ ፣ ጳጳሳቱና መሳፍንቱ ፣ "እስካሁን ድረስ ጠላትዎን የሚጥልልዎና የሚቀጣልዎ እግዚአብሔር ነው እንጂ ፣ እርስዎማ ማንን ቀጥተው ያውቃሉ? አሁንም ስለ እግዚአብሔር ብለው ይማሩልን" ብለው ልመናቸውን ስለአጸኑ ፣ የሞቱ ፍርድ ወደ እስራት ተለውጦ ፊታውራሪ ጉልላቴ ለራስ ዳርጌ ፣ ደጃች መሸሻ ለደጃች ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፣ አለቃ አድማሱ ለደጃች ወልዴ ተሰጥተው ታሰሩ ።

ፊታውራሪ ጉልላቴ ፣ በራስ ዳርጌ እጅ ሰላሌ ፣ ሸንኩርት እንደ ታሰሩ በ1887 ዓ.ም. ሲሞቱ ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄና አለቃ አድማሱ በኋላ ምሕረት አግኝተው ተመልሰው ባለሟል ሆኑ ። ገንዘብ ተቀብሎ ዐፄ ምኒልክን ከሰገነት ደርብ ላይ ገፍትሮ ለመጣልና ለመግደል የተመደበው ልጅ አበበ የሚባለው የልፍኝ አሽከር ግን እጅና እግሩን ተቆርጦ ተቀጣ ።[1]

በዚህ ዓይነት ፣ ተመሳሳይ አድማ በትግሬ በራስ መንገሻ ዘንድ ተፈጽሟል ። በአዲስ አበባ ባፄ ምኒልክ ላይ የተነሣው አድማ ከኢጣልያኖቹና ከራስ መንገሻ ስምምነት ጋር በመጠኑ የተያያዘ እንደሚመስለው ሁሉ ፣ በራስ መንገሻ የተነሣውም አድማ ራስ መንገሻን ኢጣልያኖቹ ስለከዷቸው ብቻቸውንም የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ ስለማይችሉ ፣ መቸገራቸውን በመገመት በዚህ ችግር ጠላቶቻቸው ለመጠቀም አስበው ይሆናል ።

አድማውን የወጠኑት ፣ የትልቁ የራስ አርአያ ልጆች እነደጃች ቦጋለ ናቸው ። የራስ አርአያ ቤት ትክለኛ ባላባትነቱ በእንደርታ ስለሆነ ፣ ለሹም ተምቤን ምርጫ ቤትም ሆነ ለአጋሜው ለደጃች

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 197 ፣ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ሳይጠረዝ የቀረው የታሪክ መጽሐፍ ገጽ 99 ።

ሰባጋዲስ ቤትም መግዛት እንደማይወድ ከዚህ በፊት አመልክተናል። ደጃች ደብብ አርአያ ፣ ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ከግብጾችም ከኢጣልያኖቹም ጋር ሆነው ዐፄ ዮሐንስን ሲያስቸግሩ የኖሩትና አሁንም ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር ሲዋጉ የሞቱበት ሰበብ ይኸው ነው። ወንድማቸው ደጃች ቦጋለ አርአያና ያጐታቸው የደጃች ማሩ ልጅ መሸሻ ፣ ግዴታም ሆኖባቸው ካፄ ዮሐንስ ጋር መተማ ዘምተው ነበር። ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ የመንገሻን እልጋ ወራሽነት በሰሙ ጊዜ አኩርፈው ፣ ጓዛቸውን ከነራስ መንገሻ ጓዝ ለይተው ወደ እንደርታ መጥተው ነበር። ባለፈው ደጃች ደብብ ከነራስ መንገሻ ጋር ተዋግተው የሞቱ ጊዜ ደጃች ቦጋለ አብረው ከወንድማቸው ከደጃች ደብብ ጋር ሆነው ተዋግተው ነበር።

አሁንም እኚሁ ደጃች ቦጋለ ፣ ደጃች ብሩ የደራው ፣ ደጃች ሐጎስ የገራልታው ፣ ደጃች ጒርፉ የእንደርታው ፣ ፊታውራሪ መሸሻ የተምቤኑ ሆነው ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ለመግደል አድመው ሳለ አድማውን ከመካከላቸው የቅርብ ዘመድ አውጥቶ ለነራስ መንገሻ ነገራቸው። በዚህ ጊዜ ደጃች ቦጋለ ፣ ደጃች ብሩ ፣ ደጃች ሐጎስና ደጃች ጒርፉ ተይዘው ታሰሩ። ደጃች ቦጋለ በመካከሉ ከእስር ቤት አምልጠው ወደ ሸዋ መጥተው ላፄ ምኒልክ ገቡ። ራስ መንገሻን ለመግደል ተመድበው የነበሩት ፊታውራሪ መሸሻ ፣ እጅና እግራቸው እንዲሁም መላሳቸው ተቆርጦ ከተኙበት ዘመዳቸው የደጃች ዋህድ ልጅ ደጃች ካህሳይ እንሥተው ወደ መቀሌ ወስደው በቤታቸው እንዳስተኟቸው ሞቱ።[1]

በዚህ ዓይነት ራስ መንገሻ ፣ አድመኞቻቸውን አጥፍተው ለመንግሥ ማስባቸውን ሐውዜን ላይ ለሕዝብ ከገለጹ በኋላ ኢጣልያኖቹ ስለ ከዷቸው ፣ የራሳቸውም ኃይል የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ እንደማይችል በመገንዘብ በ1886 ዓ.ም. ላይ ባለፈው ሥራቸው ተጸጽተው ፣ “ይማሩኝ ልግባ” የሚል ደብዳቤ ጽፈው በሹም አጋሜ ተስፋዬ እጅ አሲዘው ወደ ዐፄ ምኒልክ ላኩ። ንጉሠ ነገሥቱም ደብዳቤውን አንብበው ፣ “ቀድሞውንም ቢሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች አስመስለው ቢነግሩት ይሆናል እንጂ ፣ እርሱ ከልቡ አንቅቶ ይኸን ሥራ እንዳልሠራው ዐውቃለሁ” ብለው ፣ “ባለፈው ጥፋትህ ሁሉ ምሬሃለሁና ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ ይሁን” ብለው መልሱን ላኩባቸው። ቀጥሎም አንዳንድ ሽፍታ ተነሥቶ በመንገድ ማስቸገሩን ስለ ሰሙና የፋሲካን መቃረብም ተመልክተውና አጢነው ንጉሠ ነገሥቱ ፣ “ፋሲካን

1 Italia ed Etiopia . . .p. 79.



ውሰህ እንድትመጣ” የሚል መልስ አሲዘው እኚሁኑ ተስፋዬን መልሰው ላኩዋቸው።[1]

“የኢትዮጵያ ጠላቶች አስመስለው ቢነግሩት ይሆናል እንጂ ፣ እርሱ ከልቡ አንቅቶ ይኸን ሥራ እንዳልሠራ ዐውቃለሁ” ብለው የተናገሩትን ስናስታውስ ፣ ይኸን የመሰለውን የዘዴ አነጋገር ምኒልክ ብዙ ጊዜ ሲጠቀሙበት ይታያል። ጋንዶልፊ ከራስ መንገሻ ጋር መረብ ላይ በተዋዋለ ጊዜ ፣ “እንደዚህ ያለውን ሥራ የምጥዋ አገረ ገዥዎች ይሆናሉ እንጂ ፣ ወዳጄ የኢጣልያ ንጉሥ ያደርጉታል ብዬ እልጠራጠርም” ብለው የጻፉትን ከዚህ በፊት ያነበብነው ትዝ ይለናል። ከ1880—81 ዓ. ም. ምኒልክ ባፄ ዮሐንስ ላይ በሸፈቱ ጊዜ በደብዳቤ ሲወቃቀሱ ፣ “ይኸን ሁሉ እያደረገ እናንተንና እኔን ሰይጣን ሆኖ የሚያፋጀን በጌምድሬ መሸሻ ወርቄ የሚባል መካር አበጅታችሁ የተንኰሉ ሁሉ ምንጭ እርሱ ነው እንጂ ፣ ከንጉሥም ከናንተም ይኸን ያህል ተንኰል እንደሌለ ዐውቃለሁ”ብለው ዐፄ ዮሐንስ ለራስ ዳርጌ የጻፉትን ስናስታውስ ፣ ይኸ ዓይነቱ የአነጋገር ዘዴ ባፄ ምኒልክ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም ዘዴኛ ነገሥታት በብዙ ይሠራበት እንደነበረ እንገነዘባለን። ዘዴውም የሸፈተውን ልብ ወደ ሰላማዊነት ለመሳብ የሚረዳና አብሮ በሰላም ለመኖር የሚያግዝ መሆኑ ነው።

በእርግጥም ፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ፣ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አባባል ፣ ከሮማ መጥተው ፣ “ሸፍትና አንተው ንገሥ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ትደግፍሀለች” ብለው በመገፋፋት መንገሻን ከመቀሌ ፣ ጋንዶልፊን ከምጥዋ መረብ ድረስ አስጉዘው ያዋዋሉትን ኔራሲንንና ደ ማርቲኖን ወይም ራስ መንገሻን ወደዚህ ጉዳይ ገፍተው ያገቧቸውን የትግሬ መኳንንቶችን ወይም ሁለቱንም ወገኖች ይሆናል። በተለይም ያፄ ዮሐንስ ባለሟልና የልብ ወዳጅ የነበሩት አሁን ከብራቸውና ጥቅማቸው ወደ እጨጌ ገብረ ሥላሴ የተዛወረባቸው ሽማግሌው እጨጌ ቴዎፍሎስ መንገሻን ከምኒልክ በማለያየቱ ተግባርና ከኢጣልያ በማስማማቱ ጉዳይ ከሁሉም የበለጠ እንደ ነበሩበት የታወቀ ነው።[2]

ራስ አሉላ ፣ በመረቡ ስምምነትና መሐላ እስከዛሬ ሲዋጉዋቸው ለኖሩት ለኢጣልያኖች ወዳጅነት እታመናለሁ ማለቱ ቀፏቸው ፣ “ለራስ መንገሻ ብቻ እታመናለሁ” ሲሉ ፣ የውሉ ለት ያረጋገጡትን ባለፈው አንብበናል። አሁንም ራስ መንገሻ ሹም አጋሜ ተስፋዬን የዕርቅና

1 ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . .ገጽ 212 ፣ ሳይጠረዝ የቀረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ገጽ 173—175 ።

2 ያልተጠረዘው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጽሑፍ ፣ ገጽ 175 ።

የምሕረት ጥያቄ ደብዳቤ አሲይዘው ወደ አዲስ አበባ ላፄ ምኒልክ ሲልኩ ራስ አሉላ በነገሩ አልተስማሙበትም ። ራስ መንገሻ መቀሌ ሆነው ካፄ ምኒልክ ጋር ሲላላኩ በዚህም ጉዳይ የጸለምቱ ገዥ ራስ ሐጎስ ተስማምተው አብረው ባሉበት ሰዓት ፤ ራስ አሉላ ደግሞ የራስ መንገሻን ወደ ሸዋ መሔድ በመቃወም ራስ ስብሐትን ይዘው በራስ መንገሻ ላይ አድማ ዠምረው ነበር ። ለዚሁም እጨጌ ቴዎፍሎስ እንዲደረቡ ገፋፍተዋቸው ነበር ። ሽማግሌው እጨጌ ግን ፤ ሊደረቡ አልፈለጉም ። በኋላ ግን ፤ ራስ አሉላ የኢጣልያ ደጋፊነት ከቀረ ባንድ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱም ፤ ከራስ መንገሻም መጣላቱ የማያዋጣ መሆኑንና በርሳቸውም የመለየት ዓላማ የቀረው አለመተባበሩን ሲረዱት፤ "ከመረብ ወዲህ ባለው አገር ይሾሙኛል ብዬ ሳይሾሙኝ ስለቀሩ ቅር ብሎኝ ነው እንጂ፤ ጌታዬን ራስ መንገሻን ዐፄ ምኒልክንም አልካድሁም" ብለው የአክሱምን ካህናት አማላጅ ልከው ፤ ድንጋይ ተሸክመው ፤ ምሕረት ጠይቀው ለራስ መንገሻ ገቡላቸው ።

ራስ መንገሻም ፤ ምንም በጠቅላላው ምሕረት ቢያደርጉላቸው በራስ አሉላ የመጨረሻ ሁኔታ ቅርታቸው በርክት ብሎ ነበርና ከመቶ ባለጠመንጃ በቀር የቀረውን የራስ አሉላን ጭፍራ ገፈውና ወደ ሌላ ደልድለው ፤ ከግዛታቸውም ቆራርጠው ለነደጃች አምባዬ በመስጠት እርሳቸውን በአንዲት ወረዳ ብቻ ወሰኑዋቸው ። እንደዚሁም በቅርቡ የራስነት ማዕረግ የሰጧቸው ራስ ስብሐት ከራስ አሉላ ጋር በግልጽ ከመሸፈታቸውም በላይ እንዲያውም ፤ "አሉላ እርሳቸውን በራስ መንገሻ እግር ለማንገሥ አስበዋል ፤ ራስ ስብሐት ደግሞ ራስ መንገሻን ለመውጋት ከዋግሹም ብሩና ከራስ ወሌ ጋር ተላልከዋል" ተብሎ ተወርቶ ነበርና ለማናቸውም ለንጥጥር መቀሌ ድረስ ጠርተዋቸው ከመጡ በኋላ ፤ የጦር መሣሪያቸውን በሙሉ ተቀብለው ራስ ስብሐትን ከልጆቻቸው ከደጃች ደስታና ከደጃች አስገዶም ፤ ከወንድማቸው ከደጃች አባይ ጋር በአምባ ሰላማ አሰሯቸው ።[1]

እንደዚህ አድርገው ራስ መንገሻ ፤ የቤታቸውን ጣጣ ከጨረሱና ካደላደሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ተዘጋጁ ። ካፄ ምኒልክም ዘንድ የላስታው ገዥ ዋግሹም ብሩ ፤ የበጌምድሩ ገዥ ራስ ወሌ ፤ የወሎው ገዥ ራስ ሚካኤል ፤ የወረይሉው የንጉሠ ነገሥት ቤተ መንግሥት አዛዥ ቢትወደድ አጥናፌ በመቀባበል እያስተናገዱ ራስ መንገሻን እንዲሸኙ ታዘው ነበርና ፤ በዚህ ዓይነት ራስ መንገሻ ለትግሬ ጥብቅ ገዥ የዓይባውን ደጃች ተድላን ትተው ታላላቅ መኳንንቶቻቸውን

1 Italia ed Etiopia, pp. 89 - 91.



ራስ አሉላን ፤ ራስ ሐጎስን ፤ ራስ ወልደ ሚካኤል ሰሎሞንን አስከትለው በሚያዝያ ወር ከትግሬ ተነሥተው በላስታ ፤ በየጁና በወሎ አድርገው ፤ በግንቦት ወር አዲስ አበባ ገቡ ። የአክሱም ካህናትም ለምልጃና ለማስታረቅ ሥዕለ ማርያምን ይዘው አብረው መጥተው ነበር። በጉዞው ጊዜ ፤ "አዲስ አበባ ስንደርስ ተይዘን እንታሰር ይሆን ወይስ ሁላችንንም አዲስ አበባ የቁም እስር አድርገው በትግሬ ሌላ ይሾሙ ይሆን" የሚል ጥርጣሬ በአንዳንዶቹ ላይ ሲያድር ፤ ራስ መንገሻ ደግሞ ፤ "ንጉሠ ነገሥቱ ካዲስ አበባ ወጣ ብለው ባንደኛው ከተማቸው ላይ ሆነው ይቀበሉኛል" የሚል እምነት ነበራቸው ይባላል። ይሁን እንጂ እስራቱም ፤ ግዞቱም ፤ በሙሉ ምሕረት መለወጡንና ንጉሠ ነገሥቱም ከአዲስ አበባ ከቤተ መንግሥታቸው አለመነቃነቃቸውን አዲስ አበባ ሲደርሱ ተረዱት ።

ስለ አቀባበሉ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ከስጡት ዝርዝር ሐተታ ውስጥ እንደዚህ የሚል ይነበባል ።

> . . . ዐፄ ምኒልክ በሥርዓተ መንግሥት ሆነው ከዙፋንዎ (ከዙፋናቸው) ተቀምጠው ራሶችም ራስ ዳርጌ ፤ ራስ ሚካኤል ፤ ራስ ወሌ ፤ እነዚህ ራስ ወርቅ አድርገዋል ። ሊቀ መኳስቱም እንደ ሥርዓታቸው ሆነዋል ። ካህናቱም ካባ ለብሰው በቀኝና በግራ ሆነው መንበረ መንግሥቱን ያጥናሉ . . . በዙፋኑም በድንኳኑም . . . ያለው የወርቅ ምንጣፍ የወርቁ መከዳ ያስፈራል ። በዙፋኑም ሰይፈ ዣግሬዎች ባለወርቅ መክድ* ሰይፍ መዘው ግራና ቀኝ ቆመዋል ። . . . ደጃዝማቾቹም መኳንንቶቹም አጊጠው የነደደ እሳት መስለው ባዳራሹ መልተው ቆመዋል . . . የውጭውም ሠራዊት እንደ ማዕረግ እንደ ማዕረጉ የጦር መሣሪያውን እየለበሰ ፤ ሰንደቅ ዓላማውን እየያዘ ፤ ካዳራሹ ደጃፍ ዠምሮ የመዋቱ ወንዝ (አቧሬ አጠገብ) ተሻግሮ እየተነባበረ ፤ እየተጨናነቀ ተሰልፎ ነበር ። ከዚህም ሁሉ መሣሪያ በወርቅና በብር እያጌጠ ያንበሳ ጋማ ያሰረው ፤ ጐፈር የደረበው ከጌጡ ሁሉ እሱ ይደምቃል ። በዚህ ቀን እንኳን ሰውና መሬቲቱ አጌጠች ። ሰውም ወዲያና ወዲህ እንዳይል የግባቱ ተኩስ እንዳይመታው ተከልክሎ ነበር . . .

ይኸውም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ፤ ራስ መንገሻ ወደ አዳራሹ መጣ። አክሱሞችም ሥዕለ ማርያምን ይዘው ከራስ መንገሻ በኋላ ነበሩ ። ያባቱም መኳንንቶች እነራስ ሐጎስ ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ ከዐፄ ምኒልክ ከፊትዎ አልደረሱም ነበርና ድንጋይ ተሸክመው የቀረውም መኳንንት ሁሉ እንደዚሁ ሆኖ ወደ አዳራሹ ገቡ ። ድንጋዩንም እንደ ተሸከሙ ወደቁ ። ዐፄም ምሬአችኋለሁ አሏቸው ። አጋፋሪዎቹም ድንጋዩን ከላያቸው አነሡላቸው እነዚያም እጅ ነሥተው መሬቱን ስመው ቆሙ ። በዚህም

* መክድ ምርጥ ሰይፍ

ወቅት 31 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ። ያም የተሰለፈ ሰው ጠመንጃውን ሙሉ ግባት ቢተኩሰው ፣ ጢሱ ከተማውን እንደ ጉም አለበሰው ። የተ ኩሱም ብዛት ይህን ይመስላል አይባልም ።. . . ከዚህ በኋላ ግብር ገብቶ ሲበላ ሲጠጣ ውሎ ራስ መንገሻ ተሰናብቶ ወደ ሰፈሩ ተሻገረ[1]

በዚህ ዓይነት ፣ ብዙ ደም ሊያፋስስ ይችል የነበረውና በዚሁ ደም ላይ ተራምዶ ግዛቱን ለማስፋፋት ይጠባበቅ የነበረው የኢጣልያ ምኞት፣ በዳግማዊ ምኒልክ ትዕግሥትና የፖለቲካ ስልት ፣ በራስ መንገሻም እርቅ ተቀባይነት የተነሣ በፍጹም ተሰናከለ ። ራስ መንገሻ ያፄ ዮሐንስ የአሳብ አልጋ ወራሽ ሲሆኑ ፣ የዐፄ ምኒልክ አልጋ ወራሽነት በተግባር የዋለ ነው ። ነገር ግን ፣ ራስ መንገሻን ሰምን ዙፋን ተመኙ? በምን ምክንያት ዐፄ ምኒልክን ከዱ ? ብሎ መውቀስ አይቻልም ። በእርሳ ቸው እግር ያለ ማንም መስፍን አልጋ ወራሽ ከተባለ በኋላ ሊያደር ገው የሚችል ነው ። እንዲያውም እንደ ደጃች ደብብ ወይም እንደ ደጃች ሥዩም አባ ኃያል ያለ መስፍን ቢሆን ኖሮ ፣ አቅሙ እንደማይ ችል ቢያውቀውም ፣ ለእልሁ ሲል ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ተዋ ግቶ በከንቱ የብዙ ሰው ደም ሊያፋስስ ይችል ነበር ።

አሁን ግን ፣ ራስ መንገሻ ምሕረት ጠይቀው ከገቡላቸው በኋላ ፣ ዐፄ ምኒልክም ከልባቸው ምሕረት አድርገውላቸው ሐያ ቀን ያህል አዲስ አበባ በቆዩበት ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱም ከእቴጌ ጣይቱም ጋር በፍቅር ፣ በደስታ ፣ በታላቅ መስተንግዶና መንከባከብ ሰን ብተው ፣ በመጨረሻም ንጉሠ ነገሥቱ ከዘውድ በቀር ለንጉሥ የሚገባ ሙሉ ሽልማት ሸልመው ፣ ሹመታቸውንም አጽድቀው አሰናበቷ ቸውና በሰኔ ወር ከአዲስ አበባ ተነሥተው ወደ መቀሌ ሔዱ ። ራስ አሉላ ግን ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ቅሬታ ገብቷቸው ነበርና ፣ " ከዚሁ ከአደባባይዎ ደጅ እየጠናሁ መቆየት ይሻለኛል" ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ አመልክተው አዲስ አበባ ቀሩ ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ገጽ 214—215





ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ከዬ ምኒልክ ምሕረት ለመጠየቅ አዲስ አበባ የገቡበት

ለቱር ዲሞንድ

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## የኮሎኔል ፌሬዲሪክ ፒያኖ መላክና ምንም ፋይዳ ሳያገኝ ወደ መጣበት መመለስ

በኢጣልያ አገር ፣ ምጥዋ ከተያዘበት እ.ኤ.አ. ከ1885 ዓ.ም. ዠምሮ ዶ ፕሪቲስ አጉስቲኖ 1885—1887 ፣ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ 1887—1891 ዲሩዲኒ አንቶኒዮ 1891—1892 ጂዎሊቲ ጂዎቫኒ 1892—1893 እንደገና ክሪስፒ 1893—1896 እየተከታተሉ በተቀራረበ ጊዜ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነዋል ።

ባለፈው እንዳመለከትነው ፣ ጂዎሊቲ ጁዎቫኒ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ቤኔዲቶ ብሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ፒሎ ሉዊጂ የጦር ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ ፣ ምኒልክን ትተው ከመንገሻ ጋር መረብ ላይ ተዋዋሉ። "እርሱን መደገፍ በማናቸውም ረገድ አያዋጣም" የሚለው አሳብ ከአንቶኔሊ ፣ ከካፒቴን ቺኪና እንዲሁም ከአንቶኔሊ ወዲህ ነገሩን እን ጦጦና አዲስ አበባ ተቀምጦ ከተከታተለው ከዶክተር ሌዎፖልድ ትራቬርሲ እየተሰነዘረ ጸድቆ ነበር ። በበኩላቸው ዐፄ ምኒልክም ፣ እ.ኤ.አ በየካቲት 16 ቀን 1893 ዓ .ም. በይፋ ውሉን መሰረዛቸውን ገልጠዋል ። ይሁን እንጂ ፣ ኢጣልያኖች ስለቅኝ አገር ፍለጋ ያላቸው ምኞት የጋለ ከመሆኑ የተነሣ ፣ ጂዎሊቲ ተሸሮ ታኅሣሥ 15 ቀን 1893 ዓ.ም ያው ቅኝ አገር ፈላጊው ክሪስፒ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲመለስ፣ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ባሮን አልቤርቶ ብላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ሞቺኒ ስታኒስላኦ የጦር ሚኒስትር ሆኑ ። በቅኝ አገር ጉዳይ ያለውን በቀጥታ የሚመለከተው እነዚህን ሦስቱን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ነው ። እነሱም ፣ "ለኢጣልያ እንደ እንግሊዝ ፣ እንደ ፈረንሳይ ስፊ ግዛት እናተርፋለን" የሚለውን ዓላማ በመከተል በም ክር ቤቱም "ቅኝ አገር ይቅርብን ፣ አገራችን ይበቃናል ፤ ይኸንኑ መሬታችንን እናቅና" ከሚሉት ወገኖች ጋር በይፋ እየተከራከሩ ፣ የቅኝ አገር የማግኘቱን ዓላማ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ታጥቀው የተነሡ ናቸው ።

በዚሁ ጊዜ ፣ በነዚህ በሦስቱ ባለሥልጣኖች ስምምነት የኢትዮጵያን ጉዳይ በዝርዝር ያውቃል ተብሎ አንቶኔሊ በውጭ ጉዳይ

ሚኒስቴር ውስጥ ምክትል ሚኒስትር ሆኖ የደረጃ ዕድገት አግኝቶ ተሾመ ። ነገር ግን ፥ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ተሽሮ በርሱ ምትክ አዳሞሊ የሚባለው ተሾመ ።

እነዚህ ሦስት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ፥ የፊተኞቹ ባለሥልጣኖች ስለቅኝ አገር መስፋፋት የተከተሉትን የመገታትና የጥንቃቄ አሠራር በመነቃቀፍ እንደገና ባዲስ የኃይል መንፈስ ፥ “የውጫሌ ውል ይርጋ ወይም ቢለወጥም ቃሉ ይሻሻል ፤ አለዚያም በዚህ ፈንታ ኢትዮጵያ በሰሜን ሰፋ ያለ ግዛት ለኢጣልያ መልቀቅ አለባት ። ለጊዜው ግን ፥ በኤርትራ የኢጣልያ የግዛት ወሰኑ መረብ ወንዝ መሆን አለበት” ብለው ባዔ ምኒልክና ባካባቢዎቻቸው የተጠላውን አባባል ፀነሱ ። ዋናው የኢጣልያ ፍላጐት ግን ፥ በዚህ ፅንሰ አሳብ ቆይቶ ጊዜውና ወቅቱ እንዳመቸ በተለይ ካለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ ተገነዘቡት ፥ የውስጥ ጦርነት በኢትዮጵያ መቀስቀሱ ስለማይቀር በዚያን ጊዜ ፥ መላዋን ኢትዮጵያን በውስጣቸው ለማስገባት ነበር ። ያዔ ምኒልክ አሳብ ደግሞ ፥ “በውጫሌ ውል ከተጠቀሰው አውራጃ አልፈው አገር ቢይዙ እዋጋለሁ ። ይኸን ወደጐን አድርገው ቢተዉ የንግድ ሽቀጥ በወዳጅነት እየተለዋወጥሁ በሰላም እኖራለሁ ። በብዙ ጊዜ የርስ በርስ ጦርነት የተዳከመችውን አገሬን የአውሮፓን ሥልጣኔ በማስገባት አለማለሁ” የሚል ነው ።

በዚህ ተፃራሪ በሆነው አሳብ ላይ ንጉሠ ነገሥቱና የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ፥ እውነተኛ ስሜታቸውን በገሃድ ሳይገላለጡ ውስጥ ለውስጥ የሚያደርጉት የድብብቆሽ የፖለቲካ ሽኩቻ ፥ አሁን ካለንበት ዘመን ስንመለከተው ነገሩ ለኢትዮጵያ አደገኛ የሞትና የሕይወት ጉዳይ ሆኖ ይታያል ። አደጋውም የሚታየው ከመሳፍንቱ የሥልጣን ምኞት ጋር የተያያዘና ጊዜው የቅኝ አገር የወረራ ዘመን በአውሮፓዎች ዘንድ የተፋፋመበት ስለሆነ ፥ ወቅቱ ለወራሪ አውሮፓዊ እንጂ ለተከላካይ ጥቁር አመቺ አልነበረም ።

ስለዚህ ፥ በዚህ አስቸጋሪ ወጥመድ ውስጥ የሚገኙት ንጉሠ ነገሥት ፥ በራስ መንገሻም ከኢጣልያኖች ጋር መስማማት የተነሣ አደጋው ፍጥጥ ብሎ ታይቶአቸው ነበር ። ራስ መንገሻ እስቲገቡላቸው ድረስ ለኢጣልያው መልክተኛ ለዶክተር ትራቬርሲ ያነጋገር ወዝ እየሰጡ ፥ የፈገግታ መልክ እያሳዩ ፥ “ሁሉም ነገር በሰላምና በወዳጅነት ያልቃል” በሚል ባልተወሰነና በአወላዋይ ዘይቤ ፥ በአንደበት ከመደለል በቀር ፥ “መንገሻን ከዳችሁ የኔን ወዳጅነት ብታጸኑ ይኸን አደርግላችኋለሁ” ብለው በጽሑፍም ፥ በቃልም ምንም ዓይነት ግልጽ የሆነ ተስፋ አልሰጡም ። ኢጣልያኖቹም ፥ ምኞታቸው ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ



በወረራ ዓላማቸው ኃያሉ እንግሊዝ ተባባሪ ስለሆነ ፥ “መንገሻን ብን ከዳልዎና የመረቡን ስምምነት ብንሰርዝልዎ ይኸን ያደርጉልናል” ብለው የውስጥ ምኞታቸውን ገልጸው ፥ በመንገሻ ክዳትና በኢጣልያ የጦር ኃይል የሠጉትን ንጉሥ ግዴታ ለማስገባት አልደፈሩም ።

እንደሚመስለው ፥ አሳባቸው ያተኮረው ደከም ብለው የታዩዋቸውን ፥ “ራስ መንገሻን ከደን ከኃይለኛው ከምኒልክ ጋር የኖረ ወዳጅነታችንን ካጸናንና አሰብ ላይ ለግልግል መያገ ሆኖ የቆየውን ሁለት ሚሊዮን ጥይት ከአስረከብን ፥ ከዚያ ወዲያ ምኒልክ የውጫሌውንም ስምምነት ፥ የመረቡንም ወሰን ዐውቀው በይሉኝታ ይቀበሉታል ። ሳይቀበሉት ቢቀሩ መሳፍንቱን ከፋፍለን በምኒልክ ላይ ከማስነሣት ጋር ባለን የተዘጋጀ ኃይል በመጠቀም ፥ በማናቸውም ረገድ የወረራ ዓላማችን እግቡ መድረስ አለበት” የሚል ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱም ፥ ራስ መንገሻ እስቲገቡ ፥ ከፈረንሳይ አገር በነሽፍነ በኩል በሚያስቸኩል ያዘዙት መድፍና የጦር መሣሪያ እስኪደርስ ፥ በመስኮቦች በኩል ተስፋ ያደረጉት ዕርዳታ መጠኑ እታወቀ ድረስ ነገሩን የዲፕሎማሲ ዘዴ በተሞላበት ለዘብታ አቆዩት ። ራስ መንገሻ ከታላላቅ ስመ ጥር የጦር አለቆች ከራስ አሉላ ፥ ከራስ ወልደ ሚካኤል ፥ ከራስ ሐጎስ ጋር ከገቡላቸው በኋላ ፥ ከፈረንሳይ አገር የሚጠብቁት ዘመናዊ መድፍ ቢደርሳቸውም ፥ አሁንም የርጋታና የትዕግሥት ጠባያቸውን ሳይለውጡ ፥ ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች በውጫሌ ውል 17ኛ አንቀጽና በወሰኑ ላይ ያላቸውን የጠጠረ አቅዋም ይገልጹ ገሮመር ። ትራቬርሲ ባለበት የስማቸው ምልክት “ም” ያለበት ከፈረንሳይ አገር የመጣላቸውን 30 ዘመናይ መድፍ ጐብኝተው ሲጨርሱ ፥ “እንግዲህ የመጣው ይምጣ ፤ አይመጣም እንጂ ቢመጣማ በዚህ እናሳየዋለን”[1] ብለዋል ።

ቀጥለውም ከወዳጆቻቸው ከነሙሴ አልፍሬድ ኢልግ ፥ ከነሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ፥ ከነሙሴ ሽፍነ ፥ ከነሙሴ ሳቩሬ ጋር በጉዳዩ በመመካከር ፥ እንዲሁም በአካባቢያቸው መሳፍንትና መኳንንት በተለይም ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር አሳብ ለአሳብ እየተለዋወጡ ፥ አከራካሪዋንና አዋራጅዋን 17ኛ አንቀጽ ራሳቸው ኢጣልያኖቹን እንዲሠርዙ ጠየቁዋቸው ። እነሱም የንግግር ወዝ እየሰጡ ጉዳዩን በማራዘማቸው ፥ በበኩላቸው ምኒልክ መሠረዛቸውን እ.ኤ.አ. በየካቲት 16 ቀን 1893 ዓ.ም. ለየመንግሥታቱ አስታወቁ ። ቢሆንም ዶክተር ትራቬርሲ

1 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ገጽ 85—86 ።

እነአንቶኔሊ ያበላሹትን በመረቡ ለምምነት የደፈረሰውን የወዳጅነት
ግንኙነት ከሥፍራው እመልሳለሁ ብሎ ከመድከም ላይ ይገኛል ።

ነገር ግን ፣ በሮማ ያሉት አዲሶቹ ባለሥልጣኖች ካለፈው መንግ
ሥት መሪዎች ጋር በመስማማት ትራቬርሲ የሠራውን በመንቀፍ ፣
አዲሱንና የወረራ ምኞታችንንም በምኒልክ ዘንድ ለማስቀበል የትራ
ቬርሲ ችሎታውም ፣ አቅሙም ፣ ማዕረጉም ያነሰ ነው በማለት ከርሱ
በማዕረግ ከፍ ያለ ሰው እንዲላክ ሲታሰብ ፣ ምርጫው ኮሎኔል ፍሬዲሪክ
ፒያኖ ከሚባለው የጦር መኰንን ላይ ወደቀ ። ይኸው መኰንን የኢጣ
ልያ ጦር ምጥዋ ከገባ ዠምሮ ልዩ ልዩ የስላምና የወታደርነትም ሥራ
የፈጸመ ነው ። ገና ባሄ ዮሐንስ ጊዜ ከራስ አሉላ እጅ ለማምለጥና
ለስለላ እንዲመቸው ፣ "መሐንዲስ ነኝ እንጂ ወታደር አይደለሁም"
ብሎ በሐሰት ተናግሮ እስከ መታሰር ደርሶ ነበር ። ራስ መኰንንም
ከሮማ ሲመለሱ አገረ ገዥው ጄኔራል አሬሮ እንዳይቀበላቸው ያደረ
ገው እርሱ ነበረ ። ኮሎኔሉ ወደ ምጥዋ ሲመጣ ነገሩ በምስጢር ሆኖ
ስሙና ማዕረጉ በሐሰት ፣ "ኮማንዳቶሬ ባካላሪ አሲያስ የፖስታ እንስፔ
ክተር"[1] ተብሎ ነው ።

እርሱም አዲስ አበባ የገባው ወዲያው ራስ መንገሻ ከንጉሠ
ነገሥቱ ልባዊ ምሕረት አግኝተው ፣ ሹመታቸውን አስመርቀውና በኢ
ጣልያ ላይ ቂማቸውን በልባቸው ይዘው ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ
ነው ። የኮሎኔል ፍሬዲሪክ ፒያኖ ከኢጣልያ መንግሥት ተልኮ መም
ጣት ፣ በትራቬርሲ አማካይነት ለንጉሠ ነገሥቱ ተገልጾላቸው ስለነበረ
በርሳቸው ግምት ይኸው የጦር መኰንን የ17ኛውን አንቀጽ መሠረዝ
የሚገልጽ ደንበኛ የንጉሡን የኡምቤርቶን ማኅተም ይዞ የሚመጣ
መስሏቸው ነበር ። ስለዚህም መልካም አቀባበልና መስተንግዶ ተደ
ርጐለት ነበር ።

ኮሎኔሉ በመጣ በዐሥረኛው ቀን ፣ እ.ኤ.አ. ሰኔ 26 ቀን 1894
ዓ.ም ከዶክተር ትራቬርሲ ጋር ሁለቱንም እቴጌ ጣይቱ ባሉበት ንጉሠ
ነገሥቱ በቤተ መንግሥታቸው ተቀብለው የስላምታው ጉዳይ ካለቀ
በኋላ ፣ "17ኛውን አንቀጽ እንሠርዛለን እያላችሁ በማነህ ማነህ ነገሩ

1 Gli Italiani in Africa - Angelo del Boca, pp. 500- 507.



እስካሁን እንደዚሁ ተጎተተ ። መሬት አልፋችሁ እስከ መረብ ድረስ
ባንዲራችሁን ተከላችሁ" ብለው ወቀሳ በማስቀደም ፣ አሁን ስለነዚህ
ዓበይት ጉዳዮች ከመንግሥቱ ወረቀት ይዞ እንደሆን ቢጠይቁት ፣ ከጄ
ኔራል ባራቲዬሪ ተልኮ ስለሁሉም ጉዳይ ለመነጋገር መምጣቱን
ገልጾ ክርክር ከተደረገ በኋላ ፣ በመጨረሻ ከመንግሥቱ የተሰጠውን
መመሪያ መሠረት በማድረግ ፣ "በ17ኛው አንቀጽ ለኛ የከለከሉትን የጠ
ባቂነት መብት ለሌላ ኃያል መንግሥት እንደማይሰጡ ቃል ይግቡ
ልንና ይሠረዝ" የሚል አሳብ ወረወረ ። በዚህም የርስ በርስ ውይይት
ከተደረገ በኋላ ፣ "ይኸ የኛ ጉዳይ ነው እንጂ ፣ የኢጣልያን መንግሥት
የሚያገባው ጉዳይ አይደለም " የሚል ቃል ከእቴጌይቱ ሲወረወር ፣
ንጉሡም ይኸንኑ ሲያጸድቁት ቃሉ ተተርጉሞ ተነገረው ።

ከዚህ ቀጥሎ ኮሎኔሉ አሳቡን ለማስቀበል የሚያነበንበውን ከንቱ
ንግግር በጽሞና ካዳመጡ በኋላ የሰጡት መልስ ፣ "መቼ ወዳገርህ
ትመለሳለህ?" የሚል ጥያቄ ሆነ ። እርሱም ፣ "ግርማዊነትዎ ሲፈቅዱ
እመለሳለሁ" አለ ። "መልካም ነው" ብለው ሁለቱንም ለዘለቄታ
አሰናበቷቸው ። የልጥ ማረፊያውን ጣቢያ በቤተ መንግሥትና በሌላም
የመሐንዲስነት ሥራው በንጉሡ ዘንድ ለጊዜው ሞገስ ያላጣው እን
ጂኔዮር ሉዊጂ ካፑቺ የሚባለው የኢጣልያ ተወላጅ ተረከበ ። ይኸም
መሐንዲስ ወደፊት እንደምናብራራው ዋና የኢጣልያ ሰላይ መሆኑ
ተገልጾበት ከመታሰር ደርሷል ። ኮሎኔል ፒያኖና ትራቬርሲም አሳባ
ቸውም ፣ ምኞታቸውም በፍጹም ከሽፎ በሐረር በኩል አድርገው እየተ
ናደዱ ወደ አገራቸው ተመለሱ ። ከሁለቱም የበለጠ ከእንኮበር ዠምሮ
በእንጦጦም ፣ በአዲስ አበባም ብዙ ዘመን በመቀመጥ እንደ አንቶኔሊ
"የንጉሡንም የመሳፍንቱንም ልብ አገኘሁ ፤ የኢጣልያን ይዞታ በኢ
ትዮጵያ ላይ አጠነከራለሁ" ብሎ ተማምኖ የነበረው ዶክተር ትራቬ
ርሲ ፣ አሁን ከንጉሠ ነገሥቱም ከእቴጌዪቱም ፣ ከቀሩትም ባለሥልጣኖች
ከፍ ያለ ተቃውሞ ገጥሞት ባዶ እጁን ወደ አገሩ በሚመለስበት ጊዜ
በንዴት እንደ ተሞላ ፣ "አዲስ አበባን ለቅቄ ስሔድ ምኒልክን ከነአገሩ
ከነሕዝቡ አቃጥዬው በሔድሁ " ብሎ መመኘቱን በኋላ በጻፈው መጽ
ሐፉ ያረጋግጣል ።

ትራቬርሲ እላይ እንዳልነው ፣ ብዙ ጊዜ ባጠገባቸው ተቀምጦና
ጠባያቸውን ተመራምሮ በተረዳው መጠን ፣ ንጉሡን እናታልላለን ባሉ
ቁጥር ፍጻሜውን ራሳቸው መታለላቸውን ፣ ካፄ ዮሐንስ ጋር ይዋጉልናል
ብለው በመኳንት መሣሪያ ሰጥተዋቸው ከተቀበሉ በኋላ ላስታርቃችሁ
ያሉትን ፣ ወደኋላው ተመልሶ እያመዛዘነ ሁኔታውን ከገመገመ በኋላ
ሚላኖ ላይ በ1931 ዓ.ም. ባሳተመው መጽሐፉ እንደዚህ ይላል ።

> “ . . . ውስጡን ብንስማማም ፥ ሰጦታም ብንሰጥ ፥ እርዳታም ብናደርግ የምኒልክ ሁኔታ ሁልጊዜ አጠራጣሪና ውልውል ያለበት ነው። በየደብዳቤው ልውውጥ ሁሉ በመካከል ሆኜ ላስታርቅ ፥ በክርስቲያኖች (ኢጣልያና ዐፄ ዮሐንስ) መካከል ደም አይፍሰስ ከማለት በቀር ከዚህ በላይ የሚጨመር ነገር የለም ። በእውነትም ይሁን በሐሰት የሰለሞን ተወላጅ የሚባሉት ራሳቸውን አደጋ ላይ ሳይጥሉ ምቹ ጊዜ ለማግኘት የሚጥሩ ብልህ ዲፕሎማት ናቸው . . . ”

ከዚሁ አያይዞ ፤ አሁን በመጨረሻ ዐፄ ምኒልክ ፤ የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ፤ በመሐላ መረብ ላይ የተስማሙትን ፥ አለያይተው ራሱ ትራቬርሲ ለዚህ መለያየት መሣሪያ ሆኖ ለኢጣልያ መንግሥት ምንም ነገር ሳያተርፍ ከኮሎኔል ፒያኖ ጋር ባዶ እጁን መመለሱ እየቆጠቆጠው የተታለለበትን ሁኔታ እንደዚህ ሲል እውነቱን ለመግለጽ ተገዷል ።

> እኛ የማኪያቬሊ* ተወላጆች የምንባለው የበለጠ በዚህ ንጉሥ ተታለልን ። ጥፋቱም የኛ የቂልነታችንና የእምነታችን ዋጋ ነው ። በፖለቲካ ውስጥ የአሠራር ዘዴ እንጂ የሕሊና ስሜት ዋጋ የለውም ። ያገር ጉዳይ አደጋ ላይ ባለበት ሰዓት ውለታንና ወዳጅነትን ማውራት ባዶ ቃል ነው ።[1]

ብሏል ። ሌላው ቤላቪታ የሚባለው የጦር መኰንን ደግሞ በበኩሉ ፥

> ብልህና የሚጨበጥ ነገር ብቻ የሚፈልጉት ምኒልክ አውሮፓውያን በትክክል አሳባቸውን ስለማይገልጹ ፥ እነርሱም የሚያደርጉት ሁሉ ለርሳቸው ጥቅም አለመሆኑን ስለተረዱት ፥ ማናቸውንም በጥርጣሬ እያመዛዘኑ ነገሩን ሁሉ ላልተወሰነ ጊዜ ያስተላልፉት ነበር ። መስኮቦቹም ፥ ፈረንሳዮቹም ፥ እንግሊዞቹም ፥ ጣልያኖቹም የሚሉትን በጥሩ መልክ ያዳምጣሉ ። የሚያደርጉት ግን ለርሳቸው የሚጠቅመውን ብቻ ነው . . . .[2]

ሲል ጽፏል ።

በዚህ አስተያየት ፥ ከትራቬርሲ የበለጠ ቤላቪታ የሚለው ትክክለኛ ነው ። ባለፈው ከምጥዋ ወረራ ዠምሮ እስከ ውጫሌ ውል ድረስ ኢጣልያኖች አንድም ቀን እውነተኛ የወረራ ምኞታቸውን ገልጸው አያውቁም ። ወዳጅ ነን ከማለትና ገጸ በረከት ከማቅረብ በቀር

---

* ኒኮላ ማኪያቬሊ የፈሬንሲ (ኢጣልያ) ተወላጅ ነው ። ፕሪንቺፔ (መስፍኑ) በሚባለው መጽሐፉ ውስጥ “ማናቸውንም አድርገህ (ወንጀልም ቢሆን) ጉዳይህን ፈጽም እንጂ በሃይማኖትና በሕሊና ወይም በይሉኝታ ሰበብ ዓላማህን አትተው” በማለት በፍልስፍና መልክ አቀርቦታል ።

1 Let Marefia - L. Traversi PP. 301—304

2 Adua - Belltavita, P 474.



እውነተኛ አሳባቸውን በትክክል ተናግረው አያውቁም ። ምጥዋን በወረሩ ጊዜ ፥ “በቱርክና ባፄ ዮሐንስ ፈቃድ ነው” ብለው በሐሰት ለሕዝቡ አስታወቁ ። የመሪዎቹንና የሕዝቡን ልብ ለማርጋት ሲሉ ፥ “ኢጣሊያ ወዳጅነትንና ንግድን ከማስፋፋት በቀር መሬት አትፈልግም” ብለው ማወጃቸውን ፥ በዚያው ሰዓት የሐባብንና የቦጎስን ሕዝብ ወይም ካፄ ዮሐንስ የሸፈተውን ሁሉ እያስታጠቁ ፥ መቀስቀሳቸውና ራሱ የውጫሌ ውል 17ኛው አንቀጽ በተንኰልና በማጭበርበር ከስምምነቱ ውል ላይ ሊሠፍር መቻሉ ባለፈው ተገልጿል ።

ስለዚህ ፥ ትራቬርሲ በአባባሉ ኢጣልያ በገርነትና በየዋህነት በምኒልክ ተታለለች ያለው ፍሬ ቢስ ነው ። በመዠመሪያ ላይ በኢጣልያ የተታለሉ ዐፄ ምኒልክ ናቸው ። ተንኰላቸውን በትክክል ከተረዱት በኋላ ግን ፥ እርሳቸውም ተንኰላቸውን በተንኰል በመመለስ በመጨረሻ አሸንፈዋቸዋል ቢባል ትክክለኛ መልስ ይመስለኛል ።

የሆነ ሆኖ የወዳጅነቱም ፥ የፖለቲካውም መስመር ስለ አልተሳካ፥ ገጸ በረከት መበተኑም ከንቱ ሆኖ ስለቀረ ፥ መሳፍንትን አባብሎና አታሎ ማሸፈቱም ስለ አልያዘ ፥ በሁለቱም ወገኖች መካከል ያለው አለመግባባት የሚወሰነው በጦርነት ብቻ መሆኑ ከዕለት ወደዕለት እየታየ መጣ ። ስለዚህም ሁለቱም ወደ ድል ጉዳና የሚመራቸውን የጦር መሣሪያ ያዘጋጁ ዠመር ።

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## የደጃች ባሕታ ሐጐስ ከኢጣልያኖቹ ጋር በኃይላ ተዋግተው መሞት

ራስ መንገሻ ፡ አዲስ አበባ ላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ታርቀው ፡ ከእቴጌ ጣይቱና በፊት ከማያውቁዋቸው መኳንንትና መሳፍንት ከነራስ ዳርጌ ጋር ተዋውቀው በክብርና በደስታ ከሰነበቱ በኋላ ፡ በሰኔ 7 ቀን 1886 ዓ. ም. ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው ፡ ወደ አገራቸው በሚጓዙበት ጊዜ በየሠፈሩበት መጥን (ሙብልና መጠጥ) እየታዘዘ ግብሩ ሳይጐድል እስከ ወሎ ደረሱ ። በወሎና በየጁ ሲያልፉም ፡ የራስ ሚካኤልና የራስ ወሌ ሰው እያስተናገደ በክብር እስከ ግዛታቸው እስከ ትግራይ አደረሰ ።

ምንም እንኳን ዝርዝሩ ተጽፎ ባይቆየን ፡ ከኢጣልያ ጋር ጦር ነት በምንም አኳኋን እንደማይቀር በመገመት ፡ ንጉሠ ነገሥቱና ራስ መንገሻ በግልጽም ፡ በስውርም የተወያዩበት ነገር እንደሚኖር አይጠረጠርም ፡፡ ከዚህ መካከል እንደኛው ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ክሪስፒ የኢትዮጵያን መሳፍንት ከምኒልክ ለመለያየት እንደ ተመኘው ዓይነት ፡ ራስ መንገሻና ዐፄ ምኒልክም በኢጣልያ ውስጥ ያሉትን መኳንንትና የባንዳ አለቆች በተቻለ መጠን ለማስከዳት አሳብ እንደሚኖራቸውና እንደ ተነጋገሩበት አይጠረጠርም ።

ስለዚህ ፡ ራስ መንገሻ ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ ፡ ክሪስፒ የላከበትንና እርሱም አምኖ የተቀበለውን የማስከዳት መመሪያ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በጀኔራል ባራቲዬሪ የበላይ መሪነት ፡ ዓድዋ ተቀማጭ የሆነው የኢጣልያ የፖለቲካ ወኪል ቴኔንቴ ሙላዚኒ ራስ መንገሻ አሉበት መቀሌ ድረስ እየመጣ ጠብ እርግፍ እያለ ልባቸውን ለማግኘት ደጅ ይጠና ነበር ። እርሳቸውም ለርሱ ፊት ሳይነሡ በበኩላቸው በነርሱ ውስጥ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ የሚያገለግሉትን እንደነ ደጃች ባሕታ ሐጐስ ያሉትን ውስጥ ለውስጥ እየተላላኩ ለማስከዳት ይጣጣሩ ጀመር ።

ባሁኑ ጊዜ ፡ ከኢጣልያኖች ጋር ካሉት ዓይነተኛ መኳንንት መካከል ደጃች ሐጐስ ተፈሪና ደጃች ባሕታ ሐጐስ ይገኛሉ ። ራስ መንገሻ ከኙሁ ከደጃች ባሕታ ሐጐስ ጋር ውስጥ ለውስጥ በተላላኩት

መሠረት ባሕታ ከኢጣልያኖች ጋር ሲዋጉ የሞቱበት ሁኔታ ከዚሀ እንደሚከተለው ነው ።

ደጃች ባሕታ ሐጐስ የአካለ ጉዛይ ተወላጅ ናቸው ። በአምባ ጓሮ የትልቁን የራስ አርአያን ልጅ አምባዬን ከገደሉና ከሸፈቱ ወዲህ በፊት ከደጃች ደብብም ፡ ከራስ መንገሻም እየተጣሉና እየተዋጉም በሐባብ በረሃ ይኖሩ ነበር ። በመጨረሻ ለኢጣልያኖቹ ገብተው የባንዶች አለቃ በመሆን ብዙ ጊዜ ዋና መቀመጫቸውን አከለ ጉዛይ አድርገው ለኢጣልያኖቹ ሲያገለግሉ ኖረዋል ። እዚያ በሚገኙት የላዛሪስት ሚስዮን አግባቢነት እርሳቸውም ፡ ቤተሰባቸውም ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ገብተዋል ። በማናቸውም አንድነታቸውን ከኢጣልያኖቹ ጋር ስለ መሠረቱ ፡ እነርሱም ከኢጣልያኖቹ በታች ከሐበሾች በላይ አድርገው በከበሬታ ይዘዋቸው ነበር ። ኢጣልያኖች በመገርመሪያው ጊዜ ደጃች ደብብንና ደጃች ባሕታን ባንድነት አስማምተው በሁለቱም መኳንንቶች ለመጠቀም እንደ ፈለጉ የታወቀ ነው ። ዳሩ ግን ደጃች ደብብ ከወንድማቸው ከደጃች አምባዬ ገዳይ ጋር መስማማት ስለማይሆንላቸው ፡ በዚህም ላይ ሁለቱም ከመረብ ወዲያ በተለይ የአከለ ጉዛይን ግዛት ስለሚፈልጉና በዚሁ ስለሚዋጉ ፡ ሁለቱን አስማምቶ ወደፊት ኢትዮጵያን ለመውረር ለወጠኑት አሳብ መሣሪያ ለማድረግ ለኢጣልያኖቹ አልተሳካላቸውም ።በመጨረሻም ደጃች ደብብ ከኢጣልያኖቹ ከሸፈቱና ዐፄ ዮሐንስም ከሞቱ በኋላ ፡ ኢጣልያኖቹ ደጃች ባሕታ ሐጐስን አቅፈው በማናቸውም እያስደሰቱ በርሳቸው መሪነት ካሉበት ቦታ ወደፊት እየገፉ ሰገነይቲንና አካባቢውኚ ሁሉ ያዙ ። በሰገነይቲም ቲኔንቲ ሳንጉይኔቲ የሚባለውን ሾመው የደጃች ባሕታም ግንኙነት ከዚሁ ከቲኔንቲው ጋር ሆኖ የርሳቸውም መደበኛ ሥፍራ ይኸው ሰገነይቲ ሆነ ።

ይሁን እንጂ ፡ በመጨረሻ ኢጣልያኖች እያደር አገር እየያዙ ፡ የአገር ተወላጅን እያዋረዱ ፡ ክብርንና የበላይነትን ለኢጣልያኖች ብቻ ሲሰጡ በመመልከት ልባቸው ከኢጣልያኖች ሸፈተ ። ባለፈ ሥራቸውም መጸጸት ዠመሩ ። ከዕለታት አንድ ቀን ፡ ኢጣልያኖቹ አንዱን ኢትዮጵያዊ አስተኝተው ሲገርፉት እዚያው ነበሩና በልባቸው እየተናደዱ ፡ "የሀገሬ ሰው እንደዚህ እየተዋረደ ከማየው ሞት ይሻለኝ ነበር" ብለው አጠገባቸው ለቆሙት ተናገሩ ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፡ ራስ መንገሻም ተስማምተው ኢጣልያን ለመውጋት የሚዘጋጁበት ጊዜ መሆኑን ያውቁ ስለነበረ ፡ ላዩን ከኢጣልያኖች ጋር ሆነው ውስጥ ውስጡን ከራስ መንገሻና በርሳቸው አማካይነት ካፄ ምኒልክ ጋር ይላላኩ ዠመር ። የዚህንም ምስጢር



ኢጣልያኖቹ በመጨረሻው ሰሙት ። ከዚያ ፡ "አዘንግተን ይዘን ወደ አሰብ ልከን እናስረዋለን" እያሉ ተመካከረው ወሰኑ ። ጣልያኖች የደጃች ባሕታ ሐጐስን አሳብ ከሰላዮቻቸው እንዳገኙት ሁሉ እንደዚሁም ባሕታ ሐጐስ የነሱን ምክር ባንድ ያገር ተወላጅ ካቶሊክ ወዳጃቸው በኩል ተገነዘቡት ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ፡ ኢጣልያኖቹ አላይ ስሙ የተጠቀሰውን ያገር ልማድና ባህል የሚያውቀውን ቲኔንቲ ሳንጉይኔቲ የሚባለውን በሰገነይቲ ሬዚዴንቲ (ምስለኔ) አድርገው በሹመት አስቀምጠው ነበር ። የርሱም አስተርጓሚ ስመ ጥሩው ገብረ እግዚአብሔር ነበሩ ።*

ስለዚህ ፡ ደጃች ባሕታ ሐጐስ ፡ ብዙ ጊዜ ካስተርጓሚው ከገብረ እግዚአብሔርና ከዚሁ ከምስለኔው ከቲኔንቲ ጋር የሥራና የወዳጅነት ግንኙነታቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ ፡ "ኢጣልያኖቹ ሳይቀድሙኝ ልቅደማቸው" ብለው እ. ኤ. አ. ታኅሣሥ 14 ቀን 1894 (ታኅሣሥ 5 ቀን 1887 ዓ.ም.) የተለመደ ጉብኝት አስመስለው ወንድማቸውን ደጃች ሠንጋልንና ባሻ ተሱ (ተስፉ) የሚባለውን ሹማቸውን አስከትለው ወደ ሳንጉይኔቲ መኖሪያ ቤት ሔደው የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጡ ፡ በኋላ መጠጥ ቀርቦ ጭውውት ተዠመረ ። ከዚያ ባሕታ ሐጐስና ሠንጋል ፡ የኢጣልያኑን ሹም ሳያስብ በድንገት ያዙትና ተናንቀው አስተኙት ። እሱም ለመንጠቅ ሲፍጨረጨር ባሕታ ሐጐስ ደረቱን ከመሬት ጋር በጉልበታቸው ይዘው እጆቹን በእጆቻቸው እንደጨበጡ ያኛው ከሥር ዐይኑን አፍጦ ፡ "ኢጣልያ ታላቅ ናትና እግዚአብሔር ሳይቀጣህ አይቀርም" ቢላቸው ፡ እርሳቸውም ከላይ ሆነው ፡ "ኢትዮጵያ ደግሞ ከኢጣልያ የበለጠች ታላቅ ናት" ብለው መለሱለት ። በዚህ ጊዜ ገብረ እግዚአብሔር በሩጫ ደርሰው ሳንጉይኔቲን ለማስጣል ወይም ለመገላገል ሞከረው ነበር ።ነገር ግን ወዲያው አስቀድሞ እንደ ታሰበው የደጃች ባሕታ ሐጐስ አሽከሮች ገብተው ምስለኔውን ከደጃች ባሕታ እጅ ተቀብለው ፡ ወደ ውጭ አውጥተው ፡ እጅና እግሩን አስረው ባንድ ቤት አስቀመጡት ።

በዚህ ጊዜ በደጃች ባሕታ ሐጐስና በገብረ እግዚአብሔር መካከል በሳንጉይኔቲ መታሰር የተነሣ ክርክር መነሣቱን ዶሎሊባር እንደዚህ ሲል ጽፎታል ።

---

* ገብረ እግዚአብሔር ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ በኢትዮጵያ አፍቃሪነት ተጠርጥረው እንደ ታሰሩ ከታሰሩበት ከናኩራ አምልጠው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ናቸው ። ብላታ ተብለው በፊት ላፄ ምኒልክ ቀጥሎም ወደ ሐረር ሔደው ከራስ መኰንን አማካሪዎች አንዱ ነበሩ ።

ገብረ እግዚአብሔር—ይህ የሠራኸው ሥራ መልካም አይደለም ።”

ደጃች ባሕታ ሐጐስ— . . . የኔን ሥራ አንተ ትነቅፈው እንደሆነ እንጂ ፤ ሥራዬስ ደንበኛ የፍርድና የበቀል ሥራ ነው ። ይኸም በኔ ብቻ ሳይወሰን አገሩ ሁሉ ባንድነት ተነሥቶ እነዚህን የሰው አገር ነጣቂዎች ካገራችንና ከምድራችን ሳናስወጣቸው አንቀርም ። እኛንም ራስ መንገሻና ራሳቸው ምኒልክ የአሣውርታና የደርቡሾች ተወላጅ ሁሉ ይደግፈናል ። ብረት የያዘው ያገር ተወላጅ አሽከር ከነመሣሪያው ሲዞር ኢጣልያኖችን አጥፍተን የአገራችን ጌታ እኛው እንሆናለን ። ስለዚህ አንተም ከኛው ጋር ሁን ፤ ከፈረንጆች ጋር በመኖር ባገኘኸው ሥልጣኔ ታገለግለናለህ ፤ እኔም ፈረስና የጦር መሣሪያ ጨምሬ የበታችሹም አደርግሀና ያለብኸውን ከፍተኛ ደረጃ ታገኛለህ ።

ገብረ እግዚአብሔር—“አላደርገውም እነዚህን መልካም ያደረጉልህን አንተ እንደ ከዳኻቸው እኔ አላደርገውም ። ካፒታኖ ቤቲኒ ለኔ እንዳባቴ ነበር ። ሌሎችም ሹማምንት ሁሉ ለኔ በጎ ያደረጉልኝ ወዳጆቼናቸውና አሁንም በሕይወቴ እስሁ ድረስ ቴኔንቲን (ሳንጉይኔቲን) አልለየውም ።”

ደጃች ባሕታ ሐጎስ—“እንግዲያውስ ከኛ ጋር መሆን ካልፈቀድህ በነገሩ አትግባ ፤ የዠመርነውን እኛው እንወጣዋለን ፤ አንተ ግን እርጊት የታወረች እናት በአሥመራ አለህና ከበቅሎዎቹ እንዲቱን ተቀምጠህ የምሰጥህን ገንዘብ ለናትህ ውሰድላትና ከርሷ ጋር እዚያው ተቀመጥ ።”

ገብረ እግዚአብሔር—“ቴኒንቲ ሳንጉይኔቴን ካልለቀቅኸው አልሔድም ።”

ደ. ባሕታ—“በፍጹም እርሱ አይለቀቅም ።”

ገብረ እግዚአብሔር—“እንግዲያውስ እኔም ከርሱ አልለይምና አብረህ እሰረኝ ፤ ብትገድለውም እኔ ልቀብረው እፈልጋለሁ ።”

ደ. ባሕታ — “ራስህ እንደ ብረት ጥጥር ነው ። ደግ ነው አስርሃለሁ ።”

ብሎ ባንድ ቤት ውስጥ ለብቻው አሰረው ፤ በማግሥቱ አስጠራና ጠጅ ከፊቱ አቅርቦ ፤ ቢጠይቀው “ትላንት የነገርኩህን አሁንስ አሳሰብህ በትምን” ብሎ “ትናንት ከመለስሁልህ የተለየ ሌላ መልስ የለኝም” ብለው ገብረ እግዚአብሔር በአሳባቸው መጽናታቸውን ጸሐፊው ያመለክታል ።

ከዚህ በኋላ ገብረ እግዚአብሔር ፣ እዚያው ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲ ዘንድ ይታሰሩ ተብለው እንደሔዱ ፣ የታሰረውም ጣልያን ባያቸው ጊዜ አንገታቸው ላይ ወድቆ ሳማቸው ። ከዚያም አብረው ሳሉ የጣልያኑን መታሰር አይተው ፣ “እንዴት ሳይሰርቅ እንደ ሌባ ይታሰራል” ብለው ከአሳሪዎቹ ጋር ተከራክረው በኋላም ወደ ደጃች ባሕታ ተላልከው (የእግር ብረት) እስራቱን አስቀሩለት ።



ደጃች ባሕታ ፣ በሰገነይቲ የኢጣልያ መንግሥት ያስቀመጠውን ምስለኔውን ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲን ከሦስት የስልክና የቴሌግራም ሠራተኞች ጋር አሰሩ ። ሰገነይቲን ከአሥመራና ከምጥዋ ጋር የሚያገናኘውን የስልክ መስመር በጣጠሱ ። በቶሎ ወደ ዓድዋ መጥተው ከራስ መንገሻ ጋር በመደባለቅ ፈንታ ከገብረ እግዚአብሔር ጋር እየተከራከሩ በሰገነይቲ ውለው አደሩ ።

በዚህ ጊዜ ፣ በኤርትራ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀኔራል ባራቲዬሪ በከረን ይገኝ ነበርና ፣ እ. ኤ. አ. ታኅሣሥ 15 ቀን 1894 ዓ. ም. “ከሰገነይቲ የሚያገናኘው የስልክ መስመር ተቋርጧል” ማለትን በሰማ ጊዜ ፣ “ ነገሩ የስሕተት ይሆን ወይስ ተበላሽቶ ይሆን” እያለ ከሹማምንቱ ጋር እየተነጋገረ ሲወያይ ፣ ሁሉም “ነገሩ ምን ይሆን ?” እያለ ሲጨነቅ ፣ በመጨረሻ የባሕታ መከዳትና የሳንጉይኔቲ መታሰር ወሬው በትክክል መጣለት ።

ከዚህ በኋላ ፣ አሥመራ የሚገኘው ማዦር ቶዜሊም ጦሩን ከአሥመራ ወደ መሕረባ ይዞ መጣ ። ይቺ መሕረባ የምትባል መንደር ለሰገነይቲ ቅርብ ነበረችና ቶዜሊ በዚች መንደር ገብቶ ከአሥመራ የሚያገናኘውን የስልክ መስመር አስቀጥሎ ሌላ ጦር እንዲጨመርለት እየተጠባበቀ ፣ ባንድ ወገን ደግሞ ተጨማሪው ጦር እስኪደርስለት ድረስ “ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲንና ሦስቱን የቴሌግራምና የስልክ ሠራተኞች መልስልኝና እንስማማ ” የሚል መላክተኛ ወደ ደጃች ባሕታ ላከ ። ይኸንም ማለቱ ተጨማሪው ጦር ከደረሰለት በኋላ ፣ በድንገት አዘንግቶ ደጃች ባሕታን ወግቶ ለመያዝ እንጂ ፣ በእውነቱ እስረኞቹን ቢልኩለት ለመስማማት ወይም ነገሩን በዚሁ አቁሞ ደጃዝማቹን በሰላም ለመተው አልነበረም ።

ደጃች ባሕታ በበኩላቸው ፣ ወደ ራስ መንገሻ እንዲደርሱላቸው ወይም ረዳት ጦር እንዲመጣላቸው እየተላላኩ ለርሱ አወላዋይ መልስ ሰጡ ። በመካከሉ የርሱን ጦር ይዞ መጧጋት በሰሙ ጊዜ ፣ እስረኞቹን ለራስ መንገሻ ለመላክ አስቀድመው እርሳቸው ሰገነይቲን ትተው ካያለበት የተሰበሰቡትን 1600 የሚያህል ጦራቸውን እንደያዙ በሰገነይቲ አቅራቢያ የሚገኘውን በሐላይ ያለውን የኢጣልያኖቹን ምሽግ ለመውጋትና ለመያዝ ጉዞ አደረጉ ። በዚያም እንደ ደረሱ ካፒቴን ካስቴላዚ ከነጭፍራው መሽጐ የተቀመጠበትን ቅጥር አስከበበው ፣ “ የያዝኸውን የጦር መሣሪያና ዕቃ አስረክበኝና በነጻነት ከነሰዎችህ እንድትሔድ ልፍቀድልህ ” ብለው ላኩበት ። ካፒቴኑም ከውጭ የሚጠብቀው የቶዜሊ እርዳታ እስኪደርስለት ድረስ አጠገቡ ባሉት በአገር ተወላጅና በውጭ አገር ሚሲዮናች ካቶሊኮች አማካይነት

“እርሱ ከነሰዌ ካልነካኝ እኔም መሣሪያውንና ዕቃውን አስረክበዋለሁ”
ብሎ ወደ ደጃች ባሕታ ላከ ። እርሳቸው ም እውነት የሚያስረክብ መስ
ሎአቸው ከሰዎቻቸው ውስጥ ደህና ደህናውን መርጠው ላኩለት ።
እነርሱም ወደ ቅጥሩ ውስጥ እንደገቡ ካፒቴኑ እጅ እጃቸውን እየያዘ
በሰንሰለት አሳሰራቸው ።

ከዚህ በኋላ ፣ የነርሱን አለመመለስና የካፒቴኑን ክዳት በተረዱት
ጊዜ ፣ ደጃች ባሕታ በቅጥሩ ላይ ተኩስ ዠምረው ከውስጥም ያሉት
መልሰው እየተኮሱ ደንበኛው ጦርነት ተዠመረ ።ከሰባት ሰዓት እስከ
ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በቀጠለው ተኵስ ባሕታ ሐጐስ አሸንፈው ቅጥሩን
ለመጣስና ለመግባት ሲያስቡ ፣ የተኵሱን ጩኸት ይሰማ የነበረው
ማዠር ቶዜሊ በሩጫ እየገሠገሠ ከነጦሩ በድንገት ደረሰና ደጃች ባሕታ
ሐጐስን ከኋላቸው እየተታኮሰ ይወጋቸው ዠመር ። ደጃች ባሕታም
ምንም እንኳን ከኋላ በማዠር ቶዜሊ ፣ ከፊታቸው በካፒቴን ካስቴላዚ
በሁለት ወገን በሁለት ጦር መካከል ቢሆኑም ፣ ባሉበት ሥፍራ ሆነው
በቆራጥነት እየተታኮሱ ከሰዎቻቸው ጋር 11 ሰው ገድለው 20 የሚሆ
ሆኑ አብዛኞቹን ያገር ተወላጆች ወታደሮች ከአቆሰሉ በኋላ በመትረ
የስ ሩምታ ተኩሰው ጣሉዋቸውና ሞቱ ።[1]

ምናልባት ፣ በኢጣልያኖች ዘንድ እንዳሰው የመሰለ የስልክና የመ
ገናኛ ድርጅትና ግንኙነት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ቢኖር ኖሮ
በወዲያ ማዠር ቶዜሊ በፍጥነት ለካፒቴን ካስቲላዚ እንደ ደረሰለት
ሁሉ ፣ ራስ መንገሻ ወይም አንድ የጦር መኮንናቸው ወደ ምሽጉ በግ
ሥጋዌ ይደርሱ ነበር ።አገርና ወገን ወዳድ የሆኑት ደጃች ባሕታ ሐጐ
ስም ፣ በዚህ ዓይነት አሳዛኝ ሞት አይሞቱም ነበር ። ከሁሉ የበለጠ
ደግሞ የሚያሳዝነው ፣ ባሕታ ሐጐስ ከሞቱ በኋላ ቶዜሊ ሬሳቸው እን
ዳይቀበር ከልክሎ ለቀሩት መቀጣጫ ወይም ምሳሌ ይሆናል ብሎ
ያደረገው እብሪት ጨርሶ የሚያበሳጭ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፣ ራስ መንገሻ ከአዲስ አበባ ተመልሰው በዓድ
ዋና በመቀሌ እየተዘዋዋሩ ፣ ከደጃች ባሕታም እየተላላኩ ግዛታቸውን
ሲያጸኑ ቆይተዋል ። ደጃች በሕታና ማዠር ቶዜሊ ሐላይ ምሽግ በሚ
ዋጉበት ጊዜ እርሳቸው እንትጮ ነበሩ ። ምንም እንኳን ውስጡን ከደ
ጃች ባሕታ ሐጐስ ጋር በደብዳቤና በመልእክት ንግግር ቢኖራቸውም ፣
ላዩን እስከ ኮዓቲትና ሰንዓፌ ጦርነት ድረስ ከኢጣልያኖች ጋር በጉ
ርብትና ለመኖር የወዳጅነት መልክ የማሳየት ፖለቲካ ነበራቸው ።

---

1 Douze ans en Abissinie - Paul de Lauribar, Chap. 26 PP. 338 - 394 -; Gli Italiani in Africa Orientale - A. Del Boca, PP. 521 - 529.



ካዲስ አበባ ሲነሡም ፣ እኛ እስክንመጣ ድረስ ተዘጋጅ እንጂ ጦርነት
አትዠምር የሚል ያፄ ምኒልክ ትእዛዝ ያለ ይመስላል ። ራሳቸውም
ባለፈው ዓመት ጣልያኖቹ መረብ ላይ በመስቀልና በወንጌል የተማ
ማሉትን መሐላ ስለ አፈረሱባቸው ፣ ቂማቸው ገና ያልበረደ ሳይሆን
አይቀርም ። ስለዚህም አዲስ አበባ ከንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተስማሙ ፣
ከደጃች ባሕታ ጋር ውስጡን እየተላላኩ አሁንም እንትጮ ላይ ሆነው
ጣልያኖቹን ለመውጋት ወታደርና የጦር መሣሪያ ማደራጀት ላይ
ይገኛሉ ። ያለዚያ ግን ፣ ከዚሁ ጦራቸው ከፍለው ለደጃች ባሕታ ልከው
ቢሆን ኖሮ የሐላይ አሸናፊነት ለርሳቸው ይሆን ነበር ። ደጃች ባሕታ
ንም ከነሰዋቸው ሲያገኙ ወደፊት ለሚያደርጉት ለኮዓቲት ጦርነት
ያግዙዋቸው ነበር ። ነገር ግን ፣ እላይ ከጠቀስነው ከመገናኛው ጉድ
ለት በቀር ሌላውን በዚያን ጊዜ የነበራቸውን ችግር ዛሬ ማወቅና መፍ
ረድ አይቻልም ። የራስ መንገሻን ሁኔታ በዚህ ዓይነት ስንመለከት
እንደዚሁም የቲኔንቲ ሳንጉይኔንቲንና ያስተርጓሚውን የብላታ ገብረ
እግዚአብሔርን ፍጻሜ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን ።

ሰገነይቲ ላይ ምስለኔው ሳንጉይኔቲና ሦስቱ ስልከኞች እንደታ
ሰሩ ፣ በደጃች ባሕታ ሐጐስ ትእዛዝ ሹማቸው ባሻ ተስፋ ማርያም
ዐርባ የሚሆኑ ጭፍሮችን እንደያዘ እስረኞቹን ይዞ ለራስ መንገሻ
ለመስጠት ወደ እንትጮ ይጓዝ ነበር ። በመንገድም ኢጣልያኖቹ ምንም
የልብስና የጫማ ፣ የራብና የጥም ችግር ቢደርስባቸውም ፣ ጣልያኖ
ቹን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑት ገብረ እግዚአብሔር በማናቸውም
ከባላገርም ፣ ከዘበኞቹም እየለመኑ ፈረንጆችን እያበሉና እያጠጡ ጉዟ
ቸውን ይቀጥሉ ነበር ። በጉዞውም ጊዜ ገብረ እግዚአብሔር ዘበኞ
ቹን አባብለው ወይም ሌሊት በተኙበት ጊዜ የሚወዱት ሳንጉይኔቲ
የሚያመልጥበትን መንገድ ሲፈልጉለት ነበር ይባላል ። ነገር ግን ፣ ከዕ
ለታት አንድ ቀን ጉዟቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ ፣ ገብረ እግዚአብሔር
የራስ መንገሻና የደጃች ባሕታ ሐጐስ ሰው መስለው ፣ የባላገር ወሬ
ሲጠያይቁ የሐላይን ጦርነት ፣ የደጃች ባሕታን መሞት እርግጠኛውን
ሰሙና ለሳንጉይኔቲ ነገሩት ። እርሱም ይኸንኑ በሰማ ጊዜ ፣ “ የባሕ
ታን ሞት ከሰማሁ በኋላ ከእንግዲህ ወዲያ እኔ ብሞት ግድ የለኝም።
ይልቅስ እናንተ በኔ ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስባችሁ በየአገራችሁ
ተመለሱ ” ብሎ እነ ገብረ እግዚአብሔርን መከራቸው ። ነገር ግን
አንድ ጊዜ ከሰገነይቲ ዠምሮ ከርሱ ላለመለየት የቆረጡበት ነገር
ነውና ፣ በዚሁ በዠመሩት ሃይማኖት ጸንተው ፣ ነጻው ሰውዬ ከእስረ
ኛው ጋር አብረው ጉዟቸውን ቀጥለው ፣ ማታ ከሰፈር ላይ ዘበኞቹን
ተሰብስቡልኝ ብለው እንደዚህ አሏቸው ። “እስረኞቹን ወስዳችሁ ለራስ
መንገሻ ለመስጠት ማሳባችሁ ሞኝነት ነው ። ምክንያቱም ራስ መንገሻ

የኢጣልያኖች ወዳጅ ስለሆኑ፣ ከናንተ የተቀበሉትን እስረኛ መል
ሰው የሚያስረክቡዋቸው ለኢጣልያኖቹ ነውና በዚህ እናንተን የሚያ
መሰግናችሁ የለም ። ይልቅስ እናንተው ራሳችሁ መልሳችሁ ለኢጣ
ልያ መንግሥት ባለሥልጣናች ብትሰጧቸው ምስጋናም ዋጋም ታገ
ኙበታላችሁ ።”

የዘበኞቹ አለቆች ይኸን ከሰሙ በኋላ፣ ምንም እንኳን ምክሩ በል
ባቸው ቢገባ ለጊዜው እሺ ሳይሉ እንደዚሁ ነገሩን እያመዛዘኑ ቆይ
ተው፣ ሌሊትም ብርድ ነበርና እሳት ነዶ እየሞቁ ተጋድመው ሳለ፣
የዘበኞቹ ሹም ባሻ ተስፉ ገብረ እግዚአብሔርን ለብቻቸው ጠርቶ
የኢጣልያ መንግሥት በኛ ላይ ክፉ እንዳያደርግብን ሳንጉይኔቲ በመ
ስቀልና በወንጌል ይማልልንና ወደ ሰገነይቲ ተመልሰን ከወገኖቹ ጋር
እንደባልቀው” ብሎ ነገራቸው ። እርሳቸውም ይኸንኑ ነግረው ምስ
ለኔው እሳቡን በደስታ ተቀብሎ ቃሉን በመሐላ ከሰጠ በኋላ፣ በመጡ
በት መንገድ በችግርና በድካም እንደገና ወደ ሰገነይቲ ተመልሰው፣
ሳንጉይኔቲ ከወገኖቹ ተደባልቆ በዚያው ዓመት በኮዓቲት ላይ በራስ
መንገሻና በኢጣልያኖች መካከል ጦርነት የተደረገ ዕለት ሲዋጋ ሞተ ።
ገብረ እግዚአብሔር ግን፣ እስከ ዓድዋ ጦርነት ድረስ ኢጣልያኖቹን
በአዲኳላም፣ በአሥመራም በአስተርጓሚነትና በምክር ሲያገለግሉ ኖሩ ።
የዓድዋ ድል ከተፈጸመ በኋላ፣ ሬሳ ለማስቀበር የቅድሚያ ፈቃድ ለመ
ጠየቅ ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ወዳጼ ምኒልክ ሰፈር የመጣ ጊዜ አብ
ረው ለአስተርጓሚነት መጥተዋል ።

በመጨረሻ ግን፣ እያደር ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ኢጣልያኖቹን የመ
ጥላት፣ አገራቸውን ኢትዮጵያን የመውደድ ስሜት ስላደረባቸውና ስለ
ታየባቸው ተጠርጥረው በናኩራ ደሴት ታሰሩ ። ከዚያም ከጓደኞቻቸው
ከአቶ ኢያሱ ዳንኤል ጋር ከናኩራ አምልጠው ወደ አዲስ አበባ መጥ
ተው ጥቂት ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ መካር ሆነው ከቆዩ በኋላ፣ ቀጥሎ
ወደ ሐረርጌ ተዛውረው በአማካሪነት ሲሠሩ ኖረው ሞቱ ።



## ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

### በኢትዮጵያ የተሠራጨው የኢጣሊያኖች የስለላ ሥራ

በኢጣልያ ንጉሡም፣ ባለሥልጣኖቹም፣ የጦር መኮንኖቹም ጭምር
እ.ኤ.አ. በ1860 ዓ.ም. የአገራቸውን አንድነት መመሥረታቸው ይታ
ወቃል ። በፊት በአውስትሪያ ውስጥ ሲገዙ፣ የጀርማኒክን ሥልጣኔ
በመውረስ ከኢጣልያንኛው ጋር አዋህደው የያዙ ነበሩ ። በኋላም ወደ
ወገኖቻቸው ወደ ኢጣልያ ገብተው ከአውስትሪያ ጋር በተደረገው
ጦርነት የተካፈሉ ስለ ነበሩባቸው፣ ባሁኑ ጊዜ ያገኙት የነጻነት ስሜትና
ያገር ፍቅር እያቃጠላቸው በማናቸውም ግንባር አገራቸውንና መንግ
ሥታቸውን የሚያገለግሉት ባዲስ ያገር መውደድ መንፈስና በጋለ
ስሜት ነው ። የጠፋ ዕቃ መልሶ ሲገኝ ከመጥፋቱ በፊት ከነበረው
ከባለቤትነት ስሜት የበለጠ ደስታ እንደሚሰማ፣ ኢጣልያኖችም ባሁኑ
ሰዓት ደስታቸው የዚያን ያህል ነው ። ሁኔታው እኛ ኢትዮጵያውያን
ነጻነታችን (1928—33 ዓ. ም.) ለአምስት ዓመታት ተጽዕኖ ሥር
ወድቆ በ1933 ዓ.ም. ከዚህ በተላቀቅንበት ጊዜ ከነበረን የጋለ
የሥራ ናፍቆትና ያገልግሎት ስሜት ጋር የሚመሳሰል ነው ።

ስለዚህ፣ አዲስ የተቋቋመው የኢጣልያ መንግሥት፣ በኢትዮጵያ
ላይ መስፋፋትን መሠረታዊ ዓላማ አድርጎ ሲነሣ ከሁሉ አስቀድሞ
በአገሪቱ በየአውራጃው ባሉት መሳፍንት ዘንድ፣ ባገር ጐብኝነትና
በንግድ እያስመሰለ ሰላዮችን ያስቀምጥ ነበር ። ለዚህም ሥራ አብዛ
ኛውን ጊዜ የሚመረጡት የሕክምና፣ የመሐንዲስነት ወይም ያናጢ
ነት ዕውቀት ያላቸው ነበሩ ። ኢትዮጵያ እንደ ሌላው የአፍሪካ አገር
ዘመናዊ ሥልጣኔ ያልገባባት፣ ሕዝቧ በበሽታ የሚሠቃይና መታከምን
የሚፈልግ፣ በሕንፃ ቤት መኖርንና ወንዝን በድልድይ መሻገርን
የሚፈልግ ነበር ። ነገር ግን፣ አገሪቷ ራሷ መሥራት የማትችል ስለሆነች
ሰላዮች በሕክምና ወይም በመሐንዲስነታቸው ሰበብ ወደ ነገሥታቱና
ወደ መሳፍንቱ ከተጠጉ በኋላ፣ ወዳጅነት ቋጥረው ወጭ ገቢና ባለ
ሟል በመሆን የተላኩበትን የስለላ ሥራ ለማከናወን እንደቻሉ ቀደም
ሲል ተወስቷል ።

እነዚህም፣ ዐፄ ዮሐንስ ዘንድ የነበረው የመቀሌን ቤተ መንግሥት
የሠራው ናሬቲ ገሶፔ የተባለው አናጢ፣ ወደ ዐፄ ምኒልክ የተላኩት

ሊዎፖልድ ትራቬርሲና ቬንቼንሶ ራጋሲ ሐኪሞች ፣ አውጉስቶ ሳልም
ቤኒና ሊዊጂ ካፑቺ መሐንዲሶች ናቸው ። በተለይ ራስ መኰንንን ካፄ
ምኒልክ ለማስከዳት የተላከው ማዦር ቼዛሬ ኔራሲኒ ሐኪም ሲሆን
ፒዬትሮ ፌልተር ነጋዴ ነው ። እንዲሁም ለራስ መንገሻ የተላከው
አንጀሎ ደ ማርቲኖ ሐኪም ነው ። ሐኪም ወይም መሐንዲስ ባይሆ
ንም ፣ አገሌ የእገሌን አውራጃ ባህልና ቋንቋ ያውቃል ፣ ከዚያ ወረዳ
መስፍን ወይም መኰንን ጋር ተወዳጅቷል ሲባል ወደዚያ አገር
ይመደባል ። ለምሳሌ ፣ ካፒቴን ሳልቫቶሪ ፒርሲኮ የዐረብኛ ቋንቋና የእስ
ላሞችን ባህል ያውቃል ተብሎ አውሳ ወደ መሐመድ አንፋሪ ዘንድ
ተልኮ ነበር ። እርሱም ከአውሳ ወደ ዋጅራት ወደ ራያና ወደ አዘቦ
እየተመላለሰ በራያና በአዘቦዎች ዘንድ የተከበረውን ሼክ ጦልሀ ቤን
ጃፋርን ፣ ባንድ ወገን መሐመድ አንፋሪን ፣ በሌላው ወገን ከወሎ ገዥ
ከራስ ሚካኤል ጋር በማዛመድ እስላም ነክ የሆነው አገርና ሕዝብ
ባንድነት ባፄ ምኒልክ መንግሥት ላይ እንዲነሣ ከኀደኛው ከቴኔንቴ
ጂያኒኒ ጋር ሆነው በገንዘብ ከማባበል ጋር በትጋት ይሠሩ ነበር ።
መሣሪያቸው ያደረጉት ሼክ አብዱራህማን ቤን ዩሱፍ የሚባለውን ለዚህ
ተልዕኳቸውም ነው ። ይህ ሰው በመዠመሪያ ያፄ ምኒልክ አሽከርና
ባለሟል ሆኖ በመላላክ ያገለግላቸው ነበር ። በዚህም የራሳንና የጦጦ
ሴን ፣ የጥሙጋን ወረዳዎች ሰጥተውት ሲያስተዳድር ሳለ ፣ በመካከሉ
ከነዚሁ ከኢጣልያ ወኪሎች ከነፒርሲኮና አዲስ አበባ ከሚቀመጠው
ከአንቶኔሊ ጋር ተገናኝቶ ከአውሳ ወደ አዲስ አበባ እየተመላለሰ
እነርሱን በመምራት ተላምዶ ነበር ። እርሱም የመሐመድ አንፋሪን
ልጅ ስለአገባ ፣ በርሱ አማካይነት ኢጣልያኖቹ ከመሐመድ አንፋሪ ጋር
በጣም ተዛምደው ለሁለቱም ገንዘብም መሣሪያም ያፈሱላቸው ዠመር።
ሁለቱም ላፄ ምኒልክ ታማኝነታቸውን እያደር ከደው ለኢጣልያ መን
ግሥት መሣሪያ ሆኑ ። ዋናው ባላባት መሐመድ አንፋሪ በያመቱ
3,000 በኋላም 4.000 ጥሬ ብር ሲቀበል ፣ አብዱራህማን ትጉኅ ሠራ
ተኛ ስለሆነላቸው የወር ቀለቡ በመዠመሪያ 90 ብር የነበረው ፣ በኋላ
አነሰኝ ብሎ ተከራክሮ ወደ 200 ከፍ አስደረገ ። ቀለቡም ከፍ ባለ
መጠን የርሱም የአማቹም አገልግሎት እያደገ ሔደ ። በተለይ በዚያን
ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ይኽን ያህል ቀለብ እየሰጡ ፣ ማስተደደር የመንግ
ሥታቸው የኢኮኖሚ አቅም ስለማይፈቅድ ከቀለቡ ብዛት ጋር በኢጣ
ልያኖቹ ተንኮል አብዱራህማን ፈጽሞ ከዳ ። መሐመድ አንፋሪንም
አስከዳ ።

በዚህ ዓይነት ፣ ከፕሮፓጋንዳው ስልትና ዘዴ ጐን የኢጣልያ መን
ግሥት በሀብቱ ጭምር ይጠቀም ነበር ማለት ነው ። ባፄ ምኒልክ ዘንድ



የአብዱራህማን ቤን ዩሱፍ ክዳትና አድራጎቱ በትክክል ሲታወቅ
ከሹመቱ በይፋ ተሽሮ የርሱን የወረዳ ግዛቶች የኤፍራታው ገዥ
ደጃች ወልዴ አሻግሬና ደጃች መኰሪያ ገርማሜ ተካፈሉት ።[1]

ሼክ ጦልሀ የሚባለው ደግሞ ፣ የተወለደው በዶዶታ (ወረባቦ)
ውስጥ ነው ። በራያና በአዘቦ ፣ በወሎም የታወቀ የሃይማኖት መሪ
ነው ። ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፣ ዐፄ ዮሐንስ የወሎንና የራያን
እስላሞች በክርስትና እንዲጠመቁ ባዘዙ ጊዜ እምቢ ብሎ ሌሎቹንም
የሃይማኖት ወገኖቹን ይዞ ፣ ብዙ ጊዜ ካፄ ዮሐንስ ጋር ተዋግቶ በመ
ጨረሻ ወደ ሱዳን ሔዶ ከደርቡሾች ጋር በማበር በሣር ውሀ ከንጉሥ
ተክለ ሃይማኖት ፣ በመተማ ካፄ ዮሐንስ ጋር ተዋግቷል ። ሌሎቹንም
እየመራ አዋግቷል ።

ከዐፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ፣ ይኸው ጦልሀ ወደ አገሩ ተመልሶ ከአብ
ዱራህማን ጋር በመተባበር ለኢጣልያ መንግሥት መሣሪያ ሆኖ የራ
ያንና የአዘቦን አሮሞዎችና አፋሮችን እያስተባበረ ክርስቲያኖቹን እያስ
ጠቃ ከራስ ወሌም ጦር ጋር በየጊዜ ተዋግቷል ። የኢትዮጵያና የኢ
ጣልያ ጠብ እየከረረ ሲሔድ በኢጣልያኖቹ ውስጥ ጦሩን አዘጋጅቶ
በአላጌ ሲዋጋ ወደፊት እንመለከታለን ። ከዓድዋ በኋላ በሼክ ዑመር
ኑሬ አማካይነት አዲስ አበባ መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት ተቀ
በለ ። ቢሆንም ወዳገሩ በመመለስ ፋንታ በአንኮበሩ አዛዥ ወልደ
ጻድቅ ውስጥ የጨኖን ግዛት ተቀብሎ ተቀምጦ በኋላም ከልጅ ኢያሱ
ጋር ባለሟልነት ወጥኖ ነበር ። ልጅ ኢያሱ በወደቁበትም ጊዜ ደግሞ
መልሶ እስራት አግኝቶታል ።[2]

በዚሁ ዓይነት ፣ ከኢጣልያ መንግሥት ውስጡን ለስብከት ላዩን
ለሥራ አስመስለው ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተልከው የነበሩት
ጐስታቮ ቢያንኪና በሸዋ የታወቀው አውግስቶ ሳሊምቤኒ ናቸው።
ጐስታቮ ቢያንኪ ከፔሌግሪኖ ማቲውች ጋር ወዳፄ ዮሐንስ ተልኮ
መጥቶ የነበረ መሆኑን ፣ በኋላም ከመቀሌ የደንከልን በረሀ አቋርጬ
ልሔድ ብሎ በበረሀ በደንከሌዎች እጅ ሕይወቱ አልፏል ። ከመሞቱ
በፊት በ1867 ዓ . ም. ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ከኢጣልያ ንጉሥ
ኒሻንና ልዩ ልዩ ገጸ በረከት ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይዞ በመም
ጣት ፣ "አባይ ላይም አንድ ድልድይ እንሠራልዎታለን" ብሎ በማስደ
ሰት መልካም ግንኙነት ፈጥሮ ነበር ።

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ 61.
Crispi e Menelich Nel.Diario del Conte Salimbeni, PP. 34, 54 - Italia ed Etiopia, PP. 159 - 160

2 Italia ed Etiopia . . PP. 468 - 469.

ኢጣልያኖቹ ፣ መሳፍንቱን የሚሸንግሉበት ዋናው ስጦታ ስለሆነ ወደኋላ ተመልሰን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተላከውን ኒሻንና ገጸ በረከት ስንመለከት ሌሎቹም እንደ ደረጃቸው የሚላክላቸው መሆኑን እንገነዘባለን ። ከስጦታው ጋርም መስፍኑ የሚመኘውን ፍላጐት እንደሚያሟሉ ያሳያሉ ። ለምሳሌ ፣ በአባይ ወንዝ ላይ ድልድይ መዘርጋት ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታላቅ ምኞት ስለሆነ ፣ ሳሊምቤኒ ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተጠጋው የአባይን ድልድይ እሠራለሁ የሚል የሚያጓጓ የተስፋ ቃል ሰጥቶ ነበር ።

ንጉሥ ተክለ ሃማኖት ፣ ኒሻኑና ገጸ በረከቱ ከደረሳቸው በኋላ ለኢጣልያ ንጉሥ የላኩት ደብዳቤ የሁሉንም ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው ያብራራል ።

> ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ከኢጣልያ ንጉሥ ፣ የተላከ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት . . . . የእርስዎ ወረቀት ደረሰኝ 5 የእርስዎ ሽልማት የርስዎ በረከት በጐስጣቦ ቢያንኪ . . . እጅ ደረሰኝ . . . እኔም ከርሱ ጋር ሁሉንም ተጫወትሁ ፤ ሁሉንም አደረግሁ ፤ እርስዎ እንደ ጻፉልኝ . . . የእርስዎ ወዳጅነትዎና ፍቅርዎ ለኔ እጅግ መልካም ነውና እጅግ ደስ አለኝ አቶ ጐስጣቦ ቢያንኪ የኢጣልያ ዘውድ መስቀል ሽልማት ባንገቴ አደረገልኝ። የርስዎ ሁለት የዝሆን ጠበንጆች ደግሞ ሁለት አፍ ሁለት ጠበንጆች እሊህ አራቱን የርስዎ ጠበንጆች ። ደግሞ አንድ የርስዎን የአልማዝ ቀለበት የእርስዎን መነጥር የርስዎን ቀይ ሐር ጥላ የርስዎን አንድ ጊዜ የምትተኰስ ሽጉጥ ወርቅ ቅብ የጐራዴ መታጠቂያ ሁለት መስቀል የአልማዝ ዓይነት ተቀበልሁ አንድ ሰኔ አንድ ሰምሽቴ ይኸን ሁሉ የሰደዱልኝን በጐስጣቦ ቢያንኪ እጅ ተቀበልሁ ። ለዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ. . . እንግዲህ አንድ ድልድይ እንሠራለን አባይ ላይ . . . እኔም አሁን ስለርስዎ በረከት እንዳላሰናዳ ቀኑ አጠረብኝ የኔ ሀገር እንደርስዎ ሀገር አይደለም ሁሉ ቶሎ ቶሎ አይገኝበትም ። አቶ ቢያንኪ ሲመለስ በረከቱን አሰናድቼ እቆያለሁ የኔ በረከት ለርስዎ ትንሽ ነገር ነው ። . . . አቶ ቢያንኪ በጅሮንድን ሠራተኛውን መሣሪያውን ስለ አመጣልኝ ፣ እኔም አባይ ከድልድዩ አጠገብ አንድ ሀገር እሰጣለሁ ብያለሁ ። ከሸዋ ልጥ ማረፊያ የሚበልጥ ሀገር ነው . . . የፈቀዱልኝም እንደሆነ እኔም የድልድዩን ሥፍራ ድልድዩንም ወምበርቶ አዳል እሰኘዋለሁ የድልድዩን ነገር ካቶ ቢያንኪ ጋር ስንነጋገር የኔ ስም አዳል ነበረ ። . . . ተጽሕፈ በደብረ ማርቆስ ከተማ ኅዳር 13 ቀን 1876 ዓ.ም. በዘመነ ዮሐንስ በዕለተ ሐሙስ ።[1]

ከመጀመሪያው ላይ በኢጣልያ ወዳጅነት ዮሐንስ ፣ ምኒልክ ፣ ተክለ ሃይማኖትና ሌሎችም መሳፍንትና መኳንንት እንደምን እንደ

1 Documenti Amharina - I GNAZIO Guidi - Roma 1891.



ተቃትሉ ይህ ደብዳቤ ያስረዳል ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በኒሻኑና በገጸ በረከቱ ከመደሰታቸው በቀር ፣ የድልድዩ ሥራ በጣም ያማልላቸው ስለነበር ፣ ድልድዩ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ የድልድዩ መጠሪያ ስም ኡምቤርቶ አዳል ተብሎ በቀድሞ ስማቸውና በኢጣልያኖቹ ንጉሥ ስም እንዲሠየም አስበው ነበር ። ነገር ግን ፣ በኢጣልያኖቹ በኩል የድልድዩ ሥራ ለመግቢያ እንዲረዳ ምክንያት ነው እንጂ ፤ ሠርቶ ጨርሶ ለማስረከብና በዚህ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት እንዲጠቀም አይደለም ። ስለዚህ ፤ ምክንያት እየፈጠሩ በወሬ ከማራዘም በቀር ዐሥር ዓመት ሙሉ ሥራው አልተጀመረም ።

ብዙ ጊዜ ፣ ምክንያት በመፍጠር እንደ ሳሊምቤኒ ፣ እንደ ኔራሲኒና እንደ አንቶኔሊ ያሉት ባንድ ስፍራ በአዲስ አበባ ተቀምጠው በመሥራት ፈንታ ወደ ትግሬ ፣ ወደ ጎጃም ፣ ወደ ወሎና ወደ ሐረርጌ እየተዘዋወሩ ወሬ በመልቀም ፤ በፊተኛው ጊዜ ሳሊምቤኒ ካፄ ዮሐንስ፣ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ካፄ ምኒልክ ጋር ፣ ኔራሲኒ ከራስ መንገሻና ከራስ መኰንን ጋር ሠርተዋል ። ስለዚህ አሁንም ካፒቴን ፒርሲኮ፣ መሐመድ አንፋሪንና ሼክ አብዱራህማንን በቃል ስብከትና ገንዘብ በመበተን ስበዋቸው ፣ የኢትዮጵያን አቅዋም ለማድከም ከመጣር ላይ ናቸው ።

ካገር ተወላጅ ውስጥ በስውር እየመለ መሉ ለስለላ ሥራ ይቀጥራሉ ። መኳንንቱን ፣ ባለሟሎቹን ፣ አስተርጓሚዎቹን ፣ በአዲስ አበባ የሚቀመጡትንና በሥራ ምክንያት ወደ ንጉሡ ቀረብ የሚሉትን አርመኖቹንና ግሪኮቹን በቀጥታ ሰላይ ባያደርጓቸውም ፣ በስጦታና በግብዣ እየሳቡ ወዳጅ በማድረግ ወሬ ያጠራቅሙ ነበር ። በተለይ ደግሞ ፣ የንጉሡ ነገሥቱን ዋና አማካሪዎች የስዊሱን ተወላጅ ሙሴ ኢልግንና መሰሎቹን ለኢጣልያ መንግሥት መሣሪያ እንዲሆኑ በግብዣና በዘዴ ያባበሏቸው እንደነበር የሚታወስ ነው ። አሁንም ይኸንኑ ተግባራቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ከመቀጠል አላረፉም ።

ዶክተር ሊዎፖልድ ትራቬርሲ ፣ እ.ኤ.አ. በኅዳር 12 ቀን 1890 ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔዶ በደጅ ጥናት ሲጠባበቅ ለዋናው አስተርጓሚ ለግራዝማች ዮሴፍ አንድ መቶ ብር ጉቦ መስጠቱን ፣ ግራዝማቹም ስጦታውን በቸልታ መቀበላቸውን ፣ በተቀበሉትም ጊዜ ፣ "ባይቸግረኝ ኖሮ አልቀበልም ነበር ። እንዲያውም ለጣልያኖች ተገዝተሀል ተብዬ ታምቻለሁ" ብለው እንዳዋዩት ያወሳል ። በሌላ ቦታ ደግሞ "ለሌላው አስተርጓሚ ላቶ ገብርኤል ወደኔ ለመሳብ ስል የጠየቀኝን 300 ብር በሦስት ዓመት ውስጥ በሚመለስ ብድር ስም ሰጠሁት ።

በዚሁም እጋጣሚ ስለወሰኑ ጉዳይ ላነጋግረው ቻልሁ . . .”[1] ይላል ።
የመስኮቡ ተወላጅ ሙሴ ኒኮላ ሌዎንቴፍ ያፄ ምኒልክ ባለሟል ሆኖ
የደጃዝማችነት ማዕረግና ግዛትም ተቀብሎ የነበረው ለመልከት ወደ
መስኮብ አገር ሔዶ ሳለ ፤ ከኢጣልያ አምባሳደር ከኮንት ማፌይ ጋር
ንግግር ባደረገበት ጊዜ ፤ “ከምኒልክ ጋር በምናደርገው የሰላም ንግግር
እርዳንና 2 ሚሊዮን ሊሬ እንሰጥሀ” ቢሉት ፤ ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር
ሲል “እምቢ” ማለቱን ገልጾለት ፤ አምባሳደሩም ይኸንኑ ለውጭ
ጉዳይ ሚኒስትሩ ገልጿል ።[2]

በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ ምክንያት ፤ እንደዚሁም የኤ
ርትራ የግዛት ወሰናችን እስከ መረብ ይድረስ በማለት ጠቡ እየከረረ
በሔደበት 1882—87 ዓ.ም. ጊዜ ውስጥ ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን መኳ
ንንትና መሳፍንት ፤ ከንጉሠ ነገሥቱ ለመለየትና እርስ በርሱ ለማዋ
ጋት ያላደረጉት ጥረት የለም ። ራስ መንገሻን ከራስ አሉላ ጋር
ካፄ ምኒልክ አናጥሎ የማዋጋቱ ጉዳይ ከከሸፈ በኋላ ፤ ንጉሠ ነገሥ
ቱም 17ኛውን አንቀጽና የመረብን ወሰን አልቀበልም ካሉ ወዲህ
ክሪስፒ ለባራቲዬሪ በላከው ምስጢራዊ መመሪያ መሠረት ፤ ሁሉንም
መሳፍንት በተለይ ደግሞ ፤ ራስ መንገሻንና ራስ መኰንንን በዐፄ ምኒልክ
ላይ ለማስነሣት ልዩ ልዩ ሙከራ ተደረገ ። ራስ መንገሻ ከአዲስ አበባ
ወደ መቀሌ ተመልሰው በግዛታቸው ተደላድለው እንደ ተቀመጡ
ዓድዋ ያለው የኢጣልያ ወኪል ከጄኔራል ባራቲዬሪ አዲስ መመሪያ
ተቀብሎ እሳቸው አሉበት መቀሌ ድረስ እየተመላለሰ ፤ ያለፈው
ሁኔታ እንዲረሳና አዲስ የወዳጅነት ግንኙነት እንዲፈጠር በልዩ ልዩ
ዘዴ ሞከረ ። ነገር ግን ፤ ባለፈው መሐላ አፍርሰው ያታለሉዋቸውን
ስለ አልዘነጉት ራስ መንገሻ አሁን የቀረበውን የማታለል ወዳጅነት
በምንም ዓይነት ተቀብለው በምኒልክ ላይ ለመሸፈት መንገድ አል
ሰጡም ።

በሐረር በኩል ራስ መኰንንን ለማስከዳት የተመደቡት ከዚህ
በፊት ካፄ ዮሐንስ ጋር ተዋውቆ የነበረውና በኋላም ከጓደኛው ከዶክ
ተር ደ ማርቲኖ ጋር ሆኖ ፤ ራስ መንገሻንና ጄኔራል ጋንዶልፊን መረብ
ላይ አገናኝቶ ባፄ ምኒልክ ላይ ያስማማው ማዦር ቺዛሬ ኔራሲኒና
በንግድ ስም የተቀመጠው ፒዬትሮ ፌል፡ር ናቸው ። ሁለቱም በወ
ዳጅነት መልክ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት በማቅረብ ወደ ራስ መኰንን
እየተጠጉ ፤ በጥሩ አነጋገር እያታለሉ ፤ ጠላትነቱ የታወቀውን

1 La Prima Guerra d' Africa - Pal. Crispi, PP. 369 - 370; Crispi e Menelich Nel Diario . . ,PP. 130, 210

2 La Prima Guerra d' Africa . . P. 370



የኢጣልያን ወዳጅነት እየሰበኩ ራስ መኰንንን ካፄ ምኒልክ ለመለየት
ከፍ ያለ ጥረት አድርገዋል ። የማባበያው መሣሪያም ከገጸ በረከት ፤
ከጥሩ ጥሩ የእጅ ጠመንጃና የወገብ ሽጉጥ ስጦታ አልፈው ወደ መጨ
ረሻው ግድም ፤ “እርስዎም ፤ እንዳፄ ምኒልክ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ
ስለሆኑ ከምኒልክ ተለይተው በሐረር ንጉሥ ቢባሉ ፤ የኢጣልያ መን
ግሥት ማናቸውንም እርዳታ ያደርግልዎታል” የሚል ነበር ።

ለዚህም የነበረው ማባበያ ወይም ማስፈራሪያ ፤ የኢጣልያ መንግ
ሥት የዘይላን ወደብ ከእንግሊዝ መንግሥት አስፈቅዶ በዚህ ወደብና
በጅልዴሳ በኩል የኢጣልያን ጦር ሐረር አምጥቶ በወዳጅነት ጊዜ
ለመርዳት ፤ በጠብም ጊዜ ለማጥቃት እንደሚችሉ በመግለጽ ነበር ።
ኃያሉ የእንግሊዝ መንግሥት በፍጹም ወዳጃቸው ስለሆነ ፤ በዘይላ
ወደብ እንደ ልባቸው ለመጠቀም እንደሚችሉ እያጭበረበሩ ራስ መኰ
ንንን ለማግባባት ይሞክሩ ነበር ። ካሁኑ ጊዜ ላይ ሆነን ስንመለከተው
ኢጣልያኖቹ ለማጭበርበር በጣም የረዳቸው ፤ በዚያ ዘመን ኢትዮ
ጵያ ከዓለም መንግሥታት ጋር የነበራት የግንኙነት ደካማነት መሆኑ
አይጠረጠርም ። በሮማ ፤ በበርሊን ፤ በፓሪስ ይልቁንም በሎንዶን
የነዚህን አገሮች ትክክለኛውን የፖለቲካና የወታደር አቋም የኢጣ
ልያንንም ደካማ ጐን የሚገልጽ ወኪል ስለሌላት ፤ የተሠራጩት የኢ
ጣልያ ሰላዮችና ባለሥልጣኖቹ እንደ ልባቸው በመሳፍንቱና በመ
ኳንንቱ ፊት የሆነ ያልሆነውን እየቀባጠሩ የማይችሉትን እንደሚችሉ
እያደረጉ ያወሩ ነበር ።

የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባሮን ብላን ፤ ለባራቲዬሪ እ.ኤ.
አ. ጥር 4 ቀን 1895 ዓ.ም. ባደረገው ቴሌግራም ፤ “ወደ ሐረር የሚያ
ስገባውን የዘይላን በር እንድንጠቀምበት እንግሊዞች ፈቅደዋል ። ነገር
ግን እስካሁን ወረራውን ያልፈጸምነው መኰንንን በማክበር መሆኑን
እንዲያውቅ አድርግ ። ይኸን ወረራ የምንፈጽመው ጠላታችን መሆ
ኑን በግልጽ ያወቅን ዕለት ብቻ ነው ። ጊዜው ቁርጠኛ ስለሆነ ስለ
መጪው ዕድሉ ማሰብ አለበት ። አንድ ቀን ሊሞት ከሚችለው ከም
ኒልክና ዘለዓለማዊና ኃያል ከሆነችው ከኢጣልያ መምረጥ አለበት”[1]
ሲል አስተላልፎለታል ።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደ ክሪስፒ ፕላን ፤ የኢትዮጵያውያ
ንን ጠባይ ፤ የኢትዮጵያንም መኳንንት ውስጣዊ ሁኔታ ከጭፍሮቹ
በሚላከለት ራፖር ላይ ከጨረፍታ ንባብ በቀር በትክክል የሚያ
ውቀው አይመስልም ። ኢትዮጵያውያንም ሞራል የሌላቸው በቀላል

1 Memoire d' Afrique - O. Baratieri, P. 358.

ልብክትና ተስፋ አቋማቸውን የሚለዋዉጡ ይመስለዋል ። የዘለዓለማዊት ኢጣልያን መኖር ሲያምን ፣ በራስ መኰንን ዘንድም የዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ ህልውና እንደአለ ፈጽሞ ከአእምሮው ፍቆታል ማለት ነው ። እንደ ክሪስፒ ግምት ራስ መኰንን ላዬ ምኒልክ ምን እንደ ሆኑ ፣ እንደምን እንዳሳደጓቸው በሁለቱ መካከል ያለውን ልባዊ የአባትና የልጅ ፍቅር እያውቀውም ። ይኸን የመሳሰለውን በመስማትና ሌላውንም የኢጣልያኖች ሁኔታ እየተመለከቱ በመገረም ከዕለታት አንድ ቀን ራስ መኰንን ፣ "እነዚህ ጣልያኖች ሞኞች ናቸውን ኧረ በል አፈወርቅ አንተ የነበርህበት አገር (ኢጣልያ) እንደ ኔራሲኒ ያለ ደላጎ (ሞኝ) ያበቅላልን"[1] ብለው ነጋድራስ አፈወርቅን ጠየቁ ይባላል ።

እነዚህ ሁሉ የስለላ ወኪሎች ያጠናቀሩትን ፣ ለነርሱ በተገዛ ያገር ተወላጅና የውጭ አገር ሰው እጅ አንዳንድ ጊዜ በግልጽ ጽሑፍ ሌላ ጊዜ በምስጢር ወይም በተስማሙበት የቁጥር ቃል ፣ ግማሾቹ አሥመራ ለነበረው ለጄኔራል ባራቲዬሪ ሲያስተላልፉ ፣ እንደነ ኔራሲኒና እንደነ አንቶኔሊ ያሉት ደግሞ ፣ በቀጥታ ወደ ሮማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያስተላልፉ ነበር ። በኤርትራ ሆነው ወሬ ከየሰላዮቻቸው እያጠራቀሙ ለዋንኛው ለጄኔራል ባራቲዬሪ ከሚያቀርቡት የጦር መኰንኖች ውስጥ ቲኔንቲ አሌሳንድሮ ሳፔሌ የሚባል የባንዶች አለቃ የነበረው ይገኛል ። ይህ ሰው አርጅቶ በ1935 ዓ. ም. የማይጨው ጦርነት ዋዜማ ላይ ባሳተመው የማስታወሻ መጽሐፉ ፣ "ከደብረ ኃይላ ጦርነት ወዲህ ስለ ሸዋ ጦር ሠራዊት ቁጥርና ድርጅት ከኤርትራ ፣ ከትግሬ የሰበሰብሁትንና ከአዲስ አበባ እንጂኒዬር ካፑቺ በሰፊው በቁጥር ቃል የላከውን የቁጥሩን ቃል ፈትቼ ላገረገዥው (ባራቲዬሪ) ያቀረብሁት ትክክል ነበር"[2] ይላል ።

በዚሁ ዓይነት ፣ ሁሉም በየተሠማራበት አውራጃና ከተማ ፣ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር ፣ የእጅ ጥበብ ሥራና የሕክምና አገልግሎቱን በማበርከት ፣ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደ ተላከው ዓይነት ባይሆንም ፣ ከዚያ ዝቅ ያለ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት በማቅረብ ይወዳጅ ነበር ። መሳፍንቱና መኳንንቱም አንዳንዶቹ የጉዳዩን ሁኔታ በግልጽ ሳይረዱ ለያንዳንዱ የኢጣልያ ወኪል ፣ "ያንተም የኢጣልያም ወዳጅ ነን" እያሉ ከልብም ይሁን ከአፍ የሚገልጹለትን በልቡ ይተማመንበትና ይኸንኑ በቶሎ ወደ ኤርትራ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ሲያስተላልፍ

1 ዳግማዊ ዐጼ ምኒልክ — ገጽ 94—95
2 Memorie d' Africa - A. Sapelli, P. 93



እርሱም በፋንታው ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "መሐመድ አንፋሪ በፍጹም የኛው ነው ። ራስ ሚካኤል ታማኝነታቸውን ለኢጣልያ ገልጸዋል ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልእክተኞቼን በደስታ ተቀብለው አስተናግደዋል ። በከሰላ ደርቡሾችን ያሸነፍሁ ጊዜ ፣ እንኳን ደስ አለህ ብለው የደስታ መግለጫ ልከውልኛል ። ዋግሹም ብሩ ከራስ ሚካኤል የበለጠ ግልጥ በሆነ መንገድ ለኛ ታማኝነታቸውን አረጋግጠዋል ። በሐረር ራስ መኰንን ጦርነቱን በምትጀምሩበት ጊዜ ወደ ናንተ እንደረባለን ብለዋል ። እጨጌ ቴዎፍሎስና የአክሱም ካህናት የኛ መሣሪያ ናቸው . . ."[1] እያለ ሰፊ ራፖሩን ሲያስተላልፍ ሮማ ያሉት መሪዎች ልባቸው ለመደንደን ቻለ ።

ወደፊት ሲፈጸም እንደምናየው ፣ በእውነቱ ኢጣልያኖችን አደፋፍሮ መረብን አልፈው ራስ መንገሻን በመውጋት እስከ አምባ አላጌ ድረስ ያስገሠገሣቸው ይኸ ሁኔታ ነው ። ከዚህ ከተወራው ሁሉ አብዛኛው ከንቱ ተስፋ ሲሆን ፣ የአውሳው የመሐመድ አንፋሪና የዋግሹም ብሩ በስውር ከኢጣልያኖቹ ጋር መሳላክ እርግጠኛ ነው ። እንደዚሁም የአክሱሙ እጨጌ ቴዎፍሎስ ባንድ ወገን ምኒልክን በመጥላት ፣ በሌላ ወገን ባራቲዬሪ በስጦታ ስላሰከራቸው ፣ ልባቸውን ለጣልያኖቹ መስጠታቸው በሰነድ የተረጋገጠ ነው ። በኢጣልያም ጐን ሌሎቹ ኃያላን መንግሥታት ፈረንሳይ ፣ መስኮብ ፣ እንግሊዝ በአዲስ አበባ የወኪል ሰላይ ማስቀመጣቸው አልቀረም ። ወኪሎቹ ሁሉ በየበኩላቸው ለየመንግሥታቸው ጥቅም ሲሠሩ ገጸ በረከትም ማቅረባቸው የታወቀ ነው ። ነገር ግን ፣ ከሁሉም ይበልጥ በኢትዮጵያ ላይ ገዥነቱን ለመመሥረት ያተኮረው እንደ ሌሎቹ ቅኝ አገር ያልደረሰው የኢጣልያ መንግሥት ስለሆነ ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ትግል ከዚሁ መንግሥት ጋር መሆኑ ግልጽ ነው ። ኢጣልያኖቹም ፣ ሌሎቹም ይኸን ሲሠሩ ያዬ ምኒልክ አያያዝ ምን እንደነበር ታዋቂው ጸሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ ባጭሩ እንደዚህ ሲል ገልጦታል ።

> ምኒልክ ምክር ያዳምጣሉ ፤ ስጦታን ይቀበላሉ ፤ ራሳቸው ከመጠንቀቅ በቀር በማናቸውም ላይ ሳይተማመኑ በአጠራጣሪው ለሚደርሰው ፣ የጦርነት ዝግጅታቸውን ይቀጥላሉ. . . የጦር መሣሪያ ይሰበስባሉ . . . በወሎ ጐተራ እህል ያከማቻሉ . . . ለመሣሪያ መግዣ የመሬቱ ግብር አልበቃ ስላለ ፣ በከብት ላይ ልዩ ቀረጥ አውጥተው በሁለት በሬ አንድ ብር ያስከፍሉ ነበር ። . . .[2]

1 Memoire d' Afrique - O. Baratieri; Chap. 18, PP. 247 -256, Chap. 27. PP. 356 - 358.
2 Italia ed Etiopia . . .PP. 108 - 109

ይኸም አባባል እውነት ነው ። የወደፊቱ ጦርነት የማይቀር መሆኑን ደህና አድርገው የገመገሙት ንጉሠ ነገሥት ፥ ከእቴጌ ጣይቱና ከቅርብ የባለሥልጣን አማካሪዎቻቸው አሳብና ምክር እያዳመጡ ሁሉም ነገር ማለትም ፥ ለጦርነት አብነት የሆነው የጦር መሣሪያና ስንቅ እንዲዘጋጅ ማድረጋቸው የኢጣልያንንም ያለፈ ብድር ለመክፈል ገበሬው ሁሉ በየአንዳንዱ በሬ የገንዘብ ቀረጥ እንዲከፍል የጭራ ግብር ማወጃቸው እርግጥ ነው ።



# ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

## የዠኔራል ባራቲዬሪ ዓድዋ መምጣትና መመለስ—ራስ መንገሻና ኢጣልያኖች ኮዓቲትና ሰንዓፌ ላይ ያደረጉት ጦርነትና የራስ መንገሻ መሸነፍ

ያጋሜው ራስ ስብሐት ፥ ቀደም ሲል በራስ አሉላ አማካይነት ከራስ መንገሻ ጋር ታርቀው ገብተው የራስነት ማዕረግ ከርሳቸው ተቀብለው ሳለ ፥ በኋላ ከራስ አሉላ ጋር ሆነው የዓድማ ነገር ስለ ተገኘባቸው ራስ አሉላ ግማሽ ግዞት ሲያገኛቸው ፥ ራስ ስብሐት በአምባ ሰላማ እንደ ታሰሩ የሚታወስ ነው ። ራስ አሉላም በራስ መንገሻ ቅሬታ ስለ ገባቸው ፥ ራስ መንገሻም ከሸዋ ወደ ትግሬ ሲመለሱ እርሳቸው አዲስ አበባ መቅረታቸውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ራስ መንገሻ ፥ ራስ ስብሐትን ካሰሩ ወዲህ የአጋሜን ግዛት ሹም አጋሜ ተስፋዬ አስኝተው ለደጃች ተስፋዬ (የእንጣሎው) ሰጧቸው ። በአንድ ወገን በአጋሜ ባላባትነት ያላቸው ደጃች ሐጎስ ተፈሪም የራስ ስብሐትን መታሰር ፥ የደጃች ተስፋዬን መሾም ሲመለከቱ ከነጭፍራቸው ለኢጣልያኖች ገብተው ተቀመጡ ።

በዚህ ዓይነት ፥ ከራስ መንገሻ የሸፈተው ወደ ኢጣልያኖች ሲገባ ፥ ኢጣልያኖች ሐማሴንንና አከለ ጉዛይን ሁሉ እያለፉ እስከ መረብ ድረስ ተጠጉ ። የራስ መንገሻና የኢጣልያኖችም ጦርነት የማይቀር ሆነ ። በዚህ ጊዜ ዠኔራል ባራቲዬሪና ራስ መንገሻ ውስጡን ጠላቶች ሆነው ፥ ላዩን እንደ ወዳጅ ደብዳቤ እየተጻጻፉ ፥ ሁለቱም ወታደር እየመለመሉ የጦር ድርጅት ከማድረግ ላይ ይገኛሉ ። በራስ መንገሻ ዘንድ ብዙ መኳንንትና ወታደር ከነመሣሪያው ቢኖርም ፥ በኢጣልያኖችም ዘንድ እነደጃች ተስፋ ማርያም ፥ እነደጃች ሐጎስ ተፈሪ ፥ እነደጃች አሊ የእንዳመሆኔው ከነጭፍራቸው አሉ ። ከነዚህ ደግሞ የበለጡት የወር ቀለብ እየተቀበሉ ፥ ደንበኛ የጦር ትምህርት እየተማሩ ፥ የወታደር ልብስ እየለበሱ ከውስጣቸው ሙንጣዝ ፥ ቡልቅባሻ ፥ ሹምባሽ ፥ ቡዝባሽ እየተባሉ በሚሾሙ ሥር ሆነው የሚተዳደሩ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ይገኛሉ ። እነዚህ ከኢጣልያ ከመጡት የነጭ ወታደሮች ጋር ሆነው የፈረሰኛውና የእግረኛው ጦር ፥ መድፈኛውና ባለጠመንጃው በድልድል ተደራጅቶ ለወደፊቱ ጦርነት

ይጠባበቃል ። ለኢጣልያም ጦር ከአክሰ ጉዛይ ፣ ከሐማሴን ፣ ከሰንዓፌው የባንዳ ጦር በቀር ከምዕራብ በኩል የሱዳን ፣ የቤን አሚር ፣ የብሌን ፣ የሐባብ ፣ የቦጎስ ፣ የከረን ተወላጅ ለወታደርነት እየተመለመለ በአተኳኮስ እየሠለጠነ ለኢጣልያኖች ጉራቸውን አጠንክሮላቸዋል ።

በዚህ አኳኋን ፣ የኢጣልያ ጦር ዝግጅቱን ቢጨርስም በቶሎ መረብን ተሻግሮ ከራስ መንገሻ ጋር ጦርነት አልገጠመም ። ጦሩ ከዚህ ቀደም ከነደጃች አበራ ፣ ከነደጃች ባሕታ ሐጎስ ጋር በሐላይ በአደረገው ውጊያ እንዲሁም በከስላና በአቆርዳትም በኩል በአከናወነው ጦርነት ለጊዜው ስለቀናው ፣ "የኢጣልያን ጦር የሚችለው የለም" የሚል ስብከት በሕዝቡ ዘንድ ተነዝቶ ነበር ። አሁንም ጄኔራል ባራቲዬሪ ያለ ጦርነት ዝም ብዬ መረብን ተሻግሬ ዓድዋ ብገባ ሕዝቡም፣ መኳንንቱም አሜን ብሎ ይገባልኛል ፤ የዐፄ ምኒልክን መንግሥት የጠሉት እነእጨጌ ቴዎፍሎስ አገሩን ሰብከው ከራስ መንገሻ እየለዩ ወደኔ ያመጡታል ። ከዚያ በኋላ የራስ መንገሻም ጦር ምንም ማድረግ ሳይችል ይሸሽና የኢጣልያን ግዛት በሙሉ ትግሬ ላይ በሰላም አስፋፋለሁ " የሚል ምኞት አደረበት ። ለአጋሜ ሰዎች ደግሞ "ግድየላችሁም ቢቻል በሰላም ያለዚያም ከራስ መንገሻ ጋር ተዋግቼ ባላባታችሁን ራስ ስብሐትን አስፈትቼ አመጣላችኋለሁ" እያለ ሰበካቸው። ባንድ ወገን ደግሞ ራስ መንገሻን ለማዘናጋት ፣ "ወደ ዓድዋ መጥቼ ከዚህ ቀደም መረብ ላይ ተዋውለን በፈረሰው ውል ተወቃቅሰን እንደገና ወዳጅነታችንን እናድሳለን" የሚል ሐሰተኛ መልእክት አስቀድሞ እየላከ በማታለል ፣ መልስ ሳይጠብቅ ከሠራዬ ተነሥቶ ወደ ዓድዋ ተጓዘና በታኅሣሥ 21 ቀን 1887 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ዓድዋ ከተማ ገባ ። ሕዝቡም መኳንንቱም ነገሩ ገርሞት የበረታና የቆረጠው ራስ መንገሻ ወዳሉበት እየሔደ ተጠቀለለ ። የቀረው በየስፍራው ሆኖ የሚመጣውን ነገር ዝም ብሎ ይጠባበቅ ጀመር ።

የዓድዋ ካህናትና ቀሳውስት ግን ፣ በእጨጌ ቴዎፍሎስ መሪነት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ፣ መስቀል ይዘው ፣ አንዳንድ የሽመግሌ ሰዎች ጨማምረው ፣ ተሰልፈው ተቀበሉት ። እርሱም እንደ ደረሰ ከፈረስ ወርዶ የእጨጌ ቴዎፍሎስንና የቀሳውስቱን መስቀል በስብከት መልክ ተሳልሞ ንግግር ያደርግ ጀመር ። ራስ መንገሻ እላይ እንዳልነው ፣ በዚህ ጊዜ ከነጦራቸው ከዓድዋ ወደኋላ ሆነው ይጠባበቁ ነበር ። በዓድዋም ጐበዝ ጐበዙ ሁሉም ከተማውን ትቶ ወደ ራስ መንገሻ ሆኖ የዓድዋ ከተማ ከሴትና ከሽማግሌ ፣ ከካህናትና ከቀሳውስት በቀር ባዶ ነበረች ። ጄኔራል ባራቲዬሪ አዘናግቶ ራስ ስብሐትን ከታሰሩበት ለማስፈታት የሚችልበትን መንገድ እያሰበ ግማሽ ጦሩን ወደ አክሱም ሰመላክ ሲጀምር ፣ የራስ መንገሻ ጦር ወደ ዓድዋ እየተጠጋ መከበብ



ጀመረ ። በዚህም አሳቡ ስለ ተሰናከለበት ፣ ገና ም ብሎ ከራስ መንገሻም ጋር ፊት ለፊት እንዳይዋጋ ያመነታ ጀመር ። በዚሁም ላይ ፣ "ከራስ መንገሻ ጋር ሲዋጋ ደርቡሾች እንደገና በከስላ በኩል የከረንን ፣ የሐባብን ግዛት ሊወሩብኝ ይችላሉ" ብሎ ተጠራጠረ ። ዓድዋ ሲደርስ ፣ "ሰው ሁሉ ከነመኳንንቱና ከነባላባቱ ጭምር እየመጣ እንደ አገሩ ልማድ እጅ እየነሣ ይገባልኛል ፤ ራስ ስብሐትንም አስፈትቼ አመለሳለሁ"ብሎ ተስፋ አድርጎ የነበረው ሳይሳካለት ቀረ ። እንዲያውም ፣ እርሱ ዓድዋ ላይ እንዳለ ወደ መጣበት ለመመለስ ሲያስብ የራስ መንገሻ ጦር ከቦ መንገድ ከለከለው ። ይልቁንም እርሱ ከነእጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ፣ የሐማሴንና የሰንዓፌ ባንዶችና ወታደሮች በከተማው በየሰላማዊው ቤት እየገቡ ያገኙትን መዝረፋቸው ፣ ሕዝቡንም ማጉላላታቸው ስለ ተሰማ ፣ የራስ መንገሻ ሰዎች ከበው ለውጊያ ተዘጋጁ ። በኋላ ግን ፣ አጠገቡ ያሉትን ወታደሮቹን አሰልፎ ፣ "ለማናቸውም ተጠንቀቁ" ብሎ እርሱ በፈረስ እንደ ተቀመጠ ወደ ቀሳውስቱ ወደ እነ እጨጌ ቴዎፍሎስ ሔዶ ፣ "እኔ የመጣሁት እርቅና ሰላም ለማድረግ እንጂ ለጦርነት አልነበረም ። አሁንም እርቁን ካልፈለጉት በሰላም ይልቀቁኝና ወደ አሥመራ ልመለስ "ብሎ አመለከተ ። በዚህ ጊዜ ከርሱ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት አድርገው የቆዩት ባለወርቅ ጥልፍ ካባና ቀሚስ ሌላም ገጸ በረከት እየላከ አስደስቷቸው የነበሩት እጨጌ ቴዎፍሎስ ፣ "እርሱ እንደዚህ ሰላማዊ ሆኖ ፍቅር ሲያሳያችሁ እናንተ ለምን በጠብ ትፈልጉታላችሁ" ብለው ምክርም ፣ ተግሣጽም እየጨመሩ ለራስ መንገሻ ሰዎች ስለነገሩዋቸው ፣ ተስማምተው ለቀቁትና በቀጥታ ጄኔራሉ ከዓድዋ ወደ አዲ ኳላ ተመለሰ ።[1] ከዚህ ቀጥሎ ራስ መንገሻ ጦራቸውን ይዘው ከዓድዋ ወደ መረብ ተጉዘው ፣ ከዚያም ወንዙን እየተሻገሩ የዛማን ሜዳ አልፈው አክለ ጉዛይ አውራጃ ገቡ ። በዚህ ጊዜ ጄኔራል ባራቲዬሪ ሹማምንቱን ከነወታደሩ በየአለበት ለጦርነት አሰለፋቸው ።

ማዦር ቶዜሊ የሚባለው ፣ የራሱን የባታዮ ጦር ይዞ በአክለ ጉዛይ በባንዶች አለቃ በቴኔንቲ ሳንጉይኔቲ እየተረዳ በፍጥነት መጥቶ ኮአቲትን ያዘ ። ዓድዋ እንደ ቆንሲል ሆኖ ይቀመጥ የነበረው ቴኔንቲ ሙላዚኒ የሚባለው የራስ መንገሻ የፊተኛው አያያዛቸው አስፈርቶት ይዘው እንዳያስሩት ከዓድዋ ሸሽቶ መጥቶ ባሁኑ ጊዜ የሠራዬን ባንዳ ያዝ ነበርና እርሱም ባንድ ወገን መጥቶ ለማዦር ቶዜሊ ረዳት ለመሆን ኮአቲት ደረሰ ። ከማዦር ቶዜሊ ጦር በግራ በኩል ማዦር ጋልያኖ ፣ ከኋላ ደጀን ማዦር ሄዳልጎ ሆነው በኮአቲት የራስ መንገሻና

1 Memoire d' Afrique - O. Baratieri. Chap.6

የኢጣልያኖች ጦር ቅርብ ለቅርብ ተሰልፎ አደረ ። በማግሥቱ ጥር 6 ቀን (እ.ኤ. አ. 13 ጥር) ሊነጋጋ ሲል ፣ ለማነጣጠር እሚመች ስፍራ ላይ ሆኖ ካፒቴን ቺኮዲኮላ የመጀመሪያውን የመድፍ ጥይት በራስ መንገሻ ሰፈር ላይ በመተኮስ በጩኸቱ የጦርነቱን መጀመር አስታወቀ ። ወዲያው ኢትዮጵያውያኑ ወደየሰፈራቸው ተሯሩጠው መሣሪያቸውን ይዘው ተገን እየያዙ መልሰው እየተኮሱ ይዋጉ ጀመር ። ቀኑን ሙሉ እየጋለም ፣ እየበረደም ሲዋጉ የመሬቱ ወጣ ገባነት ፣ የጫካውና የእሾሁ ፣ የዳገቱና የቁልቁለቱ ሁኔታ ለኢትዮጵያውያኑ ሲረዳ ፈረንጆቹ ስለ ተቸገሩ ፣ የዚህ ቀን ጦርነት ለራስ መንገሻ ጦር የድል ተስፋ ከፍቶለት ነበር ። የኢጣልያንንም ጦር ለመከበብ ግራና ቀኝ ሲዘዋወሩ እነዚያም እንዳይከበቡ ግራና ቀኝ እየተራራቁ ሲከላከሉ ጊዜው ስለ መሸ እንደዚሁ በያሉበት አዳር ሆነ ። በማግሥቱ ጦርነቱ ተጀምሮ በሚቀጥልበት ጊዜ የኛዎቹ ስንቅና ውሀ ስለ አለቀባቸው ከኮአቲት ወደ ሺምዛና አፈገፈጉ ። “ራስ መንገሻ ወደኋላ ያፈገፈጉት ቁጥሩ እጅግ የበዛ ጦር ለጣልያኖች ደረሰላቸው ማለትን ከሐሰተኛ ሰው ስለሰሙ ነው” ይባላል ። የሆነ ሆኖ ፣ ራስ መንገሻ ከኮዓቲት ከነ ጦራቸው በሺምዛና በኩል አድርገው ወደ ሰንአፌ ሔደው ሰፈሩ ። ኢጣልያኖቹ ግን ፣ የዚህን የኮዓቲትን ጦርነት እንደ አንድ ዠብዱና ድል በማድረግ ቆጥረውታል ። የራስ መንገሻንም ከኮዓቲት ወደ ሰንዓፌ መሔድ እንደ ሽሽት ገምተውታል ። ነገሩም የሚመስል ነው ።

በዚህም ጦርነት ከራስ መንገሻ ወገን ደጃች ተድላ አይባ ፣ ወንድማቸው ደጃች አርአያና ልጃቸው ቀኛዝማች ተፈሪ ፣ የራስ ኃይሉ ማርያም ልጅ ደጃች ግዛዌ ሞቱ ። ሹም አጋሜ ተስፋዬም ቆሰሉ ። ከተራው ወታደር የሞተውና የቆሰለው አይታወቅም ። ከኢጣልያኖቹም ወገን ደጃች ባሕታ ሐጎስ ማርከው ያሰሩት ቲኔንቲ ሳንጉይኔቲ በዚህ ቀን ቆስሎ ቆይቶ ሞተ ። ከባንዳና ከደንበኛ የኢጣሊያን ጦር ግን ፣ የሞተው 90 የቆሰለው 227 ይደርሳል ።[1] በዚህም በሌላውም ጦርነት ለኢጣልያኖቹ መሣሪያ በመሆን እፊት እየቀደሙ ከወገናቸው ጋር በመዋጋት የሚያልቁት እነዚያው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እንረዳለን ። የራስ መንገሻ ጦር ከኮዓቲት ወደ ሰንዓፌ አፈግፍጎ ከሔደ በኋላ ፣ ማታውኑ የራስ መንገሻ ሰዎች ማርከዋቸው የነበሩት የባንዳ ወታደሮች ከማራኪዎቻቸው አምልጠው ወደ ኢጣልያኖቹ በመመለስ ፣ “የጠላት ጦር ተዘበራርቆ ወደ ቶኮንዳ ይጓዛል” የሚል ወሬ ለኢጣልያኖቹ አመጡላቸው ። ይህም ውጊያውን ለመቀጠል ሞራላቸውን ከፍ አደረገላቸው ።

1 Douze ans en Abissinie - De Lauribar, Chap. 28,PP. 365 - 381.



በዚህ ጊዜ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ከሌሊቱ በ9 ሰዓት ስብሰባ አድርጎ ከሹማምንቱ ጋር ተመካክሮ ፣ “ወፍ ጭጭ ሲል ተነሥቶ የጠላት ጦር አለበት ድረስ ተከታትሎ ማጥፋት ነው” የሚል ውሳኔ ተደረገ ። ከዚህ በኋላ ወታደር ሁሉ ያራት ቀን ስንቁን እንደያዘ ጉዞ ጀመረ ። የጉዞውንና የጦርነቱን ሁኔታ ጦርነቱን የተካፈለው ደ ሎሊባር እንደዚህ ይላል ።

> መንገዱ ውጣ ውረድ የበዛበት ስለነበረ ጉዞው አስቸጋሪ ነበር ። አዶ አዌይ ስንደርስ አበሾቹ ጥለዋቸው የሔዱትን ቁስለኞች አገኘን ። ከዚያ ወዲያ የመንገዱ መጥፎነት እየባሰበት ሔደ ። ደንጋያማ ተራራና ሸለቆ የበዛበት ሸለቆው ደግሞ ቀንጥር እሾህ የሞላበት ስለሆነ በዚያ ሲታለፍ በእሾህ መነከስ አለ ። አንድ ቦታ ስንደርስ ብዙ ጦር ያለፈበት ሥፍራ አገኘን ። ከዚያ የዳሪሲያንን ተራራ ወጥተን ወደ አምባሻላይ ተዘቅዝቀን ወደ እኩለ ቀን ላይ ቶኮንዳ ደረስን ። ከዚያ ከትንሽ ጊዜ በፊት ራስ መንገሻና ጦራቸው ከዚያ አልፈው ወደ ሰንዓፌ መሔዳቸውን ሰማን ። ምግብና ውሀ ያለበትን ለውጊያም የተመቸ ሥፍራ ያለበትን ቶኮንዳን አልፈው በመሔዳቸው ፍርሐት እንዳደረባቸው ተገነዘብን ። ስለዚህ አሁኑኑ የወታደራችን ሞራል ከፍ ባለበት ሰዓት በመጠቀም ያንድ ሰዓት ዕረፍት ብቻ ካደረግን በኋላ ግሥጋሤአችንን ቀጠልን ። ከቶኮንዳ ቀጥሎ ወዳለው ተራራማ ሥፍራ ሲወጣ ጉብታቸው የፈጠጠው የሐላይ ፣ የዓድዋ ወረዳዎች እንደዚሁም የመረብን ወንዝ የሚያካብቡት የተራራ ሰንሰለቶች እስከ ሐዶ ድረስ ወለል ብለው ይታያሉ ። ይኸን ጉብታ አልፈን ወደ ከስከሴ ደረስን ። ከዚያ ደንጋያማ ሸለቆና ጉብታ የሆነውን ለቀን ወሀ ያለበትን ደልዳላና ሜዳማ ሥፍራ ተመለከትን ። ጊዜውም ፀሐይ የምትጠልቅበት ወቅት ስለነበረ ፣ ጠላቂዋ ፀሐይ የወረወረችው የማታ ጮራ ልምላሜ ያለውን ቀበሌ በቀይ ቀለም አሸብርቆት ነበር ።
>
> . . . በሜዳማው ሥፍራ ራስ መንገሻና ጦራቸው እንደ ሰፈሩ ተመልከተን መድፋችንን በጥድፊያ ጠምደን ተኩስ ከፈትን ። ወዲያው ራስ መንገሻ ከድንኳናቸው ወጥተው ጦራቸውን ሰብስበው ለማዋጋት ማበረታታት ጀመሩ ። በመጀመሪያ የተተኮሰው መድፍ የራስ መንገሻን ድንኳን በታትኖ ብዙ መኳንንት ገደለ ። በዚያው ሰዓት ዠንበር ስለ ጠለቀችና ወዲያው የኛንም የነርሱንም ሰፈር ጨለማ ስለሸፈነው ፣ የጦርነቱን ጊዜ ለማግሥቱ አስተላለፍነው ። በማግሥቱ ወደ ሜዳው ተዘቅዝቀን ብንወርድ ፣ ጠላት ሌሊቱን በጥድፊያ ተዘበራርቆ ሸሽቶ ኖሮ ባዶ ሰፈር አገኘን . . . ካለ በኋላ

ከዚሁ አያይዞ ፣

> ወደ ራስ መንገሻ ድንኳን ብንገባ በመሬት ላይ ልብስ ወረቀት የቤት ዕቃና ምግብ መሥሪያ በያይነቱ ተዝረክርኮ ይታያል ። መከዳቸው በሐር ልብስ ተሸፍኖ በርሱም ላይ የሽቶ ብልቃጥና አንድ በብረት የተሰበደ ጥሩ የጸሎት መጽሐፍ ጄኔራል ባራቲዬሪ ልኮላቸው የነበረ የወርቅ ሰዓት ከባሕታ ሐጎስና ከምኒልክ እንደዚሁም ከፈረንሳዊ ክላዛሪስት ሚሲዮን አለቃ ጋር የተጻጻፉት ደብዳቤ በሙሉ ተገኘ ።

> በዚህም ባሕታ ሐጐስን ያስከዱ ራስ መንገሻ መሆናቸውን በነገሩም የላዛሪስት ሚሲዮኖች ተስማምተው እንደ ገፋፉት ተረዳን ።

ካለ በኋላ ፡ ጽሑፉን በመደምደም ይኸው ደ ሎሲባር የሚባል ጸሐፊ ባለፈው በኮዓቲት በጀግንነት የተዋጉት ትግሬዎች በዚህ በሰንዓፌው ጦርነት እንደሚገባ ሳይዋጉ ስለሸሹ ፡ ምን እንደ ነካቸው አለማወቁን ያመለክታል ።[1]

የሆነ ሆኖ ፡ ኢጣልያኖቹ በሐላይ በደጃች ባሕታ ሐጎስ ላይ ባገኙት ድልና አሁንም በዚህ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ባገኙት አሸናፊነት እየተደሰቱ በትምክህትና በኩራት መረብን አልፈው ወረራቸውን ቀጠሉ ። ጄኔራል ባራቲዬሪም ፡ ለጊዜው ሰንዓፌ ላይ ማዦር ጋልያኖን አስቀምጦ ፡ የኮዓቲትን ጦርነት ለተካፈሉት ለደጃች ሐጎስ ተፈሪ አጋሜን ሰጠ ። እርሱ ወደ ምጥዋ ሔዶ ፡ የድል አድራጊነቱን በዓል በደስታ አክብሮ ፡ ከዚያ እንደገና ወደ አሥመራ ተመልሶ የአገር ወረራውን አሳብ ያውጠነጥን ጀመር ። ራስ መንገሻም ከያዙት ከ14 ሺ ባለጠመንጃ ፡ ከ4ሺ ባለጦርና ባለጋሻ ወታደር ውስጥ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ጦርነት ከአንድ ሺ የበለጡ ከደህና ደህና መኳንንቶች ጋር ቢሞቱባቸውና ሁለት ሺ የሚሆኑ ቢቆስሉባቸውም ፡ ከተረፈው ጦራቸው ጋር ወደ ኋላ ወደ መቀሌ መጡ ። እዚያም ሳሉ የሆነውን ሁሉ ወዳጼ ምኒልክ ልከው የእርዳታ ጦር ከሸዋ እንዲደርስላቸው አመለከቱ ። ነገር ግን ፡ መላከተኛው ገና አዲስ አበባ ሳይደርስና መልሱን ሳያመጣ ከዚህ በፊት እንዳልነው ፡ ጄኔራል ባራቲዬሪ ከአሥመራ ትእዛዝ እያስተላለፈ ፡ ማዦር ቶዜሊ የደጃች ሐጎስ ተፈሪን ባንዳ ይዞ የአጋሜን ከተማ አዲግራትን እንዲይዝ ፡ ማዦር አሚሊዮ ያገር ተወላጅ ያምስተኛ ባታዮን ጦር ይዞ ዓድዋን እንዲይዝ አድርጎ የቀረው የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ደግሞ ራስ መንገሻን እንዲከታተል አደረገ ። ራስ መንገሻም ከሸዋ ጦር ሳይመጣ የተደራጀውን የኢጣልያን ጦር ብቻቸውን መውጋት ትርፉ ሰው ማስጨረስ መሆኑን ስለገመቱ ፡ ከመቀሌ ወደ እንጣሎ ፡ ከእንጣሎም ወደ ደብረ ኃይላ ተጓዙ ።[2]

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፡ በኮዓቲት ጦርነት ቆስሎ ለሚያጣጥረው ለቲኔኒቲ ሳንጉይኔቲ እተኛበት ድረስ ሔዶ ፡ “ድሉ የኛ ሆኗል” ቢለው ፡ “ይኸን ሰምቼ ብሞትም ግዴለም” የሚል ቃል ከወረወረ በኋላ ወዲያው አንገቱን ዘለስ አድርጎ ሞተ ። ጄኔራል ባራቲዬሪ የኮዓቲትንና

1 Douze ansen Abyssinie . . . Chap. 19, PP. 385 - 389.

2 Ibid. Chap. 28 - 29



የሰንዓፌን ጦርነት እያጋነነ ድል ማድረጉን ወደ ኢጣልያ አገር ቴሌግራም አስተላልፎ ነበርና ንጉሡ ኡምቤርቶ ፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክርስፒ ፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ባሮን ብላን ፡ የጦር ሚኒስትሩ ሞቼኒ ወሬውን እንደሰሙ በበኩላቸው በደስታ ተቀብለው እንኳን ደስ አለህ የሚል የደስታ መግለጫ አከታትለው ላኩለት ። የሁሉንም እዚህ ላይ ማስፈር ስለማይቻል ፡ የንጉሡንና የጠቅላይ ሚኒስትሩን ብቻ እንመልከት ።

ሮማ 18 ቀን 1895 ዓ . ም

> በኮዓቲትና በሰንዓፌ የኢጣልያ ጦር ማሸነፍ ፡ ሥልጣኔ በአረመኔ ላይ ያገኘው አዲስ ድል ነው ። ብልህነት ስላለው አመራርዎ የደስታዎ ተካፋይ ነኝ ። ሦስት ቀን ሙሉ ቁጥሩ 3 እጅ ከሚበልጠው ጠላት ጋር በደስታ ራሳቸውን ሠውተው ጦርነቱን ለተካፈሉት ለበላይና ለበታች መኰንኖች ለወታደሮችም ባለውለተኛ መሆኔን እንዲያስረዱልኝ ። እርስዎን የመሰለ ጀግናና ብልህ መሪ ሲመራቸውና እነዚህን የመሰሉ ወታደሮች ሲኖሩ ፡ በመጭው ጊዜ ቅኝ ግዛታችንን ምንም ዓይነት ተንኮልና አደጋ ሊያስፈራው አይችልም ።

ኡምቤርቶ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግሞ በበኩሉ ፡

> በአበሾች ላይ በተገኘው ድል ካንተና ከኢጣልያ ጋር የደስታ ተካፋይ ነኝ ። የወታደሩን ጀግንነት ብቻ ሳይሆን በጋሪባልዲ አርአያ በትንሽ ጦር ኃይለኛውን ጦር ለማሸነፍ የቻለው የመሪው ችሎታ ነው ። እንግዲህ የትግሬ አገር ለኢጣልያ የተከፈተ ነው ። ሳንይዘው ብንቀር የኛ ስንፍና ነው ።[1]

ክሪስፒ

በዚህ ዓይነት ፡ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ጦርነት ባንድ በራስ መንገሻ ላይ ያገኙት ጊዜያዊ ድል ከንጉሡ ጀምሮ የኢጣልያን ባለሥልጣኖች አርኪቶአል ። እንደዚሁም ይኸው ድል ተጋኖ በኢጣልያ ጋዜጦች ስለተጻፈ ፡ ሕዝቡም ሁሉ በደስታና በኩራት ተሞላ ። ከዚህ በኋላ ፡ በጄኔራል ባራቲዬሪ ይልቁንም በምክትሉ በጄኔራል አሪሞንዲ ትእዛዝ እነጋልያኖ ፡ እነቶዜሊ በየመስመሩ ወደ ዓድዋ ፡ ወደ መቀሌና ወደ አዲግራት እየገሠገሡ ፡ በየከተማው እየመሸጉ መደላደል ፡ በየወረዳው ሹም ሽር ማድረግ ያዙ ። ይኸን ሁሉ ሲያደርጉ ከሸዋና ከተቀረው ኢትዮጵያ በንጉሠ ነገሥቱ ተመርቶ ወደፊት የሚመጣው ጦር ፡ ይኸን የደስታ

1 Adua Bellavita - PP. 185 - 186; Italiani in Africa Orientale - A. DelBoca, PP.531-561.

ሁኔታ እንደሚለውጠው ሮማም ሆነ ምጥዋ ያሉት ባለሥልጣኖች ደህና አድርገው አላጤኑትም ። በመንግሥት ደረጃ በትንሹ ድል የሚታለሉና የሚደሰቱ የዋሃንና አዙረው ተከታዩን የማይመለከቱ እንደ ኢጣልያ ባለሥልጣኖች ያሉ በዓለም ብዙዎች ናቸው ለማለት ያዳግታል ። ሆኖም አባቶቻቸው ሮማውያን ኃያላን ለዓለም ብዙ የሥልጣኔ ቅርስ ያተረፉ ፈላስፎችና ዐዋቂዎች እንደነበሩ ፣ አሁንም በመካከላቸው ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ፣ ታላላቅና አስተዋዮች እንዳሉባቸውና ያሁኑም ጊዜያዊ ድል እምብዛም ያላስደሰታቸው የምክር ቤት አባላትና ጋዜጠኞች እንደነበሩ አይካድም ።



## ምዕራፍ ሐያ

### የጄኔራል ባራቲዬሪ ሮማ ደርሶ መመለስ

ከ1886—87 ዓ. ም. መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ መጀመሪያ በሐላይ ከደጃች ባሕታ ሐጎስ ጋር ፣ ቀጥሎም በኮዓቲትና በሰንዓፌ ከራስ መንገሻ ጋር በተደረጉት ጥቃቅን ጦርነቶች የኢጣልያ ወታደሮች ስለ ቀናቸው ፣ ባራቲዬሪ ራሱን እንደ ትልቅ ድል አድራጊ ቆጥሮአል ። ወሬውም በኢጣልያ ጋዜጦች እየተጋነነ ተጽፎአል ። ከሮማ የደስታ መግለጫ ከንጉሡና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድ ለጄኔራል ባራቲዬሪ የተላከለት ከመሆኑ በቀር ፣ ኒሻን ተሸልሞ ወታደራዊ ማዕረጉም ከማዦር ጄኔራልነት ወደ ሌተና ጄኔራልነት ከፍ ያለው በዚሁ ጊዜና ሰበብ ነው ።

የባራቲዬሪ ያሸናፊነት ጀብዱው ፣ የአጥቂነት ዘዴው በሮማ ጋዜጦች እየተጋነነ የተጻፈው እስከ ጀርመን አገር ድረስ አስተጋብቶ የቃል ኪዳን ጓደኛቸው የሆነው የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ጉዩም የደስታ መግለጫ ልኳል ። በተጨማሪም በቴሌግራም ወዳጁን የኢጣልያን ንጉሥ ኡምቤርቶን አስፈቅዶ ለባራቲዬሪ ከፍተኛ የጀርመን ኒሻን እስከ መላክ ደርሷል ።[1]

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ከባሪቲዬሪ ጋር በቅኝ አገር ወረራ ከመስማማታቸውም በላይ ፣ የፖለቲካ ትብብርና የግልም ወዳጅነት ነበራቸው ። በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን የመስፋፋት ጉዳይ ለመመካከርና ወዲያውም ሮማን በመጐብኘት የድል አድራጊነቱን የደስታ መግለጫ ከሕዝቡ እንዲቀበል ወደ ሮማ እንዲመጣ ጥሪ አደረገለት ። ስለዚህ ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ በዚሁ ዓመት (1887 ዓ.ም.) ከምጥዋ በመርከብ ተሳፍሮ በሐምሌ ወር ሮማ ሲደርስ ፣ ሰው ሁሉ ከመንገድ ላይ ወጥቶ በመሰለፍ በጭብጨባና በሆታ ላንድ ድል አድራጊ የሚገባ የክብርና የደስታ አቀባበል አደረገለት ።

---

1 La Prima Guerra d' Africa, Crispi, p. 297.

ከንጉሡና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ከተገናኘ በኋላ ፣ ወደ ዋናው ምክር ቤት በገባ ጊዜ የምክር ቤቱ አባሎች ቆመው ስሙን እየጠሩ በሆታና በጭብጨባ ተቀበሉት ። ከዚያ ቀጥሎ ሃምሳ ቀናት ያህል በሮማና በኢጣልያ ዋና ዋና ከተሞች በተዘዋወረበት ጊዜ ፣ የተደረገለት አቀባበልና በፊቱ የተነገረለት ዲስኩር የጄኔራሉን የኩራት መንፈስ አሟሙቀውለት ነበር ።[1]

በሮማ ፣ በዋናው ምክር ቤት ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ስለ ተደረገው የውጫሌ ውልና በተለይም ስለ አጨቃጫቂው 17ኛው አንቀጽ የፈረንሳይና የመስኮብ መንግሥታት ኢትዮጵያን ደጋፊነት ፣ የኢትዮጵያም ሕዝብ ስለ ነጻነቱ ያለው ተዋጊነት ፣ የምኒልክ ሰላም ፈላጊነታቸው ባንድ ወገን ፣ የጦር ድርጅታቸው በሌላው ወገን እየተወሳ ብዙ ክርክር ይደረግበት ነበር ። የንጉሡ የኡምቤርቶና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የክሪስፒ የቀኝ ክፍል ወገኖች ኢትዮጵያንም ፣ ንጉሠ ነገሥቱንም በንቀት ዐይን እየተመለከቱ ጦርነቱ በቀላሉ ኢትዮጵያን እንደሚያንበረክክ ተማምነዋል ። በዚህ አያያዝ ፣ “ይኸ ጦርነት አደገኛ ሁኔታ ላይ ሊጥለን ይችላል” የሚሉትን የግራ ወገኖችና በጠቅላላውም ጦርነቱን የሚቃወሙትን ሶሺያሊስቶችን ለማግባባት ይጣጣሩ ነበር ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ እንደ ክሪስፒ ቀኝ አገር የጠማውና የኢትዮጵያንም ጦር በቀላሉ ለማሸነፍ ይቻላል ብሎ ያመነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲኞር አልቤርቶ ብላን ነው ። በምክር ቤቱ ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ክርክር በተፋፋመበት ሰዓት ፣ ለተቃዋሚዎቹ ክፍሎች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሰጠው መልስ እንደዚህ የሚል የእብሪት አነጋገር ነበር ።

> . . .የቅኝ አገር ይዞታችን አደገኛ ጠባይ ቢኖረው ኖሮ አገረ ገዢው (ባራቲዬሪ) ወደ ቅኝው ግዛት አይመለስም ነበር ። የባራቲዬሪ ጉዞ የሚያጽናና እንጂ አሥጊ ነገር የለበትም ። መስኮብም በኢትዮጵያ ላይ ከሃይማኖት ግንኙነት በቀር ሌላ ጥቅም ስለሌለው በዚህም በኩል አሥጊ ነገር የለም ። የውጫሌ ውልም ምኒልክ እየቀለደ ባይቀበለውም የመጽናቱ ነገር ውልውል የለውም ። ምኒልክም በሸፈተበት እቅዋም የከፈተውን የጠብ አስተሳሰብ ኢጣልያ በመሰላት ጊዜና ምቹ ሁኔታ ታደላድለዋለች . . .

ይኸውም ማለት የሚገባውን ቅጣት እንሰጠዋለን ለማለት ነው ።

በዚህ ዓይነት ፣ ሲኞር ብላንና አለቅየው ክሪስፒ የኢትዮጵያን ነጻነት በቀላሉ ገፎ ለኢጣልያ የቅኝ አገር ልብስ ለማድረግ ነገሩን

2 L' Italia ed Etiopia, Conti Rossini, PP. 143 -146.



ሁሉ ቀላል አድርገው ተመልክተውታል ። ለዚህም እቅዋም ዋነኛው ምክንያት ፣ በቅርብ ጊዜ በኮዓቲትና በሰንዓፌ በራስ መንገሻ ላይ ባራቲዬሪ ባገኘው ጊዜያዊ ድል ነው ። ስለዚህም እላይ የተናገረውን ዲስኩር በመቀጠል ፣ እንደዚህ ሲል ይደመድማል ።

> ኢጣልያ በአፍሪካ የመሸነፍ አደጋ ያገኛታል ብሎ ያሰበ ሰው እንዳለ ሐሳቡን ተሳስቷል ። በከዳተኛውና በሽፍታው (በምኒልክ) አንጻር ኢጣልያ ወደፊት መገሥገሥና መስፋፋት ስትችል ፣ በቁጥብነትና በመከላከል አጋሜንና ትግሬን በመያዝ ብቻ ተወሰነች ። ኢትዮጵያ በዚህ በተንኮሏ ተግባር የጸናችበት እንደሆነ ለነዚህ እረመኔዎች የምንሰጠው መልስ ይህ ነው ። “ከሸዋ ተነሥታችሁ ባሪያና ከብት እንዘርፋለን ብላችሁ እስከ ትግሬ ዘልቃችሁ የኢጣልያን ቅኝ አገር የተነኮሳችሁ እንደሆነ ፣ በፈጣን መርከብ የሚገሠግሡት የባታዮ ተዋጊዎቻችን በፍጥነት በመድረስና ጄኔራል ባራቲዬሪን በመርዳት እናንተን አሸንፈው አዲስ ቅጣት ይሰጧችኋል ።

ይኸን የመሰለውን የድንፋታ አነጋገሩን በምክር ቤት ያሉት አባሎች አብዛኞቹ በጭብጨባ ተቀበሉት ። ሁኔታውን ለጊዜው ሶሺያሊስቶቹም ለመቀበል ተገደዱ ። በዚህ ዓይነት በደስታ የጋለ መንፈስ ራሱ ባራቲዬሪ ፣ ምኒልክን ለመምታትና ለማሸነፍ 10,000 ወታደርና ከ10 እስከ 15 ሚሊዮን ሊሬ እንደሚበቃው ገለጸ ። ይኸም ሁሉ ሲሆን ምኒልክ ከሸዋ ወደ ትግሬ ተጉዘው የኢጣልያን ጦር ለመውጋት እንደማይደፍሩ ያምን ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ ጄኔራሉ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ ከመከላከያው ፣ ከውጭ ጉዳዩና ከገንዘብ ሚኒስትሮቹ ጋር በየጊዜው ተገናኝቶ በአቆርዳት ፣ በከሰላ ፣ በኮዓቲት ጦርነቶች ላይ የተጓደለው የጦር መሣሪያም ፣ የሰውም ፣ የጭነትም ከብት ቁጥሩ ከፍ ብሎ እንዲሟላ ጠየቀ ። በተለይ ከመረብ በለሳ ሙና አልፎ ባሁኑ ጊዜ የኢጣልያ ግዛት ስለ ተስፋፋ ለጠቅላላው ለጦርነቱም ዝግጅት ፣ ለሰላማዊ አስተዳደርም የሚያስፈልገውን ወጭ ከዘጠኝ ሚሊዮን ሊሬ ወደ ዐሥራ እራት ሚሊዮን* ከፍ አስደረገ ። በተረፈ ለዝርዝር ጉዳዮች ሙሉ የደጋፊነት ተስፋ ከየባለሥልጣኖቹ ተቀብሎ በመስከረም ወር ተመልሶ አሥመራ ገባ ።

ራሱ ከዓድዋ ድል በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ፣ ከሮማ ወደ አሥመራ በተመለሰበት ጊዜ የነበረውን መንፈሱን በገለጸበት ምዕራፍ ላይ ፣

> . . . ወደ ምጥዋ ለመመለስ ተነሣሁ ። ካቢኔው (ሚኒስትሮቹ) ሁሉ እንደኛው ያገራችንና የቅኝ አገሩ ጉዳይ በልቡ እንዳለና ባገር ፊት ኃላፊነት እንዳለበት አምኜ ነበር ። መሳዋ ኢትዮጵያ በክንዳችን ላይ

* በዚያን ጊዜ አንድ የማሪያ ቴሬዛ ብር 4 ወይም 5 ሊሬ ይመነዘራል ።

ስትወድቅ በኢጣልያ አገር ሁሉም የተሰናዳ ነው ብዬ በማመን እኔም በጦር አለቆቼ እየተረዳሁ በምፈጽመው ሥራ የጠላትን ቁጥር ቀንሼ ሰላም ለማስገኘት ይቀናኛል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር . . . ሲል ጽፏል ።[1]

የዚህም አሳብ መደምደሚያው ፤ በኢጣልያ አገር ቅኝ ግዛትን አስመልክቶ የርሱን ምኞትና ጥያቄ ለማሟላት ባለሥልጣኑ ሁሉ ኃላፊነት እንዳለበት አምኖ ነበር ። በኢትዮጵያም ባያለበት የተሠራጨው ስላይ ባቀረበለት የስነድ ማስታወሻ በመተማመን ሕዝቡን ከነባላባቱ በመከፋፈል የኢትዮጵያን አቅዋም ለማዳከም ሞከሯል ። የተዋጊውን ጠላት ቁጥር በውጊያም ፤ በዘዴም ቀንሶና የራሱን በማበርከት ድል አድራጊነት ለመጐናጸፍና ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት አውርሶ በሰላም ለመግዛት ነበር ።

በዚህም ጊዜ ፤ በኢትዮጵያ ኃይለኛ መሪና ጽኑ ተዋጊ ሕዝብ አጋጥሞት ከሸፈበት እንጂ ፤ ይኸን የመሰለው ምኞትና ጕጕት የርሱ ብቻ ሳይሆን ፤ የሁሉም የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች አስተያየት ነበር ። ይኸም ሁኔታ በሌላው ባልሠለጠነው የእስያ ፤ የደቡብ አሜሪካና በተለይም በአፍሪካ ዓለም የተፈጸመ ስለሆነ ፤ አስተያየቱ በዚያን ሰዓት ለማንም የታወቀ ነው ። በዚያን ጊዜ ሥልጡኖቹ አውሮፓውያን ባልሠለጠነው ክፍለ ዓለም እየተሠራጩ ቅኝ ግዛት እንደ ቅርጫ ሥጋ የተካፈሉበት ዘመን ስለሆነ ሊያስገርም አይችልም ። ባራቲዬሪም አለቆቹም እንደ ሞኝ አይቆጠሩም ።

ዥኔራል ባራቲዬሪ ፤ ከኢጣልያ አገር ተመልሶ አሥመራ እንደ ገባ ከርሱ በታች የኤርትራንና አዲስ የተወረሩትን ወረዳዎች ሲያስተዳድር ከቆየው ከዠኔራል አሪሞንዲና ከቀሩትም የፖለቲካና የጦር ሹማምንት ጋር ተገናኝቶ በሚነጋገርበት ሰዓት ፤ ራስ መንገሻ ከእንጣሎ በስተደቡብ ሆነው እንደገና ለውጊያ መዘጋጀታቸውንና ከሸዋም እርዳታ ሊደርሳቸው ነው እየተባለ መወራቱን ሰማ ። ይኸንኑ እንዲያውቁት ያህል ፤ ወደ ሮማ ላለቆቹ በቴሌግራም ካስታወቀ በኋላ ራስ መንገሻንም ለመምታት ፤ ግዛቱንም የበለጠ ወደ ደቡብ ክፍል ለማስፋፋት እንዲመቸው ዋና መቀመጫውን ከአሥመራ ወደ አጋሜ ከተማ ወደ አዲግራት አዛውሮ በዚያ መሽጎ ተቀመጠ ።[2]

1 Memoire d'Afrique - Baratieri, Chap. XIV.

2 La Prima Guera d' Africa . . ., PP. 297 - 300. Adua, Bellavita, PP. 186 - 196 Gli Italiani in Afriea Orient - Angelo Del Boca, Chap. IX, PP. 531-558.



# ምዕራፍ ሐያ አንድ

## የደብረ ኃይላ ጦርነት

ዤኔራል ባራቲዬሪ ፤ ሮማ ሔዶ በሮማ ምክር ቤት በየከተሞችና በየግብዣው ላይ እንደ ድል አድራጊ ዤኔራል ፤ ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት እንደሚያወርስ የጦር መሪ ተቆጥሮ ሲመሰገንና ሲወደስ ሰንብቶ ወደ አሥመራ ተመለሰ ። ወዲያውኑም መንግሥቱና ሕዝቡ በርሱ ላይ የጣለውን እምነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ተዘጋጀ ። አሥመራም በደረሰ ጊዜ የጦር ሹምምንቱ ዤኔራል አሪሞንዲ፣ ማዦር አሚሊዮ ፤ ማዦር ቶዜሊ ፤ ማዦር ጋልያኖ ባለፈው የኮዓቲትና የሰንዓፌ የጦርነት ድል የተደሰቱና ለወደፊቱ ጦርነትም የጓጉ ስለነበሩ ፤ የርሱና የነርሱ ምኞት ባንድ ኢትዮጵያን የመውረር ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ይኸም አገር ለጊዜው የኢትዮጵያ ሰሜናዊው ክፍል ትግሬና ትግራይ ፤ ወሎ ጭምር ነው ። የቀረውም እንደ ጊዜው አመቺነትና ሁኔታ የሚፈጸም ነው ተብሎ ተወስኗል ።

በዤኔራሉ አጠገብ ያለው ጦር ሠራዊት ፤ ለጊዜው ከዚህ እንደሚከተለው ነው ። 116 የጦር መኰንኖች ፤ 672 የነጭ ወታደር ፤ 8065 በጦር ትምህርት የሠለጠነ ያገር ተወላጅ ወታደርና ሌሎች ቁጥራቸው በብዙ መቶ የሚቆጠር ጀሌ ጦር ነበር ።

በዚሁ ጊዜ ፤ ራስ መንገሻ ደብረ ኃይላ ሆነው የወታደራቸው ቁጥር ከ፬ሺ እስከ ፭ሺ ይደርስ ነበር ። በነዚህ ላይ ደግሞ ፤ አንድ ሺ አምስት መቶ የሚሆኑ ከሸዋ መጥተው የተጨመሩና ከ፪ሺ እስከ ፫ሺ የሚደርሱ ያገር ተወላጆች በክተት ዓዋጅ የተሰበሰቡ ነበሩ ። ከአዲስ አበባ የተላከላቸውንም የጦር መሣሪያና ገንዘብ በከረጢት ለየሰዉ እንደሚያድሉ ባራቲዬሪ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ በጻፈው ማስታወሻ አረጋግጧል ። ከዚሁ አያይዞ ራስ መንገሻ ከደቡብ ክፍል ከየጁ ከራስ ወሌ ፤ ከላስታ ከዋግሹም ጓንጉል ዘንድ እርዳታ ይጠባበቁ እንደ ነበርም ገልጿል ። ዋና አማካሪያቸው ሹም አጋሜ ተስፋዬም ፤ (ከሰንዓፌ ጦርነት በኋላ የአጋሜው ግዛት የሔደባቸው) አብረው እንደነበሩ ይጠቁማል ። በክረምቱ ጊዜ በነርሱ ሥልጣን ውስጥ ያሉትን ሹማምንት ራስ መንገሻ ወደ ራሳቸው ለመሳብ ያባብሉ

እንደ ነበርና በዚሁ መሠረት ደጃች ተድላ አባ ጉበን ራስ መንገሻ አስረዋቸው ሳለ ፣ ከአራት ወር በፊት ማዦር አሜሊዎ ከእስራት አውጥቶ በማዦር ቶዜሊ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ተሰጥቷቸው የነበሩት በአሁኑ ጊዜ አምልጠው ከራስ መንገሻ ጋር እንደ ተደባለቁ ያስረዳል ። የቀሩትም በሁለት አሳብ ላይ በመዋለል ስለሚገኙ ፣ መንገሻን አዘንግቶ በመውጋት የሸዋ ጦር ወደ ሰሜን ከመድረሱ በፊት አንድ የጦር ግዳጅ ፈጽመን ኃይላችንን ለማስተማመንና ራስ መንገሻንም ውጊያ እንዲያደርጉ ለማስገደድ ሰናስብ ፣ እርሳቸውም በበኩላቸው ፣ "ሕይወቴን እንደ ቴዎድሮስ እዚሁ እጨርሳለሁ እንጂ ፣ ሁለተኛ ከኢጣልያኖች ፊት አልሸሽም"[1] ማለታቸውን ከሰላይ እንዳገኘው ያረጋግጣል ።

ደብረ ኃይላ ፣ ባእንደርታና በሰለዋ መካከል እንጣሎ አጠገብ የሚገኝ ተራራማ ሥፍራ ነው ። ስለዚህ እንደ ጄኔራል ባራቲዬሪ ግምት በዚህ ተራራማ ሥፍራ ከነሠራዊታቸው የሚገኙትን ራስ መንገሻን አደጋ ጥሎ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ በመደምሰስ የትግሬን ግዛት በእጁ ካስገባ በኋላ ፣ ከደቡብ የሚመጣውን ጦር በደንብ ለመቋቋም ነው ።

በወዲህ በንጉሠ ነገሥቱ በኩል ፣ ከወላሞ ዘመቻ መልስ የመስኮብ መንግሥት መልክተኞችን ተቀብለው ካስተናገዱና የራሳቸውንም መልክተኞች እነፊታውራሪ ዳምጠውን ከላኩ በኋላ ፣ የጦርነት ዓዋጅ ዓወጁ ። የክረምቱ ጊዜ በዚህ ዓይነት አለፈ ።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው ፣ ከሰንዓፌው ጦርነት በኋላ ፣ ሹም አጋሜ ተሰፋዬ የኮዓቲትንና የሰንዓፌን የጦርነት ወሬ ፣ የኢጣልያኖቹን ወረራ ለዐፄ ምኒልክ ነግረዋቸው ነበር ። እሳቸውም ከመተማ ጦርነት ወዲህ መጥተው በየዳር አገሩ በሹመት የነበሩትን የትግሬ መኳንንት እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን ሔዳችሁ ራስ መንገሻን እያገዛችሁ ቆዩ ፤ እኛም መጣን እንደርስባችኋለን አሏቸው ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ያሉት የጦርና ያስተዳደር መኰንኖች በፊት ከነበሩት ከነሹም አጋሜ ተሰፋዬ ፣ ከነራስ ሐጐስ በቀር አዳዲሶቹ ካፒቴን ቤቲኒን ገድለው ወደ ሸዋ የመጡት ደጃች አበራ ፣ ደጃች ተድላ አባ ጉበን ፣ ከሸዋ በቅርብ የመጡት ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ፣ ፊታውራሪ ንጉሤ ፣ ቀኛዝማች አንዳርጋቸው ፣ ግራዝማች ኃይለ ማርያምና ባላምባራስ በየነ አሉ ።[2]

1 Memoire d' Afrique . . Chap. 15, PP. 213 - 215

2 Ibid, P.218



በዚህም ጊዜ ፣ በጄኔራል ባራቲዬሪ ውሳኔ ከሦስት የተከፈለ ጦር በሦስት መስመር ከዚህ እንደሚከተለው ከአዲግራት ወደ ደብረ ኃይላ እንዲዘምት ተደረገ ።

፩ኛው የግራ ክፍል ጦር በማዦር ቶዜሊ መሪነት በአጽቢ በኩል ፣ ፪ኛው በመካከል የሚዘምተው ዋነኛው ጦር በጋልያኖ እየተመራ ግንባር ቀደም ሆኖ ከአዲግራት በአጉላዕ በኩል ወደ ይሎ ከዚያ በሸሊቆት በእንጣሎ በኩል ፣ ፫ኛው ያገር ተወላጅ ጦር ያለበት በማዦር አሜሊዎ የሚመራው በሐውዜን በኩል ተጉዞ እ. ኤ. አ. ጥቅምት 9 ቀን 1895 ዓ.ም. ደብረ ኃይላ ደረሰ ።

ዋናው አሳብ ፣ አዘንግቶ በድንገተኛ አደጋ ራስ መንገሻን ከነሰዋቸው ለመደምሰስ ስለሆነ ፣ በውስጥ ዐወቅ ባላገሮች እየተመሩ በስላች መንገድ ደብረ ኃይላ መድረሳቸው ታወቀ ። በዚያን ጊዜ ፣ በራስ መንገሻ ዘንድ ምክር ተይዞ ፣ "... ከእንግዲህ ወዲያ ከዚህ መሸሸ ለኛ ውርደት ነው ። ቢቀናን ተዋግተን አሸንፈን እንመለሳለን ። ባይቀናንም ስለ ሀገራችን ተዋግተን እንሞታለን ። እርስዎ ግን ቢማረኩም ፣ ቢሞቱም ፣ ላገር ውርደት ለኢጣልያ ደስታ ነውና ከሸዋ ጦር እስኪመጣ ድረስ ወደራስ ወሌ ግዛት ወደ ሰለዋ ተጠግተው ቢቆዩ ይሻላል" ብለው ራስ መንገሻን መከሩዋቸው ። የራሳቸውም አሽከሮች መቀሌ በነበሩበት ሰዓት ፣ "ጦርነቱን ለማድረግ ካፄ ምኒልክ ፈቃድ አላገኘንምና እንደዚሁ ወደ ሸዋ እየተላላከን ዝም ብለን በእንጣሎ እንቀመጥ" የሚል አሳብ ቀደም ብለው አቅርበው ነበር ።

ከዚህ በኋላ ፣ ራስ መንገሻ አሳባቸውን ተቀብለው ከደብረ ኃይላ ወደ ሰለዋ ተጓዙ ። እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ግን ፣ እዚያው ደብረ ኃይላ ሆነው ሲጠባበቁ በማዦር አሜሊዎ የሚመራው ያገር ተወላጅ ግንባር ቀደም ወታደር መንደር ሲያቃጥል አዩት ። ከዚያ የሁለቱ ወገን ወታደር ተቀራርቦ ሲዋጋ ፣ ምንም እነዚህ በርትተው ለመመከት ቢፈትኑ የኢጣልያኖቹ ወገን በመሣሪያ ጥራት ፣ በሠራዊት ብዛት ስለበለጡ ፣ በቀላል ጦርነት አሁንም ጣልያኖቹ አሸነፉ ። ከኢጣልያኖች ወገን የሞተው 11 የቆሰለው 30 ሲሆን ፣ ከኢትዮጵያ በኩል የሞተው 30 የቆሰለው አንድ መቶ ግድም መሆኑን ባራቲዬሪ[1] ሲያመለክት ፣ ከኢጣልያ ወገን ሟቾቹ ሁሉም ያገር ተወላጆች መሆናቸውን ቤላቪታ ይገልጻል ።[2]

1 Memoire d'Afrique . . P. 218

2 Adua - E. Bellavita, P. 540

በጦርነቱም ላይ ትንሽ ጦር ይዘው ገትረው በዠግንነት የተዋጉት ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ከፉኛ ቆስለው ተማረኩ ። ከሸዋ የመጡ መሆናቸውን ስላወቁ ፣ በሸዋ ያለውን ወታደራዊ ድርጅትና የጦር አቅዋም ማዠር ሳልሳና ጋዜጠኛው ሜርካቲሊ ሲጠያይቁዋቸውና በዚሁ ጊዜ ቴኔንቲ ሞዜቲ በእንጣሎ ሲያክማቸው ሰነበተ ። ቀጥሎም በደንብ ታክመው ሲድኑ መሣሪያ ይሆኑናል በማለት ከእንጣሎ ወደ አሥመራ አዛወሯቸው ። ጋዜጠኛው ሜርካቴሊ ከደብረ ኃይላ ምርኮኞች የተገኘ ወሬ ብሎ ለማስጠንቀቅ በጻፈው ላይ ፣ “ምርኮኞች ያሁኑ ጦርነት ምንም አይደለም ፤ እውነተኛውን ጦርነት ከአንድ ወር ዐሥራ ሁለት ቀን በኋላ ታገኙታላችሁ ብለዋል” ይልና ከሁለት ቀን በኋላ ደግሞ ፣ “ሸዋ ለጦርነት ተዘጋጅቷል ፣ ትልቅ ጦርነት ሳይሆን አይቀርም ፣ የንጉሡ ሠራዊት በሚያቀባብል ጠመንጃና በብዙ ጥይት ታጥቋል ። መድፍና መትረየስም በብዛት አግኝቷል ፣ ወታደሩም ዘወትር ተኩስ ይማራል” ብለው ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም እንደ ነገሩት በጽሑፍ ያመለክታል።[1]

ምንም እንኳን ፣ አንዳንድ ጊዜ ጠንክረው ማጥቃት ወይም መከላከል ቢችሉም ፣ የኢጣልያኖች ጠባይ አብዛኛውን ጊዜ አሸናፊ ሲገጥማቸው ሽሽታቸውና መርበድበዳቸው ከመጠን በላይ ሲሆን ፣ በዚያው መጠን ተሸናፊ ያገኙ እንደሆነ ጉራቸውና ኩራታቸው የበዛ ነው ። በደብረ ኃይላ ፣ ያውም ራስ መንገሻ ሳይገጥሙ ፣ ቁጥሩ በጣም ባነሰ ጦር ላይ ስለ ቀናቸው ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሁሉም በደስታ ወደፊት ይገሠግሡ ጀመር ። በሸዋ የሚደረገውን የጦር ዝግጅት ቢሰሙትም ከንቀት፣ የተነሣ እንሸነፋለን ብለው በፍጹም አልጠረጠሩም ።

በዚህ ዓይነት ፣ ከደብረ ኃይላ ጦርነት በኋላ ወደፊት እየገሠገሡ እስከ አላጌ ፣ ከዚያም አልፈው አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ዘልቀው በደረሱበት ሹም ሽር ማድረግ ፣ ምሽግ መመሸግና ወታደር እየሰበሰቡ ለውጊያ መዘጋጀት ያዙ ። በዚሁ ጊዜ በራስ መንገሻ ትእዛዝ አምባ አላጌ ታስረው የነበሩትን ራስ ስብሐትን ጄኔራል አሪሞንዲ ከእስራት ፈትቶ በአጠገቡ አስቀመጣቸው ። ውሎ አድሮም ከተመከረ በኋላ ፣ አጋሜን እንዳይሰጣቸው ከርሳቸው በፊት የኢጣልያ ጦር ራስ መንገሻ የሾሟቸውን ሹም አጋሜ ተስፋዬን አባርሮ የአጋሜን ግዛት ለራሱ ታማኝ ለደጃች ሐጐስ ተፈሪ ሰጥቶ ነበር ።በዚህ ምክንያት ፣ አሁን ሐጐስ ተፈሪን መሻር ስለማይቻል ፣ ለራስ ስብሐት ሁለት አውላሎን ጨምሮ የእንደርታን ግዛት ሰጣቸው ። በእንዳ መሆኒም ደጃች አሊን ሾሞ በበላይ ያስተዳድር ጀመር ።

1 Italia ed Etiopia . . .Conti Rossini PP. 164- 170.



በዚህ መካከል ፣ በዋናው ጠቅላይ አዛዥ በጄኔራል ባራቲዬሪና የትግሬና የአጋሜ ግዛት አስተዳዳሪ ብሎ በሾመው በጄኔራል አሪሞንዲ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ ። ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ “እስከ አላጌ ድረስ የያዝነው አገር ሰፊ ስለሆነ ፣ የያዝነውን እያጠናከርን እንደ ጊዜው ሁኔታ ወደፊት እንራመድ ፣ ያለዚያ ከዋናው የጦር ሠፈር ድርጅታችን ከምጥዋና ከአሥመራ ፣ ከአዲግራትም በጣም ርቀን 360 ኪሎ ሜትር አልፈን ስንሔድ ደህና አድርገን ወደማናውቀው ተራራማ አገርና ሕዝብ መካከል ስንዘልቅ ፣ ቁጥጥሩም ግንኙነቱም ያስቸግረናል” ሲል ፤ ጄኔራል አሪሞንዲ ፣ “አሁኑኑ የወታደራችን ሞራል ከፍ ባለበት ሰዓት ወደፊት ገሥግሠን ከሸዋ ወደ አሸንጌ የሚጓዘውን የሸዋን ጦር አለበት ድረስ ሔደን እንውጋው” አለ ።

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ የዚህን ጉዳይ ከፖለቲካና ከጦር አማካሪዎቹ ጋር ተመካክሮ እስከ አላጌና እስከ አሸንጌ ድረስ የያዝነው አገር ብዙ ነው ። ስለዚህ በተያዙት አገሮች በሚገኙት ከተሞች በመቀሌ ፣ በዕዳጋ ሐሙስ ፣ በእንጣሎና በደብረ ኃይላ ፣ በአላጌ ምሽጋችንን እያጸናን ለዓድዋና ለመቀሌ ፣ ለምጥዋና ለአሥመራ አማካይ በሆነው በአዲግራት ዋና መቀመጫችንንና የጦር ሠፈራችንን አድርገን ወታደራችንን የበለጠ እናጠንክር ።በዚሁም ጊዜ የላስታን ሕዝብ እየሰበክን ፣ የራያንና የአዘቦን ሕዝብ ከወሎና ከአውሳ ሕዝብ ጋር በማስተባበር ፣ በምኒልክ ላይ የሚነሡበትን መንገድ እያዘጋጀን እንቆይ የሚለው የባራቲዬሪ አሳብ ጸና ።

# ምዕራፍ ሐያ ሁለት

## የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መሳፍንት ከፋፍሎ ለማስነሣት ያደረገው የመጨረሻ ሙከራና ያፄ ምኒልክ ያጸፋ መልስ

ኰሎኔል ፒያኖ ፡ ከትራቬርሲ ጋር ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ ከተመለሰ በኋላ ሁለቱ መንግሥታት በፊታቸው የተደቀነው በትክክል የኃይሉ መንገድ ብቻ ነው ። ላፄ ምኒልክ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትርም ፡ እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ፡ እንደ መልካም አገረ ገዥም ሆነው የወን ድም ንጉሣቸውን በቅን ልቦና ፡ በትሑት ሕሊና የሚያገለግሉት ራስ መኰንን ፡ የኢጣልያን አገር የጦር ኃይሉን ድርጅት ፡ የመድፍና የመትረየሱን ፡ የጠመንጃውን ብዛት ከነፋብሪካው በየከተማው እየዞሩ ጐብኝተው ተመልሰዋል ። ይኸንኑ ለንጉሡ በዝርዝር ስለ ገለጹ ፡ ከእንደዚህ ያለው መንግሥት ጋር መዋጋት ዋዛ አለመሆኑን ምኒልክ ተረድተዋል ። አብዛኛውን ጊዜ ሌላው "እንበለው" ሲል እነርሱ የሰላም መንገድ ይከተሉ የነበረበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው ። ይሁን እንጂ ፡ የሰላም መልክ በሚያሳዩበት ጐን በሰላማዊ እነጋገር ኃያል የሆነውን የአውሮፓ መንግሥት እያዘናጉ የመሣሪያውን ስብሰባ ፡ የወታደሩን ድርጅት በግልጽም በስውርም በትጋት ማካሔዳቸውን ቀጥለው ነበር ።

የኢጣልያና የእንግሊዝ መንግሥታት ፡ ቀድሞ ከነበራቸው የወዳጅነት ውል በቀር እ.ኤ.አ. በግንቦት 5 ቀን 1894 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒና የእንግሊዝ እምባሳደር ሰር ፍራንሲስ ክላር ፎርድ ፡ ሮማ ላይ በውጋዴንና በእንግሊዝ ሱማሌ ወሰን ስላለው ጉዳይ የፕሮቶኮል ፊርማ ተፈራርመው ወዳጅነታቸውን አጽንተዋል ። በዚሁ ዓመት በሰኔ ወር ኰሎኔል ፒያኖ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ኢጣልያ በእንግሊዝ እንደ ተደገፈች ወሬው አዲስ አበባ ደርሷል ። የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ፡ እ.ኤ.አ. በ1843 ዠምሮ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር የሸዋ ንጉሥ ወጥነውት የነበረውን የወዳጅነት ውል እንደገና በማደስ ፡ በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያና የፈረንሣይ ወዳጅነት ባዲስ መንፈስ ተቀስቅሷል ። በዚያው አንጻር ከመስኮቦች ጋር ያለው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተመሳሳይነት እየተጠቀሰ ፡ መስኮብና ኢትዮጵያ

መላክተኛ እየተለዋወጡ ወዳጅነታቸውን አጠባብቀዋል ። የኢትዮጵያ ዕድልም ይበልጥ ሲቃና በዚህ ጊዜ ፈረንሳይና መስኮብ ባንድ ወገን፣ እንግሊዝ በሌላው ወገን ሆነው ጀርመን ፣ አስትሪያ ፣ ኢጣልያ የተዋዋሉትን የሦስቱን የቃል ኪዳን ስምምነት (Triple Alliance) ለማፍረስ የጋራ ጉራ በመፍጠራቸው ሁኔታው ለኢትዮጵያ የፖለቲካም የወታደራዊ ጥቅምም ሰጥቷል ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከነዚህ ሁለት መንግሥታት ጋር ወዳጅነታቸውን በሚያጠባብቁበት ጊዜ ፣ የኢጣልያ መሪዎችም እነፒያኖ ወደ ሮማ ከተመለሱ በኋላ ከምኒልክ በኃይልም ፣ በዘዴም የውጫሌን ውል የማጽደቁና የመረብን ወሰንነት የማግኘቱ ጉዳይ ከሸፈባቸዋል ። አሁን ያላቸው ምርጫ መሳፍንቱን እንደገና ባዲስ ስጦታና ተስፋ አባብሎና ገፋፍቶ በምኒልክ ላይ ከማስነሣቱ ላይ ዐርፏል ።

ፒያኖና ትራቬርሲ ፣ በሐምሌ ወር ላይ ኢትዮጵያን ለቀው ወደ አገራቸው ተመልሰው የመልእክታቸውን አለመሳካት በራፖር ለመንግሥታቸው አቀረቡ ። በሚቀጥለው በነሐሴ ወር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ የሚከተለውን መመሪያ በምስጢር ለኤርትራው ገዥ ለጄኔራል ባራቲዬሪ እንደዚህ ሲል አስተላለፈለት ።

> ይቅርታ የማይደረግለት የምኒልክ አቅዋም አንድ የመከላከያ ፕላን እንድናበጅ ያስገድደናል ። በዮሐንስ ላይ ምኒልክን እንደ ደገፍን አሁን የምኒልክን ባላንጦች ማበረታታት አለብን ። በትግሬ መንገሻ ፣ በሐረር መኰንን ከግል ምኞታቸው በቀር በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የጥላቻና የበቀል ምክንያት አያጡም ። ምኒልክ ሲሞት በኢጣልያ የበላይ ጠባቂነት ሥር የንጉሠ ነገሥታዊው ግዛት በደቡብና በሰሜን የተከፋፈለ ሁለት መንግሥት ሊሆን ይችላል ። በሌላም አኳኋን ለኛ በሚጠቅመን ረገድ ሌላ መንገድ ሊገኝ ይችል ይሆናል ። አሳቡን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ቀላል አይደለም ። ነገር ግን ሊሆን የሚችል ነው ። ክቡርነትዎ አጥማጅና ዘዴ በመፈለግ ከመንገሻና ከመኰንን ዘንድ ልንልካቸው ለሰምንችለው ብልህነታቸው የተረጋገጠውን (ሰላዮችና ቀስቃሾች) ወኪሎች አሳብዎን እንደሚገልጡልኝ አምናለሁ ።[1]

ባሪቲዬሪ ፣ ከክሪስፒ ለተላለፈለት መመሪያ የሰጠውን መልስ ለጊዜው ማግኘት አልተቻለም ። ይህም ምናልባት አብዛኛውን ጊዜ እንደ

1. Italia ed Etiopia, Conti Rossini, P. 105 Italia in Africa, Angelo Del Boca, P. 508.



ዚህ የመሳሰለውን ምስጢራዊ ጉዳይ የሚለዋወጡት በቁጥር ቃል ስለሆነ ፣ ቁጥሩ ተፈትቶ እጽሑፍ ላይ ባለመስፈሩ ይሆናል ።

በዚህ ፈንታ ፣ ከዚህ ጉዳይ ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲኞር ብላን ከሮማ እ.ኤ.አ. በ16 መስከረም 1894 ዓ.ም ጥብቅ ምስጢር ብሎ ቁጥር 34947 ለዠኔራል ባራቲዬሪ ያስተላለፈለት ቃል እንደዚህ የሚል ነው ።

> ለክቡር የኤርትራ ቅኝ አገር ገዥ. . . ቁጥር 1563. . . ስለ ሐረር የጻፉልኝን ራፖር በምስጋና ተቀብያለሁ ።
>
> በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና (ክሪስፒ) በክቡርነትዎ መካከል በ10 ፣ በ11 ፣ በ12 ቀን ባለፈው ወር (ሐምሌ) ልውውጥ የተደረገው ቴሌግራም እኔም ወድጄ የተስማማሁበት በአቢሲኒያ ጉዳይ ለምናደርገው እርምጃ መመሪያችን ነው ። የምናደርገው ሁሉ በሰሜን በራስ መንገሻ ዘንድ ፣ በደቡብ በራስ መኰንን ዘንድ የኛ የበላይነት ስሜት የበለጠ ከፍ እያለ እንዲሔድ ማድረግ ነው ። እነሱን ከፋፍሎ በነዚህ ሁለት አውራጃዎች ላይ ኢጣልያ የበላይ ጠባቂነቷና በቁጥጥሯ ከጊዜ ጋር ሊረጋገጥ ይችላል ።
>
> የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ (ክሪስፒ) በትግሬ በኩል ላለው ለመቶ አለቃ ሙላዚኒ አስፈላጊውን መመሪያ እንዲሰጡት ፈቅደዋል ። እንደዚሁም በራስ መኰንን ዘንድ ለሚሆነው ለመጀመሪያው መረጃ አሰባሰብ ለካቫሊዬር ፌልተርም ፣ እንደዚሁም ምንም እንኳ አስቸጋሪ መሆኑ ቢሰማኝ ፣ በራስ መኰንን በኩል ላለው ጉዳይ ከፌልተር የተሻለና ከፍ ያለ ሰው መምረጥ እንዳለብን ይሰማኛል ። የሆነ ሆኖ ፣ ክቡርነትዎ ከመንግሥት ትእዛዝ ሳይጠብቅ የተመቸውን ጊዜ መርጠው ሥራውን ለመጀመር ትእዛዝ መስጠት ይችላሉ ።
>
> በኔ በኩል የምጨምረው በቅኝ አገዛዝ ፖለቲካችን ኢጣልያን በሚመለከተው ጉዳይ የሐበሻ ጉዳይ ታላቅ ቁም ነገር ያለው ሆኖ መገኘቱንና የዚህም ጉዳይና አሠራራችን ሁሉ ያሁኑም የመልእክታችን ልውውጥ ምስጢሩ በጥብቅ መጠበቅ አለበት ። ፊርማ ብላን ።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የበለጠ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ፣ በተለይ በንጉሡ በኡምቤርቶና ቅኝ አገር በሚፈልጉት በቀኝ ክንፍ አማካሪዎች ዘንድ ታላቅና ብልህ መሪ ተብሎ ግምት የተጣለበት ነው ። በተደጋጋሚ ጠቅላይ ሚኒስትርነትንም የያዘው በዚሁ ምክንያት ነው ። ነገር ግን ፣ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን የጠነከረ አቅዋም በትክክል ሳያጠና ይኸን የመሰለውን መመሪያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አማካይነት በቀላሉ ሲሰጥና አሳቡ ከሥራ ላይ እንደሚውል ማመኑ ሞኝነቱን ወይም ችላ ባይነቱን ያሳያል ። በጠቅላላው ኢትዮጵያ ላይ የኢጣልያንን የበላይ ጠባቂነት በምኒልክ በኩል ፈትኖ አልሆንለትም ። ይኸ ሁሉ ውዝግብ የተፈጠረውም በዚህ ምክንያት መሆኑን

እየተገነዘበው ፣ ሁለቱን መሳፍንት ራስ መኰንንንና ራስ መንገ
ሻን በምኒልክ ላይ በማስነሣት ፣ በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ ሁለት
መንግሥታት አቋቁሞ ፣ ኢጣልያ ከሁለቱ የመንግሥታት ኮርቻ ላይ
ተቀምጣ እንደልቧ ጋልባ መላ ኢትዮጵያን ለመግዛት እንድትችል
ከማሰብም ፣ ከመምከርም ወደኋላ ለማለት አልቻሉም ።

ከርሱ ግምት ትናንት መረብ ላይ ወንጌልና መስቀል ቀርቦ በመ
ሐላ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ከተስማሙ በኋላ ፣ የተከዱት ራስ መን
ገሻ ፣ የተዋዋላቸው ጄኔራል ጋንዶልፊ ከተሻረና በርሱ እግር ከመ
ጣው ከባራቲዬሪ ጋር ንግግር እንኳ የተነፈጋቸው መስፍን ፣ ዛሬ እን
ደገና እኛ ከፈቀድን ኑ ብንላቸው አቤት ብለው ሮጠው ይመጣሉ ።
መሣሪያም ካገኙ አፈሙዛቸውን ያለማመንታት ወደ ምኒልክ ያዞራሉ
ነው ። ከሁሉ ደግሞ የሚገርመው ፣ ራስ መ ኰንን ያፄ ምኒልክ አክ
ስት የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ልጅ መሆናቸውን ፣ ከልጅነት እስከ ዕው
ቀት ባፄ ምኒልክ ቤት ያደጉት ፣ ከባላምባራስነት ሦስት ደረጃ (ግራዝ
ማች ፣ ቀኛዝማች ፣ ፊታውራሪ) ዘለው በደጃዝማችነት ደረጃ የሐረር
ገዥ የሆኑት ፣ አሁንም ከጨርጨር ግዛት ጭማሪ ጋር በራስነት ማዕ
ረግ የከበሩት ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ የበኵር ልጅ መስለው በሙሉ
ሥልጣን የሚሠሩት ፣ በተለይ በውጫሌ ውልና በወሰኑ ጉዳይ የኢጣ
ልያኖችን ማጭበርበር እየተመለከቱ የሚናደዱት ፣ መንገሻን የከዱ
ኢጣልያኖች አሁን ምኒልክን ክዳና በሐረር እናንግሥህ ቢሏቸው ፣ እን
ደምን ሊያምኑንና መሣሪያ ሊሆኑን ይችላሉ ብለው አለመጠርጠራ
ቸው ፣ የኢጣልያኖችን የሞኝነት ብልጠት ሊያሳውቅ ከማስቻሉም
በላይ አስገራሚ ነው ።

ነገር ግን ፣ ይኸን የመሳሰለው አሳብ በገራገሮቹና ከንቱ ድንፋ
ታና ጉራ ከሚያጠቃቸው ኢጣልያኖች ዘንድ የሚደቀነው በጠቅላ
ላው የጥቁርን ዘር ከነአቅዋሙ ከመናቃቸው የተነሣ መሆኑ አይጠረ
ጠርም ። በነርሱ ግምት በአፍሪካ የሚገኝ ሁሉም ቂል ነው ። አንድነ
ትም ፣ ኅብረትም ፣ ያገር ፍቅርና የነጻነትም ስሜት የለውም ። ላበላ
ውና ላለበሰው ይሞታል ። ስለዚህም ነው አፍሪካውያኑ በቅኝ አገዛዝ
ሥር ለመውደቅ የበቁት ብለው ፣ የኢትዮጵያንም በነጻነት መኖር
በአጋጣሚና በፈረንጆች ቸልተኝነት እያመካኙ ፣ ኢጣልያ በቀላሉ
መሳፍንቱን ከፋፍላ ልትገዛቸው እንደምትችል በተለይ የቀኞቹ ክፍ
ሎች ያምናሉ ።

ይሁን እንጂ ፣ በነዚሁ ጐን በምክር ቤቱ በግራ በኩል ተቀም
ጠው በፊት ዐፄ ዮሐንስን ፣ አሁንም ዐፄ ምኒልክን የሚደግፉ
ነበሩበት ። ጣልያኖቹን ሁሉ ባንድ የከፋትና የቂልነት መስመር



መመልከት ትክክል አይሆንም ። በዶጋሊ ጦርነት ጊዜ በራስ አሉላ
መሪነት ባለቁት 500 የኢጣልያ ወታደሮች ምክንያት የቀኞቹ በራስ
አሉላና ባፄ ዮሐንስ ተናደው ፣ "ጦር ልከን እንበቀል ፤ ደርቡሾቹን
በኢትዮጵያ ላይ እናስታጥቅ" እያሉ ሲያውኩ ኡሊስ ባርቢዬሪ
የሚባለው አማካሪ ፣ "ጥፋተኞቹ አበሾች አይደሉም ። በዶጋሊ የሞ
ቱትን መበቀል ከፈለጋችሁ 5 መስቀያ አበጅታችሁ እነርሱን ወደ
ሞት አገር የላኩዋቸውን ባለሥልጣኖች ፣ ባንዱ መስቀል ላይ ዲ
ሮቢላን (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረ) ፣ በሁለተኛው ላይ ሪኮቲን
(የጦር ሚኒስትር የነበረ) ፣ በሦስተኛው ላይ ሞቺኒን ፣ በአራተኛው ላይ
አርጌውን ደቀስቋሳ ደ ፕረቲስን (ጠቅላይ ሚኒስትር) የነበረ ፣ አምስተ
ኛውን ለክሪስፒ መድቡት" ያለውን ማስታወሱ ይበቃል ።[1] እነዚህ
ሁሉ ስቅላት የፈረደባቸው ባለሥልጣኖች የምጥዋን መያዝና ቀጥሎ
ያለውን የኢትዮጵያ መሬት ወረራ በኃይል የደገፉና የመሩ ናቸው ።

የክሪስፒና የብላን መንግሥት ፣ መሳፍንቱን ባፄ ምኒልክ ላይ ማስ
ነሣት ለቅኝ ግዛት መስፋፋት መፍትሔ መሆኑን እንዳመነበት ፣ ዐፄ
ምኒልክም በርሱ ውስጥ ያሉትን የኤርትራ መኳንንት ማስከዳት ጣላ
ትን ለማዳከም የሚረዳ መሆኑን በበኩላቸው ተገንዝበዋል ። በዚሁ
መሠረት ፣ ራስ መንገሻ አዲስ አበባ ውስጥ ከዐፄ ምኒልክ ጋር ተወያይ
ተው ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ ፣ እርሳቸው ለኢጣልያ መሣሪያ በመሆን
ፈንታ እንዲያውም ለኢጣልያኖች ታማኝ ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩ
ትን ደጃች ባሕታ ሐጐስን በምን አኳኋን አስከድተው ከኢጣልያኖቹ
ሲዋጉ እንደ ሞቱ ባለፈው አንብበናል ።

እንደዚሁም ፣ ነገሩ እዳር አልወጣም እንጂ ፣ ደርቡሾቹን በኢትዮ
ጵያ ላይ ለማስነሣት ተሞክሮአል ። በመጨረሻ ደግሞ ፣ ጣሊያኖች አሳ
ባቸውን ለውጠው ራሳቸው በከሰላና በአቆርዳት ከደርቡሾቹ ጋር በሚ
ዋጉበት ጊዜ ክርስቲያን ለክርስቲያን መረዳዳት ይገባልና እርዱን
ብለው ላፄ ምኒልክም ፣ ለራስ መንገሻ ዮሐንስም ጥያቄ አቅርበው
ነበር ። አሁን ግን ፣ የኢጣልያ ጠላትነትና አገር ወራሪነት ግልጽ
እየሆነ መጥቶ ሁለቱ መንግሥታት በጠብ ተለያይተዋል ። ኢጣልያኖ
ቹም ከመረብ እያለፉ የትግሬን አውራጃ መውረር ሲጀምሩ ፣ በምዕ
ራብ በኩልም ለመስፋፋት በከሰላና በአቆርዳት ተዋግተዋል ። የከሰ
ላን ከተማ እጅ ማድረጋቸው በአዲስ አበባ ተሰምቶ ስለነበረ ፣ ዳግ
ማዊ ምኒልክ በኢጣልያኖች ላይ ደርቡሾቹን ለማስነሣት የሚችሉበት

1 Gli Italiani in Africa - Angelo Del Boca, PP. 287 - 288

ጉዳይ በቤተ መንግሥቱ ውይይት ተነሥቶ አንዳንዶቹ ሱዳንን ፣ "ዘራ
ፊና ቀማኛ ናቸው" ሲሉ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ለኛ ጠላትነት ከኢጣልያ
ደርቡሽ ይሻለናል ። ምክንያቱም ደርቡሽ ባገር ውስጥ ሲገባ ያገኘ
ውን ዘራርፎ ወደ አገሩ ይመለሳል ። ጣልያን ግን ፣ መሬቱን ራሱን
ይሠርቃል" አሉ ይባላል ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከደርቡሾች ጋር በኢጣልያ ላይ ለመስማማት ራስ
ቢቶደድ መንገሻ አቲከምንና የቋራውን ገዥ ራስ መሸሻ ቴዎድሮ
ስን ጉዳዩን እንዲያጠኑ ከደጃች ቢተው ጋር ተመካከረው ከደርቡሾቹ
ጋር በገዳሪፍ በኩል ግንኙነት እንዲደረግ ንጉሠ ነገሥቱ አዘው ነበር ።
በዚሁ መሠረት ፣ ደርቡሾቹን ለመሳብ ሲሉ በሚያዝያ ወር 1887 ዓ.ም
እንደዚህ የሚል ደብዳቤ ጽፈው ነበር ።

> በኔና በናንተ መካከል አንድ ጊዜም ጦርነት ተደርጎ አይታወቅም...
> አሁን ከዚህ ቀደም ከመጣብን ጠላት ሁሉ የባሰ ጠላት መጥቶብናል ።
> የመጣው እኔንና እናንተን ባሪያ አድርጎ ለመግዛት ነው ። የኔና
> የናንተ ቀለም አንድ ነው ። ስለዚህ የጋራ ጠላታችንን ለማባረር
> እንተባበር ።

በዚሁ መሠረት ፣ ደጃች አራዶ (አርአዶ) የሚባሉ ካፄ ምኒልክ
ወደ መተማ (መጺጋ —ካፍታ) ተልከው ከደርቡሾች ጋር መነጋገራቸ
ውን ፣ የዓድዋለትም ኡስማንኤል አዝራ ፣ ቅና አሊ ፣ ኤት ታይሽ የሚ
ባሉ የሱዳን ተወላጆች ተባብሮ የመዋጋቱን ነገር ለመወያየት በን
ጉሡ ሠፈር መታየታቸውን የኮንቲ ሮሲኒ መጽሐፍ ይጠቁማል ። የዓ
ድዋለት ግን ጦርነቱን አልተካፈሉም ። ከጦርነቱ በኋላ በሌላ ቀን
በተርኩፍ መጥተው ከኮሎኔል ስቲፋኒ ጋር ተዋግተው መሸነፋቸውን
ያረጋግጣል ።[1]

በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች መሳፍንቱም ፣ መኳ
ንንቱም ፣ ምሁራኑም ፣ አስተርጓሚዎችም ፣ በጠቅላላው የቤተ መንግ
ሥቱም ፣ የቤተ ክህነቱም ሰዎች እንደ እቴጌ ጣይቱ ቤቶቹ ሳይቀሩ
በሚወዳቸውና በሚተማመንባቸው ሕዝብ እየተደገፉ ፣ እንዳንድ ቤተ
ሰብ ሆነው የጠላትን ወረራ ይቃወሙ ነበር ። ስለዚህም መሳፍንቱን
በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለማስነሣትና እርስ በርስ አዋግተው የመንግሥ
ቱን አቅዋም ለማድከም ፣ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች የሚያውጠነጥኑ
ትን ሤራና ውስጣዊ አድማ እየተከታተሉ ያከሽፉት ነበር ። እንዲሁም

---

1 Italia ed Etiopia -Conti Rossini (ከዠኔራል ቢጋና) Veigano Ettore Guesseppe
ራፖር ላይ ገጽ 135—136



በዚያው አንጻር በጣልያን ላይ ጠላት ለመፍጠር በኢጣልያ ሥር
በሹመትና በገንዘብ እየተደለሉ የሚያገለግሉትን ሹማምንት ለማስ
ከዳት በበኩላቸው ምኒልክና ጣይቱ ከአበሮቻቸው ጋር ይጣጣሩ
እንደነበረ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል ።

ባለፈው ጊዜ ፣ የኢጣልያ ሰላዮች በንግድና በፖለቲካ ወኪልነት፣
በሕክምና ፣ በመሐንዲስነትና በአገር መርማሪነት በየአውራጃው ተሠ
ማርተዋል ። በየመሳፍንቱ አጠገብ ተሰግስገው ለመሳፍንቱ እንደ
ብርቅ የሚቆጠረውን የጠመንጃ ፣ የሽጉጥ ፣ የሥጋጃ ፣ የጨርቃ ጨር
ቅና የሽቶ ሽቀጥ እያደሉ ወሬ ፣ ለሚያመጣ ጸሐፊና አስተርጓሚ የገን
ዘብ ጉርሻ እያጠገቡ በመስለል በኢትዮጵያ መንግሥት አቅዋም ላይ
አድማ ያውጠነጥናሉ ። እዚሁ አገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው
ተንኮላቸውን በተንኮል ከመቃወም በቀር በሮማ ምክር ቤት የቀኙና
የግራው ክፍል የሚያደርገውን የከረረ ጠብና ክርክር ምኒልክና ተከ
ታዮቻቸው በሥፍራው በመገኘት ጠቡን ለማፋፋም ቀርቶ ጉዳያቸው
ንና ሰላማዊ አቅዋማቸውን ፣ ጥቃታቸውንና ብሶታቸውን በተቃዋሚ
አማካሪዎችና በጋዜጦቻቸው በኩል የመግለጽ አቅም አላገኙም ።

በታላቁ የምክር ቤት እነኡሊስ ባርቢዬሪ ፣ እነገብርኤል ሮዛ ፣ እነ
ናፖሊዎን ኮላጅያኒ ፣ እነፊሊፖ ቱራቲ ፣ እነአንድሪያ ኮስታ ፣ እነኢም
ብሪያኒ ማቲዎ ከነጓደኞቻቸው ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተማረ ያል
ሠለጠነ በአውሬነት የሚኖር ነውና ኢጣልያ ይዛ ልታሠለጥነው ይገ
ባል" ከሚሉት የቀኝ ክፍሎች ጋር ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ ሥል
ጣኔ ያለው ሕዝብ ነው ፤ አሁንም ሰላምና ጸጥታ በሚፈልገው በምኒ
ልክ መሪነት የአውሮፓን ሥልጣኔ ባገሩ ውስጥ ከማስገባት ላይ ይገ
ኛል ። አበሻን እናሠልጥን ከማለት የራሳችሁን ወደኋላ የቀረውን አው
ራጃ (ሲሲል ሳርዲኛ . . .) አሠልጥኑ መሬቱን አልሙ" እያሉ መጨ
ቃጨቃቸውን ጭምጭምታውን በፈረንሳዮቹ በነሞንዶን ፣ በመስኮ
ቦቹ በነሌዎንቴቭ በኩል ዘግይቶ ከመስማት በቀር ችሎታቸው ከዚህ
አልፎ ሮማ አይደርስም ።

በአለፈው ዘመን ፣ የውስጡ የርስ በርስ ጦርነታችን ፣ የቤተ ክህ
ነቱ ስለ ሥልጣኔ ያለው ጥብቅ ተቃዋሚነት ፣ የነገሥታቱና የመሳፍ
ንቱ ባለጉልታዊ አቅዋም ሁሉም ተደራርበ ኢትዮጵያን ከሥልጣኔ
ወደኋላ አስቀርቶ ከዚህ ሁኔታ ላይ ማስገኘቱ አሳዛኝ መሆኑ ቢታወ
ቅም ፣ በዚያው ባላቸው የኋላ ቀር አቅዋም ፣ የኛዎቹ ፖለቲካውን በፖ
ለቲካ ፣ ወታደራዊውን በወታደራዊነት አቅዋም እየታገሉ የመጨረሻ
አሸናፊ መሆናቸው ከአድናቆት ጋር ያስመሰግናቸዋል ።

# ምዕራፍ ሐያ ሦስት

## ስለ ዋግሹም ብሩ መያዝ — ስለ መሐንዲሱ ካፑቺ መታሰር

ዋግሹም ብሩ፣ ከላይ ከነገደ ዛጉዬ ከወረዱት ከላስታ ባላባቶች ከዚህ እንደሚከተለው ይወለዳሉ ። የላስታው ወንድ ወሰን ላዔ ፋሲል በስድስተኛ ደረጃ የምትወለደዋን ወርቅ ውኀን አግብተው ደጃች በቀቱንና ራስ ኃይሉን ፣ ደጃች ተድላን ፣ የዋድላውን ራስ መሸሻንና ወይዘሮ አይቼሽን ይወልዳሉ ።

ከዋግ ደግሞ ፣ ዋግሹም ክንፉ ዋግሹም ወሰንንና ወይዘሮ በተሐን ይወልዳሉ ። ወይዘሮ በተሐ ከአቶ አምኃ ዋግሹም ገብረ መድኅንን ፣ ገብረ መድኅን ከወይዘሮ አይቼሽ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስንና ዋግሹም ብሩን ይወልዳሉ ። ዋግሹም ወሰን ደግሞ ዋግሹም ተፈሪን ፣ ተፈሪ ዋግሹም ከበደን ፣ ዋግሹም ከበደ የታወቁትን አርበኛ ማገር ዠኔራል ኃይሉንና ደጃች በላይን ይወልዳሉ ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባለቤት ወይዘሮ ላቀች የዋግሹም ብሩ ልጅ ናቸው ።

ዋግሹም ብሩ ፣ ከወንድማቸው ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ጀምሮ ባፄ ዮሐንስም ፣ አሁንም ባፄ ምኒልክ ጊዜ የዋግሹምነቱን ሹመት ይዘው ላስታንና ዋግን ያስተዳድራሉ ። አዲስ አበባ በመጡ ጊዜ ፣ በታላቁ ቤተመንግሥት በአዳራሹ ግብር በተደረገበት ሰዓት ሌሎች ራሶች በብር ሰንና ብርት እጃቸውን ታጥበው ሲበሉ ፣ ለዋግሹም ብሩ እንደ ቆየው ልማድ የወርቅ ሰንና ብርት ቀርቦላቸው መታጠባቸውን ፣ ዋግሹሙም ሁለት ጊዜ ብር በእጃቸው ተርፍሰው እብርቱ (ማህን) ላይ ማፍሰሳቸውን ከዚህ በፊት ተገንዝበናል ።

እርሳቸውም ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስም ከአዲስ አበባ ወደ የግዛታቸው እንደ ተመለሱ ራስ መንገሻ ከኢጣልያኖቹ ጋር በኵዓቲትና በሰንዓፌ ሲዋጉ የጦርነቱን ወሬ በጽሕፈት አድርገው ወደንጉሠ ነገሥቱ ልከዋል ፡፡ ዋግ ሹም ብሩና ራስ መንገሻ በወሰን እየተጣሉ የቆየ ጠብ ነበራቸው ። ምናልባት በ1863 ዓ.ም. ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስና ዐፄ ዮሐንስ ተዋግተው ያፄ ዮሐንስ አሸናፊነትና ዙፋን መቀማት ቂሙ ከወንድማቸው ከዋግሹም ብሩ ገና አልጠፋም ይሆናል ። በዚሁ የተነሣ ራስ መንገሻ ከኢጣሊያኖች መዋጋታቸውንና የርሳቸውንም ጠብ ገልጠው

ወዳዐፄ ምኒልክ ልከው ኖሮ ንጉሠ ነገሥቱም፣ "ውሾች እርስ በርስ ሲጣሉ ሌላ አውሬ ሲመጣባቸው የራሳቸውን ጠብ አቁመው ጠላታቸውን ባንድነት ይመክታሉና እናንተም ተስማምታችሁ ጠላትን መክቱ። የሚያስታርቃችሁም ቁም ነገረኛ አቶ በየነን ልኬያለሁና ታረቁ። የኢጣልያኖችንም ወረራ ራስ መንገሻ ስለ ጻፈልኝ፣ ለአውሮፓ መንግሥታትና ለጣልያኖችም ጽፌያለሁ። የአቶ በየነን* ቃል ደህና አድርገህ አድምጠው። ደብዳቤውንም እንብበህ ከሰው እጅ እንዳይገባ መልሰህ ላክልኝ። እስከዚያም ስንቅ እያዘጋጀህ ጠብቀን" የሚል ለዋግሹሙ ጽፈውላቸው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን ለመጻፍ የተገደዱት፣ "ራስ መንገሻ በኢጣልያኖቹ በተሸነፉበት ወቅት ዋግሹሙ ከግዛታቸው ከላስታ አልፈው ወደ ትግሬ ግዛት ስለገፉ፣ በዚህ ከራስ መንገሻ ጋር ተጣልተዋል" የሚለው ወሬ በአዲስ አበባ በርክቶ ተወርቶ ስለነበረ ነው።[1]

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ፣ ዋግሹም ብሩ ካፄ ምኒልክ እየተሰወሩ ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር እየተጻጻፉ ወሬ ያቀብሉ ነበር። ከጠላት ጋር በጐን ለመላላክ ያደረሳቸው እርግጠኛው ምክንያት አይታወቅም። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም፣ "ዋግሹም ብሩ ተሸረው ልጃቸው ጓንጉል ተሾመ" ከማለት በቀር፣ በመጽሐፋቸው ሌላ ዝርዝር አልሰጡም። መቸም በዚያን ጊዜ እነዚህን የመሳሰሉትን መሳፍንትና መኳንንት ከንጉሠ ነገሥት ማዕከላዊ መንግሥት የሚያሸፍታቸው፣ "የማዕረግ ስሜና ግዛቴ አነሰ፣ በግቢ በቤተ መንግሥቱ የምጋበዝበት መሶቤ ተዋረደ" የሚለው ቅሬታ ነው። በዚህ ምክንያት እንዳይባል አዲስ አበባ የመጡ ጊዜ እስከ አደባባይ ነጋሪት እያስመቱ መግባታቸው፣ በግብር ጊዜ ራሶች በብር ሰንና ብርት ሲታጠቡ እርሳቸው የወርቅ ሰንና ብርት ቀርቦላቸው መታጠባቸው ተጽፏል። መሶባቸው ከራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ዝቅ ብሎ፣ ወይም በሽልማት ጊዜ ወይም ለርሳቸው የተላከው መስተንግዶ አንሶ በዚህ ተቀይመው እንደሆነ አናውቅም። ምንም እንኳን፣ ብሩ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ወንድምና በዕድሜም በጣም የሸመገሉ ቢሆኑ፣ መንገሻ የንጉሠ ነገሥቱ ያፄ ዮሐንስ ተከታይ አልጋ ወራሽ፣ ባይታደሉ ነው እንጂ መንገሥ እንኳን ይገባቸው ነበርና፣ በዘመኑ እንደ ነበረው ልማድና አስተሳሰብ ከርሳቸው ጋር መፎካከሩ የሚያምር አልነበረም።

ባለፈው ምዕራፍ እንደ ጠቀስነው፣ የኢጣልያ ሰላዮች በኢትዮጵያ በተሠራጩበት ሰዓት፣ ከአዲስ አበባ ወደ ግዛታቸው ወደ ላስታ

* አቶ በየነ ይመር በኋላ ቀኛዝማች ተብለው የፖስታ ሚኒስትር የነበሩት ይሆኑ፧

1 Italia ed Etiopia . . . Conti - Rossini - PP. 127 - 131.



እንደ ተመለሱ ካፄ ምኒልክ ጋር መጻጻፋቸውን ሳያቋርጡ፣ ባንድ ወገን በታማኝ መላከተኛ አማካይነት፣ ከመረብ ወዲህ የተያዘውን የትግሬን ግዛት ከሚያስተዳድረው ከጄኔራል አሪሞንዲ ጋር ዋግሹም ብሩ መጻጻፋቸውና አንዳንድ ወሬ ማቀበላቸው በሰነድ የተረጋገጠ ነው። ይኸንንም ዓይነት አድራጎት አንዳንድ የዘመኑ መሳፍንት የሚከተሉት የአኗኗር ዘዴ ነው። ባጋጣሚ ከሁለቱ ኃያላን አንደኛው ቢሸነፍ፣ ካሸናፊው ጋር ተስማምቶ የተሻለ ኑሮን ለመቀጠል እንዲችል ቀደም ብሎ በመጻጻፍ ወዳጅነት ለመፍጠር ሙከራ ያደርጋል። በዚህ ጊዜ፣ አንዳንድ መሳፍንት አንድ የግል ቁጭት ሲያድርባቸው በወገንና በጠላት መካከል ያለው ልዩነት ይጠፋባቸዋል። የኢጣልያኖች የፕሮፓጋንዳቸው መላስ ደግሞ፣ በዚያው አንጻር የማር ወለላ የሚፈስበት ሆኖ ይታያል። በዚህ ሁኔታ ቀደም ባለው ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ በትንሹ፣ ዐፄ ምኒልክ በትልቁ ተታለው እንደነበረ የታወቀ ነው። በመጨረሻ ግን፣ ኢጣልያ መርዘኛ ጠላት ከመሆን አልዘለለም።

ጊዜያዊው የትግሬ አስተዳደሪ የነበረው ጄኔራል አሪሞንዲ፣ "ዋግሹም ብሩ በዚህ ጽሕፈት ቤት ዘንድ የታወቀውን ታማኝ አሽከራቸውን ከመቅደላ ልከው ንጉሠ ነገሥቱ ከእንጦጦ ገና አለመነሣታቸውን፣ ያልተነሡትም የጅማው አባ ጅፋር ሸፈተ ስለ ተባለ መሆኑን፣ የኢጣልያን ወረራ ለማገድ ራስ ሚካኤል፣ ራስ አሉላ፣ ራስ መንገሻ እቲከም መታዘዛቸውን፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለምኒልክ አለመታዘዛቸውንና የኢጣልያ ወዳጅ መሆናቸውን፣ መስኮቦቹ መስቀልና ንዋየ ቅድሳት እንጂ፣ መድፍ ስለአላመጡ ምኒልክ መቀየማቸውን፣ መሐመድ አንፋሪ በአውሳ በምኒልክ ላይ መሸፈቱን፣ ጓንጉል ዘገዬ ጓሊማ ላይ የሸዋን ጦር ለማስቸገር ማሰቡን" አስረዱኝ ይላል። ይኸ ጊዜ በማናቸውም ግንባር የተፈተነው ዕርቅ ስቶ ንጉሠ ነገሥቱ ከተት ሠራዊት ብለው ወደ ትግሬ ለመዝመት የሚዘጋጁበት ሰዓት ነው። በዚህም ጊዜ የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት የላኳቸው መልክተኞች በሌዎንቴቭ መሪነት አዲስ አበባ ሲገቡ መድፍ ያመጣሉ ተብሎ ተስፋ ተደርጎ ሳያመጡ ቀርተዋል። የጅማው አባ ጅፋር ሸፈተ ተብሎም በሐሰት ተወርቶአል። አሪሞንዲ እላይ እንዳመለከት ነው፣ ይኸን ማስረጃ ከዋግሹም ብሩ ካገኘ በኋላ እርሱ ደግሞ እ.ኤ.አ ኅዳር 29 ቀን 1895 ዓ.ም. ላለቃው ለጄኔራል ባራቲዬሪ ማስተላለፉን ይገልጻል።[1] ዋናው ግን፣ የዋግሹም ብሩ ክዳት የተገለጸው እንጂኒየር ካፑቺ የተያዘለት ነው።

1 Documenti sul combattimento di Amba Alagge e sulla diffesa di Maccale- Enrico Voghera, P. 33, Allegato no. 10.

የኢጣልያኖች የስለላ ሥራ ፣ ከሌሎች ከተሞች ይበልጥ ያተኮረው ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት በአዲስ አበባ ነበረ ። በዚህም ራሱ ዋና ወኪል ሆኖ ከተቀመጠው ከኮንት አንቶኔሊ በቀር እነሊዎፖልዶ ትራቪርሲ ፣ እነኮንት ሳልምቤኒ ሁሉ በተቻለ መጠን አዲስ አበባን በጠብ እስኪለቁ ድረስ ካገር ተወላጅ ጋር ግንኙነት በማድረግ ስለላቸውን አላቋረጡም ነበር ።

ከእነዚህ ሁሉ የበለጠ አዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ በስለላ ሥራው በኢጣልያ ባለሥልጣኖች ዘንድ የታወቀውና ከፍተኛ ግምት የተሰጠው እንጂኒየር ሉዊጅ ካፑቺ ነው ። ይህ ሰው እ.ኤ.አ. በ1870 ዓ.ም. ከነማርኬዝ አንቲኖሪ ጋር ወደ ሸዋ (አንኮበር) መጣ ። ከርሱም ጋር ጕሴፔ ኪያሪኒ የሚባለው ጓደኛው አብሮት ነበር ። ማርኬዝ አንቲኖሪ ልጥ ማረፍያ የሚባለው መሬት ለማረፊያ ተሰጥቶት በዚያ ሲኖር ከዕለታት አንድ ቀን ወደ አደን ሲሔድ የገዛ ጠብመንጃው ባርቆበት ሞተ ። ኪያሪኒ ደግሞ ፣ አንቶኒዮ ቼኪ ከሚባለው ከሌላ ጓደኛው ጋር ሆነው አገር እንመረምራለን ብለው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሔደው ሳለ ፣ ከከፋ አልፈው ጌራ ሲደርሱ የጌራ ንግሥት (ጌራጌኔ) አገሩ በወቅቱ በማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ሥር ባለመሆኑ ፣ "የምኒልክና የጐበና ሰላዮች ሳትሆኑ አትቀሩም" ብላ አሰረቻቸው ። ኪያሪኒ ሲሞት አንቶኒዮ ቼኪ ምጥዋ ያሉት ኢጣልያኖች ላጄ ዮሐንስ ነግረው እርሳቸው ለጐጃሙ ለራስ አዳል (ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት) "ተላልከህ አስፈታው" ብለው ስለላኩ ፣ ራስ አዳል ከጌኔ ጋር ተላልከው አስፈትተውታል ። ከዚያ ወደ ውጋዴን ሔዶ የዓድዋ ጦርነት በየካቲት ሊደረግ እርሱ ቀደም ብሎ በኅዳር ወር ሞቃዲሾ አጠገብ ላፎሊ ከሚባለው ሥፍራ ሲደርስ የተከተሉት ሰዎች ከድተው ገደሉት ።

እንጂኒየር ካፑቺ ግን ፣ ዐፄ ምኒልክ አንኮበርም ፣ እንጦጦም ፣ አዲስ አበባም የነበሩ ጊዜ ሳይለይ ፣ ስራሱም ንግድ እየነገደ ፣ በተረፈ የታዘዘውን የቤትና ማናቸውንም የመሐንዲስነት ሥራ እየሠራ በማገልገልና ንጉሠ ነገሥቱን በማስደሰት ኖረ ። ዐፄ ምኒልክም ወደኋላ የቀረች አገራቸውን ለማሠልጠን ባላቸው ፍላጐት የእጅ ብልሃትና ትጉኅ ሠራተኛ በጣም ይወዱ ነበርና ፣ በሙያው አቅርበውት በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የብዙ ሕንፃ ሥራ ተካፋይ ነበር ። አሁን ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ወዲህ ፣ በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ ያለው አይስማማንምና ሠርዙ ፣ አንድ ጊዜ ተዋውለናልና አንሰርዝም ፣ አገር ይዛችኋልና ልቀቁና በወዳጅነት እንስማማ ፣ አንለቅም በሚለው አሳብ ክፍ ያለ ውዝግብ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል በተቀሰቀሰበት ሰዓት ፣ መሐንዲሱ



ካፑቺ ካንዳንድ ባለሥልጣኖች ይልቁንም ካስተርጓሚዎችና ከጸሐፊዎች ጋር በግል ወዳጅነት እየተገናኘና ወሬ እየሰበሰበ ምሥጢራዊ የሆነ የጽሑፍ ግልባጭ እስከ ማግኘት ደርሷል ። ያንን በግልጽም በቁጥር ቃልም እያደረገ ፣ በሸምበቆ ዘንግ ውስጥ እያስገባ ወደ ሮማ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ ብዙ ጊዜም ወደ አሥመራ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ አንድ አንድ ጊዜም ዘይላና ኤደን ለሚገኙት የኢጣልያ ቆንስሎች ይልክ ኖሯል ። እስኪያዝ ድረስ 95 ጊዜ በቁጥር ቃል እያደረገ በልዩ ልዩ መንገድ የስለላ ወሬ ጽፏል ። የተያዘበት 96ኛው ስለ መስኮቦች አገባብ የሚናገር ነው ።

ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ ኢጣልያ አገር ለሚገኘው ጓደኛው ለጄኔራል ዳልቬርሜ እ.ኤ.አ. ግንቦት 12 ቀን 1895 ዓ.ም. ከምጥዋ በጻፈለት ረዥም ደብዳቤ ውስጥ በመጨረሻ ፣ "...ከኮዓቲት ጦርነት ወዲህ ምኒልክ ወደፊት ገፍቶ ቅኝ አገሮቻችንን ለመውረር ፕላን እንዳለው የካፑቺ ደብዳቤዎች ያስረዳሉ ። የካፑቺ ስም በጋዜጣ እንዳይወጣ ተጠንቀቅ"[1] ብሎታል ። በኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቤተ መዛግብት ስለርሱ የሚናገረው ማስታወሻ ደግሞ እንደዚህ ይላል ። "መሐንዲሱ ካፑቺ ፣ ብልሁ ደፋሩ ፣ የተከበረው ...የሸዋውን ጥብቅ ቁጥጥር አልፎ ጠቃሚ ማስረጃዎችን ይልክ ነበር"[2] ከዚሁ በማያያዝ ፣ "እንደዚሁ እንደ ለመደው ፣ ከዕለታት አንድ ቀን የስለላ ደብዳቤውን አዘጋጅቶ ፣ በሸምበቆ ዘንግ ውስጥ በዘዴ አስገብቶ በዘይላ በኩል ለኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲልክ ፣ ያው የተላከው ፖስታ አመላላሽ ምስጢሩን አውጥቶ ያቶ ጳውሎስ ዘበኞች ይዘውት ወደ አዲስ አበባ አመጡት" ሲል ያስረዳል ። የተያዘው ፖስተኛ ስሙ ደስታ መሆኑን ዶክተር ሳሊምቤኒ በጻፈው ማስታወሻ ያረጋግጣል ።[3]

የርሱም በስለላ መያዝ በዙሪክ (ስዊስ) ጋዜጣ ተጽፎ ነበር። ከዚያ በኋላ ራሱ በጽሑፍ ያስፈረው ቃል እንደዚህ የሚል ነው ።

> በየካቲትና በመጋቢት መካከል ስለኔ ጉዳይ ስብሰባ ተደርጎ ሳለ ፣ ንግሥቲቱ (ጣይቱ) በገርፉ (አዳል) በኩል ወደ አገሩ ይግባ ብላ ልታስገድለኝ ስታስብ ንጉሠ ነገሥቱ አገር ለቆ ይውጣ አሉ ። አዛዥ ወልደ ጻድቅ ደግሞ ፣ እዚሁ መያዝ ሆኖ ይቀመጥ ስላሉ የርሳቸው አሳብ ጸደቀ ። ...ግንቦት 8 ቀን 1895 ዓ.ም. ምኒልክ ከአዲስ አበባ ወደ ወረይሉ ሔዱ ...ከሁለት ቀን በኋላ የምንነጋገረው ነገር አለና እንድትመጣ የሚል ቃል ስለ ደረሰኝ ፣ ወደዚያ እንደ ሔድሁ ታሰርሁና

---

1 Precursori del Impero Africano - R -Truffi, PP. 196- 197.

2 Ibid, P. 228

3 Crispi e Menelich . . P. 246.

የውጭ አገር ሰዎች ያሉበት አንድ የፍርድ ዓይነት ጉባኤ ሆነ። በጉባኤው ላይ የነበሩ ስድስት የፈረንሣይ፣ ሁለት የእርሞን፣ አንድ የግሪክ ተወላጆች ነበሩ። ክሱ በሰላይነት ነበርና ንጉሡ የምትጸጸፍ በትን የቁጥር ቃል ብትሰጠኝ እለቅሀለሁ አሉኝ። እኔም የቁጥሩን ቃል አልሰጥም ብዬ እስራቴ አላግባብ መሆኑን ተከራከርሁ። ስለዚህ ጉዳይ፣ እዚያ ያሉት ፈረንጆች አሳባቸው ተጠይቆ በዚያን ጊዜ ሙሴ ሽፍን ስለ ሁሉም ሆኖ፣ "ስላገርዎ ጸጥታ ሲሉ በዚህ ሰውዬ ላይ ማናቸውንም እርምጃ ለመውሰድ መብት አለዎት ..." ብሎ ተናገረ .... ሙሴ ሞንዶን ግን፣ መሰቀል አለበት ብሎ ነበር ... ከዚህ በኋላ ወደ ኮላሽ አምባ ተወስጄ ታሰርሁ። .... ከዚያም ለማምለጥ ስሞክር ተይዤ በእግር ብረት ታሰርሁ። ... ከዚያ ደግሞ በኅዳር ወር እግር ብረቱ ወለቀልኝ። ..[1]

በዚህ ዓይነት፣ ከአዲስ አበባ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 20 ቀን 1895 ዓ.ም. በቁጥር 88 ያስተላለፈው የቁጥር ቃል ሰላዪ ምኒልክ ጉዞ ወደ ቦሩ ሜዳ፣ ስለ ተከተላቸው የሠራዊት ቁጥርና እንደዚሁም ኢትዮጵያና መስኮብ በመተባበር ከኢትዮጵያ የእንግሊዝ ሥልጣን እንዲወገድ ሁለቱ መንግሥታት መመካከራቸውን የሚገልጽ ነው። ካፑቺ በኮላሽ አምባ እንደታሰረ፣ ከግንቦት ወር 1887 ዓ.ም. ጀምሮ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ እስከ ኅዳር ወር 1889 ዓ.ም. እንደቆየ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግሥታት ስምምነት አድርገው ምርኮኞች ሁሉ ሲለቀቁ፣ እርሱም በዚህ ጊዜ አብሮ ተለቀቀ።

ዳግማዊ ምኒልክ፣ ከወላሞ (ወላይታ) ጦርነት እንደ ተመለሱ፣ ሹም አጋሜ ተሰፋዬ ከራስ መንገሻ ተልከው መጥተው፣ "ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ወሎ ብቅ ቢሉ ወደፊት ገፍቶ ብዙ አገር የያዘው የኢጣልያ ጦር ወደ መጣበት ሊመለስ ይችላል" ብለው በነገሯቸው ጊዜ፣ ላዩን አዲስ የሚሠራውን የግሼን ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ለመጎብኘት አስመስለው፣ ውስጡን ኢጣልያኖቹን ለማስፈራራት ወረይሉ ሔዱ። በዚህም ወቅት ዋግሹም ብሩ ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር ግንኙነት አድርገው ይላላካሉ የሚለው ወሬ በዝቶ ነበርና ካፑቺ በታሰረ በሁለተኛው ወር ዋግሹም ብሩም ታሰሩ።

የዚህን ጉዳይ በዘመኑ ንጉሠ ነገሥቱን እየተከተሉ የጦርነቱን ሁኔታና ያገር ውስጥ ወሬ ባዲስ አበባ ለቀሩት ፈረንሳዮች በጽሕፈት ያስረዱ የነበሩት አስተርጓሚው ግራዝማች ዮሴፍ፣ ለሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ የጻፉለትን ስናነብ የነገሩን ምክንያት በትክክል ያብራራልናል። ደብዳቤውም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

1 Precursori del Impero Africano - R.Truffi, P.P. 225 - 231.



ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን በሰኔ 13 ከጻፍሁልዎ በኋላ የተገኘ ወሬ እልክልዎታለሁ። ዋግሹም ብሩ ጃንሆይ ሊሰጠርተዋቸው መጡ። ከዚህ በኋላ ደጃች ሐጎስ ተፈሪ በአዲግራት (ከኢጣልያኖች ጋር) ያለ፣ የላከው ሰላይ ከጃንሆይ ፊት ቀርቦ ቢጠይቁት ለጌታ እድራለሁ ብዬ መጣሁ አለ። በኋላ ግን፣ ዐርባ ዥራፍ ይገረፍ ብለው ቢያዙ ሦስት ጊዜ እንደ ተመታ እውነቱን ልናገር አለ ምስጢሩን አወጣ። ዋግሹም ብሩ ካፖት (ካፑቺ) የሚባል ነጋዴ ታስረ ብለው ወደ ጀኔራል ባራቲዬሪ ቢልኩ እውነቱን ለማወቅ፣ ደግሞ ራስ አሉላ ትግሬን ሁሉ ይዘው ተነሥተዋል ቢሉ፣ ያሉበትን ለማወቅ ጃንሆይም ወረይሉ መክረማቸውንና አለመክረማቸውን ለመመርመር መጣሁ ብሎ ተናገረ። ከዚህም በኋላ በጣም ቢገረፍ እንደሱ ያሉ ሌሎች ሰባት ሰላዮች አስያዘ። እነዚያም ሰባቱ የጃንሆይ ጠበንጃ ይዘው ሰላይ ሆነው ተገኙ። ይህ ሁሉ የክፎች ሥራ ነው።

በሰኔ 10 ቀን እሑድለት ራሶችን ሁሉ በጧት አስጠሩ። ደጃዝማቾችም ተጠሩ። አራዳ ላይ ነጋሪት ወጥቶ ይመታ ጀመር። ዋግሹም ብሩም ከመኳንንቶቻቸው ጋር ተጠርተው ገቡ። ዘበኛው ሁሉ ተሰልፎ ነበር። ከዚህም በኋላ ጃንሆይ የወቀሳ ደብዳቤ አጽፈው ራስ ቢቶደድ መንገሻን፣ አለቃ ገብረ ሥላሴን አሲይዘው ከነዚህ በራት ሊጋባ ሠራዊቱን ዘበኞች አስከትለው የዋግሹምን እጅ ለመያዝ ሰደዱ። እጃቸው ከተያዘ በኋላ የወቀሳ ደብዳቤ ተነበበ። ቃሉም ይህ ነው።

... የካፑቼን (ካፑቺን) መያዝ ወደ ኢጣልያኖች ልከሃል። ራስ መንገሻ ሲዋጋ እርዳኝ ቢልህ ሳትረዳው ቀረህ። ሹም አጋሜ ተሰፋዬ ወደኔ ሲመጣ ሽፍታ ልከህ አስወጋኸው። የፈሰስ ብር* አውጣ ብልህ እምቢ አልህ። ለወታደር ቀለብ ያስራት እህል ሰብስብ ብልህ ሳትሰበስብ ቀረህ። ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎህ በኢጣልያኖች ሰፈር የሰቀጣው ጌታ ከገባልን ምኒልክ ሊያቅተን ነወይ እያሰኘህ ታስደነፋብኛለህ። ይህን የመሰለ ነገር ሌላ ሌላ ነገር ሁሉ ደግሞ የወቀሳ ደብዳቤ ተነበበላቸው። ከዚህ በኋላ አገርህን ለልጅህ ለዋግሹም ኃንጉል ሰጥቸዋለሁ። አንተም ጉዳዩን ሰጨርሰ እፈታሃለሁ ነፍጥህን ከብትህን በደብዳቤ ለኃንጉል አስረክብ አሏቸው። ከዚህ በኋላ አራዳ ላይ ዓዋጅ ሲነገር የዋግ ሰው ዋግሹም ብሩን ማሰሬ እየወሳሰተ ቢያስቸግረኝ ነው። አገሩን ለሌላ ሰው አልሰጠሁብህም ለጌታህ ልጅ ነው። ይህንም ማድረጌ እንድትወደኝ ባውቅህ ነው። ዋግሹም ኃንጉልን ያልተከተልህ አይቀጡ ቅጣት እቀጣሀለሁ ብለው ዓዋጅ አስነገሩ።[1]

በዚህ ዓዋጅ ዐፄ ምኒልክ፣ በዚህ የጦርነት ሰዓትና በዓድዋ ውጊያ ዋዜማ የላስታንና የዋግን ሕዝብ ላለማሳዘን ጥንቃቄ እንዳደረጉ ይታያል። ሌላ ደጅ ጠኚ ሳይጠሩ ሹመቱን ለግዞተኛው ልጅ ለዋግሹም ኃንጉል መስጠታቸው በዚህ በጉልተኝነት ዘመን ሕዝቡ

* የፈሰስ ብር ለጦርነቱ ከሕዝብ ላይ መዋጮ እንዲደረግ የታዘዘው ፈሰስ ይባላል።
1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ቪዳዬ ፋይል ቁ. 92.

"ጌታችን ቢታሰሩ የተሾመው ያው የጌታችን ልጅ ነው" ብሎ ደስ ብሎት ኅብረቱን እንዳይነፍግ ነው ። በእውነትም ዋግሹም ጓንጉል ከዚህ ጊዜ ዠምሮ በአላጌውም ፥ በመቀሌውም ፥ በዓድዋውም ጦርነት ሳይለዩ አገልግሎታቸውን ላገራቸውና ለንጉሠ ነገሥቱ በትጋት በመቀጠል ያባታቸውን ጉድለት አሟልተው ፈጽመዋል ። በዚህ ላይ ደግሞ ፥ ወይዘሮ ላቀች ብሩ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባለቤት ከመሆናቸው በላይ የዋግሹም ብሩ ትውልድ ከዋድላ ፥ ከደላንታ ፥ ከትግሬና ከጐጃም ባላባቶች ጋር በአምቻ በጋብቻ ስለተሳሰረ ፥ በዚህ በጦርነት ዋዜማ ሕዝቡን ለማስተባበር ያለግልፍታ በብልህነት ሁሉንም አስታሞ መያዝ ያስፈልጋል ። ያፄ ምኒልክ ጠባይ ከዚህ ሁኔታ ጋር ሰምና ወርቅ ሆኗል ማለት ይቻላል ።


በዓለም አቀፍም ፥ በአገር ደረጃም ቢሆን ፥ በማናቸውም ጊዜ ስላይ ሆኖ ያገሩን ምስጢር ለባዕድ ያቀበለ ቅጣቱ ከፍ ያለ ነው ። በጦርነት ሰዓት ደግሞ አገሩን ከድቶ ያገሩን ወታደራዊ ምስጢር ለወራሪ ጠላት ያቀበለ በሞት እንደሚቀጣ አይጠረጠርም ።

ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መሳፍንት በመከፋፈል ፥ በተለይ በዘመነ መሳፍንት በቀላሉም ፥ በከባዱም ጉዳይ እርስ በርሷ ስትተላለቅ ኖራለች ። ያ ጊዜ አልፎ አሁን የሰላምና የጸጥታ ጊዜ ተገኝቶ ሕዝቡም ወታደሩም ከጦርነት ሁካታና ከምዝበራ ሊያርፍ የዠመረበት ጊዜ ነው ። በደቡብ ኢትዮጵያ በከፋ ፥ በወላሞ ፥ (ወላይታ) በአሩሲ ፥ (አርሲ) በሲዳሞ ፥ በባሌ በሐረርጌ ጦርነት ቢደረግም ፥ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ወሰኗን ለማግኘት የብሔርን አንድነት ሰብስቦ አንድ ብሔራዊ ቤተሰብ ያለበት መንግሥት ለማዋቀር ስለሆነ ፥ ጦርነቱ ወግና ሥርዓት ያለው ነው ።

ስለዚህ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ በተለመደ ትዕግሥታቸው ፥ ዋግሹም ብሩን በሞት በመቅጣት ፈንታ ለጊዜው በግዞት ቦታ አስቀምጠው እንዲያውም ፥ "ጉዳዩን ስጨርስ (ከኢጣልያ ጋር የማደርገውን ጦርነት) እፈታሃለሁ" ማለታቸው ፥ ሹመቱን ከቤተሰባቸው አለማውጣታቸው ጉዳዩን በኃይል ሳይሆን ፥ በልስላሴና በማስታመም እንደ ያዙት በግልጽ ይታያል ። ይህም የርስ በርስ ጦርነትን አግዶ በዚህ ፈንታ የሕዝብን ክንድ በጠላት ላይ ያስተባብራል ።

በዚህ ዓይነት ትዕግሥት ነው ዐፄ ምኒልክ እያንዳንዱ ፥ "ማን ከማን ያንሣል ፥ ማን ለማን ያደገድጋል" እያለ እርስ በርስ በመዋጋት የተለያየውን መስፍን ሁሉ ፥ በሥልጣናቸው ጥላ ሥር ሰብስበው በአንድ እግር አቁመው በማዋጋት ወደፊት የምናነበውን ዓለምን ያስደነቀውን የዓድዋ ድል ያገኙት ።





ደጃዝማች ባሕታ ሐጐስ በሐላይ፤ ራስ መንገሻ ዮሐንስ በቆአቲትና በሰናፌ እነ ቀኝ አዝማች ኃይለማርያም በደብረ ኃይላ የተዋጉባቸውን ቀበሌ የሚያሳይ ካርታ

# ምዕራፍ ሐያ አራት

## የኢትዮጵያና የመስኮብ ግንኙነት

ምኒልክ በአንኮበር ካባታቸው ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ጋር ካሳለፉት ያሥር ዓመት እድገታቸው ዘመን ይልቅ ፤ በጐንደር በደብረ ታቦር ባፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ያሳለፉት ያሥር ወይም የዐሥራ አንድ ዓመት ዘመን ብዙ ትምህርት የሰጣቸው ይመስላል ። በ1857 ዓ.ም በ21 ዓመታቸው ከመቅደላ አምልጠው ወደ አንኮበር ሲመለሱ ፤ ከፉና በጐን በመለየት ካፄ ቴዎድሮስ ደገኛውን ወገንና አገር የማሠልጠኑን ስሜት ወርሰው ተመልሰዋል ።

ያፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዞች ፤ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ባፄ ዮሐንስ መሸነፍ ፤ የርሳቸውም በ1870 ዓ.ም. ላፄ ዮሐንስ መገበር መሠረታዊው ምክንያት ፤ በጦር መሣሪያ ብዛትና ጥራት ልዩነት መሆኑ በትክክል ገብቷቸዋል ። የጐራዴ ፤ የሰይፍ ፤ የካራ ፤ የጩቤ ፤ የጦርና የጋሻ መሣሪያነት ጊዜው ያለፈበት መሆኑና ላሉበት ዘመን እምብዛም እንደማያገለግል ተረድተዋል ። በነዚህ ፈንታ ከጠላት ለመከላከል ወይም ጠላትን ለማጥቃት ፤ ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ዙፋን ለመውጣትና በዚያም ለመቆየት ፍቱን መፍትሔው በባሩድና በጥይት ተተኳሹ ዘመናዊው ጠበንጃና መድፍ መሆኑን በደንብ ተገንዝበውታል ።

ስለዚህም ፤ ከሁሉ በፊት የመሣሪያዎቹ ባለቤት ከሆኑት ከአውሮፓ መንግሥታት መሪዎች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ለማድረግ ፤ በቅድሚያ የነዚህን አገር የተለያዩ ዜጐች ባጠገባቸው አስቀምጠው መንከባከብን ሥራዬ ብለው ተያያዙት ። ቀጥሎ በነዚህ ወዳጆቻቸው አማካይነት ወርቅና የዝሆን ጥርስ እየላኩ በመዠመሪያ ከኢጣልያ በወዳጅነቱ ዘመን ፤ ቀጥሎ ከኢጣልያ ጋር ወዳጅነቱ ወደ ጠብ ስለ ተለወጠ በነሙሴ ኢልግ ፤ በነሙሴ ሽፍነና በነሳቡሬ አማካይነት ከፈረንሳይ መንግሥት የጦር መሣሪያ በግዥ መሰብሰባቸውን ባለፈው አንብበናል ።

ከነዚህ ከወዳጅ አገሮች አንዱ ፤ የመስኮብ መንግሥት ሆኖ ተገኝቷል ። ይህ አውሮፓዊና እስያዊ መንግሥት በአፍሪካ ዙሪያ ምንም ዓይነት ቅኝ አገር ስለሌለው ፤ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም እንኳን ካፄ

ዮሐንስ ዘመን ዠምሮ ከሁለቱም ወገን የግንኙነት ፍላጎት ባይጠፋ በቅድሚያ በቱርኮች ፣ ቀጥሎም በእንግሊዞች ተጽእኖ ሥጋት ስለነበር ግንኙነቱ እየተወጠነ መልሶ ሲቋዘቅዝ ቆይቶ ነበር ። አሁን ግን ፣ የኢጣልያ አጥቂነት ፣ የእንግሊዝ ተባባሪነት እየተጫጫኑ በሚሔድበት ጊዜ ፣ የኢትዮጵያ ወዳጆች መስለው የቀረቡት ፈረንሳይና መስኮብ ናቸው ። ለመስኮብ ወዳጅነት ወጣኞቹ አቺኖቭ ኒኮላይ ኢቫኖቪችና ማሽኮብ ባሲሊ የተባሉት የጦር መኰንኖች ፣ እንደዚሁም ኤፍሬም የሚባሉት የቤተክህነት ሰው ናቸው ። ከነዚህ ሁሉ የበለጠ ካፄ ምኒልክ በመተዋወቅና በመወዳጀት ለመስኮብና ለኢትዮጵያ መቀራረብና መወዳጀት ዋና አማካይ የሆነው ሊዎንቴቭ ኒኮላይ ስቴቫኖቪች የሚባለው የጦር መኰንን ነው ። እሱም ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ፣ የእስክንድር ምርጥ የክብር ዘበኛ መኰንን ነበር ። አንዳንዶቹ ኮሎኔል ፣ ብዙዎቹ ኮንት ሊዎንቴቭ እያሉ ስለሚጠሩት ፣ የቤተሰቡ ደረጃ ከመሳፍንቱ ዝቅ ያለ ፣ የባላባትነት ደረጃ ጭምር ነበረው ማለት ነው ። ይኸንንም የኮንት ሥያሜ እንዲጠራበት ከኒሻን ሽልማት ጋር ዐፄ ምኒልክ በደብዳቤ የምስክር ወረቀት ፈቅደውለታል ።*

ኮንት ሊዎንቴቭ ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፣ ከመስኮብ ወደ አዲስ አበባ ፣ ከዚህም ወደዚያ እየተመላለሰ ፣ ሁለቱ መንግሥታት የሚጠቃቀሙበትን መንገድ ያከናውን ነበር ። የመስኮቡን ንጉሠ ነገሥት የሣልሳዊ እስክንድርንና እሳቸው እ. ኤ. አ. በ1894 ዓ. ም. ከሞቱ ወዲህ የልጃቸው የዳግማዊ ኒኮላን አሳብና ምኞት ላፄ ምኒልክ ፣ የምኒልክን አሳብና ምኞት ላገሩ ንጉሠ ነገሥት እየገለጠ የበለጠ አቀራርቧል ። ኒሻኑን የተሸለመውና ኮንት የተባለውም ከዚህ አገልግሎት በኋላ ነው ። የመቀራረቡ ዓላማ የፖለቲካና የጥቅም ጉዳይ ባይጠፋበትም ፣ ዋናው ሁለቱን ያቀራረባቸው እርቶዶክሳዊ የክርስትና ሃይማኖት ተመሳሳይነት ነው ። የነዚህንም ሁለት አገሮች ግንኙነት የእንግሊዝና የኢጣልያ የፖለቲካ ባላጋራ የነበረው ፈረንሳይ በመልካም ዐይን ተመልክቶታል ። የኢጣልያ መንግሥትና ከርሱ ጋር ተባባሪ የሆነው የእንግሊዝ መንግሥት ግን ፣ በክፉ ዐይን በመመልከት ግንኙነቱን ለማሰናከል ከመጣር አላረፉም ።

ስለዚህ ፣ በዚህ የኢጣልያኖች አጥቂነት በከፋበት ሰዓት ፣ ሊዎንቴቭ ካፄ ምኒልክ ተልኮ በመስኮብ አገር የኢትዮጵያን ጉዳይ ሲነጋገር

---

* ሞዓ አንበሳ . . .ዳግማዊ ምኒልክ . . . ከመስኮብ መንግሥት ተልኮ መጥቶ የኔን መንግሥት በመልካም ስላገለገለ ወዳጃችንን ሙሴ ሊዎንቲፍን በኒሻናችን አከብረን . . . ስለ ማገልገሉ ኮንት ብለነዋል ። በሰኔ 4 ቀን 1888 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ።



ከሰነበተ በኋላ ፣ በ1887 ዓ.ም. ሌሎች መስኮቦች አስከትሎ በጥር ወር ላይ ፣ በጅቡቲ በኩል ወደ ሐረር መንዛቸው ተሰማ ። ንጉሠ ነገሥቱ ፣ “ አክብረህ ተቀብለህ ወደኔ ላካቸው” የሚል አስቸኳይ ደብዳቤ ለራስ መኰንን ላኩ ። መልክተኞቹም ከሐረርጌ በአዋሽ በኩል ፣ በየረርና በከረዩ አድርገው ምንጃር ሲደርሱ ፣ መልካም አቀባበልና መስተንግዶ እየተደረገ ፣ በየካቲት ወር ላይ አዲስ አበባ ሲደርሱ ከሁሉም የበለጠ ያክብሮትና የወዳጅነት አቀባበል ተደርጎላቸው ሰነበቱ ።[1]

የመስኮብ መንግሥት መልክተኞች በኮንት ሊዎንቴቭ መሪነት መጥተው ስጦታውንም ፣ የወዳጅነት ደብዳቤውንም አቅርበው ሲወያዩና ሲመካከሩ ከሰነበቱ በኋላ ፣ በዚህ በኮንት ሊዎንቴቭ አማካሪነት አንድ የኢትዮጵያ የመልእክተኛ ጓድ ወደ ፒዮትሮቡርግ* እንዲላክ ታስቦ ተወሰነ ። በተለይ አሁን የኢጣልያኖች አጥቂነት እየተጫነ ሲሔድ ከፈረንሳይ በተጨማሪ የመስኮብንም ወዳጅነት ማግኘቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆነ ። በመዠመሪያ ላይ የመልእክተኞቹ መሪ የሚሆነው ሲመረጥ ፣ ምርጫው ከሊቀመኳስ አባተ ቧያለው ላይ ወድቆ ነበር ። በኋላ ግን ፣ አባተ ቀርተው ለዚህ መልእክት ፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ ተመረጡ ። ከርሳቸውም ጋር ቀኛዝማች (በኋላ ደጃዝማች) ገነሜ ፣ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ፣ ልጅ በላቸው ፣ አቶ ዮሴፍ (አስተርጓሚ) ፣ ልጅ ረዳ (የሊዎንቴቭ አስተርጓሚ) ተመደቡ ።

ፊታውራሪ ዳምጠው** አቋቋማቸው ያማረ ፣ ንግግራቸው የሚጥም ፣ የሸዋ ተወላጅ መሆናቸውን ጸሐፊው ሁሉ ስለሚጠቅስ ፣ ምናልባት ለዚህ የመልእክት መሪነት ያስመረጣቸው ይኸው ያቋቋምና የመልክ ማማር ይሆናል ። ሊቀ መኳስ አባተ ያፄ ምኒልክ ዋና ባለሟል ቢሆኑም ፣ ብልህነታቸው ቢነገርም ፣ የሰውነታቸው አጠር ቀጠን ማለት አስቀርቷቸው ይሆናልና ወይም ባሁኑ ጊዜ ወደፊት ከኢጣልያኖች ጋር ውጊያው እንደማይቀር ስለታመነ ከፈረንሳይም ፣ ከሌላም አገር ከመጣው አዳዲስ ጠበንጃና መድፍ ጋር የጦር ሠራዊቱ ከመለማመድ ላይ ስለሚገኝ ፣ ለዚህ ቴክኒካዊ ተግባርና የጦር መሣሪያ ልምምድ ያባተ መጉደል ይጐዳል ተብሎ ይሆናል ።

በመስኮብ አገር አባትየው እስክንድር ሞተው በዙፋን ላይ ለወጡት ልጃቸው ለዳግማዊ ኒኮላና ለባለቤታቸው የሚቀርበው ገጸ በረከትና

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 59 ።
Chronique du Regne de Menelik II . . .M. de Coppet. Vol 1, PP 369 - 370.

* ከሞስኮ በፊት የነበረው ዋና ከተማ አሁን ሌኒንግራድ የሚባለው ነው ።

** የራስ ደስታ አባት

ደብዳቤ ሲዘጋጅ ሰነበተ ። የግጽ በረከቱን ዓይነት ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ዕፁብ ድንቅ የሆነ ዘውድ ፣ ማሰፊያ የወርቅ መስቀል ፣ አርባዕቱ ወንጌል መጽሐፍና ሌላም የኢትዮጵያ ብዙ ዕቃ ፣ ንግሥቲቱም እቴጌ ጣይቱ ለመስኮብ ንግሥት (አሌክሳንድራ) በረከት (ስጦታ) የሚሔድ ዕፁብ ድንቅ የተባለ በወርቅ አጫዋች ያጌጠ የሐር መሶብ ፣ የሴት ወይዘሮ መሣሪያ የወርቅ የእግር ከታብ ፣ወርቅ አልቦ ጠልሰም ፣ ወርቅ ድሪ ፣ ወርቅ ወለባ . . .[1] መሆኑን ገልጸውታል ። ካፄ ምኒልክ የተላከው ደብዳቤም እንደዚህ የሚል ነው ።

ይድረስ ከክቡር ወልዑል ቄሣር ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ኒኮላ . . .

ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን ። ከርስዎ ዘንድ የተላኩ መኳንንቶች በደህና ደረሱ ። እኛም በክብርና በደስታ ተቀብለናቸው የክቡር አባትዎን ሞት ሰምተን እጅግ አዝነን ነበር ። እርስዎ በእግዚአብሔር ፈቃድ በሕዝብዎ መውደድ ባባትዎ ዙፋን መቀመጥዎን ሰምተን በጣም ደስ ብሎናል ። ግዛትዎና ዕውቀትዎ እየበዛ እየተረፈ እንዲሔድ እጅግ ተስፋ አለን ። ያባትዎን የጥንት ፍቅርና ወዳጅነት አለመርሳታችንን ለማስታወቅ ኃዘንዎና ኃዘናችን አንድ ዘንድ እንዲተባበር ብለን ከንጉሠ ነገሥት (እስክንድር) መቃብር ላይ የሚደረግ የኢትዮጵያ ዘውድ ሰደናል ። ከዘውዱም ጋራ የታመኑ ሰዎቻችንን ሰደናል ። ዳግመኛም የክርስቲያን ሃይማኖት አርቶዶክሳዊት ወንድሞቻችሁ መሆናችንን የሚያስረዳ ፍቅራችንንም የሚያሳይዎ ወንጌልና የወርቅ መስቀል ልከናል ። እርስዎም በክቡር (እክብረው) እንዲቀበሉን ተስፋ አለን ። ክቡር አባትዎ ዊክቶር (ቪክቶር) ማሽኮፍን ወደኛ የላኩ ጊዜ የጻፉልኝን የፍቅር ደብዳቤያቸውን ቃል እርስዎም እንዳይረሱ እናውቃለን ። ዕድሜዎን እንዲያራዝም መንግሥትዎን የእርቅ የሰላም አድርጎ እንዲያስነብትዎ ፣ መልካም አሳብዎን ሁሉ እንዲፈጽምልዎ ይልቁንም ክርስቲያን በመርዳትዎ እንዲጠብቅዎ ልዑል እግዚአብሔርን እለምናለሁ ። በሚያዝያ በ22 ቀን ባዲስ አበባ ከተማ በ1887 ዓ.ም. ተጻፈ ። 2

የኢጣልያ መንግሥት ፣ በውጫሌ ውል በማታለል አጭበርብሮ ያገባውን ያሥራ ሰባተኛውን አንቀጽ እየጠቀሰ ፣ "ኢትዮጵያ በኔ ቁጥጥር ሥር ስለሆነች በኔ በኩል ካልሆነ በቀር ከማንም መንግሥት ጋር በቀጥታ መነጋገርም መዋዋልም አትችልም" በማለት አሁንም ከመስኮብ መንግሥት ጋር የምታደርገውን ግንኙነት ከመቃወም ላይ ይገኛል ። ሁኔታውንም ሌሎች ኢጣልያኖች ሲባረሩ ፣ በመሐንዲስነትና

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ 59 ፣ ገጽ 223 - 224 ።

2 ከቤተ መንግሥት መዝገብ የተገኘ ደብዳቤውን የገለበጠው አበበ ይባላል ። ዓመተ ምሕረቱና ወሩ የተጻፈው በአማርኛ ነው ።



በአናጢነት ስለ አስደሰታቸውና ቤተ መንግሥቱን ስለሠራ ፣ ምኒልክ ወደው ባስቀሩት በእንጂኒየር ሉዊጂ ካፑቺ አማካይነት በዝርዝር ተረድተውታል ።

እርሱም ፣ ዐፄ ምኒልክ በወዳጅነት ከሚያደርጉለት አስተያየትና ቸርነት ያገሩ ጉዳይ ስለባሰበት ፣ ወደርሱ የቀረቡትን በተለይ አስተርጓሚውን የልጥ ማረፊያውን አቶ ዮሴፍን በገንዘብና በመጠጥ እያባበለ ፣ በካቶሊክ የሃይማኖት አንድነት እየተጠቀመ ፣ ምስጢር የሆነውን ሁሉ ከርሳቸው በመረዳት በምስጢራዊ የቁጥር ቃል እያደረገ ወደ አሰብ ፣ ወደ አሥመራም ፣ ወደ ሮማም ይልካል ። አሁንም ዮሴፍ የመልክተኞቹ አባል ሆነው ሲቆጠሩ ፣ "አይሆንም እርሱ ልክ ኢጣልያዊ ነው" ብለው ራስ መኰንን አሳስበው ነበር ይባላል ።

በእርግጥ ፣ መላክተኞቹ ከአዲስ አበባ ከመነሣታቸው በፊት ይኸው ካፑቺ ፣ "ዮሴፍ መልካም ሰላያችን ስለሆነ ሁሉንም ነገር ከርሱ ትረዳላችሁ" የሚል የቁጥር ቃል በቁጥር 95 እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 26 ቀን 1895 ዓ.ም ወደ ካይሮም ፣ ወደ ሮማም ለባለሥልጣኖቹ ማስተላለፉን ካርሎ ዛጊ በመጽሐፋቸው ጠቅሰውት[1] ይገኛል ። በዚሁ መሠረት የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ፒዮትሮቡርግ ለሚገኘው ሲልቬስትሬሊ ጁሴፒ ለሚባለው ጉዳይ ፈጻሚያቸው ፣ መልክተኞቹ መስኮብ ከተማ ከደረሱ ዠምሮ በዮሴፍ አማካይነት ጉዳዩን በጥብቅ እንዲከታተል ትእዛዝ አስተላልፈውለት ነበር ። ነገር ግን የኢትዮጵያ መላክተኞች በመስኮብ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ ጉዳይ ፈጻሚው በብዙ ረገድ ዮሴፍን ለመገናኘት ቢፈልግም ዮሴፍ እጠረጠራለሁ ብለው በመፍራት ሊገናኙት አልፈለጉም ።[2]

መልክተኞቹ ከአዲስ አበባ በ1887 ዓ.ም. ግንቦት ወር ላይ ተነሥተው ፣ በሐረር በኩል አድርገው ፣ ጅቡቲ ገብተው ትንሽ እንደቆዩ በሰኔ ወር መዠመሪያ ላይ ከጅቡቲ ሜሳጀሪ ማሪቲም (ኢራባዲ) በሚባለው የፈረንሳይ መርከብ ተሳፍረው ፖርት ሳይድ ደረሱ ። ከዚያም ቺዛሬቪች ወደሚባለው የመስኮብ መርከብ ተዛውረው እ.ኤ.አ. በ29 ሰኔ ኦዴሴያ ሲደርሱ ፣ በዚያ ያለው አገረ ገዥ ፣ የሲቪልና የጦር ሹማምንቱን አስከትሎ ከፍ ያለ የክብር አቀባበል አደረገላቸው ። በሐምሌ 1 ቀን ከኦዴሴያ ተነሥተው ፣ በባቡር ተጉዘው ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት መናገሻ ከተማ ወደ ፒዮትሮቡርግ እስኪደርሱ

1 I Russi in Etiopia, C. Zaghi. PP. 109 - 110, 171.

2 I Russi in Etiopia, PP., 171 - 172.

በየመንገዱ ፣ በየከተማው የተደረገላቸው የጋለ አቀባበል ከፍ ያለ የወንድማማችነት መሆኑን በዘመኑ የነበሩት ጸሐፊዎች መዝግበውታል ።

ፒዮትሮቡርግ ከተማ ሲገቡ ፣ የከተማው ከንቲባ ራትኮቭ ራጎቭ የጦሩ አዛዥ ጄኔራል ቴምፌቭ ፣ የቀሩትም መኳንንትና ሹማምንት የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ፣ የከተማውን ሕዝብ አሰልፈው ተቀበሏቸው ። ቀጥሎም በቀጥታ የቅዱስ ጴጥሮስን ካቴድራል ተሳልመውና የሟቹን ንጉሥ መቃብር ጐብኝተው ፣ በመቃብሩ ላይ እንደ ደንቡ የተዘጋጀላቸውን ያበባ ጉንጉንንና ከአዲስ አበባ ይዘው የመጡትን የወርቅ ዘውድ አስቀመጡ ። ከዚያ የአውሮፓ ሆቴል ወደሚባለው ትልቅ ማረፊያ ወስደው እንደ የማዕረጋቸው ክፍል ሰጥተው አስቀመጧቸው ። ባሉበትም ሆቴል የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ፣ የግልም ሰዎች እየመጡ የወንድምነታቸውን ስሜት በፍቅርና በወዳጅነት መልክ ገለጡላቸው ። ከዚህ በኋላ በሐምሌ 7 ቀን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሉቫኖቭ ርስቶቭስኪ የሚባለው መስፍን ፣ ከዚያም አከታትለው የፍርድ ፣ ያገር ግዛት ፣ የገንዘብ ፣ የመገናኛ ፣ የጦር ሚኒስትሮችና የፈረንሳይ አምባሳደር እየተቀባበሉ ሲያነጋግሯቸው ሰነበቱ ።

በዚሁ ጊዜ ፣ የታላቁ የቅዱስ ሲኖዶስ መሪ ፓቤደኖሺቭ ኮንስታንቲ ፒትሮቪች የሚባሉት በቅድሚያ ወዳረፉበት ሆቴል ሔደው ከነፊታውራሪ ዳምጠው ጋር ተዋውቀው በወዳጅነት ሲጨዋወቱ ቆዩ ። ቀጥሎም ወደ መኖሪያ ቤታቸው መልክተኞቹን በሙሉ ወስደው ፣ ምሳ ጋብዘው ሲጨርሱ ባደረጉት ዲስኩር ለምኒልክ ምስጋና ከማቅረብ ጋር የሃይማኖት ወንድሞቻቸውን ኢትዮጵያውያንን በመቀበላቸው መደሰታቸውን ጠቅሰው ፣ “ኢትዮጵያ በልማት እያበበች ፣ በኃይል እየጠነከረች ፣ ሃይማኖቷንና አገሯን እንድትጠብቅ ”[1] ያላቸውን የጋለ ምኞት ገልጸውላቸዋል ።

ይኸ ሁሉ ከሆነ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ኒኮላ መልክተኞቹን በቤተ መንግሥታቸው የሚቀበሉበት ቀን እ.ኤ.አ. ሐምሌ 13 ቀን 1895 እንዲሆን ተወሰነ ። ሹማምንቱ መልክተኞቹ ወዳረፉበት ሆቴል ሔደው በመዠመሪያ ለዋናው መልክተኛ ለፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ በስድስት ታላላቅ ነጫጭ ፈረሶች የሚሳብ በጣም ያጌጠ ወርቅማ ሠረገላ ቀረበላቸው ፤ ሁለተኛው በአራት ፈረስ የሚሳበው ሠረገላ ለአባ ገብረ እግዚአብሔር ፣ ሦስተኛው በሁለት ፈረሶች የሚሳበው ለቀኛዝማች ገነሜና ለልጅ በላቸው ፣ ከነርሱም ኋላ ኢትዮጵያን

1 I Russi in Etiopia, C. Zaghi PP. 143-149.



የሚያውቁ ልዩ ልዩ የመስኮብ ሰዎችና ተራ ኢትዮጵያውያን ተቀምጠዋል ። ከነዚህም መካከል ለዚህ ግንኙነት በጣም የተጣጣረው ኮንት ሊዎንቴቭ ይገኛል ።

ጉዞው ካረፉበት አውሮፓ ሆቴል ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲያመራ ፣ ግራና ቀኝ የተሰለፈው ሕዝብ በሆታና በጭብጨባ እየተቀባበለ በመሸኘት ከቤተ መንግሥቱ በራፍ ደረሱ ። በዚያም የቤተ መንግሥቱ የፕሮቶኮል ሹምና ዋናው ጸሐፊ ከተቀበሏቸው በኋላ ፣ ወደ ቤተ መንግሥቱ ዘልቀው በቅድሚያ የጐበኙት የሟቹን የእስክንድር ሣልሳይን ባለቤት ፣ የንጉሠ ነገሥቱን እናት ማሪያን ቤዶሮቭናን ነው ። ከዚያ ንጉሠ ነገሥቱ ኒኮላ በአዳራሻቸው ሆነው ወደሚጠብቋቸው ተመርተው ሔደው ፣ እጅ ነሥተው ፣ ዋናው መልክተኛ ፊታውራሪ ዳምጠው ንግግር አደረጉ ። ፊታውራሪው በንግግራቸው አስፋፍተው የገለጹት ዐፄ ምኒልክ በደብዳቤያቸው ላይ ያመለከቱትን ሲሆን ፣ ለዚህ መልእክት የበላይ ሆነው የንጉሠ ነገሥታቸውን የወዳጅነት ደብዳቤ ለመስኮቡ ንጉሠ ነገሥት ፣ የእቴጌ ጣይቱን ደብዳቤ ለንግሥት አሌክሳንድራ ቢዶሮቭና ለማድረስ በመቻላቸው መደሰታቸውንና ምንም እንኳን ስለ ሣልሳይ አሌክሳንድር ሞት ቢያዝኑም ፣ ስለኒኮላ መንገሥ ምኒልክ የተሰማቸውን ደስታና መልካም ምኞት ገልጸዋል ።

በዚሁ ጊዜ ፣ ቀድሞ ለራሳቸው በወርቅና በአልማዝ ተጊጦ ለተላከላቸው ኒሻን አጸፋ ፣ ዐፄ ምኒልክ ለንጉሠ ነገሥት ኒኮላ የላኩትን በወርቅና በጌጣጌጥ አምሮ የተሠራውን ዛንገት የሚጠለቀውን የሰሎሞን ኒሻን ከምስክር ወረቀቱ ጋር አስረከቡ ። በበኩላቸው መምህር ገብረ እግዚአብሔር የወርቁን መስቀልና አርባዕቱን ወንጌል ከቡራኬና ከመንፈሳዊ አነጋገር ጋር አቀረቡ ። በዚህ ጊዜ ሁሉ ኮንት ሊዎንቴቭና ጓደኞቹ ፣ ታላላቅ የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አልተለዩም ።

በዚህ ዓይነቱ አቀባበል ፣ በንዴት ሆዳቸው የበሸቀው የኢጣልያ ዋና ጉዳይ ፈጻሚ ሲኞር ሲልቬስትሬሊ ጆሴፔና ጓደኞቹ ናቸው ። የፈረንሳዩ ሚኒስትር ሞንቲቤሉላን ጉስታቭ ፣ ሉዊ ሐኖቶ ለሚባለው የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲጽፍ ፣ “ሲልቬስትሬ በኢትዮጵያውኑ ጉብኝትና በተደረገላቸው የጋለ አቀባበል ተበሳጭቶ ፣ ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ፣ አነጋገሩ ሁሉ አንድ የውጭ አገር ዲፕሎማት ካለው የለዘበ ዲፕሎማሲያዊ አነጋገር የወጣ ነበር”[1] ሲል እንደ ገለጹለት ተመዝግቧል ።

1. I Russi in Etiopia, C. Zaghi, P. 129.

ይኸው የኢጣልያ ጉዳይ ፈጻሚ ቀጠሮ ጠይቆ ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከልዑል ሉባኖቭ በተገናኘበት ቀን ፣ "ኢትዮጵያ በኢጣልያ ሥር ሆና ፣ ምኒልክ እንደሸፍታ የሚቆጠር ሆኖ ሳለ ፣ እናንተ የሱን መልክተኞች በዚህ ዓይነት የክብር አቀባበል መቀበላችሁ የማይገባ ነው ። ይኸንኑ ወቀሳዬን በጽሑፍ እገልጻለሁ" ብሎ ረዥም ንግግር በሚያወርድበት ጊዜ ፣ ሚኒስትሩ በዝምታና በጽሞና ሲመለከተውና ሲያዳምጠው ከቆየ በኋላ መደምደሚያውን ፣ "ኢትዮጵያ ነጻ መንግሥት መሆኗን ፣ ምኒልክም የነጻዪቱ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን እና ምናለን ። ቀድሞውንም ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ አለኝ የምትለውን የበላይ ጠባቂነት መብት አልተቀበልነውም ። ስለዚህም እንደዚህ ያለው የነጻ መንግሥት መሪ መልክተኞቹን ሲልክ በመልካምና በመሰለው መንገድ መቀበል የመስኮብ መንግሥት ትክክለኛ መብቱ ስለሆነ ፣ በዚህ ምክንያት የኢጣልያ መንግሥት ለሚያቀርበው ክስና ወቀሳ ደንበኛ መልሱን እንሰጣለን" ሲል መለሰለት ።

ከዚህ በኋላ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ለዚህ አጸፋውን እመልሳለሁ በሚል ስሜት ከአውሮፓውያን መንግሥታት ጋር የመስኮብ መንግሥት ያለውን የባህልና የንግድ ልውውጥ ለማሰናከል ተጣጣረ ። እንደዚሁም በኢትዮጵያ ስሜን ዤኔራል ባራቲዬሪ ከመንግሥቱ መመሪያ በመቀበል በፊት ካፄ ዮሐንስ ጋር ባለሟል ከነበሩትና አሁን በቅርታ በአክሱም ከተቀመጡት ከእጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር ግንኙነት አድርጎ ፣ እጨጌውንና ካህናቱን በገንዘብና በልዩ ልዩ ስጦታ በመሳብ ፣ በትግራይና በትግሬ ላሉት የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ፣ "ምኒልክ በሃይማኖት ከማይመስላቸው ከመስኮብ መንግሥትና ቤተ ክህነት ጋር ግንኙነት አድርገው የኖረውን የተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ሊለውጡ ነው" የሚል ስብከት በቃልም ፣ በጽሑፍም እያደረገ ማስበተን ዠመረ ። የዚህም የፕሮፓጋንዳ ጽሑፍ በኢጣልያ አገር እየተዘጋጀ በእስክንድርያም ፣ በኢየሩሳሌምም እየተበተነ ፣ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም የኢየሩሳሌም ገዳም መምህራንና መነኮሳት በንጉሣቸው በምኒልክ ላይ እንዲነሡ ያልተሞከረ ነገር የለም ። ዳሩ ግን ፕሮፓጋንዳው ብዙ መንገድ ሳይራመድ እየከሸፈ ሔደ ።

የሆነ ሆኖ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠውና ባልደረቦቻቸው በመስኮብ ከተማ ወዲያና ወዲህ እያሉ በጉብኝትና በግብዣ ሲዘዋወሩ ፣ ከየሚኒስትሮቹ በተለይ ከውጭ ጉዳይና ከጦር ሚኒስትሮቹ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ፣ የንግግሩን ውጤት ፣ ወደፊት የመስኮብ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመርዳት ያቀደውን ፣ የኢጣልያ ጉዳይ ፈጻሚና ጓደኞቹ ለማወቅ አጥብቀው ይጣጣሩ ነበር ። ከዚህ በፊት እንደ ጠቀስነው ፣ የኢጣልያው



ጉዳይ ፈጻሚና ባልደረቦቹ ከዮሴፍም ፣ ከረዳም ወሬ ለማግኘት ቢጣጣሩ አልሆንላቸውም ።

በፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ የሚመራው የመልእክት ጓድ አላላክ የፖለቲካ ፣ የሃይማኖት ፣ የወታደርነት መልክ ስለ ነበረው ስለ ፖለቲካው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጋር ካደረጉት ውይይት በቀር አብዛኛው የፊታውራሪ ዳምጠው ግንኙነት ያበከረው ከጦር ሚኒስትሩ ጋር ነበር ። ኦዴሳ በደረሱበት በመዠመሪያው ቀን ፊታውራሪው ባማረ ፈረስ ላይ ተቀምጠው ዐሥራ አምስት ሺ የሚሆነውን የወታደር ሰልፍ እየዞሩ በጐበኙበት ሰዓት ከፍተኛ አድናቆት ነበራቸው ። ከዚያም የመልእክቱ ጓድ ዐርባ ቀን ሙሉ በመስኮብ በቆየበት ጊዜ ከየጦር አለቆቹ ጋር በመገናኘት ተወያይተዋል ። በጉብኘት ፣ በሰልፍና በግብዣ ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ፣ ጋዜጦች ሁሉ የሁለቱን መንግሥታት ወዳጅነት ፣ የሁለቱን ሕዝብ ወንድማማችነት እያጐሉ ሲጽፉ ፣ "በነጻነት የቆየችውንና የከበረችውን ክርስቲያኒቱን ኢትዮጵያ በፍራንቼስኮ ክሪስፒ የሚመራው የኢጣልያ መንግሥት የውጫሌን ውል አመካኝቶ ውጊያ በመዠመሩ ወንጀለኛ ነው" እያሉ በጽሑፍ ሲነቅፉ ኢትዮጵያን ሲደግፉ ፣ በየስብሰባው ጐልማማውና በደማቅ ቅላት መልካቸው ያሸበረቀው ፊታውራሪ ዳምጠው ብቅ ባሉ ቁጥር የተሰበሰበው መኳንንትና መሳፍንት ከነሕዝቡ በደመቀ ሁኔታ ሲቀበላቸው ሰነበተ ።

በዚሁ ጊዜ ኮንት ሊዎንቴቭ በበኩሉ ፣ "ዳግማዊ ምኒልክ ዘራቸው ከሰሎሞንና ከንግሥት ሳባ የወረደ ፣ ብልህ ፣ ቸርና ደግ ንጉሥ ከመሆናቸው ጋር ባገራቸው የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማግባት የሚጣጣሩ ፣ ላገራቸው ጸጥታና ሰላም የሚፈልጉ ሲሆኑ ፣ በሌላው በኩል ያገራቸውን ነጻነት ለመከላከል ቆርጠው የተነሡና ስላገራቸው ነጻነት የመጨረሻ ደማቸውን ለማፍሰስ የቆረጡ ናቸው ። ሕዝቡም ኩሩ ተዋጊ ፣ ሃይማኖቱንና አገሩን ንጉሡን ወዳድ ነው" እያለ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ሰነበተ ።[1]

በዚህ ዓይነት ክብርና ደስታ ከሰነበቱ በኋላ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠውና ባልደረቦቻቸው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዳግማዊ ኒኮላ ለስንብት ቀርበው ፣ አንድ ራሱ ማኅደሩ በወርቅና መጨበጫው በአልማዝ ያጌጠ ጠመንጃና ልዩ ልዩ የወርቅ ፣ የአልማዝ ቀለበት እንደዚሁም በቅዱስ አሌክሳንድር ኒቭስኪ የተሠየመ በዕንቁና በአልማዝ የተንቆጠቆጠ ባንገት የሚጠለቅ ኒሻን ለምኒልክ ፣ ቀጥሎም መሸፈኛው

1. I Russi in Etiopia, C. Zaghi, pp. 156-158

በከር ሥራ ያጌጠ በውስጡ የሴት የመታጠቢያ ቤት ልዩ ልዩ ዕቃ ፣ አንድ ያንገት ድሪ ፣ በከንድ የሚደረግ አምባርና የገሮ ጉትቻ ለእቴጌ ጣይቱ ፣ አንድ “ ኤክስፐሬስ ” የሚባል ጠመንጃና አንድ የአልማዝ ቀለበት ፣ አንድ ልዩ የኪስ ሰዓት ፣ አንድ በከበረ ድንጋይ ያጌጠ ጐራዴ ለፊታውራሪ ዳምጠው ፣ ለራስ መኰንንም በቅድስት ሐና የተሠየመ ባንገት የሚጠለቅ ባለ ኮርዶን ኒሻን ተላከ ። እንደዚሁም ለቀሩት ተከታዮች እንደ የማዕረጋቸው ተሰጥቷል ። ሌሎችም መሳፍንትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ለመላክተኞቹ ብቻ ሳይሆን ላፄ ምኒልክና ለእቴጌ ጣይቱ አንዳንድ የመታሰቢያ ስጦታ በየስማቸው ላኩ ።


ከዚህ በኋላ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠውና ባልደረቦቻቸው ንጉሠ ነገሥቱንና ንግሥቲቱን ሌሎችንም በደስታ ፣ በፍቅርና በናፍቆት ስሜት ተሰናብተው በመጨረሻ ከጦር ሚኒስትሩ ስለርዳታ አንድ መቶ ሃምሳ በርዳን ጠመንጃ ተቀብለው ወደ ኦዴሳ ተመለሱ ። አካሔዳቸው በቱርክ ዋና ከተማ በስንጣንቡል (ኮንስታንቲኖፕል) በኩል ስለነበረ ፣ የቱርኩ ሡልጣን የእልፍኝ አስከልካዩን አህመድ አሊ ባሻን ልኮ ከመርከባቸው ላይ በማስመጣት በቤተ መንግሥቱ ግብዣ አደረገላቸው ። ከዚያም ከሡልጣኑ ተሰናብተው በመርከብ ወደ እስክንድርያ (ግብፅ) ከዚያ ወደ ፖርትሳይድ ተመልሰው በመጡበት ሚሳጀሪ ማሪቲም በሚባለው የፈረንሳይ መርከብ ተሳፍረው በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ጅቡቲ ሲደርሱ ከራስ መኰንን የተላኩ ሰዎችና የፈረንሳይ ባለሥልጣኖች ተቀበሏቸው ።

ከዚህ በኋላ ፣ ወደ መስኮብ አገር ያደረሳቸው ሌምንቴቭ አሁንም እስከ ጅቡቲ ካደረሳቸው በኋላ ፣ በፍቅር ተሰነባብቶ ወዳገሩ ሲመለስ እንፊታውራሪ ዳምጠው በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከንጉሠ ነገሥታቸው ጋር በመገናኘት ኒሻኑንና ገጸ በረከቱን ለንጉሠ ነገሥቱና ለእቴጌ ጣይቱ አስረከበው የሆነውን ሁሉ በቃልና በጽሑፍ ሳይገልጹ አይቀሩም ። ዳሩ ግን ፣ የዚህን ጉዳይ የሚነግረን ምንም ጽሑፍ የለም ። ከአዲስ አበባ አነሣሣቸውን የጠቀሱት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ “. . .ወደ መስኮብ መንግሥት የተላኩት እንፊታውራሪ ዳምጠው በዕንቁ ፣ በአልማዝ የተሸለመ ለንጉሠ ነገሥት የሚገባ መዝመሪያውን ኒሻን ይዘው መጡ ”[1] በማለት ቀንጨብ አድርገው ዝርዝሩን አልፈውታል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 225 ። በተረፈ ስለሌላው ዝርዝር ሁኔታ ካርሎ ዛጊ የጻፈውን በሙሉ ማንበብ ያስፈልጋል ።



እንፊታውራሪ ዳምጠው ፣ አዲስ አበባ በመስከረም ወር 1888 ዓ.ም. እንደ ደረሱ ፣ ወዲያው ምንም ያህል የዕረፍት ጊዜ ሳያገኙ ለዓድዋ ጦርነት የከተት ዓዋጅ ተደርጎ ንጉሠ ነገሥቱ ጦራቸውን አስከትለው በጥቅምት ፪ ቀን ካዲስ አበባ ወደ ሰሜን ለዘመቻ ሲጓዙ ፊታውራሪ ዳምጠውም የራሳቸውን ጦር ይዘው የዠግንነት አሟሟት ወደሚጠብቃቸው ወደ ዓድዋ አብረው ዘመቱ ።



ፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ

መልካም ቤተሰቦች ከተባለው ከራስ ቢቶደድ መኰንን እንዳልካቸው መጽሐፍ



ኒኮላይ ሰርጌዬቪች ሌዎንቴቭ
ከቫቲካን ቤተ መጽሐፍ

# ክፍል ሦስት

## የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት

# ምዕራፍ ሐያ አምስት

### የክተት ዓዋጅ — የንጉሠ ነገሥቱ ጉዞ ወደ ትግሬ — ወታደራዊ ድርጅትና አቅዋም

ዶክተር ትራቬርሲና ኮሎኔል ፒያኖ ወዳገራቸው እንደ ተመለሱ ፥ ዠኔራል ባራቲዬሪ በሰሜን ማጥቃቱ ቢታወቅም ፥ ዳግማዊ ምኒልክ የውጫሌን ውል መፍረሱን ለየመንግሥታቱ ከማስተላለፍ በቀር በቶሎ የጦርነት ዓዋጅ አላወጁም ። ሁልጊዜም ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ያለው ጠብ እንደማያቋርጥና ጦርነትም እንደማይቀር በልባቸው ተገንዝበዋል ። በሰበብ በአስባብ በሚያገኙት አጋጣሚ እየተጠቀሙ ፥ መሠረታዊ ጥያቄያቸውንም ሳይለቁ ላይ ላዩን ፥ "ወዳጅነታችን ለምን ይቅር ፥ በከንቱስ ለምን የክርስቲያን ደም ይፍሰስ ፥" የሚል ደብዳቤ እየጻፉ ጊዜ ያራዝሙ ነበር ። ጊዜ ያራዘሙባቸው ምክንያቶች ሦስት ናቸው ።

ሀ/ ወደፊት ለሚያደርጉት ጦርነት በቂ የምግብ ስንቅና የጦር መሣሪያ በደንብ እስኪዘጋጅ ድረስ ፥

ለ/ ራስ መኰንን በ1881 ዓ.ም. ሮማን የጐበኙ ጊዜ የሐረርን ጉምሩክ ቀረጥ እንደ ማያዣ አድርገው ከኢጣልያ ባንክ የተበደሩት አራት ሚሊዮን ሊሬ (አንድ ሚሊዮን የማሪያ ቴሬዛ ብር) እስኪከፈል ፥

ሐ/ ሌላው አውራጃ ሁሉ ለማዕከላዊ መንግሥት ሲታመን ፥ በወላሞ ንጉሥ ጦና አስቸግሮ ስላመጣ እርሱ በዘመቻ ተገዶ እስኪገብርና ደቡባዊ ዠርባቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ ነው ።

ስለዚህ የኢጣልያን የወታደር ብዛትና ትጥቁን ፥ የጦር መሣሪያውን ብዛትና ዐይነት ፥ ራስ መኰንን ሮማን በጐበኙ ጊዜ ባይናቸው ያዩትን

በዝርዝር ባስረዱዋቸው መጠን ከእንደዚህ ያለው አውሮፓዊ ሥልጡንና ኃያል መንግሥት ጋር የሚደረገው የገሃድ ጦርነት በዋዛ እንደማይፈጸም ያውቃታል ። ዝግጁነትም ፣ ብዛትም ያላቸው የጦር መኳንንትና ወታደሮች ቢኖሩዋቸውም ፣ እነዚህኑ በዘመናዊ የጦር መሣሪያ ካላስታጠቁ ብዛትና ዝግጁነቱ ሁሉ ዋጋ ቢስ እንደሚሆን ከቅርቡ ከመቅደላው ጦርነት ስለሚገነዘቡት ፣ በዚህ ጊዜ አሳባቸው ያተኮረው በተቻለ መጠን በጥድፊያ መድፍ ፣ ጠመንጃና ጥይት ከመሰብሰቡ ላይ ነው ። ከቀድሞ ዠምሮ በእጃቸው የነበረ ጠመንጃና ጥይት ፣ በቅርቡም ከአሰብ የመጣላቸው ሁለት ሚሊዮን ጥይት እጃቸው ቢገባም ፣ ይኸም እንደማይበቃ ዐውቀውታል ። ከጀርመን አገር አንድ መቶ ሺ ጠመንጃ አዘው የነበረውን ፣ የጀርመን መንግሥት ከኢጣልያ ጋር ባለው የቃል ኪዳን ዝምድና ምክንያት እምቢታውን ስለገለጠ ጉዳዩ አሳሳቢ ሆነ ። በዚሁ ጊዜ የመሣሪያ ማግኛው ምንጭ ፈረንሳይና መስኮብ ብቻ ነበሩ ።

ስለዚህ ፣ ከወዳጆቻቸው ከመስኮብ ዘንድ በሌዎንቴቭ በኩል ፣ ከፈረንሳይ መንግሥት በሸፍነና በነእርኑ አማካይነት የተቻለውን ያህል ሰበሰቡ ። ስለ መሣሪያው ዝግጅት ነጋድራስ አፈወርቅ በጻፉት መጽሐፍ ከዚህ የሚከተለውን አስፍረው ይገኛል ።

> ዐጤ ምኒልክ . . . ነገራቸውን ሁሉ እያበጃጁ እያሰናዱ ተጋፍቶ ቢመጣም እንገጥመዋለን ፣ ተጋፍቶ ባይመጣም ተደራጅተን ሰናበቃ አለፈቃዳችን የያዘውን አገር ግፋን ሔደን (ወደ ፊት ገፍተን) እናስለቅቃለን ይሉ ዠመር ። በዚሁ ቆርጠው ተቀምጠው ሳለ አንድ ቀን ከፈረንሳዊ የገዙት 30 ያህል የስምዎ (የስማቸው) ምልክት "ም" የተጣፈበት መልካም መድፍ ደርሶላቸው ደስ እያላቸው ሲአዩ ቆዩና በሐኪም ትራቬርሲ ፊት እንግዲህ የመጣው ይምጣ አይመጣም እንጂ ቢመጣ በዚህ እናሳየዋለን [1] አሉ . . .

ይኸን የተናገሩት ፣ ጣልያኖቹ ከራስ መንገሻ ጋር በኮዓቲትና በሰንዓፌ ከነቀኛዝማች ኃይለማርያም ጋር በደብረ ኃይላ ከመዋጋታቸው በፊት ትንሽ ጊዜ ቀደም ብሎ ነው ። ነገር ግን ፣ በማናቸውም ኢጣልያኖቹ እስከ መረብ ድረስ ከመግፋታቸው የተነሣ ለመዝመት አስበው ነበር ። በደቡብ ካሉት ጠቅላይ ግዛቶች ሐረርጌን ጨምሮ በማዕከላዊው መንግሥት ሥር ተጠቃለው ሳለ ባቅራቢያ ካሉት አውራጃዎች ፣ እላይ እንዳልነው ፣ የወላሞ ንጉሥ አፈንግጦ እነራስ መንገሻ አቲከምን ቢልኩ አልበገር አለ። እርሱንም ሳያሳምኑና ዠርባቸውን

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ — ገጽ 86 ።



ሳያስተካክሉ ወደፊት ዘልቀው ወደ ትግሬ መዝመቱም ቅርታ አሳድሮባቸዋል ።

በዚህ ምክንያት ራስ ሚካኤልን ፣ ራስ መንገሻ አቲከምን ፣ ጅማ አባ ጅፋርን ፣ ሊቀመኳስ አባተንና ሌሎችንም አስከትለው በኅዳር 7 ቀን 1887 ዓ.ም ካዲስ አበባ ተነሥተው በ27 ቀን ዳሞት ከጦና ከተማ ገቡ ። ነገር ግን ፣ በዚህ ጦርነት በከንቱ ለሚጠፋው ሳገሩና ለባላገሩ አዝነው ፣ "አገር ከጠፋ በኋላ ሲያቀኑት ያስቸግራል ። ገንዘብም በግድ ካልሆነ በቀር በፈቃድ የሰጡት አያልቅም ። አገርህን አታስጠፋ ፤ ግብርህን ይዘህ ግባ" ብለው በመጨረሻ የማስጠንቀቂያ ምክር ለጦና ቢልኩበት የእምቢታ ቃል መለሰ ።

ከዚህ በኋላ ወታደሩን በየመሪው በግራና በቀኝ ፡ በፊት ለፊትም ልከው ፣ ጦርነቱ ተዠመረ ። ውጊያው ወደ ማለቂያው ሲደርስ ጦና ከወላሞ ወደ ቦረዳ ሸሽቶ ነበር ። ወታደር እግር በግር ተከታትሎ ደርሶበት በጥይት ተመትቶ ተያዘ ። ጦርነቱ አልቆ አገሩ ጸጥ ሲል ፣ ወታደር የማረከውን ሰውና ከብት ፣ በተቻለ መጠን ለየባለቤቱ እንዲመልስ አዘዙ ። ለወላሞ ግዛትም ራሱን ጦናን መልሰው ሾመውና አደላድለው ሲጨርሱ ፣ እርሳቸው ወደ ከተማቸው በጥር 11 ቀን ተመልሰው ገቡ ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ጦርነቱን ለመካፈል መጥተው የነበሩት ፡ ጀጌ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በሰፈሩበት ሰዓት ተሰናብተው ፣ በቆጫና በገሙ በኩል አድርገው ፣ ከፋ ከግዛታቸው ገቡ ።[1]

ዐፄ ምኒልክ ፡ ከወላሞ ሲመለሱ ፣ ከራስ መንገሻ ተልከው የመጡት ሹም አጋሜ ተሰፋዬ ፣ ራስ መንገሻ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ከኢጣልያኖች ጋር ሁለት ጊዜ ተዋግተው ስለ ተሸነፉ ፣ የትግሬን ግዛት ለቀው ወደ ራስ ወሌ ግዛት መግባታቸውን በዝርዝር ለንጉሠ ነገሥቱ አስረዱ ። ቀጥሎም አዲስ አበባ ገብተው እንደ ሰነበቱ ፣ በደብረ ኃይላ እነቀኛዝማች ኃይለማርያም ተዋግተው አሁንም ጣልያኖች ማሸነፋቸውን ሰሙ ። ከዚህ በኋላ ፣ የጣልያን ጦር ወደፊት እየገፋ አዲግራትንና መቀሌን በመያዝ መሽጎ ፣ ግንባር ቀደሙ ጦራቸው ወደ አላጌ መገሥገሡ ተሰማ ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ 218 - 220
Une Expedition-Avec le Negus Menelich, J.C.Vanderheym Chap. IV,PP. 107 - 161.

ቢሆንም ቀደም ብለን ያወሳነው፣ የኢጣልያ ብድር እንዲከፈል ሰው ሁሉ በቀንድ ከብት አንድ ብር (የቀንድ ብር ወይም የፈሰስ ብር) እንዲያዋጣ ቀደም ብሎ ትእዛዝ በያለበት ተላልፎ ነበር። ገንዘቡ ተሰብስቦና በራስ መኰንን አማካይነት ተከፍሎ፣ ስለ ዋስትና በኢጣልያኖች እጅ ተይዞ የነበረውን የሐረር ጉምሩክ በዚሁ ሰሞን አስለቀቁ።

ጦናን ከአሳመኑና ይኸንንም አንድ ሚሊዮን ብር ከፍለው ከዕዳ ነጻ ሲሆኑ የጦርነት ዓዋጅ ገና አላሳወጁም ነበር። ከወላሞ እንደተመለሱ በግንቦት ወር ወደ ወረይሉ ሔደው ዋግሹም ብሩን አስረው ልጃቸው ጓንጉልን ሾሙ። የኢጣልያኖቹንም የወረራ ሁናቴ በቅርቡ ካረጋገጡ ወዲህ በሰኔ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ክረምቱን በሙሉ ሲዘጋጁ ከርመው፣ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ መክረው፣ ዘክረው ከጨረሱ በኋላ፣ በመስከረም ወር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክተት ዐዋጅ በይፋ በነጋሪት ዐወጁ።

> እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም።
>
> አሁንም አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል። እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ የሰዉን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር።
>
> አሁን ግን፣ በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ ለምሽትህ ለሃይማኖትህ ስትል በሐዘን እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን፣ ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ። [1]

በዛሬ አስተያየት፣ ይህ የንጉሠ ነገሥቱ የክተት ዓዋጅ አንድ የበታች መኰንን ከፊቱ ላለው ወታደሩ በንግግር የሚያስጠነቅቀው ዓይነት ይመስላል እንጂ፣ ካንድ ከበላይ የንጉሠ ነገሥት መሪ የተሰጠ ጠቅላላ የክተት ዓዋጅ አይመስልም። "የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም፣ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም" ሲሉ የቃል ዛቻ ይመስላል።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ...ገጽ 225። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሳይጠረዝ በቀረው ታሪካዊ ጽሑፋቸው የዓዋጁን ቃል በጥቃቅን አባባል ለየት አድርገው አስፍረውታል። ገጽ 187።



ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱና ወታደሩ አብረው የሚጓዙ፣ አብረው የሚበሉ፣ አብረው የሚሠሩና የኑሮአቸው ሕይወት ለክፉውም ለደጉም የተሳሰረ ስለሆነ እያንዳንዱ ወታደር ይህን የክተት ዐዋጅ በቀጥታ በነፍስ ወከፍ ለራሱ እንደ ነገሩት ያህል በመመልከት ትእዛዙን ወዶ አክብሮ ይቀበለዋል። በአማላጅ በወዳጅ እድናለሁ ብሎ ተስፋ እንዳያደርግ ነገሩን መሐላ ደምድሞታል። በዚህ ላይ ደግሞ በዐዋጁ ውስጥ የኢጣልያ ስም አልተጠቀሰም። ይኸም በጊዜው ለጥንቃቄ ወይም ነገሩን ላለማባባስ በምክር የተደረገ ዘዴ ይመስላል። የሆነ ሆኖ ይኸን ዐዋጅ በመስከረም ወር ካደረጉ በኋላ፣ ላገር ጥበቃ አጎታቸውን ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴን ሾመው እርሳቸው በጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ካዲስ አበባ ወደ ዘመቻው ተጓዙ።

የኢትዮጵያ ወታደር፣ የኢጣልያ አጥቂነት እንደ ታወቀና የክተት ዐዋጅ ከታወጀ ወዲህ፣ ለዚህ ለዓድዋ ጦርነት ቀረብ ያለው የጐጃም፣ የቤጌምድር፣ የወሎና የላስታው ከ300 እስከ 500 ኪሎ ሜትር ያህል፣ የሸዋና የሐረር፣ የባሌ፣ የአሩሲ፣ የከምባታ፣ የሲዳሞ፣ የጅማ፣ የከፋ፣ የወለጋና የኢሉባቦር ጦር ከ600 እስከ 1000 ወይም እስከ 1500 ኪሎ ሜትር ድረስ ርዝመት ያለውን አገር በእግሩ አቋርጦ ተጉዟል። አብዛኛው አጭር ሱሪና ጥብቆ ለብሶ በዚያ ላይ ነጠላውን ደርቧል። የሚራመደው በባዶ እግሩ ከደንጊያና ከእንጨት እንቅፋት ጋር እየታገለ ውስጥ እግሩን እሾህ በሙቀት ጊዜ ረምጫ እያቆሰለው ነው።

ለራሱም ቆብ ስለሌለው የፀሐይ ሐሩር የሌሊት ቁር ይፈራረቅበታል፤ ቢታመም ባገር ባህል መድኃኒት ከመጠቀም በቀር ደንበኛ ሕክምና አያገኝም። በጉዞም ላይ እያሉ ራሱን የባህሉን መድኃኒት እንደ ልብ ማግኘቱም ይቸግራል። ከዐፄ ምኒልክ ጓዝ ጋር በከረጢት የተያዘ ቁስል ማድረቂያ ዮድና ዶፈር፣ ለራስ ሕመም አስፒሪን፤ እንዳለ ቢታወቅም ባቅራቢያ ላሉት ሹማምንትና ዘበኛ እንኳን ማድረሱ ያጠራጥራል።

ተዋጊ ወታደር፣ ስንቅ አቀባዩ ገባር፣ ድንኳን ተካዩ፤ አብዛኛውን ጊዜ በራሱ ወጭ ለስንቁ ያዘጋጀውን ጥራጥሬ እህል (ሽምብራ፣ አተር፣ ባቄላ)፣ የተቆላ ወይም በእሳት በስሎ የተፈጨ የገብስና የስንዴ ዱቄት በየአረፈበት በውሃ ነክሮ አድበልብሎ የሚበላውን በሶ ባንድ ትከሻው መዋጊያ ጠመንጃውን ወይም ጦሩን በሌላ ትከሻው ተሸክሞ ይጓዛል። ግማሹም ጠመንጃውን ራሱ ተሸክሞ፣ ስንቁን በአህያ ላይ አድርጎ፣ የመጓዝ ዕድል ያለው አለ። የጉዞውን ድካም ለማዘናጋት ከወንዶቹ ውስጥ ሽለላና ቀረርቶ እያሰማ የሚጓዝ አለ። ከሴቶቹም የሚያንጐራጉሩና አዋጊ ግጥም የሚገጥሙ ይገኛሉ።

ማታ በሠፈር ከደረቅ መሬት ላይ ሣር አጭዶ ጐዝጕዞ ይጋደማል ። እንቅልፍም ሊወስደው ይችላል ። አህያ የሌለው እንደልቡ ሲ.ተኛ ፣ ባለአህያው ግጦሽ ለአህያው መፈለጉና አህያውን አውሬ እንዳይበላበት የመጠበቁ ግዴታ ስለአለ ባለአህዮችና ባለአጋስሶች በየፈረቃ የመተኛት ግዴታ አለባቸው ።

መኳንንትና ሹማምንት እንደየማዕረጋቸው ለብሰው ፣ በበቅሎ ተቀምጠው ፣ ባርኔጣ ደፍተው ፣ አንዳንዶቹም ሻሽ አስረው ፣ አሽከር አስከትለው ፣ ሲጓዙ ውለው ቀን ለምሳ ፣ ማታ ለራት ከቤታቸው ሲነሡ ያስያዙትን ቋንጣ ፣ ዳቦ ቆሎ ፣ ድርቆሽ ፣ ጭኮ ወይም ጥረኾ ይመገባሉ ። ጊዜያዊ መጠጥና ውሃ በእርኮትና በጐባበጠ ቀንድ የመጠጣት ፣ በድንኳን ውስጥ የመተኛት ዕድል አላቸው ። ከጉዞው በቀር በሠፈረበት ቦታ የጦርነቱ ጊዜ እየተራዘመ በሔደ መጠን ፣ የስንቅ ማለቅና ሌላውም ሁሉ ችግር ለነርሱም ቢሆን እየተባባሰ መሔዱ የማይቀር ነው ።

ሌላው ጭፍራ ፣ አሽከርና ገረድ በእግሩ ሲጓዝ እነርሱ በከብት ጀርባ ይጓዛሉ ። ሌላው እብርድ ላይ ሲ.ተኛ እነርሱ በድንኳን ውስጥ ፣ ከምንጣፍ ላይ ብልኮና ጋቢ ለብሰው ይተኛሉ ። እንደዚህ ያለው ያኗኗር ልዩነት በኢጣልያኖቹም በኩል አለ ። ሆኖም ረዥሙን ጉዞ በየቀኑ እበቅሎ ላይ ሆኖ ዳገት መውጣቱ ፣ ቁልቁለት መውረዱ ፣ ሸለቆ ፣ ወንዛወንዝና ሰፋፊ ሜዳ ማቋረጡ ፣ ሁሉም ቢሆን ለሰውነት አድካሚና አሰልቺ ፣ ጭንና ባትን የሚያደነዝዝ ነው ።

ከነርሱ የበለጠ ግን ፣ እነርሱን በመከተል ጠመንጃና ጐራዴ ፣ እርኮትና ሌላም ዕቃ ተሸክሞ በጌታው በቅሎ ኋላ የሚኳትነው አሽከር ፣ በጀርባዋ የስንቁን አገልግል ወይም ሹሮና ድልህ በቅላቅል ተሸክማ የምታጓዘው ገረድ አሁን ካለንበት ዘመን ላይ ሆነን ስናጤነው ሁለቱም የነበረባቸው ድካም ከፍ ያለ ነው ። ከተወሰነው ሠፈር ቀን ለምሳ ፣ ሌሊት ለመኝታ ጌታውና ሌላው ጭፍራ ሲያርፍ ፣ አሽከር ድንኳን የመትከል ፣ እንጨትና ውሃ ፣ ሣር ለበቅሎ የመፈለግ ግዴታ አለበት ። ገረድም መብል የማዘጋጀቱ ጉዳይ ይጠብቃታል ። ጌትዬው በድንኳን ውስጥ ፣ በሥጋጃ ወይም በካሊም ፣ አለዚያም በቁርበት ላይ ሲ.ተኛ አሽከርና ገረድ ቀን ለብሰው የዋሉትን እንደ ለበሱ ፣ እንደተራው ወታደር እጠራ ሜዳ ላይ የጌትዬውን ድንኳን ከበው ይተኛሉ ።

ከአዲስ አበባ ወይም ከሌላው ከተማ ተመርጣ የመጣችው የጭን ገረድ የምትባለው የጌታዋን መኝታ አነጣጥፋ ፣ እግር አጥባና ራት አብልታ ፣ እሷም የተራረፈውን በላልታ ከጌታዋ ጋር በድንኳን



ውስጥ የመተኛት መብት ይኖራታል ። ይኽን ሁኔታ ባለቤት ሴት ወይዘሮ የተስማሙበትና ያገር ባህል የፈቀደው ስለሆነ ፣ በመኝታም በመብልም የጭን ገረድ ከሌሎች የተሻለ ዕድል አላት ማለት ነው ።

በዚህ አያያዝ ፣ አሽከርና ገረድ የተጐዱ ፣ ጌትየው የተጠቀመና ድልወት ያገኘ ይመስላል ። ነገር ግን በጦርነቱ ወቅት ገረድና አሽከር ይልቁንም ገረዲ ወደኋላ ከጓዝ ጋር ትቆያለች ። የተሻለ ኑሮ ያገኘው የጦር መኰንን ከወታደሩ ጋር እጦርነቱ እፍላ ላይ ገብቶ የመዋጋት ግዴታ አለበት ። በመጨረሻም በዕድል ካልዳነ በቀር የመቁሰልና ጭራሹንም የመሞት አደጋ አለበት ።

የሆነ ሆኖ ፣ በዚህ ዐይነት የኋላ ቀርነት ችግር መካከል ወደፊት እንደምናነበው ፣ የኢትዮጵያ ወታደር ረዥሙን የወራት መንገድ በእግሩ ተጉዞ ፣ የራሱን ጥራጥሬ እህል በልቶ ፤ ንጹሕ ውሃ ተጐንጭቶ ከባሕር ማዶ በባቡርና በመርከብ ተሳፍሮ የመጣውን ድርጅቱ የተሚላውን ፣ በጦር ትምህርት ቤት የሠለጠነውና በማናቸውም ምቾት ያልተለየውን የፈረንጅ ወራሪ ተዋግቶ በማሸነፍ ፣ አገሪቱን ከባርነት ውርደት በማዳን ፣ ለሚመጣው ትውልድ አኩሪና አስመኪ. ታሪክ አወረሰ ።

በርሱ አንጻር ፣ የሠለጠነውና መልካም ልብስ ለብሶ ፣ በጥሩ መብልና መጠጥ ሰውነቱን ገንብቶ ፣ ላገሩ ቅኝ አገር ለማውረስ በድንፋታና በእብሪት የመጣው የኢጣልያ ወታደር የመሸነፍን ወራዳ ጽዋ ቀምሶ ፣ ለወገኑ መጥፎ ዝናን ለዘላለም አተረፈ ። በድልወት የተቀናጣው ባለመለዮውና ባለጫማው የኢጣልያ ወታደር ለየካቲት 23 ቀን እጥቢያ በሌሊት ጉዞ ሲደናበር የእንዳ ኪዳነ ምሕረት ፣ የአባ ገሪማ የማርያም ሸዊቶ ዳገትና ቁልቁለት ፣ ሸለቆና ጉብታ ፣ ጠጠርና ደንጊያ ሲያዳክመው ፣ የኛው ወታደር ዱሮውን በለመደው አኗኗር ሁሉንም ችግር በጠቅላላው በመቋቋም ጠላቱን ተዋግቶ አሸነፈ ።

መቻም ቢሆን መማርም መሠልጠንም ተገቢ ነው ። ነገር ግን ራሱ ሠለጠንሁ ብሎ ፣ በድልወት ኖሮ ፣ ሌላውን መናቅ ራስን በተናቀው እጅ ያዋርዳል ። የምዕራቡም ፣ የምሥራቁም ሥልጡኑና ገናናው የሮማ የቄሣሮች መንግሥት የወደቀው ባልሠለጠኑና ባልተማሩ ፣ በሚንቋቸው ነገዶች እጅ ነው ። ንጉሡ ኡምቤርቶና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ከባለሥልጣኖቻቸው ጋር ይኽን ያባቶቻቸውን የሮማውያንን ያለፈ ታሪክ በክፍል እንደ ተማሩት አይጠረጠርም ። ይሁን እንጂ ፣ በዚህ ኢትዮጵያን ለመውረር በተነሡበት ዘመን በደንብ አላጤኑትም ። ነገር ግን ይኽን ያጤኑት ድል ከተመቱ በኋላ መሆኑ ነው ። የዚህም ትርጉሙ 'ዥብ ከሔደ ውሻ ጮኸ' እንደሚባለው መሆኑ ነው ።



DÉFILÉ DE LA CAVALERIE DEVANT MÉNÉLIK (PAGE 190).

የምኒልክ ጉዞ
ለቱር ዲሞንድ ከኤች አደን መጽሐፍ



የወላሞ ባላባት ጦና

ከአባ ማስያስ መጽሐፍ




ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ
ከሞሪስ ደኮፒ መጽሐፍ



በዚህ ዘመን ያንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ትጥቅ

ከገ፫ን ዴስም መጽሐፍ

የዓፄ ምኒልክና የሠራዊታቸው ጉዞ ወደ ሰሜን



# ምዕራፍ ሐያ ስድስት

## በራስ መኰንን አዝማችነት ግንባር ቀደም የሆነው ጦር አባጊ ስለመድረሱ—ራስ መኰንን ከጀኔራል ባራቲዬሪና ከማዦር ቶዜሊ ጋር የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተገነዘብነው ፡ የኢጣልያ መንግሥት መሠረታዊ አሳብ ቢቻል መላ ኢትዮጵያን ፡ ያም ቢቀር የሰሜኑን ክፍል በሙሉ ይዞ ከዚያም ሁኔታው እየታየ ወደፊት መግፋትና ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት መፍጠር ነው ። ለዚህ ዓላማ የሚያስፈልገው በጀት ዐሥራ አራት ሚሊዮን ሊሬ ግድም ተፈቅዷል ። ይኸውም በኢትዮጵያ ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የማርቴሬዛ ብር ይሆናል ። ወታደሩም በየጊዜው ከናፖሊ ወደብ እየተሳፈረ ፡ ምጥዋ ላይ እየተራገፈ ፡ አሥመራና አዲግራት ላይ እየተከማቸ በየመሥመሩ ይደለደላል ። ቀድሞ ከተያዘው ከሠራዬ ፡ ከሐማሴን ፡ ከአከለ ጉዛይ ፡ ከሐባብ ፡ ከቦጐስ ፡ ከከረን አውራጃዎችና አሁን በቅርቡ ከተያዘው ከእንደርታ ፡ ከአጋሜ ፡ ከተምቤን ፡ ከገረአልታ ፡ ከእንዳ መሆኒ የሚገኘው ያገር ተወላጅ በግድም በውድም እየተመለመለ በድርጅት ታጥቋል ። ሌላው ደግሞ የነራስ ስብሐት ፡ የነደጃች ሐጐስ ተፈሪ ፡ የነደጃች ዓሊ ፡ የነሼክ ጠልሃ ነጭ ለባሽ ባንዳ በየባላባቶቹ አማካይነት ጠመንጃ እየተቀበለ ዝግጅቱ በኢጣልያኖቹ በኩል በትጋትና በቅልጥፍና ይራመዳል ። በዚያው መሥመር የስለላውና ባለባቶቹን የመከፋፈሉ ጉዳይ በግልጽም በምስጢርም ይካሔዳል ።

ባለፉት የኮአቲት ፡ የሰንዓፌና የደብረ ኃይላ ጦርነቶች ፡ የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ራስ መንገሻን ሊያጠቁ የቻሉት ለጦርነት ባሠለጠኑት በዚህ ያገር ተወላጅ ጦር ከፍተኛ ድጋፍ መሆኑ አይጠረጠርም ። የኢጣልያ መንግሥት ላገሩ እንግዳ ቢሆንም ፡በሀብት ምጣኔና በቴክኒክ ከፍ ያለ የሠለጠነ መንግሥት ስለሆነ ፡ ሁሉንም ጉዳይ በየመስኩ በማዘጋጀት ያገር ተወላጁን ለጦርነት በማሠልጠን በሹመትና በገንዘብ ወሬ ነጋሪ ፡ አስረጅና መንገድ መሪ እየገዛ የወራሪነት ተግባሩን በደንብ ይመራል ።

ከወዲህም ባዬ ምኒልክ በኩል ዝግጅቱም ፡ ስለላውም እየተከናወነ ፡ የኢጣልያ መንግሥት ከመረብና ከበለሳ ሙና ወዲህ የያዘውን

ወረዳ ሁሉ በሰላም እንዲለቅ አጥብቀው እንደጣሩ በትክክል ይታያሉ ። በዚህም በኩል ለጦርነት ዝግጅቱና ሰላም ፍለጋው ጐን ለጐን ይሔዳሉ ። በኢጣልያ በኩል የተፈለገው ደግሞ ፣ በጦርነት ወይም በሰላም አገር ማግኘት ብቻ ስለሆነ ፣ የሁለቱ መንግሥታት አሳብ በፍጹም የተለያየ በመሆኑ ፡ ሁለቱም ወደ ጦርነቱ መምጣት ግዴታቸው ሆነ ።

በኢትዮጵያ ባለፈው የሃምሳ ዓመት ታሪክ ውስጥ የሥልጣን መያዝ መሠረት የጦር ኃይል ነው ። ዐፄ ቴዎድሮስ ከመሳፍንቱ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዙፋን የወረሱት ፣ አሁንም ዐፄ ምኒልክ በንጉሠ ነገሥት ዙፋን የተቀመጡበት በጦር ኃይል ነው ። እውነት ነው ፣ ከነገሡ በኋላ ነጋሢው ሁሉን እንዳመሉ ሲያስተዳድረው ፣ የመስፍኑን ወይም የመኰንኑን ክብሩን ሲጠብቅለት ፣ በሹመትና በሽልማት ሲያሳድገው ፣ ለሕዝብ ትክክለኛ ፍርድ መስጠቱ ሲታይ ፣ ከየትም ክፍል ቢወለድ ፣ "ይኸስ ይገባዋል ፣ ሺ ዓመት ያንግሠው" የሚባል አለ ። ዐፄ ምኒልክ በዚህ በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ሁሉን እንዳመሉ በመያዝ ፣ ለሁሉ በተቻለ መጠን የሚገባውን በመስጠታቸው ፣ ለውጊያ ፣ ለቅጣት ፣ ለበቀል ሳይቸኩሉ ሁሉንም በትዕግሥት እያመዛዘኑ ስለሚሠሩ ይነስ ይብዛ በዚህ ጊዜ ባገሪቱ የሕብረት ስሜት ፈጥረው መጭውንና ከባዱን ጦርነት እንደ ምንም ሲወጡት ይታያል ።

ይኸውም ሆኖ ፣ የቅርብ ረዳታቸው ራስ መኰንን ኢጣልያን በጐበኙበት ሰዓት የእግረኛውን ፣ የመድፈኛውንና የመርከበኛውን ወታደር ትጥቁን ፣ የጦር መሣሪያውን ብዛትና ጥራት ባይናቸው ያዩትን በዝርዝር ለንጉሠ ነገሥቱ ማስረዳታቸው የማይቀር ነው ። ባንድ ወገን የፈረንጅን ጦር አንችለውም የሚል ጥርጣሬ ባፄ ምኒልክና በመኰንን ዘንድ ሊያድር ይችላል ። በሌላው ወገን ፣ "እኛ ወደፊት ገፍተን ከኢጣልያ ስንዋጋ ከኋላችን አገሌና አገሌ ሸፍተው ቢወጉንስ ? እነ አገሌ ተነጥለው ወደ ጠላት ቢደረቡስ ? በስንት ጣር ያገኘነውና ያቋቋምነው መንግሥት መልሶ ቢፈርስስ!" የሚል ሥጋት ሊያዋልላቸው ይችላል ። በዚህ አንጻር ደግሞ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከነገሡ ጀምሮ ያደራጁት የጦር ሠራዊትና በሹመት በማዕረግ ያሳደጉት የጦር አለቃ ብዛቱን ፣ ንቃቱን ፣ ታማኝነቱን ሲያዩት ይበራታሉ ። ከኢጣልያ በወዳጅነቱ ጊዜ የተቀበሉትና ከፈረንሣይ መንግሥት በንጹሕ ወቄት ወርቅና በዝሆን ጥርስ* የገዙት ጥሩ ጥሩ የጦር መሣሪያ

* አንድ ወቄት ወርቅ (በ1909 ዓ.ም.) ከ37—39 የማርያቴሬዛ ብር ሲሆን አንድ ፈረሱላ የዝሆን ጥርስ ከ180 እስከ 210 ብር ያወጣል ።



በእጃቸው መኖሩን ሲረዱና በዙሪያቸው ፣ ባገዛዝ ብቻ ሳይሆን በጋብቻና በወዳጅነት በፍቅር ገመድ ያሰሩዋቸውን የመኳንንትና የመሳፍንት ብዛትና ሕብረት ሲመለከቱ ልባቸው በኩራትና በአሰኝታ መጽናናቱ የታወቀ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ባላቸው ያስተዳደር ዘዴና አስተዋይነት ጐን ንቁና ብልህ የሆኑት ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ያላቸው የፖለቲካ ፣ የጦርና ያስተዳደር ልምድ ፣ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መተባበር ፣ በዘመዶችና ቁጥራቸው በበረከተ መሳፍንትና መኳንንት መከበባቸው ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ልብ በአለኝታ የተመላ ሳይሆን አልቀረም ።

ቢሆንም በቤተ መንግሥቱ በዚህ የጦርነት ዋዜማ ሦስት ክፍል ይታያል ። በአንደኛው ክፍል እንደ እቴጌ ጣይቱ ፣ እንደ ራስ ወሌ ፣ እንደ ደጃች በሻህ አቦዬ ፣ እንደ ፊታውራሪ ገበየሁ ፣ እንደ ሊቀ መኳስ አባተ ያሉት ፣ "ኧረ እንበለው የምን መለማመጥ" የሚሉ ናቸው ። በሁለተኛው ክፍል ከንጉሠ ነገሥቱ ዠምሮ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ራስ መንገሻ አቲከም ፣ ራስ መኰንን ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄ ፣ አፈንጉሥ ነሲቡ ፣ (አቶ) ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሁኔታውን በማመዛዘን ነገሩን በለዘብታና በዘዴ ይዘው ሰላማዊ መንገድ የሚፈልጉ ናቸው ። ሦስተኛ ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ራስ አሉላ ፣ ራስ ሐጐስ ባሁኑ ጊዜ የተወረረው አገር የትውልድ አገራቸው ስለሆነና የኢጣልያ መንግሥት ስለከዳቸውም ጦርነቱን አጥብቀው እንደሚፈልጉት ግልጥ ነው ።

ስለዚህ ፣ በጠቅላላ የሁሉም አሳብ ተመዛዝኖ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሚመራባቸው አሳቦች በሁለት ላይ በግልጽ እንደ ተመሠረቱ ይታያል ።

፩ኛ. በማናቸውም ረገድ በትዕግሥት በሰላም ኢጣልያኖችን ካገር ለማስወጣት መፈተን ፤

፪ኛ. የሰላሙ መንገድ በፍጹም የከሸፈ እንደሆነ ጠንክሮ መዋጋት ነው ።

የኢጣልያ መንግሥት ግን እላይ እንዳልነው ፣ እንደ እንግሊዝና እንደ ፈረንሣይ ፣ እንደ ጀርመን ፣ እንደ ቤልጅክ በግድ ቅኝ አገር ማግኘት አስፈላጊዬ ነው ብሎ በእንግሊዝ ፣ በአውስትሪያ ፣ በጀርመን ደጋፊነት ቆርጦ የተነሣ ነው ። ባለፉት በተደረጉት ጦርነቶች በቀላሉ ራስ መንገሻን ስለ አሸነፈ ፣ "በያለበት ያሉት መሳፍንት ባፄ ምኒልክ ውስጥ ሕብረት አድርገው ኢጣልያን ሊወጉ አይችሉም ። ቢዋጉም የአንድነትና ያገር ፍቅር ስሜት ስለሌላቸው ጦርነቱ ሲዠመር

ወዲያው ይፈርሳል ። ያዬ ምኒልክና የራስ መኰንን ሰላም ፈላጊነት
ከፍርሃት የተነሣ ነው ” የሚል ግምት ስለ አደረሰበት ፤ እነሆ ከዋናው
የጦር ሰፈሩ ከአሥመራ 300 ኪሎ ሜትር ፣ ከአዲግራት 200 ኪሎ ሜትር
ግድም ዘልቆ እስከ አላጌ ከደረሰ በኋላ ፤ ቀጥሎም ከአላጌ 150 ኪሎ
ሜትር አልፎ አሸንጌ ላይ ደረሰ ። ታዋቂው የጦር መኰንን ማዦር ቶዜሊ
ብዙ ጦር ይዞ በመጀመሪያ እስከ አሸንጌ ድረስ የጦሩ ሜፍ ከደረሰ
በኋላ ፤ ባሁኑ ጊዜ ከአለቆቹ ተመካክሮ ወደኋላው ቀለስ በማለት ለው
ጊያ ከሚመቸው አላጌ ጉብታ ከበሩ ላይ በደንብ መሽጎ ተቀምጧል ።

ማጆር ቶዜሊ ፤ የአራተኛው ያገር ተወላጅ ባታዮ ጦር አዝማች
ሆኖ ከዚህ በፊት እንደ ተመለከትነው ፤ በሐላይ ደጀች ባሕታ ሐጐስን
ተዋግቶ የገደለ ነው ። ከመግደሉም በላይ ሬሳቸው ለመቀጣጫ እንዳይቀ
በር መከልከሉ ይታወሳል ። ከዚያ በኮአቲት ፤ በሰንዓፌና በደብረ ኃይ
ላው ጦርነት ለከፍሉ ዋና መሪ ሆኖ ተዋግቷል[1] ። በዚህ ምክንያት
ቶዜሊ የራሱን የባታዮ ጦር ይዞ ብቻውን የንጉሡን ጦር ሊመልስ
ይችላል ተብሎ ግምት የተጣለበት ከፍተኛና ዝግና የጦር መኰንን
እንደሆነ ተገምቷል [2] ።

አሁንም ለጦርነት ምቹ የሆነውን ከፍታው እስከ 3013 ሜትር
የሆነውን የአምባ አላጌን መተላለፊያ በደንብ መሽጎ ለጦርነት ይጠ
ባበቃል ። በውስጡ የያዘው የጦር ኃይል ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።
ኤሴል ፤ ካኖቬቲ ፤ ፔርሲኮ ፤ ሪቺ ፤ ብሩዚ በሚባሉ ሻምበሎች የሚመራ

| | | |
|---|---|---|
| የነጭ ወታደር ፤ | 1350 | ባለጠመንጃ |
| የባንዳ ጦር ፤ | 300 | ” |
| የራስ ስብሐትና የደጃች ዓሊ ጦር | 350 | ” |
| የሸህ ጦልሃ ጦር | 350 | ” |
| በአንጌራ የሚመራ 4 መድፍ | | |
| በጠቅላላ | 4 መድፍና 2350 | ባለጠመንጃ |

እነዚህን እንደያዘ በአምባ አላጌ መሽጎ ሲጠባበቅ ንጉሠ ነገ
ሥቱ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ መንቃንቃቸውን ፤ ከዚያ በራስ መኰ
ንን የሚመራው ግንባር ቀደም ጦር ከደሴ ወደ አሸንጌ መጓዙን ፤
እርግጠኛውን ወሬ ከሰላዮቻቸው ባገኙ ጊዜ ጀኔራል ባራቲዬሪ ፤
ቶዜሊ ከነጦሩ ወደ መቀሌ ተመልሶ እንዲመሽግ ይልክበት ዘንድ
ለጀኔራል አሪሞንዲ ጽፎለት ነበር ። ነገር ግን በጊዜ ማጣር ፤ በመንገዱ

---

1 Lettere e Diari, F. Lemmi, P.9.

2 L' Assedió di Macalle, V. Mantegazza, P. 327



ወጣ ገባነትና ርቀት የተነሣ ፤ ቶዜሊ ወደ መቀሌ ሳይመለስ እር
ዳታም ሳይደርስለት ቀድመው እነራስ መኰንን አላጌ ጥግ መድረሳ
ቸውን ተመለከተ ።

አዲስ አበባ ላይ ባለፈው የተመለከትነው የክተት ዓዋጅ ከታ
ወጀ በኋላ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ በጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም. ከአዲስ
አበባ ተነሥተው ፤ በጊዳ በኩል አድርገው ፤ በጥቅምት 18 ቀን ወረ
ይሉ ከተማ እንደገቡ ራስ ሚካኤልን ፤ ራስ ወሌን ፤ ራስ መንገሻ አቲ
ከምን ፤ ራስ መኰንንን ፤ ራስ አሉላን ፤ ዋግሹም ጓንጉልን ፤ ደጃች
ወልዴን ፤ ፊታውራሪ ገበየሁን ፤ ፊታውራሪ ተክሌን ፤ ሊቀ መኳስ አድ
ነውን ፤ ቀኛዝማች ታፈሰን ፤ “ ቀድማችሁ ወደ አላጌ ዝመቱ ። የሚቀ
ላችሁ እንደሆነ ውጉት ። የሚከብዳችሁ እንደሆነ ወደኔ ላኩብኝ ”
ብለው አስቀድመው መላካቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሲያረ
ጋግጡ[1] አንዳንድ ጽሑፍ ደግሞ ፤ “ እኔ እስክመጣ ድረስ ከባችሁ
ተቀመጡ እንጂ አትዋጉ ” ብለው እንደነበረ ያመለክታል ።

የሆነ ሆኖ ፤ ይህ ግንባር ቀደም ጦር በራስ መኰንን አበጋዝ
ነት ከወረይሉ ተነሥቶ በመጓዝ ላይ እንዳለ ከደብረ ኃይላ ጦርነት
የመጡት ራስ መንገሻ ከነጦራቸው በአሸንጌ ሲጠባበቁ ነበርና ከነ
ራስ መኰንን ጋር ተገናኝተው ሁሉም ጉዟቸውን ወደ አላጌ ቀጠሉ ።
ከዚህ በፊት እንዳልነው ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተለው ፖለ
ቲካ ኢጣልያኖችን በሰላም ለማስወጣት ስለሆነ ፤ ራስ መኰንን
አላማጣ ላይ ሳሉ እ. ኤ. አ በኅዳር 26 ቀን 1885 ዓ. ም. ከዚህ
የሚከተለውን ደብዳቤ ለጀኔራል ባራቲዬሪ ላኩለት ። ያማር
ኛው ደብዳቤ ስለማይገኝ ትርጕሙን ከፈረንሳይኛ ወደ አማርኛ በቃል
ስንመልሰው እንደዚህ የሚል ነው ።

ለታወቀው ወዳጄ ለጀኔራል ባራቲዬሪ የኤርትራና የአካባቢው
አገረ ገዥ ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

የተላከ ከራስ መኰንን የሐረርና የዙሪያው አገር ሁሉ ገዥ ። የጌን
ጤንነት ማወቅ የፈለጉ እንደሆነ እስካሁን ድረስ ደህና ነኝ ። ሐረር
የነበርሁ ጊዜ ለኛም ለናንተም መንግሥት የሚበጀውን ከፌልተር ጋር
ተነጋግረን ነበር ። አሁንም ደም በከንቱ ሳይፈስ ጉዳዩን ሁለታችን
በግል ተነጋግረን ብንፈጽመው መልካም ነው ። ግርማዊነታቸው እኔን
ወደ ትግሬ ሲልኩ ከሁሉ በፊት ከእርስዎ ጋር ተነጋግሬ ለመጨ
ረስ ነው ። የሚበጀውን በቶሎ እንዲልኩብኝ ተስፋ አለኝ ። ሙሴ ፌል
ተር እንደሌለም ፈልገው ካለበት ያስጠሩት ።

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 230—231 ።

ይህን ደብዳቤ ከአላማጣ ከራስ መኰንን የተላኩት ሰዎች አጉላዕ ድረስ ወስደው ፥ ለቶዜሊ አደረሱ ። ቶዜሊ ለጀኔራል አሪሞንዲ ከሰጠው በኋላ ፥ እርሱ ደግሞ የደብዳቤውን አጭር አሳብ በቴሌግራም አዲግራት ለሚገኘው አለቃው ለጀኔራል ባራቲዬሪ አስታውቆ እንደዚህ የሚል መልስ መጣለት ።

ከራስ መኰንን ጋር ንግግር ለመጀመር ፈቃዴ መሆኑን ፊልተርንም ከዘይላ አስጠርቼ እንደማስታውቀው የምንገናኝበትን ቦታ ራስ መኰንን እንዲያስታውቀኝ ፥ እስከዚያ የሁለታችንም ጦር ወደፊት ሳይሔድ በያለበት እንዲቆም ተዋጉ ብዬ እንዳላዝ የራስ መኰንንም ጦር የጦር ማጥቃት ነገር እንዳይፈጽም ለራስ መኰንን አስታውቅ ።

ይኽን የመሰለውን አሳብ ለጀኔራል አሪሞንዲ አስታወቀ ። እንደዚሁም ፥ " የምንገናኝበትን ሁኔታና ሥፍራ እየተነጋገርህ ቆይ " ብሎ ለማጆር ቶዜሊ ትእዛዝ አስተላለፎ ፥ ጉዳዩንም ሮማ ላሉት አለቆቹ ካደረሰ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ደብዳቤ በቀጥታ ለራስ መኰንን ጻፈላቸው ።

. . . ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን በሙሉ ጤንነት ስለ መገኘትዎ ደስ ብሎኛል ። እኔም ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁንና ደህና ነኝ ። ድልን ባገኝ እንኳን ጦርነት ተደርጎ የክርስቲያን ደም መፍሰሱ ለኔ በጣም ያሳዝነኛል ። ሁለታችን ተገናኝተን ደም የሚፈስበትን መንገድ ብናስወግድ በጣም ደስ ይለኛል ። ንጉሣችን ኡምቤርቶ ምኞታቸው ይኸው ነው ። ስለዚህም ከርሳቸው ሙሉ ሥልጣን ተቀብያለሁ ። እርስዎም ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ሙሉ ሥልጣን ተቀብለው እንደሚመጡ እምናለሁ ።

ስለዚህም የምንገናኝበትን ዝርዝር ጉዳይ እንዲያዘጋጅ ለማጆር ቶዜሊ ልኬበታለሁ ። ከርስዎም በኩል አንድ ሰው ተወክሎ ወደ ማጆር ቶዜሊ እንዲላክ ፤ ሙሴ ፊልተርም ከርስዎ ጋር ያደረገውን ንግግር ገልጾልኛል ። ወዳጆችም ስለሆናችሁ ከዘይላ ተፈልጎ እንዲመጣ ልኬያለሁ ። ስለ ሀገርዎ ምንም ፍርሃት አይሰማዎት ። እግዚአብሔር ለርስዎና ለመላዋ ኢትዮጵያ ጤንነት እንዲሰጥ እመኛለሁ [1] ።

ራስ መኰንን የጻፉለት እ.ኤ.አ. ኅዳር 26 ቀን ሲሆን ፥ እርሱ የመለሰው ከስምንት ቀን በኋላ በታኅሣሥ 3 ቀን ቢሆንም መልሱ በፍጹም ሊደርሳቸው አልቻለም ። በዚህ ዐይነት ካባራቲዬሪ ጋር የመጻጻፉ ጉዳይ ውጤት አልሰጠም ። የተፈለገው ፊልተርም በጊዜው አልተገኘም ። ስለዚህ ያን ሁሉ ሠራዊት ይዘው እንደዚሁ መቆየት ስለአልቻሉ ፥ እዚያው እጠገባቸው ለሚገኘው ለማጆር ቶዜሊ መጻፍ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፈው ላኩለት ።

1 Memoire d'Afrique , Baratieri, P. 263.



"የመጣሁት ጦርነት ለማድረግ ነው ያስከተልሁትን ጦር እንደዚሁ ላስናብተው አልችልም ። የባራቲዬሪ ወዳጅነት ስለያዘኝ የሰላም እማካይነት ለማድረግ ፈልጌ ነበር ። ከጀኔራል ምንም መልስ ስለአልመጣልኝ ንጉሡም ከአሸንጌ ወዲህ ስለ ተጠጉና እኔም መንገዱን ይዤ ከቆምሁ መተላለፊያ አያገኙም ።"

ቶዜሊም ለዚህ ደብዳቤ ቀጥሎ ያለውን በድንፋታ የተሞላ መልስ ሰጠ ።

የባራቲዬሪን መልስ ጠይቀኸኛል ደብዳቤህን ልኬዋለሁ ። በታኅሣሥ 2 ለጻፍከው በ4 ታኅሣሥ መልሼልሃለሁ ። ወደፊት መጓዝህ ለሰላም ከአሰብኸው ጋር ይጋጫል ። ወደፊት መራመድ ጦርነት ፍለጋ ነው ። ከዚህም ጦርነት የሚከተለውን ማንም መጥና ሊያውቀው አይችልም ። ለመሔድ መነሣት የሰው ችሎቱ ነው ፥ የመድረሱ ነገር ግን በእግዚአብሔር እጅ ነው ። በመቅደላና በሰሐጢ የሁለት ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዕድል ተወስኗል ። ሦስተኛው ንጉሠ ነገሥት ከሰሎሞን ዙፋን ይወጣ ዘንድ ኢጣልያ ለመርዳት ብትደስትም ፥ ከሰባት ዓመት በፊት የሠራችውን መልሳ ለማፍረስ ችሎት አላት ። [1]

ዋናው መሪ ባራቲዬሪ ፥ ለራስ መኰንን በርስዎታ ሲጽፍ ቶዜሊ አንባቢ እንደ ተመለከተው በአንተታ ነው የጻፈው ። የአጻጻፍ ሥነ ሥርዓት አለማወቅ ይሁን ወይንም በንቀት አለዚያም በትርጓሚ ስሕተት አይታወቅም ። አጻጻፉ ፍጹም ድንፋታና ትምክህትን የተሞላ ስለሆነ በንቀትም ሊሆን ይችላል ። ሁለቱ ነገሥታት ዐፄ ቴዎድሮስና ዐፄ ዮሐንስ ሕይወታቸው በመቅደላና በመተማ እንዳለፈ ፥ የሦስተኛውን ንጉሠ ነገሥት የምኒልክን ሕይወት እኛው የገነባነውን መልሰን እናፈርሰዋለን ባይ ነው ። መተማ እላለሁ ብሎ በስሕተት ሰሐጢ ብሏል ። " ከሰባት ዓመት በፊት ኢጣልያ የሠራችውን መልሳ ለማፍረስ ችሎት አላት " ብሎ የሚጠቅሰው ፥ ኢጣልያ በሰላሙ ጊዜ ለዐፄ ምኒልክ ያቀበለችውን የጦር መሣሪያ እርዳታ መጥቀሱ ነው ወይም መሣሪያ አቀብለን ያደራጀነውን የምኒልክን መንግሥት እኛው እናፈርሰዋለን ለማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፥ የሰላሙ ነገር ከዚሁ ላይ ስለቆመ ይኸን ደብዳቤ በታኅሣሥ ፪ ቀን ጽፎ እንደላከ በ፫ኛው ቀን ጦርነቱ ተደርጎ እልኸኛውና ደፋሩ ቶዜሊ የምኒልክን መንግሥት አፈርሳለሁ ሲል የራሱን ሕይወት አጣ ።

1 Adua, E. Bellavita, PP 243 - 244.
ደብዳቤዎቹ የተተረጐሙት ከኢጣልያንኛው ጽሑፍ መሆኑን አመለክታለሁ ።



ራስ መኰንን ወ/ሚካኤል በዓድዋ ጦርነት ጊዜ
ከሞንታዶኔ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሐያ ሰባት

## የአምባ አላጌ ጦርነትና ድሉ

ራስ መኰንንና ማዦር ቶዜሊ ፣ እነዚያን ደብዳቤዎች ከተለዋወጡ በኋላ ፣ ራስ መኰንን ከበው መጠባበቅን እንጂ ፣ በቶሎ በጦር ማጥቃቱን የፈለጉ አይመስልም ። ምናልባት እርሳቸው ቶዜሊ ስድስት ራሶች ያሉበትን ጦር ደፍሮ በመውጋት ፈንታ ጦሩን ይዞ ወደ አዲግራት ይመለሳል የሚል ግምት አድርገባቸው ይሆናል ።

ነገር ግን ፣ ቶዜሊ ባንድ ወገን ያሰበት ምሽግ ለመመከት ምቹ መሆኑን ፤ በሌላ ወገን "የኢትዮጵያውያን ጦር ምንም ቁጥሩ ቢበዛ የድርጅቱ ክንውንና የመሣሪያው ጥራት ከኛ ያነሰ ነው" የሚል የንቀት ግምት ስለ አደረበት ፣ ከዚህ ሁሉ ጋር ከዚህ በፊት ባደረጋቸው ጦርነቶች እየቀናው ዝብዱው በነጮችም ፣ በጥቁሮቹም ዘንድ ደምቆ የታወቀለትና በዚህም የሳቮያ ኦርድር ሚሊቴር ኒሻን ተሸልሞ ስለ ነበረ ፣ ባሁኑ ጦርነት ሌላ ዝብዱ ሠርቶ ሌላ ሽልማት በመመኘት ጦርነቱን ራሱ ዐውቆ እንደ ፈለገው አይጠረጠርም ። በዚህም ላይ ዕድሜው ዐርባ ዓመት የአፍላነትና የሙሉ ሰውነት ጊዜ ነበረ ። ይህ የአፍለኛነት ዕድሜ በኢጣልያዊ ግንፍል ደም ላይ ሲጨመር ፣ በሁሉም መጋጋልና መደንፋት በዚህ ዘመን ያለ የኢጣልያ ጦር መኰንን ዐይነተኛ ሥዕል ነው ። ስለዚህ በየተራራው ዙሪያ የኢትዮጵያ ጦር እንደ ሠፈረ ከዚህ በፊት ያወሳናቸውን የጦር ሹማምንት ከዚህ እንደሚከተለው አሰልፎ ለመዋጋት ወሰነ ።

አንደኛ ፣ የራስ ስብሐትና የደጃች ዓሊ ጦር ግንባር ቀደም ሆኖ ፣ ከኋላው በቀኝ በኩል የካፒቴን ኤሲል ክፍል ጦር እየደገፈው የመጀመሪያውንና የታችኛውን መስመር ይዞ እንዲዋጋ፤ ይኸም ያገር ተወላጅ የሆነውን አስቀድሞ በማዋጋት የነጩን ጦር ለመቆጠብ መሆኑ ይታወቃል ። ራስ ስብሐት በራስ መንገሻ ትእዛዝ ከታሰሩበት ፣ ከአምባ ሰላማ ፣ አሪሞንዲ ካስፈታቸው በኋላ ባሁኑ ጊዜ በግድም በውድም የኢጣልያኖቹ መሣሪያ ሆነዋል ማለት ነው ።

ሁለተኛ ፣ ከኤሲል ክፍል በስተቀኝና በመካከል ከአላጌ መንገድ ጋር የሚያገናኘውን ሥፍራ ይዞ የካፒቴን ካኖቬቲ ክፍል ጦር ፈሳሹን ወንዝ ተከትሎ ፤

ሦስተኛ ፣ የካፒቴን አንጌራ ጦር በኋላው በካፒቴን ፔርሲኮ ጦር እየተደገፈ በቀኝ በኩል ከአምባው ባንደኛው ዘቅዛቃ ሥፍራ ፤

አራተኛ ፣ የሼህ ጦልሃና የቲኔንቲ ቮልፒቺሊ ጦር የተወሰነ ባንዳ ጨምሮ በቀኝ በኩል ያለውን የቶጉራንና የሙጃን መተላለፊያ መንገድ በመያዝ ፤

አምስተኛ ፣ የካፒቴን ሪቺ ፣ የካፒቴን ብሩዚ እና የካፒቴን ፓጇላ ጦር ከኋላ ደጀን እንዲሆን አሰልፎ እ. ኤ. አ. በታኅሣሥ 7 ቀን 1895 ዓ.ም. (ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም.) ጦርነቱ ተጀመረ ።

በኢጣልያኖቹ ጽሑፍ ፣ የጦርነቱ ከፋች ራስ ወሌ መሆናቸውን ያመለክታል ። በኛ በኩል ግን ፣ የጦርነቱ ጀማሪ ፊታውራሪ ገበየሁ መሆናቸው በብዙ ሰነድ የተደገፈ ነው ። እርሳቸውም ባንድ ወገን ከዚህ በፊት በዶጋሊ ጦርነት ራስ አሉላ እንዳሉት ፣ ለጌታዬ ላዔ ምኒልክ ድግስ እንጂ ፣ የጦር መስተንግዶ እንዲጠብቃቸው አላደርግም በማለት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቶዜሊ ጦር ፊት ለፊት መድፍም እየተኮሰ እያላገጠም ስለ አበሳጫቸው ፣ ከጠቅላይ አዛዡ ከራስ መኰንን ትእዛዝ ሳይጠብቁ ጦርነቱን ከፈቱ ። እንደ ርሳቸው ጀግንነት የሚሰማቸው ቀኛዝማች ታፈሰና ፊታውራሪ ተክሌ ተከታትለው ሔደው ውጊያውን አማሙቀው ቀጠሉ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ራሶቹ ሁሉም በየድንኳናቸው ስለነበሩ የተኩሱን ድምፅ በመስማት የጦር መሣሪያቸውን ታጥቀው ከየድንኳናቸው ወጥተው ወደ ጦርነቱ ሲያመሩ ፣ ሹም አጋሜ ተስፋዬ የአላጌን ምሽግና አቀማመጥ የሚያውቁት ወደ ራሶቹ ቀርበው ፣ "የአላጌ በር እንኳን ጠመንጃና መድፍ ተጠምዶበት በደንጊያ እንኳን አንድ ሰው ሊከላከል ይቻላልና አልጋውን እንዳታፈርሱት በምኒልክ አምላክ ወደየድንኳናችሁ ግቡ " ብለው ተማጥነዋቸው ነበር ። ራሶቹ ግን ፣ እርስ በርሳቸው ተመካከረው ፣ " እኛ እዚህ ተቀምጠን የንጉሡን አሽከር ፊታውራሪ ገበየሁን ዝም ብለን እናስገድለዋለን " ተባብለው ወደ ጦርነቱ ቦታ ሔደው ገጠሙ ። ፊታውራሪ ገበየሁም ምንም እንኳን ሰሞኑን ታመው ቢሰነብቱ በበቅሎ ሆነው ዘንጋቸውን ይዘው ፣ " አይዞህ ጥይትም ያለቀብህ በጐራዴ በለው " እያሉ ወታደሩን እያደፋፈሩ ማዋጋታቸውን ከራስ መንገሻ ዮሐንስ መላከተኛ የሰሙትን ማስታወሻ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አስቀርተውልናል ።[1]

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . .ገጽ 240—245 ።



ስለዚህ ፊታውራሪ ገበየሁ ፣ ወደ ከፈቱት የጦርነት ቦታ ራሶቹ ደርሰው በቀኝ በኩል የራስ ወሌ ጦር በራስ ስብሐትና በካፒቴን ካኖቬቲ የሚመራውን ፣ በመካከል የራስ መኰንንና የራስ ሚካኤል ጦር የኤሴልንና የፔርሴኮን ጦር ፣ በስተጀርባ የራስ መንገሻና የራስ አሉላ ጦር ከሼክ ጦልሃና ከአንጌራ ጦር ጋር ውጊያ ገጠሙ ። በራስ ወሌ ግንባር ያለው በራስ ስብሐት የሚመራው ጦር ተዳክሞ ወደ ኋላው ተመልሶ ከሚደግፈው ከኤሴል ጦር ጋር ተደባልቆ በመመከት ተዋጋ ። ራስ መኰንን ቀደም ብለው ከካፒቴን ካኖቬቲ ጦር ጋር ሲዋጉ ወዲያው ለርዳታ የራስ ሚካኤል ጦር ደርሶ ሲያጠቃ ፣ በዚህ ግንባር ያለው የኢጣልያ ጦር ምንም በርትቶ ቢከራከር አልሆነለትም ። ከአምባ አላጌ ምሽግ ጀርባ በምዕራብ በኩል የዘመቱት እነ ራስ አሉላም በበኩላቸው ሲያጠቁ ፣ የኢጣልያ ጦር እስከ ረዥም ጊዜ ድረስ ሊመከት አልቻለምና በቅድሚያ የሼክ ጦልሃ ጦር ሽሽት ጀመረ ።

ዋናው አዝማች ማዦር ቶዜሊ ፣ ወዲያና ወዲህ እያለ ጦሩን ሲያዋጋ ፣ የጦሩ ግንባር ሰፊ መሆኑን በመመልከት ፣ በየአለበት የአለውም ጦር የመከበብ አደጋ እንደ ገጠመው ተረዳ ። የጦሩን ግንባር ለማጥበብና ኃይሉን ለመሰብሰብና ለማዋጋት ከሞከረ በኋላ ፣ የሁሉም መዳከም ስለ ተቃረበ ፣ ተጠባባቂውንም ጦር ጨምሮ ሪቺ ፣ ኤሴል ፣ ካኖቬቲ በመጨረሻ ኃይላቸው እንዲዋጉ አዘዛቸው ። እነርሱም እንደ ታዘዙት ሲዋጉ ከመካከላቸው ካፒቴን ሪቺ ተመትቶ ወደቀ ።

በዚሁ መካከል ፣ አስቀድሞ እርዳታ እንዲመጣለት መቀሌ ለጄኔራል አሪሞንዲ ልኮ ነበርና መጣ አልመጣም እያለ ወዲያና ወዲህ እየተንቆራጠጠ ሳለ ፣ ውጊያው ጧት የጀመረ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ከቀጠለ በኋላ የኢጣልያ ጦር ሽሽት ጀመረ ። ቶዜሊ ሁሉም ጦር ወደኋላው ተመልሶ ፣ ከተረፈው ተጠባባቂ ጦር ጋር ሆኖ በመጨረሻ ኃይል እንዲዋጉ አዘዘ ። የመጨረሻው ጦርነት በሚደረግበት ላይ ብዙ እልቂት ደርሶ ፣ በዚሁ ጦርነት ብሩዚና ሙላዛኒ እየተመቱ ወደቁ ። የመቶ አለቃ ስካላ ከነሕይወቱ ተማረከ ። ካፒቴን አንጌራም ክፉኛ ቆሰለ ። ከመድፍ ተኳሾች ውስጥ የሱዳን ተወላጆች ነበሩና አበሾቹ ከሚማርኳቸው ብለው መድፎቻቸውን እንደ ተጫኑ ከነበቅሎቻቸው እየገፉ ገደል ሰደዷቸው ።

ከዚህ በኋላ ፣ ወታደሩ ምሽጉን እየለቀቀ በቶጐራ መንገድ አድርጎ በያለበት እየተዘበራረቀ ሸሸ ። ማዦር ቶዜሊም ፊቱን በሐዘንና በንዴት እንዳጨመደደ ወደታች ሲወርድ ፣ መንገዱን የራስ አሉላ ሰዎች ዞረው እንደ ያዙበት ተመለከተ ። በዚያን ጊዜ አንዳንዶቹ ፣ እንደ ሌሎቹ ራሱን እንዲያድን ቢመክሩት ፣ " ያደረጉትን ያድርጉኝ " ብሎ

ወደ ጠላቶቹ ፊቱን እንደ መለሰ ወዲያው ከደረቱ ላይ ተመትቶ
ወደቀ ። በወቅቱም "አላጌ እበሩ ላይ ሲወድቅ ማገሮር ፣ እንደ ግራኝ
ሁሉ በሰባት አረር" (ጥይት) ተብሏል ።

በዚህ ዐይነት ፣ አለቅዬው ተመትቶ ሲወድቅ በኮዓቲት ፣ በስንዓፌ ፣
በደብረ ኃይላ ራስ መንገሻ ዮሐንስንና ጦራቸውን በያለበት ሲያሳድድ
የኖረው ያራተኛው ባታዮ ጦር በዚህ ዓይነት ፍርስርሱ ወጣ ። የቆሰለ
ውም ፣ ደህናውም ፣ ነጩም ያገር ተወላጁም በየግንባሩ ወደ መቀሌ አቅ
ጣጫ ይሸሽ ጀመር ። [1]

በመጀመሪያ ላይ እንደ ተመለከትነው ፣ ጦርነቱ በጠቅላይ
አዛገዡ በራስ መኰንን ትእዛዝ ሳይሆን በአበጋዙ በፊታውራ
ገበየሁ ስለተከፈተ ፣ ምንም እንኳን ድሉ የኢትዮጵያውያን ሆኖ
ራሳቸውም በደንብ የተካፈሉት ቢሆን ፣ የጦርነቱ ጉዳይ በድል አድራ
ጊነት ከተደመደመና የመጀመሪያውን የጦር ኃይላቸውን ከአሳዩ በኋላ ፣
ራስ መኰንን ጦርነቱን ያለትእዛዝ የጀመሩትን ፊታውራሪ ገበየሁንና
ቀኛዝማች ታፈሰን አሰሩዋቸው ። የአምባላጌን የድል የምስራች ወሎ
ግዛት ውስጥ ለሚገኙት ላዔ ምኒልክ ለመንገር በደብዳቤና በቃል አሽከ
ራቸውን የላኩ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ናቸው ።

ደብዳቤውም እንደዚህ የሚል ነው ።

ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት
ዘኢትዮጵያ መድኃኔዓለም ጤና ይስጥልኝ ብዬ እጅ እነሣለሁ ። ልጅዎ
ራስ መንገሻ ። ጃንሆይ ጦርነቱ አልታሰበም ነበር ። ፊታውራሪ ገበየሁ
ሔዶ ገጠመው ። እኔም በጀርባው መኳንንቱም በግንባር ገቡበት ። ከመ
ኳንንቱ ሠራዊቱ ፣ ከሠራዊቱ መኳንንቱ እንደዚህ ያለ ተዋጊ ታይቶ
ተሰምቶ አይታወቅም ። ይህ ሁሉ የሆነ በምኒልክ ሀብት ነው ። ፈረ
ንጅ እንኳን መድፍና ወጨፎ ይዞ የአላጂ (አላጌ) አምባ ሲሰበር ፣ ከጥ
ንት ባባቶቻችን በደንጊያ ይመለስ ነበር ። ከዚህ በፊት ተደርጎ የማ
ያውቅ ዛሬ በምኒልክ ሀብት ተደረገ ። እንግዲህም የምኒልክ ሀብት
ይጠብቀናል ። በ10 ወ 108ወ8ቱ (1888) ዓ.ም. እመ 4ቱ ለታኅሣሥ
ተጻፈ ። ማኅተም ራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ
ነገሥት ዘኢትዮጵያ [2]

የጦር የበላይ አዛገዡ ራስ መኰንን እያሉ ፣ ራስ መንገሻ የጦርነ
ቱን የድል ወሬ ለመግለጽ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ የላኩበት

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 239 - 241, Italia ed Etiopia, Conti - Rossini, PP. 197 - 208. Lettere e Diari F.Lemmi , PP. 9-20.

2 ከፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ቪዳዬ ዶሲዬ ፣ ቁ.82



ምክንያት ለአንባቢም ለጸሐፊም ግር ሳያል አይቀርም ። ምክንያቱን
ስንመረምር ምንም እንኳን ራስ መኰንን የጠቅላላው የጦር አበጋዝ
ቢሆኑ ፣ ራስ መንገሻ ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ የዐፄ ዮሐንስ ልጅ በመ
ሆናቸው ፣ በክብርም በማዕረግም ከራስ መኰንን በዚያን ሰዓት ከፍ
ብለው ስለሚታዩ ፣ በዚህም ላይ ጦርነቱ የተደረገበት የአምባአላጌ
ሠፍራ በራስ መንገሻ ግዛት ውስጥ ስለሆነ ፣ የበላይነት መብት
ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብለው እንደሆነ አይታወቅም ። ይሁን እንጂ መላ
ከተኛው ፣ የድሉን ብሥራት ላዔ ምኒልክ ይነግር ዘንድ በቃል የላ
ኩት ራሶቹ በኅብረት ይመስላል ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ከአዲስ አበባ ተጉዘው ወረይሉ (ወሎ) እንደ
ደረሱ ፣ ከዚያ በኅዳር 23 ቀን ውጫሌ ባሻ ጮፌ ፣ ከዚያ በመርሳና
በጭራ ወንዝ ፣ በአላ ወንዝና በጉሊማ አድርገው ሆርማት ላይ በሠፈ
ሩበት ጊዜ የአላጌን ጦርነት ሰሙ ። በታኅሣሥ 1 ቀን ከሆርማት
በማይ ሽምበቆ ፣ በቢትሞ አድርገው ፣ አላማጣ ደርሰው ድንኳን ተተ
ክሎ ሰፈር ሆነ ። በአላማጣ እንደ ሰፈሩ ይኸን ደብዳቤ የያዘው ፣ በቃ
ልም የተላከው ፣ የራስ መንገሻ መላክተኛ ወደፊት ቀድሞ በየተራራው
ላይ የሚጓዘውን ወታደር እያቋረጠ ፣ እየተንደረደረ ሲሮጥ የሚጓዘው
ሰው ባየው ጊዜ ፣ "ከወዴት መጣህ እባክህ ወሬውን ንገረን" ቢሉት ፣
'እኔ ከራሶቹ ዘንድ ነው የመጣሁት ፣ አላጌ ላይ የዘለቀው ጦር ኢጣ
ልያኑም አለቀ ፣ መድፉም ነፍጡም ተማረከ" ብሎ ወደ ንጉሠ ነገ
ሥቱ ሰፈር በግሥጋሴ ደረሰ ። ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት ድን
ኳን ገብቶ ፤

"ኢጣልያኑ አላጌን አምባውን ይዞ መድፉን አልቦ ነፍጡን ስልፎ
ተቀምጦ ነበር ። ፊታውራሪ ገበየሁ ወደፊት ቀድሞ ሲጓዝ ፣ ፊት የቀ
ደመው የርሱ ጦር ከኢጣልያው ዘበኛ ጋር ተገናኝቶ ተታኮሰ ። ፊታ
ውራሪ ገበየሁም ከሹማምንቱ ጋር እንዲህ አለ ። እንግዲህ ይህ ጦር አም
ሮብን ሳለ ለጌታችን አልጋ መሞት ይገባናል . . . እንዲህም ተባብለው
ጭፍራው አንድ ጊዜ ገባበት ። አምስቱን ክቢ እንደሸረው ተኩሱ ከነ
ራስ መኰንን ሰፈር ተሰማ . . . እነሱም ከየድንኳናቸው ታጥቀው
ሲወጡ . . . ሹም አጋሚ ተሰፋዬ . . . አይሆንም ብሎ አግጠና
ቸው . . . ራሶቹ ከዚህ ተቀምጠን የጃንሆይን አሽከር ገበየሁን
እናስገድላለን ብለው እየተሰለፉ ሔዱ ። ሠፍራውም እንኳን ለክብት
ለእግረኛም ቢሆን እጅግ የከፋ ገደል ነበር ። ሰዉ ግን ፣ የመድፉንም
የነፍጡንም ተኩስ ቁም ነገር አላለው ። እጅ ለጅ ተያይዞ ዕፁብ
ድንቅ ተብሎ የተመሰገነ ውጊያ ተዋግቶ ድል አድርጎ ፈጀው ።
. . . . ነገር ግን ፣ ፊታውራሪ ገበየሁንና ቀኛዝማች ታፈሰን ሳይታ
ዘዙ ስለተዋጉ አስረናቸዋል ብለዋል ራሶቹ ።"

ሲል ለንጉሠ ነገሥቱ መንገሩን የጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ
ያረጋግጣል ።

ከዚሁ አያይዞ ፣ ዐፄ ምኒልክ መልክተኛውን ሸልመው ፣ “እኔም መጣሁ ። እግዚአብሔርም ሁልጊዜ ቀኙን ለኛ ያድርገው ” ብለው መልሰው እንደ ሰደዱት ፣ በዚያም ሰሞን ልጁም ፣ ዐዋቂውም “ገበየሁ ገበየሁ “እያለ እንዳነሣው ፣ “ጐበዝ አየሁ” የሚል ሥያሜም እንዳወጣለት የጸሐፌ ትእዛዙ ጽሑፍ ያመለክታል ።[1] በዚህም ጊዜ —‘ ከነፍጥ ጐበዝ ፣ አየሁ (የጠመንጃ ስም) ከአሽከር ገበየሁ’ ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።

የአላጌ ጦርነት በንጉሠ ነገሥቱም ፣ በራስ መኰንንም ዘንድ እንዳልተፈለገና ንጉሠ ነገሥቱ የአላጌን የጦርነት ወሬ አዲስ አበባ ላሉት በአሳብም ፣ በምክርም ፣ የጦር መሣሪያም በማቀበል ፣ ለሚረዱዋቸው ፈረንሳዮች በላኩት ደብዳቤ ላይ ገልጸውታል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ካዲስ አበባ በዐዋጅ ሠራዊታቸውን ሰብስበው የሔዱት ለጦርነት መሆኑ ራሱ የከተቱ ዐዋጅ በግልጽ ያስረዳል ። ነገር ግን ፣ በዚህ ዘመን ምዕራባውያን የእስያንና የአፍሪካን ዓለም ተከፋፍለው የያዙበት ፣ ጠባቸው የሚያስፈራ ፣ ሥልጣኔያቸው የሚጠቅም መሆኑን በደንብ ስለ ተረዱት ፣ በተቻለ መጠን “አጥቂ” መስሎ አለመታየትን ዋና ዓላማ አድርገው ይዘውታል ። በአዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገር ወዳጆቻቸውም የሚመክሩዋቸው ይኸንኑ ነው ። ስለ ኢጣልያ ንጉሥና ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች በጻፉ ቁጥር ንጉሠ ነገሥቱም ፣ ራስ መኰንንም በደብዳቤያቸው ውስጥ ደጋግመው የሚጠቅሷቸው ዐረፍተ ነገሮች አንደኛው ፣ “ጉዳያችንን በሰላምና በወዳጅነት እንጨርስ ” ሁለተኛው ፣ “የክርስቲያን ደም በከንቱ አይፍሰስ” የሚሉ ናቸው ።

የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ግን ፣ ይኸን አቅዋም የፍርሃት አድርገውት እነዐፄ ምኒልክ እንደሚመኙት የያዙትን ወረዳ ሁሉ በሰላም ለመልቀቅ አልፈለጉም ። በራሳቸው ጉልበትና በሥልጣኔያቸው በመመካት ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሌላው የአፍሪካ ሕዝብ ሁሉ በመናቅና በማኰሰስ ፣ እንደገና ከያዙት እያሰፉ አዲስ ወረዳ በመያዝ ፣ ለኢጣልያ የቅኝ አገር መፍጠርን በበኩላቸው ዓላማ አድርገው ይዘውታል ። እስከ አላጌም የደረሱት በዚሁ ዓላማ መሆኑን ባለፈው አመልክተናል ።

ስለዚህ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ መቀሌ ከገቡ በኋላ ፣ የአላጌን ድል አዲስ አበባ ላሉት ፈረንጆች ሲጽፉ አድራሻውን ለሙሴ ሞንዶን

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 241 ።



ቪዳዬ አድርገውለታል ። ምክንያቱም ሞንዶን በዚህ ጊዜ “ለታ” ለሚባለው ለፈረንሳይ ጋዜጣ ወኪልና ለንጉሠ ነገሥቱም ወዳጅ ስለ ነበረ ነው ። ጣልያኖቹ ኢትዮጵያንና አስተዳደሩን እያጥላሉና እረመኔ እያስመሰሉ በመጻፍ ወረራቸውን “ የሚገባ ነው ” ለማስኘት ፣ በአውሮፓ ወሬያቸውን በጋዜጣ ሲነዙ ፣ እርሱ ከአዲስ አበባ እየጻፈ በመላክ የጣልያኖቹን ፕሮፓጋንዳ የሚያስተባብል ፣ ዐፄ ምኒልክን በማሞገስ ከልብ የሚደግፍና አማርኛም የተማረ ነበር ።

ከንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈለትን ደብዳቤ እንደሚከተለው እንመልከት ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን ። እንዴት ሰንብተሃል ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። ከናንተ ከተለያየሁ ኢጣልያኖችን እጅግ አልገፋም ብዬ ነገሩን በዝግታ ይዤው ነበር ። በዝግታ መያዜ ግን ፣ የክርስቲያን ደም ሳይፈስ በመካከሉ ድንገት እነዚያን የሚያስታግሥ ምክር ከአውሮፓ ይመጣል ብዬ ነበር ። ኋላ ግን ነገሩን አስተውዬ ባየው ከቶ እኔ የፈራሁ እነሱ የበረቱ መስሏቸው አሸንጌ ድረስ በር ለመያዝ መጡ ። የኔም ሠራዊት አስቀድሜ የሰደድኳቸው መኳንንት ሁሉ ሳይደርሱ የኢጣልያ ወታደር የፊተኛውን ጦር አዘላስቅ አይቶ ተመልሶ አላጌ ላይ በሩን ይዞ ሰፈረ ። የኔም ጦር ተከትሎ ከአላጌ ወዲህ አይባ ላይ ሰፈረ ። ከዚህ በኋላ ሰፈሩን እያዩ ጣልያኖች መተኰስ ጀመሩ ። የኔም ወታደር አላስችል ቢላቸው ካለቆቻቸው ትእዛዝ ሳያገኙ ወጥተው ጦርነት ገጥመው በኅዳር 28 ቀን ድል አድርገው ፈጁት ። የፊተኛው ጦር ዐሥራ ሁለት አለቆች ይዞ የመጣ ማጆር ቶዘሊ ነበር ። ከርሱ ስምንት ሞተዋል 1 ሁለቱ ተማረኩ ። ዠኔራል ባራቲዬሪ * ለርዳታ መጥቶ እመንገድ ሲደርስ ድል ያደረገው የኛ አባራሪ ጦር ቢደርስበት ጥቂት ራሱን ሆኖ ከዚያ ሸሽቶ መቀሌ ከርዱ ገብቶ የኛ ጦር ከቦት ተቀምጧል ። አሁንም ደስ ብሎኛል ደስ ይበልህ ። ሁሉንም እንድታውቀው ራስ መንገሻ የሰደደልኝን ደብዳቤ ሰድጄልሀለሁ ። ደስታውንም ላንተ መላኬ የሁሉም ሽማግሌ ነህና አዲስ አበባ ላሉት ፈረንጆች ሁሉ እንድትነግራቸው ይሁን ። ለቀሩት ፈረንጆች ሁሉ አለመላኬ ደብዳቤ ችኰላ ቢሆንብኝ ነውና ለሁሉም አንተ ንገርልኝ የራስ መንገሻን ደብዳቤ ከራስ ዳርጌ ተቀበል ።

በታኅሣሥ በ6 ቀን በአሸንጌ ሰፈር በ፲888 ዓ. ም. ተጻፈ ።[1]

* ባራቲዬሪ ያሉት አሪሞንዲ ለማለት ነው ። ቶዜሊን ለመርዳት መጥቶ በሽሽት የተመለሰው አሪሞንዲ እንጂ ፣ ዋንዬው ባራቲዬሪ አይደለም ። ምናልባት ወሬ ነጋሪያቸው አሪሞንዲ በማለት ፈንታ ባራቲዬሪ ብሏቸው ይሆናል ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቤት .. ከሞንዶን ዶሲዬ ፣ ቁ.82

ዳግማዊ ምኒልክ ፡ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ራስ መንገሻ ዮሐንስ የጻፉላቸውን ደብዳቤ በራስ ዳርጌ አማካይነት ለሞንዶን ቪዳዬ መላካቸው ፡ ምናልባት በዚህ ጊዜ ኢጣልያኖቹና ወገኖቻቸው "እነንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፡ እነራስ ሚካኤል ንጉሠ ነገሥቱን ከድተዋል ። ራስ መንገሻም ከድተው ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር እየተጻጻፉ ለጣልያን ሊገቡ ነው" የሚባል ወሬ ይነፍስ ስለነበር ይሆናል ። ይልቁንም ራስ መንገሻ ፡ ምንም ራሳቸው ከኢጣልያኖቹ ጋር በኮአቲትና በሰንዓፌ ቢዋጉ አሁንም ለሚቀጥለው ጦርነት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቢሰለፉ ፡ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፡ የዙፋን ወራሽነቱ መቅረት እያደር እየቆጫቸው ውስጡን በኅዳር 23 ቀን 1887 ዓ.ም. ለኢጣልያ ንጉሥ ከጻፉ ወዲህ በነሐሴ 23 ቀን 1887 ዓ.ም. ደግሞ ለንግሥት ቪክቶሪያ ፡ " መንግሥቴን ተቀምቼያለሁና እርዱኝ " የሚል የጥያቄ ደብዳቤ ጽፈው ኖሮ ፡ በአላጌ ጦርነት ጊዜ መላክተኛው ካይሮ ደርሶ ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች መነጋገሩ በውጭ አገር ጋዜጣ ተጽፎ ነበር ።

ምናልባት ፡ የዚህኑ ወሬ ሞንዶን ቪዳዬ ከፈረንሳይኛ ጋዜጣ ላይ አንብበ የራስ መንገሻን አለመታመን ላፄ ምኒልክ ጽፎላቸው እርሳቸው ደግሞ ለዚሁ የራስ መንገሻን መታመን ከደብዳቤያቸው ላይ እንዲረዳው ልከውለት ይሆናል ። ዳሩ ግን ፡ ራስ መንገሻ ባለፈው ዓመት ሁለት ጊዜ ከኢጣልያ ጦር ጋር ተዋግተው ያን የመሰለ የመሸነፍ አደጋ ደርሶባቸዋል ። ያንን ቁጭት ለመወጣት በጦርነት ከነራስ መኰንን ጋር ከመሰለፋቸው ከአራት ወራት በፊት ለንግሥት ቪክቶሪያ መጻፋቸው ፡ በእውነትም ኢትዮጵያውያን አንድነት የላቸውም ያሰኛል ። በወቅቱም የእንግሊዝ መንግሥት በምንም ዐይነት እርዳታ ለማድረግ እንደማይችል የታወቀ ነው ።

የአላጌ ጦርነት የተከናወነው ፡ ብዛቱ በተለያየ ወታደሮች መካከል መሆኑ አይጠረጠርም ። የኢትዮጵያውያኑ ቁጥር ከኢጣልያኖቹ ጸሐፊዎች በተሰጠው ግምት ከሃምሳ ሺ በላይ ባለጠመንጃ ሲሆን ፡ የኢጣልያኖቹ ከዚህ በፊት እንደ ተመለከትነው ሦስት ሺ አይሞላም ። ነገር ግን ፡ በደንበኛ አካዳሚካዊ የጦር ትምህርት የተዘጋጀ ወታደርና ይኸን ባላገኘ ወታደር ፡ እንደዚሁም ምሽግ ይዞ በሚመከትና ከውጭ በሚያጠቃ መካከል የተደረገ ጦርነት ስለሆነ ፡ የተዋጊ የቁጥር ልዩነት የሚጫነው በመጠኑ ነው ። ጥሩ የመሣሪያ ትጥቅ ያለው አንድ መቶ ወታደር እንደ አላጌ ያለውን ምሽግ በቅድሚያ ከያዘ መቶ ሺ ጦር ሊመልስ ይችላል ። እነሹም አጋሜ ተስፋዬና ራሳቸው ራስ መንገሻም በቃልም ፡ በደብዳቤም የገለጹት ይኸንኑ ነው ።



የሆነ ሆኖ ፡ የአላጌ ጦርነትና ድሉ ለኢጣልያ መንግሥት ትልቅ የማስጠንቀቂያ ደወል ነበር ። ኢጣልያኖቹ ግን ፡ ይኸን የደወል ድምፅ ሰምተው በመማር ፡ ጉዳዩንም ዐፄ ምኒልክ እንደ ተመኙት በትዕግሥት ወደ ሰላም በማቅናት ፈንታ ፡ አውሮፓዊ ክብራቸው ባንድ ባልሠለጠነ አፍሪካዊ ጦር እንደ ተነካ በመቁጠር ፡ በኢጣልያም ፡ በኤርትራም ያሉት ሁሉ ከቀድሞው የበለጠ አበክረው በመናደድ የሚበቀሉበትን ጊዜና ሥፍራ ይመርጡ ዠመር ። አዳዲስ ጦርም ከኢጣልያ አገር ወደ ኤርትራ የሚመጣው ፍጥነቱ ከዚህ በፊት ከነበረው ይበልጥ ተቀላጠፈ ። ቢሆንም ከኮዓቲትና ከደብረ ኃይላ ጦርነት ድል በኋላ ፡ ይህ የአላጌ ሽንፈት ኤርትራ ባሉት የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ዘንድ ፡ "በፍጹም የማንበገርና የማንደፈር ነን" የሚለው ልባዊ የትምክህት እምነት አጠራጣሪ ሆነ ። በአላጌ ውጊያ ኢጣልያኖች አስገድደው ባሰለፉት የኤርትራ ፡ የደንከል ፡ የራያና የአዘቦ ፡ የሐባብና የቦጐስ ፡ የከረንና የሱዳን ተወላጅ ዘንድ ነገሩ የተገላቢጦሽ እየሆነ ሔደ ። በጦርነቱ የተካፈሉት ላልተካፈሉት ያፄ ምኒልክን ጦር አወጋግ እያደነቁና እያጋነኑ አወሩ ። ከአላጌ ጦርነት በፊት በነበሩት የባንዳ ወታደሮችና በቅርብ በተመለመሉት ባገር ተወላጆች ዘንድ ፡ "ጣልያንን ማን ይችለዋል" የሚል እምነት አድሮ ነበር ። አሁን ግን ፡ በተለይ ጦርነቱን ተካፍለው የሸሹትና ለሌሎቹ ያወሩት ፡ ያለቆቹን የነገበየሁ አባ ጐራን ፡ የነታፈስ አባ ትንታግን አመራርና የወታደሩን ድፍረትና ጀግንነት በዝርዝር ሲተርኩት ፡ በፊት የነበራቸውን እምነት ከመሠረቱ አናጋው ። በዚህ ምክንያት ፡ በአላጌ አካባቢ ያሉ የእንዳ መሆኔ ፡ የአበርጋሌ ፡ የእንደርታ ፡ የዋጅራት ፡ የሰለዋና የገራልታ ሕዝብ በየወረዳው መመሥረትና ማስተዳደር ፡ ሹም ሽር ማድረግ የጀመሩትን ኢጣልያኖች እየተዉ ፡ ብዙ የትግሬ መኳንንትና ሹማምንት ከነጭፍራቸውና ከነመሣሪያቸው እንዲያውም አንዳንዶቹ ጠላትን እየወጉ ወደ ወገናቸው በመደባለቅ የኢትዮጵያን ጐራ አጸኑት ።

የኢጣልያ ጠቅላይ አዛዥ ነገሩን ሰምቶ ፡ እንደነመቶ አለቃ ጋምቢ የመሳሰሉትን ሹማምንት እየላከ አንዳንዶቹን ቢያስጠብቃቸውም ፡ ሁሉም በየጊዜው እየመጡ ለራስ መኰንን ይገቡ ጀመር ። እነዚህም የትልቁ ራስ አርአያ ልጆች ደጃች ተድላ አባ ጉበን ፡ ልጅ አብርሃ ፡* ደጃች ገብረ ሚካኤል ፡ ሹም ደራ መንገሻ ፡ ደጃች ብሩ ናቸው ።

---

* ደጃች ደብብ ካፄ ዮሐንስ ተጣልተው ከኢጣልያኖቹ ጋር በነበሩበት ሰዓት ታናሽ ወንድማቸውን አብርሃን ለኢጣልያኖቹ ሰጥተዋቸው ነበርና ጣልያኖቹ ቶሪኖ ወስደው አስተምረው መልሰው አምጥተው መሣሪያ አድርገዋቸው ነበር ።ከዓድዋ በኋላ ደጃዝማች ተብለው ትግሬን (እንደርታን) በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ከዋግሹም አባተ መዋጋታቸው በልጅ ኢያሱም ጊዜ ያገር ግዛት ሚኒስትር መሆናቸው ወደፊት ይገለጣል ።

ራስ መኰንንም ፣ የገቡላቸውን ሁሉ ፈቃደኞች የሆኑትን ለራስ መንገሻ ዮሐንስ አስረከቡዋቸው ። ወደዚህ እየከዱ የሚመጡትን ሹማምንት ለማገድ መጥቶ የነበረውን ቲኔንቲ ጋምቢን ቀደም ብለው የገቡት ደጃች ተድላ አባ ጉበን ማርከው ይዘው ከርሳቸው ጋር እስረኛ ሆኖ አገር ላገር ከዞረ በኋላ ፣ በመጨረሻ ደጃዝማቹ ለራስ መኰንን አስረከቡትና በአላጌ ጦርነት ላይ ከተማረኩት ከሌተና ስካላና ከሁለት ዝቅተኛ መኰንኖች (ኮፓራሎች) ጋር ተደባልቆ በራስ መኰንን ሠፈር ብዙ ጊዜ ቆይቷል ።[1]

በኢትዮጵያ በኩል ግን ፣ ምንም እንኳን የወታደሩ ድፍረት ፣ የመሳፍንቱ ኅብረት በጣም ቢያስደስታቸውም ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ልባቸው በኩራትና በትምክህት አልተሞላም ። በተለይ አዲስ አበባ ፈረንጆች ፊት የጦርነቱንም ደረጃ ዝቅ በማድረግ በነፈታውራሪ ገበየሁና በነቀኛዝማች ታፈሰ ወደ መላከክ እያዘነበሉ ፣ ነገሩ እንዳይባባስ ያላቸውን የልስላሴ ፖለቲካ በጽሑፍም በተግባርም ያሳያሉ ። ራስ መኰንንም የተከተሉት ይኸንኑ አርአያ ነው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ኅዳር 28 ቀን በተደረገው ጦርነት ማገርር ቶዜሊ ፣ ካፒቴን ካኖቬቲ ፣ ካፒቴን አንጌራ ፣ ካፒቴን ፔርሴኮና ሌሎችም ሹማምንት በድምሩ አምስት ካፒቴኖች ፣ ዐሥር የመቶ አለቆችና ሁለት ምክትል የመቶ አለቆች በጦርነቱ ላይ ሞተዋል ። ራስ መኰንን ከጦርነቱ በኋላ የነዚህን ሬሣ ከያለበት አስነሥተው ራሳቸው በሰልፍ ቆመው ፣ እዚያው አላጌ አጠገብ በሚገኘው ቤተ ማርያም በሚባለው ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀበሩዋቸው ።[2]

ከዚህ በፊት እንዳነበብነው ማገርር ቶዜሊ ፣ አምና 1887 ዓ. ም. ደጃች ባሕታ ሐጐስ ፣ ከራስ መንገሻና ካፄ ምኒልክ ጋር ተላልከው ፣ ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲን አስረው የሸፈቱ ጊዜ ፣ አሁን በአላጌ ያለቀውን ጦሩን አስከትሎ ፣ በሐላይ ወግቶ ከገደላቸው በኋላ ሬሳቸውን በሜዳ ጥሎ ለመቀጣጫ በማለት አላስቀበረም ነበር ። አሁን ራስ መኰንን እርሱንና ወገኖቹን በክብር ሲያስቀብሩ ፣ የደጃች ባሕታ ሐጐስ ወንድሞች እነአዝማች ሠንጋል በዚያው ነበሩና ፣ "የኛን ወንድም ያላስቀበረው ቶዜሊ ለምን ይቀበራል" ብለው ተከራከሩ ። የዚህን ጉዳይና ሌላም የአላጌን የጦር ወሬ ጨማምረው በስፍራው የነበሩት

1 Italia ed Etiopia . . . PP. 209-214; Memoire d' Afrique - O Baratieri PP. 282-285 .

2 Adua, Bellavita, PP. 236 - 237 . La Prima Guerra d' Africa -R Bataglia - PP 644 - 656



አስተርጓሚው ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሡ ነገሥቱ ከጻፉት ሰፋ አድርገው ለዚያው ለሞንዶን ጽፈውለታል ።

ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን ከዚህ ቀደም ያላጌን ጦርነት የምሥራች ጃንሆይ የላኩብዎት ጊዜ የጦርነቱን ሁኔታ ውጊያቸውን ሳልከብዎት የቀረሁት ፣ ከመንግሥት ቤት የሚወጣው ደብዳቤ የተተካከለ ወሬ መሆን ይገባዋልና ይኸውና ዛሬ ጨርሼ እልክብዎታለሁ ። ከዚህ ቀደም ጃንሆይ ሳይልኩ ራስ መንገሻ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ጋር እርቅ ለማድረግ ጀምረው ነበር በእርቁም ሲመላለሱ የነበሩ አባ አናንያ የሚባሉ ኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ መነኩሴ ፣ ሊቄ ወልደ ኢየሱስና ግራዝማች ሳዶር ናቸው ።[1]

በመጨረሻው ግን ዐፄ ምኒልክ ፣ ለጦርነት ሲመጡ እናንተ ለእርቅ አልመጣችሁም ሰላዮች ናችሁ ብሎ አሰራቸው ። ከዚህ በኋላ ሞት ይገባችኋል ብሎ ሊያስደበድባቸው ሳለ ፣ ሌዩተና አስካላ የሚባል ከሹሞቹ መካከል ተነሥቶ መልክተኛ ወጊድ ይባላል እንጂ ይሞታልን ብሎ ከሞት አተረፋቸው ። ሞት ቢቀርላቸው እስራት አይቀርላቸውም ብሎ አስሮ ምጥዋ ሰደዳቸው ። ይህም ሌዩተና አስካላ ዛሬ አላጌ ላይ የተማረከው የመድፈኞች አለቃ ነው ። ጃንሆይም የየጁን መሬት ጨርሰው በታኅሣሥ በ4 ቀን አላማጣ ከሚባል አቀበት ከግርጌው የዋግሹም ግዛት ክፍል የሚሆን ሰፍረው ሳሉ ያላጌን ጦርነት ድል የማድረግ የምሥራች መጣላቸው ።

ከዚህ በኋላ ፣ የምሥራቹን ወደናንተ ልከው አሸንጌ ላይ ወጥተው ሰፈሩ ። ከዚህም ላይ የፊታውራሪው ጦር ድል ማድረግ ለመጨረሻው ድል የምሥራች ምልክት ነውና ሠራዊቱ ሁሉ ተሰልፎ ግባት ቢተኩስ በዱር በገደል የነበረ ወደ ኢጣልያንም ተጠግቶ የነበረ ሽፍታ ሁሉ መግባት ጀመረ ። ያላጌም ጦርነት ፊትም በደብዳቤ ያገኘነው ከተዋጋውም ከሠራዊቱ አፍ ያገኘነው ይህ ነው ። ጄኔራል ባራቲዬሪ ምጥዋ ሳለ ከሸዋ ጦር መጣብን ብለው ቢልኩበት ፣ ዓድዋም የነበረውን አዲግራትም የነበረውን ጦር አንድ ላይ ጠቅላችሁ ወደፊት ቀድማችሁ ከማገርር ቶዜሊ ጋር ያላጌን በር ያዙ ብሎ ላከ ። ማገርር ቶዜሊም ጦሩን ጠቅሎ ያላጌን በር ይዞ ምሽግ መሸገ ። ጄኔራል ባራቲዬሪም አምባ ነው ። መንገዱም እንኳን ያራት ራሶች ጦር አንድነት ሆኖ ለመሔድና ያንድ ፊታውራሪ ጦር ለማስጎዝ እጅግ ያስጨንቃል ብሎ ነው ይኸን ያደረገው በኅዳር በ27 ቀን የፊታውራሪ ገበየሁ ጦር ከአላጌ ወዲህ ዳቦር (ደቦር) ከሚባል ሜዳ ሰፈረ ። የቀሩትም ራሶች ወደ ኋላ ሰፍረው ነበር ። በ28 ቅዳሜ ጧት በፊታውራሪ ሰፈር ላይ ማገርር ቶዚሊ መድፍ መተኮስ ጀመረ ። የጃንሆይ ሠራዊት ግን ሰንበትን ለማክበር ያንለት ለመዋጋት ፈቃድ አልነበረውም ። ነገር ግን

1 ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ግራዝማች ሳዶር ናኩራ እንደታሠሩ ሞቱ ። ሁለቱ ካህናት መዩገሻ ሆኖ በቆየው በማገርር ቶማስ ሳልሳ ተለውጠው ተለቀዋል ። Italia ed Etiopia ገጽ 205 ፣ የማስታወሻ ቁጥር 3 ። በዚህ ጽሑፍ ላይ ሌተና አስካላ የሚሉት በደብዳቤያቸው እንደ ገለጹት በአምባላጌ ሲዋጋ የተማረከው ደንበኛ ስሙ Scala ነው ።

ጠላት ከተነሣ ወዲያ ጊዜ መስጠት የሞኝ ሥራ ነው ብለው የኋለ ኛው ጦር ሳይደርስ ፊት የነበረው የፊታውራሪዎች ጦር እጅግ የሚ ያስጨንቀውን ዳገት በእግርና በፈረስ ወጥቶ የጦሩን ገዳም (ከምችቱን) አፈረሰው ። መድፉም ተያዘ ማገ፫ር ቶዜሊም ከባልንጀሮቹ ጋር ከዚ ያው ሞተ ። ከማገ፫ር ቶዜሊ ጋር የሞቱ ጣልያኖች ከ30 ይበልጣሉ ። 3 ፈረንጆች ግን ተማረኩ ። ከተማረኩት ከሦስቱ ኢጣልያኖች አንዱ ሊዬትና እስካላ የሚባል የመድፈኛ አለቃ ነው ። ይህ ጦርነት ሲደረግ የኛ ወታደሮች የሸሸው ጦር እንዳያመልጣቸው በዳገትና በቁልቁለቱ ፊሣውን እየረገጡ እስከ ማታ ድረስ ጋለቡበት ።

ጄኔራል አሪሞንዲ የሚባለው ግን ፣ ከኰሎኔል ጋሊያኖ ጋር ኮረ ብታ ወዲያ ሰፍረው ሳለ ፣ የጦርነቱን የመድፉን የጠመንጃውን ተኩስ በሰሙ ጊዜ ለመርዳት ሲነሱ የኛ ጦር የሸሸውን ሲያባርር ከሰፈሩ በት ደረሰባቸው ። ዕቃውን ትቶ መድፉን ብቻ ጭኖ ሸሸ ። የኛም ሰው ተከትሎ ብዙ ሰው ፈጀበት ። ጨለማ ገላገላቸው ። ኰሎኔል ጋልያኖ መቀሌ ከእርድ ገብቶ አደረ ። የተማረኩት መድፎች አራት ናቸው ። የተማረከው ዕቃ ግን የይሩ ባሩድ የዱቄቱ የብሩ ጠበንጃውም ባሳገር ማረከው እስካሁን ይለቀማል ። ይኸን ያህል ጠበንጃና መድፍ ሲተ ኮስ አላጌ ላይ የወደቁ የኛ ወታደሮች 276 ሞቱ 349 ቆሰሉ ። ማገ፫ር ቶዜሊን ተከትሎ የሔደ ባሻ ባዙቅና የትግሬ ጦር አንድም አላመሰጠም ። ደጃች ባሕታ በሞተ ጊዜ ጣልያኖቹ አይቀበር ብለው ከልክለው ነበር ። ዛሬም አላጌ ላይ የሞቱትን ጣልያኖች ራስ መኰንን ሳስቀብራቸው ቢሉ የደጃዝማች ባሕታ ወንድሞች አይቀበሩብን ብለው ለራስ መኰንን ቢሙሁ ፣ ይህ የከርስቲያን ሥራ አይደለም እነዚያ ቢከፉ እንደነዚያ እንከፋም ብለው አስቀበሯቸው ። ከዚህ በኋላ የጃንሆይ ሠራዊት የመ ቀሌን እርድ ከቦ ተቀመጠ ። እርሱ ግን የእርቅ ነገር እየተላላከ ሌት ሌት ካቡን እየካበ እርድን አጠነከረ . . . [1]

እላይ በግራዝማች ዮሴፍ ጽሑፍ እንደ ተገለጸው ፣ ጄኔራል አሪሞን ለማገ፫ር ቶዜሊ ድጋፍ ለመሆን አንድ ሺ አምስት መቶ ጦር ይዞ ሌሊቱን ሁሉ ወደ አላጌ ለመድረስ ሲገሠግሥ አድሮ በአራት ሰ ላይ አፍጐል ደረሰ ። ከዚያም በሩቅ የአላጌን ተራራ የጥይት ጭ አጥቁሮት ተመለከተ ። ከዚያ ተነቃንቆ በዐሥር ሰዓት አዲአሩ ጉብታ ላይ ሰፍሮ ሳለ ፣ ቶዜሊን በሕይወት እንዳለ ቆጥሮ ከዚህ የ ከተለውን ደብዳቤ ጻፈለት ።

. . . እዚህ የደረስሁት ባራት (10) ሰዓት ነው ። ከምሽት በፊት ከዚህ ተነስቼ ወደ ማይ መዝጊ ሳልጠጋ አልቀርም ። የጠላት ጦር በርከቶ እንደሆነ ወደኋላህ እንድትመለስ ጠቅላይ ገዥው በጥብቅ ያዘዘውን ልኬብሃለሁ ። ያንተ ጦር ወደኋላ መለስ ቢል ከኛ ጦር ጋር ተገናኝቶ ከዚያው የሁሉም ጦር ተጠቃሎ ከአገረ ገዥው (ባራቲዬሪ)

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ዶሲዬ ፣ ቁ.82



ጋር መቀሌ ላይ ይጠቃለላል ። ጥይትና ዱቄት የያዙት የብሌክን (ያገር ተወላጅ ሹም) ሰዎች በቴኔንቲ ኪያሪኒ መሪነት መጥተዋል ።

አሪሞንዲ ይኸን ለቶዜሊ ጽፎ ሳለ ደብዳቤው አላጌ ሳይደርስ ፣ በዐሥር ሰዓት ተኩል ላይ ፣ ከጦርነቱ ቦታ የሚሸሹትን የኢጣልያኖ ችና የባንዳ ወታደሮችን የሚያባርሩት የነራስ መኰንን ወታደሮች ያ.ር ሰው ተኩስ ከፈቱበት ። ዝርዝር ወሬውንም ፣ ከሞት የተረፉት ሦስት መቶ ባንዳዎች ከሦስት የኢጣልያ መኰንንኖች ጋር ደርሰው ነገሩት ። ከአላጌ የሸሹት ራስ ስብሐት ጄኔራል አሪሞንዲን ባገኙት ጊዜ ፣ "ከስድስት ሳምንት በፊት በጠላት ላይ ተጠንቀቁ፣ ከኛ በቁጥር ይበል ጣልና ለምን ሠራዊቱን ባንድነት አትሰበስቡም ብዬ ላገረ ገዥው ለባራቲዬሪ ነግሬው ነበር ። ያለዚያ (ቢሰማኝ ኖሮ) ይኸ ሁሉ እልቂት አይደርስብንም ነበር"[1] ብለው ብስጭትና ቁጣ ጭምር ነገሩት ።

ከዚህ በኋላ ፣ አባራሪዎቹ መተኮሳቸውን ሲቀጥሉ የጄኔራል አሪ ሞንዲ ፈረስ ተመትቶ ሞተ ። ቢሆንም የኦዶኔ ክፍል ወታደሮች ጠንከር ብለው ስለመከቱ ፣ አደጋ ላይ የተገኘው ጄኔራል አሪሞንዴና ወታደሩ የመሸሻ ጊዜ አግኝቶ ፣ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ከሩብ ላይ ተኩሱ ጋብ ስላለ ፣ ጊዜውንም ምሽት ስለ ተከተለው ፣ በራሪዎቹ የአፍ ጐልን ሜዳ አቋርጠው ከሌሊቱ በዐሥር ሰዓት መቀሌ ገቡ ።

በአላጌው ጦርነት ፣ በጠቅላላው ከኢጣልያኖቹ ወገን ሁለት ሺ ወታደር ማለቁን ጠቅላይ አዛዡ ባራቲዬሪ በጻፈው መጽሐፍ አረጋ ግጧል ። ስለዚህ ከዘመተው ጠቅላላ ጦር የተረፈው ሦስት መቶ ሃምሳ ግድም ብቻ ነው ማለት ነው ። በኛ በኩል በግራዝማች ዮሴፍ ደብ ዳቤ ላይ እንደ ተገለጸው ፣ የሞቱት ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ፣ የቆሰ ሉት ሦስት መቶ ዐርባ ዘጠኝ ናቸው ።

1 Italia ed Etiopia . . P. 212

# ምዕራፍ ሐያ ስምንት

## የዳግማዊ ምኒልክና የሠራዊታቸው መቀሌ መግባት—የኢትዮጵያ ድርጅትና የጦር ኃይል

ባለፈው እንደ ተመለከትነው ፣ ዳግማዊ ምኒልክ በየመንገዱ ሰፈር እያደረጉ ከየአለበት በየአለቃው እየተሰለፈ ለጦርነት የሚመጣውን ተቀብለዋል ። ባንዳንድ ሰፈርም ስለ ደስታ ግባት እያስተኮሱ የሸፈቱ እስገብተዋል ። ብዙ ሠራዊት ብዙ ባለበቅሎና ፈረሰኛ ለማስተላለፍ የሚያስቸግረውን ውድማ መንገድ ሲያስጠርጉ ፣ አባጣ ጐባጣውን ሲያስደለድሉ ፣ ጫካውን ሲያስመነጥሩ ፣ በየአደሩበት ድግስ እየተደገሰ ሰንጋ እየታረደ ግብር እየተበላ ተጉዘው ከአዲስ አበባ በተነሡ በሦስተኛው ወር መጀመሪያ ላይ በታኅሣሥ 5 ቀን ወፍላ ፣ በ8 አሸንጌ ፣ በ11/1888 ደምባልአ ደረሱ ። እዚህም በደረሱ ጊዜ ቀድመው የአላጌን ጦር የደመሰሱት እነ ራስ መኰንን በሰፈሩበት ሥፍራ በሽታ ገብቶ ፣ ብዙ ፈረስና በቅሎ ሞቶ መንገድ አላስሔድ ስላለ ፣ ከአሸንጌ በታኅሣሥ 23 ቀን ተጉዘው የቀድሞውን ጐዳና ፣ ወደ እንጣሎ የሚሔደውን ሰቀው ፣ በቀኝ በኩል አልፈው መሐን ሕዝባ ከደረሱ በኋላ መንገድና ስንቅ ለማዘጋጀት እዚሁ ላይ ሰፈሩ ።

በመሐን ሕዝባ ላይ ሳሉ ፣ ወደ ኋላ ዘግይተው የነበሩት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦራቸውን አስከትለው ፣ ከጐጃም ተነሥተው ፣ በቤጌምድር አድርገው ፣ በታኅሣሥ 15 ቀን ደርሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኙ ። ከዚያ ንጉሠ ነገሥቱ በ19 ከመሐን ሕዝባ አልፈው በ22 እንዳ መሆኒ ፣ ከዚያ በ23 ዋጀራት ገቡ ። ይኸም ስፍራ ባንድ ወገን የአላጌ ጦርነት ለት ብዙ ጣልያንና ባንዳ ያለቀበት ስለነበረ ፣ የሬሳው ሽታ ከማስቸገሩ በቀር መንገዱ ውድማ የበዛበት ስለሆነ ፣ በሦስትና በአራት መስመር በየጫካው ውስጥ መንገድ እየተከፈተ ሲሠራ ጕድጓዳው ሲሞላ ሰነበተ ። ከመንገዱ መጥፎነትና ጠምዛዛነት የተነሣ እንዱን የወንዝ ውሃ ሠላሳ ስምንት ጊዜ ማለፋቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጻፉት ማስታወሻ ያረጋግጣል ።

ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱና ሠራዊቱ ፣ በብዙ ችግር ጠባቡን መንገድ በታኅሣሥ 24 እና 25 ቀን አልፈው በ26 ቀን ጨለቆት ሰፍረው

ሳሉ ፣ ወደፊት ቀድመው የነበሩት ራስ ሚካኤል ፣ ራስ ወሌ ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ፣ ራስ መኰንን ፣ ራስ አሉላና ደጃች ወልዴ ወደኋላቸው ተመልሰው ፣ ጨለቆት መጥተው ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ነሥተው ተገናኙ ። አላጌ ላይ የተማረከውንም መድፍ አስረክበው ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ለጣልያን እንደሆነ የያዝነው የኛው ይበቃናል " ብለው ከአላጌ የተማረከው መድፍ ወደ አዲስ አበባ ተላከ ።

በዚሁ በጨለቆት በታኅሣሥ 28 ቀን የልደትን በዓል (ገናን) አክብረው ፣ በ29 ከጨለቆት ተጉዘው መቀሌ ሰፈሩ ። በዚህም ቀን ስሜንን የእቴጌ ጣይቱን አገር የሚገዙት የእኅታቸው የወይዘሮ ደስታ ልጅ ደጃች ገሠሠ ስለነበሩ ፣ ከስሜን 500 በግ ብዙ ቅቤ ይዘው ገቡ ።[1]

በዚያን ዘመን ፣ በኛ በኩል የጦርነቱን ታሪክ መዘርዘር ፣ ማናቸውንም የተደረገውን በጽሑፍ ማስቀረት ስለ አልተለመደና ወደ ጊዜያችን የተላለፈ ባለመኖሩ ፣ በዓድዋ የተዋጋውን ትክክለኛውን የወታደሩንና የሹማምንቱን ፣ የጠረኛውንና የነፍጠኛውን ፣ የመድፈኛውን ቁጥር ለይተን አናውቅም ። ኢጣልያኖች በያለበት ሰላዮቻቸውን አሠራጭተው በሰበሰቡትና በዕርቅ እያመካኙ ሹማምንቱ እነማጕር ሳልሳና እነቲኔንቲ ፓርቲኒ ከንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር በነበሩበት ጊዜ በግምት የሰጡት የወታደር ቁጥር በብዛትና በማነስ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

| | ሲያንስ | ሲበዛ |
|---|---|---|
| የዳግማዊ ምኒልክ | 34,000 | 38,000 |
| የእቴጌ ጣይቱ | 5000 | 6000 |
| የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት | 5000 | 6000 |
| የራስ ሚካኤል | 14,000 | 15,000 |
| የራስ መኰንን | 15,000 | 16,000 |
| የራስ ቢትወደድ መንገሻ | 5000 | 6000 |
| የራስ ወሌ | 6000 | 7000 |
| የራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ የራስ የአሉላንና የራስ ሐጐስን ጨምረው | 3000 | 4000 |
| የዋግሹም ጓንጉል | 10,000 | 11,000 |
| የፊታውራሪ ገበየሁ | 13,000 | 14,000 |
| ድ ም ር | 110,000 | 123,000[2] |

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ገጽ 239—244 ።

2 La Giornata di Adua - R.Mazzucconi, P. 202.



በጣም አሳንሰው የሚያቀርቡት ደግሞ ፣ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ። ይኸንንም ያቀረበው በሰላይነት የተያዘው መሐንዲሱ ካፑቺ ነው ።

| | | |
|---|---|---|
| ራስ መኰንን | 8000 | |
| ራስ ሚካኤል | 8000 | |
| ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት | 5000 | |
| ራስ መንገሻ ዮሐንስ | 5000 | |
| ራስ ወሌ ብጡል | 5000 | |
| ራስ መንገሻ አቲከም | 3000 | |
| ዋግሹም ጓንጉል | 2000 | |
| ያፄ ምኒልክ ዘበኞች (የልፍኝ) | 3000 | |
| የእቴጌ ጣይቱ ጦር የደጃች ገሠሠ ጭምር | 4000 | |
| የዕቃ ቤት የጠጅና የሥጋ ቤት | 1500 | |
| የንጉሠ ነገሥቱ ዕውቅ የሆነው ጦር ባቶ | | |
| (በፊታውራሪ) ሀብተ ጊዮርጊስ የሚታዘዘው | 3000 | |
| በበጅሮንድ ባልቻ የሚታዘዘው | 3000 | |
| በሊቀ መኳስ አባተ የሚታዘዘው | 2000 | |
| ራስ ወልደ ጊዮርጊስ | 5000 | አውሳ የዘ |
| ደጃዝማች ተሰማ ናደው | 5000 | መቱት |
| ራስ ዳርጌ | 3000 | አዲስ አበባ |
| ደጃች ሉል ሰገድ | 3000 | ለጥበቃ የቀሩት |
| ድ ም ር | 68,500 | |

አዲስ አበባ የቀሩትና አውሳ የዘመቱት 16,000 ሲቀነስ በስሜን የዘመተው 52,500 ጦር መሆኑ ነው ። በምርኮኝነት አዲስ አበባ ከርሞ በኋላ በእርቅ ወደ አገሩ የተመለሰው ጄኔራል አልቤርቶኒ ሌላ የበዛ ዝርዝር ይሰጥና ሲያንስ 111,000 ሲበዛ 122,000 ያደርገዋል ። ከዓድዋ ድል በኋላ ለዕርቅ ወዳፄ ምኒልክ የተመላለሰው ማጕር ሳልሳ ደግሞ 130,000 ተዋጊ ፣ ከ60 እስከ 70 ሺ አሽከርና ገረድ ያደርጋል ። እነዚህ እንደዚህ ከፍ ያለ ቁጥር የሚያቀርቡት እንደዚህ ባይበረከትኖሮ በዋዛ አንሸነፍም ነበር ብለው ለመግደርደር ፣ ያቀረቡት ይመስላል ። እንደ ክሎሺት እንደ ግለይሽን ያሉት ከ150,000 እስከ 200,000 አድርሰውታል ።[1]

1 Italia ed Etiopia - Conti - Rossini, PP. 340-342, Gli Italiani in Africa Orientale A. Del Boca., PP. 651 - 652.

በዚህ ዐይነት ፣ ሁሉም የተለያየ ቁጥር ቢሰጥም ፣ በመካከለኛና በሚመስል ቁጥር 100,000 ግድም ባለጠመንጃ ይኖራል ብሎ ለማ ሰብ ይቻላል ። ንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥነት ዘመን ጀምሮ ፣ ከጦቡ በፊት ከኢጣልያ መንግሥት በግዥ ካገኙት በቀር ፣ በወዳጆቻቸው የውጭ አገር ሰዎች በእንጂኔር ኢልግ ፣ በሽፍነ ፣ በሶለዬ ፣ በላባሉ ፣ በሪምቦ ፣ በባራል ፣ በሳቩሬ ፣ በብሬሞ ፣ በቦሬሊ ፣ በቢኖ አማካይነት በየ ጊዜው በግዥ የሰበሰቡት ተጠራቅሞ ፣ ባሁኑ ጊዜ በእጃቸው 189,000 ልዩ ልዩ ጠመንጃ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ዐርባ አራት ሺ ጥይቶች ዐርባ ስድስት መድፎች ፣ አራት መትረየሶች እንደ ነበሩዋቸው የሚያ ረጋግጡ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ያፄ ምኒልክን የጦር ኃይል ከዚህ የሚያስበልጡም የሚያሳንሱም አሉ ።[1]

እነዚህ ሁሉ የተለያዩ መሳፍንትና መኳንንት ፣ በተለይ በየአውራ ጃው ትክለኛ መሳፍንት ወይም ባለጉልት የሆኑት እነንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ እነራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ እነራስ ሚካኤል ፣ "እንደምን ላፄ ምኒልክ አበሩላቸው" በማለት ያልተደነቀና ያልተገረመ የለም ። በተለይ ጣልያኖቹ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው የካቲት 23 ቀን ዋና ውን ጦርነት እስከ ጀመሩ ድረስ ፣ እነዚህ እላይ የተጠቀሱት ባፄ ምኒልክ ላይ ሸፍተው በየአገራቸው ይቀራሉ ወይም ከጦር ሰፈር እን ዋጋም ብለው ተመልሰው ወደ አገራቸው ይገባሉ የሚሉና ጐጃ ሚው ፣ ትግሬው ፣ ወሎዬው ፣ ከሸዌው ጋር አይዋደድምና እነዚህ ሁሉ ተስማምተው በኅብረት ጣልያንን አይወጉም ብለው የሚያምኑ ነበሩ።

ማንቴጋዛ የሚባለው ፣ "ወዳፄ ምኒልክ በዕርቅ ምክንያት አንድ ወኪል እንልክ የነበረው ፣ ጊዜ ለማግኘት ወይም አንድ ራስ ንጉ ሡን እንዲከዳ ለመገፋፋት ብቻ ነበር"[2] ብሏል ። ዋናው አዝማች ዤኔራል ባራቲዬሪ ከዓድዋ በኋላ ባዘጋጀው መጽሐፉ ፣ "ራሶቹን ለመ ጀመሪያ ጊዜ ምኒልክ በኛ ላይ ለማስለፍ ዐወቀበት"[3] ብሏል ። በኢት ዮጵያ የታሪክ ጥናት ስመ ጥሩ የሆነው ኮንቲ ሮሲኒ ደግሞ ፣ "ምኒልክ ታላላቆቹ አለቆች እንዲከተሉት ለማስገደድ ያደረገው ከንውን አስደ ናቂ ነው" ይልና ከዚያ እልፍ ብሎ ፣ "አበሻን በሙሉ በጐኑ አሰ ልፎ ለማዋጋት በመሰብሰብ ረገድ ምኒልክ አንድ ተአምራት ፈጽ ሟል ... ይኸን የመሰለውን ያውም ከዚህ ያነሰውን ያንድነት ታሪክ ለመፈለግ ከአህመድ ወልደ ኢብራሂም ጋር ወደ ተደረገው ጦርነት መሔድ አለብን[4] ..." ብሏል ። ወደ ግራኝ ጦርነት ማለቱ ነው ።

---

1 La Giornata di Adua, R. Mazzucconi, PP. 202 - 203, Chronology of Menelik II-C.P. Rossenfield PP.160 - 162
2 L' Assedio di Maccalle, V. Mantegazza, P. 325.
3 Memoire d' Afrique, O. Barratieri, p. 351.
4 Italia ed Etiopia, Conti - Rossini, Gli Italiani in Africa, Del Boca, P.252.





ደጃዝማች ባልቻ
ከሞሪስ ደኮፒ

በዚህ ዐይነት ፥ ሁሉም የተለያየ ቁጥር ቢሰጥም ፥ በመካከለኛና በሚመስል ቁጥር 100,000 ግድም ባለጠመንጃ ይኖራል ብሎ ለማሰብ ይቻላል ። ንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥነት ዘመን ጀምሮ ፥ ከጠበበፊት ከኢጣልያ መንግሥት በግዥ ካገኙት በቀር ፥ በወዳጆቻቸው የውጭ አገር ሰዎች በእንጂኔር ኢልግ ፡ በሽፍን ፡ በሶለዬ ፡ በላባሉ ፡ በሪምቦ ፡ በባራል ፡ በሳቩሬ ፡ በብሬሞ ፡ በቦሬሊ ፡ በቢኖ አማካይነት በየጊዜው በግዥ የሰበሰቡት ተጠራቅሞ ፡ ባሁኑ ጊዜ በእጃቸው 189,000 ልዩ ልዩ ጠመንጃ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ዐርባ አራት ሺ ጥይቶች ዐርባ ስድስት መድፎች ፥ አራት መትረየሶች እንደ ነበሩዋቸው የሚያረጋግጡ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ያፄ ምኒልክን የጦር ኃይል ከዚህ የሚያስበልጡም የሚያሳንሱም አሉ ።[1]

እነዚህ ሁሉ የተለያዩ መሳፍንትና መኳንንት ፥ በተለይ በየአውራጃው ትክለኛ መሳፍንት ወይም ባለጉልት የሆኑት እንንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፡ እንራስ መንገሻ ዮሐንስ ፥ እንራስ ሚካኤል ፥ "እንደምን ላፄ ምኒልክ አበሩላቸው" በማለት ያልተደነቀና ያልተገረመ የለም ። በተለይ ጣልያኖቹ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው የካቲት 23 ቀን ዋናውን ጦርነት እስከ ጀመሩ ድረስ ፥ እነዚህ እላይ የተጠቀሱት ባፄ ምኒልክ ላይ ሸፍተው በየአገራቸው ይቀራሉ ወይም ከጦር ሰፈር አንዋጋም ብለው ተመልሰው ወደ አገራቸው ይገባሉ የሚሉና ጎጃሜው ፥ ትግሬው ፥ ወሎዬው ፥ ከሸዌው ጋር አይዋደድምና እነዚህ ሁሉ ተስማምተው በኅብረት ጣልያንን አይወጉም ብለው የሚያምኑ ነበሩ።


ማንቴጋዛ የሚባለው ፥ "ወዳፄ ምኒልክ በዕርቅ ምክንያት አንድ ወኪል እንልክ የነበረው ፡ ጊዜ ለማግኘት ወይም አንድ ራስ ንጉሡን እንዲከዳ ለመገፋፋት ብቻ ነበር"[2] ብሏል ። ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ከዓድዋ በኋላ ባዘጋጀው መጽሐፉ ፥ "ራሶቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ምኒልክ በኛ ላይ ለማሰለፍ ሀወቀበት"[3] ብሏል ። በኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት ስመ ጥሩ የሆነው ኮንቲ ሮሲኒ ደግሞ ፥ "ምኒልክ ታላላቆቹ አለቆች እንዲከተሉት ለማስገደድ ያደረገው ክንውን እስደናቂ ነው" ይልና ከዚያ እልፍ ብሎ ፥ "አበሻን በሙሉ በጐኑ አሰልፎ ለማዋጋት በመሰብሰብ ረገድ ምኒልክ አንድ ተአምራት ፈጽሟል . .. ይኸን የመሰለውን ያውም ከዚህ ያነሰውን ያንድነት ታሪክ ለመፈለግ ከአህመድ ወልደ ኢብራሂም ጋር ወደ ተደረገው ጦርነት መሔድ አለብን[4] . . ." ብሏል ። ወደ ግራኝ ጦርነት ማለቱ ነው ።

1 La Giornata di Adua, R. Mazzucconi, PP. 202 - 203, Chronology of Menelik II-C.P. Rossenfield PP.160 - 162
2 L' Assedio di Maccalle, V. Mantegazza, P. 325 .
3 Memoire d' Afrique, O. Barratieri , p. 351.
4 Italia ed Etiopia, Conti - Rossini, Gli Italiani in Africa, Del Boca, P.252.





ደጃዝማች ባልቻ
ከሞሪስ ደኮፔ



ራስ አባተ ቧ ያለው

ከአናራቶሪ

# ምዕራፍ ሐያ ዘጠኝ

## የመቀሌ ምሽግና ማገሮር ጋልያኖ - ከኢጣሊያ አገር የሚላከው ጦርና በምክር ቤት የተደረገ ክርክር

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፡ የአላጌን ውድቀት ራሱ ማስታወቅ ግዴታው ስለ ነበረ ፡ ይኸንኑ ላለቆቹ ካስታወቀ ወዲህ አሁንም ከአሸንጌ ወደ መቀሌ የሚያመሩትን የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ብዛት እየዘረዘረ ፡ አዲስ የጦር ወታደር እንዲጨመርለት እየደጋገመ ከመጠየቁ በፊት በኮዓቲት ፡ በሰንዓፌና በደብረ ኃይላ ጦርነት ጊዜ የተደነቀውንና የተከበረውን ያህል ፡ አሁን ደግሞ ከየአለቆቹ ወቀሳ አዘል ትእዛዝ ይደርሰው ጀመር ። በቀጥታ የሚጻጻፉቸው አለቆችም አንደኛ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ፡ የመከላከያ ሚኒስትሩ ሞቺኒና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ናቸው ። ከርሱ ወገን ፡ "የንጉሡ ጦር ብዙ ስለሆነ እርዳታ ላኩልኝ" ሲል እነርሱ ደግሞ ዓይነትና መጠን መወሰን አለብህ ይሉታል ። " መልካም የ14 ባታዮ ጦርና 5 (ባትሪ) የመድፈኛ ጦር " ይላከልኝ ብሎ ሲመልስ ፡ "የለም ኢትዮጵያን በሙሉ የመያዝ ዓላማ የለንምና የያዝነውን ቅኝ አገር ለማጥበቅ ይኸን ያህል ጦር ይበዛል ። ስለዚህ የዘጠኝ ባታዮ ጦርና ሦስት የመድፈኛ ክፍል ይበቃሃል" በመባባል ክርክራቸውን በቴሌግራም ይመላለሱ ነበር ።* በፊት በኮዓቲቱ በደብረ ኃይላው ጦርነት ይወዳደሱ የነበሩት አሁን የአላጌ መሸነፍ ከተሰማ ጀምሮ የክሪስፒና የባራቲዬሪ የፖለቲካ ቡድኖች በምክር ቤትም በየጋዜጣውም ወቀሳና ንትርክ በዝቶባቸው ነበር ። ቶስካኔሊ የሚባለው የምክር ቤት አባል በረዥም ንግግሩ ውስጥ ፡ "አበሾች ገና ከመወለዳቸው ጦረኞች ናቸውና ጦርነቱ በፍጹም ይቅርብን " ያለውን ጠቅላይ ሚኒስትሩና ወገኖቹ ሊገነዘቡለት አልቻሉም ።

---

* አንድ ባታዮ ጦር በውስጡ 25 የጦር መኰንን 800 ወታደር ያለው ይሆንና 27 የመትረየስነት ጠባይ ያለው ጠመንጃ 6 ቀላል መትረደየስ 8 ከባድ መትረየስ 6 ሞርቲዮ (አጫጭር መድፍ) ባለ 81 የሆነ 3 መድፍ ታንክ የሚያፈርስ ። አንድ ባትሪ ደግሞ በውስጡ 4 መድፍ ያለው ነው ። ይኸም እንደ አገሩና እንደ ዘመኑ የቁጥሩ መጠን ይለያያል ። የኢጣልያ አንድ ባታዮ ባለ 700 ወታደር ነው ።

1 L' Assedio d' Maccalle, Vico Mante - gazza, PP. 77- 85.

ስለዚህ ራሱ ክሪስፒ ባንደኛው ቴሌግራም ፡ “ጊዜው ላንተም ለሁላችንም አደገኛ ነው ። የጠየቅኸውን ልከንልሃል ፤ ከጠየቅኸውም በላይ እንልከልሃለን ። አለማሰብና አለመጠንቀቅ መከራ ያመጣ እንደ ሆነ በዚህ እኛ ምንም ጥፋት የለብንም” ብሎ ከላከለት በኋላ ቀጥሎ በዚያው ሰሞን ደግሞ ፡ “መንግሥት በሰውም በመሣሪያም የጠየቅኸውን ልኮልሃል ። አገሪቱ አንድ ሌላ ድል ትጠብቃለች ፤ እኔም ራሴ እጠብቃለሁ ። ይኸም ድል አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ያበሻን ጉዳይ የሚደመድም መሆን አለበት ። በምታደርገው ተጠንቀቅ ፤ የራስህና የኢጣልያኖች ክብር ያለበት ነገር ነው ።”[1]

የዚህም ቀጥተኛ ትርጉሜው ፡ የአውሮፓዊውና የሠለጠነችው የኢጣልያ ጦር ባልሠለጠነችው አፍሪካዊቷ በኢትዮጵያ ጦር መሸነፉ ያንተም ፡ የኢጣልያም ክብር ተነክቷልና ይኸን የአላጌን መሸነፍ የሚያስረሳ ኢትዮጵያም ሁለተኛ እንዳታንሰራራ የሚያደርግ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ የሚሆን ጦርነት አድርገህ በድል አድራጊነት ስማችንን አድስህ ለኢጣልያንም ቅኝ አገር አውርሳት ነው ። በዚህም ላይ ኢትዮጵያን እንደ ማናቸውም የጥቁር አገር ስለሚቆጥራት ፡ በአፍሪካና በእስያም ከዚህ በፊት እንዳልነው እንግሊዞችና ፈረንሣዮች ፡ ጀርመኖችና ቤልጃኮች አብዛኛውን ጊዜ ቅኝ አገሮቻቸውን ሁሉ በቀላል ጦርነት ስለያዙ ፡ የኢጣልያ መሪዎችም ኢትዮጵያን የሚመለከቷት በዚሁ ዓይነት ነው ። በዚህ ስሜት አያሌ መማክርት የአላጌው ውድቀት ክብራቸውን እንደነካ በመቁጠር ይኸንኑ በእጥፍ ለመበቀል የሁሉም ምኞት ነው ። በዚህም ጐን እላይ እንዳልነው የነክሪስፒ የፖለቲካ ባላጋራዎች ሥልጣን ለመያዝ ሲሉ የመንግሥቱን አስተዳደርና የጦሩንም አመራር በምክር ቤትና በጋዜጣ ይነቅፉታል ። የአላጌንም ውድቀት ለአባባላቸው በቂ ምስክር አድርገው በማቅረብ ሥልጣን ለመረከብ ይሟገታሉ ።

የሆነ ሆኖ ፡ ጄኔራል ባራቲዬሪ የጠየቀው የእርዳታ ጦር አላጌንም ለመበቀልና በኢትዮጵያ ለመስፋፋት ከኢጣልያ አገር ተሰብስቦ በናፖሊ ወደብ ሲሣፈር ሲል ፡ በሹማምንቱና በወታደሩ መንፈስ ታላቅ ደስታ ነበር ። ከመሳፍንቱ ጀምሮ ሁሉም እኔ ልሒድ እኔን ስደዱኝ እያለ የመከላከያ ሚኒስትሩን በደጅ ጥናት የሚያዋክበው ብዙ ነበር ። ከሲቪል ሳይቀር ብዙዎቹ አማላጅ እየላኩ የተመለመሉ አሉ ። የየዘማቹ ቤተሰብና ነዋሪው ሰው ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ የሚጠብቀውን የመሸነፍ አደጋ ሳይገነዘብ ዘማቾቹን በዘፈን ፡ በደስታ ፡ በትልቅ በዓል

1 LA Prima Guerra D' Africa - Bataglia PP - 282 - 284



ለመሸኘት ሁሉም ለየራሱ ኮሚቴ አበጅቶ ለየወታደሩ ሲጃራ ፡ መጠጥና ልዩ ልዩ ስጦታ እየተሰበሰበ ለዘማቹ ይታደል ነበር ። ወደ ናፖሊ ወደብ ከመድረሳቸው በፊት ወታደሩን ያሳፈረው ባቡር በሚቆምበት ጣቢያ ሕዝቡ እየተሰበሰበ በደስታና በሆታ ይሸኛቸው ነበር ። የየባታዮው ጦር በየክፍሉ ሆኖ ወታደሩ ከመርከብ ላይ ሊሣፈር አቅራቢያ በዘማቹና በቤተሰቡ መካከል የበረከተ ሁካታ ፡ የስንብት መሳሳም ሲደረግ ፡ ሥነ ሥርዓቱ ሁሉ ተዘበራርቆ ስለ ነበርና ሹማምንቱ ሥርዓት ለማስከበር ሲሞክሩ በዚህ ሥፍራ ቆሞ ይኸን ትርዒት በደስታ ይመለከት የነበረው አድሚራል ኮርሲ ፡ “አንድ ጊዜ ተውዋቸው የፈለጉትን ያድርጉ” የሚል ቃል ሲወረውር ፡ በዚያ የቆመው ቤተሰቡ ሁሉ ጭብጨባውን በደስታ ገለጠ ።

የዓድዋ ጦርነት ከመደረጉ በፊት ፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 29 ቀን ወደ ኢትዮጵያ የሚዘምቱት ወታደሮች ከናፖሊ ወደብ በተነሡበት ቀን ንጉሡ ራሱ ተገኝቶ ሸኝቷቸዋል ። ከመነሣታቸው በፊት ባደረገላቸው ዲስኩር ፡ “መኳንንት ምክትል መኳንንትና ወታደሮች ሆይ! የራሴን የወታደርነትና ያገሪቱን ሰላምታ እኔው ራሴ ላቀርብላችሁ ፈለግሁ ። በወንድሞቻችን ደም የተቀደሰችውና የምትሔዱባት አገር ለናንተ እንግዳ አይደለችም ። በርሷም ላይ የኛ ድል አድራጊነትና የመሥዋዕትነት ሙያውና ዋጋው ፡ ማስታወሻው ገና በትኩሱ እንዳለ ታገኙታላችሁ ። እነዚህንም ምሳሌዎች እናንተም ትፎካከሩባቸዋላችሁ ። ወታደሮች ሆይ ! የኢጣልያንን ምኞት ለወታደር ጓደኞቻችሁ እንድታደርሱ ባንዲራዋን ለመከላከል የሁሉም ልጆቿ እሽቅድምድም ነው ” የሚል የማበረታቻ ቃል ይገኝበታል ።[1]

በዚህ ዓይነት ፡ የኢጣልያ ወታደር በፊትም የተላኩት አሁንም ከአላጌ ጦርነት ወዲህ በጥርና በየካቲት ወር ከኢጣልያ አገር የተሣፈሩት ሁሉ በጠቅላላው ኤርትራም ከገቡ በኋላ ፡ ሁሉም መኰንኖችና ወታደሮች ጦርነት የጠማቸውና ድል ማድረግ የናፈቃቸው በድል አድራጊነታቸውም የተረጋገጡ ነበሩ ። ይሁን እንጂ ፡ የአላጌን ጦርነት የተካፈሉትና በሽሽት ወደ መቀሌ የተመለሱት ብቻ ከኋላ ያለውንም የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ወሬ በመስማት ስለኢትዮጵያ ጦር ያላቸውን አስተያየት ሳይለውጡ ይኸውም ማለት ሳያሠጋቸው አይቀርም ።

ጄኔራል አሪሞንዲ ፡ ፈረሱ በአባራሪዎቹ ኢትዮጵያውያን ተመትቶ ከሞተበት በኋላ በሌላ ፈረስ ሆኖ በሽሽት ከነጭፍራው መቀሌ ገብቶ

1 Francesco Crispi, La Prima Guerra d' Africa, P. 407

ዋናው የነራስ መኰንን ጦር መቀሌ ከመድረሱ አስቀድሞ በፊቱ ሦስት ጉዳዮች ተደቅነዋል ።

፩ኛ የመቀሌን ምሽግ አፈራርሶ የራሱን ጦር ጠቅሎ ወደ ዋናው ጦር በፈር ወደ አዲግራት መዛወር ፤

፪ኛ ወይም ያንድ ክፍል ጦር እዚሁ ከመቀሌ ምሽግ እንዲከላከል ትቶ እርሱ የቀረውን ጦር ይዞ ወደ አዲግራት መሔድ፣

፫ኛ ሁሉንም ጦር እንደያዘ እዚሁ መቀሌ ቀርቶ ወደፊት የሚጓዘውን የኢትዮጵያን ጦር መመከት ነው ።

ነገር ግን ፤ ጀኔራል አሪሞንዲ ምሽጉ ምንም በደምብ የተመሸገና የሦስት ወር ስንቅ የያዘም ቢሆን ፤ "ለብዙ ሠራዊት ሥፍራውም ስንቁም አይበቃም" በሚል አሳብ ይዋልል ነበር ። ጉዳዩን በውስጡ ካሉት ሻለቆች ከነጋልያኖ ከነአሚልዮ ጋር ሌሊቱን ተመካከረበት ። አንዳንዶቹ ፤ "ምሽጉን አፍርሰን ጠቅለን መሔድ የአገራችንን ክብር ይነካል" ስለአሉ ፤ ጋልያኖ "እኔ የራሴን የባታዮ ጦር ይዤ እዚሁ ለመከላከልና ሕይወቴንም ቢሆን ላገሬ ክብር ለመሠዋት ቆርጫለሁ" ብሎ ተናገረ ። በዚሁ ተወስኖ ለጋልያኖ 21 የጦር መኰንኖች ፤ 176 የነጭ ፤ 1150 ያገር ተወላጅ ወታደሮች ፤ አንድ የመድፈኛ ክፍል ተሰጠውና ቀረ ። አሪሞንዲም የቀረውን ጦር ይዞ ሲነጋ ራስ መኰንን ከመድረሳቸው በፊት በችኮላ አለቃው ወዳለበት ወደ አዲግራት ፍርሃት ባለበት ግሥጋሤ ሔደ ። የዚህን ጉዞ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ፤ "አሪሞንዲ የሦስቱን ቀን ጉዞ ባንድ ሌሊት አቋረጠው" ሲሉ ተችተዋል ።[1]

ጋልያኖ ፤ ጦርነት የጠማውና የኢትዮጵያን ጦር ይንቅ እንደነበረ በግል ከወዳጆቹ ጋር የተጻጻፋቸው ደብዳቤዎች ያመለክታሉ ። የአላጌ ጦርነት ከመደረጉ ከአንድ ወር በፊት በዚሁ በመቀሌ የነርሱው አገር ተወላጅ ናሬቲ በሠራው ባዬ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ተቀምጦ ሳለ ሊቤሪና ለሚባለው ኢጣልያ አገር ላለው ወዳጁ እንደዚህ የሚል ደብዳቤ ጽፎ ነበር ።

በጣም የተወደድሽው ሊቤሪና

የዛሬ ሐያ ዓመት አንድ ናሬቲ የሚባል የኢብሬያ አናጢ ሠርቶት በነበረ ባዬ ዮሐንስ አዳራሽ ዙፋን ላይ ተዝናንቼ በመዘርጋት በመልካም ጤንነት የምገኝ መሆኔን ስመግለጽ እነዚህን ጥቂት መስመሮች እልክልሃለሁ ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 241-242



ከሦስት ቀን ጀምሮ የአራተኛው ባታዮ ጦር የጀመረውን ይኸን ምሽግ ለማስጨረስ የኔ ወታደሮች እንዲያግዙ እዚሁ ላይ ቆይቻለሁ ። ሥራውም አልቆ መልካም መከላከያ ሆኗል ። . . . ነገ ከጀኔራል አሪሞንዲ ጋር አዲግራት እንሔዳለን. . . መንገሻ በመሸሹ ምክንያት የተቋረጠው ጦርነት የቆመ አይመስለኝም ።

. . . ምኒልክም አንድ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግን አያውቅበትም ። ዛሬ ጦርነት ይፈልጋል በማግሥቱ አይፈልግም በዚህ መካከል እኛ አየር ላይ ተንጠልጥለን ቀረን . . . በሮማ የኛ ድል አድራጊነት ይጠበቃል. . .1

መቀሌ ከአዲግራት 115 ኪሎ ሜትር ፤ ከዓድዋ 120 ፤ ከአምባ አላጌ 74 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ የእንደርታ ከተማ ነው ። ዐፄ ዮሐንስ መቀሌን ዋና ከተማ አድርገው እስካሁን ያለውን ቤተ መንግሥት አሠርተው አድምቀውት ነበር ። አሁን ጋልያኖ መሽጎ የተቀመጠበት ቦታ ዐፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸው ካሠሩት ቤተ መንግሥት ወደ ደቡብ ምሥራቅ አለፍ ብሎ የእንዳ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ካለበት ከፍተኛ ቦታ ላይ ነው ። ከፍታው ከባሕር የመቀሌ 2062 ሜትር ሲሆን ፤ የእንዳ ኢየሱስ 2240 ሜትር ነው ። ከዓመት በፊት ከደብረ ኃይላው ጦርነት በኋላ ጀኔራል ባራቲዬሪ መቀሌ የገባለት ግማሹ ሕዝብ ካህናቱም ጭምር በውድም ፤ በግድም ተሰልፈው የተቀበሉት ጊዜ ፤ የመቀሌ ከተማ ለአላጌና ለአሸንጌ ፤ ለአዲግራትና ለአሥመራ አማካይ በመሆኑ የእንዳ ኢየሱስ ጉብታ ጠላትን ለመከላከል የሚያመች መሆኑን ተመልክቶ ሟቹ ቶዜሊ የምሽጉን ሥራ እንዲጨርስ አዞት ነበር ። ከዚያም ቶዜሊ ወደፊት ወደ አላጌ የዘመተ ጊዜ የምሽጉን ሥራ ይኸው ጋልያኖ ከአሪሞንዲ ጋር እየተቅማማ ወደ ፍጻሜ አድርሶታል ። የእንዳ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንም ለምሽጉ ሥራ እንቅፋት ስለሆነ ፤ ታቦቱን አስወጥቶ በቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ላይ ራሱ የኢጣልያ ባንዲራ ተሰቅሎበት በውስጥና በበራፉ መድፍና ጠበንጃ ተጠምዶበታል ።[2]

በራስ መኰንን የሚመራው ጦር በኅዳር 28 ቀን የአላጌን ምሽግ ከደመሰሰ በኋላ ፤ ከዚያም ለእርዳታ የመጣውን የጀኔራል አሪሞንዲን ጦር ወደ መቀሌ እያባረረ የአላጌ ጦርነት በተደረገ በሦስተኛው ቀን ወደ መቀሌ ምሽግ አቅራቢያ ደረሰ ። እንደ ደረሱም የራስ መኰንን አሳብ ሁልጊዜ በሰላም መንገድ ኢጣልያንን ከገር አስወጣለሁ የሚል ተስፋ ስለሆነ ፤ በሚጓዙበት ጊዜ እርሳቸው

1 Lettere e Diari, F. Lemmi, PP. 62-63.

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 245

ለጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ "እንደ የሚታመን ሁነኛ ሰው የኛን አሳብ ለመንግሥታችሁ ሊያቀርብ የሚችል ላክልኝ" ብለው አንድ ደብዳቤ ላኩበት ። እርሱም ለዚህ ጉዳይ የተመረጠውን መኰንን ይዞ የሚሔድ ሰው ይላኩልኝ ብሏቸው ለዚሁ ብላታ እንግዳ ተሰማ የሚባሉትን መርጠው ላኩለት ።[1]

ከዚህ በኋላ ፣ ኡምቤርቶ ፓርቲኒ የሚባለውን መርጦ ፣ ከርሱም ጋር ሙንጣዝ ሐመድ የሚባለውን ላስተርጓሚነት ፣ ሌላ ደግሞ ተራ ወታደር ላጃቢነት ልኮአቸው በታኅሣሥ 18 ቀን 1895 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ራስ መኰንን ሰፈር ደረሱ ። እርሳቸውም መልክተኛውን በደንብ ተቀብለው ስለ አነጋገሩት በጣም ደስ አለው ።

ምንም እንኳ ፣ ራስ መኰንን ዕርቁን አጥብቀው ከልብ የሚፈልጉት ቢሆን ፣ ኢጣልያኖች ደግሞ የዚህን የእርቅ ንግግር ጊዜ የሚጠቀሙበት ምሽግ ለማጠንከሪያ ፣ በዕርቁ ሰበብ በራሶቹና በሠራዊቱ መካከል ወዲያና ወዲህ በማለት ሲያጋጥማቸው የመኳንንቱን ስሜት ለማወቂያ ፣ የመሣሪያውንና የወታደሩን ቁጥር ለመገንዘቢያ ፣ የየአለቃውንና የወታደሩን ሥነ ሥርዓት አጠባበቅና የሞራሉን ደረጃ ለመገመቻ ነው ። ቲኔንቲ ፓርቲኒ ከምርኮኛው ከቲኔንቲ ስካላ ጋር እንዲጫወትና አብሮ እንዲያድር የተፈቀደለትን ጊዜ ለዚህ ለስለላና ስውይይት ነው ያደረገው ። እንደ እውነቱ ራስ መኰንን በዚህ በጦርነት ሰዓት መልክተኛው ከምርኮኛው ጋር ተገናኝቶ እንዲሰነብት መፍቀዳቸው የሚገባ ባይሆንም ፣ የራሳቸው አስተሳሰብ ምን እንደ ነበረ ለመገመት ያዳግታል ።

ራስ መኰንን ለጠቅላይ ገዥው አንድ ደብዳቤ ፣ በሐረር ሳሉ ለሚያውቁትና ስለዕርቁ ጉዳይም አነጋግረውት ለነበረው ለፒዬትሮ ፌልተር ሌላ ደብዳቤ ቲኔንቲ ፓርቲኒን አሲይዘው ላኩት ። እርሱም እነዚህን ደብዳቤዎች ይዞ መቀሌ ምሽግ ደርሶ ከዚያ ወደ አዲግራት ሔዶ ለጄኔራል ባራቲዬሪ አስረከበ ። ባራቲዬሪም በጉዳዩ ሮማ ካሉት ባለሥልጣኖች ጋር በቴሌግራም ሲነጋገርበት ሰንብቶ ወደፊት እንደምናነበው ፣ ይኸው ፌልተር ካለበት ተፈልጎ ወደ መቀሌ እንዲሔድና ከራስ መኰንን ጋር እንዲነጋገር ተወሰነ ።

ቢሆንም ፣ ፓርቲኒ አዲግራት በነበረበት ጊዜ ባራቲዬሪ ሮማ ካሉት አለቆቹ ጋር በቴሌግራም በሚወያይበት ሰዓት ከነርሱም ግልጽ ትእዛዝ ሳይመጣለት ጉዳዩ በማነህ ማነህ እየተወዛገበ ጊዜው

1 Italia ed Etiopia .. Conti -Rossini, P. 239.



ስለተራዘመ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ወደ መቀሌ የሚደርሱበት ቀን ስለተቃረበ ፣ ራስ መኰንን እንደዚሁ መጠበቅ ጉዳዩና ሁኔታው ስለ አሠጋቸው ፣ ለዚሁ በመቀሌ መሽጎ ለተቀመጠው ለማዦር ጋልያኖ ከዚህ የሚከተለውን ቁርጠኛ ደብዳቤ ጻፉለት ።

> እኔ ባንተ የሚታዘዘውን ትንሽ ምሽግ ለመውጋት አልመጣሁም ። እኛ ብዙ ስለሆንን ያንተን መድፎች ምንም አንፈራም ። አላጌን ልታስታውስ ይገባል ። በከንቱ ደም እናፍስስ ። እኔ እስከ ምጥዋ ድረስ ሸኚ ልስጥህ ። ጓዝህንም ሁሉ እዚያው ድረስ ልልክልህ እችላለሁ ።

እርሱም በበኩሉ ለዚህ መልስ ፣ "ከስፍራዬ አልንቃነቅም ፤ ጓዙንና ምሽጉን መውሰድ የፈለግህ እንደሆነ ናና ውሰድ ። በመድፍ በትር እቀበልሃለሁ" የሚል ቁርጠኛ መልስ ላከባቸው ። የጋልያኖ መልስ በአላጌ ጦርነት ቀዜማ ቶዜሊ ከመለሰው የድፍረት መልስ ጋር ተመሳሳይ ነው ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ያኛው በውጊያ ሲሞት ይኸኛው ባፄ ምኒልክ ፈቃድ ነፍሱን አድኖ ለጊዜው ከወገኖቹ ተደባልቋል ።

ራስ መኰንን ፣ ማይ መዝጊ ሆነው ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ ጽፈውት የነበረው ደብዳቤ ፣ "የአላጌው ጦርነት የተደረገው ያለኔ ፈቃድ ነው ። መጥፎ ነገር ነው የሆነው ። አሁንም የባሰውን ለማስወገድ አንድ ታማኝ ሰው ተደርጎ ጉዳዩን በሰላም እንጨርስ" የሚል ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ በዚሁ ምዕራፍ በመጀመሪያው ገጾች ላይ እንደተመለከትነው ፤ የኢጣልያ መንግሥት የአላጌን ውርደት በሌላ በማያዳግም ድል መመለስ ስለፈለገ ፣ ከዚህም ድል በኋላ ሰፊ ግዛት ማግኘት ዋናና ከሥር የተነሣበት ዓላማ ስለሆነ ካፄ ምኒልክም ፣ ከራስ መኰንንም የሚሰነዘረው የሰላም ፍላጎት የጦር አለቆቹ ካለው የበለጠ ለመዘጋጂያ ፣ ጦር ለማደራጂያ ፣ ምሽጎችን ለማጠንከሪያ ከማድረግ በቀር ሰላሙን በምንም ዓይነት አልፈለጉትም ። ዕርቅና ሰላም ቢፈልጉም የሁለቱ መንግሥታት ሰላም አፈላለግ መንገዱ በፍጹም የተራራቀ ነው ። የኛ መሪዎች ሰላም ፍለጋ የተያዘውን አገር ለማስለቀቅ ሲሆን የኢጣልያኖቹ ደግሞ ፣ "የኛ ባንዲራ መውለብለብ እስከ ጀመረበት እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ያለውን አገር እንደ ያዝን የውጫሌ ውልም እንዳለ ረግቶ መኖር አለበት" የሚል ነው ። ልዩነቱ በሌላ ታላቅ ጦርነትና ድል አድራጊነት ካልተፈታ ሌላ መፍትሔ የለውም።

እንደዚህ ያለውን ቁርጠኛ ሐሳብ የሆነውን ጉዳይ ከጦርነትና ከኃይል ሥራ በቀር የሚገላግለው መንገድ ስለሌለ ፣ ሁለቱም ወገኖች

1 L Assedio di Meccalle..,PP. 301 -341.

ባንደበታቸው ሰላምን እያወሩ ፣ "ደም በከንቱ አይፍሰስ" እየተባባሉ ላዩን ሳይሆን ውስጡን ተዋውቀው ሁለቱም ፣ በእርቅና በሰላም ፍለጋው ጊዜ እየተጠቀሙ የጦር ሠራዊታቸውን ያደራጃሉ ።

በዚሁ ጊዜ ፣ የኢትዮጵያን ሁኔታ በውቃለሁ የሚለው 12 ዓመታት ያህል ባፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ልዩ መልክተኛ ሆኖ የተቀመጠውና በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ የተነሣ ከንጉሠ ነገሥቱም ከእቴጌ ጣይቱም ተጣልቶ ወዳገሩ የተመለሰው አንቶኔሊ በሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትርነት ተሾሞ ነበር ። ነገር ግን ፣ ከሚኒስትሩ ከሲኞር ብላን ጋር ስለ አልተስማማ ፣ ወደ አርጀንቲን ተልኮ በቦኔስ አይሬስ የኢጣልያ ሚኒስትር ሆኖ ተቀምጧል ።

ከዚያም ሳለ ፣ ከአምባ አላጌ ጦርነት ወዲህ በደብዳቤም በቴሌግራምም ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ክሪስፒ ልዩ ልዩ ምክር ከመላክ አልተቆጠበም ። እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ 12 ቀን 1895 ዓ. ም. በላከው ቴሌግራም የሰጠው ምክር ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

> በልዩ ጥንቃቄና በረጋ መንፈስ ድሉ እርግጠኛ እንዲሆን ሸዎችን በትግሬ አገር ማዳከም ። አዲግራትን ትቶ አሥመራንና ከሰላን መከላከል ። ራስ ስብሐትን መጠርጠር ። በሐረር ላይ ህማች ወታደር መላክ ጠቃሚ ነው ። ከዮሐንስ ለመገላገል በምኒልክ ለመጠቀም ያደረግነውን አሁንም ከጐጃሙ ንጉሥ ማድረግ ። በድፍረቱ ይቅርታ ። አንቶኔሊ.[1]

ውስጥ ዐወቅ የሆነው አንቶኔሊ ሮማም ፣ አዲስ አበባም የነበረ ጊዜ የምኒልክን ኃይልና ድርጅት በቅርብ ከማወቅ የተነሣ በምጥዋና በአሥመራ ያሉት አገረ ገዥና የጦር አለቆች ተመቸን ብለው ወደፊት እየቀደሙ አገር መውረራቸውን አልተስማማበትም ነበር ። አሁንም በዚህ ቴሌግራሙ ምንም እንኳን የኢጣልያ ወታደር መቀሌንም አዲግራትም ደርሶ መመሸጉን ባይዘነጋውም ፣ የርሱ አስተያየት የኢጣልያ ጦር ከምዕራብ በከሰላ ፣ ከምሥራቅ በአሥመራ በደንብ መሽጐ በተረፈ ግራና ቀኝ እየተነኮሱ በመውጋት ፣ ጠላትንም ከግራና ቀኝ በማስነሣት ፣ የሸዋ ጦር በትግሬ አገር ተዳክሞ ወዳገሩ እንዲመለስና ከዚያ በኋላ ሁኔታው እየተመዛዘነ የመስፋፋቱ ጉዳይ እንዲቀጥል ነው ። ምክሩ በመጠኑ አደገኛ እንደነበረ የታወቀ ነው ። የዚህ ዐይነቱ ዓላማ በመቶ ሺ የሚቆጠር ሠራዊት ሳስከተሉት ንጉሠ ነገሥት በትግሬ ለረዥም ጊዜ በሚቆዩበት ሰዓት ፣ በስንቅ ማለቅና በሌላውም ችግር ውስጥ እንዲገቡ አስቦ ነው ።

ነገር ግን ፣ በማናቸውም ረገድ ኢጣልያኖቹ የአላጌን መሸነፍ እንደ ውርደት ስለ ቆጠሩት ፣ ለዚህ በቀል አንድ የድል ብድር

1 La Prime Guerra d' Africa, Crispi, 394



በቶሎ ካልመለስን ብለው ጦርነቱን በትጋት ከማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ ። በቅርብም በሩቅም ያለ መካር ከዚህ ዓላማ ሊመልሳቸው አልቻለም ። የአላጌ ጦርነት ውጤት እንደ ተሰማ በሮማ ምክር ቤቱ ተከፍቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ የሚደረገውን ጦርነት በደንብ ለመምራት ፣ የአላጌውንም ብድር በደንብ ለመመለስ የሚያስችል ሐያ ሚሊዮን ሊሬ በጀት እንዲፈቀድለት ጠየቀ ። የቅኝ አገር ወረራን ከሚቃወሙት መማክርት ዓይነተኛው ኢምብሪያኒ የሚባለው በዚሁ ጉዳይ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር የጋለ ክርክር አደረጉበት ። "ይኸ ሐያ ሚሊዮን ከወዴት ይመጣል... በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ ፣ ሌላ ሐያ ሚሊዮን መጠየቃችሁ አይቀርም . . . ክሪስፒ ሐበሻን የቁማር ግዛት ለማድረግ ሲፈልግ ነገሩን የጨዋታ ነገር አድርጐታል ። ሌላ መሸነፍ እንደሚደርስብን አስታውሱ . . . ." ብሎ በድፍረት ሲናገር ፣ ከቀኝ ክፍል ታላቅ የታቃውሞ ሁካታ ደረሰበት ። አነጋገሩ ጓደኞቹን እነካቫሎቲንና እነዲሩዲኒን ሲያስደስት ፣ የቀኝ ክፍሎችን የበለጠ ያናደዳቸው ፣ "ከአላጌ መሸነፍ በኋላ ካላረፋችሁ ሌላ መሸነፍ ይደርስባችኋል" ሲል በድፍረት የሰነዘረው ቃል ነው ።[1]

ስለዚህ ፣ በዚህ ጊዜ ከሥልጣን ላይ ያሉት የነክሪስፒ ወገኖች በውጭውም ፣ በምክር ቤቱም ውስጥ ስለ በረከቱ የጦርነቱ ጉዳይ ከመቀጠል አላቋረጡም ። የብልሁ የምክር ቤት አባል የኢምብሪያኒ ትንቢትም ወደፊት እንደምናነበው በትክክል ይደርሳል ።

1 Abissinia - Ed. Scarfoglio. PP. 183 - 184.

# ምዕራፍ ሠላሳ

## የንጉሠ ነገሥቱ ጦር አሰፋፈር — በመቀሌ ምሽግ የመጀመሪያው ጦርነት

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በታኅሣሥ 28 ቀን የገናን በዓል በጨለቆት ካሳለፉና በ29 መቀሌ ደርሰው ከነራስ መኰንን ጋር ከተገናኙ በኋላ ፣ ከመቀሌ ከእንዳ ኢየሱስ ምሽግ የተተኰሰ የመድፍ ጥይት ከማይደርስበት ሥፍራ ሰፈሩ ።በመቀሌ ምሽግና እርሳቸው በሰፈሩበት ሥፍራ መካከል 6500 ሜትር ስለሆነ ፣ በዚያን ጊዜ በኢጣልያኖቹ እጅ ያለው የመድፍ ጥይት የሚሔየደው ፫ ኪሎ ሜትር 850 ሜትር ብቻ ስለሆነ ፣ የሰፈሩ ጉዳይ በጥናት እንደ ተደረገ ያስታውቃል ። እንዲያውም በዚህ ጊዜ ከፈረንሳይ አገር ተገዝቶ የመጣውና በኢትዮጵያውያኑ እጅ ያለው የመድፍ ጥይት እስከ 4500 ሜትር ድረስ ሔዶ ስለሚመታ ፣ የመድፉ ዓይነት ከኢጣልያኖቹ የኢትዮጵያውያኑ ይሻላል ማለት ነው ።[1]

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በመቀሌ እንደ ደረሱ ምሽጉን ባንድ የጦር ክፍል አስከብበው እርሳቸው ግን መቀሌን አልፈው 110 ኪሎ ሜትር ድረስ ተጉዘው ዋናው የኢጣልያ ጦር ተከማችቶ ወደሚገኝበት ወደ አዲግራት ሔደው ለማጥቃት ሊሞክሩ ይችሉ ነበር ። ነገር ግን በአላጌ እንደሆነው ይኸንንም በመቀሌ የመሸገውን ጦር በሙሉ እየጠረግሁ አልፋለሁ በሚል ስሜት ፣ "እነዚህን ጣልያኖች ከጉድጓዳቸው* ሳላስወጣ ወደ ግራም ወደ ቀኝም አልል" ብለው በዚያው ሰፈሩ ።

እንደዚሁም ጀኔራል ባራቲዬሪ የአላጌን መሸነፍ ከውርደት ቆጥሮ አዲስ የድል ብድር እመልሳለሁ እያለ በሚመኝበት ጊዜ ፣ የገዛ ጦሩ መቀሌ ላይ ተከቦ ሲጨነቅ ከአዲግራት ገሥግሶ በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራውን ጦር ለመግጠም ጉልበቱን አልተማመነውም ። በዚህ ምክንያት ጋልያኖ ፎከሮ ፣ "በመቀሌ ቀርቼ ያገሬን ባንዲራ እከላከላለሁ

---

1 Italia ed Etiopia, Conti - Rossini,P. 248; The Campaign of Adwa and the Rise of Menelik, G.F.H.Berkeley, Chap. Vl, PP. 178 -216

* ከምሽጋቸው ለማለት ነው ።

እንዳለው ዕድሉ ያውጣው” ብሎ ባራቲዬሪ አዚያው አዲግራት ምሽጉን እያጠነካከረ ተቀመጠ ።

ስለዚህ ፣ ዐፄ ምኒልክ ጦራቸው መቀሌ ደርሶ ሰፈሩን ተከፋፍሎ ከያዘ በኋላ ፣ በምሽጉ ዙሪያ ራቅ እያለ ከዚህ እንደሚከተለው ሰፈረ ። ከምሽጉ በምዕራብ በኩል በደብሪ የሸዋ ጦር ፣ በምሥራቅ በኩል የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የራስ መንገሻ ዮሐንስ ጦር ፣ በጋምቤሳ በኩል የራስ መንገሻ አቲከም ፣ የራስ ወሌ ፣ የደጃች ወልዴ ጦር ፣ ወደ ጩለቆት በሚወስደው መንገድ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ፣ የራስ መኰንንና የፊታውራሪ ገበየሁ ጦር ፣ ጦሩ በዚህ ዐይነት ከሰፈረ በኋላ ፣ ስለ ጦርነቱ አጀማመርና አመራር በስፍራው የነበሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሚከተለውን ጽፈዋል ።

> ድንኳን በሚተከልበትና ጭነት በሚራገፍበት ጊዜ አንድ በቅሎ ፈርጦ ወደ ኢጣልያኖቹ ሰፈር ሮጠ ። አንድ ሰው ሊመልሰው ሲሮጥ ባዩ ጊዜ ኢጣልያኖቹ የመድፍ ተኩስ ዠመሩ ። ኢጣልያኖቹ አብዝተው መተኮሳቸውን ንጉሠ ነገሥቱ በተመለከቱ ጊዜ ፤ ሊቀ መኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን ሒዱ እናንተም ተኩሱባቸው ብለው አዘዙና የምሽቱ ጊዜ በመድፍ ተኩስ አለፈ ። ወደ ማታ ንጉሡ እንደገና ሊቀ መኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን ጠርተው ፣ “እነዚህን ኢጣልያኖች ከጉድጓዳቸው ሳላስወጣ ወደግራም ወደቀኝም አልሔድም ፤ እናንተም የጠላት መድፍ ጥይት የማይደርስበትን ሥፍራ መርጣችሁ ከዚያ ሆናችሁ ምሽጉን በመድፍ ምቱት ” ።

ብለው አዘዙዋቸው ።

ካሉ በኋላ ፣ ሊቀ መኳስ አባተ ጦራቸውን ይዘው በምሽጉ በስተግራ የኢጣልያኖቹን ቃፊር ጠባቂ አባርረው ምሽግ አበጅተው ፣ መድፍና መትረየሳቸውን እንደ ጠመዱ ፣ በጅሮንድ ባልቻም በስተቀኝ በኩል እንደዚሁ ሌሊቱን ተገን (ምሽግ) ሠርተው መድፍና መትረየሳቸውን ጠመዱ ። ኢጣልያኖቹም የኢትዮጵያኖቹን መጠጋት ባወቁ ጊዜ የመድፍና የጠመንጃ ተኩስ አበረከቱ ። አነጣጥሮ በመተኮስ የተመሰገኑት ሊቀ መኳስ አባተም ፣ በሩቅ በሚያሳየው መነጽራቸው ታቦቱን አውጥተው የያዙትን የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተመልከተው አስተካክለው ቢተኩሱ ፣ የመድፉ ጥይት በመስኮት ገብቶ ያንዱን መድፍ እግር ሰባበረው ፤ ኢጣልያኖቹም ከተበላሸው መድፋቸው ላይ ጭስ መነሣቱን ባዩ ጊዜ እየተኮሱ የመድፍ ጥይት ሊቀ መኳስ አባተና በጅሮንድ ባልቻ ባሉበት ቦታ ላይ እንደ በረዶ አወረዱባቸው ። ነገር ግን አንድም ሰው አልቆሰለም ። . . .በዚህ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፣ ከድንኳናቸው ወደ ላይ ካለው ከፍተኛ ስፍራ ላይ ሆነው የመድፉን ውጊያ በመነጽር ሲመለከቱ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የቀሩት መኳንንትም እንደ ርሳቸው ያዩ እንደነበረ ጸሐፊው ዘርዝረውታል ።



ከዚሁ አያይዘው ፣ እቴጌ ጣይቱም የድንኳናቸውን መጋረጃ ገልጠው ሲመለከቱ ፣ በእርሳቸው አጠገብ አዛዥ ዘአማኑኤል ቆመው ስለነበረ እቴጌይቱ ወደርሳቸው ፊታቸውን አዙረው ፣ “ሒድና ከሊቀ መኳስ አባተ እየተመካከርህ ምንጩን ለመያዝ ትችል እንደሆነ ሞክር” ብለው አዘዙዋቸው ። እሳቸውም ሒደው እንደ ታዘዙት ከሊቀ መኳስ አባተ ጋር ቢነጋገሩ ሊቀ መኳሱ ፣ “የምንጩ ሥፍራ ጥልቅና ወደ ኢጣልያኖቹ ምሽግ የቀረበ ነው ። በምንጩና በምሽጋቸው መካከል አንድ መቶ ሃምሳ ክንድ የሚሆን እርቀት አለ ። ቢሆንም መተላለፊያውን በመድፍ ሳስጠብቅ ቆይቼ ፣ ሌሊት ሲሆን ወታደር ልኬ ምንጩን አስይዛለሁ” ብለው መለሱላቸው ። አዛዥ ዘአማኑኤል ይኸን መልስ ከሊቀ መኳስ አባተ ተቀብለው ለእቴጌይቱ ቢነግሩዋቸው ፤ በጣም ደስ እንደ አላቸውና ነገሩንም ለዐፄ ምኒልክ እንደአመለከቷቸው ፣ ንጉሡም “መልካም ነው” ብለው ስለመለሱ እቴጌ ለወታደሮቻቸው ፣

> እስካሁን ድረስ እምሽጉ ውስጥ ገብተን ለመዋጋት ደስታችን ነው ትሉ ነበር ። ነገር ግን ወደ ምሽጉ ገብቶ ለመዋጋት እንደዚህ ለበዛችሁት ጦር የምሽጉ መንገድ ጠባብ ስለሆነ ፣ ከኢጣልያኖቹ መድፍና ጥይት የበለጠ እርስ በርሳችሁ ትገዳደላላችሁ ። ስለዚህ ሒዳችሁ ጣልያኖቹ ውሀ እንዳይቀዱ ምንጩን ጠብቁ እናንተም እስካሁን እምሽግ ገብተን እንዋጋለን የምትሉት የሚዳን ጦርነት እንደማትፈሩ ተስፋ አለኝ ። በዚህ ጦርነት ተዋግተው ለተረፉት ደስ የሚያሰኝ የክብር ሽልማት እሰጣቸዋለሁ ፤ ለሞቱትም ተዝካራቸውን አወጣላቸዋለሁ ፤ ልጆቻቸውንም አሳድግላቸዋለሁ ፤ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን ”

ብለው እንዳሰናበቷቸው ዘርዝረዋል ።

እቴጌይቱ በዚህ ንግግር ካሰናበቱዋቸው በኋላ ፣ ወታደሮቹ የጦር መሣሪያቸውን በደንብ አዘጋጅተው እንደ ተቆጣ ነብር መስለው ከቀኑ በ11ኛው ሰዓት ወደ ምንጩ ተጓዙ ። እቴጌም ሌሊቱን ሙሉ ፣ “አምላኬ ሆይ አታሳፍረኝ እርዳኝ” እያሉ ሲጸልዩ ሲያዝኑ አደሩ ። 11 ሰዓት ሲሆን እላይ እንደ ተባለው ፣ ገብረ ጊዮርጊስ ድልነሤና ሸዋዬ የሚባሉት አሽከሮች ተነሥተው በነርሱ ውስጥ ለየአንዳንዳቸው የሚታዘዝ ሦስት መቶ ባለጠመንጃ ወታደር ይዘው ወደ ምንጩ ከሔዱ በኋላ የሚተኩሱበትን ምሽግ እንደ አበጁ ጸሐፌ ትእዛዝ በደንብ አብራርተውታል ።

ከዚህም አያይዘው ፣ ኢጣልያኖቹ ምንጩ ወደ ምሽጉ በመቅረቡ ምክንያት አበሾች መጥተው ይይዙታል ብለው እንደ አላሰቡ ፣ ነገር ግን ባወቁ ጊዜ ሐሙስ ከማታው በሦስት ሰዓት መድፋቸውን እየጐተቱ ወጥተው ባለጠመንጃዎች ጭምር ምንጩን በሚጠብቁት

ላይ በድንገት ደርሰው ውጊያ እንደ ገጠሙዋቸው ፣ ጠባቂዎቹም ጠንከረው ከመዋጋታቸው የተነሣ ጣልያኖቹ ወደ መጡበት መመለስ ግድ እንደ ሆነባቸው ፤ በማግሥቱ ሊቀ መኳስ አባተ ከበጅሮንድ ባልቻ ጋር ተስማምተው ጣልያኖቹ ያሉበትንና መድፋቸውን የጠመዱበትን በመነጽር ተመልክተው በመድፍ መቱት ። ጣልያኖቹ ጓዛቸውን መድፍ ወደማይደርስበት ቦታ እንደ አዛወሩ ፤ ሊቀ መኳስ አባተ በምሽግ ያሉትን በጥብቅ እየጠበቁ ፣ ወዲያና ወዲህ ሲሉ በመድፍና በመትረየስ እየመቱ ጣልያኖቹ ምሽጉን እስኪለቁ ድረስ ሳይተኙና ከመሣሪያቸው ሳይለዩ ሰነበቱ ። በዚህ ሳምንት ሊቀ መኳስ አባተ የሠሩትን ማንም ሊሠራው እንደማይችል ፣ እቴጌ ጣይቱም በየቀኑ ከሌሊቱ ከዘጠኝ እስከ ዐሥር ሰዓት ድረስ ውሃውን ለሚጠብቁ ወታደሮች ብዙ መጠጥ የያዘ ቀንድና በመሶብ እንጀራ ሥጋም እየጨመሩ ይልኩ እንደነበር ፣ የጦር ወታደሮቹም እየበሉ እየጠጡ ሕይወታቸውን ላገራቸውና ለንጉሣቸው ለመሠዋት ሲሉ ፣ አንድ ቀንም መሣሪያቸውን ትተው ሳይተኙ ጠላት ውሃ እንዳይወስድ እየተከላከሉ ቆይተው ፣ በመጨረሻው ምሽጉን እስከ ማስለቀቅ መድረሳቸውን በሚገባ ገልጠውታል ።[1]

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በዚህ ጽሑፋቸው እቴጌ ጣይቱ ፣ ከመኳንንቱ ሊቀ መኳስ (ራስ) አባተ ፣ በጅሮንድ (ደጃዝማች) ባልቻ ፣ ከወጣት ሹማምንት ገብረ ጊዮርጊስ ፣ ድልነሤና ሸዋዬ የሚባሉትን ጉበዛዝት አዘው በእንዴት ያለ አኳኋን የመቀሌን ጦርነት እንደተካፈሉ ያሳዩናል ። ከሁሉ በበለጠ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የመቀሌን ምሽግ ለማስለቀቅ ሊቀመኳስ አባተ ዐሥር ቀን ሙሉ ያለ ዕረፍት ምሽጉን እየተቆጣጠሩ የኢጣሊያ ወታደር ከሰፍራው ሲነቃነቅ በመድፍና በጥይት እየመቱ ጠላትን ዕረፍት እንዳሳጡት አሳይተውናል ። የርሳቸውም አጻጻፍ ይነስ ይብዛ ጣልያኖቹ ከጻፉት ጋር ይገጥማል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ...ምዕ. 62 ፣ ገጽ 242-249 ።



# ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

## በመቀሌ ምሽግ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ጦርነት—ምሽጉን በሰላም ለማስለቀቅ የተደረገ ስምምነት

በመቀሌ ምሽግ በተደረገው ጦርነት ፣ ሊቀ መኳስ አባተና በጅሮንድ ባልቻ ከሌሎች መኳንንት የበለጠ እንደ ተካፈሉ ባለፈው ተመልክተናል ። በምሽግ ውስጥ ያለው ጦር ያለውሃ መኖር እንደማይችል በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ ፣ "ለሚሞተው ተዝካሩን እወጣለሁ ፤ ልጁን አሳድጋለሁ ፤ ዠግንነት ሠርቶ ለተረፈው ሽልማት እሸልመዋለሁ" ብለው አበረታትተው ፣ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው ሦስት መቶ ነፍጠኛ የሚታዘዙእቸውን ድልነሤን ፣ ሸዋዬን ፣ ገብረ ጊዮርጊስን እንደ ምንም ብለው ፣ ምንጩን እንዲይዙ እንደ ላኩዋቸው ፣ እነዚህ ሦስት ወጣት የልፍኝ የበታች ሹማምንት መሆናቸው በታሪካዊው መጽሐፍ ተመልክቷል ።

በመቀሌ ምሽግ አቅራቢያ የሚገኙት ምንጮች ሦስት ናቸው ። አንዱ ከምሽጉ በስተምሥራቅ በጣም ራቅ ያለ ነው ። ሁለተኛው በስተሰሜን በኩል ያለው ነው ። ሦስተኛው በስተደቡብ በኩል ያለው ሲሆን ፣ ለምሽጉ የሚቀርበውና ሁለቱም ወገኖች ባለቤት ሆነው ይዘው ጦርነቱን ለመቀጠል የፈለጉት በደቡብ በኩል ያለውን ነው ። እንደ ኢጣልያኖቹ አጻጻፍ ፣ ይህ ውሃ ርቀቱ ከምሽጉ 400 ሜትር ያህል ነው ። ሊቀ መኳስ በግምት 150 ክንድ ያሉት ይኽንኑ መሆን አለበት ። እነሸዋዬ ሌሊቱን አድፍጠው ምሽጉን ከያዙ በኋላ ፣ በዚያ ሌሊት እጅ በእጅ አፈር በመቆለልና ካብ በመካብ ምሽጋቸውን በጣም አጠንክረውት ስለነበረ ፣ ሲነጋ ኢጣልያኖቹ ከምሽጋቸው ቢተኰሱ እነዚህ ለተተኰሱ የተኰስ መልስ በመስጠት ሊበገሩ አልቻሉም ።

እ. ኤ. አ. ጥር 9 ቀን ለዐሥር አጥቢያ ጣልያኖች ሌሊቱን በሰባት ተኩል ፣ በስምንት ተኩል ፣ በዐሥር ሰዓት ተሩብና በዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ እየወጡ በመዋጋት ምንጩን ለማስለቀቅ ሞክረው በኛዎቹ ጥብቅ ተከላካይነት ሳይሳካላቸው ስለቀረ ፣ ሁሉም ወደ የምሽጋቸው በመሸሽ ተመልሰው ገቡ ። ከዚህ በኋላ በኢጣልያኖቹ ዘንድ ምክር ተይዞ ፣ "እንግዲህ እዚሁ በፊተኛው ቀን በምሽጉ

ውስጥ የያዝነውን ለነጩም ፤ ለጥቁሩም ወታደር ለሴቱም ለሕፃናቱም
ለከብቱም በድርጎ ወሃ እየቆጠብን እየሰጠን እንጠጣ ። ይኸንንም
እየተቆጣጠረ የሚያስፈጽም አንድ ሹም ይደረግ ። የያዝነው ወሃ
አልቆ ካልቸገረን በቀር ትርፉ ሰው ማስጨረስ ስለሆነ ፤ ሁለተኛ ወጥ
ተን ምንጭ ለማስለቀቅ አንዋጋም” ሲሉ በምክር ወስነው የኢትዮ
ጵያ ጦር ወደ ምሽጉ እየተቃረበ እንዳያጠቃ ወይም አዘንግቶ ባንደ
ኛው ግንባር እንዳይገባ በምሽጋቸው ዙሪያ ቁጥቋራቸውን በጣም
አጠበቁ ። ቀድሞውንም ቢሆን ዙሪያውን ካብና አሸዋ የሞላባት ከረ
ጢት ተደርጎ በዚያም ላይ መድፈኛው መድፉን ፤ ነፍጠኛው ጠመን
ጃውን አልቦ በተራ እየተቀያየረ ሁሉም ወደ ኢትዮጵያውያን ሠፈር
ዐይኑን አፍጦ ይጠባበቅ ነበር ።

ቪኮ ማንቴጋዛ የተባለው ጸሐፊ ፤ ባለፈው እንዳልነው እ.ኤ.አ
ጥር 9 ቀን ለ 10 አጥቢያ በደቡብ በኩል ኢጣልያኖቹ ወጥተው
ለመዋጋት ሞክረው የነበረው ሳይሳካ መቅረቱን ፤ በሰባት ተኩል ፤
በስምንት ተኩል ፤ ባሥር ተሩብ ፤ በዐሥራ አንድ ተኩል ጣልያኖቹ
ወጥተው የተዋጉ ጊዜ ባንደኛው ጦርነት ሁለት ጊዜ መድፍ ተተ
ኮሰ ። ያንደኛው መድፍ ጥይት በኢጣልያኖቹ መድፍ አፍ ገብቶ እን
ደሰባበረው ይገልጻል[1] ። ይህ መድፍ በማይጠረጠር ከሊቀ መኳስ
አባተ የተተኮሰ መሆን አለበት ። በዚሁ ምክንያትም ፤

“አባተ አባ ይትረፍ ነገረኛ አዋቻኪ ሰው
ይኸን መድፍ ከዚያ መድፍ አቆራረጠው”

ተብሎ እንደ ተገጠመላቸው በገሃድ ተነግሯል ።

በዚሁ ጊዜ ፊልተር የሚባለው ፤ ከኢጣልያ አገር የተነሣው
የኢጣልያ ጦር ውስጡን አዲግራት እስኪደርስ ድረስ ጊዜ ለማግኘት ፤
ላዩን ሁለቱን መንግሥታት ለማስታረቅ በራስ መኰንን ጥሪ መጥቶ
ነበርና ፤ ይኸው ፊልተር በንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር በነበረበት ሰዓት
ባንደኛው ግንባር የኢጣልያ ወታደሮች ከምሽጉ ውስጥ እየተኮሱ ብዙ
ሰው አጠቁ ። ዐፄ ምኒልክ ራስ መኰንንን ተቆጥተው በሐረር ጦርና
ምሽጉ ውስጥ ባሉት ኢጣልያኖቹ መካከል እ. ኤ. አ. ጥር 11 ቀን
1896 ስለ ተደረገው ጦርነት ፤ ከዚህ በፊት በዕርቅ ሰበብ መጥቶ
የነበረው በለጠው ራፖር እንደሚለው ፤ ሲነጋጋ በሰሜንና በምሥ
ራቅ በኩል ባለው መወጣጫ ላይ ትልቅ ጦርነት ተዠመረ ። ጦርነ
ቱም በመትረየስ ጭምር ስለነበር በተከላካዮቹ ላይ ጉዳት አደረሱ።

[1] In uno di essi la batteria nemica situata ad Inda Jesus sparo due colpi une dei quali imbocco una cannonier e cannonier danni in batteria, P. 258.



በጣም ተጭነው ጉዳት እንደሚያደርሱ ቢታወቅ ጣልያኖቹ ወደፊት
ቀደም ብለው ተጠምደው የነበሩትን መድፎች እየፈታቱ በትከሻ
እየተሸከሙ ወደ ውስጥ አገቡዋቸው ። ጦርነቱ እስከ 11 (5) ድረስ
ከቆየ በኋላ ፤ እንደገና በ12 እና በ13 (6—7) ሰዓት ተፋፍሞ
ከሁለቱም ወገን ጉዳት ደርሶ ሳለ ኢትዮጵያውያኑ ወደኋላ አፈገፈጉ።
ጣልያኖቹም ሊያባርሩዋቸው አልቻሉም ።

በበኩሉ ማንቴጋዛ የሚባለው ፤ ሸዎቹና ትግሬዎቹ ብዙ ሰው ቢያ
ልቅባቸው በዚህ ቀን ምሽጉን ለመውረር ቁርጠኛ ሆነው ብዙ አደጋ
በጣልያኖቹ ላይ ባደረሱ ጊዜ ፤ ምናልባት ሐበሾቹ ወደ ውስጥ ለመግ
ባት ቢከናወንላቸው ምሽጉን በቦምብ ለማፈራረስ ዋናው አዛዥ
አስቦ ነበር ። ነገር ግን ፤ ኢጣልያኖቹ አስተካክለው በሮምታ ተኩ
ሰው ብዙ ጠላት ፈጅተው የተጠመደውንም መድፉቸውን ባፈራረሱ
ጊዜ ባንዶቹ ጠመንጃቸውን ወደ ላይ ሰቅለው በመጨፈር ደስታ
ቸውን እንደ ገለጹ ፤ ከዚያም ጨለማው ገላግሎ ሐበሾቹም ስለሸሹ
ጨለማውን ተገን አድርገው ያገር ተወላጅ ወታደሮች ከምሽጉ ወጥ
ተው ሐበሾቹ ወደ ምሽጉ አጠገብ ቀርበው ከተዋጉበት ቦታ ጠመን
ጃና ጥይት ፤ ጋሻም ሌላም ዕቃ አግኝተው ወደ ውስጥ ማግባታቸውን
ይገልጻል ። ይኸው ጸሐፊ ከዚህ አያይዞ ይኸን ትንሽ ጦር ይዞ ጋል
ያኖ አበሾቹን ከምሽግ ወጥቶ እያሳደደ ለመውጋት ባለመቻሉ መጸጸ
ቱን ፤ አበሾቹም በኃይል ወደ ምሽጉ ገብተው ለማሸነፍ ባለመቻላ
ቸው እየተናደዱ ከእንግዲህ ወዲህ በምሽጉ ያለውን ጦር በረኃብና
በጥም ብቻ እናሸንፈዋለን የሚል አሳብ እንደ ወሰኑ ያረጋግጥና በዚህ
ቀን ጦርነት ሁለት የካፖራልነት (10 አለቆች) ማዕረግ ያላቸውና
አምስት ያገር ተወላጆች ሲሞቱ ፤ አንድ ጣልያንና ሐያ አራት ባንዶች
መቁሰላቸውን ያመለክታል ።[1]

በዚህ የጦርነት ጊዜ ሁሉ ፤ አስታርቃለሁ ብሎ የመጣው ፊልተር
በንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር ነበርና ልለ ጦርነቱ ከኛ በኩል ያለው የጽ
ሑፍ ሰነድ ደካማ ስለሆነ ፊልተር የሚለውን ማንበቡ ይጠቅማል ።
ይህ ፒየትሮ ፊልተር የተባለው የኢጣልያ ተወላጅ ብዙ ዘመን በሐ
ረርጌ ቢየኒፊልድ ለሚባለው ለቡና ንግድ ማኅበር ወኪል ሆኖ በተ
ቀመጠበት ጊዜ ከራስ መኰንን ጋር ተዋውቆ ነበር ። የኢጣልያ መን
ግሥትም ፒየትሮ ፊልተርን ከቺዛሬ ኒራሲኒ ጋርም ፤ ብቻውንም ሆኖ
ከራስ መኰንን ጋር ወዳጅነቱን እንዲያጠና ፤ እርሳቸውም ከዐፄ ምኒ
ልክ ሸፍተው የሚለዩበትን መንገድ ሁሉ እንዲፈልግ ታዞ የነበረው
መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

[1] L' Assedio di Macalle - V. Mantegazza, PP. 275 - 380; The Campaign of Adwa and The Rise of Menelik - Berkeley' Chap. VI-VII.

በኢጣልያ ላይ የጦርነት ዐዋጅ ከታወጀ በኋላ ፡ ይኸው ሰውዬ በ1888 ዓ.ም. በመስከረም ወር ከሌሎቹ የኢጣልያ ተወላጆች ጋር ሐረርን እንዲለቅ ታዞ ባሁኑ ሰዓት በዘይላ ይገኝ ነበር ። ስለዚህ ፌልተር በቴሌግራም ከዘይላ ተጠርቶ ወደ አዲግራት ሔደና ከጄኔራል ባራቲዬሪ ጋር ተገናኘ ። ከዚያም ተልኮ ከሁለት የእጋሜ ሹማምንት ጋር ወደ መቀሌ መጣ ። የኢጣልያ ጦር ከኢጣልያ እስኪደርስ በሐሰት ስለ ዕርቅ እንደምን እንደ ተነጋገረና የመጣበትን ጉዳይ እንደምን አፍጻሚ እንዳደረሰ ራሱ ፌልተር ከዐደዋ ድል በኋላ ተጠይቆ ለመንግሥቱ በጽሑፍ ካስረከበው ሪፖርት ውስጥ ከዚህ እንደሚከተለው ዋና ዋናውን የአማርኛውን ትርጉም እንመልከት ።

መስከረም 23 ቀን ከሌሎች ጋር ሐረርን ለቅቄ ወደ ባሕር ጠረፍ ሔድሁ ። በዚሁም ጊዜ ራስ መኰንን በንጉሠ ነገሥቱ ጥሪ ከሐረር ወደ ሸዋ ሔዱ ። አስተድሮ የኛ ወረራ በትግሬ የሚቆምበትንና ወሰ የሚተርፍበትን ጠይቀውኝ ነበር ። እኔም ምንም እንኳን ውል ለመዋዋል ከመንግሥቱ ባልታዘዝም የውሉን አለመቅረት* እንደገና ለአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ቢገለጹ እንደዚሁም የኢጣልያ ጦር እስካሁን የያዘውን አገር እንዲያዝ እንዲፈቅድለት ንጉሠ ነገሥቱ ቢፈቅዱ ይሆናል ብዬ በመልእክት ተነጋገርን ጉዳዩ ፍሬ ሳያገኝ እንደዚሁ ቀረ . . . ከዚያ በ6 ታኅሣሥ (እ.ኤ.አ.) ከዘይላ ተነሥቼ በ12 አዲግራት በደረስሁ ጊዜ የአምባ አላጌ ግጥሚያ ተፈጽሟልና ምንም ለማድረግ አልተቻለም ። የሆነ ሆኖ ፡ ከያለበት ሠራዊት እስኪሰበሰብ የምንጠብቀውም ጦር ከሮማ እስኪደርስ 20 ቀን ያህል ጠላት ጊዜውን በከንቱ የሚያጠፋበትን መንገድ ፈልጌ እንዳገኝ አገረ ገዢው ቢጠይቁኝ እፈትናለሁ ብዬ መልስ ሰጠሁት ።

ይኸን ካለኝ በኋላ ደግሞ ፡ ባራቲዬሪ እንደገና የምጠብቀው ጦር የሚደርሰው በጥር 3 ነውና በ20ኛው ቀን ላይ 15 ቀን ጊዜ እንዲጨመር አድርገው ብሎ አገረ ገዢው ለመነኝ ። በዚህ ዓይነት ከአዲግራት ሐጂ አጉላዕ በደረስኩ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ሰፈር ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መድረሳቸውን ሰማሁ ። በኛ ዘንድ ግን ፡ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ስለሸፈቱ ዐፄ ምኒልክ ሊወጓቸው ሔዱ ተብሎ ታምኖ ነበር ። ይኸንን ወሬ ለጠቅላይ አገረ ገዢው አስረዳሁ ። በጥር 6 ቀን ራስ መኰንን ሰፈር ደረስሁና በደህና ተቀበሉኝ ። ወዲያውም ሐረርኔ የተነጋገርነውን የዕርቅ ነገር እንደምንነው ቢሉኝ ፡ የአምባ አላጌ ነገር በኛ ወገን ሁኔታውን አባብሶታል ። ቢሆንም እንደዚያው የተነጋገርነውን መውረት በማድረግ ውሉን መዋዋል ሳይቻል አይቀርም አልሁዋቸው ። ወዲያው ይኸንኑ ለመንገር ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሔደው ምክር ተያዘና የትግሬ ግዛት ከአልተለቀቀ ውጊያው መቀጠል አለበት የሚል ውሳኔ ተደረገ ። ቢሆንም ራስ መኰንን በራስ ሚካኤል እየተረዱ የመቀሌው

* የውሉን አለመቅረት የሚለው የውጫሌን ውል 17ኛውን አንቀጽ ጭምር ማለቱ ነው ።



ምሽግ እንዳይወጋ ወደፊትም የኢትዮጵያ ጦር ከመገሥገሥ የሚዘገይበትን ሁኔታ ተነጋግረው ጨረሱ ። ከዚህ በኋላ ወደ ዋናው ምክር ቤት ቀርበህ ተነጋገር ቢሉኝ ፡ እኔ መቼም በደንብ አሳብ ለአሳብ እየተለዋወጥሁ ለመዋዋል የመኰንንነት ሥልጣን የለኝም ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ የሚፈልጉትን ለይተው በደብዳቤ ጽፈው ቢሰጡኝ ለበላይ ላደርስ እችላለሁ ብዬ መለስሁ ። ራስ መኰንንም እስቲ የሚቻለኝን አደርጋለሁ ብለው እሥፈራቸው ትተውኝ ሔዱ ። ከአምባ አላጌ ጦርነት የተማረከው ቴኔንቲ ስካላ ከኔ ጋር ሆኖ እንዲጫወት ፈቅደውለት ነበር ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ በምሽጉ ባሉት ጣልያኖች ያሉት ወታደሮች ተጠግተው እንዳይዋጉ የሚከለክሉ እንደ ፖሊስ ያሉ የራስ መኰንን ዘበኞች ነበሩ ። ዳሩ ግን ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከደረሱ ጀምሮ ባንዳንድ ክፍል ያሉ ወታደሮች መተኮሳቸው አልቀረም ነበር ። በጥር 7 ቀን የባሰ ነገር ሆነ ። ከንጉሠ ነገሥቱ አንድ የጦር ክፍል ትእዛዝ ሳይቀበል የመቀሌን ምሽግ ዝም ብሎ ወጋው ። ነገር ግን እምሽግ ያሉ ኢጣልያኖች በቀላሉ ወግተው መለሷቸው ። ከጠላት (ኢትዮጵያ) ወገን ብዙ ሰው አለቀ ። ይኸን ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ክፉኛ ተቆጡ ። እቴጌ ጣይቱና ወገኖቻቸው ተናደው ራስ መኰንንን በገሃድ ከሰሱዋቸው ። ወዲያው ምክር ተያዘ በምክሩም ውስጥ ራስ መኰንን ተገለሉ ። ከዚህ በኋላ አቡነ ማቴዎስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባሉበት ንጉሠ ነገሥቱ ራስ መኰንንን ጠርተው ፡ "ከኢጣልያኖች ጋር ተስማምተሃል ኰሎኔል ጋሊያኖ ምሽጉን እስኪሠራ ጊዜ ሰጠኸው ። እኔ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያልኩትን (ፌልተርን) በሰፈርህ አስቀምጠኸዋል" ብለው እንደከዳተኛ ወቀሷቸው ። ራስ መኰንንም "እምነቴን ለመግለጽ ምን ማድረግ ይገባኛል" ቢሉ ፡ "በል አንተው ጊዜ ሰጥተህ የመቀሌን ምሽግ እንዳስመሸግኸው አንተው ራስህ ተዋግተህ አስወጣ" አሏቸው . . . በኔም ዘንድ ትእዛዙ ከማን እንደመጣ አይታወቅም በዙሪያዬ ዘበኛው ተጠራ ቴኔንቲ ስካላም አስተርጓሚዎቼንም ሁሉ ከኔ አራቁዋቸው . . .

ከዚህ በኋላ ፡ ከጧቱ በ11 ሰዓት የመቀሌን ምሽግ መውጋት ተጀመረ ። ወደ ተራራው የተጠጉትን ቡድኖችና ወታደሮች በምሽጉ ውስጥ ያሉት የኛ ወታደሮች ፈጁዋቸው ። ራስ መኰንንም ራሳቸው ራስ አሉላ በጉናቸው ሆነው እየገላገሉ ባይጠብቁቸው ኖሮ ቢዋጉ ሊሞቱ ነበር ። ከዚህ በኋላ ምኒልክ ራስ መኰንንን አስጠርተው የቀድሞውን እምነታቸውን መለሱላቸው ። ወዲያውም እንግዲህ ውጊያውን ትተህ ዕረፍት አድርግ ። ሬሳውንም አስቀብር አሏቸውና የ12 እና የ13 ጥር ቀን በቀብርና በለቅሶ በሐዘን አለፈ ።

ወደ ማታ ራስ መኰንን ጠርተው ሬሳችንን ለማንሣት እንድንችል ተኩሱ እንዲቆም ከኰሎኔል ጋሊያኖ ተነጋገር አሉኝ ። እሱም ብነግረው ከጥር 10 እስከ 11 ቀን ድረስ በብዙ ውጊያና በብዙ መሥዋዕትነት የያዙትን ምንጭ ይልቀቁና ውጊያዩን ሳቁም ስላለ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። በጥር 14 ቀን ለኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ለዝግጅት ያስፈልግ የነበረው የ15 ቀን ጊዜ መሙላቱን ሳውቅ እንግ

ዶሀ አለናብቱኝና ወደ አዲግራት ልሒድ ብዬ ራስ መኰንንን ጠየቅሁ ። እርሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱን ቢጠይቁ ከኔ ጋር ይነጋገር ብለው ራስ መኰንንና ራስ ሚካኤል ባሉበት ጠርተው አነጋገሩኝ ። የምሽጉን ጽናትና ብርታት አይቼ እኔም በአሳቤ ጸናሁ ።

ከዚህ በኋላ ፥ የንጉሡን ቃል በደብዳቤ ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ ይዤ እንድሔድ ተደረገ ። በደብዳቤው ላይ የተገለጸው ፥ "የተከበበው የመቀሌ ጦር በደህንነቱ ወደ አዲግራት እንዲሔድ መፍቀዳቸውና ከኢጣልያም ጋር የሰላም ውል ለማድረግ በማዦር ሳልሳ አማካይነት እንዲከፈት" የሚል ነው ። ከዚህ በኋላ በጥር 17 ቀን እዳጋ ሐሙስ ደርሼ አራት ጊዜ በመካከሉ እየተመላለስሁ የገመትሁት መሣሪያ የያዘው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ቁጥር 80000 መሆኑን ፥ የመቀሌም ጦር ውሃ ማጣቱን ጨምሬ የንጉሠ ነገሥቱን መልእክት ለጄኔራል ባራቲዬሪ ነገርሁ ። ከዚያ የኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የንጉሠ ነገሥቱን አሳብ መቀበሉን የሚያስረዳ አንድ ደብዳቤ ላፄ ምኒልክ ፥ ምሽጉን ለያዘው ለኰሎኔል ጋልያኖ አንድ ደብዳቤ ሰጥቶኝ ሁለት ጊዜ ወደ ጠላት ሰፈር ተመላለስሁ ። ላፄ ምኒልክም የተጻፈውን ደብዳቤ ሰጠሁ ። ንጉሡም ደስ አላቸው ። ጥር 20 ቀን ወደ መቀሌ ምሽግ ገባሁ ። ውሃ በፍጹም አልቆ ነበር ። መሣሪያም እንዷቸው ነበር ። ምንጩን ሁለት ሺህ የሚሆኑ አበሾች ከበው ይጠብቁ ነበር ። ከምሽጉም የተተኰሰ ጥይት እንዳይመታቸው ከለላቸውን አበጅተዋል ።. . . ወዲያው ምክር ተደርጎ ምሽጉን ለመልቀቅ ቁርጥ አሳብ ተደረገ ። ከሁሉም ይበልጥ የሚያስቸኩለው የውሃው ነገር ነበር ። እንስሶቹ ከጥር 11 ቀን ጀምረው አልጠጡም ። ላንድ ሰው የተሰጠውና በጁ ያለው ውሃ ለ6 ቀን ሩብ ሊትር ነበር ። ስለዚህ ወደ ንጉሠ ነገሥቱም ሩጬ 1500 ሊትር ውሃ በባታዮው ልክ እንዲሰጥና ከብቶቹም እንደ ልባቸው እንዲጠጡ አስፈቀድሁ ።

ከዚህ በኋላ ፥ ከዐፄ ምኒልክ ወታደሩም መሣሪያውም ሴቱም ካህናቱም ከብቱም ሳይነካ መቀሌን ለቀው ወደ እዲግራት ይሒዱ የሚል የፈቃድ ወረቀት ተቀበልሁ ። የኰሎኔል ጋሊያኖ ጦር ሲወጣ አደጋ እንዳያገኘው ዋስ የሆኑት ራስ መኰንን ነበሩ ። ስለዚህ የመውጣቱ ነገር በጥር 21 ተወሰነና . . . ከምሽጉ መውጣት ተጀመረ ። ወታደሩም መውጣት የጀመረው በራስ መኰንን ወታደር ተከቦ እየተጠበቀ ነው ። ከምሽግ በሚወጣው ወታደር ላይ አደጋ እታድርጉ የሚል የጠበቀ ትእዛዝ ተደርጎ ነበር ። ቢሆንም ትንሽ ግጭት ተደርጎ የቆሰሉ ጥቂት ሰዎች አሉ ። ከዚህ በኋላ ለጦር መሣሪያና ለዕቃ መጫኛ አስፈቅደን በቅሎና ግመል ከገበያ ገዝተን በጥር በ23ኛው ቀን ወደማታ ጉዞ ተጀመረ . . . በ30 ከእዳጋ ሐሙስ ጦሩ ተጉዞ አዲግራት ገባ ።

በፌልተር እጅ ጄኔራል ባራቲዬሪ ለጋልያኖ የላከው መልእክት እንደዚህ የሚል ነው ። "ስለ ሕይወታችሁ የተሰጠው ዋስትና መተማመኛው የተረጋገጠ መሆኑን ስትረዳው ምሽጉን ለቀህ ውጣ ። ያለዚያ ግን ፥ መንግሥት ባንተ ላይ ያለውን የብርታትና የልምምድ



ዕውቀት ስለሚያምነው፥ በመሰለህ መንገድ ጉዳዩን እንድትፈጽም ላንተው ትቼልሃለሁ ።" ይኸንንም የመውጫ ቃል ያስተላለፈለት በኢጣልያ ንጉሥ በኡምቤርቶ ስም ነው ። ምክንያቱም መኰንኑ ሞገደኛ ብጤ ስለሆነ ፥ ባንድ ወገንም የመቀሌ ምሽግ ጉዳይ ወሬው እስከ ንጉሡ የደረሰ ስለሆነ ፥ ይኸንኑ ተገንዝቦ ያለ ክርክር እንዲወጣ ይመስላል ።

በዚሁ ሰሞን ፥ "ጋልያኖ አንድ ጭብጥ ወታደር ይዞ የመቀሌን ምሽግ በዠግንነት እየተዋጋ ብዙውን የኢትዮጵያ ጦር መለሰ" የሚል ወሬ በኢጣልያ አገር ተጋኖ ተወርቶ ስለነበረ ፥ በዚህ ምክንያትም የጦር ሚኒስትሩ ሞቼኒ ይኸንኑ በራፖር ለንጉሡ ለኡምቤርቶ አመልክቶ በዚሁ በጀብዱ ሰበብ የሌተና ኮሎኔልነት ማዕረግ ታዞለት በቴሌግራም ለባራቲዬሪ ተላልፎለት ነበር ።

ፌልተር ፥ እላይ የተጠቀሰውን መልእክት ወደ ምሽጉ ሔዶ የሰጠው ጊዜ የመሾሙንም ወሬ ሲሰማ ጋልያኖ ፥ "ለዚህ የሚያበቃ ሥራ መቸ እንደልቤ ሠራሁና" ብሎ አለቀሰ ። ይኸን ማለቱ ከምሽግ ውስጥ ሆኜ እንደልቤ አልተዋጋሁም ማለቱ ነው ። ከምሽግ ብቅ ቢል የሚደርስበትን ስለሚያውቅ ፥ ፍርሃቱን በግልጽ መናገር አልፈለገም ።

የሆነ ሆኖ ፥ ጋልያኖ ሲወጣ በርሱም በጦሩም ላይ ምንም ጉዳት እንዳይደርስበት ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠው ተስፋ በትክክል ለመፈጸም ዋሱ ራስ መኰንን ስለሆኑ ፥ ይኸንኑ እንዲያምን ፌልተር ራስ መኰንንን ይዟቸው ወደ ምሽጉ ገባ ። ሁለቱም ከገቡ በኋላ ማዦር ጋልያኖ ፥ "ሲወጣ ከነወታደሮቼ ይዘው ቢያስሩኝስ ቢገድሉኝስ" የሚል ጥርጣሬ አድሮበት ነበርና ይኸንኑ ጥርጣሬውን ደጋግሞ ለራስ መኰንን ስለገለጸ ፥ ራስ መኰንንም ምንም ደጋግመው በመሐላ ቢያረጋጡለት ማመን እቃተው ። ወዲያው ራስ መኰንን እዚያው አጠገባቸው እተደገነው መድፍ አፍ ፊት ሔደው ተደቅነው ፥ " በሉ እንግዲህ ተኩሳችሁ እኔን ግደሉ ። እኔ እንደዚህ ሳምናችሁ እናንተ በመሐላ የምነግራችሁን እንዴት አታምኑኝም" ብለው ስለ ተናገሩ ፥ ወዲያው በፌልተር አጽናኝነት ጋልያኖ ልብ ገዛና ለጭፍሮቹ እንውጣ የሚል ትእዛዝ በሰጠ ጊዜ ፥ ሁሉም ጓዙን እየጫነም እየተሸከመም መውጣት ጀመረ ።[1]

ማዦር ጋልያኖ ፥ "እኔ እዚሁ ቀርቼ እከላከላለሁ" ብሎ ከጄኔራል አሪሞንዲ ከተለያየበት ከታኅሣሥ 8 ቀን 1895 ዓ.ም. ጀምሮ

---

1 L' Assedio di Macalle . . ., PP. 277 - 408; The Campaign of Adwa. Chap. VII.

እስከ ጥር 21 ቀን 1896 ዓ. ም. እ. ኤ. አ. ድረስ አንድ ወር ከ13 ቀን ያህል መከቶ ከቆየ በኋላ ፣ በዚህ ቀን ከምት አፋፍ የደረሰበትን ምሽግ ለቆ ወጣ ። ባንዲራችንን አውርደን ወደ አዲግራት መሸሽ ለኛ ውርደት ነውና እዚሁ እሞታለሁ ብሎ የነበረውን አሳብ ባሁኑ ሰዓት ለውጦ ባንዲራውን ከተሰቀለበት አውርዶ ጠቅሎ መውጣት ግዴታ ሆነበት ። ሲወጣም የነጩና የጥቁሩ ወታደር ፣ የወታደር ሚስቶችና ከመቀሌ ከተማ እያስገደደ ያስገባቸው ሁሉ ነበሩ ። ግማሹ የቆሰለው በቃሬዛ ሆኖ ወይም እያነከሰ ፣ በበሽታና በውሃ ጥም የተጐዳው እያቃሰተ በማዝገም ላይ ነበር ። በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ላይ እንደምንረዳው ፣ አንዳንዶቹ ያገኙትን ውሃ አብዝተው ከመጓጓት ጋር ስለጠጡ ፣ ወዲያው የሞቱም የታመሙም አሉባቸው ።

ጋልያኖ ከነጭፍራው ከነጓዙ እንደወጣ እንዲሰፍር የታዘዘለት ስፍራ ከራስ መኰንን ድንኳን ሐያ እርምጃ ርቆ ነበርና ራስ መኰንን ባስተርጓሚው ባቶ ወልደ አማኑኤል አማካይነት ለጋልያኖና ለጭፍራው ሁሉ የሚያስፈልገውን ሁሉ አደረጉለት ። በተለይ በመቀሌው ምሽግ በተደረገው ጦርነት ዘመድና ጓደኛው የሞተበት ሁሉ ንዴቱ አልበረደም ነበርና ጋልያኖ ከነጭፍራው አደጋ እንዳይደርስበት የሰፈረበትን ቦታ ራስ መኰንን ታማኝ በሆነ ጭፍራ አስከብበው ያስጠብቁት ነበር ።

በዚህ ጦርነት ፣ ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱት ስማቸው የታወቀው ፊታውራሪ ግሌህ ፣ ቀኛዝማች በሻህ አባ ስርጃው ፣ ቀኛዝማች ታመነ ፣ አቶ አባይነህ እና ሌሎች ዐሥራ አንድ ሹማምንትና ከራስ መኰንን ብቻ 500 ወታደሮች መሞታቸው በኢጣልያኖቹ በኩል ተመዝግቧል ። በኛ በኩል እስከ 150 ድረስ ብቻ እንደሞቱ ተጠቅሷል ። በዚሁ ጦርነት ራስ መኰንን ወደፊት ቀድመው ለመዋጋት ሲሉ ፣ ራስ አሉላ በእጠገባቸው ሁነው እየከለከሉ ሲጋብዟቸው ነበርና የራስ አሉላ ጋሻ ጃግሬ ተመትቶ በዚሁ ወቅት መሞቱን ኮንቴ ሮሲኒ ይጠቅሳል[1] ።

በዚህ በመቀሌ ጦርነት ፣ ከኢጣልያ ወገን የሞቱትና የቆሰሉት ስማቸውና ማዕረጋቸው በደንብ ተመዝግቦ ስለሚገኝ እንደኛው አያጠራጥርም ። የእነሱም ቁጥር ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተመለከተው ነው ።

1 Itallia ed Etlopia . . ,P. 251



| | |
|---|---|
| የነጭ ወታደሮች የሞቱ | 4 |
| የነጭ የበታች መኰንንኖች የሞቱ | 5 |
| የጥቁር ወታደሮች በውጊያ የሞቱ | 17 |
| በውጊያ ቆስለው በኋላ የሞቱ | 6 |
| የነጭ ወታደሮች የቆሰሉ | 6 |
| የበታች ሹማምንቶች የቆሰሉ | 3 |
| በውጊያ የቆሰሉ ጥቁሮች | 62[1] |

ከምሽግ በሚወጡበት ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፌልተርን ለማነጋገር መላክተኛ ሲልኩበት ከመላክተኛው ጋር ካለመግባባት የተነሣ ፣ ጋልያኖን ይዘህ ና ያሉት መስሎት ፌልተር ጋልያኖን ይዞት ወዳፄ ምኒልክ ሔደ ። በሔደም ጊዜ ጋልያኖን ሰው ሁሉ ይመለከተው ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት አዳራሽ በር ሁለቱም በተጠጉ ጊዜ የልፍኝ አስከልካዩ ወጣ ብሎ የተጠራኸው አንተ ብቻ ነህ እንጂ ፣ እሱ አልተጠራምና አይገባም ብሎ ጋልያኖን ከለከለው ። በዚህ ጊዜ ከምሽግ ድረስ እኔ ይዤው መጥቼ ትቼው መግባት አይሆንልኝም ብሎ ስላመለከተና እንዲገቡ ስለ ተፈቀደ ፣ ሁለቱም ወዳፄ ምኒልክ የድንኳን አዳራሽ ገቡ ። በገቡም ጊዜ ፌልተርን ለሰላምታ ሲጨብጡ ንጉሠ ነገሥቱ ጋልያኖን አልጨበጡትም ። የተዘጋጀውም ወንበር ለፌልተር ብቻ ነበርና ፌልተር ራሱ በመቀመጥ ፋንታ ለማስከበር ሲል ጋልያኖን አስቀመጠውና እርሱ ስለቆመ ፣ ለርሱም ሌላ ወንበር መጥቶለት ተቀመጠ ።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ይኸን ሰው ለምን ይዘኸው መጣህ" የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡለት ፣ ስሕተቱ የመልክተኛው መሆኑን ገልጾ፣ "ይኸን የመሰለ የርስዎ ወታደር ለንጉሡ ለመሞት የቆረጠ ዠግና እኔ ንጉሥ ዘንድ ቢቀርብ በጣም ያከብረዋል" ብሎ መለሰ ።
ፌልተር ራሱ እንደ ጻፈው ፣

> በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ላንድ የልፍኝ አሽከራቸው በዦሮው አንድ ትዕዛዝ ሲሰጡት መላክተኛው እንደ ቀስት ተወርውሮ ወጣ ። ሩብ ሰዓት ያህል ከእኔ ጋር ብቻ እንደ ተነጋገርን መላክተኛው አንድ በሐበሻ የርሱዋን ዓይነት ያላየሁዋት በብር የመረገት ሥራ የተንቆጠቆጠች በቅሎ ይዞ መጣ ። በዚያን ጊዜ ምኒልክ ፣ "ያውልህ ፌልተር የኛ አገር ሌላ ነገር እንደናንተ አገር አያፈራምና ይኸን (ለጋልያኖ) ስጠው እንደሚያስደስተው ተስፋ አለኝ" ብለው የኔን እጅ ብቻ ጨብጠው እሰናበቱን . . . ።[2]

ሲል ያረጋግጣል ።

1 L'Assedlo di Macalle . . PP. 390 - 429.
2 La Vicenda Africana - Pietro Felter, PP. 47 - 52.

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

## የመቀሌው ጦርነት በኛ በኩል ባለው ሰነድ—የማዣር ጋልያኖ ጦር ከመቀሌ ወደ አዲግራት መሔድ

ባለፈው ያነበብነው ፣ ይነስ ይብዛ ከኢጣልያኖቹ ጽሑፍ የተገኘ ነው ። በኛ በኩል ዝርዝር ጽሑፍ ስለሌለን እስከዛሬ ድረስ የአላጌን፣ የመቀሌንና የዓድዋን ጦርነት የምናውቀው በመጠኑ ነው ። እርሱም ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ነጋድራስ አፈወርቅ ባጫጭሩ በተዉልን መጽሐፍ አማካይነት ነው ። ከነርሱ ወዲህ ብላቴን ጌታ ኅሩይና ከዚያ ወዲህ በመጠኑ ሁላችንም ጽፈናል ። የታሪክ መጽሐፍ ነገር ሁል ጊዜ ባገራችን በዝርዝር ማስፈር ስላልተለመደ ፣ እንኳን ራቅ ያለው የዓድዋ የቅርቡ የማይጨውም ጦርነት ጣልያኖቹ ለሕዝባቸው በብዛት ባገለጡት ዓይነት በዝርዝር ለሕዝባችን አልጻፍንም ። ጦርነቱ ካገር ነጻነት አልፎ የብዙ ሕዝብ ሕይወት የተሠዋበት እንደመሆኑ መጠን ዝርዝሩን በሕይወት ላሉና ወደፊት ለሚወለዱት ኢትዮጵያውያን ማቆየት የሚገባ መሆኑ የታወቀ ነው ።

በዚህ በዓድዋ ጊዜ ፣ በኢጣልያኖቹ በኩል በየጦሩ ግንባር ሆነው የተደረገውን ሁሉ እየጻፉ በየላኩዋቸው የጋዜጣ ቡድን ወኪሎች ወደ ኢጣልያ አገር የሚያስተላልፍ ቢዞኒ የሚባል የሴኮሎ ወኪል ፣ ሜርካቲሊ የሚባል የትሪቡና ወኪልና ሌሎችም ነበሩ ። በኢጣልያ አገር የቀኝና የግራ ክፍሎች የፖለቲካ ቡድኖች ስላሉ ፣ ጋዜጠኞች የሆነውን ሁሉ እየሰበሰቡ ለየክፍላቸው ስለሚልኩ ፣ አንባቢው ሕዝብ እንደየጣዕሙ ጉዳዩን መከታተል ይችላል ። አንዳንድ ጊዜም በጦር መሪዎቹ ላይ ስሕተት ሲገኝ እየነቀፉ ወይም መሪዎቹ ከመንግሥታቸውና ከሕዝባቸው ለመሰወር የሚፈልጉትን እነሱ እያጋለጡ ስለሚገልጹት ፣ ያልሆነ ነገር ጽፋችኋል እየተባሉ አላግባብ እየተወነጀሉ በዋናው አዛዥ በጄኔራል ባራቲዬሪ ትእዛዝ ከኤርትራ ይባረራሉ ።

የኛዎቹ በዚህ ለዓት እዚህ ደረጃ ስለ አልደረሱ ፣ ያዲስ አበባና የሌላውም የኢትዮጵያ ወረዳ ሕዝብ የጦርነቱን ወሬ የሚያዳምጠው ወሬው ካረጀ በኋላ ከመንገደኛ ነው ። ይሁን እንጂ ፣ ከዚህ በፊት በአ

ላጌ ጦርነት ላይ እንደ ተመለከትነው ፣ አዲስ አበባ የሚቀመጡ ብዙ የውጭ አገር ሰዎች የኢትዮጵያና ያጼ ምኒልክ ወዳጆች ነበሩ ። ከእነሱም አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ወዳጆች ሆነው ወደ አውሮፓ መሪዎች ዘንድ በመላክ የጦር መሣሪያ በማቅረብ ለዘመኑ የሚበጀውን የፖለቲካና ያስተዳደር ጉዳይ በመምከር አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱ አሉ ። ከነርሱም መካከል ሞንዶን ቪዳዬ የሚባለው ለታ ለሚባለው ጋዜጣ ወኪል የሆነ ብቻ ሳይሆን ፣ ብዙ ጠቃሚ አሳብና የአውሮፓንም ወሬ ለንጉሠ ነገሥቱ በማቅረብ የሚያገለግላቸው ከዚህ ከኢትዮጵያ የተደረገውን ሁኔታ ለዚሁ የጋዜጣ ድርጅት ወደ ፓሪስ በማስተላለፍ ፣ የጣልያን ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዝሩትን መጥፎ ወሬ ያስተባብል ነበር ።

ለርሱም በጦሩ ግንባር ሆነው የተደረገውን በጽሑፍ የሚያስተላልፉለት ዋናዎቹ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ዋናው አስተርጓሚ ግራዝማች ዮሴፍ ናቸው ። አንድ አንድ ጊዜም ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው በቀጥታ በስማቸው ይጽፉለታል ። በፊት ስለ አምባአላጌ እንዳየነው አሁን ደግሞ ግራዝማች ዮሴፍ ስለ መቀሌው ጦርነት ለዚሁ ጋዜጣ ወኪል በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ የጻፉትን ስናነብ ፣ ፊልተር በእርቅ አስመስሎ ጊዜ ለማግኘት ወደ ሰፈር የመጣው ለማታለል መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተገነዘቡት ይገልጻል ። ጽሑፉ ከአምባ አላጌው ታሪክ የቀጠለ መሆኑን እያስታወሰን ፣ የዮሴፍን አባባል በቀጥታ እንመልከት ።

> ... ከዚህ በኋላ የጃንሆይ ሠራዊት የመቀሌን እርድ (ምሽግ) ከቦ ተቀመጠ ። እርሱ ግን ቀን የእርቅ ነገር እየተላላከ እያታለለ ሌት ሌት ካቡን እየካበ እርዱን አጠነከረ ። ጃንሆይ ግን ከአሸንጌ ተጉዘው አላጌ ላይ በጦር የሞተው ሰውና የከብት ጥንብ ሽታው በመንገድ አላላልፍም ቢላቸው ፣ የጭሮራትን መንገድ አስጠርገው ተጉዘው ጨለቆት ገቡና ሰፈሩ ። ከጃንሆይ ጋር የነበረው ሠራዊት እርዱን ከቦ ለማፍረስ ሲፈልግ የጃንሆይ ብልህነት ከሠራዊታቸው አለወገን በከንቱ አንድ ሰው እንኳን ቢሞትባቸው እንዳይወዱ ያውቁታል ። ከእርድም ውስጥ የሚያሰነብት ውሀ እንደሌለው ቢያውቁ በዙሪያው የነበረውን ምንጭ ሁሉ በዘበኛ አስጠበቁት ። እርሱ ግን ፣ የኛን ሰዎች በእርቅ ስም ያታለለ ጊዜ ሌትም ቀንም እየቆፈረ በጉድጓድም በበርሜልም ጥቂት ውሃ አጠራቅሞ ነበር ። እንደሱ ብልሃት ስንቅ የሌላቸው ዘርፈው የሚያድሩ ናቸው ። ጥቂት ቀን ጠብቀውኝ ጥለውኝ ይሔዳሉ መስሎት ነበር ። ውሃም የሰረቀ መስሎት ፈርቶ ይለቅልኛል ሲል ከነጋሀ እስከ ማታ ድረስ መድፍና ነፍጥ ይተኩስ ጀመር ። የኛ ወታደሮች ግን በልባቸው ብዙ ንዴት ነበረና ጠንክረው ጠበቁ ። በመስኮትም እያሾለኩ ብዙ ሰው ብዙ ከብት ፈጁበት ። ውሃ ሲጠብቁ የራስ መኰንን ዘበኞች ቢሞቱ ራሳቸውን አላስነካ ብለው በራስ መኰንን ሰው መድፍ እየተኮሰ አላስቀርብ አላቸው ። ከፍርሃታቸው ብዛት የተነሣ በእርዱ ፊት ለፊት አንድም ሰው ሲያልፍ አንድ ግርም አሜጅ ሲታይ መድፍ ሲተኩስ ይውል ነበር ። እርሱ ግን የእርዱን ካብ ሲከብ በመቀሌ ዙሪያ የነበሩትን ባላገሮች ካህናቱንም ወንዶቹንም ሴቶቹንም ልጆቹንም ሰብስቦ አግብቷቸው ነበርና በኢጣልያኖቹም ዘንድ ርኀራኄ ስለሌለ ፣ ውሃ ጥም ቢጸናባቸው አንዳንድ ሴቶች ሌሊት በካቡ እየተንከባለሉ ይወርዱ ጀመር ። ውሃም ብናጠጣቸው ወሬውን ሳይነግሩን ውሃውን ጠጥተው ይሞቱ ጀመር ። ከነዚያም ቀጥሎ ሠራተኛው ወታደሩ ውሃ ጥም ቢበረታበት እየከዳ መውጣት ጀመረ ። ከእርዱም ውስጥ ያለው ከብትና ባላገር ሁሉም በውሃ ጥም አለቀ ። እርዱም ተባሪ ቢጠፋበት በሩቅ ይገማ ጀመር ። አንድ ቀን ውሉ ቢሆን ሁሉም አልቆ ያድር ነበር ። ጃንሆይም እንደ ተጨነቀ ቢያዩት ፣ ልባቸው ራርቶ በእርሱ ሥላሴ የተፈጠረውን ሕዝብ እኔ የክርስቲያን ንጉሥ እንደ አሕዛብ ንጉሥ ክርስቲያኑን በውሃ ጥም አልፈጀውም ብለው ፊልተር የሚባለውን የሐረርጌውን የኢጣልያ ነጋዴ አስታርቃለሁ ብሎ መጥቶ ከራስ መኰንን ሰፈር ቆይቶ ነበርና አስጠርተው "ከሆነ ጌታችሁ መምጣታችሁ የሰው አገር እንይዛለን ማለታችሁ ከጉድባ ውስጥ ገብቶ በውሃ ጥም ለማለቅ ነውን" ብለው ጠየቁት ። እርሱ ግን የታየ ነገር ስለሆነ ምላሽ አጣ ። ጃንሆይም እንደ ናንተ ክፉት ብሔድ ፍጥረት ሁሉ ያልቅ ነበር ። አሁንም ለጄኔራል ባራቲዬሪ እንዲህ ብለህ ንገረው ። "የሰው አገር እይዛለሁ ብሎ የመጣ ሰው ከጉድባ ውስጥ እየገባ በውሃ ጥም አያልቅም ነበር ። ጠላታችሁን ውደዱ (አፍቅሩ ጸላእተክሙ) ያለውን የወንጌል ቃል ለመፈጸም እኔ ግን ፣ የክርስቲያን ንጉሥ ነኝ እንጂ የአሕዛብ ንጉሥ አይደለሁም ። አሁንም ክርስቲያኖች በከንቱ እይለቁ ሰዎችህን ልከህ አስወጣ ፣ ትጥቁንም እንደ ሆነ አንድነት ተሰብስበባችሁ ቀዩኝ እኔም እመጣለሁ" ብለው ፊልተርን ላኩበት ። ሰዎቹን ይልቀቁልኝ የእንዳ ኢየሱስን እርድ ያስረክቡዎ የሚል ቃል ከንጉሥ ኡምቤርቶ ይዞ በተላከ በአራተኛው ቀን ተመልሶ መጣ ። ከሞት የተረፉት ከጉድባ የነበሩ ኢጣልያኖች ያለቃቸው ዶብላቤ ቢመጣላቸውም እርዳታም እንዳጡ ቢያቁት ጭንቅም ቢበዛባቸው ነጭ ሰንደቅ ዓላማ ተከሉ ። ውሃም ለራሳቸውና ለከብታቸው ለመኑ ። ጃንሆይም ከእርዱ ውስጥ ያለውን ደሃ አስወጡ ብለው አዝዘው አስወጡት ። ለነዚያም ለከብቶቻቸውም ውሃ ዳረጓቸው ። ደሃውም ከብቱም ወሀ እየጠጣ ይሞት ጀመር ። እንኳን ሰው ውሻውም ውሃ እየጠጣ ሞተ ። የኛም ሠራዊት ይኸን እያየ በድንጋው ሞት አዘነ ። ነገር ግን የኛ ሠራዊት ጃንሆይ በሠሩት በጎነት አገራችንን ለዘረፈ ታቦታችንን ላቃጠለ እንዲህ ያለ ወረታ ለምን ይደረግለታል ብሎ ተከፋ ። አይዋጋላቸው ካቡን ጨረሰ በኋላ ለምን ከእርዱ ውስጥ ውሃ እንደሌለ ምስጢር እንዳያወጡባቸው* ነው አሉን ። ይህም ለቀባሪው አረዱት የሚሉት ተረት አይደለምን ? ያገራችንን መሬት አጣ ነውር እነዚያ ዶብቀው ሊያድኑ ብለን ሳትንባቸው ። ጃንሆይ ግን



* እዚህ ላይ የተዘለለ ዓረፍተ ነገር አለ ። የተዘለለው ዓረፍተ ነገር "ላይ፣የጋላቸው ሕዝቡን ለምን ከምሽግ አግብቶ ዘጋበት ቢሉ ውሃ ያለመኖሩን ምሥጢር እንዳያወጡበት ነው አሉን" ይመስላል ።

> እነዚያንም ዕቃቸውንም የሚጭኑበት ቢያጡና እጅግ ቢቸገሩ የገንዘብ መውደድ ይመስልብኛል ብለው የኪራይ በቅሎ ሰጥተው ከነዕቃቸው ሒዱ ብለው ሰደዱአቸው ። እነዚያ ጣልያኖች ግን ከውሃው ጥፋት የተነሣ ከባሻ ባዙቂ (የጥቁር ሹማምንት) ጋር ሊዋጉ ደርሰው ነበር ። እንደነዚያ ከፋት ቢሆን አንድ ወሬ ነጋሪ ባላመለጠም ነበር ። የምኒልክን ደግነት ሲቻለው የሚተው ንጉሥ በኢትዮጵያ መኖሩን የሰማ አውሮፓ ምን ይል ይሆን እንላለን ። እስከዛሬ ድረስ የተደረገውን የጦር ነገር ይኸውና ላኩሁብዎ[1]

እንዲሁም እኝሁ ግራዝማች ዮሴፍ ፡

> . . .ይህ ሁሉ ሲሆን ከመቀሌ ተነሥተን ያል (ፈረሰማይ) እስከንደርሰ ድረስ ኢጣልያኖች የእርቅ ወሬ ሲያወሩ ሰነበቱ ። የነዚያ ሹማምንቶችና ፌልተር የሚባለው ነጋዴ ከሰፈር ሲመላለሱ ነበር ። ጃንሆይም ተንኮላቸውን ዐውቀውባቸው ቶሎ ቶሎ ገሥግሠን ዛታ ላይ ሰፈርን ። ኢጣልያኖቹም ከአዲግራት ወጥተው እዳጋ ሐሙስ ላይ ሰፍረው ነበር ። የኛም ጦር ወጥቶ እጠገባቸው ሰፈረ ። እነዚያም የጦሩን ብዛት ባዩ ጊዜ ለመድፍ የሚያመች ሰፍራ ፈልገው ካብ ይከቡ ጀመር ።

ብለው ሲጽፉ ፣ ፌልተር ከኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሰላም ፈላጊ መስሎ የመዘጋጃ ጊዜ ለማስገኘት ተልኮ እሰፈራቸው የመጣበትን የማታለል ሰበብ ዐፄ ምኒልክ እንደ ተረዱት ያስታውቃል ። በዚህም ንጉሠ ነገሥቱ የጦር ድርጅቱን ሥራ ከማከናወናቸውም በላይ ወሬና መረጃ መጥቀሙን ተረድተው የየጊዜውን ሁኔታና የጠላትንም አሳብ ያስመረምሩ ነበር ማለት ነው ። በተረፈ በሌላ ረገድ የፌልተርና የግራዝማች ዮሴፍ አጻጻፍ በመሠረቱ አንድ ነው ። ግራዝማች ዮሴፍ ባጻጻፋቸው ንጉሠ ነገሥታቸውን የማድነቅና የማስደነቅ ፣ የማከበርና የማስከበር ነገር ሲያሳዩ ፣ ጣልያኑም የራስ መኰንንን የቅን ወዳጅነት መሳሪያ አድርጎ የኢትዮጵያን መንግሥት በዕርቅ ስም እያታለለ ከኢጣልያ አገር የሚመጣው የእርዳታ ጦር እንደርታ እስኪገባ ድረስ የ35 ቀን ጊዜ እንዲያሰጥ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ተልኮ የመጣበትን መልእክት ፈጽሞ ከተመለሰ በኋላ ፣ ባለፈው ባነበብነው ራፖር ውስጥ የርሱን ወገኖች በአጻጻፉ ለመደገፍና ለሚሠሩት ሁሉ ደንበኛ መንገድ ለመስጠት እንደ ሞከረ ያሳያል ። ቢሆንም ነገሩን በጠቅላላው ስንመለከት ያፄ ምኒልክ ዋና አሳብ ፣ "በወሃ ጥም ሊያልቅ የነበረውን የጦር ሠራዊት ከሞት አትርፌ ዕቃውን የሚጭንበት አጋሰስ አዝዤ ሸኚ ሰጥቼ ስልከለት የአውሮፓ ሕዝብ ይፈርደኛል ፤ ጠላቴንም ይወቅስልኛል ፣ እርሱም ይኸን ሁሉ አመዛዝኖ ሕዝቤን ሳላስጨርስ በእርቅ አገሬን ለቆ ይሔዳል ፤ እምቢ ቢልም የተከተለኝ የጦር ሠራዊት

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ቪዳዬ ዶሲዬ የተገኘ ።



የርሱን ጦር ለመምታትና ለማሸነፍ በማናቸውም ሥፍራ በማናቸውም ጊዜ አይሰንፍም የሚል ነው ።

በዚህ የተደራረበ አሳብና ተስፋ ላይ በመመሥረት ለጠላት የእርቅና የሰላም መንገድ ማሳየታቸውን ሳይለቁ ደግሞ የፍርሃት መስሎት የልብ ልብ እንዳይበቃው ፣ "የክርስቲያን ንጉሥ ነኝ እንጂ ፣ የአሕዛብ ንጉሥ አይደለሁም አሁንም ክርስቲያኖች በከንቱ አይለቁ ሰዎችህን ልከህ አስወስድ ፤ አገር ሊፈልግ የመጣ ጦር ጉድባ ውስጥ አይገባምና ትዋጉም እንደሆነ አንድነት ተሰብሰባችሁ ቆዩኝ" ብለው ለዋናው ጠቅላይ አዛዥ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ላኩበት ። እርሱ ግን ፣ ርኅራኄያቸውንም ጉልበታቸውንም ቢሆን የፖለቲካና የእርቅ መንገዳቸውንም ከምንም አልቆጠረውም ። የጠበቀው የእርዳታ ጦር ከጥር ወር ጀምሮ ከኢጣልያ በመርከብ እየተጋዘ ሲደርስለት ፣ በወሃ ጥም ሊሞት የነበረው የመቀሌው ጦር በነጻ ተለቆ በእጁ ሲገባ የዕርቁን ነገር በጭራሽ ትቶ ለዋናው ለዓድዋ ጦርነት ይዘጋጅ ጀመር ።

ቢሆንም ፣ የኢጣልያ ጦር ያላግባብ የሰው አገር ወሰን ጥሶ የወራሪነት ሥራ በሚፈጽምበት ጊዜ ፣ ከዚሁ ያንድ ባታዮ ጦር በመቀሌ ምሽግ ውስጥ ሆኖ የብዙ ኢትዮጵያውያን ደም አፍስሶ ሳለ በወሃ ጥም ቢያልቅም ፣ ሊዋጋ የመጣ ጠላት ነውና ዐውቆ እጁን ካልሰጠ ዝም ብለው ቢረሹት ያም ቢቀር ያለውል እጁን እንዲሰጥ አድርገው መሣሪያውን በሙሉ ቀምተው ወታደሩን በምርኮኝነት ይዘው ለሚፈልጉት የእርቅ ድርድር ሊጠቀሙበት በቻሉ ነበር ። ይኸንንም ሲያደርጉ ከጦርነትና ከወታደርነት ሕግ ወጡ ተብሎ በዓለም አያስፈርድባቸውም ነበር ።

ይኸን የመሰለውን ከዚህም የባሰውን ሁለት የአውሮፓ መንግሥታት በሚዋጉበት ጊዜ እርስ በርሳቸው ይፈጽሙታል ። ሲፈጽሙም ደንበኛ አፈጻጸም መሆኑ በማንም ዘንድ ይገመታል ። በዚህ ዘመን በቅኝ አገርነት ለመገዛት የተፈረደባቸው የአፍሪካና የእስያ አገር መሪዎች ግን ፣ ከፈረንጆች ጋር በሚዋጉበት ጊዜ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ሰበብና ቋፍ ያለበት ነው ። የአንድ አውሮፓዊ መቁሰልና መሞት አገር ወረራን የሚያስከትልበት ጊዜ ነው ። ይኸንንም የገዥነትና የተገዥነት መደብ ለይቶ የፈጠረው አውሮፓውያን በቴክኒክና በሌላው የመሠልጠናቸው ጉዳይ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በዕርቅና በሰላም ጣልያንን ለማስወጣት የመቀሌንም ጦር በነጻ ለቀው የርኅራኄ ፣ የሥርዓት መንገድ በጥብቅ የፈለጉበት ምክንያት ከአውሮፓ የሚሰነዘረውን ሰበብና ምክንያት ለማስወገድ ሲሉ ነው ። በዚህ ጊዜ የፈረንሳይና የመስኮብ መንግሥታት ለኢትዮጵያ

እጋዥ ቢሆኑም ፣ የጀርመንና የእንግሊዝ መንግሥታት ለኢጣልያ የቃል ኪዳን ጓደኛ ስለነበሩ በተለይ የሱዳን ፣ የኤደንና የሕንድ ጌታ የሆነውና እንዲሁም በበርበራና በዘይላም መዳፉን ያሳረፈው የእንግሊዙ እያያዝ ለኢትዮጵያ አስፈሪ ነበር ። ስለዚህም ጦብ ላለመፍጠርና ሰላማዊ ሆኖ ለመታየት የኛዎቹ ይጣጣሩ ነበር ።

እ.ኤ.አ. 1936 (1927 ዓ.ም) የሙሶሊኒ መንግሥት በጉንደር ቆንስላ ዘበኞች መካከል በተነሣው የርስ በርስ ጠብና የወልወል ግጭት ራሱ ፈጥሮ ጠቅላላውን ወረራ ለመፈጸም ተጠቅሞበት እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

በዓድዋም ጊዜ ፣ በኢጣልያኖች ጋዜጣ አማካይነት ያንዳንድ ጸሐፊ ወሬ በመስማት ፣ "የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭን አገር ሰው የማያከብር ፣ እርስ በርሱ የሚፋጅ ፣ በጠላቱና በምርኮኛው ላይ የጭካኔና የአረመኔነት ሥራ የሚሠራ ነው" እየተባለ በአውሮፖች ዘንድ ይወራ ስለነበረ ፣ ይህ ወሬ ሐሰት መሆኑን ለማስተባበል በንጉሠ ነገሥቱና በራስ መኰንን ዘንድ ከፍ ያለ ጥረት ይደረግ ነበር ። ሞንዶን ቪዳዬ ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ የጋዜጣ ወኪል ከመሆኑም በላይ አዲስ አበባ ላሉት ለኢትዮጵያ ወዳጆች ለነሙሴ ኢልግ ፣ ለነሙሴ ሸፍነ ፣ ለነሙሴ ሳቡሬ ፣ ለነሙሴ ሊዎንቴቭና ለቀሩትም ሁሉ እንደ ሸማግሌ የሚቆጠር ሰው ስለነበረ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ማናቸውንም የጦርነቱን ሁኔታ ለርሱ በቀጥታ ይጽፉለት ነበር ። በዚህም ላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ለአውሮፓ ፣ የአውሮፓንና የኢጣልያንን አገር ሁኔታ ፣ በምክር ቤትና በጋዜጣ የተባለውን ሁሉ ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ በጽሑፍ ይገልጽል ። ማናቸውንም ደኅኛ ነገር የሚመክር ሰው ነበርና ንጉሠ ነገሥቱም በበኩላቸው ፣ ኢጣልያኖቹ ስለሚያወሩት ሐሰተኛ ወሬ የጻፉለትን በሚከተለው እንመልከት ።

> ሞገ እንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን እንዴት ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። በታኅሣሥ 16 ቀን በአዲስ አበባ ከተማ የተጻፈ ደብዳቤህ ደረሰኝ ። ከአውሮፓ የመጣውን ወሬ ስለላክህብኝ እግዚአብሔር ያመስግንህ ። እንግዲህም የሚመጣውን ወሬ ተሉ ተሉ እንድትልክልኝ ይሁን ። የኛን የጦርነት ደብዳቤ ከግራዝማች የሴፍ ደብዳቤ ታገኘዋለህ ። የኢጣልያኖች የውሸት ወሬ አያልትም ሁላችንን እንደ ገደሉ ያወራሉ ። እኛ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ሁላችንም ደህና ነን ። እኛን በሕይወት ያለነውን ሞቱ እያሉ ይልቅ የሞቱትን የሰዎቻቸውን ቁጥር ማወቅ ደግ ነበር ። የተማረኩትን ኢጣልያኖች እንዳይበድሉ ብለህ የላክብኝን እኛ ባገራችን እንኳን ክርስቲያንን ፣ አሕዛብንም ቢሆን ከተማረከ በኋላ እንዳንበድል ታውቂታላችሁ ። እውንም አክብሬ ማስተመጫ ኢጣልያኖች ያመስግኑኛል ብዬ አይደለም ። የክርስቲያን ሥርዓት እንዳይጉድል ብዬ ነው ። በአዲስ



> አበባ ከተማ ያሉት ፈረንጆች አንተ ቤት ተሰብስበው አላኔ ላይ የኔ ሰዎች ስለአደረጉት ድል ብዙ ደስታ ስላደረጉ እኔም ደስ አለኝ ። በየካቲት 13 ቀን በ1887 ዓ.ም. ተጻፈ ።

ሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ፣ በራስ ዳርጌ አማካይነት ወይም በግራዝማች የሴፍ በኩል የሚደርሰውን ደብዳቤና የጦርነቱን ማስረጃ አዲስ አበባ ላሉት የውጭ አገር ሰዎች ጓደኞቹ ነገሩን ማስረዳቱን ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን የጦርነት ድል ባገኙ ጊዜ ፈረንጆቹ እርሱ ቤት ተሰብስበው የደስታ በዓል ያደርጉም እንደነበረ በደብዳቤው ተገልጿል ።

በርሱና በእንደሴራው በራስ ዳርጌ መካከል የቅርብ ግንኙነት ነበር። እርሱም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የሚልከው በርሳቸው በኩል ስለነበረ ፣ በተረፈ የጦርነቱንም ሁኔታ የድሉንም ደስታ ይካፈሉ እንደ ነበር ከዚህ ቀጥሎ ያለው ወደርሱ የተጻፈው የትልቁ የራስ ዳርጌ ደብዳቤ ያስረዳል ።

> የተላከ ከራስ ዳርጌ ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን ከተለያየን ብዙውን እንዴት አመሸህ ። የሰደድህልኝንም ደብዳቤ አየሁት ። ነገር ግን ይድረስ ወደ ጃንሆይ የሚል ቢሆን ጃ(ደንገር) ብሎኝ ነበር ። ከቤትህ ሽማግሌዎች ጠርተህ የደስታ ፈንጠዝያ ያደረግኸውን ሰማሁ ። እኔም እንደዚሁ ከቤቱ ገብቼ ከአሽከሮቼ ጋር ፈንጠዝያ ሳደርግ ዋልሁ ። እግዚአብሔር ደግሞ ጭራቹን ያብጀልን ። ደግሞ ሙሴ ኮለ ሼት ሲሔድ ተገናኝተን ተመካከረን ሁሉንም እንልከዋለን ።*
>
> ዝ ማኅተም ዘእራስ ዳርጌ ርእሰ መኳንንት ፤

ስለ መቀሌ ምሽግና ስለ ጋልያኖ አወጣጥ ጉዳይ ፣ በበኩላቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በመጽሐፋቸው እንደዚህ ሲሉ አስፍረውታል ።

> ... ፊልተር የሚባል የኢጣልያ ነጋዴ... ኢጣልያኖችን ለማስታረቅ ወደ አዲግራት ሔዶ ነበርና ያንለት ወደ ሰፈር መጣ ካፄ ምኒልክም ዘንድ በደረሰ ጊዜ እንደዚህ አለ ። መቀሌ ከእርድ ውስጥ የነበሩት ኢጣልያኖች ተመልሰው አዲግራት ካልገቡልን የእርቅ ነገር መነጋገር አይሆንልንም አሉ ብሎ ነገራቸው ። ዐፄ ምኒልክም በመየ ጥም ተከበው በእጇ ጨብጫቸው ፣ በእግሬ ረግጫቸው የነበሩትን እነዚህን አልነካቸውም። አንተው እንደ ተመኘኸው ሰጥቼ እሰድጃለሁ።

---

* ኮልፌት የሚባለው በዓድዋ ጦርነት ጊዜ በበጅሮንድ ባልቻ ውስጥ ሆኖ የዓድዋን ጦርነት የተካፈለ ፈረንሳዊ ነው ይባላል ። ለመካፈሉ የተረጋገጠ ምንጭ የለም ። ይልቅስ የመትረየስና የመድፍ አተኳኩስ ለኢትዮጵያውያን ያስተማረ ይመስላል ።

1 እነዚህ ለምንዶን ቪዳዬ የተጻፉት ደብዳቤዎች በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በእጅ ሰነድ ክፍል በቁጥር 82 በሙሴ ምንዶን ፋይል ይገኛሉ ።

ነገር ግን ፣ እነዚህን ሰዎች ከነመድፋቸው ፣ ከነነፍጣቸው መስደዴ የሞኝነት አይምሰልህ ። ስለፍትር(ስለሰላም) ያደረግሁት ነው ። ደግሞ እነዚህን ጥቂት ሰዎች አልነካቸውም ማለቴ መንግሥቱን ለማክበር ነው ። አሁንም ብትታረቁም ድንቅ ፤ ጦርነትም ከከጀላችሁ እነዚህን ጨምራችሁ ጠቅላችሁ ኑ ።[1]

ፊልተር "እነዚህ ካልተቀቁ የሰላም ንግግር አይዠመርም" ብለዋል ያለው ሐሰትን የተንተራሰ አባባል ነው ። ባፄ ምኒልክ ዘንድ ያለውን ሰላም ፈላጊነት በመጠቀም ሰዎቹን ለማስለቀቅና ከዚያ በኋላ ለመዋጋት በኢጣልያኖቹ በኩል ያለውን የጋለ ፍላጎት ያውቀዋል ። የርሱም አመጣጥ ጊዜ ለማግኘያ መሆኑን ባለፈው ተመልክተነዋል ። ዳግማዊ ምኒልክም ባነጋገራቸው ፣ "እነዚህን መስደዴ የሞኝነት አይምሰልህ" ሲሉ የኢጣልያኖቹን ተንኮል እንደተገነዘቡት ያመለክታል። ነገር ግን ከላይ እንዳመለከትነው ፣ እነዚህን በመልቀቅ ለጠብ ምክንያትና ሰበብ የሚሆነውን ሁሉ በማስወገድ የዓለምን ፍርድ ለማግኘት በጣልያን ላይ ለማስፈረድ ሲሉ የተቻለውን ያህል እንደተጣጣሩ ይታያል ። ባንደ ወገን ደግሞ ፣ "ብትታረቁም ድንቅ ፣ ጦርነትም ከከጀላችሁ እነዚህን ጨምራችሁ ኑ" ማለታቸው ለድል አድራጊነታቸው የተማመኑ ይመስላል ።

የዚህን የፖለቲካ ውዝግብ ደህና አድርጎ የማያጤነው ወታደር የጋልያኖ ጦር ከነጦር መሣሪያው ጓዙን ጠቅሎ ከምሽጉ በወጣ ጊዜ ዘመድና ወገኑ የሞተበት ሁሉ በቁጭት እያወካ ለመቃወም የንቅናቄ ምልክት ባሳየ ቁጥር ፡ "ተው እርጋ" እያሉ ጠመንጃቸውን አንግበው ፡ በቀኝ እጃቸው ዘንግ ይዘው ኢጣልያኖቹን ከነባንዳዎቻቸው ከበው ይከላከሉ የነበሩት በመቀሌው ጦርነት ይበልጥ የተጎዱት የሐረር የጦር ሹማምንት ናቸው ። በምኒልክ ቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓትን የተካኑት ወደ አውሮፓ በመሔድ ዘመናዊው የሥልጣኔ ጮራ ገረፍ ያደረጋቸው ራስ መኰንን በፋንታቸው ይህን ግብረ ገብነት ለጭፍሮቻቸው አስተምረዋል ማለት ነው ። መኰንን ለምኒልክ አገረ ገዥና የጦር መሪ ከመሆናቸው አልፈው ፣ ልክ እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚቆጠሩ የዲፕሎማቲክ ኃላፊ ጭምር ናቸው ። ሰላዩ ካፑቺ ለኢጣልያን ባለሥልጣኖች በጻፈው ራፖር ውስጥ ፣ "ከሁሉ የበለጠ የኛ ኃይለኛ ጠላት ራስ መኰንን ነው ፤ ምክንያቱም መኰንን ባንድ ወገን ብልህና ታታሪ ፣ በሌላ ወገን የምኒልክ ታማኝ በመሆኑ ነው" የሚሉ ቃላት አስፍሯል ።[2]

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ.62 ገጽ 249,250
2 I Russi in Etiopia - Carlo Zachi, P. 76.



ከመቀሌ ምሽግ የጋልያኖ ጦር ከመውጣቱ በፊት ስምምነት እንደ ተደረገ የኢጣልያ ባንዲራ ወርዶ ነጭ ባንዲራ ተሰቅሎ ነበር። አሁን ደግሞ ፣ ምሽጉን በሙሉ እጅ ካደረጉ በኋላ በጅሮንድ ባልቻ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዘው ሔደው ግባት (የደስታ ተኩስ) እየተተኮሰ የኢትዮጵያ ባንዲራ በገሃድ ተሰቀለ ።

ማናቸውም ዝግጅት በዚህ ዓይነት ከተፈጸመ በኋላ ፣ ጋልያኖ ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው በቅሎ ተቀምጦ ጉዞው ተዠመረ ። ምንም እንኳን ለጠቅላላው የበላይ ጠባቂነት የራስ መኰንን ቢሆንም ፣ እርሳቸው ደግሞ ፊታውራሪ ደሳለኝን በቅርብ ሆነው እየጠበቁ አዲግራት እንዲያደርሱት አዘዋቸው ነበርና በማናቸውም ዝርዝር ጉዳያቸውን ጣልያኖቹ በአቶ ወልደ አማኑኤል አስተርጓሚነት ይጠይቁ የነበረው ፊታውራሪ ደሳለኝን ነበር ። ለፊታውራሪ ደሳለኝም ረዳት ከዚህ በፊት በዕርቅ ምክንያት ወደ መቀሌ ምሽግ ተመላልሰው የነበሩትና ከጋልያኖም የተዋወቁት ብላታ እንግዳ የሚባሉ ነበሩ ።

እ.ኤ.አ. ጥር 22 ቀን ወደ ማታ ጋልያኖ ከነጓዙ ሰፈሩን ለቆ በራስ መኰንን ጦር እንደ ተከበበ ፣ የኢትዮጵያን መኳንንት የበረከቱ ድንኳኖች እያቋረጠ ወጥቶ በቅርብ ከሰፈረ በኋላ ፣ በማግሥቱ እዚያው ውሎ ሆኖ በጥር 24 ቀን እሱና ጦሩ ጉዟቸውን ቀጥለው የንጉሠ ነገሥቱ ቀዩ ድንኳን የተተከለበትን የማሳቦን ሜዳ እያዩ ወደ ማይመኸያን አመሩ ። በዚህ ዓይነት በየመንገዱ እያረፉ በጥር 28 ቀን አይባ ደርሰው ሳለ ፣ በመካከሉ አስቀድሞ እንደተነጋገሩት ስለእርቅ ጉዳይ ከባራቲዬሪ ትልቅ ሰው ተመርጦ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ ነበርና ሳይመጣ ስለዘገየ ራስ መኰንንም አይባ ላይ ሰፈሩ ። ጋልያና እስከ ድንኳናቸው ድረስ እየሔደ ፣ "ጉዟችን ዘገየብን" እያለ ሲከራከር እርሳቸውም ፣ "ባራቲዬሪ ማገርር ሳልሳን አልካለሁ ብሎ እስካሁን ባለመላኩ ቃሉን አልጠበቀም" እያሉ ሲመልሱ ቆዩና በመጨረሻ ሹማምንቱ መያዣ ሆነው እንዲቆዩ ተደረገ ። ጋልያኖና ጓዙ በፊታውራሪ ደሳለኝ መሪነት ወደ አዲግራት ጉዟቸውን ቀጥለው በሐውዜን አልፈው እዳጋ ሐሙስ ደርሰው የሁለት ሰዓት ዕረፍት አደረጉ ። አዲግራት በናፍቆት የሚጠበቀው ጋልያኖና ጓዙ እዳጋ ሐሙስ የመድረሳቸው ወሬ ሲሰማ ፣ ጠቅላይ አዝማቹ ሌተና ጄኔራል ባራቲዬሪ ራሱ እንደ ታጀበ ጋልያኖን ለመቀበል ጉዞ ጀምሮ በጥር 30 ቀን ተገናኙ።

በመንገድ በተገናኙ ጊዜ ፣ ጄኔራሉ ከፈረሱ ላይ ወርዶ አንገቱን እንቆ ሲስመው ሌሎቹ የጦር አለቆች የቀሩትን እያቀፉ ይስሙ ነበር ። "የኢትዮጵያ ጦር በወሃ ጥም ይጨርሳቸዋል እንጂ በዋዛ አይለቃቸውም ። ከምሽግም እንዲወጡ ያደረገው በእጁ ከገቡ በኋላ እንደ

ልቡ ለመፍጀት ቢል ነው ። አልነካቸውም ብሎ ቢምልም ፣ ቃሉን ሊያከብር አይችልም” የሚል እምነት በኢጣልያኖቹ ዘንድ ነበርና አሁን በዚህ ዓይነት ሁሉም በደህና ሁኔታ ደርሰው ከፊታውራሪ ደሳለኝ እጅ በክበረታና በሐቅ ሲረከቧቸው ከደስታ ጋር መደነቃቸውን አልደበቁም ። ከዚያ ጄኔራል ባራቲዬሪ ከፊታውራሪ ደሳለኝ ጋር መያዣ ሆነው ወደ ኋላ ስለቀሩት ሹማምንት ወዳጄ ምኒልክ ስለሚላከው ባለሥልጣን አጭር ንግግር ካደረጉ በኋላ ፣ በፈረሱ ላይ ወጥቶ በጐን የሌተና ኮሎኔልነት ማዕረግ የተቀበለውን ጋልያኖን አድርጎ ጉዞውን በመቀጠል ወደ ዋናው ሰፈሩ ወደ አዲግራት ሔደ ። እዚያም በደረሱ ጊዜ የጦር ሠራዊቱ በሙሉ በሰልፍ በብረት ሰላምታ ሲያቀርብ ለዚህ ሰላምታ መልሱን ይሰጥ ዘንድ ጄኔራሉ በፈቃዱ ለማስከበር ሲል ለኰሎኔል ጋልያኖ ተወለት ።

ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት በሰልፍ ፣ በሙዚቃና በዘፈን ከተፈጸመ በኋላ ፣ ቁስለኛውንና ደካማውን ወደ ሆስፒታል የማስተኛቱ ፣ ለተራቆቱት ወይም ልብሳቸው ለተጐሳቆለው ለነጭና ለጥቁር ወታደር ልብስና ጫማ የማደሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ ፣ እነዚህ የኤርትራንና የኢጣልያንን አገር ወሬ ሲጠያየቁ ፣ እነዚያ ደግሞ በ43 ቀን ውስጥ በመቀሌ ምሽግ ስለ ተደረገው ጦርነት ፣ ስለ አወጣጣቸውና ስለ ጠቅላላው ሁኔታ ማወቅ እየፈለጉ ሲጫወቱ ሰነበቱ ።[1] በኢጣልያ አገር የጋልያኖ ከመቀሌ ወደ አዲግራት ለመሔድ መቻል እንደ አንድ ታላቅ ድል ተቆጥሮ ሰሞኑን ሕዝቡ ሁሉ በዘፈን ፣ በደስታና በዕልልታ በዓል አድርጎ ስላከበረ ፣ ዶሚኒኮ ፉሪኒ የሚባለው ጸሐፊ ፣ “የኢጣልያን ሕዝብ ዘፋኝነትና ቀላልነት ያሳያል” ሲል ከተቸ በኋላ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ፣ “በመቀሌ ምሽግ ተከላክለው ወደ አዲግራት ለተመለሱት ልዩ ኒሻን ተዘጋጅቶ ይሰጥ” የሚል አሳብ ለምክር ቤቱ ቢያቀርብ ሲድኔይ ሶኒኖ የሚባለው አባል ፣ “ለተሸነፉት ይኸ ይሰጥ ካልክ ላሸነፉት ምን ልትሰጥ ነው” ብሎ አፌዘበት ።[2]

---

1 L' Assedio di Maccalle, V. Mantegazza, PP. 398 - 428 ; Memoire d' Afrique, O. Baratieri , PP. 322 - 330; Gli Italiani in Africa Orientale, A.Del Boca, PP. 624-657.

2 Gli Italiani in Africa Orientale PP. 626 -627.



# ክፍል አራት

## የዓድዋ ጦርነት

## ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

### የኢትዮጵያ ጦር ከመቀሌ ወደ ዓድዋ መዛወር—ስለ እርቅ ጉዳይ ማጆር ሳልሳ ተልኮ ወደ ዐፄ ምኒልክ እንደመጣ

በመቀሌ ምሽግ መለቀቅ በተደረገው ስምምነት ሁለቱም መንግሥታት ተጠቅመዋል ማለት ይቻላል ። የኢጣልያ ጥቅም አንደኛ በስምምነቱ ሰበብ ከኢጣልያ ለሚመጣው ጦር የመዘጋጃ ጊዜና ሁለተኛ በውሃ ጥምና በረኃብ ሊያልቅ የነበረውን አንድ ክፍል ጦር ከነመሣሪያው በደህና ማግኘቱ ነው ። የኢትዮጵያ ጥቅም ደግሞ በማናቸውም ረገድ በተለይ ለትግሬ እንደዋና ከተማ የሚቆጠረውንና ያፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የሚገኝበትን መቀሌን አስለቅቆ ጠላትን እስከ አዲግራት ድረስ መግፋቱ ከአላጌ ጦርነት ወዲህ ይኸኛው ደግሞ እንደ ሁለተኛ ድል መቆጠሩ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ሁልጊዜ ደም ሳይፈስ ጠላትን ካገር አስወጣለሁ የሚለው ተስፋ ፈጽሞ ከአሳባቸው ስለ አልጠፋ ፣ የስምምነቱን ጉዳይ ወደ ፍጻሜ ሳያደርሰው ለፌልተር ፣ “የሰው አገር እወስዳለሁ ብሎ የመጣ እንድባ ገብቶ በውሃ ጥም እያልቅም . . . አሁንም በከንቱ አይለቁ ፤ ሰዎችህን ልከህ አስወስድ ፤ ትዋጉም እንደሆነ አንድነት ተሰብስባችሁ ቆዩኝ ፣ እኔም እመጣለሁ” የሚል በራሱ የመተማመንና የከረረ ቃል ነገረው ወደ ባራቲዬሪ ከላኩ ወዲህ ፌልተርም ፣ “እኔ የመጥቀል ሥልጣን የለኝም ፣ ሌላ ትልቅ ሰው ይመጣል” ብሎ ቃል ሰጥቶ ነበር ። ነገር ግን ፣ ጣልያኖቹ ጊዜ ለማግኘት እንጂ ሰላም ለማድረግ በፍጹም ስለማይፈልጉ ፣ ለወሬ ያህል ይመጣል የተባለው ሳይመጣ በመዘግየቱ ከጋልያኖ ጭፍሮች ውስጥ ዘጠኝ መኰንኖች እንደ መያዣ ቀይተው ነበር ። እነዚህም “ግደሉም ይሒዱ” ተብለው በመጨረሻ ተለቀው ወደ ወገኖቻቸው ሔዱ ። በኋላም ባራቲዬሪ ስለ ሰላም ለመጥቀል ትልቅ ሰው ይላካል ያለውን በማመን ዳግማዊ ምኒልክ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ከንራስ መንገሻ አቲከም ፣ ይልቁንም የውጭ ጉዳዩን ተግባር ከሚፈጽሙት ከራስ መኰንን ጋር ተመካከረው

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለኢጣልያ ንጉሥ ጽፈው ለባራቲዬሪ ላኩለት ።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ. . .ለግርማዊ ኡምቤርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ሰላም ለርስዎ ይሁን ። ስላምና ወዳጅነት መፈለግዎን ጄኔራል ባራቲዬሪ ስለነገረኝ ደስ ብሎኛል ። የራሴን የክርስቲያንነት እምነት ለመግለጽ ስል በእንዳ ኢየሱስ ምሽግ ተከበው ተጨንቀው በወሃ ጥም አልቀው በአግራችን ውስጥ ሊረገጡ የቀረቡትን ከነዕቃቸው በመልካም ሁኔታ በራስ መኰንን ሽኝነት አስወጥተን ሰደድናቸው ። አሁንም ተነጋግሮ ስለ ሰላም ሊዋዋል የሚፈልጉትን ሰው ያስታውቁኝና እኔም ጠቡ ቀርቶ ስለ ሰላም የሚነጋገረውን ወኪሌን አደርጋለሁ ።

ይኸን ከጻፉና ለንጉሡ ይልክ ዘንድ ለባራቲዬሪ ከላኩ በኋላ ፥ ዳግማዊ ምኒልክ ከሰፈሩበት ከመቀሌ በማግሥቱ ተነሥተው ወደ ሐውዜን ፥ ከሐውዜን ወደ ፈረስ ማይ ፥ ከፈረስ ማይ ወደ ሳውሪያ ፥ ከዚያም ወደ ግራቸው ታጥፈው በገንደብታ አድርገው ዓድዋ ገብተው በተለይ ዬሐ ከሚባለው ጥንታዊና ታሪካዊ ቦታ ሠፈራቸውን አደረጉ ። ሐውዜን የነበሩ ጊዜ ወደ አዲግራት ስለቀረቡ ፥ ይወጉናል የሚል ፍራቻ ኢጣልያኖቹ አድሮባቸው ለጦርነት መሰናዳት ይዘው ነበር ።

ዋናው አዝማች ፥ ያዬ ምኒልክን ደብዳቤ ራሱን ወደ ሮማ ለመላክ ጊዜው አጣዳፊ ስለሆነ ፥ የደብዳቤውን አሳብ በቴሌግራም አስታውቆ በጠቅላላው የመንግሥቱ አሳብ ምን እንደሆነ እንዲገለጽለት በጥር 28 ቀን ጠይቆ ስለነበረ ፥ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከባሮን ብላን ዘንድ እንደዚህ የሚል ቃል ዕለቱን መጣለት ።

> ባሁኑ ለጦርነት በተሰለፍንበት ሰዓት ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ላይ የሚኖረንን አቅዋማችንን የሚያረጋግጥ አንድ የጦርነት ድል ኢጣልያ ሳታገኝ አሁን በሚደረገው የስላም ውል ምንም ዐይነት ጥቅም እንደ ማይገኝ የንጉሡ መንግሥት ያምናል ።[1]

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ደግሞ በበኩሉ ፥ "እምባ አላጌና መቀሌ ክብር ቢኖረውም ፥ ሁለት ውድቀት ያገኘንባቸው ናቸው ። የኢጣልያ የንጉሡ ክብር በእጅህ ነው ያለው" ሲል አስተላለፈለት ። ትርጓሜው በአላጌና በመቀሌ መካከል ምንም እንኳን የኛዎቹ ክብር ያለው የመከላከል ሥራ ቢሠሩም ፥ መጨረሻው መሸነፍ ስለሆነ እንደ ምንም ተዋግተህ አሸንፈህ አንድ ድል አግኝተህ ክብራችንን አድስ የሚል ነው ። በነዚህ ዐይነት ከዚህ ከሁለት የኢትዮጵያ ድሎች በኋላ አንድ የመመለሻ ድል በጣም እንደ ናፈቃቸው ይታያል ።

1 Italia ed Etiopia . . Conti - Rossini . . . PP. 257 - 264; Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca, PP.629 -630; The Campaign of Adwa and the Rise of Menelik, Chap. VII, PP. 217 -238.



ስለዚህ ባራቲዬሪ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ወደ ዓድዋ ሲጓዝ ፥ ሐውዜን በሰፈረበት ጊዜ ከአዲግራት ወጥቶ መዋጋት እየዳዳው ፥ ማሸነፍም እየጓጓ ደግሞ እየፈራና እያመነታ ፥ በዚሁ መካከል ጠቅላይ ሚኒስትሩም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም ጦርነቱን እየገፉፉ ለሚያስተላልፉለት ቴሌግራም እርሱም በበኩሉ የኢትዮጵያን የጦር ድርጅት እየ ጠቀሰ በሌላው ወገን ደግሞ ፥ በገዳሪፍ ደርቡሾች ለውጊያ መሰብሰባቸውን በመግለጽ ለጊዜው ውጊያው አስቸጋሪ መሆኑን ገልጾ ነበር። በዚህም ዓይነት ብዙ ውዝግብ ካለቆቹ ጋር ከገጠመ በኋላ መደ ምደሚያውን ከኢትዮጵያ ጋር የእርቅ አሳብ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተነድፎ ቀደም ብሎ ተልኮለት ነበር ። ከሮማ የተላከው ኩራትና ዕብሪት የተሞላበት የዕርቅ ድርድር የሚከተለው ነው ።

፩ኛ. የኢጣልያ መንግሥት እስከ አሸንጌና እስከ ተከዜ ድረስ ሙሉ ትግሬን ጠቅሎ በቀጥታ ገዥነት እንዲኖረው ፥

፪ኛ. የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ በቀረው እስከ ሱማልያ ፥ ከወዲህም እስከ አሞ ወንዝ መጨረሻ ድረስ ባለው በኢትዮጵያ ግዛት ላይ የበላይነቱ እንዲታወቅ ፥

፫ኛ. ለውጭው ዓለም የኢትዮጵያ ወኪልና ጠባቂ ኢጣልያ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅና በኢትዮጵያ ያሉ የውጭ አገር ሰዎች (ይኸውም ማለት ለኢትዮጵያ የሚረዱት የመስኮብና የፈረንሳይ ተወላጆች) እንዲወጡ ፥

፬ኛ. ንጉሠ ነገሥቱና የአውራጃ ገዥዎች ቁጥሩን ከሚወስንላቸው አልፈው የኢጣልያ መንግሥት ሳይፈቅድ ወታደር እንዳያደራጁ፥

፭ኛ. ራሶችና ያውራጃ ገዥዎች ከመሾማቸው በፊት ለፈቃድ የኢጣልያ መንግሥት እንዲጠየቅ ፥

፮ኛ. በኤርትራ አንድ ወራሪ ቢመጣ ንጉሡና ራሶቹ ኃይላቸውን ይዘው ወጥተው እንዲረዱ ፥

፯ኛ. በንጉሡና በራሶቹ መካከል ፥ በራሶቹና በሹሞቻቸው መካከል ክርክር ቢፈጠር ጉዳዩ ለኢጣልያ መንግሥት ቀርቦ እንዲወሰን የሚል በ7 አንቀጽ ላይ የተመደበ ነበር ።[1]

ጄኔራል ባራቲዬሪ ይኸን የመሰለ የማይታሰብ የስምምነት አሳብ ቢደርሰውም ፥ ራሱ እንደ ገለጸው በነጻነቱ የሚኮራና ተዋጊ ሕዝብ የተዘጋጀ ጦር እያለው ተዋግቶ ከመሸነፉ በፊት ይኸን የመሰለውን

1 Tomasso Salsa, E Canevari E Comisso PP 288—290

አሳብ እንደማይቀበል ስለሚያውቅ ፣ ይኸንኑ ከበላዮቹ ጋር በምስጢር ሲነጋገርበት ቆይቶ ነበር ። የበላዮቹም ኢትዮጵያን ገና ከመጀመሪያ እንደ ራሳቸው ይዞታ በመቁጠር በአሳጊና በመተሌ መሸነፋቸው እየቆጠቆጣቸው ፣ ይኸ ሁሉ ሁኔታ ሊታደስ የሚችለው ከዚህ በላይ ያለው ጥያቄ ሲፈጸም ብቻ ነው የሚል አሳብ ነበራቸው ። ነገር ግን ፣ ባራቲ ፍሬ እንደ ምንም የቀረበውን አሳብ አስቀርቶ ጉዳዩን ከሁለት መድቦ አቀረበ።

፭ኛ. የውጫሌ ውል ታድሶ እንዲረጋ ፣

፮ኛ. የኢጣልያ ባንዲራ እስከ ተሰቀለበት ድረስ ያለው አገር ለኢጣልያ እንዲሰጥ ።

የሚል አሳብ ባጭሩ አዘጋጅቶ በማግሥር ሳልሳ እጅ እ. ኤ. አ. የካቲት 11 ቀን 1896 ወዳጼ ምኒልክ ላከ ። ማግሥር ቶማስ ሳልሳ በዚህ ጊዜ ዋና የፖለቲካውን ክፍል የሚመራ የታወቀ ወጣትና ብልህ የጦር መኰንን ነው ። ምክትል ሹፍ ዴታ ማግሥሩም እርሱ ነው ። ከርሱም ጋር ካፒቴን አንጌራ የሚባለው የኢጣልያ ጦር መኰንንና የታወቁት አስተርጓሚ ገብረ እግዚአብሔር አብረው መጥተዋል ። ነገር ግን ፣ ስብሰባውን በምንም አኳኋን አልተካፈሉም ። በነ ማግሩም ጊዜ ዋናዎቹ የንጉሠ ነገሥቱ አስተርጓሚዎች ግራዝማች ዮሴፍና አቶ ወልደ እግኑኤል ናቸው ። ወደ ፍሬው ነገር ከመግባታችን በፊት ከአዲግራት ወደ ዓድዋ (ፍሃ) መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር የሰነበተ ጊዜ ያየውን ራሱ ማግሥር ሳልሳ ኢጣልያ አገር ላለው ለወንድሙ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ያሰፈረውን መመልከቱ ይጠቅማል። ቃሉ እንደዚህ የሚል ነው ።

ውድ ወንድሜ ሆይ . . . መንግሥታችን ምንም እንኳን ሊሆን የማይችለውን ውል ጨምሮ ዕርቅ እንድናደርግ ቢፈትድ አገረ ገዥው (ባራቲየሪ) ይኸንን ዕርቅ እንድፈጽን ሳይሆን የቀረው ቢቀር አገረ መንግሥትን የጠላትን ኃይልና አቀማመጥ እንድመለከት አዞኝ ወደዚያ ስሔድ መጀመሪያ ከራስ መኰንን ሰፈር ደረስሁ ። እዚያም ሆኜ ባለቆቻቸው ዙሪያ በደንብ የተተከሉትን 2500 ድንኳኖች ያሉበትን ሰፍራ ተመለከትሁ ። ከእም ጋር ካፒቴን አንጌራ ነበር ። ራስ መኰንንም ምንም እንኳን ቢታመሙ ፣ በተለ በፍቅር መልክ ተቀብለውን የመግባበትንም ጉዳይ ባጭሩ ከተነጋገርን በኋላ መሪ ሰጥተው ወዳጼ ምኒልክ ላኩን ። . . . 2 ኪሎ ሜትር ስፋት 5 ወይም 6 ኪሎ ሜትር ቁመት ባለው በዮሃ ረባዳ ስፍራ ላይ ከራስ መኰንን ሰፈር በስተጀርባ ስንደርስ አስደናቂውን የንጉሡን ሰፈር አየን ። ሹለቆዎቹና ስፍራዎቹ በሙሉ በድንኳን ተሸፍነዋል ። የድንኳኖቹም ቁጥር 20000 ይመስለኛል ። የነርሱም የትልቅነታቸው መጠን የቀለማቸው ዓይነት ልዩ ልዩ ነው ። አብዛኛው ነጭ የቀረው ጥቁር የሸዋ ጨርቅ ነው ። በረባዳው ስፍራ ከመካከል ልዩ ልዩ የሚያማምር ቀለም ያላቸው ከከበረ ጨርቅ የተሠሩት የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳኖች አሉ ። ቁመታቸው 2 ሜትር ተኩል ሆኖ በዚያው በድንኳኑ ዙሪያ ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ትልቅ



የዙሪያ መጋረጃ ክፍል አለ ። የውስጠው ክፍል የጨርቅ ፣ የውስጠኛው ንጉሡ ታላላቅ ሰዎችን የሚቀበሉበት የሐር ነው ።

ንጉሡ እስካሉበት እስከንደርስ በምናጸርጥበት ሰፈር ሰው ሁሉ በመገረም ይመለከተን ነበር. . . ሰፈሩን ሰናልፍ እጅጋ ሥሉስ ከሚባለው ገበያ ደረስን ። በዚህም ገበያ 5 ወይም 6 ሺህ የሚሆኑ ወታደሮች እህልና ጨርቃ ጨርቅ በትልቁም ይገበያዩ ነበር ።

በንጉሡ ድንኳን አጠገብ ትንሽ ደቂቃዎች እንደ ቆየን ዐፄ ምኒልክ ወዳሉበት ገባን ። እርሳቸውም በአንድ በወርቅ የተሠራ ልብስ በለበሰ መከዳ ላይ. . .ተቀምጠው ባሉበት ክፍልም የፈረንሣይና የሩሲያ ብዙ ሥጋጃዎች ተነጥፈው ነበር ። 2 የእንጨት ባለቆዳ ወንበሮች ነበሩ . . . በንጉሠ ነገሥቱም ዙሪያ ራሶች ተቀምጠው ነበር ። ንጉሡና ከነርሱም ትራ ጥቁር በርኖስ ለብሰው ራሳቸውን ሻሽ አስረው ሲታዩ በንጉሡ በስተጀርባ በልዩ ልዩ ልብስ ያጌጡ አለቆች ቆመው ነበር ።

ምኒልክ በፍሡሕ ገጽ ከተቀበሉኝ በኋላ ፣ እንደ አውሮፓ ደንብ እጃቸውን ዘርግተው ጨበጡኝና ቀኖሉ እወንበሩ ላይ እንድቀመጥ አመለከቱኝ ። ትንሽ የሰላምታ ንግግር ከተለዋወጥን በኋላ ፣ ሒዱ ትንሽ ዕረፉና በኋላ እንነጋገራለን ብለው ሲያሰናብቱንም እንደዚሁ በደስታ እጃችንን ጨበጡን ። በዚህ በመጀመሪያው ግንኙነት ከምኒልክ በቀር የቀሩትን ራሶች በጨረፍታ እንኳ ደህና አድርጌ አልተመለከትኳቸውም ። እነርሱም (እኔና ምኒልክ በምንነጋገርበት ጊዜ) አንድ ጊዜም ንግግር ከአንደበታቸው አልወጣም ። ምኒልክ 53 ወይም 54 ዓመት ዕድሜ እያላቸው ከ40 ዓመት ትንሽ የሚያልፉ ይመስላሉ ። ቆዳቸው ብዙ ጥቁር አይደለም ጢማም ናቸው ፤ ጢማቸውንም በመጠኑ ሽበት ወርታል ። ደስ የሚያሰኝ መልክ(ገጽታ) አላቸው ።. . . ከብዙ አስደሳች ሁኔታ ጋር ፣ ሲነጋገሩ ደጋግመው ፈገግታ እያሳዩ ነው ። . . .ከዚያ ወጥተን ወደ መድፈኞች አለቃ ወደ በጅሮንድ ባልቻ ዘንድ. . .ሔደን ባበሻ ደንብ ቁርስ አደረግን . . . ቀድሞ የማውቃቸውንም ሹማምንት አግኝቼ እኔ ያመጣሁትን ወይን ጠጅ አብረን ጠጣን ። በዚሁም ጊዜ ንጉሡ ሳያስጠሩን ብዙ ሰዓቶች አለፉ ። በመጨረሻው አንድ ሹም መጥቶ "በንግግሩ ላይ ራስ መኰንን እንዲገኙ ፈልጌ ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ቢጠራም ሰጊዜው ስለታመመ አልቻለምና ለዛሬ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ቢሆንም መጥታችሁ ሰሰላምታ ብንገናኝ መልካም ነው" የሚል የንጉሡን ቃል ነገር ይዞን ሔደና ሰላምታ ተሰጣጣን ። ከዚያም ጉዳዩ በመዘግየቱ ይቅርታ ጠይቀው አሰናበቱንና ወደ በጅሮንድ ባልቻ ድንኳን ሔደን ወደ 12 ሰዓት ግድም እራት ተጋበዝን ። በዚያም ጭውውት ተደርጎ በየሸለቆው የሚታየውን የሰፈር እሳት በአድናቆት ከተመለከትን በኋላ ወደ መኝታችን ሔድን ። በማግሥቱ በ2 ሰዓት ተኩል ተጠርተን ከራስ መኰንንና ከአቶ(ፊታውራሪ) ሀብተ ጊዮርጊስ ጋር በንነጋገር ሁለቱም አለቆች ንጉሡ ወዳሉበት ድንኳን እየሔዱ ንግግሩ 4 ሰዓት ሙሉ ፈጀ . . .በመጨረሻ ንጉሡን ለመሰናበት በሔድን ጊዜ በንጉሡ አጠገብ ከንጉሡ መቀመጫ ዝቅ ያለ ተደርጎላቸው የተቀመጡት ንግሥ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ ። ሰውነታቸው ወፍራም . . . ነው ። መልካቸው ግልጽና አስደሳች ፣ ዓይናቸው የብልህ የሆነው

የወሎው ራስ ሚካኤል ጢማቸውን ያሳደጉት ራስ መንገሻ (ዮሐንስም) ሰውነታቸው ጠንካር ፣ የራስ ጠጉራቸው ጢማቸው አጠር ያለው መልካቸው የሚያስፈራው ራስ አሉላ ነበሩ ።

ለመሔድ ተሰናብተን በየበቅሎቻችን ከወጣን በኋላ አንዳንድ ሹሞች በንጉሡ ቃል የምንነግራችሁ አለና ቆዩ እያሉ ሰበብ እየፈለጉ ሊያቆዩን አስበው ነበር ። እኔ ግን ፣ በከንቱ ጊዜ መፍጃ መሆኑን ተረድቼ መንገዴን ቀጠልሁ ።. . .[1]

ማዡር ሳልሳ ፣ ይኸን ደብዳቤ ኢጣልያን አገር ላለው ወንድሙ ሲጽፍ ያየውን ቀላሉን ነገር እንጂ ስለእርቁ ጉዳይ የተነጋገረውን ፍሬ ነገር አይገልጽም ። ምክንያቱም የእርቅ ነገር በዚያን ጊዜ እንደ ምስጢር የሚታይ የመንግሥት ጉዳይ ስለሆነ ነገሩን ላለማባከን መሆኑ የታወቀ ነው ። ነገር ግን ማዡር ሳልሳ ዓፄ ምኒልክ ወይም ለራስ መኰንን ያቀረበው ያው ከዚህ ቀደም ያነበብነው ነው ። ይኸንንም አሳብ ዐፄ ምኒልክ በፍጹም ሳይቀበሉት ቀርተው እንደ መለሱት ጄኔራል ባራቲዬሪም ፣ ማዡር ሳልሳም በኋላ ዘመን ባዘጋጁት ጽሑፍ ይገኛል ። በኛም በኩል ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በጻፉት መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ቀጥሎ ያለው ነው ።

. . . ከዚህ በኋላ ለኢጣልያ ወታደር ስንቅና ገንዘብ* ማዡር ሳልሳ ጸሐፊውንና ትንሽ አበሻ ብዙቅ ወታደር አስከትሎ መጣ ። የኛ ወታደር እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበረከተውን በሩቅ የሚታየውን ጦራችንን በዐይኑ አይቶ ለመሰለልና ለመገመት እንጂ ምናልባት ለእርቅ ብቻ አልመጣም ። ለርሱም በበጅሮንድ ባልቻ ሰፈር ድንኳን ተተክሎለት ነበር ። ሲመሽም ጠጅም የጮማ ከብት ዳቦ (እንጀራ) ለራት ተላከለትና በክብር አስተናገዱት ። የመጣለትም እቴጌ ጣይቱ "ይህ ሰው ለስለላ እንጂ ለእርቅ የመጣ አይመስለኝም" ብለው ለባለሟሎቻቸው ተናግረው ነበር ። በማግሥቱ ባዳራሽ ሥጋጃ ተነጠፈ ። ዐፄ ምኒልክንም ፣ ራስ መንገሻ አቲከምን የሳይንትን ገዥ ፣ ራስ መኰንንና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን ጠሩዋቸው ። እነርሱም ከንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ከተቀበሉ በኋላ ማዡር ሳልሳ ወደሚገኝበት አዳራሽ ሔዱና የመጣበትን ምክንያት ጠየቁት ። እርሱም "ከዚህ ቀደም ባንዲራችን ተተክሎበት እስከነበረው እስከ አላጌ ድረስ ያለውን አገር ልቀቁልንና እንደገና ባንዲራችንን እንትከልበት" ብሎ ለገሮም ለልብም ደስ የማያሰኝ መልስ ሰጠ ። ለንጉሠ ነገሥቱም ሊያቀርብ ያሰበው የዕርቅ አሳብ ይህ መሆኑን ስለገለጸ ፣ ይኸው ቃል ላዔ ምኒልክ ተነገረና እንደዚህ የሚል የንጉሠ ነገሥቱ መልስ ተሰጠው ። "እኔ የመጣሁት እናንተ የተከላችሁትን ባንዲራ ለመንቀልና ለመጣል ነውና ይኸን የመሰለውን የሰላም ውል አልቀበልም. . . በተረፈ ግፍ

1 Tomasso Salsa, E. Canevari E. Comisso, PP. 288-290.

* የሰንቅና የገንዘብ ኃላፊ የሆነውን ለማለት ነው ፤።



የማይወደው በእግዚአብሔር ተማምኜ በመጣችሁበት መንገድ እቀበላችኋለሁ ። በአገሬ በኢትዮጵያ ላይ የሮማ ሰንደቅ ዓላማ እንዲተከልበት አልፈቅድም ።"

ከዚህ በኋላ ፣ ማዡር ሳልሳ ተሰናብቶ ሲሔድ ራስ ቢትወደድ መንገሻ ወደ እቴጌ ጣይቱ እልፍኝ ገብተው ማዡር ሳልሳ የጠየቀውን ነገሩዋቸው ። በዚያን ጊዜ እቴጌዪቱ ፣ "የእሥራኤል አምላክ ሆይ ይኸን ግፍ ተመልከት ፣ በመድፋቸውና በጠበንጃቸው ተመክተው የፈቀዳቸውን ተናገሩ ፤ እኛም በክርስቶስ ኃይል እንፈራቸውም" ብለው በራስ ቢትወደድ ፊት ተናገሩ ።

ማዡር ሳልሳም ከንጉሡ ከተሰናበተ በኋላ ፣ ሰፈሩን እስኪወጣ ድረስ በበጅሮንድ ባልቻ እየተሸኘ ወጣና ወደ አለቃው ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ ተመለሰ ።[1]

ይህ በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ የሚገኘው አነጋገር ታሪኩ ባራቲዬሪም ሳልሳም ከጻፉት ጋር ይጋጠማል ። እንዲያውም ሳልሳ የእርቁን ቃል በራስ መኰንንና በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አማካይነት ብቻ መሆኑን ሲጽፍ ጸሐፌ ትእዛዝ ፣ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም መኖራቸውን በመግለጽ አብራርተውታል ። የሆነ ሆኖ ማዡር ሳልሳ ካዔ ምኒልክ የተቀበለውን ቃል ለጠቅላይ አዛዡ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ከአስረዳ በኋላ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ግራዝማች ዮሴፍ ያቆዩንን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፎ ለጦርነት ይዘጋጅ ጀመር ።

ትብጻህ ኀበ ጥቀ ልዑል ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተላከ ከጄኔራል ባራቲዬሪ የመንግሥት ታላቅ መኰንን የኤርትራ ግዛት ገዥ እግዚአብሔር ለጃንሆይ ሰላምና ጤና ይስጥልኝ ። ጃንሆይ ለመንግሥታችን የሰደዱትን ማዡር ሳልሳ ቃል በቃል ነገረኝ ። ጃንሆይ ይህ ይሁንልኝ ብለው የተናገሩትን መንግሥታችን ሊቀበለውና ነገሩንም በእንዲያው ሊያስረዝመው አይችልም ፤ ጃንሆይ የኔ መንግሥት የሚፈልገውን ውል ያውቃሉ ። የኢጣልያ መንግሥት ጃንሆይን ደስ ለማሰኘት የእርቁን ነገር ለማድረግ አንድ ሰው ሰደደ ። ተስፋም አድርጎ ነበረ ለኛና ለጃንሆይ አንድ የሚጠቅም ነገር ለማድረግ እንዲህ ከሆነ የእርቁ ነገር እንደቀረ ይቁጠሩት ። ከኛ እያንዳንዱ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ይሆንለታል ።[2]

በዚህ ደብዳቤ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ የዕርቁን አሳብ ለዘለቄታው እንደ ዘጋው ያመለክታል ። በደብዳቤው መጨረሻ ፣ "እንዲህ ከሆነ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ.62 ገጽ 252-254

2 ከሞንዶን ቪዳዬ ዶሲዬ ፣ ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቁ. 82
Memoire d' Afrique, PP. 346-355

የዕርቁ ነገር እንደቀረ ይቁጠሩት ። ከኛ እያንዳንዱ የፈለገውን ነገር ለማ ድረግ ይሆንለታል” ማለቱ ፤ ከጠረፍ እስከ አላጌ ድረስ ሙሉው የት ግሬ ግዛት ካልተሰጠን ጦርነት ለማድረግ መዘጋጀታችንን ይወቁት ማለቱ ነው ። ለዚህ ደብዳቤ ዐፄ ምኒልክ መልስ መስጠታቸው በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ፤ በጄኔራል ባራቲዬሪም በሌላም መጽ ሐፍ አልተገኘም ። የሆነ ሆኖ ፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሁለቱም ወገኖች አሳብ ለአሳብ በግልጽ ስለ ተዋወቁ ከቀድሞ የበለጠ ለጦርነቱ ይዘ ጋጁ ዠመር ።[1]

1 Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca, PP. 633-636.





ዐፄ ምኒልክ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ

ከኔላ ቴራ ዴ ንጉሥ ከተባለው መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሠላሳ አራት

## የንራስ ስብሐት ወደ ኢትዮጵያ ጐራ መመለስ — የአንቶኒሊ ማስጠንቀቂያ የኢትዮጵያ ጦር በግዳ ፤ የኢጣሊያ ጦር በምሽግ ለውጊያ ስለ መፈላለጋቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ በዩን ከእቴጌ ጣይቱ ፤ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ከሌሎችም ጋር በሰፈሩበት ሰዓት ሁለት አስደሳች ነገር ገጥሟቸዋል ። አንደኛው ፤ ከራስ መንገሻ የሐንስ ጋር ባላቸው ጠብ የተነሣ ለኢጣል ያኖች ገብተው ያገለግሉ የነበሩት የራስ ስብሐትና የደጃች ሐጎስ ተፈሪ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ጐራ መመለስ ነው ። ሁለቱም የስመ ጥሩው የአጋሜ ባላባት የደጃች ሰባጋዲስ ተወላጆች ስለሆኑ ፤ የአጋሜና ይነስ ይብዛ የእንደርታም ሕዝብ ስለሚከተላቸው ፤ እነዚህ ሁለት መኳንንት ቀድሞ ከኢጣልያ ጋር በነበሩበት ጊዜ በግናቸውም ረገድ በወታደር ምልመላ በስንቅ አቀራረብ በወሬ ስለላ ጣልያንን ይጠቅሙበት ከነበረው ጐራ አሁን ወደ ወገናቸው ሲመጡ ፤ ለኢትዮጵያ የሚሰጡትና በውነትም የሰጡት ጥቅም ብዙ ሲሆን በዚያው መጠን የኢጣልያን የጦር ጐራ ከፉኛ ጐድተውታል ። የኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒና ጠቅላይ የጦሩ አዛዥ ባራቲዬሪ ፤ “ኢትዮጵያ አንድነት የሌላት አገር ነች ። ጦርነቱ ገና ሳይዠመር የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ምኒልክን ከድተው ወደያውራጃቸው ይመለሳሉ ። ወይም ወደኛ ይገባሉ” ብለው ሲጠባበቁ ፤ ይልቁንስ ከነርሱ ጋር የነበሩት ወደአገራቸው ጐራ መግባት ጀመሩ ።

ሁለተኛው ያጼ ምኒልክና የመኳንንቱ ደስታ በአውላ የመሐመድ አንፋሪ የመሸነፉን ወሬ መስማታቸው ነው ። ጦርነቱም በጥር 12 ቀን ተፈጽሞ ይኸን ወሬ ለማብሰር ከአውሳ የመጣው መልእክተኛ ዩሃ ዐፄ ምኒልክ ዘንድ የደረሰው ፤ በየካቲት 22 ቀን የዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ ነው ። የዚህም ሁሉ ሁኔታ የኢትዮጵያን ወታደር ሞራሉን ከፍ እያደረገው ሲሔድ የኢጣልያኖችን ዝቅ እያደረገው መጥቷል ።

እስካሁን ድረስ ንጉሠ ነገሥቱን በጣም ያስቸገራቸው ፤ አንደኛ ኢጣልያኖች እንደዚያው እንደ መቀሌ በአዲግራት ፤ በእንቲጮና በሳውሪያ መሽገው ከምሽጋቸው ውስጥ ሆነው መጠባበቅ አንጂ ወደ

ሜዳ ወጥተው አለመግጠማቸው ፤ ሁለተኛ ጦርነቱን ከፈሩት ደግሞ
ታርቀው አገር ለቀው አለመሔዳቸው ፤ ሦስተኛ ቤቱን ንብረቱን ትቶ
ለጦርነት የመጣው ቁጥሩ ከ80,000 እስከ 100,000 የሚደርሰው
ጦርና የርሱ ተከታይ አሽከር ገረድ ቤቱን ለቆ ከወጣ አምስት
ወር ስለሆነው ፣ በዚህም ጊዜ የያዘው ስንቅ በሶውም ፣ ጭብጦውም ፣
ቆሎውም አልቆበት ስለሚራብና በዙሪያው የሚገኘውን አገር ፣ ትእ
ዛዝ እየተላለፈ ፣ በመዝረፍ ከባላገሩ ጋር ጠብ ማብቀሉ ፣ ያለበት
አገር በከብትና በእህል ረገድ ይኸን ያህል ስለማያወላዳ ፣ ተዋ
ጊውን ወታደር እየቀለበ ለከብቱም ሁሉ ሣር እያቀረበ ሊያዋጋ አይ
ችልም ። ከደቡብ አውራጃዎች እያጓዙ ወታደሩን የማጥገቡ ነገር
በዚያን ጊዜ የማጓጓዣው ድርጅት ጉድለት በተለይ ሰሩቅ አገር
የተሟላ ባለመሆኑ ችግር ፈጥሯል ። እስከዚህም እስከ አምስት ወራት
የተደረሰው በዚሁ በአህያና በአጋሰስ እየተጫነ ፣ በሰውም ትከሻ
ከሩቅ አውራጃዎች በሹማምንቱ ፣ በጭፍራው ፣ በገባሩና በገበሬው
ትጋትና ድካም የመጣ ነው ።

ዋና ስንቅ መስፈሪያው ወረይሉና ቦሩ ሜዳ ላይ ነው ። ከሸዋ
የሚመጣው ወታደር ሁሉ በያዘው ስንቅ ተጨማሪ ቦሩ ሜዳ ላይ
ተሰፍሮ እየተሰጠው ነው ጉዞውን ወደ ሰሜን ቀጥሎ እዚህ ሰዓት
የደረሰው ። ቦሩ ሜዳና ወረይሉ (ሆሪው) የስንቅ ኃላፊ የሆኑት ቢቶ
ደድ አጥናፌ ተክለ ዮሐንስ ፣ ከሸዋና ከየትኛውም ክፍል በከብትም
በሰው ትከሻም የሚመጣውን ዱቄቱንም ፣ ጥራጥሬውንም እየተቀ
በሉ ወደጦሩ ግንባር በመላክ ታላቅ አገልግሎት ማድረጋቸው ቢታ
ወቅም ፣ ጊዜው በተራዘመ መጠን ችግሩ በጣም እየከበደ ይሔዳል።

ዳግማዊ ምኒልክም ፣ መሳፍንቱም ፣ መኳንንቱም ፣ ወታደሩም በዚህ
ሁሉ ችግር መካከል ስለሚገኙ ፣ ይኸን ሁሉ ጦር ይዘው ንጉሠ ነገ
ሥቱ ወይ ካልተዋጉ ወይ ካልታረቁ ፣ እንደዚሁ ዝም ብለው ባሉበት
ሥፍራ ሰረጅም ዘመን መቆየት አይሆንላቸውም ። በዚህ ምክንያት
ከዩሃ ተነሥተው መረብን አልፈው ሐማሴንንና አከለ ጉዛይን ለመ
ውጋትና ከዚሁ ከኤርትራ በተለይ ከምጽዋና ከአሥመራ ወደ አዲግ
ራት ፣ ወደ ሳውሪያ ለዋናው የኢጣልያ ጦር ሠራዊት የሚመጣውን
የመጓሪያና የምግብ እርዳታ ለማቋረጥና ጣልያኖቹን አስገድዶ እንዲ
ዋጉ ለማድረግ ታስቦ በቅድሚያ እንሊቀ መኳስ አባተ ወደ መረብ
ቦታውን ለማጥናት ተላኩ ፤ እነርሱ ደግሞ ፣ "የመረብ ወሃ ስለ ደረቀ
እንኳን ለጀንሆይና ለሠራዊቱ ለእኛም እዚህ ላለነው አልበቃንምና
ጃንሆይ እዚያው ቢቆዩ ይሻላል" የሚል መልእክት አስተላለፉ ።
የነርሱንም ሐሳብ በኋላ እነራስ መንገሻ ዮሐንስ አጽድቀውታል ።



ስለዚህ አልፎ የመሔዱ ጉዳይ በወሃ እጦት የተነሣ ሳይሳካ ቀረ ።
አሁን በፊታቸው ያለው ወይ ከምሽጉ ድረስ ሔደው የኢጣልያን
ጦር መውጋት ወይም በልዩ ልዩ ዘዴና ወታደራዊ ንቅናቄ (ማነቨር)
የጠላት ጦር ከምሽጉ እንዲወጣ ማስገደድ ነው ። ወደ ምሽጉ
ሔዶ መዋጋት ሕዝብ ማስጨረስ መሆኑን ከመቀሌውም ጦርነት
ተምረውታል ። አሁንም በቅርብ ያሉት እነራስ መንገሻም ፣ ሌሎቹም
ወደ ምሽግ ተጠግቶ የመዋጋቱ ነገር እንዳይታሰብ በጥብቅ አስጠን
ቅቀዋል ።

ስለዚህ ፣ በኢጣልያኖች በኩልም ፣ "የኢትዮጵያ ጦር ወደ ምሽጉ
መጥቶ ካልወጋን በቀር ሜዳ ላይ ወጥተን አንችለውምና በተቻለ
መጠን ከምሽግ ወጣ እያሉና እየተነኳኩሱ ወደ ምሽግ በመመለስ በን
ዴት ወደ ምሽግ መጥቶ እንዲዋጋ ማድረግ ነው" እያለ ሰጣልያኖቹ
የሚመክረው ብዙ ነው ። በነርሱም በኩል ተመሳሳይ ችግር ስላለባቸው
እንዲያውም ፣ "ከምሽግ ወጥቶ ወደኋላ ወደ አሥመራ መመለስ
ይሻላል " ብለው አሳብ የሚያቀርቡም ነበሩ ይባላል ።

ከዚህ ቀደም እንዳመለከትነው ፣ በአርጀንቲና የኢጣልያ ወኪል
ሆኖ የተቀመጠው ኢትዮጵያን ዐውቃለሁ ባዩ አንቶኔሊም ካለበት
ከሩቅ አገር የሚልከው ምክር ይኸንኑ የሚያሳስብ ነው ። የዓድዋ
ጦርነት ሊደረግ ስምንት ቀን ሲቀረው እነራስ ስብሐት የኢጣል
ያን ጐራ ትተው ከመጡ ወዲህ ፣ ይኸው ሰውዬ እ. ኤ. አ.
የካቲት 21 ቀን 1896 ዓ . ም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በላከው ማሳሰቢያ
ውስጥ ፣

> "...ከዚህ በፊት ራስ ስብሐትን መጠርጠር ያስፈልጋል ብዬ
> በቴሌግራም አስተላልፌ የነበረው እነሆ አሁን ከሁለት ወር በኋላ
> መሸፈቱን (ወዳፄ ምኒልክ መዞሩን) ሰማሁ...አሁን በደረስንበት
> ሁኔታ በዚህ ዓመት በተቻለ መጠን ዓላማችን መከላከል እንጂ ማጥ
> ቃት የለብንም ። መቶ ሚሊዮን(ሊሬ) እንኳን ቢኖረን በዚህ ዓመት
> የኢትዮጵያን የቁማር ግዛት ማላመን አንችልም ። ከሁለት ወር በኋላ
> የዝናሙ ጊዜ ይዠምራል ። ከራት ወር በኋላ ደግሞ በሚያጥለቀልቀው
> ዝናም ወንዞቹ ሁሉ በጐርፍ ይሞሉና መንገድ ሁሉ ይዘጋል ። ከሌላ
> ስሕተት ላይ እንዳገና ካልወደቅን በቀር እንደ ምንም እየተከላከሉ
> ቆይቶ ምኒልክን ከነሠራዊቱ ወደ መጣበት ሲመለስ ማየቱ የተሻለ
> ነው ። በክረምቱ ወራት እስከ ጥቅምት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ
> ለሚመጣው ዘመቻ በፕላን መደራጀት ነው ። ባናበዛው ኖሮ ምኒልክ
> እስከዚህ ሊወጋንም ባልፈለገ ነበር ..."[1] የሚል ይገኝበታል ።

---

1 La Prima Guerra d' Africa, F. Crispi, PP. 295 - 297

ውስጥ ዐወቅ እንደ መሆኑ መጠን የአንቶኔሊ ምክሩ ተቃሎ የሚታይ አይደለም ። በእውነትም የኢጣልያ ጦር ከምሽግ ወጥቶ ባያጠቃ የዐፄ ምኒልክ ጦር ወደ ምሽጉ ሔዶ ማጥቃትም ፣ በትግሬም ያን ሁሉ ጦር ይዘው ለብዙ ጊዜ መቆየትም ስለማይሆንላቸው ነገሩ ግራ አግቢ ነበር ። ለውጊያው ተስፋ ቆርጠው ወደ ሸዋ ቢመለሱም ፣ ባንድ ወገን ከየካቲት ወይም ከመጋቢት እስከ ጥቅምት ባለው ጊዜ ውስጥ አዳዲስ ወታደር እየመለመሉ ከኢጣልያ አገርም ጦር ጨማምሮ ለመደርጀት ያመቻዋል ።

ራሱ ጠቅላይ አዛዥ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ በበኩሉ ከምሽግ ወጥቶ በሜዳ መዋጋትን ስለፈራ ፣ አበሾቹ እስከ ምሽጉ ድረስ ሔደው ቢወጉት ድልን እንደሚያገኝ ያምን ነበር ። በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ምኒልክ ካሉበት ከዬሃ የርሱ ጦር ወደ መሸገበት ወደ እንትጮ ጠጋ ብለው በገንደብታ በሰፈሩበት ጊዜ ውጊያና ድል ለናፈቀው አለቃው ለክሪስፒ እ. ኤ. አ. በየካቲት 9 ቀን 1896 ዓ. ም. ባስተላለፈው ቴሌግራም እንደዚህ ብሏል ።

> የኛና የሸዋ ጦር በትንሽ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ሁለቱም ጥሩ ጥሩ ስፍራ ይዘው ፊት ለፊት ሆነው ይጠባበቃሉ ። እምሽጋችን ድረስ መጥተው ላለመዋጋት መቁረጣቸውን ሰላዮቼ ገልጸውልኛል ። በርግጥም ከምሽጋችን መጥተው ቢወጉን ድል ማድረጋችን እርግጥ ነው ። ከኛ የበረከተው ጦርና ደህና ሥፍራ ይዞ የሚጠብቀንን ሔደን ብንወጋው ድሉ አጠራጣሪ ነው ።. . . ድሉ ቀንቶን ጠላት ቢሸሽም ወጣ ገባ በሆነ አገር የኛ የነጩ ወታደር እንደ ጥቁሩ ጠላትን እንደልብ ሊያባርር አይችልም ። [1]

በዚህ ጊዜ ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦር አንዱ ቅኝ አገር ለማግኘት ፣ ሌላው ያገሩን ነጻነት ለመጠበቅ ለጦርነት በተሰለፉበት ሰዓት ሁለቱም ድልን ሲመኙ ፣ ወደዚህ ድል የሚያመራውን ቁርጠኛ ጦርነት ለማድረግ የሁለቱም ፍላጐት ለየብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። ከዚህ በላይ ላለቃው ለክሪስፒ እንዳስተላለፈለት ፣ "ዐፄ ምኒልክ ካሉበት ከገንደብታ እስከ መሸግሁበት እስከ እንትጮ ፣ እስከ ሳውሪያ ድረስ መጥተው ቢወጉኝ ምሽጌን ይዤ በመዋጋት ድልን አገኛለሁ" ብሎ በናፍቆት እንደሚጠባበቅ ሁሉ ዐፄ ምኒልክም ፣ "የተደበቀበትን ምሽግ ለቆ ወደ ውጭ ወደ ሜዳ ወጥቶ ምነው በተዋጋሁና በለየልን" በሚል ምኞት ተይዘው ይጠባበቃሉ ። እኚህን "ወደ ምሽጉ ሔደው አይዋጉ ፤ ሠራዊትዎን ያስጨርሳሉ ። ያንንም ከሜዳ ሔደህ አትግጠም ሠራዊትህ ያልቃል" የሚላቸው የየግል መካር በብዛት አሏቸው ማለት ነው ። ቢሆንም ፣ ሁለቱም ከጥንቃቄና ራስን ከመጠበቅ ጋር ወታደራዊና ስልቱዊ ንቅናቄ ማድረጋቸው አልቀረም ። ዐፄ ምኒልክ ከነበሩበት ከዬሃ ተነሥተው ወደ ገንደብታ ፣ ከዚያም ወደ አሳይ መጥተው ሰፈሩ ። ጣልያኖችም ከተኩዝ በስተደቡብ ያለውን ሳውሪያ (ሱዋሪያ) የሚባለውን ይዘው መሸጉ ። ከዚህም ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ የኢጣልያ ሹማምንት ፣ ሦስት መቶም አምስት መቶም ወታደር እያስከተሉ አገርና ስፍራ ምርመራ ሲወጡ እነቀኛዝማች ታፈሰ በሩቅ እያዩ ፣ ሲያባርሯቸውና እስከ ምሽጋቸው እያደረሱ በመመለስ ጦርነት ሲያደርጉ ሰንብተዋል ። ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስም ባንድ ወገን የጠላት ወታደር የሚመላለስበትን መንገድ በሚያውቁት አገር በአጋሜና በእንደርታ እየሔዱ ሲያስናክሉና በማይ መሬት እነፊታውራሪ አምባዬ በሞቱበት ቀን ኃይለኛ ጦርነት ማድረጋቸው አልቀረም ።

ብዙ ጊዜ ደግሞ ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች የደፈጣ ጦርነት እያደረጉ ጣልያኖቹን ያበሳጩአቸው ነበር ። ዝም ብለው መንገድ አሳልፈው በጫካ ተደብቀው ተኳኩሰው ከተነኮሷቸው በኋላ ጣልያኖቹ ውጊያ ሲያምራቸው ይሰወሩባቸዋል ። ስለዚህ አንድ ካርዴላ የሚባል ሻምበል በጻፈው መጽሐፍ ፣ "እነዚህ ጥቁሮች ፈሪዎች ናቸው ። ሲያዩን ይሸሻሉ ፤ ተበታትነን ስንጓዝ ደግሞ ይወጉናል ጭካኔያቸውም ከፍ ያለ ነው [1] . . ." ሲል አመልክቷል ። የነርሱ ከምሽግ አለመውጣት በፍርሃት መሆኑን ግን ፣ ይኸው ካርዴላ ሊጠቅሰው ስለአልፈለገ ፣ አድላዊ ጸሐፊ ነው ማለት ይቻላል ። ካርዴላ ፣ "እነዚህ ጥቁሮች ፈሪዎች ወይም የፈሪ ጨካኞች ናቸው" ብሎ የጸፈውን የመቀሌን ጦርነት የተካፈለው ኮሎኔል አሜን—ዶላጂኒ "ባበሾች ላይ ፈሪ የፈሪ ጨካኝ ብለህ የጻፍከው ከውነት የራቀ ነው ፣ በመቀሌ ጦርነት ፊት ለፊት እየተዋጉ በምሽጋችን ፊት የፌሳ ቁልል ትተው የለምን ?" በማለት አስተባብሏል ። ወደፊት ይኸው ካርዴላ በዓድዋ ሲዋጋ ስለ ተማረከ ፣ የሐበሾቹን ዠግንነት የራሱን ፈሪነት በልቡ ሳይገነዘበው አይቀርም ።

ይሁን እንጂ ፣ ዋናው የኢጣልያ ጦር በእንትጮና በሳውሪያ መሽጎ ስለ ተቀመጠና ወጥቶ ከመዋጋትም ስለዘገየ ፣ ዐፄ ምኒልክ ከዚህ ቀደም

---

1 Memoire d' Afrique . . ,PP. 349 -350

1 Da Adua al Congo ,E. Cardella, PP. 17 -18

እንዳሰቡት ፣ የመሸገውን ጦር እንዳለ ትተው በግራ በኩል ወደ ሐማ
ሴን ለመዝለቅ ያሉበትን ገንደብታን ለቀው ወደ አሳይ (ያባ—ገሪማ
ጉልት) ከዚያም ወደ ዓድዋ ዘልቀው ሰፈሩ ። በዚያ ሳሉ ምናልባት
ኢጣልያኖች መጥተው በድንገት ውጊያ የገጠሙ እንደሆነ በማለት
ለጥንቃቄ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ራስ ሚካኤል ፣ ራስ ወሌ ፣ ራስ ቢት
ወደድ መንገሻ ፣ ራስ መኰንን ግንባር ቀደም ሆነው በአባ ገሪማ በኩል
ተሰልፈው እንዲጠብቁ ተደረገ ። ዳሩ ግን ፣ ጣልያኖቹ ከሰፈራቸው ሳይ
ነቃነቁ ዐፄ ምኒልክም ከአባ ገሪማ ዓድዋ መጥተው መሣሪያቸውን
እንደያዙ ሁሉም ሲጠባበቁ ዋሉ ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከዚህ በፊት ወደ ኤርትራ ለመዝመትና ጣልያኖ
ችን ከጀርባ ለማጥቃት እንዲያጠኑ እነሊቀ መኳስ አባተን ልከው
እንደነበረ አሁን ደግሞ ራስ መንገሻ ዮሐንስን ፣ ራስ መኰንንን ፣ ፊታ
ታውራሪ ገበየሁን ፣ ፊታውራሪ ተክሌንና ሊቀ መኳስ አድነውን “ወደ
ፊት ሒዳችሁ አዲኳላ ሰፍራችሁ ጠብቁኝ ፣ እኔም ከናንተ ቀጥዬ እመ
ጣለሁ” ብለው ልከዋቸው ነበር ። እነሱም ታዘው ከሔዱ በኋላ መረብ
ሲደርሱ የመረብን ወንዝ ደርቆ ስላገኙት ፣ ከዚህ በፊት እነሊቀ መኳስ
አባተ እንዳሉት ፣ “እዚህ የጃንሆይ መምጣት ይቅርና ለኛም እዚህ
ላለነው የመረብ ውሃ ስለደረቀ ፣ ሰውም ከብትም ከትናንት ጀምሮ
ወሃ ለማጠጣት ተቸግረናል” የሚል መልስ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ።
ስለዚህም ወደ ሐማሴን ዘልቆ ኢጣልያኖቹን በጀርባ የመክበብና ቅኝ
አገር አድርገው የያዙትን ሐማሴንን ፣ እከለ ጉዛይንና ሰናፌን የመው
ረሩ ነገር ቀረ ።

መረብንም ተሻግሮ ለመዝመት የታሰበበት አንደኛው ጉዳይ ፣
“የያዝነው ግዛት የሚወረር ከሆነ ከምሽጉ ወጥቼ ብዋጋ ይሻላል”
ብሎ የጣልያን ጦር ከምሽጉ እንዲወጣና እንዲዋጋ ለማድረግ የታሰበ
ዘዴ ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ በመጨረሻ ለሰውም በተለይ ለከብት
ሣርና ወሃ በማይጠፋበት በዓድዋ መቆየቱ ይሻላል ተብሎ ተመከረና
ዋናው ሰፈር በዓድዋ እንዲሆን ተወሰነ ። ቢሆንም ጣልያኖች ዐፄ
ምኒልክ እስከ ሐማሴን ዘልቀው ከገርባ ለመውጋት ያላቸውን ሐሳብ
ከሰላዮቻቸው በሰሙ ጊዜ በጣም ሠግተው ነበር ። የኢትዮጵያ ጦር ወደ
ሐማሴን ሔዶ በምጽዋ በኩል ከአሥመራና ከአዲኡግሪ ሳውሪያ ላለው
ለዋናው ጦራችን ስንቅም ፣ መሣሪያም የሚያመላልሰው የተቋረጠ እን
ደሆነ ጦሩ ዙሪያውን ተከቦ በመቀሌ እንደ ሆነው ዓይነት ችግር እንዳ
ይፈጠር በመሥጋት የኢጣልያ ጦር አዛዥ አንድ ብልሃት መፍጠር
ስለ አስፈለገው ፣ አበሾቹ ወደ መረብ እንዳይጓዙ ከአዲግራትና ከሳው
ሪያ ምሽግ ሠራዊቱ እሚዋጋ እየመሰለ በመውጣት የንጉሡ ጦር ባለ
በት በኩል በሰልፍ እንዲታይ ጄኔራል ባራቲዬሪ አዘዘ ። በዚህ



ምክንያት የካቲት 17 ቀን የታዘዘው ጦር በሰልፍ ለውጊያ እስመስሎ
ወጥቶ ወደፊት ይጓዝ ጀመር ።[1]

የኢትዮጵያ ቃፊር ጠባቂዎች ፣ የኢጣልያኖችን በሰልፍ መምጣት
በሩቅ ሲመለከቱ በፍጥነት ለንጉሠ ነገሥቱ አስታወቁ ። በዚያን ጊዜ
ዐፄ ምኒልክ የኤፍራታውን ገዥ ደጃች ወልዴንና ያክስታቸውን ልጅ
ደጃች በሻህ አቦዬን ፣ “ወደፊት ቀድማችሁ ሌሊቱን ተጠባበቁ ። እኔም
ሊነጋ ሲል ጦሬን አስከትዬ እደርስባችኋለሁ” ብለው እነርሱ ወደፊት
ቀድመው እንዲጠባበቁ አደረጉና እርሳቸው በማግሥቱ ሊነጋ ሲል ጦራ
ቸውን ለውጊያ ግራና ቀኝ አሰልፈው ራሳቸው ከመካከል ሆነው ነጋሪ
ታቸውን እያስጎሸሙ ወደፊት ተጓዙ ። ዳሩ ግን ፣ “የኢጣልያ ጦር
ያፄ ምኒልክን ንቅናቄ ባየ ጊዜ ፣ በሰልፍ እንደወጣ ምንም ሳይታኮስ
ተመልሶ በግሥጋሤ እምሽጉ ገባ” የሚለው ወሬ ላፄ ምኒልክ ስለ
መጣላቸው ፣ እርሳቸውም ሠራዊቱም እዘኑ ። ይኸን ዓይነቱን ወጣ
ገባ የማለት ሰልፍ ኢጣልያኖች ደጋግመው ሠሩበት ። በዚያን ጊዜ
የኢትዮጵያ መኳንንትና ጦር ሠራዊት ፣ “ብቅ ይሉና ስንመጣባቸው
እንደ ኤሊ እድንጋያቸው ውስጥ እየገቡ ይሸሸጋሉ ፤ እልፍ ስንል ደግሞ
ብቅ ይላሉ ምን ይሻላል” እያሉ በብስጭት እጉረመረሙ ። ከዚያ በኋላ
የሚያደርጉት ቢያጡ የጦር አለቆች ተሰብስበው ፣ “እዚሁ እያለንበት
እንደርና ነገ በጧት ሔደን እምሽጋቸው ድረስ እንግጠማቸው” ብለው
ተማከሩ ። የነርሱንም ምክር ንጉሠ ነገሥቱ በእሽታ አጸደቁት ።

በዚህ ምክር ሁሉም ተስማምቶ ከጨረሰ በኋላ ፣ ከዚህ ቀደም እን
ዳመለከትነው ራስ መንገሻ ዮሐንስ ወደፊት ቀድመው በሌላ ክፍል
ይጠባበቁ ስለነበረ ፣ የዚህን የምክር ውሳኔ በሰሙ ጊዜ በጦራቸው ታጅ
በው በፈረስ ሆነው በግሥጋሤ መጥተው ፣ “ጃንሆይ ጉድባ ጎድቦ ምሽግ
መሽጎ በተቀመጠ ጠላት ላይ በኃይል ብንገባ ሠራዊታችንን ከማስጨ
ረስ በቀር ምንም ጥቅም አናገኝም ። ዐፄ ዮሐንስ ያ ሁሉ ጦራቸው
መተማ ሔዶ ያለቀው በዕንጨት እተመሸገው ምሽግ ገብቶ አይደለ
ምን? ስለዚህ ከድንጊያ እተመሸገው ምሽግ ይኸን ሁሉ ጦር ልና
ስጨርስ አይገባምና እኔ በዚህ አልስማማበትም” ብለው ተናገሩ ።
ሁሉም የርሳቸውን ምክር ልብ አድርጎ ተገነዘበው ። ዐፄ ምኒልክም
“እንግዲህ ወዲያ ኢጣልያኖች በሙሉ መጥተው መታኮሳቸውን ሳላይ
ጦሬን ሁለተኛ አሰልፌ አልነሣም” ብለው እየተበሳጩ ወደ ድን
ኳናቸው ተመለሱ ።[2] ሁለቱም ባላጋራዎች በዚህ መካከል የስንቁ

---

[1] Memoire d' Afrique . . Chap. XXIX

[2] ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ. 63 Italia ed Etiopia . . Conti - Rossini, PP. 300-315.

ነገር ከሥጋት ላይ ጥሏቸዋል ። በኢጣልያኖች በኩል ለመብል የሚሆን ሥጋም እልቆ የጭነት በቅሎአቸውን እያረዱ የበሉና የሚበላ ዳቦ ለማግኘት ልብሳቸውን ላገር ተወላጅ ወታደር የሸጡ የኢጣልያ ወታደሮች አሉ ። [1]

እቴጌ ጣይቱም ፣ ራሶቹም ፣ ሹማምንቱም ፣ ወታደሩም በዚህ ነገር በጣም እያዘነ ምን ማድረግ እንደሚሻል በሚወያይበት ጊዜ ፣ እቴጌ ጣይቱ ፣ ደጃች በሻህ አቦዬን ጠርተው ፣ "ወንድሜ ሆይ ምን ይመስልሃል ይኸውና ጦራችንን ሁለት ጊዜ እያሰለፍን እየወጣን ሁለት ጊዜም ምንም ሳናደርግ ተመለስን ። ይኸም የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ አዝኛለሁ" ብለው አማከሩዋቸው ። ደጃች በሻህም ፣ "ጦርነት የሚጀመረው ድንገት ሳይታሰብ ነው ። በጦርነት የሚሞቱትም ገና እህል ውሃቸው ባያልቅ ነው ። ይልቅስ ወደፊት ለሚሞቱት ይዘኑ እንጂ በሌላው ነገር አይዘኑ" ብለው መለሱላቸው ። በኋላም የዓድዋ ውጊያ ለት ደጃች በሻህ አቦዬ በጦርነቱ ላይ ስለሞቱ እቴጌ ይኸንኑ ንግግራቸውን እስታውሰው አዘኑላቸው ። [2]

በዚህ በየካቲት ወር ፣ የኢጣልያና የኢትዮጵያ ጦር አለቆች አንድ ዓይነት የስንቅ ችግር በነበረባቸው ጊዜ ሁለቱ ወገኖች አሳባቸው አልፈጸም ቢላቸውም ፣ በብዙ ችግር በብዙ ውይይትና ዘዴ ፈጠራ አንዱ ሌላውን ወደሚያሸንፍበት ምቹ ሥፍራ ስቦ ለመዋጋትና ለማሸነፍ ሲጣጣር ሰነበተ ። በዚሁ መሠረት ባራቲዬሪ ፣ "በየጊዜው ከምሽግ ውስጥ እንደሚዋጋ ጦር ብቅ እያላችሁ ለኢትዮጵያ ጦር በሰልፍ እየታያችሁ ሲመጡባችሁ ደግሞ ወደ ምሽጋችሁ ተመለሱ" ማለቱ ለጦርነት ሲል ፣ ቤት ንብረቱን ለቆ ከወጣ አምስት ወር ያለፈው የኢትዮጵያ ጦር በንዴት የተመለከተውን ጦር ተከታትሎ እስከ ምሽጉ ድረስ ሔዶ ሲዋጋ የመጣውን ጦር ምሽጋችንን ከለላ አድርገን በመድፍና በመትረየስ በጠመንጃም ፈጅተን በቀላሉ ድል እናደርጋለን በማለት ነው ። ነገር ግን ፣ የነርሱን ብልሃት እነራስ መንገሻም ፣ እነራስ ስብሐትም በትክክል ስለሚያውቁት ፣ ወደ ምሽግ ተሔዶ ጦርነቱ እንዳይደረግ በጥብቅ ማሳሰባቸውን ተመልክተናል ። ንጉሠ ነገሥቱም እነራስ መኰንንም ቢሆኑ የምሽግ ጦር አስቸጋሪ መሆኑን እንደማይስቱት የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ፣ ብዙ ቀን በመፋጠጥ ጊዜው ካለፈ በኋላ ፣ ዐፄ ምኒልክና ሹማምንቶቻቸው ደግሞ የኢጣልያ ጦር ልብ አግኝቶ ምሽጉን ለቆ


1 Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Doca, PP. 640-641.

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 258




ወደ ውጭ እንዲወጣላቸው በበኩላቸው ልዩ ልዩ የመሳቢያና የማታለያ ወሬ ይፈጥሩ ጀመር ። ከዚሁም አንደኛው የኢጣልያ ጦር የልብ ልብ በቅቶት ወጥቶ እንዲዋጋ ፣ "የኢትዮጵያ ወታደር ስንቅ እልቆበት ለዘረፋ በያገሩ ተበትኗል ። ይበልጡም በያገሩ ተመልሶ ገብቷል ። እነራስ እገሌም ሞተዋል ። ወይም ከድተዋል ። ዐፄ ምኒልክ ታመዋል" እያሉ ዐውቀው ያስወሩ ጀመር ። ባንድ ወገን ደግሞ እነ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ እነራስ መኰንን ፣ እነራስ ሚካኤል ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እየተማከሩ ፣ "ጦርነቱን ብትጀምር ዞረን ወደናንተ እንገባለን" እያሉ ቢቸግራቸው ለጣልያኑ አዛዥ እስከ መጻፍ መድረሳቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ነጋድራስ አፈወርቅ ያረጋግጣሉ ። [1]

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . .ገጽ 258 ፣ ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ፣ ገጽ 32-33



ራስ ወሌ ብጡል ከልጃቸው ከደጃዝማች ዓመዴ ጋር

ከካርሎ አናቶሪ መጽሐፍ



ራስ መንገሻ ዮሐንስ በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ
ከኤሪትሪያ ኔልፓሳቶ



በጦርነት ሰዓት የኢጣልያኖችን ጐራ በስውር ለቀው ወደወገናቸው ወደ ዓፄ ምኒልክ ጦር መጥተው የተደባለቁት ራስ ስብሐት

# ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

## የኢጣልያኖች ተታይላነትና የጄኔራል ዳቦርሚዳ ደብዳቤዎች

ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ ፈረንጆች ከቆዳ ቀለማቸው የበለጠ በሥልጣኔያቸው ስለሚመኩ ፣ ባልሠለጠነው በእስያና በደቡብ አሜሪካ ፣ ይልቁንም ከመልኩ መጥቆር ጋር በሥልጣኔ በጣም ወደኋላ ቀር በሆነው በአፍሪካ ላይ ከጥላቻ ጋር የተደባለቀ ንቀት መኖሩ በየጽሑፉ ላይ ይነበባል ። ናቂዎቹ ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን ተወላጅም ሁሉ በጠቅላላው አረመኔዎች እያሉ መጥራትን ያዘወትራሉ ።

ወደ ቀይ ባሕር ጠረፍ ኢትዮጵያን ቅኝ አገር ለማድረግ የሚመጡት የኢጣልያ የሲቪልና የጦር ሹማምንት ከንቀት የተነሣ ፣ በቀላሉ ያፄ ምኒልክን ጦር አሸንፈው ለኢጣልያ ቅኝ አገር አውርሰው በመመለስ የሹመት ደረጃና ኒሻን ለመሸለም ዋና ጉጉት አላቸው ። ወዳፄ ምኒልክ ለእርቅ እያስመሰለ ይመላለስ የነበረው ማዦር ቶማሶ ሳልሳ የሚባለው ፣ "ቁጥሩ ትንሽ የሆነው ወታደራችን ብዙውን የጠላትን ኃይል ለማሸነፍ መቻሉ አጠራጣሪ አይደለም . . . " በማለት እርግጠኛ ሆኗል ።[1]

ራሱ ጠቅላይ አዝማቹ ባራቲዬሪ ፣ ቀደም ሲል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለባሮን ብላን ባስተላለፈው መልእክት ፣ "ጄኔራል ናፒዬሪ ቴዎድሮስን ለማሸነፍ ከፈጀበት የወታደሮች ቁጥርና ጊዜ ባነሰ በምኒልክ ጦር ላይ ድል አድራጊነትን እቀዳጃለሁ" ብሎ ደንፍቶ ነበር ።[2] ከዚህም አያይዞ ከኢትዮጵያ ጦር አንጻር የኢጣልያን ተዋጊ ጦር በፖለቲካ መብሰሉን በወታደራዊ ሥነ ሥርዓት የሠለጠነ መሆኑን በመገምገም ለድል አድራጊነቱ አልተጠራጠረም ።

ሌላው ጄኔራል ማቲዎ አልበርቶኒ የሚባለው ፣ በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ አጠገቡ ያሉት ደጃዝማች ፋንታ የሚባሉት የባንዳ ሹም ፣ በዚህ ጦርነት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ቢመክሩት ፣ "አበሾች

1 Il Generale Tomaso Salsa, E. Canevarie. G. Comisso, PP. 268 -269.
2 Gli Italiani in Africa . . Del Boca, P. 560.

ገና ሲያዩን ነው የሚሸሹት” ሲል መለሰላቸው ። የርሱም ጓደኛ ጄኔራል አሪሞንዲ ዡሴፔ ጄኔራል ባራቲዬሪ በመጨረሻ በቶሎ ጦርነቱን ላለመጀመር የሚያደርገውን ጥንቃቄ በመንቀፍ ምክንያት እያበዛ ነገ ተነገ ወዲያ እያለ ጊዜ በማራዘሙ እየተበሳጨ ፤ “አሁን ጠላትን ልቡ እስኪጠፋ እያደኑ ማባረር ነው” ያለውን አንጀሎ ደልቦካ መዝግቦት ይገኛል ።[1]

ከነዚህ የበለጠ ደግሞ ፤ የነዚህ ጄኔራሎች ጓደኛ ጄኔራል ቪቶሪዮ ኢማኑኤል ዳቦርሚዳ ባንድ ወገን ካፄ ምኒልክ ሠፈር በዘዴ አታሎ የኢጣልያን ጦር ከምሽጉ ለማስወጣት የተነዛውን ሐሰተኛ ወሬ በመተማመን ፤ ወዲያውም እንደ ጓደኞቹ ጄኔራሎች የኢትዮጵያን ጦር በመናቅ ፤ የኢትዮጵያን የወታደር ድርጅት በቀላሉ አፈራርሶ የአላጌውንና የመቀሌውን የውርደት ብድር ለመመለስና በክብርና በድል አድራጊነት ወደ አገሩ ለመመለስ እርግጠኛ እንደነበረ ከዓድዋ ጦርነት ከሐያ ቀን በፊት ወደ ኢጣልያ አገር ለባለቤቱ የጻፈው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ደብዳቤ ያስረዳል ።

እንትሎ የካቲት 10 ቀን 1896 (የካቲት 3/1888) የልጆቻችንን ደብዳቤዎች ተቀበልሁ ። ግልጽ በሆነው ፍቅራቸው ልቤ ተነክቷል ። ካንድ ወር በኋላ የምንመለስ(ወዳገራችን) አይመስለኝም ። በአፍሪካ ነገሩ ሁሉ እየተጐተተ መርዘም አለበት ። ጠላት ወደፊት ከገፋ በኋላ ወደኋላ መለስ ብሏል ። * እኛም ከአለንበት ከአዲግራት ወደእንትሎ እልፍ ብለናል ። ከአለንበት ስድስት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ የጠላት ጦር ይታያል ። የቀረው ወደኋላ ያለው በጋራ ተሸፍኗል ። እኔ እንደማስበው በድንገት አደጋ ጥለን ብንወጋው የሚሸሽና በትንሽ ወታደሮች መሥዋዕትነት ከፍ ያለ ፍሬ (የድል) የሚገኝ ይመስለኛል ።

የኛ ወታደሮች ፤ የውጊያ አምሮት እያላቸው እነዚያ (ሐበሾቹ) ግን ፤ ሰላዮቻችን እንደሚሉት ወደቤታቸው መመለስን እንጂ ፤ በጦርነቱ እምነት የላቸውም ። ነገር ግን የዕርቅ ድርድር ተይዟል ። ** እኔ ለዕርቁ ፍሬነት እምነት የለኝም ። ንጉሡ (ምኒልክ) በረዥሙ ጦርነቱን አዘጋጅቶ 80,000 ወታደር ከአሰከተተና የግዛቱን ሀብት ከፈጀ በኋላ ምንም እንኳን ክብሩ የኛ ቢሆን ፤ በአምባ አላጌና በመቀሌ ከቀናው በኋላ እኛ የምናቀርበውን ውል ተቀብሎ ወደቤቱ ለመመለስ ይችል ይሆን ። ኢጣልያስ ብትሆን ከነርሱ የተሻለ በዓለም የማይገኘውን 20,000 የጦር ወታደሮቿን ወደዚህ በመላክ ከፍ ያለ መሥዋዕት ከአደረገች ወዲህ ከአንድ አረመኔ ሕዝብ የሚቀርብላትን የውል አሳብ ነመቀበል ትዋረዳለችን፣ የዕርቁ ድርድር ጉዳይ እየተራዘመ ሲሔድ

---

1 Gli Itallani in Africa . . ,, PP. 640 -642.

* መረብን አልፎ ለመዝመት ታስቦ በወሃ እጦት የቀረውን ለማስታወስ ይመስላል ።

** ማዥር ሳልሳ ከነራስ መኰንን ጋር ያደረገውን ለመጥቀሱ ነው ።



የጠላትን ሁኔታ እያባሰበት ይሔዳል እንጂ ፤ ቢሆንም ለኛ አዋራጅ ዕርቅ ሊደርስብን አይችልም ። እኔ ግን ጠላት ወደኋላ የተመለሰ እንደሆነ ያጋጠመኝን መልካም ዕድል አጣለሁ* ምክንያቱም ወደኋላ ሲያፈገፍግ ኃይላችንን ይዘን እርሱን እየተከታተልን ፈልገን ለመውጋት የስንቁ ነገር (ችግሩ) ይከለክለናል ። 1

ይኸው ለውጊያና ለዝርብዱ በዚህም ለመሾምና ለመሸለም ጉጉት ያደረበት ጄኔራል ፤ ከዚያ ወዲህ የዓድዋ ጦርነት ሲደረግ ስምንት ቀን ሲቀረው በጻፈው ሌላ ደብዳቤ ላይ ፤

የኔ ፍና እትፍሪ ። እዚህ ያለጥንቃቄ የሚሆን ነገር የለም ። ሁለቱም ባላጋራዎች በጣም ጠንቃቃ ሆነዋል ። . . . በግልጽ ሜዳ በገሃድ መዋጋት አይፈልጉም . . . አበሾች መዋጋት ወይም መመለስ እንዳለባቸው በኛ በኩል የታመነ ነው ። ምክንያቱም ጠላት 80,000 ተዋጊ ጦር ሲኖረው ከሴትና ከልጅ ጋር በድምሩ 150,000 ተቀላቢ ስለሆነ እነዚህን ለመቀለብ ያለበት አገር እህሉ ስላለቀ አይችልም ። ከምሽጋችን መጥቶ ለመውጋት አይደፍረንም ። ስለዚህ በመጭው ጊዜ ወደ ኋላው ይመለሳል ብለን እንጠባበቃለን ። በዚያን ጊዜ በትግሬ የፈቀደንን ለማድረግ እንችላለን ። ተመልሰው ተዘጋጅተው ለመምጣት ብዙ ዓመት ይፈጅባቸዋል ። ዋናው ከሐበሻ አገር ተዋጊ የሆነው የትግሬ ሕዝብ ከኛ ጋር ስለሚሆን ምንም ማድረግ አይችልም ። . . . መቼም ባለፈው ከደረሰው አድራጐት ያላጌና የመቀሌ ውድቀት በኋላ ዕርቅ ማድረጉ ለኛ አዋራጅ ነው ። . . .ከኢጣልያ አገር የጦሩ እርዳታ ከደረሰ በኋላ ባራቲዬሪ ጉልበቱን ተማምኖ ውጊያ የጀመረ እንደሆነ መፍትሔው በመጋቢት ላይ ይለያል ። ** ስለዚህ ወደ ኢጣልያ አገር መመለሳችን በበጋው ነው ማለት ነው . . . ትናንት የሁለት ባታዮ ጦሬን ይዤ ለምርመራ በወጣሁ ጊዜ በወታደሮቻችን ፊት ላይ ይታይ የነበረው ደስታ ይገርምሻል ። ሁሉም ወደፊት ገሥግሠው መታኮስ ይፈልጋሉ ። 2

በነዚህ ሁለት ደብዳቤዎች ፤ ይህ የኢጣልያ ጄኔራል የራሱን ወታደሮች “በዓለም የማይገኙትን” ሲል ካገሩ ያልወጣ ወይም በንባብ ያልበሰለ ፤ ዓለምን የማያውቅ በዓለም ያሉትን የጀርመንን ፤ የጃፓንን ፤ የቱርክን የሌሎችንም አገሮች ወታደሮች ዠግንነት የማያውቅ በሞኝነት የራሱን ወገን ብቻ የሚያጋንን የዋህ ጄኔራል መሆኑን ያሳያል ። በዚህም ላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ አረመኔ የሚል ሥያሜ እስታቀፎታል ። አረመኔ በራሱ ግዛት ሳይቆጠብ የሌላውን አገር ካልገዛሁ

---

* ተጥግቶ ዠግንነትን አሳይቶ የመሾም ፤ የመሸለም ዕድል ማለት ነው ።

1 Lettere e Diari . . . ,F Lemmi, PP. 82-83.

** እውነትም የዓድዋ ጦርነት የተደረገው እ.ኤ.አ. መጋቢት 1 ቀን ስለሆነ ትንቢቱ ይዞለታል ።

2 Lettere e Diari . . ,,F. Lemmi, PP.83-84

ብሎ የንጹሐኑን ደም የሚያፈስ ነው ወይስ የራሱን ነጻነት የሚከ
ላከል ? በመቀሌ ተከበው በወሃ ጥምና በረኃብ ሊያልቁ የነበሩትን ሸኝ
ስጥቶ በነጻ መልቀቅ የጠላቱን ሬሳ እስነሥቶ በደንበኛ ቦታ ማስቀ
በር ፡ ይኸ ሁሉ ያረመኔ ሥራ አልነበረም ። ዳሩ ግን ፡ ይኸን ሁሉ የጦሩ
አለቆችና የፖለቲካ ባለሥልጣኖቹ ከፍርሃት ቆጥረውታል ።

ዳቦርሚዳ ፡ እሽናፊነቱን መቶ በመቶ በማመን ፡ "ጠላት ወደኋላ
የሸሸ እንደሆነ ለመከታተል ስንቅ ስለሚቸግረን ፡ ያጋጠመኝን ዕድል
እጣለሁ . . .እንደዚሁም ከአገሬ ለውጊያ መጥቼ ጠላት የሸሸ እንደሆነ
እሸንፌ በዚሁ የማገኘው ክብርና ዝና ይቀርብኛል . . . ጠላት ስንቅ
አልቆበት ወደቤቱ (አዲስ አበባ) ሲመለስ ፡ በመላው ትግሬ የፈቀድ
ነውን እናደርጋለን" ሲል ፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ በዚህ ጊዜ ያላትን
ድርጅት የማያውቅ ካለፉት ከአላጌና ከመቀሌ የውጊያ ውጤቶች
ለመማር ያልፈለገ በጠቅላላው አመዛዛኝ አእምሮ የሌለው ሞኝነ
ትና ግትርነት ያጠቃው ተራ የጦር ኣለቃ ነው ማለት ይቻላል ።

በዚህ ላይ ደግሞ ፡ ጦርነቱ ይቅርብን የሚል ሕዝባዊ ድምፅ እንዳ
ይቀሰቀስ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሮማም እሥመራና ምጥዋም ያሉት
የሲቪልና የጦር ሹማምንቶች በኢትዮጵያ ያለውን ደንበኛ የመከላ
ከያ ሁኔታ እየደበቁ በአምባላጌና በመቀሌ የደረሰውንም እያወላገዱ
በከንቱ የኢትዮጵያን የመከላከል ሁኔታ እያራከሱ ፡ የነርሱን ጀብዱ
እያጋነኑ በመጻፍ ሐቀኛውንም ጋዜጣ ጸሐፊ እያባረሩ ፡ ብዙውን
ሁኔታ ከተዋጊው ወታደርና ጄኔራል ለመደበቅ መሞከራቸው
ግልጽ ነው ።

በጠቅላላ ፡ ኢጣልያኖቹን በጄኔራሎቻቸው መልክና ጠባይ ልን
ወስዳቸው እንችልም ። በመካከላቸው በኢጣልያ አገርና በሮማ ታላ
ላቅ አስተዋዮች ፡ ብልሆች ሞራል ያላቸው ደግነትም ርኅራኄም የሞላ
ባቸው ይገኛሉ ። በዚህ ምክንያት ፡ በምክር ቤት ውስጥ ሳይቀር ክሪስ
ፒና ወገኖቹ ኢትዮጵያውያን አረመኔዎች ናቸው ፡ እየገዛን ልናሠለጥ
ናቸው ይገባል እያሉ ሲደነፉ ፡ ሌሎች በተለይ የግራ ክፍሎች
እስከዛሬ በነጻነት የቆየችውን አገር በኃይል ወርሮ በቅኝ አገዛዝ
ልያዝ ማለት ወንጀልም አብደትም ነው እያሉ ሽንጣቸውን ገት
ረው የሚሟገቱ ሞልተዋል ። ከነዚህም ውስጥ ኮስታ አንድሬያ
ይገኛል ። ይኸም አማካሪ በአምባላጌ ለወደቁት የክብር ሰላምታ ይሰጥ
በተባለበት ጊዜ ፡ "በፖለቲካ ብልሹነት ያላግባብ ለወደቁት ኢጣል
ያኖች ክብር ከመስጠቴ ጋር ያገራቸውን ነጻነት ሲከላከሉ ለወደቁት
አበሾችና የሸዋ ተወላጆች የክብር ሰላምታ መስጠት ይገባል" በማለቱ



በምክር ቤቱ እጭር ሁካታ ተፈጥሮ ነበር ። ከርሱም ጋር ይኸን በመ
ሰለው አሳብ የተባበሩትን ኢምብሪያኒ ማቴዎ ፡ ኡሊስ ባርቢዬሪ ፡ ገብ
ርኤል ሮዛ ፡ ናፖሊዎን ኮላጅያኒ የሚባሉትን ስማቸውን መጥቀስ
ተገቢ ይመስለኛል ።[1]

1 Gli Italiani in Africa . . PP. 287 - 289; La Prima Guerra D' Africa, R. Battaglia, PP. 242 - 258.

# ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

## የመጨረሻው የኢጣሊያኖች ተስፋ ልጅ ጉግሣ ዳርጌ

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ የኢትዮጵያን መሳፍንትና መኳንንት ፣ ሹማምንቱንም፣ ባላባቱንም ጠቅላላውን ተዋጊ ጦር በክተት ዐዋጅ ቀስቅሰው ለዚህ ጦርነት ከአዲስ አበባ ከተነሡ ዠምሮ ከአላጌ እስከ መቀሌ ከድል ወደ ድል እየተራመዱ ፣ እንደልቡ ፈንጭቶ እስከ አምባላጌ የደረሰውን የኢጣልያን ጦር እየጠረጉ ወደ ዓድዋ አካባቢ ነድተውታል ። ወደ ኢጣልያኖች በውድም ፣ በግድም ተጠግቶ የወረራ መሣሪያ የሆነውን ኢትዮጵያዊ መልሰው ለእናት አገሩ እንዲሰለፍ ለማድረግ በዓዋጅና በመልክት እየጋበዙ አስገብተውታል ። በሌላውም ረገድ ኢትዮጵያ ካሳለፈችው የጦርነትና የዕልቂት ዘመን ዐርፋ ሰላምና ጸጥታ እንድታገኝ ለጣልያኖቹ ባለሥልጣኖች የሰላም እጃቸውን ከመዘርጋት ሳያቋርጡ ፣ በማናቸውም ረገድ በሚያደርጉት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ተግባር እነሱ ቢያምኑም ፣ ቢክዱም የኢጣልያን ጒራ እያዳከሙበት ሔደዋል ። ሰላምን የሚፈልጉት ከኀይል ተጽዕኖ ጋር ጦርነቱንም የሚቀጥሉት የሰላምን መንገድ በመከተል ስለሆነ ፣ ኢጣልያኖቹ ከጥቁር ሕዝብ እንደዚህ ያለ ያልጠበቁት ከፉ ጠመዝማዛ የፖለቲካና የጦርነት መዘዝ ገጥሟቸዋል ። የተማመኑባቸው ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ ተፈሪ ፣ ኢጣልያንን ከድተው ወዳጼ ምኒልክ መደረብ ፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደምናነበው ፣ በአውሳ የመሐመድ አንፋሪ በነአዛዥ ወልደ ጻድቅ ተመትቶ መሸነፍ ፣ የመሳፍንቱ በምኒልክ የሥልጣን ጥላ ሥር ተባብሮ ለጦርነት ባንድ እግር መቆም ፣ ለኢጣልያ የተደጋገመ ታላቅ በትርና የራስ ምታት ሆነባት ።

ነገር ግን ፣ ከመሐመድ አንፋሪ ከዳት በቀር ገንዘቡም ፣ ስጦታውም ተበትኖ ፣ የወዳጅነት ስብከቱና ማስፈራራቱም በየወቅቱ ተፈራርቆ ለከዳት የሚነቃነቅ መስፍን ባገር ውስጥ ስለጠፋ ፣ ለምኒልክ የዙፋን ባላንጣ ሆኖ ራሱ ከድቶ ሌሎቹን የሚያስከዳ ቢቸግራቸው ከውጭ አገር ይፈላለጉ ዠመር ። በዚህ ምክንያት ፣ ቀደም አድርገው ዐፄ ምኒልክ አገልጋያቸው በነበረው በስዊሱ ተወላጅ በእንጂነር አልፍሬድ ኢልግ አማካይነት የራስ ዳርጌን ልጅ ጉግሣን ከከተማና ከአፈ ወርቅ (በኋላ ነጋድራስ አፈወርቅ) ጋር ለትምህርት ወደ ስዊስ አገር ልከዋቸው ፣ ሦስቱም ወጣቶች በስዊስ አገር በኔሻተል ኮሌጅ ይማሩ ነበር ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ካርሎ አልቤርቶ የሚያደርጉት ቢያጡ ፣ "ጉግሣ የራስ ዳርጌ ልጅ ስለሆነ ዳርጌም የሣህለ ሥላሴ ልጅ በመሆናቸው ፣ እንደ ምኒልክ ለዙፋኑ ቀራቢ ስለሆኑ ጉግሣን በማባበልም ፣ በማስገደድም ከኔቸተል ኮሌጅ አናጥለን ወደ ዠኔራል ባራቲዬሪ ብንልከው ፣ ዤኔራሉ ይኸን ይዞ ከምኒልክ ብዙ ሰው ለማስከዳት ይችላል " የሚል የሚያሳፍርና ወራዳ የሆነ ክንቱ ተስፋ አደረባቸው ።

ስለዚህ ፣ ጉግሣን ከጓደኞቹ ከከተማና ከአፈወርቅ ጋር (ምናልባት ኢጣልያንኛ በሚያውቀው በአፈወርቅ በኩል) አባብለው ወደ ኢጣልያ ጠረፍ ጠጋ ሲል እ. ኤ. አ. በታኅሣሥ ወር በ1895 ዓ.ም. በግዴታ ይዘው ወደ ሮማ ለማምጣት እንደ ወሰኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ለዤኔራል ባራቲዬሪ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አስተላለፈለት ።

የሐበሻው መስፍን ጉግሣ በታኅሣሥ ወር በመጀመሪያዎቹ ቀኖች ሮማ ይገባል ። ክቡርነትዎ መስፍኑን በምኒልክ ላይ መሣሪያ አድርጎ ለመጠቀም ይመኙ እንደሆነ አባብለን (አግባብተን) ወደ ምጥዋ ልከን በሥልጣንዎ ሥር እንዲሆን እናደርጋለን ።

ዤኔራሉ አሳቡን ከተቀበለው በኋላ ፣ ጉግሣንና ጓደኞቹን ከስዊስ ነጥቀው ወደ ሮማ አስመጧቸው ። ንጥቂያው ማባበልና ማጭበርበር አለበት ። ከዚህ በኋላ ሮማ ምንም ያህል ውለው ሳያድሩ ፣ በመርከብ ወደ ምጥዋ ተልከው እንደ ደረሱ ፣ ከዚያ በእንክብካቤ ዤኔራሉ ወዳለበት ወደ እዳጋ ሐሙስ አደረሱት ። ዤኔራሉም ከአንገት በላይ የሆነ አክብሮት እያሳየ ጉግሣን አነጋገረው ። ሌሎቹም ሹማምንቶች አክብሮት እንዲያሳዩት አደረገ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ይኸን የመንገሥ አምሮት የሌለውን ወጣትና ዐይን አፋር ተማሪ ፣ ከስዊስ አገር አታለውና አስገድደው ወደ ሮማ ፣ ከሮማ ወደ እዳጋ ሐሙስ መላካቸውን የሰማና ፣" ከምኒልክ ብዙ መሳፍንት ያስከዳልናል " በሚሉ ምኞት ልባዊ ያልሆነ የማታለል አክብሮት ማድረጋቸውን የተመለከተ ሁሉ ሣቀባቸው ። መስፍኑ ጉግሣም ከዬ ምኒልክ ሠፈር አንድም ሰው ሊያነቃንቅላቸው አልቻለም ። ተስፋ ሲቆርጡ አክባብረው ፣ እንከባክበው የመሣሪያነቱ ጉዳይ ስለሳተ አመናጭቀው ወደ ነበረበት ወደ ስዊስ መለሱት ።

ራሱ ዤኔራል ባራቲዬሪ ፣ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ በግዞት አገሩ ገብቶ በዕረፍቱ ጊዜ በጻፈው መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ያሠፈረውን ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።



... ከሮማ ወደ ሠፈራችን ስለ ተላከው የሸዋ መስፍን ትንሽ እናገራለሁ ። ...የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ባሮን ብላን ኢትዮጵያዊው መስፍን ጉግሣ ሊጠቅም ይችላልን ብሎ በቴሌግራም ጠየቀኝ ። ይህ መስፍን የራስ ዳርጌ ልጅ ሲሆን ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ለምኒልክ ያጎት ልጅ ነው ። ... ስለዚህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለጠየቀኝ አወን ብዬ መለስሁ ። ስለዚህ ጉግሣ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር ምጥዋ ከዚያም አዲግራት ደረሰ ። ለርሱና ለጓደኞቹ ማናቸውም አክብሮትና እስተያየት ተደረገላቸው ። በእዳጋ ሐሙስ ሠፈር ድንኳናቸው በዋናው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ድንኳን አጠገብ ተተከለላቸው ። ነገር ግን ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመጠቀም የሠነዘረው ዓላማ ከመጠን ያለፈና የሳተ ነገር መሆኑ እርግጠኛ ነበር ።

መስፍኑ ጉግሣ ፣ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የምኒልክ ያጎት ልጅ በመሆኑ በሸዋ ሠፈር ምንም የመታወቅና የመሰማት ክብር ሊኖረው አልቻለም ። በመከበር ፈንታ እንዲያውም ከሸዋ በመራቁና ያውሮፓን ሥልጣኔና ልማድ በመውሰዱ ምናልባት ሳይናቅ አይቀርም ። እርሱም ትንሽ ወጣት የተዋጊነት መንፈሱ ያነሰ ፣ ግለኛ ፣ ዝምተኛ ፣ ሁኔታውና መንፈሱ የቀዘቀዘ ፣ በጣልያኖቹ ሠፈር በመገኘቱ የደነገጠና የበረገገ ነበር ። የሱ ጸሐፊ በኑሮው አውሮፓዊ የሆነ የጣና ሐይቅ ተወላጅ (አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ) ስለ ራሱም ስለ መስፍኑም ሲናገር ፣ ጣሊያኖችን እንደሚወዱና ለማገልገል ፈቃደኞች መሆናቸውን ደጋግሞ ይናገር ነበር ።* ነገር ግን ፣ በእዳጋ ሐሙስ በጥር ወር መጨረሻ ጉግሣ ሊስባቸው የሚችለው በንጉሠ ነገሥቱ ጦር ሠፈር ያሉት ወዳጆቹ እነማን መሆናቸውን ለማወቅ ተፈልጎ ቢጠየቅ ትንሽ አወላውሎ አንዳንድ ስም ሰጠ ። ላለመጻፍና ራሱን ላለመግለጽ እንደ ሐበሻ ልማድ ምክንያት እየፈጠረ ጊዜ ያራዝም ዠመር ። ... በማናቸውም ረገድ በጠላታችን ሠፈር መካከል ሆኖ ጠብና ልዩነት ለመፍጠር ከዐይን አፋሩ ከጉግሣ ሌላ ማናቸውም ዓይነት ሹም ... ሊጠቅመን በቻለ ነበር ። ...ጉግሣም ምንም እንኳን ለሐበሻ መስፍንነቱ የሚገባውን ክብር ብናደርግለት ፣ እርሱ ግን ሐበሾቹን በማየት አደጋ እንዳይደርስበት ማናቸውንም ምክንያት እየፈጠረ ከእዳጋ ሐሙስ ወደ አዲግራት ከዚያም ወደ ምጥዋ ተመለሰ ። 1

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከባራቲዬሪ ጋር ውስጡን ተመሣጥረው ጉግሣን ከስዊስ ወደ ሮማ ከዚያም ወደ ምጥዋ ለመላክ በሚዘጋጁበት ሰዓት የኢትዮጵያን መሳፍንት ለመከፋፈል የተመደቡት ፣ በኢትዮጵያ የነበሩትና በኋላ በጦርነቱ ዋዜማ ካገር እንዲወጡ የተደረጉት ፣ እነቺዛሬ ኔራሲኒ ምንም ካገር ቢወጡ

---

* በዚህ የባራቲዬሪ ማስታወሻ ላይ አፈወርቅ ገብረየሱስ ከሰባት ዓመታት በፊት የውጫሌን ፣ ውል ከጋዜጣ ላይ አንብቤ አደገኛ መሆኑን ለደጃች መኰንን ገለጽሁላቸው ሲሉ አሁን በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ምን ለወጣቸው ገንዘብ ወይስ ኃይል! አይታወቅም።

1 Memoire d' Afrique, Gen. Baratieri, PP. 354 - 355, I Russi In Etiopia, 2vol, Carlo Zaghi, P. 245

በጐን ወደ የመሳፍንቱ እየተላላኩ ለማሸፈት ያላቸውን ምኞት በፍጹም ተስፋ ቆርጠው አልተውቱም ።

ከዚህ በፊት ፣ በሐረርና በአካባቢው ራስ መኰንንን እንግሥ ከምኒልክ ለመለየት ፈትኖ ያልተሳካለት ሐኪሙ ቼዛሬ ኔራሲኒ የኢጣልያ መንግሥት በምኒልክ ፈንታ ጉግሣን ደጋግፎ ለማንገሥ ያለውን ዓላማ አባትየው ራስ ዳርጌ ዐውቀው ተደስተው በጉዳዩ እንዲተባበሩ ደብዳቤ ልኮላቸው ኖሯል ። ደብዳቤውን የላከው ከኤደን መሆን አለበት ። የርሱ ደብዳቤ ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት ተፈልጎ ሊገኝ አልቻልም ። የራስ ዳርጌ መልስ ግን ፣ ቃሉ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

> የተላከ ከራስ ዳርጌ ይድረስ ከሐኪም ኔራዚኒ እንዴት አለህ እኔ እግዚአብሐር ይመስገን ደህና ነኝ ። ወረቀትህም ደረሰልኝ ። እኔ ከዚህ ቀደም አላውቅህም ነበር ። አሁን በወረቀትህ ነው ማወቄ ። ከዚህ ቀደም ይህን ያህል ቀን ሳላውቅህ መቅረቴ ምንኛ ተጐድቻለሁ ። አሁንም የልጄን የልጅ ጉግሣን ነገር ወደ ኢጣልያኖች መግባቱን የሳከህብኝን ሰማሁ ። ይኸማ ከሆነ መልካም ነው እንጂ ምንነገር አለ ። ያጤ ምኒልክን አልጋ መቀበል ነው እንጂ ። እኔም አባቱ አዲስ አበባን አልጋውን ይገፎ ተቀምጫለሁ ። ምን የሚቸግር ነገር አለ ። ዳሩ ግን ፣ ያንተ ደብዳቤ ብቻ ነው እንጂ የመጣው የሌላ ደብዳቤ አልመጣም ። ይህ ነገር አሰት ውሸት የሆነ እንደሆነ አንተንም ኔራዚኒ የተባልከውን ናዚራ እባብ ባለ መርዝ ያስመስልሃል ። ኢጣልያኖችንም ጉልበት ቢያንሳቸው የሐበሻን ጉልበት የፈሰጉ ያስመስላቸዋል ። ያንተንም ሐኪምነት የመልካም ፣ የደግ የነበርከውን የውሸትና የቅጥፈት ሐኪም ያስመስልህ ይመስላል ። ዳሩ ግን ፣ ሐሰቱንም እውነቱንም የሚያውቅ መለኮት (አምላክ) ይመልከት ። በጥር በ1 ቀን ተጻፈ ባዲስ አበባ ከተማ በ፲፰፻፹፰ 1888 ዓመተ ምሕረት (ዝ ማኅተም ዘእራስ ዳርጌ ርእሰ መኳንንት)

ራስ ዳርጌ ፣ ያፄ ምኒልክ አጐት ብቻ ሳይሆኑ ሁለቱ ከልብ እንደ አባትና እንደ ልጅ የሚተማመኑ ናቸው ። ኔራሲኒ ጉግሣን ለማስከዳትና በርሱና ብርሳቸው ለመጠቀም ያቀደው አሳብ በጣም ገርሟቸው በሰጡት መልስ ፣ “ ናዚራ እባብ ባለመርዝ ፣ ውሸታምና ቀጣፊ ሐኪም ” እያሉ በመሳደብና በማፌዝ ቀልደውበታል ።

የምኒልክና የጣይቱ ጠንካራና የደረጀ መንግሥት ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም የሆነ የተሻለ አስተዳደር በማሳየት ፣ ሁሉን እንደ ልማዱ በመያዝ በትዕግሥት ፣ በሰላም ፣ በቸርነትና በመልካም ሁኔታ ላይ ስለ ተመሠረተ ፣ በዚህም በሌላውም ጊዜ ቢሆን እንኳን ሕዝብ የማያውቀው ተማሪው ጉግሣ ቀርቶ ራሳቸው ትልቁና የተከበሩት አባቱ ራስ ዳርጌ ቢከዱና ወደ ኢጣልያ ቢዞሩ ፣ የምኒልክን መንግሥት የጠነከረ አቅዋምና የጦርነቱን ጐራ እምብዛም ሊያናጉት የሚችሉ አይመስልም ።



# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

## የአውሳ ጦርነትና—የመሐመድ አንፋሪ መሸነፍ

የኢጣልያ ሰላዮች ፣ በኢትዮጵያ በየአውራጃው ተሠራጭተው የየአካባቢው መሳፍንትና ባላባት ከንጉሠ ነገሥቱ ከዐፄ ምኒልክ እየሸፈቱ እንዲለዩ በስጦታም ፣ በማባበልም የሚያደርጉትን ጥረት በመቀጠል ወደ አውሳው ባላባት ወደ መሐመድ አንፋሪ ለስብከትና ካፄ ምኒልክ ለመለየት የተላከው ካፒቴን ሳልቫቶሪ ፔርሲኮ መሆኑን እመልከተናል ።

የአውሳ ባላባቶች ምንም እንኳን አካባቢያቸው ለተወሰነ ጊዜ የቱርኮችና የግብጾች ተጽዕኖ ቢደረግበትም ፣ ቱርኮችና ግብጾች ከተባረሩ ወዲህ እንደገና ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴና ከሌሎች የሸዋ መሳፍንት ጋር ግንኙነታቸውን አጽንተው ይኖሩ ነበር ። በዚሁ መሠረት የእውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ ለንጉሥ ምኒልክ ታዛዥም ፣ ወዳጅም ሆኖ ከአውሮፓ ፣ ከፈረንሳይም ከኢጣልያኖችም ፣ በእሰብ በኩል ለንጉሥ ምኒልክ የሚመጣውን የጦር መሣሪያና ዕቃ እየተቀበለ ወይም ለሚያደርሱት ሸኚ እየሰጠ ፣ ወደ አንኮበር ለአዛዥ ወልደ ጻድቅ በመላክ መልካም ግንኙነቱን ጠብቆ ይኖር ነበር ። ሙንሲንጀር ባሻ የሚባለው በአውሳ በኩል ባፄ ዮሐንስ ላይ የጦር ግንባር ለመክፈት እንደ እ.ኤ.አ. 1875 ዓ.ም. ሲተላለፍ ፣ የእንፋሪ ሰዎች በገደሉት ጊዜ ያስገፈፈውን አንዳንድ የጦር መሣሪያና ዕቃ ወደ ንጉሥ ምኒልክ በመላክ በማናቸውም ረገድ ታማኝነቱን እስከዚህ ድረስ አላጐደለም ነበር ። [1]

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ወዲህ ፣ በመጀመሪያው ጊዜ ይኸው መልካም ግንኙነት አላቋረጠም ነበር ። ነገር ግን ፣ ባለፈው እንዳነበብነው በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ የተነሣ በንጉሠ ነገሥቱና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለው ጠብ እየተባባሰ ሲሔድ እነኮንት አንቶኔሊ በአውሳ በኩል በሚተላለፉበት ጊዜ ከመሐመድ አንፋሪና ከአማቹም ከአብዱራህማን ጋር መሣሪያና ሌሎች ስጦታዎችም በማድረግ ተወዳጁ ። እደያር ሁለቱንም ከንጉሠ ነገሥቱ ሊለዩዋቸው ቻሉ ።

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 232

በመጨረሻ መሐመድ አንፋሪና አማቹ አብዱራህማን ፣ የኢጣልያን ወዳጅነትና የበላይ ጠባቂነት ሁለቱም እንዲቀበሉ በመገፋፋት ያገሩንና የሕዝቡን ሁኔታ በቅርብ ሆኖ እንዲያጠናና ወታደርም እየመለመለ እንዲያዘጋጅ ከዚህ በፊት በአላጌው ጦርነት ሰዓት ስሙን የጠቀስነው ይኸው ካፒታኖ ሳልቫቶሬ ፔርሲኮ በ1886 ዓ. ም. ወደ አውሳ መሐመድ አንፋሪ ዘንድ በነዋሪ ተቀማጭነት ተላከ ። ይኸው የኢጣልያ መኰንን የዐረብኛ ቋንቋና የእስልምንና ባህል ዐውቃለሁ ባይ ስለሆነ ፣ ለማለያየቱ ተግባር ምርጫው እርሱ ላይ ወደቀ ።

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ ይኸንኑ መኰንን በ1886 ዓ.ም. ወደ አውሳ ሲልከው በጽሑፍ ያሳሰበው ዋና ዋናው ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

> የምሰጥህ ዝርዝር ትእዛዝ የለኝም ። እንዲያውም የሥራህን ነጻነት እንዳላጠብ ትእዛዝ ከመስጠት መራቅን እመርጣለሁ ። ነገር ግን የመልእክትህ ዋና ፍሬ ነገር የኢጣልያንን የበላይ ጠባቂነት የኤርትራን ቅኝ አገር ታላቅነት እየገለጽህ መሐመድ አንፈሪንና አውሳን ወደኛ ለመሳብና ለመያዝ ነው ። ይኸንንም ከዚህ ቀደም በጽሕፈትም ፣ በቃልም እደራዬን እንደ ገለጽሁልህ በጥበብና በትዕግሥት የነሱን አሳብና ልማድ በመፈጸምና ከነርሱ ጋር በማናቸውም እየተመሳሰልህ ነው. . . ስለ ምኒልክ ሲነሣ ይህ ንጉሥ በኢጣልያ የበላይ ጠባቂነት ውስጥ መኖሩንና መልካም ግንኙነት ያለን መሆናችንን እንደሚረዳ ግለጽለት ።
>
> መሐመድ አንፈሪ ፣ እሺ የሚል እንደሆነ የባንዳ ወታደር ለመመልመል አስብበት . . . በሐረር በኩል ሳያልፍ ያበሻ መንግሥት መገናኛውን በኛ በኩል እንዲያደርግ የአሰብ መንገድ በግድ የኛ መሆን አለበት . . . ከአዋሽ በላይ ያሉ የጋላ አገሮች ከወሎ ጋር የሚገናኙበትንና ለጦርነት የሚመቸውን ፍሬያማና ጠንካራ ቦታ መርምረህ እጥና ። ትራቬርሲ ዘወትር መልካም ነው እያለ ስለሚመካበት ስለ አዳሌ ጉቦ ስለ ጋምቦ ትንሽ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ ። እንደዚሁም ፈረንሳዮች የሚያደርጉትን ለማወቅ ተጣጣር ።. . . ለዚህም ሁሉ ሥራህ አብዱራህማን ይረዳሃል ። እርሱም ብልህ ነው ማናቸውንም ተስፋ የሚያደርገው ከኛ ነው ። ብዙ ነገር መጠየቅና ብዙ ነገር ያስፈልገኛል ማለት ይወዳል ። አንተም ይኸን ሲልህ ፣ መልእክቱ ሁሉ በመልካም ሲፈጸም ሁሉንም ታገኛለህ እያልህ የተለመደውን የብልህት መልስ ስጠው ።
>
> የሚወድህ አ. ባራቲዬሪ
>
> ከረን 4/1894

እንደዚሁም ከካፒቴን ፔርሲኮ ጋር ቴኔንቴ ካርሎ ጂያኒኒ የሚባል ተላከና ሁለቱም አሰብ ከሚገኙ የኢጣልያ ኮሚሳሮች ከነፒስታሎዛ



እየተመካከሩ መሐመድ አንፋሪንና ልጆቹን እነመሐመድ አይደስን ፣ እነአንፈሪን ፣ መሣሪያም ፣ ልዩ ልዩ ስጦታም እየሰጡ በልዩ ልዩ መንገድ የኢጣልያን ታላቅነት ፣ የኢትዮጵያን መንግሥት ታናሽነት ፡ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጥገኝነት ውስጥ መገኘቷን እያስረዱ ሁለቱን ዓመት ቆዩ ። በኋላም ካፒቴን ፔርሲኮ አምባላጌ መጥቶ ከሞተ ወዲህ አውሳ ያሉት ኢጣልያኖች የአምባ አላጌ ጦርነት የሆነ ጊዜ የተገላቢጦሽ ፣ "የምኒልክን ጦር የኢጣልያ ጦር አሸነፈው" ብለው አወሩ ። በአምባ አላጌ የኢጣልያኖችን ድል መሆንና የመቀሌን መከበብ ሁሉ እርግጠኛውን ነገር መሐመድ አንፋሪ እንዳያውቅ ፣ ከዐፄ ምኒልክ መልክተኛም ጋር እንዳይገናኝ ኢጣልያኖቹ አጥብቀው ሲጥሩ ቆዩ ። የዚህም ምክንያት እስካሁን ለመሐመድ አንፋሪና ለሌሎችም ሲሰብኩ የቆዩት የኢጣልያንን ኃያልነት ስለሆነ ፣ አሁን "የኃይለኛው የኢጣልያ ጦር በኢትዮጵያ ጦር ተሸነፈ" ማለት የተሰማ እንደሆነ የመሐመድ አንፋሪ አሳብ እንዳይለወጥና ከምኒልክ ጋር እንዳይደረብ ነው ።

መሐመድ አንፋሪ ፣ ዋናው ጦርነት እስኪዠመር ድረስ ከማዕከላዊው መንግሥት ከድቶ ጨርሶ ወደነርሱ መሆኑን ሳያረጋግጥ በጣም አወላውሎ ለሁለቱም ወገኖች ለየብቻ ታማኝነቱን ይገልጽ ነበር ። በመጨረሻ ግን ፣ ከኢጣልያኖች ወገን ተጽዕኖው ስለ በረከተበት ወደ ኢጣልያኖቹ ተደረበ ። አዛዥ ወልደ ጻድቅም የተለመደውን ያመቱን ግብር ቢጠይቁ ሳይልክ ቀረ ። ከአምባ አላጌ ጦርነት በኋላ ከዓድዋ ጦርነት በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ኢጣልያኖቹና ሽማግሌው መሐመድ አንፋሪ ፣ ልጆቹና ሹሞቹ በተቀመጡበት ስብሰባ እየተደረገ ሲመከር ሲዘከር ሰነበተ ። በስብሰባውም ላይ አብዛኛውን ጊዜ ኢጣልያኖቹ ለመሐመድ አንፋሪ የሚወተውቱት ፣ "እኛ በሰሜን በኩል የምኒልክን ኃይል ጨርሶ ለማጥፋት የበቃ ኃይል አለን ። ነገር ግን ፣ እናንተም የኛ የቃል ኪዳን ጓደኛ እንደ መሆናችሁ መጠን ከድሉም በኋላ በግንባራችሁ ያለውን ለምለሙን አውራጃ ለመካፈል እንዲመቻችሁ አሁን በቶሎ ወደ አንኮበርና ወደ ሐረር የአውሳ ጦር ይላክና ከሸዋ ጦር ጋር ይዋጋ ። በሸዋ ጦር ላይ የአውሳ ጦር የሚፈጽመውን አደጋ ሁሉ የኢጣልያ መንግሥት ከፍ አድርጎ እየገመተ ልዩ ልዩ ድጋፍና ገንዘብም መሣሪያም ለመስጠት ተዘጋጅቷል" እያሉ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፣ ከዐፄ ምኒልክ ወገን ከግብር ማስገበርና የሩቅ ግንኙነት ከማድረግ በቀር ኢጣልያኖች የሚያወሩትን እያስተባበለ ፣ በአምባ አላጌም በመቀሌም እየተሸነፉ መመለሳቸውን በተጨባጭ

የሚያስገነዝብ አልነበረም ። የሆነ ሆኖ ፡ አንፋሪ ግብር በመከልከሉ ዐፄ ምኒልክን መክዳቱ ታወቀ ። ኢጣልያኖችም ፥ “ እርሱን መሣሪያ አድርገው በአንኮበርና በሐረር ግንባር ጦር ሊልኩ ነው ” የሚባል ወሬ ተሰምቶ ነበርና ዳግማዊ ምኒልክ ከአዲስ አበባ ተጉዘው ውጫሌ (ወሎ) በደረሱ ጊዜ ክዳቱን ስላረጋገጡ ፥ የሸፈተውን መሐመድ አንፋሪን እንዲወጉ ሦስት ታላላቅ መኳንንት ላኩ ። እነዚህም ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፡ ደጃች ተሰማ ናደው ፥ የአንኮበሩ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ሲሆኑ የበላይ መሪውም አዛዥ ወልደ ጻድቅ ናቸው ። ምክንያቱም ከሁለቱ መኳንንት በሥልጣን እንኳን ባይሆን በዕድሜ ስለሚሸመግሉ ነው ። እንዲሁም ጦርነቱ የሚደረግበት የአንኮበርና የአውሳ አውራጃ የርሳቸው ክፍል በመሆኑ ጭምር ነው ። ሁለቱ ታላላቅ መኳንንት ራስ ወልደ ጊዮርጊስና ደጃች ተሰማ በሥልጣን እንዳይቀናኑና ተባብረው እንዲሠሩ ለማድረግ ከሁለት ላንዳቸው በመስጠት ፋንታ የጦር አበጋዝነቱን ለአንኮበሩ አስተዳዳሪ ለአዛዥ ወልደ ጻድቅ የሰጧቸውም ይመስላል ። የሆነ ሆኖ ፥ እነዚህ ሦስቱም መኳንንት የየራሳቸውን ጦር ይዘው በአዛዥ ወልደ ጻድቅ መሪነት በታኅሣሥ ወር በእርሳ ፥ በሁለዳዊ ፥ በሁምራ በኩል ሲያልፉ በጥር 17 ቀን ብዙ ጊዜ በማመንታት የቆየው መሐመድ አንፋሪ ጦሩን ይዞ መጥቶ ጦርነት ገጠማቸው ።

ስለ ጦርነቱ ግራዝማች የሴፍ ከተዉት ማስታወሻ በተጨማሪ በሌላ ጽሑፍ ሙሉው ባይገኝም ፥ እነዚሁ እነራስ ወልደ ጊዮርጊስ ወደ አውሳ ሲዘምቱ የዋሉበትንና ያደሩበትን መንገድ በዘረፋ ምክንያት ከዳዊ አገር ባላገር ጋር ወታደር መታኮሱን ፥ በዚህም አዛዥ ወልደ ጻድቅ ፥ “ጠላታችን ገና ወደፊት እያለ በግና ፍየል ጥይቱን ከፈጀው እኔስ ለምን እሑዳለሁ ። ጠላታችንንስ በምን እንወጋዋለን”* ብለው ራስ ወልደ ጊዮርጊስንና ደጃች ተሰማን ተቆጡአቸው ።

ሁለቱም መኳንንት ወረራ የሔደውን ሰው ሁሉ ገርፈው ያመጣውንም በግና ፍየል ደጃን ለዋለው ሰው እንደ ሰጡበት ይኸው ጽሑፍ ይገልጻል ። ከዚህ አያይዞ ኢቂ መስጊድ በሰፈሩበት ጊዜ ፥ “እናንተ የመጣችሁት እኔን ለመውጋት አይደለም ፤ የምትሹት አብዱራህማንን ስለሆነ እሱ የሚገኘው ቲሮ ነውና ሚሌን ይዛችሁ ወደ ቲሮ ሒዱ ። ደግሞ አሽከሮቻችሁ አሽከሮቼን ገድለው ጦር ፥ ጋሻ ፥ ጩቤ ወስደዋልና መልሱ ። ከዚህም ሰፍራ የዋላችሁና ያደራችሁ እንደሆነ አዳል

* ትርጕሙ ወታደራችሁ በግና ፍየል እየቀማ ከባላገር በመታኮስ እዚሁ ጥይቱን ከጨረሰ በኋላ ከመሐመድ አንፋሪ ጋር በምን እንዋጋለን ማለት ነው ።



መጀኑ ይፈጃችኋል ፤ ሚሊን ተሻግራችሁ እደሩ” የሚል የመሐመድ ሐንፈሊ (አንፋሪ) መልስ መጣ ። ከዚያ ከደባል ተነሥተው በጥር 17 ቀን ሰርዶ ሰፍረው ሳለ ፥ ከከተማው ጦሩን አስከትቶ የሁለት ቀን መንገድ ተጉዞ መጥቶ ጦርነት እንደ ገጠማቸውና ድል እንደሆነ ፥ የመሐመድ ሐንፈሉም አሊ የሚባል የሚወደው ልጅ ፡ የወንድሙ ልጆች ፥ ሦስት ያጐቱ ልጆች እንደሞቱ ይነበባል ። እነአዛዥ ወልደ ጻድቅም ከዚህ ድል በኋላ ወደፊት አልፈው ከከተማው አድሌ ገብ (ሐደሊ ገብ) በሰፈሩ ጊዜ ፥ ኢጣልያኖቹ የሰጡት ወጨፎ ወተርሴ እንደ ተገኘ ፥ ከዚያ በኋላ ባገሩ ጠባቂ አድርገው እንደ ተመለሱ በማረጋገጥ የአውሳውን ታሪክ ይፈጽማል ።[1]

ሦስቱ ታላላቅ መኳንንት ፥ ኢጣልያኖች በጣም ተስፋ ያደረጉበትን ፥ መሐመድ አንፋሪን በጥር 17 ቀን ሲያሸንፉ ፥ ላገራቸውና ለንጉሣቸው ከፍ ያለ ሙያ ሠርተዋል ። በዓድዋ በኩል የተሰለፈው ዋናው ንጉሡ ያሉበት ጦር መኳንንቱም ፥ ወታደሩም ሞራሉ ከፍ እንዲልና ዋናውን ጦርነት በልበ ሙሉነት እንዲቀጥል አድርገውታል ። የአውሳውን ድል ለመንገር ከነአዛዥ ወልደ ጻድቅ የተላኩት ሰዎች ዐፄ ምኒልክ ዘንድ የደረሱት በየካቲት 22 ቀን እንደሆነ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ገልጸውታል ።[2] በጥር 17 ቀን ድሉን ካገኙ ወዲህ ፥ መልክተኞቹ ወደ ዐፄ ምኒልክ ለመድረስ ከአንድ ወር በላይ ጊዜ ፈጅተዋል ማለት ነው ። የዚህ ወሬ በትክክል በተሰማ በማግሥቱ የካቲት 23 ቀን የዓድዋው ጦርነት ተደረገ ማለት ነው ።


የአንኮበሩ ሊቅ አለቃ ዘወልዴ አዛዥ ወልደ ጻድቅ እዚህ (አውሳ) ድል አድራጊነት በቅድሚያ እንደቀናው አንተም ምኒልክ በዚያ (በዓድዋ) ደግመህ አሸንፍ ለማለት ቀጥሎ ያለውን ሣህልክ ቅኔ ተቀኙ ።

ምኒልክ ድግም ድምፀ የብቦ
እስመ ወልደ ጻድቅ ቀደመ ድምፀ ይባቤ በገቦ
ዓልቦ ዘነግሠ ቅድመ ዚአከ
ወድኅረ ዚአከ ዘይነግሥ ዓልቦ

1 ከፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከእጅ ጽሑፍ ከፍል የተገኘ ።
2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ምዕ.63



አዛዥ ወልደ ጻድቅ
ከደ ካስትሮ ኔላ ቴራ ዴል ንጉሥ




ራስ ወልደጊዮርጊስ አቦዬ

ኢንአቢሲኒያ ከሚባለው ከአናራቶሪ መጽሐፍ

## ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

### በኢጣሊያኖች ዘንድ የጦርነት ምክር — በሰላይ ተታለው ከምሽግ ወጥተው ለመዋጋት እንደቆረጡ

ባዬ ምኒልክ ዘንድ ባለፈው እንደ ተመለከትነው ፤ ጣልያኖች ከምሽግ ወጥተው አለመዋጋታቸው ፤ መረብን ተሻግሮ የመውረሩ ነገር በአንድ ወገን በወሃ እጦት የተነሣ መቅረቱ ፤ ወደሰሜን አቅጣጫ ጦር ሠራዊቱን አነቃንቆ ጣልያኖችን ከምሽግ የማስወጣቱ አሳብ መሳቱ ፤ ስንቅ አልቆ ወታደር አንዳንድ ጊዜ እስከ ሺሬ ድረስ እየዘለቀ በዘረፋ ከባላገር ጋር መጣላቱ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ ነበር ። ይህ የተደራረበው ችግር ሁሉ አንድ መፍትሔ ለመፈለግ አስገድዷል ። ለዚህ ሁሉ የተገኘው መፍትሔ ፤ እንደ ምንም በሰላዮች አማካይነት አታሎ ከምሽግ ጣልያኖቹን እንዲወጡና እንዲዋጉ ማድረግ ስለሆነ ይህንኑ ለመፈጸም በየካቲት 23 ቀን በተደረገው የጦርነት ዋዜማ ንጉሠ ነገሥቱና ራሶቻቸውም ትኩረት ሰጥተዋል ። በዚህም ተግባር የእንትጮው ተወላጅ ባሻ አውአሎም ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል ።

በዐፄ ምኒልክ በኩል ፤ ይኸን የመሰለ ችግር ሲኖር በጄኔራል ባራቲዬሪ በኩል ያለው ችግር ይነስ ይብዛ ተመሳሳይ ነው ። በሁለቱ ጦር መሪዎች መካከል ልዩነት ቢኖር ፤ እርሱ የበላይ አዛዦች ሲኖሩት ዐፄ ምኒልክ የበላይ የለባቸውም ። እርሱ ወደ ምሽጉ ለመሳብ ፤ እርሳቸው ወደ ሜዳ እንዲወጣ ለማድረግ በመሞከር በዓላማ ይለያያሉ ። በሁለቱም የጦር ሠፈር የሁለቱም ወገን ሰላይ ተሠማርቶ ወሬውን ለየክፍሉ ያቀብላል ። በቃፊርነት የሚያገለግሉትም እየተቀያየሩ ሥራቸውን በየበኩላቸው በትጋት ይሠራሉ ።

ጄኔራል ባራቲዬሪ ወጥቶ ለመዋጋት አዳጋች መሆኑንና ፤ በምሽግ መቆየቱም የስንቅ ማለቅ ችግር እንደሚያስከትል ተረድቶታል። በቅርብ ከድተው ወደ ወገናቸው የሔዱት እነራስ ስብሐት የአጋሜንና የእንደርታን ሕዝብ ከማሳደም ጋር ከጀርባው መንገድ እያፈረሱና የስልክ ሽቦ እየቆራረጡ ፤ በማይ መሬት እንደሆነው ፤ አንድ አንድ ጊዜም ይዋጉታል ። ይኸ ሁሉ ተደራርቦ ሥጋትና አሳብ በራሱ ኃላፊነት ላይ ተንጠልጥሎ እንቅልፍ ነሥቶታል ።

ከሁሉ የበለጠ የሚያናድደው ከሮማ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚያስተላልፍለት ምጸትና ወቀሳ አዘል ቴሌግራም ነው ። ባንድ ወገን ፣ “ በአንድ ውጊያና ድል የአምባላጌንና የመቀሌን ውርደት ሊመልስ አልቻለም ” ብለው በሮማ በርሱ እግር ፣ “ከርሱ በብዙ ረገድ የተሻለ ነው” ብለው የሚያምኑበትን ጄኔራል ባልዲሦራን እ.ኤ.አ. በየካቲት 22 ቀን ሾመውታል ።

በተወሳሰበ አሳብ ላይ የሚገኘው ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ “እበሾች እመሽግሁበት መጥተው ይወጉኝና አሸንፋቸዋለሁ” ብሎ ጠብቆ ሞኝ ባላጋራ በማጣት ሳይሆንለት ከቀረ ወዲህ ፣ “ ከአለንበት ከአዲግራት ወደኋላ ወደአዲ ኡግሪና ወደ ሰናፌ ተመልሰን ለስንቅ ማግኛው ለአሥመራና ለምጥዋ ቀረብ ባለው ሥፍራ ሆነን እንከላከል” አለ ። የበታች የጦር አለቆቹ ፣ “በእምባ አላጌና በመቀሌ ድል እየሆንን የለቀቅነው አገር አንሶ ፣ አሁን ደግሞ ከአዲግራትና ከሳውሪያ ወደኋላ ከተመለስን ጨርሶ የመሸነፍ ያህል ነው ” ብለው ተከራከሩት ። በመጨረሻ የመሣሪያና የስንቁ ኃላፊ ሌተና ኮሎኔል ራፓሞንቲ እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 4 ቀን በኋላ ፣ በከብትና በስንቅ ማለቅ የተነሣ አዲግራትና ሳውሪያ ላለው ጦር ስንቅ ለማቀበል አለመቻሉን ለጄኔራል ባራቲዬሪ በቴሌግራም አስተላልፎለታል ። ስለዚህ የዚህ ሁሉ የችግር ሐተታ የተጫነው ይኸው ጠቅላይ አዛዥ አንድ ውሳኔ በቶሎ ለመወሰን በግድ አስፈላጊነቱ ተሰማው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ወደኋላ ማፈግፈግ ወይም ወደፊት ገፍቶ መዋጋት የሚገባ መሆኑን ከበታች ጄኔራሎች ጋር ለመመካከር የካቲት 20 ቀን በድንኳኑ ውስጥ ሰበሰባቸው ።
የተሰበሰቡትም ፣

ጄኔራል ጉሴፔ አሪሞንዲ — የብርጌድ አዛዥ
” አማኑኤል ዳቦርሚዳ — ” ”
” ማቴዎ አልቤርቶኒ — ” ”
” ጉሴፔ ኤሌና — ” ”
ኮሎኔል ቫሌንዛኖ — ሼፍዲታ ማዦር

ናቸው ። እነዚህም በተሰበሰቡ ጊዜ ዋናው አዛዥ ሌተና ጄኔራል ባራቲዬሪ ከስንቁ ኃላፊ ከሌተና ኮሎኔል ራፓሞንቲ ፣ አሥመራ ከሚቀመጠው ከምክትሉ አገረ ገዥ ከጄኔራል ላምቤርቲ የተላኩትን ቴሌግራሞች ኮሎኔል ቫሌንዛኖን እንዲያነብ አዘዘው ። ከተነበበና አንዳንድ ንግግር ከተደረገ በኋላ ጄኔራል ባራቲዬሪ እንደዚህ አላቸው ። “የመ



ጨረሻው ውሳኔ የሚሰጠው ከኔ በመሆኑ ፣ አሁን የጠራኋችሁ ለጦርነት ምክር አይደለም ። ነገር ግን እንደ ዘወትሩ ቅን ልባችሁን ገልጣችሁ አሳባችሁንና የጦር ሠራዊቱን ሁኔታ እንድትገልጹልኝ ነው ።”

ከዚህ በኋላ በመጀመሪያ ጄኔራል ዳቦርሚዳ እንደዚህ ሲል ተናገረ ።

> በአሁኑ ጊዜ አንድም ወታደር ከጠላት ጋር ከተሰለፍን ከሦስት ወር በኋላ ወደኋላ እንመለስ የሚል አይገኝም ! ኢጣልያም ወደኋላ ከመመለስ ሁለት ወይም ሦስት ሺህ ሰው በጦርነት መሠዋትን ትመርጣለች ። እንዲያውም ስንቅ ከማለቁ የተነሣ ፣ ሌሎች እመርከብ ላይ ያሉት ወታደሮች ሳይደርሱ እኛው በቶሎ እንዋጋ . . . የወታደሩም ከፍ ያለው ሞራሉ (መንፈሱ) ወደኋላ እንመለስ ያልነው እንደሆነ ዝቅ ብሎ ይዋረዳል ። ሹማምንቱም ሁሉ አሳባቸው ከዚህ ያልወጣ መሆኑን በዋስትናዬ አረጋግጣለሁ ። ወደኋላ እንመለስ ያልን እንደሆነ ግን ፣ በቁጥር የሚበልጠን በጉዞና በመንገድ ከኛ የሚፈጥነው መንገዱን ሁሉ የሚያውቀው ጠላታችን ከሸፈቱብን ሰዎች ጋር ተስማምቶ በሰላዮቹ እየተመራ ተከታትሎ እየወጋ አደጋ ሊያደርግብን ይችላል ።1

ከጄኔራል ዳቦርሚዳ ቀጥሎ የተናገረው ጄኔራል አልቤርቶኒ ነው ። እርሱም ያገር ተወላጅ ጦር አዛዥ በመሆኑ ፣ ወዲያውም ያገር ውስጥና የኢትዮጵያንም ጦር ሁኔታ በስለላ የሚያስመረምር ነበርና በተራው እንደዚህ ብሎ ተናገረ ።

> የጠላት ጦር እየጐደለ ሔዷል ። ግማሹ ወደ ሽሬ ለዘረፋ ተበትኗል ። ግማሹ ወደ ሸዋ መመለስ ጀምሯል ። ዓድዋ በቀረውም ጦር ላይ በሽታ ገብቶበታል ። . . . ጉበዙ ኰሎኔል ስቴባኒ የሁለት ባታዮ . . . ካፒቴን አደኔ የሁለት ክፍል (ኮምፖኝ) ጦር ይዘው ደርሰዋል ። ማዦር ባሌ ኃይለኛውን የ7ኛውን ቦታዮ ጦር ይዞ ነገ ጧት ይደርሳል ። መድፎቻችን በደህና ሥፍራ ተጠምደዋል ። ወደ ዓድዋ የሚወስዱ መንገዶች ለሰአሉ በነዚያ አልፈን ይኸን የሰነፈውን የጠላት ጦር አደጋ እንጣልበት ። እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ ስምምነት በመካከላችን ሳይኖር እዚህ ደርሰናል ። አሁን ግን ፣ ወደፊት አልፎ ለመዋጋት የሁላችን ፈቃድ ነው . . . ወደኋላ ያፈገፈግን እንደሆነ ግን ፣ እስካሁን ደክመን ያቆምነውን የጠላት ጦር ለቀን ቅኝ አገራችንን ለወረራ አሳልፈን መስጠታችን ነው ። ከዚህም በቀር ወደኋላ መመለስ የኛን ጦር መንፈስ ሃምሳ በመቶ ያቀዘቅዘዋል ።

ጄኔራል አልቤርቶኒ ፣ በስብሰባው ይኸን ቃል መናገሩን ጄኔራል ባራቲዬሪና ሌሎች ጸሐፊዎች ሁሉ በጻፉት ይገኛል ። ነገር ግን ፣ እርሱ ራሱ በኋለኛው ዘመን በጻፈው ማስታወሻ የቀረውን ሁሉ መናገሩን ሲያ

1 Adua, E. Bellavita, PP, 318 - 319 . La Prima Guerra d' Africa, R, Battaglia, PP, 733-786

ምን ፣ "ያበሾቹን መታመም ወይም ወደ ሸዋ መመለስ አልተናገርኩም" ሲል ከዷል ። ይኸውም የጦርነቱ የአጀማመሩ ምክንያት የስለላው ሥራ ስለነበረ ፣ አልቤርቶኒ ብዙ ጊዜ በምርኮ አዲስ አበባ ሰንብቶ ወደ አገሩ ሲመለስ የጦርነቱን ኃላፊነት ከራሱ ላይ ለማስወገድ "አላልሁም" ያለ ይመስላል እንጂ ፣ ከዓድዋ በፊት ባለው ጊዜ ሳይናገር አልቀረም ።

ከርሱ ቀጥሎ የተናገረው ጄኔራል አሪሞንዲ በፋንታው እንደዚህ አለ ።

> ያግሮቹን ቁጥር ሰላዮቹ የሚያመጡልን ከመጠን እያበዙ ነው ። ጠላት በመካከሉ ስምምነት ስለሌለው እኛን ለመውጋት ያመነታል። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ ወደፊት ቀድሞ መውጋት እንጂ ፣ እዚህ ውጊያ መጠበቅ ከንቱ ነው ። እንደዚህ ከተሰበሰብን በአንድነት ወደፊት አልፈን መዋጋት ይሻላል ። ከውጊያም ይበልጥ በሽታ ሊጨርሰን ይችላል ። ወደኋላ መመለስ ወታደሮቻችንን አስንፎ አልሆነ ሥፍራ ላይ ወደ መከላከል ያደርሰዋል ። ወደ ፈረሰው አገር ስንመለስ አገሬው ስለሚነሣብን ለጠላትም ይመቸዋል ። ከጠላት ጋር እንደዚህ ቅርብ ለቅርብ ተሰልፈን ብዙ ሳምንቶች ወጥተን ሳንዋጋ ማሳለፍም ስንፍና ነው ።

ከርሱ ቀጥሎ በመጨረሻ የተናገረው ፣ ባለፈው ጥር ወር ከኢጣልያ አገር የመጣው ጄኔራል ጕሴፔ ኤሌና ነው ። ከሁሉ መጨረሻ የተናገረው በሽምግልናው መሆኑን ራሱ ከውጊያው በኋላ ጄኔራል ባራቲዬሪ በተከሰሰበት የወታደር ፍርድ ቤት ጉባዔ በሰጠው ምስክርነት ሲገልጽ ፣ ራሱ የተናገረው ቀጥሎ ያለው መሆኑን ጨምሮ ያስረዳል ።

> አራተኛው ተናጋሪ እኔ ስለሆንኩ ፣ ሽምግልናዬ በመጨረሻ የመናገርን መብት እንደሰጠኝ ገለጽሁ ። በተረፈ እጦሩ ግንባር (እምሽጉ) ከደረስሁ 12 ቀኔ ብቻ ስለሆነ በጠላት ላይ በቁጥሩም በመንገዱም በውጊያውም ስፍራ አመራረጥ በሁኔታው ሁሉ የግል አስተያየት ስለሌለኝ የምሰጠው ቃል መሠረቱ የጓደኞቼ አሳብ ብቻ ነው ። ስለዚህ የነርሱን አሳብ በመከተል ወደፊት ሔደን እንዋጋ የሚለውን ቃል ደግፌ የግል አሳቤን እንደዚህ በሚል ቃል ወሰንሁ ። "ወታደራችንን አጠቃለን እንሰብስብና ጠላታችንን አለበት ድረስ ሔደን እንፈልገው ።"

ከመጨረሻው ተናጋሪ ከጄኔራል ኤሌና ቀጥሎ የተናገረውና ጉባዔውን የዘጋው ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ነው ። በእውነቱ የርሱ አነጋገር አስተያየቱም ከነርሱ የተለየ ነው ። በሹመትም ከፍ ያለ በእእምሮም የበሰለ ስለሆነ ፣ እንደ ሌሎቹ የራሱን ጦር አጋኖ የኢትዮጵያን ጦር ሳያኮስስ በአጭሩ እንደዚህ አለ ። "ምክሩ የድፍረት ነው ። ጠላታችን ጉበዝና ሞትን የሚንቅ ነው ። ለመሆኑ የወታደሮቻችን



ሞራል (መንፈስ) እንደ ምንድነው ?" ብሎ ጠየቀ ። ሁሉም ጄኔራሎች በተጠንቀቅ ቆመው "በጣም ጥሩ ነው" ብለው መለሱለት ። ከዚያ በኋላ ፣ "እጠላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቻችን የሚያመጡልኝን እጠብቃለሁ ፤ እነርሱ ወዲያው እንደ ደረሱ አንድ ውሳኔ እቆርጣለሁ" ብሎ ጄኔራሎቹን አሰናበተ ። ዋነኞቹ የብሪጌድ ጦር አዛዦች ይኸን በሚመካከሩበት ጊዜ ፣ የቀሩት የጦር አለቆች ከድንኳኑ ውጭ ሆነው ውሳኔውን ይጠባበቁ ነበር ።[1]

በጄኔራል ባራቲዬሪ ንግግር በመጨረሻው ፣ "ከጠላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቻችን የሚያመጡልኝን ከሰማሁ በኋላ አንድ ውሳኔ እቆርጣለሁ" ያለው የእንትጮው ተወላጅ ባሻ አውአሎምን ነበር ። እርሳቸውም በስለላ እንደምን አገራቸውን እንዳገለገሉ ያገራችን ሽማግሌዎች ፣ ከሚያውቁት ጋር ካርሎ አናራቶሬ የሚባለው ኢጣልያዊ እንደዚህ ሲል ጽፏል ።

> ባሻ አውአሎም የሚባለው ከሰላዮቻችን አንዱ ነበረ ። እርሱም ለጠላታችንም ሰላይ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት ከብዙ ቀን በፊት በራስ መንገሻ አቅራቢነት ከዐፄ ምኒልክ በተገናኘ ጊዜ ሃምሳ ብር ጉርሻ ተቀብሎ ራስ መንገሻ ሊያውቅ የሚፈልገውን እየመረመረ በመግለጽና እንደዚሁም ራስ መንገሻ የሚለውን ለባራቲዬሪ በመንገር ጠንክሮ እንዲሠራ ከምኒልክ አደራ ተቀብሎ ተሰናበተ ። ከዚህም ቀን በቀር ከንጉሡ ጋር ሁለተኛ አልተገናኘም ። ራስ መንገሻ እንደነገረው አውአሎም ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ መጥቶ ፣ "የኢትዮጵያ ጦር ስንቅ አልቆበታል ። ብዙም ወታደሮች ሞተዋል ፤ የቀሩትም ታመዋል ። ስለዚህ በዓድዋም ከመቀመጥ ወደኋላም ከመመለስ ፣ ወደፊት ወደ ቅኚው አገር መረብን ተሻግረው አልፈው ስንቅ ሊፈልጉ ነው ።" አለ ዚያም ደግሞ በመጋቢት 1 ቀን 'የካቲት 23 ቀን' ንጉሡ እንደ ፊተኛው አሳቡ ወደኋላ ለመመለስ ነው ብሎ ተናገረ ። ከዚህም ወሬ የስንቁ ማለቅ የበሽታው መግባትና ወደኋላ ለመመለስ መታሰቡ እውነት ነው ። ወደፊት ወደ ኤርትራ ሊገቡ አስበዋል ያለው ግን አበቱ ነው ። ባራቲዬሪ ለመዋጋት የቆረጠው በተለይ በነዚህ ወሬዎች ተመሥርቶ ይመስላል ።

ባሻ አውአሎም ፣ በ22 ሰዓት (ከሌሊቱ በ4 ሰዓት) የተደረገውን የኛን ሰልፍ በተመለከተ ጊዜ የኢጣልያኖች ጦር መጣ ብሎ እንዲነግር አንድ ወጣት ላከ ። ምኒልክ ግን ፣ ሌሊት አገር ለመፈተሽ የወጡ ወታደሮች ይሆናሉ እንጂ ጣልያኖች ውጊያ ቆርጠው የሚወጡ አይመስሉኝም ሲሉ መጠርጠራቸውን ገልጸው ፣ ቢሆንም በጥንቃቄ መጠባበቅ ነው የሚል ትእዛዝ ለራስ መንገሻ ላኩባቸው ። ይኸም ሰላይ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ጋር ሆኖ ወደፊት ተጉዞ እኩለ ሌሊትም ራዓዮ ተራራ ሲደርስ ከኛ ጦር ውስጥ አምልጦ የቱሪቶ ባታዮ ከመ

---

1 Memoire d' Afrique ..(Chap.) XXX; Italia ed Etiopia, PP. 316 - 321

ድረሱ በፊት ወደ ራስ መንገሻ ሰፈር ደረሱና በጊዜው ለራስ አሉላ ለራስ መንገሻ ለዋግሹም ጓንጉል ነገረ ። ለነዚህም ራሶች ራስ ወሌና ራስ መኩንን ደረሱላቸውና ሁሉም በአንድነት ግንባር ተደመሩና የኢጣልያ ጦር መታኮስ ሲጀምር ለመዋጋት ተዘጋጁ ...[1]

ሌላ ደግሞ ፣ ግዕዝኛ ጽሑፍ ለሰላ ከባራቲዬሪ የተላከው ባላምባራስ ገብረ እግዚእ የሚባል መሆኑን ይጠቅሳል ። ገብረ እግዚእ ከባሻ አውአሎም ጋር ተነጋግሮ ሁለቱም ወደ ዐፄ ምኒልክ ገብተው "ጣልያንን ከምሽጉ ብናወጣልዎ ምን ይሰጡናል" ብለው እንደ ጠየቁዋቸው ፣ ንጉሡም ብዙ ብር ለመስጠት በመሐላ ቃል እንደ ገቡላቸው ይገልጻል ። ከዚህ በኋላ ባላምባራስ ገብረ እግዚእ ወደ ባራቲዬሪ ሒዶ የሠራዊቱን ስንቅ ፍለጋ መበተን ፣ ምኒልክ ለመሸሽ ማሰባቸውን ነግሮ እንዲወጣ ማድረጉን[2] ያረጋግጣል ። እንደዚሁም ግግሹ ሰላይ ፣ "ዐፄ ምኒልክ ታመዋል ፣ ራስ ወሌ ሞተዋል" እያለ በማውራት የኢጣልያ ጦር ከምሽግ እንዲወጣ ገፋፍቷል ማለት ነው ።

ስለዚህ የስለላ ጉዳይ ግዕዝኛው ሰነድ እንደዚህ ይላል ።

"ወእምዝ ፈነዎ ጀኔራል ባራቲዬሪ ለባላምባራስ ገብረ እግዚእ ወልደ አብ ከይሲ ከመ ይኩን ኀበ ባሻ አውአሎም እንተ ሰብአ ዓይን ዘው እቱ ሰላይ ዘኢጣልያን ዘይነብር በጥቃ ዓድዋ ወተማከሩ እሉ ደቂቀ አባ ከይሲ ወቦኡ ኀበ ምኒልክ ወይቤልዎ ምንተ ትሁበነ ከመ ናውጽእ ለከ ሠራዊተ ጣልያን እምነ እርድ ። ምኒልክኒ ንጉሥ አሠፈዎሙ ለእለ ባሻ እውአሎም ከመ ይሁቦሙ ብዙኀ ብሩረ ወመሐለ ሎሙ ወእምዝ ሖረ ባሻ (ባላምባራስ) ገብረ እግዝእ እኅወ አውአሎም በጽሐ እንኪጪው ወዜነዎሙ ለጀኔራል ባራቲዬሪ ወአሪሞንዲ ከመ ተዘርወ ሠራዊተ ንጉሥ ለሐሚሠ እክል እስመ ጸንአ ቦሙ ረኃብ ወተርፈ ምኒልክ ለባሕቲቱ ወይፈቅድ ይጕየይ ከመ ያድኅን ርእሶ ወሰበ ሰምኡ ዘንተ እሉ ጀኔራል ተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሐ ወተነፍሐ ቀርን ።"

ባለፈውም እንደ ተመለከትነው ፣ ከዚህ በላይም አናራቶሬ እንደ ጻፈው ፣ ዐፄ ምኒልክ ኢጣልያኖቹ እስከ መሸጉበት እስከ ሳውሪያ ሔደው እንዳይዋጉ ሠራዊታቸውን ማስጨረስ ስለሆነ ፣ ዝም ብለው የኢጣልያኖችን ከምሽግ መውጣት ለብዙ ጊዜ እንዳይጠብቁ በሰፈር በሽታ ገብቶ ከዚህም የባሰ ወታደሩ ስንቅ አልቆበት የሚራብ ፣ በዚህም የተነሣ በዘረፋ ከባላገሩ ጋር የሚጣላ በመሆኑ ከፍ ያለ ችግር እንዳይፈጠር ብዙ አስበውበታል ። እንወጣም ብለው ያስቸገሩትን ኢጣልያኖች ከምሽግ አውጥቶ ለመዋጋት ይኸን የመሰለ በተንኮል

1 In Abissinia, Carlo Annaratore, P. 343

2 የኢትዮጵያ ጥናት (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ቁ. 681 ፣ ገጽ ፻28—፻29



የማስወጣት ዘዴ መፍጠር አስፈለጋቸው ። ይህን ዘዴ ባለፈው ከአናራቶሬ ወይም ከግዕዝኛው ጽሑፍ እንደ ተገነዘብነው ፣ "የሐበሾች ጦር ስንቅ አልቆበት ተርቧል ። ግማሹም ታሟል ። ብዙም ሞቷልና አሁንም በድንገት ደርሰህ ብትወጋው ታሸንፈዋለህ" እያለ ለኢጣልያኖች ታማኝ መስሎ ተናግሮ የሚያሳምን ሰው ሲፈለግ ፣ የዚህ ተግባር በራስ መንገሻ ዮሐንስ አማካይነት በባሻ አውአሎም ላይ ወደቀ ። እርሳቸውም ወገኖቻቸውን በደንብ ለማገልገል ቢሉ አስመስለው በቀጥታ ወይም በነርሱ ታማኝ በነበሩት ዘባላምባራስ ገብረ እግዚእ አማካይነት ለባራቲዬሪ ነግረዋል ። በመጨረሻም የኢጣልያ ጦር አዛዥ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አንድ ጊዜ ፣ "ወደ ኋላዬ ልመለስ" ሌላ ጊዜ ፣ " በምሽጌ ተቀምጬ ሐበሾቹ እርስ በርሳቸው ተጣልተው ወይም ስንቅ አልቆባቸው ሲበተኑ እዋጋለሁ" እያለ ብዙ ጊዜ የቆየውን አሁን ባሻ አውአሎምና ጓደኞቻቸው በነገሩት ወሬ ተመርኩዞ በየካቲት 22 ቀን ማታ ከምሽጉ ወጥቶ ለመዋጋት እንዲቆርጥ አደረጉት ።

ጀኔራሎቹን ሰብስቦ አሳባቸውን ከሰማ በኋላ ፣ "እጣላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቼ ከተመለሱ በኋላ አንድ ውሳኔ እሰጣለሁ" ብሎ በነበረው መሠረት የነዚህን የሰላዮች ወሬ ከሰማ በኋላ ፣ የመጨረሻውን የኢጣልያና የኢትዮጵያ ዕድል የሚወሰንበትን ትልቁን የዓድዋ ጦርነት ለማድረግ ጀኔራል ባራቲዬሪ እ. ኤ. አ. የካቲት 29 ቀን(የካቲት 22 ቀን) ማታ ጦሩን ከዚህ እንደሚከተለው አሰልፎ ለመውጣት ተዘጋጀ ።

፩ኛ. ጀኔራል ዳቦርሚዳ 3800 ወታደር 18 መድፍ ይዞ በቀኝ በኩል
፪ኛ. " አሪሞንዲ 2493 ወታደር 12 መድፍ ይዞ በመካከል
፫ኛ. " አልቤርቶኒ 4076 ወታደር 14 " " በግራ በኩል
፬ኛ. " ኤሌና 4150 ወታደር 12 መድፍ ይዞ ከኋላ ተጠባባቂ ሆኖ እንዲዘምቱ ተደረገ ።

የነዚህ ድምር 14,579 ወታደር 56 መድፍ ነው ። ሌሎች 5000 ግድም የሚሆኑት ውስጥ ግማሾቹ ከዋናው ጠቅላይ አዛዥ ከጀኔራል ባራቲዬሪ ጋር ሆነው ፣ የቀሩት ደግሞ በልዩ ልዩ አገልግሎት ተከፋፍለዋል ። ከነዚህ ውስጥ 6790 የሚሆኑት በተጽዕኖዎቻቸው ሥር ካደረጉት ከልልና ከሱዳን ከሌላም ኢጣልያኖች ከያዙት አገር የተሰበሰቡ ያገር ተወላጅ ወታደሮች አሉበት ። በተረፈ ከማገሮር አሚሊዮ 1300 ጦር በሰሜን በኩል በዩሃ አራተኛ የጦር ግንባር ከፋች ሆኖ እንዲዘምት ተደርጓል ።[1]

1 Memoire d' Afrique...Chap. XXXII; Italia ed Etiopia, P. ; 330in Abyssinia C. Annaratore.. PP. 345 - 350; The campaign of Adwa.. PP. 261 - 271,

ጀኔራል ባራቲዬሪ ፣ በዚህ ዓይነት ጦሩን ከፋፍሎ ከደለደለ በኋላ ፣ እ.ኤ.አ. የካቲት 29 ቀን (የካቲት 22 ቀን) ያወጣው ትእዛዝ የዳቦርሚዳ ፣ የአሪሞንዲና የአልቤርቶኒ ጦር እያንዳንዱ ከማታው በሦስት ሰዓት የሳውሪያን ምሽግ እየለቀቀ በዓድዋ አቅጣጫ ጉዞውን እንዲጀምርና እነርሱም ጉዞ ከጀመሩ አንድ ሰዓት ቆይቶ ተጠባባቂው የኤሌና ጦር ተከትሎ እንዲጓዝ ነው ። አስቀድሞ እንማገርር ሳልሳ ያዘጋጁት ያገር ፣ የስፍራ ፣ የወንዛ ወንዝና ፣ የተራራዎች ምልክት ያለበት የጦር ፕላን ተሠርቶ ስለነበረ ፣ የዚሁ ፕላን አንዳንድ ግልባጭ ለአዝማቾች ተሰጥቶአቸዋል ። ሊዋጉ ያሰቡት በደንበኛ ፕላን ስለሆነ ፣በዚህ በፕላኑና በምክርም በተወሰነው መሠረት የቀኙ አዝማች የዛህላን በር የረቢ አሪዮኒን መንገድ ይዞ እንዲጓዝ ፣ የመካከለኛው አዝማችና ተጠባባቂው ጦር የእንዳ ገብጣን አቅጣጫ ይዞ እንዲጓዝና የግራው አዝማች በኪዳነ ምሕረት በር በኩል እንዲሔድ ተወስኗል ።

እንደ ወጣው ትእዛዝ ፣ እያንዳንዱ ወታደር 112 ጥይት ፣ የሁለት ቀን ስንቅ ፣ ከላይ የሚደርበውን ካፓ (መንጣልያ) ፣ የውሃ ኮዳና የዳቦ መያዣውን እንዲይዝ ፤ የእርድ ከብት ከነመሣሪያው በሠራዊቱ ኋላ እንዲጓዝ ፤ የዠኒ ክፍሎች (ምሽግና የጦር ስፍራ የሚያከናውኑት ) ስልከኞችና ቴሌግራም አስተላላፊዎች መሣሪያዎቻቸውን ይዘው በየክፍላቸው ሆነው ከየክፍሉ የጦር አለቆች የሚሰጣቸውን ቃል ለጠቅላዩ ሹም በፍጥነት እንዲያስተላልፉ ትእዛዝ በዝርዝር ተሰጥቷል ። ምንም እንኳን ጦሩ በቀኝ ፣ በግራ ፣ በመካከልና በኋላ አራት ላይ ቢከፈል ፣ ከዋናው ሰፈር ለጦርነት ጉዞ የሚጀመርበት ሰዓት ቢለያይ ፣ አንዱ ሠራዊት ሌላውን ርቆት እንዳይሔድና ተነጥሎ በመገሥገሥ ከጠላት ጦር ጋር ብቻውን ገጥሞ አደጋ እንዳይደርስበት ከበላዩ አዛዥ ለየጀኔራሎቹ ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቷል ። የመንገድ መሳሳትም እንዳይኖር ተጠንቶ የተዘጋጀው የካርታ ፕላን ለየአለቆቹ ከመታደሉ በቀር ፣ በነርሱ ውስጥ ሆነው የሚያገለግሉት ያገር ተወላጆችና ባላገሮች መንገድ እንዲመሩ እየተከፋፈሉ ለየክፍሉ ጦር ተሰጥተው ነበር ።

ከነዚህም ጋር የዓድዋን አካባቢ የሚያውቅ እንደሚረዳው ፣ ሚዳ ቢኖርም በሚዳው ላይ ተበታትነው የሚታዩ ብዙ ጉብታዎች ስላሉ ፣ በነዚህ ጉብታዎች ሆነው “ቴሌግራፍ ኦፕቲክ” በሚባል መሣሪያ እየተመለከቱ ፣ “ለገሌ ረዳት ጦር ይጨመርለት ፤ እገሌ ወደፊት ይግፋ ወይም ወደኋላ አፈግፍጎ ለእገሌ ይደረብና ይኸን ስፍራ ይያዝ”የሚል ትእዛዝ የሚሰጡ የፕላንና የሎጂስቲክ ሹማምንት ተመድበዋል ። የነርሱን ትእዛዝ ደግሞ እያፋጠኑ ለየክፍሉ የጦር አለቃ የሚያደርሱ የፈረሰኛ ጓዶች አሉ ። ተዋጊ የጦር አባል ሞቶ ወይም ቆስሎ በወደቀ



ጊዜ በቶሎ አንሥተው የሕክምና እርዳታ የሚያደርጉት ሁሉ በየክፍላቸው በደንብ ተደልድለው ተሰልፈው ነበር ።

እንደዚሁም ፣ ወሬው ለኢትዮጵያ ጦር ደርሶ ተጠንቅቀው እንዳይጠብቁ በማለት ከሰፈር የመነሻው ጊዜና ሰዓት ለማንም እንዳይነገር በጥብቅ ታዞ ነበር ። ነገር ግን ይኸ ሁሉ ከኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ሾሮ ያመለጠ አልነበረም ። ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ግራዝማች ዮሴፍ ተማርኮ በኢትዮጵያውያን እጅ ከገባው ከጀኔራል አልቤርቶኒ ጋር ጭውውት ሲያደርጉ ፣ ስለ ስለላ ጉዳይ አንሥተው በተነጋገሩበት ጊዜ ፣ “እናንተ ሰላዮቻችን የምትሏቸው ምኒልክ የላኩላችሁን ነው ። የናንተ ሰላዮች ይነስ ይብዛ በሙሉ ለንጉሡ የሚታዘዙ ናቸው ። እርግጠኛውን በናንተ በኩል የተደረገውን በትክክል ይነግሩን ነበር ” ብለው እንዳጫወቱትና የተማረኩትም የኢጣልያ ሹማምንቶች ከባታዮ ወታደሮቻቸው ውስጥ ሰላዮች የነበሩትን እንደ ተመለከቷቸው ፣አልቤርቶኒ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ያወጣው ማስታወሻ በኮንቲ ሮሲኒ ታሪካዊ መጽሐፍ ላይ ተብራርቶ ተገልጿል ።[1]

እዚህ ላይ አንባቢ ሊገነዘበው የሚገባው ፣ በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል የነበረውን የተሳካ የጦር ድርጅት ብቻ ሳይሆን ለድል ዋና መድን የሆነውን የስለላ ሥራ ነው ። የጦርነቱንም ድል ያስገኘው ምንም እንኳን የሠራዊቱ ዠግንነት ፣ የነገበየሁ ፣ የነታፈስና የነበሻህ አቦዬ የጋለ አርበኝነት ቢሆንም ፣ ለመዋጋት ዕድል የተገኘው ከምሽግ አልወጣም ብሎ ያስቸገረው የኢጣልያ ጦር በነዚህ ሰላዮች ተታሎ በመውጣቱ ነው ። የኢጣልያን ጦር ያወጣጡን ሁኔታ ፣ የጉዞውን ፣ የጦርነቱን አጀማመርና ፍጻሜ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመልከት ።

1 Italia ed Etiopia.. PP. 325 - 326.

# ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

## የዋናው ጦርነት አጀማመርና ፍጻሜ በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ

የኢጣልያ ጦር ፤ በ1887 ዓ.ም. በኮአቲትና በሰንዓፌ ራስ መንገሻን፣ ደብረ ኃይላ ላይ እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን በጦርነት ያሸነፈ ጊዜ "ከዚህ በኋላ የኢጣልያንን ጦር ማንም ሊመልሰው አይችልም ፤ የሚ ዋጋንም ቢኖር ፤ ሁልጊዜ አሸናፊዎቹ እኛ ነን" የሚል ጽኑ የየዋህነት እምነት ሮማም ለቅኝ ግዛት በመጡትም ኢጣልያኖች ዘንድ አደረ ።

በዚህ ምክንያት ፤ ከደብረ ኃይላ ጦርነት ወዲህ ልጓሙ እንደ ወለቀለት ፈረስ ከደብረ ኃይላ እየፎለሉ ረዥሙን የአጋሜን ፤ የእን ደርታን ፤ የእንዳ መሆኔን ወረዳዎች አልፈው ዋጀራት ፤ አሸንጌ ሐይቅ አጠገብ ደረሱ ። በንጉሠ ነገሥቱ ከኋላ የተደገፈው ግንባር ቀደሙ የነራስ መኰንን ጦር መጠጋቱን ሲሰሙ ፤ ከአሸንጌ ሐይቅ ወደኋላ መለስ ብለው አላጌ ላይ መሸጉ ። የአላጌው ጦር ሲፈርስ እንደ ታላቅ ውርደት ቆጠሩት ። በቁጭት " የአላጌውን መሸነፍ እንመልሳለን" ሲሉ የመቀሌው ተደገመ ። "ሁለቱንም ውርደቶች በእጥፍ እንደማያ ዳግም አድርገን እንመልሳለን" ሲሉ የዓድዋው ተሠለሰ ። ጣልያኖቹም ወደፊት እንደምናነበው ፤ "በዓድዋ ድል ሳናደርግ መታረቁ የኢጣልያን ክብር ይነካል "ብለው በሮማ ዋና ምክር ቤት ተከራክረዋል ። ሦስተ ኛውም ውጤቱ የመሸነፍ በትርና ውርደት ማግኘት ሆነ ። ከዚህ ሁሉ ሽንፈት በኋላ ፤ በየጊዜው ተለምነው የገፈተሩትን ዕርቅ ሁሉ በመጨ ረሻ በግዴታ ሊቀበሉ ተገደዋል ።

በዚሀ ዘመን ፤ በኢትዮጵያ በኩል የታየው የጦር አመራርና የፖ ለቲካው አረማመድ ዘዴ አስደናቂ ነው ። ደንበኛ የጦርና የፖለቲካ ትምሀርት ያልተማረው ወገን ፤ ተማርኩና ሠለጠንኩ የሚለውን ወገን በሁለቱም ግንባር አሸንፎታል ። ኢትዮጵያውያኑ በዝግታ ፤ በትዕግሥት ዕለት በዕለት የጦር ኃይላቸውን እያጠናከሩ ሲሔዱ ባገኙትም ድል ኩራ ትና ትምክህት አሸንፏቸው ሳይገነፍሉ ፤ በየድሉ ማግሥት የሰላም እጃ ቸውን ለኢጣልያ ሲዘረጉ ቆይተዋል ። የሁለቱን ጦር ሠራዊት ዕድል የወ ሰነው የዓድዋው ጦርነት ተጀምሮ ሳለ ፤ ጣሊያኖች የተማመኑበት ግንባር

ቀደሙ ጦር ፈራርሶ ከሚደነፋት ጌኔራሎች አንዱ ተማረከባቸው ፤ ሁለቱ ሞቱ ፤ አራተኛው ከዋናው አዝማች ጋር ወደ አሥመራ ለመሸሽ ተገደደ ።

ቀጥሎም ፤ የኢትዮጵያ ተዋጊዎች ዓድዋ ላይ ሠፍረው ሳለ ፤ ግንባር ቀደሙና ቃፊር ጠባቂው የጠላት ጦር እስከ ገንደብታ ዘልቆና የኢጣልያ ጦር ከምሽግ ወጥቶ መዋጋቱን ሲጠባበቁ ፤ እነሆ በመጨረሻ እንደ ተመኙት ፤ የኢጣልያ ጦር ደርሶ ባለፈው ምዕራፍ እንደ ተገነዘብነው ፤ ግንባር ቀደሙ ጦር ሊፈታ ቻለ ። ያወጣጡንና ያጀማመሩን ሁኔታ በኢጣልያኖች በኩል ያለውን ባለፈው በዝርዝር ተመልክተነዋል ። ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ላይ የሚገኘው ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

> ...ከኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ውስጥ የተከዜን ወንዝ ተሻግሮ እስከ ጸለምት ግማሹ ወደ ሽሬ የቀረውም ወደ ተምቤን ስንቅ ፍለጋ ሔዶ ስለነበረ ፤ ቅዳሜ ማታ(የካቲት 22 ቀን) ዐፄ ምኒልክ ቀኛዝማች ታፈሰን አስጠርተው እንደዚህ አሉት ። "ስንቅ ፍለጋ የሔዱት ... ተመልሰው የገቡ እንደሆነ ሰኞ እንሔዳለን (ወደ ሐማሴን) ። ስለዚህ አንተ በሌሊት ተነሥተህ ከግምጃ ቤት ጓዝ ወስደህ መተላለፊያችንን እንዳያውኩ በየሠፈሩ የሞቱትን የበቅሎና የፈረስ ሬሣ እያቃጠልህ አጥፋ ።" ቀኛዝማች ታፈሰንም ማዘዛቸው ለጦርነትም ለሌላውም ጉዳይ ሁሉ ታፈሰ ሥራውን ሁሉ የማከናወን ስጦታ እንዳለው በማወቃቸው ነው ። ቀኛዝማች ታፈሰም እሺ ብሎ እንደ ታዘዘው ሔደ ። የዚህም ቀን ቃፊር ሆኖ የማስጠበቁ ተራ የራስ መንገሻ ዮሐንስ ነበር ። ቀኑም (ሲነጋ) የካቲት 23 ቀን የጊዮርጊስ በዓል ነበር ።
>
> ከሌሊቱ 11 ሰዓት ግድም የኢጣልያ ጦር በድንገት ደረሰ ። 500 ከሚሆኑት በር ከሚጠብቁት ከራስ መንገሻ (ዮሐንስ) ወታደሮች ጋር ገጠመ ። እነዚህም መልሰው ሲዋጉ ሁለት ባሻ ቡዙቅ ማረኩና ቢጠይቋቸው ፤ "ግማሹ ያፄ ምኒልክ ጦር ስንቅ ፍለጋ መሔዱን ስለ ሰሙ ኢጣልያኖቹ በድንገት አደጋ ጥለው ለመዋጋት አራት ጌኔራሎች በአባ ገሪማ በኩል ፤ አንደኛው ጌኔራል በማርያም ሸዊቶ በኩል ተሰልፈው ይጓዛሉ" ብለው ተናገሩ ። ይኸን ሲሰሙ ከቃፊር ጠባቂዎቹ አንዱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር እየሮጠ ሲሔድ በመንገድ ቀኛዝማች ታፈሰን አገኘና የያዘውን ወሬ ነገረው ። በዚያን ጊዜ ቀኛዝማች ታፈሰ ከበቅሎ ወርዶ እፈረሱ ላይ ተጋባና በግልቢያ ወደ ንጉሡ ድንኳን ደረሰና ለአልፍኝ ዘበኞቹ ንገሩልኝ አለ ... ዐፄ ምኒልክም ከድንኳኑ ወጣ ብለው ምነው ብለው ቢጠይቁት ኢጣልያኖች አደጋ ለመጣል መምጣታቸውን ተናገረ ። ዐፄ ምኒልክ ኢጣልያኖች ተሰልፈው በጣም ተጠግተው ጦርነቱን ካልዠመሩ በቀር ጦሬን አስለፌ ሁለተኛ አልወጣም ብለው ስለነበረ "በከንቱ አስልፎ ሊያስጣኝ ሳይሆን ሊዋጋ የመጣ መሆኑን ታምናለህን ?" ብለው ታፈሰን ቢጠይቁት "ዛሬስ እርግጥ ነው" ብሎ መለሰ ። በዚያን ጊዜ ዐፄ ምኒልክ



> " ሔዳችሁ ይኸን ወሬ አረጋግጡ" ብለው በጅሮንድ ኪተማንና* የፈረስ ዘበኞችን አዘዙ ። ከዚያ ወታደሩን ሁሉ መሣሪያውን ይዞ እንዲነሣ ካዘዙ በኋላ ራሳቸውም የጦርነት ልብሳቸውን ለበሱና ወደ አዳራሹ ድንኳን ሔደው ተቀመጡ ። በዚህን ጊዜ ፀሐይ ወጣች ፤ የትግሬ ጦርም ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ ሳያቋርጥ ይታኮስ ነበርና ሲነጋ በሩቅ የጠበንጃው ጢስ ይታይ ነበር ። የራስ ሚካኤልም ሰዎች ወዲያው ሔደው ወደ ጦርነቱ ተጨመሩ ።
>
> ከጦሩ ሁለት ሲሶ ግማሹ ስንቅ ፍለጋ የቀረውም አክሱም ጽዮንን ለመሳለም ሔዶ ያለው አንድ ሲሶ ብቻ ነበር ። በሰፈር የነበረው የተዙሱን ብዛት በሰማ ጊዜ ሁሉም መሣሪያውን እየያዘ ወደ ጦርነት ሲጓዝ ዐፄ ምኒልክም በበቅሎ ሆነው ተከተሉት ። በዚህም ቀን አገልጋይ ከጌታው ፤ ወታደር ካለቃው ተለያዩና ሁሉም ነዶ እንዳየ ዝንጀሮ ወደፊቱ ጦርነትና መድፍ ወዳለበት ሳገሩና ለንጉሡ ለመሞት ገሠገሠ ። ማንም ሰው "መድፍ ይመታኛል ፤ የጠበንጃውም ጥይት ይመታኛል" ብሎ በልቡ ፍርሐት ያደረበት የለም . . . አለቃው ሲወድቅ ወታደር ፤ ወንድሙ ሲወድቅም ወንድሙ አያነሣውም ። ቁስለኞቹ ራሳቸው "አልጋው ይርጋ እንጂ እኔን ስትመለስ ታነሣኛለህ ። ስለዚህ እንዳታነሣኝ በመሃይምን እንደበቴ ገዝቼሃለሁ" ይሉ ነበር ። ጥይቱ ያሰቀበት ወታደር ከቆሰለው ወገብ ላይ ወስዶ ተኩሱን ይቀጥላል ። አንዳንዱም በሩቁ ሰፍራ እየሮጠ ተዋግቶ ድካም ሲሰማው ዐረፍ ማለት ይጀምርና ወዲያው ተነሥቶ "ጮማ ሳበላኝ ጠጅ ሳጠጣኝ ጌታዬ ለምኒልክ ብድሩን እንዴት ነው የምመልሰው "ይል ይደነፋና ጦርነቱን እንደገና ይጀምራል ።
>
> ንጉሡ ወደ ጦርነቱ ቦታ ሲደርሱ ፤ አቡነ ማቴዎስና የማርያምን ታቦት የያዙት ካህናት በኋላቸው ነበሩ ። እቴጌ ጣይቱም ከዘበኞቻቸውና ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሆነው በአቡነ ማቴዎስና በታቦቷ ጉን ነበሩ ። የአክሱም ካህናት ቅዳሜ ማታ እንደ ጥንቱ ያስተዳድሩን ብለው ለንጉሡ ለማመልከት መጥተው አድረው የነበሩት በዚህን ጊዜ የእመቤታችንን ሥዕልና ሰንደቅ ዓላማ ይዘው በእቴጌ ጣይቱ ግንባር ተሰልፈው ነበር ። የጽዮን እምቢልተኞችም በእቴጌይቱ ፊት ይጫወቱ ነበር ። . . . ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ እስከ 4 ሰዓት ድረስ ተዙሱ ሳያቋርጥ ከሁለቱም ወገን ሲተኮስ ድምፁ እንደ ሐምሌ ጐርፍ ከመድፉ ተኩስ የሚወጣውም ጢስ የተቃጠለ ቤት ይመስል ነበር ። . . . . በዚህ ቀን ፤ በዓድዋ በዐይናችን ያየነውንና በጆሮአችን የሰማነውን ለመጻፍ ችግር ነው ። በዚህ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ በማጀራታቸው ድንጋይ ተሸክመው በጉልበታቸው ተንበርክከው በጋለ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር ። በወታደር በታጠሩት ንጉሠ ነገሥት ላይ የመድፍና የጠበንጃ ጥይት እንደ ዝናም ይወርድ ነበር ።
>
> እቴጌ ጣይቱ ጥቁር ጥላ አስይዘው ፤ ዐይነ ርግባቸውን ገልጠው በእግር እየተራመዱ በንጉሠ ነገሥቱ ልጅ በወይዘሮ ዘውዲቱና በደንገጡሮች ታጅበው ወደፊት ጉዟቸውን ቀጠሉ ። ወዲያውም

*በጅሮንድ ኪተማ ማለት ከዓድዋ ድል ወዲህ አንድ ጊዜ አፈ ንጉሥ ቀጥሎ ደጃዝማች ተብለው ያገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ናቸው ።

የኋላው ወታደር ሲያመነታ አይተው ፣ “በርታ ምን ሆነሀል ድሉ
የኛ ነውና በለው” ብለው በተናገሩ ጊዜ ወንድ ሴት ሲያበረታው
መሸሽ አይሆንለትምና ሁሉም ወደፊት ገፋ ። እቴጌይቱ በዚህ ቀን የሴ
ትነት ባሕሪያቸውን ትተው እንደ ወንድ ወታደሮቻቸውን በቀኝና በግራ
አሰልፈው ወደ ጦርነቱ ገቡ ። መድፈኞቻቸውም በቀኛቸው በኩል ጠም
ደው እየተኮሱ በመካከል የሚዋጋውን የጠላት ጦር ይመቱ ጀመር ።
. . . አቡነ ማቴዎስ ፣ የማርያምን ታቦት አስይዘው ከቀሳውስትና ከመ
ነኮሳት ጋር ሆነው የጊዮርጊስን ስብሐተ ፍቁርን እያዜሙ ሲከተሉ
ዜማው ሳያልቅ ድሉ ተፈጸመ ። ንጉሡ ግን ፣ የሚሸሹትን ኢጣልያኖች
እየተከተሉ የሚወጉትን ወታደሮቻቸውን እየመሩ ሲሔዱ ከቀድሞዎቹ
እንደሳር ቅጠል በጣም የሚበረከቱ ኢጣልያኖችን አገኝተው ሲዋጉ
የተዘረሩም መጠን ከፊተኛው የበለጠ ሆነ ። በዚያም ላይ የኢጣልያ ብዙ
ጀግኖች ወደቁ ። የቀሩትም ሸሹ ። . . .

በዚህን ቀን ፣ ብዙ መነኮሳት የሰሌን ቆባቸውን እንደደፉ ብጫ
ካባቸውን እንደደረቡ የቆዳ ቀሚስ ለብሰው ፣ ግማሹ ከንጉሠ ነገሥቱ
ዙሪያ ግማሹ ከቴጌይቱ ዘንድ የቀሩትም በተዋጊው መኳንንትና
ወታደር ዘንድ ሆነው ወዲያና ወዲህ እየተላለፉ ሲዋጋ ወደ ጦርነቱ የሚ
ገባውን እያናዘዙ ፣ ከጦርነቱ ሲሸሽ ያሰበ ሲያገኙ እየገዘቱ ሲያ
በራቱና ሲያዋጉ ዋሉ ። የኢትዮጵያም ጦር ከጦርነቱ የሸሸውን
የኢጣልያን ጦር የራቀውን በጥይት የቀረበውን በጦርና በጎራዴ እየ
መታ ፈጀው ። . . . የመጀመሪያው ጦር በተሸነፈ ጊዜ ዐፄ ምኒ
ልክ ወደፊት እየገፉ ጦር ያነሰበትን ግንባር እየመረመሩ በፍጥነት
ጦር እየላኩ ሲያዋጉ ጊዜው 5 ሰዓት ሆነ ። እንደዚህም እያደረጉ
ተራራውን ካለፉ በኋላ 2,000 የሚሆኑ ኢጣልያኖችና ባሻ ብዙቆች
ባንድ ዋሻ ውስጥ አበጅተው የሚዋጉትን አገኙ ። በዚያን ጊዜ ከበ
ቅሎቻቸው ወርደው በዋሻውና በምሽጉ ላይ እንዲተኩሱ መድፈኞቻ
ቸውን አዘዙ ። በዚያን ጊዜ በዋሻው ውስጥ ጣልያኖችና ባሻ ብዙ
ቆች እግዚኦ እያሉ ጮሁ . . .

የንጉሡ እሽከር ሊቀ መኳስ አባ ተምሳስ ዣንጥላውን እንዳስ
ያዘ* “ውጋ በርታ” የሚለውን ነጋሪቱን ያሰማጸረጥ እያስጎሸመ ሲያ
ዋጋ ዋለ ። ይኸንንም ሁሉ ሲያደርግ የምኒልክ ውቃቢ ስለ ጠበቀው
እርሱንም የተቀመጠበትንም በቅሎ የመድፍና የጠበንጃ ጥይት አል
ነካውም ። የመጀመሪያው ድል ወደ ተፈጸመበት ስፍራ እቴጌይቱ
መጥተው ቆመው በእርኮትና በገምቦ ያለውን ወሀና መጠጥ በገረዶች
እያስቀዱ ቁስለኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢጣልያኖችም ሳይቀሩ እንዲ
ጠጡና እንዲረኩ አደረጉ ።

9 ሰዓት ገድም ሲሆን ፣ ያፄ ምኒልክ ጦር ቁስለኛና ምርኮ እየያዘ
ከጦርነቱ ቦታ መመለስ መጀመሩን ባዩ ጊዜ እቴጌይቱ ፣ “ንጉሡ

*ለደንቡ በጦርነት ጊዜ ንጉሡ የሚለብሱትን ለብሶ የሚያዋጋና ንጉሡን ከመመታት
የሚያድን ሊቀ መኳሱ ነበር ። አሁን ግን ፣ አዛዥ አባ ተምሳስ ይኸን ሥፍራ
መያዛቸው ምናልባት ሊቀ መኳስ አባተ ራሴ እዋጋለሁ እንጂ ይኸን ሥፍራ
አልይዝም ብለው ይሆናል ።



ሳይመለሱ ወዴት ነው የምትመለሱት? አሁንም ቁስለኞቻችሁንና ምር
ኮኞቻችሁን ለኔ እየሰጣችሁኝ እናንተ ወደዚያው ተመለሱ” ብለው
ጮሁባቸው ። ይኸንንም ትእዛዝ ቢያለበት አስተላለፉ ፤ ከርሳቸውም ጋር
ያሉት እህታቸው ወይዘሮ አዛለች ምርኮ ይዘው የሚመለሰውን ሰው
ባየችው ጊዜ . . . ፣ “ንጉሥህን ጮማና ጠጅህን ትተህ የምትመለሰው በዓ
ድዋ ቤት አለህን” . . . ብላ ሰፈፈች . . . ። ያፄ ምኒልክ ደግነት ወንዱን ብቻ
ሳይሆን ሴቱንም መነኮሳቱንም ሁሉ አጀገነው (ጉበዝ አደረጋቸው) ።
በዓድዋ ጦርነት እቴጌ ጣይቱና አብረው የነበሩትን ሴቶች ማድነቅና ማጋ
ነን ይገባናል ። አለሥራቸው ሲሠሩ ውለዋልና ታሪኩን ጽፈን ለመፈ
ጸም አንችልም ።

እቴጌይቱ እንዳዘዙት ፣ ከጦሩ ግንባር የተመለሰው ጦር ምርኮኛ
ውንና ቁስለኛውን እያስረከበ ንጉሡ ወደሚዋጉበት የጦርነት ቦታ
ተመልሶ ከተዋጋ በኋላ ፣ “የጠላት ጦር ገና አልተሸነፈምን ምነው ቆዩ
ጊዜውስ መጨለሙ አይደለምን” ብለው እንዲመለሱ ቢሉ ፣ አንድ
ወታደር እቴጌይቱ ላፄ ምኒልክ ቢልኩ ንጉሡ ፣ “በግራ በኩል ተኩስ
እሰማለሁ በዚህ በኩል ግን ሁሉም አልቋል” የሚል ቃል ከመለሱ
ላቸው ወዲህ ወደ ሰፈር መመለስ ጀመሩ ። እቴጌይቱም የንጉሡን
መመለስ ሲያዩ ወደ ሰፈር ተመለሱ ። ጊዜው ድንግዝግዝ ያለ ጊዜ
ነበር ። እቴጌ ወደ ድንኳኑ በደረሱ ጊዜ እውስጥ ገብተው መከዳ ብቻ
ላለበት ዙፋን እጅ ነሥተው ተቀመጡ . . . * ዐፄ ምኒልክ ወደ ሰፈር
ሲገቡ ግን ጨልሞ ነበር ። ወታደሮቹም ቁስለኛውን በከብት የሞ
ተውን ሬሳ በቃሬዛ አድርገው ወደ ሰፈር መግባት ጀመሩ ። በግራ
በኩል ያለው የኢጣልያ ጦር ገና ስላልተሸነፈ ፣ በዚያ በኩል ያሉት
ጦረኞች እስከ ሌሊቱ 5 ሰዓት 6 ሰዓት ድረስ ሲገድሉ ፣ ሲማርኩ
ቆይተው በኋላ ተመለሱ ። 1

የዚህ የጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ታሪክ ፡ ወታደሩ በእንዴት
ያለ ቆራጥነትና ዠግንነት እንደተዋጋ ፣ “ሁሉም ጮማ ሳበላኝ ፣ ጠጅ
ሳጠጣኝ ጌታዬ ለምኒልክ እሞታለሁ” እያለ ወደፊት እየገሠገሠ ጠላ
ቱን በመግደል ራሱም ሳገሩ መሠዋቱን ፣ ንጉሠ ነገሥቱም
ዋና መሪ ሆነው ጦር ከበዛበት ወደ አነሰበት ወታደር በመቆ
ጣጠር እያደላደሉ ፣ “በዚህ አለፉ ፣ በዚህ በኩል ተዋጉ” እያሉ በጦር
ነቱ መካከል ተገኝተው ሲያዋጉ መዋላቸውን ፤ በንጉሠ ነገሥቱ ኋላ
አቡነ ማቴዎስና ቀሳውስቱ የሚሸሽ ባገኙ ጊዜ ውጊያውን እንዲቀ
ጥል በማዘት ሲመልሱት ፣ የቀሩትም መነኮሳት የሰሌን ቆብ የደፉ
ብጫ ካባ ደርበው ፣ የዳባ ቀሚስ ለብሰው በጦርነቱ መካከል ወዲያና
ወዲህ እየተላለፉ የሚሞተውን በማናዘዝ ፣ የሚሸሸውን በመገዘት

*መከዳ ላለበት ዙፋን እቴጌዪቱ እጅ መንሣታቸው ንጉሠ ነገሥቱ ባይቀመጡበትም
ዙፋን የተከበረ የሥልጣን ምልክት ነው ።
1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ገጽ 261—264 ።

ላገራቸውና ለሃይማኖታቸው ደንባቸው የሚፈቅድላቸውን የአዋጊነትና
የመንፈሳዊ አባትነት ሥራቸውን መፈጸማቸውን ያመለክታል ። በጊ
ዜው የነበረው መንግሥትና ሕዝብ ኅብረት አንድ በመሆኑ ፤ በወራሪ
ነት የመጣበትን ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀውን ጠላት ክፉኛ መትቶ
አሸነፈው ። ይህም በአፍሪካ አህጉር ከዚህ በፊት ያልተደረገ ድል
አድራጊነትን የሚያንጸባርቅ የድል ኮከብ ብርሃኑን በኢትዮጵያ የነጻ
ነት አየር ላይ እንደ ፈነጠቀ ኖረ ።

ከሁሉ በበለጠ ሁኔታ በውጫሌ የውል ክርክር ጊዜ ፤ በፖለቲ
ካው ተግባር ያልተለዩትና በአንቶኔሊና በኢጣልያኖች የወራሪነት
ሐሳብ ሲናደዱ ሲቆጩ የቆዩት እቴጌ ጣይቱ ፤ በዚህ በዓድዋ ጦርነት
የሠሩትን ሙያ ጽሑፉ አጉልቶ የተናገረውን ተመልከተናል ። ድል
ማድረግም ፤ ድል መሆንም የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ፈቃድ
መሆኑን በመገንዘብ በቅድሚያ ጦርነቱ ሲጀመር ፤ በማኅራታቸው
ድንጋይ ተሸከመው ፤ በጉልበታቸው ተንበርከው እግዚአብሔርን በጸ
ሎት ከለመኑ በኋላ ፤ ቀጥሎ ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ
ከንጉሠ ነገሥቱ ኋላ ከጳጳሱ ጐን ሆነው ለተጠማ መጠጥና ውሃ
እየሰጡ ፤ የቆሰለውን እያሳከሙ ፤ የሚሸሽ ወይም ወደፊት ለመግፋት
የሚያወላውል ሲያገኙ ለእቴጌነታቸውና ለቁንጅናቸው መሸፈኛ የሆ
ነውን ዐይነ ርግብ ከፊታቸው ላይ እንሥተው እንደ ወንድ ፤ " ወደፊት
ግፋ በለው " እያሉ በጩኸት እየተናገሩ ሲያዋጉ መዋላቸው ፤ ይል
ቁንም አንዳንድ ወታደር ወይም የጦር አለቃ ተዋግቶ ለጊዜው
የማረከውን የጣልያን ወታደር ወደኋላ እርሳቸው ወዳሉበት ይዞ
ሲመለስ ፤ " ንጉሡ ሳይመለሱ የት ነው የምትመለሱት ፤ አሁንም ምር
ኮኛችሁን ለኔ አስረክቡኝና እናንተ ተመልሳችሁ ውጊያውን ቀጥሉ "
ያሉት ፤ ለዚህ ጦርነት ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥለው ደንበኛ አሳቢ ትጉኅ
መሪና አዋጊ መሆናቸውን እንገነዘባለን ። የጦርነቱ ድል የሚገኘው
ጠንክሮ በመዋጋት እንጂ ፤ ጣልያንን ማርኮ በመመለስ አለመሆኑን
ተገንዝበው ምርኮኛህን ለኔ ተወው ፤ ጦርነቱን ቀጥል ማለታቸው በአ
ስተዋይነት መምራታቸውን ያስረዳል ። እንደዚህ አድርገው ጠቅላላው
ጦር የሚዋጋበትን ሲያስቡ ፤ በተለይ የግላቸው ቁጥሩ ከአምስት እስከ
ስድስት ሺ የሚደርሰው ጦራቸው በውስጡ አራት መድፍ ይዞ መዋ
ጋቱም አይዘነጋም ።

በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ላይ ፤ " የኋለኛው
ሰልፍ እንደ መወዝወዝ (ይኸውም ማለት እንደ ማወላወል) ሲል ባዩት
ጊዜ ፤ እቴጌ ቃልዎን አፈፍ አድርገው (ይኸውም ማለት ጮኸው) ተና
ገሩ ። "እይዞህ አንተ ምን ሆነሃል ድሉ የኛ ነው ብለው አሉት ።
ሰዉም የተናገሩትን ቃልና እቴጌን ባየ ጊዜ ሴት ሲያጣና (ሲያበረታ)



ወንድ መሸሽ አይሆንለትምና ጸጥ አለ" ወደፊት በሚነበበው በኢጣልያ
ንኛው ጽሑፍ ላይ ደግሞ ፤ "በዚሁ ጊዜ ተጠባባቂው የ7ኛው ባታዮን
ጦር ደርሶ እንድነት ያደረጉት መቋቋም ሐበሾችን ወደኋላ 1000
ሜትር ያህል እንዲያፈገፍጉ አደረጋቸው " የሚለው ተገናዛቢ ነው ።
ዐይነ ርግባቸውን ገልጠው ወይዘሮ ዘውዲቱንና ደንገጡሮቻቸውን
አስከትለው በኢጣልያኖች መቋቋም የተነሣ የኛን ወታደር ማፈግ
ፈግ ሲያዩ ፤ " ምን ሆንክ አንተ ድሉ የኛ ነው ብለው " ያሉት በዚህ
ጊዜ ነው ማለት ነው ። ይህ አንድ መስመር የማይሞላው ኃይለ ቃል
እንታቸው ወይዘሮ አዛለች ወደኋላ በምርኮ ሰበብ ሊመለስ ላሰበው
ጦረኛ ወታደር ፤ " ንጉሥህን ትተህ የምትመለሰው ዓድዋ ቤት አለ
ህን " ብለው ከሠነዘሩት ጋር ተባብሮ ታላቅ የድል ፍሬ ካስገኙት
ሰበቦች አንዱ ነው ማለት ይቻላል ።

ስለዚህ ፤ በዚህ ጦርነት ከጦር ሠራዊቱ እኩል በየተግባራቸው
ተሠማርተው ዘመቻውን የተካፈሉትን የቤተ ክህነት ሰዎች ከአቡነ
ማቴዎስ ጋር ፤ ሴቶቹንም ከእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ጋር በዚ
ያን ጊዜ ባሳዩት መሥዋዕትነት በተገኘው ድል የተጠቀምንና ዛሬ
የምንመካ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሁሉ ሳናደንቅና ሳናመ
ስግን አናልፍም ። እንግዲህ በኛ በኩል የጦርነቱን አዠማመሩን ፤ አካ
ሒዱንና አፈጻጸሙን ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ላይ
በዚህ ዓይነት ከተገነዘብን በኋላ ፤ በኢጣልያኖቹ በኩል የካቲት 22
ቀን በዋናው ጦርነት ዋዜማ ሲመክርና ሲዘክር ተውሎ ለ23 አጥ
ቢያ ሌሊቱን ተጉዘው ጦርነቱን የዠመሩበትን ሁኔታ በሚቀጥለው
ምዕራፍ እንመለከታለን ።

በዚህ ታላቅ ጦርነት ሽማግሌው ራስ ወልደ ሚካኤል ሰሎሞን
የነራስ ኃይለ መለኮት አባት ምንም በእድሜ ገፍተው ቢያረጁ የአሽከ
ራቸውን እጅ እንደጨበጡ ይዋጉ ነበር ። እንደርሳቸውም በእድሜ
የገፉት በዠግንነት የታወቁት ራስ ደረሶ ምንም እንኳን የጦር አዛዥነቱ
ወደ ራስ ወርቁ ቢዛወር ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አልለይም ብለው
መጥተው ጦርነቱን ተካፍለዋል ። ይኸ ሁሉ ያገር አፍቃሪነትንና
አንድነትን ያመለክታል ።



ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ
ከሞሪስ ደኮፔ



ከዓፄ ምኒልክና ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በኅብረት የዓድዋን ጦርነት
የተካፈሉት ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ

ከሞሪስ ደኮፔ

# ምዕራፍ ዐርባ

## የኢጣሊያኖች የሌሊት ጉዞ — የግራው አዝማች ጦር መደምሰሱ — የአርበኛው ጦር አበጋዝ የፊታውራሪ ገበየሁ አሟሟት — የጄኔራል አልበርቶኒ መማረክ

ማናቸውም ድርጅትና ጥንቃቄ ከተደረገ በኋላ፣ የካቲት 22 ቀን ከማታው በሦስት ሰዓት ከሩብ የጄኔራል አልቤርቶኒ፣ የጄኔራል አሪሞንዲ፣ የጄኔራል ዳቦርሚዳ ጦር ተሰልፎ ከምሽጉ ወጣ። በአራት ሰዓት ተኩል ላይ ተጠባባቂው የጄኔራል ኤሌና ጦር ተከተለ። ዋናው አዝማች ከደጀኑ ጦር ፊት ቀድሞ ይጓዝ ነበር። ከሰፈራቸው ዓድዋ ኢትዮጵያውያን እስካሉበት ድረስ ርዝመቱ 15 ኪሎ ሜትር ስለሆነ፣ ይህ ጉዞ 8 ሰዓት እንደሚፈጅባቸው ገምተው እንደነበረ ባራቲዬሪ ያረጋግጣል። የጦር መኰንኖቹ ጦርነት እያማራቸው አለቅዬው ጄኔራል ባራቲዬሪ በኃላፊነቱ ምክንያት ለጥንቃቄ ሲል የጦርነቱ ጊዜ ወደ ኋላ በመራዘሙ፣ ከማገር ማልሳ በቀር ጄኔራሎቹም ወታደሮቹም በተለይም በቅርብ ጊዜ ከኢጣልያ አገር የመጡት ሹማምንቶችና ወታደሮች እየተበሳጩ በጄኔራል ባራቲዬሪ ላይ ሲያጉረመርሙበት ነበርና አሁን የናቁትን ጦርነት ለመግጠም ጉዞው በመጀመሩ ሁሉም በልቡ ደስታ እየተሰማው አስቸጋሪውን የሌሊት መንገድ መጓዝ ጀመረ። ምንም መንገዱ ወጣ ገባ፣ በቆዳ ጫማ ለተሸፈነ ለፈረንጅ እግር የማይስማማ ቢሆንም፣ ይህ ሌሊት ሙሉ የጨረቃ ሌሊት ስለነበረ የደስታ መንገዳቸውን ይበልጥ አቃናላቸው።

ከሦስቱ ዋና አዝማቾች አንዱ የግራው አዝማች ጄኔራል አልቤርቶኒ የሦስቱ ጦር ሠራዊት ሳይለያይ እየተጠባበቀ በአቅራቢያ ሆኖ እንዲጓዝ ተብሎ ከበላዩ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ከፕላን ጋር በጽሑፍ የተሰጠውን ትእዛዝ ተላልፎ ወደፊት ገሥግሦ በመጀመሪያ ጦርነት የጀመረ እርሱ ነው። ይኸንን ያደረገበትን ምክንያት፣ ብዙ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ ዓይነት ተርጉመውታል። ግማሾቹ "የአበሾቹን ኃይል በመናቅ ብቻዬን አሸንፋቸዋለሁ ብሎ ነው" ሲሉ፣ ግማሾቹ "በአለቅዬው በባራቲዬሪ ላይ እርሱና አሪሞንዲ ንቀት ስለ ነበራቸው፣ እርሱ ቀደም ብሎ ከአበሾቹ ጋር ተዋግቶ የድል አድራጊነትን ዝና ለግሉ

ለማስቀረት ነው”[1] ብለዋል የቀሩት ደግሞ፥ “የሦስቱ አዝማቾች አቅጣጫ የጉዞ መሥመር ለየብቻ በመሆኑ ወጣ ገባውን መንገድ በዝርዝር ባለማወቅና የሌሊት ጉዞ በመሆኑ የጦርነት ጓደኞቹ ወደኋላ መቅረታቸውን ሳይገነዘብ፥ ወደፊት ቀድሞ ጦርነቱን በስሕተት ጀመረ” ይላሉ። የሆነ ሆኖ በርሱም አሳቦ፥ “በኢትዮጵያውያኑ ጦር ላይ ድንገት ደርሼ አደጋ አደርሳለሁ” ሲል፥ እነርሱ ደግሞ አስቀድመው ወሬውን እንደ ሰሙት ተጠባብቀው እንደ ተቀበሉት የታወቀ ነው።

የርሱን ጉዞና የጦርነቱን አኳኋን የታወቀው ደራሲ ኮንቲ ሮሲኒ ከጻፈው ላይ ዋና ዋናው የሚከተለው ነው።

የአልበርቶኒ ጦር ከሰፈሩ ደንበኛ ጉዞውን ጀመረ። ለርሱም መሪ የሚሆኑ ከጠቅላይ አዛዡ የተሰጡት 6 ያገር ተወላጆች ሲኖሩ 7ኛውና 8ኛው ደግሞ የአልቤርቶኒ ልዩ ታማኞች ነበሩ። ከነርሱም ጋር ስፍራዎችንና መንገዶችን ደህና አድርጎ የሚያውቀው ፊታውራሪ አይኩን የሚባለው ባንዳ አብሮት ነበር ።

. . እስከ ገንደብታ ድረስ በቀላሉ ከተጓዘ በኋላ . .በ9 ሰዓት ተኩል ከአሪሞንዲ ጦር ጋር ተገናኘ . .

የአሪሞንዲ የነጭ ወታደር ባስቸጋሪው መንገድ እንደልብ ስላልተራመደ፥ ያገር ተወላጅን ጦር የያዘው አልቤርቶኒ ወደፊት በማሥጋቤ ደርሶ እንዲይዝ በፕላኑ ተወስኖ የነበረውን ስፍራ አሳሳተ።...በፕላኑ ላይ የኤራራ ጉብታ በማለት ፊንታ ኪዳነ ምሕረት ተብሎ ተመልክቶበት ስለነበረም ስሕተቱ ተፈጠረ።... ሌሎቹን እንዳይቀድም ከበላይ ትእዛዝ እያለው ከሌሎቹም የጦር ጓደኞቹ ለመገናኘት ፈጣኖቹ ያገር ተወላጆች መልከተኞች እያሉት፥ እንደዚሁም በግራውም በኩል በማርያም ሻዊቶ ላይ የጠላት ጦር መኖሩን ሰምቶ ሳለ፥ ይኸንን ሁሉ እያወቀ ችላ ብሎ ወደፊት የገፋበትን ምክንያት ማወቅ ችግር ነው። ኤራራ በደረሰ ጊዜ ጠላት በፍጹም በዚህ ስፍራ አልነበረበትም። የኤራራን በር አልፎ በምዕራብ በኩል ጦሩ አሽቆለቆለ። መንገዱ መጥፎ ከመሆኑ የተነሣ፥ አንዳንድ ጊዜ ተቀጣጥሎ እያንዳንዱ ሰው ከመሔድ በቀር ሁለት ሰው ጐን ለጐን ሆኖ ለማለፍ አይችልም ነበር። በዚህም የሌሊት ጉዞና በመጥፎ መንገድ ካገር ተወላጅ ወታደር ጋር አብሮ መራመድ ያቃታቸው የነጮች ወታደሮች ነበሩ። ይሁን እንጂ፥ እነሱም ችግሩን አልፈው ወደ ተመደበው ስፍራ በደስታ ለመድረስ ቻሉ።... እንደዚሁ ሆኖ የጦሩ ጫፍ ከሌሊቱ 5:30 (በዐሥራ አንድ ሰዓት ተኩል) እዲ በቂ በር ላይ ደረሰ።... እዚያም ላይ ሆኖ ጄኔራል ባራቲዬሪ በስሜን ምዕራብ የሚገኘውን ዓድዋን በስሜን ያለውን መነኩሴቶን በደቡብ ያለውን ስንደዶን

1 Ventitre anni di vita Africana, G.Pantano, Chap. VII.



ተመለከተ። መሪዎቹም በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኘውን የጐስሶን በሰሜን በኩል ያለውን የእንዳ ኪዳነ ምሕረትን ጉብታ አመለከቱት።

በዚህም ሳለ እኋላ የነበረው ጦሩ በሙሉ ከተተ. . . ከዚያ የኪዳነ ምሕረት በር አልተያዘም ነበርና በዚህ ምክንያት አልቤርቶኒ ተቆጣ።. . . ከዚያም ወደ መነኩሴይቶ ጉብታ ላይ ወጥቶ ሐበሾቹ ያሉበትን የሻዊቶን ሰፈር ይቃኝ ጀመር።. . . ከዚያ መውረድ ሲጀምር የተኩስ ድምፅ ስለተሰማ ግንባር ቀደም ሆኖ የተላከው የማዦር ቱሪቶ ጦር ከጠላት ጋር መታኮስ መጀመሩን ተረዳ።. . . ከቱሪቶ ጋር የገጠመው የጠላት ጦር ቁጥሩ አምስት ወይም ስድስት ሺ ይሆናል። ለነዚህም ከሰሜን ወደ ደቡብ እየመጡ ተጨመሩላቸው። ማዦር ቱሪቶ በዚህ ጊዜ የባታዮውን ጦር በሙሉ አሰልፎ ሲነጋ 6:10 (ዐሥራ ሁለት ሰዓት ከዐሥር ደቂቃ) ላይ ጦርነት ተጀመረ። ከሐበሾቹ ወገን ተዋጊዎቹ የራስ መንገሻ ዮሐንስ፥ የዋግሹም ጓንጉል ሰዎች ነበሩ። ለነርሱም በፍጥነት የሰሜኑ የደጃች ገሠሠና የበጅሮንድ ባልቻ ጦር ደረሰላቸውና ጦርነቱ ከሁለቱም ወገን ተፋፋመ። ማዦር ቱሪቶም እርዳታ እንዲደርስልኝ ሲል ሌተና ሳርቤሪስን ወደ ጄኔራል አልቤርቶኒ ላከው። መልክተኛውም ሲሔድ በመንገድ ወሬ ለመጠየቅ ከአልቤርቶኒ ከተላከው ከካፒቴን ባሲ ጋር ተገናኘ። ባሲም ከርሱ ጋር ሆኖ ሁለቱም ወደ ጦርነቱ ተመለሱና እስከ መጨረሻ ተከላከሉ እያሉ ወታደሮቻቸውን ግማሽ ጦር ወደ አባ ገሪማ፥ ግማሹንም በቀኝና በኋላ ቢታትነው ከቢ. እንዳይደረግባቸው አደረጉ።

ስለዚህ በሐበሾቹ ላይ ድንገት አደጋ ጥለን እናስደነብራለን ተብሎ የነበረው አሳብ ሳተ። ባራቲዬሪ ለጦርነት መምጣቱ ወሬው በሐበሾቹ ዘንድ እንዳይሰማ ምንም ቢጣጣር፥ በሐበሾቹ ሰፈር የጦርነት ግንጋኔ እንደነበረ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ቀን የጊዮርጊስ በዓል ስለነበረ፥ ብዙ ወታደሮች እያስፈቀዱ ገና በዋዜማው ወደ አክሱም ሔደው ያስቀድሱ ነበር። ነገር ግን በዚሁ ንጉሡ ባሉበት በዓድዋ ሰፈር “በያላችሁበት ተጠንቀቁ” የሚል ለፋፊ በየሰፈሩ ይሰፍ ነበር። ሌሊቱን በጉዞ ላይ ታማኝ መሪ ሆኖ ከ6 ሰዎች ጋር የተቆጠረው ያገር ተወላጅ ሰውዬ ጠፋ።* 1 የቦታው ሹም ፊታውራሪውም በዚሁ ሌሊት እንደጠፉ አልቤርቶኒ አረጋግጧል።...ከልዩ ልዩ ምንጭ እንዳገኘሁት ከሐበሾቹም ጽሑፍ እንደ ተረዳሁት ጦርነቱ ሲጀመር ዐፄ ምኒልክ፥ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፥ ራስ መኰንን፥ ራስ መንገሻ አቲከም ራስ (ፊታውራሪ) ገበየሁ ሌሎችም ብዙ አለቆች ከሌሊቱ ከ4 (ከ10 ሰዓት) ጀምረው ዓድዋ በሚገኘው በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ያስቀድሱ ነበር። ቀዳሹም አቡነ ማቴዎስ ነበሩ። እርሳቸውም በሚቀድሱበት ጊዜ ክፍት በሆነው በር በኩል የጦርነቱ ተኩስ ወደ

*የመሪዎቹንና የጠፋውን መሪ ስም በዝርዝር አይናገርም። ነገር ግን መርተው በኋላ የጠፉት ባሻ እውዓሉም መሆናቸው ነው። በጠፉ ጊዜ የጦሩ መሪ “እውዓሉም እውዓሉም” እያለ ቢጣራ “ዘወዓልኩ እያውዕለኒ” በዋልክበት እያውለኝ ብለው መለሱለት ይባላል። 1 የእቴጌ ጣይቱ አጭር የሕይወት ታሪክ፥ ታደሰ ዘወልዴ፥ ገጽ 25።

ውስጥ እየገባ ተሰማ ። ወዲያው ተመልሰው የኢጣልያኖችን መምጣት
ተናገሩ ። በዚህም ጊዜ ምኒልክ የድንጋጤም ፣ የመበርገግም መልክ
አልታየባቸውም ይባላል ። በጸጥታ ቆመው ጥቂት ደቂቃዎች እንደቆዩ
ወደ አቡነ ማቴዎስ ጠጋ ብለው ትንሽ ንግግር ከተለዋወጡ በኋላ
ተመልሰው እስፍራቸው ቆሙ ። ከዚህ በኋላ አቡነ ማቴዎስ በቀኝ እጃ
ቸው መስቀላቸውን ከፍ አድርገው ይዘው በዚያ ላሉት ሁሉ እንደዚህ
ብለው እስተዛዝነው ለቅሶ ጭምር ተናገሩ ። "ልጆቼ ሆይ ዛሬ የእግ
ዚአብሔር ፍርድ የሚፈጸምበት ቀን ነው ሒዱ ለሃይማኖታችሁና ለን
ጉሣችሁ ሙቱ ኃጢአታችሁም ይሰረይላችኋል (እግዚአብሔር ይፍታ)"

አቡኑ ይኽን ተናግረው ሲጨርሱ ፣ መኳንንቱ ሁሉ እየተሽቀዳ
ደሙ የአቡኑን መስቀል ተሳልመው ከወጡ በኋላ ፣ እያንዳንዱ በችኮላ
ወደየሰፈሩ ሔዶ በሰፈርም የነበረው የጦርነቱን መጀመር ሰምቶ እመ
ዘጋጀት ላይ ነበር ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ብቻ ቁርባን ለመቀበል
ሊቆዩ አሰበው ነበር ። ነገር ግን ፣ ዐፄ ምኒልክ ኃጢአትዎ ወርዷል ፤ ይል
ቅስ እዚህ መቆየት አደጋ ነው ስለአሏቸው እርሳቸውም ወጥተው ሔዱ ።
በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምኒልክ ብቻ ቆዩ ።

ማገር ቱሪቶ የያዘው የኪዳነ ምሕረት በር ዓድዋ ለሰፈረው ለዋ
ናው ለሸዋ ጦር ወለል ብሎ ይታየው ነበር ። . . . የኢጣልያን ጦር
መምጣቱን ሲያረጋግጡ የንጉሡና የራስ ሚካኤል ጦር ደግሞ ፡ በግራ
በኩል ለመክበብ ወደ ኪዳነ ምሕረትና ወደ አባ ገሪማ ጉብታ ተጓዘ ።
ደጃች በሻህም ፈረሰኞቻቸውን ይዘው በጕን ጫፍ ቀደሙ ። አጋማሹ
የራስ መንገሻ ጦር በቀኝ በኩል ወደ ማይ እጋም ዘልቀው በዠርባ
ሊመጡ ነበር ። ነገር ግን ዘባን ቀይህ ሲደርሱ በዘዴ ቀርቶ ወደ ዓድዋ
ወደ ማርያም ሸዊቶ የሚያሳልፈውን የረቢ አሪዬኒን መንገድ . . . እን
ዲይዙ ታዘዙ ። የንጉሡም ጦር ከዓድዋ መጥቶ የዘባን ቀይህን ስፍራ
ይዞ ከቆየ በኋላ ፣ ማይ እጋም ወጥቶ ከአልቤርቶኒ ጦር ጋር በማርያም
ሸዊቶ ከጄኔራል ዳቦርሚዳ ጦር ጋር ውጊያው ተጀመረ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ጄኔራል አልቤርቶኒ ያለበትን ሁኔታ ለማስታወቅ
ለጄኔራል ባራቲዬሪ እንደዚህ ሲል 6፡30 (በ12 ሰዓት ተኩል) ላይ
ጻፈ ። "ጠላት ሳያውቅ የኪዳነ ምሕረት በር በ11 ሰዓት ተያዘ ።
ጠላት በዓድዋ ዙሪያና በማርያም ሸዊቶ ይገኛል ። የአንደኛው ባታዮ
ጦር (ቱሪቶ) ከበሩ አልፎ ወደፊት ዘልቆ የተፋፋመ ጦርነት እማድ
ረግ ላይ ነው ። እርሱንም በመርዳት ባንዶች አብረው ይዋጋሉ ።
6ኛው ባታዮ በቀኝ ያለውን ተራራ ይዟል ። የቀሩት ሁለት የባ
ታዮ ወታደሮች መድፋቸውን እንደያዙ ተሰብስበው ይጠባበቃሉ ።
ትልቅ ጦርነት ሊደረግ የቀረበ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ይሰማኛ
ልና የአሪሞንዲ ጦር ተቆጥኖ ይድረስ ። ግማሹንም የጠላት ጦር እንዲ
ይዝልን የዳቦርሚዳ ጦርም ወደፊት ቢገሠግሥ መልካም ነው ። "ጄኔ
ራል አልቤርቶኒ መልክቱ በ7፡30 (በአንድ ሰዓት ተኩል)እንደሚደርስ
አስቦ ነበር ። ነገር ግን ለባራቲዬሪ የደረሰው ከ8፡30 (ከሁለት ሰዓት
ተኩል) በኋላ ነው ።

ግንባር ቀደም ሆኖ ጦርነቱን የጀመረው የማገር ቱሪቶ ጦር ፣
በጥይትና በመድፍ አንዳንድ ጊዜ በሳንጃ የጨበጣ ውጊያ አድርጎ



ሐበሾቹ ስለአዩሉ ፣ ጥግቱ እየሞተ የቀረው ቢግረከ ቢቀበል ፣ ከዚያ
የተረፈው በዚሁ በቱሪቶ እየተመራ ወደኋላው ሸሽቶ ወደ ዋናው
ወደ አልቤርቶኒ የጦር ሰፈር ደረሰ ። . . . የአበሾቹም ጦር
እየተከታተለ ደርሶ ዋናው ጦርነት ስለ ተጀመረ ፣ ጄኔራል አልቤርቶኒ
የቀረው በመድፍና በጠበንጃ በሚዋጋበት ጊዜ ሻርፐኔል የሚባለው
የሚፈነዳ ቦምብ እንዲተኮስ አዘዘ ። ይኸንንም ማድረጉ ሐበሾቹ በዚህ
ተዠስ ድንጋጤ እንዲሸበሩ ነው ። በዚሁ ጊዜ ሐበሾቹ 1500 ሜትር ካሬ
የሚሆን ቅርበት ያለውን ስፍራ ይዘው አንድ አንድ ጊዜ 1000ሜትር ተጠ
ግተው ሲዋጉ በዚሁ ቦምብና በመድፍ ብዙ ሰው አለቀባቸው ። ወደኋላም
ማፈግፈግ ሲጀምሩ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ለአልቤርቶኒ የጻፈው መልስ
መጣለት ። ደብዳቤውም የሚገልጸው የአሪሞንዲ ጦር . . . በረቢ አሪዬኒ
ተጠባባቂው ጦር በገንደብታ መገኘቱን ነው . . . በዚህ መካከል የአባጊን
በር የሰበረው ፊታውራሪ ገበየሁ ጦሩን ይዞ ለወታደሮቹ ምሳሌ በመሆን
እፊት ሆኖ እየመራ በግሥጋሴ ወደ ጦርነቱ ገባ ። ከርሱም ጋር
ሦስት ወይም አራት ሺ የራስ ሚካኤል ፣ ሦስት ሺ የፊታውራሪ ተክሌ
አንድ ሺ አምስት መቶ የፊታውራሪ ተፈሪ ጦር ደረሰ ። ከዚህ በኋላ
በሁለቱ መካከል የሚደረገው ጦርነት ከልክ ያለፈ የጋለ ሆነ ። ከሁ
ለቱም ወገን በኋላ የነበሩት እፊት ሆነው ለጀመሩት እየደረሱላቸው
የብዛት ውጊያ ሲደረግ የጥይቱ ጩኸት አስደናቂ ነበር ። . . . ከኢጣ
ልያኖቹ ወገን እያንዳንዱ ወታደር 142 ጥይት ብቻ ይዞ ነበርና*
ጥይት በማለቁ የመሸነፍ አደጋ እንዳይደርስና ሌላ ጥይትም በቅ
ርቡ ለማግኘት ስለማይቻል ፣ ሹማምንቶቹ ወዲያና ወዲህ እያሉ እየቆ
ጠቡ እንዲተኩሱ ለየወታደሩ ትእዛዝ ይሰጡ ነበር ።

የሐበሾቹ ጦር ከመካከለኛው ፀቀር በግራ በኩልም ስለ ተጫነ
ዠኔራል አልቤርቶኒ ተጠባባቂው ባታዮ እንዲመጣ አዘዘ ። በዚሁ ጊዜ
የእቴጌ ጣይቱ ጦር ስድስት ሐኪንስ **የሚባሉትን መድፎች ይዘው
ከተዋጊው 3,000 ሜትር ርቀው መድፍ እየተኮሱ ምንም እንኳን
በጣልያኖቹ ላይ ጉዳት ባያበዙ ተዋጊዎቹን ሐበሾች ስለ ደገፏቸው
ወደፊት ሁሉም በኪዳነ ምሕረት በር በላጸት እየገፉ ይዋጉ ጀመር ።
በዚሁ ጊዜ ተጠባባቂው የ7ኛው ባታዮ ጦር ደርሶ እንድነት ያደረ
ጉት መቋቋም ሐበሾቹን ወደኋላ 1000 ሜትር ያህል እንዲያፈገፍጉ
አደረጋቸው ።

በዚህ ዓይነት ፣ ተዋጊው የጦር ሠራዊት ወደፊት ለመግፋት እን
ዳመነታ ባየ ጊዜ ፣ ቀይ ልብስ የለበሰው ፊታውራሪ ገበየሁ ወደ ሰዎቹ
ፊቱን አዙሮ . . . "የአምባ አላጌው አሸናፊ ፊታውራሪ ገበየሁ በምን
አኳኋን እንደሞተ ወደ ሸዋ በሕይወት የሚመለሱት ይናገሩ" ብሎ
ተናግሮ ፣ እንደ አንበሳ ተወርውሮ ወደ ኢጣልያኖቹ መስመር
ገብቶ ሲዋጋ ፣ በ3 ሰዓት ላይ በመትረየስ ተመትቶ ኪዳነ ምሕረት አበሩ

---

* በፊተኛው ላንድ ወታደር የተሰጠውን 112 ጥይት ብሎ የነበረውን አሁን 142 አድርጎታል ።

** Hotcaiss 6 Benjamin Berkley. የመድፍና መትረየስ ሥራን ያመነጨ ሰው ነው ። በፈረንሳይዮች በኩል ወደ ኢትዮጵያ የመጣው መድፍ በርሱ ስም ይጠራል ።

ላይ ወደቀ ። የርሱም ሞት የርሱን ሰዎች አስደንግጦ ወደኋላ እንዲ
ያፈገፍጉ አደረጋቸው ። ግማሾቹ ግን ፣ ተኩሳቸውን ሲቀጥሉ ባለ የነ
ርሱ የመድፉም ተኩስ ለጊዜው ዝም አለ ።

አልቤርቶኒ ድሉ እንደ ተቃረበ ተስፋ አደረገ . . . ነገር ግን
በዚህ ጊዜ ወደ ጦርነቱ ግንባር የመጡት ዐፄ ምኒልክ ያደፋፈሩአ
ቸው ወታደሮች ወደፊት እየገፉ መጥተው እንደገና ሲጀመር ጦር
ነቱ ከፊተኛው የበለጠ ሆነ . . . ይልቁንም በሦስት ሰዓትና በሦስት
ሰዓት ተኩል መከከል አበሾቹ ሁለት ጊዜ እየገፉ የመጡትን የ7ኛው
ባታዮ ጦር እያገደ አቆማቸው ። ቀጥሎም ከ8ኛው ባታዮ ጦር ጋር
ሆነው የጨበጣ ጦርነት ሆና ትልቅ እልቂት በተደረገበት ሰዓት ከነ
ጮቹ በቀር ያገር ተወላጅ ባንዳና የሱዳን ተወላጆቹም በጉብዝና
ተዋጉ ። እነርሱንም ካፒቴን ፒያንኪኒ ፣ "ጉበዞች ደህና እንደዚህ
በጸጥታ እነጣጥሩና ተኩሱ ። ያለዚያ ጩኸት ብቻ ይሆናል" እያለ
እያነጣጠሩ በጠላት ላይ ደህና አድርገው እንዲተኩሱ ያሳያቸው
ነበር ። ቢሆንም ከሦስት ሰዓት ተኩል በኋላ ሁኔታው እየከፋ
ሔደ ። ከአባ ገሪማ የወረዱት ወደ ጦርነቱ እየቀረቡ ባደረጉት
ውጊያ ከኢጣልያኖቹ ወገን በቆራጥነት በመድፍም ፣ በጠበንጃም በሳ
ንጃም ቢከላከሉ የሐበሾቹ ጦር እየበዛ ሔደ ። ጄኔራል አልቤርቶኒም
ተጠባባቂ ጦር ለማዘጋጀት ካፒቴን ባሲን ወደየባታዮዎቹ ቢልክ
ሁሉም ተደባልቆ ስለሚዋጋ ለተጠባባቂ የሚሆን ሰው አለመገኘቱን
ነገረው ። ጦርነቱም በዚህ ዓይነት ሲቀጥል ጥይት እንደሚያልቅና
ለረዥም ጊዜ ለመመከት አለመቻሉን ተረዳው ። ካገር ተወላጅ ጦር
ውስጥ ባለበት ግንባር ብዙዎቹ አለቁ ። በነርሱ ይተኩስ የነበረው ጠበ
ንጃና መድፍም ስለተረፈ ፣ በነርሱ ፈንታ ነጮቹ እየተተኩ ተኩሱን
ቀጥለው ነበር ። ዳሩ ግን ሁሉም ከንቱ ሆነ ። ሬሳና ቁስለኛ ማንሻም
ስላልተገኘ ስፍራው በሬሳና በቁስለኛ ተሸፈነ ። የጦር መሣሪያውም
አለቀ ። በዚህ ጊዜ የባታዮው የልፍኝ አስከልካይ ካፒቴን ባሲ ወደ
ጄኔራል አልቤርቶኒ ጠጋ ብሎ ፣ "ጌታዬ ጄኔራል ምን ማድረግ
ይሻላል!" ብሎ ጠየቀው ። ጄኔራሉም "የባታዮዎቹ ጦር አልቋል ከኋላ
የነጭ ወታደር እርዳታ ይደርስልናል ብለን ተስፋ የለንም ። እዚህ ካሉት
ጋር ወደኋላ እንሽሽ ማለትም ከንቱ ነው ። ስለዚህ ሁላችንም እዚሁ
ቀርተን እንሙት" ብሎ መለሰለት ። እንደዚህ ሆና የኢጣልያኖች ጦር
ወደመሸነፍ በቀረበበት ጊዜ የሐበሾቹ አለቆች ተጠጉ ። ንጉሡና ቀዩ
ግንጥላቸው በሩቁ ታየ የሚሉ ወሬ ተወራ ። በዚህ ጊዜ የ7ኛው
ባታዮ ጦር ካገር ተወላጅ ሹማምንት ጋር ሽሽት ጀመረ ። እነ
ርሱንም እየተከተለ ሁሉም ሽሽቱን ያዘ . . . ጄኔራል አልቤርቶኒም
በማገር ጋሜራ ግማሾቹን ባንዶች ይዞ ከርሱ ለየት ብሎ ወደ አን
ዲት ጉብታ ለመውጣት ሲሞክር ፣ አልቤርቶኒ ከጥቂት ባንዶች ጋር
እንዳለ ሐበሾቹ ሊከቡት ሲፈልጉ ከርሱ ጋር የነበሩት ባንዶቹ ከፊቱ
እየተበታተኑ መጥፋት ጀመሩ ። ጄኔራል አልቤርቶኒ ከትናንት ማታ
ጀምሮ አንድ ጊዜም ከፊቱ ካልተለየው ከፊታውራሪ አይኩን ጋር
ብቻውን ቆሞ ነበር ። ፊታውራሪም እንዲሸሽ ጄኔራሉን ቢጐተጉተው
ዝም ብሎ ቆመ ። በዚህ ጊዜ ጋሜራም በሩጫ ሔዶ አሁን ጊዜ እያለው
እንዲያመልጥ ቢጐተጉተው ፣ "እባክህ አንድ የምትገድለኝን ጥይት
እየጠበቅሁ ነበር አልመጣ አለችኝ" ብሎ መለሰለትና ዝም ብሎ



እፈረሱ ላይ ሆኖ ይመለከት ነበር ። በኋላ ግን ፣ ከፈረስ ወደ በቅሎ
ተዛውሮ ማገር ጋሜራን ለመፈለግ በበቅሎ ሆኖ ወደ ዘቅዟታ ስፍራ
ሲተላለፍ የተቀመጠበት በቅሎ በጥይት ተመትቶ ወደቀና እርሱም
አብሮ ወድቆ ሲንከባለል ጠላቶቹ ደርሰው ማረኩት ። በዚህም አኳኋን
የድብልቅልቅ ጦርነት ከተደረገ በኋላ በዚሁ ጊዜ ጋሜራንም ይኸን
የመሰለ አደጋ አገኘው ። እስከዚህ ጊዜ ቆይተው የነበሩት የኢጣልያን
ሹማምንቶች በውጊያው ላይ አለቁ ። . . . ካፒቴን ቢያንኪኒ ሆዱን
ተመትቶ ወደቀ ። ቴኔንቲ ባሬቲ ጉሮሮ ግንዱን ተመትቶ በወደቀ ጊዜ
ጓደኛውን ኮርዲላን ፣ "በሰማይ ላይ እንገናኝ" ብሎ ተናግሮ ሞተ ። . .
ስለዚህ በግራ በኩል የተረፈው የኢጣልያ ጦር በሙሉ ተከበበ ።

የሐበሾቹ መኳንንቶች የጦር ልብሳቸውን ለብሰው ጦርና ጠበንጃ
በያዙ ወታደሮቻቸው ታጅበው ሲመጡ ፣ ሊቀ መኳስ አባ ተምሳስ ነጋሪ
ቱን ውጋ ውጋ እያሰኘ ወደፊት የሚገሠግሡትን ጠላቶቹን ለማገድ
ሲዋጋ ዶ ርዛ "ሒድና ለመከላከል አልቻልሁምና ወደኋላዬ እንድመ
ልስ የእግረኛ ጦር ላክልኝ" ብሎ መልቲዶን ወደ ጄኔራል አልቤርቶኒ
(ያልተማረከ መስሎት) ሲልክ ፣ በዚያው ሰዓት የራስ መንገሻ አቲከም
ወታደሮች በጌታቸው እየተመሩ ሳይታሰብ በጀርባቸው በኩል ጦራ
ቸውን እየሰበቁ ሰይፋቸውን እያወዛወዙ እየተጯጯሁ ደረሱባቸውና
አመትረየስ ተኳሾቹ ላይ ወደቁባቸው . . . ካፖራል ሳልቶ የሚባለው
መሐል እራሱ እሁለት ተፈልጦ ወደቀ ፣ ትረፒፒ ከፉኛ ቆስሎ ወደቀ ፣
ሌተና ኮርዲላ በጨበጣ ሲዋጋ ቆስሎ ተማረከ ፣ ካፒቴን ማዘቶ ቀኝ
እጁን ስለቆሰለ ፣ በግራ እጁ በሽጉጥ ተታኩሶ ሞተ ። ሌተና አይኒስ
መትረየሱን እንደ ጨበጠ በሰይፍ በትር ሞተ ። ሌተና ሳያ በሁለት
ጥይት ቅልጥሙን ተመትቶ ሳለ ድጋሚ ጭንቅላቱን ተመታ . . .
ማገር ደርዛ በሚያስደንቅ ጸጥታ እጁን እኪሱ ውስጥ እንዳደረገ
በመትረየስ ሲያዋጋ ቆይቶ ከሚኞቹ ጋር ወደቀ . . . ከሐበሾቹ ወገን
የሞቱትም ብዙዎቹ ናቸው ። ደጃች ጫጫ የሚባለው በጣም ዝግና
የሆነው የጉላ* አገረ ገዥ በዚሁ ስፍራ ሞተ ። እርሱም እንደ ብዙዎቹ
ዝግኖች ታዝኖለታል ። . . . 1

በጄኔራል አልቤርቶኒ የሚመራው ግንባር ቀደም ጦር ፣ በዚህ ዓይ
ነት ተሸንፎ ማለቁን ኮንቲ ሮሲኒ ፣ ከፖሴራ ፣ ከባራቲዬሪ ፣ ከቤላቪታ ፣
ከጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጻሕፍት እየቀሰመ በዝርዝር
የጻፈው በዚህ ዓይነት ይጨርሳል ። ኢጣልያዊ ጸሐፊ እንደመሆኑ ፣
ጦርነቱን ኢጣልያኖቹ በዠግንነት እንደምን እንደመከቱ ፣ እያንዳንዱ
የጦር መኰንን በዠግንነት መሠዋቱን ሲገልጽ ከውስጣቸው እጃቸውን
እየሰጡ የተማረኩትን ግማሹ ጦር ማለቁን እያየ ወደኋላ የሸሹትንም
እዚህ ምዕራፍ እምብዛም ዘርዝሮ አልገለጸውም ። ቢሆንም በመጨ
ረሻው ላይ ግን ፣ የሞቱትንና ከጦርነቱ እየሸሹ ወደ አሥመራ የገቡትን

---

* ጉላ ፣ በአንኮበርና በአሳግርት መካከል የሚገኝ የሸዋ ወረዳ ነው ።

1 Italia ed Etiopia, Conti Rossini, PP.361-381. The Campaign of Adwa . . ., G. Berkeley, Chap. X, PP 272-313. La Prima Guerra d, Africa, R. Battaglia, PP. 733-776.

ከነቁጥራቸው ገልጾታል ። የኢጣልያኖቹን እያጋነነ ከነስማቸው ሲያ
ነሣ ፣ የኢትዮጵያን ወገን ከፊታውራሪ ገበየሁና ከደጃች ጫጫ በቀር
እምብዛም አልዘረዘረም ። የዚህም አንዱ ምክንያት ኢጣልያዊ ጸሐፊ
በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ፣ በሥፍራውና በጊዜው ስለሌለበት ከሐበሾቹ
ውስጥ እነማን በጀግንነት እንደሞቱ ስማቸውን እየጠቀሰ ሊተ
ርክ አይችልም ። የተዋጉት የኢጣልያ ሹማምንቶችም ፣ የጠላቶቻቸውን
የኢትዮጵያውያኑን ስምና ሥራ በዝርዝር ስለማያውቁ ፣ ቢያውቁም በዚ
ያን ዘመን አብዛኛዎቹ ጽፈው ስላላስቀሩት ፣ የኛም ወገኖች ዘርዝር
በያይነቱ የመጻፍ ልምድ ስለሌላቸው ፣ ብዙ አስደናቂ ጀግንነት የሠሩት
ተራ ወታደሮች ፣ የበላይና የበታች አለቆች የብዙዎቹ የጀብዱ ሥራቸ
ውም ስማቸውም እንደ ተቀበረ ቀርቷል ። ቢሆንም የመጀመሪያውን
ግንባር ቀደም ጦር የተዋጉት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ዋግሹም ጓን
ጉል ፣ ራስ መንገሻ አቲከምና ደጃች ገሠሠ ፣ በጅሮንድ ባልቻና ፊታው
ራሪ ገበየሁ ፣ ደጃች በሻህና ደጃች ጫጫ ፣ አዛዥ አባ ተምሳስ መሆ
ናቸውን ፣ ከነዚህም መካከል በተለይ ሁለቱ ታላላቅ የጦር አለቆች
ፊታውራሪ ገበየሁና ደጃች ጫጫ በዚሁ ጦርነት አስደናቂ የጀብዱ
ሥራ እየሠሩ መሞታቸውን ትውልዱ ኢጣልያዊ የሆነው የኢት
ዮጵያን ታሪክ የሚያውቀው ኮንቲ ሮሲኒ ሳይደብቅ ገልጾታል ።
በአጻጻፉ ከሁለቱም የፊታውራሪ ገበየሁ አባ ጐራን አሟሟት ፣
"ከፊት ያሉት ጭፍሮቹ የማመንታት መልክ ሲታይባቸው ፣ ከኋ
እንደ አንበሳ ተወርውሮ በጠላቶቹ ሰልፍ ገባ " የሚል ቃል ጨምሮ
አድንቆ ጽፎላቸዋል ። ሌሎቹም የጦርነቱን ማስታወሻ የጻፉ የኢጣል
መኰንኖች የጀግናው ሬሳ የማዕረግ ልብሱን እንደ ለበሰ ወደኋላ ሲ
ሰስ ፣ በምርኮኝነት ተይዘው የነበሩት የኢጣልያ ሁለት የመቶ አለቆች
ጉልዮልሞ ፒኒና ፋዞ ማየታቸውን ገበየሁም ከንጉሡ የጐበዛዝት የጦር
አለቆች ውስጥ አንዱ መሆኑን በማስታወስ ገልጸዋል ።[1]

በዚህ ጦርነት ፣ የራስ መኰንንን ወሳኝ አወጋግ ኮንቲ ሮሲኒ እም
ብዛም አላገነነውም ። ነገር ግን ፣ ምንም እንኳን ራስ መኰንን የዘመ
በት አቅጣጫ በመነኩሲቶ ግንባር ቢሆንም ፣ በፊታውራሪ ገበየ
በኩል የኢጣልያ ጦር በጣም መጫኑን በመገንዘብ የማህሉ የ
ሪሞንዲ ጦር ለአልቤርቶኒ የደረሰ እንደሆነ አደገኛ ሁኔታ
እንዳይፈጠር ሲሉ ካሉበት ሠፈር ወደቀኝ በኪዳን ምሕረ
ጉብታ በኩል ተቀልብሰው ከአልቤርቶኒ ጦር ጋር በስሜ
በኩል ሲዋጉ ቀኝ እጃቸውን ተመትተው ወደቁ ። ያቆስላቸውንም

---

1 Adua,E. Bellavita, P 354. Gli Italiani in Africa. Angelo Del Boca, p
656-692. La Prima Guerra d' Africa R.Bataglia pp. 733-776.



የኢጣልያ መኰንን ልጃቸው ቀኛዝማች ይልማ ተኩሰው መግደላ
ቸውን ፣ መኰንንም ከወደቁበት ተነሥተው ቁስላቸውን አስረው
ጦርነቱን መቀጠላቸውን ግራጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ በግዕዝኛ ጽሑፋ
ቸው ያመለክታሉ ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ የጦር አበጋዙ የፊታውራሪ ገበየሁ መሞትና የራስ
መኰንን መቁሰል ሲሰማ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ጥርጣሬና ሥጋት
አሳድሮ እንደ ነበርና ጦሩ ወደ ኋላው መለስ እንዲል ለማዘዝ አስበው
ነበር ይባላል ። ነገር ግን እቴጌዪቱም እነራስ መንገሻ ፣ እነራስ
ሚካኤል ፣ እነንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በየግንባራቸው ደህና አድርገው
በመመከት አሥጊ የነበረው ሁኔታ ተሻሽሎ በዚህ ፈንታ በመጀመ
ሪያው የጦርነቱ ወቅት አሸናፊነት ያገኘ መስሎት የተደሰተው
ጄኔራል አልቤርቶኒ ራሱ ተሸንፎ ተማረከ ። የርሱም መማረክ
ወገኖቹን ሲያስደነብር በኢትዮጵያውያን በኩል የድል ሙራ የሚፈ
ነጥቅ መሆኑ አይጠረጠርም ።

---

1 ዜናው ለልዑል ራስ መኰንን ፣ ገጽ 53 ።



የተማረከው ጄኔራል ማቴዎስ አልቤርቶኒ
ከማዙኮኒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ አንድ

## የመጀመሪያው ብርጌድ ጦር ተዋግቶ ስለ መሸነፉ
## የጄኔራል አሪሞንዲና የኮሎኔል ጋልያኖ ፍጻሜ

በኢትዮጵያውያን በኩል እንደዚያው እንደ ጣልያኖቹ፥ በግራ በኩል የአልቤርቶኒ ጦር በዘመተበት ግንባር የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፥ የእቴጌ ፥ የፊታውራሪ ገበየሁና የደጃች ጫጫ ጦር በመጨረሻም የንጉሡ ነገሥቱ ዘበኛ እንደ ዘመተ፥ አሁን በመካከል ዘምቶ ሲዋጋ በምንመለከተው በጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ፊት ለፊት ለውጊያ የተሰለፉት ራስ ሚካኤልና ራስ ወሌ ናቸው። ይኸም ጦር በጠቅላላ የቤጌምድር፥ የየጁ፥ የአማራ ሳይንት፥ የወሎና የአካባቢው መሆኑ ነው።

ነገር ግን፥ በዋዜማው በየካቲት 22 ቀን ማታ ኢጣልያኖቹ ከምሽግ ወጥተው ሌሊቱን ተጉዘው ግራና ቀኝ እየተጠባበቁ በጧት በኢትዮጵያውያን ጦር ላይ አደጋ የመጣሉ ጉዳይ በፕላን ስሕተት ወይም ለየብቻ ድል አድራጊነትን በመመኘት፥ ይልቁንም የኢጣልያኖቹ የሌሊቱ ግሥገሣ በነአውአሎም አማካይነት ባሻ ምኒልክ ዘንድ ከሌሊቱ ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ስለተሰማ ከሽፎባቸዋል ። በዚህ ምክንያት ሦስቱም ጄኔራሎች ጦርነት የጀመሩባቸው ሰዓቱም ስፍራውም የተለያየ ስለሆነ፥ የግራውን አዝማች የጄኔራል አልቤርቶኒን ጦር በረፋድ ሰዓት ላይ የደመሰሰው የኢትዮጵያ ጦር ወደ ግራው ተቀልብሶ በመካከል ሆነው ለሚዋጉት ለነራስ ወሌ ጦር ተደራቢ ሆኖ የአሪሞንዲን ጦር ለማጥቃት የተመቸ ሆኗል።

የአሪሞንዲን ጦር ወደ ሰባት ሰዓት ላይ ፈጽሞ የደመሰሰው ጦር በቀኝ በኩል ይዋጋ በነበረው በጄኔራል ዳቦርሚዳ ጦር ላይ ደርሶ እስኪጨልም ድረስ ተዋግቶ መደምሰሱን ወደፊት እንመለከታለን። ደጋግሞም ከጄኔራል ባራቲዬሪ በተሰጠው ፕላን መሠረት አሪሞንዲ ለአልቤርቶኒ ቢደርስለት ዳቦርሚዳና በኋላ ያለው የጄኔራል ኤሌና ተጠባባቂ ጦር ከአልቤርቶኒና ከአሪሞንዲ ጋር ተባብሮ ቢዋጋም፥ በመካከል ለተሰለፉት ለራስ ወሌና ለራስ ሚካኤል በጧት ለተዋጉት ለነፊታውራሪ ገበየሁ ጦርም በሌላው የጦር ግንባር ያለው የበረከተው የኢትዮጵያ ጦር ወደነዚሁ በመሰብሰብ መዋጋቱ ስለማይቀር ፥

እንዲያውም በሦስት በመሥመር የተከፈለውን ጦር ለየብቻ በየተራ በመ
ዋጋትና ጦርነቱ ጧት የጀመረ ላይን እስኪይዝ በመቆየት ፈንታ
ድምሩ የኢጣልያ ጦር በድምሩ የኢትዮጵያ ጦር ተሸንፎ ምናልባት
ውጊያው ወደ ስድስትና ሰባት ሰዓት ላይ ሳያልቅ አይቀርም ነበር
ማለት ይቻላል ። በዝርዝር ተበታትኖ ያዘነፈ ያው ጦር በድምር ተዋ
ግቶ ለማሸነፍ የሚከለክለው ነገር ሊኖር እንደማይችል ይገመታል ።

... ግን ፣ ጄኔራል አልቤርቶኒ በኢትዮጵያ ጦር ሰፈር በቀኝ
በኩል ከዘመቱት ጓደኞቹ ከአሪሞንዲና ከዳቦርሚዳ ተለይቶ ወደፊት
ገሥግሦ ጦርነቱን በመገርመር ተዋግቶ ተሸነፈ ። ተሸንፎም
ሲማረክ ይኸን ሁሉ የደረሰበትን አደጋ ጓደኞቹ ጄኔራሎችና የበላዩ
አለቃው ጄኔራል ባራቲዬሪ አያውቁም ነበር ። ለምሳሌ አልቤርቶኒ
ጧት በሚዋጋበት ጊዜ ፣ "እርዳታ ይድረስልኝ" የሚል ደብዳቤ ጽፎ
ባንድ ፈጣን ፈረሰኛ እጅ ለጄኔራል ባራቲዬሪ የላከ ጊዜ በርሱ አሳብ ፣
" ደብዳቤው በቶሎ ደርሶ በጦርነቱ ሰዓት የእርዳታው ጦር ይደር
ሰኛል " የሚል ምኞት ነበረው ።

ነገር ግን ፣ አዛዡና ታዛዡ 55 ማይል ተኩል ከመራራቃቸውና ከመ
ንገዱ ወጣ ገባነት የተነሣ ፣ መላክተኛው ደርሶ የእርዳታው ጦር ከመድ
ረሱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ጦሩ ተሸንፎ አልቤርቶኒም ተማርኮ
የሞተው ሞቶ የተረፈው ከጦርነቱ ጉራ 'እግሬ አውጭኝ' ብሎ የሚሸ
ሸው የጣልያን ጦር በመንገድ ከእርዳታው ጦር ጋር ተገናኘ ። የሸ
ሹት ፣ ጦርነት ካልቀመሱት ጋር ተገናኝተው በአሪሞንዲና በዶጀኑ
መሪ በጄኔራል ኤሌና ውስጥ ሆነው እንደገና ባዲስ ኃይል ለመዋ
ጋት ተዘጋጁ ። የጦርነቱን ዝርዝር ታሪክ ኮንቲ ሮሲኒና ሪዶልፎ
ማዘኮኒ ከጻፉት ላይ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል ።

> ... የጄኔራል አልቤርቶኒ ጦር ተሸንፎ የተረፈው የነጭና የጥ
> ቁር ወታደር እየሸሸ የሸዋው ጦር እያባረረ ፣ የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር
> ወደ አለበት ወደ ዝባን ዳዕሮና ወደ ራዓዮ ተራራ ደረሱ ። ...በአሪሞ
> ንዲ ውስጥ ለውጊያ የተሰለፉት ከፍተኛ የጦር አለቆች የመቀሌው
> ጋልያኖ ፣ ቦድዋ ፣ ቪያንቺኒ ፣ ደስቲፋኖ ፣ ኮምፒያኖ ... ይባ
> ላሉ ። እነዚህም የየክፍል ጦራቸውን ይዘው ሲጠባበቁ ሐበሾቹ ከኋላ
> እየተከታተሉ የነጩንና የጥቁሩን የኢጣልያን ጦር እያባረሩ ደረሱ ።
> በዚህ ጊዜ የመድፈኛው አዛዥ ሎፍሬዶ መድፎቹን አስጠምዶ ሊተ
> ኩስ ሲል፡ አባራሪዎቹና ተባራሪዎቹ ቅርብ ለቅርብ ስለሆኑ አንዳንድ ጊዜ
> ተደባልቀው ስለሚዋጉ ደርቦ እንዳይመታቸው ስለፈራ ተኩሱን ማቆም
> ግድ ሆነበት ... መልሶ ሲተኩስም ፡ አባራሪዎቹ ተኩሱን ሰምተው
> ተበታትነው በየጫካው በየሸለቆውና በየቁጥቋጦው ገቡ ። በመድፈኛ
> ተባራሪዎቹን የባንዳ ወታደሮች ለማቆምና ለማዋጋት ተፈልጎ ነበር ።
> ግን በፍጹም ሊቆሙና አበሾቹን ሊመክቱ አልቻሉም ። የዚህንም ወሬ



ጄኔራል ባራቲዬሪ በሰማ ጊዜ የሚሸሹት ተሰብስበው በራዓዮ ቁልቁ
ለት ላይ እንዲመክቱ ሲል የጦር ሹማምንት ላከ ።

ከአልቤርቶኒ ጦር የሸሹት የጥቁር ወታደሮች ፣ ለእርዳታ የመጡ
ትን የነጭ ወታደሮች አግኝተው ከተጠራቀሙ በኋላ ፣ ወደፊት የሚገ
ፉትን የኢትዮጵያውያኑን ጦር ለመመከት ተዘጋጁ ። ነገር ግን በዝባን
ዳዕሮ በኢራሩ ጠባብ መንገድ በኩምሮ ታህታይ በኩል ያዬ ምኒልክ
ጦር እየገፋ ክብ ይዞ ... ጀመር ። ከዚያ ወደ መቀራረብ ደረሱና በሁለ
ቱም በኩል ኃይለኛ ጦርነት ተጀመረ ... መድፈኛውም በሰባት
መቶና በሺ ሜትር ርቀት ሲታኰስ ፣ የቀረውም በየጫካው በየሸለቆው
በሩቅም በቅርብም ሆኖ እየተታኰሰ ይዋጋ ጀመር ። ... ተደበላ
ልቆ በሳንጃና በጐራዴ በጨበጣ ጦርነት እየተደባደበ መገዳደል ...

በዚህ ጊዜ ፣ የሸዋ ጦር እየበረከተ ሔደ ። ዐፄ ምኒልክም በደቡብ
በኩል የአልቤርቶኒን ጦር ፈጅተው ከጨረሱ በኋላ ፣ በላጻትና በአባ
ገሪማ ተራራ መካከል አልፈው በማይ ቆዳ በኩል ወርደው በአቦ
በኩል አሻቅበው ወደ ሰማይታ ወጡ ። ከዚያም ወደ ሰሜን ወደ አዲ
በቂ አዘቅዝቀው ማይ አጋም ከሚባለው መንደር ቆመው የማርያም
ሸዊቶን ውጊያ በሩቁ ይመለከቱ ጀመር ። በዚያም የንጉሡና የራሶቹ
ጦር በሁለት በኩል ተከፍሎ አንደኛው በግንባሩ ያለውን የኢጣልያኖ
ቹን ጦር ሲገጥም ፣ የቀረው እየተሯሯጠ በምዕራብ በኩል በዝባን
ዳዕሮ ያለውን ጦር ገጠመ ። የቀረውም ወደ ቤላህ ተራራ ሔዶ የዳቦር
ሚዳን ጦር በዠርባ በኩል ገጠመው ። የዝባን ዳዕሮን ጉብታ ቀድሞ
መያዝ ጠቃሚ መሆኑን ጄኔራል ባራቲዬሪ ተረድቶት ስለነበረ ፣ በቶሎ
እንዲይዝ ለኰሎኔል ስቲፋኒ ሁለት ጊዜ ላከበት ። ኰሎኔሉም ይቺን
የዝባን ዳዕሮን ተራራ ጫፍ ቀድሞ ለሚይዝ ሽልማት አደርግለታለሁ
ብሎ ለጭፍሮቹ ተስፋ ሰጠ ። አንድ ዐርባ የሚሆኑ አነጣጣሪ ወታደ
ሮች(ቤርሳሊየሪ) በሌተና ኰሎኔል ኮምፒያኖና በካፒቴን ፉብሮኒ ...
እየተመሩ ዳገት ቁልቁለቱን በችግር አልፈው ወደጫፍ ተጠጉ ዳሩ
ግን ጫፉ በሐበሾቹ ተይዞ ተገኘ ። ቢሆንም ኮምፒያኖ 'አይዟችሁ
ልጆች ዛሬ ማታ ዓድዋ ገብተን ኮክ እንበላለን' እያለ ወታደሮ
ቹን ያበረታታ ነበር ። የቀረው የሬጂማው አዛዥ አለበት ቦታ ሆኖ
ኮምፒያኖ አንዱን ያበሻ ወታደር በሰይፉ መትቶ ቁልቁል ሲወረው
ረውና ቀጥሎ ብዙ አበሾች እርሱን ከበው ሲገድሉትና ከርሱ ጋር
ያሉት ጣልያኖችም በዚያው ቦታ እየተዋጉ ሲያልቁ በሩቁ ይታዩ
ነበር ። ስለዚህ በ10፡30 (በአራት ሰዓት ተኩል) የተራራው ጫፍ
በአበሾቹ እጅ ተረጋግጦ መያዙ ታወቀ ።

የዝባን ዳዕሮ ጫፍ የአሪሞንዲን ጦር በቀኝ በኩል ለመምታት
ባንድ ወገንም አልፎ የዳቦርሚዳን ጦር ለመውጋት ምቹ ስፍራ ስለ
ሆነ ፣ የዚህ ጫፍ በአበሾች እጅ መያዝ ለሁለቱም ክፍል የኢጣልያ
ጦር ፍጻሜ ምልክት ሆነ ። ስለዚህ እዚሁ ስፍራ ሆነው የኢትዮጵያ
ወታደሮች በመጀመሪያው ባታዮ ጦር ላይ እየተኰሱ ሲመቱ እንደዚሁ
ከግራና ከቀኝ ከበው እየተታኰሱ ዋናውን የብሪጌድ ጦር ከፉኛ ተያ
ያዙት ። የመጀመሪያው ባታዮ ጦርም እየተታኰሰ በዠግንነት ቢጋደ
ልም ፣ አበሾቹ ቁጥቋጦ ፣ ዲብና ቋጥኝ ተገን እየያዙ እየተጠጉ በመታ
ኰስ ብዙ ጉዳት አደረጉ ። ስለዚህ ጣልያኖቹ ባሉበት ቦታ መከላከል
ከንቱ መሆኑን ስለ ተመለከተ ፣ ማዦር ደስቲፋኖ ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ

ለቀኛፍርሟ ትእዛዝ ሰጠ ።... በዚህ ጊዜ ገሚሱ ሲሸሽ የቀረው እንደ ጉርፍ የመጡትን የጠላት ወታደሮች ለማገድ ሲታኰስ የቀረውም የሁለቱ ወገን ጦር ተደባልቆ በጨበጣ ይዋጋ ጀመር ።...

በዚህ ትልቅ የድብልቅልቅ ጦርነት ጊዜ ቲኔንቲ ከሻሊኒ ወታደሮቹን እያበረታታ ለማዋጋት 'ኢጣልያ ሕያው ትሁን' ብሎ ቢጮህ ጩኸቱን ከፉ ሳይጨርስ ሙሉ ለሙሉ ደረቱን በጥይት ተመትቶ ወደቀ ። ትንሽ ቆይቶ 3ኛው ክፍል የኰሎኔል ጋሊያኖ ጦር ሌሎችም መጥተው ወደ ጦርነቱ ተጠመዱና የራዓዮ ጦርነት ይቀጥል ጀመር ። የአገር ተወላጅ ወታደሮች በጋሊያኖና በሌሎቹ ሹማምንት እየተ[illegible] አድርገው መከቱ ።... ከብዙ ሰዓት ውጊያ በኋላ በግራ በኩል የኢጣልያ ጦር ደከም መፍረስ ሲጀምር በብዙ ፣ ነገድ (ብሔረሰቦች) የተከፈለው የኢትዮጵያ ጦር በያለበት ከቦ በራዓዮና በግርያም ሸፍቶ ያለውን የኢጣልያን ጦር በርትቶ መውጋቱን ቀጠለበት ።

በኋላም የኢጣልያ ጦር መዳከሙን ሲመለከት ፣ ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ከተጠባባቂው ጦር ውስጥ ያንድ ሬጂማ ጦር መጥቶ ወደ ጦርነቱ እንዲገባ ጄኔራል ኤሌናን አዘዘው ። ዳሩ ግን ከ24 የክፍል ጦር (ኮምፓኒ) ውስጥ 5 ብቻ ሲጠባበቅ የቀሩት ባንድ ወገን ገና አስቀድመው እጦርነቱ ውስጥ ገብተው ይዋጉ እንደነበረ ዋናው አዝማች አልተረዳውም ነበር ።... አበሾች የዝባን ዳዕሮን ጉብታ ሌላውንም ምቹ ሥፍራ ይዘው በኢጣልያኖችና ባገር ተወላጅ ወታደር ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አደረጉበት ... ግማሾቹም አበሾች በየጫካውና በየቁጥቋጦው ውስጥ ሆነው እንጣጥረው እየተኰሱ የማያዩዋቸውን ኢጣልያኖች ይገድሉ ጀመር ። ኢጣልያኖችም አንዳንድ ጊዜ አበሾቹን ሳያዩ ፣ ከጥይታቸው የሚወጣውን የባሩድ ጢስ ብቻ እያዩ ለመተኰስ ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ምንም የረባ ጉዳት በጠላቶቻቸው ላይ ሊያደርጉ አልቻሉም ። ስለዚህ ግማሹ ሽሽት ሲጀምር የቀረው በእልህ ያለበትን ስፍራ ይዞ እየተዋጋ ሲተላለቅ ያበሾቹን ብዛትና ኃይል ክቢያቸውንና የሚያደርጉትን ጉዳት ሁሉ በተመለከተ ጊዜ ጄኔራል ባራቲዬሪ 11:30 (በአምስት ሰዓት ተኩል) ላይ በጥሩንባ ወደኋላ እንዲሸሹና ከተጠባባቂው ጦር ጋር ሆነው እንዲመክቱ ለኢጣልያኖቹ ትእዛዝ አስተላለፈ ።

በዚህም ጥሩንባውን ከሰማው ውስጥ ግማሹ በሥርዓት ወደኋላ ሲያፈገፍግ ግማሹ በየበኩሉ እግሬ አውጭኝ ብሎ ሸሸ ። የቀረው ደግሞ ጥሩንባና ትእዛዝ ያልሰማው አለቀ ።... በዚህ በተዘበራረቀ መልስ ላይ ጄኔራል ባራቲዬሪና ጄኔራል አሪሞንዲ ተገናኝተው ተስፋ በመቁረጥ ተያይዘው እጅ ለእጅ ተጨባበጡ ይባላል ። ከዚያም ሁለቱም ጉራዴያቸውን እንደ ጨበጡ ተዘባርቆ የሚሸሸውን ወታደር ለማቆምና በሥርዓት አድርገው ለማዋጋት ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን በራሪውን ለማቆም በፍጹም የማይቻል ሆነ ። በዚሁ መካከል ትእዛዝ ለመስጠት ወደኋላ ቀረት እንዳለ ጄኔራል አሪሞንዲ ተመትቶ ወደቀ 1 ... ስለዚህ የመካከለኛው ዘማች ጦር በዚህ

1 Italia ed Etiopia ....,pp. 380-400



ዓይነት ሲደመሰስ ዋናው አዝማች አሪሞንዲና እንደ ጋሊያኖ ያሉት የታወቁት የጦር አለቆች በዚሁ ጦርነት ሕይወታቸው አለፈ ።

ስለ ጄኔራል አሪሞንዲ አሟሟት ኮንቲ ሮሲኒ ከዚህ በላይ በተጻፈው ዓይነት ሲተርክልን ፣ ሪዶልፎ ማዙኮኒ የሚባለው ሌላው ጸሐፊ ደግሞ እንደዚ ይላል ።

“ጄኔራል አሪሞንዲ ...... በጦርነቱ በግራ በኩል ሆኖ ጦርነቱን ለመምራት አንድ ከፍ ያለ የድንጋይ ቋጥኝ ላይ ተቀምጦ የጠላትን ጦር ሲመረምር በቀላሉ ቀኝ እጁን ተመታ ። ባገዛ እጁ የተመታውን እጁን በመሐረብ አስሮ መነጽሩን በግራ እጁ ይዞ መመልከቱን ይቀጥል ጀመር ። አጠገቡ የነበረው ያይን ምስክር የሆነው አስተርጓሚው እንደዚህ ሲል ቃሉን ሰጠ ። የእግራ ፈረሰኞች በብዛት ሲመጡ አይቶ መድፈኞች እንዲተኩሱ ትእዛዝ ለመስጠት ቢሔድ ፣ መድፈኞቹ ሞተው ግማሾቹም ቆስለው የጋሊያና የባታዮ ጦርም ተበታትኖ አገኘው ። በዚህ ጊዜ ወደኋላ ሽሹ የሚል ትእዛዝ ደርሶት ሹማምንቱን ሲሰበስብ አንድ ጥይት ደረቱን መትቶ ጣለው ። 1

ስለዚሁ ጄኔራል አሟሟት ኮንቲ ሮሲኒ በሌላ ሥፍራ ላይ ከቃል የሰማውን የጻፈው እንደዚህ ይላል ።

እግሩን ቆስሎ ምናልባት ባንድ መድፍ ሥር ተቀምጦ ሳለ ወደኋላ የሚሸሹት ሹማምንቶቹ አግኝተው እንዲሸሽ ቢለምኑት እምቢ አላቸው... ወዲያው በቅሎዬን አምጣልኝ ብሎ አንድ የራሱን ወታደር ቢልክ ፣ በቅሎውን ይዞ ይጠብቅ የነበረው አሽከር (ባንዳ) ተገድሎ በቅሎውም ጠፍቶ አገኘው ። አንድ የጥቁር ወታደር አሪሞንዲ ሌሎች ኢጣልያኖች መድፍ ለመጫንና ለመሸሽ ሲሞክሩ እነርሱን ሲረዳ ተመትቶ ወደቀ ይላል ። የቀሩት ደግሞ ጄኔራል አሪሞንዲ ከሰዓት በላይ ሸሽቶ ወደ ዬሃ ሲሔድ ሰላማውያን መስለው ቆመው የነበሩ ባላገሮች አጠገብ ሲደርስ እነርሱ በጠበንጃ ገደሉት ።

ጄኔራል አሪሞንዲ በጦርነት መሞቱ ሲታወቅ የሞተበት አኳኋን ግን በዚህ ዓይነት ተለያይቷል ። እላይ እንዳልነው ፣ በዚህ የአምባ ራዓዮ ወይም የዝባን ዳዕሮ ጦርነት የአሪሞንዲ ጦርና ሌሎችም ብዙ የኢጣልያ ወታደሮችና የጦር ሹማምንት አልቀዋል ማለት ነው ። ከነዚህ ውስጥ በመቀሌ ምሽግ መከላከል ስሙ የታወቀው ሌተና ኮሎኔል ጕሴፔ ጋሊያኖ ይገኝበታል ። ጋሊያኖ የዓድዋ ጦርነት በሚደረግበት ጊዜ በተጠባባቂው የደጀን ጦር መሪ በጄኔራል ኤሌና ውስጥ ተመድቦ 3ኛውን የጥቁር ባታዮ ጦር ይዞ ተሰልፎ ነበርና በአምባ ራዓዮ የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ብዙ ሰዓት ተዋግቶ ወደ መሸነፍ ሲያዘነብል ካለቆቹ ታዞ ለእርዳታ መጥቶ ተዋጋ ። የአሪሞንዲ ጦር ጨርሶ ሲጠፋ እርሱም ያገር ተወላጅ ወታደሩን ይዞ ሲዋጋ ቆይቶ ከርሱ ጋር ከዘመተው አንድ ሺ ሁለት መቶ ጦር ሦስት መቶ ተርፈው

1 La Giornata di Adua, R. Mazzuconi, pp. 275-277

ሲሸሹ የቀሩት አለቁበት ። ከርሱ ጋር ከነበሩትም ዐሥራ ስም ንት ሹማምንት ያመለጠ አንድ ብቻ ነበር ። እርሱም በዚሁ ጦርነት ሞቶ ተገኘ ።[1]

ስለ ሌተና ኮሎኔል ጋልያኖ አሟሟትም ፣ ወሬው በሦስት ዓይ ነት ተተርኮ ይገኛል ።

፩ኛ ግምባሩን ቆስሎ ደሙን እያዝረከረከ ፣ "ጌቶች ሆይ ሰዎቻች ሁን እንደያዛችሁ ፍጻሜያችንን (አሟሟታችንን) እናሳምር " ብሎ አጠገቡ ላሉት ሹማምንትና ባንዶች ተናግሮ ወደኋላው ዘወር እን ዳለ ፣ ከዚያ ወዲያ ጉብታ እንደ አዘገመና ከዚያ ወዲያ አለመታየ ቱን እንደ የጦር ሹም ማውራቱ ተጽፎ ይገኛል ።

፪ኛ. መንጋጋውን በግራ በኩል ተመትቶ ደሙ በጣም ይወርድ ስለነበረ ፣ በቅሎውን ይዘው ወደሚጠብቁት አሽከሮቹ ሔዶ ባንድ ደንጊያ ላይ ተቀምጦ ውሃ አምጡልኝ ብሎ ጨርቁን በውሃ እየነከረ ደሙን ለማቆም ሲሞክር የኢትዮጵያ ወታደሮች በድንገት ደርሰው ማረኩት ። ጋልያኖ መሆኑንም ስላወቁ የደስታ ጥይት ወደ አየር እየ ተኮሱ ጐትተው ወደ ታችኛው ሸለቆ ወሰዱት ። በዚያም ለንጉሣችን እናቀርብሃለን ብለው ሲጐትቱት እርሱም 'የርሱን (የምኒልክን) ፊት አላይም' ብሎ ሲተናነቅ አንዱ በጥይት መትቶ ገደለው ።[2]

፫ኛ. ማዝዮር ባቲስታ አሜሊዮ የሚባለው ለጦር ምክትል ሚኒ ስትሩ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ፣ " ካሣ ኃይሉ የሚባለውን አሽከር ( ያገር ተወላጅ ወታደር ) በመጋቢት 10 ቀን የእስረኞቹን ወሬ እንዲያጠያ ይቅ ልኬው ስለነበረ ፣ ጋልያኖ ከተማረከ በኋላ የመቀሌን ምሽግ የለቀቀ ጊዜ ፣ ሁለተኛ አልዋጋም ብሎ የነበረውን መሐላ አፍርሶ ሰዎ ቹን ስለወጋ ጥፋተኛ ነው ብሎ አንድ ሊቀ መኳስ እምኒልክ ላይ ከሶት በጥይት ተደበደበ"[3] ይላል ። አንድ የደራሲው ስም ያልታ ወቀ የግዕዝ ታሪክ ፣ መቀሌ የነበረው ጋልያኖ ሁለተኛ ወደ ንጉሥ መጥቶ እንዳይዋጋ በመሐላ ከሔደ በኋላ ፣ ተመልሶ መጥቶ ሲዋጋ ተማ ረከ ማራኪው ወደ ንጉሡ ልውሰድህ ቢለው እምቢ ስላለው ገደለው " ቢል ባጭሩ ደምድሟልና ይኸኛው ሊታመን ይችላል ።[4]

1 Italia ed Etiopia . . . P. 404.

2 La Giornata di Adua, PP.276—277.

3 Lettere e Diari, . . . P.56.

4 ወማገር ጋሊያኒ (ጋሊያኖ) ዘነበረ በመቀሌ ወዘመሐለ ከመ ኢይመጽእ ዳግመ ለባእስ መጽአ ተማኅሪኮ ወሰበ አበየ ይሑር ቅድመ ገጸ ምኒልክ ንጉሥ ቀተሎ እንተ ማኅረኮ ፣ የኢትዮጵያ ጥናት IES, No. 681, P. 129. (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)





በዓድዋ ላይ የሞተው ጄኔራል አሪሞንዲ

ከማዙኮኒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ ሁለት

## የቀኝ አዝማቹ የብሪጌድ ጦር ተዋግቶ መሸነፍ — የጄኔራል ጆሴፔ ዳቦርሚዳ አሟሟት

ቀደም ብሎ በተደረገው ጦርነት ድል ለተመታው ጦር፤ ግንባር ቀደም ሆኖ የጥቁሩን ወታደር ይዞ በአምባ ኪዳነ ምሕረት የተዋጋው ጄኔራል አልቤርቶኒ ከተማረከና በመካከል በአምባ ራዓዮ የዘመተው የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ተሸንፎ ከፈረሰ በኋላ፤ ተጠባባቂ ሆኖ በረቢ አሪዬኒ የነበረው የጄኔራል ኤሌና ወታደሮችና በዋናው አዝማች በጄኔራል ባራቲዬሪ ዙሪያ የነበሩት ከውስጣቸው በከፊል እየተመረጡ ሔደው የተሸናፊዎቹን ዕድል መካፈላቸው ታውቋል። ይኸ ሁሉ ሲሆን፤ በቀኝ በኩል የዘመተው ጄኔራል ዳቦርሚዳ ለብቻው ተለይቶ ወደ ማርያም ሸዊቶ ሔዷል። ጄኔራሉ በሩቅ የጥይት ተኩስ መስማቱ ባይቀርም፤ በጓደኞቹና በቀረው የጦር ሠራዊት ላይ የደረሰውን የመሸነፍ አደጋ በትክክል ያወቀ አይመስልም።

ለብቻው ተነጥሎ ሔዶ ለመዋጋት የፈለገበትን ምክንያት በኋላ የተነሡ ጸሐፊዎች፤ “እንደ አልቤርቶኒ ብቻውን የኢትዮጵያን ጦር ተዋግቶና አሸንፎ የድል አድራጊነትን ክብር ለብቻው ለመውሰድ ተመኝቶ ነው” ሲሉ ጽፈዋል። ከዚሁ አያይዘው፤ “ያለዚያ አልቤርቶኒ ወይም አሪሞንዲ በሚዋጉበት ጊዜ ወደኋላ ወደ አምባ ራዓዮ ወደ ግራው ወደ እምባ ኪዳነ ምሕረት ታጠፍ ብሎ ለእርዳታ ቢደርስ ኖሮ የሐበሻ ጦር ሳይሸነፍ አይቀርም ነበር” ብለው እንደ መሰላቸው አመልክተዋል። የቀሩት ደግሞ፤ “በመለገም ሳይሆን በፕላንና በመንገድ ስሕተት ለብቻው ወደ ማርያም ሸዊቶ ተመርቶ ሔዶ አብረውት የነበሩትም የነጭ ወታደሮች አገርና መንገድ የማያውቁ ከመሆናቸውም በላይ በመንገዱ መጥፎነት ከጫካው ብዛት፤ ከስፍራው ወጣ ገብነት የተነሣ ከመድከም ጋር በሌሊት ጉዞ በስሕተት ወደቀኝ ወደ ማርያም ሸዊቶ ርቆ ሔደ ለብቻው ተዋግቶ ለብቻው ተሸነፈ” ብለው በታሪክ ፊት የስሕተት እንጂ፤ የመለገም ወይም የራስ መውደድ ኃላፊነት እንዳይወድቅበት ተከላክለውለታል። በተለይ የርሱ የልፍኝ አስከልካይ የነበረው ኮሎኔል ቤላቪታ ስሕተቱን በፕላን አሠራር፤ በትእዛዝ አሰጣጥና ባመራር ረገድ በባራቲዬሪ ላይ አድርጎታል።

የእሪሞንዲና የኤሌና ጦር በሚዋጋበት ጊዜ ፣ እደጋ ላይ መሆኑን
ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ተገንዝቦ የዳቦርሚዳ ጦር መጥቶ
እንዲረዳ ለማድረግ እነ ኮሎኔል ባሌንዛኖን ፤ እነማዡር ሳልሳን ዳቦር
ሚዳን እንዲፈልጉ ልኳቸው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ይህ ጄኔራል ከነጦሩ
ርቆ ለብቻው ከመሔዱ የተነሣና ግማሹ ስፍራ በድል አድራጊዎቹ
ኢትዮጵያውያን ስለተያዘ ፣ መላከተኞቹ ብዙ ሰዓት ተንከራተውና
ባዝነው አጣነው ብለው ተመለሱ ።

በኢጣልያኖቹ ጽሑፍ እንደሚገኘው ፣ ጄኔራል ዳቦርሚዳ በው
ስጡ ሦስት ሺ ስምንት መቶ ስምንት የጦር ወታደር ፣ ዐሥራ ስምንት
መድፍ እንደያዘ ፣ እንደ ጓደኞቹ ሌሊቱን ተጉዞ ሲነጋ ወደ ማርያም
ሸዊቶ አቅራቢያ እንደ ደረሰ ፣ በያለበት ጦሩን ከፋፍሎ ያሠማራ ጀመር ።
ማጆር ደ ቬቶ የሚባለው የጦር አዛዥ የጥቁር ወታደሮች ጦር ጨምሮ
ግንባር ቀደም በማድረግ ወደ ማርያም ሸዊቶ ላከው ። በዚህም ጊዜ በአባ
አቤል አጠገብ ቃፊር ሆኖ ይጠባበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በማይ
ቶጉ ሆኖ ቁልቁል የሚወርዱትን ጣልያኖች ተመለከተና ከዚያ ራስ
መንገሻ ወዳሉበት ወደ ጌራ ሔደ ። በዚያው አቅራቢያ በኤረር የሸዋ
ጦር ስለነበረ ፣ ግንባር ቀደሙ የማጆር ደ ቬቶ ጦር ወደ አምባ ድሪ
ያም አቀበት ሊወጣ ሲል ተኩስ ተጀመረ ። ወዲያው በፍጥነት ተዥሱ
ተጋግሎ ይዋጉ ጀመር ። የቀሩት የጥቁሩም ፣ የነጩም ወታደሮች ባንድ
ነት ሆነው እንደ ጐርፍ የመጡባቸውን የኢትዮጵያውያንን ሠራዊት
ገትረው ሲዋጉ ደ ቬቶ ወታደሮቹን ይዞ ሳያስብ ፣ ባዶ መስሎት ድሪ
ያም ጉብታ በተለይ አድግባ ከሚባለው ስፍራ ሲደርስ ራስ መንገሻ
(ዮሐንስ) በድንገት ተቀብለው ተዋጉትና ሞተ ። የግንባር ቀደሙ ጦር
ቢያልቅም ፣ ዋናው የዳቦርሚዳ ጦር በአራት ሰዓት ተኩል ተኩስ
በተጀመረበት ጊዜ ከዚህ እንደሚከተለው ተሰልፎ ነበር ።

በግራ በኩል ፤ 10ኛው ባታዮ በደፎኒስካ አዝማችነት ፣ በቀኝ
በኩል በአምባ ድሪያም 6ኛው ባታዮ በፕራቶ አዝማችነት ፣ በታች
በኩል 5ኛው ባታዮ በጆርዳኖ መሪነት ፤ 18 መድፎችም በሸለቆ ውስጥ
ተጠምደዋል ። በቀኝ በኩል 14ኛው ባታዮ በሶላሮ መሪነት ፤ 2ኛው
ባታዮ በኮሎኔል አይራጊ የሚመራው ከኋላ ይጠባበቅ ነበር ። ከነዚህም
በቀር አምባ ኤረር ላይ በኢትዮጵያውያኑ ተከበው ሊያልቁ የነበሩትን
ጣልያኖች ያዳናቸው ማዡር ደ አሚቺስ በዚሁ ስፍራ ይገኝ ነበር ።

የዚህን ጊዜና ስፍራ ጦርነት ካፒቴን ኪዬሪቺ የተረከው እንደዚህ
ይላል ።

ከኤረር ጉብታ መቶ ሜትር የሚያህል ወደታች አንደ ወረደን
ተጠባባቂው ጦር በድንገት ወደኋላ ሲያፈገፍግ አየነው ። ደ አሚቺስ



እኛ ወደ ተውነው ጉብታ እንድንመለስ አዘዘ ። በዚሁ መካከል ድንገት
ከያለበት ዡሮ የሚያደነቁር የጥይት ጩኸት ተሰማ ። ኢጣልያኖችም
በዚሁ ጥይት በትር እየተጨፈጨፉ ተረባርበው ወደቁ ።

በዚህ ጊዜ ፤ ጥይቱ ከአኩል ሰዓት በፊት ከለቀቅነው ከቅርብ
ስፍራ መምጣቱን ተረዳነው ። ነገር ግን ፣ ከሣሩ እርዝማኔ የተነሣ
ተኳሾቹን በፍጹም ማየት የተሣነን ቢሆንም ፣ ተሰልፈን የጥይት ተኩስ
በሚሰማበት አቅጣጫ እንተኩስ ጀመር ። ዳሩ ግን ፣ ተኩሳችን ፍሬ
የሰጠ አይመስለኝም ። በመጨረሻ አምሳ የሚሆኑ የጠላት ወታደሮች
ስላየሁ ፤ በሳንጃ ተዋግተው እንዲያባርሯቸው አዝዤ ቀጥሎ በሩጫ
ሔጄ እኛንና ወገኖቻችንን የሚለየውን ስፍራ ያዝሁ ። ከዚያ በሰልፍ
ሆነን በቅሎቻችንን ከሚጠብቁት ጋር የሚማቱትን ሐበሾች መውጋት
ጀመርን . . . እነዚህ ሐበሾች ሐሞት (ጉብዝና) ያላቸው መሆናቸውን
መካድ አይገባም ። የሚተኰስባቸውን ጥይት ሳይፈሩ ጭንቅላታቸውን
አጐንብሰው ሰይፋቸውን እያወዛወዙ በቅሎዎቹ የታሰሩበትን ጠፍር
በጥሰው ለመውሰድ እየሮጡ ሲመጡ እኔው ራሴ አይቻቼዋለሁ ።
ብዙዎቹንም አጠገባችን ከደረሱ በኋላ በሸጉጥ ልንመታቸውና ልንገ
ድላቸው ችለናል ። በግራ በኩል ተደብቆ የኛን ጦር ያጭድ የነበረ
ውንም የጠላት ጦር ሞኒና የሚባለው ጐበዝ መኰንን ከጭፍሮቹ ጋር
ገጥሞ በሳንጃና በጩበጣ ተዋግቶ ካሉበት አስወጥቶ ሲያባርር እርሱ
ራሱ ተመትቶ ወደቀ ።

ቢሆንም ባለንበት ስፍራ ለመቆየት ከየአለበት በዙሪያችን በብ
ዛት የሚተኰሰው ጥይት አላስቻለንም ። እኛም በያቅጣጫቸው መልሰን
ብንተኩስ አልሆነንም ። በዚህ ጊዜ አዝማቹ ማዡር ባለበት በኩል
'እየምሸጋችሁ' የሚል ጩኸት ስለተሰማ ፣ በየቁጥቋጦውና በየቋጥኙ
ውስጥ አልፈን አንዲት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ደረስንና የቤተ ክርስ
ቲያኑን ቅጥር እንደ ምሽግ ተገን ይዘን ተቀመጥን ። ይሁን እንጂ በዐ
ሥር ደቂቃ ውስጥ 150 ወታደሮችና 3 መኰንኖች አስቁብን ።
. . .ምሽግ ይዘን ትንሽ እንደ ተነፈስን ጠላት እያደር በብዛት እየተ
ኰሰ እያየነው ይከበን ጀመር ። አነጣጥረን ለመተኮስ የምንችለውም
የጥይት ጪስ በሚታይበት በኩል ብቻ ነው ።. . . የትግሬን ጦር የያ
ዙት ራስ መንገሻና ራስ አሉላ በአዲ ፈቂ በራዕድ በረቢ አሪዬኒ ያለው
ጦር ለእርዳታ ሳይመጣላቸው ጦርነቱን እንዳይጀምሩ ትእዛዝ ተቀብ
ለው ነበር ። የተጠበቀው የእርዳታ ጦር ከአራት ሰዓት ጀምሮ በብዛት
ከመጣላቸውና የኢጣልያ መድፎች መጮህ ከጀመሩ ወዲህ ዋናው
የሸዋ ጦር የዳቦርሚዳን ጦር በኃይል ገጠመው ። የመድፉ ድምፅ
ከቀሰቀሳቸው ወዲህ በአባ እቤል በግራ በኩል የጠላት ሠራዊት
በብዛት ተገኝቶ በብዛት እየተኰሰ የኢጣልያኖችን የእግረኛ ጦር ከፋኛ
ፈጀው ። ኢጣልያኖቹ እታች ሆነው ወደላይ ወደ አበሾቹ የተኰሱት
ምንም ያህል ጉዳት አላደረገም ። ይልቅስ ዐሥራ ስምንቱ መድፎች
የጥይት ነበልባላቸውን እየተፉ ጠላት የያዘውን ስፍራ ማስቸገራቸው
ግልጽ ነው ። በዚህ ሰዓት ዋናው የዳቦርሚዳ ጦር በሙሉ ጦርነቱን
ጀመረ ። . . .ወታደሮቹም ሹማምንቱም ዋናው አዛዥም ፤ ምንም እን
ኳን አንድ ታክቲክ (የጦር መላ) ቢጐድል ደንበኛ የጦርነት ሞያ
ቸውን አሳዩ ። በነርሱም ብርታትና ዘዴ ጠላት እየለየ ለመምታት

ሳያስችለው ቀረ ። እንዳሰበውም ከቦ ለመፍጀት እንዳይችል ጠንክረው ተከላከሉት ።

ቢሆንም ጊዜው በረዘመ ቁጥር ፣ የጠላት ጦር እየተጫነ ሔዶ የኢጣልያኖቹንም እርምጃ እግር በእግር ሐበሾቹ ይቃወሙ ነበር ። ሐበሾቹ በኃይል ተቀስቅሰው ጣልያኖቹ የያዙትን ስፍራ ለማስለቀቅ ሲሞክሩ በጥይት ኃይልና ብዛት መለሷቸው ። ከተመለሱም በኋላ እንደገና እየተዋጉ የፈለጉትን ስፍራ በመቀማት ብዙ ስፍራዎች እየሔዱ እየተመለሱ ካንድ እጅ ወደ ሌላው እጅ ተዘዋውረዋል ።

ስለዚህ ፣ ጣልያኖቹ እስከ 13 ሰዓት ድረስ በዚሁ በአባ አቤል በማኅበረ ጸዳል በአጽገባ . . . ገትረው አራት ጊዜ የበረከተውን የኢትዮጵያውያንን ጦር ከመለሱና ስፍራቸውን ከአጠበቁ በኋላ ጄኔራል ዳቦርሚዳ በመልካም ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን በዚሁ ጊዜ ለዋናው ጠቅላይ አዛዥ ለጄኔራል ባራቲዬሪ መልክት ልኮ ነበር ። ዳሩ ግን አልደረሰለትም . . . ኢጣልያኖቹ ውጊያውን ቆም አድርገው መድፎቻቸውን የተሻለ ስፍራ ፈልገው ከጠመዱ ለየባታዮም መሣሪያ አጓልተው ከአከፋፈሉ በኋላ ፣ የቆመው ጦርነት እንደገና ተቀሰቀሰ ። ይሁን እንጂ ፣ ከ13 (7) ሰዓት ቀጥሎ ባለው ጊዜ የኢጣልያኖች ኃይል ወደ መድከም ቀረበ ። በአምባ ራዓዮ ተዋግተው የጄኔራል አሪሞንዲን ጦር የመቱት የዐፄ ምኒልክ ወታደሮች ተገልብጠው ወደዚህ ስለመጡ የዳቦርሚዳ ጦር በወታደር ግድግዳ ከጊዜ ወደጊዜ እየተከበበ ሔደ ። የንጉሡ መድፈኞች በግራ በቀይህ ዘባን በኩል እንደዚሁም በቀኝ በአባ አቤል በኩል ድምፃቸውን እያሰሙ ሲያጠቁ የቀረው የእግረኛ ጦር ከቢውን ብቻ እየሠራ ውጊያውን ስጊዜው አላላ . . . የኢትዮጵያውያን ጦር በየጫካው ተሰግስጎ ከቦ እየተጠባበቀ ሁለት ሰዓት ያህል ያለውጊያ ሲቆይ . . . የኢጣልያ ጦር ከፉኛ ስለ ተከበበ ፣ በዚሁ ጊዜ አንድ የመውጫ መላ መፍጠርና ባንድ ፊት እየተዋጉ ጥሶ መውጣት ግዴታ ሆነ ። . . . ስለዚህ እስካሁን በብርታት ወታደሮቹን ሲያዋጋ የቆየው ኰሎኔል አይራጊ እፈረሱ ላይ ወጥቶ ሲመራ ተነሣ ። በመታከስ ከንዳቸው የዛለው መላላቸው በውሀ ጥም የተያዘው ወታደሮችም ሲከተሉት ተነሡ ። ነገር ግን ዐሥር ሜትር ያህል እንደ ተራመዱ ብዙዎቹ እየተመቱ ወደቁ ።. . .

አዝማቹ ጄኔራል ዳቦርሚዳ ፣ የመከበቡ ሁኔታ በጣም ስላሠጋው የቀሩትም የብርጌድ ወታደሮች ወሬያቸው ስለ ጠፋበት ፣ ተቸግሮ መላ ከተኛ ለመላክ ቢያስብ በዙሪያው ካሉት የቅርብ አገልጋዮቹ መኰንኖች ግማሾቹ ሞተው የቀሩትም ቆስለው ወይም ተበታትነው አገኛቸው ። ከዚህ በኋላ ጭንቅላቱን አነቃንቆ እጆቹን ወደኋላ አጣምሮ ይዞ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ ከተንጐራደደ በኋላ ፣ ቆም ብሎ ቀና አለና ፈረስ አምጡልኝ አለ ። ከመጣለትም በኋላ እንዳንድ ወጣት ዘሎ እፈረሱ ላይ ወጣና የመጨረሻ የመጣስ ሙከራ ለማድረግ ወደ ውጊያው መስመር ሔደ ። ኰሎኔል አይራጊና ሌሎቹም ሹማምንት ተከተሉት ። በዚያን ጊዜ ጄኔራሉ በሠራዊቱ ፊት ጥሩሩን አውልቆ እየወዛወዘ 'ሳቮያ ሳቮያ' ብሎ ደጋግሞ ጮኾ ግልቢያ ሲጀምር ፊታቸው በአቧራና በላብ የተሸፈነው ወታደሮቹ የጄኔራላቸውን ድምፅ ሲሰሙ ያለፈው ድካማቸው ሁሉ ተወገደና ሳንጃቸውን እያወዛወዙ



'ሳቮያ' እያሉ እነሱም በጩኸት መልስ ሰጥተው እየተጯጯሁ ተከተሉት ።* ዳሩ ግን ፣ በዚሁ ጊዜ ከሐበሾቹ የተተኰሰው ጥይት እየረፈረፈ በየመንገዱ ዘራቸውና ስፍራው በሬሳና በቁስለኛ ተሸፈነ ። መሬቱም የነርሱን ደም ጠጣ ። . . . ዐሥራ ስምንቱ መድፎችም እነሱን ለመጠበቅና ለመደገፍ አልቻሉም ። ለመድፎቹ ጥይት የሚያጐርሱት እየተመቱ ወደቁ ።

ከኢጣልያኖቹ በኩል መከላከል መድከሙን ሲረዱ ሐበሾቹ የያዙትን ስፍራ እየለቀቁ ቁልቁል ወደ ጣልያኖቹ ወርደው ይታኮሱ ጀመር ። የተረፉትም ጣልያኖች የሞቱትን ጓደኞቻቸውን ለመበቀል ተስፋ በቆረጠ ንዴት እየተታኰሱ ብዙ ፈጁ ። ከነርሱ መካከልም አንድ ሲኞር ቦኮኒ የሚባል የሚላኖ ተወላጅ በፈቃደኝነት የብርጌዱን ጦር ከረቢ አሪዩኒ ተከትሎ የመጣ ሲቪል ነበር ። እርሱም አንድ የአሜሪካን ካራቢን ጠበንጃ ይዞ አንዳንድ ጊዜ እየዘፈነ ፣ አንዳንድ ጊዜ እያንጣጠረ ብዙ ጠላት በመግደሉ የጦር መኰንኖቹን ሁሉ አስደነቀ ፣ እንደዚሁ አድርጐ እየተዋጋ እየተሳለቀ ሲዋጋ ቆይቶ እርሱም በፉንታው ተመትቶ ወደቀ ።. . . **

ከዚህ በኋላ ጄኔራል ዳቦርሚዳ ወደኋላ ሽሽት እንዲያደርጉ ለኢጣልያኖቹ ትእዛዝ አሳለፈ ። መተላለፊያውም እሾህ ቋጥኝ የሞላበት በመሆኑ ወደኋላ ለመሸሽ ሁሉም ተፋፈገ ። ትእዛዝም ለየክፍሉ ለማስተላለፍ መተላለፊያ ቸገረ ። በዚህም ጊዜ ሐበሾቹ ምንም ከነርሱም ወገን እልቂትና ድካም ቢኖር ፣ የሚሸሸውን እየተከተሉ እየተጠጉ ስለሚፈጁ ፣ ጄኔራሉና ሹማምንቱ አንዳንድ ጊዜ ፊታቸውን አዙረው እየተዋጉ አጥቂዎቹ እንዲገቱ በራሪዎቹ ትንሽ የመሸሻ ጊዜ እንዲያገኙ አደረጉ ። እየተመለሱ ሹማምንቱ ሐበሾቹን ለማቆም በሚዋጉበት ጊዜ ብዙ የጦር መኰንኖች እየተመቱ ይወድቁ ነበር ። በዚህ መካከል ጄኔራል ዳቦርሚዳ ተመትቶ ወደቀ ። . .1 .

ከዚህ በላይ የተጻፈው ፣ ሪዶልፎ ማዙኮኒ የሚባለው ከመንግሥቱ የባሕር መዝገብ ቁጥር 29 ላይ ወስዶ ባዘጋጀው መጽሐፍ የሚገኝ ነው ። ሌሎቹም እነፖሎራ ፣ እነኮንቲ ሮሲኒ በጦርነቱ ላይ ከዋሉት ከነቤላቪታና ከሌሎቹም ከቃልም ፣ ከጽሑፍም እየሰበሰቡ የጄኔራል ዳቦርሚዳ የጦርነት ታሪክ የተጻፈው በዚሁ ዓይነት ነው ። እንደ ተለመደው ጸሐፊ ሁሉ በመሠረቱ እየተስማማ በዝርዝር ይለያያልና ኮንቲ ሮሲኒ የዚህን ቀን ጦርነት ሲተርክ ፣ በማርያም ሸዊቶ

---

* SAVOYA የንጉሡ የኡምቤርቶ የነጋሢነት አስመኪ መደበኛ ሥፍራ ነው ። አሁን ይኸ ሥፍራ በፈረንሳይ ምሥራቅ በኩል ይገኛል ፤ ስሙም በፈረንሳይ አጠራር SAVOIE ይባላል ።

** Luici Bocconi የሚባል በሚላኖ በንግድ ሥራ የሚኖር ነበር ። እርሱም ወታደርነት ሳይኖረው የኢትዮጵያን ጦርነት በመናቅና በማቃለል ወደ ሽርሽር እንደሚመጣ በመቁጠር በፈቃደኝነት የመጣ ነው ።

1 La Giornata di Adua, Ridolfo Mazucconi PP. 281—301 Libro verde, No 29.

የተደረገውን ጦርነት ልክ እንደ ሪዶልፎ ይተርከና አንዳንድ እዚያ ኛው ላይ የማይገኝ ቃል እርሱ እንደዚህ የሚል ጨምሯል ። "ጄኔራል ዳቦርሚዳ ሽሽቱን ሲይዝ በቀኝ እጁ ጥሩሩን እንቆ ይዞ ያለቅስ ነበር ። ኮሎኔል አይራጊም 'ወደኋላ እንመለስ ፣ ነገር ግን ይህ መመለስ(መሸሽ) በዝግታና በሥርዓት መሆኑን እንዳትዘነጉ' የሚል ቃል በጩኸት ለተረፈው ሠራዊት ተናገረ ።"

በሽሽትም ጊዜ ሐበሾቹ ራቅ ሲሉ በጥይት ፣ አንዳንድ ጊዜም ሮጠው በሚሸሹት ጣልያኖች ላይ እየደረሱ በጎራዴና በሰይፍ ይማታሉ ። አንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ወታደሮች እየተናነቁ ሁለቱም ተያይዘው ከቋጥኝ ላይ ቁልቁል ወድቀው ሲንከባለሉ መታየታቸውን እየጨመረ ፣ እያስፋፋ ይጽፋል ። ዋናው አዛዥ ጄኔራል ዳቦርሚዳ ሲሞት በትክክል ያየው ለጊዜው ስለጠፋ ፤ የጄኔራል ዳቦርሚዳ አሟሟት እንደ ሌሎቹ በተለያየ ሁኔታ ተተርኮ ይገኛል ።

፭ኛው. ጄኔራል ዳቦርሚዳ እላይ እንደ ተጻፈው ፣ ከጦር ሹማምንቱ ከኰሎኔል ራጊ ፣ ከማዦር ፕራቶና ከማዦር ደ ሬኒስካ ጋር ሆኖ እሸሽት ላይ እንዳለ ለተረፈው ጦር የመሸሻ ጊዜ ለማስገኘት ፊቱን እየመለሰ በሚዋጋበት ጊዜ ተመትቶ ወደቀ ። በወደቀ ጊዜም "ኢጣልያ ሕያው ትሁን" ብሎ ጮኾ ሞተ የሚሉ አሉ ።

፮ኛው. በዑሃ ሸለቆ በተለይ አዲ ቂልጠይ ከሚባለው ስፍራ ሲዋጋ መሞቱን አልቤርቶ ፖሌራ ይጽፋል ። ከዚሁ አያይዞ የዓድዋ ጦርነት በተደረገ በሦስተኛው ወር ሬሣ ቀባሪዎች ጣልያኖች በመጡ ጊዜ ፣ "በሱንኮሂና ሲዋጋ ክፉኛ ቆስሎ ሳለ ውሃ እንድሰጠው ለመነኝና ከሰጠሁት በኋላ ፣ ወዲያው ሞተ" ብላ እንዲት ያገር ተወላጅ አሮጊት ሴት እንደ ነገረቻቸው በርሷም አመልካችነት ዐፅሙን ሰብስበው ባንድ በተለየ ስፍራ አከማችተው ድንጋይ ቀልለው ስሙንም እንደ ጻፉበት ይኸው ጸሐፊ ያመለክታል ።[1]

፯ኛው. በኮንቲ ሮሲኒ መጽሐፍ ውስጥ ከዊልድና ከካፒ ቶላ መጻሕፍት የተገኘ ተብሎ እንደሚቀጥለው ተጽፏል ።

ጄኔራል ዳቦርሚዳን የገደለው ባሻ ገብሬ ይባላል ። ባሻ ገብሬ ራሱ እንደ ተረከው ፣ ከዓድዋ ሁለት ሰዓት ያህል ሒዶ ብዙ ውሃ በሚፈስበት አጠገብ ቁጥራቸው ትንሽ የሆነ ኢጣልያኖች ሲዋጉ አገኘ ።

I La Battaglia d' Adua Scritta . . . ,A. Pollera,



ከነርሱ መካከል አንድ ሽምግል ያለ የወርቅ መነጽር ያደረገ በቀኝ እጁ ሽጉጥ ይዞ ነጭ ሻምላውን በወገቡ እንዳንጠለጠለ ይታይ ነበር ። በርሱ አጠገብ መድፍ ከተጫኑ ከሦስት በቅሎዎች በቀር ሌላ የጭነት ከብት አልነበረም ። ይኸም ሽማግሌ ወደርሱ የሚቀርበውን እየተኰሰ በመጨረሻ ሦስት የባሻውን ጓደኞች ገደለ ። በርሱም (ገብሬ) ላይ በተኰሰበት ጊዜ ተገን ይዞ ዳነና መልሶ ተኩሶ ሽማግሌውን መታው ። የጥይቱ በትርም ከትከሻው በታች አልፎ በግራ ጡቱ ወጥቶ ገደለው ። ባሻ ገብሬ ከዚያ ወደ ሬሣው ሒዶ ከገፈፈው በኋላ የወርቁን መነጽር ለንጉሡ ሰጠና የቀረውን የግሉ ወረቀቶች ያሉበትን የኪስ ቦርሳውን አዲስ አበባ ይዞት መጥቶ ታይቷል ። ይኸንንም ቃል ዊልድና ቶላ የሚባሉት ፈረንጆች የሰሙት በቀጥታ ከገዳዩ ከባሻ ገብሬ አንደበት ነው ። በተለይ ቶላ የኪስ ቦርሳውንም አይቶታል ። 1

ኮሎኔል ኤሚሊዮ ቤላቪታ ለጄኔራል ዳቦርሚዳ የልፍኝ አስከልካይ ነው ። በጦርነቱ ጊዜ አብሮ ዘምቶ ሳለ ፣ የጄኔራል ዳቦርሚዳን ፍጻሜ በምን አኳኋን እንደሞተ አያውቅም ።ከጦርነቱ በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ፤

. . . የኛ መድፈኞች ባደረጉት የውጊያ ተግባር የድል ተስፋ አሳድረውብን ነበር ። . . . በ13 ሰዓት (7) ዳቦርሚዳ አያያዛችን መልካም ነው የሚል ወሬ ለባራቲዬሪ እስከ መላክ ደርሶ ነበር ። ዳሩ ግን ፣ በዚህ ጊዜ ባራቲዬሪ ወደኋላው ሸሽቶ ስለነበረ መልእክቱ አልደረሰውም ። ይሁን እንጂ ፣ ወዲያው ውጊያው ተፋፍሞ በኛ ስፈር የሚሞተውና የሚቆስለው እየበረከተ ሔደ ። እስከ 15(9) ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ጠላት ከአለበት ጉብታ ሆኖ ሊመለከተንም ፣ ሊቆጥረንም ስለቻለ በጥሩ ዓይነት እያስተካከለ በሩምታ የሚተኩሰው ጥይት አንድም የተቃና ቁርጠኛ ሥራ ለመሥራት አላስቻለንም ። . . . ሽማግሌው ኰሎኔል አይራጊ ቆስሎ በሚደማው ፈረሱ ላይ ሆኖ በፉከራና በግለት ጭፍሮቹን ለማዋጋት ሦስት ጊዜ እየወጣ እስከ 10 ሜትር ድረስ ወደ ጠላቶቹ እየቀረበ ሲያዋጋ ጠላት እንደልቡ ወታደሩን ያጭደው ጀመር ።

በዚያን ጊዜ ፣ ጄኔራል ዳቦርሚዳ ጭንቅ ገባው ። ወደኔም ፊቱን አዙሮ የሌሎቹን የብርጌድ ጦሮች ወሬ ማጣት እንዴት መጥፎ ነው አለኝ . . . እኔም ወሬ ለመፈለግ ሔድኩ . . . ከዚህ በኋላ ጄኔራል ዳቦርሚዳ አንድ ጊዜ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ራሱ የተረፈውን ጦር እየመራ ወደ ጦርነቱ ተመልሶ ለመግባት ኰሎኔል አይራጊንና ሌሎቹን የጦር መኰንኖች እንዳስከተለ የራስ ቁሩን በእጁ ወደ ሰማይ ዘርግቶ "ሳቮያ" እያለ ደጋግሞ በመጮህ ፈረሱን አስጋልቦ ወደ ጦርነቱ ሲገባ ፤ ሁሉም ተከትሎት ገባ. . . ሁሉም አንድ ባንድ እየተመቱ ቀድሞውኑ በደም አቀላው መሬት ላይ ተረፈረፉ . . . መድፈኞቻችንም ሁልጊዜ እንደ ተምበረከኩ በተቻለ መጠን በመድፍ ተኩሰ አገዙ ።

1 Italia ed Etiopia . . . PP. 445—446. Li Italiani in Africa—a Del Boca—pp. 683—690.

> . . . ነገር ግን ሼዎቹ ከያለበት እየተኛጐደጐዱ ስለ ወረዱና ማጥቃታ
> ቸውን ስላጠነከሩ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። በዚያን ጊዜ ዳቦር
> ሚዳ ሌላ የምናቀርበው ተጠባባቂ ጦር እንዳለ ጠይቆኝ አለመኖሩን
> ባስረዳው ወደኋላ መመለስን (ሽሽትን) አዘዘ . . ጄኔራሉ ፊቱ አዝ
> ኗል ፤ መናገርም አልቻለም. . . በሽሽት ጊዜ በመንገድ ሰው ሁሉ ተጨ
> ናንቆ አንዳንድ ሬሳና ቁስለኛ እየረገጠ የሚያመልጥ ግማሾቹ ለሁለት
> ወይም ለሦስት የጋማውን ከብት የተቀመጡ አንዳንዶቹ በራሳቸው
> መሔድ ያቃታቸው የከብቱንም ጭራ እየጐተቱ የሚራመዱ ነበሩ ።
> በዚህም ጊዜ ከኋላ እየተተኮሰበት አንዳንዱ ይወድቃል . . . ቀበሌው
> ሁሉ በጠላት ቁጥጥር ውስጥ ስለሆነ ፥ ሁሉም ራሱን ለማዳን በሚሸሽ
> በት ጊዜ ወደኋላ የነበረው ጄኔራሉ (ዳቦርሚዳ) ጠፉ ።. . . እኔም ወደ
> ኋላ ተመልሼ ብፈልገው አጣሁት ። ሼዎቹም ለድሉ እርግጠኛ ስለሆኑ
> ጥይት ስላለቀባቸው ይሁን ወይም ስለደከማቸው የማሳደዱን ነገር
> ትተው ሬሣና ቁስለኛ ይገፉፉ ግማሾቹም ምርኮኛ ይሰበስቡ ጀመር ።
> ጊዜው መሸ ። ከዚያ እንደምንም በየሸለቆው የሞተውን ፥ ከፉኛ የቆሰ
> ለውን አልፈን 300 የምንሆነው በመጋቢት 4 ቀን (እ.ኤ.አ.) አዲ ቀይህ
> ገባን ። 1

ስለ ጄኔራል ዳቦርሚዳ አሟሟት ከጦርነቱ በኋላ ተማርኮ አዲስ
አበባ የነበረው ጄኔራል አልቤርቶኒ ለቤተሰቦቹ በጻፈው ማስታወሻ
ላይ ፥ "የጄኔራል ዳቦርሚዳን በጦርነቱ ላይ መሞት የራስ ሚካኤል
ሹማምንትና በኋላም ራስ መኰንን ከአድናቆት ጋር እንዳረጋገጡለት ፥
የሰላሙ ውል ከተፈጸመ በኋላ ፡ ምኒልክ ሻምላውንና ያንገት መጠምጠ
ሚያውን 'ለቤተ ሰቡ ስጥለት' እንዳሉት ፥ ስለአሟሟቱ ደግሞ ወደ
ማታ መቶ ከሚሆኑ ተራፊ ጣልያኖች ጋር ባንድ ጉብታ ላይ ሆኖ
እየተታኮሰ በጠላቶቹ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ቱርክ ባሻ (ታምሬ) ከኋላ
ካለው ከፍተኛ ቦታ ሆኖ አነጣጥሮ ከመታውና ከጣለው በኋላ
ሮጦ ሔዶ እንደ ገፈፈው ፥ ጥሩ አድርጎ ፈረንሣይኛ የሚናገረው ግራዝ
ማች ዮሴፍ አጫወተኝ" 2 ሲል ያረጋግጣል ።

በዚህ ዐይነት ፥ የዳቦርሜዳ ገዳይ በትክክል መጠሪያ ስማቸው ባይ
ጠቀስም ቱርክ ባሻ ታምሬመ ሆናቸው ነው ። ምናልባት በኮንቴ ሮሲኒ
ጽሑፍ በስሕተት ባሻ ገብሬ ያለው ቱርክ ባሻ ታምሬ ለማለት
ይሆናል።

---

1 Adua, E.Bellavita, PP. 380—390.

2 Lettere e Diari . . . P.80 .





በዓድዋ ጦርነት ላይ የሞተው ጄኔራል ዳቦርሚዳ

ከማዙኮኒ

# ምዕራፍ ዐርባ ሦስት

## የዳግማዊ ምኒልክ ከጦሩ ግንባር ወደ ሠፈር መመለስ

ከዋናው የዓድዋ ጦርነት ወዲህ እስካሁን በዝርዝር የተመለከት ነው ፤በጽሑፍ ማስረጃ እንደልብ የሚገኝበትን የኢጣልያኖችን ወገን ነው ። ምንም እንኳን ሰነድ ያነሰና የተበታተነ ወይም በዘመኑ ተዘርዝሮ በመታተም በደንብ ለጊዜያችን ያልተላለፈ ቢሆንም ፣ በመጠኑ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ ግራዝማች ዮሴፍና ነጋድራስ አፈወርቅ በየመልኩ የተዉልን ማስታወሻ መሠረታዊ ሰነድ ነው ። በተለይ የንጉሠ ነገሥቱ አስተርጓሚ የነበሩት ግራዝማች ዮሴፍ በጦርነቱ ቦታ ተገኝተው ለሞንዶን ቪዳዩ በራፖር መልክ ያስተላለፉት ጽሑፍ ከዚያ በፊት ያልታተመ በመሆኑ በመጠኑ ዝርዝር አሳብ ስላለበት በታሪክ ፊት ጠቃሚነቱ ግልጽ ነው ።

በዚህ ሰነድ ውስጥ ግራዝማች ዮሴፍ ፣ በመሠረታዊውና በታሪካዊው ጽሑፍ ውስጥ አገራቸው ትግሬ መሆኑንና የደጃች አርአያ ዘመድ መሆናቸውን ጭምር ጠቅሰው ማዣር ሳልሳን ለእርቅ ከአሥመራ ወደ እንትጮ ሲመጣ ከፊታውራሪ ደሳለኝ ጋር ሔደው መቀበላቸውን ያረጋግጣሉ ። እኚህ ሰው ከቀድሞ ጀምሮ ዐፄ ምኒልከን ባስተርጓሚነት ያገለገሉ ከመሆናቸውም በላይ ፣ ከወንድማቸው ከጊዮርጊስ ንጉሤ ጋር ወደ አሰብና ወደ ኤደን እየተመላለሱ በመሣሪያ መሰብሰቢያው ጊዜ ሲሠሩ ቆይተው እንደዚሁም በውጫሌው ውል በተነሣው ሰፊ ክርክር ሁሉ ከራስ መኰንን ጋር ተካፍለዋል ።

እኚሁ ሰው ራስ መኰንን ፣ የኢጣልያን አገር የጐበኙ ጊዜ ከተከታዮቻቸው ውስጥ ብዙዎቹ በዘመኑ አነጋገር የራስ ሎሌዎች ሲሆኑ ፣ ግራዝማች ዮሴፍ ብቻ በቀጥታ ያፄ ምኒልከ አስተርጓሚና ሎሌ ናቸው ።

አሁንም ግራዝማቹ ፣ በጦርነቱ ሰዓት ከንጉሠ ነገሥቱ ምን ጊዜም ሳይለዩ በዋናው ሥራቸው ባስተርጓሚነቱ ላይ የጦርነቱን ሁኔታ እየጻፉ ፣ አዲስ አበባ ላሉት ለነሞንዶን በማስተላለፍ በነርሱም አማካይነት በፈረንሣይኛ ጋዜጣ እንዲታተም ማድረጋቸውን ከመቀጠል አላረፉም ። ከዚህ በፊት እንደ ጠቀስነው ፣ የርሳቸው ጽሑፍ በኛ ዘንድ ያሰው ጠፍቶ ሊገኝ የቻለውም የጻፉለት ሙሴ ሞንዶን አዲስ አበባ

በነበረበት ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱና ከየመኳንንቱ የተጻጻፉባቸውን ደብዳቤዎች በማጓጓዝ አጠራቅሞ ከኢትዮጵያ ከወሰዳቸው ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ለፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የሰጠውና በቁጥር 82 ተመዝግቦ የተቀመጠው ነው ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ካህናትና ሴቶች ሳይቀሩ ባንድነት አስተባብረው ኢትዮጵያውያንን ባንድ እግር አቁመው ፣ በአገር ወራሪ ፊት አሰልፈዋል ። ቀኑን ሙሉ በማዋጋት ይኸን ዓለም የተደነቀበትን ድል ባገኙበት ማታ ወደ ሰፈራቸው ሲመለሱ ፣ አዲ ፈቂ ጕታ ላይ ወጥተው በእንዳ ሰንበት ቤተክርስቲያን ገብተው ይኸን ድል ለሰጣቸው እግዚአብሔር ምስጋና አቅርበዋል ። አዲ ፈቂ በእንዳ ኪዳነ ምሕረት በመነክሲይቶ ተራራ መካከል የሚገኝ ነው ። የአዲ ፈቂም ተራራ ከባሕር ከፍታው 2062 ሜትር [1] ነው ። ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ወደዚህ መሔድን የመረጡት ምናልባት ጦርነቱ የተደረገው የካቲት 23 ቀን እሑድ ስለሆነ ፣ የአዲ ፈቂ ቤተ ክርስቲያን እንዳ ሰንበት (የሰንበት ቤተ ክርስቲያን) ስለሆነ ፣ 'ዕለተ ሰንበት የለቱ ስት ቀናኝ' በሚሉ እምነት ይሆናል ።

ከዚያ ወርደው ሠራዊቱ ፣ "እየገደለ ሰጠው ላሞራ! " እያለ በሆታ እያጀባቸው ፣ በደስታና በእልልታ ወደ ሰፈራቸው ደረሱ ። ወደ ድንኳናቸው ገብተው በዙፋናቸው እንደ ተቀመጡ ፣ ጦርነቱን እንደ ወንድ በትጋት የተካፈሉት የሚወድዋቸው ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ በኢትዮጵያ ልማድ ለዠግና ፣ ለገዳይ እንደሚደረገው ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ተቀመጡበት ዙፋን ቀርበው ፣ እጅ ነሥተው የድል አድራጊነት ምልክት የሆነውን የወርቅ ሎቲ በዦሮአቸው አንጠለጠሉላቸው [2] ።

በማግሥቱም ፣ በዓድዋና በአክሱም ዙሪያ ያሉ ካህናት ለድሉ በዓል ተሰብስበው ነበርና ምሪቱ በቅድሚያ ለአክሱም ካህናት ስለ ተሰጠ ፣ ካህናቱ ከድኅ ውስጥ "ሞያ ለሞት በዓሮ ለጣኦት ወገብረ ትንሣኤ በሰንበት" [3] የሚለውን ጥቅስ ገሥው አዜሙ ። ምስማከም "አንተ ቀጥቀጥኮ አርእስቲሁ ለከይሲ ወትሁቦሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ" የሚለው ከዳዊት መዝሙር ተዘመረ ።

1 Guida deil' Africa Orientale, P.224.
2 Storia di Etiopia ,Conti Rossini, P.449
3 የድጓው ትርጉም "ሞትን አሸንፈ ጣኦትንም ሻረ ፣ በሰንበትም ትንሣኤ አደረገ" ተብሎ ለጌታችን በጳውሎስ የተነገረውን ለምኒልክ ለማውረስ ነው ። ጢሞቴዎስ ምዕ.1 ቁ. 10 ፣ ዕብ.2 ቁ. 14



በአዲስ አበባ ገና የጦርነቱ ወሬ ሳይሰማ ውጊያውና ድሉ በተፈጸመበት ቀን የጊዮርጊስ ለት የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ መምህር ጽጌ የሚባሉት ሊቅ የተቀኙት መወድስ ቅኔ እንደ ትንቢት ሆና ተደንቆላቸዋል ። ቅኔው ታሪካዊ ስለሆነ እንደሚከተለው አስፍረነዋል ።


በሕፅነ ምኒልክ ይረፍቅ ሰማዕተ ልዕልና
ወበሕፅነ ሰማዕት ይትሐወስ አበረ ምኒልክ ላዕክ
እስመ እም ሮምያ ፈተተ አድባረ ድንጋጼ ወሀውከ
ምኒልክ ንጉሠ አድኅና ዘኢየር መልአከ
ወእግረ ምኒልክ ኢይትሐወከ
እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔ ፍኖት ወልደ አምላከ
ቡርክትሂ ገነተ ጽጌ እስመ ውእቱ ቡሩክ
ዓለመ ምኒልክ ቀዳማዊ ዘይመጽእ ምኒልክ
ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ
በጽባህ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ መሥዋዕተ ሠርክ[1]

በሙሉ ሁሉን መተርጐሙ ምንም ያህል ስለማይጠቅም ፣ ከሙሉው እንዳንዱን ፍሬ ነገር ግዕዝ ለማያውቁ እናብራራለን ። አምስተኛውና ስድስተኛው ሐረግ ፣ "ወእግረ ምኒልክ ኢይትሐወክ ። እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔፍ—ኖት ወልደ አምላከ" "መንገድ ጠራጊው ወልደ አምላክ በፊቱ ስለሚሔድ ፣ የምኒልክ እርምጃ አይደናቀፍም" ማለት ነው ። ወልደ አምላክ የራስ መኰንን የክርስትና ስም ስለሆነ ፣ መኰንን ግንባር ቀደም ጦር አዝማች እየሆኑ በአላጌና በመቀሌ እየተዋጉ ለንጉሠ ነገሥቱ የጦርነት ጉዟቸውን ያቀኑትን ለመጥቀስ ነው ።

ከሁሉ የቅኔ ሐረጎች የመጨረሻው መስመር ፣ "በጽባህ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ መሥዋዕተ ሠርክ" "የሮማ ጥፋት እንደ ዕለት መሥዋዕት በጧት ቀርቧል" ያሉት ለባለቅኔው እንደ ደንበኛ ትንቢት ተቆጥሮላቸዋል ። በእርግጥም ግንባር ቀደም ሆና በጧት ግሥጋሤ ደርሶ የተማረከው የጄኔራል አልቤርቶኒ ጦር የተመታውና የኢጣልያ ጦር ቅስሙ የተሰበረው ከጧቱ ላይ ስለሆነ ፣ "በጽባሕ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ . . ." ብለው የጦርነቱ ዕለት የጦርነቱን ወሬ ኀይሰሙ የተቀኙትና በተግባር የተፈጸመው በትክክል ተገናኝቷል ። አዲስ አበባም እንደገቡ ዐፄ ምኒልክ ይኸንኑ ሰምተው ሸልመዋቸዋል ይባላል ።

1 መጽሐፈ ቅኔ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 255

## የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት የተዋጋበትን የዓድዋንና የአካባቢውን ሠፈር የሚያሳይ ሠሌዳ




ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፤— ጸ ፡ ት ፡ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ፡ ምዕ ፡ 62—63 ገጽ 242—268
ITALIA ED ETIOPIA CC. ROSSINI. PP. 344—447 GLI ITALIANI IN AFRICA— A. DEL BOCA. PP. 649—691

# ምዕራፍ ዐርባ አራት

## በዓድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱትና የቆሰሉት

የኢትዮጵያውያንን ዠግንነት ፣ አንዳንዶቹ ጣልያኖች ሲያደንቁ አብዛኞቹ በከንቱ ለማስተባበል ይሞክራሉ ። ሲጽፉም የተገላቢጦሽ የነርሱን የተሸነፉትን አንዳንዱን የጦር መኰንናቸውን ፣ "በዠግንነት ተዋግቶ ሞተ ! አገሌን የመሰለ አርበኛ በሚያስደንቅ አኳኋን እየተዋጋ ወደቀ" ሲሉ ፣ የኢትዮጵያውያንን ዠግንነት ግን ፣ "እንደ አውሬ እየተጯጯሁ መጡብን ፣ ፊት ለፊት ጉራዴ መዘው ከመድፋችን ላይ ሲወድቁ ዐይን የላቸውም" በሚል ማጥላላት ባለበት አነጋገር ሲገልጹ ይፈልጋሉ ። በጥቁሮቹ በኢትዮጵያውያን ዠግንነት ተሸነፍን ማለትን በመሰቀቅ የተሸነፉበትን ሰበብ ወደሌላ አቅጣጫ እየመሩ ፣

፩ኛ. የዠኔራል አልቤርቶኒ ግንባር ቀደም ጦር በፕላን የተመደበለትን ሥፍራ አልፎ ስለዘለቀ ፤

፪ኛ. አልቤርቶኒ በሚዋጋበት ጊዜ ሌሎች ዳቦርሚዳና አሪሞንዲ ለየራሳቸው ድልን በመመኘት ለእርዳታ ሳይደርሱለት ስለቀሩ ፣

፫ኛ. ከአገር ተወላጅ በቁጥር የሚበልጡት የነጭ ወታደሮች በተለይ በቅርብ የመጡት በማያውቁትና ወጣ ገባ በሆነ መንገድ በሌሊት ጉዞ ሰውነታቸው ስለደከመ ፣

፬ኛ. በወታደር ቁጥርም ፣ የኢጣልያን የወታደር ቁጥር የኢትዮጵያ አራት ጊዜ ስለሚበልጠው እያሉ ልዩ ልዩ ምክንያት መስጠታቸውን ባለፈው ተመልክተነዋል ።

በጦርነትም ሆነ በስፖርት የውድድር ሜዳ የተሸነፈ ወገን ፣ ሁልጊዜም ምክንያት አያጣምና ሊያስደንቅ አይገባም ። ቢያሸንፉ ኖሮ ይኸ ሁሉ አሁን የተሰጠው ምክንያት ይቀርና ሌላ የዠግንነት ልዩ ቀለም እየተሰጠው ድል የማድረጉ ዝና ከበቂ በላይ በተጋነነ ነበር ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ በቁጥር የኢትዮጵያ ወታደር ቢበልጥም በዝግጅትና በጠቅላላ የጦር ትምህርት ዕውቀት ኢጣልያኖቹ ስለሚበልጡ ፣ በቁጥር ማነሳቸውን ያላቸው ሥልጣኔ ሊክሰው በቻለ ነበር ።

ቢሆንም ብዙ የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ከጀኔራሎቻቸው ጋር በጀግንነት እየተዋጉ መሞታቸውን ማንም ሊክድባቸው አይገባም ። በዓድዋና በአካባቢው ፣ በየሜዳውና በየሸለቆው የተረፈረፈው ሬሣ ራሱ ምስክር ነው ። ዠግና ከሁለቱም ጦር ሠራዊት ውስጥ መኖሩን ሳንዘነጋ ፣ ይኸን ስመ ጥር ድል ያወረሱን ያባቶቻችን ዠግንነት ምንጊዜም የሚረሳ አይደለም ። በውጊያው ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተካፋይ ሆኖ የሕይወቱን መሥዋዕትነት በመክፈል አንጸባራቂ ድል አግኝቷል ።

እያንዳንዱ ጀግና ግዳጁን በጥንቃቄ ባያከናውን ኖሮ ይህ አኩሪ ድል ባልተገኘ ነበር ። ከሞቱትና ከቆሰሉትም ውስጥ የማናውቃቸው ስለሚበዙ ፣ ስማቸውንና ዠብዷቸውን ለትውልድ ለማስተላለፍ ብንመኝም አልሆነልንም ። ቀድሞውን በዘመኑ በማስታወሻ ስላልተላለፈና በዚያን ዘመን ጦርነቱን የተካፈሉት በሕይወት ስለሌሉ እንደዚሁ መቅረቱ ያሳዝናል ። በዠግንነት ከሞቱት መካከል ያንዳንዶቹን በተለይ የመኳንንቱን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በተዉልን መጽሐፍ ላይ ስማቸውና አሟሟታቸው ባጭሩ የተጠቀሰው ከዚህ ቀጥለው ያሉት ናቸው ።

ሀ/ ደጃች በሻህ አቦዬ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ደፋር ይባላል ። የዐፄ ምኒልክ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽ ልጅ ፣ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ፣ የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስና የደጃች ሰማ አቦዬ ወንድም ናቸው ። ባገልግሎት ከወንድማቸው በኋላ ፣ ንጉሥ ከተባሉት ከራስ ወልደ ጊዮርጊስና ከነራስ መኰንን አያንሱም ። ምናልባት እነዚህ ዝንባሌያቸው ወደ አስተዳደር ጭምር ሲሆን ፣ በሻህ መንፈሳቸው ፍጹም ወታደራዊ ይመስላል ። ታናሽ ወንድማቸው ወልደጊዮርጊስ ራስ ሲባሉ የርሳቸው በደጃዝማችነት መቆየት ሰበቡ ይኸው ይሆናል ።

በ1870 ዓ. ም. ዐፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ዐፄ ምኒልክን ለማስገበር የመጡ ጊዜ ካፄ ምኒልክ አሽከሮች ጠና ጠና ያለው ፣ “ዛሬ ዐፄ ዮሐንስን በጦር ትጥቅ እንችልምና አሁን ገብረን እኛም ወደፊት መሣሪያ ሰብስበን በሚመች ጊዜ እምቢ እንላለን” ሲል ፣ እንደ በሻህ አቦዬ ያሉት ጉበዛዝቱ የጦር መኰንኖች “እንበለው!” እያሉ ይፎክሩ ነበር ። በፉከራም ጊዜ ፣ “ካፄ ዮሐንስ ጦር ሃምሳ ባለሰናድር ማርኬ እመጣለሁና ተዋሰኝ” የሚል ኖሯል ። በዚያው ሰሞን የዕርቁን ጉዳይ ለመጨረስ ደጃች ናደው በሚመላለሱበት ጊዜ ደጃች በሻህ አቦዬ ያፄ ዮሐንስ ሠራዊት በሜዳ ላይ ሲጓዝ አይተው እልህ ይዟቸው ፣ “በማን አገር ሜዳ እንዲህ ሆነህ ትጓዛለህ” ብለው በፈረስ ጋልበው ሔደው አንድ ባለ ቀሚስ ገድለው ተመለሱ ። በዚህም ምክንያት ፣ “ለሃምሳ ሰናድር



ዋስ የጠራችሁ ፣ በሻህ አቦዬ ከፈለላችሁ” ተብሎ በስንኙ ሞት ተገጥሞላቸዋል ።

ከነራስ ጉበና ፣ ከነራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር ዳር አገሩን እያቀኑ በግራኝ ወረራ ምክንያት ተነጣጥለው በየባላባቶቻቸው እየተገዙ ይኖሩ የነበሩትን እውራጃዎች እንደገና ለማዋሐድ ዐፄ ምኒልክ በሚያደርጉት ዘመቻ እርሳቸውም ከመጀመሪያዎቹ ጋር ሆነው የከፋንና የጌራን ሕዝብ በማሳመን ወገን ከወገኑ እንዲደባለቅ አድርገዋል ። በዚሁ ምክንያት ፣ ደጃች (በኋላ ንጉሥ) ወልደ ጊዮርጊስ ሲሙን ፣ ደጃች (ራስ ቢቶደድ) ተሰማ ናደው ኢሉባቦርን ሲያስተዳድሩ ፣ ደጃች በሻህ አቦዬ ጌራና ከፋ ተሰጥቷቸው ነበር ። ስለዚህ የደጃች በሻህ አቦዬ አንዱ ጉብዝናቸውን የሚያመለክተው በዚያን ዘመን ከነበሩት ከደጃች ኃይሌ እንዳርጋቸው ጋር በማመሳሰል ፣ “ከጉበዞቹ የምናውቃቸው በሻህ አቦዬ ፣ ኃይሌ እንዳርጋቸው” ተብሎ የተገጠመላቸው ነው ።

የበሻህን ሞት እቴጌ ጣይቱ ሰምተው በሐዘን እንዳስቀሱላቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጠቅሰው ከዚሁ በማያያዝ ስለደጃች በሻህ አቦዬ አሟሟት ፣ “ታላቅ የመኰንን እርበኛ የንጉሠ ነገሥቱ ያክስትዎ ልጅ ደጃዝማች በሻህ የፈረሱ መሪ አባ ደፋር ተብሎ በውነት ስሙ የተጠራው . . . ካልጋ ወርዶ ከበቅሎ ላይ ፣ ከበቅሎ ወርዶ ከፈረስ ላይ ሆኖ ተቀማጥሎ ያደገው ባለመጣብር ፈረሱን ሐያ ሁለት ቃዳ መሬት የሚራመደውን ለጓሚ* ይዞበት ባንድ ወገን ሔደ ። በእግሩ ሲሮጥ የወታደር ፈረስ ተውሶ ከአባራሪ ላይ ወደቀ” [1] ሲሉ በራሳቸውና በዘመኑ አነጋገር ገልጸውታል ።

ስለዚህ ፣ ጦርነቱ እንደ ተጀመረ ከመድፉና ከጠበንጃው ተኩስ ብዛት የተነሣ ግርግር ሆኖ በግርግሩ ላይ የጭናቸውን በመጣብር ያጌጠውን ፈረሳቸውን የያዘው አሽከር ባንድ ወገን ሔዶ ስለጠፋ ፣ በግራቸው ሲሮጡ አንድ ወታደር ምናልባትም ከጭፍሮቻቸው አንዱ ሊሆን ይችላል ፣ ፈረሱን ሰጥቷቸው በርሱ ላይ ተጋብተው እያባረሩ ጠላትን ሲወጉ ተመትተው ወደቁ ። ተዋግተው የሞቱት ከጀኔራል አልቤርቶኒ ጦር ጋር በአምባ ኪዳነ ምሕረት ላይ በተደረገው ጦርነት ነው ። በርሳቸው ሞት የተናደዱ ጭፍሮቻቸው በቁጭት ብዙ የኢጣልያ ምርኮኛ ገደሉ ይባላል ።

---

* ለጓሚ ማለት በቅሎ ወይም ፈረስ እየሜኒ ፣ እያራገፈ ፣ እየቀለበ የሚኖር ተከታይ አሽከር ነው ። ከዛሬው የመኳንንት ሹፌር ጋር ሊመሳሰል ይችላል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 266

ለ/ ከደጃች በሻህ አቦዬ ጋር በዚሁ ቀንና ስፍራ በጀግንነት ተዋግተው የሞቱ የጉላው ገዥ ደጃዝማች ሚጫ ናቸው። የርሳቸው የጀግንነት አኳኋት ባጭሩ እንጂ ዝርዝር የለንም። ሲዘምቱ የጉላን ጦር ይዘው ነው የዘመቱት፣ በዘመኑ የጉላ ጦር አስፈሪ ነበር። ሠፈሩ አዲስ አበባ የጉላ ሠፈር የሚባለው ነው። እርሳቸውም የነደጃች ተሰማ፣ የነደጃች ብርቄ አባት ናቸው። በአገልግሎት ዕድገት ያገኙ የመናገሻ እርሞ ናቸው ይባላል። ጉላ በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የሚገኝ በዚያን ጊዜ ባለነጋሪት ደጃዝማች የሚሾምበት ታላቅ ወረዳ ነበር።

ሐ/ ደጃች በሻህና ደጃች ሚጫ በሞቱበት የጦር ግንባር ስመ ጥሩው የንጉሡ የጦር አበጋዝ ፊታውራሪ ገበየሁ አባ ጎራ ሞተዋል። እርሳቸውም ዐፄ ምኒልክ ሐረርጌ ከአሚር አብዱላሂ ጋር ከዘጠኝ ዓመት በፊት በ1879 ዓ.ም. የተዋጉ ጊዜ ሻቃ ገበየሁ እየተባሉ ጦርነቱን ተካፍለዋል።

በ1881 ዓ.ም. ሻቃ ገበየሁ የሰናድር ያዥዎች ሹም እንደ ነበሩና በውስጣቸው የሚያዙት ጦር ቁጥሩ 3000 እንደነበረ በጣልያኖች የባሕር መዝገብ (ሊብር ቬርዴ-ቅጠልማ መጽሐፍ) ተጽፎ ይገኛል።[1] በግዛት አንድ ጊዜ አማግርትን፣ ሌላ ጊዜ የጉራጌን አውራጃ ተሹመው አስተዳድረዋል። የትውልድ አገራቸው ተጉለት ነው ይባላል። መቃብራቸውም እንጉለላ ኪዳነ ምሕረት ነው።

በዚህ ዓመት አላጌ ላይ በተደረገው ጦርነት ዋናው የድሉ ባለቤት እርሳቸው እንደነበሩ በዚያው ምዕራፍ ላይ አመልክተናል። የመቀሌውንም ጦርነት በደንብ ተካፍለዋል። እንዲያውም ራስ መኰንን የዕርቅ ነገር በሚነጋገሩበት ጊዜ ገበየሁ እየተዋጉ ስላስቸገሩ፣ እንደ አላጌው እንዳይዋጉ ራስ መኰንን አስረዋቸው ሳለ፣ በኋላ ላይዋጉ አስምለው እንደ አስለቀቋቸው ከኢጣልያኖቹ ወገን የተጻፈው መጽሐፍ ያረጋግጣል።[2] ከብዙ ጦርነት በኋላ፣ በስምምነት ጋልያኖ ጦሩን ከምሽግ ይዞ ወጥቶ በራስ መኰንን ሠፈር አጠገብ እርሱና ሹማምንቱ የሰፈሩ ጊዜ፣ "የአላጌውን የሐበሻ ጀግና የፈረንሣይ ጋዜጠኞች በጣም ያወደሱትን ፊታውራሪ ገበየሁን አይተውታል"[3] ሲል ማንቴጋዛ የሚባለው ጸሐፊ ጠቅሶታል።

ፊታውራሪ ገበየሁ፣ የዓድዋ ጦርነት ለት በምን አኳኋን እንደ ሞቱ ኢጣልያዊው ጸሐፊ፣ "በእምባ ኪዳነ ምሕረት ላይ ጢት ከጀኔራል

1 Assedio di Maccalle. V. Mantegazza, P.260
2 Italia ed Etiopia P.P. 242—243
3 Assedio di Maccalle . . ., 413.



አልቤርቶኒ ጦር ጋር በተደረገው ውጊያ የኢጣልያኖቹ መድፍ ክፉኛ ባጠቃበት ሰዓት ወታደሩ ማፈግፈግ ቢጀምር ለወታደሩ "ወደ ሸዋ የሚመለሱ፣ የአላጌው ጀግና ፊታውራሪ ገበየሁ በምን አኳኋን እንደሞተ ይናገሩ" ብሎ ጮኸ። "እንደ አንበሳ ተወርውሮ በጦርነቱ ላይ ገባ። በዚያን ጊዜ በመትረየስ ተመትቶ በ3 ሰዓት ላይ ወደቀ" ያለውን እናስታውሳለን። ከዚሁ አያይዞ ከመሞቱ በፊት ጭፍሮቹ አንሥተው አንድ ቁጥቋጦ ውስጥ ከበውት እንደ ነበረ የተማረከው ኢጣልያዊ የጦር መኰንን ቴኔንቴ ካሩሶ የሚባለው ባበሾቹ እጅ እንደ ተያዘ ማየቱን አመልክቷል።[1]

ስለገበየሁ አኳኋት ጆቫኒ ቴዶኒ የሚባለው የጦር መኰንን፣ ተማርኮ እስከ አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ የነበረው በጻፈው ማስታወሻ ላይ በበኩሉ ከላይኛው አባባል በትንሹ ለየት አድርጎ እንደዚህ ይላል። "... በቢያንኪኒና በማሶቶ *በሚመሩት መድፎች እየተመቱ አበሾቹ ወደኋላ ሲያፈገፍጉ አይቶ፣ ፈሪ ሁሉ እንዴት ትሸሻላችሁ፣ እኔ እንዴት እንደምሞት ለንጉሡ ሒዳችሁ ንገሩ ብሎ ፈረሱን ባለንጋ በትር አስነሥቶ በግልቢያ በሚዘንመው የመድፍ ጥይት መካከል ገባ። እርሱን ሲያይ ሁሉም እየሮጠ ተከትሎት ገብቶ ከመድፈኞቹ ጋር ተጨፋጭፎና ገድሎ መድፎቹን ማረከ። የገበየሁ ሬሳ ከወደቀበት ቦታ የኛዎቹም የጀግኖች ሬሳ አብሮ በመውደቅ የርሱን ሬሳ አከበረው" በዚያው ሰሞን ምርኮኛ በመሆን በንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር ሳለ ባይኑ እንዳየው፣ ስለገበየሁ ሰው ሁሉ ያለቅስ እንደነበረ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ከሞት የተረፈው በያለቃው ተሰልፎ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሲያልፍ፣ የፊታውራሪ ገበየሁን የተጫነ በቅሎ የገዛ ወጣት ልጁ ይዞ (ተቀምጦ) ሲያልፍ ምኒልክ አይተው ማልቀሳቸውን ያረጋግጣል።[2]

ስለዚህ፣ የአላጌውን ምሽግ በመስበር በኢጣልያ ላይ የመጀመሪያውን የድል ደወል ያሰሙት፣ የመቀሌን ጦርነት በመካፈል እጃቸው የቆሰለው፣ አበጋዙ ፊታውራሪ ገበየሁ አባ ጉራ የዓድዋ ለት ወደር በሌለው ጀግንነት ላገራቸው ነጻነት፣ ለሚወዷቸው ንጉሠ ነገሥት ክብርና ፍቅር ሲሉ ሕይወታቸውን ሠውተዋል። በዚያን ጊዜም፣ "የዐድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው" ተብሎ ተገጥሞላቸዋል።

መ/ ፊታውራሪ ተክሌ የወለጋው ገዥ ያፄ ምኒልክ ልጅ የደጃች

1 Italia ed Etiopia . . .,PP. 251, 368—369.
* Pianchini & Masotto የሚባሉት ሁለቱ የመቶ አለቆችና የመድፈኛ ክፍል ሹማምንት ናቸው።
2 Riccordi di un Prigioniero di Menelik, Giovanni Tedone, PP.142—143

አስፋው ወሰን ሞግዚት የነበሩት ናቸው ። እንደነፊታውራሪ ገበ
የሁ ላሄ ምኒልክ የቆዩ የጦር መኰንን ናቸው ። በ1881 ዓ.ም. ሜጫን
ይገዙ እንደነበረ በኢጣልያኖች ማስታወሻ ይገኛል[1] ። የወሰጋ ገኘ
ሳሉ በዐዋጁ መሠረት ጦራቸውን አስከትተው አዲስ አበባ ከገቡ
በኋላ ፣ በራስ መኰንን ጦር ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው የአላጌን ጦር
ነት ከነፊታውራሪ ገበየሁ ጋር ተካፍለዋል ። የዓድዋ ጦርነት ዕለትም
እንደነፊታውራሪ ገበየሁ ጧት በተደረገው ውጊያ ላይ በዠግንነት
ወድቀዋል ።

ሠ/ ቀኛዝማች ታፈሰ ዓባይነህ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ትንታግ
ነው ። በዓድዋ ዘመቻ ዕድሜያቸው 25 ዓመት ነበር ። በዕድሜ ወጣት
ቢሆኑም ዠግንነታቸው ከፊታውራሪ ገበየሁ ጋር በመጠኑ ተመሳሳይ
ነው ። በግዛታቸው በግረቆ ሲኖሩ በአደን ስመ ጥሩ ስለነበሩ ወደ
አዲስ አበባ በመጡ ቁጥር የዝሆን ቀንድ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርቡ
እንደ ነበር ፣ በውጊያ ጦርጦራ ወታደር ፣ ለሁሉ ሥራ ከተፎ ሥል
ጡን ስለነበሩ ላስቸጋሪው ሥራ ሁሉ ዐፄ ምኒልክ “ታፈስን ጥሩ”
ይሉ እንደነበር ፣ ብርታታቸውንና ጠንካራነታቸውን እያዩ “ይሞትብ
ኛል” እያሉ ንጉሠ ነገሥቱ እጅግ አጥብቀው ይሳሱላቸው እንደነበረ
ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል ። በአላጌ
ጦርነት በከፍተኛ ዠግንነት እንደ ተካፈሉ ተመልክተናል ። በዚሁ
ጦርነት ሃምሳ የሚሆኑትን ጣልያኖች ባንድ ጕራዴ እንደ ጨፈጨፉ ፣
አንድ ላይ ቆመው የተኮሱት አይር (ቀለህ) እንደ አርበጫ (ኩይስ
ቁልል) እንደ ተቆለለ ፣ በአሁኑ በዐድዋ ጦርነት ሰሞን መነጽር ይዘው
ከጭፍሮቻቸው ጋር ወደፊት እየዘለቁ በየተራራው ላይ ሆነው የኢጣ
ልያኖችን ከምሽግ መውጣትና አለመውጣት ቃፊር ሆነው በመጠባበቅ
አንዳንድ ጊዜም በርከት ብሎ ከወጣ የነጭና የባሻ ብዙቅ ወታደር
ጋር ተገናኝተው በመዋጋት ግዳይ ላሄ ምኒልክ ይጥሉ እንደነበረ
ጸሐፌ ትእዛዙ አመልክተዋል ። ከዚሁ አያይዘው የኢጣልያኖቹን
ከምሽግ መውጣት በመጀመሪያ ለንጉሠ ነገሥቱ በፈረስ ጋልበው
ያስረዱ እርሳቸው እንደነበሩ ከገለጹ በኋላ ፣ የዓድዋ ጦርነት ለት ስለ
አሟሟታቸው እንደዚህ ብለዋል ። “አድኅ ያልጨረሰው ቀኛዝማች
ታፈስ እንኳን ሰውና የውድማ ዝሆን ሲፎክር ድምጡን ሲሰማ ይጨ
ነቅ የነበረው ተኩሶ ሲጥል በጕራዴ ሲመታ ፣ ከሁለተኛው ሰልፍ
ሰማዕታ ከሚባለው አገር ሲደርስ ክንዱን ቆሰለ ። በቆሰለም ጊዜ አሽ
ከሮቹ እንግዲህ ከጥላ ሥር እናሳርፍህ አሉት ። እርሱ ግን ለኢጣልያ
ወታደር እንዱ እጄ ይበቃል ብሎ ሲያባርር ከዚያ ላይ ወደቀ. . .”

1 Assedio di Maccalle . . . P.260.



በማለት ጽፈውላቸዋል[1] ።

በዚህ ዓይነት ቀኛዝማች ታፈስ አባይነህ ተዋግተው የሞቱት ፣
በረዓዮ ተራራ በማይ እጋምና በሰማዕታ በኩል ከዘመተው ከዠኔራል
አሪሞንዲና ከተጠባባቂው ከዠኔራል ኤሌና ጦር ጋር በተደረገው
ውጊያ ላይ ነው ። ተመትተው የወደቁትም ከሰማዕታ ጉብታ አጠገብ
መሆኑ ነው ። ቀኛዝማች ታፈስ ዓባይነህ የልዑል ራስ እምሩ አጐት
ያባታቸው የደጃች ኃይለ ሥላሴ ታናሽ ወንድም ናቸው ።

ረ/ ፊታውራሪ ዳምጠው ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ሸኘው የራስ
ደስታና የማዦር ዤኔራል አበበ ዳምጠው አባት ናቸው ። በ1881
ዓ.ም. እነፊታውራሪ ገበየሁ ሻቃ እየተባሉ ሰናድር ያዥን ሲያዙ ፣
እርሳቸው ባላምባራስ ተብለው የፈረሰኛ ዘበኛ አለቃ ነበሩ ። በኋላ
የፊታውራሪነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

እንደ ጸሐፌ ትእዛዝ አጻጻፍ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠው ሲዋጉ የሞቱት
በዚሁ ቀኛዝማች ታፈስ በሞቱበት የጦር ግንባር በሰማዕታ ጉብታ
ይመስላል ። ተዋግተው የሞቱትም ከመስኮብ በተመለሱ በዐሥረኛው
ወር ምንም የዕረፍት ጊዜ ሳያጣጥሙ በዙረት ላይ እንዳሉ ማለት
ነው ።

በተረፈ ከነዚህ በቀር በዓድዋ ጦርነት ሕይወታቸውን የሠዉት
ከየመጽሐፉ የተለቀሙት ቀጥለው ያሉት ናቸው ።

፩/ ደጃች ማን እየ የፈረስ ስማቸው አባ ባሕር ፣ ቀድሞ የደጃች
አመንሸዋ የጦር አዛዥ ነበሩ ። ደጃች አመንሸዋ ሲሞቱና
ጦራቸው ለራስ መኰንን ሲሰጥ ፣ እርሳቸውም ወደ ራስ
መኰንን ዞረው ባሄ ምኒልክ ፈቃድ ደጃዝማች ተብለው
ጨርጨርን ይገዙ ነበር ።[2]

፪/ ፊታውራሪ ወልዴ ሚካኤል የሜታው ባላባት የፊታውራሪ
ገረሡ ልጅ ፣

፫/ ቀኛዝማች አባይነህ የቀኛዝማች ታፈስና የደጃዝማች ኃይለ
ሥላሴ አባት ፣

፬/ ቀኛዝማች ተገኘ ወርቅ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የታወቁ
ዠግና ፣

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 267 ።
2 ቼ በለው ፣ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ፣ ገጽ 28 ።

፭/ ፊታውራሪ እምባዬ ከዓድዋ በፊት በማይ መሬት ጦርነት የሞቱ፣
፮/ ቀኛዝማች ተሰማ ወልዴ፣
፯/ ፊታውራሪ ሸንኮሩ የደጃች በሻህ ጭፍራ፣
፰/ ባላምባራስ በለው፣
፱/ " እደራ፣
፲/ " ሰይፉ፣
፲፩/ አቶ ሙላቱ የፈረስ ዘበኛ።

የካቲት 23 ቀን ከማለዳ ጀምሮ እስከ አኩለ ሌሊት በቀየው በዚህ ጦርነት የሞቱት ብዙዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። በንጉሥ ተከለ ሃይማኖት፣ በየራሶቹና በየደጃዝማቾቹ ውስጥ ሆኖ ዘምቶ የሞተውና የቆሰለው ብዙ መሆኑ ሲታወቅ ከሰነድ ጥፋት የተነሣ፣ ስማቸውን በዚህ የታሪክ መጽሐፍ ላይ ለማንሣት አለመቻሉ ያሳዝናል።

ከዚህ ጋር ደግሞ፣ ካፒቴን ክሉቤት የሚባል የፈረንሳይ ተወላጅ በበጅሮንድ ባልቻ ውስጥ ሆኖ በመድፍ ኢጣልያኖችን በመውጋት ኢትዮጵያን የዓድዋለት ማገልገሉን ልናስታውስ ይገባል። እርሱም በፈረንሣይ ጦር ሠራዊት ውስጥ በመድፈኛ ክፍል ሳለ፣ ላፄ ምኒልክ ገብቶ በጦር ትምህርትና በሌላውም በብዙ ወታደር ነክ ጉዳይ ሲመክርና ሲያገለግል የቆየ ነው። በጦርነቱ ዋዜማ ዓመቱን ሁሉ ወታደሩን የጠመንጃና የመድፍ አተኳኮስ ሲያስተምር ነበረ ይባላል። በኋላም ጦርነቱን ለመካፈል አልጋውን ከሚጠብቁት ከራስ ዳርጌ ተሰናብቶ ከአዲስ አበባ ወደ ጦሩ ግንባር መጥቶ የካቲት 22 ቀን ደረሰ። በማግሥቱ ሲዋጋ ውሎ ከድሉ በኋላ በተራው እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ መኰንን ባፄ ምኒልክ ፊት ሲፎክር የተማረኩት ኢጣልያኖች አይተውታል።

ጆቫኒ ቴዶኒ የሚባለው ምርኮኛ የጦር መኰንን በጻፈው ውስጥ ስለ ካፒቴን ክሉቤት እንደዚህ ይላል። "...በ6 ሰዓት በንጉሡ ድንኳን ፊት እኛ እስረኞቹ ስናልፍ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን በራፍ ላይ እግሩን አጣምሮ የተቀመጠ ጠጉሩ ወርቅማ (ብሎንድ) ... እኛን በንቀት እያየ የሚስቅ ነጭ አየሁ።..."[1] ብሏል።

በተረፈ በዓድዋ የወደቀውና የቆሰለው የኢትዮጵያ ወታደር ከነመኳንንቱ ቁጥሩ በትክክል አይታወቅም። ግራዝማች ዮሴፍ አዲስ

1. I Riccordi di un Prigioniero, G. Tedone, P. 44; IL Generale Salsa; E. Ganevari P. 97.



አበባ ላሉት ለሙሴ ሞንዶን ሲያስተላልፉ፣ የሞቱትን ቁጥር 3867 አድርገውታል። እነኮንቲ ሮሲኒ ከብዙ የኢጣልያ መጽሐፎችና ከቃል ጥያቄ ለቅመው የሞቱትን ቁጥር ከ5 እስከ 7 ሺ ከፍ ሲያደርጉት፣ ግማሾቹ ከ7 እስከ 10 ሺ አድርሰውታል። የቁስለኛውንም ልክ ወደ ሟቾቹ ቁጥር የሚያደርሱት አሉ። ሚስተር በርክሌ የሚባሉት እንግሊዛዊ የሟቾቹን ኢትዮጵያውያን ቁጥር 7ሺ፣ የቁስለኛውን ቁጥር 10 ሺ አድርሰውታል።[1]

ንጉሠ ነገሥቱ፣ ከመሳፍንቱ፣ ከመኳንንቱና ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰፈራቸው ከተመለሱ በኋላ በተገኘው ድል ምንም እንኳን ደስታ፣ ቢደረግ ስለሞቱትና ስለቆሰሉት በደስታው ጐን ሐዘን፣ ዋይታና ለቅሶ፣ እንደ ተደረገ የታወቀ ነው። በማናቸውም ድል አድራጊ አገር እንደሚደርሰው የንጉሠ ነገሥቱም የሁሉም ደስታ በሐዘን የተበረዘ ነው ማለት ይቻላል። ወደ ሰፈር መልስ ከሆነ በኋላ፣ ከማግሥቱ ዠምሮ ንጉሠ ነገሥቱ በያለበት የወደቁትን የኢትዮጵያውያኑን ሬሣ እያስለቀሙ ሲያስቀብሩ፣ ቆስሎ የወደቀውን ወይም በቃሬዛ ከየክፍል ጦሩ የመጣውን ሁሉ በመድኃኒት ሲያሳክሙ፣ በየመንደሩም እያሳደሩ ሲያስታምሙ፣ በየጦሩ ጐራ በየአለበት የተበታተነውን የጠላት መድፍና ጠመንጃ፣ ጥይትና ቀለህ ሲያሰበስቡ ሰነበቱ። ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌይቱ ዠምሮ ሁሉም በዕብሪተኛው ጠላት ላይ በተገኘው ድል የተደሰተ ቢሆንም ከታወቁት አርበኞች ከነገበየሁ፣ ከነታፈስ ጋር በጠቅላላው ቁጥራቸው እስከ 7 ሺ የሚደርስ ከመኳንንት፣ ከሹማምንትና ከተራ ወታደርም ስለሞተው ወገኑ፣ ሁሉም ማዘኑ የታወቀ ነው።

ይህን አስመልክተው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ "ከስልፍ ላይ ስለቀሩት እጅግ አጥብቆ ሐዘን ሆነ" ካሉ በኋላ፣ እልፍ ብለው "ንግሥቲቱ እቴጌ ጣይቱ ስለ አሽከሮቻቸው፣ ስለ ወዳጆቻቸው፣ ስለ ክርስቲያኑ ማለቅ መራራ ሐዘን አዘኑ። ብርሃን የመሰለ ፊታቸው አጥላስ (ጥላት) እስኪመስል አለቀሱ ... ነገር ግን፣ እንደ ተሹሱ ብዛት፣ እንደቀኑ ርዝመት፣ ሰው ሞተ ብሎ ያዘነ የለም። ባሏም፣ ልጅዋም፣ ወንድሟም የሞተው እንኳን አልጋው ቀመልን ነው እንጂ፣ ባሌ ልጄ ወንድሜ ሞቱብኝ ብሎ ያዘነ የለም"[2] ሲሉ ገልጸውታል። ያዘነ የለም ማለታቸው ያንጋገር ፈሊጥ ወይም ከሐዘኑ የተገኘው ድል መብለጡን ለማመልከት ነው እንጂ፣ ሐዘኑማ ሐዘን መሆኑ አይቀርም። በሐዘኑ ላይ ግን፣ የድል አድራጊነትና የነጻነት ደስታ ተበርዞ ሐዘኑን አቀዝቅዞታል ማለት ነው። እነዚህ ሁሉ አልቀው ድሉ ባይገኝ ኖሮ ሐዘኑ ከመራራ ደረጃ ላይ ይደርስ ነበር።

1 Italia ed Etiopia ... P. 452, G.F.H. Berkeley PP. 346—347
2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ—ገ.ሥ. ገጽ 257—268

# ምዕራፍ ዐርባ አምስት

## የኢጣሊያ ጦር መፍረስና ቅጥ ያጣ ሽሽት

ቁጥሩ ሐያ ሺ የሚደርሰው ባንድ ሌተና ጄኔራልና ባራት ማዦር ጄኔራሎች የተመራውና ጦርነት የጠማው ፣ ሰላም ያንገፈገፈው የኢጣልያ ጦር እነሆ ባዼ ምኒልክ የጦር ሠራዊት ተመትቶ ፍርስርሱ ወጣ ። የሞተው ሞቶ የተረፈው ሸሸ ። ከአልቤርቶኒ ጦር የተረፈው ወደ ሳውሪያ ፣ ከዳቦርሚዳና ከአሪሞንዲ ጦር የተረፈው በዱሃና በመሬት ማይ በኩል አድርጎ ፊቱን ወደ መረብ ፣ ወደ አዲ ቀይህ ፣ ወደ አዲግራት ፣ ወደ አሥመራ መለሰ ። በየበኩሉ ቅጥ ባጣ መንገድ እየተዝረከረከ በቁስል እየተሰቃየ ፣ ረኃብና ጥም ፣ እርዛትና ድካም እያንገፈገፈው እየወደቀና እየተንገዳገደ ከመንዝ ላይ ይገኛል ።

ጣልያኖቹ ፣ ለድሉ በፍጹም እርግጠኞች ከመሆን የተነሣ ፣ "ምናልባት የተሸነፍን እንደሆነ እዚህ ቦታ ተገናኝተን በዚህ መሥመር እየተከታተልን ወደ መጣንበት እንመለሳለን" የሚል ከጠቅላይ አዛዡ የተሰጠ ምንም ዐይነት ፕላን አልነበረም ። የጦርነቱ አመራር ራሱ ከፕላን ውጭ ሆኖ እንደ ተዘባረቀ የሽሽቱ ነገርም ከዚያ የበለጠ ተበላሽቶ ብዙ ወታደር በየፊናው ሲሔድ ፣ የኢትዮጵያ ወታደር እየደረሰ በጥይትና በጐራዴ ሲያተራምሰው ባላገር በበኩሉ እየተቀበለ በዱላና በሽመል እየመታ የገደለው ብዙ ነበር ።

ጄኔራል አልቤርቶኒ ፣ በቅድሚያ ሲማረክ ፣ ጄኔራል አሪሞንዲና ዳቦርሚዳ በጦርነቱ ሜዳ ላይ ሞተዋል ። የተጠባባቂው ጦር አዛዥ ጄኔራል ኤሌናና ዋናው ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ ብቻ አምልጠው ወደ አዲ ቀይህ አመሩ ። እነርሱም በየጦሩ ሜዳ ድል አድራጊው ጦር እያዋከበ መምጣቱን ተመልከተው ለጊዜው ባጋጣሚ አጠገባቸው ከተገኙት ጋር ተመካከረው የጦርነቱን ፍጻሜ ሳያዩ ፣ "ከመከበባችን በፊት እናምልጥ" ብለው ሸሹ ። ጠቅላይ አዛዡ ፣ የጄኔራል አልቤርቶኒን መማረክ ፣ የሁለቱን ጄኔራሎች ማለትም የዳቦርሚዳንና የአሪሞንዲን መሞት አያውቅም ነበር ። የራሳቸው የኢጣልያኖቹ የታሪክ ሰነድ እንደሚያመለክተው ፣ እጦር ግንባር ከቀረበው 17,000 ወታደር ውስጥ ወደ አሥመራና ወደ አዲግራት ሸሽተው ነፍሳቸውን ያዳኑት

258 መኮንኖች ፥ 4666 የነጭ ፥ 4,000 የጥቁር ወታደሮች ናቸው[1] ። በርክሌይ በጠቅላላው የሞተውን የነጩንም ፥ የጥቁሩንም ቁጥር በድምሩ 6133 አድርጎታል[2] ።

ከኢጣልያኖቹ ትራፊ ጦር አጋማሹ አባራሪውን ለመከላከል እንዲመቸው ባንድነት ተሰብስቦ ሲጓዝ የቀረው ተበታትኖ ። ባንድነት ያለውንም ፥ እየተበታተነ ይጓዝ የነበረውንም ፥ አባራሪው ወታደርና ባላገር በጠበንጃም በዱላም እየመታ ብዙ መጨረሱን ባለፈው አንብበናል ። ወታደሩም የካቲት 22 ቀን ለ23 አጥቢያ ሲጓዝ አድሮ የየካቲት 23ትን የውጊያ ቀን የተካፈለ በመሆኑ ፥ ለየካቲት 24 ቀን አጥቢያ ባለው ሌሊት ለመሸሽ ድካም ፥ ረኃብና ውሃ ጥም ስላጠቃው የቆሰለም ስላለበት ፥ የሽሽት ጉዟቸው ለኢጣልያኖቹ የጻዕርና የመከራ ሽሽት ነበር ማለት ነው ። ከጦርነቱ አገማመርና አፈጻጸም የዚህኑ የሽሽት ሁኔታ ከኛ ወገኖች ይልቅ ፥ ከበራሪዎቹ አንዱ የጦር መኰንን የዓድዋ ጦርነት በሆነ በዐሥራ አራተኛው ቀን ከምጥዋ ለናቱ የጻፈላት ደብዳቤ ሁኔታውን በትክክል ያስረዳል ።

የምስግድልሽና አስደሳቿ የኔ እናት*

ከሁሉ በፊት በእግዚአብሔር ፊት እንስገድ ። ከሞት ተርፌ ሕያው የሆንኩት በተአምራት ነው ። የካቲት 29(22) ቀን ከማታው በ10 (4) ሰዓት ጠመንጃና ጥይት ትንሽ የተፈጨ የቆርቆሮ ሥጋ ብቻ ይዘን የቀረውን ሁሉ ትተን እንድንጓዝ ትእዛዝ ስለመጣ ፥ በሦስት በኩል በሦስት አዝማች ተከፍለን ጉዞ ጀመርን ። እኔ የነበርሁት በዳቦርሚዳ ውስጥ ነበር . . . የተወጠነውም አሳብ በድንገት በጠላት ላይ ደርሰን አደጋ ለመጣል ነበር ። በዚህ ዓይነት ከማታው 10(4) ሰዓት ጀምረን እስኪነጋ 7(1) ሰዓት ድረስ ተጉዘን ስለ ደረስንና ስንደርስም ገና ድሮ ፀሐይ ስለወጣ ፥ በድንገት ደርሶ ጠላትን የማስደንገጡ ነገር ሳተ ። መንገዱ ድንጋይማ ደረቅ ወሃ የሌለበት . . . ስለሆነ ሠራዊቱ እየደከመ ወደቀ ።

በ7 ሰዓት ከ14 (ባንድ ሰዓት ከዐሥራ አራት ደቂቃ) ላይ በቀኝ በኩል ተኩስ ስለ ተሰማ ፥ ጠላታችን ያለበት የመሰለን በግራ በኩል ነበርና ሁላችንም ተደነቅን . . . ቢሆንም በስንት ድካም የአፍሪካ ፀሐይ እያቃጠለን ጉዟችንን ቀጥለን በግራና በቀኝ ተራራ ወዳለው ሥፍራ ደርሰን ወደ ተራራው ለመውጣት ስላልቻልን ፥ በሥሩ ቆመን ሳለ በፊታችን በቀኝ በኩል ግሩም የሆነ አስደናቂ የጥይትና የመድፍ ተኩስ ይሰማን ነበር ። ወዲያው ከፊታችን የአልቤርቶኔ ጦር በሙሉ

1 Italia ed Etiopia . . . PP. 447—448.

2 The Campaign of Adwa . . . Chap. XII, PP.335—368.

* በኢጣልያንኛ «Mammina Mia, Adorata, Diletta» ይላል ።



እየሸሸ ሲመጣ ተመለከትነው ። ተጥሎም በድንገት የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደ መጋረጃ ሆነው ከያለበት ፈልቀው በፊታችን ያሉትን ሁለት ተራሮች እየተሽቀዳደሙ ያዙዋቸው ። ተጥሎም እየፎከሩ እየተጯጯሁ እየተኰሱ በላያችን ላይ የጥይት በረዶ አወረዱብን ። ግማሾቹ ተደብቀው ስለሚተኩሱም ልናያቸውና ልንተኩስባቸው አልቻልንም ። ጥይታቸውም ጭስ የለውም ። ስለዚህ ከነርሱ በሚተኰሰው ጥይት የኛ ወታደሮች እንደ ዝንብ ይረግፉ ጀመር ። ቢሆንም ጣልያኖቹ መልሰው መታኰሳቸውን አልተዉም ።

ከዚህ በኋላ የባታዮው ወራችን ወደኋላ አፈግፍጎ የጉብታ ሥፍራ ለመያዝ አሰበ ። ነገር ግን በጥይት ተከበን ስለነበረ ፥ በተነቃነቅን ቁጥር የጥይቱ መዓት ስለሚወርድብን ምንም ማድረግ አልተቻለም . . . ይሁን እንጂ ፥ እንደ ምንም ብለን ከወገኖቻችን ተለይተን ወደ ጉብታው ደርሰን ተገን ይዘን ትንሽ እንዳረፍን . . . ወዲያው እነሱም እየተኰሱብን እኛም እየመለስን ስንተኩስባቸው በውጊያ እስከ 4(10) ሰዓት ቆየን ። . . . ከዚያ ሸሽተን ባንድ የሰንበሌጥ ግር ባለበት ሥፍራ ውስጥ ተደብቀን የሞቱትንና የተረፉትን ወታደሮቻችንን መቁጠር ጀመርን ። ከኔ ጋር በሙሉ ከነበሩት ከመቶ ዐሥራ ምስቱ ሰባ ብቻ ተርፈው አገኘናቸው ። ከነርሱም ብዙዎቹ ቆስለዋል . . . እኛ ሰባዎቹ ከዋናው የባታዮ ወራችን ተለይተን ብቻችንን በማናውቀው አገርና ስፍራ አንድ ጠብታ ውሃ በማይገኝበት ተገኝተን እንግዲህ ወዴት እንሒድ? ወይስ ምን እናድርግ? እያልን እንመካከር ጀመርን ። አለንበትም ስፍራ አጠገብ አንድ ከፉኛ የቆሰለ ማዦርና 6 በቅሎዎች አገኘን ። ከዚያ እኛ ሹማምንቱ እርስ በርሳችን ምክር ካደረግን በኋላ ፥ ወደ ምሥራቅ እንሻገርና ሰፈራችንን እናገኝ ብለን ውሳኔ አደረግንና ቁስለኞቻችንን በበቅሎ ጭነን ጉዞ እንደ ጀመርን በቅሎዎቹ አልራመድ ስላሉ ከኋላ እየደበደብን በመንዳት ጉዟችንን ቀጠልን . . . የቀሩት ቁስለኞች እያቃሰቱ ወዮ ወሁ እያሉ በኋላ ይከተሉን ነበር ። በድንገት ከኋላችን የጥይት ድምፅ ተከትሎን ስለተሰማ ቁስለኞቹ መራመዳቸውን ትተው አመሬት ላይ ተዘርረው ተኙ ። ተነሡ ብለን ብንቆጣም ፥ ብናባብልም አልሆነም . . . በዚህ ሰዓት እከፉ ሁኔታ ላይ መሆናችን ስለ ተሰማን እኔና ካፒቴኑ በየሽጉጣችን ለመገዳደል ተፈቃቀድን ። ነገር ግን ይህ አሳብ ወዲያው ከላያችን ተወገደና በብዙ ጭቅጭቅ የተኙትን ቁስለኞች አስነሣንና በዚያ በሾሃማና ጠጠርማ መንገድ ከኋላችን ተኩስ እየተከተለን ስንጓዝ ድንገተኛ ያልታሰበ ጥቁር ደመና በሰማይ ላይ ታየና ዝናም መዝነብ ጀመረ ። ዝናሙን አጠራቅመን የምንጠጣበት መግሪያ ስለሌለን፥ በዝናም የራሰውን ልብሳችንን እየመጠጥን ተጓዝን ። ሲመሽ ከማታው በ10(4) ሰዓት አንድ የለመለመ ስፍራ አግኝተን በዚያ ሰፈረን አደርን ። በዚያም ባደርንበት ጊዜ ጠላቶቻችን ጥይት እየተኰሱ ሁለት ወታደር ሁለት በቅሎ ገድለው ምስቱን ወታደሮች አቆሰሉብን ። ከሌተናዎቹ (ከመቶ አለቆቹ) አንዱ ከቁስለኛው ማዦርና ከዐሥር ወታደር ጋር ወደኋላ ደከመው ቀሩ . . . መረብ ወንዝ ደርሰን ዕረፍት አደረግንና . . . እንደገና ከሌሊት በ10(4) ሰዓት ተነሥተን . . . በመንገድም አንዳንድ ጊዜ መዋጋት ነበረብን ። ከኛ ጋር ካሉት ግማሹ ልብሱ አልቆ በውስጥ ሹራብ የሚሔድ ሜማው አልቆ በሸሚዝ ቁራጭ ወይም በኛሽ ሜማውን አስር ይሔዳል ። አንዳንዱም ደክሞት አልሔድ

ሲል እንዲራመድ በዱላ ስንደበድበው ወደኋላ ተሰይቶ እንዳይቀርም
ባላገር እንደሚገድለው ስለሚያውቅ የግዱን መራመድ ይጀምራል ።
እኛ ሹማምንቱ ወታደሮቻችን በግድ እንዲራመዱ ለመደብደብ
ጭካኔ አስፈልጎን ነበር ።. . . እንደዚሁ ባንድ ቦታ ውለን ስንጓዝ
ከጫካ ውስጥ ተተኩሶ አንድ ጓደኛችን ተመታ ። ሊድን የማይችል
መሆኑንም ስናውቅ ትንሽ ውሃ አጠገቡ ትተንለት ጥለነው ሔድን ።
ባንድ ስፍራ ስንደርስ በፊት ለፊት እሳት በብዙ የሚነድ አየን ።
የጠላት ሰፈር መሆኑንም የሚመራን ያገር ተወላጅ ስለ ተናገረ እጉብታ
ላይ ወጥተን መሣሪያችንን ጠምደን ተኛን ። ከዚያም በማግሥቱ የኛ
ዎቹ ወዳንድ መንደር ገብተው ስንቅ ሲፈልጉ ከባላገሩ ጋር ተዋጉና
ሦስቱ ሞቱ ። እኛም በሩቅ እየተኮስን ባላገሮቹን ብዙ እየገደልን አባ
ረርን ። ቢሆንም እንደገና ጉዞ ጀምረን የምንጓዝበት ሜዳ ውሃ የሌለ
በት ስለሆነ ውሀ ጥም እንደገና ያሰቃየን ጀመር ። ወታደሩም እየተኛ
ስላስቸገረን ተነሡና ተራመዱ ለማለት የኔም የራሴ ምላሴም ጉሮሮ
ዬም በውሃ ጥም ተዘጋና መናገርም አቃተኝ ።

የሆነ ሆኖ ፣ ውሃ እፊታችን እቅርብ አለ እያልን እያባበልን እስነ
ሥተን ሁሉም እያቃሰተና እያላዘነ ይጓዝ ጀመር ። ሲነጋ መጋቢት
5 ቀን (የካቲት 27 ቀን) አንድ የረጋ ውሃ አየንና እኔና ካፒቴን
ተሯሩጠን ተዘርግተን በብዙ ጠጣን ። ከጠጣንም በኋላ ከውሃው ጋር
የግመል ሽንት እንዳለበት ተረዳን ። ነገር ግን መቶ ሜትር እልፍ
ስንል ሌላ መልካም ውሃ ተገኘና ሁሉም እንደልቡ ይጠጣ ጀመር. .
በማግሥቱ ከሌሊት በ4(10) ሰዓት ጉዞው ቀጠለ ። የውሃ ጥም አሰቃ
የን ። በምናልፍበት መንገድ ለምለም ሣር ስለነበረ ከርሱ እየነጨን
እያኘክን እንደ እንስሳ ጐምጅተን ውሀውን እንመጥ ነበር ።. . .በመ
ጨረሻ አንድ ውሀ የተጠራቀመበትን ስፍራ ሲነጋ ስላየን ለውም
ከብቱም ወደዚያ እየተሯሯጠ ሔዶ ጠጣ . . . ሔደን ሔደን ባንድ ሜዳ
ላይ ስንደርስ የኢጣልያኖች ሬሣ እተረፈረፈበት ደርሰን ሁሉም ራቁ
ቱን የሆነ ግማሹ ሰውነቱን የተቆራረጠ ነበረበት ። ስንደርስ አንዱ
ከፉኛ ቆስሎ አልሞተ ኑሮ ተነሥቶ የጦርነቱን ሁኔታ ትንሽ አነጋገ
ረን . . . የነዚህን የዝግኖቻችንን ሬሣ ለአሞራና ለጅብ ትተን በሐዘን
አልፈናቸው ሔድን ። ሌሎች ያልሞቱ ሁለት ጣልያኖች ራቁታቸውን
ተነሥተው እየሮጡ ተከተሉን ። ከሁለት አንዳቸው በጣም ለሞት የቀ
ረበ መሆኑን ስለተረዳን ከውሃ አጠገብ ጥለነው ሔድን ። አንደኛው
ግን ጉዞውን ከኛ ጋር ቀጠለ . . . የኛ ሰፈር ወደ ነበረበት አቅራቢያ
ስንደርስ ደስ ብሎን ነበር ። ዳሩ ግን ዐሥር ቁስለኛ ያስከተለ አንድ
የ50 አለቃ (ሰርጀንት) አገኘንና ሰፈራችን ሁሉ በጠላት መያዙን ገለጸ
ልን ። የጦር ሠራዊታችን ሁሉ ወዴት ሔደ ብለን ብንጠይቀውም
“የፈረሰ ይመስለኛል” ብሎ ወዴት እንደሚገኝ አለማወቁን ስለነገረን
እኛ ሹማምንቱ እርስ በርሳችን እየተያየን የጦራችንን መፍረስ ተገነ
ዘብን ።

ከዚህ በኋላ ምን ይሻላል በፊታችንም በኋላችንም አበሾች አሉ ።
ለድላ የምንሆነው የደከምነው ሰዎች ከዚሁ ሐያ ቁስለኛ ስምንቱ
የጸናባቸው ሆነን ወዴት እንሔዳለን እየተባባልን ስንከራከር ቆይተን
ወደ ሰሜን 300 ኪሎ ሜትር እንደገና ተጉዘን አሥመራ ከመድረስ
በቀር ሌላ የደኅንነት መንገድ አለመኖሩን ብንረዳውም ይኸንንስ



ሰደከመ ጉልበት ያለስንቅ በጠላት አገር በተናደደና በሚዋጋን ባላ
ገር መካከል አልፈን እንደምን እንደርሳለን ከተባባልን በኋላ በርቱ
ተበረታቱ ልጆች ተባብለን ጉዞውን ጀመርን ። ስንጓዝ ውለን በ6(12)
ሰዓት አሁንም ጉዟችንን ስንቀጥል ከወደፊታችን ሰዎች ሲመጡ አየ
ንና ጠላቶቻችን መስለውን ለተኩስ ተሰናዳን ። በዚያ ጊዜ አንድ
ወታደር “የጦር መኰንን ነው” ብሎ (በኢጣልያ ቋንቋ) ስለጮኸ
መተኮሳችንን ትተን ብንመለከት ፣ በውነትም የጠፉትን ወታደሮች
ለመፈለግ ሲል ባላገርና ወታደር አስከትሎ የሚመጣ የአሜሊዮ ባታዮ
የጦር መኰንን መሆኑን ተገንዝበን ተያይተን ስንገናኝ እርስ በርሳችን
እንላቀስ ጀመር ። ከዚያ እነሱን አግኝተን በነርሱ እየተመራን የደከ
ምን የቆሰልን ብንሆንም ፣ እንዳማረብን ብረታችንን በትከሻችን እንደ
ያዝን ከ6 ቀን ጉዞ በኋላ ቁስለኞቻችንን ሳንተው (አሥመራ) ደረስንና
ቅልጥማችን እየተንቀጠቀጠ በዚያ ለነበረው ለማገሮር አሜሊዮ የብ
ረት ሰላምታ አቀረብንለት ። በዚያ ያሉት ነጮችም ጥቁሮችም እየተደ
ነቁ እያዩን ሹማምንቱም በላያችን በናፍቆት እየወደቁ ሳሙን ። ከዚያ
ደንበኛ ዕረፍት አደረግን ። እንደ ሕልምና ተረት የመሰለንን የኛንም
መብል (ሚኒስትሮኒ) አቀረቡልን . . .

ሲል የጦር መኰንኑ የሽሽቱን ሁኔታ በዚህ ዓይነት ዘርዝሮ ይደመድ
ማል[1] ።

ድንገተኛ አደጋ በመጣል የኢትዮጵያን ነጻነት ደምስሰው አገሬ
ቱን ለመውረር ፣ እንዲሁም በአላጌና በመቀሌ የደረሰባቸውን የወታደ
ርነት ውርደት ለማደስና የኢጣልያን መንግሥትና ሕዝብ መንፈስ
በኩራት እንመላዋለን ብለው የመጡት ፣ የኢጣልያ የጦር መኰንኖችና
ወታደሮች እነሆ እጦርነቱ ላይ የሞቱት የአሞራና የጅብ ራት ሲሆኑ፣
ጥቂቶቹ በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ተማረኩ ። የቀሩት ደግሞ ተዝ
ረከርከው ወደ መጡበት ተመለሱ ። ይህ ሁሉ ከመድረሱ በፊት ዐፄ
ምኒልክና የወንድም አገልጋያቸው ራስ መኰንን እርቅ ሆኖ በሰላም
እንዲመለሱ ምን ያህል ጣልያኖቹን እንደ ለመኑዋቸው ከዋናው
ከዓድዋ ጦርነት በፊት ባሉት ምዕራፎች በሰፊው ተገልጿል ።

እውነት ነው ፣ ጠላትን በማናቸውም ረገድ ለማጥቃት ሲሞከር
ሞራል ፣ ይሉኝታና ሐቀኝነት እንዳይገባበት ኒኮላ ማኪያቬሊ የሚባ
ለው የነርሱው ተወላጅ በፍልስፍና መንገድ አስተምሯል ። ሐቀኝነት
የማይወዱ የመንግሥታት መሪዎችም ሠርተውበታል ። ዐፄ ምኒልክም
የባራቲዬሪን ጦር ከምሽግ እንዲወጣ ያደረጉት በተንኮል መሆኑን አን
ዘነጋም ። ቢሆንም ሌሎቹ ለከዳታቸው ወይም ለተንኮላቸው ይሉኝታ

1 Lettere e Diari . . . PP. 92-99.

ሲበርዙበት ፡ ኢጣልያኖቹ ግን በፍጹም ተንኮል ይሠሩበት ነበር ። ነገር
ግን በተንኮልም ፡ በማታለልም ፡ በጦርነትም ቢመጡ ዐፄ ምኒልክና
መኳንንቶቻቸው ተንኮሉን በተንኮል ፡ ጦርነቱን በጦርነት መልሰው
ይኸን ትውልድን ለዘለዓለም የሚያኮራ ድል ሊያቀዳጁ ቻሉ ። በዚህ ድል
አድራጊነት ያገሪቱንም ነጻነት ከሚያኮራው የድል ክብር ጋር ለኛ
ለዛሬው ትውልድ አስተላለፉልን ። ለአባቶቻችን ኅብረትና ዠግንነት
ከፍ ያለ አድናቆትና ምስጋና መስጠት ይገባናል ። ይህ ከዚህ በላይ
ያየነው ከዳቦርሚዳ የጦር ግንባር የሸሸውን የጦሩን ሁኔታ ነው ። የሁሉም
ይነስ ይብዛ ይኸው ነው ። አንዳንዶቹ ግን ፡ ቀደም አድርገው ከጦር
ነቱ ቦታ ሽሽት የዠመሩት ባገር ተወላጅ ወታደርና ባንዳ እየተመሩ
በተሻለ ሁኔታ ሸሽተው ወደ ሰፈር ደርሰዋል ። ግማሾቹ ደግሞ በተለይ
ያገር ተወላጅ ወታደርና አንዳንድ የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ድሉ
እንደሳተ ቤተሰቦቻቸውና ሚስቶቻቸው ስንቅና ልብስ እየያዙ መጥ
ተው ከመንገድ እያገኙ የወሰዱዋቸው አሉ ።

በግራ በኩል በዤኔራል አልቤርቶኒ ውስጥ የባንዳ ጦር ይዞ
የተዋጋው ቲኤንቲ አሌሳንድሮ ሳፔሊ የሚባለው ከሞትም ፡ ከምርኮም
ተርፎ አገሩ ከገባ በኋላ በጻፈው ማስታወሻው ላይ ስለዚሁ መልስ ጉዞ
እንደዚህ ይላል ።

> . . .በጧት ከንቲባይ አብተ ማርያምን ይዠ በረዓየ ውስጥ አዲ
> ፈቂ ከሚባለው በር ደረስሁ. . .የማዠር ቱሪቶ ጦር ሲዋጋ የጥይቱ
> ድምፅ ይሰማን ነበር . . . ከዚያ የኛ ወታደር እየሸሸ ሲመጣ አየነው. . .
> የንጉሡ ነጋሪት ያለማቋረጥ ሲጐሸምና ሲያጓራ ይሰማን ነበር ። ባጠ
> ገቤ ያሉትም ሹማምንት የንጉሡ ነገሥቱን ዠንጥላ ሰይተው ያውና
> እያሉ ያረጋግጡ ነበር ። የኛዎቹ ምንም ቢከላከሉ የሸዋው ጦር እየተ
> ኸጐደጐደ መጣ ። ከዚያ ሁሉም ይሸሽ ጀመር . . . ከዚያ ሮጨ ሌላ
> ውን የባንዳ ጦር ወደሚያዘምተው ወደ ቲኤንቲ ሉካ ዘንድ ስሔድ
> እርሱና ጦሩ በሚዋጉበት ጊዜ ፊታውራሪ ተድላ ሞቶ ወንድምየው
> ባላምባራስ ምኒልክ ቆሰለ . . .* ከዚያ ግራና ቀኝ እንደ ተከበብን
> 'ተማረክ ተማረክ' የሚለውን ቃል በሚያጓራው የመድፍና የጠመንጃ
> ድምፅ መካከል እያዳመጥን ሽሽት ያዝን ። አንዳንድ ጊዜ የሚሸሸ
> ውን እንደ ምንም አቁመን ስንከላከል ፡ የሚያዋክቡን የጋላ ፈረሰኞች
> ጋብ ይሉ ነበር ። እነርሱም ከረዓየ እስከ እንኪሎ 'እንትጮ' ድረስ
> እያባረሩ ያዋክቡን ነበር . . .
>
> አንዳንድ ጊዜ እየተናደድሁ የሚሸሸውን አቁሜ ለማዋጋት
> እስከ መማታት ስደርስ ፡ በባንዳው ወታደርና በሕዝቡ ዘንድ ከበሬታ
> ያለው ደጃች ፈንታ 'በከንቱ አትድከም በራሪውን የሕንፃ ግድግዳ
> እንኳን አያቆመውም ፤ ድሮውኑ በሰንበት መዋጋት አልነበረብንም'

* የባንዳ አለቆች ።



> አለኝ. . .* ከዚያ ሸሽተን ሊነጋ ሲል በሰሳ ወንዝ እኩለ ቀን ሲሆን
> አዲ ቪአዲ ደረስን ። በዚያም የቀድሞ ወዳጄን የገበአቲ ጓንጉልን
> ወዳጆች አገኘሁ ። ለተረፉትና ከኔ ጋር ላሉት ወታደሮቼም እህል
> አገኘሁ ። ውሃ ግን በዚያ አቅራቢያ ስለጠፋ ወደ ቆሐቲት አመራሁ ።
> እዚያም ሳለሁ የተረፉ ባንዶች አግኝቼ ያለቃቸውን የቲኤንቲ
> ሉካን መሞት የዠኔራል ባራቲዬሪን ወደ አዲ ቀይህ መጓዝ ሰማሁ. . .
> ሁለት ሌሊት እንቅልፍ በማጣት በቀኑ ሽብር ሰውነታችን ደክሞ
> ዝሎ ሳለ ፡ ሰውነቱን ለማንቃት የሽንኩርት ቁራጭ ሁልጊዜ የሚያኝ
> ከው ይኸው ደጃች ፈንታ እንዳርፍ መከረኝ ላርፍ ስል ፡ አንዲት ሴት
> በፈረስ ሆና አንድ ወታደርና ሁለት ገረዶች አስከትላ ወደኛ ስትመጣ
> አየሁ ። ለካስ የኔው ሴት የሆነችው ወይዘሮ አምለሱ የጦሩን መፍረስ
> ወሬ ሰምታ ሞቼ እንደሆነ ለመቅበር ፡ ተማርኬም እንደሆነ ለማጽና
> ናትና ለመርዳት መጥታ ኖሯል ። ገረዶቿ የቆርቆር (ቧት) መብል
> መድኃኒት ሻሽ እርቧ ደግሞ በፈረቧ ኮርቻ ውስጥ እቤት የነበረ
> 200 ብር (ማሪያ ትሬዛ) ደብቃ ይዛ ኖሯል ። በዚህ ሰዓት የነበረኝን
> የግንኙነትና (ከርቧ ስንገናኝ) የስሜቴን መንቀሳቀስ አድናቆቴንና
> ባለውለታነቷን ልዘረዝረው አልፈለግሁም ። ሌሎች ደግሞ ሴቶች
> ባሎቻቸውን ለመርዳት የመጡ ነበሩ ። ብዙዎቹ ግን እንደ አምለሱ
> አልታደሉም ።. . .1 ይኸውም ሞተዋል ማለቱ ነው ።

* ደጃች ፈንታ በራስ አሉላ ውስጥ የታወቁ የጦር አለቃ ነበሩ ። የመተማንም ጦርነት ተካፍለዋል ። በኋላ ከኢጣልያኖች ጋር ግንኙነት አድርገሃል ተብለው ታስረው ሳለ ከዚያ አምልጠው ወደ ደጃች ደብብ ሔዱ ። ደብብ ከራስ አሉላ ጋር ተዋግተው ስለሞቱ ከራስ አሉላ ምሕረት አግኝተው ገብተውላቸው የዓድዋ ጉምሩክ ሹም ሆኑ ። በከዓቲትም በራስ መንገሻ ውስጥ ሆነው ከኢጣልያኖች ጋር ተዋግተዋል ። በኋላ ግን ኢጣልያኖቹ አሸናፊ ስለሆኑ ፡ ለነርሱ ታማኝ በመሆን የዓድዋን ጦርነት ከሳፔሊ ጋር ሆነው ተካፍለዋል ማለት ነው ።

1 Memorie d'Africa (1883-1906). A. Sapelli, PP.115-121.

# ምዕራፍ ዐርባ ስድስት

*ሴተና ዤኔራል አንቶኒዎ ባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ ምጥዋ እንደገባ—ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ስለ ዕርቅ ጉዳይ ወደ ምኒልክ እንደመጣ—ሴተና ሮቤርስ ባይኑ የተመለከተው የኢትዮጵያ ሠፈር—የዕርቁ ለጊዜው አለመሳካት*

ከንጉሡ ጀምሮ እስከ መሳፍንቱ ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ እስከ ተራው ሠራተኛ ፣ ከመከላከያ ሚኒስትሩ አንሥቶ እስከ ተራው ወታደር ድረስ የነበሩት ኢጣልያኖች ፣ ኢትዮጵያ በዚህ በምኒልክ አገዛዝ ወቅት የነበራትን ጠንካራ የውስጥ ሁኔታ ባለማወቅ ወይም ዐውቆ በመናቅ በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸው የመስፋፋት ምኞት ከፍ ያለ እንደነበር ተመልክተናል ። ዐፄ ምኒልክም ያን ያህል የሰላምና የእርቅ ነገር ደግመው ፣ ደጋግመው የፈተኑት ምንም የተደራጀ ጦር እንዳላቸው ቢያውቁም ፣ “እንሸነፍ ይሆን? በብዙ ድካም የተገነባው መንግሥታችን ፣ ብሔራዊ ግዛታችን መልሶ ይፈርስና ውርደት ያስከትልብን ይሆን” በሚል ሥጋት ውስጥ እንደነበሩ አይጠረጠርም ። ብዙ ጊዜ እንዳልነው ፣ ራስ መኰንን ኢጣልያን የጐበኙ ጊዜ የመንግሥቱ መሪዎች ሆን ብለው የወታደርና የመሣሪያ ድርጅታቸውን በጥንቃቄና በዝርዝር አሳይተው መልሰዋቸዋል ። ይህም ለጦርነቱ ሠግተው ንጉሡንም እንደሚያሠጉ በማመን ያደረጉት ይመስላል ። ጦርነቱ የተካሔደው በአንድ በኩል ለድል አድራጊነቱ ባልተጠራጠረ ፣ አሸናፊነቱን በተማመነ ፣ ራሱን ከፍ አድርጎ በኩራትና በትዕቢት ተወጥሮ የቅኝ ግዛት አምሮት ባሰከረውና በሌላው ወገን ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ ለድል አድራጊነቱ በሥጋና በግድ የእናት አገሩን ነጻነት ለመከላከል ብቻ ለውጊያ በቆረጠ ሕዝብ መካከል ነው ። ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በኩራትና በትምክህት ተመልቶ እስከ አላጌ ድረስ በግሥጋሤ የመጣውን ኃይለኛ የጠላት ጦር ፣ በሰላም እምቢ ያለውን በውጊያ እየጠረጉ እስከ ዓድዋ ዘልቀው በሰፈሩበት ሰዓት ፣ የኢጣልያ መንግሥት በባራቲዬሪ አማካይነት ፣ ዝናን ፣ የወታደር ክብርን የሚያድስ ፣ ሰፋ ያለ ግዛት የሚያወርስ ድል በጉጉት ተጠብቆ ድሉ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ ። ከዓድዋ ጦርነት ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ በሮማ ምክር ቤት በጥንቃቄ ምክር ተደርጎ በኢጣልያ የጦር ሠራዊት ውስጥ

ከፍተኛ ዝና የነበረው ከጄኔራል ባራቲዬሪ በደረጃም በችሎታም የሚበልጠው ሌተና ጄኔራል አንቶኒዮ ባልዲሠራ በኤርትራ ጠቅላይ አዛዥ ተብሎ ተሾመ ። ይኸ ሰው ከዚህ በፊት ኢጣሊያ እ.ኤ.አ. በ1888 ዓ.ም. ሰሜን ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር በነበረ ጊዜ ባራቲሪዬ በርሱ ውስጥ ኰሎኔል ነበረ ።

ባልዲሠራ ሲመጣ ፣ ደልማይና እና ሐሸ የሚባሉ ሁለት ሌተና ጄኔራሎች ፣ ቤዚስቲ ፣ ባርቢዬሪ ፣ ጋዜሬሊና ግዛ የሚባሉ አራት ማጆር ጄኔራሎች በውስጡ ሆነው ብዙ ጦር ይዘው እንዲዘምቱ ተወሰኗል ። ጄኔራል አንቶኒዮ ባልዲሠራ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቀበለው ትእዛዝ አሥመራ እንደ ደረሰ ፣ አዲስ ይዟቸው የሚሔደውን ከጄኔራል ሐሸ ጦር ጋር ቁጥራቸው ወደ ዐሥራ አምስት ሺ የሚደርሰውን ወታደሮች ኤርትራ ካሉት ሐያ ሺ ወታደሮች ጋር ደባልቆ ጠቅላላውን ቁጥሩን ሠላሳ አምስት ሺ የሚደርሰውን ሠራዊት ከሁለት ላይ ከከፈለ በኋላ ፣ አንዱን ክፍል ለሌተና ጄኔራል ሐሸ ሰጥቶ እርሱ የሁሉም የበላይ ሆኖ በግጥጋት ያጼ ምኒልክን ኃይል አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ሰባብሮ ኢትዮጵያን የመውረሩን ጉዳይ በቶሎ ወደ ፍጻሜ እንዲያደርስ ነው ። ባራቲዬሪ እስካሁን ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ አሁን በዚህ ዐይነት አልሠራም ያለ እንደሆነ ወደ ሮማ እንዲመለስ ነበር ።

ጉዳዩም ጄኔራል ባልዲሠራ ፣ አሥመራ ደርሶ በሥራ እስኪገለጸው ድረስ በጥብቅ ምሥጢር እንዲያዝና ጄኔራል ባራቲዬሪም እንዳይሰማ ጥንቃቄ ተወስዶአል ። በጋዜጦችና በደብዳቤዎች ላይ በኢጣልያም በኤርትራም ፖስታ ቤቶች ጥብቅ ቁጥጥር ተደርጓል ። አንዳንድ ጸሐፊዎች ባራቲዬሪ ምስጢሩን ከአንዱ ወዳጁ ተጽፎለት ስለተረዳው ባልዲሠራ ከመድረሱ በፊት ጦርነቱን ዠምሮ ተሸነፈ ይላሉ ። የሆነ ሆኖ ፣ በግናቸውም ረገድ በዚህ ዐይነት ከፍተኛ ድርጅት ባልዲሠራ ከኢጣልያ ተነሥቶ ወደ ምጥዋ በመርከብ በሚጓዝበት ጊዜ ባራቲዬሪ ጦርነቱን ጀምሮ ባለፈው ባነበብነው ዐይነት ተሸንፎአል ። በሽሽት ወደ አዲ ቀይህ ደርሶ የመሸነፉን ቴሌግራም ከአዲ ቀይህ ወደ ሮማ መጋቢት 3 ቀን እ.ኤ.አ. አስተላልፎ በማግሥቱ ወደ አሥመራ ለመሔድ ከአዲ ቀይህ ወደ ሰገነይቲ በሚጓዝበት በመጋቢት 4 ቀን በበኩሉ በሰፊ ፕላን ተዘጋጅቶ የመጣው ባልዲሠራ ነገሩን ሁሉ ሳያውቅ በዚሁ በመጋቢት 4 ቀን ምጥዋ ከገባ በኋላ የኢጣልያን ጦር የመሸነፉን መርዶ ሰማ ። በሐዘንም ወደ አሥመራ ተጓዘ ። የሚወደውንና የሾመውን የቀኙን ወገን የክሪስፒን መውደቅና የማይወደውን የግራውን ክፍል የዲሩ ዲኒን መሾም አሥመራ ሰምቶ አዲስ ትእዛዝ ይጠባበቅ ጀመር ። ከዓድዋ ድል በኋላ ‘ምኒልክ የማይሸነፍ ነው’ የሚል እምነት በኢጣልያ አገር በባለሥልጣኖች ላይ ስላደረ ፣ በፊት



እምቢ ያሉትን ዕርቅ አሁን በግድ ጠይቀው እንዲቀበሉ ሁኔታው አስገደዳቸው ። ስለዚህ ጄኔራል ባልዲሠራ የዓድዋ ጦርነት በሆነ በአራተኛው ቀን ምጥዋ ሲደርስ ካሳሰበው ሁኔታ ላይ ወደቀ ። ከምጥዋ ወደ አሥመራ የመጣ ጊዜ የኢጣልያ ጦር ዓድዋ ላይ ተሸንፎ ግማሹ በሞትና በምርኮ መፍረሱን ፣ ከምርኮና ከሞት የተረፈው በብዙ ሥቃይና መከራ ፊቱን ወደ አሥመራ አድርጎ መሸሹን ፣ አዲግራት ያለው አንድ ክፍል ጦር በነራስ መንገሻና በነራስ ስብሐት ጦር ተከቦ ብዙ የኢጣልያ ወታደሮች ተማርከው በቀናው የኢትዮጵያ ጦር እጅ እንዳሉና በርከት ያሉት ደግሞ በየቀበሌው በትግሬ ሹማምንት እጅ በምርኮኝነት መኖራቸውን ሰማ ። በተለይ ደግሞ ፣ “ቀናው ጦር ከኋላ ከእንትጮ ተጉዞ መረብን አልፎ ኤርትራን ለመውረር ይዘጋጃል ። ግንባር ቀደምና አሳሽ ሆነው እነራስ ስብሐት ፣ እነደጃች ሐጐስ በመሬት ግይ ወደ ደንጐሎ ፣ እነደጃች አርአያ ወደ ዳግር ተከሌ ያመራሉ” የሚለው ወሬ ባልዲሠራን ከትልቅ ሥጋት ላይ ጣለው ። ባጼ ምኒልክ ዘንድ ያለው የስንቅ ማለቅ ወይም ያለማለቅ ሁኔታ ፣ ራሶቹ ፣ ወታደሮቹ ከየአውራጃ ከወጡ ሰባት ወር ያህል ስለሆነ ፣ ወደየአገራቸው ለመመለስ ያላቸው ናፍቆትም ምን ያህል እንደሆነ በትክክል ሊገነዘበው አልቻለም ። ዐፄ ምኒልክ በርሱ በኩል ያለውን ችግር እንደማያውቁ እርሱም በርሳቸው በኩል ያለውን በግልጽ አያውቅም ነበር ። ይኸን የመሰለው አለመተዋወቅ ፣ ሁለቱም ከትምክህትና ከኩራት ርቀው የሰላምን መንገድ እንዲፈልጉ አስገድዷቸዋል ።

ጄኔራል ባልዲሠራ ፣ ይኸን በመሰለ አሥጊ ሁኔታ ላይ ባለበት ሰዓት በበኩሉ አዲስ ከተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ከዲሩዲኒ ጋር በቴሌግራም እየተስማማ ፤

፩ኛ ከያለበት እየሸሸ ወደ ኤርትራ የሚመለሰውን የደካከመና የተሸበረ ጦር እየተቀበለ በማጽናናትና ልብ በመስጠት አዲስ ከመጣው ጦር ጋር ደባልቆ ማናቸውንም ነገር ማደራጀት ፣

፪ኛ ንጉሠ ነገሥቱ ጦር ይዘው መረብን ተሻግረው ኤርትራን ለመውረር ምናልባት የመጡ እንደሆነ እንደ ተቻለ መከላከል ፣

፫ኛ/ በዓድዋ አካባቢ በዩሃ ፣ በማርያም ሸዊቶና በእንዳ አባ ገሪማ የወደቀውን የኢጣልያኖች ሬሳ ሰብስቦ ለመቅበር በማስፈቀድ ሰበብ ፣ የሰላም ንግግር በመጀመር ንጉሠ ነገሥቱ መረብን እንዳይሻገሩ ማቆየት ፣

፯ኛ የኢጣልያ ጦር በዓድዋ ሲፈርስ በአዲግራት ምሽግ እንደ ተከበቡ የተቀመጡትን ጣሊያኖች በስምምነት ማስለቀቅ፣

፰ኛ በከሰላ በኩልም ኢጣልያኖች በደርቡሾች ተከበዋል የሚሉ ወሬ ስለተሰማ ለነርሱም እርዳታ መላክ ።

ስለዚህ ፣ በሌሎቹ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች በትጋት ከማ ከናወን ጋር በ፯ኛና በ፰ኛ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች ለመፈ ጸም ፣ ከጦርነቱ በፊት ወዳጄ ምኒልክ ዘንድ በመላክ የታወቀው ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ተመረጠ ። ለርሱም ረዳት የሚሆነው የኢትዮጵያውያንን ባህልና የትግርኛ ቋንቋ የሚያውቀው የአዲኳላ ምስለኔ ቴኔንቲ ሮቬርሲ ተጨመረለት ። ከነዚህም ጋር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ባስተርጓሚነት በኢጣልያኖች ዘንድ የታወቁት ፣ ደጃች ባሕታ ከኢጣልያ ሸፍተው የሰገነይቴውን ምስለኔ ቴኔንቴ ሳንጉይኔቲን ያሰሩ ጊዜ ስለ ኢጣልያዊው መኰንን እስራትና መጉላላት ከባሕታ ሐጎስ ጋር የተጣሉትና በዚህም ሥራቸው ሁሉ በኢጣልያኖች ዘንድ በጣም የተ ወደዱት አቶ ገብረ እግዚአብሔር ተሰጡት ።

በዚህ ዐይነት ማዦር ሳልሳ እነዚህን እንዳስከተለ በሐያ ሰው ታጅቦ ከአሥመራ ወደ አዲኳላ መጣ ። ከጄኔራል ባልዲሠራ እንደ ታዘ ዘው የአዲኳላ ምስለኔ ስለ ሰላም እንዲዋዋል የኢጣልያ መንግሥት ማዦር ቶማሶ ሳልሳን መሾሙን ዐፄ ምኒልክ ዐውቀው እንዲቀበሉት ለራስ መኰንን ደብዳቤ በመላክተኛ እጅ በቶሎ ላከ ። አዲኳላ ሆነው ሌቱንም ምንም እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ሲጠብቁ አድረው መልሱ ስላልመጣ ፣ መቼም መፈቀዱ አይቀርም ብለው ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው በየካቲት 27 ቀን (መጋቢት 6 ቀን) ጉንደትን አለፍ እንዳሉ ከራስ መኰንን ዘንድ ከተላኩት መላክተኞች ጋር በመንገድ ተገናኙና ከራስ መኰንን የተጻፈውን ደብዳቤ ለሳልሳ ሰጡት ። በደብዳቤው ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ሳልሳን ለመቀበል መፍቀዳቸው ፣ እነርሱንም እየመሩ የሚወስዱ ሁለት መኳንንት ታዘው መንገድ መጀመራቸው ተገለጸለት ።

በዚህ ዐይነት ተጉዘው አዲ ቆሆት ሲደርሱ ፣ ከሁለቱ መኳንንት ጋር ተገናኙ ። እነርሱም ፊታውራሪ ደሳለኝ የራስ መኰንን መላክተኛ፣ ደጃች አርአያ የራስ መንገሻ ዮሐንስ መላክተኛ ናቸው ። ከእነርሱም ጋር በመልካም መግባባትና ሰላምታ ከተገናኙ በኋላ ፣ አዲቆሆት የደጃች አርአያ ግዛት ስለሆነ ፣ በመልካም መስተንግዶ አድረው በማግ ሥቱ ከመጋቢት 11 እ.ኤ.አ. ዠምሮ ተጉዘው ዐፄ ምኒልክ ሰፈር እስኪደርሱ ድረስ ያዩትን ሁኔታ በቀጥታ ከራሱ ከቴኔንቴ ሮቬርሲ ጽሑፍ መመልከት የተሻለ ነው ።



. . . ከአዲ ቆሆት በማግሥቱ ተነሥተን 2 ሰዓት እንደ ተጓዝን ዐፄ ምኒልክ ያሉበትን እኛም መኳንንቱም አናውቅም ነበርና አስተ ዋዩ ፊታውራሪ ደሳለኝ በያዘው መነጽር አተኩሮ ሲያይ እንደ ደመና የቆመ አቧራ ተመለከተና ወደ ፈረስ ማይ የሚጓዘው የሸዋ ጦር (ዐፄ ምኒልክ) ነው ብሎ ነገረን ። ወደዚያም ለመድረስ የዩሃን ሜዳ ማቋረጥ ነበረብን ። በዚሁ ሜዳ በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የሞቱት ያብዛኞች ጣልያኖች ሬሳ ፊታቸውን ወደ አንዲት ፈሳሽ ወንዝ አድርገው እንደወደቁ ይታዩ ነበር ። ሜዳው በሙሉ በሬሳ ተሸፍኖ ነበር ። በአፍሪካ 6 ዓመት ስኖር ብዙ ቁስለኛና ሬሳ አይቻ ለሁ ፣ የአቀርዳትንም የጦር ሜዳ ተመልክቻለሁ ። ነገር ግን በዚህ ቀን በዩሃ ሜዳ እንዳየሁት የመሰለ የሬሳ ብዛት በፍጹም አይቼ አላ ውቅም ። ጦርነቱ በተደረገ በ8ኛው ቀን በመካከሉ ሳልፍ ሬሳውን አሞራዎቹ ሳይገፉት ጅብም ሳይነካው እንዳለ ነበር . . . ሬሳው አንዱ ካንዱ የተቀራረበ በመሆኑ በቅሎቻችን በእግራቸው እንዳይረግጡት በጥንቃቄ እንመራቸው ነበር ። . . . በሬሳ የተሸፈነው ረዥሙ ሜዳ አለቀ ድረስ በመሐረቤ አፍንጫዬን ይዤ ዐይኖቼን ባጋማሽ ከድኜ አቋረጥሁ ።

የማዦር ሳልሳ ተከታይ ሆኖ የተላከው ሌተና ሮቬርሲ ፣ የጉዞ ን አስቀያሚና አሠቃቂ ሥዕል በዚህ ዓይነት ካመለከተ በኋላ ምኒልክ ከዓድዋ ወደ እንትጮ ተዛውረው አሉበት አዳራሽ ገብቶ ውን ሁኔታ ደግሞ እንደዚህ ሲል በመተረክ ያቀርባል ።

. . .ምኒልክ በዙሪያቸው ያጌጠ ልብስ የለበሱ መኳንንቶች አስከት ለው ከዓድዋ መጥተው እንትጮው እንደ ደረሱ ሰፈር አደረጉ ። ከሰዓት በኋላም እቴጌ ጣይቱ ደረሱ ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መጠናቸው የተለያየ ነጫጭ ድንኳኖች በትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ ተተክለው አየናቸው ። የሹማምንቱ ድንኳኖች ልዩ ልዩ ቀለም ነበሩዋቸው ። ሰፈሩ በሥነ ሥርዓትና ፍጥነት ባለው ጊዜ ውስጥ ተሠርቶ አልቆ ሳየው እስካሁን ድረስ በዐይኔ ፊት የሚደቀን ያማረ ሥዕል ሆኖ ይታ የኛል ። በ4 (10) ሰዓት አንድ የራስ መኰንን ወታደር መጥቶ ወደ ጌታው ወሰደን ። ከርሱም አንዱ ሹም ተቀብሎ ከራስ መኰንን ድንኳን ሁለት መቶ ሜትር ርቆ የተዘጋጀልንን ድንኳን አስረከበን ። ከማታው በ8 ሰዓት (2) ራስ መኰንን ወደ ድንኳናቸው ጠርተውን ተገናኙንና መጠጥ ጋበዙን ። ከዚያ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ነገ ትገናኛ ላችሁ ብለው አሰናበቱን ። ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ ጧትና ማታ ምግ ባችን በደንብ ይመላለስልን ነበር ።

በማግሥቱ ጧት ፣ ፊታውራሪ ደሳለኝ መጥቶ እየመራ ወደ ንጉሡ ወሰደን ። 500 ሜትር ርቀት ባለው በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ዙሪያ ያልታወቀ ሰው እንዳይገባ ጩኸትና ልፍለፋ እንዳይደረግ ወታደሩ እንደ አጥር ሆኖ ይጠባበቃል ። ከዚህ የወታደር አጥር ላይ ስንደርስ የጭን ከብቶቻችንንና ተከታዮቻችንን ትተን እንድንገባ ተገደድን ። ወዳንድ ልዩ ድንኳን ገብተን ዐርፈን እንደቆየን አንድ ሰው መጣና ማዦር ሳልሳን ጠራው ። መሣሪያ አለመያዙን ለማረጋገጥ እየበረበረ ከፈተሸው በኋላ ወዳጄ ምኒልክ ይዞት ሔደ ። እኩል ሰዓት ከቆየ በኋላ

፬ኛ የኢጣልያ ጦር በዓድዋ ሲፈርስ በአዲግራት ምሽግ እንደ ተከበቡ የተቀመጡትን ጣሊያኖች በስምምነት ማስለቀቅ፤

፭ኛ በከሰላ በኩልም ኢጣልያኖች በደርቡሾች ተከበዋል የሚሉ ወሬ ስለተሰማ ለነርሱም እርዳታ መላክ ።

ስለዚህ፤ በሌሎቹ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች በትጋት ከማከናወን ጋር በ፪ኛና በ፬ኛ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች ለመፈጸም፤ ከጦርነቱ በፊት ወዳጄ ምኒልክ ዘንድ በመላክ የታወቀው ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ተመረጠ ። ለርሱም ረዳት የሚሆነው የኢትዮጵያውያንን ባህልና የትግርኛ ቋንቋ የሚያውቀው የአዲኳላ ምስለኔ ቴኔንቴ ሮቬርሲ ተጨመረለት ። ከነዚህም ጋር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ባስተርጓሚነት በኢጣልያኖች ዘንድ የታወቁት፤ ደጃች ባሕታ ከኢጣልያ ሸፍተው የሰገነይቲውን ምስለኔ ቴኔንቴ ሳንጉይኔቲን ያሰሩ ጊዜ ስለ ኢጣልያዊው መኰንን እስራትና መጉላላት ከባሕታ ሐጎስ ጋር የተጣሉትና በዚህም ሥራቸው ሁሉ በኢጣልያኖች ዘንድ በጣም የተወደዱት አቶ ገብረ እግዚአብሔር ተሰጡት ።

በዚህ ዐይነት ማዦር ሳልሳ እነዚህን እንዳስከተለ በሐያ ሰው ታጅቦ ከአሥመራ ወደ አዲኳላ መጣ ። ከጄኔራል ባልዲሠራ እንደ ታዘዘው የአዲኳላ ምስለኔ ስለ ሰላም እንዲዋዋል የኢጣልያ መንግሥት ማዦር ቶማሶ ሳልሳን መሾሙን ዐፄ ምኒልክ ዐውቀው እንዲቀበሉት ለራስ መኰንን ደብዳቤ በመላክተኛ እጅ በቶሎ ላከ ። አዲኳላ ሆነው ሌቱንም ምንም እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ሲጠብቁ አድረው መልሱ ስላልመጣ፤ መቼም መፈቀዱ አይቀርም ብለው ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው በየካቲት 27 ቀን (መጋቢት 6 ቀን) ጉንደትን አለፍ እንዳሉ ከራስ መኰንን ዘንድ ከተላኩት መላክተኞች ጋር በመንገድ ተገናኙና ከራስ መኰንን የተጻፈውን ደብዳቤ ለሳልሳ ሰጡት ። በደብዳቤው ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ሳልሳን ለመቀበል መፍቀዳቸው፤ እነርሱንም እየመሩ የሚወስዱ ሁለት መኳንንት ታዘው መንገድ መጀመራቸው ተገለጸለት ።

በዚህ ዐይነት ተጉዘው አዲ ቆሆት ሲደርሱ፤ ከሁለቱ መኳንንት ጋር ተገናኙ ። እነርሱም ፊታውራሪ ደሳለኝ የራስ መኰንን መላክተኛ፤ ደጃች እርአያ የራስ መንገሻ ዮሐንስ መላክተኛ ናቸው ። ከእነርሱም ጋር በመልካም መግባባትና ሰላምታ ከተገናኙ በኋላ፤ አዲቆሆት የደጃች እርአያ ግዛት ስለሆነ፤ በመልካም መስተንግዶ አድረው በማግሥቱ ከመጋቢት 11 እ.ኤ.አ. ጀምሮ ተጉዘው ዐፄ ምኒልክ ሰፈር እስኪደርሱ ድረስ ያዩትን ሁኔታ በቀጥታ ከራሱ ከቴኔንቴ ሮቬርሲ ጽሑፍ መመልከት የተሻለ ነው ።



. . . ከአዲ ቆሆት በማግሥቱ ተነሥተን 2 ሰዓት እንደ ተጓዝን ዐፄ ምኒልክ ያሉበትን እኛም መኳንንቱም አናውቅም ነበርና አስተዋዩ ፊታውራሪ ደሳለኝ በያዘው መነጽር አተኩሮ ሲያይ እንደ ደመና የቆመ አቧራ ተመለከተና ወደ ፈረስ ማይ የሚጓዘው የሸዋ ጦር (ያፄ ምኒልክ) ነው ብሎ ነገረን ። ወደዚያም ለመድረስ የዩሃን ሜዳ ማቋረጥ ነበረብን ። በዚሁ ሜዳ በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የሞቱት ያብዛኞች ጣልያኖች ሬሳ ፊታቸውን ወደ አንዲት ፈሳሽ ወንዝ አድርገው እንደወደቁ ይታዩ ነበር ። ሜዳው በሙሉ በሬሳ ተሸፍኖ ነበር ። በአፍሪካ 6 ዓመት ስኖር ብዙ ቁስለኛና ሬሳ አይቻለሁ፤ የአቀርዳትንም የጦር ሜዳ ተመልክቻለሁ ። ነገር ግን በዚህ ቀን በዩሃ ሜዳ እንዳየሁት የመሰለ የሬሳ ብዛት በፍጹም አይቼ አላውቅም ። ጦርነቱ በተደረገ በ8ኛው ቀን በመካከሉ ሳልፍ ሬሳውን አሸናፊዎቹ ሳይገፉት ጅብም ሳይነካው እንዳለ ነበር . . . ሬሳው አንዱ ካንዱ የተቀራረበ በመሆኑ በቅሎቻችን በእግራቸው እንዳይረግጡት በጥንቃቄ እንመራቸው ነበር ።. . . በሬሳ የተሸፈነው ረዥሙ ሜዳ አለቀ ድረስ በመሐረቤ አፍንጫዬን ይዤ ዐይኖቼን ባጋማሽ ከድኜ አቋረጥሁ ።

የማዦር ሳልሳ ተከታይ ሆኖ የተላከው ሌተና ሮቬርሲ፤ የጉዞውን አስቀያሚና አሠቃቂ ሥዕል በዚህ ዓይነት ካመለከተ በኋላ ዐፄ ምኒልክ ከዓድዋ ወደ እንትጮ ተዛውረው አሉበት አዳራሽ ገብቶ ያየውን ሁኔታ ደግሞ እንደዚህ ሲል በመተረክ ያቀርባል ።

. . .ምኒልክ በዙሪያቸው ያጌጠ ልብስ የለበሱ መኳንንቶች አስከትለው ከዓድዋ መጥተው እንትጮው እንደ ደረሱ ሰፈር አደረጉ ። ከሰዓት በኋላም እቴጌ ጣይቱ ደረሱ ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መጠናቸው የተለያየ ነጫጭ ድንኳኖች በትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ ተተክለው አየናቸው ። የሹማምንቱ ድንኳኖች ልዩ ልዩ ቀለም ነበሩዋቸው ። ሰፈሩ በሥነ ሥርዓትና ፍጥነት ባለው ጊዜ ውስጥ ተሠርቶ አልቆ ሳየው እስካሁን ድረስ በዐይኔ ፊት የሚደቀን ያማረ ሥዕል ሆኖ ይታየኛል ። በ4 (10) ሰዓት አንድ የራስ መኰንን ወታደር መጥቶ ወደ ጌታው ወሰደን ። ከርሱም አንዱ ሹም ተቀብሎ ከራስ መኰንን ድንኳን ሁለት መቶ ሜትር ርቆ የተዘጋጀልንን ድንኳን አስረከበን ። ከማታው በ8 ሰዓት (2) ራስ መኰንን ወደ ድንኳናቸው ጠርተውን ተገናኙንና መጠጥ ጋበዙን ። ከዚያ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ነገ ትገናኛላችሁ ብለው አሰናበቱን ። ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ ጧትና ማታ ምግባችን በደንብ ይመላለስልን ነበር ።

በማግሥቱ ጧት፤ ፊታውራሪ ደሳለኝ መጥቶ እየመራ ወደ ንጉሡ ወሰደን ። 500 ሜትር ርቀት ባለው በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ዙሪያ ያልታወቀ ሰው እንዳይገባ ጩኸትና ልፍለፋ እንዳይደረግ ወታደሩ እንደ አጥር ሆኖ ይጠባበቃል ። ከዚህ የወታደር አጥር ላይ ስንደርስ የጭን ከብቶቻችንንና ተከታዮቻችንን ትተን እንድንገባ ተገደድን ። ወዳንድ ልዩ ድንኳን ገብተን ዐርፈን እንደቆየን አንድ ሰው መጣና ማዦር ሳልሳን ጠራው ። መሣሪያ አለመያዙን ለማረጋገጥ እየበረበረ ከፈተሸው በኋላ ወዳጄ ምኒልክ ይዞት ሔደ ። እኩል ሰዓት ከቆየ በኋላ

ያው ስውዬ መጥቶ በተራዬ ጠራኝ ። በኔ ላይ ያደረገው ምርመራ ከፍ ያለ ነው ። ኮቴንና የውስጥ ልብሴን ሳይቀር ባርሜጣና ኪሶቼን እየደጋገመ ፈትሾ አንድ የርሳስ መቅረጫ ስንጢዬን አስቀርቶ የቀረውን መልሼ እንድለብስ ፈቀደልኝና ለጓደኛው አስረከበኝ ። እርሱም እየመራ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን አገባኝ . . .

በመጀመሪያ ዋናው የመልእክቱ መሪ ማጆር ሳልሳ ከገባ በኋላ ቀጥሎ ራሱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ተጠርቶ መግባቱን ሲያወሳ ፣ ላስተርጓሚነት የመጡት ገብረ እግዚአብሔር ለመግባት አልተፈቀደላቸውም ማለት ነው ። ይኸው ሮቬርሲ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ከገባ በኋላ ፣ ባይኑ ያየውንና በጆሮው የሰማውን ለዛሬ ትውልድ የተወልንን ማስታወሻ በቀጥታ ከጻፈው የሚቀጥለውን መረዳቱ ጠቃሚ ነው ።

እየመራ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ውስጥ አገባኝና በስመ ጥሩው ንጉሥ ፊት ቆምሁ ። ንጉሡ ከሙሉ ዕድሜ አጋማሽ አለፍ ያሉ ናቸው ። ለስላሳ የብልህ መልክ አላቸው ። ቆዳቸው ግን ጥቁር ነው ። ያበሻን ቤተ መንግሥት ሥርዓት ካለማወቄ የተነሣ ለአውሮፓ ንጉሥ እንደሚደረገው እጅ ነሥቼ ማጆር ሳልሳ አጠገብ ወዳለች ባዶ ወንበር የኔ ሳትሆን አትቀርም በማለት ሔጄ ቆሜ ስጠባበቅ ምኒልክ ወደርሳቸው እንድቀርብ ጠቀሱኝና ተጠግቼ እጃቸውን ዘረጉልኝና ለመጨበጥ ቻልሁ ። ከዚያ አንዳንድ ጥያቄ ካቀረቡልኝ በኋላ ፣ እንድቀመጥ ፈቀዱልኝና ስቀመጥ እኔ ከመድረሴ በፊት ከማጆር ሳልሳ ጋር የጀመሩትን ንግግር ይቀጥሉ ጀመር ። በዚህ ንግግር ሰዓት ያፄ ምኒልክ ሁኔታ ገረመኝ ። ንግግሩ በሚቀጥልበት ሰዓት በመልካቸው ላይ ምንም ሥጋት ሳይታይ በግድየለሽነት አንዳንድ ጊዜ በፈገግታ የደስታ መልክ እያሳዩ ይነጋገሩ ነበር ። . . . ሰሞኑን ካንድ የመንግሥት ባላጋራ ጋር ሲዋጋ ቆይቶ መንግሥታዊ ንግግር ከሚያደርግ ንጉሥ ይልቅ ምንም ነገር ሳይደርስበት ተዝናንቶ የዕረፍት ጊዜ የሚያሳልፉ ይመስሉ ነበር ።

. . . በዋናው ንግግር መካከልም ተራ ንግግር ጣልቃ እያገቡ በኢጣልያ አገር ታላቅ እንቁላል የሚወልዱ ልዩ ልዩ ዶሮዎች አሉ ሲባል የሰሙት እውነት መሆኑን ፣ ቀጥሎም በፊተኛው ጊዜ የሚያውቋቸውን የኢጣልያ ሹማምንት የነካፒቴን አንጌራን የነሴተና ፓርቲኔን የነ ፊልተርንና የሌሎቹንም ደህንነት ይጠይቁ ነበር ። እነዚህም ሁሉ ከሞት መትረፋቸውን ሲሰሙ ደስታቸውን ይገልጹ ነበር ። በዚህ ዓይነት የግዴለሽነት ሁኔታ ማሳየታቸው የዘዴ መንገድ እንደሆነ ገብቶኛል ። . . .

ማጆር ሳልሳና ዐፄ ምኒልክ የወሰን ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ እኔ በምኒልክ አጠገብ ያሉትን ራሶች እመለከት ነበር ። ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ በቀር የቀሩትን ገና ማየቴ ነበር ። በዚያም የሚታዩት ራሶች የሰውነታቸው ቅርፅ ልዩ ልዩ ነው ። . . . ወፍራሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ማዕዘንማ ቅርፅ ያላቸው ራስ መኰንን ፣



አጠር ቀጠን ያሉት ራስ መንገሻ አቲከም የስፖርት ሰው የሚመስሉት ራስ ሚካኤል . . . መልከ መልካሙ የትግሬው ራስ መንገሻ ይታዩ ነበር ። እነዚህ ሁሉ የለበሱት ያማረና በወርቅ ያጌጠ ልብስ ነበር ። . . . ምኒልክ ከሳልሳ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ እነዚህ ራሶች ዝም ብለው ይመለከቱ ነበር ። በኋላ ግን ፣ ከራሶቹ ጋር ለመመካከር ማጆር ሳልሳ ወደ ውጭ ይወጣ ዘንድ ንጉሡ ለመኑትና ወጣ ። ከራሶቹ ከተመካከሩ በኋላ እንደገና ሳልሳን አስጠሩት ። በዚያም ጊዜ አንዳንድ የምኒልክን የቀድሞ አሳቦች ራሶቹ ለውጠውት አዲስ ሁኔታ ተፈጥሮ ክርክር ተደረገ . . .

በዚህ ሮቬርሲ በተወልን የጽሑፍ ማስታወሻና ደ ሉሊባር ያሳተመው አነጋገር ልክ ነው ። "ዐፄ ምኒልክ ከሙሉ ዕድሜ አጋማሽ አለፍ ያሉ ናቸው" ያለው ፣ ዐፄ ምኒልክ የዓድዋ ጦርነት ጊዜ ዕድሜያቸው 52 ዓመት ከመንፈቅ ስለሆነ ፣ ግምቱ ልክ ነው ። "ትልቅ ጦርነት ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ባደረጉበት ሳምንት ሲነጋገሩ የሥጋትና የፍርሃት መልክ በማሳየት ፈንታ ተዝናንተው በግድየለሽነት አነጋገሩን" ያለው ፣ እንኳን ድልን ባገኙበት ሳምንት ፣ በጦርነቱም ሰዓት ቢሆን ዐፄ ምኒልክ ይኸን ዓይነት አቅዋም ማሳየት የተለምዶ ባሕርያቸው ነበር ። በሰላም ንግግር ጊዜ ይኸው ዐይነቱ አቅዋም ጠላትን ከሥጋት ላይ ጥሎ ከጠላት የበለጠ ለመጠቀም ይረዳል ። "የአንጌራን ፣ የፓርቲኒንና የፊልተርን ጤንነት ጠየቁ" ያለውም ፣ እነዚህ ሦስቱም ከዓድዋ ጦርነት በፊት በመቀሌው ከብ ጊዜ በዕርቅ ሰበብ እየመጡ በራስ መኰንን አማካይነት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የተዋወቁ ናቸው ።

ሌላው የሮቬርሲ ዝርዝር ፣

ከድንኳናችን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ስንመላለስ ፣ ቁጥሩ በበረከተ ተቀራርቦ በተተከለ ድንኳን መካከል ማለፍ ነበረብን ። የሚንቀሳቀሰው የወንዱ ፣ የሴቱ ፣ የልጁ ብዛት ልክ እንደ አንድ ትርዒት ይመስላል ። ምንም እንኳን ጠባቂና አጃቢ ቢኖረን ሕዝቡ ወራዶች እያለ ይሰድበን ነበር ።

ከሁሉም በስድብ ረገድ ሴቶቹ ይበልጡ ነበር ። እኛም እየሰማን እንዳልሰማ እናልፍ ነበር ። ይኸንኑ ለሳልሳ ስነግረው ፣ ነገ ለእቴጌይቱ ሰላምታ ለማቅረብ ስንሔድ የበለጠ ሳይደርስብን አይቀርምና ለኢጣልያ ስንል ሁሉንም መዋጥ አለብን አለኝ ።

ይላል ። ከዚህ አያይዞ ፣

ዐፄ ምኒልክ ዘንድ ቀርበን ንግግር በምናደርግበት ጊዜ እቴጌን እጅ እንድንነሣ እንዲፈቀድልን ብናመለክት ሸፈንፈን ብለው ቆይተው

ግጁስም እኔው እነግርላችኋለሁ አሉ ። የባለቤታቸውን ጠባይ የሚያውቁት ስለሆንና እቴጌይቱ በመጥፎ ሁኔታ እንደሚቀበሉን ተገንዝበው ስላስቀሩን ውስታ አድርገውልናል ።

ከዚያ ደግሞ አልፍ ብሎ በሌላ ቦታ ላይ ፤

አምስት ቀን በቆየንበት ጊዜ ደህና መስተንግዶ ተደርጎልን ነበር ። ራሶቹ ሁሉ መልካም አስተያየት አድርገውልናል . . . ምኒልክ የዓድዋውን ጦርነት አንሥተው እኛን ለማሳዘን አንድ ቀንም የቁጣና የወቀሳ ነገር አንሥተው አያውቁም . . . ጥረታቸው ሁሉ ያተኮረው ወደ አንድ ሰላም ለመድረስ ነው ።

ሲል ይደመድማል [1] ።

ሌላው ጸሐፊ ከዚሁ እያይዞ ፤

በድል አድራጊነት ሰዓት ምኒልክ ከሹመት አባቶቻቸው የሚለዩበት ሁኔታ አላቸው ። ድል በተገኘበት የሁካታ ሰዓት በተሸናፊዎች ላይ መጨከን አይወዱም ። ዘወትር የምሕረት እጃቸውን ለጠላታቸው ይዘረጋሉ ። 2

ሲል የንጉሠ ነገሥቱን ችሎታና ጠባይ አመስግኗል ። ከሹመት አባቶቻቸው የሚለው ፤ ዐፄ ቴዎድሮስንና ዐፄ ዮሐንስን ማለቱ ይመስላል ።

በዚህ ዓይነት ፤ የጦር መኰንኖቹ ከጦርነቱ በፊት በኢትዮጵያውያን ላይ የነበራቸው የንቀት አስተያየት ከጦርነቱ በኋላ የተለወጠ ይመስላል ። ባለፈው በአላጌ ጦርነት አገር ሊወር የመጣው የጠላት መኰንን ፤ ማዦር ቶዜሊ ከነጓደኞቹ በክብር መቀበሩ በመቀሌ ብዙ ነፍስ ያጠፋውና ያስጠፋው ጋልያኖ በዓድዋ ጦርነት ከመሞቱ በፊት በሸኝ ወደ ወገኖቹ እንዲደባለቅ መደረጉ የሚታወስ ነው ። አሁን ደግሞ ፤ በብዙ መሥዋዕትነት የዓድዋ ድልን ቢያገኙም፤ ከወገናቸው ብዙ ዘመድ አዝማድ የሞተባቸው ራሶችና ንጉሠ ነገሥቱ ምንም የቁጣ መልክ ሳያሳዩ ፤ ሰላም መፈለጋቸውን ሲገነዘበው ፤ ይኸን የመሰለው የማሸነፍ ዕድል በኢጣልያኖች እጅ ገብቶ ቢሆን ምን ዐይነት የኩራትና የትዕቢት አቅዋም እንደሚኖራቸው ሮቬርሲ የሁለቱን ሕዝብ የጠባይ ልዩነት በሕሊናው ሳያመዛዝነው አልቀረም ።

ቴኔንቲ ሮቬርሲ ፤ ከዚህ በላይ ያነበብነውን ጠቃሚ ዝርዝር ሲሰጡን ፤ ማዦር ሳልሳ ከጄኔራል ባልዲሠራ ተልኮ ወደ ዐፄ ምኒልክ የመጣበትን ዋናውን የእርቅ ጉዳይ ካፄ ምኒልክም የተሰጠውን መልስ አልጻፈውም ። ለማንኛውም ዋናው መላከተኛ ማዦር ሳልሳ በዘመኑ አዘጋጅቶት ከሞተ በኋላ ወገኖቹ በስሙ ካሳተሙት መጽሐፍ ላይ አንዳንድ መረጃዎች እንመለከታለን ።

1 Douze ans en Abyssinie ,Paul de Laulibar, PP.537-567.
2 Menelik II I'Etiopia le relationi Con I'Italia, Et. Falcone, p 156.



በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማዦር ሳልሳ ከአሥመራ ወደ አዲኳላ ከዚያ ወደ ዐፄ ምኒልክ መጥቶ ላዩን ሬሣ ለማስቀበርና የተማረኩትን የኢጣልያ ሹማምንቶች ስም ለማወቅ ሲሆን ፤ ውስጡን ግን ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኤርትራ ሳያመሩ ጠቅላላ እርቅ የሚደረግበትን ለመፈተን ነበር ። ካፄ ምኒልክ ጋር ተነጋግሮ ያገኘውን መልስ ወደ አዲኳላ ተመልሶ በስልክ ለጄኔራል ባልዲሠራ መንገሩ ፤ ከዚያ ወደ ዐፄ ምኒልክ ሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ በመምጣት የመጨረሻውን የእርቅ አሳብ ከዐፄ ምኒልክ ተቀብሎ በቀጥታ አሥመራ ሔዶ በቃል ጭምር እያስረዳ ጽሑፉን ለጄኔራል ባልዲሠራ ማስረከቡ ፤ ይኸንንም በአማርኛ ተጽፎ የተላከለትን ጄኔራል ባልዲሠራ ወደ ኢጣልያንኛ አስተርጕሞ በቴሌግራም ለኢጣልያ መንግሥት ማስተላለፉ ተጽፏል ።

በመጋቢት 8 ቀን 1888 ዓ. ም. በዐፄ ምኒልክ ዘንድ የተገለጸው የዕርቅ አሳብ ፤ ውጫሌ ላይ የተደረገው ውል በኢትዮጵያና በኢጣሊያ በሙሉ መፋቁን፤ አዲስ ውልም የሚያበጁበት በኤውሮፓ ያሉ ነገሥታት ሁሉ እንደሚዋዋሉት ውልና ሥርዓት እንደሚሆንና የወሰኑም ጉዳይ እንዳለ እንደሚቆይ ይገልጻል ።

ጄኔራል ባልዲሠራም የዕርቁን አሳብ ተቀብሎና የራሱንም አጭር አሳብ ጨምሮ ወደ ሮማ ለመንግሥቱ በቴሌግራም አስተላልፏል ።

ባልዲሠራ ይኸን ቃል ወደ ሮማ ለመንግሥቱ ካስተላለፈ በኋላ፤ ከኢጣልያ መንግሥት ዘንድ ፤ "ይኸንን የመሰለውን እርቅ እንድታደርግ ፈቅደንልሃል ። ነገር ግን ከእርቁ በፊት የውጫሌ ውል ከመሰረዙ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለኢጣልያ እምቢ ያለውን የበላይ ጠባቂነት መብት ለሌሎች ያውሮፓ ኃያላን እንዳይሰጥ ቃል አስገባ" የሚል ቃል ተጨምሮ መጣለት ። እርሱም በበኩሉ ፤ "ይህ ሁኔታ ባገራቸው ላይ ያላቸውን ሙሉ ሥልጣናቸውን እንደሚቀንስባቸው እየተገነዘቡ የውጭን አገር ጠባቂነት እንዳትቀበሉ ውል ግቡ ብንላቸው አይፈቅዱም ። በዚህ ምክንያት ስንከራከር ፤ ጦሩን ይዞ ምኒልክ ወደ ሸዋ የተመለሰ እንደሆነ እርቁ ፈርሶ ጠቡ ይቀጥላል" የሚል ቃል ጨምሮ ወደ ኢጣልያ አገር እንደገና መልስ ሰጠ ።

በዚሁ መካከል ፤ ከሮማ መልሱ ሳይመጣ ስለቆየና ሳልሳ ከአሥመራ መልሱን ይዞ ወደ ዐፄ ምኒልክ ሊመለስ ቃል የገባበት ጊዜ መጋቢት 25 እ.ኤ.አ. (መጋቢት 16 ቀን) ስለ ደረሰ ጄኔራል ባልዲሠራ ሳልሳን ወደ ዐፄ ምኒልክ እንዲሔድ አሰናበተው ። ሳልሳ በአዲግራት በኩል አድርጎ ወደ ዐፄ ምኒልክ በሚጓዝበት ጊዜ ፤ "የሌላን መንግ

ሥት ጠባቂነት ኢትዮጵያ እንዳትቀበል ምኒልክን በውል ማስገባት ፍጹም አስፈላጊ ነው” የሚል ከኢጣልያ መንግሥት ለባልዲሠራ መልስ ስለ መጣለት ፤ ይኸንኑ ቃል በግሥጋሤ ባልዲሠራ ለሳልሳ ከመንገድ እንዲደርስለት ላከለት ። ሳልሳም ያንን እንደያዘ ከአዲግራት እልፍ ከራስ መኰንን ጋር ተገናኙ ። ከዚያ ሁለቱም አብረው ወደ ምኒልክ ዘንድ ቀርበው ሳልሳ ላፄ ምኒልክ የተላከበትን አዲስ ሐሳብ አቀረበ ።

በዚህ ጊዜ ምኒልክ በፊት በጽሑፍ የላኩትን የውል አሳብ እንደ መጨረሻ ቆጥረውት ሳለ ፤ አሁን ግን ከማዦር ሳልሳ ጋር አስቀድሞ በተነጋገሩት ላይ አዲስ አሳብ በመጨመሩና የቀድሞ አሳባቸው ስለ ተለወጠ ተገረሙ ። በርሳቸው በኩል የእርቁን ውል ጽፈው አትመው ሰጥተውት የራሱንም አሳብ ለእርሳቸው ትቶ ከሔደ ወዲህ ይጠብቁ የነበረው ከኢጣልያ ንጉሥ ዘንድ አንድ ታላቅ ባለሥልጣን ተልኮ መጥቶ በዚሁ በቀረበው ሐሳብ ተዋውለው ዘለቄታ ውል አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ለመዋዋል ነበር ። አሁን ግን ፤ ምንም እንኳን በጠቅላላው የቀረበውን ውል የኢጣልያ መንግሥት ቢቀበል በዚህ ላይ ፤ “የሌላ መንግሥት ጠባቂነትን ሳትቀበሉ ውል ግቡ” የሚል ቃል ካልተጨመረ አይሆንም የሚል የመንግሥቱን መልስ ይዞ ስለመጣ ዐፄ ምኒልክ በዚሁ ተናደው ፤ “የሰጠሁህን ጽሑፍ መልሰህ አምጣ ። ያንንም እስከታመጣ ድረስ እዚሁ መያዣ ሆነህ ተቀመጥ” ብለው ማዦር ሳልሳን እንደ መያዣ አቆዩት ። ይኸንንም ጄኔራል ባልዲሠራ እንዲያውቀው ከዚህ እንደሚከተለው ደብዳቤ ጻፉለት ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከጄኔራል ባልዲሠራ ሰላም ላንተ ይሁን ። ማዦር ሳልሳ መጀመሪያ የመጣው ተርታ የሆኑትን ነገሮች ለመነጋገር ከዚያ ከኢጣልያ የንጉሥ ማኅተም ይዞ መጥቶ ዘለቄታ ያለው ውል ልንዋዋል ንግግራችን በዚሁ አልቆ ነበር ። ሁለተኛ ጊዜ ወደኔ ሲመጣ ንግግራችንን በጽሑፍ አድርገን የኔን ንግግር ጽፌ ለርሱ ሰጠሁት ። የርሱንም ለኔ ሰጠኝና ይኸንኑ ከናንተ ጋር ተነጋግሮ እንዲጨርስና አሳቡም እንዲመለስ ሔደ ። አሁን እንደገና ወደኔ ተመልሶ የተነጋገርንበት ሁሉ ቀረና አዲስ ነገር ይዞ ስለመጣ የእርቁ ነገር ቀርቶ ቃሉን ስለለወጠ ፤ ደግ ነው እንግዲህ ጽፌ አትሜ የሰጠሁህን መልስልኝና የራስህንም ውሰድ ብለው ጽሑፉን አሥመራ ትቼው ነው የመጣሁት አለኝ ። እኔም አስመጥተህ እስክትሰጠኝ ድረስ እዚሁ እኔ ዘንድ ቆይ ብዬ አቆይቼዋለሁ ። ይኸንንም መጻፌ በሌላ ምክንያት ያቆየሁት እንዳይመስላችሁ ብዬ ነው ።

መጋቢት 28 ቀን 1888 ዓ.ም.

ዐፄ ምኒልክ፣ ከየካቲት 23 ቀን እስከ የካቲት 28 ቀን በዐድዋና በፈረስ ማይ ከሰነበቱ በኋላ ፤ መረብን አልፈው ወደ ኤርትራ ለመሻገር



ከዓድዋ ወደ እንትጮ ተጓዙ ። ከቶማሶ ሳልሳ ጋር የእርቅ ጉዳይ ጀምረው ይኸም ተንኮል ያለበት በመሆኑ ሳይሳካ ቀርቷል ። ይህ የተንኮል ዘዴ ባፄ ምኒልክ ዘንድ ታውቆ እንደ ነበረ ግራዝማች ዮሴፍ ለምንዶን ባስተላለፉት ጽሑፍ ላይ እንደዚህ ተብሎ ተገልጿል።

እንትጮ ሳለን ከጻፍሁልዎ ወዲህ የተገኘ ታሪክ ይህ ነው ። ማዦር ሳልሳ የሚባል የኢጣልያ ሹም የሞተውን ልቅበር ብሎ ወደ ጃንሆይ ላከ ። ጃንሆይም ምን ከፋኝ ከተቻለህማ ቅበር እንጂ ብለው ተቀባይ ሰው ላኩለት ። ጃንሆይ ግን ፤ እንደ ልማዱ የማታለል ምክንያት እንደሆነ ዐውቀውበት ነበር ። እነዚያም ሊቀበሉት የሔዱት ሰዎች የራስ መኰንን ፊታውራሪ ደሳለኝና የኔ ዘመድ የሆኑ ደጃች አርአያ ነበሩ ። እነዚያም ሬሳ በወደቀበት ማሀል ይዘውት መጡ ። የሬሳውንም ብዛት ባየ ጊዜ የጦሩ ብርታት ታወቀውና አጥብቆ ደነገጠ ። የኢጣልያኖች ሬሳ የወደቀበት ካባ ገሪማ ጀምሮ እስከ መረብ ድረስ ነበር ። አወዳደቁም ተነባብሮ መሬቱ አይታይም ነበር ። ስለዚህም ምክንያት እንኳን ለመቅበር አይቶ ለመጨረስ አልተቻለውም ። እርሱ ግን ፤ ልቅበር ማለቱ እጅግ ተንኰለኛ ሰው ነበርና ጃንሆይ ወደ ሐማሴን መንገዱን (መንገዳቸውን) ቢለግ በመቅበር ምክንያት መጥቶ የእርቅ ነገር ጀመረ . . .

በማለት ግራዝማች ዮሴፍ ፤ የሳልሳና ያለቃው የባልዲሠራ ተንኮል በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ መታወቁን ገልጸዋል ። እንደ ርሳቸውም አባባል ሁለቱ የኢትዮጵያ መልክተኞች ሳልሳን እየመሩ ያመጡት ሆነ ብለው ሬሳ በብዛት በተረፈረፈበት ቀበሌ ይመስላል ። የባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ መምጣቱ ወሬው ሳይሰማ አይቀርምና ሳልሳ በብዙ ሬሳ መካከል ሲያልፍ ብዛቱን በሚመለከትበት ጊዜ የኢትዮጵያን ወታደር ጀግንነት አጢኖ ላለቆቹ የወደፊቱን ጦርነት መክሮ እንዲያስቀር ታስቦ ይሆናል ። መቼም ባራቲዬሪ ጦርነቱን በመራበት ጊዜ ፕላኑ ሁሉ ስለ ተበላሸበት ፤ ባሁኑ ጊዜ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች የተማረከባቸውንና የሞቱባቸውን የጦር መኳንንትና የወታደር ቁጥር በትክክል ስለማያውቁት ፤ ሳልሳ በዚህ ጉዞው ከተማረከው ይልቅ የሞተው እንደሚበልጥ ይረዳዋል ማለት ነው ።

ከዚሁ አያይዘው ግራዝማች ዮሴፍ፣ ስለ ኢጣልያኖች መሸበር ማዦር ሳልሳ ደግሞ በጠባዩ እርቅም ጦርነትም የማይፈልግ ሰው ስለመሆኑ፤

ጃንሆይ ከዓድዋ ተጉዘው ደብረ ዳሞ አጠገብ የሰፈሩ ጊዜ ምጥዋ ድረስ ተሸብሮ ነበር ። የዓዲ ቀይህን የሰንነይቲን እርድ (ምሽግ) አፈር ባሩድና ዕቃውን አቃጥሎ ነበር ። ጉማ ድረስ ወረደ ። ወታደሩም ነፍሱን እየጣለ ወደ ምጥዋ ይሸሽ ነበር ። ስለዚህ ሸሽቶ ከዓድዋ ጦርነት ያመለጠ የኢጣልያ ወታደር ፍርሃት አድሮበት ነበር ። ማዦር ሳልሳ ግን እርቁንም ጦርነቱንም የማይወድ ሰው ነው ። በጥር ከጦርነቱ በፊት በየሐ የሰፈርን ጊዜ አስታርቃለሁ ብሎ መጥቶ ነበር ። ጃንሆይም ምን ከፋኝ እርቅ ከፈለጋችሁ አገሬን ልቀቁልኝ ቢሉት ፤ ተመልሶ

ሐዶ ለባራቲዬሪ ነግር የጦር ባንዲራ አስተከለ ። ኋላም በየካቲት 23 ቀን የመጨረሻው ጦርነት የሆነ ጊዜ አንድ መድፍ ሳይተኮስ ፣ የዐሥር ነፍጥ ተኩስ ሳይሰማ በፈረስ ሸሽቶ አዲኳላ ገብቶ አደረ ። ይኸንንም በፈረስ ማምለጡን የነገረን እርሱ ራሱ ነው” ።

ብለዋል ።

በዚህ አነጋገር ግራዝማች ዮሴፍ ፣ “ንጉሠ ነገሥቱ በእንትጮ አልፈው ደብረ ዳሞ አጠገብ ሰፍረው የነበረ ጊዜ ከመረብ ጀምሮ እስከ ምጥዋ ድረስ ተሸብሮ ነበር” ያሉት ትክክለኛ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት እያመለጡ ከመረብ ባሻገር የሔዱ የኢጣልያ ዘማቾች ሁሉ፣ የጦር ነቱን ብርታትና የኢጣልያኖቹን እልቂት ፣ የኢትዮጵያን ወታደር ጉብዝና እያጋነኑ በመናገራቸው ከነርሱ የሰማው ሁሉ ልቡ እንደሚሸበር አይጠረጠርም ፤ በእርግጥም ተሸብሯል ።[1]

“ሳልሣ ጦርነትም እርቅም የማይፈልግ ነው ። የዋናው ጦርነት ዕለት አንድ የመድፍ ጥይት ሳይተኮስ በፈረስ አመለጠ” ያሉትም የሚመስል ነው ። ሳልሳ ጦርነቱን ተቃውሞ እንደነበር ከድሉ በኋላ ፀ6ኛው ቀን ለእናቱ በጻፈው ደብዳቤ ፣

> ውድ እናቴ ፣ በጦርነት ስለሞቱብን ኢጣልያኖች አቀባበር እና ሐለሰላም ውስታ ለመዋዋል ተስፋ አድርጌ ይኸው ወደ ዓድዋ መሔዴ ነው . . . በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የተደረገውን ሁኔታ ልዘረዝ ርላችሁ አልችልም ። ይህ የእብደት ጦርነት እንዲቀር በማናቸውም ኃይሌ ታግዬ ነበር . . . ዳሩ ግን ለመታገል ብቻዬን በመሆኔ ጄኔራ ሎቹ አገረ ገዡውን (ባራቲዬሪን) ገፋፍተው ይኸን የመሰለውን አደ ገኛ ሥራ እንዲፈጽም አደረጉት . . . [2]

ሲል ያመለክታል ።

---

1 Sul Campo di Adua—Ximenes, P.5

2 Tomaso Salsa,E. Canevari . . . ,PP. 295—296.





ጄኔራል ባልዲሠራ

ኢጣሊያ በአፍሪካ ከሚለው መጽሐፍ

ሔዶ ለባራቲዬሪ ነግሮ የጦር ባንዲራ አስተከለ ። ኋላም በየካቲት 23 ቀን የመጨረሻው ጦርነት የሆነ ጊዜ አንድ መድፍ ሳይተኮስ ፣ የዐሥር ነፍጥ ተኩስ ሳይሰማ በፈረስ ሸሽቶ አዲኳላ ገብቶ አደረ ። ይኸንንም በፈረስ ማምለጡን የነገረን እርሱ ራሱ ነው ” ።

ብለዋል ።

በዚህ አነጋገር ግራዝማች ዮሴፍ ፣ “ንጉሠ ነገሥቱ በእንትጮ አልፈው ደብረ ዳሞ አጠገብ ሰፍረው የነበረ ጊዜ ከመረብ ጀምሮ እስከ ምጥዋ ድረስ ተሸብሮ ነበር” ያሉት ትክክለኛ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት እያመለጡ ከመረብ ባሻገር የሔዱ የኢጣልያ ዘማቾች ሁሉ፣ የጦር ነቱን ብርታትና የኢጣልያኖቹን እልቂት ፣ የኢትዮጵያን ወታደር ጉብዝና እያጋነኑ በመናገራቸው ከነርሱ የሰማው ሁሉ ልቡ እንደሚሸበር አይጠረጠርም ፤ በእርግጥም ተሸብሯል ። [1]

“ሳልሣ ጦርነትም እርቅም የማይፈልግ ነው ። የዋናው ጦርነት ዕለት አንድ የመድፍ ጥይት ሳይተኮስ በፈረስ አመለጠ” ያሉትም የሚመስል ነው ። ሳልሳ ጦርነቱን ተቃውሞ እንደነበር ከድሉ በኋላ በ6ኛው ቀን ለእናቱ በጻፈው ደብዳቤ ፣

> ውድ እናቴ ፣ በጦርነት ስለሞቱብን ኢጣልያኖች አቀባበር እና ለሰላም ውለታ ለመዋዋል ተስፋ አድርጌ ይኸው ወደ ዓድዋ መሔዴ ነው . . . በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የተደረገውን ሁኔታ ልዘረዝርላችሁ አልችልም ። ይህ የእብደት ጦርነት እንዲቀር በማናቸውም ኃይሌ ታግዬ ነበር . . . ዳሩ ግን ለመታገል ብቻዬን በመሆኔ ጄኔራሎቹ አገረ ገዥውን (ባራቲዬሪን) ገፋፍተው ይኸን የመሰለውን አደገኛ ሥራ እንዲፈጽም አደረጉት . . . 2

ሲል ያመለክታል ።

1 Sul Campo di Adua—Ximenes, P.5

2 Tomaso Salsa,E. Canevari . . . ,PP. 295—296.





ጄኔራል ባልዲሣራ

ኢጣሊያ በአፍሪካ ከሚለው መጽሐፍ

# ምዕራፍ ፀርባ ሰባት

## የዓድዋ ድል በኢጣልያንና በአውሮፓ ተሰምቶ ያደረሰው ስሜትና ረብሻ

የኢጣልያ መንግሥት ፥ በውጭ የእንግሊዝንና የጀርመንን መንግሥታት ድጋፍ እንዳገኘና በውስጥ አስተዳደሩ ደግሞ ፥ በቀኝና በግራ ክንፍ የተከፋፈሉ ሁለት የፖለቲካ ቡድኖች መኖራቸውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። የግራው ክንፍ በሶሺያሊስትነቱ ቅኝ አገር ይቅርብን ሲል ፥ የቀኙ ክፍል ንጉሡንና መሳፍንቱን ፥ ባላባቶቹንና ሀብታሞቹን ጨምሮ እንደ ሌሎቹ የአውሮፓ መንግሥታት በአፍሪካ ቅኝ አገር ፈጥረን ኢጣልያን ኃያል እናድርጋት የሚል ነው ። በዚህ በተለያየ ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች በምክር ቤት ሁል ጊዜ የተከራከሩበትን ሁኔታም ባለፈው ጠቅሰናል ።

በግናቸውም ረገድ ፥ ከላይ ንጉሡ እየደገፈ የቀኞቹ የምክር ቤት አባሎች የድምፅ ብልጫ እያገኙ ቅኝ አገር ለማግኘት በነጀኔራል ካርሎ—ዤኒ ፥ በነጀኔራል ሳንግርሳኖና በነጀኔራል ባልዲሠራ መሪነት የኢጣልያ ወታደር እ.ኤ.አ. በ1885—87 ዓ.ም. ምጥዋ ተራግፎ በየጊዜው አካባቢውን ለመውረር የበቃው በዚሁ ምክንያት ነው ። ወደ ዚህም ለጦር ነትም ላገዛዝም የሚላኩት ጀኔራሎች ባራቲዬሪ ጭምር ሁሉም ከቀኝ ክፍል ይኸው ማለት የቅኝ አገርን ፍላጎት ከሚደግፉት ወገኖች እየተመረጡ ነው ።

የኢጣልያ ጦር ፥ በኮአቲትና በሰንዓፌ ላይ ያገኘው ድል አደፋፍሮት ወደፊት ገሥግሦ አላጌ የመሸገ ጊዜ እ.ኤ.አ. በ1895 ታኅሣሥ 3 ቀን ጉዳዩ ለምክር ቤት ቀረበ ። ከሬፑብሊክ (ሶሺያሊስት) ወገን የሆነው ኢምብሪያኒ የሚባለው ፥ "እንደ አውራ ድመቶች ጨዋታ ክሪስፒ የሚያስከትለውን መዘዝ ሳያመዛዝን ዝም ብሎ እውር ጭፍትን ወደፊት ይገሠግሣል" ብሎ በወቀሰ ጊዜ ፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ፥ "የቅኝ አገራችን ሥራ በደንብ ይራመዳል፥ ልማቱም ይስፋፋል ፥ ሰላሙም ተረጋግጧል" በሚል መልስ ከእውነት የራቀ አባባል ሰጥቷል ። ክርስፒም ቀጥሎ ፥ "እንደ አገራችን ያለ ታላቅ መንግሥት ፥ ትንንሽ ጦርነት ቢያደርግና ለዚህም ወጭ ቢሰጥ መታሰብ የለበትም"

በሚል እንጋገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ሰጥቶአል ። ለማናቸውም "የርሱን አመራር የሚደግፉና የማይደግፉ ይታወቁ" በተባለበት ጊዜ ሙራቶሪ የሚባለው ሶሺያሊስት ፥ "መንግሥት ይለወጥ" የሚል አሳብ (ሞሲዮን ደ ሳንሱር) አቅርቦ ለነበረው ከምክር ቤቱ አባሎች 131 ተቃዋሚ 267 ደጋፊ ስላገኘ ፥ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ የወረራ ሥራውን በደንብ ይቀጥል ዘንድ ተፈቀደለት ። ምክር ቤቱ ይኸን በወሰነ በስድስተኛው ቀን የአላጌ ውድቀት ፥ ከዚያም የመቀሌው መሸነፍ ቢሰማም ሁልጊዜ በቀኙ ክፍል ድጋፍ የተነሣ ክሪስፒ ከነአጋሮቹ ሊወድቅ አልቻለም [1] ነበር ። ክሪስፒንና አጋሮቹን ሊጥል የቻለው ይህ ያሁኑ የዓድዋ ጦርነት ብቻ ነው ። ይኸውም የዓድዋ መደምደሚያ ድል ለቀኞቹ ውድቀት ፥ ለግራዎቹ ማንሠራራት ምክንያት ሆኗል ።

ከዓድዋ የጦር ግንባር የሸሸው ጄኔራል ባራቲዬሪ ፥ የክሪስፒ የግል ወዳጅና የፖለቲካ ጓደኛው ፥ በጠቅላይ ጦር አዛዥነቱ ዓድዋ ላይ ድል እንደ ተመታ ፥ በሦስተኛው ቀን ለርሱና ለወገኖቹ መራራ የሆነውን የመሸነፍ ወሬ ለኢጣልያ መንግሥት በቴሌግራም ማስታወቅ ግዴታ ሆነበት ። ሲያስታውቅም ራሱ የነበረበትን የጦር ግንባር ሁኔታ፥ በምን አቅጣጫና አኳኋን ሌሎቹ ጄኔራሎች ጦርነቱን እንደ ጀመሩ ገልጾአል ። ነገር ግን ፥ ራሱ ከመከበብና ከመማረክ ለመዳን ሲል ስለ ሸሸና የሦስቱን ጄኔራሎች የዳቦርሚዳን ፥ የአሪሞንዲንና የአልቤርቶኒን ፍጻሜ ስለማያውቅ መግለጫው ከዚህ እንደሚከተለው ደበሰበሰ ያለ ነበር ።

ቅዳሜ ዓድዋ ያለውን የሸዋ ጦር እንዲወጉ ጦሩን ከሦስት ላይ ከፍዬ አንዱን ተጠባባቂ አድርጌ እንዲዋጉ አዘዝሁ . . .የግራው ጦር ወደፊት ቀድሞ መቸገሩን ስለሰማሁ የዳቦርሚዳ ጦር እንዲረዳ ትእዛዝ አስተላለፍሁ . . . በዓድዋ በኩል ጦርነቱ ተጧጡፎ ነበር ። . . .በሌላ ውም በኩል በድፍረት ወደፊት እየተኸርኰደኰዱ የሚዋጉትን የጠላት ወታደሮች ለማገድ ስለ አልተቻለ ሁሉም ሊበላሽ ቻለ . . . ከዚያ ወደተ ነሣንበት ወደ ማውሪያና ወደ ሰሜን ሁሉም ፊቱን መልሶ ሰፊ መተ ላለፊያ እየፈለገ ሔደ . . . ከኔም ጋር ኤሌናና ቫሌንዛኖ ወደ አዲቀ ይሀ መጥተዋል . . . የዳቦርሚዳ ወሬ የለኝም ። የአሪሞንዲንና የአልቤ ርቶኒን ሁኔታም አላውቅም ። ወሬውም የተለያየ ነው . . . ስለመፍረሳ ችን አደገኛ ሁኔታም የማቀርበው አሳብ የለኝም ። የተዋጉትን የነጭ ወታደሮች እንደገና አዘጋጅቶ ለማዋጋት ግን አይቻልም ።

የጥቁሩም ወታደር የበለጠ ተዘበራርቋል ፥ ምራላቸው እንደነጮቹ ተበጥብጧል ። በዚህ ፈንታ የጠላቶቻችንና የሽፍቶቹ ሞራል ከፍ

1 Adua, E. Bellavita,P. 227



ብሏል ። የአዲግራት ምሽግ በማይሸነፉ ሽፍቶች ስለተከበበ ምሽጉን ለቀው እንዲወጡ ማዘዝ የሚቻል አይመስለኝም ። ዛሬ ሌሊቱን ወደ ሰገነይቲና ወደ አሥመራ እሔዳለሁ ። በዚሁ ጊዜ ነገ ጧት አሥመራ የሚገባው ላምቤርቲ የቅኙን አገር አስተዳደር ይዞ ከመንግሥቱ ጋር ይጸጸፋል ።

ባራቲዬሪ [1]

በበኩሉ ይኸው የርሱ ምክትል ጄኔራል ላምቤርቲ ከባራቲዬሪ በፊት እ.ኤ.አ. በመጋቢት 2 ቀን ይኸንኑ የመሸነፍ ወሬ ለጦር ሚኒ ስትሩ አስተላልፏል ። በዚህ ጊዜ ሌተና ጄኔራል ባልዲሠራ ከሮማ ባራቲዬሪን ለመተካት ተሾሞ ሲመጣ በዓድዋ በኢጣልያ ጦር ላይ የደረሰውን አደጋ አያውቅም ነበር ። ወሬውን የሰማው የዓድዋ ጦርነት በሆነ በአራተኛው ቀን ምፅዋ የገባለት ነው ። እንደዚሁም የባልዲሠራን በርሱ እግር ተሾሞ ምፅዋ መግባቱን ባራቲዬሪ በትክክል ያወቀ አይመስልም ። የሆነ ሆኖ ፥ በዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ አሸናፊነት የኢ ጣልያ ተሸናፊነት በቅድሚያ ከላምቤርቲ ቴሌግራም የተላለፈውን ወሬ የስቴፋኒ የወሬ ወኪል በነዛው ጊዜ በመላው አውሮፓና ዓለም ትልቅ ያልታሰበ ቦምብ የፈነዳ ያህል መገረምን ፥ በኢጣልያ አገር ታላቅ ድንጋጤንና መሸበርን አፈራ ። በተለይ የዚህ የጦርነቱ አደጋ የሚመለከተው የቅኝ ግዛት አጥብቀው በመፈለግ የታወቁትን የመን ግሥቱ መሪዎች የነበሩትን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ፍራንቼስኮ ክሪስፒን ፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ብላንን ፥ የጦር ሚኒስትሩን ሞቼኒን የገንዘብ ሚኒስትሩን ሶኒኖንና መሰሎቻቸውን ስለሆነ ፥ ኃፍረቱ ሐዘኑና ድንጋጤው በተለይ በነዚህ ላይ በርክቶ የሚሆኑትን አሳጥቷቸው ነበር ። በዚህም ጊዜ የግራ ክፍሎች "ያልነው ደረሰ" በማለት ሐዘን የተደባለቀበት ደስታ ሲሰማቸው እነዚያ ራሳቸውን ዘቅዝቀው መደበቅ ግዴታቸው ሆኖ ነበር ።

ወሬው በየከተማውና በየባላገሩ በተሰማ ቁጥር ነጋዴው ሱቁን እየዘጋ ፥ ገበሬውም እርሻውን እየተወ ፥ ጥበበኛውም ከምድብ ሥራው እየወጣ በሩጫ ወሬ ወደሚገኝበት ሥፍራ እየሔደ ፥ አባትና እናት የልጆቻቸውን ፥ ሚስቶች የባሎቻቸውን ሞትና ደህንነት ለመጠየቅ እየተርገበገቡ ሲሸቀዳደሙ በየመንገዱና በየአደባባዩ ፥ "ወይ ልጄ! ወይ ባሌ!" የሚሉት ዋይታና ለቅሶ ይሰማ ነበር ። አንዳንዶቹ ጠና ያሉት እንደ ማበድ እያሉ በግድ እየተያዙ ታሰሩ ። አንድ ልጅዋ ባራተኛው ባታዮ ጦር ውስጥ የዘመተባት ሴት ያራተኛው ባታዮ ጦር ምንም አል ተረፈም የሚሉ ወሬ እንደ ሰማች ልበ በሽተኛ ነበረችና ወዲያው

1 Memoire d' Afrique P. 393

የልቧ ትርታ ቆሞ ሞተች ።[1] ከዓድዋ ቀደም ብሎ ከኢጣልያ ወታደሩ እየተመለመለ በሚላክበት ጊዜ በሚላኩት ወታደሮችና በሸኝዎቹ ልብ የነበረው ደስታ ካሁኑ ሐዘንና ለቅሶ ጋር ሲመዛዘን ነገሩ የተለያየ ነው ። እንዚያው ጣልያኖች የዚያን ጊዜ የደስታቸውን ዋጋ አሁን ከልክ ያለፈ በማዘን የበለጠ ሲከፍሉ ታዩ ። የፊተኛው የደስታው መሠረት ፣ "የኛን ጦር አንድ የጥቁር ጦር አይደፍረውም" በሚል እምነት ነበር ። አሁን ግን ፣ በናቁት ሕዝብ ተሸንፈው ያልታሰበው ሲደርስ ሐዘኑን የበለጠ ጽኑ አደረገው ።

ከፍተኛውና መካከለኛው ሕዝብ ይኸን የመሰለ ሐዘንና ዋይታ ሲደርስበት ፣ የወጣቶቹና የግራ ክፍሎች ሠራተኞች ሞልሚንቲ ፖምፒዎ ዠራርዶ በሚባል የሶሺያሊስት አማካሪ (ዴፒቲ) እየተመሩ በስድስት መቶና በሰባት መቶ እየተከፈሉ በሮማ "ሆ!" እያሉ አንዳንድ ጊዜም የቀኝ ክንፎችን ለማናደድ ፣ "ምኒልክ ሕያው ይሁን" እያሉ በጩኸት ሲዞሩ ከተማው የመሸበር መልክ ያዘ ። ነጋዴውና የከተማው ሰው እየፈራ በሩን እየዘጋ ተደበቀ ። በሌሎችም ከተሞች ወሬው በተዛመተ መጠን ግርግሩና ግጭቱ በርክቶ ነበር ።[2] በሚላኖ በግራና በቀኝ ክንፎች መካከል ግጭት ተፈጥሮ አንድ ሰው ሲሞት ዐሥራ አራት ቆሰሉ ። በፓቪያ ያሉ የባቡር ሠራተኞች ሁለተኛ የኢጣልያ ወታደር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይላክ ሐዲድ ያፈራርሱ ጀመር ።

ከሁሉ ከተሞች ግርግሩ የነበረው በዋናው ከተማ በሮማ ነበር ። በዚያም ወጣቶቹ በጩኸት ትእይንት በሚያደርጉበት ጊዜ አዲስካልኬ የሚባለው መስፍን በትሪቶኒ እውራ ጐዳና በጋሪ ተቀምጦ ሲያልፍ አግኝተው በፊቱ ላይ ጭቃ እየረጩ ከበቡት ። ወዲያውም "ምኒልክ ሕያው ይሁን" በል እያሉ አስፈራሩት ። እርሱም "ኢጣልያዊ ስለሆንኩ ኢጣልያ ሕያው ትሁን እላለሁ እንጂ ምኒልክ ሕያው ይሁን አልልም" እያለ ሲጨቃጨቅ ፣ በመካከሉ የንጉሡ ዘበኞች (ካራቢኒሪዎች) ደርሰው በግድ አስጥለውት በጋሪው ለማምለጥ ቻለ ። በዚሁ ጊዜ የመሸነፉ መዋረድ አንሶ እዳር ቆሞ የሚመለከተውን በጣም ያስገረመውና ያነደደው ፣ "ክሪስፒ ይውደቅ ፣ ምኒልክ ሕያው ይሁን" የሚለው ጩኸት በወጣቶቹ ዘንድ መሰማት ነው ።

"ምኒልክ ሕያው ይሁን" ብለው ወጣቶቹ እየጮሁ መስፍኑም እንዲጮህ ለማስገደድ የሞከሩበት ምክንያት የጦርነቱን አጀማመር ከሥር ጀምረው በራሳቸው በሶሺያሊስት ጋዜጦች ይከታተሉ የነበሩት

1 La Prima Guerra d' Africa , R. Battaglia, PP. 793—800.

2 Douze ans en Abyssinie . . . PP. 528-530; Adua, Belavitta P. 394.



በተለይ የግራ ክንፎቹ ፣ የኢጣልያን መንግሥት አጥቂነትና የኢትዮጵያን ተከላካይነት ፣ ያፄ ምኒልክን ያላሠለሰ እርቅና ሰላም ፈላጊነት ፣ የክሪስፒንና የአጋሮቹን አብሪትና ተጋፊነት በሰፊው ተረድተው በትችት ጊዜ ሁሉ ፣ "ምኒልክ ጥሩ ክርስቲያን ክርስፒ ግን አረመኔ ነው" እያሉ ያትቱ ዠመር ። በዚህም ላይ በአላጌ የሞቱት የኢጣልያ ወራሪ የጦር መኰንኖች በክብር መቀበራቸውን ፣ ኮሎኔል ጋሊያኖ ከነጦሩ ብዙ ደም አፍሶ ሞት ሲገባው ሳለ ፣ ከመቀሌ በሰላም ተሸኝቶ ወደ አዲግራት ሔዶ ከወገኖቹ መደባለቁን ያውቁ ስለነበረ ፣ በዚህ ዓይነት የተገፋው የኢትዮጵያ ጦር ማሸነፉ የሚገባ ነው በማለትና እላይ እንዳልነው ፣ "ምኒልክ ሕያው ይሁን! ምኒልክ ክርስቲያን፣ ክርስፒ አረመኔ" እያሉ በመጮህ የፖለቲካ ባላጋራዎቻቸውን በንዴት ለማብሸቅ ነው ። ከንጉሡ ጀምሮ መሳፍንቱ ሁሉ የቅኝ አገዛዙን የሚደግፉ ፣ "እኛም ሔደን እንዋጋ" እያሉ የሚጋበዙ ነበሩባቸው ። ወጣቶች በዚህ ቀን አዲስካልኬ የሚባለውን መስፍን ጭቃ እየረጩ ያጉላሉበት ምክንያትም ጠቅላይ ሚኒስትሩን ክሪስፒን በመደጋገፍ አገሪቱን እዚህ አደጋ ላይ ያደረሱት የበለጠ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባሎች ጭምር ናቸው በማለት ነው ።

እነዚሁ ወጣቶችና እንደዚሁም ወደ ኢትዮጵያ ለጦርነት የመጡት የሹማምንቱም ፣ የወታደሩም ቤተሰቦች በጠቅላላው በዚህ ጦርነት ያገራቸው ውርደት የተሰማቸው ሁሉ ተሰብስበው ፣ "አንድ ድል እንጠብቃለን" ወይም "አንድ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚደመድም ድል ሳታገኝ እርቅ የለም" እያለ ባራቲዬሪን በቴሌግራም ያጣድፍ ወደ ነበረው ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ክሪስፒ ቤት ሔደው እያወኩ የስድብ ናዳ በማውረድ ግማሹም ደንጊያ እየወረወረ ቤቱን በመደብደብ አስቸገሩት ። በእንደዚያ ያለ መከራ ላይ ሳያስበው የወደቀው ፍራንቼስኮ ክሪስፒ በፖሊስ ኃይል ተከላካይነት ትእይንተ ሕዝብ አድራጊዎቹ ከተወገዱለት በኋላ ፣ "የወታደርዎን ደም ጊዜ ጠብቀው ይበቀሉለት" የሚል ቃል ለንጉሡ ጽፎ ከጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ተሰናበተ ።

የዓድዋ ድል ፣ በኢጣልያ አገር ይኸን የመሰለ ሽብር ሲፈጥር በሌላው ዓለም የሰጠው ስሜት የተለያየ ነው ። የድሉ ወሬ በፈረንሣይ አገር ሲሰማ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ በቀለምና በዘር አንድነት ፣ የተነሣ ወይም በፖለቲካ ዝንባሌ ምክንያት የነጭ ዘር ወይም የቀኙ ክፍል ጥቃት ቅር ያላቸው ባይጠፉም ፣ አብዛኛው የፈረንሣይ ሕዝብና በተለይ የመንግሥቱ መሪዎች በደስታ ተቀብለውታል ። ጣልያኖቹ ስሜን ኢትዮጵያ ከገቡ ጀምሮ የፈረንሳይን ወኪሎችና ዜጎች ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ያስቸግሩ ነበር ። በዚሁ ምክንያት

ባራቲዬሪ ኤርትራ ብሎ በያዘው ግዛት ይገኝ የነበረውን የፈረንሳይን የላዛሪስት ሚሲዮን እ.ኤ.አ. ጥር 22 ቀን 1895 ዓ.ም. በትእዛዝ ካገር እንዲወጡ ማድረጉ ይታወሳል ።[1]

በመስኮብ አገር ያለው ስሜት ከዚሁ ከፈረንሣይ ጋር ተመሳሳይ ነው ። እንዲያውም የመስኮብ መንግሥት ወዳጅነቱን ለመግለጽ የቀይ መስቀል ጓድ ወደ ኢትዮጵያ ልኮ በዓድዋ ጦርነት የቆሰለውን ሁሉ በማከም ስለረዳ ፣ ምስጋና ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብሏል ። በዚሁ አጸፋ የጀርመንና የእንግሊዝ መንግሥታት ግን ፣ የዓድዋን ድል የሰሙት “ይኸ እንደምን ሊሆን ቻለ” በሚል የመገረምና የቁጭት ስሜት ፣ ነው ። በዚሁ ምክንያት የእንግሊዝ ምክር ቤት ተከፍቶ ጉዳዩ በሚጠናበት ሰሞን የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ጆ ናትናኤል የሚባለው ስለ ዓድዋ ድልና ስለ ኢጣልያኖች መሸነፍ ንግግር ሲያደርግ ፣ “. . .የሐበሾች ማሸነፍ የኢጣልያንን ጦር መፍረስ ብቻ ሳይሆን ለግብፅ አደገኛና በአፍሪካ ላለው የአውሮፓ አቅዋም አሥጊ ነው ። ስለዚህ ወደፊት ገፍቶ አደጋውን ማቆም የተከበበውንም ከሰላን አድኖ የግብፅን ወሰን በደንብ መከላከል ያስፈልጋል . . . ኢጣልያም ለባንዲራዋ ክብር ስትል ፣ እንደገና ተዋግታ የመሸነፍ ብድሯን እንደምትመልስ እተማመናለሁ . . .” የሚል ቃል ይገኝበታል ። ይኸንንም የመጨረሻውን የድል በቀል በተናገረ ጊዜ የትልቁ ምክር ቤት አባሎች አሳቡን በጭብጨባ ተቀበሉት ።[2]

ሔንሪ ስታንሌይ የሚባለው እንግሊዛዊ ፣ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ዓድዋ ድል አንድ የኢጣልያ መጽሔት አዘጋጅ ለጠየቀው መልስ ሲሰጥ ፣ “. . .ኢጣልያኖች የደረሰባቸው ውድቀት አሳዛኝ ነው ። በመላው የእንግሊዝ አገር መገረምን አትርፏል ። ከሰላን በእንዴት ያለ ወታደራዊ ጥበብ የያዘው ባራቲዬሪ አሁን የደረሰበት በትር በራሳችን እንደ ደረሰብን ቆጥረነዋል. . .” የሚል ቃል ይገኝበታል ። ከዚሁ አያይዞ “ሥልጡኑ ዓለም ኢጣልያንና በአበሻ አገር ያሉትን የወታደሮቿን ሁኔታ አተኩሮ ይመለከታል ። ያገሪቱ ክብር ስለተነካ ኢጣልያ በምትወስደው እርምጃ ክብሯ ወይም መዘበራረቋ ሊታይ ይችላል. . . የባራቲዬሪ ድል መሆን ቢያሳዝነንም ፣ መጨረሻው አይደለም . . .ተስፋ እንደ ምናደርገው በብልሃቱ አሻሽሎ መሸነፍን ለምኒልክ መልሶ ሊሰጠው ይችላል. . .”[3] ብሏል ።

1 Adua, Bellavita ,P. 167; Nota Al, Chap. XIV
2 Abyssinia ,E. Scarfoglio . . . PP.263-264
3 Precursori del'Impero, R. Truffi, P. 195.
La Prima Guerra D, Africa-R. Bataglia PP. 705-710



ከሁሉ የበለጠ የኢጣልያ ተሸናፊነትና የኢትዮጵያ አሸናፊነት በመላው ዓለም ፣ በገዥዎችና በተገዥዎች ዘንድ የሚያስከትለውን የፖለቲካና ያገዛዝ ውዝግብ በትክክል የተመለከተ የሎንዶን ታይምስ ጋዜጣን የሚመራው ጸሐፊ ነው ። እርሱም እንደዚህ ሲል አትቷል ።

“. . .የኢጣልያኖች በምኒልክ መሸነፍ በታሪክ ሲታወስ የሚኖር ነው ። ይኸም ድል አድራጊነት እስከዛሬ አረመኔ እየተባለ በአውሮፖች ይናቅ የነበረውን የአፍሪካ መንፈስ የሚቀሰቅስ ነው ።”

ካለ በኋላ ከዚሁ አያይዞ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ አውስቶ ፤

. . .ኢጣልያኖች ከሌሎቹ አውሮፓውያን ዝግንነትም አያያዝም አንሷቸው አይደለም ። ወደ አፍሪካ ቅኝ አገር ለማግኘት ፊታቸውን ባዞሩበት ሰዓት በቀላል ሊያዝና ሊገዛ የሚችለው ክፍል ቀደም ብሎ ስለ ተያዘ ወደ አልተያዘው (ወደ አስቸጋሪው) ተመለከቱ ። ኢጣልያኖች ንጉሡን የአሳመኑ መስሏቸው ሲታለሉ እርሱ ግን ፣ (ምኒልክ) በመሣሪያ እየተዘጋጀ የአጸፋውን ኃይል አሳያቸው ። የርሱም ድል ማድረግ የመላ አፍሪካ ድል ነው ። ይኸም ዓይነቱ አስተያየት ወደፊት እያየለ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው ። በነዚህ አገሮች (አፍሪካውያን) ዘንድ ወሬው በነፋስ ክንፍ በረሃውን ሁሉ አቋርጦ በፍጥነት የሚሮጥ ስለሆነ ፣ ከጫፍ እስከ ጫፍ አሁንም ታውቋል ። ወደፊትም አፍሪካ አውሮፓን ማሸነፉ ስለታወቀ ፣ ቁጥሩ ይኸን ያህል ተብሎ ሊገመት ለማይችለው የአፍሪካ ሕዝብ የሕይወት ንቃትና የመከላከል ስሜት ያሳድራል ። ስለዚህ ጉዳዩ አደገኛ ስለሆነ በኢጣልያኖች መሸነፍ ተደሳቾች መሆን ምቹ አይደለም ። ይኸ መሸነፍ የሁላችንና የሌሎችም ጭምር መሸነፍ ነው ። የሥልጣኔ መሸነፍም አይደለም ፤ የቅኝ አገር ገዥ የሆነችውና የነገይቱም አውሮፓ መሸነፍ ነው. . .”[1]

ጸሐፊው “መደሰት የለብንም ። የሁሉም አውሮፓ ውድቀት ነው” የሚለው ፣ በኢትዮጵያ ማሸነፍ በኢጣልያኖች መሸነፍ ፈረንሳዮችና መስኮቦች መጠነኛ ደስታቸውን በየጋዜጣው ስለገለጡ ለማስጠንቀቅ የሰነዘረው ነው ። መላው አውሮፓ በአንድነት ጉዳዩን በጽሞና አጢኖ ወዲያውኑ ይህ የዓድዋ ድል በአፍሪካና በሌላውም ኋላቀር አገር ላደረሰው የኩራትና የትምክህት ስሜት ካሁኑ መፍትሔውን እንዲያበጅ የሚጋብዝ ነው ።

ይኸ ሁሉ በጠቅላላው የሚያሳየን እንደ ስታንለይ አባባል ፣ “ኢጣልያ በጥቁሮች ሐበሾች በመሸነፍ ኃፍረት ተከናንባ እንደዚሁ አትቀርም ። ሌላ ቁጥሩ የበረከተ ጦር ልካ እንደገና ተዋግታ ክብሯን

1. L'Italia in Africa, Serie Storico Militare, Vol 1, Tome II, A Vitale ,PP. 122-123.

ትመልሳለች" የሚል ስሜት እንዳላቸው እንገነዘባለን ። የእንግሊዞችም ዋና ሥጋታቸው የኢትዮጵያ ያሸናፊነት ዝና በቅኝ አገሮቻቸው በአፍሪካና በተለይም በግብፅ አስተጋብቶ ያገዛዛቸውን አቅዋም እንዳያናጋባቸው ነው ።

በዚሁ ጐን ፥ የጀርመን መንግሥት ከኢጣልያ ጋር ባለው የስምምነት ውል ጋዜጦቹና ባለሥልጣኖቹ የኢጣልያን መሸነፍ በሐዘንና በንዴት እንደ ተቀበሉት የበለጠ በዚህ የመሸነፍ ውድቀት ለማጽናናትና የወዳጅነቱን ስሜት ለመግለጽ ራሱ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ዊልሄም ሮማ ድረስ ሔዶ የኢጣልያን ንጉሥ ጐበኘ ።[1]

እውነትም በመካከለኛው ምሥራቅና በግብፅ አገር ዓረቦቹ የኢትዮጵያን አሸናፊነት በደስታ እንደ ተቀበሉት ይታያል ። በዚሁ በድሉ ሰሞን የኢጣልያ መርከብ የዓድዋ ድል ወሬው ሳይሰማ ወታደር ጭና ወደ ምጥዋ ለመድረስ ፖርትሳይድ የቆመ ጊዜ በደረሰው የመሸነፍ አደጋ ምክንያት ወታደሩ ከመርከብ ወርዶ ፖርትሳይድ እንዳይታይ ተከልክሎ ነበር ። የጦር መኰንኖቹ ግን ፥ በፈቃዳቸው ወርደው ወዲያና ወዲህ ሲሉ በዚያ የነበሩ የፈረንሣይና የመስኮብ ፥ የግሪክና የሕንድ ተወላጆች እያዩ አፌዘውባቸዋል ። ዓረቦቹም ጠጋ እያሉ ፥ "ጣልያን አይረባም" እያሉ ይጮሁባቸው እንደነበረ ተመዝግቦ ይገኛል ።[2] የዓድዋ ድል አድራጊነት በተለይ በኢትዮጵያውያን ዠግንነት የተፈጸመ ቢሆንም የድሉን ደስታ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር የተጫነውም፥ ገና ያልተጫነውም የእስያም ፥ የአፍሪካም ሕዝብ ተካፍሎታል ማለት ይቻላል ። በዓድዋ የምኒልክ አሸናፊነት ፥ "አውሮፓዊ በዕውቀት የገፋ ፥ በትምህርት የተራቀቀ ፥ በሀብት የለማ ስለሆነ በጥቁርና በብጫ ሕዝብ ፈጽሞ ሊሸነፍ አይችልም" የሚባለውን የቆየውን እምነትና አባባል ስለ አስተባበለው የቅኝ አገር ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በየትኛውም ክፍለ አህጉር ያለው የነጭ ዘር በነገሩ ታምበታል ። በአውሮፓም ድጋፍ ኢጣልያ በቶሎ ይኸን ውርደት መበቀል እንዳለባት ያብዛኛው አውሮፓዊ ምኞት ነበር ።

1 L' Italia in Africa, A Del Boca, P. 720.
2 Sul Campo di Adua, Ximenes, P. 2 L'Italia in Africa ,A. Del Boca, PP.694—701.



# ምዕራፍ ዐርባ ስምንት

## የጄኔራል ባራቲዬሪ ፍጻሜ

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አፍሪካ የመጣው እ.ኤ.አ. በ1887 ዓ.ም. ከጄኔራል ሳን ማርሳኖ ጋር ነው ። ወደ አፍሪካ እንደተሻገረ በዚሁ በሳን ማርሳኖ ሥር ሲሠራ ቆየ ። በሳን ማርሳኖ እግር ጄኔራል ጄኒ ባልዲሠራ ፥ ከርሱም ቀጥሎ ጄኔራል አሬሮ ፥ ከአሬሮም ጋንዶልፊ ተከታትለው በተሾሙበት ጊዜ ፥ ባራቲዬሪ ወደ ኢጣልያም አገር እየሔደና እየመጣ በነዚህ ሥር ሆኖ በኰሎኔልነት ማዕረግ በብዙ ክፍል ሲያገለግል ኖረ ። በኋላም በ1892 ዓ.ም. ጄኔራል ጋንዶልፊ ተሽሮ በርሱ እግር ኤርትራ በሚል ሥያሜ የያዙትን የሰሜን ኢትዮጵያን ክፍል ጠቅላይ ገዥነት ተሾመ ።

በማናቸውም ረገድ እርሱም እንደ ሥራ ጓደኞቹ ለድል አድራጊነቱ በመተማመን በጦርነቱ ዋዜማ ሮማ ላለው ወዳጁ ለጄኔራል ዳልቬርሜ በሚጽፍለት ደብዳቤ ውስጥ ፥ "ለሁሉም ተዘጋጅቻለሁ በመጋቢት ወር ላይ ትግሬን ለመውረር የሚያስችለኝ ኃይል አገኛለሁ" ይል ነበር ። በሌላው ደብዳቤ ደግሞ እውነቱን ደበቅበቅ እያደረገ እርሱን ጦርነት እያማረውና የሚዋጋው እንዳጣ ያህል በመቁጠር ፥ "...ጠላት ለመመከት እንዲገደድ አዘንግቼ ለመውጋት እስባለሁ... ለመዋጋትም ተስፋ አለኝ" እያለ ይጽፍ ነበር ።[1]

የዓድዋ ጦርነት በየካቲት 23 ቀን ሊደረግ ሲል ፥ በየካቲት 22 ቀን ማታውኑ ምክር ሲደረግ ግን ጄኔራሎቹ "እንበለው ጠላትን አለበት ድረስ ሔደን ፥ እኛው ፈልገን እንውጋው" ባሉበት ሰዓት እርሱ፥ "ጠላት ኃይለኛ ነው ምክራችሁ የድፍረት ነው ። ለማንኛውም የጦር ሠራዊታችን ሞራል እንደምን ነው" ያለውን ስናስታውስ ፥ ውሎ አድሮ በቁርጠኛው ቀን ግን እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያን ጦር ከመናቅ እንደ ተቆጠበና በተቻለ ለመጠንቀቅ እንዳሰበ ይታያል ።

ዳሩ ግን ፥ ጦርነት መከፈቱ ግዴታም ውዴታም ሆኖበት ጦርነቱ ተጀምሮ የማንባር ቀደሙ ጦር ከተመታ በኋላ ፥ ከጦርነቱ ላይ እየሸሸ

1 Precursori del'Impero, R. Truffi, P.195.

በላዩ ላይ እየጋለበ የመጣበትን ያገር ተወላጅና የጣልያን ጦር እንደ ገና ልብ ሰጥቶ አቋሞ ለማዋጋት በፈረሱ ላይ እንደሆነ አንድ ጊዜ፣ "ቪቫ ኢታሊያ" ቀጥሎ "ሳቮያ"* ብሎ እየጮኸ በሞከረበት ጊዜ ባንድ ወገን በረኃብና ጥም፣ በሌላ በኩል የሌትና የቀን ጉዞ ድካም፣ በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያውያኑ ቁርጠኛ አወጋግ ያስደነበረው ጦሩ ሊቆምለት ስለአልቻለ በመጨረሻ በሽሽቱ እርሱም ተጋባበት ። እንዲያውም ከአብዛኛው በራሪ የግረኛ ወታደር እርሱና ጥቂት አጃቢ ሹማምንቱ በፈረስ ስለነበሩ ቀድመው አዲ ቀይሀ ገብተዋል ።

ባራቲዬሪ፣ ከቅርብ የሥራ ጓደኞቹ ጋር በሚሸሽበት ጊዜ የቀኙ አዝማች ጄኔራል ዳቦርሚዳ ገና በመዋጋት ላይ ስለነበር፣ ፍጻሜውን ለመጠበቅ ያባራሪዎቹ ተጽእኖ አላስቻለውም ። በሽሽቱ ጊዜ እንቅልፍ ካጣ ውሎ አድሮ ነበርና በፈረሱ ላይ እርሱም ሌሎቹም እያንጐላጁ ሲሔዱ፣ መንገድ አሳስተው ወዳላሰቡት አቅጣጫ ርቀው ሔደው ነበር ይባላል ።

እንደዚሁም፣ በዚሁ በሽሽት ጊዜ አንዳንድ ጊዜ ፈረሱን እያስጋለበ ሲሔድ፣ መነጽሩ ከፊቱ ላይ ወድቆ ጠፋ ። ቆም ብሎም እንዳይፈልግ አባራሪዎቹ ስለሚያጣድፉት የዕውር ጭፍኑን ይጋልብ ዠመር ። በዚህም ጊዜ ከጭፍሮቹ አንዱ ቲኔንቴ ማሮዚ "እሾዐ አለ! ወደ ቀኝ አሁን ጫካ አለ! ወደ ግራ አሁን ራስዎን ዝቅ ያርጉ ወይም ከፍ ያርጉ" እያለ በአጠገቡ ሆኖ ይመራው ነበር ። በዚህ ዓይነት ችግር ከዓድዋ አዲቀይሀ፣ ከአዲቀይሀ ሰገነይቲ ደርሶ ዐረፍ ባለበት ሰዓት ከጦር መኰንኖቹ አንዱ ቲኔንቴ አሊሳንድሮ ሳፔሊ ቀረብ ብሎ ሊያጽናናው ሲሞክር፣ "...እኔ ከጉዳይ አልገባም! ኢጣልያ ግን መበቀሏ አይቀርም"[1] አለ ። ከሰገነይቲ ወደ አሥመራ ሔዶ አዲስ ተሾሞ ከመጣው ከጄኔራል ባልዲሠራ ጋር ከተገናኘ በኋላ ምጥዋ ሲደርስ እግሩ ተጥመለመለ ። ቆሞ መራመድም ስለ አቃተው የሚራመደው በሁለት ሰዎች ተደግፎ ነበር ። ጠጋ ብለው ጋዜጠኞች ለማነጋገር ሲፈልጉ፣ "ዕንቅልፍ ካጣሁ ስምንት ቀን ሆኖኛል" ከማለት በቀር ሊያነጋግራቸው አልቻለም ።[2]

የሆነ ሆኖ፣ ከዚህ በኋላ አሥመራ ላይ በጄኔራል ባራቲዬሪ ለመፍረድ አዲስ ልዩ የጦር ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ. ሐምሌ 14 ቀን 1896 ዓ.ም.

* "ቪቫ ኢታሊያ" ማለት 'ኢጣልያ ትኑር' ማለት ነው ። "ሳቮያ" ደግሞ የኢጣልያ ነጋሢዎች የሚጠሩበት የዘራቸውና የትውልዳቸው መደበኛ ሥፍራ ነው ።

1 Memorie d' Africa, A. Sapelli, P.122.

2 La Giornata di Adua, R.Mazzucconi, P. 355.



ተቋቋመ ። ክሱንና ፍርዱን ለመመልከት የተመደቡት አዲስ ከሮማ የመጡት ከፍተኛ የጦር ባለሥልጣኖች ፤

፩ኛ/ ሌተና ጄኔራል ደል ማይኖ ኮንቴ ሊኬኖ... ሊቀመንበር

፪ኛ/ " " ሐሽ ኒኮላ ......... አባል

፫ኛ/ ማዦር ጄኔራል ጋዙሬሉ ፊሊፖ ........ "

፬ኛ/ " " ቢዘስቲ ሉዊጂ ....... "

፭ኛ/ ካባሊዬሬ ራቤራ ሚኬሌ ............ ጸሐፊ

የመንግሥቱ ጠበቃ ፊስካሌ ሚሊታሬ የሚባለው ክሱን በሁለት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ከፍሎ እንደዚህ ሲል መሥርቶታል ።

፩ኛ/ ይቅርታ በማይደረግለት መንገድ እንዲመራው በውስጡ የተመደበለትን ጦር ሠራዊት በማያሸንፍበት አኳኋን መጋቢት 1 ቀን 'የካቲት 23' በጠላት ሠራዊት ፊት ወስዶ አጋፍጦ እንዲሸነፍ አድርጓል ።

፪ኛ/ ከጦርነቱ ሥፍራ በ12 ሰዓት ከ30 ደቂቃ (ስድስት ሰዓት ተኩል) ሸሽቶ በመሔድ ተዋጊውን ሠራዊት ከተሸነፈ በኋላ እስከ መጋቢት 3 ቀን ድረስ ያለምንም አዛዥና ያለምንም መሪ ትእዛዝ አደጋ ላይ ትቶት ሔዷል የሚል ነበር ።

ለዚህ መልስ ራሱ ጄኔራል ባራቲዬሪና ጠበቃው በሰጡት ቃል ፤

፩ኛ/ ጄኔራል በራቲዬሪ ሁኔታው አስፈሪ መሆኑን በመገንዘብ ከአዲግራትም ከሣውሪያም ወደኋላ ጦሩን ይዞ ከመረብ ወዲያ መመለስ ሲያስብ አራቱ አዝማች ጄኔራሎች ወደፊት ገፍተን እንዋጋ ብለው እንዳደፋፈሩት ፤

፪ኛ/ ከኢጣልያ አገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ፣ "እስካሁን ያደረግሃቸው ጦርነቶች ወግ የሌላቸው 'Tisi Militare' ናቸው" በማለት በቴሌግራም ወቅሶ የታወቀ ጦርነት ለማድረግ መገፋፋቱን፣

፫ኛ/ አዝማቾቹ ጄኔራሎች የሰጣቸውን ፕላን ሳይከተሉ በየፊናቸው ሔደው ለየብቻ መዋጋታቸውን፣

፬ኛ/ የሸሸበት የአዲቀይሀ አቅጣጫ ለተዋጊው ሠራዊት ማናቸውንም ትእዛዝ ለማስተላለፍ የቴሌግራፍና የመላከተኛ ድርጅት ስለሌለ፣ በዚህም ላይ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች በጠቅላላው ጦርነቱን ይፈልጉ እንደነበረ እርሱም በቂ እርዳታ ጠይቆ ሳይሳካለት

መቅረቱን ፣ ምጥዋም ያለው ስንቅ ግለቁን ስለተረዳ ፣ ከመዋጋት በቀር ሌላ ምርጫ እንደሌለው ብዙ የሰነድ ጽሑፍ በማቅረቡና ከሞትም ከምርኮም ፣ ተርፎ የተመለሰው የተጠባባቂው ጦር አዛዥ የነበረው ጄኔራል ኤሌና ከችሎቱ ላይ ቀርቦ የሰጠው የምስክርነት ቃል የርሱን አባባል ስለ ደገፈው ፤

ፍርድ ቤቱ ጠበቃውና ተከሳሹ ከዚህ በላይ ያቀረቡትን መልስ ከመረመረ በኋላ ፣ በጄኔራል ባራቲዬሪ አመራር ጉድለት ፣ ቸልተኝነትና ችሎታ ማጣት ቢኖርበትም ፣ በጠቅላላው ሆነ ተብሎ የተፈጸመ የጦርነት ወንጀል አልሠራም ። ስለዚህ ከማንኛውም የጦር አዛዥነት ወርዶ በግሉ ሊኖር ይችላል ተብሎ በነጻነት ተለቀቀ ።[1]

ከዚያም ወዳገሩ ገብቶ የጦርነት ማስታወሻውን ጽፎ ከጨረሰና ካሳተመ በኋላ፣ በተወለደ በ60 ዓመቱ እ.ኤ.አ. በ1901 ዓ.ም. ሞተ ። ይህ ጄኔራል በመጀመሪያ ወቅት የከሰላ አሸናፊ ፣ የኮዓቲትና የሰንዓፌ ድል አድራጊ ተብሎ ከመረብ ምላሽ ወዲያና ወዲህ ሲል ሕዝቡም ፣ ሠራዊቱም በያለበት በሆታና በአክብሮት እየተሰለፈ ፣ ሚሲዮናውያኑ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ሲቀበሉት ሥልጣናዊ ሕይወቱ በደስታ የተከበበ ነበር ። ባለፈው እንዳነበብነው ፣ ከኮዓቲትና ከሰንዓፌ ድል በኋላ ኢጣልያ አገር የተደረገለትን የክብር አቀባበል ያነበብነውን እንመለስበትም ። ወደዚህ አድጋ የጣለውም ሲመረመር ያ አሸናፊነትና በዚህ አሸናፊነት ያገኘው ክብር ነው ። እንደ አብዛኛው የጦር መሪ ጄኔራል ኦሬስቴ ባራቲዬሪ ሕይወቱ በክብር ተጀምሮ በሐማር የተፈጸመ ነው ።

1 Adua, E. Bellavita, PP.394-413; Memoire d'Afrique, PP.531- 540.





በዓድዋ ጦርነት የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ

ኢታሊያ ኢን አፍሪካ ከሚባለው መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ ዘጠኝ

## በምክር ቤት የተነሣው ሁካታ — በሮማ የመንግሥት ለውጥ — ያዲሱ መንግሥት አዲስ ፖለቲካ—የክሪስፒ ፍጻሜ

በኢጣልያ አገር ክሪስፒ፣ ምንም እንኳን የሥራ ስንብቱን ለንጉሥ ኡምቤርቶ ቢያቀርብ ሹመቱን የሚቀበለው እስኪታወቅ ድረስ እርሱም ሚኒስትሮቹም በጣም የተጠሉ ቢሆኑም፣ በሥፍራቸው እንዲቆዩና የተለመደውን ሥራ እንዲቀጥሉ ተደረጉ። በዚህም ጊዜ በዓድዋ መሸነፋቸውን ከሰሙ ወዲህ ቅኝ አገር ይቅርብን በሚሉት በሬፑብሊካኑና ቅኝ አገር ለኢጣልያ ያስፈልጋታል በሚሉት የቀኝ ክንፍ ቡድኖች መካከል ክርክሩ በውጭም በምክር ቤቱም አልበረደም ነበር። ብዙዎቹ የባራቲዬሪ ፍርድ ወደ ሮማ ይምጣና በርሱ ብቻ ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ በክሪስፒና በሚኒስትሮቹም ላይ ይፈረድባቸው የሚሉ ነበሩ።[1]

የቀኙ ክፍሎች ሌተና ጄኔራል ባልዲሠራ ይዞ በሔደው ጦር ላይ በርከት ያለ ጦር ተልኮ እንደገና የበቀል እርምጃ ይወሰድ የሚሉ ነበሩ። ክሪስፒም የዚህኑ ፖለቲካ ወደ ፍጻሜ የሚያደርስ ከራሱ ቡድን ውስጥ የተከበረው ሳራኮ ዡሴፒ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥፍራ እንዲይዝ ለንጉሡ አሳስቦ ነበር። ዳሩ ግን፣ በተደረገው ውይይትና በግራ ክንፎች መቃወም ባሁኑ ጊዜ የቀኝ የፖለቲካ ቡድን አባል የሆነው የርሱ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በፍጹም እንደማይሆን ተወሰነ።

ከዚህ በኋላ፣ እ.ኤ.አ. በመጋቢት 4 ቀን (የካቲት 27) ምክር ቤቱ ተከፍቶ የምክር ቤት አባሎች ከሌላው ቀን በተሟላ አኳኋን ገብተው ስፍራቸውን ያዙ። ባንድ ወገን የዘማች ቤተ ዘመድ ስድብ፣ በሌላው ወገን የሬፑብሊካኖች ወቀሳ ያደከመው ክሪስፒ፣ የሥራ ጓደኞቹን ሚኒስትሮች እንዳስከተለ ራሱን ቁልቁል ደፍቶ ወደ መሬት እያየ በሐዘን መልክ በምክር ቤት ውስጥ ገብቶ በስፍራው ተቀመጠ።

---

1 Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca, PP. 709. La Prima Guerra d' Africa- R. Bataglia - PP.693 750,

በዚህ ጊዜ ፣ የፊተኛው ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ተነቦ የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ክሪስፒን ለንግግር ጋብዞት ወደ መናገሪያው ሥፍራ ሲወጣ ታላቅ ጸጥታ ሆነ ። ሁሉም ዐይኑን እርሱ ፊት ላይ ሰክቶ ይመለከተው ጀመር ። ወዲያው "ስንብት ጠይቄ ንጉሡም ስንብቱን እንደ ተቀበሉት ለምክር ቤቱ ሳስገነዝብ ክብር ይሰማኛል. . ." የሚለውን ቀዳሚ ቃል እንደ ወረወረ ሃምሳ ከሚሆኑ ከርሱ ወገኖች በቀር በምክር ቤቱ ያሉት በሙሉ ለመመልከት የገባው ጭምር አንድ ጊዜ በኅብረት ፣ "እንኳን ለቀቅህ! እንኳን ለቀቅህ! ውጣ! ውጣ!" በሚል ጩኸትና ስሜት የጭብጨባ ነጐድጓድ አወረዱበት ። በግራ በኩል ያሉት አግካሪዎች "አሶጣው አሶጣው"* የሚል የጩኸት ድምፅ አሰሙ ። ጩኸቱ ቆም ሲል ክሪስፒ ፣ "ካቢኔው የተለመደውን ተራ ሥራ ለመምራት በስፍራው ይቆያል" የሚል ድምፅ ሲያሰማ ዛቫታሪ የሚባለው አባል ፣ "ያንተ ነገር በቅቶናልና ልንሰማህ አንፈልግም" ብሎ ጮኸበት ። የቀሩትም ከመቀመጫቸው እየተነሡ ጣታቸውን እየዘረጉ የስድብ መዓት ያወርዱበት ጀመር ። ታላቅ ሁከት በምክር ቤቱ ሊፈጠር ሲል ፣ ፕሬዚዳንቱ ለማረጋጋት ሞክሮ በፍጹም የማይቻል መሆኑን ሲገነዘበው ፣ "ለዛሬው ይበቃል" ብሎ ምክር ቤቱን ስለዘጋው በግድ ሁሉም ተበተነ ።[1] በውጭም በአመራሩ የተበሳጩ ክሪስፒን ለመደብደብ በመንገድ ላይ የተጠባበቁ ነበሩ ። በጸጥታ ጠባቂዎች ብርታት ዳነ ። ሰሞኑንም እቤቱ ብቻውን በነበረበት ሰዓት ያለቅስ ነበር ይባላል ።[2]

ከዚያ በማግሥቱ ፣ በፍራንቼስኮ ክሪስፒ እግር የተከበረው ማርኬዜ አንቶኒዮ ዲ ሩዲኒ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥፍራ እንዲይዝ ተሾመ ። በርሱም አቅራቢነት በዕድሜው ገፋ ያለው ሪኮቲ በንጉሡ ፈቃድ የጦር ሚኒስትርነቱን ሥፍራ ተሾመ ። በዚሁ ሰሞን ኢምቢሪያኒ የሚባለው የሬፑብሊካኖቹ ወገን በፊትም ቅኝ አገር ይቅርብን ይል ነበረ ፤ አሁንም ከአፍሪካ በፍጹም ለቀን እንውጣ የሚል አሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ነበር ። ነገር ግን ክርክር ተደርጎ አዲሱ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋትን ዓላማ ትቶ ከመረብ በመለስ ባለው ግዛት ብቻ መከላከልና ካፄ ምኒልክ ጋር የሰላም መንገድ ፈልጎ ምርኮኞቹን ማስለቀቅ በሚል ሐሳብ ላይ ፣ በዚሁ ክርክር ተደርጎ ይኸው አሳብ 219 የድጋፍ ድምፅ በ119 የተቃውሞ ድምፅ ሰጥተውበትና 72 ድምፅ ሳይሰጡ ቀርተው በአጠቃላይ የድጋፉ ድምፅ ብልጫ ስላለው ውሳኔው አልፎ ጸደቀ ።

* Alla Porta alla ! porta !

1 La Giornata di Adua,, R. Maz., PP. 323-325

2 Fracesco Crispi, Giuseppe Ardau. PP.393-395.



በዚሁ ጊዜ የቀኝ ክፍሎች ፣ "በጥቂር ወታደር ተሸንፎ መታረቅ ለኢጣልያ ታላቅ ውርደት ስለሆነ ፣ አስቀድሞ ክሪስፒ ባዘዘው መሠረት ማናቸውንም መሥዋዕት አድርገን ለጄኔራል ባልዲሠራ ጦር ልኮ ምኒልክን መውጋትና ማሸነፍ ይገባል" እያሉ ይከራከሩ ነበር ። ለዚሁ መልስ ፣ አዲስ የተሾመው ሪኮቲ የሚባለው የጦር ሚኒስትር "ምኒልክ የማይሸነፍ ነው ፤ ጦርነቱን እንደገና ለመጀመር መቶ ሃምሳ ሺ ወታደር አንድ ሚሊያርድ ተኩል ሊሬ ያስፈልጋል. . . ስለዚህ ባልዲሠራ ከመረብ በለሳሙና ወዲህ እንዲመለስ ዐሥር የባታዮ ጦራችንም ወደ ኢጣልያ እንዲመለስ አዝዣለሁ ። ጠላትም ጠቡን የቀጠለ እንደሆነ ተመልሰው ይሔዳሉ" የሚል መልስ ሰጠ ። ይኸን የመሰለው መልስም ፣ በንዴት በቀል የፈለጉትን የክሪስፒን ወገኖች በፍጹም አላስደሰተም ። የሆነ ሆኖ ፣ በጣም ከሁሉም የተጠበቀው ንግግር ያዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የአንቶኒዮ ዲ ሩዲኒ ስለሆነ ፣ ለዚሁ መጋቢት 17 ቀን ምክር ቤቱ እንደገና ስብሰባ አደረገ ። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም በፕሬዚዳንቱ ጋባዥነት ከመናገሪያው ላይ ወጥቶ ባደረገው ንግግር ውስጥ ፤

> ንጉሡ የፊተኛውን መንግሥት ስንብት ተቀብሎ ሪኮቲንና አዲሱን መንግሥት ሾሟል ።. . . በአፍሪካ ኢጣልያ ትኑር እያሉ የወደቁትን ዠግኖቻችንን እናስባቸው. . . ጄኔራል ባልዲሠራ በተሻለ መንገድ ከምኒልክ ጋር ንግግር አድርጎ ጉዳዩን በሰላም መንገድ እንዲጨርስ ትእዛዝ ተላልፎለታል ። ለኛ የሚጠቅመው እስኪረጋገጥ የጠቡ ሁኔታ ሊቀጥል ይችላል. . . ይሁን እንጂ ፣ በማናቸውም ረገድ የመስፋፋት ፖለቲካ እንደማናደርግ በምክር ቤቱ ፊት ዋስትናዬን እሰጣለሁ. . . ትግሬንም ለመውረር ምንም ዓይነት ዓላማ የለንም. . . ንጉሡ ትግሬን ውሰድ ብለው ቢሰጡን እንኳ ጥቅማችንን የሚቃወም መጥፎ ስጦታ ስለሆነ አንቀበልም . . . በትግሬ ሀብት አለ ብለው የሚያምኑ በመካከላችን እንዳሉ ኢትዮጵያን የማያውቁ ናቸው ፣. ."[1]
> የሚሉ ቃላት ይገኛሉ ።

ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ስብስብ ያለ ሰላማዊ አሳብ ፣ በብዙዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ በዚሁ እንዲፈጸም በምክር ቤቱ በድምፅ ብልጫ ከጸደቀ በኋላ ፣ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለጄኔራል ባልዲሠራ በአዲግራት ተከበው የተቀመጡትን ኢጣልያኖች እንዲያድንና አጋሜን ለቆ እንዲወጣ ካፄ ምኒልክ ጋር ግንኙነት አድርጎ እስረኞቹ የሚለቀቁበትን መንገድ እንዲፈልግ ትእዛዝ አስተላለፈለት ። ይኸም ባለፈው ምዕራፍ ዐፄ ምኒልክና ዠኔራል ባልዲሠራ በማገሮር ሳልሳ በኩል የተጻጻፉበት ውሳኔ ያላገኘው መሆኑ ነው ።

1 Storia Diplomatica . . . Durante il [Regno di Menelik . . . , C- Rossetti, PP. 185- 186.

ይሁን እንጂ ፥ ይህ ውሳኔ በምክር ቤቱ ውስጥ ያሉትንም በውጭ
ያሉትንም የቀኝ ክፍሎች አናደዳቸዋል ። እነርሱንም በጣም የቆጫቸው
ሰፊ ግዛት ከማጣቱ የበለጠ በጥቁር መንግሥት ተሸንፈው ታረቁ
የሚለው የውርደት ወሬ ነው ። ስለዚህ ለቀኝ ክፍሎች አንጋፋ የሆ
ነው ክሪስፒ ምንም ከሥልጣኑ ቢሰናበት ፥ ለንጉሡ ከዚህ ቀጥሎ ያለ
ውን የጸጸትና ወደ አዲስ ጦርነት የመገፋፋት ደብዳቤ ጽፎ ተሰናበተ ።

ግርማዊ ሆይ !

አለቃው ስለሆኑ ሠራዊትዎን ይበቀሉለት !

የሐበሻ በትር ሳይቀጣ ቢቀር ዝግንነትና የዝብዱ ሙያ በኛ
ዘንድ እንደሞቱ ይቆጠራሉ ። በውስጥዎም ያሉት የሚታረድ የበግ
መንጋዎች እንጂ ፥ መዋጋትና ማሸነፍ የሚችሉ የወታደር ቡድኖች
አይደሉም ማለት ነው ። ይኸም ይዞታ የኢጣልያንን ኃይልና መከበ
ሯን የማይፈልጉትን የውጭ ጠላቶችና እንደዚሁም ንጉሣዊው አገዛዝ
እንዲወድቅ የሚፈልጉትን የውስጥ ጠላቶች* የሚረዳ ነው ። አሁን
በአፍሪካ የደረሰው ከመጋቢት ወዲህ በፓርላማችን የጦር ሚኒስት
ርዎ ያደረገው የፈሪ ዲስኩር** ውጤት መሆኑ ነው ። ምኒልክ የማይ
ሸነፍ አይደለም ! የማይሸነፍ ያስመሰለው በጋዜጣና በምክር ቤታችን
መንግሥታችን ሊወጋው አለመፈለጉ ስለ ተጻፈና ስለ ተነገረ ነው ።

ይኸንኑ የመሰለ ውድቀት በ1866 ደርሶብን ነበር ። በአድሚራል
አልቤኒ ስንፍና የጠላት ድል ተረጋገጠ ። በዚሁ ዓይነት ስንፍናችን
አውስትሪያ በባሕር ኃያል ለመሆን በቃች ። ግርማዊነትዎ ይኸን
ፖለቲካ ይለውጡ ። ሁሉም ነገር መፍትሔ አለው ። ግርማዊነትዎ ከፈ
ለጉ መኖር የማይገባውን አረመኔ ሕዝብ ለመቅጣት የሚችሉ በሚሊ
ዮን የሚቆጠሩ ክንዶች በግርማዊነትዎ ዙሪያ ይዘረጋሉ ። ያለዚያ በሥ
ልጣኔ ላይ እውነተኛ ስድብ ነው ። ይች ደብዳቤዩ በልብዎ ውስጥ
ለመግባት ኃይል እንደምታገኝ ተስፋ አለኝ ። በማናቸውም ረገድ
ቃሌ ባይደመጥም ፥ እኔ ግን በወታደርነቴና በሠራተኛነቴ የተነሣ
ለግርማዊነትዎ ይኸን በማሳሰብ ተግባሬን እንደ ፈጸምሁ ዐውቃለሁ ።

ፊርማ ክርስፒ [1]

ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ፥ ኢትዮጵያ እንደልብ የሚጋለብባት አፍ
ሪካዊት አገር እንደ ሆነች ያምን ነበር ። ባለፈው ፥ "የትግሬ
አገር ለኢጣልያ ክፍት ነው ሳንይዘው ብንቀር የኛ ስንፍና ነው" ብሎ

---

*የግራ ክንፎች በዚህ ዘመን እንደ ፈረንሳዊ መንግሥት በሬፑብሊክ ለመተዳደር ጽኑ
ፈቃድ ያላቸውን የውስጥ ጠላት ሲላቸው ፥ ኢጣልያ ኃያል እንዳትሆን የምትፈልገው
የውጭ ጠላት የተባለችው ፈረንሳይ ናት ።

**የፈሪ ዲስኩር የሚለው አዲሱ የጦር ሚኒስትር ሪኮቲ "ምኒልክ የማይሸነፍ ነው"
ብሎ በምክር ቤት የተናገረውን በመውቀስ ነው ።

1 F.Crispi, G. Ardali, PP. 396-398



የነበረውም በዚሁ መንፈስ ነው ። የአላጌን ውድቀት እንደ አንድ
ትልቅ መደፈር ቆጥሮት አንድ ጊዜ ፥ "አንድ ድል እጠብቃለሁ" ሌላ
ጊዜ "የኢትዮጵያን ጉዳይ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ የሚደመድም ድል
ልታስገኝ ይገባል" እያለ አፍሪካ ላለው አዝማቹ ለባራቲዬሪ ቴሌግ
ራም ያዥጐደጉድለት እንደነበረ የሚታወስ ነው ። አሁን ያ መን
ፈስ በፍጹም ከድቶት ከመሰደብ ፥ ከመንጠጥ ፥ ከሽረትና ከውርደት
አድርሶታል ። ይልቁንም ባልጠበቀው መንገድ አንድ ጊዜ ለዘለቄታው
የውጫሌውንም ጉዳይ ፥ የኢጣልያንም የመስፋፋት ምኞት የሚደ
መስስ የድል አድራጊነቱ ዕድል ከርሱ እጅ ወጥቶ በኢትዮጵያ
እጅ ሲገባ ቢናደድ ቢበሳጭ እውነት አለው ። ነገር ግን በጣም የሚያ
ሳዝነው ለንጉሡ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ፥ "መኖር የማይገባው አረመኔ
ሕዝብ" በሚል ቃል የኢትዮጵያን ሕዝብ መሳደቡ ነው ። በነዳቦርሚዳ
ደብዳቤ ላይ እንደ ተገነዘብነው ፥ ክሪስፒም በፍጹም የኢትዮጵያን
ውስጣዊ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ታሪኳንም አያውቅም ማለት ነው ።
በጥንታዊነት ፥ ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ቅድሚያ ነበራት ። በአሁኑ ጊዜ
ካለው ዘመናዊ ሥልጣኔ ወደኋላ ብትቀርም በጥንታዊ የአክሱም ሥል
ጣኔ ከቀደምቶቹ አንዷ መሆኗን አላጤነውም ፤ ወይም በወረራ ምኞት
አእምሮው ስለታወረ ሳያስበው በናቀው ሕዝብ መሸነፉም ስላደ
ነዘዘው የሚያውቀውንም ላለማወቅ ዐውቆ ልቡን አደንድኗል ማለት
ነው ።



**የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ**

**ከፍራቴሊ ትሬንስ መጽሐፍ**



የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክሪስፒ
ከፍራቴሊ ትሬነስ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሃምሳ

## ዳግማዊ ምኒልክ መረብን አልፈው ያልሔዱበት ምክንያት ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በዓድዋ ጦርነት ዕለት ይኸን ከፍ ያለ ድል አድራጊነት ካገኙ ወዲህ ፣ ከመረብ እስከ ምጥዋ ድረስ ያለው የኢጣልያ ጦር "የምኒልክ ጦር መጣ መጣ" እያለ ሲሸበር ፣ እርሳቸውም ወደ ሐማሴን ለመዝለቅና ጨርሶ የኢጣልያንን ኃይል ከጠረፍ ለማጥፋት በአሳባቸው ሳይመጣ አልቀረም ነበር ። ወደ ሐማሴን ለመዝለቅ ከዓድዋ ወደ እንትጮና ወደ ፈረስ ማይ መሔዳቸው ለዚሁ አሳብ መሆኑን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴም ፣ ግራዝማች ዮሴፍም ጠቅሰውታል ። ወደ ሐማሴን ያልዘለቁበትን ምክንያት ጸሐፌ ትእዛዝ ብዙ ሠራዊት የሚያሳልፍ መንገድና በቂ ውሃ በመጥፋት መሆኑን ገልጸዋል ። ይኸም የማይታበል መሆኑ በብዙ የኢጣልያ መጻሕፍት ተረጋግጧል ።[1] ግራዝማች ዮሴፍ ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት ለእርቅ ሳልሳን በመላኩ ምክንያት መሆኑን እንገለጹበት ላይ የመጣው ለተንኮል እንጂ ለእርቅ አለመሆኑን ጠቁመዋል ። በእውነትም ከአዲስ አበባ ሳይነሡ በተለይም ከአምባ አላጌ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ ኢጣልያኖች ሲመጆቸው ውጊያ ፣ ሳይመቻቸው እርቅ ፈላጊዎች መሆናቸውን በሰፊው ተረድተውታል ። ከዓድዋ ድል በኋላ መረብን አልፈው ኢጣልያኖቹን ለማጥፋት ኃይላቸውን ቢተማመኑት ኖሮ የሳልሳ መምጣት መሠረት ሆኖ ወይም ለይሉኝታ ወይም ከኢጣልያ ጋር የእርቅና የዝምድና ነገር አምሯቸው ወደፊት መግፋትን አይተውትም ነበር ።

ከዚህ በፊት በ1879 ዓ.ም. ዶጋሊ ላይ ራስ አሉላ የኢጣልያንን ጦር ካሸነፉ በኋላ ምጥዋን ገሥግሠው አልያዙም ። ቢፈልጉ መያዝ ይችሉ ይሆናል ። በኋላ ግን የመዘዙን ብዛት አመዛዝነው እንደ ተዉት የታወቀ ነው ። አዲስ ጦር ካስመጡ በኋላ ፣ እንዲያውም ጣልያኖቹ ወደፊት አልፈው ሰሐጢን ይዘው መመሸጋቸውን ዐፄ ዮሐንስ ሰምተው እነሱን ለመውጋት በእሥመራና በጊንዳ በኩል ከስማንያ ሺ ጦር የበለጠ ይዘው መጥተው የሰሐጢን ምሽግ መድፈሩም ካንድ ወር

[1] La Prima Guerra d' Africa, Pal. Crispi, Chaps. VIII-IX

በላይ በዚያ ፀረሀማ ቀበሌ ለመቆየት የስንቁ፣ የውሀና የግሩ ጉዳይ ሳያስችላቸው ቀርቶ ወደ ዓድዋ መመለሳቸውን ባለፈው ያነበብነው ትዝ ይለናል። የምጥዋን ወደብም ለመውረር አልከጀሉም። የምጥዋን ወደብስ ለጊዜው ቢይዙ ኖሮ የወደብ አስተዳዳሪነቱን የሚይዝና ከባሕር በኩል የሚመጣን ጥቃት ለመከላከል ችሎታ ያለው ኃይል ነበራቸውን? ብሎ ያጠያይቃል። ለዚያውም ለዶጋሊው አልቂት ተቆጥተው ያኮረፉት እንግሊዞች ዝም ብለው ይመለከቱ ነበርን?

አሁንም ዐፄ ምኒልክ፣ ከዓድዋ ድል በኋላ ወደፊት ለመግፋት እንቅፋት የሆኑ ብዙ ችግሮች በፊታቸው እንደ ተደቀኑ አይጠረጠርም። ከነዚህም ውስጥ በትክክል የምንረዳቸው፤

ሀ/ ከቤቱ ከንብረቱ ከተለየ ስምንት ወራት ያህል ያለፈው የጦር ሠራዊትና ሹማምንት፣ ከረምት ከመግባቱ በፊት ወደ ቤቱ መመለስን ከመናፈቅ በቀር አዲስ ጦርነት ለማድረግ ምኞት አልነበረውም። ቢኖረውም ችግሩ አላስቻለውም።

ለ/ የተዋጊው ጦር ከነጓዙ ከገረድና ካሽከሩ ጋር ቁጥሩ ከመቶ ሺ ስለሚበልጥ፣ ለዚህ ሁሉና ለከብቱ ጭምር የሚበቃ ስንቅ፣ ሣርና ውሀ ይልቁንም በቆላማው በምጥዋ አካባቢ ስለማይገኝ፣ ለመዋጋት ምኞት ቢኖረውም እንኳን አይችልም። ከዓድዋ ጦርነት በፊት እንኳን በዚሁ የተነሣ በወታደሩና በትግሬ ባላገር መካከል በዘረፋና በስንቅ ችግር ግጭት እየተደረገ ቅርታ መግባቱን ተመልክተናል።

ሐ/ ከግራኝ አህመድ አነሣሥ በኋላ ይልቁንም የጐንደር መንግሥት ከደከመ ወዲህ፣ ከማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን ቁጥጥር ውጭ ሲኖሩ በዐፄ ምኒልክና በስመ ጥር መኳንንቶቻቸው በነራስ ጐበና፣ በነደጃች በሻህ አቦዬ፣ በነራስ ወልደ ጊዮርጊስ፣ በነራስ ተሰማ፣ በነራስ መኰንን ብርታትና ትጋት በቅርብ ጊዜ በዘዴም በጦርነት ኃይልም ወደ እናት አገር ቢተጠቃለሉት አውራጃዎች የየአካባቢው ገዥዎች ቀድሞ የለመዱትንና አሁን ያጡትን ሥልጣን ለማግኘት የልብ አምሮትና ምኞት እንደሚኖራቸው፣ እንደነበራቸውም ግልጽ ነው። የየአካባቢው ባላባቶች የሥልጣን አምሮታቸውን ለመፈጸም ያፄ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግሥት ጋር ሲዋጉ መድከም እንደሚረዳቸው የታወቀ ነው።



ስለዚህ፣ በዓድዋ የደከመውን ጦር እስከ ምጥዋ ድረስ እየመሩ ሲሔዱ፣ ከኋላቸው ምን እንደሚጠብቃቸው አይታወቅም። እንኳን የቅርቦቹ ባላባቶች ይቅሩና አንዳንድ ተመልካቾች፣ "እርስዎ መረብን ሲሻገሩ ባባታቸው አልጋ መቀማት ቅር ያላቸው ራስ መንገሻ የትግሬን ጦር ይዘው ከኋላ ሊወጉዎት አስበዋልና ቢበቃዎት ይሻላል" ብለው የመከሩዋቸው የትግሬ ተወላጆች አሉ ይባላል። በአላጌ ጦርነት ጊዜ፣ "ያባቴን አልጋ ተቀምቻለሁና እርዱኝ" ብለው በምስጢር ለእንግሊዝ መንግሥት ደብዳቤ የጻፉት አሁንም ቢመቻቸው፣ ይኸውም ማለት ዐፄ ምኒልክ ቢደከሙ፣ ራስ መንገሻ ጉልበታቸውን ቢተማመኑበት በኃይላቸው ለመጠቀም እንደማይመለሱ የታወቀ ነው። ሁለቱ ቢዋጉ ደግሞ የሁለቱ ውጊያ ለማን እንደሚጠቅም መረዳቱ ለማንም አያዳግትም። ባለፈው ጊዜ፣ የኢጣልያ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር የጠበቀውና ያጣው ይኸንኑ የርስ በርስ ጦርነት ነው። የርስ በርሱን ጦርነት ቢያገኝ፣ እንደገና ለመመለስ ይችል ነበር። "እስካሁን ከጦርነት ያልተለዩት ራስ መንገሻ ከኋላ ሊወጉዋቸው አይችሉም" ብለን ብናምንም፣ ከቀረው ችግር ጋር የዚህ ወሬው መሰማቱ ብቻ ወደ ጥርጥር መውሰዱ የታወቀ ነገር ነው። በብዙ ድካም ተጠቃሎ የተሰባሰበው የኢትዮጵያ ግዛት ሳይናጋ እንዲረጋ የተፈለገ እንደሆነ፣ "ዐፄ ምኒልክ ሠራዊታቸው ዓድዋ ላይ ጣልያንን ድል አደረገ። አሁንም እንዳለ ነው፤ አልተነካም" የሚባለው ወሬ በትክክል የሥልጣን ጉጉት ለነበራቸው ባላባቶች እንዲደርሳቸው ያስፈልጋል። ያለዚያ በስንት ድካም የተጠናከረው የግዛት አንድነት እንደገና ይበታናል ብሎ የሚያሠጋ ይሆናል። በጠቅላላው የነጻነት ጥቅሙና ዋጋው፣ በባዕድ የተገዥነት ጉዳቱ፣ የዚያን ጊዜ የዛሬውን ያህል እንኳን አልተሰበከም፤ ብዙም አልታወቀም። ጊዜው የፊውዳሊዝም (የባለጉልት) ጊዜ ስለሆነ፣ እያንዳንዱ አገሩንና ነጻነቱን ቢወድም፣ አልጋን የመያዝ ምኞት በየአውራጃው መሳፍንት ዘንድ ስለነበረ፣ ይህ እንዳይደርስባቸው ምኒልክና ታማኞቻቸው መጠንቀቅ እንደ ነበረባቸው ይታወቃል።

ከሁሉ የበለጠ ደግሞ በኢጣልያኖች ዘንድ ያለው የድርጅት ሁኔታ አሥጊ ነበረ። ጄኔራል ባራቲዬሪ ድል በሆነ በአራተኛው

ቀን ጄኔራል ባልዲሠራ ቁጥሩ ዐሥራ አምስት
የሚደርስ አዲስ የጦር ወታደር ይዞ ምጥዋ ደርሶ የዓድዋ
ውጊያ ውጤቱን ሰምቶ፤ ድንጋጤም ሽብርም እንደ ደረሰበ
ቢታወቅም ከዓድዋ ጦርነት የሸሹትን ሰብስቦ እንደ ምን
የጦሩን ቁጥር እስከ ሐያ ሺ አድርጎ ከመረብ ባሻገር ያለው
አገር ለመከላከል ቆርጦ ይጠባበቅ እንደነበረ ግልጽ ነው

በዚሁም ጊዜ፤ ሳልሳን ለእርቅ መላኩን ምንም እንኳን አዲ
ጠቅላይ ሚኒስትር ዲሩዲኒ ቢፈቅድለት፤ የዓድዋ ድል ወሬው በሮ
እንደ ተሰማ ሕዝቡ በሐሳብ ተለያይቶ የነበረውን ባጠቃላይ መልስ
እናስታውስ ።

አንደኛው ክፍል፤ መላውን ኢትዮጵያን መያዝ አልተቻለም ። ከ
ረብ ወዲያ ያለው ግዛት ደረቅ ስለሆነ ገንዘብ ከማስወጣት በቀር የ
ረባን ነገር የለምና ቢለቀቅ ይሻላል የሚል፤

ሁለተኛው ክፍል ፤ ጄኔራል ባልዲሠራ ከመረብ ወዲህ ከአስ
እስከ ከሰላ ያለውን ይዞ መከላከሉ የሚገባ ነው የሚሉ፤

ሦስተኛው ክፍል፤ የቅኝ አገር የማግኘቱና የማጣቱ ጉዳይ እንኳን
ወደጐን ቢቀመጥ ባንድ አፍሪካ ውስጥ በሚገኝ ባልሠለጠነ የጥቁ
መንግሥት የኢጣልያ ጦር ተሸንፎ ተመታ ተብሎ በታሪክ ወደፊ
ተጽፎ የሚኖረው ለሞራላችን አሳፋሪ ነገር ነው ። ቢያስፈልግ
ቁጥሩ ሠላሳ ሺ የሚደርስ የጦር ኃይል ለጄኔራል ባልዲሠራ ተጨም
ጦርነቱን መቀጠልና መበቀል አስፈላጊ መሆኑን ወትውተዋል ። በ
ብዳቤ ወይም በጋዜጣ፤ "በሮማውያን ታሪክና ሐውልት መካከል ሆ
ይኸን ምኒልክ ከድሉ በኋላ ያቀረበልንን እርቅ ተቀብለን
ነቱን ብናቆም ያባቶቻችን ሐውልት ይታዘበናል ፤ ዐፅማቸውም ይ
ቅበናል" እያሉ ከክሪስፒ በኋላ መንግሥቱን የሚመሩትን ጠቅ
ሚኒስትሩን ዲ ሩዲኒን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ጋይታኖንና የ
ሚኒስትሩን ሪኮቲን ገፋፍተዋቸው ነበር ።

ነገር ግን፤ ባለፈው የታየው ያፄ ምኒልክ ፤ የመሳፍንቱና የ
ንንቱም ኅብረት፤ የሠራዊቱ ዝግጁነትና ብርታት ስላሠጋው የኢ
ልያ አዲሱ መንግሥት ወደ አፍሪካ እያከታተለ ጦር በመላክ
ውሮፓ የራሱን የኢጣልያንን መንግሥትና ግዛት ወደ ድካም
ሉም ወደ ውድቀት እንዳያደርሳቸው በማሰብ ለሕዝቡም ለም
ቤቱም ይኸንኑ በሰፊው እያስረዱ በማሳሰብ ጦርነቱን የመቀጠ
ነገር እንዲቆም አደረጉ ። ዲ ሩዲኒንና ወገኖቹን የቀኝ ክፍሎችና ጋዘ
ዎቻቸው ፤ "ኢጣልያ አገራችንን የኃፍረትና የሐዘን ጥቁር ልብ



ለዘለዓለም አከናነቧት ፤ ኢጣልያ በአባ ገሪማ ሸለቆ ተቀብራ ቀረች" እያሉ የወቀሳና የስድብ ናዳ ሲያወርዱባቸው መሰንበታቸው የጸጸቱንና የንዴቱን መጠን ያስገነዝበናል ።[1]

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፤ በመሠረቱ በሶሺያሊስቶች እየተረዳ ከሕዝብና ከምክር ቤት የዓድዋን ጦርነት እንዲበቀል ሁካታ ጭምር ከአገር አፍቃሪዎችና ከቀኝ ክፍሎች እልሀ ያስበትን የበቀል ማሳሰቢያ በዚህ ዓይነት ማባበልና ማስረዳት ለማቆም ሞከሯል ። ያፄ ምኒልክ ጦር መረብን አልፎ ምጥዋን ጭምር ልውሰድ ቢል ግን መንግሥቱ የሚደግፈው ጄኔራል ባልዲሠራ ያለውጊያ ሊለቅ አይችልም ። ውጊያም ቢደረግ ከዓድዋ በበለጠ መሥዋዕትነት እንጂ በዋዛ አይፈጸምም። ዓድዋ ድል የሆነው የጄኔራል ባራቲዬሪ የአራት ብርጌድ ጦር ነው ። ከዓድዋ በኋላ ምጥዋ ከባልዲሠራ ጋር የመጡት ጄኔራሎች ካለፉት በደረጃም በማናቸውም ብልጫ ነበራቸው ። ምናልባት ጄኔራል ባልዲሠራ ቢሸነፍ፤ ሌላ ጄኔራል ለመተካት የኢጣልያ መንግሥት ለጊዜው ይችላል ። ዐፄ ምኒልክ ቢሸነፉ ግን ፤ በሰላም መንገድ የተደራጀ ጦር ይዞ ወዲያው የሚተካና የሚዋጋ መቅረቡ በዚያን ጊዜ እንደ ሕልም ይቆጠራል ። የዚያን ጊዜው የመንግሥታችን አቅዋምና ድርጅት ይኸን ዕድል ለማግኘት አይችልም ። ዐፄ ምኒልክ ቢሸነፉ ባራት ማዕዘን ባሉት መሳፍንት ዘንድ አልጋ ለመያዝ ፤ ከማዕከላዊ ሥልጣን ለማፈንገጥ በሚያሳዝን አኳኋን ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የርስ በርስ ጦርነትና ሁከት እንደሚኖር አይጠረጠርም ። በዚህም ሁኔታ እንደ ተለመደው የኢጣልያም ሆነ የሌላ መንግሥት በደንብ ይጠቀምበታል ።

በዓድዋ ጦርነት ፤ ዐፄ ምኒልክ ሙሉ ጦራቸውን ይዘው ከመሳፍንትና ከመኳንንት ጋር ሲዘምቱ ፤ ከኢጣልያ ወገን ጄኔራሎች እንጂ ንጉሡ የቀረው ቀርቶ የጦር ሚኒስትሩ እንኳን አልዘመተም ። የኛ ወገኖች የጦር መሣሪያ የሚያገኙት በግዥና በደጅ ጥናት ሲሆን ኢጣልያኖች ግን ፤ ራሳቸው እየሠሩ እንደ ልባቸው ያገኛሉ ። በአፍሪካ ጦርነት የጥቁር ወታደር የነጭን ወታደር ተዋግቶ ነጻነቱን ያዳነ የለም ። እየተዋጋ አንድ ጊዜ ቢያሸንፍም ፤ መጨረሻውን እየተሸነፈ ሁሉም ከኢትዮጵያ በቀር ለፈረንጆች ተገዥ ሆኗል ። ባሁኑ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ከኢጣልያ በቀር የጀርመንና የእንግሊዝ ሕዝብ ተናደደ። ወሬውም በየቅኝ አገሮቻቸው ዘንድ በመሰማቱ አንድ ዓይነት የነጻነት ስሜትና የመዋጋት መንፈስ በተገዥዎቻቸው ዘንድ እንዳያሳድሩ ሥጋትም ጥንቃቄም ነበረባቸው ። ጊዜው በአፍሪካም በእስያም ለነጭ

---

1 Abyssinia ,Scarfoglio,PP. 342-345

ሕዝብ ያደላበት ዘመን ስለነበረ፣ የዚህ ዘመን ዕድል ነጭን ገዥ ሌላውን የቀለም ሕዝብ ተገዥ አድርጎ ስለ መደበው፣ ያሁኑ ያፄ ምኒልክ ድል አድራጊነትና የኢትዮጵያ ነጻነት በአፍሪካ የዓለም መስኮት ላይ ቦልኮ የታየ ወይም የተሰማ ድንቅና ብርቅ ነው። ከዚህ ድል በኋላ ምኒልክ ይበልጥ ገፍተው የምጥዋን ወደብ ቢወሩ ኖሮ እንኳን ኢጣልያ እንግሊዝም አይታገሥም ነበር።

ስለዚህ፣ ይኸን ሁሉ ስንመለከት ባፄ ምኒልክ መንግሥትና በረዳቶቻቸው ዘንድ የነበረውን ችግር ለማወቅና የተከተሉት ፖለቲካ ስሕተት የሌለበት መሆኑን እንረዳለን። ነገር ግን፣ "ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው" እንደሚባለው ባልዲሠራ አዲስ ይዞ የመጣውን ጦር አስከትሎ ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ ባሉት ቀኖች መረብን አልፎ ቢዋጋ እስከ ወሎ ያለውን አገር ሊይዘው ይችል ነበር" እያሉ ጣልያኖቹ በበኩላቸው ይቆጩ ነበር። ፖላሜንጊ ክሪስፒ የሚባለው ኢጣልያዊ ስለ አፍሪካ ጦርነት ባዘጋጀው የሰነድ መጽሐፍ ውስጥ፣

> በጦርነቱ እንደኛው ብዙ ሰው ያለቀበት ምኒልክ ያላሰበውን ድል ካገኘ በኋላ ስንቅ ሰላጣ ወደ አሥመራ ወይም ወደ ጉራዕ ለመግፋት አልደፈረም። ዤኔራል ባልዲሠራ ባለው ጦር ከምኒልክ ላይ ዋጋ ምኒልክ ወደ አገሩ (ወደ ሸዋ) ከተመለሰ በኋላ መላውን ትግሬንና አጋሜን ይዞ ዓድዋ ላይ ሆኖ ምርኮኞቹን መልስ እያለ መጭውን ጊዜ ዝም ብሎ ለመጠባበቅ በቻለ ነበር። ምኒልክም አሁን እንዳደረገው ሐበሻን ባንድነት ሰብስቦ እንደገና ለመዋጋት ብዙ ዓመታት በፈጀበት ነበር። እኛም በስሕተታችን ኅብረት የሰጠነው አገር (ኢትዮጵያ) ተለያይቶ ሲፈርስ ለማየት ጊዜ እናገኝ ነበር።[1]

ሲል ገልጿል።

በኛም በኩል፣ "የኢጣልያ ጦር ዓድዋ ድል እንደሆነ ዐፄ ምኒልክ ወዲያው ወደ አሥመራ ቢገሠግሡ ኖሮ፣ የኢጣልያን ጦር አጥፍተው የምጥዋን ወደብ እጅ ያደርጉ ነበር" እያሉ ያንጊዜም ዛሬም ብዙ ሰዎች ሲናገሩ በኢጣልያኖችም በኩል፣ "አዲስ ጦር ተልኮ እንበቀል" ሲሉ በዚያን ጊዜ የነበረውን ዝርዝሩን ችግር ለማይመለከት ወይም መመልከት ለማይፈልግ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ቀና መስሎ መታየቱ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ፣ ወደዚህ ወደ አልተረጋገጠ ሁኔታ ለመግባት ሁለቱም የመንግሥታት መሪዎች ከሥጋት ጋር ጥንቃቄ ስለሚያደርጉበት፣ ሁለቱም ወገኖች ለጊዜው በመረብ ክልል መታረቅ የተሻለ ሆኖ

---

1 La Prima Guerra d' Africa, Pal. Crispi, Chaps. VIII-IX.



አገኙት። ጣልያኖችም የመሸነፍ ቁጭታቸውን ተሸክመው እንደ ታገዱ ዐፄ ምኒልክም መረብን አልፈው ኢጣልያን የመውጋት እምሮታቸውን ውጠው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በምክር ቤት ለመማከርቱ ሲያስረዳ፣ "...እንደገና ጦር ልኬ ትግሬን መያዝ አልፈልግም ፣ እንኳን በጦር ለመያዝ ምኒልክ እንደዚሁ ውሰደው ብለው ቢሰጡኝም አልቀበልም" ያለው፣ በዚህ ዓይነት አነጋገር በቁጭትና በቁጣ "አዲስ ጦር ልከን እንበቀል" እያሉ ያስቸገሩትን ለማግባቢያ ያመጣው የንግግር ፈሊጥ ነው እንጂ፣ እንኳን ዐፄ ምኒልክ ውሰድ ብለውት አዲስ በተላከው በጄኔራል ባልዲሠራ ጦር ማሸነፍ እንደሚችል ቢተማመንና እርግጠኛ ቢሆን ኖሮ የመሸነፍ ኃፍረቱን ለብሶ ከሚቀመጥ ይልቅ፣ "ተዋጋ ተበቀል" የሚል ትእዛዝ ለጄኔራል ባልዲሠራ ከማስተላለፍ የሚቦዝን አልነበረም።

ዐፄ ምኒልክ ወደፊት ያልገፉበትን ምክንያት እንደገለጽነው ሁሉ፣ በኢጣልያንም ዘንድ የነበረው የወታደሩና የድርጅቱ አቅምማነስ ፣ የመንግሥቱ ሀብት መቆርቆዝ፣ የሶሻሊስቶች ጦርነት አለመፈለግ ፣ የኢትዮጵያ ኅብረትና ተዋጊነት ሁሉም ተባብሮ ኢጣልያ መንግሥትም የመሸነፍ ኃፍረቱን ውጦ በመረብ ወሰን ለመዋዋል ፣ የተዋጋበትን የውጫሌን ውል ሰርዞ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ለማወቅ አስገደደው። ይኸውም ባለፈው እንዳነበብነው፣ የኢጣልያ መንግሥት አዲስ ጦር ልኮ የደረሰበትን ኃፍረት ሳይበቀል መስማማት በአውሮፓ፣ በተለይ በእንግሊዝና በጀርመን አገር ትዝብትን፣ በራሱ ሕዝብ ዘንድ ሮሮና ቁጭትን አሳድሯል።

# ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

## የኢጣልያ ወታደር በሆኑት ያገር ተወላጆች ላይ የተፈጸመው ቅጣት

በየትም አገር ቢሆን አገሩን ከድቶ ከጠላት ጐን ተሰልፎ ወገኑን የወጋ ተወላጅ እንደ ትልቅ ከሐዲ ተቆጥሮ የሞት ቅጣት እንደሚፈረድበት የታወቀ ነው ። ነገር ግን ይኸን ፍርድ በሥርዓት መስጠት የሚቻለው በአንድ በሕገ መንግሥት በሚተዳደር አገርና መሠረቱ የጸና መንግሥት ሲሆን ነው ። በዚህ በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ በሥልጣኔ ወደኋላ ቀረት ያለችው የኢትዮጵያ ሁኔታ ከዚህ ለየት ይላል ። በጽኑ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተና የተደላደለ መንግሥት ባለመኖሩ ጉልበት ያለው ከሌለው ላይ ዘውድን ለመቀማት የሚችልበት ፣ አንድ መስፍን የውጭ አገር መንግሥት እርዳታ ተደግፎ ሌላውን ጥሎ የራሱን መንግሥት የሚያቆምበት ዘመን ነው ።

ለምሳሌ ፣ የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ያለፈው ዘውድና ሥልጣን በመቀማማትና በጦርነት ላይ ነው ። ዐፄ ቴዎድሮስም የራስ ዓሊን መንግሥት በሕጋዊ መልክ ሳይሆን በጉልበት ወረሱ ። ጉልበት ለማግኘት ባጀማመራቸው ጊዜ ላይ በሱዳን ጠረፍና በቋራ ቆላ ከሚገኙ ሽፍቶች ጋር ፣ "እናንተም እኔም ብንቀማ አብረን እንካፈላለን" ብለው ከሽፍቶች ጋር እስከ መማማል የደረሱበት ጊዜ አለ ።[1] ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር እንግሊዞች ሲዋጉ መንገድ በመስጠት ስንቅ በማቀበል ደጃች ካሣ(ዐፄ ዮሐንስ) እንግሊዞችን ረድተዋል ። ለዚህ ውለታ እንግሊዞች ወዳገራቸው ሲመለሱ ይዘው ለመሔድ ያልፈለጉትን የጦር መሣሪያ ለደጃች ካሣ ሰጥተዋል። በዚህ መሣሪያ ደጃች ካሣ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው የንጉሠ ነገሥትነትን ዘውድ ተቀዳጅተው "ዐፄ ዮሐንስ" ለመባል በቅተዋል ። ዐፄ ዮሐንስ ከእንግሊዞችና ከግብጾች ጦርነት ባገኙት መሣሪያ ከርሳቸው በፊት "የሸዋ ንጉሥ" እየተባሉ ቆይተው በኋላ ፣ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" እያሉ ማኅተም በማሠራት ለንጉሠ

---

1 የቴዎድሮስ ታሪክ በቢርሊን እንደሚገኝ አብነት አሳታሚ ኢኖ ሊትማን ገጽ 6—8

ነገሥትነት ቀረብ ብለው የነበሩትን ምኒልክን አስገብረው የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣናቸውን ለማረጋገጥ ችለዋል ።

በመሣሪያ ብዛት ላይ ዮሐንስ የገበሩት ምኒልክ ፡ የተገዥነት ቁጭታቸውን በልባቸው አድርገው ከየትም በኩል መሣሪያ መሰብሰብን ዋና ዓላማ አድርገው ያዙ ። ኢጣልያኖች በምጥዋ በኩል መጥተው ካፄ ዮሐንስና ከራስ አሉላ ጋር ለጦርነት በተፋጠጡበትም ጊዜ ፡ ምኒልክ በአሰብና በአንኮበር በኩል ከኢጣልያኖች ፡ በጅቡቲና በድሬዳዋ በኩል ከፈረንሣዮች ጋር ግንኙነት በማድረግ የጦር መሣሪያ ይሰበስቡ ነበር ። ኢጣልያኖችና ዐፄ ዮሐንስ ለጦርነት በተፋጠጡበት ጊዜ "አስታርቃለሁ" ብለው ላፄ ዮሐንስም ፡ ለኢጣልያ ንጉሥም ደብዳቤ ጽፈው የነበረውን ተመልክተናል ።

በዛሬ ዘመን ይህ የመሳፍንትና የነገሥታት አቅዋም የሚያስኬድ አይደለም ። በአንድ ሕገ መንግሥትና ምክር ቤት ባለው በተደላደለ መንግሥት ውስጥ በምክር ቤት ፈቃድ መሪው ከውጭ ጠላት ጋር ለጦርነት በተሰለፈበት ሰዓት ያንድ ክፍል መስፍን "ላስታርቅ" ቢል ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው ። ከጠላት ጐን የተሰለፈም ቢኖር በከሐዲነት ያስጠይቃል ። በዘመኑ በመሳፍንትና በባለጉልት በተከፋፈሉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ግን ፡ ሁሉም በየፈናው ወደ ዙፋን ለመውጣት በሚያደርገው ሙከራ እንደልቡ ከውጭ መንግሥት በመላላክ የራሱን አቅዋም ለማጠንከር ይጣጣራል ። ከዚህም በኋላ ምን አልባት በታሪክ ፊት ይወቀሳል እንጂ ለጊዜው ተቀጣ የሚለው ኃይል የለም ።

ያፄ ዮሐንስ ሥልጣን ይበልጥ በተስፋፋበት በተለይ በትግሬና በመረብ ባሻገር የሐጼጋው ራስ ወልደ ሚካኤል ለሹም ተምቤን ምርጫ ልጅ አልታዘዝም ብለው ምጥዋ አካባቢ ለሚገኙት ለግብጾች ገብተው ዐፄ ዮሐንስን ይወጉ ነበር ። ደጃች ደብብ ያፄ ዮሐንስ አጐት የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ላፄ ዮሐንስ አልገዛም ብለው የኢጣልያኖቹ ዋና መሣሪያ ነበሩ። ጣልያኖች አሥመራ ሲገቡ ዋናው መሪ እርሳቸው ነበሩ ። ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ራስ መንገሻ የትግሬን ግዛት አስመርቀው በሚገዙበት ጊዜ የአጋሜው ባላባት ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ ተፈሪ ፡ የራስ መንገሻን የበላይነት በመቃወም ለኢጣልያኖቹ ገብተው ዋና ባለሟል ሆነው ስብሐት የእንደርታን ፡ ሐጎስ የአጋሜን አውራጃ ተሾመው እንደነበር የሚታወስ ነው ። እንደዚሁም በጎጃም ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር የተቀያየሙት ልጆቻቸው ራስ በዛብህና ደጃች በለው ፡ ካፄ ዮሐንስ ጋር የተጣሉት እነደጃች ሥዩም አባኃያል ወደ ሸዋ መጥተው ካፄ ምኒልክ ጋር ይኖሩ ነበር ። የሸዋን ዙፋን የሚፋለሙት መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል ከፈረንሳይ ሰዎች ጋር ሲጻጻፉ ደጃች መሸሻ ሰይፉ



ደግሞ ምኒልክን ለመቃወም ወዳፄ ዮሐንስ ጠጋ ብለው ነበር ። በዚህ ዓይነት የከዳተኝነቱና የታማኝነቱ ጉዳይ በዚህ ዘመን ከዕለት ጥቅምና ከግል ምኞት ጋር የተያያዘ ነበር ። በያንዳንዱ ዘንድ ያገር ፍቅር ቢኖርም ፡ ነገሥታቱ በበለጠ ያገር ፍቅር የሚያድርባቸው የመንግሥ ፍላጎታቸውን ካሟሉና ሙሉውን የንጉሠ ነገሥትነትን ሥልጣን ከያዙ በኋላ ነው ። ከዚያ በፊት ግን ፡ የዙፋን ባላንጣውን ለማጥቃት ሲል ሁሉም ከአገር ጠላት ጋር እስከ መወዳጀት ይደርሳል ማለት ነው። በዚህም ዓይነት ነገሩ በትክክል ከታሰበ ዐፄ ዮሐንስም ፡ ዐፄ ምኒልክም ፡ ራስ መንገሻም ዳኛ ከተገኘ ሁሉም የሚያስጠይቃቸውን ሠርተዋል ማለት ይቻላል ።

ስለዚህ ፡ የኢጣልያ መንግሥት እ.ኤ.አ. በ1879 ዓ.ም. አሰብን ከሩባንቲኖ ኩባንያ በግዥ ፡ በ1885 ዓ.ም. ምጥዋን በወራሪነት ከያዘ ወዲህ በየጊዜው ወደፊት እየገፋ በሐማሴን ፡ በአከለ ጉዛይና በሠራዬ በመስፋፋት ከዚያም ለመግፋት አቅም እንዳልነበረው ሲረዳ በውጫሌ ውል አሳቦ እስከ አሥመራ ድረስ ያለውን ለመያዝ እንደሞከረ ግልጽ ነው ። ከዚህ በኋላ የኢጣልያ መንግሥት በዚህ ሳይወሰን በየአውራጃው ጣልያኖቹን የበላይ ፡ ያገር ተወላጆቹን መኳንንትነታቸውን እያደረገ እየሾመ ፡ ካገር ተወላጅ ውስጥ ለወታደርነት እየመለመለ ፡ ኮትና ሱሪም እያሰፋ ፡ የወር ቀለብ እየወሰነ በመስጠት በባታዮ የተከፋፈለ ልዩ ልዩ ያገር ተወላጅ የጦር ወታደር አቋቁሞ ነበር ። ከራሱ የመንግሥት መሪዎች ምንም አበል የማያገኘውም ወታደርና ባላገር በዚህ አበልና ጥቅም እየተደለለ ወደ ጠላት ይሔዳል ።

ለነዚህም ሁልጊዜ አዛዡ ኢጣልያዊው መኰንን ሲሆን ፡ ካገር ተወላጅም ውስጥ እየመረጠ "ሙንጣዝ ፡ ቡልቅ ባሻና ባሻ ብዙቅ" እያለ እየሾመ ቅጥረኛውንም በምጥዋ ፡ በጊንዳ ፡ በአሥመራ ፡ በከረን ፡ በከሰላ ፡ በአዲ ወግሪ ፡ በሰገነይቲና በአዲ ቀይህ እየደለደለ ያስቀምጣል ። በአስፈለገበት ጊዜና ቦታ እየላከ ከነራስ አሉላና ከነራስ መንገሻ ጋር ሲያዋጋቸው ኖሯል ።

የወር ቀለባቸው ፤ ለእግረኛ ወታደር በቀን አንድ ፍራንክ* ከሃምሳ ሳንቲም ፡ ለመድፈኛና ለፈረሰኛ ወታደር በቀን አንድ ፍራንክ ከስልሳ ሳንቲም ፡ ለሙንጣዝ በቀን አንድ ፍራንክ ከዘጠና አምስት ሳንቲም ፡

---

* በዚህ ጊዜ አንዱ የማሪያቴሬዛ ብር ባገር ውስጥ ፍራንክ አምስት ሊሬ መመንዘሩንና ይህ ምንዛሬ በየወደቦቹ ላይ የሚለዋወጥ መሆኑን ዶ.ሉቢ.ባር ያመለክታል ። ጽሑፉ ፍራንክ ያለው በፈረንሳይ እንጂ በኢጣልያኖቹ ሊሬ ነው ።

ለቡልትባሽ በቀን ሁለት ፍራንክ ፣ ከሠላሳ አምስት ሳንቲም ፣ ለባሻ ባዙቅ በቀን አምስት ፍራንክ ይከፈላቸዋል ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ፣ የኢጣልያ ጦር መረብን አልፎ ወደ አጋሜ ፣ ወደ እንደርታ እየገባ በአዲግራት ፣ በእንትጮ እየመሸገ በተቀመጠበት ሰዓት እነዚሁ ያገር ተወላጆች ባለቆቻቸው የኢጣልያ ሹማምንት እየተመሩ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር በኮአቲት ፣ በሰንዓፌ ፣ በደብረ ኃይላ ያደረጉትን ውጊያ ፣ በኋላም በአላጌና በመቀሌ ከነራስ መኰንን ጋር ያደረጉትን ጦርነት ሁሉ በየምዕራፉ አንብበነዋል ። ያገር ፍቅር በአውሮፓው ዓይነት ባልተስበከበት በዚህ ዘመን እነዚህ ሁሉ ያገር ተወላጆች ስጠላት ተቀጥረው ሲዋጉ ፣ ሲሞቱም ፣ ሲገደሉም አገርንና ወገንን መክዳታቸው በትክክል የሚታወቃቸው አይመስልም ። ዘመኑ "ላለበሰኝና ላበላኝ ጌታዬ እሞትለታለሁ" የሚባልበት ዘመን ነው ። የኢኮኖሚ አለመስተካከል ፣ የልማትና የሕግ እጦት ፣ የጉልተኛነቱ ዘመን ራሱ ይኸን ያሰኛል ።

የዓድዋ ጦርነት የተደረገ ዕለት ፣ ከኢጣልያኖች ጋር ግንባር ቀደም ሆኖ በጄኔራል አልቤርቶኒ አዝማችነትና በሌሎቹም አዝማቾች ውስጥ ተሰልፎ ወገኑን የተዋጋው ያገር ተወላጅ ቁጥሩ 6000 ይደርሳል ። እነዚህም በመካከላቸው አንድ አንድ የሱዳን ተወላጅ ቢኖርም ፣ አብዛኞቹ ግራዝማች ዮሴፍ በደብዳቤአቸው እንደ አመለከቱት ፣ ከሦስት የደጃዝማች አገሮች ከሐማሴን ፣ ከሠራዬና ከአከለ ጉዛይ ተሰብስበው የሰንዓፌንና የኮዓቲትን ፣ የአምባ አላጌንና የመቀሌን ጦርነት የተካፈሉ ናቸው ። አሁንም በአለቆቻቸው እየተመሩ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. በተደረገው የዓድዋ ጦርነት በኪዳነ ምሕረት ፣ በአምባ ራዓዮ ተዋግተው ብዙ የኢትዮጵያን ጦር ፈጅተዋል ። እንዲያውም በኮንቴ ሮሲኒ መጽሐፍና በሌሎችም እንደሚገኘው የነጮ ወታደር በመንገድም ፣ በረኃብና በውሀ ጥምም እየደከመ ሰውጊያ ሲላላ እነርሱ በብርታት እየተዋጉ በብዙ ወገኖቻቸው ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሰዋል ። ከጋልያኖ ጋር በመቀሌ ምሽግ ሲዋጉ ቆይተው በኋላ ወጥተው ከርሱ ጋር ተለቀው የሔዱት የዓድዋ ጦርነት ለት እየፎከሩ በሚያስደንቅ አኳኋን ተዋግተው ጉዳት ማድረሳቸውን ኮንቴ ሮሲኒ የመዘገበውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

1 Douze an en Abyssinie De. Laulibar P.84



የሆነ ሆኖ ፣ ድሉ የኢትዮጵያውያን ስለሆነ ጣልያኖቹና እነዚሁ በኢጣልያ የተመለመሉ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ግማሾቹ በሞትና በሽሽት ሲያመልጡ ግማሾቹ ተማረኩ ። ዐፄ ምኒልክ የካቲት 24 እና 25 ቀን ሬሳ በማስለቀምና በማስቀበር የሁለት ቀን ጊዜ ካሳለፉ በኋላ ፣ በነዚህ በተማረኩት ያገር ተወላጅ ወታደሮች ላይ ለመፍረድ በየካቲት 25 ቀን ችሎት አደረጉ ። በነርሱ ላይ ዐፄ ምኒልክ የእስራት ቅጣት ብቻ ለመፍረድ አስበው እንደ ነበርና በዚሁ እቴጌ ጣይቱ ፣ አቡነ ማቴዎስ ፣ ራስ ወሌና ይልቁንም ከነርሱ ጋር ሲዋጉ የኖሩት ራስ መንገሻና ራስ አሉላ አይሆንም ብለው እንደ ዘመኑ ከፍ ያለ ቅጣት እንዲቀጡ እንዳስፈረዱባቸው በየመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል ። በተለይ ራስ መንገሻ ፣ "የነዚህ ከዳተኞች እጅና እግራቸው ይቆረጥልኝ" ብለው ላፄ ምኒልክ አጥብቀው አቤት ማለታቸውን ግዚሜኔስ የሚባለው የኢጣልያ የጦር መኰንን መዝግቦታል ።[1]

ስለዚህ ፍርድ በኢጣልያን ጦር ውስጥ ሆኖ ዐሥራ ሁለት ዓመት ያገለገለው ዶ ሉሊባር የሚባለው በበኩሉ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ጽፎ ወደ አማርኛ የተረጐምነውን ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት ።

> የቀብሩ ጉዳይ ካለቀ በኋላ ፣ ከጦርነት በተማረኩት አንድ ሺ ሁለት መቶ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ላይ ስለሚሰጠው ፍርድ ንጉሡ ታላላቅ የመንግሥቱን አለቆች ሰበሰቡ ። ምኒልክ በጠባያቸው ምሕረትን የሚወዱ በመሆናቸው ቅጣቱ ቀላል ይሁን የሚሉት ወገኖች ዋና መሪ ነበሩ ። ነገር ግን እቴጌ ጣይቱ በራስ ወሌ ፣ በራስ መንገሻ ፣ በራስ አሉላ ፣ በአቡኑም እየተደገፉ እነዚህ በፈቃዳቸው በኢጣልያ ተቀጥረው ራስ መንገሻን ፣ ራስ አሉላን ፣ ደጃች ባሕታ ሐጎስን ሲወጉ የኖሩ አሁንም የንጉሠ ነገሥታቸውን ጦር የፈጁ ስለሆኑ ሞት እንጂ ምሕረትና ይቅርታ አይገባቸውም ብለው ተናገሩ ።
>
> በዚህም ብዙ ክርክር ሲደረግ ከቆየ በኋላ ፣ አብዛኛው መኳንንት የጣይቱን አሳብ ስለደገፈ እግራቸውን የከዱ ፣ ወገናቸውን የወጉ ናቸውና ፍትሐ ነገሥት እንደሚለው ይፈረድባቸዋል ብሎ ጉባዔው ወሰነ ። ፍትሐ ነገሥቱም አገሩን የከዳ ቀኝ እጅና ግራ እግሩ ይቆረጣል ስለሚል ይኸው ቅጣት ተፈጸመባቸው ። 2

እነዚህ ያገር ተወላጅ ወታደሮች የዕለት እንጀራና ቀለብ ለማግኘትም ሲሉ ፣ ካገራቸው መሳፍንትና መኳንንት ከነራስ መንገሻ ፣ ከነራስ አሉላ ጋር ሆነው ከሚያገኙት የበለጠ ፣ ከኢጣልያኖች ጋር በመሆን ቀለብና ልብስ በማግኘት የተሻለ ምቾት ተሰምቷቸው

1: Sul Campo Di Adua - PP. 35 - 36.
2: Douze ans en Abys. P. 623; I Riccordi di un prigionre di'Meoelik, C. Tedone, PP.44-48-; Menelik II Le Relazioni con L' Italia,E. Falcone,P.133

ነበር ። የኢጣልያ መንግሥት ያሉበትን አገርና አካባቢውን ስለ ያዘ ፥ "ምንም ቢሆን ራስ መንገሻም ፥ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ምኒልክም ፈረንጅን ተዋግተው ሊያስለቅቁት አይችሉምና ለኑሮ የሚያዋጣው ጣልያኖቹን ማገልገል ነው" ብለው በማመንና በመዋጋት በመጨረሻ እዚህ ዓይነቱ አሠቃቂ ቅጣት ላይ ለመውደቅ መብቃታቸው ያሳዝናል ።

ግራዝማች ዮሴፍ ፥ ለሙሴ ሞንዶን ባስተላለፉት ራፖር ላይ ስለነ ዚህ የአገር ተወላጅ ምርኮኞች እንደዚህ ሲሉ ጠቅሰዋል ። "ባሻ ባዙቆች ግን ጦርነት ሲጀመር ባዩ ጊዜ ምንም ገንዘባቸውን ብንበላ አገራችንንና ንጉሣችንን አንወጋም ብለው አስቀድመው ሸሹ ። የቀረ ውን እላጌ ላይ የተማረከውን ምረውት ነበርና በድሉ (የጦርነት ዕለት) የተገኘው ብርቱ ቅጣት ተቀጣ ።"

ከአላጌ ጦርነት ወዲህ ንጉሠ ነገሥቱ በትግሬ ግዛት እንደገቡ ፥ "...ከጠላቴ ጋር ሆነህ የወጋኸኝ ያገር ተወላጅ ወታደር እይቀጡ ቅጣት እቀጣሃለሁ ፥ እርስትህን እነቅልሃለሁ" የሚል ዓዋጅ ዓውጀው በዚህም ዓዋጅ መሠረት ፥ እነራስ ስብሐት መጥተው እንደ ገቡላ ቸው እንብበናል ። የዐድዋ ጦርነት ዕለት በግራዝማች ዮሴፍ ራፖር እንደ ተገለጸው ፥ ግማሾቹ ወገናችንን አንወጋም ብለው የሸሹት በዚሁ ምክንያት መሆን አለበት ።

ነጋድራስ አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ ፥ ዳግማዊ ምኒልክን በብዙ ረገድ ካመሰገኑ በኋላ በነዚህ ያገር ተወላጆች ላይ በተሰጠው ፍርድ ብቻ ነቅፈዋቸዋል ።[1] ነቀፋቸውም የሰው አእምሮ የሚቀበለው ትክክለኛ ነቀፋ ነው ። ነገር ግን ዐፄ ምኒልክ በዚያን ሰዓት ለነዚያ የጠላት ወታደሮች ቅጣቱ ይቅለልላቸው ባሉበት ጊዜ በሐሳብ ያልደገፏቸውን እቴጌ ጣይቱንና ራስ ወሌን በተለይ ደግሞ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከ ታቸውን ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ተቃውመው ለነዚህ ፥ "የቀለለ ቅጣት ይሰጥ" ብለው በንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣናቸው ቢያዙ ኖሮ በላያቸው ላይ ቅርታ ሊፈጥርባቸው ይችል ነበር ። ቅርታውም መንግሥታቸውን ሊያናጋባቸው ይችላል ። ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ወደ ጭከናው ያዘነበላቸው ፥ ባለፈው ዓመት በኮዓቲትና በሰን ዓፌ ጦርነት ጊዜ ያገር ተወላጁ የኢጣልያ የቅጥር ወታደር በነርሱ ወታ ደርና ሹማምንት ላይ በውጊያ ያደረሰውን ጉዳት በማስታወስ ነው ።

እንደዚህ በመሰለ ጉዳይ ፥ በሥልጣናቸው በመጠቀም ከራሶቻ ቸው የተለየ ውሳኔ ማድረግ በዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ የተለመደ አይደለም

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ : : : ገጽ 102—106



እንዳንድ ጊዜ ራሶቹ በርሳቸው ሲመሩ ብዙውን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ በራሶቹ ፈቃድ ይመራሉ ። ይኸን የመሰለው አቅዋም ሁሉን ባንድነት አስተሳስሮ የዓድዋን ድል ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ዘመናቸውም ዘመነ ሰላም እንዲሆን ረድቷቸዋል ።

በፍርድ ሰዓት ፥ በችሎቱ አደባባይ በንጉሠ ነገሥቱ ዠርባ የዓድዋ ለት ሲዋጉ የዋሉት መኳንንትና ወታደሮች አለቃቸው ፥ ዘመዳቸውና ጓደኞቻቸው የሞቱባቸው ሁሉ "ይቆረጡ ይቆረጡ" እያሉ ያውኩ ነበር ይባላል ።[1] እነዚህንም እምቢ ብሎ ማሳዘኑና የፍትሐ ነገሥቱንም ቃል ለውጦ ማሻሻሉ በዚያን ጊዜ አስቸጋሪ ነው ። በሁኔታው ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው በዛሬው መንፈስ አይደለም ። በዚያን ዘመን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በዚያን ቀን በነበረው የንዴትና የቁጭት መንፈስ ነው ። ፍርድ የተደረገው ከጦርነቱ በኋላ በሁለተኛው ቀን ነው ። ይኸም ቀን ሬሳው ተሰብስቦ እንኳን ያላለቀበት ቀን ስለሆነ ፥ በጸጥታና በጽሞና ወንጀልንና ቅጣትን እመዛዝኖ ትክክለኛ ፍርድ መስጠቱ አዳጋች ሆኖ የሚታይ ይመስላል ።

ስለዚህ የሚዛናዊውን ፍርድ የቁጭትና የንዴት ስሜት ተጭኖ በዛሬ አእምሮአችን ሊያስቅቀን የሚችለውን ቅጣት ያን ጊዜ በእነ ዚህ ባልታደሉ ሰዎች ላይ አስፈጽሟል ። ይኸን የመሰለው ቅጣት ዋናዎቹን ባላጋራዎች ጣልያኖቹን ስላልነካ ለጠላቶቻቸው የሚላሉ ፥ በወገኖቻቸው ላይ የሚጨክኑ ፍርደ ገምድል አስመስሏቸዋል ። የዚህ ዓይነቱ ቅጣት እንኳን ጣልያኖቹን ተቀጥረው የተዋጉትን ሱዳኖቹን እንኳን አላገኛቸውም ። የፍርዱ መሠረት እነዚህ ወገናቸውን የከዱ ሲሆኑ ፥ እነዚያ ግን ጠላትነታቸው የታወቀና መንግሥታቸው አዟቸው ነው ፤ አይፈረድባቸውም የሚል ነው ።

1 Empress Taytu and Menilek II Chris Prouty — p. 158.

# ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

## የምሥራች ለሙሴ ሞንዶን—የስሞታ ደብዳቤ ለርዎ ጳጳስና ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥት

ዘመኑ የነጭ ዘር የገነነበት ፤ ሥልጣኑን በእስያም ፤ በአሜሪካና በአፍሪካ የዘረጋበት መሆኑ ግልጽ ነው ። በተለይ ከአምስቱ ክፍለ አህጉር በማናቸውም ረገድ ወደ ኋላ የቀረው አፍሪካ ለተገዥነት የተጋለጠ ነበር ። ቀደም ብለው ኃያላኖቹ እየተሽቀዳደሙ በመፋለም በፋሾዳ እንደ ደረሰው ፤ ለውጊያ እየተፋጠጡ አንዳንድ ጊዜም እየተዋጉ ቆዩ ። በመጨረሻ ደግሞ ፤ አፍሪካን በጠብና በውጊያ በመያዝ ፈንታ በሰላምና በስምምነት እንከፋፈል ብለው እ.ኤ.አ. የካቲት 26 ቀን 1885 ዓ.ም. በ38 አንቀጽ ላይ የሠፈረ የርስ በርስ ውል በጀርመን ከተማ በቤርሊን የተዋዋሉት ይታወሳል ። ዘመኑ እንኳን የብዙ ጦር መመታትና መሞት ፤ የብዙዎች በምርኮ ተይዞ እንደ መንጋ መነዳት ይቅርና ያንድ ነጭ በአፍሪካ ውስጥ መቁሰል ከዚያም አልፎ መገደል ያንን ነጩ የሞተበትን አገር በኃይል ለመያዝ እንደ በቂ ምክንያት ያስቆጥር እንደነበረ ግልጥ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፤ ምንም እንኳን የአጥቂነቱና የወራሪነቱ በደል ከኢጣልያ ወገን መሆኑ ቢታወቅም ፤ በዓድዋ ዘመቻ በኢጣልያን ጦር ላይ በድል አድራጊነት በመውጣትና ከፊሉን በመግደልና በማቁሰል ፤ የቀረውንም በመማረክ ስለ አዋረዱት ፤ የነጭ ዘር ሁሉ በዚሁ ትናዶ እንዳይዘምትባቸው ሥጋት ያደረባቸው ይመስላል ። በእርግጥም የዚህ ጦርነት ውርደት በቅኝ አገዛዝ ሥር ለወደቁት የደስታና የአለኝታ ስሜት ሲያሳድር ፤ በገዥዎች ዘንድ ውርደትንና ኃፍረትን ማሳደሩን ፤ በተለይ በእንግሊዞችና በጀርመኖች ዘንድ የደረሰውን የጸጸትና የበቀል ስሜት ተመልክተናል ። በኢጣልያም አገር በመንግሥቱ መሪዎች ዘንድ ተሸንፎ መታረቁ መራራ ጉርሻ ሆኖባቸው ነበር ። እንደገና "ከቀድሞው የበለጠ እጥፍ ጦር ይላክ" እያሉ ሲወተውቱ ፤ አዲሱን ካቢኔ ለማቋቋም የተመደቡት ባለሥልጣኖች ፤ የእርቅ እጅ መዘርጋት ግዴታ የሆነባቸው ሌላ የመውጫ መንገድ ስለጠፋ እንጂ በልብ ፈቃድ አለመሆኑ ግልጽ ነው ። በዚሁ ጊዜ ኤድዋርዶ ስካርፎሊዮ የሚባለው ጸሐፊ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርኪዝ ዲ ሩዲኒ አንቶኒዮ

ስታራባ ካፄ ምኒልክ ጋር በመልእክት የእርቅ ድርድር ለማድረግ መወሰኑን በሰማ ጊዜ ፣ ለሮማ ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት የሚከተለውን ጽፎ አስተላልፎአል ።

> የሐበሻ ኢትዮጵያ በመሆን ፋንታ የኢጣልያ ኢትዮጵያ እስከ አልሆነች ድረስ ማናቸውንም መፍትሔ አልቀበልም . . . ባንድ አሸ ናፊ ጠላት ፊት የሚሸሽ ንጉሥስ ምን ይረባናል? ኢጣልያ ጦርነቱን ካልፈለገች በወገቧ አጕንብባ ላሸናፊው አረመኔ (የኢትዮጵያ ንጉሥ) እጅ መንሣት አለባት ። ስለዚህም የጦር ሠራዊት ድርጅታችንና የመር ከብ ኃይላችን ይፈታና እኛንም የሮማው ሊቀ ጳጳስ ያስተዳድረን ፣ የቀረው ቢቀር በልባችን ከእንግሊዝ ቅኝ አገር የሰፋውና የታመመው ልባችን መድኃኒትና ሰላም ያገኛል ።[1]

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ባገር የውስጥ አስተዳደር ጣጣ የተከበቡት ዳግማዊ ምኒልክ በዓድዋ ድል አድራጊነት መንፈሳቸው ቢረካም የዠኔራል ባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ ምጥዋ መግባት ደስታቸውን ጥር ጣሬ ባለበት ሥጋት በርዞታል ። ከሁሉ የበለጠ በኢጣልያኖች መሸ ነፍ ጉዳይ ይነስ ይብዛ አውሮፓውያን ሁሉ በዘርና በቀለም አንድ ነት ምክንያት በነገሩ መታመም ገብቷቸዋል ።

በተለይ "እንግዲህ ንጉሡ ተሸሮ ፓፓው ያስተዳድሩን" ብሎ ስካር ፎሊዮ የጠቀሳቸው የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በመላው የኢጣልያ ሕዝብና በካቶሊክ አገሮች ሁሉ ተደማጭነት ያላቸው ስለሆኑ ምኒልክም የልባቸውን ወቀሳ ለርሳቸው በደብዳቤ ገልጸዋል ። በዚህ ጊዜ የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የቀድሞ መጠሪያ ስማቸው ዮአኪም ፒቹ በስመ ጵጵስና ሊዎን 13ኛ የተባሉት ናቸው ። እርሳቸውም እ.ኤ.አ. ከ1878 እስከ 1903 ዓ.ም. ድረስ የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ተብለው በመን በረ ጴጥሮስ ተቀምጠዋል ። ለርሳቸው ምኒልክ ሮሮአቸውን ለመግለጽ የላኩት ደብዳቤ ለመስኮብ ንጉሥ ከጻፉት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እዚህ ላይ ማስፈሩን ትተን ለሞስኮብ ንጉሥ የጻፉትን ደብዳቤ በዚሁ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ አስፍረነዋል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዓድዋ በዘመቱበት ሰዓት አዲስ አበባን የሚጠብቁት አጐታቸው ራስ ዳርጌ መሆናቸውን ፣ እርሳቸውም አዲስ አበባ ባሉት ፈረንጆችና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል ሆነው ከንጉሠ ነገሥቱ ለፈረንጆቹ የሚላከውን ፣ ከፈረንጆቹ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የሚ ሔደውን በመቀበል ያስተላልፉ ነበር ። እንደዛሬ የስልክ መስመርና

1 Abyssinia (1888 - 1896) E. Scarfolio, vol. II PP. 253-258; Gli Italiani in Africa Orientale, A Del Boca, PP. 706 - 708.



የሬዲዮ መገናኛ በሌለበት በዚያን ዘመን መልእክቱ ሁሉ በእግረኛና በጋማ ከብት በተቀመጡ የሰው መልክተኞች ብቻ እንደነበረ የታወቀ ነው ። ለዚህ ግን ፣ የተደራጀ የአዋላና የፖስተኛ አመላላሽ ነበረ ። ለማንኛውም የዓድዋን ድል እነራስ ዳርጌ በስንተኛው ቀን እንደሰሙ አናውቅም ። ምናልባት እንደ ጉዳዩ ትልቅነት መልክተኛው ፈረስ በመለዋወጥ ወሬው ባጭር ጊዜ ውስጥ ደርሶ ይሆናል ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከዘመቱበት ከጥቅምት ወር ጀምረው እዋናው ከተማ በቀሩትና በሌላውም አውራጃ ባሉት አገራቸውንና ንጉሣቸውን ወዳ ጆች ዘንድ ሐዘንና ጭንቀት እንደነበረ ፣ በየአብያተ ክርስቲያኑና በየገዳማቱ ጸሎትና ምሕላ እንደሚያዝ እርግጥ ነው ።[1] ስለዚህ በዚ ያው በጭንቀቱ መጠን አሁን ደግሞ የድሉ ወሬ ሲሰማ ደስታው የዚያን ያህል መሆን አለበት ። የዚህን ሁኔታ የሚዘረዝር ጽሑፍ ደራ ሲው አላገኘም ። የዚህንም የድል ብሥራት ያበሠረው ለራስ ዳርጌ የተጻፈው የንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ እንደሚሆን የታወቀ ሲሆን ፣ ደብ ዳቤው የት እንደሚገኝ አይታወቅም ወይም በፍጹም ጠፍቶ ይሆናል ። በሌላ በኩል ግን ለሙሴ ሞንዶን ቢዳዬ ንጉሠ ነገሥቱ የጻፉለት የምሥ ራች ደብዳቤ በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የተገኘው እንደዚህ የሚል ነው።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚ አብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን እንዴት ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። የምሥራች በእግ ዚአብሔር ቸርነት የየካቲት ቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት ኢጣልያንን ድል አድርጌ መታሁት ። አልሆነ ስፍራ ላይ ካብ ከቦ ለጦርነት አልመቸኝ ብሎ ነበር ። ሠራዊት ቢራብብኝ ዓድዋ ላይ ስፍሬ ሠራዊቱን ቀለብ ሰድጄ ተበትኖ ሳለ ፣ ያን ሲሰማ ሌሊት በጨረቃ ሲገሠግሥ አድሮ እስፈሬ ድረስ መጥቶ ገጠመኝ ። እምላከ ኃያላን ረድቶኝ ፈጀሁት ። ደስ ብሎኛል ደስ ይበልህ ። መጋቢት በ3 ቀን በእንትጮው ሰፈር ተጻፈ በ1888 ዓመተ ምሕረት ።

እንደዚሁም ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጻፉት እንደዚህ የሚል ነው ።

> ይድረስ ከወዳጄ ከሙሴ ሞንዶን ። እንዴት ነዎ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። የምስራች ኢጣልያኖችን ዳግመኛ እንዳይነሡ አድርገን ድል መታናቸው ። ታሪኩም እንዲህ ነው ። እንትጮው ከሚ ባሰው አገር ላይ ካብ ከቦ ለጦርነት የማይመቸን ቢሆን ወደ ሐማሴን ልንገዝ ዓድዋ ላይ ስፍረን ሳለ ፣ ሠራዊት ተርቦ ነበርና እህል ዘረፋ

1 መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፣ መንግሥቱ ለማ በዚህ መጽሐፍ ገጽ 145—146 የአለቃ ወልደ ያሬድ ጭንቀት የቀሩትንም እንመለከታለን ።

ሥራዊታችን እስከ ሽፌ ድረስ ተበተነ ። ኢጣልያ ግን ይኸን ቢሰማ እህል ዘረፋ የሔደው ሳይመለስ ልፍጀው ብሎ ሌሊት በጨረቃ ሲገሠግሥ አድሮ እሑድ የየካቲት ጊዮርጊስ እለት በአንድ ሰዓት ዐድዋ አፋፍ ላይ ዘለቀ ። የኛም ሰው እየተሰለፈ በየግንባሩ ሔዶ ከገጠመው ። ወዲያው መድፍና ወጨፎ ፣ የወዲሁ ውኸግራ በተተኰሰ ጊዜ የዚህን ግርማ እግዚአብሔር ያሳይዎ ኢርቱእ ናስተማስሎ (ከምን ጋር እናመሳስለው ዘንድ አንችልም) እንዳለው ልንተወው ይገባል ። ነገር ግን በየበሩ እንገት (ምቹ ሥፍራ) እየያዘ ከሶስት ላይ ተሰልፎ ነበር ። የፊተኛው ሲሻር ደግሞ ሁለተኛው ከቢ ገጠመን ። ደግሞ ይህ ሲሻር ሦስተኛው ከቢ ገጠመን ። ሦስተኛው ግን ሲሻር ሁሉም ጀርባ ሰጠ ። ወእርኃብኩ መከየድየ በመትህቴየ ወኢደክመ ስኰናየ እንዳለው ሆነ ።1 ወታደር እደከመ ድረስ እባሮ ሲመለስ ደግሞ ባላገር ተቀብሎ መረብ ድረስ ፈጀው ። ደግሞ ደልዳላውን ወሬ ከግራዝማች ዮሴፍ ደብዳቤ ያገኙታል ። በመጋቢት በ3 በዓድዋ ሰፈር ተጻፈ ።

ማኅተም ዘእለቃ ገብረ ሥላሴ

ዘውእቱ ጸሐፌ ትእዛዝ 2

በዚህ ደብዳቤያቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ "የፊተኛው ሲሻር ደግሞ ሁለተኛው ከቢ ገጠመን ፤ ደግሞ ይህ ሲሻር ሦስተኛው ከቢ ገጠመን ፤ ሦስተኛው ግን ሲሻር ሁሉም ዠርባ ሰጠ. . ." ያሉት መዠመሪያ ግንባር ቀደም ሆኖ በእምባ ኪዳነ ምሕረትና በአባ ገሪማ በኩል የተዋጋውን የዤኔራል አልቤርቶኒን ጦር ነው ። "የፊተኛው ሲሻር ሁለተኛው ከቢ ገጠመን" ያሉትም ፣ የመዠመሪያው ብሬጌድ ጦር ከኋላ የተጠባባቂውን የዤኔራል ኤሌናን ጦር ጨምሮ በአምባ ራዓዮ የተዋጋውን የዤኔራል አሪሞንዲን ጦር ነው ። "ሦስተኛው ሲሻር ሁሉም ጀርባ ሰጠ" ያሉትም ፣ የሁለተኛውን ብሬጌድ ጦር ይዞ በማርያም ሸዊቶ የተዋጋውን የዤኔራል ዳቦርሚዳን ጦር ሲያስታውሱ ነው ። እንደ እውነቱ ግን ፣ ሁሉም በየግንባሩ የገጠመው የዤኔራል አልቤርቶኒም ፣ የዤኔራል አሪሞንዲም ጦር ዠርባውን እየሰጠ የሸሸው የራሱ ጦር እየተመታ በፈረሰበት በተለያየ ሰዓት እንጂ ፣ ሁሉም በያለበት የዘመተው ጦር ሲመሽ የፈረሰውን የዳቦርሚዳን ውጊያ አልጠበቀም ። ሁሉም በየበኩሉ የተዋጋውም ፣ የሸሸውም የሌላውን ዕድል ሳይጠብቅ በተለያየ መንገድ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ የጻፉት ከእንትጮ ሲሆን ፣ ጸሐፌ ትእዛዙ የጻፉት ከዓድዋ ሆነው ነው ። ሁለቱም የጻፉበት ቀን አንድ ነው ። ምናልባት

1 የዳዊት መዝሙር 26.12

2 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቁ. 82 ፤ ደልዳላውን ወሬ ከግራዝማች ዮሴፍ ደብዳቤ ያገኙታል ያሉት ፣ ፍሬ ነገሩ ወደ አዲስ አበባ በተደረገው የመልስ ጉዞ ላይ ይገኛል ። ግማሹም ባለፈው ምዕራፍ ላይ የተወሳ ነው ።



ንጉሠ ነገሥቱ ከጦሩ ጋር ወደፊት ሲያልፉ ፣ ጸሐፌ ትእዛዙ የጦር ሰው ስላልሆኑ ወደኋላ ወደ ዓድዋ ከዋናው ጓዝ ጋር ቀርተው ይሆናል ። ዳግማዊ ምኒልክ የድል አድራጊነታቸውን ወሬ ለፈረንሳይ መንግሥትና ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥትም ጽፈዋል ።

የመስኮብ መንግሥት ፣ ገና ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት በመፈለግ በ1878 ዓ.ም. መልክተኛ ልኮ ነበር ። አሁንም ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተቋረጠውን ወዳጅነት ለመቀጠል በ1887 ዓ.ም. ሊዎንቴቭ የሚባለውን አንድ ሐኪም አንድ የመድፈኛ ሹም ፣ አንድ የቤተ ክህነት ሰው ጨምሮ አዲስ አበባ ልኮ ዐፄ ምኒልክም ለዚሁ መልስ በዐድዋ ጦርነት ሕይወታቸውን የሠውትን ፊታውራሪ ዳምጠውን ዋና መልክተኛ አድርገው ልከው እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

አሁን ዐፄ ምኒልክ ፣ በዓድዋ ኢጣልያኖችን አሸንፈው ወደ ከተማቸው ተመልሰዋል ማለትን ወሬ ስለሰማ ፣ በመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ አንድ ዤኔራል ፤ አራት ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ስድስት የፈረሰኛ ፣ ዐሥራ አንድ የመድፈኛ መኰንኖች ፣ ሐያ የሚሆኑ ዝቅተኛ መኰንኖች ፣ አራት ሐኪሞች ፣ አንድ የቤተ—ክህነት ሰው በድምሩ ዐርባ ሰባት የሚሆኑ መስኮቦች ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኝተው እንደ ዘመኑ ለሁሉም ቤት ተሠርቶላቸው ተቀመጡ ። ሐኪሞቹም በትጋት ኢትዮጵያውያኑንና ኢጣልያኖቹን ቁስለኞች በማከም አገልግሎት አበርክተዋል ። ንጉሠ ነገሥቱም የወዳጅነትና የእርዳታ መልክ ያሳዩዋቸውን የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ኒኮላን ደስ ለማሰኘት ብለው በልደታቸው ቀን ሃምሳ የኢጣልያ ምርኮኞች በነጻ ለቀው በኮንት ሊዎንቴቭ መሪነት ወዳገራቸው በሰላም እንዲመለሱ አድርገዋል ።

በዚሁ ወዳጅነት ዳግማዊ ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ መቀሌ በነበሩበት ሰዓት ስለዓድዋ ጦርነትና ስለድሉ አንድ ደብዳቤ ጽፈውላቸዋል ። ደብዳቤው ሲነበብ ከደስታና ከምሥራች ይልቅ የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶና መንግሥቱ በርሳቸው ላይ የዋለውን የግፍ ሥራ የሚገልጽ ነው ። ይኸም ምንም እንኳን የወዳጅ አገር ንጉሥ ቢሆንም ፣ ዞሮ ነጭ በመሆኑ ምናልባት ቅርታ እንዳይገባው ጦርነቱ ለማድረግ የተገደዱት ኢጣልያ በእብሪትና በግፍ ስለ መጣባቸው መሆኑን ለማመልከት ይመስላል ። የደብዳቤውን ትክክለኛ ግልባጭ ከዚህ እንደሚከተለው እናንብብ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ኒቆላዎስ ቄሳር ሁለተኛ ፤

ሰላም ለርስዎ ይሁን

ክቡር ንጉሠ ነገሥት ሆይ ፣

በዚህ ደብዳቤ የሚጻፈውን ግፌን አስታውቀዎታለሁ ። የኢትዮጵያን ነጻነቷን ፣ ራሷን የቻለች መንግሥት ባጠገቧም ወዳጅ የሌላት መሆኗ አስቀድሞ በሮፓ ነገሥታት ሁሉ የታወቀ ነው ። ከግራኝ ጀምሮ እስከ አሁን በአሕዛብ እጅ ተከባ ዘወትር በጦርነት ድካም ነው ኑሮአችን ። ከሮፓ የጦር መሣሪያ አስመጥቼ ሠራዊቴን ዘወትር ከጦርነት ድካም አሳርፋለሁ ስል ከንጉሥ ኡምቤርቶ አባት ጋር የፍቅርን ነገር ጀመርኩ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም መንግሥት በያዙ ጊዜ እንደ አባቱ ፍቅርን እወዳለሁ ብለው ቢልኩብኝ እኔም እንዳባትዎ ታፈቀሩኝ እሺ ብዬ ፍቅርን ተቀበልኩ ። ኮንት አንቶኔሊ የሚባል የኢጣልያ ሰው በገንዘብዎ ጠበንጃ ልግዛልዎ ቢለኝ ብዙ የዝሆን ጥርስና ወርቅ ሰጥቼው ይዞ ሔዶ ከንጉሥ ኡምቤርቶ አስፈቅዶ ገዝቶልኝ ቢመጣ ከመንግሥት ፈቃድ በማግኘቱ እጅግ ደስ አለኝ ። ሁለተኛም ንጉሥ ኡምቤርቶ ኮንት አንቶኔሊን የመንግሥት መልከተኛ አድርገው ወደኔ ሰደዱት ። ተልኮ ያመጣውም ቃል ይህ ነው ። ነጋዴም እንዲነግድ የጦር መሣሪያ እንዳይከለከል ይፈቀድልዋል ። እርስዎም ባሪያ እንዳይሸጥ ያስከለክላሉ ። በሌላ መንግሥት ያለ መሣሪያ ሁሉ ብትፈልጉ በኛ በር ይመጣላችኋል አይከለከልም ። እንደ ሮፓ ነገሥታት የተጠላው ውል ባምስት ዓመት ይለወጣል ፤ የተወደደው ይረጋል ። ምጥዋ ሐሩር ሆኖብናል ። ለሰዎች ማሳረፊያ ጥቂት ነፋስ ያለበት ስፍራ እንዲሰጡን የፍቅርን ውል ይህን እናድርግ ብለዋል አለኝ ። እሺ ይሁን ብዬ እኔም ለመንግሥቴና ለኔ የሚስማማ የሚጠቅም ቃል በአማርኛ በትክክል አድርጌ አስጥፌ ብሰጠው ዐሥራ ሰባተኛው ክፍል ላይ ቃሌን በኢጣልያ ቋንቋ ለውጠው ከጥንት ጀምሮ ነጻ የነበረውን መንግሥቴን የሚያዋርድ የማይስማማኝ ቃል ቢሆንብኝ እኔ ባስጣፍኩት በአማርኛው ቃል ይርጋ ፤ የኢጣልያ ቋንቋ ከኔ ከአማርኛው ጋር ያልተካከለ ነው ። አሁንም በትክክል እናድርገው ብዬ ወደ ንጉሥ ኡምቤርቶ ብልከባቸው ምላሽ ሳይሰጡኝ ቀሩ ። እኔም ነገሩ ለተንኮል እንደሆነ ዐውቄ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ አስቀድሜ ለሮፓ ነገሥታት ሁሉ ከንጉሥ ኡምቤርቶ በውሉ ነገር እንዳልተስማማን አስታወቅሁ የውነት ፍርድ አገኛለሁ ስል ። ሁለተኛም አምስት ዓመት ሲደርስ የጠላነው እንዲቀር የወደድነው እንዲረጋ ሰው ይላኩልኝ ብዬ ብልክ ፣ እስከ ወረቀቱም ምላሽ አስቀሩት ። ከዚህ ወዲህ ይልቅ ክፉ ነገር እየበረታ ሔደ ። አሽከሬን ደጃች መሸሻን አሰፍርድ አሰሩት። አገር አልፈው የሾምኩትን ሹም ራስ መንገሻን ወግተው አባረው አገሬን ትግሬን በሙሉ ያዙት ። ከዚያ አልፈው ላስታ መሬት እስከ አሸንጌ ድረስ ወጡ ። ከዚያ ወዲያ አገር የሚጠብቁ መኳንንቶች ከኔ ብሰድ ፣ አላጌ ላይ በር ይዘው ቆይተው ተዋጉአቸው ። የእግዚአብሔር ኃይል በኔ ሰዎች አድሮ ድል አደረጓቸው ። እኔም ወደዚያ ተከትዬ ብሔድ መቀሌ እርድ ገብተው አገኘሁ ። ጦርነት ከሆነ ክትልቁ



ጋር እዋጋለሁ እናንተ ክርስቲያኖች በውሀ ጥም አትለቁ ብዬ እስከ መሣሪያቸው ከእርድ አስወጥቼ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ሰደድኩለት ። እኔም ከዚያ ተጉዤ ዓድዋ እከተማዬ ስፍሬ ጄኔራል ባራቲዬሪ እውነት የመሰለ የእርቅ ቃል ላከብኝ ። እኔም እርቅ ከፈለጉ ብዬ ሠራዊቴን ቀለብ ሰድጄ ሳስ ፣ እንደ ሮፓ ነገሥታት ሥራት ሁሉ ጠብ መፈለጋቸውን ሳያስታውቁኝ *እንደ ወምበዴ ሥራት ሌሊት ሲገሠግሥ አድሮ ሲነጋ ግምባር ካደረው ዘበኛ ጋር ጦርነት ዠመረ ። ጥንት ከአሕዛብና ከአረመኔ አገራችንን ጠብቆት የሚኖር አምላክ ከኛ ባይለይ በእግዚአብሔር ኃይል ድል አደረኳቸው ። ከዚያ ሔጄ እሥመራንም የኔን አገር ሁሉ በሙሉ አስለቅቃለሁ ብዬ ተጉዤ ሳለሁ ጄኔራል ባልዲሠራ በኢጣልያ ሠራዊት ሁሉ ላይ ተሾሜ መጥቻለሁ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም ሲሰዱኝ እርቅ ነውና እምፈልግ እርቅ አድርግ ብለውኛል ብሎ በማዠር ሳልሳ እጅ ወረቀት ቢልክልኝ ፣ እኔ በወደድሁት ከታረቃችሁ የሚስማማኝ ቃል ከሆነ እውነተኛ ሰው አዲስ አበባ እከተማዬ ድረስ ይምጣና ይጨርስ ብዬ እኔም ወደ ከተማዬ ተመለስኩ ። እስካሁን በትግሬ አለሥራት ያለቀው መኳንንትና ባላገር የሮፓ ነገሥታትና መኳንንት ሁሉ የተደረገውን ግፍ አመለከታለሁ ። የኢጣልያ ገንዘብ በላያችን ላይ የለብን ። ካገራቸውም ድምበራችን የራቀ ነው ። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነጻነቱና እራሱን የቻለ መንግሥት የሆነውን በተንኮል ሊወስዱት እንዴት ይቻላቸዋል ። ይህንን የግፍ ፍርድ በሙሉ ልቦናዎ በውል እንዲመለከቱት ተስፋ አለኝ ። ኢጣልያኖች ግን ፣ ይኸን ሁሉ ግፍ ሲያደርጉብኝ እነሆ እኔ የማደርገው የነበረው እነሱን ማክበር ሲመጡ በሥራት መቀበል ፣ ሲመለሱ በሥራት መሸኘት ደግሞ በተሰጠኝ ሥልጣን ሁሉ የባሪያ ንግድ መከልከል በኔ መንግሥት አፈንዴ መሐመድ ብቻ የባሪያ ንግድ አልተው ብሎኝ ስለዚህ አውሳ ጦር ሰድጄ አስጋሁት ። ይህ ፈቃድ የኔ ብቻ አይደለም የሞላ የአውሮፓ እንደሆነ ዐውቃለሁ ። በመጋቢት 23 ቀን በመቀሌ ሰፈር ተጻፈ በ1888 ዓመተ ምሕረት ።1

* (Ultimatum) የጦርነት ማስጠንቀቂያ ሳያስቀድሙ ለማለት ነው ።

1 ማዳም ራይት ከሰጡኝ ሰነድ ውስጥ ገጽ 152—157



የፄ ምኒልክ አማካሪ ሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ
ከምኒልክ ኤኑ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

## የኢጣልያ ምርኮኞችና ወደ አዲስ አበባ ጉዟቸው

የካቲት 23 ቀን በተደረገው ጦርነት ተሸናፊው የኢጣልያ ወታደር ዕድሉ ከሦስት ላይ የተከፈለ ነበር ። ከፊሉ በጦርነት ላይ የቆሰለና የሞተ ፤ ከፊሉ ከጦርነቱ ላይ የሸሸ ፤ የቀረው ደግሞ የተማረከ ነው ። ከነኝህ ከሦስቱ መደቦች ለወታደሩ የትኛው እንደሚሻል ለማወቅ ሲፈለግ ለዠግንነትና ለታሪክ የሞቱት ሲሻሉ ነፍሳቸውን ለማዳን ደግሞ የሸሹትና የተማረኩት ናቸው ። ሸሽተው አሥመራ ከገቡትና እጃቸውን ሰጥተው በመማረክ እስከ አዲስ አበባ ከመጡት የየትኞቹ ዕድል እንደሚሻል በትክክል አይታወቅም ።

የእስረኞቹ በብዛት መማረክ ፤ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለወደፊት የክርክር አቅዋም በጣም ረድቷል ። ጣልያኖች ቀድሞ እምቢ ያሉትን የውጫሌን ውል ለመሰረዝ የተገደዱትና አዲስ የመጣው የዤኔራል ባልዲሠራ ጦር መረብን አልፎ እንዳያጠቃ ከመንግሥቱ መሪ ትእዛዝ የተቀበለበት ሰበብ አንዱም በምርኮኞቹ ምክንያት ነው ።

ምንም እንኳን የሚቹ ፤ የምርኮኛውና የሸሸው ቁጥሩ ገና ባይታወቅ የዘማቹ በተለይም የምርኮኞቹ ቤተሰቦች በተጨቃጨቁበት ሰበብ መንግሥቱ የምርኮኞቹን ሕይወት ለማዳን ሲል የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት በውል ለማወቅ የተገደደው ፤ በጦርነት ከመሸነፉ ጋር አንዱም ምርኮኞቹን ለመረከብ ይመስላል ። ቤላቪታ ፤ "በእስረኞቹ መለቀቅ በጣም አሥጊ ከነበረው ከእስረኞቹ ጉዳይ አገሪቱ (ኢ.ጣልያ) ካንድ ቅዠት ነጻ ወጣች" ሲል አትቷል[1] ። ለኢጣልያ ሕዝብ የእስረኞቹ ጉዳይ አያያዝ የመንፈስ ዕረፍት አሳጥቶት ነበር ማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፤ የጦርነቱ ዕለትም በማግሥቱም የተማረከው የኢጣልያ ወታደርና ሹማምንቱም ፤ እዚያው ዓድዋ ሳሉ በመጀመሪያ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዲያልፉ ተደርጓል ።

ቲኔንቲ ሮቤርሲ ከማዠር ሳልሳ ጋር በእርቅ ሰበብ ከንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር አምስት ቀን በቆየበት ጊዜ የተመለከተውን ሲገልጽ ፤

---

1. Tante Anzie sulla sorte dei prigienieri . . Al paese parve di essersi liberate da un incubo, Adua, Bel. P. 445.

በደረስንበት ቀን ገና ለሹማምንት ያልታደሉት እርዛትና ድካም ረኃብ ያጠቃቸው የኢጣልያ ምርኮኞች ወዲያና ወዲህ እያሉ ከሐበሾቹ ምጽዋት ይለምኑ ነበር ። ይኸንንም ማየቱ ለኛ ሥቃይ ሆኖብን ነበር ። . . .

ሲል በማስታወሻ ያመለክታል ።

ከሁሉ የበለጠ ስለ እስረኞቹ ጉዳይ ዘርዘር አድርገው የጻፉት ግራዝማች ዮሴፍ እንደ ተለመደው ለሞንዶን ቪዳዬ ባስተላለፉት ባንድ ራፖር ላይ ፤

. . . ንጉሠ ነገሥቱ የተማረኩት ኢጣልያኖች በአንድ ሰው ትእቢት* በግድ ታዘው የመጡ ወታደሮች መሆናቸውን ያውቃሉና እንደ ሹመታቸው ሹማምንቱን ወታደሩን እንደ ማዕረጉ በሚገባ አድርገው ልብስ የሌለውን ልብስ አልብሰው የቆሰለውንም ከሞት የተረፉትንም ሐኪሞች ሰብስበው እያስታመሙ አስቀምጠውታል ።

የሚል ጽፈዋል ።

ከዚህ እያይዘው በመንገድ ላይና በሰፈር ላይ ሳሉ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ በኩል የተደረገላቸውን ቸርነት ሲያመለክቱ ፤

. . . የጁ ስንደርስ ከላስታ የመጣው ምርኮኛ ሁሉ ከሰፈራችን ተቀላቀለ ። ጃንሆይም በያገሩ ዳቦ አስጋግሩ ብለው ግብር ሲያገቡ ለኢጣልያ ምርኮኞች ሁሉ ቀቅሉ እያሉ ባንድ ወገን ለኢጣልያ ወታደር ባንድ ወገን ለኛ ወታደር መንገድ ለመንገድ ግብር እያስገቡ ይዘውት መጡ ። የዛሬው ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ እቴጌ ጣይቱ ለኛም ወታደር ለኢጣልያም ወታደር የሠሩት የበጎነት ሥራ እያደረ የሚያስደንቅ ነው ። . . . ለኢጣልያኖችስ ያደረጉላቸው ርኅራኄ እናታቸውም ቢኖሩ እቴጌ እንደ ሠሩላቸው ርኅራኄና በጐነት የሚሠሩላቸው አይመስለኝም ። መንገድ ለመንገድ ስንመጣ ጢት ጢት እንዳይርባቸው ሠላሳ ከረጢት ዳቦ እየተቆረሰ ሰፈር እስኪሆን ድረስ መንገድ ለመንገድ ላገኙት ኢጣልያ ሁሉ ሲያድሉት ይውሉ ነበር ። ሰፈር ሲሆን የነዚያው ወጥ ከእቴጌ ቤት እየተሠራ ይሔድላቸው ነበር ። መንገድ ለመንገድ የኢጣልያ ቆብ ያደረገ ወታደርና ገረድ ያገኙ እንደሆነ እያስገፈፉ ቆብ ለሌለው ይሰጡት ነበር ።** የደከመውንም የታመመውንም የኛ ወታደር በእግሩ እየሔደ ከመንገድ ወድቆ እንዳይቀር አገር በሌለበት ሥፍራ ከመንደር እስኪደርስ ያስጉዙት ነበር ። አገር ሲደርስ በብርቱ ትእዛዝ በጣም እንዲያስታምሙ ደብዳቤ እየተጻፈ ተመራ ። ጢት ጢት ዳቦውን ከለመዱ በኋላ ቀን ሲርባቸው ስንጓዝ እቴጌን በሩቅ ባዩ ጊዜ የኢጣልያ ወታደሮች ሁሉ ኤኮ ኤኮ እልዳቦ (ባለዳቦዋ ያቻት) እያሉ ወደ እቴጌ ይሮጡ ነበር . . . እንደ ለማዳ አውሬ ግማሹ የእቴጌ አጀብ የኢጣልያ ወታደር ነበር ። የወንጌል ቃል በእቴጌ ሲፈጸም አየን . . .

ብለዋል ።

* ባንድ ሰው ትእቢት ታዘው የመጡ ያሉት ይህ ሰው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ እንደሆነ ይገመታል ።

** ከኢጣልያኖች የተማረከውን መለዮ የኛ ወታደርና ገረዶች አድርገው ሲሔዱ እያስጣሉ ለኢጣልያኖቹ ይሰጡ ነበር ማለት ነው ። የኢጣልያኖቹን ቆብ ገረዶች ሲያደርጉት ጣልያኖቹ ሳያፍሩበት አይቀሩም ።



በዚህ ዓይነት ፣ ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ የተጓዙት የኢጣልያ ምርኮኞች ፣ እነዚያ ልብሳቸው አልቆ በውስጥ ሱሪ የተጓዙት ፣ ጫማቸው አልቆ በሻሽ አስረው ፣ በመውደቅና በመነሣት በስንት ጣር ወደ እሥመራ የሸሹት የኢጣልያ ወታደሮች ፣ ከጦርነቱ በፊት ጦርነት ከልክ ያለፈ ያማራቸው ነበሩ ። የጦርነቱ ቀን በመራዘሙ የተበሳጩም ነበሩ ። ኢጣልያ አገር ላሉት ለዘመዶቻቸው ፣ "ከንዴ ጠንካራ ነውሺዎችን ለመፍጀት ቸኩያለሁ" ወይም "ሳልጽፍ የቆየሁት መጀመሪያ ካበሾቹ ጋር ተዋግቼ ዠግንነት ከሠራሁ በኋላ እጽፋለሁ ብዬ ነው" አንዳንድ ጊዜም ፣ "ባበሾቹ ላይ ዠግንነት ሠርቼ ኒሻን መሸለም እምሮኛል" የሚሉ በአሽናፊነታቸው የተማመኑ ፣ ዠብዱ ሠርተው ኒሻንና ክብር የናፈቃቸው እንደነበሩ ወደኋላ መለስ ብለን እናስታውስ ። አሁን ይኸ ሁሉ መና ቀርቶ ከናቁት ሠራዊት ምጽዋት እየለመኑ ፣ በናቁት ሠራዊት እየተነዱ የወታደርነት መለዮዋቸውን ገረድ አድርጋው ስትሔድ ሲያዩ በልባቸው እንደሚገረሙ የታወቀ ነው ። አንዳንዶቹ መኰንኖች አፋቸውን አውጥተው በጉዳዩ ተወያይተው ፣ ተሣሥቀውበት ወይም ተላቅሰውበት እንደሆነ አይታወቅም ። በታላቅ የሥነ ጽሑፍና የሥነ ጥበብ ሥራ የተደነቁት የነሚሸል አንጀሎ ፣ የነራፋኤል ወገን የሆኑት ጣልያኖች እንደ አንግሎ ሳክሶኖች ደስታንና መከራን በመሸከም ከበድ ብለው መታየት አይሆንላቸውም ።

አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ ፣ ስለ ምርኮኞቹ እኚሁ ያስተርጓሚ ጸሐፊ የሆኑት ግራዝማች ዮሴፍ ሲያትቱ እንደዚህ ብለዋል ።

. . . አንድ ግብጣን (ካፒቴን) አዲስ አበባ ላይ ታሞ ሞተ ። የቀሩት ወታደሮች በያገሩ ተመሩ ። ምግቡን እንደጠገበ አብሉ ብለው አዘዙ(ምኒልክ) ። ዛሬ ከባላገር ጋር በጣም ተስማምቷል ። ልብሱንም እንዳገሩ እየተሰፋ ሰጡት ። ሹማምንቱም ትልልቆቹም አዲስ አበባ የገባን ጊዜ በየሹማምንቱ ቤት ተመሩ ። ሰባት ሰባት ብር ደመወዛቸውን ሰጧቸው ። ቀለባቸውን ከጐተራ እያወጣ ሥጋ ሳይቀር መኳንንቱ እየተቀበለ ተጠንቅቆ ይቀልባል ። ከመንገዱም ላይ የኢጣልያው ሹማምንት የወደደውን እንዲገዛ ብለው አራት አራት ብር ሰጥተዋቸው ነበር ። ከገባን በኋላ እንደ ሹመቱ እንደ ትልቅነቱ ዐሥርም ዐሥራ አንድም ለትንሹ ስድስት ብር ላማራቸው ነገር መግዣ ሰጧቸው ።

በቀረው ሠራተኛው ሥራው እየተጠየቀ በየሥራው ለሠራተኛው አከፋፈሉት ። ደመወዙንም ምግቡንም እንደ ሥራው ሰጡት ። ደግሞ ከወዲያ አገር ፖስታ ሲመጣ ስማቸው እንዳይጠፋ ቢያሉበት አገርም ለመስደድ ስማቸውን አጽፈነዋል ። ለሠራተኛውና ለመኳንንቱ ልብስ ሁለት መዘውር* የኢጣልያ ስፌ ሲሰፋ ይውላል ። ጫማቸውም

* መዘውር የሚሉት ጣቃውን ይመስላል ።

ሲመጡ አልቆ ነበርና የእንጨት መዝገብ* እንደ የሮፓ ሥራ እንኳያ ጠርበው አበጅተው የነዚያ ሰፊና የኛው ሰፊ ወሳፍቻው እንደ ፈረንጆች ተበጅቶ ሲሰፉ ይውላሉ ። ማስም(ቀዳም) አገሩ ሁሉ እያለፋ ያገባል ። በገበያ ያለ እየተገዛ ይገባል ። በገበያ የተገኘው ባርኔጣ ሁሉ እየተገዛ በራሰ በራሱ እየለካህ መርጠህ ውሰድ ብለውት እየመረጠ ሲወስድ ይውላል ።

ጄኔራል አልቤርቶኒን ግን ፣ ከእዛዥ ዛማኔል ቤት ማለፊያ ቤት ሰጥተውት ምንጣፉንም ፣ አልጋውንም ከምድር የሚነጠፈውም ምንጣፍ የሌሊት ልብስም ሰጥተውታል ። የጄኔራል ባራቲዬሪ ወጥቤቶች ከወታደሩ ውስጥ ቢገኙ እንዳገሩ ወጥ እየሠሩ ያበሉታል ። እንደዛሬ ያለውን ጌትነት ከጭፍሮቹም መሐል አግኝቶት አያውቅም ። እርሱ ግን ቁጡ ሰው ነው ቢደላውም እንደሆነ አያውቅም ። ይህንም እንዳልል ዓድዋ ላይ የተማረከ ጊዜ ጃንሆይ ጠርተው ቢጠይቁት ይቆጣ ጀመር ። ጃንሆይ ግን "ቁጣ ትናንትና የጦሩ ዕለት ነበር እንጂ የዛሬ ቁጣ ይረባል?" አሉት ።

ዛሬ በአዲስ አበባ ያሉት ጣልያኖች ሥራቸውን ሲፈቱ አዲስ ሙዚቃ እያበጁ ሲዘፍኑ ይውላሉ ። እንኳን ይጉላሉና የኛ ወታደር እንደነዚያ አልደላውም ። ጃንሆይ የምርኮኛ ቅምጥል አበጅተውልናል።

አንድ ነገር ብቻ የሚያስፈራ ነገር አለ ። እጅግ ጠግቧልና የሠራተኞችን የኢጣልያ ዲቃሎች ሰናሳድግ ፣ ሁለት ሺ የኢጣልያ ኢትዮጵያ ጥለውብን የሔዱ እንደሆነ ከዚህ ጃንሆይ ብዙ አሳብ አለብዎት (አለባቸው) ። ያሥመራ ባለጋዜጦች ተሰለቡ ይላሉ ፤ መሰለባቸውም በዚህ ይገኛል ።[1] . . .

በማለት ግራዝማቹ ስለ እስረኞቹ ጽሑፋቸውን በዚህ ይደመድማሉ ።

ዳግማዊ ምኒልክም ፣ እቴጌ ጣይቱም ለነዚህ ምርኮኞች ይኸን የመሰለ መንከባከብ ለማድረግ የሚገደዱት ፣ ግራዝማች ዮሴፍም ይኸንኑ በዝርዝር ለሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ለመግለጽ የሚጣጣሩበት ዋናው ምክንያት ስለምርኮኞቹ በአውሮፓና በኢጣልያ አገር ፣ "የኢትዮጵያ መንግሥት ባይፈጃቸውም በረኃብና በእርዛት ያጉላላቸዋል" የሚል ከፍተኛ ሥጋት ነበር ። እንደዚሁም አዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገር ተወላጆች በተለይ ፈረንሣዮቹ ምንም እንኳን የኢትዮጵያና የንጉሠ ነገሥቱ ወዳጆች ሆነው የኢጣልያኖቹ መሸነፍ ምናልባት ቢያስደስታቸውም ፣ ዘራቸውና ወገናቸው በሆኑት በነዚህ ጣልያኖች ከተማረኩ በኋላ የመጉላላት ሁኔታ ቢያዩባቸው አይወዱም ። በጠቅላላው በዚህ በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ አውሮፓ የዓለም አዛዥ ፣ የዓለምን ዕድል እንደልቡ የሚወስን መሆኑ ግልጽ ነው ። ከጃፓን በቀር አውሮፓ የብጫንና የጥቁርን ሕዝብ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ በበላይ

---

* የእንጨት መዝገብ የእግር ልክ መለኪያ (ሞዴል) ሳይሆን አይቀርም ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በሞንዶን ዶሲዬ ፣ ቁጥር 82



የሚያስተዳድርበት ወቅት ነበር ። በዚህ ወቅት ጥቁሮቹ ኢትዮጵያውያን አሸናፊዎችና ማራኪዎች ፣ ነጮቹ ጣልያኖች ተሸናፊዎችና ተማራኪዎች ሆኖ መገኘት ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ በአድናቆት የሚታይበት ዘመን ነው ። እስያና አፍሪካ ነጻነታቸውን ባገኙበት በዚህ ባሁኑ ዘመን (1960—1975 ዓ.ም.) የዚህ ዓይነቱ ድልና የምርኮኛ አያያዝ ቢፈጸም ላያስደንቅ ይችላል ። ያን ጊዜ ግን ሁኔታው ካሁኑ የተለየ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ በአሸናፊነታቸውና የነጮች ምርኮኞች በእጃቸው በመውደቃቸው በአውሮፓ የሚሰጠውን ስሜት ከሚያስከትለው መዘዝ ጋር ተገንዝበውታል ። በፊተኛው ጊዜ ከጦርነቱ በፊት እርቅና ሰላም ያለመታከት ይፈልጉ እንደ ነበር ፣ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ የዓለምን ደንብና ሕግ የምታከብር መሆኗን ለማሳየት ሲሉ ፣ ስለ ምርኮኞች ሁኔታ በኢጣልያና በአውሮፓ የተቀሰቀሰውን ሥጋት ለማርጋት እነዚህ ምርኮኞች በልብስ እንዳልታረዙ በምግብ እንዳልተጐዱ እንዲያውም የሙዚቃ መሣሪያ እያበጁ የምርኮኝነታቸውን አሳዛኝ ሊሆን የሚገባውን ጊዜ በደስታ እንደሚያሳልፉ በአስተርጓሚያቸው አማካይነት ለሙሴ ሞንዶን ፣ በሞንዶንም አማካይነት ፓሪስ ለሚታተመው "ለታ" ለሚባለው ጋዜጣ እንዲደርስ አድርገዋል ። በዚህም ጋዜጣ አማካይነት የኢጣልያና የአውሮፓ ሕዝብ የምርኮኞቹን ሁኔታ እንዲረዳው ለማድረግ ይጣጣሩ ነበር ። ምርኮኞቹ ራሳቸው ከየዘመዶቻቸው ጋር እንዲጻጻፉ ስለ ተደረገም በመጀመሪያ ጊዜ "ተገደሉ ፤ ተሰለቡ ፤ ተራቡ ፤ ተራቆቱ" እየተባለ በኢጣልያ ጋዜጦች ተወርቶ የነበረው ሁሉ ፍጹም ሐሰት መሆኑ ሲገለጽ ሁኔታው የኢትዮጵያን መንግሥት ፣ የዚህን ዘመን መሪዎቿንና ሕዝቡን ጭምር በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገምታቸው ችሏል ።

ለአለመሰለባቸው ግራዝማች ዮሴፍ እንደ ማስረጃ አድርገው የጠቀሙት ምርኮኞች ከኢትዮጵያ ሴቶች ጋር በመገናኘት የክልስ ዲቃላ ማበርከታቸውን ሲሆን ፣ ይኸውም የክልስ መበርከት ሁኔታ ለወደፊቱ አሥጊ መሆኑን አውስተዋል ። ይኸ ሁሉ በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች በኩል እየተፈጸመ ምርኮኞቹና ቤተሰቦቹ በሚጻጻፉበት ጊዜ የምርኮኞቹ ቤተሰቦች የኢትዮጵያን ሕዝብ ገና እንደ አረመኔ መቁጠራቸው ያሳዝናል ። ያንድ ምርኮኛ እናት ከአዲስ አበባ ደህንነቱን ለጻፈላት ልጅዋ መልስ ፣ " . .በሕይወት መኖርህን ማወቄ ደስ አለኝ . . .ከሚወዳችሁ ቤተሰብ ተለይታችሁ በአረመኔ ሕዝብ እጅ ወድቃችሁ ምን ዓይነት ሕይወት እንዳላችሁ ማን ያውቃል" ብላ የጻፈችለት የቤተሰቦቹን ውለታቢስነት ያስታውቃል ። ወይም እርሱ በሕይወት መኖሩን ብቻ ይሆናል የጻፈላት ።

ግራዝማች ዮሴፍ ፣ የፈተኞቹን ራፖርች ለሞንዶን ቪዳዬ ይጽፉ የነበረው ከትግሬ ግዛት መሆኑን እናስታውሳለን ። ይኸኛውን የሚጽፉለት እርሱም ፣ እርሳቸውም አዲስ አበባ ባሉበት ጊዜ ነው ። ምናልባት ወደ ፓሪስ ለጋዜጣ የሚልከውን እንዲረዳው አዘጋጅተው ያቀርቡለት ብሏቸው ይሆናል ። ሞንዶን ቪዳዬ በኢትዮጵያ ያሳለፈው ጊዜ ፣ እ.ኤ.አ. ከ1891 ዓ.ም. ዠምሮ እስከ 1897 ዓ.ም. ድረስ ሰባት ዓመት ነው ። ዓድዋ በተዘመተ ባመቱ ወዳገሩ ተመልሷል ።

ከዚህ ድልና ምርኮ በኋላ ፣ ለኢጣልያ መንግሥት ያለው ምርጫ ፣ "እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ያለው አገር ያስፈልገኛል ፤ ኢትዮጵያን በጠቅላላው በበላይ ሆኜ በጠባቂነት ስም እገዛለሁ" የሚለውን የሕልም እንጀራ በግድ ሰርዞ ይንቀው ከነበረው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ራሱን በማስተካከል በእኩልነት እግር ቆሞ ውልና ስምምነት ማድረግ ነው ።



# ምዕራፍ ሃምሳ አራት

## የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ መመለስ — ያዲስ አበባው አቀባበል

ዳግማዊ ምኒልክ ከዓድዋ ጦርነት በፊት መቀሌን እጅ ካደረጉ በኋላ ፣ በየጊዜው እየተዘዋወሩ የሰፈሩባቸው እንደ ቅደም ተከተሉ መቀሌ ሐውዜን ፣ ፈረስ ማይ ፣ ሳውሪያ ፣ ገንደብታ ፣ ዓድዋ ሲሆን ፣ ከድሉ በኋላ ደግሞ ዓድዋ እንትጮ ፈረስ ማይ እንትጮ መቀሌ ናቸው ። ስለዚህ ወደ አዲስ አበባ የተመለሱት ከእንትጮ በመቀሌ በኩል ነው ማለት ነው ።

ባለፈው እንዳነበብነው ማዦር ቶማሶ ሳልሣ ፣ በመጨረሻ ያቀረበውን እሳብ ሳይቀበሉት ከቀሩ ወዲህ በትግሬ ላይ የራስ መንገሻን ሹመት አጽድቀው ለአክሱም ንቡረ እድነት በእጨጌ ቴዎፍሎስ ፋንታ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ይኖሩ የነበሩትን መነኩሴ መምህር ወልደ ጊዮርጊስን ሾሙ ። መምህር ወልደ ጊዮርጊስ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሲኖሩ ከዚያ ወደ ጐጃም ተሻግረው በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዘንድ ተከብረው የሚኖሩ ነበሩ ። በእምባቦ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሚዋጉበት ጊዜ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦር ውስጥ ሆነው ሰይፋቸውን ታጥቀው ወዲያና ወዲህ እያሉ የሚሸሸውን በግዝት እየገሠፁ በርትተው ማዋጋታቸው ይነገርላቸዋል ። በኋላ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ አዲስ አበባ የመጡ ጊዜ ላፄ ምኒልክ እደራ ብለው ትተዋቸው ስለሔዱ ፣ በየጊዜው ልዩ ልዩ የቤተ ክህነት ሹመት ይዘው ቆይተው አሁንም የዓድዋውን ጦርነት ከአቡነ ማቴዎስ ጋር ሆነው ተዋጊውን በማበረታታትና በማጽናናት አስደስተው ነበርና የአክሱምን ንቡረ እድነት ተሾሙ ።[1]

እንደዚሁም ንጉሠ ነገሥቱ የትግሬን ጠቅላላ ግዛት ለራስ መንገሻ አጽድቀው ፣ የትግሬም ሕዝብ በጦርነቱ ሰዓት ስለ ተጐዳ ፣ ለርዳታ ይሆን ዘንድ 30,000 ጥሬ ብር ሰጥተው ሁሉንም ከደለደሉ በኋላ ወደ ሸዋ ጉዞ ተጀመረ ። በዚህ መካከል ከራስ መንገሻ ጋር ተጣልተው

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 269

ለኢጣልያኖች ገብተው የነበሩትና በኋላ ወዳፄ ምኒልክ መጥተው የዓድዋን ጦርነት የተካፈሉት ራስ ስብሐትና ጓደኛቸው ደጃች ሐጎስ በዚህ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ ምን እንደ ተሾሙ የሚናገር ጽሑፍ አልተገኘም ። ምንም በጽሑፍ ባይገኝ ንጉሠ ነገሥቱ ቀድሞ ጠበኞች የነበሩትን ሁለቱን ራሶች አቃርበው ያስታረቁዋቸውና ራስ ስብሐትም በራስ መንገሻ ውስጥ የአጋሜን ሹመት የተሾሙ ይመስላል ።

ያፄ ምኒልክ ከዓድዋ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ፣ ለጊዜው የኢጣልያ መንግሥት ከዓድዋ ድል በኋላ አሳቡ በትክክል ስለ አልታወቀ ጥቂት ጊዜ ዕረፍት አድርገው እንደገና አዲስ ጦርም ፣ ስንቅም ጨማምረው ከአዲስ አበባ ወደ ትግሬ በመሔድ ኢጣልያኖቹ እርቅ እምቢ ብለው ጦርነቱን የቀጠሉ እንደሆነ ለመዋጋት መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ ። እስከዚያም ድረስ ራስ መንገሻ ከጄኔራል ባልዲሠራ ጋር በተቻለ መጠን ሳይዋጉ እየተስማሙ እንዲቆዩ ትእዛዝ ሰጥተዋቸዋል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የእርቅ ስምምነት እስኪያደርጉ ባለው ጊዜ ውስጥ ፣ ሬሳ በማስለቀምና የባከነ ምርኮኛ በመሰብሰብ ረገድ የራስ መንገሻና የጄኔራል ባልዲሠራ ሹማምንት ሁሉንም በኅብረትና በስምምነት ይሠሩ ነበር ።[1]

ስለዚህ ፣ "ትግሬን ለልጄ ለራስ መንገሻ ሰጥቻለሁ" የሚል ዓዋጅ ነግረው ምናልባት ጣልያኖችም እንደገና ጠብ ቢያነሡ ፣ ራስ መንገሻን ይረዱዋቸው ዘንድ ራስ ወሌን አዘው ከጦርነቱ የተማረኩት ጣልያኖች በየሹማምንቱ ተደልድለው አብረው ወደ አዲስ አበባ መልስ ሆነ ። በዚህም ጉዟቸው ንጉሠ ነገሥቱ ከእንትጮ መቀሌ የገቡለት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መቀሌ ላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው በሳምሬ በኩል አድርገው ወዳገራቸው ወደ ጐጃም ሔዱ ። ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱ ማይጨው ደረሱ ። ቀድሞ ወደ ዓድዋ ሲዘምቱ ከዚያ ሰፍረው ሳሉ የከብት በሽታ ገብቶ ይፈጅ ስለነበረ ፣ ለማይጨው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተስለው የነበረውን ለመፈጸም ብዙ መሬት ብዙ ላምና በሬ ሰጥተው ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት ብለው እንደ ገደሙት ፣ ከዚያ በያደሩበት ግብር እያበሉ በግንቦት 15 ቀን አዲስ አበባ መግባታቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ይገልጻሉ ።[2]

1 Sul campo di Adua, E. XimenesXII, PP. 154 - 168

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ምዕራፍ 64



በዚህ ጉን ሊቀ መኳስ አባተ ፣ ከጦርነቱ ላይ የተማረከውን 60 መድፍ ፣ ጥይትና ጠበንጃ ከየጦርነቱ ሜዳ አሰባስበው የተበላሸውን በተቻለ መጠን እያስበየዱ በ500 ሚስንጅር በቅሎ አስጭነው በትጋትና በታላቅ ጥንቃቄ ከዓድዋ በተምቤን በኩል አድርገው አዲስ አበባ በደህና ገቡ ። ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ ፣ ሠራዊቱም ሁሉ ከፍ ካለ አድናቆት ጋር እንዳመሰገኗቸው ይገልጻሉ ። ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ የንጉሠ ነገሥቱን ጉዞ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በዚህ ዓይነት ሲያመለክቱ ፣ በበኩላቸው ግራዝማች ዮሴፍ እንደዚህ ሲሉ ጨምረዋል ።

> . . . ከትግሬ መሬት ተመልሰው ጃንሆይ ሲነሡ ትግሬ ለቀረው ጦረኛ የሰጡት ብር ከዐሥር እልፍ* በለጠ ። አገሩም እጅግ ጥጋብ ሆነ፤ ማድጋ ማድጋ ተሸመተ ። የትግሬ ሰው ግን ፣ ከኢጣልያ ጋር በብርቱ ደም ተቃባ ። እንትጨው ከእርድ ውስጥ የነበረውን እይርና ገንዘብ ሁሉ የኛ ጦር ሳይደርስ የትግሬ ባላገር ተሻማው እንጂ ፣ የሸዋ ሰው ከድሉ ላይ ካገኘው ነፍጥና እይር በቀር ሌላ አላገኘም ። ራስ መንገሻም ባላገር የወሰደውን ነፍጥና እይር ጠበንጃና ጥይት ሸዋ ከገባን በኋላ ልቅም አድርገው ከባላገር ተቀበሉት ።[1]

ከዚህ አልፈው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ፣ ግራዝማች ዮሴፍም ንጉሠ ነገሥቱ ከነሠራዊታቸው ሲመለሱ አሸንጌ አካባቢ ዞቢል ውስጥ ሲደርሱ ፣ የአዘቦ ኦሮሞዎች ሸፍተው ሰፈር ለመምረጥ ወደፊት ቀድመው የነበሩትንና የእቴጌይቱን ገረዶች እንደ ተተናኮሏቸው ሲገልጹ ፣ ኤድዋርድ ዘይሜንስ የሚባለው ጸሐፊ በበኩሉ ምኒልክ ለራስ መኰንንና ለራስ ወሌ ትእዛዝ ሰጥተው በሺ የሚቆጠሩትን ሸፍቶች እንዳስቀጧቸውና ቀጥሎም ደጃዝማች እንዳርጋቸው የሚባሉት የራስ መንገሻ (ዮሐንስ) ሹም እዚሁ ወረዳ ተቀምጠው እንደ ዘረፉዋቸው ያመለክታል ።[2]

* አንድ እልፍ ዐሥር ሺ ፣ ዐሥር እልፍ መቶ ሺ ስለሆነ ፣ በቁጥር ግራዝማቹ ከጸሐፊ ትእዛዙ ተለያይተዋል ። ምናልባት ጸ.ት.ገ. ሥላሴ ለራስ መንገሻ የተሰጠውን ብቻ ሲጽፉ ግራ.ዮሴፍ ለሌሎችም መኳንንት የተሰጠውን ደምረው ይሆናል ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቁ.82

2 Sul Campo di Adua . . .PP. 74 -75.

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ በገቡበት ቀን ፥ በሊቀ መኳስ አባተና በጭፍሮቻቸው ትጋት ቀደም ብለው አዲስ አበባ ደርሰው በደንብ ተጠምደው የሚጠባበቁት መድፎች የደስታ ድምፃቸውን አሰሙ ። በተረፈ ምንም ተጽፎ ባናገኘው ከመናገሻ ከተማ ውጭ ከሰባት ወራት በላይ በዘመቻ ያሳለፉት ንጉሠ ነገሥት ከነጦራቸው የድል አድራጊነትን ግርማ ተጐናጽፈው ከከተማው ሲገቡ ወንዱ በሆታ ፥ ሴቱ በእልልታ ፥ በታላቅ የደስታ ግርግር እንደተቀበሏቸው የታወቀ ነው ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የቤተ ክህነቱን አቀባበል ሲያመለክቱ በዚህ ታላቅ አገባብ ላይ የከተማውን ሕዝብ የሞቀ አቀባበል አልዘረዘሩትም ።

በካህናቱ በኩል የተደረገውን አቀባበል ግን ፥ የእንጦጦ ማርያምና የራጉኤል ፥ የሥላሴና የዑራኤል እንደዚሁም የጊዮርጊስ ካህናት ልብሰ ተከህኗቸውን እየለበሱ ቀደም ብለው በሰፊው ጃንሜዳ ተሰብስበው ይጠብቁ ስለነበረ ፥ " ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ኢጣልያ "መሬቷ በኢጣልያ ደም ታጥባ ፋሲካ (ደስታ) አደረገች የሚለውን ጠቅሰው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት አሸበሸቡ ሲሉ አመልክተዋል ።*

ለዚህ ለዓድዋ ድል ተስማሚ የሆነ ቅኔ የአክሱሙ አለቃ መንክር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መወድስ ቅኔ ለንጉሠ ነገሥቱ አበርክተዋል ።**

አመ ተክለ አሚን ጸለየ በልማደ ኖኅ
ሥላሴ ይኅድሩ ውስተ ቤተ ምኒልክ ሴም
ወሎቱ ይክሥቱ መጽሐፈ ዕጻሃ ለሮም
ምኒልክ ክዓወ በላዕለ ሮሜ ምሉዓ ጽዋዓ መዓቱ ዘቱሱህ በደም
ምረረ ሐሞቱ ለምኒልክ እስከ ነጥዒም ሐደገ ወጻግመ ኢይጥዕም

ለዓለም

ለምኒልክሂ አመ ኃበ ዓጽሙ ዘተክለ ሃይማኖት ዓጽም
ምኒልክ ለእመ ሐመ ተክለ ሃይማኖት የሐምም
ባህቱ ኢይሕምም ይብል ተክለ ሃይማኖት ፍጹም
ምኒልክ ይህየወኒ ወኢይሙተኒ ለዓለም ። (1)

---

* በድጓ ዜማ ውስተ "ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ" የሚለውን በደመ ኢጣልያ ብለውታል ።

** የቅኔው ፍሬ አሳብ በላይኞቹ መስመሮች በተክለ ሃይማኖት ጸሎት ሥላሴ ከምኒልክ ቤት አድረው የሮማን የመከራ የዕዳ ጽሑፉን እንደ ገለጹላቸው ያመለክታል ።

1. መጽሐፈ ቅኔ መልአከ ብርሃን አድማሱ ገጽ 312



ከሁሉ የበለጠ የጐጃሙ ሊቅ መምህር ወልደ ሥላሴ እንደ መልክ አድርገው ፥ ላፄ ምኒልክ በግእዝ ደርሰው ያበረከቱት የደራሲውን ሊቅነት ብቻ ሳይሆን ፥ እኙሁ ምሁር የፖለቲካውንም የጦርነቱንም ታሪክ በትክክል የተከታተሉት ይመስላል ። ድርሰታቸውንም ብላንሻር የሚባለው የፈረንሣይ ሊቅ ወደ ፈረንሳይኛ ተርጒሞት ሙሴ ፋርኔ የሚባሉት ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ በጻፉት የሁለት ቅጽ መጽሐፍ ላይ ጨምረው በሕትመት አራብተውታል ። ሁሉን በዚህ ምዕራፍ ለማስፈር ስለማይቻል አጀማመሩን ብቻ ከዚህ ቀጥለው ባሉት መስመሮች ብንመለከት የሁሉንም አሳብ ይገልጽልናል ።

ጣልያን በትግሬ አገር ስለ መሸነፉ

1/ ሰላም ለዝክረ ስምከ መልአክተ ኩሉ ዘኮነ
ወበግርማሁ ግሩም እንተ አጥፍዓ ጣልያነ
ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ መድኅን
ቀተልኮ ለዓላዊ ከምድረ ትግሬ መካን

የእንግሊዝ መንግሥት ለኢጣልያ መደረቡን በመጥቀስ ደግሞ እንደዚህ ብለዋል ።

2/ ሰላም ለአእናፊከ ከመ ጼና ገነት ምዑዝ
ሱራሬሆን ሠናይ ወጥቀ ሐዋዝ
ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ አርዝ
ሶበ ተለቅሃ ኢጣልያ ወርቀ አይሁዳዊ እንግሊዝ
ዘይከፍል ሰዕነ አሐዘ ትካዝ ።

በዓድዋው ጦርነት ጠቅላይ አዝማች በገኔራል ባራቲዬሪና በንጉሡ በኡምቤርቶ ላይ ሲተቹ ደግሞ ፤

3/ ሰላም ለአፉከ ለፈጣሪ ዘየአኩቶ
ኢይትናገር ሰላቀ ወኢይነብብ ከንቶ
ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ለኢትዮጵያ ማኅቶቶ
ኃልቀ ማንጀር (ማገዮር) ወሰዕነ ፍኖቶ
ገኔራል ባራቲዬሪ ሶበ ገብዓ ደንገፀ ኡምቤርቶ

ከዚያ ወዲያ በየጊዜው ለዳግማዊ ምኒልክ ፥ ለእቴጌ ጣይቱ ፥ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ የተደረሰው የአማርኛ ግጥም ብዙ ነው ። የአብዛኞቹ ገጣሚዎቹ ስም አይታወቅም ። ከብዙው በጥቂቱ ከዚህ የሚከተለው ነው ።

1/ ጣልያን ገጠመ ከዳኛው ሙግት
አግቦ አስመሰለው በሠራው ጥይት
አሁን ማን አለ በዚህ ዓለም
ጣልያን አሰደንጋጭ ቀን ሲጨልም
ግብሩ ሰፊ ነው ጠጁ ባሕር
የዳኛው ጌታ ያበሻ ባሕር

ሼዋ ነው ሲሉት ዓድዋ የታየው
ሺናሻ መላሽ ወንዱ አባ ዳኘው
አይኰረተም እጁ የዘናው
ወንዱ ምኒልክ ዝንታለም ይቅናው
ወዳጁም ሣቀ ጠላቱም ከሳ
ተንቀሳቀሰ ዳኘው ተነሣ
አራቱ አህጉር ለሱ እጅ ነሣ
ፈረሱ ዳኘው ሚስቱ ጣይቱ
ምጥዋ ወርዳ ቀዳች ወጥ ቤቱ[1] (ከሐሰን አማኑ)

2/ ምኒልክ ተወልዶ ባያነሣ ጋሻ
ግብሩ እንቁላል ነበር ይኸን ጊዜ አበሻ ።
በሠራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ
ተፈጠመ ጣልያን አበሻ እንዳይደርስ ።
ምኒልክ ተጉዞ የምትጠይቁኝ
ፊትም አላለፈ ኋላም አይገኝ ።
መድፉን መትረየሱን ባድዋ መሬት ዘርቶ
እንክርዳዱን ነቅሎ ስንዴውን ለይቶ
የዘራውን እህል አጭዶና ወቅቶ
ላንቶኔሊ አባየው ፍሬውን አምርቶ ።
እንዳቀና ብሎ ለምኖ መሬት
ንግድ ሊያስፋበት ሊዘራ አትክልት
እየመጣ ሲሰጥ ግብሩን ለመንግሥት
ለጓዙ ማረፊያ አገር ቢሰጡት
ተጠማኝ ስንብቶ ሆኖ ባለርስት
ወሰን እየገፋ ጥቂት በጥቂት
እውነት እርስት ሆነው ተቀበረበት ።
ባሕር ዘሎ መምጣት ለማንም አትበጅ
እንደ ተልባ ስፍር ትከዳለች እንጂ
አትረጋምና ያለተወላጅ ።
የዳኘው አሽከሮች እየተባባሉ
ብልት መቆራረጥ እንድነት ያውቃሉ
ዓድዋ ከከተማው ሥጋ ቆርጠው ጣሉ ።
የእስክንድር ፈረስ መቼ ተወለደ*
የምኒልክ ፈረስ በክንፎቹ ሔደ ።
ደንገላሳ ሲዘል እየተንጓደደ
የሮማውን ኩራት በእግታ አሰገደ ።
አገርህን ምኒልክ እንዳሁን ፈትሻት
አጁን ቀምሼ አላውቅ እያለ ሲያማህ
ቀመስና እጅህን መጥቶ ጠላትህ
ሮም ላይ ተሰማ ለጋስ መሆንህ ።

1 ዝክረ ነገር ፡ ብላቴን ጌታ ማኅተም ሥላሴ ፡ ገጽ 879—880
* ትልቁ እስክንድር በክንፉማ ፈረስ ወደ ሰማይ ወጣ ከተባለው ጋር በማመሳሰል



አባተ በመድፉ እምሳውን ሲገድል
ባልቻ በመትረየስ ነጥሎ ሲጥል
የጐጃሙ ንጉሥ ግፋ በለው ሲል
እቴጌ ጣይቱ እቴጌ ብርሃን
ዳዊቷን ዘርግታ ስምዓኒ ስትል
ተማራኪው ባዙቅ ውሀ ውሀ ሲል
ዳኘው ሰጠው አለ ሠላሳ በርሜል ።
እንደ በላዔ ሰብእ እንደመቤታችን
ሲቻለው ይምራል የኛማ ጌታችን[1]

1 የኢትዮጵያ ታሪክ ካፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ. (9ነኛ እትመት) ገጽ 148

# ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

## የአዲግራት ምሽግ መለቀቅ

አዲግራት የአጋሜ አውራጃ ከተማ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ የስመ ጥሩው ባላባት የደጃች ሰባጋዲስ ተወላጆች ራስ ስብሐት ፣ ደጃች ሐጎስ ተፈሪና ሹም አጋሜ ተስፋዬ በአጋሜ ግዛት ሲጣሉበት ቆይተው በመጨረሻ ለኢጣልያ ያደሩት ሐጎስ ተፈሪ ፣ በ1887 ዓ. ም. ከኢጣልያ መንግሥት ተሾመው ይዘውት ነበር ። ጄኔራል ባራቲዬሪ አዲግራት ከገባ ወዲህ ምንም እንኳ ዋና ተቀማጭነቱ አሥመራ ቢሆን ፣ አዲግራትን በደንብ አስመሽጎ የወታደርና የስንቅ ዋና መከማቻ አድርጎ መላውን ትግሬን ለመያዝና ለመቆጣጠር መነሻና መገስገሻ አድርጎት ነበር ። እንቶዜሊ ደብረ ኃይላ መጥተው ከነቀኛዝማች ኃይለማርያም ጋር ያደረጉት ጦርነትና አላጌ መጥተው እየተዋጉ የሞቱት ከአዲግራት የጦር ሰፈር ተነሥተው ነው ።

በመጨረሻ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ወደ ሰሜን ተጉዘው በመጀመሪያ መቀሌ ቀጥሎ ዓድዋ ገብተው የጦርነቱ ጉዳይ በተፋፋመበት ሰዓት ጄኔራል ባራቲዬሪም ከነጦሩ መጥቶ የተቀመጠው በዚሁ በአዲግራት ነበር ።" ዳግማዊ ምኒልክም ከነጦራቸው መጥተው ቢከቡን ከምሽግ ውስጥ ሆነን ለማጥቃትና ለማሸነፍ እንችላለን " በማለት ብዙ ቀን በተስፋ ተጠባብቆ ሳይሔዱለት ቀሩ ። በዚህ ፈንታ ከርሱ ጋር የነበሩት ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ ከዚሁ ከአዲግራት ምሽግ አምልጠው ወጥተው ከወገናቸው እንደ ተደባለቁ ባለፈው አመልክተናል ። ዐፄ ምኒልክም በበኩላቸው ፣ የኢጣልያ ጦር ከአዲግራት ምሽግ ወጣ ብሎ በሜዳ ሊገጥማቸው ባለመቻሉ ተናደው ፣ " የሰው አገር ሊፈልግ የመጣ ሰው ጉድባ ገብቶ ይደበቃልን " ብለው ወደ ሐማሴን ለማምራት ከዓድዋ ወደ ገንደብታ የተንቃነቁ ጊዜ ፣ ባራቲዬሪም በበኩሉ በማጕር ፕሬስቲናሪ የሚመራ ያንድ ሻለቃ ጦር እዚያው አዲግራት ትቶ የንጉሡን ጦር እርምጃ ለማገድ ከአዲግራት ወደ እንትጮ ተዛውሮ መሽጎ ተቀመጠ ።

ጄኔራል ባራቲዬሪ ከዓድዋ የጦር ሜዳ ያመለጠ ጊዜ ፥ ወደ አዲግራት
ምሽግ በመሸሸ ፈንታ የተጓዘው አዲግራትን ወደቀኝ ትቶ በረቢ አርአ
የኒና በእንትጮ አድርጎ ወደ ሰንዓፌ ከዚያም ወደ አዲቀይህ በመጨ
ረሻም ወደ አሥመራ ነው ። ሌሎች ሃምሳ አምስት የሚሆኑ የጦር መኰ
ንኖችና ወታደሮች ግን በስንት ድካም ከዓድዋ ተጉዘው አዲግራት ምሽግ
ገብተው ሕይወታቸውን ከሞትና ከምርኮ ለማዳን ችለዋል ።የዓድዋ
ድል ከተሰማ በኋላ ደግሞ ፥ ከምሽግ ውስጥ እየወጡ ለመጥፋት ከሞከ
ሩት ያገር ተወላጅ ወታደሮች ውስጥ አንዳንዶቹ ማምለጥ ሲችሉ ፥
አንዳንዶቹ ደግሞ በኢጣልያኖች እየተመቱ ሞተዋል[1] ። ስለዚህ ከዓ
ድዋ ድል በኋላ የአዲግራት ምሽግ በነራስ ስብሐት ጦር ተከቦ እንደ
ተቀመጠ ብዙ ጊዜ ቆይቷል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፥ ወደ አዲስ አበባ ከመመለሳቸው በፊት ጄኔራል
ባልዲሠራ ለእርቅ ድርድር ማዦር ሳልሳን የላከው ጊዜ የተስማሙበ
ትን የእርቅ አሳብ በመለወጥ ፥ "ዐፄ ምኒልክ ለኛ እምቢ ያሉትን የጠ
ባቂነት መብት ለሌላ መንግሥት እንዳይሰጡ ቃል ይግቡ" የሚል
አሳብ ስለ አመጣ ፥ የፊተኛውን የተስማማንበትን ጽሑፍ እስከታመጣ
ድረስ እዚሁ እኔ ዘንድ ትቀያለህ" ብለውት ይኸንኑ በጽሑፍ ለባል
ዲሠራም እንደ ገለጹለት እናስታውሳለን ።

በዚህ ምክንያት ፥ እርሳቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው የደከመውን
የጦር ኃይላቸውን እንደገና አደራጅተው በአዲስ ኃይል ወደ ትግሬ
እስኪመለሱ ድረስ ራስ መንገሻን በትግሬ ግዛት አደላድለዋል ።
በግዛት የሚዋሰኑዋቸው ራስ ወሌ ብጡል ፥ ምናልባት ኢጣልያኖቹ እን
ደገና አንሰራርተው በራስ መንገሻ ላይ ጦርነት ቢያነሡ እንዲረዱዋቸ
ውና እንደ ደብረ ኃይላው ጊዜም አይለውባቸው ወደ የጁ ቢያፈገ
ፍጉ እንዲቀበሉዋቸው አድርገው ፥ በዚሁ ጊዜ በየሰነዱ ላይ እንደም
ንገነዘበው ፥ ዐፄ ምኒልክ ለራስ መንገሻ ማዦር ሳልሳን አስረክበው
የሰጧቸው ትእዛዝ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ ጄኔራል ባልዲሠራ ከደብረ ኃይላው ጦርነት ቆስለው የተማረኩ
ትን እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን በነጻ ሲለቅ ፥

፪ኛ/ የኢጣልያ ትራፊ ጦር ከውጭ እንደ ተከበበ የተቀመጠበትን
የአዲግራትን ምሽግ በሰላም አስረክቦ ለቆ ሲወጣ ፥

፫ኛ/ በማዦር ሳልሳ እጅ የተላከውን የእርቅ ድርድር የሚያመለክ
ተውን የጽሑፍ ሰነድ ሲመልስ ማዦር ሳልሳ ወደ ወገኖቹ እን
ዲመለስ ፥

1 Sul Campo di Adua . .PP. 98-99.



፬ኛ/ እኛ ከሸዋ እስክንመለስ ድረስ ባልዲሠራ ጠብ እንዳይጭር በተ
ቻለ መጠን የስምምነት መልክ እያሳየህ የሆነውን ሁሉ ቶሎ
ቶሎ ላክልን የሚል ነው ።[1]

በዚሁ ጊዜ ፥ ምንም ተጽፎ ባናገኘው ፥ በፊት ጠበኞች የነበሩት
እነራስ ስብሐት ፥ እነደጃች ሐጐስ ተፈሪ እነደጃች ተድላ አባ ጉበን
በስምምነት በራስ መንገሻ ውስጥ ሆነው በሕብረት እንዲሠሩ ያስማሙ
ዋቸው መሆኑን ሁኔታው ያስታውቃል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፥ በሚያዝያ ወር ላይ ከትግሬ ወደ አዲስ አበባ
ካመሩ ወዲህ ከላይ በተጠቀሰው አሳብ መሠረት ፥ ጄኔራል ባልዲሠራና
ራስ መንገሻ በዓድዋ ፥ በዩሃና በእንትጮ ስለ ወደቁት የኢጣልያኖች
ሬሣና ዓፅም ማስለቀም ፥ በትግሬ መኳንንት እጅ በምርኮ ወይም ቆስ
ለው በምሪት ስለ ተቀመጡት ጣልያኖችና ስለ አዲግራት ምሽግ መለ
ቀቅ ጉዳይ በየጊዜው በጽሑፍና በመልከተኛ አማካይነት ግንኙነት
ጀመሩ ። በራስ መንገሻ በኩል የዚህን ጉዳይ ለመፈጸም የተወከሉ በፊት
ከኢጣልያኖች ጋር የነበሩት ደጃች ተድላ አባ ጉበን ፥ ወጣቱ ልጅ
አብርሃ ፥ * በጅሮንድ ብሩ ፥ አሳላፊ ኃይሉና ሌሎችም ሲሆኑ ፥ ከኢጣልያ
ኖች ወገን ደግሞ ኮሎኔል አሪሞንዲ የሟቹ የጄኔራል አሪሞንዲ ወን
ድም ፥ ማዦር አንጌራና ሞንታናሪ ናቸው ።በነርሱ ውስጥ ደግሞ ፥ ዋናው
አስተርጓሚ አቶ ገብረ እግዚአብሔርና ሌሎችም የባንዳ ሹማምንት
አሉ ። ባንድ ወገን ደግሞ የራስ አሉላ ሰዎች ፊታውራሪ ፈንታ ፥ ልጅ
ተሰማ ፥ ልጅ ተስፋዬ የሚባሉት ከራስ መንገሻ ወኪሎች ከነአሳላፊ
ኃይሌ ጋር በማስረከቡ ረገድ ጠብ እየተቀሰቀሰ እኛ የራስ አሉላን
እንጂ ፥ የራስ መንገሻን ትእዛዝ አናውቅም በማለት ክርክር ይደረግ
ነበር ።ሆኖም በመጨረሻ የጠቅላይ ገዥው የራስ መንገሻ አሳብ ተፈ
ጻሚነት ስለነበረው ፥ በማናቸውም ጣልያኖቹ በራስ መንገሻና በሹማም
ንቶቻቸው አያያዝ ተደስተው ነበር ።በዚህ ጊዜ ከሁሉ የበለጠ ለኢጣ
ልያኖቹ ወዲያና ወዲህ እያሉ በትጋት የዚህን ጉዳይ ይፈጽሙላቸው
የነበሩት ገብረ እግዚአብሔር ናቸው ። ስለዚህም በዚሁ ሰዓት የነበ
ረው ዘይመንስ የሚባለው በጻፈው ውስጥ ፥ "ወጣቱ ታማኙ ፥ ብልሁ
ቀልጣፋው ገብረ እግዚአብሔር ለኛ አልማዝ ነው ። እርሱም የሳንጊዩይኔቲ

1 Storia Diplomatica . . C. Rossetti, P. .187, Adua, Bellavita, P. 432.

* ልጅ ተድላ አባ ጉበንና ልጅ አብርሃ ሁለቱም ያፄ ዮሐንስ አጐት የትልቁ የራስ
አርአያ ልጆች ናቸው ። አብርሃን በታላቅ ወንድማቸው በደጃች ደብብ አማካይነት
ኢጣልያኖች በልጅነታቸው ወስደው በቶሪኖ ከተማ ቢያስተማሩዋቸውም ባሁኑ ጊዜ
ኑራቸውን ከራስ መንገሻ ጋር አድርገዋል ።

አስተርጓሚ ነበር ። ባሕታ ሐጎስ ሳንጉይኔቲን ያሰረው ጊዜ በእስረኝነት አብሮ ከመካፈሉ በቀር በብዙ ጥበብና በወንድምነት መንፈስ እንዲያመልጥ አድርጎታል ።ገብረ እግዚአብሔር በኮዓቲት እንዳደረገው አሁንም በዓድዋ ተዋግቷል ”[1] ብሏል ።

ስለዚህ አሁንም እነጄኔራል አሪሞንዲ የሞቱበትን ስፍራ በመጠቆም ምርኮኞቹና ቁስለኞቹ ተለቀው ወደ አሥመራ በነጻ እንዲሔዱ ለራስ መንገሻ በቃልም ፣ በጽሑፍም በማሳሰብ ከሹማምንቶቻቸውም ጋር ተባብረው በመሥራት ገብረ እግዚአብሔር ለኢጣልያኖቹ አገልግሰዋል ። ስለቁስለኞች ጉዳይ ለራስ መንገሻ ደብዳቤ ጽፈው ኖሮ ለዚሁ ከራስ መንገሻ የተሰጣቸውን መልስ ከዚህ እንደሚከተለው እናነባለን ።

> መልእክት የራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከገብረ እግዚአብሔር ካሳላፊ ኃይሉ ። እንዴት ሰነበታችሁ እኔ ደህና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን ። የስደድህልኝ 'ገብረ እግዚአብሔር' ደብዳቤ ደረሰኝ ። የመምጣታችሁን ነገር አንድ ጊዜ አይባል ሁለት ጊዜ ሦስት ጊዜ ከራስ አሉላ ደብዳቤ ስድጄአለሁ ። የኢጣልያ ቁስለኞች እስተእሁን የዘገዩም በጣም እስቲድኑ ብዬ ነው እንጂ በሌላ ነገር አይደለም ። አሁንም በዩሃ በንትሙው ያሉ ቁስለኞች እሺ ይውሰድዋቸው ። ለራስ አሉላም ይስጧቸው ብዬ ልኬባቸዋለሁ ። ከናንተ ጋር ለመጡ መኳንንት በብዙ ሰላምታ ስጡልኝ ። ተጻፈ አመ 20 ወ 6 ለግንቦት (፲ 888 ዓ.ም.)

“ከናንተ ጋር ሳሉት መኳንንት ሰላምታ ስጡልኝ” ያሉት እላይ ለተጠቀሱት የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ለነኮሎኔል አሪሞንዲ መሆን አለበት ። “ለራስ አሉላም ይስጧቸው ብዬ ጽፌአለሁ” ያሉት በራስ አሉላ ሰዎች እጅ የሚጠበቁ ስምንት የኢጣልያ ምርኮኞች ከነዚሁ አንዱ ሌሪ የሚባል የመቶ አለቃ ያለበት ነበሩ ። ሁለት ሦስት ጊዜ ከራስ መንገሻ ተጽፎላቸው ሳለ ፣ ራስ አሉላ ምርኮኞቹን ለመልቀቅ ቅር ያላቸው ይመስላል ።ከዶጋሊ ጀምሮ እስከ ዓድዋ ከኢጣልያኖቹ ጋር ሲዋጉ የኖሩት ዝግናው አሉላ አባ ነጋ ፣ ምናልባት ለጠቅላላው ወረራና ጦርነት አንድ ውልና ገደብ በይፋ ሳይበጅለት ምርኮኛን ለጠላት ማስረከቡ ቅር ብሏቸው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ፣ የምርኮኞቹና የቁስለኞቹ ጉዳይ በነራስ ስብሐት በነደጃች ሐጎስ ተፈሪ እጅ ያሉትም ጭምር ባንዳንድ ምክንያት

1 Sul Campo di Adua, Ximenes, PP. 227-228.



እየተወዛገበ በሚቆይበት ጊዜ፣ ጄኔራል ባልዲሣራ አዲስ ከኢጣልያ አገር ይዞት የመጣው ብዙ ጦር ነበረውና በዚያ እየተመካ የማስፈራሪያ ቃል ለራስ መንገሻ በደብዳቤ ጽፎ ላገሬውም እንደዚህ የሚል ቃል በአማርኛ አጽፎ እንዲበተን አደረገ ።

> እኔ ዤኔራል ባልዲሣራ ትልቁ የመንግሥት መኰንን የኤርትራቅኝ አገር ገዥ ለአጋሜና ለትግሬ ሕዝብ ፣ ስሙኝ እኔ የመጣሁት ምርኮኞቼን ለመውሰድና ሰላም ለማድረግ ነው ። ራስ መንገሻ ምርኮኞቼን ካልሰጠኝ ጦርነት አድርጌ አገሪቱን ለማፈራረስ ግዴታዬ ነው። መንግሥት የሚለው ይኸን ነው ። ምርኮኞቼን ስጡኝ ፤ እናንተም ወደ የቤታችሁ ተመልሳችሁ አሁን የዝናም ጊዜ ስለሆነ እርሻችሁን እረሱ እኔ ወታደሮቼን እንጂ መዣሪያም አልፈልግ . . . ወታደሮቼን እስከ ሦስት ቀን ካላገኘሁ አጋሜን በሙሉ አጠፋዋለሁ ።

ይኸም የተለመደውን የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ጉራ ለመንዛትና በዚህ ዓይነት አስፈራርቶ በማወናበድ በአዲግራት ምሽግም በውጭም ያሉትን ጣልያኖች በቶሎ ከነሕይወታቸው ለመረከብ ነው እንጂ ፣ ካለበት ቦታ ተንቃንቆ ጦርነት ለማድረግ ሁኔታው አያመቸውም ። የመንግሥቱም መሪ ትእዛዝ ልክ በኢትዮጵያ በኩል እንዳለው ከነራስ መንገሻ ጋር በተቻለ መጠን በሰላም ለመቆየት ነው ።

አዲግራት በውጭ በራስ ስብሐትና በደጃዝማች ሐጎስ ጦር እንደተከበበ እምሽጉ ውስጥ ያሉትም ኢጣልያኖች ፣ “ከውስጥ እየተዋጋን እናልቃለን እንጂ ፣ ምንም ቢሆን እጃችንን ለነራስ ስብሐት አንሰጥም” ብለው ሁለቱም ወገኖች በዚህ ዓይነት ተፋጠው ሳለ ፣ በመካከሉ ራሱ ጄኔራል ባልዲሣራ ከአሥመራ ከነጦሩ በሌተና ጄኔራል ዴል ማይኖንና በሌተና ጄኔራል ሐሸ ታጅቦ ወደ አዲግራት አቅራቢያ መጥቶ በአቅራቢያው በቸርሰበር ሰፈረ ። ከዚያም ጄኔራል ዴል ማይኖን ካንድ ክፍል ጦር ጋር ወደ አዲግራት ልኮ ከባቢዎቹ እነራስ ስብሐት በኢጣልያ ጦር እንዲከበቡ ሞከረ ። ይኸውም ሁልጊዜ ለማስፈራራት ካልሆነ የውስጠኞቹም ፣ ዴል ማይኖም እነራስ ስብሐትን ለመውጋት አልደፈሩም ። ሁለቱም ወገኖች በማስፈራራት ሲጠቀሙ ፈልገዋል ። ቢሆንም የጄኔራል ባልዲሣራ ዓላማ ቢቻል በሰላም ባይቻል አስፈራርቶ ፣ ሁለቱም ሳይዝ የቀረ እንደሆነ በግዴታ ተዋግቶ የተከበቡትን ነጻ አውጥቶ ለመመለስ ነው ። ስለዚህ አልፎ አልፎ ምንም እንኳን አንዳንድ ግጭት ቢፈጠርም ፣ ሁለቱም ወገኖች የጦርነቱን ጉዳይ በማስፈራራት ደረጃ ብቻ እየተጠቀሙ በዚያው ጊዜ ሁለቱ ጠቅላይ አገረ ገዥዎች (መንገሻና ባልዲሣራ) በቁም ነገር መሠረታዊ የሆነውን ምሽጉን የመልቀቁንና እስረኞቹን የመለዋወጡን ጉዳይ በሰላም ጨረሱ ። ከዚህ በኋላ ጄኔራል ባልዲሣራ እ.ኤ.አ. ግንቦት 4 ቀን 1896 ዓ.ም “ለመያዝ የሚቻለውን

ጓዝና መሣሪያ ይዛችሁ ውጡ” የሚል ትእዛዝ ለምሽጉ አዛዥ
ለማገርር ፕሬስቲናሪ በጽሑፍ አስተላለፈለት ።

ከምሽጉ ውስጥ ያሉት 1500 የሚሆኑት የኢጣልያና ያገር ተወ
ላጅ ወታደሮች ፤ ዐሥራ ሁለት መድፍ ከሦስት መቶ ሃምሳ ጥይት
ጋር ፤ ስድስት መትረየስ ከመቶ ሰማንያ ሺ ጥይትና ከብዙ ጠመንጃ
ጋር ናቸው ። እነሱም ከምሽጉ ውስጥ ሆነው እንደ ተከበቡ የሚደር
ስባቸውን ሲጠባበቁ ከውጭ በጀኔራል ባልዲሠራና በራስ መንገሻ
መካከል ስለ እነርሱ ዕድል የሚደረገውን ንግግርና ስምምነት
እያውቁም ነበር ። ስለዚህ ከስምምነቱ በኋላ የጄኔራል ባልዲሠ
ራን መምጣትና ለመውጣት የሚችሉ መሆናቸውን ያበሠረው ሌተና
ቦድሮቦ የሚባለው ነው ። ቀጥሎ በጄኔራል ባልዲሠራ ትእዛዝ ሌተና
ጄኔራል ዴል ማይኖ ወደ ምሽጉ ገብቶ በታየ ጊዜ ታላቅ ደስታ ሆነ ።
ከዚህ በኋላ የኢጣልያ ባንዲራ ወርዶ ከምሽግ ውስጥ ያለው የቆሰ
ለውና የታመመው በቃሬዛ ፤ ግማሹ በከብት እየሆነ ደህነኛው
መሣሪያውን እየያዘ በሰልፍ መውጣት ጀመረ ። ሲወጣም ጠብ እንዳ
ይነሣ ግራና ቀኝ የቀጥታ መሥመሩን ብቻ ይዞ ወደ አሥመራ
መንገድ እቅጣጫ እንዲሔድ ታዞ ነበር ።

በዚህ ጊዜ ፤ ውጭ የከበበው ወታደርና ኢትዮጵያዊ ባላገር በብዛት
ቆሞ በሚመለከትበት ጊዜ ፤ ግማሹ የሚወጡትን ወታደሮች ማጉላላ
ትና መዝረፍ ፤ ግማሹም ወደ ውስጥ ገብቶ ዕቃ መሻማት ስለፈለገ
ጣልያኖቹን በደንብ ሳይጉላሉ ለማውጣት የታዘዙት ሹም አጋሜ
ተስፋዬና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ ፤ ጭፍራ ጭፍራቸውን ይዘው ይጠብቁ
ነበር ። ብዙ ጊዜም ወታደሮቻቸው በኃይል ዘራፊውን ይበትኑ ነበር።

በዚህ ዓይነት እጠባበቅና ጥንቃቄ ፤ በአዲግራት ምሽግ የነበሩት
የኢጣልያ ወታደሮች ወጥተው ሲያልቁ ራስ መንገሻ በኢትዮጵያ መን
ግሥት ስም ምሽጉን በሙሉ ተረከቡ ። በዚሁም ጊዜ በስምምነቱ
መሠረት እነዚያ ምጥዋ ናኩራ ታስረው የነበሩት ቀኛዝማች ኃይለ
ማርያም ፤ ልጅ ብሥራት መንግሥቱ ፤ መምህር ሐናንያ ፤ ሊቄ ወልደ
የሱስ ለራስ መንገሻ ተሰጡ ። * እንደዚሁም ራስ መንገሻ በእጃ
ቸው የነበሩትን ማገርር ቶማሶ ሳልሳንና ሌሎቹንም የኢጣልያ ምር
ኮኞች በይፋ አስረከቡና ባልዲሠራም ከነጭፍራው ወደ አሥመራ

* ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ከሸዋ ሔደው በደብረ ኃይላ ጦርነት ቆስለው የተ
ማረኩ ፤ መምህር ሐናንያና ሊቄ ወልደየሱስ ስለእርቅ ከራስ መንገሻ ዘንድ ተልከው
ሳለ ጄኔራል ባራቲዬሪ ሰላዮች ናችሁ ብሎ ያሰራቸው መሆናቸውን እናስገነዝባለን።
ልጅ ብሥራትም የታሰረው በዚሁ ሰበብ ሳይሆን አይቀርም ።



ጉዞውን ጀመረ ። ከተማው አዲግራትና አውራጃው አጋሜም በፍጹም
ከኢጣልያ ቁጥጥር ነጻ ሆኖ ለራስ መንገሻ ተመለሰ ።

በርክክቡ ጊዜ የኢጣልያ መኮንኖች ፤ “ለሰላም ንግግር የተላከ
ውን ሳልሳን ማሰር እንዴት ይገባል” ብለው ራስ መንገሻን ቢወ
ቅሷቸው ፤ ራስም መልሰው ፤ “ እንደዚህ ያለውን የተማርነው ከናንተው
ነው ። ከሳልሳ በፊት ስለእርቅ የላክናቸውን እነመምህር እናንያን በማ
ሰር የቀደማችሁ እናንተ ናችሁ” ብለው በማሾፍ መለሱላቸው ይባላል ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት

## የመስኮብ የቀይ መስቀል ሐኪሞች አዲስ አበባ መድረስና ያበረከቱት የሕክምና አገልግሎት

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ፣ በጀኔራል ስቬይቭ የተመራውን የመስኮብ የቀይ መስቀል ሐኪሞች አመጣጥና አገልግሎት እንደዚህ ሲሉ ባጭሩ ጠቅሰው አልፈውታል ።

> በዚህም ጊዜ የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት በኢጣልያ ጦርነት የቆሰለውን የኢትዮጵያ ሠራዊት መድኃኒት እያደረጋችሁ አድኑ ብለው የቀይ መስቀል ማኅበር ሐኪሞች ሰደዱ ። ሐኪሞቹም በሐምሌ 28 ቀን 1888 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገቡ ። ለቁስለኛውም ለሐኪሞቹም ቤት ተሠርቶ መድኃኒት ማድረግ ዠመሩ ።[1]

ባለፉት ምዕራፎች ፣ ከዓድዋ ጦርነት በፊት የፊታውራሪ ዳምጠው ከተማንና የጓደኞቻቸውን መስኮብ ደርሰው መመለሳቸውን ፣ እንደ ተመለሱም ፊታውራሪው ወደ ዓድዋ ዘምተው በውጊያው ላይ መሞታቸውን አንብበናል ። አሁንም በዚያው በተወጠነው የወዳጅነት ግንኙነት መሠረት በሊዮንቴቭ አሳሳቢነት የሁለቱን መንግሥት ወዳጅነት ለማጠንከር በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል ውጊያው እንደማይቀር በመገመት ፣ የመስኮብ መንግሥት በአማካሪነትም በሕክምናም ኢትዮጵያን የሚረዱ በርከት ያሉ ሐኪሞችና የጦር መኰንኖች ያሉበት የቀይ መስቀል ጓድ አቋቋመ ።

በቅድሚያ ኮንት ሊዮንቴቭ ከፒዮትርቡርግ እ.ኤ.አ የካቲት 1 ቀን 1896 ዓ.ም. ወደ ዙሪክ ከተማ (ሲዊስ) ደረሰ ። በዚያም ወዳጁና ያጼ ምኒልክ ዋናው አማካሪ እንጂኔየር አልፍሬድ ኢልግ በለገሐር

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ.64 ፣ ገጽ 271

ጡብቆ ተገናኘው ። በዙሪክ በኢልግ ቤት ሲጨዋወቱ ካደሩ በኋላ ስለቀይ መስቀሉ ማኅበር ጓድ ጉዞ ከአውሮፓ በምጥዋ በኩል አድርገው ወደ ዐፄ ምኒልክ ለመዝለቅ ታስቦ ነበር ። የጓዱ አቅዋም የሕክምና ሰብአዊ አገልግሎት ባሕርይ ያለው ስለሆነ ፡ እንደዚህ ያለውን ጉዞ የኢጣልያ መንግሥት አይቃወምም የሚሉ ተስፋ ነበር ። በዚህም ጊዜ የዓድዋው ጦርነት ገና አልተጀመረም ። በየካቲት 23 ቀን ለመፈጸም ጥቂት ጊዜ ነው የቀረው ። በእርግጥም የተፈጸመውም ሊዎንቴቭና ጓዶቹ ወደ ኢትዮጵያ ለመድረስ በጉዞ ላይ እንዳሉ ነው ።

ነገር ግን ከኢልግ ጋር ሲመካከሩ ፡ የኢጣልያንና የኢትዮጵያን ጦርነት መባባስ ከሊዎንቴቭ የበለጠ በቅርብ የተከታተለው ኢልግ የምጥዋውን መስመር እንደማይሆን ስለ አስገነዘበው ጉዞው በፈረንሳይ የወደብ ከተሞች በማርሴይና በጅቡቲ በኩል እንዲሆን ተወሰነ ። ይህንንም ከኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሲኞር ብላን መመሪያ በመቀበል ፓሪስ የሚቀመጠው ካርሎ አልቤርቶ ማፌይ፣ “ለምን በፈረንሳይ ወደቦች ያልፋሉ’’በማለት ለፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ክርክር አቅርቦ ነበር ። እንደዚሁም ማርሴይ የሚቀመጠው ካርካኖ የሚባለው የኢጣልያ ቆንሲል ጓዱ በማርሴይ ሲያልፍ ፡ የሰዎቹን ቁጥርና የያዙትን መሣሪያ ለማየት ተጣጥሮ ነበር ። ነገር ግን በወሬ ካልሆነ በቀር በትክክል ለማወቅ አልቻለም ።

የሆነ ሆኖ ፡ ከማርሴይ በየካቲት 16 ቀን ያራ በሚባል በፈረንሳይ መርከብ ተሳፍረው እስከንድርያ በደህና ከደረሱ በኋላ ፡ ከዚያም ኑብያ በሚባል መርከብ ተጉዘው ጅቡቲ ገብተው ከጅቡቲ ወደ ሐረር ገቡ ። በዚህም ጉዞ ላይ እንዳሉ የዓድዋ ድል ተፈጽሞ ንጉሠ ነገሥቱ በዓድዋና በአካባቢው ስለ እርቅና ስለ ምርኮኞች ጉዳይ በማዦር ሳልሳ አማካይነት ከጄኔራል ባልዲሣራ ጋር በመጻጻፍ ያንድ ወር ጊዜ ካሳለፉ በኋላ ፡ ወደ ሸዋ ለመመለስ አሸንጌ ሐይቅ አጠገብ ፈረስ ማይ እንዳሉ ሊዎንቴቭ ከጅቡቲ በግሥጋሤ መጥቶ ተገናኛቸው ። እርሳቸውና መኳንንቶቻቸውም በፍቅርና በደስታ ተቀበሉት ። ምንም እንኳን ስለ ወዳጁ ስለ ፊታውራሪ ዳምጠው መሞት ቢያዝንም ፡ በተገኘው ድል እንደሚደሰት የታወቀ ነው ። ከዚህ በኋላ ሌዎንቴቭ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጣ ። ሐኪሞቹና የጦር መኰንኖቹ ግን በግንቦት ወር ሐረር ገብተው ግማሾቹ እዚያው ሐረር ቆይተው የቀሩት በሙሉ በሐምሌ ወር አዲስ አበባ ገብተው ንጉሠ ነገሥቱና መኳንንቱ የጋለ አቀባበል አድረጉላቸው ።

የመልእክቱ ጓድ የበላይ መሪ ማዦር ጄኔራል ስቬዶቭ ሲሆን ቁጥራቸው እስከ ስልሳ አንድ ይደርሳል ። ከነዚሁ አምስት የኤታ



ማዦር መኰንኖች ፡ ሰባት ሐኪሞች ከስድስት ረዳቶቻቸው ጋር ሁለት ፋርማሲስቶች ፡ ከአራት ረዳቶች ፡ ዐሥራ ሁለት የሴት ፡ ሐያ አንድ የወንድ አስታማሚዎች ፡ ሁለት አስተርጓሚዎች ካንድ መነኩሴ ጋር ፡ እንደዚሁም ፕሮፌሰር ፖሎቶቭ የሚባል የኢትዮጵያን ቋንቋና ሥልጣኔ የተመራመረ ይገኙባቸዋል ። የዘመኑ ጸሐፊ በጄኔራል የሚመራው የመስኮብ ጓዶች ብዙ ሹማምንት ፡ ብዙ የጦር የሕክምና መሣሪያ ስለያዙ በምኒልክና በመኳንንቶቻቸው ዘንድ ትንሽ ሥጋትና ጥርጣሬ ጥሎ እንደ ነበረና በኋላም በወዳጃቸው በኮንት ሊዎንቴቭና አገላለጥ ማግባባት ሁኔታው ተስተካከለ ። ከቀይ መስቀሉ ጓድ ጋር የመጡት የጦር መኰንኖች የአመጣጣቸው ዓላማ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል የተጀመረው ጦርነት እየባሰ የሔደ እንደሆነ በኢትዮጵያ ጐን ተሰልፈው ኢጣልያን ለመውጋት ፡ ጦርነቱ አልቆ እንደሆነ ከሁለቱም ወገን የቆሰለውን እያከሙ ለማዳንና በዚያውም ለዘለቄታ የሚሆን በሐረርና በአዲስ አበባ ነዋሪ የሕክምና ሆስፒታል ለማቋቋም መሆኑንም ገለጠ ። እያደርም ሁኔታው እንዳመቸ የመስኮብ መንግሥት በኢትዮጵያ ተደግፎ አንድ የወደብ ከተማ አግኝቶ በንግድና በፖለቲካ መስከ ለመጠቀም መሆኑን አብራርቶአል ።

ከዚያም ለሐኪሞቹ ከሁለት ላይ ለሕክምና ተስማሚ በሆነ ቦታ ላይ ቤት ተሠርቶ ሐኪሞቹ ቀዳጆቹም ፡ የወንድና የሴት አስታማሚዎቹም ከነመሣሪያቸው እሁለት ቦታ ተመድበው የሕክምና ሥራቸውን በትጋት ዠመሩ ። አሁን የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ባለበት ሥፍራ ዋናው የሕክምና ቤት ተሠርቶ ፡ ሠላሳ የሚሆን አልጋ ተዘርግቶ በየቀኑ ሁለት መቶ ሃምሳ ቁስለኛ ሲታከም ፡ ሐረር የቀሩትም እስከ አንድ መቶ ሰው ያከሙ ዠመር ። በዚህም ጊዜ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመስማማት የኢጣልያንንም ቁስለኞች አብረው በማከም በኢጣልያኖቹ በኩል ተመስግነዋል ። በጠቅላላው ከኢትዮጵያ ወገን የታከሙት ቁጥራቸው ዐሥራ አንድ ሺ ስድስት መቶ ሲሆን ፡ ከነዚሁ ሰባት መቶ ሃምሳ ቀዶ ጥገና የተደረገላቸው መሆኑን መስኮቦቹ የተዉት ሰነድ ያመለክታል ።

ቀጥሎም የመስኮብ መንግሥት ሌጋሲዮን ከተከፈተ ወዲህ ፡ በሌጋሲዮኑ የሚሠሩት የኮር ዲፕሎማቲክ አባሎች ከነጸሐፊዎቻቸው ቁጥራቸው በርክቶ የመስኮብና የኢትዮጵያም ወዳጅነት እየተስፋፋ ሲሔድ የእንግሊዝና የኢጣልያን ፡ ቀጥሎም እስካሁን ለሁለቱም ወዳጅ የነበረውን የፈረንሳይን መንግሥት ጨምሮ በመጠኑ ከሥጋት ላይ ጥሎ ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፡ የመስኮብና የኢትዮጵያ ወዳጅነት ሥር እየሰደደ ከመሔድ አላቋረጠም ። ያፄ ምኒልክ ፡ የእቴጌ ጣይቱና የመኳንንቱ ሁሉ

ምስጋና ለመስኮብ መንግሥትና ሕዝብ አላቋረጠም ። ዘቅናትና በም ቀኝነት የሆነ ያልሆነውን እያስወሩ ብዙ የአውሮፓ ተወላጆች ሊዎን ቴቭንም ከምኒልክ ለማጣላትና ለማራቅ ሞክረው ነበር ። ይሁን እንጂ አልሆነላቸውም ። እንዲያውም በመጨረሻ ያለፈ አገልግሎቱን በመገምገም በ1890 ዓ.ም. በግንቦት ወር ዳግማዊ ምኒልክ የራስ ተሰማ የነበረውን የገሙ ጐፋን አስተዳዳሪነት ጨምረው ከሙሉ ሽል ማት ጋር የደጃዝማችነት ማዕርግ ሰጥተው አከበሩት ።

ይኸን ሹመት ተቀብሎ በ1891 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ሲሔድ ፣ ልክ እንደ አንድ የኢትዮጵያ ከፍተኛ መኰንን በሁለት ሺ የእግረኛና የፈረሰኛ ወታደር ታጅቦ ተጓዘ ። ከእርሱም ጋር ዓረቦ ችና ሴኔጋሎች የራሱ ወገኖች እነፊታውራሪ ባቢቾፍ ፣ እነ ሰቢሎን ፣ ሌሎችም ዶክተር ካን ማሪዮስቡሼ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የተመደቡት አብረውት ነበሩ ። እሱም ልክ እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት ልማድ ለበታቾቹ የፊታውራሪነት ፣ የቀኛዝማችነት . . .ማዕረግ እየሰጠ ለሠራ ዊቱም ግብር እያገባ በግብነት ጭፍራውን ያስደስት ነበር ይባላል።[1]

እንደዚህ እምሮበት ወደግዛቱ ከገባ በኋላ ፣ ደጃዝማች ሊዎንቴቭ እንደቀሩት የኢትዮጵያ ደጃዝማቶች እንደአገሩ ልማድ አቅሙን ዐውቆ ሥልጣኑን ገታ አድርጎ በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ሥር እየ ታዘዘ በቀጥታ የተሰጠውን አውራጃ በጸጥታና በሰላም ማስተዳደር አልቻለም ።

በዚህ ፈንታ በወርቅ ፣ በብረት ማዕድን ፣ በዝሆን ጥርስ ንግድ ለመክበር ተነሣ ። ከንጉሠ ነገሥቱም ያስፈቅድ ከፈረንሳይ ፣ ከእንግ ሊዝና ከቤልዥክ የንግድ ኩባንያዎች ጋር በቀጥታ እየተጻጻፈ ማኅበር ለማቋቋም በአክሲዮን ተካፋይ እንዲሁኑ ሌሎቹን የማኅበር አባሎች እየ ጋበዘ የወርቅና የብር ሌላም ማኅበር ለማቋቋም ይጣጣር ዠመር ። "በገሙጐፋ ፣ በእም ወንዝ ግራና ቀኝ ያለው አገር ለሕይወት ጤናማ ሲሆን ወርቅ ፣ ብረታ ብረት ፣ ብርና መዳብ ለማውጣት የሚያመች ፣ እህልና ቡና ሌላውንም ማናቸውንም አዝርእት የሚያበቅል ገነት የሆነ መልካም አገር ነው" እያለ የውጭን አገር ኩባንያዎች በማኅ ኅት ማኅበሮቹ እንዲቋቋሙ አደረገ ። ዳግማዊ ምኒልክ በቅድሚያ ሳያስታውቅ ይኸንንም ሁሉ የሚጻጻፈው በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ መሆኑን መግለጡ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሲሰማ ታላቅ ቅርታ በገዛ እጁ ፈጠረ ። እንደ ቀድሞው በመወደድና በመክበር ፈንታ ፣ "ለሥልጣንና ለሀብት የጓጓ አታላይና ደፋር ነው" የሚል ግምት በቤተ መንግሥቱም ፣ በውጭ አገር መልክተኞችም ዘንድ አሳደረ ።

1 I Russi in Etiopia . . .PP. 237 - 256, 270 - 302.



ስለዚህ ፣ ይኸን ሁሉ የሰሙት ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ምኒልክ አዲስ አበባ ለሚገኙት ለውጭ አገር መልክተኞች ሚኒስትሮች ለእን ግሊዙ ለሚስተር ሐሪንግተን ፣ ለፈረንሳዩ ለሙሴ ላጋርድ ፣ ለመስኮ ቡ ለሙሴ አርሎቭ ፣ ለኢጣልያው ለሲኞር ቺኮዲኮላ በጻፉት ደብዳቤ ፣

> ደጃዝማች ሌዎንቲፍ በእንግሊዝና በቤልዥክ አገር ከኔ ያስፈ ቀደ በማስመሰል ብዙ የወርቅ የማዕድን ማኅበር ማቋቋሙን ሰማሁ። . . . በኔ በኩል በኢትዮጵያ መሬት ላይ የወርቅ ማዕድን ለማውጣት በምንም ዓይነት የፈቀድሁለት ነገር የለም ። . . . እስካሁን ወሬውን ሰምቼ በቶሎ ያልጻፍሁላችሁ ነገሩ ወሬ ስለ መሰለኝ እርግጠኛውን ነገር እስከረዳው ድረስ ብዬ ነው ። እርሱም ከኔ ፈቃድ ወጥቶ በራሱ ፈቃድ እንደዚህ ያለውን ነገር ያደርገዋል ብዬ ስለ አልጠረጠርሁ ነበር . . . አሁንም ይኸን ነገር ሐሰት መሆኑን ላገራችሁ መንግሥ ትና ሕዝብ ወደ አገራችሁ ስትመለሱ አስታውቁ . . .[1]

በማሰት አስታወቁ ። እርሱም ከግዛቱ ተሽሮ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ በመጥፎ ሁኔታ ወደ አውሮፓ ተመለሰ ። ፍጻሜውን ለጊዜው አናውቅም ።

1 I Russi in Etiopia, PP. 368 - 371.

# ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት

## ስለ ምርኮኞች ነጻነት የሮማ ሊቀ ጳጳስ ልዮን 13ኛና ዳግማዊ ምኒልክ የተለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎች

በኢጣልያ አገር ፣ ስለ ዓድዋ ድል ብድር መመለስና አለመመለስ የተደረገው ሁካታ እያደር ሲቀዘቅዝ ስለ ምርኮኞቹ ያለው ሥጋትና ክርክር እየበዛ ሔደ ። በተለይ የዚህ ሥጋት ያደረባቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የምርኮኛ ቤተ ሰቦች ናቸው ። እነርሱም የሞተውን ፣ የቆሰለውንና የተማረከውን በትክክል ለይተው ባለማወቅ ይህ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው ፣ የተማረኩትም ነጻ የሚሆኑበትን መንገድ የመንግሥት መሪዎችን እየፈለጉ በአቤቱታ አሰለቹዋቸው ። እያንዳንዱ የዘመዱን ሁኔታ ባለማወቅ ቤተሰቦቹ ምንም እንኳ ተቺጋሪዎች ሆነው መንግሥቱን ቢያስቸግሩትም ፣ በጠቅላላው የኢጣልያ ሕዝብ በጉዳዩ ማሰቡ አልቀረም ። በፊተኛው ዘመን ሕዝቡም ፣ ቤተ ክህነቱም ፣ ከመቀሌውና ከዓድዋ ጦርነት በፊት ስለ ወረራውና ስለውጊያው ፈቃደኛ ሆነው ለመዝመት ወይም ዘማቾቹን በዘፈን በመሸኘት ይደሰቱ ነበር ። አሁን ግን ፣ በዓድዋ የተረጋገጠው የኢትዮጵያ ድል አድራጊነት የሁሉንም ቅስም ስለ ሰበረው የቀኝ ክፍሎች ፣ "የመበቀያ ጦር እንላክ" ያሉትንም መንግሥቱን የተረከበው የግራው ክፍል "እይሆንም ከሰላም በቀር የሚያዋጣን የለም" ብሎ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ስለ ወሰነ ፣ ባሁኑ የሁሉም አሳብ ያተኮረው ኢትዮጵያ ላሉት ምርኮኞች እርዳታ የሚላከበትን መንገድ መፈለግ ብቻ ሆነ ። ንጉሡ ኡምቤርቶ ግን በዚህ ጊዜ እንደቀኙ ቡድን በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ብስጭት እድሮበት እርሱም እንደ ማኩረፍ ብሎ ተቀምጧል ።

ስለዚህ ፣ ከሕዝብ ውስጥ በተለይ ባንዲት ቼዛሪኒ በምትባል የንጉሡ የኡምቤርቶ የቅርብ ወዳጅ በሆነች የሚመራ የሮማ እመቤቶች የእርዳታ ማኅበር ተቋቋመ ። ዓላማው ለሕዝብ ጥሪ አድርገው የእርዳታ ገንዘብና ልብስ እንዲሰበሰብና እርዳታው ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ለምርኮኞቹ እንዲደርሳቸው ለማድረግ ነበር ። ይኸንኑ የሚያከናውኑ ሰዎች ተመረጡ ። የእርዳታውም ገንዘብ ከተሰበሰበ በኋላ ኮንት ካርሎ ቢርስዊዝ

የሚባለው ዋና መሪ ሆኖ ኡንዲንና ዋትካሜልን በመጨመር
የእርዳታውን ገንዘብ ይዘው ከኢጣልያ አገር ተነሥተው ግማሾቹ
በዘይላ ፣ ግማሾቹ በጅቡቲ በኩል ሲጓዙ ፣ ከጅቡቲ ወደ ሐረር መን
ገድ የጀመረው መሪው ኮንት ቬርስዊዝ በመንገድ በፀሐይ በትር
ታሞ ሐረር ሲደርስ ሞተ ። ሌሎቹ እነኡንዲን በኢትዮጵያ መንግ
ሥት ፈቃድ ወደ አዲስ አበባ መጡ ። አዲስ አበባ በደረሱ ጊዜም
በ150 ወታደር የታጀቡ ሹማምንት መጥተው በታላቅ ክብር ተቀ
በሏቸው ። እንጂኒዬር አልፍሬድ ኢልግ በንጉሠ ነገሥቱ ስም ቀርበው
የንጉሠ ነገሥቱን ሰላምታ አቀረቡላቸው ። በማግሥቱ በብዙ ካህናት
ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔደው በአምስት ሰዓት ላይ ወደ
ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው ንግግር አድርገው ፣ የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ደብ
ዳቤ እንዳስረከቡ ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ በላኩት ራፖር ላይ ገልጸ
ዋል ።

ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከልዮን 13ኛ ለዳግማዊ ምኒልክ የተጻፈው
ደብዳቤ ከኢጣልያንኛ ወደ አማርኛ ሲተረጐም ቃሉ እንደዚህ የሚል
ነው ።

በጣም ኃያል ለሆኑት ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከልዮን
13ኛ ፓፓ በጣም ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት ሰላምና ገናንነት ለርስዎ ይሁን ።
የጵጵስናችን ዘመን በጀመረበት ጊዜ የሊቀ ካህንነታችን ኢዮቤልዩ በተ
ከበረ በ10ኛው ዓመት ልባዊ በሆነ ተግባር ሰላም ይሉን ዘንድ ወደዱ*
ይህም የደግነት ምስክር መሆኑ ነው ። በዚህም ደግነት ልባችንና
ልብዎ ተገናኝቷል ። ዛሬ አንድ ንጉሣዊ ልግሥና እንዲያደርጉ የምክር
ቃላችንን ክርስቲያናዊና ንጉሣዊ ለሆነው ልብዎ ለመላክ አሰብን ።
ይህ ድል ብዙ ምርኮኞች በእጅዎ ጥሎልዎታል ። እነዚህ ምርኮኞች
በወጣትነታቸውና በጎልማሳቸነታቸው ዘመን የኑሮአቸው ተስፋ
ባበበበትና የብርሃኑ ጉህ በቀደደበት ሰዓት ካገራቸውና ከቤተሰባቸው
ተነጥለው ይገኛሉ ።

የነርሱ ምርኮ የግርማዊነትዎን ዝናና ገናናነት ምንም ሊያስፋ
ፋው አይችልም ። ይልቅ የነርሱ የምርኮ ጊዜ በረዘመ መጠን በሺ
የሚቆጠሩት የእናቶቻቸውና የንጹሐኑ ሚስቶቻቸው የመንፈስ ሐዘን
እየበዛ ሔደ፣ል ። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበልነው ለክርስቲ
ያን አገሮች ሁሉ በሚስፋፋው የተቀደሰ መልእክት (ሐዋርያነት)
እንደ ልጆቻችን ያህል እንወዳቸዋለን ። ስለዚህ ያንድ አባት ልብ በቅ
ድስት ሥላሴና በተባረከችይቱ ድንግል ወይም ከዚህ ዓለም በአለው
በሚወዱት ስም የሚያቀርብልዎትን ልመና ይቀበሉና ሳይዘገይ

* ንጉሠ ነገሥቱ ከዚህ በፊት ከዚያው ከትግሬ እንዳሉ የጻፉላቸውን ሲያወሱ
ነው ።



ነጻነታቸውን ይስጡዋቸው ። ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ይኸን የደግነት
ሥራ ባለመሥራት እምቢታዎን ባለም ነገሥታት ዐይን ፊት አይግለጹ ።
ይህችን ክብር ያላትን ገጽ (ደብዳቤ) በመንግሥትዎ ዜና መዋዕል ያስ
መዝግቧት ። በወንድማማችነትና በሰብአዊነት ተግባር እንጻር ያለው
የጦር መብት ምንድነው የዚህን ብድር ርኅሩኅ አባት እግዚአብሔር
በብዙ ይክስዎታል ። እንደዚሁም በሺ የሚቆጠሩ ድምጾች ከነዚያው
የመጀመሪያይቱ የኛ የምትሆን ባንድነት ሊያመሰግኑዎ ይነሣሉ ።
እስከዚያም ለንጉሣዊው ቤተ ሰብ እግዚአብሔር በረከት እን
ዲያወርድ እንለምናለን ። ሮማ እቅዱስ ጴጥሮስ አጠገብ 11 ግንቦት
1896 ዓ. ም. በ19ነኛው ዘመነ ጵጵስና ተጻፈ ።

ይህ ደብዳቤ ፣ ሊቀ ጳጳሱ ለንጉሠ ነገሥቱ ለዳግማዊ ምኒልክ የጻ
ፉት ነው ። አጻጻፋቸው አክብሮት ያለበት ሆኖ ዐፄ ምኒልክ ከዓ
ድዋ ድል በኋላ በእጃቸው ለወደቁት ምርኮች ርኅራኄ አድርገው
በቶሎ እንዲፈቱዋቸው በአባትነት የሚለምን ነው ። እንደ እውነቱ
ቢሆን ፣ የሮማ ሊቀ ጳጳስ የክርስቲያኖች ሁሉ የበላይ አባትነት እንደ
ሚሰማቸው ሁሉ አስቀድሞ ኢጣልያኖቹ ባሕር ተሻግረው ፣ "የሰው
አገር ካልወረርን" ብለው ለጦርነት ሲዘጋጁ ፣ የአምባላጌና የመቀሌ
እልቂት በተደረገበት ጊዜ ሁሉ ከሁለቱም ወገን ለሚፈሰው ደም በመ
ራራት እቅርባቸው የሚገኙትን እንደ ልጆቻቸው የሚመለከቷቸውን
ንጉሡን ኡምቤርቶንና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ክሪስፒን ፣ "የሰው አገር
ለመውጋት ጦር አትላኩ የሰው አገር መፈለግ ይቅርባችሁ" ብለው
አልመከሩዋቸውም ። ሶሺያሊስት የሆኑት ጣልያኖች የተቃወሙትን
ያህል እንኳን ቀርቶ ከዚያም ያነሰ ለዚህ ለግፈኛ ወራሪነት ያባትነት
ድምፃቸውን እሰሙ የሚል ጽሑፍ አልተገኘም ። ከዚህ በፊት እንዳል
ነው የርሳቸው ምኞት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በጦርም ይሁን በፖለቲካ
ይዛ በበላይ እንድታስተዳድር የመንግሥቱን ሥልጣን መከታ አድር
ገው የሮማ ቤተ ክርስቲያን ቢቻል መላውን ፣ ያለዚያም የተቻለ
ውን ያህል የካቶሊካውያንን ቁጥር አበርክተው መንፈሳዊ ሥልጣናቸው
በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ነው ። አሁንም ምኒልክ ከዚያው ከዓድዋ በመ
ጋቢት ወር ላይ ለጻፉላቸው ሮሮ ፣ "እውነትዎን ነው ፣ የኢጣልያ ንጉ
ሥና ጠቅላይ ሚኒስትር አገርዎን ለመውረር በመሞከራቸው አጥፍተ
ዋል" አላሉም ።

ይሁን እንጂ ፣ ዐፄ ምኒልክ ምንም እንኳ የሊቀ ጳጳሱ ንግግርና
የምርኮኞቹም ሁኔታ ቢያሳዝናቸው ፣ በእጃቸው የወደቁትን ምርኮ
ኞች ፣ ስለ ወሰኑም ጉዳይና ስለ ግናቸውም አንድ ውል ከማድረጋ
ቸው በፊት መልቀቅ ፣ ለመንግሥታቸውና ለሕዝባቸው እንደገና ሁከት
መፍጠርን ስለሚያስከትልባቸው ፣ የዚህን የችግራቸውን ምክንያት የሚገ
ልጽ ደብዳቤ አዘጋጅተው ምንሲኞር መቃርዮስን መልሰው ላኩ
ዋቸው ። የላኩት ደብዳቤ ትክክለኛ ግልባጩ የሚከተለው ነው ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአ
ብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ወደ ክቡሩ ወደ ተቀደሱ የሮም ሊቀ ጳጳሳት ሊዮን 13ኛ
ሰላም ለርስዎ ይሁን ። የከበረው ያባትነትዎ ደብዳቤዎ ባቡነ መቃርዮስ
እጅ ደረሰልኝ ። በዚህም ደብዳቤዎ የቀድሞው መላላካችንን እሳምሮ
የሚያስታውስ ፤ እግዚአብሔር ከኔ እጅ የጣላቸውን ስለ ኢጣልያ ምርኮ
ኞች የሰብአዊነት ሥራ እንድሠራ የሚያመለክት መሆኑን በጣም እየሁ ።
ደግሞም የከበረ ቅድስናዎ ከአቡነ መቃርዮስ የበለጠ መልክተኛ ነገ
ሩን በጣም አስረድቶ አጣፍጦ ሐሳብዎን የሚናገር መላክ እንዳይቻ
ልዎ ዐወቅን ። የክርስቲያን ሁሉ አባት የላከው እጅግ የሚያስደንቅ
ደብዳቤዎን ባነበብሁ ጊዜ ልቤን መታው ። ዳግመኛም የከበረውን የመ
ልክተኛዎን የቃል ንግግር በሰማሁ ጊዜ ልቤ ቅድስናዎን በማክበር ስለ
መኑኝ ጉዳይ ለመፈጸም ጨክኖ ነበር ። እኔ ሳልፈልገው በዚህ በክፉ ጦር
ደማቸው ሰፈሰሰው በክንቱ ላለቁት ወታደሮች እጅግ አለቀስሁ ። ነገር
ግን ፤ ቅድስናዎ የተመኙትን ለመፈጸም የኢጣልያ መንግሥት ያልታሰ
በው የዛሬ ሥራቸው የማያስፈጽመኝ ሆነ ። ይህንንም ማለቴ የእርቅ ፈቃ
ድና በደህና ስመላላክ መመኘታቸውን ካሳዩኝ በኋላ ፤ ሥራቸው በጦርነት
እንደ አለን እድርገው ይሔዱ ኸመር ። አሁንም የሚገባኝ ንጉሥነቴና
የሕዝብ አባትነቴ ይህን ዐውቆ በእጄ ያለውን የእርቅ መያዣ መል
ቀቅ የማይቻለኝ ሆነ ። ቅድስናዎ ያሰበውን ሐሳብ ደስ ለማሰኘት የኔም
መልካሙን ሐሳብ ለመፈጸም ከለከለኝ ። በክርስቲያንነቴና በንጉሥነቴ
ልብ አውጥቼ አውርጄ ሳበቃ ፤ የፍቅሬን ምልክትና ብዙ ማክበሬን
በሌላ ቀን እደርገዋለሁ ማለት ስለ ሆነብኝ ዛሬ ሳይሆንልኝ በመቅ
ረቱ እጅግ ያሳዝነኛል ። እግዚአብሔር እደራ የሰጠኝ መንግሥቴን
የሕዝቤን ነጻነት የምፈልግ ስለሆንሁ ፤ ክርስቲያኖች ሁሉ በማክበር
የሚሰማውን የቅድስናዎን ድምፅ ለኛ ብለው እንዲያሰሙልን ተስፋ
አለን ። ይህ የሆነ እንደሆነ ከዘመዶቻቸውም ስተለዩ ምርኮኞች በቅ
ርቡ ለመመለስ እንዲመቹን ማድረግም ነው ። ነገር ግን ይህ ነገር እስ
ኪጨረስ ድረስ ከኔ ዘንድ ያሉትን ምርከኞች እንደ ክርስቲያን ሥራ
ከዚህ ቀደም ጠብቄ በመልካም አድርጌ እንዳኖርኋቸው ይልቁንም
ከእንግዲህ ወዲህ ስለእርስዎ ፍቅር በጣሙን ጠብቄ በደህና አሳምሬ
እንዳኖራቸው በዚህ አይጠርጥሩኝ ። መስከረም 12 ቀን በአዲስ አበባ
ከተማ ተጻፈ ። በ1889 ዓመተ ምሕረት ። 1

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ
ልመና እስረኞቹን ለመልቀቅ አስበው ሳለ ፤ በመካከሉ የኢጣልያ መን
ግሥት ባንድ ወገን ፤ "ስላምና መልካም ግንኙነት እደርጋለሁ " እያለ
በሌላ ወገን የበደል ሥራ መፈጸሙን ስለ ቀጠለ ፤ የምሕረት አሳባቸውን

1 Bibliothecae Apostolicae Vaticanae Codice Manu SCR1PT1 . . .
በቁጥር 88 የሚገኝ ። Adua- E. Bellavita PP. 447 - 449



እንደለወጡ ያስረዳል ። ይህ በደል የተባለው " ዶልዊክ " የሚባል የሆ
ላንድ መርከብ ወደጅቡቲ ለንግድ ሲመጣ "በውስጡ ለኢትዮጵያ መን
ግሥት የሚሆን የጦር መሣሪያ ጭኗል "ብለው በሆላንድ ያሉ የኢጣ
ልያ ዲፕሎማቶች ስለጠቆሙ ፤ መርከቡ የባብ ኤል መንደብን የባሕር
ሰርጥ አልፎ ጅቡቲ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ፤ በኢጣልያ መንግሥት
ትእዛዝ ኢይና የሚባለው የኢጣልያ የጦር መርከብ በማሳደድና በመ
ማረክ ወደ ምጥዋ ሒዶ እንዲራገፍ አስገደደው ።

ሃይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሆነው የቂሳርያ ኤጲስ
ቆጶስ ክቡር አባ መቃርዮስ የሊቀ ጳጳሱን ደብዳቤ ይዘው መጥተው
እስረኞቹን ለማስፈታት በቤተ መንግሥቱ እጠገብ ተቀምጠው ዐፄ
ምኒልክን ደጅ ይጠኑ ነበር ። በዚሁ ሰዓት ዐፄ ምኒልክም፤ "ሊቀ ጳጳሱንና
አባ መቃርዮስን ደስ ለማሰኘት ሙሉውን ምርኮኛ ያም ቢቀር በመስ
ኮብ ንጉሠ ነገሥት ልደት የለቀቁትን ያህል ሊለቁ ነው" እየተባለ
ይወራ ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱና እማካሪዎቻቸው ስለዚሁ ጉዳይ በሚመ
ካከሩበት ጊዜ በመካከሉ፤ "ለኢትዮጵያ መሣሪያ የያዘውን የሆላንድ
መርከብ ኢጣልያኖች ማረኩት" የሚለው ወሬ ሲደርስ ነገሩ ወዲያው
ደፈረሰ ። በዚህም ዓይነት የኢጣልያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር የጀ
መረውን የጠብ መንገድ አልተወም ተብሎ ተገመተ ።መቃርዮስ ለር
ዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በጻፉት ራፖር ላይ ፤ "ንጉሠ ነገሥቱ ዤኔራሉንና
የጦር መኰንኖቹን አስቀርተው ፤ የቀረውን ምርኮኛ ወታደር በሙሉ
ለመልቀቅ ተስፋ ከሰጡኝ በኋላ በመካከሉ እንጅኒየር ኢልግ "በመር
ከቡ መያዝ ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ አሳባቸውን ለወጡ ብሎ እያ
ዘነ ነግሮኛል "ሲሉ ጠቅሰዋል ።

ይሁን እንጂ ፤ የምርኮኞቹን አለመለቀቅ የእስናከለው የመርከቡ
መማረክ ብቻ አይመስልም ። ነገር ግን አጥቂና ወራሪ ሆኖ የመጣው
የኢጣልያ ጦር ምንም እንኳን በዓድዋ የተሸነፈ ቢሆን ፣ ዤኔ
ራል ባልዲሡራ ኤርትራ ከመጣ ወዲህ ያዲግራትን ምሽግ ለማ
ስለቀቅ ከነራስ ስብሐት ጋር ለጦርነት ተሰልፏል ። "እንደገና መረብ
ንም ተሻግሮ የዓድዋን ብድር ሊበቀል ከነራስ መንገሻ ጋር ውጊያ
ለመግጠም ያስባል " እየተባለ በሚወራበት ሰዓት ፤ የመርከቡ መማ
ረክ ስለ ተጨመረ ደንበኛ ውል ሳያደርጉ እነዚህን እንደ ዋስትና በእጃ
ቸው የወደቁላቸውን ምርኮኞች በሊቀ ጳጳሱ ልመና ፤ በአባ መቃርዮስ
ደጅ ጥናት ብቻ መልቀቅ እንደማይገባ ጉዳዩ በምክር ተጠንቶ ተወሰ
ኗል ማለት ነው ።እርሳቸውም ራሳቸው ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በጻፉት
ደብዳቤ ውስጥ ፤ "ራሴንና ቅዱስነትዎን ደስ ለማሰኘት ስል የሰላም
መድን የሚሆኑትን ምርኮኞች በዚህ ዓይነት ሁኔታ እያለን ለመልቀቅ

በሕዝብ ላይ ያለኝ የአባትነትና የንጉሥነት ተግባር ይከለክለኛል ” ሲሉ የጨመሩት ቃል ነገሩን በትክክል አብራርቶት ይገኛል ።

ከዚህ ቀደም እንዳልነው ፣ የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን ጠረፍ ወርሮ እስከ አምባላጌ ሲደርስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በነገሩ ገብተው ለመገላገል እንኳ አልሞከሩም ። አሁንም በርሳቸው አማላጅነት ንጉሠ ነገሥቱ ምርኮኞቹን ከለቀቁ በኋላ ፣ ወዲያው ጄኔራል ባልዲሠራ በምኒልክ በኩል የተጠየቀውን ለማሟላት የሚችል መሆኑን ለመሞከር እንኳ ይሞክሩ ይሆናል ብንል የኢጣልያ መንግሥት እሺም እምቢም ለማለት ነጻነት ስለአለው ፣ ለዚህ ምንም ዋስትና የሌለው ነገር መሆኑ የታወቀ ነው ። የኢጣልያ መንግሥትም ከተመቸው ከእሺታ ይልቅ ወደ እምቢታው ማዘንበሉ ግልጽ ነው ። ደግሞ በዚህ ላይ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በአካል ኢጣልያዊ ከመሆናቸው በቀር የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖቷን የምታስፋፋውና የተከታይ ቁጥር የምታበዛው ከጥንት ጀምሮ የካቶሊክ ነገሥታት ከእስፓኝ ፣ ከፖርቱጋልና ከፈረንሣይ እየተነሡ በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ በፋፊ አገር እየወረሩ የቅኝ ግዛት ባስፋፉ መጠን መሆኑ በማንም ዘንድ ይታወቃል ። አሁንም የኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ጉዳዩን አሰናክሎት እርሳቸውም የምርኮኛ ቤተሰብ ስለ አስቸገራቸው ነው እንጂ ፣ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ዓድዋ ላይ አሸንፋ መላዋን አገሪቱን ብትይዝ ደስታ እንደሚሰማቸው የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴውን ልኮ ደንበኛ የሰላም ውል አድርጎ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት እስኪያውቅ ድረስ እነዚህ ምርኮኞች እንዳሉ እንዲቆዩ ያደረጉበትን ምክንያት እንዲገነዘቡላቸው ከዚህ በላይ ያነበብነውን አስተዛዛኝና አጽናኝ ደብዳቤ በመጨመር ፣ በተለይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለእስረኞቹ ልዩ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው አረጋግጠው አባ መቃርዮስን መልሰው ላኩ ።

የሮማ ርእሰ ሊቃ ጳጳሳት ልዮን 13ኛ ከሮማ አንድ ታላቅ የካርዲናልነት ማዕረግ ያለው በመላክ ፈንታ አባ መቃርዮስን ኦርቶዶክሳዊ የቄሣርያ ኤጲስ ቆጶስ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ረዳት የሆኑትን የሊቀ ጳጳሱን ደብዳቤ ይዘው እንዲመጡ ያደረጉበት ምክንያት ለኢትዮጵያውያንና ለዐፄ ምኒልክ እንደ ሃይማኖት አባት ስለሚቆጠሩ ፣ በመንፈሳዊ አባትነት በማባበል ነገሩን አቃንተው ምርኮኞቹን ሊያስፈቱ ይችላሉ በሚል ተስፋ ነው ። አሁንም አባ መቃርዮስ በዚህ ዓይነት የመልሱን ደብዳቤ ይዘው ወደ ሮማ ሲመለሱ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ለማስደሰት ሲሉ ፣ ዐፄ ምኒልክ እስረኞቹን ለመልቀቅ የተቸገሩበት ምክንያት በሙሉ እንደ ተገለጸላቸውና እንደ ተረዱት ፣ አዲስ



አበባ በሰነበቱበት ጊዜ ሁሉ መልካም መስተንግዶ እንደ ተደረገላቸው ከንጉሠ ነገሥቱም ሲሰናበቱ ለመታሰቢያ ትልቅ መስቀል ተቀብለው በደስታ ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ እንደ ተመለሱና ከዳግማዊ ምኒልክ የተጻፈውን ደብዳቤ ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እንዳስረከቡ እኚሁ አባ መቃርዮስ በኋላ በጻፉት ራፖር ላይ በሰፊው ገልጸውታል ።[1]

በዚህ አወዛጋቢ ጉዳይ መሐንዲስ አልፍሬድ ኢልግ እየገቡ በማማከር አባ መቃርዮስን እየመሩ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ በማቅረብና በማነጋገር ፣ ደብዳቤውንም በማዘጋጀት ይሠሩ እንደነበሩ በዚሁ ራፖር ላይ ተጠቅሷል ። ስለዚህ ይኸን የመሰለ ከፍ ያለ የፖለቲካ ጉዳይ ሲገጥም ከሌሎቹ ይበልጥ ከፈረንጆች ወገን እኚሁ የስዊስ ተወላጅ ሙሴ ኢልግ ፣ የፈረንሳዩ ተወላጅ ሙሴ ሞንዶን ፣ የመስኮብ ተወላጅ ኒኮላ ሊዮንቴቭና ከኢትዮጵያ ወገን ደግሞ ራስ መኰንን ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄ አስተርጓሚው ግራዝማች ዮሴፍና ሌሎችም የግናውታቸው በምክርም ፣ በተግባርም የንጉሠ ነገሥቱ የሥራ ተካፋይ መሆናቸው እርግጥ ነው ።

ስለዚህ ፣ የእስረኞቹ መለቀቅ ጉዳይ ከኢጣልያ መንግሥት ጦርነት ወይም ሰላም ፈላጊነት አቋም ጋር የተያያዘ መሆኑን የኢጣልያ መንግሥትም ፣ የሮማ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ተረድተውታል ። ስለሆነም የኢጣልያ ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ኩርፊያው የማያዛልቅ መሆኑን በመረዳት ስለዚህ በመጨረሻ ባለሙሉ ሥልጣን ወኪሉን ወደ አዲስ አበባ ልኮ ደንበኛ ውል እንዲዋዋል ተገደደ ።

1 Storia Diplomatica C. Rossetti—PP.183—206

# ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት

## ማዡር ቼዛሬ ኔራሲኒ የመዋዋል ሥልጣን ተቀብሎ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣ

ዐፄ ምኒልክ ፥ ከእቴጌ ጣይቱና ከቅርብ ረዳቶቻቸው ጋር ከዓድዋ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው እንደገቡ የቀሩትም ታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት ከታናናሽ ሹማምንትና ከተከታዮቻቸው ጋር ወደየአውራጃቸው ተመለሱ። ቤታቸውን ለረጅም ጊዜ ለቅቀው በዘመቻው ምክንያት ሲንከራተቱ የነበሩ ሁሉ ፥ ባሁኑ ጊዜ ይነስ ይብዛ የስምንት ወራት ጣመናቸውን በየቤታቸው በማቃለል ላይ ይገኛሉ ። ዘመዱና ወዳጁ የሞተበት ፥ የቆሰለበትና አካሉ የጐደለበት ወገን ሐዘንተኛ መሆኑ ባይቀርም ቁስለኛውም ፥ አካሉ የጐደለውም ሁሉም ባሁኑ ጊዜ በተገኘው ድል ይነስ ይብዛ መጽናናቱ የማይቀር ነው ።

በዚህ መካከል ፥ ባፄ ምኒልክና በቅርብ ረዳቶቻቸው መንፈስ የሚመላለሰው በምፅዋ በኩል አዲስ ጦር ይዞ የመጣው ጄኔራል ባልዲሠራ የልብ ልብ በቅቶት ያለፈውን የመሸነፍ በቀል ለመመለስ መረብን ተሻግሮ ራስ መንገሻ ዮሐንስን ማጥቃት ይዠምርና ወደ ጦርነቱ እንመለስ ይሆን ወይስ ፈረስ ማይ ሳሉ ፥ በማዡር ሳልሳ አማካይነት የተወጠነው የሰላም ድርድር ወደ ፍጻሜ ይደርስ ይሆን የሚል ነው ። ይኸም ማለት በጦር የተሸነፈው የኢጣልያ መንግሥት ፥ "ከእንግዲህ ወዲህ የጦርነት ነገር በቃኝ ። የውጫሌን ውል ሠርዤ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነትና መንግሥት ዐውቃለሁ" ብሎ ለመዋዋል እንደራሴ ይልክ ይሆን የሚለው አወላዋይ ሁኔታ ነው ። ምንም እንኳ ፓሪስ ባሉት በነአቶ ዘውገ (ነጋድራስ) ወይም በፈረንሳዮቹ በነሙሴ ሽፍነና አቦክ በሚገኙት በነሙሴ ላጋርድ አማካይነት ውሎ አድሮ የኢጣልያንን መንግሥት አቅዋም መስማታቸው ባይቀር በሮማ የሚደረገውን ግርግር በሶሻሊያሊስቶቹ ተጽእኖ ፥ በኢኮኖሚም ውድቀት በክሪስፒ እግር የተተካው ዲ ሩዲኒና አብዛኛው የካቢኔው የምክር ቤት አባሎች ከእንግዲህ ወዲያ ሰላም እንጂ ፥ ጦርነት አለመፈለጋቸውን የየዕለቱን የኢጣልያን መንግሥት አቅዋም ምኒልክና ረዳቶቻቸው በትክክል አያውቁትም ። መወላወሉንም የሚፈጥረው ይኸው ያለማወቅ ሁኔታ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ወደ ሰላም ለመመለስ ከተገደደበት ከጦርነቱ አለመሳካት በቀር የእስረኞቹ በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ መቆየትና የየምርኮኛው የቤተሰብ አባል በየዕለቱ የሚያቀርበው አቤቱታና ውትወታ ነው ። የዚህ ሁሉ ተጽዕኖ አስገድዶ ባለፈው እንዳነበብነው ፣ በምክር ቤት የሰላሙ መንገድ በድምፅ ብልጫ ካለፈ በኋላ ወዳጄ ምኒልክ ተልኮ በውል እስረኞቹን ለማስፈታት የሚችለው ሰው ሲመረጥ ምርጫው ከማዦር ቼዛሬ ኔራሲኒ ላይ ወደቀ ።

ማዦር ኔራሲኒ እንደ እ.አ.ኤ. በ1849 ዓ.ም. በሞንቴች ላቺእኖ (ሲዬና ደቡብ ኢጣልያ) ተወልዶ ያደገ ነው ። ካደገ በኋላ ደንበኛ ሥራው ሕክምና ነበረ ። ከኢጣልያ ወደ ምሥራቅ በሚመላለሱ መርከቦች ላይ የሁለተኛ ደረጃ ሐኪም ሆኖ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ወደ ውጭ ጉዳይ ተዛውሮ በፖለቲካና በስለላ ሥራ ተሠማራ ። ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ በሚመላለስበት ጊዜ እ.ኤ.አ. በ1885 ዓ.ም. ዐፄ ዮሐንስ ዘንድ መጥቶ ተገናኝቷል ። ከዚያ ወዲህ ከኢጣልያ ወደ አሥመራ መቀሌ ፣ ዓድዋ ፣ ሐረር ፣ ዘይላ ከዚያም ወደ ኢጣልያ በመሔድ ኢትዮጵያ ስለምትወረርበት መንገድ በመላላክ ብዙ ጊዜ ተመላልሷል።

የመልዕክቱ ዋና መሠረት ፣ በስሜን በኩል በትግሬ ራስ መንገሻን በምሥራቅ በኩል በሐረር ራስ መኰንንን የተለያየ የንጉሥነት ተስፋ በመንግሥቱ ስም እየሰጠ ካፄ ምኒልክ ሥልጣን ለይቶ ለማሸፈትና በግርግሩ መካከል የኢጣልያ ሥልጣን በኢትዮጵያ ላይ እንዲዘረጋ ለማድረግ ነበር ። በዚህ ምክንያት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከብላን መመሪያ እየተቀበለ ባደረገው ተንኮል ከጓደኛው ከደማርቲኖ ጃኮሞ ጋር ሆኖ በኋላ ባፄ ምኒልክ የፖለቲካ ዘዴ ሊፈርስ የቻለውን በምኒልክ ጀርባ በ1883 ዓ. ም. እ. ኤ. አ. በሐምሌ ወር ላይ በስሜን ኢትዮጵያ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት አስፋፊ የሆነውን ጀኔራል ጋንዶልፊንና ራስ መንገሻ ዮሐንስን መረብ ላይ ማዋዋሉ ይታወሳል ።

ይኸም እያያዘ ፣ በስሜን በኩል እነሊዎፖልዶ ትራቬርሲ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ከቀረ በኋላ ፣ በኢጣልያ መንግሥት ትዕዛዝ ከአሥመራ ወደ ሐረር ተዛውሮ የራስ መኰንንን አቅዋም ፣ የጦራቸውን ድርጅት በሚሰልልበት ወቅት ከመንግሥቱ በመታዘዝ በተቻለ መጠን ራስ መኰንንን ካፄ ምኒልክ ለማስከዳት በሐረር ብዙ ጊዜ ተቀምጦ ቢሞክርም ሳይሳካለት ቀርቶአል ። በስሜን በኩል ጦርነቱ የማይቀር መሆኑን ሲረዳው ከሐረር ወደኤደን ይልቁንም ወደ ዘይላ እየተመላለሰ ፣ ከባለሥልጣኖቹ እንግሊዞች ጋር በመመሳጠር በዘይላ አድርጎ ወደ ሐረር የሚደርስ የጦር ግንባር ለመክፈትና ወደስሜን የዘመተውን ጠቅላላ የኢትዮጵያ



ጦር በሁለት ወገን ጠምዶ ግራ ለማጋባት ሙከራ ማድረጉ ከዚህ በፊት ተመልክቷል ።

ቀጥሎ በሁለም አንጻር ተስፋ የማይቆርጠው ቼዛሬ ኔራሲኒ ፣ በተለይ በኢጣልያ አገር ያሉት ባለሥልጣኖችና በሰሜን ኢትዮጵያ ያሉት ጀኔራሎች ፣ "የምኒልክ አቅም ሲገታን ከቶ አይችልምና ከምጥዋ እስከ እንጦጦ መውረር ነው" የሚለው ፕሮግራም እንዳስጐመጀው በመግለጽ እ.ኤ.አ. በ1895 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ለወዳጁ ጽፎ እንደነበረው ሁሉ፣ አሁንም የዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ የምኒልክን የጦር ድርጅት ለመከፋፈል ሲል ጉግሣ ዳርጌን ከአውሮፓ ወደ አሥመራ ያመጡት ጊዜ በጦርነቱ ሰዓት ከተማውን ለሚጠብቁት ላባትዬው ለራስ ዳርጌ የማግባቢያ ቃል ጽፎ ኖሮ ሐቀኛውና ታማኙ ሽማግሌ ራስ ዳርጌ ፣ "ኔራዚኒ የተባልከውን ናዚራ እባብ ያስመስልሃል" ብለው በማሾፍ የመለሱለትን እናስታውሳለን ።

በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ፣ በፖለቲካና በስለላ ሥራ እንጂ የውትድርና ሙያ ስለሌለው ውጊያውን አልተካፈለም ። በዚያን ሰዓት እሱ ከዘይላ ወደ ሐረር የሚላከውን የአዲሱን ጦር ግንባር ጉዳይ ለመምከር በኤደን ነበር ። በዚህ ወደብ ባንድ ሆቴል ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ፣ የኢጣልያን ጦር የመሸነፍ ወሬ ሬውተር የሚባለው የእንግሊዝ የወሬ ተላላኪ በቴሌግራም ወደ እንግሊዝ አገር ሲያስተላልፍ ሲያስበውና ሳይጠረጥር ስለሰማ ታላቅ ድንጋጤና ብርክ ወረደበት ። የሚያደርገውንም አጥቶ መንፈሱ በሐዘን ፣ ሰውነቱ በድንጋጤና በመሸበር ተበጠበጠ ። ስለዚህ በኢጣልያ አገር ላለው ትንሽ ትልቁን ለሚጽፍለት ባለሥልጣን ወዳጁ ለጀኔራል ሉቺኖ ዴል ቬርሜ ጦርነቱ በተደረገ በአምስተኛው ቀን እ.ኤ. አ. መጋቢት 5 ቀን 1896 ከኤደን በጻፈለት ደብዳቤ ውስጥ እንደዚህ የሚሉ ቃላት ሠፍረዋል ።

> የተወደዱ ጀኔራል የምታጽናና አንዲት ቃል እባክዎ ይጻፉልኝ ፣ እኔ ከሦስት ቀን ወዲህ (ወሬ ከሰማሁበት) ሕይወትም ደምም የለኝም ። እንዴት ያለ አደጋ ሆነ! እንዴት ያለ የሞራል በትር በላያችን ደረሰ! እኔ በድል አድራጊነታችን ተማምኜ ነበር . . . እዚህ አደን ሆቴል ፈረንሳዮች ስለሞሉ በላዩ ላይ ያለውን ጭንቀት ሊገምቱት ይችላሉ ፤ እንግዲህ የኢትዮጵያ ኩራትና ትምክህት የት ይሆን መድረሻው . . .[1]

እንግዲህ ይኸ ሰውዬ ነው አሁን ከኢጣልያ መንግሥት ሥልጣን ተቀብሎ ካፄ ምኒልክ ጋር ሊዋዋል ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው ። ቀደም ብሎ በሮማ በምርጫው ጊዜ ግማሾቹ ከፍ ያለ የጀኔራልነት

1 Precursori del' Impero Africano - R. Truffi PP. 101 103, 128 - 129, 146 - 148

ማዕረግ ያለው ቢላክ ይሻላል ሲሉ እርሱ ደግሞ ፣ ኤደን ላይ እንዳለ በወገኖቹ በመደገፍ ያገሩን ባህልና ቋንቋ እንደሚያውቅና የራስ መኰንን ወዳጅ በመሆኑ መልዕክቱን ለማከናወን እንደሚችል ስለአመለከተ ፣ የመልክተኛነቱ ሥልጣን በርሱ ላይ ስለተመደበ ወደ ሐረር ለራስ መኰንን ሥልጣን እግኝቼ መጥቻለሁና ንጉሠ ነገሥቱ እንዲቀበሉኝ እያለ ደጋግሞ በመጻፍ ይወተውት ገ መር ። ወዳጄ ምኒልክም ደብዳቤ እያይዞ ልኮላቸው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ የርሱን ተንኮልና መርዛማ ጠላትነት አሁንም በመንፈሱ ላይ የደረሰበትን ብስጭት የኛዎቹ አያውቁም ። በዚህ ምክንያት ለጻፈላቸው ደብዳቤ ራስ መኰንን ነሐሴ 7 ቀን 1888 እንደዚህ ሲሉ መለሱለት ።

የተላከ ከራስ መኰንን የሐረርና የአውራጃዋ ገዥ ይድረስ ከወዳጄ ከማገር ናራሲኒ . . . በሰኔ በ27 ቀን ዓመተ ምሕረት 1896 እ.ኤ.አ. ዘኢላ ከተማ ወደ ጃንሆይ የላከውን ደብዳቤ ላክሁት ። ጃንሆይም የደብዳቤህን ቃል አይተው የዚህ ቀደሙን ወዳጅነታችንን የሚያስታውስ ቃል ነበርና ብዙ ደስ አሰኛቸው ። ወደ ጃንሆይም ለመውጣት ፈቅደውልሃል ። አሁንም መምጣትህ ከሆነ ከዘኢላ ሳትነሣ እኔ ስለ ወዳጅነቴ የሚጠቅምህን አንድ አንድ ምክር ላመልክትህ ። ጃንሆይን ዳግማዊ ምኒልክ ከኢጣልያ ጋር የጠፋውን ፍቅር ለመመለስ አይጠሉም ፤ ይፈልጉታል እንጂ ። ስለዚህ መንግሥታችሁ ከኢትዮጵያ ጋራ እንደገና ፍቅርን ለመጀመር ከፈለገ የሚቀናውን የጃንሆይ አሳብ ላመልክትህ ። መጀመሪያ ነገር የውጫሌ ውል ፈጽሞ ካልጠፋ ኢትዮጵያም ፣ ራሷን የቻለች ለራሷም የምትበቃ ባለ ነጻ መንግሥት መሆኗን የኢጣልያ መንግሥት ካልተቀበለ ካላወቀ ፣ ይኸውም በኈረቤቶቻችን በሮጳ (አውሮፓ) ነገሥታት ምስክርነት ካልተጨረሰ ፣ የምትመጣበት ጉዳይ ይቃናልህ አይመስለኝም ። በከንቱ መንገድ አይምታህ ። ለምርኮኞችም የሚጠቅም ነገር ለማድረግ አይመችህም ።

ሁለተኛ ነገር ይኸን ሁሉ የተናገርነውን ነገር የሚፈጽም ሙሉ ሥልጣንህን የሚያስረዳን የታመነ ፣ የተደላደለ ከንጉሡ ከውጭ አገር ሚኒስቴር ከጦርነት ሚኒስቴር በመንግሥታችሁ ማኅተም የተረጋገጠ ደብዳቤ እንደሌለህ ጃንሆይ ጉዳይ ብለው አይቀበሉህም ፤ አስቀድመህ እወቀው ። ይኸንን ሁሉ ነገር በብዙ አድርጌ አሁን ሳንተ ሰወዳጄ ማመልከቴ ሳትነሣ የጃንሆይን አሳብ እንድትረዳው ። አንተም በከንቱ መንገድ እንዳይመታህ ብዬ ነው ። እነዚህን ሁሉት ትልልቅ ፍሬ ነገሮች በውል ለመፈጸም ከመጣህ የቀረው ነገር አያስቸግርም ። ጃንሆይ ከፍቅር ማደስ በቀር ሌላ አሳብ የለባቸውም (የላቸውም) ። ይልቅ አንተኑ የተላክህበት ነገር በቶሎ እንዲቀናህ ይረዱሀል እኔም እንደ ልማዴ በፍቅርና በማክበር አልረሳህም ። ከማገር ሣልሳም ጃንሆይን ቆቦ ድረስ ሸኝቶ የተመለሰ ጊዜ የተነጋገርነው ቃል እንዲህ ነው ። ከኢጣልያ መንግሥት አንድ ትልቅ ሰው ባለ ሙሉ ሥልጣን የእርቅን ነገር ተነጋግሮ የሚፈጽም ሰው እስከመጣ (እስኪመጣ) ድረስ



ሠራዊታችሁ መረብን አይሻገር ፤ የኛም አይሻገርም ብለን ነገር እስኪፈጸም አቆይተነዋል ። ጤና ይስጥህ ። ተጻፈ ሐረር በነሐሴ 7 ቀን 1888 ዓ.ም.[1]

ይኸን ሁሉ የተሟላ ጥያቄ ላፄ ምኒልክ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ አስታውቆ ኖሮ ወዲያው ከንጉሠ ነገሥቱ "ይለፍ ፤ አትከልክለው" የሚል ለራስ መኰንን ደርሷቸዋል ። ለራሱም ጳጉሜ 2 ቀን 1888 ዓ. ም. በተጻፈ ደብዳቤ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ምንም ችግር እንዳያገኘው እንዲያውም በማናቸውም ዕርዳታ እንዲያደርጉለት ማኅተማቸው ያለበትን የይለፍ ወረቀት ጽፈው ልከውለታል ። ስለዚህ በዘይላ በኩል አድርጎ ጊዜው የክረምት መውጫ ስለነበረ ከነጓዙ በችግር ሐረር ገባ ። ራስ መኰንንም በክብር ተቀብለው መልካም መስተንግዶ አደረጉለት ። ከዚያም ጓዙን የሚጭንበት አጋሰስና ለርሱ በመረሻት ያጌጠች ሠጋር በቅሎ ከሰጡት በኋላ ፣ ወደ አዲስ አበባ ተጉዞ በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ 1889 ዓ. ም. (በአውሮፓ አቆጣጠር) ጥቅምት 6 ቀን 1896 ዓ.ም. አዲስ አበባ ደረሰ ።[2]

እንደ እውነቱ ይኸን የመሰለው ሰውዬ ፣ እንደዚህ ያለውን ከፍተኛ ሥልጣን ተቀብሎ ልምጣ ሲል የኢጣልያ መንግሥትም እሱን ሲወክል የኢትዮጵያ መንግሥት የሰውየውን ያለፈውን አድራጎትና የደረጃውንም ዝቅተኛነት ጠቅሶ ለመቃወምና ለዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ስለኢትዮጵያ የተሻለ ስሜት ያለውን ባለሥልጣን ለመጠቆም በቻለ ነበር ። የኢጣልያ መንግሥትም እምቢ ለማለት ባልደፈረ ነበር።

ነገር ግን ፣ በብዙ ያስተዳደር ጣጣ የተከበቡት ዐፄ ምኒልክ ከቅርብ ረዳቶቻቸው በመምከር ፣ "በኢጣልያ መንግሥት የግል ጉዳይ ገብተን እገሌ ይሁን እገሌ አይሁን ማለት አይገባንም ። የንጉሥ ማኅተም ያለበት ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ የመጣውን ማናቸውንም ሰው እንቀበላለን" የሚል ስሜት አድሮባቸው ይሆናል ።

---

1 Archivio storico Diplomatico. poz. 1. 1pos 1. 7 ROMA

2 Precursori del Impero Africano - R. Truffi PP.159 -163

# ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ

## የጦርነቱ ኪሣራ ጥያቄ—በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል የተደረገው ውል

በሠለጠኑትና እኩያ በሆኑት አገሮች መካከል ጦርነት ሲደረግና አንዱ ወገን ሲሸነፍ፣ ተሸናፊው መንግሥት ብዙ ጊዜ በወሰን ያሉትን አከራካሪ መሬቶች ከማጣት በቀር ሁለቱ በተስማሙበት ግምት ተሸናፊው ለአሸናፊው የጦር ካሣ ይከፍላል። ይኸን ሁሉ የሥርዓቱንና የሕጉን አንቀጽ ጠቅሶ የሚከራከር ሒሳቡን በደንብ የሚተምን የተማረ የሰው ኃይል በኢትዮጵያ በኩል መጉደሉ የታወቀ ነው። በጦር ሜዳ ተሰልፎ በጀግንነት የሚዋጋው፣ እንደ ዘመኑ ልማድ አገር የሚያስተዳድረው፣ ዳኝነት የሚሰማው ተርፎ ተትረፍርፎ ሳለ፣ በዚህኛው ግንባር ግን፣ የአገሪቱ ደካማ ጐን ይታያል ማለት ይቻላል።

ስለዚህ፣ ዐፄ ምኒልክ ለዚህኛው ቴክኒክ ላለበት ጉዳይ ይጠቀሙ የነበሩት የአውሮፓን ሁኔታ የኢጣልያንም ሳይቀር እየተከታተለ የሚያስረዳቸው ብዙ ጊዜ ስሙን የጠቀስነው ሞንዶን ቪዳዬ ነው። ለጦር መማሪያ ግዥና አቀራረብ ሊዎን ሸፍኑ፣ ወሰን ሳይኖርባቸው የቅርብ አማካሪዎች፣ እንግዳ አስገቢዎች በተለይ ዋናው የስዊሱ ተወላጅ አልፍሬድ ኢልግ ሲሆን፣ ከርሱም ጐን ሌዎንስ ላጋርድ፣ ሳቡሬ አርማንድ፣ ፒዬር አርኑ የሚባሉ ፈረንሳዮች ይገኙበታል። ከነዚህም ጐን ከዓድዋ ጦርነት በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ የተቀበለው ኒኮላ ሊዎንቴቭ የሚባለው የመስኮብ ተወላጅ አለበት።

እነዚህም የተለያዩ የውጭ አገር ዜጎች፣ አዲስ አበባ ሳሉ በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ ሆነው የተለያዩ አገልግሎት ሲያበረክቱ በየአገራቸውም በሚቆዩበት ጊዜ፣ "ለምሳሌ ሊዎንቴቭ ፒዬትሮ ቡርግ (የዛሬው ሌኒንግራድ)፣ እነሽፍኑና እነሞንዶን ፓሪስ፣ እነላጋርድ አቦክ (ጅቡቲ) በሚገኙበት ጊዜ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የሚነዙትን መጥፎ ወሬ በመቃወም፣ ለኢትዮጵያና ለንጉሠ ነገሥቱ የሚጠቅመውን አገልግሎት ያበረክቱ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም ለያንዳንዱ የውጭ አገር አገልጋይ ከሚያደርጉት ሹመት፣ ስጦታና ሽልማት ጋር

ልባዊ ወዳጅነት ስለሚያሳዩት ፡ የውጭ አገሮች ዜጎች ኢትዮጵያን
እንደ አገራቸው ፡ ምኒልክን እንደ ራሳቸው መሪ ይመለከቷቸው ነበር ።
አልፍሬድ ኢልግ በሚጻጻፍበት ደብዳቤ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ባለ
ሥልጣን የራሱ ማኅተም ነበረው ። በማኅተሙ መካከል የጽሑፍ ስሌዳ
ሆኖ ከወደላይ ወገን በአማርኛ ፡ "ቢቶደድ ኢልግ" ሲል በታች በኩል
"የመንግሥት አማካሪ" የሚል ይገኝበታል ። ከዓድዋ በኋላ
ደግሞ ሙሴ ላጋርድ ቀድሞ የፈረንሳይ መንግሥት በጅቡቲ አገረ
ገዥ የነበረው ከመንግሥቱ ተሰናብቶ ያፄ ምኒልክ አማካሪ በነበረ
በት ሰዓት ከመኳንንቱም ፡ ከማንም ጋር የሚጻጻፍበት ማኅተም ተመ
ካከሉ ስሌዳ ያለው ሆኖ በስሌዳው ላይ አክሊልና ስሌዳውን ሁለት
የቆሙ አንበሶች እንደሚደግፉት ሲታይ ፡ በላይ በኩል በግዕዝ "እግዚእ
ዕቀባ ለኢትዮጵያ" የሚል ፡ በታች በኩል "ላጋርድ የእንጦጦ ዱክ"
ይላል ። "እግዚእ ዕቀባ ለኢትዮጵያ" ማለት ጌታ (አምላክ) ኢትዮጵያን
ጠብቃት" ማለት ነው ።

አሁን ከኢጣልያ ጋር የዕርቅ ድርድር በተዠመረበት ሰዓት አል
ፍሬድ ኢልግ ቀደም ብሎ ፡ ሊዎንቴቭ ከተል ብለው ሁለቱም ወደ
ሮማ ሔደው የኢጣልያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ስለሚከፍለው የጦር
ኪሣራ መነጋገር ዠምረዋል ።

ኢልግ ከአዲስ አበባ ወደ ዙሪክ (ስዊስ) ሔዶ ከዚያም ወደ
ሮማ ዘልቆ ስለ ኪሣራውና ስለ እርቁ ጉዳይ በምኒልክ ስም ለመነ
ጋገር በሚዘጋጅበት ጊዜ ፡ ባለቤቱ ማዳም ኢልግ ባሏ የምኒልክ ባለ
ሚል አማካሪ በመሆኑ ፡ አሁን ሮማ ለመሔድ በሚያስብበት ጊዜ ፡
"በዓድዋ በኢጣልያኖች መሸነፍ የተበሳጩት ወገኖች ቢገድሉህስ"
በማለት ተከላከላ ነበር ። ነገር ግን ፡ በወዳጁ በኢጣልያዊው በአወግ
ስጦስ ፍራንዘይ አማካይነት ተጻጽፎ ማረጋገጫ ከተቀበለ በኋላ በሰኔ
ወር ወደ ሮማ ሔደ ። ከዚያም ሊዎንቴቭ በነሐሴ (1888) ደርሶ ሁለ
ቱም የኢጣልያ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ኪሣራ
እንዲከፍል አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ማርኬዝ ዲ ሩዲኒን ቢጠይ
ቁት ፤

. . . የኢትዮጵያ መንግሥት ለምርኮኞች ያወጣውን ኪሣራ
በመቶ ሺ ወይም በሚሊዮን የሚቆጠር ሊሬ ቢሆን እከፍላለሁ እንጂ
የጦር ኪሣራ አልከፍልም ። በዚህ ምክንያት እስረኞቹ ቢቸገሩም ቢሞ
ቱም እንደ ፈቀደው ። ምኒልክ የጦር ኪሣራ ከፈለጋቸው እዚሁ ሮማ
ይምጡና በመጠየቅ ይሞክሩኝ . . .

ብሎ መቁረጡን ፡ ይኸንኑ ለንጉሥ ኡምቤርቶ ማመልከቱንና ን
ሡም አሳቡን እንደ ደገፈ ታወቀ ።



በአዲስ አበባም ፡ ይኸው የኢጣልያ መንግሥት አቅዋም በት
ክክል ከታወቀ ወዲህ ፡ ንጉሠ ነገሥቱና አማካሪዎቻቸው የራሳቸውን
ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ለማስፈጸም ያላቸውን አቅዋም በመገምገም
ዋናው ፍሬ ነገር የዓድዋን ጦርነት ያስከተለውን የውጫሌውን
ውል የኢጣልያ መንግሥት ሠርዞ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ካወቀ
ውሉ ይፈረም ፡ እስረኞቹም ተለቀው አገራቸው ይግቡ ተብሎ የውለ
ታው ነገር እንዲፈጸም ተወሰነ ።

ውለታው በአማርኛና በፈረንሳይኛ ጐን ለጐን ሆኖ እንደሚከተ
ለው ይነበባል ።

በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢጣልያ መንግሥት ማኸል (መካከል) የተደረገ
የዕርቅ ውል ይህ ነው ።

በቅድስት ሥላሴ ስም እንዠምራለን ።

ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክና በስም መዠመሪያ
ኡምበርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ጦርነት ለማስቀረት

ዱሮ የነበረውን ፍቅራቸውን መልሶ ለማደስ ስለወደዱ ከዚህ ቀጥሎ
የሚጻፈውን ውል ተዋዋሉ ። ይህንንም ውል ለመዋዋል ከኢጣልያ
ንጉሥ ሙሉ ሥልጣን የተቀበለ በሳንሞሪስዎ በሳንላዛር በኢጣልያም
ዘውድ ኒሻን የተሸለመ ማጆር ዶክተር ሲዛር ኔራሲኒን መርጠው
ላኩ ። የማጆር ኔራሲኒ ሥልጣን የተካከለ መልካም መሆኑ ስለታየ
የከበረ ማጆር ኔራሲኒ በኢጣልያ ንጉሥ ስምና ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒ
ልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ተቀምጠው ቀጥሉ የሚጻ
ፈውን ክፍል ሁሉ ተስማምተው ተዋዋሉ ።

## መዠመሪያ ክፍል

በኢትዮጵያና በኢጣልያ ማኸል የተደረገው ጦርነት ጭራሽ ቀርቷል ።
እንዲህ ስለሆነ በኢጣልያ ንጉሥና በጃንሆይ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት
በወራሾቻቸውም ለዘላለም እርቅና ፍቅር ይኖራል ።

## ሁለተኛ ክፍል

በ25 ሚያዝያ በ1881 በውጫሌ ሰፈር የተደረገ ውልና በኋላ ታርሞ
የተጨመረውም ውል ሁሉ ጨርሶ ተፍቋል ። እንደ ተፋቀም ጭራሽ
ይቀራል ።

## ሦስተኛ ክፍል

የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን ነጻነት ራሱን የቻለ ባለ ነጻ መንግ
ሥት መሆኑን ጨርሶ ተቀብሎአል ።

## አራተኛ ክፍል

እነዚህ ሁለቱ በዚህ ውል የሚዋዋሉ ነገሥታት ባገሩ ድምበር ነገር ሳይስማሙ ቢቀሩ በእርቁ ቶሎ ለመዋዋልና ለሁለቱም አገር የዕረፍት መልካም እርቅ ለማድረግ ስለወደዱ፥ እስከ ዓመት ድረስ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣልያ ንጉሥ የመረጡዋቸው ሽማግሎች በፍቅር ተስማምተው የወሰኑን ነገር እንዲጨርሱ ተዋውለዋል ። ወሰኑ እስኪወሰን ድረስ ግን፥ ሁለቱ ተዋዶው ዛሬ ባሉበት በመቆያው ወሰን በመረብና በበለሳ በሙና ወንዞች ሳይተላለፉ እረግተው ይቆያሉ ።

## አምስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግሥት ተስማምተው እስኪጨርሱ ድረስ የኢጣልያ መንግሥት ከዚህ አገር ለማንም ማን መንግሥት መስጠትና መልቀቅ አይቻለውም ። ዛሬም የኢጣልያ መንግሥት በጁ ከያዘው አገር መልቀቅ ያማረውም እንደሆነ ለኢትዮጵያ መንግሥት ይመልሳል ።

## ስድስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢጣልያ መንግሥት የጥበብና የንግድ ሥራ ለመርዳት ቢፈልጉ ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው ውሉን ኋላ ማድረግ ይመቻቸዋል ።

## ሰባተኛ ክፍል

ይህ አሁን የተደረገው ውል እነዚህ ሁለቱ የተዋዋሉ ነገሥታት በጥንቃቄ ለሌሎቹ ነገሥታት ያስታውቃሉ ።

## ስምንተኛ ክፍል

ይህም አሁን ያደረግነው ውል ከዛሬ እንሥቶ ለ3 ወር ድረስ በኢጣልያ መንግሥት ፈጽሞ ይታተማል ።

## ዘጠነኛ ክፍል

ይህ ዛሬ የተደረገው የዕርቅ ውል ተካክሎ ባማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ ከሁለት ላይ ይጻፋል ። ታትሞም ሲያበቃ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና በኢጣልያ ቤተ መንግሥት ይቀመጣል ።

በዚህ ተስማምተው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ራስዎና የከበረ ማጆር ኔራሲኒ በኢጣሊያ ንጉሥ ስም ተቀብለው በየማኅተማቸው ይህን ውል አተሙ ።

በጥቅምት በ17 ቀን ተጻፈ ባዲስ አበባ ከተማ በ1889 ዓመተ ምሕረት ።



# ምዕራፍ ስድሳ

### የምርኮኞቹ አኗኗር — ስለነርሱ የተደረገው ስምምነት ስለወጣው የኪሣራ ገንዘብና የምርኮኞቹ አገራቸው መግባት

ስለ ምርኮኞቹ በተለይ የተደረገውን ውል ከማንበባችን በፊት፥ ወደ ኋላ መለስ ብለን ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ ባደረጉት ጉዞ ከነጻነታቸው በፊት በኢትዮጵያ ተበታትነው በየመኳንንቱ ቤት በምሪት በነበሩበት ሰዓት የሆነውን መመልከት ታሪኩን የበለጠ የሚያሟላው ይመስላል ።

በዓድዋ ጦርነት ወደ መገባደጃው ላይ የመድፍ፥ የመትረየስና የጠመንጃ ድምፅ ጋብ ሲል እግረኛም፥ ፈረሰኛም ጣልያኖችን እያራወጠ ሲከብ፥ ሲያባርርና ሲማርክ የሆነውን አስደናቂ ትርዒት ለዛሬ ታሪክ አንባቢ እንደ ብርቅ ስሌዳ ሆኖ በመገረም ዐይንና ሕሊና ሊታይ ይችል የነበረውን አስገራሚ ሁኔታ የኛዎቹ አሸናፊዎች በዝርዝር በጽሑፍ ሊያወርሱን አልቻሉም ። በልዩ ልዩ ሞያና በሥነ ጽሑፍ፥ በአስተዳደር ዘዴ የሠለጠኑት፥ በልማት የበለጠጉት፥ በዚህ ቀን ሳያስቡትና ሳይጠብቁት የመሸነፍ አደጋ የደረሰባቸው ወገኖች ግን ሁኔታውን በማስታወሻ መዝግበውት ይገኛል ።

ከነዚህም ውስጥ ማዦር ጂዮቫኒ ጋሜራ፥ ቴኔንቲ ዠራልዶ ፖንታኖ (በኋላ ዤኔራል)፥ ሐኪም ኒኮላ ዳማቶ፥ ሴርጂንቲ ጂዮቫኒ ቲዶኔ፥ ፍራንቼስኮ ፍሪዚና ሉዊጂ ጉይ ስድስቱ ከምርኮኞቹ ውስጥ የነበሩት የተዉት ማስታወሻ በመጨረሻ ጊዜ ለተነሡት ታሪክ ጸሐፊዎች ለነሉካ ዴይሳቤሊ፥ ለነኮንቲ ሮሲኒ ለነአንጀሎ ዴልቦካ ጠቅሟል ። ማዦር ጋሜራን የማረከው አንድ የባሻነት ማዕረግ ያለው የራስ መኰንን ጭፍራ እንደ ነበረና ከማረከው ዠምሮ ባሻው በጎ ነገር እንዳደረገለት፥ ከዚያም የራስ መኰንን ልጅ ይልማ (በኋላ ደጃዝማች) የሱፍ ብርድ ልብስ ሲሰጡት ፥ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደ ኮረጆ ያለ ዕቃ መያዣ እንደ መጸወቱት፥ አፈ ንጉሥ ነሲቡ እጅ የወደቀው የመቶ አለቃ ፖንታኖ የበለጠ ዕድለኛ በመሆን ከተማረከበት ሰዓት እንሥቶ አፈ ንጉሡ እንደ ልጃቸው እንዳንከባከቡት፥ "ሁለት ጠላቶች እያንዳንዳቸው ግዳጃቸውን ከፈጸሙ በኋላ ሊወዳጁ መቻላቸውን" ጠቅሰው፥ "እንግዲህ ይኸኛውን ልጄን (ደጃች ደምስ በኋላ ራስ)

ባለቤቴ ሰጥታኛለች ። የአንተን ልጅነት ደግሞ አምላክ ሰጥቶኛልና
የሚያስፈልግህን ጠይቀኝ” ብለውት ፣ በዚያ አስቸጋሪ በሆነው
ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ በተደረገው ጉዞ ላይ የሚተኛበት የበሬ
ቁርበት ፣ እንድ ጋቢ እጀ ጠባብና ኩታ እንደሰጡት ፤ ለጄኔራል አል
ቤርቶኒ የሚጓዝበት ፈረስ ፣ የሚያድርበት የተለየ ድንኳንና አገልጋ
ዮችም ተሰጥቶት እንደነበር ፤ ሁሉም ለተሰጠው ምርኮኛ መንከባከብ
እንዲያደርግ ከንጉሠ ነገሥቱ መመሪያ ትእዛዝ ተሰጥቶ እንደ ነበረ
ያወሳል ።[1]

እነዚሁ ምርኮኞች በተዉት ማስታወሻ ላይ ፣ ጉዞው ሁለት ወር
(ሚያዝያና ግንቦት) እንደፈጀ ፣ በመንገድ ላበሾቹም ለምርኮኞቹም
ስንቅ አልቆ በየመንገዱ ሰው ይሞት እንደነበረ ፣ ከኢጣልያኖቹም
ውስጥ ከዐርባ እስከ ሠላሳ የሚሆኑ ቁስለኞች በመንገድ ሞተው
እንደ ተቀበሩ ፣ የጉዞውና የረኃቡ ችግር ሁሉንም ስለ ጠመደው ፣ አሽና
ፊዎቹ ለራሳቸው አድልተው በምንም ዓይነት ምርኮኛውን እንዳ
ልበደሉ ፣ ሁሉም በጉዞው ላይ በመልካም ዐይን እየተያየ አልፎ አልፎ
እውሬ እየታደነ ይበላ እንደነበረ ፣ አንዳንድ ምስኪን ባላገሮችም
“ውሀ ፣ ዕንቁላልና ዶሮ ለነዚህ ፈረንጆች እንስጣቸው” እያሉ ይሽ
ቀዳደሙ እንደነበሩ ፤ ከሁሉ የበለጠ ደግሞ በጉዞ ላይ እንጀራና ዳቦ
እንዲታደላቸው በማድረጋቸው የእቴጌ ጣይቱን ቸርነት በማስታወ
የጉዞውን ሁኔታ ፍሪዚና ፍራንቼስኮ የሚባለው ተጓዥ ምርኮኛ ባይ
ያየውን እንደዚሁ ሲል ገልጾታል ።

> ...የግንባር ቀደሙ ጦር በፊታውራሪዎቹ ይመራል ። ከግንባር
> ቀደሙ ጦር ኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በብር ዕቃ ባጌጠች ጥሩ በቅሎ ላይ
> ተቀምጠው በታላላቅ አለቆች ፣ በፈረሰኞችና በግል ዘበኞቻቸው
> ታጅበው ይጓዛሉ ። እንደ ዘወትሩ የሐር ካባ ደርበው የራስ ማሰሪያ
> (ሻሽ) አስረው ፣ በዚያ ላይ ሰፊና ዝርግ ጥቁር ባርኔጣ አድርገው
> የፀሐዩ ጮራ እንዳያስቸግራቸው በፈረስ ያሉ ሰፋፊ ጃንጥላ ይዘው
> ይከልሏቸዋል ። ከርሳቸው ኋላ ጣይቱ ሁለመናቸውንና ፊታቸውን
> በሐር ጨርቅ ተሸፍነው ሲጓዙ ....

ከርሳቸው ኋላ ደግሞ ብዙ ራሶች በየግል ጭፍሮቻቸው ታጅበ
እንደሚጓዙ ፣ ከነርሱም ጋር ካህናትና የበታች ሹማምንት ግ
በፈረስ በበቅሎ በግመልም የሆነው የበረከተ መሆኑን ፣ የጭ
አጋሠሥና የአህያውን ብዛት በጠቀሰበት ላይ ሁለት የጭነት
ኖች እንደ ነበሩና እንደዚህ ሆኖ ይጓዝ የነበረው ሁሉም ቅልጥ
እንደነበረው ያወሳል ።

1 Venti Anni di Vita Africana, Gen. Pantano, PP. 74 - 81; Gli Italiani in Africa
PP. 719 -722.



በዚህ ዐይነት ምርኮኞቹ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ፣ በየመኳንንቱ
ቤት ተመርተው አብዛኞቹ በነዚያው ከዓድዋ ዠምሮ ባመጧቸው
መኳንንት እጅ እንዲቆዩ ሲደረግ ፣ ዋናው ጄኔራል አልቤርቶኒ በአዛዥ
ዛማኤል (ዘአማኑኤል) እጅ ተመርቶ ደንበኛ የምርኮኝነት እንክብ
ካቤ አልጎደለበትም ። የቀሩትም ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው መመ
ሪያ መሠረት በተቻለ መጠን የበሬና የበግ ሥጋም ዶሮና እንቁላል
እንደዳረጐት እየተሰጣቸው ፣ ግማሾቹም ራሳቸው እየሠሩ ሲቀለቡ
ከርመዋል ። በዚህ መካከልም አንዳንዶቹ ቅሚያና ሴት ጉተታ እያ
በዙ ፣ ከጠባቂዎቻቸው ጋር ጠብ እያበቀሉ ያስቸገሩም አሉ ።

ከላይ የተጠቀሰው ፍሪዜና ፍራንቼስኮ የሚባለው የሃምሳ አለቃ
ጠባቂውን ደብድቦ በዚሁ ተይዞ ራስ ዳርጌ ላይ በቀረበበት ሰዓት ፣

> ...እግዚአብሔር ዓድዋ ላይ ቀጣችሁ ። አሁን እስረኞች ሆና
> ችሁ ሳለ እናንተ አረመኔ እያላችሁ ትሰድቧቸው የነበሩት ንጉሠ
> ነገሥት ራርተው በመልካም ብትያዙ እናንተ አበዛችሁት ።...
> ጠባቂዎቻችሁን እየተሳደባችሁ ትማቱ ዠመር...?

ሲሉ ያቀረቡለትን ተግሣጽ ጓደኛው ሉዊጂ ጉይ የተወውን
ማስታወሻ ዴልቦካ አብራርቶ ጽፎታል ።[1]

እንደዚህ ሆነው ከቆዩ በኋላ ፣ ለምርኮኞቹ ከኢጣልያ አገር እነ
ርሱን ለመርዳት በተቋቋመው ኮሚቴ አማካይነት በማገር ኔራሲኒ
እጅ ጥሬ የማሪያ ቴሬዛ ብርና ልዩ ልዩ ልብስ ከታደላቸው ወዲህ ፣
ልብሳቸውንና ጫማቸውን በመለዋወጥ እያማረባቸው ሔደ ። በመጨ
ረሻም ስለ ሁለቱ መንግሥታት የወደፊት ወዳጅነትና ግንኙነት በጥ
ቅምት 17 ቀን 1889 ዓ.ም. ደንበኛ ውል እንደ ተደረገ በዚሁ ቀን
ምርኮኞቹን በሚመለከተው ጉዳይ ከዚህ እንደሚከተለው ተዋዋሉ ።
የውሉ አርእስቱና መቅድሙ እንደ ፊተኛው ሲዠምር አንቀጾቹ በት
ከከል እንደዚህ የሚሉ ናቸው ።

## መዠመሪያ ክፍል

> በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥት ማኸል ዛሬ ስለ ተደረገው
> የዕርቅ ውል በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ያሉ የኢጣልያ ወታደሮች ምር
> ኮኞች ተሰቀዋል ። ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እኒህን ምርኮ
> ኞች በማፍጠን (በፍጥነት) ሰብስበው ሲያበቁ ይህ የዕርቅ ውል ተጠን
> ቅቆ* ታትሞ ሲመጣላቸው ሐረርጌ ላይ ከኢጣልያ መንግሥት ሙሉ
> ሥልጣን ተቀብሎ ለመጣው ሰው ያስረክባሉ ።

1 Gli Italiani in Africa ... PP. 726 - 728.
* ጸድቆ ከኢጣልያ አገር ሲመለስ

## ሁለተኛ ክፍል

እነዚህ የጦር ምርኮኞች ወዳገራቸው ሲመለሱ እንዳይቸገሩ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢጣልያ የቀይ መስቀል ማኅበር ጂልዴሳ* ድረስ መጥተው እንዲቀበሏቸው ይፈቅዱላቸዋል ።

## ሦስተኛ ክፍል

የኢጣልያ ንጉሥ መልክተኛ እኒህ ምርኮኞች ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በብርቱ አቀማምጠው ማስቀመጣቸውን እሱ ራሱ ስላየ እንዲህም አድርጎ አቀማምጦ ለማስቀመጥ ብዙ ገንዘብ እንደ ፈጁ ስለዐወቀ ፣ ይኸነን ስለኒህ ያወጡትን ገንዘብ የኢጣልያ መንግሥት እንዲከፍል ባለዳ መሆኑን ተቀብሏል ። ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግን ፣ የገንዘቡን ኪሣራ ነገር የኢጣልያ መንግሥት እንዳወቀ ፈርዶ ሊሰጣቸው (እንዲሰጣቸው) ፍርዱን በኢጣልያ መንግሥት ላይ ጥለውታል ።

በዚህ ውል ተስማምተው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ራስዎና የከበረ ማዦር ኔራሲኒ በኢጣልያ ንጉሥ ስም ተቀባብለው በየማኅተማቸው ይህን ውል አተሙ ። በጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ. ም. ተጻፈ ።

ከዚህ ውል ዝምሮ እስረኞቹ ሙሉ ነጻነት አግኝተው ከአዲ
አበባ ውጭም ፣ በአዲስ አበባም ያሉት አዲስ አበባ ላይ ተሰብ
በው ወደ ሐረር የጉዞው ነገር በትጋት ተያዘ ። ስለ ኪሣራው አቀ
በልም በሁለቱ መንግሥታት ወኪሎች መካከል ንግግር ሲደረግበ
በሰነበተበት ሰዓት ፣ ከኢትዮጵያውያኑ ወገን ከሠላሳ እስከ ዐርባ ሚሊ
ዮን ሊሬ ሲጠየቅ ፣ ምኒልክ ዐሥራ ሁለት ሚሊዮን እንዲሆን ግ
ባቸውን ፣ "ይኸማ ከዚያው ከጦር ካሳ የበለጠ ሆነ" የሚል ከ
ራሲኒ በኩል ክርክር ቀርቦ በአራት ሚሊዮን ላይ እንዲመደብ ተ
ራከረ ። በመጨረሻ ሁለቱም ወገኖች ዐሥር ሚዮን ሊሬ እንዲሆ
ተስማምተው ይኸም ያለወለድ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እ
ዲከፈል ተስማሙ ።[1] በዚያን ዘመን ምንዛሪ አንዱ የማሪያ ቴሬ
ብር አራት ሊሬ ስለሆነ ፣ ከፍያው በማሪያ ቴሬዛ ብር ሲታሰብ ወ
ሁለት ሚሊዮን ተኩል ይሆናል ማለት ነው ።

በተረፈ ማዦር ኔራሲኒ ከዚህ በላይ የተደረገውን የሰላምና የ
ዳጅነት ውል ካደረገ ወዲህ ፣ እላይ እንዳልነው እስረኞቹ ተከፋፍለ

* ጊልዴሳ ወይም ጂልዴሳ በድሬዳዋና በዘይላ መካከል የሚገኝ ፈሳሽ ወንዝ የሚ
ኝበት ትንሽ ከተማ ነው ።

1 Gli Italiani in Africa Orientale, PP. 731 - 732 ; Storia Diplomatica . . .
. . . C. Rossetti, Chap. VII. PP. 181—206



ከየተላኩበት እንዲሰበሰቡና ሐረር ላይ እንዲጠራቀሙ ተደረገ ። ከነዚሁ ውስጥ አራት የሚሆኑት የኢጣልያ ምርኮኞች ከጄኔራል አልቤርቶኒ ጋር አዲስ አበባ ነበሩ ።

ማዦር ኔራሲኒ ከዘይላ ወደ ሐረር ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ጊዜ ፣ ከኢጣልያ አገር ለምርኮኞቹ አስፈላጊያቸውን ነገር መግዣ ከኢጣልያ መንግሥት ዘንድ ዐርባ ሺ የማሪያ ቴሬዛ ብር እንደዚሁም የሮማ እመቤቶች እያዋጡ የላኩት ልዩ ልዩ ጥቅል ዕቃ መጥቶ በየጊዜው ለምርኮኞቹ ታደለ ። ከዚያ የውሉ ቃል በኢጣልያ መንግሥት ከጸና በኋላ ፣ ቁጥራቸው አንድ ሺ ስድስት መቶ የሚሆኑት የኢጣልያ ምርኮኞች ከኢጣልያ አገርና ከምጥዋ ሊቀበሏቸው በመጡት በቀይ መስቀል ሠራተኞችና በሌሎችም ትጋት በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖችም አጋዥነት ከአዲስ አበባ ሐረር ፣ ከዚያም በጀልዴሳ በኩል አድርገው ወደ ዘይላ ፣ ከዘይላ ወደ ኢጣልያ አገር በሰላም ተጓዙ ።

ከአዲስ አበባ በተነሡ ጊዜ ፣ ለኢጣልያኖቹ በሙሉ ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት የመሰናበቻ ታላቅ ግብር ተደርጎ ግብሩ እንዳለቀ በምርኮኞቹ ስም ጄኔራል አልቤርቶኒ የምስጋና ዲስኩር አድርጎ ሲጨርስ ኢጣልያኖቹ ተነሥተው ፣ "ምኒልክ ሕያው ይሁን!" ብለው ደጋግመው እየጮሁ አመሰገኑ ።

የዓድዋ ዕለት በቀኝ በኩል አዝማች ሆኖ ሲዋጋ የሞተው የጄኔራል አሪሞንዲ ሻምላ ተማርኮ የነበረውንም "ለዘመዶቹ ለመታሰቢያ እንዲሆናቸው ስጦታ" ብለው ንጉሠ ነገሥቱ ለጄኔራል አልቤርቶኒ አስረከቡት ። ጠላቶች የነበሩት የኢጣልያን ምርኮኞች በዚህ ዓይነት ደስታ ፣ እርቅና ሰላም ወዳገራቸው ተመለሱ ።

በዓድዋ ጦርነት የተማረኩትን ቁጥራቸውን የሚያበዛውና የሚቀንሰው አለ ። ያበዛው እስከ ሁለት ሺ ፣ ያሳነሰው እስከ አንድ ሺ አምስት መቶ ያደርሰዋል ። ነገር ግን ፣ በጣም የቆሰሉና የማይሔዱ ምርኮኞች በትግሬ በየመንደሩ ተመርተው ይታመሙ ከነበሩት ውስጥ ግማሾቹ የሞቱ ፣ ግማሾቹ በራስ መንገሻ ትእዛዝ ለጄኔራል ባልዲሠራ ተሰጥተው ወደ አሥመራ ተልከዋል ። አንዳንዶቹ በንጉሠ ነገሥቱ ጦር እየተጠበቁ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዙ በመንገድ የሞቱ እንዳሉ በሰፊው ተመልክቷል ። አዲስ አበባም ከደረሱ በኋላ በየአውራጃው ለየሹማምንቱ ተመርተው የሰላሙ ውል እስኪፈጸም ድረስ አንዳንድ ሕይወታቸው ያለፈ ይገኙባቸዋል ። ከዚህም በተጨማሪ ባለፈው የሐምሌ ወር ስምምነቱ

ከመፈረሙ በፊት የመስኮብ ንጉሥ ኒኮላ የነገሡበትን ዕለት ባከበሩበት ጊዜ ስለርሳቸው ክብር ሃምሳ ምርኮኞች ተለቀው በጅቡቲ በኩል ወደ አገራቸው እንዲገቡ ተደርገዋል ።[1]

ስለዚህ ፣ ኤሚሊዮ ቤላቪታ የሚለው ትክክል እንደሆነ የሰላሙ ውል ከተፈረመ በኋላ ወደ አገራቸው የተመለሱት አንድ ሺ አንድ መቶ ዐርባ አምስት ፣ ከነዚሁ ውስጥ ሃምሳ ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ፣ ሃምሳ አንድ ዝቅተኛ መኰንኖች የሚገኙበት ከአዲስ አበባ የተለቀቁ ሲሆኑ ፣ መቶ ሃምሳ ሐረር በራስ መኰንን እጅ የነበሩ ተጨምረው ነው ።[2]

እነዚህ ሁሉ ከኢጣልያ አገር በመጣው የቀይ መስቀል ድርጅት እየተረዱ ከዘይላ ወደብ ተሳፍረው በሚያዝያና በግንቦት ወር 1889 ዓ.ም. ላይ አገራቸው ገቡ ። አንዳንዶቹ ሹማምንት ወዳገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ከጠባቂዎቻቸው የኢትዮጵያ መኳንንት ጋር በፍቅር ፣ በደስታ ተሰነባብተው ሲሔዱም ከየጠባቂዎቻቸው ለቤተሰቦቻቸው ደብዳቤ ይዘው የሔዱ ይገኙባቸዋል ። ከዚህ በፊት ስሙን ያነሣነው ፓንታኖ የሚባለው የመቶ አለቃ ምርኮኛ ዓድዋ ላይ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ለአፈ ንጉሥ ነሲቡ ተሰጥቶ ይዘውት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሳለ ፣ ወዳገሩ ሲመለስ ለእናቱ እንዲያደርስ የሰጡት ደብዳቤ እንደዚህ ይላል ።

> . . . ልጅሽ ተማርኮ በእኔ እጅ ቆይቶ ነበር. . . በዚያ በተማረከበት ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ለኔ አደራ ብለው ሰጡኝ ። እኔም ጃኖ ኩታ አልብሸ በፈረስ አስቀምጨ ወዳገሬ (አዲስ አበባ) አመጣሁት ። እኔም አንድ ቀንም ሳላስርበው ዓመቱን ጠጅ እያጠጣሁ ትኩስ ሥጋ እያበላሁ አኖርሁት ። አሁን ግን ፣ የእግዚአብሔር ምሕረት ወርዶ ባንቺም የፍቅር ጸሎት ይኸው ልጅሽን ልኬልሻለሁ ። መድረስ አለመድረሱን እግዚአብሔር ያውቃል ። ወዳንቺ በደህና መድረሱን አረጋግጭልኝ ። ይኸን ሁሉ ለልጅሽ ማድረጌ እኔም ልጆች ስለ አሉኝ ነው ።

ባለቤታቸው ወይዘሮ ደስታም በበኩላቸው ፤ "ባንቺ ውቃቢ በእግዚአብሔር ምሕረት ልጅሽ ከሞት ተርፎ መጥቶ በዐይነ ሥጋ ልትገናኙ ነው ። መድረሱንና ካንቺ መገናኘቱን ጻፊልኝ ። የሚል ጽፈዋል "[3] ። በዚህ ዐይነት ምርኮኞቹ በተለይ ሹማምንቱ በመልካም ተይዘው እንደነበር ለመረዳት አያዳግትም ።

1 Storia Diplomatica . . .P. 19
2 Adua . . , PP. 445 - 446.
3 Meoelik II, L' Etiopia eled Relazioni Con Italia, Falcooe, P. 132





አፈ ንጉሥ ነሲቡ
ከሞሪስ ደኮፒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ስድሳ አንድ

## ከዓድዋ በኋላ የኢትዮጵያ ነጻ መንግሥትነት በይፋ መደላደል — የኃያላን መንግሥታት እንደራሴዎች ወደ አዲስ አበባ መምጣት—ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት

ከብዙ ጊዜ ክርክርና ከብዙ ደም መፋሰስ በኋላ ጥቅምት 17
ቀን 1889 ዓ.ም በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገው የሰ
ላም ውል በውስጡ የተዘረዘሩት አንቀጾች ግልጽ ስለሆኑ ፣ ስለነርሱ
ሰፊ ሐተታ ማድረግ አያሻም ። ባንደኛው አንቀጽ የጄኔራል ባራቲ
ዬሪ ጦር በዓድዋ ከተሸነፈ በኋላ ፣ ጄኔራል ባልዲሠራ በርካታ ጦር
ይዞ ስለመጣ እንደገና ይዋጋና ሌላ ደም መፋሰስ ይቀጥል ይሆናል
ተብሎ ይጠረጠር የነበረው ተወግዶ ሰላም መተካቱ ተገልጿል ።
በሁለተኛው አንቀጽ ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም በተደረገው
የውጫሌ ውል መሠረት ኢጣልያ ፣ "በኢትዮጵያ ላይ የበላይነትና
የጠባቂነት መብት አለኝ" ብላ አጥብቃ የተከራከረችበት ውል
በፍጹም መሰረዙ ፣ በሦስተኛው አንቀጽ የኢትዮጵያን ፍጹም ነጻ
መንግሥት መሆኗን ማወቋ ተመልክቷል ።

ስለዚህ ከዐፄ ዮሐንስ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ አንገቦ
የነበረው የኢጣልያ የገዥነት ምኞት ለጊዜው ተዘጋ ። ለኢትዮጵያም
አንድ የድል አድራጊነትና በራስ የመተማመን መንፈስን የያዘ ከፍ
ያለ ታሪካዊ የክብር ገጽ በዓለም ታሪክ ፊት ተከፈተ ። ከ16ኛው
መቶ ዓመት ጀምሮ በተለይ ይህ 19ኛው መቶ ዓመት ለአውሮፓ
ውያን መንግሥታት የወራሪነት ፣ ለደቡብ አሜሪካ ፣ ለእስያና ለአ
ፍሪካ አህጉር የተወራሪነት ዘመን ነበረ ። በተለይ በአፍሪካ ሁሉም
ሲወረር ፣ ከመወረር የተረፈች አገር ኢትዮጵያ ስትሆን ቅኝ አገር ያል
ደረሳት አገር ኢጣልያ በመሆኗ ፣ የነዚህ የሁለቱ አገሮች ክርክርና ጦር
ነት በዚህ ዓይነት ሲፈጸም አብዛኛው የዚህ የውል ጥቅም ለኢትዮ
ጵያ ያመዝናል ማለት ይቻላል ። ይኸም ጥቅም የተገኘው ከዓድዋ
ድል ሲሆን ድሉም የተገኘው በዚሁ ጦርነት ሕይወታቸውን በደስታ

በሠዉት አባቶች ነው ። ይህ ድል አድራጊነት የንጉሡ ነገሥቱ ፣
የእቴጌይቱ ፣ የመሳፍንቱ ፣ የመኳንንቱና የሹማምንቱ ብቻ ሳይሆን
ማር ገባሩም ፣ እህል ጫኙም ፣ ገረዱም ፣ አሽከሩም ፣ በቅሎ ለጓሚ
ውም ፣ እንጨት ፈላጩም ፣ ውሀ ቀጅውም ሣር አጫጁም ሁሉም
ለዚህ ድል ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል ። ለዚህ ጦርነት ሕይወቱን
የሠዋው የሸዋ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ትግሬው ፣ ጐጃሜው ፣ ቤጌምድ
ሬውና ስሜነኛው ፣ ወሎዬው ወለጋው ፣ አሩሲው ፣ ሐረርጌው ፣ ጋሞው ፣
ሲዳሞው ፣ ከፋው ፣ ከምባታው ፣ ወላይታው ሐድያው ስለ ተካፈለ ፣
የዚህ ድል አድራጊነት ክብሩም ኩራቱም የጋራ የኢትዮጵያውያን
ሁሉ ነው ።

በዚያን ጊዜ በነበረው የዓለም ሁኔታ በአውሮፓ ፊት አፍሪካ
ለተገዥነት የወደቀ ሲሆን ፣ በነጭ ዘንድም ጥቁር የተናቀና ነጭን ለማ
ገልገል በባሕርዩ የተመደበ ፣ ራሱን የማይችል ፣ ነጻነት የማይገ
ባው ሆኖ ይታመን ነበር ። የዚህን እምነት እንኳን ጠላቶቻች
ንና ከጠላቶቻችን ወገን የሆኑት እንግሊዞች ቀርተው ለኢትዮጵያ ያግ
ዛሉ የሚባሉት ፈረንሳዮች እንኳን ይነስ ይብዛ ያምናሉ ። ስለዚህ
የአፍሪካ አህጉር ባለቤት እንደሌላት ፈረንሳይ ፣ እንግሊዝ ፣ ጀርመን ፣
ኢጣልያ ፣ እስፓኝ ፣ ፖርቱጋል ፣ ቢልዥከና ሌሎች ሰባት አገሮች እ.ኤ.አ
በ1884—1885 ዓ.ም በበርሊን ስብሰባ አድርገው አፍሪካን ለመከ
ፋፈል የሚያስችላቸውን የያዙትን አገር የሚያጠብቁበት ውሳኔ
እንዳሳለፉ የሚታወስ ነው ።

በ19ነኛው መቶ ዓመት ፣ ዓለም በዚሁ የገዥነትና የተገዥ
ነት መካከል እያለ በአፍሪካ ኢትዮጵያውያን የአውሮፓን ኢጣል
ያኖች በጦርነት አሸንፈው መለሱዋቸው ። ግማሾቹን ማርከው በውል
ለቀቁዋቸው ። ያገራቸውን ነጻ መንግሥትነት አደላድለው ያዙ ሲባል ፣
በገዥው በአውሮፓና በሚገዛው በእስያና በአፍሪካ ሕዝብ ዘንድ የድሉ
ዜና እንደ ብርቅና ድንቅ ሆኖ ነው የተገመተው ። ከዚህ በፊት እን
ዳልነው ፣ ቅኝ አገር ያላቸው መንግሥታት የሌላቸውም ቢሆኑ የነጭን
ውርደትና ጥቃት ከልብ ባለመቀበል የዓድዋ የድል ወሬ ለአብዛኞቹ
መራራ ወሬ ሳይሆን አልቀረም ። መራራም ባይሆን ቅርታን መፍጠሩ
የማይጠረጠር ነው ። ከነጮች ውስጥ ባለፈው ጊዜ ደጋግመን እንዳመ
ለከትነው ፣ መስኮብ በሃይማኖት አንድነት ፣ ፈረንሳይም ከእንግሊዝና
ከኢጣልያ ጋር ባላት የፖለቲካና የጥቅም ግጭት የተነሣ ፣ ለኢትዮጵያ
ማገዛቸውን እናስታውሳለን ። ይሁን እንጂ ፣ የዓድዋ ድል የተከና



ወነው በመሠረቱ በወዳጅ አገሮች እርዳታ ሳይሆን ፣ የአሚሚታቸውን
ዓይነት ባየነው በነዚያ ባባቶቻችን ደምና መሥዋዕትነት ነው ። በዚያ
ቅኝ አገዛዝ በሰፈነበት ዘመን አባቶቻችን የማይናቁና ነጮችን ለማገ
ልገል በፍጹም ያልተፈጠሩ መሆናቸውን ከጥንት ታሪክ ተያይዞ
በመጣው መሠረት ነጻነትና እኩልነት የሚገባቸው መሆኑን በጽሕፈ
ትና በንግግር ሳይሆን በደማቸው አስመሰከሩ ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከጃፓን ፣ ከቻይና ፣ ከታይላንድ በቀር
የቀረው የእስያና የአፍሪካ ግዛት ነጻነቱን ተገፎ በእንግሊዞችና በፈ
ረንሳዮች ፣ በቱርኮችና በሌሎችም ተከፋፍሎ ሲገዛ ኢትዮጵያ ነጻ
አገር ነበረች ። በኢትዮጵያ ላይ ቀደም ብሎ ከመሳፍንት ዘመን
ወዲህ ምንም እንኳን እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ቆንሲል አልፎ
አልፎ መላካቸው ባይቀር ፣ አንድ ጊዜ ቱርኮች ወይም ግብጾች
አለዚያም እንግሊዝ ከዛሬ ነገ ግዛታቸው ያደርጉታል እየተባለ
ማመንታት ስለነበረ ፣ አንድም መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ደንበኛ
የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለማድረግና ነዋሪ ሚኒስትር ወይም አም
ባሳደር ልኮ ለማስቀመጥ ያቀደ አልነበረም ።

ግብጾችን ዐፄ ዮሐንስ ድል አድርገው ከመለሷቸው ወዲህ ፣ ኢጣ
ልያኖች በቱርኮችና በግብጾች እግር ተተክተው ከፍ ባለ ድርጅት
ኢትዮጵያን በሙሉ ለመያዝ ከግብጾች የበለጠ ምኞትና ተግባር አሳይ
ተዋል ። የነርሱንም በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት እቅድ ሁኔታ ኋያ
ላኑ የእንግሊዝና የጀርመን መንግሥታት መደገፋቸው ይታወቃል ።
ሌሎች መንግሥታት በዝምታ በሩቁ ሁኔታውን ከመመልከት በቀር
ደንበኛ የዲፕሎማቲክና የወዳጅነት ግንኙነት ለማድረግ እምብ
ዛም የጣረ መንግሥት አልነበረም ።

በዚህም ላይ ኢትዮጵያ ከአክሱም ዘመን ጀምሮ ቀዋሚ ታሪክ
ያላት አገር መሆኗን አውሮፓውያን ቢያውቁም ፣ ባሁኑ በ19ነኛው
ዘመን ተደራጅቶ በኃይል የተነሣባትን የሠለጠነ አውሮፓዊ መን
ግሥት በሥልጣኔ ኋላ ቀርነት የታወቀችው ኢትዮጵያ በኃይል ተዋ
ግታ ትመልሰዋለች የሚል እምነት አልነበራቸውም ። ባለፉት ምዕ
ራፎች በዝርዝር እንደ ተመለከትነው ፣ ኢጣልያኖች ሕዝቡንና ባላባ
ቱን ከማዕከላዊው መንግሥት ለመለያየት የሚያደርጉትን ጥረት በጋ
ዜጣ በመስማት በኢትዮጵያ ውስጣዊ አንድነት ላይ የማይጠራጠር
አልነበረም ። ቢሆንም ሁለቱ ጠላቶች በአላጌና በመቀሌ ከተቆራ
ቆሱ ጀምሮ ለዋንኛው ለዓድዋ ጦርነት መሰለፋቸውን የሚያውቁ

መንግሥታት ሁሉ ነገሩ ይለያል በማለት በሩቅ ሲመለከቱ ቆይተው ሳይታሰብ የኢጣልያ ጦር የመሸነፉ ወሬ ሲሰማ ሁሉም በመደነቅ ባሕር ተዋጡ ። ከዚያም ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ የኢጣልያ መንግሥት ድሉን በመበቀል ፋንታ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴውን ልኮ በውጫሌ ውል ላይ የነበረውን የጠባቂነት ምኞቱን ሁሉ ሰርዞ ፣ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ዐውቆ የሰላም ውል ተዋውሏል ። የዚህ ውል ግልባጭ በደንብ የደረሳቸው መንግሥታትና ሌሎችም ወሬውን ከጋዜጣ የተረዱት ሁሉ ፣ የኢትዮጵያን የተረጋገጠ መንግሥትነት በውድም በግድም ወደ ማወቅ ደረሱ ። አጠራጣሪው ነገር ሁሉ ከየተመልካቹ ልብ ተወገደና ከብዙ ዘመን ጀምሮ የኖረው የኢትዮጵያ መንግሥት አሁንም ነጻነቱን እንደያዘ በደንብና በድርጅት የሚራመድ መሆኑን ተገነዘቡ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ሁሉም ወደዚሁ አገር መላከተኛ ለመላክ ይሽቀዳደም ጀመር ። ልዑል ሐንሪ የሚባል የኦርሊያንስ (ፈረንሳዊ) መስፍን ስለ ኢትዮጵያ ጉብኝቱ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ፣

> . . . ያለፈው ዓመት የሐበሻን ዘር የተዋጊነቱን የዠግንነቱን የኃይሉን ምስክርነት በሚያንጸባርቅ መንገድ ገልጾልናል ። በመጋቢት 1 ቀን 1896 (የካቲት 23 1888 ዓ. ም.) ከዚህ በፊት በቅኝ አገር ታሪክ ውስጥ ተደርጎ የማይታወቅ አድራጎት መፈጸሙን አየን ። አንድ የነጭ ጦር በገሃድ በተደረገ የሰልፍ ጦርነት በጥቁር ጦር ተመትቶ ፈረሰ ። ይኸም የነጭ ኃያል መንግሥት በአንድ ውል ላይ የነበረውን አንቀጽ ባጉል ተርጕሞ ለመውረር መብቱን ራሱ በወሰደበት ምክንያት ነው ። 1

ብሏል ። ሌላው ጸሐፊ ደግሞ ፤

> ከ2ሺ ዓመት በፊት ሐኒባል በሮማውያን ካገኘው ድል ወዲህ በዓለም ያንጸባረቀው የዓድዋ ድል አፍሪካ በአውሮፓ ላይ እንዳገኘው ታላቅ ድል ይቆጠራል ።" 2

ሲል በአድናቆት ጽፏል ።

ስለዚህ ፣ በኛ በኢትዮጵያውያንና በአፍሪካውያን ብርዕና አንደበት ብቻ ሳይሆን የተገኘው ድል ፣ የመላው አፍሪካ ድል መሆኑን በዘር ልዩነት የማያምኑት የአውሮፓ ጸሐፊዎች አምነውበታል ማለት ነው ። በዘር ልዩነት የሚያምኑትም ምንም የመብሸቅ ስሜት ባይሰያቸው የሚያንጸባርቀውን ሐቅ ማስተባበል አይሆንላቸውም ።

1) Une Visite a l' empereur Menilik . . .,P.3.
2) Ethiopie d' Hier et d' Aujourd' hui - Andre Davy , P.106.



በዚህ ምክንያት ፣ ከዓድዋ ድል በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ ጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ.ም ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ያደረጉትን የሰላም ውል ለወዳጆቻቸው ለፈረንሳይና ለመስኮብ እንደዚሁም ለእንግሊዝና ለሌሎቹም መንግሥታት በይፋ አስታወቁ ። እነዚሁ መንግሥታት የኢትዮጵያን መንግሥት ማወቃቸውን ለማረጋገጥ በማከታተል ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሮቻቸውን ከዚህ እንደሚከተለው እየላኩ የንግድና የወዳጅነት ውል መዋዋል ጀመሩ ።

ሀ. የፈረንሳይ መንግሥት ሙሴ ሌዎንስ ላጋርድን በመጋቢት ወር 1889 ዓ . ም ፣

ለ. የመስኮብ መንግሥት ሙሴ ፓ.መ..ቭላሶቭ በዚሁ ዓመት በጥር ወር ፣

ሐ. የእንግሊዝ መንግሥት ጀምስ ረኔል ሮድን በግንቦት ወር በዚሁ ዓመት ቀጥሎ ሌተና ኮሎኔል ጐርን ላን ሐሪንግተንን ፣

መ. የኢጣልያ መንግሥት መጀመሪያ ማዦር ኔራሲኒን ፣ ቀጥሎ ካፒቴን ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላን ላኩ ። የቀሩትም እንደ ጀርመን ፣ እንደ ቤልጅክ ያሉት መንግሥታት ይኸንኑ መስመር መከተል ግዴታቸው ሆነ ። 1

መልዕክተኞቹም ከየግል መንግሥታቸው የተላኩበትን የሹመት ደብዳቤ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው ሰፋፊ ቦታ እየተመሩ የየራሳቸውን የመኖሪያና የቢሮ ቤት እየሠሩ ሌጋሲዮናቸውን እያቋቋሙ ተቀመጡ ። በዚህ ጊዜ በአዲስ አበባ የሹመት ደብዳቤ ለማቅረብና ከኢትዮጵያ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ለማድረግ ከመጡት ውስጥ በወዳጅነት የሚታዩትና በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሞገስ አግኝተው መንከባከብ ያገኙት ፣ በጦርነቱ ሰዓት ኢትዮጵያን በመሣሪያም በአሳብም የረዱት የፈረንሳይና የመስኮብ መልክተኞች ናቸው ። በዚያን ሰዓት ሽር ጉድ የሚሉትም የነዚህ አገሮች ተወላጆች እነሊዎንቴቭ ፣ እነሞንዶን ቪዳዬ ነበሩ ። የእንግሊዝና የኢጣልያ መልክተኞች ባለፈው የጠበኛነት ሁኔታዎች ገርበብ ብለው ለመታየት ሁኔታው ያስገደዳቸው ይመስላል ።

ቢሆንም ፣ ከዕርቁ በኋላ እያንዳንዳቸው በይፋ ከመንግሥታቸው ተልከው ለመጡት የዲፕሎማቲክ አባሎች ለሁሉም ይነስ ይብዛ

1 1 Russi in Etiopia, PP. 240 -279.

እንደደንቡ የክብር አቀባበልና የመንከባከብ መስተንግዶ ተደርጎላቸዋል ። የዳግማዊ ምኒልክም መንግሥት ለሁሉም የእኩልነት መልክ ከማሳየት አልተቆጠበም ።

የአቀባበሉን መጠነኛ ሥዕል ፣ የእንግሊዙ ዋና መላክተኛ ከተከታዮቹ ጋር ወዳፄ ምኒልክ በቀረበበት ሰዓት እንዳጋጣሚ በዚያው የነበረው ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስነው የፈረንሳይ ተወላጅ ልዑል ሐንሪ የኦርሌያንስ መስፍን ከዚህ እንደሚከተለው ያቀርብልናል ።

...የእንግሊዝን መልእክተኞች ለመቀበል ሲዘጋጁ ንጉሠ ነገሥቱ በአዲስ አበባ የምንገኘውን አውሮፓውያን ሁሉ ባጠገባቸው እንድንሆን ጋበዙን ... ከቦንቫሎና ከወገኖቹ በቀር ለንጉሠ ነገሥቱ ክብር ስንል ሁላችንም ኒሻናችንን አድርገን ነበር ። ሊዎንቴቭ በኒሻን ተንቆጥቁጦ ኡኒፎርሙን ፣ ምንዶን ጥቁር ልብሱን ለብሰው ይታዩ ነበር ... ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም አድርገው ወደ ግል አትክልታቸው ውስጥ አስጠርተውን ነበር ። እዚያም ሆነን (ታላቁ ቤተ መንግሥት) በፊታችን ሜዳው ለጥ ብሎ ይታየን ነበርና በኮባ ጥላ ሥር ሆነን የእንግሊዞችን መላክተኞች ግራና ቀኝ ከፊትና ከኋላ ፈረሰኛና ወታደር አጅበዋቸው ፈረሰኞች ከፊት ፊት ሆነው ደንገላሳ እያስነሡ ፈንጠዝያ ሲያሳዩ ይታየን ነበር ... አጀቡ መጠጋት ሲጀምር ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ መቀበያው አዳራሽ ሲገቡ እኛም አብረን ገባን ። ያጌጠው አዳራሽ ሠላሳ ሜትር ቁመት ፣ ሐያ ሜትር የሚሆን ወርድ ነበረው ። ንጉሠ ነገሥቱ የወርቀ ዘቦ አጎበር ባለው ውስጥ በከፋይ ባጌጠው ዙፋን ላይ ተቀምጠው በጥሩ ከፋይ የተከፈፈ ካባ ለብሰው ራሳቸውን በብጫ ቀለም የሐር ሻሽ አስረው ይታዩ ነበር ። በጣታቸው ላይ ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዘንድ ሊዎንቴቭ ያመጣላቸው ትልቅ ያልማዝ ቀለበት ያበራ ነበር ። በአንገታቸውና በደረታቸው ላይ የመስኮብ ከፍተኛው ኒሻንና ከፈረንሳይ የሌዥዮን ዶነር ፕላክ ጋር ባንድነት ያንጸባርቅ ነበር ። ከዙፋኑ በስተቀኝ እኛን ወዳጆቻቸውን ፈረንሳዮችንና መስኮቦችን አስቀምጠውን በግራ በኩል ትንሽ ራቅ ብሎ አንድ ወታደር ዘውድ የደፋና መስቀል የጨበጠ የአንበሳ ሥዕል ያለበትን ባንዲራ ይዞ ቆሞ ነበረ ። የባንዲራው ወርቅማ ሥዕል ቅጠልማና ቀይ ቀለም ተባብሮበታል ። በርሱ አጠገብ የቤተ መንግሥቱ ታላቆች ተቀምጠው ነበር ። ... ብዙው ጥሩ ጥሩ የሐር ልብስ የለበሰ ነው ።

ያዳራሹ ዙሪያ በጦር ሠራዊት ተመልቷል ። የጠቅላላው ሠራዊት ትርዒቱ ፣ የለበሰው ሐር ቀለሙ የተለያየ ነው ። ግማሹ በመድፉ ዠርባ ቆሞ ግማሹ ከጉማሬ ቆዳ የተሠራውን ጋሻ አንግቦ ጠበንጃውን ይዞ ... በወርቅና በብር ያጌጠውን ልብስ በለበሱት መካከል የአራዊት ቆዳ የለበሱ ሲታዩ ዐይንን አይመታም ። ይኸውም ማለት በትከሻቸው የነብር ቆዳ የደረቡና ክንዳቸው ነጻ የሆኑት ግማሾቹ ያንበሳ ጐፈር የለበሱ ነበሩ ።

...ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዞቹ እስኪደርሱ ድረስ እንደልባችን እየተዘዋወርን ለመመልከትና ፎቶግራፍ ለማንሣት ፈቅደውልን ነበር ።



...ወደ አዳራሹ በሚወስደው መንገድ ላይ 60 መድፎች ከነዚሁ ከሦስቱ አንዱ እጅ ከኢጣልያኖች የተማረኩት ተጠምደው ያሉበትን ቦታ እያቋረጡ አልፈው እንግሊዞቹ ሲመጡ ታዩ ።

ዋናው መሪ ሮድ የዲፕሎማት ዩኒፎርሙን እንደ ለበሰ ከሌሎቹ ቀደም ብሎ በንጉሡ ፊት ሲደርስ እጅ ነሣ ። ምኒልከም እጃቸውን ዘርግተው ጨበጡት ። ከዚህ በኋላ ከኛው ፊት በተደረደረው ወንበር ላይ እንግሊዞቹ ተቀመጡ ። በሮድ ቀኝ ኰሎኔል ዊንጌት ከርሱ ተከታትለው አንድ ግብጻዊና የሕንድ የፈረሰኛ የጦር መኮንኖች ተቀመጡ ። በነርሱ ዠርባ 8 ረጃጅም ዠርጋዶች የሕንድ ወታደሮች ራሳቸውን በሻሽ ያሰሩ በነርሱም ፊት ለፊት ሊዎንቴቭ ያመጣቸው ሁለት የኮዛክ ወታደሮች ነበሩ ። ...ሮድ ፈረንሳይኛ ደህና አድርጎ ስለሚያውቅ በግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚነት ስለጉዞው ...ንግግር ከተለዋወጡ በኋላ ፣ ሮድ ከንግሥቲቱ የያዙት መልእክት እስ ስላለ አንድ አገልጋይ በግልጽ ሰማያዊ ሐር የተሸፈነ እንደ ከረጢት ያለ አመጣለት ። በዚያን ጊዜ መላክተኛው ሁሉ ብድግ ብሎ ሲቆም ከውጭም የመድፍ ድምፅ ያስተጋባ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሮድ ቆሞ '60 ዓመት ሙሉ ለግዛቷ ሰላም በሰጠችውና ከሌሎች አገሮች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ባደረገችው የእንግሊዝ ንግሥት የሕንድ ንግሥተ ነገሥታት ቪክቶሪያ የወዳጅነት መልከቷን ለንጉሠ ነገሥቱ አደርስ ዘንድ ታዝዣለሁ ። በሐበሻም ላይ የጠላትነት ስሜት እንደሌለን የጥንቱን የእንግሊዝንና የሐበሻን ግንኙነት እንደገና ለማደስ መፈለጋችንን አረጋግጣለሁ' ብሎ ደብዳቤውን ሲሰጣቸው ንጉሠ ነገሥቱ ተቀብለው በጭናቸው ላይ አቆዩና አጠገባቸው ካሉት ከግብጽ ከዲቭና ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ደብዳቤዎች ጋር ደባለቁት ። ቀጥሎ የንግሥቲቱን ጤንነትና ያውሮፓን ወሬ ጠያይቀውት ካበቁ በኋላ ...ሮድ እያንዳንዱን የመልክተኛ አባል በስሙ እየጠራ ለንጉሠ ነገሥቱ እያቀረበው ሰላምታ እየሰጠ አለፈ ። ...ንጉሠ ነገሥቱ ከሮድ በቀር የማናቸውንም እጅ አልጨበጡም ። ...ከዚህ በኋላ እንግዲህ ደክሟችኋልና ነገ እነጋግራችኋለሁ ብለው አሰናበቷቸው ።

የጅቡቲ (ኦቦክ) አገረ ገዥ የነበረው ሙሴ ሊዎንስ ላጋርድ በኢትዮጵያ ተቀማጭና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርነት ተሾሞ ሲመጣ የተደረገለት አቀባበል ከሁሉ የበለጠ ነበር ። ገና ሐረር ሳይደርስ ራስ መኰንን ልጅ ቢራቱ የሚባለውን መስፍን ከ3,000 አጃቢ ጋር ልከው በረሃውን ሳይጨርስ አሳጅበውታል ። ራሳቸው 15ሺ ጦር ይዘው ኮምቦልቻ ድረስ በመሔድ በታላቅ ክብር ተቀብለውና በደስታ አስተናግደው ወደ አዲስ አበባ ሸኝተውታል ። ካፄ ምኒልክም ጋር በይፋ የተገናኘለት በታላቅ ክብርና ፍጹም በሆነ ወዳጅነት ተቀብለው ካነጋገሩት በኋላ አንገቱን በማቀፍ የደስታ ስሜታቸውን ገልጸውለታል ።[1]

1 L' Empire des Negus, Pierre - Alype, P. 93.



ከዓድዋ ድል በኋላ የእንግሊዝ መልክተኛ አዲስ አበባ ሲገቡ
ከቤተ መንግሥት መዝገብ ቤት

# ምዕራፍ ስድሳ ሁለት

## የራስ መንገሻ ዮሐንስ መክዳትና አንከበር መታሰር

ራስ መንገሻ ፣ የዓድዋን ጦርነት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በመሰለፍ ተዋግተው ድል ከተገኘ በኋላ ፣ በትግሬ ግዛት ንጉሠ ነገሥቱ አቋቋመዋቸው እንደዚሁም በጦርነቱ ጊዜ ለተጐዳው ሰዋቸው የሚሰጡት 30,000 የማሪያ ቴሬዛ ብር ዳረጐት ሰጥተዋቸው ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ ባለፉት ምዕራፎች ተዘርዝሯል ። ከዚያም ወዲህ ዝምድናው እየጠበቀ እንዲሔድ ሲባል ፣ በንጉሠ ነገሥቱና በእቴጌ ጣይቱ መልካም ፈቃድ የእቴጌን ታናሽ ወንድም የራስ ወሌን ልጅ ወይዘሮ ከፋይን ድረውላቸዋል ። ደጃች ሥዩም አባ ጐበዝ የሚባሉትንም ዋና የራስ መንገሻ ባላንጣ ራስ መንገሻን እንዳያስቸግሩ ባፄ ምኒልክ ትእዛዝ በግዞት እንዲቀመጡ ተደርጎ በጠቅላላው የራስ መንገሻ ሥልጣን በትግሬ አገር ተረጋግጦ ነበር ።

ነገር ግን ፣ ራስ መንገሻ በመተማ ጦርነት ፍጻሜ ላይ ያፄ ዮሐንስ አልጋ ወራሽነታቸው ተነግሮላቸው ስለነበረ ፣ ባፄ ምኒልክ በኩል የተደረገላቸው ሁሉ ከልብ ያስደሰታቸው አይመስልም ። "ንጉሠ ነገሥትነቱ እንኳን ቢቀርብኝ በትግሬ ለምን አልነገሥሁም" የሚል ቅሬታ ያላቸው ይመስላል ። ባፄ ምኒልክ ዘንድ ደግሞ የመንገሻ መግባትና መታመን ከልብ አለመሆኑን ፣ ንጉሥ ቢባሉም ባይባሉም ፣ ሲመቻቸው ከዚህ ቀደም በመረብ እንደ አደረጉት እንደሚከዱ የተገነዘቡት ይመስላል ። በዚህም ላይ በወሎም ራስ ሚካኤል ፣ በሐረርም ራስ መኰንን ንጉሥ መሆን ሳያምራቸው አልቀረም ። ነገር ግን ፣ ምኒልክ ትክለኛ ባላባትነትን ነቅለው ዕድገት ባገልግሎት ላይ ብቻ እንዲመሠረት ስላሰቡ ፣ የንጋሢነትን ደረጃ በዘመናቸው ለማንም ላለመስጠት የወሰኑ ይመስላል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ምኒልክም ጥርጣሬያቸውን በልባቸው እንደያዙ ፣ መንገሻም የመንገሥ ፣ ይኸውም ያልሆነ እንደሆነ የመሸፈት ዓላማቸውን ደብቀው ሁለቱም በሕብረት የበላይና የበታች ፣ አባትና ልጅ መስለው በመሥራት እስካሁን ቆይተዋል ። በእቴጌ ጣይቱም በኩል የወንድሜን የራስ ወሌን ልጅ ወይዘሮ ከፋይን አግብቶ ስለ ወለደ

ዝምድናችን ጸንቷል ብለው ከመተማመን ጋር እንደ ደጃዝማች
ገብረ ሥላሴ ባሪያ ጋብር ያሉት የኛ የልብ ታማኝ አገልጋዮች ስለሆኑ ፣
በትግሬ በኩል ያለው ችግር እየተቃለለ ሔዷል የሚል ስሜት
በቤተ መንግሥቱ ያደረ ይመስላል ።

በዚህ መካከል ፣ ራስ መንገሻ በ1889 ዓ. ም. በጥቅምት ወር ላይ
እንደ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አባባል ፤ "ጃንሆይን ናፍቄያለሁና
እንድመጣ ይፍቀዱልኝ" ብለው ቢልኩ ፣ "እሺ መልካም ነው ።
ልደትን ከኛ ጋር እንድትውል ሆነህ ና" ብለው መልስ ላኩባቸው ።
ለርሳቸው ማረፊያ የደጃች ወልዴ* ቤት ማናቸውም ታድሶ እል
ጋው ፣ እጎበሩ ፣ መጋረጃው ተዘጋጅቶ ሲጠብቃቸው በታኅሣሥ ወር
መጨረሻ ለገና ጾም መፍቻ የገሃድ ለት ገብተው በተዘጋጀላቸው
ቤት ዐርፈዋል ። የግንኙነቱን ፣ የሚጋዘውን ፣ የመስተንግዶውን ዓይነ
ትና መጠን ፣ ወደ ግቢ ሲመላለሱ የግብዣውን፣ የሽልማቱንም ዓይነ
ትና ብዛቱን ከተረኩ በኋላ የከዳቱን ሰበብ ጸሐፌ ትእዛዙ ሲያወሱ ፣ እን
ደርታ የባላገር ልጅ ተስፋዩ የሚባል ያዬ ዮሐንስ የልፍኝ አስከል
ካይ የነበረ በአሁኑ ጊዜ የራስ መንገሻ አሽከር ሆኖ እንደሚያገለ
ግል ፣ ስለዚህም ራስ መንገሻ ፣ ራስ ስብሐትን አስረው ተስፋዩን
ሹም አጋሜ ብለው እንደ ሾሙት ፣ ሌላ ደግሞ ባሻ ተወልዱ
የሚባለው እነዚህ ሁለቱ ራስ መንገሻን እንግሥው ተስፋዩ ራስ
ለመባል ፣ ተወልዱ ቱርክ ባሻ ለመሆን እንዳነሣሡዋቸው ፊትም እናን
ግሥሃለን ብለው ለኢጣልያ ያስገቡዋቸው** እነዚህ መሆናቸውንና
ራስ መንገሻ ግን ሰውነታቸው ጸጥ ያለና የረጉ ናቸው በማለት መዝግ
በውት ይገኛል ።[1]

ከዚሁ እያይዘው ይኸው ባሻ ተወልዱ ወደ አቡነም ፣ ወደ እጨ
ጌም ፣ ወደየመኳንንቱም እየዞረ ፣ "የመጣነው ሊያነግሡን ነው ። ጌታ
ችንን መቼ ነው የሚያነግሡልን" እያለ ማውራቱን ፣ የዚህንም ወሬ
እቴጌ ጣይቱ ሰምተው ማዘናቸውን ፣ ከዚያም እቴጌ ሹም አጋሜ ተስ
ፋዩን አስጠርተው ፣ "ምንድነው እንደዚህ እያላችሁ ታወራላችሁ"
ብለው ቢጠይቁት እንዳልሰማና እንዳልመከረ ሁሉ ፣ "አልሰማሁም
ግን አስበውና" የሚል መልስ መስጠቱን ፣ ከዚያ ተስፋዩ ወደ ራስ
መንገሻ ሔዶ "እንነግሣለን ብላችሁ ታወራላችሁ . . . በማናቸው
አገር ትነግሣላችሁ መንግሥት እንደዚህ ዋዛ ነው" ብለው እቴጌ

* በኋላ ራስ የተባሉት የደጃች መሸሻ አባት ።
** መረብ ከጀኔራል ጋንዶልፊ የተዋዋሉትን ሲጠቅሱ ነው ።
1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . . ምዕ. 65 ገጽ 272-274



ተቆጡኝ ብሎ ለራስ መንገሻ መንገሩን ፣ ራስ መንገሻም በልባቸው
ተቆጥተው ከነተስፋዩ ጋር ሲመካከሩ አድረው በማለዳ እንደመጡ
ወደ እቴጌ ዘንድ መጥተው ፣ "ትላንትና ሹም አጋሜ ተስፋዩ የእቴ
ጌን ቁጣ ነገረኝ ። እኔም እጅግ አድርጌ አዘንሁ ። እኔ ዘበኛ በር ጠባቂ
ነኝ ። የሚመጣውን ነገር ሁሉ ለናንተ ልነግር መጣሁ እንጂ እነግ
ሣለሁ ብዬ አልመጣሁም . . . ደግሞስ እግዚአብሔር የሚያነግሠኝ
ከሆነ ያለሁበት ቦታ ጠፍቶት ነውን ለየመኳንንቱ የምነግሠው
መቼ ነው እያልሁ የምጠይቀው" ብለው በቁጣ ቃል መናገራቸ
ውን ፣ እቴጌይቱም ለዚህ መልስ . . . ንጉሥ እንዲህ ሲወዱህ ሲያ
ፈቅሩህ ይህንን የሰሙ እንደሆነ ይቀየሙብሃል ፤ ሰውም ያነውርሃል ብዬ
ነው እንዲህ መናገሬ ። አንተ የዋንት የጌታ ልጅ ነህ ፤ ፊትም እያ
ትህ ስሑል ሚካኤል* ራስ ተብለው ነው የገዙ . . . ራስ ወልደ
ሥላሴም ራስ ተብለው ገዙ ። የኛም አባት ደጃች ውቤ** ከምጥዋ
እስከ ባምብሎ ድረስ ደጃዝማች ተብለው ገዙ ። "አንተ ዛሬ መንግሥት
(መንገሥ) ምን አሳሰበህ . . ." ብለው ቢመክሩአቸውም ፣ ምክሩ
ለመንገሥ የተነሣውን ምኞታቸውን ሲያበርድ አልቻለም ።

ስለዚህ ከአዲስ አበባ ተሰናብተው ቅርታቸውንና ለመሸፈት
ማሰባቸውን ሳይገልጡ ከንጉሡ ነገሥቱ ፣ ከእቴጌይቱም ተሰነባብተው
ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ መሸፈታቸው ተሰማ ። ቢጠሩም "እኔ ለዘ
መቻ የሚሆን ባይሆን ወታደር እልካለሁ እንጂ ራሴ አልመጣም"
ብለው ስለላኩ መሸፈታቸው በእርግጥ ታወቀ ። ዐፄ ምኒልክ በተለ
መደ ትዕግሥታቸው ወዲያው ጦር ልከው ፣ "ሒድ ውጋው ፣ ግር
ከው ፣ ግደለው" ሳይሉ አባብለው የሚያስገቡበትን በዘመኑ በኢትዮ
ጵያ የተከበሩትን አበውና አረጋውያን መምህር ዜናን ፣ መምህር ፈቃ
ደን ፣ መምህር አካለ ወልድን ፣ የሐይቁን መምህር አባ ዓምደ ሥላሴን ፣
የማሸኑን ግራ ጌታ ውቤንና አባ ወልደ ገብርኤልን መስቀል አስይ
ዘው በመላክ ፣ "የትግሬን አድባራት ሁሉ ይዛችሁ እኔ በድየህ እን
ደሆነ ማረኝ ፣ ይቅር በለኝ ብላችሁ መስቀሉን ተሸክማችሁ ውደቁና
አስታርቁኝ" ብለው ላኩ ። እቴጌ ጣይቱም ለብቻ ብዙ የማባበያ ቃል
ጨምረው "ልጄ ስለ መድኃኔ ዓለም ፣ ስለ ተሰቀለው ጌታ . . .

* እያትህ ያሉት የሩቅ ዝምድና ቀጠራ ነው እንጂ የሩቁ ራስ ስሑል ሚካኤል
ለራስ መንገሻ የእናታቸውም ያባታቸውም አባት አይደሉም ። በራስ ስሑል
ሚካኤልና በራስ መንገሻ ማሕል 6 ዘር ይወርዳል ።
** ይኸውም እንደዚያው እንደ ራስ ስሑል ሚካኤል ፣ ውቤ ለእቴጌ ጣይቱ አጎት
ናቸው እንጂ አባት አይደሉም ።

እማጥኜሃለሁ ፡ ይህን ክፉ አሳብህን ተው ፡ የሰይጣናትን ክንፋቸውን
ሰበረው . . .” የሚል ቃል ጨማምረው ቢልኩ ራስ መንገሻ አንድ ጊዜ
ቆርጠው የተነሡበት ጉዳይ ስለሆነ ፡ የመነኮሳቱም ልመና የእቴጌም
መማጠን በዚህ ጊዜ አልሠራም ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ራስ መኰንንን ከሐረር አስ
ጠርተው ሐረርን እንደያዙ በትግሬ ላይ ሾሟቸው ። ይኸው በዐዋጅ
ተነገረና መኰንን ከአዲስ አበባ ወደ ትግሬ እንዲሔዱ ታዘዙ ። የወ
ሎውም ራስ ሚካኤል ራስ መኰንንን እንዲረዱ ታዘዙ ። ለትግሬም
ሕዝብ ቀጥሎ ያለው ዐዋጅ ተነገረ ።

ስማ የትግሬ ሰው ፤ ራስ መንገሻ ፊት ደጃዝማች ሥዩምን አስሬ
እሱን ብሾመው ከዳኝ ። አሁን ደግሞ እሾሁን ነቅዬ * አደላድየው
ሾሜው ብመጣ እኔን አባቱን ከዳኝ ። የትግሬ ሰው አድባራቱም
መኳንንቱም ራስ መንገሻን ሰወደው ጠልቶኛልና ግፌን እይልኝ ።
እኔ ግን ፡ ያፄ ዮሐንስን ወረታ እመልሳለሁ ብዬ መኳንንትና ወታደር
ሳይወደው በግድ ሾሜው ነበርና መሬት አሰናበተችው እንጂ እኔ
በድየው አይደለም ። አሁንም የትግሬ ሰው ራስ መንገሻ ከዳኝ ብዬ
በሱ ተናድጄ አላጠፋህም ። እግዚአብሔር የሰጠኝን አገሬን (ትግሬን)
በጄ አድርጌ አለማዋለሁ ። ደስ አሰኝሀለሁ ። አይዞህ ግባ በየአባትህ
እተክልሃለሁ ። አባትህን መርቅ ፤ አባትህን እርገም ፤ ልብህ ያሰበውን
የሚያደርግልህን ለባሕርይህ የሚስማማህን ልጄን ወዳጄን ራስ መኰ
ንንን ሰጥቸሃለሁ ። ከሐረር ጋራ ትግሬን ማድረጌ አንተን እንዲያስ
ማህ ፡ አንተን እንዲጠቅምህ ብዬ ነው ። የሱን ይሰጣችኋል እንጂ
ከትግሬ የሚፈልገው ነገር የለም ። [1]

የራስ መንገሻን አሸፋፈት መኳንንቱም ፡ መሳፍንቱም ያወገዙት
ይመስላል ። ስለዚህ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ ለጻፉላቸው መልስ የጐጃሙ
ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጥቅምት 17 ቀን 1892 ዓ. ም. በጻፉት
ደብዳቤ እንደዚህ ብለዋል ።

ኃበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢ
ትዮጵያ ። ጃንሆይ የራስ መንገሻን ነገር እዚያው አዲስ አበባ ሳለሁ
ሁሉንም አመልክቼዎ ነበር ። የርሱም ነገር የቀረው ሁሉ ምሕረትዎ
ትዕግሥትዎ ቀርቶ ፊት ደጃዝማች ሥዩምን አስረው የሰጡት ፡ ኋላም
ድፍን አበሻን አስከትለው ዘምተው ከጠላታችን ከኢጣልያ ተዋግ
ተው ሠራዊትዎን አስፈጅተው እርሱን ሾመው ለቁስለኛው መዳኛ
ለሠራዊቱ ደመወዝ ሰጥተው የመጡት ውለታዎ አይበቃም ነበር . . .
አሁንም ሰውን አስፈጅቶ እሱ አራት አምስት ሆኖ ቢወጣ

* እሾሁን ነቅዬ የሚሉት ሥዩም አሳ ጉበዝን ሽረው የሰጧቸውን ለማውሳት
ወይም ጣልያንን በድል መልሼ ለማለት ይሆን ?

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 291



ምን መውጣት (መሸፈት) ነው ። አሁንም የኃጢአት ውዝፍ ይኖረ
ዋል ። ያንን ጨርሶ ከእጅዎ ይወድቃል እንጂ መውጣቱ ሊሰነብት
አይደለም ። [1]

ራስ መንገሻ ፡ በዚህ አያያዝ ሲሸፍቱ አስታራቂም እምቢ ሲሉ
ምኞታቸውን ከአቅማቸው ጋር ማመዛዘን የተሳናቸው ይመስላል ።
ያለፈውንም ያፄ ዮሐንስንና የንጉሥ ምኒልክን የግንኙነት ታሪክ
በደንብ አጢነው ከራሳቸው አቅዋም ጋር አላመዛዘኑትም ።

ከዓድዋ ድል በኋላ ፡ ያፄ ምኒልክ መንግሥት በጣም መደርጀ
ቱን እየተገነዘቡትና ጣሊያኖችም ፡ እንግሊዞችም ፡ ሌላም መንግሥት
በዚህ ጊዜ በፍጹም ሊረዳቸው የሚችል እንደሌለ እያወቁት ፡ ያን
ያህል የልመና ብዛት ሲወርድላቸው ልባቸው በሸፍትነት የጠጠረ
በት ምክንያት ከዚህ ራቅ ካለው ዘመን ላይ ሊገባን አይችልም ።
ከመረቡ ስምምነት ወዲህ ከአመዛዛኙና ከታወቁት አርበኛ ከራስ አሉላ
ጋር ያጣላቸውም ይኸው አጉል አቅዋማቸው ነው ። የበታች መሸፈ
ቱንም ፡ መገዛቱንም ያላወቀበት እንደሆነ ለበላዩ ችግር ይፈጥራል ።
በደካማ አቅም ኃይለኛን መግጠምና ሰውን በከንቱ ማስጨረስ
ፋይዳ የሌለው መሆኑ ግልጽ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ ከራስ መኰንን ጋር ራስ ሚካኤልን ፡ ዋግሹም ጓን
ጉልን ፡ ደጃዝማች አባተን አድርገው ወደ ትግሬ ሲልኩ ፡ “ ዐውቆ
እጁን ቢሰጥ ይዛችሁት ኑ ፤ እምቢ ካለ ውጉት ” ብለው መመሪያ
ከሰጡ ወዲህ ከሸዋም የሔዱት ራስ መኰንንና ደጃች አባተ ከዋግ
ሹም ጓንጉልና ከራስ ሚካኤል ጋር ተገናኝተው ወደ መቀሌ ሲጓዙ
ራስ መንገሻ መቀሌን ለቀው ኢጣልያኖች ከዓድዋ ጦርነት ቀደም
ብለው መሽገውበት ወደ ነበረው ወደ እዳጋ ሐሙስ ሔደው በዚያ
ለመከላከል አሰቡ ። በዚያም ሳሉ ፡ ከራስ መኰንንም ከራስ ሚካ
ኤልም እንዲገቡ የምክር ቃል ተልኮ ስለአልገቡ በጀርባ በአ
ጋሜ በኩል 4000 ባለ ጠበንጃ ዘልቆ በተደረገው ጦርነት
የራስ መንገሻ ጦር ክፉኛ ተጐዳ ። ከዚህ በኋላ ፡ ራስ መንገሻ
“ ትግሬን አገርዎን ለወደዱት ይሹሙበት እኔን ለእጄ አስምሩኝ”
ብለው እጃቸውን ለራስ መኰንን ሰጡ ። በዚህም ጊዜ ቀድሞ የአጋ
ሜን ሹመት ለተሰፋዬ ሰጥተው አስረዋቸው የነበሩትን ራስ ስብሐ
ትን በአጋሜ መልሰው ሾመዋቸው ከርሳቸው ጋር አስተባብረዋቸው

1 ከታላቁ ቤተ መንግሥት የቀድሞ የጽሕፈት ሚኒስቴር መዝገብ ቤት ቁ. 42
ተመዝግቦ የተገኘ ።

ነበረና እርሳቸውም በዚህ ቀን አብረው ለራስ መኩንን እጃቸውን ሰጡ ።

ዐፄ ምኒልክም ፣ ከአዲስ አበባ መጥተው ወሎ ላይ ሆነው ሁኔታውን ይጠባበቁ ነበር ። ራስ መኩንን ላስተዳደር መቀሌ ሲቀሩ ፣ ራስ ሚካኤል እስረኞቹን እንደያዙ መጥተው በየካቲት ወር መዠመሪያ ላይ 1892 ዓ.ም. ወረይሉ ገቡ ። መንገሻም ፣ ስብሐትም እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ደንጊያ ተሸክመው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ወድቀው ምሕረት ለመኑ ። ሁለቱም በጠባቂ ሆነው አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ፣ አንዱን ዓመት እንደ ቁም እስር ሆነው በአዲስ አበባ ቆዩ ። በእቴጌይቱ አማላጅነት ራስ ስብሐት አጋሜን አገራቸውን አስመርቀው ወደ አዲግራት ሲመለሱ ፣ ራስ መንገሻ “ እጃቸውን ቢሰጡም ልጆቻቸውን ደጃዝማች ሥዩምንና ደጃዝማች ጉግሣ አርአያን በትግሬ አስቀርተው አሁንም እየተላላኩ አሸፍተዋል” ተብለው ተወቅሰው አንድ ዓመት ያህል በደንዲ ደሴት ታሰሩ ። ከዚያ በ1894 ዓ.ም. ወደ አንኮበር ተዛውረው በአዛዥ ወልደ ጻድቅ እጅ ታስረው ሲኖሩ በጥር ወር 1898 ዓ.ም. አንኮበር ሞቱ ።[1]

ራስ መንገሻ ፣ በአንኮበር በጉብታው ላይ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤተ መንግሥት በጠባቂ ሲኖሩ ፣ አገረ ገዥው ወህኒ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ወደማታ እየሔዱና አደግድገው እየገቡ አብረው ራት እየበሉ ሲያጫውቷቸው አምሽተው ወደ ቤታቸው ይመለሱ እንደነበረ ፣ ጠያቂም ከየአለበት ሲመጣ በወህኒ አዛዡ ፈቃድ እየገባ ራስ መንገሻን ያጫውታቸው እንደነበረ ፣ ያዛዥ ወልደ ጻድቅ አሽከር የነበረ ሽማግሌ አንኮበርን በጐበኘንበት ቀን ለደራሲውና ለደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ አጫውተውናል ። ከሽማግሌው ከተለያየን በኋላ ደጃዝማች ዘውዴ “ይገርማል በትግሬ አገር የሚወራው መንገሻ በአንኮበር በእግረ ሙቅ በጥብቅ ታስረው ሕዝቡ በዙሪያቸው እንዳይደርስ ተናካሽ እባብ በዙሪያቸው ተደርጎባቸው ግራ ቀኝ ሲነቃነቁ ይነከሳቸው ነበር ” የሚል ነው ብለው በነገሩ አሳዛኝነት ሁለታችንም መገረማችንን ደራሲው ያስታውሳል ።

* ደንዲ ከአምቦ በስተደቡብ የሚገኝ ደሴት ነው ።

1 Maurice de Coppet, Chronique du Regne De Menelik II, vol. II, PP. 471-483, 620, 621 Annaratore, in Abyssinia, PP. 60-63.



# ምዕራፍ ስድሳ ሦስት

## ከውጭ መንግሥታት ጋር የተደረጉት ውሎች
## የሦስቱ መንግሥታት የከፍፍል ስምምነት

ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ ኢጣልያ በውጫሌ ውል የተነሣ ተመኝታ የነበረውን የበላይነት ጉዳይ ሰርዛ ከኢትዮጵያ ጋር በይፋ በእኩል መንግሥትነት ደረጃ እ.ኤ.አ.በ1897 ዓ.ም. የወዳጅነት ውል ካደረገች ወዲህ ፣ የውጭ መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸውን የንቀትና የማወላወል ሁኔታ ወደጐን አድርገዋል ። ከዓድዋ በፊት ኢጣልያን ይደግፍ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ሳይቀር መልከተኞቹን ልኮ ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ግንኙነት ለማድረግ ተገደደ ። ወዲያው በዚሁ ዓመት ሌጋሲዮኑን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብአዲስ አበባ ከከፈተ ወዲህ ፣ እ.ኤ.አ. በግንቦት 14 ቀን 1897 በ6 አንቀጾች የተከፈለ የወዳጅነት ስምምነት ፣ እንደዚሁም በዘይላና በሌሎችም የእንግሊዝ ቅኝ አገሮችና በኢትዮጵያ መካከል ስላለው የወሰን ክልል ፣ ስለ ጸጥታ ፣ ስለ ቀረጥና ስለ ጦር መሣሪያ መተላለፍ ጉዳይ ደንበኛ ውል ተዋዋለ ። ቀጥሎ በ15 ግንቦት 1902 ዓ. ም. እ.ኤ.አ. በሱዳን በኩል ስላለው ወሰን ፣ ስለ አባይና ስለ ጁባ የወንዝ ፈሳሾች ጉዳይ በ5 አንቀጾች የተከፈለ ውል በተጨማሪ ተዋዋሉ ።

የፈረንሳይ መንግሥት ፣ በዚሁ በ1897 ዓ.ም በመጋቢት 20 ቀን ስለ ወሰንና ስለ አሰል (አውሳ) ጨው አወጣጥ ጉዳይ ከተዋዋሉ ወዲህ እ.ኤ.አ. በ1909 ዓ.ም. በጥር ወር ጅቡቲን ስለሚያዋስነው ጉዳይና በዚያም በኩል ስለሚገባውና ስለሚወጣው ሸቀጥ ፣ ስለሁለቱ አገሮች ዜጐች አጠባበቅና መብት ፣ ስለ ንግድ ልውውጥ ፣ ስለ ጦር መሣሪያም በ9 አንቀጽ የተከፈለ ደንበኛ ውል አደረገ ።

በዚሁ ዐይነት ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት በሩቁና በቸልታ ይመለከት የነበረው የአሜሪካ መንግሥት ወኪሉን ሚስተር ሮበርት ስኪነርን ልኮ በ1903 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር በ7 አንቀጽ የተከፈለ ስለ አሜሪካንና ስለ ኢትዮጵያ ዜጐች በየአገራቸው በነጻ ለመዘዋወር ስለሚችሉበት ጉዳይ ፣ ስለ ንግድ ፣ ስለ ወኪል ልውውጥና በጠቅላላው ስለ ወዳጅነት ውል ተዋዋለ ።

በዓድዋ ጦርነት አካባቢ የጀርመን መንግሥት ፍጹም የኢጣ
ልያ ወዳጅ ነበረ ። በመቀሌው ጦርነት ለተዋጋው ለኮሎኔል ጆሴፔ
ጋልያኖ የኒሻን ሽልማትም መላኩን እናስታውሳለን ። የዓድዋ ድል
ወሬው እንደ ተሰማ ኩብስጭት ላይ የወደቀውን ንጉሡን ኡምቤርቶን
ለማጽናናት ከበርሊን ወደ ሮማ እስከ መጓዝ የደረሰው፣ የጀርመን ንጉሠ
ነገሥት ዳግማዊ ዊልሄልም አሁን ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ የኢጣልያ
መንግሥትና ሌሎቹም እየተሽቀዳደሙ ከምኒልክ ጋር በውል ሲወ
ዳጁ እርሱ ወደኋላ መቅረት አልፈለገም ።

ስለዚህ ፍሬደሪክ ሮዘን የሚባለውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል
አድርጎ ወደ አዲስ አበባ በመላክ እ.ኤ.አ. በመጋቢት 7 ቀን 1905
ዓ.ም. በ6 በተከፈለ አንቀጽ ሌሎቹ መንግሥታት እንዳደረጉት የመ
ስለ የወዳጅነት ፣ የመቀራረብ ፣ የንግድ ልውውጥንና የዜጎች መብ
ትን በሚመለከት ተዋውሎ ተፈራረመ ። የጀርመንንም አርአያ በመከ
ተል የአውስትሮ — ሐንጋሪ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ፍራንሷ ዮሴፍ
ሙሴ ሎዊ ሆህኔል የሚባለውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል ልኮ ከጀ
ርመን መንግሥት ጋር ከተደረገው ስምምነት ጋር ተመሳሳይ የሆን
ውል በመጋቢት 21 ቀን 1905 ዓ.ም. ተዋዋለ ። ከነዚህም በኋላ የቤ
ልዥክ ንጉሥ ሙሴ ሄኒን ሀ የሚባለውን ልኮ ተዋዋለ ።[1]

ከነዚህ ሁሉ ሦስቱ ኃያላን እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይና ኢጣልያ በቅኝ
አገሮቻቸው አማካይነት ከኢትዮጵያ ጋር ስለሚዋሰኑ ፣ በልዩ ልዩ
መንገድ በኢትዮጵያ ሀብት በየበኩላቸው ለመጠቀም በቀጥታ ም በጐ
ንም ፣ በሐቅም በተንኮልም ብዙ የሚሸርቡት መንገድ እንደነበረ የታ
ወቀ ነው ። የዓድዋ ድል የነጭን የዘር ክብር በመንካቱ ፣ ቅርታን
በመፍጠሩ ጐን ፣ ወሬው በየቅኝ አገሩ ሕዝብ መሠራጨቱ ለየትኛ
ውም የአውሮፓ ኃያል አላስደሰተም ። በዚህም ላይ ባሁኑ ጊዜ የም
ኒልክ መንግሥት የሥልጣኔ ሥራ አገርማመር በመጠኑ ከሥጋት ላይ
መጣሉ የታወቀ ነው ። ምክንያቱም አንድ የሠለጠነ ሕዝብ በምንም
ዐይነት በሌላው መገዛትን አይቀበልም ። በአሁኑ ጊዜ የአውሮፓ ገዥ
ነት የሌሎቹ ተገዥነት መሠረታዊ ሰበቡ የሥልጣኔ ልዩነት መሆኑ
ግልጽ ነው ። አንድ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አፍሪካዊ አገር መሠልጠኑንም ፣
በጦር ኃይል መደራጀቱንም ሁሉም አይወዱትም ፤ አይቀበሉትም ።

ስለዚህ ፣ እነዚህ ሦስት ኃያላን ሲወያዩ ቆይተው ፡ እርስ በርሳቸ
ውም የተስማሙበትን ፡ ከኢትዮጵያ ጋር የተዋዋሉትንም ውል

1 L'Ethiopic et les convoitses allemandes, P. Alype, PP. 121-227:
Storia Diplomatica dell, Etiopia . . . C. Rossetti, PP. 221 - 222, 225, 239, 291- 293.



የሚያጠቃልል በሎንዶን ከተማ የሦስቱ መንግሥታት ወኪሎች ስለ እን
ግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኤድዋርድ ግሬይ ፣ ስለ
ፈረንሳይ አምባሳደሩ ሙሴ ፖል ጋምቦን ፣ ስለ ኢጣልያ አምባሳደር
ሲኞር ዲ ዡሊያኖ ፣ "የሦስቱ መንግሥታት ስምምነት" ተብሎ የሚ
ጠራውን የከፍፍል ስምምነት እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ 13 ቀን 1906 ዓ.ም.
ተዋዋሉ ።

የመዠመሪያው አንቀጽ ሦስቱ ተዋዋዮች ፡ ኢትዮጵያ እስካሁን
ያደረጋቻቸውን ውሎች በማክበር የኢትዮጵያን የፖለቲካና የወሰን
ግዛት ለማክበር መስማማታቸውን ፤

በሁለተኛው አንቀጽ ፡ እነዚሁ ኃያላን ከኢትዮጵያ በሚያገኙት
የንግድ ፣ የኢንዱስትሪና የእርሻ ውል በምንም ዓይነት አንዱ የሌላ
ውን ጥቅም የሚፃረር ሥራ እንዳይሠራ ለየወኪሎቻቸው መመሪያ
እንደሚሰጡ ፣

በሦስተኛው አንቀጽ ፡ ባገር ውስጥ የርስ በርስ ጠብና የባለሥል
ጣን ልውውጥ ቢደረግ ሦስቱም ኃያላን የገለልተኛነት አቅዋም እን
ደሚወስዱ እንጂ ፣ ባገር ውስጥ ጉዳይ እንዳይገቡ ቃል መግባታቸ
ውን ፤ ነገር ግን የየግል ጥቅማቸውን እንደዚሁም የሌጋሲዮን ሠራተ
ኞቻቸውንና የዜጐቻቸውን ሕይወት ለመጠበቅ እርምጃ ለመውሰድ
መስማማታቸውንና በነገሩም ሊገባ የሚፈልገው ኃያል አስቀድሞ
ከሁለቱ ኃያላን ጓደኞቹ ጋር ከተስማማ በኋላ መሆን እንዳለበት ።

በአራተኛው አንቀጽ ፣ ምናልባት የኢትጵያን ነጻነትና አንድነት
የሚሽር ከውጭ አንድ ኃይል ቢመጣ ሦስቱ ኃያላን በመዠመሪያው
አንቀጽ እንደ ተጻፈው ፣ "የኢትዮጵያን አንድነትና ነጻነት ለማስጠ
በቅ" ግዴታ መግባታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ፤

ሀ/ እንግሊዝና ግብፅ ፡ በአባይ ወንዝ ስላላቸው የፈሳሽ ወሃ
አከፋፈል ጉዳይ . . .

ለ/ ኢጣልያ ፣ በኤርትራና በሱማሌ በኩል ስለአላት ቅኝ አገር ፣

ሐ/ ፈረንሳይ ፣ የጅቡቲ ቅኝ አገር ግዛቷና ከጅቡቲ እስከ አዲስ
አበባ የሚዘረጋውን የባቡር ሐዲድ መስመር የሚጠበቅበ
ትን ፤

በአምስተኛው አንቀጽ ፤ የፈረንሳይ መንግሥት እ.ኤ.አ መጋ
ቢት 9 ቀን 1904 ዓ. ም. በኢትዮጵያና በፈረንሳይ መካከል ስለ
ምድር ባቡር መዘርጋት ያደረገውን ውል ለሁለቱ ኃያላን እንደሚ
ያስታውቅ ፣ እንደዚሁም በነሐሴ 8 ቀን 1904 ከድሬዳዋ እስከ አዲስ

አበባ ስለሚራዘመው የሐዲድ መስመር ካፄ ምኒልክ የተሰጠውን
የፈቃድ ውል ለሁሉቱ ኃያላን እንደሚያስታውቅ ።

በስድስተኛው አንቀጽ ፡ የባቡሩ ሐዲድ ከአዲስ አበባ እስከ ድሬ
ዳዋ ፡ ከድሬዳዋ እስከ አዲስ አበባ እንዲራዘም ምናልባትም ከድሬ
ዳዋ ወደ ሐረርም ቅርንጫፉ እንዲዘረጋ መስማማታቸውንና በነዚ
ህም የሐዲድ መስመሮች የሦስቱ አገሮች ሸቀጦችና ዕቃዎች በጅ
ቡቲ ሲተላለፉ ቀረጥ እንዳይጠየቁ ።

በሰባተኛው አንቀጽ ፡ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ስለ ተዘረጋው
ባቡር አስተዳደር በማኅበሩ ውስጥ የእንግሊዝ ፡ የኢጣልያና የኢትዮ
ጵያ መንግሥት ተካፋይ የሚሆኑበት . . . .በእንግሊዝና በኢጣልያ
የባቡር ወደቦች የፈረንሳይና የኢትዮጵያ ሸቀጥ በነጻ የሚያልፍበት ፤
በስምንተኛው አንቀጽ ከዚህ በፊት ለእንግሊዝ ስለተሰጠው
ውል የፈረንሳይ መንግሥት በምንም ዓይነት እንደማይገባ ፤

በዘጠነኛው አንቀጽ ከአዲስ አበባ ወደ ምዕራብ የሚዘልቅ የባ
ቡር መስመር ለመዘርጋት የውጭ መንግሥት ተባባሪነት ቢያስፈ
ልግም ተፈጻሚነቱ በእንግሊዝ የበላይነት ጥበቃ መሆን እንዳለበት ፤
በዚሁ መሠረት ፡ ከእንግሊዝ ሱማሌ በኢትዮጵያ ግዛት አልፎ ወደ
ሱዳን የሚዘልቅ የሐዲድ መስመር ለመዘርጋት ካፄ ምኒልክ በነሐሴ
28 ቀን 1904 ዓ.ም. ቢፈቀድም ፡ በቅድሚያ የፈረንሳይንና የኢጣል
ያን መንግሥታት ስምምነት እንደሚያስፈልግ ፤ በኢትዮጵያ ስለሚዘረ
ጋው ሐዲድ አስቀድሞ ካልተፈቀደ በቀር ተፎካካሪ የሚሆን ሌላ
መስመር ላለመዘርጋት ሦስቱም እንደ ተስማሙ ።

በዐሥረኛው አንቀጽ ፡ ሦስቱ ኃያላን መንግሥታት እርስ በርሳቸው
በግልጽ እየተወያዩ የየግል ጥቅማቸውን እንደሚጠብቁና በሦስቱ
መካከል አለመስማማት ቢፈጠር ኃላፊዎቹ የገመሩትን ሥራ አቁ
መው ሁኔታውን ለየመንግሥታቸው ማስታወቅ እንዳለባቸው ፤
በዐሥራ አንደኛው አንቀጽ ፡ በአንደኛውና በአምስተኛው
አንቀጽ ከተባለው ውጭ በኢትዮጵያ መሬት ውል ቢወሰድም የተጠቀ
ሱትን ሁለት አንቀጾች ስምምነት የሚፃረር እንደማይሆን ።[1]

ይህ የሦስቱ ኃያላን ውል በ1884—85 ዓ.ም. በርሊን ከተማ
በርክት ያሉት የአውሮፓ የቅኝ አገር ያላቸው ኃያላን እርስ በእርሳ
ቸው በሰላም አፍሪካን ለመከፋፈል ካደረጉት ስምምነት ጋር

1 Storia Diplomatica . . . PP. 319-325.



ብዙም ልዩነት ያለው አይመስልም ። በበርሊን ማንም አፍሪካዊ በራሱ
ጉዳይ ያልተካፈለበትን አፍሪካን በሰላም ያለጠብና ያለፉክክር ለመከ
ፋፈል ተዋዋሉ ። አሁንም ባለፈው ክዓድዋ ጦርነት ቀደም ብሎ ባለው
ጊዜ እንግሊዝ የፈረንሳይን ይዞታ በመቃወም ፡ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ
እንድትስፋፋ ስትደግፍ ነበር ። ኢጣልያም "ኢትዮጵያን ለመውረ
ርና በሥልጣኔ ሥር አውላታለሁ ብዬ ለተነሣሁባት ለኢትዮጵያ ከሞ
ስኮብ ጋር በመተባበር መሣሪያ እያቀበለች በፖለቲካና በሞራል እየደገ
ፈች አስቸገረችን" ብላ ፈረንሳይን ትወቅስና ትከስ የነበረው ፡ በዚህ
ጊዜ ሁሉም ወደጐን ተደርጓል ። ፈረንሳይም በእርግጥ እስከ ዓድዋ
ፍጻሜ ድረስ የነበራትን አቋም ትታ ኢትዮጵያን ወደጐን ገሸሽ
በማድረግ ፡ ሦስቱ የቅኝ አገር ኃያላን ላፄ ምኒልክ ሳያማክሩ የኢትዮጵያ
ወኪል በሌለበት የኢትዮጵያን ሀብትና ፈሳሽ ወንዝ ያለጠብ ለመከ
ፋፈል ያለፈውን የርስ በርስ ፉክክራቸውን የሚደመድም ይኸን
የመሰለ ውል አደረጉ ።

በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ ፤ የኢትዮጵያን ግዛት ፤ አንድነትና
ነጻነት ለማክበርና ፡ በውስጥ ጉዳይም ላለመግባት ምንም እንኳን ቃል
ቢገቡ ፡ ይኸ ሁሉ የባቡር መስመር በነርሱ ወጭና ቁጥጥር ውስጥ
በያለበት በሚሠራጭበት ጊዜ ፡ " ጥቅማችንን ፤ የዜጐቻችንን ሕይወ
ትና መብት እንጠብቃለን " ሲሉ ፡ ከኢትዮጵያውያን ባለሥልጣኖች
ጋር ጠቡ የማይቀር ነው ። በጠቡ ሰበብ ውሎ አድሮም በትክክል ማስ
ተዳደር አልቻላችሁም ፡ ከኛ ጋር አልተዋሐዳችሁምና በኛ ሥል
ጣን ተዳደሩ ማለታቸው የማይቀር ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፡ በታኅሣሥ 13 ቀን 1906 ዓ.ም. ሎንዶን ላይ ያደረ
ጉት ይኸ የስምምነት ትክክለኛ ግልባጭ በሐምሌ ወር ላይ አዲስ
አበባ በሚቀመጡት ወኪሎቻቸው አማካይነት ለንጉሠ ነገሥቱ
ላፄ ምኒልክ ቀረበ ። እርሳቸውም ከወገኖቻቸው ጋር መክረው ዘከ
ረው እንደዚህ ሲሉ መለሱ ። " . . .የሦስቱ መንግሥታት ስምምነት
ደርሶኝ ተመለከትሁት ። የኢትዮጵያን ነጻነት እንጠብቃለን በሚ
ለው በመጀመሪያው አንቀጽ ደስ ብሎኛል ፤ አመሰግናለሁ ። ስለቀ
ረው መንግሥቴን ስለሚመለከተው ጉዳይ ኃያላኑ በራሳችሁ በተስ
ማማችሁበት ውል የኔ መንግሥት የሚገደድበት ውል የለም ።" ይኸ
ውም ማለት የኢትዮጵያን ጉዳይ የኢትዮጵያ ወኪል በሌለበት ብቻ
ችሁን በተስማማችሁበት ጉዳይ እኛን ሊያስገድደን የሚችል የለም
ማለት ነው ። መልሱም የተሰጠው እንደ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በኅ
ዳር 25 ቀን 1899 ዓ.ም. መሆኑ ተመዝግቧል ።[1]

በዚህ ዓይነት ፡ የሦስቱ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒ
ስትር ባለሥልጣኖች ሲወያዩበትና ሲወዛገቡበት ፡ ጋዜጠኞችም የየራ

ሳቸውን መንግሥት ጥቅም በማሳነስ ፤ የሌላውን በማስበለጥ ጥቅሙንም ችግሩንም እያነሡ ሲነታረኩበት ሰንብተው ፤ በመጨረሻም የንጉሠ ነገሥቱ ድርቅ ያለው አጭር ተቃውሞ ጉዳዩን ለዘለቄታ ወድቅ አደረገው ።[1] በዚህም ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ፤ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥት የቆየውን መጥፎ አቅዋማቸውን ለመለወጥ የዓድዋ ድል ቢያስገድዳቸውም ፤ ቀድሞውኑ የታወቀ ሽካራ መሆኑን አልሳቱትም ። የፈረንሳይም ወደነዚሁ ጐራ በጥቅም መተሳሰሩ ስለገባቸው ፤ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የፈረንሳይን ግንኙነት ቀዝቀዝ እያደረጉ እያደር ከጀርመን መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት እያሻሻሉ በመሔድ የጀርመንን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሩን አጉስት ፍሬደሪክ ሮዘንን አቀረቡት ። ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የጀርመን ዐዋቂዎች በቤተ መንግሥቱ ባለሟል ሆነው ገባ ወጣ ማለት ጀመሩ ። የነርሱም አስተርጓሚ የታወቁት ከንቲባ ገብሩ ስለሆኑ በርሳቸውም አማካይነት ግንኙነቱ ሰፋ እያለ ሔደ።

የጀርመንም ዋና ምኞት ፤ ኢጣልያ እስከዚህ ዘመን ድረስ አውስትሪያ ተጨምሮ የሦስት አገሮች የቃል ኪዳን ዝምድና በሚባለው ውል ተሳስራ ከቆየች በኋላ ፤ አሁን ሸርተት እያለች ወደ እንግሊዝና ወደ ፈረንሳይ ብትጠጋም ፤ በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ከብዙ ዘመን ዠምሮ በግዛት ከተስፋፋው ከቱርክ የኦቶማን መንግሥት ጋር በመተባበር ከኢጣሊያና ከግብረ አበሮቹ መንግሥታት ጋር እየተፋለምሁ በኢትዮጵያም ፤ በሌላውም ኋላ ቀር የአፍሪካ አገር ላይ በመሠራጨት ንግዴን አስፋፋለሁ የሚል ነበር ።

የጀርመን መንግሥት ፤ በኢትዮጵያም በሌላውም የአፍሪካ ፤ የእስያና የባልካንም አገር የዚህን ዓይነት ፖለቲካ ሲከታተል ቆየ ። በመጨረሻም የአውስትሪያው መስፍን በፈረንሳይ በሚደገፈው የሰርቢያ መንግሥት ተወላጅ እጅ ተገደለ ። የዚያም ሰበብ የመዠመሪያውን የዓለም ጦርነት እ.ኤ.አ 1914—18 አስከተለ ። የጀርመን መንግሥት ከቃል ኪዳን ጓደኞቹ ከአውስትሪያና ቱርክ ጋር ሲሸነፍ ፤ እንኳን አዲስቅኝ አገር ሊያገኝ ይቅርና በእጁ የያዘውንም በአሸናፊዎቹ በእንግሊዝናበፈረንሳይ ተቀማ ።[2]

ዳግማዊ ምኒልክ ፤ ቀድሞ በኢጣልያ ላይ ፈረንሳይን አጋር በማድረግ እንደ ተጠቀሙ ፤ አሁን ደግሞ ፈረንሳይ ከኢጣልያና ከእንግሊዝ ጋር በኢትዮጵያ ላይ ስለ ዶለተች በፈረንሳይ ፤ በኢጣልያና በእንግሊዝ ላይ በጀርመን አጋርነት ለመጠቀም ተመኝተው ነበር ።

1 Storia Diplomatica, PP.325 - 331 .

2 L'Ethiopie et les convoitises allemandes, PP. 5—73



# ምዕራፍ ስድሳ አራት

## ዓድዋ ያስገኘው ዓለም አቀፋዊ ዕውቂያና የወሰን ስምምነት

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመታወቋ ሁኔታ ልዩ ልዩ የጊዜ ወቅት አለው ። ይኸም ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ይለያል ።

ሀ/ ከክርስትና በፊት ከሺ ዓመተ ዓለም ዠምሮ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ በጥንት የግብጾችና የግሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ስሟ በልዩ ልዩ መንገድ ተጠቅሶ ይገኛል ።[1]

ለ/ ከክርስቶስ ልደት በኋላ እስከ ዐሥረኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ድረስ ሥልጡኑ የአክሱም መንግሥት ፤ በምሥራቅና በምዕራብ የሮማ ቄሣሮች መንግሥት እንዲሁም በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በጣም ስሙ የገነነና የታወቀ ሲሆን ፤ ነገሥታቱ እነኢዛና በሮማ ቄሣሮች በነቆስጠንጢኖስ ዘንድ እንደ ወንድሞች ይቆጠሩ ነበር ።[2]

ሐ/ የአክሱም መንግሥት ውድቀት ካገኘው ጊዜ ዠምሮ ፤ ይኸውም ማለት ከዘጠነኛው መቶ ዓመት እስከ ዐሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት ከልደት በኋላ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር የነበራት ግንኙነት የተዳከመ ነበር ። "ቄስ ዮሐንስ በሚባል ንጉሥ የምትመራ አንድ አገር አለች" እየተባለ በአውሮፓ ቢወራም ፤ በየትኛው ክፍለ አህጉር መሆኗ አይታወቅም ነበር ። የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ዳግማዊ "ይቺን አገር ፈልጋችሁ አግኙልኝ" ብሎ እነፔድሮ ዲኮቪልሃምን ላከ ። በስንት ጥረት እ.ኤ.አ. በ1486 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ደርሶ ከዘመኑ ንጉሠ ነገሥት ከዐፄ እስክንድር ጋር መገናኘቱ በየታሪኩ ተጽፏል[3] ።

መ/ ከ16ኛው መቶ ዓመት እስከ 18ኛው መቶ ዓመት ድረስ በነበረው ጊዜ ግሪኮች ፤ አርመኖች ፤ ፖርቱጋሎችና ኤስፓኞች ወደ

1. የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጔ ፤ ተ.ጸ.መ. ፤ ምዕ 1 ፤ ገጽ 11-18 መጽ. ነገሥት 13 ፤ ዘኍልቁ 121 ፤ ምዕ. 5 ገጽ 109—140

2. Storia d' Etiopia, Conti Rossini. Chap. 5, PP. 109—140.

3. የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ፤ ተ.ጸ.መ. ፤ ምዕ. 54 ።

ኢትዮጵያ መመላለስና በኢትዮጵያም መኖር ዠመሩ ። ከእነርሱም
እንዳንዶቹ በተለይ ፡ “ከግራኝ አህመድ ወረራ ወዲህ በተዋሕዶ
ሃይማኖትና በካቶሊክ ሃይማኖት ልዩነት የተነሣ ፡ ኢየሱሳውያኑ ባዔ
ሱስንዮስ ዘመን በቀሰቀሱት ጦርነት ሰበብ ብዙ መጻሕፍት ስለ ኢትዮ
ጵያ መጻፍና ያገሪቱ ሁኔታ ይበልጥ መታወቅ ዠመረ ። በዚህ ጊዜ
ውስጥ በመጽሐፉ ኢትዮጵያን ለዓለም በደንብ ያሳወቀ ፍራንችስኮ
አልቫሬዝ ነው ።

ሠ/ ከ18ኛው እስከ 19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ እን
ግሊዞች ፡ ፈረንሳዮች ፡ ጀርመናች ፡ መስኮቦች፡ ኢጣልያኖች በአገር ጐብ
ኝነት መልክ ይመላለሱ ነበር ። ባዔ ቴዎድሮስ እነሣሥና ከእንግሊ
ዞች ጋር ባደረጉት ጦርነት ሰበብ ከዚያም ወዲህ ያዔ ዮሐንስ ሁለት
ጊዜ በግብፅ ጦር ሠራዊት ላይ ድል በማግኘታቸው ፡ ቀጥሎም የኢጣ
ሊያ መንግሥት ሰሜን ኢትዮጵያን በመውረሩና በውጫሌ ውል የተ
ነሣ የበላይ ልሁን ብሎ በመከራከሩ ፡ ኋላም በዐድዋ ላይ በመሸነፉ
ወሬው በአውሮፓ እየተስፋፋ ስለተጻፈ ፡ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ
ከፈተኛው ጊዜ የበለጠ መታወቋ እየቀጠለ ሔደ ።

በኢትዮጵያ ይህ ሁሉ ሲሆን ፡ ሌላው የአፍሪካ ክፍለ አህጉር በአ
ውሮፓ ኃያላን ተከፋፍሎ ተይዞአል ። ይዞታውም በ19ኛው መቶ ዓመት
መገባደጃ ላይ በበርሊን የጋራ ስምምነት ተረጋግጧል ። ኢትዮጵ
ያም ነጻ ብትሆንም ፡ አንድ ቀን ካንድ አውሮፓዊ ሥልጣን
ውስጥ መውደቋ አይቀርም የሚል ግምት ነበረ ። በተለይ
ቅኝ አገር ካላገኘውና ለማግኘት ከሚጣጣረው ከኢጣልያ እጅ አታ
መልጥም የሚል አስተያየት አልጠፋም ። በዚህም ላይ አመች ወቅት
ቢፈጠር ይኸውም ማለት በኢትዮጵያ የርስ በርስ የጦርነት ትርምስ
የተፈጠረ እንደሆነ አገሪቱን ከሱዳን አልፎ የአባይ ምንጭ ያስበ
ትን ምዕራብ ኢትዮጵያን እንይዛለን የሚል ምኞት በእንግሊዞች
ዘንድ ነበር ። እንደዚሁም ኢጣልያም ፡ ፈረንሳይም በየበኩላቸው ለመ
ስፋፋትና በግልጽ ሳይሆን ስወርወር ባለ መንገድ ኢትዮጵያን ለመ
ያዝ አጋጣሚ ጊዜ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ ።

በዚሁ የማድባት አያያዝ የአውሮፓ ኃያላን “አንድ ቀን እንከፋፈላ
ታለን” በሚሉ የጐጉት ተስፋ ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ ጋር በቁም
ነገር ተነጋግር ሌጋሲዮን ለመክፈትና የወሰን ውል ለማድረግ
የፈለገ የለም ። ስለዚህ ኢትዮጵያን በየወሰናቸው ለመያዝ አመቺ
ጊዜ ሲጠበቅ ፡ በመካከሉ የኢጣልያ መንግሥት ለብቻዬ
እወስዳታለሁ ብሎ በቀሰቀሰው ጦርነት ዓድዋ ላይ ሊሸነፍ
ቻለ ። መሸነፉን ለመበቀል የበቃ ኃይልና ጉልበት እጥቶ



በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር በ1889 ዓ. ም. በተዋዋለበት ውል ውጫሌ ላይ
የተደረገው ውል በፍጹም መሠረዙንና የኢጣልያ መንግሥት የኢት
ዮጵያን ሙሉ ነጻነት ማወቁን አረጋገጠ ። ከዚያ ወዲህ የኃያላኑ
አቅዋም የተለዋወጠና ቅኝ አገር በኢትዮጵያ ዙሪያ ያላቸውም የሌላ
ቸውም የአውሮፓ ኃያላን በአዲስ አበባ ነዋሪ መላክተኛ ለማስቀመጥ
ይሽቀዳደሙ ዠመር ። ከዚህ በኋላ እያንዳንዱ መላክተኛ ሰፋፊ ቦታ
እየተመራ ሕንፃ አሠራ ። ይኸም ለአዲስ አበባ ከተማ ድምቀት
ሰጠ ። የመልክተኞቹም ነዋሪነት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ
የመታወቋ ሁኔታ የተደላደለ ምስክር ሆነ ።

በዚሁ ዓይነት ፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በኃያላኑ ዘንድ ያልታወ
ቀው የወሰን ክልል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከልሎ እንዲታወቅ ፍላ
ጐቱ በሁሉም ወገን ተገለጠ ። መቼም ያንድ መንግሥት ጥቅሙ
መኖሩ ብቻ አይደለም ። ነገር ግን ፡ በመንግሥታት ዘንድ ሕጋዊ መታ
ወቅ ሲኖረውና ግዛቱን አረጋግጦ የኔ ነው ብሎ የሚከራከርበት
ዓለም አቀፋዊ የወሰን ክልል ሲኖረው ነው ። አንድ መንግሥት
ደግሞ መታወቅንና ከወሰንተኞቹ መንግሥታት ጋር የመካለልን
መብት የሚያገኘው ፡ በከተማው የመንግሥታትን ወኪሎች ለመቀ
በል ፡ የንግድና የወዳጅነት ውል ለመለዋወጥ ዕድል የሚኖረው ፡ በቅ
ድሚያ የመንግሥቱ አንድነትና የሕዝቡ ሕብረት ሲረጋገጥ በከተማ
ውና በየአውራጃዎቹ ሰላምና ጸጥታ ሲሰፍን ነው ።

እስከአሁን ድረስ እላይ እንዳመለከትነው ፡ የአውሮፓ ኃያላን
በሌጋሲዮን ደረጃ ወኪል ለማስቀመጥ ችላ ያሉት ፡ ወሰን መካለሉ
ንም ያልፈለጉት ፡ አንደኛ የአንድነታችንና የጸጥታችን ሁኔታ በማያ
ቋርጥ ውስጣዊ ጦርነት ስለሚሰናከል ፡ ሁለተኛም ውስጣዊው ጦር
ነት ተራዝሞ ምቹ ጊዜ የፈጠረ እንደሆነ ለመውረር እንዲቻል ነበር ።
የውስጥ አንድነታችን ባዔ ቴዎድሮስና ፡ ባዔ ዮሐንስ
ኃይልና ድካም ከተደላደለ በኋላ ፡ ዐፄ ምኒልክ ደግሞ በፋንታቸው
ኃይሉን በትዕግሥትና በሰላም ስለ አጠናከሩት የዓድዋ ለት ፡
ጣልያንና ምዕራባውያን ባልጠበቁት መንገድ ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ
ከነመሳፍንቱ ባንድ እግር ቆሞና ባንድ የሥልጣን መስመር ተሰልፎ
ወራሪ ጠላቱን መለሰ ። ከዚህም በኋላ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ ኀብ
ረትም ፡ የጸና የመንግሥት አቅዋምም እንዳላት ተገነዘቡ ። ከዚህ ግንዛ
ቤም በኋላ ኢጣልያና የቀሩትም የአውሮፓ ኃያላን የወረራውን
ስሜት ሠርዘው ሌጋሲዮን በመክፈት ወኪል ማስቀመጥና ወሰን መካለ
ልንም ዠመሩ ።

ኢትዮጵያን በወሰን የሚያካልሏት ፡ እንደ አሁኑ ያገር
ተወላጆች የሚመሯቸው መንግሥታት እነ ጅቡቲ ፡ እነ ሱማሌ ፡ እነ

ኬንያ ፥ እነ ኡጋንዳ ፥ እነ ሱዳን ሳይሆኑ እነሱን ይገዙ የነበሩት አውሮፓውያን አገሮች ናቸው ። እነሱም ታላቋ ብሪታኒያ ፥ ኢጣልያና ፈረንሳይ ነበሩ ። ዐፄ ምኒልክም የወሰን ክልል የተዋዋሉት ከነዚሁ መንግሥታት ጋር ነበር ።

በዚህ መሠረት ፥ የፈረንሳይ መንግሥት በዓድዋ ጦርነት ባመቱ መጋቢት 12 ቀን 1889 ዓ.ም. አዲስ አበባ ባስቀመጠው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በሙሴ ሊዎንስ ላጋርድ አማካይነት ተዋዋለ ።

የኢጣልያ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓድዋ በፊት እ.ኤ.አ. የካቲት 3 ቀን 1891 ዓ. ም. ስለወሰን ጉዳይ ተዋውለው የነበረው ኢጣልያ በውጫሌ ውል የበላይነት አገኛለሁ በማለት በቀሰቀሰችው ክርክርና ጦርነት ምክንያት ከሥራ ላይ ባለመዋሉ ፥ ከዓድዋ ድል በኋላ እ.ኤ.አ. በ1900 ዓ.ም. አዲስ አበባ የሚቀመጠው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ካፒቴን ፌደሪኮ ቺኮዲኮላ በኢጣልያ ንጉሥ ስም በሁለት አንቀጽ የተከፈለ የወሰን ውል ካፄምኒልክ ጋር ተዋዋለ ።

የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ ፥ እ.ኤ.አ. በግንቦት 14 ቀን 1897 ዓ.ም. ጀምስ ሬኔል ሮድ በእንግሊዝ ንግሥት በቪክቶሪያ ስም ካፄ ምኒልክ ጋር የንግድና የወዳጅነት ውል ባደረገ ጊዜ ፥ በሁለተኛው አንቀጽ ላይ ሁለቱ ወገኖች በወኪሎቻቸው አማካይነት በእንግሊዝ ሱማሌ ያለውን ወደ ሐረር የሚዘልቀው መንገድ ሁልጊዜ ክፍት እንደሚሆን ፤ በአራተኛው አንቀጽ ስለቀረጥ ፥ በአምስተኛውና በስድስተኛው አንቀጽ ስለጦር መሣሪያ አገባብና አወጣጥ በጽሑፍ አስፍረውት የነበረውን መሠረት በማድረግ ፥ አሁንም ሬኔል ሮድ በእንግሊዝ መንግሥት ስም ፥ ራስ መኰንን ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ሆነው በደብዳቤ ልውውጥ የእንግሊዝ ሱማሌንና የሐረርን ግዛት በመካለል ተስማምተዋል ።

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የእንግሊዝ መንግሥት በሱዳን በኩል ስለ አለው የግዛቱ ወሰን ሌተና ኮሎኔል ጊርሀን ላን ሐሪንግተን በእንግሊዝ ንጉሥ በኤድዋርድ ሰባተኛ ስም ፥ ዐፄ ምኒልክ በራሳቸው ስም እ. ኤ. አ. ግንቦት 15 ቀን 1902 ዓ. ም. በአምስት አንቀጽ የተከፈለ ውል ተዋውለዋል ።



# ክፍል አምስት

### ከዓድዋ በኋላ የልማት ሥራ አወጣጥን

## ምዕራፍ ስድሳ አምስት

### ለልማት ሥራ ተባባሪዎች

ከዓድዋ ድል በኋላ ፥ ዐፄ ምኒልክ በድል አድራጊነት ግርማ አዲስ አበባ ገብተው ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የመጨረሻ ውል ከተዋዋሉና የየመንግሥታቱን ወኪሎች በክብር በየተራ ተቀብለውና ሠፈር ለይተው በመስጠት ሌጋሲዮኖች ከተከፈቱ በኋላ ፥ ንጉሠ ነገሥቱና የሥራ ባልደረቦቻቸው ያተኮሩት የአውሮፓን ሥልጣኔ በየመልኩ ወደ አገር ውስጥ እስገብተው የልማት ሥራ ከማስፋፋት ላይ ነው ።

በአውሮፓ እነሚካኤል ፋራዳይ የኤሌትሪክን የብርሃን ዘዴና ጉልበት ፥ እነ አሌክሳንድር ግራሃምቤል በቴሌፎን መነጋገርን አግኝተው ፥ ሌላውም ወሃን ከወንዝና ከምንጭ በቧምቧ እየጠለፉ ወደ ቤት ውስጥ በማስገባትና ወደ እርሻ ቦታ በመጠላለፍ ሰብላቸውን እያበረከቱ አገራቸውን ሲያለሙ ፤ የሕክምና ፥ የኢንዱስትሪ ፥ የሜካኒክ ሥራ በየመልኩ እየተሻሻለ ሲሔድ ኢትዮጵያ በጥንቱ ኋላ ቀር መሣሪያ ስትጠቀም ረዥም ዘመን አሳልፋለች ።

በኤሌትሪክ ብርሃን በመጠቀም ፋንታ ፥ የፀሐይ ብርሃን ከጠፋ በኋላ ለቤት ውስጥ ብርሃን ዝቅ ያለው ቤተሰብ በምድጃ የእንጨት እሳት ፥ የእራት ጊዜ በተቀጠቀጠ የድግጣና የከትከታ እንጨት ሲጠቀም ፥ ከፍ ያለው ቤተሰብ በጧፍና በሻማ ከዚያም እልፍ ሲል በኩራዝ ፥ በፋኖስ ይጠቀማል ። በጣም ከፍ ያሉ ዘመናዊ ቤተሰቦችና የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች ወደ መጨረሻው ዘመን በማሾ ብርሃን መገልገል ዠመሩ ። አውሮፓ በቴሌፎንና በፖስታ አገልግሎት ሲጠቀም ፥ በኢትዮጵያ መልእክትን በቃል ወይም በጽሑፍ ለሌላው ለማድረስ ወይም ከሌላው ከቅርብም ይሁን ከሩቅ ለመቀበል ፈጣን የሰውና የከብት ጉልበት እየተመረጠ ከወረዳ ወረዳ ፥ ከሠፈር ሠፈር

በመቀባበል ነው ። ሕክምናን በተመለከተ ከግሪኩ ከሂፖክራትስ (460 ከክርስቶስ በፊት) ዠምሮ በአውሮፓ በልዩ የቅመማ ዘዴ እየተመጣጠነ በመኪኒክና በቴክኒክ ምርመራ በሽተኛ ሲታከም ፤ በኛ ዘንድ በመላና በአጋጣሚ የሥራ ሥርና የቅጠላ ቅጠል ጭማቂ መጠኑና ፈዋሽነቱ ባልተረጋገጠ መንገድ ሲሠራበት ቆየ ። የአስማትና የድግም ቃላት በክታብ ተደርጐ ባንገትና በደረት ሲያዝ ጤንነት እንደሚሰጥ ይታመን ነበር ።

ሌላው አውሮፓ የሚራመድበት የሳይንስ ፤ የፍልስፍና ፤ የሥነ ጽሑፍ የእርሻና የመሐንዲስ ደንበኛው ትምህርት ሲሰጥ ፤ በኢትዮጵያ በቤተ ክህነት በኩል የሚሰጠው ብሉይና ሐዲስ ፤ ቅኔና ዜማ ትምህርት ሆኖ ቆየ ። ይኸውም ማለት የኢትዮጵያ መሠረታዊ ትምህርት በመንፈሳዊ ትምህርት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሆነ ማለት ነው ። መገበያያውም ገንዘብ ይበልጡን ሸቀጥ ለሸቀጥ ነበር ።

መቼም ይኸን የኋላ ቀርነት ሁኔታ ለማዳንና ሥልጣኔን ፤ ጥበብን ባገራቸው ለማስገባት እንኳን የቅርቦቹ እነ ዐፄ ቴዎድሮስና እነ ዐፄ ዮሐንስ ቀርተው ፤ የሩቆቹ እነ ዐፄ ልብነ—ድንግል (1500—1533 ዓ.ም.) አገራቸውን የሚያሠለጥን ጥበበኛ ከአውሮፓ ስለ መፈለጋቸው ለፖርቱጋል ነገሥታት ለአማኑኤልና ለልጁ ለዮሐንስ ፤ “ሥዕል የሚሥሉ ፤ መጻሕፍት የሚያትሙ ፤ የጥበብ ሥራ የሚያስተምሩ ሐኪሞች ፤ መሐንዲሶች ወርቅና ብር ከመሬት የሚያወጡ የቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓት የሚያስተምሩ ላኩልን” ሲሉ በግዕዝኛ የጻፉት ደብዳቤ በግልጽ ይነበባል ።[1]

ዳሩ ግን ፤ በልዩ ልዩ ምክንያት ሃይማኖቱና የኖረው ባህል እየተጫጫነ ፤ የውስጥ ጦርነትም ፋታ አልሰጥ እያለ ፤ እስከ ዐፄ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነት ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ የኋላ ቀርነቷን እንደ ያዘች ስታዘግም ኖረች ። የመንግሥት መደበኛ ከተማ ከአክሱም ወደ ላሊበላ ፤ ከላሊበላ ወደ ሸዋ (ደብረ ብርሃን ፤ መንዝ ፤ የረር ቦካን) ፤ ከሸዋ ወደ ጐንደር በተዘዋወረበት ዘመን (ከ10—19ነኛ ምዕት ዓመት) በደብዳቤና በቃል ከመመኘት በቀር ዓለም ሊሻሻል የቻለበትን ዘመናዊዉን የሥልጣኔ ትምህርት በየዘርፉ በቁርጠኛ ውሳኔ ባገሪቱ በየመልኩ ለማስገባት የታደለ ንጉሠ ነገሥት የለም ። ያፄ ቴዎድሮስም ጥረት በጋፋት የታየው የጦር መሣሪያው ሥራ ሁኔታ ውጤቱ አልቀጠለም ።

ዐፄ ምኒልክ ፤ በአንኮበር በምርኮ ወደ ጐንደር ሔደው ቴዎድሮስ ዘንድ እንደ ልጅ የእንክብካቤ እድገት እያገኙ የጦርነትና

1 የግራኝ አህመድ ወረራ—ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ ገጽ 154 — 156



የፖለቲካ ውዝግብ ባሳለፉበት ወቅት ፤ ብዙ የአስተዳደር ዘዴና ስልት በአዕምሮአቸው አጠራቅመው ተመልሰዋል ። ጠባያቸውንም ብልህነት፤ ትዕግሥትና እርቆ አስተዋይነት ስለተዋሐደው ፤ ወደ ሸዋም ከተመለሱ ወዲህ ጧትና ማታ አውሮፓ ደርሰው ከመጡት ኢትዮጵያውያንና በአጠገባቸው ከሚገኙት አውሮፓውያን ስለውጭ ሥልጣኔ በመስማት ላገራቸው ለኢትዮጵያ ዕድል ፤ ለሚወዱትና ለሚወዳቸው ሕዝብ የወደፊት ደህንነት መፍትሔው የአውሮፓን ሥልጣኔ ከማስገባት በቀር ሌላ አማራጭ መንገድ እንደሌለ ተረዱት ።

ስለዚህ ፤ ከሁሉ በፊት በመሳፍንትና በመኳንንቱ ጐን የአውሮፓ ተወላጆች የአማካሪ ቡድን አቋቋሙ ። ከእነዚህም መካከል የስዊሱ ተወላጅ አልፍሬድ ኢልግ የሚባለው የመሐንዲስነት ሙያ ያለው ነው ። እርሱም ከሁሉ የበለጠ ተሰሚነት ያለው አማካሪያቸው እንደነበረ ባለፈው ተጠቅሷል ።

ይህ ሰው ፤ ከሁሉም በይበልጥ የተመረጠበት ምክንያት ፤ በስዊስ ተወላጅነቱ ሳይሆን አይቀርም ። ስዊስ በአውሮፓ መካከል የምትገኝ በፌዴራሲዮን የምትተዳደር ፤ ከፖለቲካ ውዝግብና ከጦርነት ገለልተኛ የሆነች ፤ ቅኝ አገር በየትኛውም ክፍለ አህጉር የማትፈልግ ስለሆነች ፤ የዚች አገር ዜጋ የሆነ አማካሪ ምክሩ የቀና ለየአገራቸው ከሚያደሉት ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ ተወላጆች የተሻለ እንዲያውም የነዚህን ተንኮል ያለበትን የምክር ዘዴ ተፈላልጎ ምስጢሩን ለምኒልክ የሚገልጽ መሆኑ አይጠረጠርም ። የኢጣልያኖቹ የነአንቶኔሊ የነትራቬርሲ የነካፑቺ ወዳጅነት ከምን ላይ እንደ ጣላቸው ንጉሠ ነገሥቱ በቅርቡ ከዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ ተረድተውታል ። እንግሊዛዊም አማካሪ በቤተ መንግሥታቸው በፍጹም አልታየም ። ይልቅስ በዚህ ፈንታ የእንግሊዞች ባላንጣ የሆኑት ፈረንሳዮቹ እነሞንዶን ፤ አነሸፍነ በተለይ ሙሴ ሊዎንስ ላጋርድ የራሱን የመንግሥቱን ሥራ እርግፍ አድርጎ ትቶ ያፄ ምኒልክ ልባዊ አማካሪያቸው ሆነ ።

ስለዚህ ዐፄ ምኒልክ ፤ የነዚህን የውጭ አገር ተወላጅ አማካሪዎች ምክር በመስማት እውጭ አገር ደርሰው መጠነኛ ዕውቀት እየቀሰሙ የተመለሱትን የነግራዝማች ዮሴፍን ፤ የነነጋድራስ ዘውገን ፤ የነአቶ አጥሜን ፤ የነ አቶ መርሻ ናሁ ሠናይን ፤ የነብላታ ገብረ እግዚአብሔርን ፤ የነከንቲባ ገብሩን ፤ የነአለቃ ታየን ፤ የነነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝን ፤ የነአቶ ኃይለማርያም ሰራብዮንን አስተያየት በማዳመጥ በአገራቸው የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት ታጥቀው ተነሡ ። መስኮብ ተምረው የተመለሱት ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት

እንዳጋጣሚ ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም በወደቁበት ሰዓት ስለሆነ ለማገልገል አልታደሉም ። ከነዚህም በቀር ከመሳፍንትና ከመኳንንት መካከል የፈረንጅን አገር በመላክተኛነት ከጐበኙት ከራስ መኰንን ፣ ከደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ፣ ከሊቀመኳስ (በኋላ ራስ) ናደው በቀር የውጭውን አገር ያላዩት እነራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ፣ እነ ሊቀመኳስ አባተ ይነስ ይብዛ ሥልጣኔን በማስገባት ረገድ ተቃዋሚዎች አይደሉም ። በፈረንጅ ትምህርትና ሥልጣኔ አገባብ የተነሣ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንና ነዋሪው ባህላችን ይለወጥብናል ብለው የሚቃወሙት የሃይማኖት ሰዎችና እነሱንም የሚደግፉት ወገኖች ቢሆኑም ፣ "እምዬ ምኒልክ" እስከ መባል የደረሱት ንጉሠ ነገሥት ፣ የሚያደርጉትን ሁሉ ሕዝብ እንደሚቀበላቸው ስላወቁት ፣ የቴክኒኩን ጥበብ ይኸስ የሰይጣን ሥራ ነው እያሉ ከማማት አልፈው የገሃድ ተቃውሞ ማድረግ አልቻሉም ።

ምናልባት የሥልጣኔው ውጥን ከዓድዋ ድል በፊት ቢሆን ኖሮ የገሃድ ተቃዋሚ ባልጠፋ ። አሁን ግን ፣ "ጣልያንን ያህል ጠላት በቅዱስ ጊዮርጊስ እርዳታ አሸንፈው ከውጭ ጠላት አዳኑን " የሚለው ዝና ከመበርከት ጋር በፍርድ ትክክለኛ ዳኝነታቸው ፣ ዘወትር እየተደገሰ በሰፊው ለወታደር ፣ ለካህናት ግብር በማብላት ቸርነታቸው ፣ ለግላቸው ጥሬ ሀብት ወይም ርስተ ጉልት ልሰብስብ አለማለታቸው በሁሉ ዘንድ ስለታወቀ መወደድን ፣ መከበርን ስለሰጣቸው የሚያደርጉት ሁሉ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ ። የሹመት ደረጃ ከማዕረግ ስምና ከሽልማት ጋር የቅርብ ዝምድና ፣ የነገድ ልዩነት ሳይመለከቱ መንግሥትን በቅን ልቦና ፣ በንጹሕ ሕሊና ላገለገለ ሁሉ ያለ አድልዎ መስጠታቸው ፣ የመኳንንቶቻቸውን ቁጥር በብዛት ሲያበረክት ፣ በነዚህም ዘንድ ያደረው የንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር ሁልጊዜ በሁሉም አካባቢ እያደገ ከመሔድ አላቋረጠም ።

ባለቤታቸውን እቴጌ ጣይቱን በመንግሥቱ የፖለቲካና የአስተዳደር ሥራ ሲያስገቡ ከመደገፍና ከማበረታታት በቀር ፣ "ሴት ነሽ ምን አገባሽ " የሚለው ስሜት አልነበረባቸውም ። "ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ "የሚል ማኅተም አሠርተው በበኩላቸው የአስተዳደር የቅርብ ረዳት ሲሆኑ ፣"የኢትዮጵያ ብርሃን እኔ ነኝ እንጂ አንቺ አይደለሽም " የሚል የዝና ሽሚያ በመንፈሳቸው አላሳደሩም ።

እ. ኤ. አ. በ1900 ዓ. ም. በሙሴ አልፍሬድ ኢልግ አማካይነት ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ተጠርቶ የመጣው ሙሴ ሔግ ለሩ የሚባለው የፈረንሳይ ተወላጅ ወደ አዲስ አበባ ከመጣ ወዲህ እስከ ወለጋ ዘልቆ የደጄሳን ወንዝና የአባይን ዳር ዳሩን ተመልክቷል ።



ከዚያም ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሰ በምኒልክ ፊት ፣ "የደረሱባቸውን የወረዳዎች የወንዞችና የተራራዎች ካርታ በፊታቸው ዘርግቼ አብረን ስንመለካከት የጋራዲቢን ትልቁን ተራራ የምኒልክ ተራራ ብዬ ልሠይመው ነው" ብዬ ባመለከታቸው ፣ "የለም አይሆንም ፣ በግዛቴ በኔ የተሠየመ ሌላ ተራራ አለና ይኸኛውን ሥያሜ ለግርማዊት እቴጌ ጣይቱ አድርገው " የሚል መልስ ሰጡኝ ሲል ወዳገሩ ሲመለስ ባወጣው መጽሐፍ አሰፍሮታል ።[1]

በእውነትም በዚሁ መጽሐፉ በመጨረሻው ገጽ 446 ተጥሎ በቁጥር 2 ባዘጋጀው ካርታ ላይ የጣይቱ ጋራ ዲቢ ብሎ ያመለከተው ይነበባል ። ከውጭ አገር የመጡ ዜጐችም ገጸ በረከት ለራሳቸው ሲያቀርቡላቸው ይኸኛው ለእቴጌ ይሁን ያሉበት ጊዜ እንደነበረ ባለፈው አመልክተናል ።

ይኸን የመሰለው ከቅናትና ከምቀኝነት የራቀ አሳበ ሰፊነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ፣ መኳንንትና መሳፍንት ባንድ የሥልጣን ዘንግ አቁሞ የአውሮፓን ኃያል መንግሥት በዓድዋ ላይ ድል ሊመታ ቻለ ። አሁንም በሚቀጥለው ምዕራፍ ተዘርዝሮ የሚገኘውን የሥልጣኔ የሥራ ዘርፍ ለመዘርጋት ሲነሡ ያለተቃውሞ በቤተ መንግሥትም ፣ በቤተ ክህነትም በኩል ሊያስተባብር የቻለው ይኸው የማይናወጥ ከምቀኝነትና ከተንኮል የራቀው ዝንባሌያቸው መሆኑ አይጠረጠርም ።

1 Menelik et nous H. Le Rou, P. 420



ዐፄ ምኒልክ በመካከለኛ ዘመን ዕድሜያቸው

ለቱር ዲሞንድ



ምኒልክ በቢሾፍቱ ሐይቅ ዳር የዲናሚት ፍንዳታ ሲመለከቱ

ሉቱር ዲሞንድ

# ምዕራፍ ስድሳ ስድስት

## ባለሞያ ንጉሠ ነገሥት — ልዩ ልዩ የሥልጣኔ ውጥን

መቸም ሥልጣኔ ባገር ውስጥ ለማስገባት ፣ መሪው ራሱ ለሥልጣኔ ዋጋ የሚሰጥና ራሱም በመጠኑም የዕውቀት ጮራ የፈነጠቀበት መሆን አለበት ። ባጠገባቸው የነበሩት ፈረንጆችም ምኒልክ ጥና የፖለቲካ ሰውና መልካም አስተዳዳሪ መሆናቸውን በገለጡበት ጐን ስለ ሥልጣኔ ፣ ስለ እጅ ጥበብ የነበራቸውን ልዩ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው በመሥራት በተግባር ያሳዩ እንደነበር ይገልጻሉ ።

ሙሴ ሲልቪያን ቪኒራስ የሚባለው የፈረንሳይ ጸሐፊ እ. ኤ. አ. በ1897 ዓ. ም. ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ ወዳገሩ ሲመለስ ባወጣው መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለው አባባል ይገኛል።

> ...ከዚህ ንጉሥ የማይረሳ ማስታወሻ ይዤ ተመልሻለሁ ። ግልጽና ብልህ የሆነ አስተያየት አለው ። ማናቸውንም የእጅ ጥበብና የመካኒክ ሥራ ማየት ማወቅ መረዳት ይፈልጋል ። እንደ አንድ ሰዓት ሠሪ ሰዓቶችን ሁሉ ራሱ ፈታቶ ራሱ መልሶ ይገጣጥማቸዋል ። የጠመንጃ ፣ የመድፍ የመትረየስ የአሠራራቸውና የአጠቃቀማቸው መንገድ በርሱ ዘንድ ምንም ምስጢርነት የላቸውም ። የግንብ ሥራን ከነመሣሪያዎቹ እንደ አንድ የሠራተኞች ባለሙያ መሪ ያውቃል ። ባገራቱ ውስጥ ከርሱ የተሻለ አርኪቴክት (መሐንዲስ) የለም ። የዕውቀት ነገር ከሆነ ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ በዝርዝር ማወቅ ይፈልጋል ።... እርሱ ለማሠራት የደቀናቸውን ሁሉ ዝርዝር ነገሮች ለመግለጽ ለብቻው አንድ መጽሐፍ ያስፈልጋል ። 1”

ሌላው ባጠገባቸው ብዙ ዘመን የቆየው ዶክተር ሜራብ የሚባለው ሐኪም በበኩሉ ስለምኒልክ የዕውቀትና የሥልጣኔ ፍላጐት የጻፈውን ሁሉ እዚህ ላይ ለማስፈር ጊዜና ሥፍራ አይበቃም ። እሱም እንደ ሌሎቹ ምኒልክን እንደ መስኮቡ ትልቁ ጴጥሮስ ፣ እንደ ጀርመኑ ንጉሥ እንደ ትልቁ ፍሬደሪክ ይቆጥራቸዋል ። ስለ ዕውቀታቸው ስለሥራ ወዳድነታቸው ብዙ ሐተታ ከሰጠ በኋላ ፣ “ከሚያስደስታቸው

---

1 Une Mission Francaise en Abyssinie, PP. 177-180.

ከጠበንጃ ፡ ከመድፍና ከመትረየስ ስጦታ በቀር የበለጠ የደስታ ስሜት የሚሰጣቸው ፡ ባገራቸው በኤሌትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀስ ማናቸውም የመካኒክ ሥራ መሆኑን" ካወሳ በኋላ ፡ ዊሊ ሂንዝ ጀርመናዊ ጥበበኛ የብር ገንዘብ አዲስ አበባ እየሠራ በሚያወጣበት ሰዓት ምኒልክ በቀን ሦስት ጊዜ ፡ አልፎ አልፎ አራት አምስት ጊዜ ወደ ፋብሪካው እየተመላለሱ ሥራውን ይቆጣጠሩ እንደነበር ፡ አንዳንድ ጊዜ ራሳቸው ሺስ በማዞር ፡ ሞረድ በመሞረድ ሌላውን ሁሉ እየተዘዋወሩ ብልህ የሆነ እርዳታ ይሰጡ እንደነበረ ገልጾአል ፡፡ ከሞቱም በኋላ ዊሊ ሂንዝን አግኝቶት ፡ "በምኒልክ ሞት ዓለም የተሻለውን መሐንዲስ እንዳጣ መገንዘቡን" እንደ ገለጸለት ያወሳል ፡፡[1]

በእርግጥም ፡ ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፡ የመዠመሪያው ያስተዳደር ዘመናቸው ያተኮረው ፡ ባገሪቱ አራት ማዕዘን እየተዘዋወሩ አገሩ በማሳመን ፡ ጸጥታ በማስጠበቅ ፡ ከማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ያፈነገጡትን አውራጃዎች በመሰብሰብ ፡ ከኢጣልያ ጋር ያለውን የጦርነት ውዝግብ በድል አድራጊነት እልባት ከመስጠቱ ላይ ነበር ፡፡ በዚህ ወቅት የልማት ሥራ ለማስፈጸም ጊዜውና ሁኔታው አላመቻቸውም ፡፡ አበከረው ወደ ሥልጣኔና ወደ ልማት ያተኮሩት ከዓድዋ ድል በኋላ ነው ፡፡

ከዚያ በፊት ከአክሱም መንግሥት የገናንነት ውድቀት ወዲህ (ከ10ኛ መቶ ዓመት) በኢትዮጵያ የሚሰጠው ትምህርት ፡ በመንፈሳዊ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነበር ፡፡ ይኸንንም የሚከታተለው አብዛኛው ተማሪና አስተማሪ የቤተክህነት ወገን የሆነው ነው ፡፡ የትምህርቱም ደረጃ ከፊደል ዠምሮ በፊደለ ሐዋርያ ፡ በወንጌልና በዳዊት ደገማ አልፎ በቅኔ ፡ በጸዋትወ ዜማ ፡ በብሉይና በሐዲስ ፡ በሊቃውንትና በመጻሕፍት መነኮሳት ወዘተ . . . ይደመደማል ፡፡

ይኸንንም የቤተ ክህነት ሰዎች ሲማሩና ሲያስተምሩ ፡ እንደ ውጭ አገር መምህራን በወንበር ተቀምጠው ሒሳብና ጽሕፈት ዠምግራፊ ሳይጨመር መምህሩ ከመደብ ላይ፥ ተማሪዎቹ በመሬት ላይ ሆነው ከቃል ወደ ቃል እየተላለፈ ነው ፡፡ ትምህርቱን አልፎ አልፎ የነገሥታት ልጆች በብርቅ ይከታተሉታል ፡፡ ብዙዎች በአስተዳደር መስክ የተሠማሩ አገረ ገዥዎች ፡ ዳኞች ፡ ያግርኛውን ጽሑፍ የማያነቡም የማይጽፉም ነበሩ ፡፡

1 Impression D'Ethiopie; L'Abyssinie sous Menelik II. Dr. Merab Tome II. PP.55-57.



የሃይማኖትን ለውጥ ያስከትላል በሚሉ ሥጋት ዓለም የሠለጠነበትን ወይም ለመሠልጠን የሚሻማውን ዘመናዊውን የፍልስፍና ፡ የሳይንስ ፡ የእርሻ ፡ የመሐንዲስነት ፡ የሕክምና ትምህርት ከእጅ ጥበብ ከኢንዱስትሪው ጋር ኢትዮጵያውያን ሲሸሹት ስለኖሩ ፡ እስከ ዐፄ ምኒልክ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ ለአውሮፓ ሥልጣኔ በሯን ዘግታ ኖረች ፡፡ በዚህ ምክንያት በሕግ ዕውቀት የተመረቀ ኢትዮጵያዊ ከመጥፋቱ፥ የተነሣ የውጫሌ ውል በተደረገበት ሰዓት 17ኛው አንቀጽ በትርጉም የሚያስከትለውን መዘዝ አጢኖ ከመዠመሪያው ላይ ያስጠነቀቀ ያለ አይመስልም ፡፡ ከኢጣልያ መንግሥት ስለ ተበደሩት ገንዘብ ጉዳይ ወደ ሚሊዮን የሒሳብ ቁጥር ወደ ስብርባሪ ቅናሽ እየገባ ይኸንኑ ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር ራስ መኰንን ሲጻጻፉ ፡ "የዚህን ሒሳብ አቆጣጠር አለመድነውም" ሲሉ የጻፉትን ማስታወስ ይበቃል ፡፡

ስለዚህ ዐፄ ምኒልክ ከምድር ባቡሩ ፡ ከመንገዱና ከስልኩ መገናኛ ማስገባት ወዲህ አሳባቸው በፍጹም ወደ አውሮፓ ትምህርት አዘነበለ ፡፡ ያለዚህም ምንም ዐይነት የተሻለ አኗኗርና አስተዳደር እንደማይገኝ ባለፈው ጊዜ ካፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዠምሮ በብዙ መንገድ ተረድተውታል ፡፡ ከመዠመሪያ የነጋሢነት ዘመናቸው ላይ ቢወጥኑት በተቃዋሚ ብዛት ውጥኑ እንደሚበላሽ ስለ ተረዱት ፡ ቸል ያሉትን ከዓድዋው ጦርነት ወዲህ ከምርኮኞቹም ፡ ለርዳታ ከመጡት ከመስኮቦቹም ጋር አብሮ በመኖር በማየትና በመስማት የቤተ ክህነቱም ፡ የቤተ መንግሥቱም ባለሥልጣኖች ስለ ሥልጣኔ ያላቸው የተቃውሞ አስተያየት ላላ እያለ ሔዷል ፡፡

ቢሆንም ፡ የካቶሊክ እምነት ካላቸው ከፈረንሳዮቹ ወይም ዐረማርያም ከሚባሉት ከእንግሊዞች መምህራንን በመፈለግ ባገር ውስጥ ጠብ እንኳን ቢቀር ቅሬታና ማጉረምረም እንዳይፈጠር ሲሉ የተዋሕዶ ሃይማኖት ከመነጨበት ፡ ጳጳስ ከሚመጣበት ከእስክንድርያ (ከግብፅ) አገር መምህራንን በገንዘብ ቀጥረው ማስመጣትን መረጡ ፡፡ ለመምህራኑም የበላይ ሹም የአቡነ ማቴዎስ የቅርብ ዘመድ የሆኑትን ፕሮፌሰር ሐና ቢይ ሳሊም የሚባሉትን በመሾም ዛሬ በስማቸው የሚጠራውን የዳግማዊ ምኒልክን ትምህርት ቤት በ1900 ዓ.ም. አቋቁመው የመሳፍንትም ፡ የመኳንንትም ፡ የደሃ ልጆችም ቁጥራቸው እስከ 150 የሚደርስ ወጣቶች ተደባልቀው ይማሩ ገቡ ፡፡ ለሌላው ምሳሌ ለመሆን ሲሉ ላሊጋ ወራሽነት ያጨዋቸውን የልጅ ልጃቸውን ኢያሱንም አስገቡ ፡፡[1]

1 L' Ethiopie tell e qu'ell itait en Septembre ,1935, A.Zervos,P.223.

የዚህን ጉዳይ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ዝርዝር ሁኔታ ሳያቀርቡልን ባጭሩ እንደዚህ ብለው አልፈውታል ። “ . . . አስተማሪዎችም ከእስክንድርያ በደሞዝ አስመጥተው የተማሪ ቤት አሠርተው የመኳንንቱ ልጅ ሁሉ ያውሮፓ ቋንቋ ትምህርት ዠመረ ።”[1]

ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመ በኋላ ፤ የቤተሰብ አባት የሆነው ሁሉ ልጁን እንዲያስተምር ፤ ሳያስተምር ቢቀር እንደሚቀጣ ንጉሠ ነገሥቱ በዐዋጅ ያስጠነቀቁት ፣ ስለ ትምህርት መስፋፋት ያላቸውን የጋለ ምኞት ይገልጻል ። በ1898 ዓ.ም. ያወጁት ዐዋጅ እንደዚህ የሚል ነው ።

ሞዓ አንበሳ . . . .

እስካሁን ማንም የእጅ ሥራ ዐዋቂ የነበረ ሰው በውርደት ስም ይጠራ ነበር ። ስለዚህ ማንም ሰው ለመማርና ለመሠልጠን የሚደክም አል ነበረም ። በዚህ ጉጂ በሆነ ሁኔታ ብንኖር ቤተክርስቲያኖች ይዘጋሉ። ይልቁንም ክርስቲያንነት አይገኝም ። በሌሎች ሀገሮች እያንዳንዱን ነገር ብቻ መማር ሳይሆን አዲስ ነገሮችም ይሠራሉ ። ስለዚህ ከዛሬ ዠምሮ ለወደፊት ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ሁሉ ከስድስት ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን ። ልጆቻቸውን ለማስተማር ለማይተጉ ቤተሰቦች ወላጆቻቸው ሲሞቱ ንብረታቸው ለልጆቻቸው መሆኑ ቀርቶ ለመንግሥት ይተላለፋል ። ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን የሚያዘጋጀው መንግሥት ነው ።[2]

ከትምህርቱ ጐን ዐፄ ምኒልክ ሌላው ያሰቡበት ጉዳይ የሕክምናው ነው ። በስማቸው የሚጠራው የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሕንፃ ከመሠራቱ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ የራሳቸውንም ፣ የጠላታቸውንም ቁስል የሚያድኑበት በየዘመቻው አብሮ የሚዞር እንደ ዮድ ፣ እንደ ዶፈርና እንደ ታብሌት ያሉ መድኃኒቶች መኖራቸው ቢታወቅም ፤ በኢትዮጵያ ሕሙማን የሚታከሙበት ምንም ዐይነት የመንግሥት ሐኪም ቤት አልነበረም ። ነገር ግን ፣ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ለእርዳታ በመጡት የመስኮብ ሐኪሞች አማካይነት በንጉሠ ነገሥቱ አንቃቂነት ዛሬ ከቀድሞው ተሻሽሎ አገልግሎት ከመስጠት ላይ የሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተቋቋመ ።

በፍርድ ረገድ ፤ ቀድሞ ከያለበት የሚመጣውን አቤት ባይ ፣ ፍርድ ሰሚ አንድ አፈንጉሥ ብቻ ሆኖ ነገረተኛ ሁሉ መቸገሩን ተመልክተው ፤ ኢትዮጵያን ከስድስት አውራጃ ላይ ከፍለው ላንዱ ክፍል ሁለት ወንበሮች (ዳኞች) በመሾም የነገረተኛን ጉዳይ ለማቅለል ሞክረዋል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 336

2 ዝክረ ነገር — ገጽ 600



ቀድሞ ወታደር በየባላገሩ እየተመራ በንብረቱ ብቻ ሳይሆን በሚስቱ ላይ ሳይቀር ይፈጽም የነበረው ግፍና በደል እንዲታገድ ሲሉ እያንዳንዱ ባላገር በምርት ከሚያገኘው እህል ከዐሥር አንዱን ብቻ እየከፈለ በጐተራ እንዲያስቀምጥና ወታደር ከጐተራው ቀለቡን እንደ ደረጃው እየተቀበለ ራሱ አብስሎ እንዲመገብ “የዐሥራት ዐዋጅ” ብለው ያወጡትና ባላገሩን ከውርደትና በወታደር ከመጠቃት ያዳኑት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ።[1]

እንደዚሁም እስከዚህ ዘመን ድረስ ሕዝቡ ሸቀጥ በሸቀጥ ግማሹም በአሞሌ ጨው በጥይት ከመገበያየቱ በቀር ለከፍተኛ ዋጋ የሚጠቀመው በመካከለኛው ምሥራቅ በ1780 ዓ.ም. አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ በገባው የአውስትሪያዋ ንግሥት የማሪያ ቴሬዛ መልክ ባለበት ብር ነበር ። በዚህም ጸጸት ተሰምቶአቸው ከፈረንሳይ ኩባንያ ጋር ተዋውለው እ. ኤ. አ. በ1894 ዓ. ም. 20,000 ብር በመልካቸው ብር ከነሽርፍራፊው አሳትመው በርሱ መገበያየት ተዠመረ ።

ባንድ ጊዜ በመዠመሪያ የታተመው አንድ ብር ፣ የብር አላድ (አጋማሽ) የብር ሩብ ፤ የብር ስምንተኛ (መሐለቅ) እንደዚህም የብር ሐያኛና ግማሽ ግራም የሚመዝንና የዚህ ዐሥራ አራተኛ ቤሳዎች ታትመው ከገበያ ላይ ዋሉ ። የብሩ ክብደት 28 ግራም ከ0.75 ግራም ሲሆን ፣ ባንድ ወገኑ “ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ 1889 (በኢትዮጵያ አኃዝ)” የሚል ጽሑፍና የራሳቸው ዘውድ የደፉ ሥዕል ሲታይ ፣ በግልባጩ ዘውድ የደፋና በቀኝ እጁ ባንዲራ ያለበት ባለመስቀል ሰንደቅ የጨበጠ አንበሳ ሆኖ በዙሪያው ፤ “ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ አንድ ብር” የሚል ጽሑፍ ይነበባል ። ከዚያም ወዲህ በፓሪስ ቁጥሩ በርከት ያለ ብር ከነቅንስናሹታትሞ ባገር ውስጥ ገባ ።

ይኸንን አዲስ ገንዘብ ሕጋዊ መገበያያ እንዲሆን እንደዚህ የሚል ዐዋጅ ዐወጁ ።

ሞዓ . . . ከዚህ ቀደም ነጋዴም ወታደርም ባላገርም የሆንክ ሰው ሁሉ በየገበያውና በየመንገዱ በየሥፍራው ሁሉ በጥይት ስትገበያይ ትኖር ነበር ። አሁን ግን በኔ መልክና ስም የተሠራ ብር ፣ አላድ ፤ ሩብ፣ ተሙን መሐለቅ አድርጌልሃለሁና በዚህ ተገበያይ እንጂ እንግዲህ በጥይት መገበያየት ይቅር ብያለሁ . . . ይኸንንም ዐዋጅ አፍርሶ ጥይት ርስ በርሱ ሲሻሻጥና ሲገዛዛ የተገኘ ሰው . . . ባንዳንድ ጥይት አንዳንድ ብር ይከፈል . . . ኅዳር 22 ቀን 1901 ዓ. ም. እንጦጦ ከተማ ።

2 ዝክረ ነገር ... 2ኛ እትም ፤ 1962 ዓ ም ፤ ገጽ 198

ዐዋጁ ቢታወጅም ፥ ቢበተንም ከመቶ ዓመት በፊት ዠምሮ ባገር ውስጥና በአካባቢው ሥር ሰዶ የቆየውን የማሪያ ቴሬዛን ብር ፈጽሞ ሳይደመስሰው እስከ ጊዜያችን መድረሱን እናስታውሳለን ።

ከዚህም ጋር ከ1878 ዓ.ም. ዠምሮ ከእንጦጦ ወርደው ከእቴጌ ጣይቱና ከመኳንንቶቻቸው ጋር ያዳመቁት የአዲስ አበባ ከተማ ከዕለት ወደዕለት እያማረበት ሔደ ። ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ የሚቀመጡበት ቤተ መንግሥት ፤ አንድ ያማረ እልፍኝ ፥ ሠራዊቱን ግብር የሚያበሉበት ሰፊና ታላቁ አዳራሽ ፥ የእንግዳ መቀበያው ፥ የኪዳነ ምሕረትና የገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎች ፥ የጠላና የጠጅ ቤቱ ፥ የእንጀራና የሥጋ ቤቱ እየተለየ ተሠራ ። እንደዚሁም በቤተ መንግሥቱ ራቅ ባለው አካባቢ በጉለሌ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፤ ከእንጦጦ በታች ራስ ዳርጌ ፥ በጊሚራ ሠፈር እነራስ ሚካኤል ፥ ከዚያም እነራስ መኰንን ዙሪያውን እነንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ፥ እነራስ መንገሻ አቲከም ፤ እነራስ አባተ ፥ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ . . .በየስማቸው ልዩ ልዩ ያማረ ቤት ሠሩ ። ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆነው የእንግሊዝ ፥ የመስኮብ ፥ የፈረንሳይ ፥ የኢጣልያና የጀርመን ሌጋሲዮኖች ተቋቋሙ ። በቤተ መንግሥቱ ለመዠመሪያ ጊዜ የኤሌትሪክ መብራት ሲያንጸባርቅ ፤ ወሃ ከእንጦጦ በቧምቧ መጥቶ ሲንፏፏ ፥ እቴጌ ጣይቱ ለእንግዳ ማሳረፊያ ሆቴል ሲከፍቱ ያውሬ መፈንጫ የነበረችው አዲስ አበባ በርግጥ ያንድ ሥልጣኔ የገፋ መንግሥት መዲናነቷን እያረጋገጠች ሔደች ።

ባስተዳደር በኩል በተለያየ መልክና ሥያሜ ባለሥልጣኖች በየክፍሉ ከጥንት ዠምሮ መኖራቸው የተረጋገጠ ነው ። ዐፄ ምኒልክ የሠለጠኑት የአውሮፓ አገሮች አስተዳደር ባገራቸው እንዲገባ ስለፈለጉ ፣ ሀሥራሁለት ቢሮዎችን በዘመናዊ እቅድ በቅድሚያ አሠርተው ከጨረሱ በኋላ፥እላይ የተወጠነው የአስተዳደርና የልማት ሥራ በደንብ እንዲካሔድ ለጊዜው ከዚህ የሚከተሉትን ዘጠኝ ሚኒስትሮች ሾሙ ። 1 አፈ ንጉሥ ነሲቡ የፍርድ ፥ 2 ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ የጦር ፥ 3 ሊቀመኳስ ከተማ ያገር ግዛት ፥ 4 ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ የንግድና የውጭ ጉዳይ ፥ 5 በጅሮንድ ሙሉጌታ የገንዘብ ፥ 6 ከንቲባ ወልደ ጻድቅ የእርሻ ፥ 7 ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጽሕፈት ፥ 8 ቀኛዝማች መኰንን ተወንድ በላይ የሥራ ፥ 9 አፃኸ መታፈሪያ የግቢ ሚኒስትር ።[1]

1 ዝክረ ነገር ... ከ2ኛ እትም 1962 ዓ. ም. ገጽ 54



ከነዚህም በቀር ሚኒስትር ሳይሾምባቸው ባዋጅ ተቋቁመው በሥራ እስኪያጅ የሚመሩ የስልክና የፖስታ እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር ተመሠረቱ ። እነዚህም በየክፍላቸው የሚተዳደሩበት ሕግና ደንብ እየተጠና በዐዋጅ መልክ ተሰጣቸው ። ከመረብ ባሻገር ካለው ክፍል በስተቀር በአገሪቱ ሰላምና ጸጥታ ሰፈነ ። አገር ለአገር የሚተላለፈው ነጋዴ፡ ቅሚያና ዘረፋ ቀረለት ። ገበሬው ያለምንም ሥጋት ማረስ ቻለ ። የውጭ አገር ጐብኝ ሳይቀር ከአውራጃ ወደ አውራጃ የንጉሠ ነገሥቱን የይለፍ ማኅተም ይዞ ሲተላለፍ ድርጎና መሪ እየተሰጠው እንደልቡ ይዘዋወር ዠመር ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፡ ራሳቸው በበላይ ሥራውን ሁሉ ከመቆጣጠር አልፈው አንዳንድ ጊዜ በየሥፍራው እየተገኙ በሥራው በመካፈል የእጅ ሠራተኛውን ሁሉ ስለ አነቃቁት ለግብርና ፥ ለንግድ ፥ ላስተዳደር ፥ ለመንግሥትም ፥ ለግልም የሚያገለግለው የመሣሪያ ምርት እየበረከተ ሔደ ። ቀድሞ የእጅ ሠራተኛነት ያስንቅና ያሰድብ የነበረውን ለማስቀረት ሲሉ ፥ ላሠሪዎቹ አለቆች የማዕረግ ስም ከመስጠትና ከመሸለም ጋር ሠራተኛንና ሥራውን ለማስከበር ሲሉ ቀጥሎ ያለውን ዐዋጅ ዐወጁ ።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ን.ነ. ዘኢት . . . . ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ተወኝ ። ከዚህ ቀደም ብረት ቢሠራ ጠይብ ፥ ሸማ ቢሠራ ሸማኔ ፥ ቢጽፍ ጠንቋይ ፥ ቤተ ክርስቲያን ቢያገለግል ደብተራ እያላችሁ አርሶ ነጪን ከጥቁር (ጤፍና ሌላ ዘር) አምርቶ የሚያገባውን አራሽ ክዘውድ (ከባለ ዘውድ) ይበልጣል የሚባለውን ገበሬ እያላችሁ ነጋዴን ነግዶ ወርቁን ግምጃውን ይዞ ሲገባ አንተ ነጋዴ ገጣባ (የአህያ የበቅሎ የፈረስ) አጣቢ እያላችሁ በየሥራው ሁሉ ትሰድባላችሁ ። እጁ ምናምን ሥራ የማያውቀው ሰነፉ ብልሁን እየተሳደበ አስቸገረ ። ቀድሞም ይህ ሁሉ ፍጥረት የተገኘው ካዳምና ከሔዋን ነው እንጂ ሁለተኛ ፍጥረት የለም ። ይኸ ሁሉ ካለመማር የተነሣ ነው ። አዳምንም ብላዕ በአፈ (በሐፈ) ገጽከ (በድካምህ ወዝ ብላ) ብሎታል ። ይህ ከቀረ ሁሉ ባዘንተኛ (ሥራ ፈት) ከሆነ መንግሥት የለ ፤ አገር የለ ፤ በወዲያ አገር ግን ፤ ባውሮፓ ሁሉ አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ ነፍጥ (ጠበንጃ) ባቡር ቢሠራ . . . መሐንዲስ እየተባለ ፡ እየተመሰገነ ሠራተኛውም ብዙ (ቀለብ) ይጨምርለታል እንጂ በሥራው አይሰደብበትም ። እናንተ ግን ፤ እንዲህ እየተሳደባችሁ ማረሻ የሚያሾል አሳጥታችሁ አገሬን ባዶ ልታደርጓትና ልታጠፏት ነው ። እንግዲህ ግን (ለወደፊቱ) እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው እንጂ ሌላውን መስደብ አይደለም ። ዳግመኛ ግን ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንዳንድ ዓመት ይታሰራል ። ሹማምንትም አስረህ ለማስቀመጥ የሚቸግርህ እንደሆነ አስረህ (ከአውራጃ) ወደኔ ስደድልኝ ። ጥር 17 ቀን 1900 ዓ.ም. ።

ይህ ፀዋጅ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ አገራቸውን አውሮፓ ወደ ደረሰበት የልማት ደረጃ ለማድረስ ሠራተኛ ፡ ሥራና የሥራ መሣሪያ መፍትሔ መሆናቸው በትክክል እንደ ገባቸው ስለሚያስረዳ ፡ ብዙም ሐተታ መስጠት አያስፈልግም ። ንጉሠ ነገሥቱ አገራቸውን ለማሠልጠን ፡ ላገራቸው ሕዝብ ልማትን በማልማት ሰላምና ጸጥታን ከተሻለ ሕይወት ጋር ለማውረስ ብዙ እንደጣሩ እንረዳለን ።



# ምዕራፍ ስድሳ ሰባት

## የመገናኛ መስመር ፡ የምድር ባቡር ፡ የመንገድና የስልክ መዘርጋት —የአቶሞቢል መታየት

የአውሮፓና የአሜሪካ ዓለም ፡ ከምድር ባቡርና ከአቶሞቢል በፊት በፈረስና በበቅሎ በሚሳብ ሠረገላ ሲጠቀሙ ፡ በኢትዮጵያ የቅርቡንም የሩቁንም መንገድ ፡ ተራው ሰው በእግር ፡ ከሹም ገምሮ እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ድረስ በፈረስና በበቅሎ ዠርባ ተቀምጠው ይጓዙ ነበር ። የሚፈረስ ለጉግስና ለጦርነት ጊዜ ሲመረጥ ፡ በተለይ ለዘወትር ጉዞ የሚመረጠው በቅሎ ነው ። የበቅሎውም ፀይነት እንደ ተቀማጩ ደረጃ ፡ የሚጫነው የበቅሎ ዕቃ ደረጃው ልዩነት አለው ። ከሁሉ የበለጠ ሰጋር በቅሎ ይመረጣል ።

በዚህ ፀይነት ፡ ፀፄ ቴዎድሮስ ከደምቢያና ከጐንደር የኢትዮጵያን የተበታተነውን አውራጃ በአንድነት ለመሰብሰብ ወደ ጐጃም ፡ ወደ ሰሜን ፡ ወደ ላስታ ፡ ወደ ወሎና ወደ ሸዋ በተደጋጋሚ የተመላለሱት ዳገት ቁልቁለቱን በእግር ፡ ሜዳውን በበቅሎ ዠርባ ነው ። ፀፄ ዮሐንስም የቴዎድሮስን መርሕ ተከትለው ይኸንኑ አንድነት ለማጠንከር ከመቀሌ ወደ ቤገምድር ፡ ወደ ጐጃም ወደ ወሎ ፡ ወደ ደብረ ታቦርና ወደ ሸዋ በበቅሎ ተመላልሰዋል ። ከመቀሌ ወደ ሰሐጢ ጣልያንን ለመውጋት ፡ ከሰሐጢ ተመልሰው ወደ ጐጃም ፡ ከጐጃም ወደ መተማ የዘመቱትም በበቅሎ ነው ። ፀፄ ምኒልክም ከአንኮበር ወደ እንጦጦ ፡ ከእንጦጦ ወደ አሩሲ ፡ ወደ ሐረር ከዚያም ወደ ወሎና ወደ ቤጌምድር ፡ ከቤጌምድር በጐጃም በኩል ወደ ሸዋ ፡ በወሎ ፡ በአላጌና በመቀሌ በኩል ለጦርነት ወደ ዓድዋ የዘመቱትና ከድሉም በኋላ በትግራይ ወዲያና ወዲህ ተዘዋውረው በወሎ በኩል አዲስ አበባ የተመለሱት በክብት ዠርባ ላይ ነው ። በየዕለቱ በከብት ዠርባ ላይ መጓዝ የቱን ያህል አድካሚ መሆኑን ሁኔታውን የሚያውቀው ይገነዘበዋል ፡ በሰውነት ላይ ያለው የሁልጊዜ ንቅናቄና የጭንና የባቱ መደንዘዝና መዛል ፡ ካለንበት ዘመን አንጻር ሲመለከቱት አድካሚና አሰልቺ ነው።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፡ ምኒልክ ከርሳቸውና ከሕዝባቸው በአኗኗር የሚሻሉት አውሮፓዎች በሌላውና በዚህ በጉዞ ረገድ ያላቸውን ያናፏርና የጉዞ ዘዬ ከወዳጆቻቸው ከአውሮፓ ተወላጆች ከነሙሲ ላጋርድና በተለይ ከቅርብ የወዳጅ አገልጋያቸው ከአልፍሬድ ኢልግ ዘወትር ወሬውን በመስማት ማጥናታቸው አልቀረም ።

አልፍሬድ ኢልግ ፣ በስዊስ አገር ተወልዶ በማደግ በመሐንዲስነት ከተመረቀ ወዲህ እ. ኤ. አ. በ1878 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከንጉሥ ምኒልክ ተገናኝቶ የቅርብ ረዳት ሆኖ ያገለግል ገመር ። በዚያን ሰዓት ወደ ንጉሡ ቀረብ ካሉት ኢጣሊያኖች ከነአንቶኔሊ ፡ ከነኪያሪኒ ፡ ከፈረንሳዮች ከነሪምቦና ከነሸፍነ ጋር ወዳጅነት ያዘ ። ፡ ላዔ ምኒልክም እያደር የቅርብ ባለሟል በመሆን እንግዳ አስገቢ ፣ ዕቃና የጦር መሣሪያ አስመጭ ሆነ ። የኢጣልያኖች አጥቂነት እየበረከተ ሲሔድ ፡ ለምኒልክ ታማኝነቱን እያጸና የኢጣልያኖች ባላንጣ ከሆኑት ፈረንሳዮች ከነሽፍነ ፡ ከነሞንዶን ጋር እየተባበረ በታማኝነት ላዔ ምኒልክ አገልግሎቱን በመቀጠል በመጨረሻ የመንግሥት ዋና አማካሪ እስከ መባል ደረሰ ።

ስለዚህ ፣ ከዓድዋ ጦርነት በፊት ዐፄ ምኒልክ የአውሮፓን ሥልጣኔ ባገራቸው ለማስገባት ከተነሣሡባቸው ዘርፎች አንዱ የዚህኑ የጉዞ ድካም የማሻሻሉ ጉዳይ ስለ ሆነ ፣ በአውሮፓ የሐዲድና የባቡር መስመር በመሐንዲሶቹ በነቪቪያን ከተገኘበት ከ1823 ዓ.ም. ዠምሮ ሲሠራበት እንደቆየ ፣ እንደዚህም ዐፄ ምኒልክ ለዓድዋ ጦርነት ሁለት ዓመት ሲቀር ለዚሁ ፣ ለወዳጅ አገልጋያቸው ለአልፍሬድ ኢልግ ከጅቡቲ እስከ ሐረር ፣ ከሐረር እስከ እንጦጦ ፣ ከእንጦጦ እስከ ከፋ ፡ ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ የሐዲድ መንገድ እንዲዘረጋ መጋቢት 1 ቀን 1886 ዓ.ም. በተፈረመ ውል ፈቀዱለት ። በዚህ ውል ውስጥ ከ1 እስከ 3 አንቀጽ መስመሮቹ የሚዘረጉባቸውንና የውሉ ጊዜ የሚቆየው እስከ 99 ዓመት መሆኑን ፡ አራተኛው አንቀጽ እስከ ሁለት ዓመት ሥራው ያልተዠመረ እንደሆነ ውሉ እንደሚፈርስ ፤ አምስተኛው አስገዳጅ ነገር ካልመጣ በቀር የባቡሩ አካሔድ በምንም ዐይነት እንደማይቆም ፤ ስድስተኛው ኩባንያው የቴሌግራፍ ሥራ እንዲያቋቁም በዚህም የቴሌግራፍ መስመር የመንግሥት መልእክት በነጻ እንዲተላለፍ ፤ በሰባተኛውና በስምንተኛው አንቀጽ ያለ ኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ኩባንያው የማንኛም ወታደርና የጦር መሣሪያ ወዳገር ማስገባትም ፣ ካገር ማስወጣትም እንደማይችል ፣ በሰላሙ ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮችና የጦር መሣሪያ ሁለቱ ወገኖች በተስማሙበት ዋጋ እንደሚመላለሱ ፡ በጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደርና



የጦር መሣሪያ በነጻ እንደሚመላለስበት ያረጋግጣል ። በዘጠነኛውና በዐሥረኛው አንቀጽ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ኩባንያው ስለሚያገኙት የቀረጥ ጥቅም ፣ በዐሥራ አንደኛውና በዐሥራ ሁለተኛው አንቀጽ የኢትዮጵያ መንግሥት ኩባንያው ለሚዘረጋው መስመር አስፈላጊ የሆነውን ቦታ በግራና በቀኝ ከነ ዕንጨቱ ከነደንጊያው እንደሚሰጥና መስመሩንም እንደሚያስጠብቅ ፣ በዐሥራ ሦስተኛው አንቀጽ ኩባንያው ለሐዲዱ ሥራ የሚያስመጣው ማናቸውም ዕቃ ከቀረጥ ነጻ ስለመሆኑ ፤ ዐሥራ አራተኛው የውሉ ጊዜ (99 ዓመት) ሲያልቅ ፡ ኩባንያው የባቡሩን መስመር የሚያንቀሳቅሰውን መሣሪያ ጭምር ለኢትዮጵያ መንግሥት በነጻ አስረክቦ እንደሚለቅ ፤ በዐሥራ አምስተኛው አንቀጽ ለዚህ ፈቃድ 10,000 ብር ንጉሠ ነገሥቱ ከኩባንያው እንደሚቀበሉ ሆኖ ፡ በጥሬው ገንዘብ ፈንታ የባለአክሲዮንነት መብት የጽሑፍ ሰነድ እንደሚቀበሉ ያረጋግጣል ።

ይኸንኑ ውል በመጋቢት 1 ቀን 1886 ዓ.ም. ከአልፍሬድ ኢልግ ጋር አድርገው እንደቆዩ ፣ ኢልግ ገንዘብ ስላጣ የፈረንሳይን መንግሥት በምትኩ አስገባ ። በጥር 21 ቀን 1900 ዓ.ም. የቀድሞውን ውል የሚያሻሽል በ18 አንቀጾች የተከፈለ ውል የባቡሩን ሥራ ኃላፊነት ከፈረንሳይ መንግሥት ከተቀበለው ከዶክተር ቢታሊያ ጋር ተዋዋሉ ። ምንም እንኳ በሰፊ ምኞት ለስሙ የሐዲዱ መስመር ከጅቡቲ እስከ ሐረር ፣ ከሐረር እስከ እንጦጦ ፡ ከእንጦጦ እስከ ከፋ ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ መሆኑ ቢጠቀስም ፣ አልተሠራም ። ምክንያቱም በዚህ ረጅም መስመር የሐዲድ ሥራ መሥሪያና ማስፈጸሚያ በቂ ገንዘብ በመታጣቱ ይመስላል ። በቅድሚያ እስከ ድሬድዋ ድረስ በመጨረሻም ዛሬ እንደሚታየው ፡ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ብቻ ተፈጽሞ መሥራት ዠመረ ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ የአውሮፓን የሰውና የሸቀጥ ማመላለሻ ዘዬ ባገራቸው ለማስገባት ይኸን የምድር ባቡር ውል ከተዋዋሉ ወዲህ የሐዲዱ መስመር ላገር ያተረፈው ጥቅም ግምቱ በብዙ አንጻር ብዙ ነው ። መስመሩ የሚያልፍባቸው ጣቢያዎች ቀድሞ ደሳሳ የሣር ክዳን ቤቶች የነበሩባቸው ወይም የከብት መዋያ ፡ ያውሬ መፈንጫ የነበሩት ከአቃቂ እስከ ደወሌ ድረስ የሚገኙት እነሞጆ ፡ እነቢሾፍቱ ፣ እነናዝሬት እነወልንጪቲ ፣ እነ ድሬዳዋ . . . የደመቁ ከተሞች ለመሆን በቁ ።

ከሐዲድ መስመር ውጭ ባገሪቱ ከተሞች የሚገናኙበት ፡ የመንግሥት ሠራተኛ ፡ ወታደር ፡ ነጋዴና ባላገር እንደልቡ የሚዘዋወርበት ጥርጊያ መንገድና ድልድዮች በያለበት እንዲሠሩ ፡ በዚህ ዘመን ጥረት መደረጉን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እንደዚህ ሲሉ አሥፍረውት ይገኛል ።

> ...የድልድይም ሥራ ከዚህ ቀደም በሀገራችን በሸዋ አይታወቅም ነበር ። በርስትና በጉልት በከብት የተጣላ ሰው ሁሉ በጋውን እወም በሮች (ዳኞች) ላይ ሲነጋገር ይባጃል (ይቆያል) ክረምት ሲገባ ግን ፡ ውሀ እንዳይወስደው ከሐምሌ አቦ(ሐምሌ 5 ቀን) ወዲያ እመስከረም አቦ (መስከረም 5 ቀን) ድረስ ... ዳኞች እያሰናበቱት በየቤቱ ገብቶ ይከርም ነበር ። በክረምትም ድንገተኛ ነገር ያገኘው ሰው ወደ ዳኛ ሲሔድ ውሀ እየወሰደው በያመቱ ብዙ ድሀ ያልቅ ነበር ። ዐፄ ምኒልክ ግን ፡ ይኸን ሁሉ ተመልክተው ከፈረንጅ አገር በደመወዝ ሠራተኛ አያስመጡ በ1889 ዓ. ም. በያገሩ ፡ በየወንዙ ብዙ ድልድይ አሠሩ ። ያባይም ወንዝ ጥንት በቀድሞ ነገሥታት (በነዓፄ ፋሲል) ተሠርቶ የነበረውን ድልድይ ጠላት አፍርሶት በሰባራው ድልድይ የሚሻገር ሰው አልነበረም ። በዚህ ዘመን ግን ፡ ሠራተኛ ሰደው አባይን ሰባራውን ድልድይ አሳምረው አስበጁት ። በዚህም ድልድይ የሚመላለሰው ሰው ሁሉ የምኒልክን የጣይቱን ዕድሜ ያርዝም ... እያለ እየመረቀ ያልፋል ።[1]

ከአባይ በቀር ጸሐፌ ትእዛዝ በጽሑፋቸው ያልጠቀሷቸውን ድልድዮች ፡ ሙሴ ሞሪስ ደኮፔና ዶክተር ሜራብ ከተጠገነው የአባይ ድልድይ በቀር በአዲስ አበባ ከመካከል አራዳ ተነሥቶ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሌጋሲዮኖች ወዳሉባቸው መንገዶች የተሠሩትን ሦስት ድልድዮች (የራስ መኰንን ፡ የቀበናና የፍቅረ ማርያም) ድልድዮች መሆናቸውን ደብረ ማርቆስንና አዲስ አበባን ለማገናኘት አባይ ላይ የብረት ድልድይ ለማሠራት ታስቦ መሣሪያውም ሚላኖ (ኢጣልያ) ካለው ኩባንያ ታዞ በማጓጓዝ እጦት ሥራው መታጐሉን በጽሑፍ ገልጸውታል ።[2]

በዚህ ዘመን ከተደረጉት የሥልጣኔ ልማቶች መካከል ዋነኛ ሆኖ የሚቆጠረው ፡ የስልክ መስመር የመዘርጋቱ ጉዳይ ነው ። በመልእክት ረገድ ያለውን የከብትና የእግር ጉዞ ችግሩን ባለፈው ባንጠቅሰውም ፡ ማንም አስተዋይ የሚገነዘበው ነው ። የስልኩን አገባብ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፡ "በ1892 ዓመተ ምሕረት ባስልክ

1. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ...ገጽ 333—334
2. Chronique du Regne de Menelik . vol.II PP.525-526.



መነጋገር በኢትዮጵያ ተዠመረ" በማለት ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳይገቡ ጠቅሰውት ያለፉትን በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ሚኒስትር የሆኑት ሙሴ ሞሪስ ደኮፔ በመጠኑ ሲያብራሩ ፡ ከ1897 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) ዠምሮ በሁለት የፈረንሳይ መሐንዲሶች ሐረርን ከአዲስ አበባ የሚያገናኝ መስመር ተዘርግቶ የነበረው ሥራውን መሥራት የዠመረው ከሁለት ዓመት በኋላ በ1899 ዓ.ም. መሆኑን ፡ ከዚያም በተከታታይ አውራጃዎችን ከዋናው ከተማ ከአዲስ አበባ የሚያገናኙ የስልክ መስመሮች መዘርጋታቸውን ፡ ከነዚህም ዋነኛው መስመር አዲስ አበባንና አሥመራን የሚያገናኘው መሆኑን ፡ በመጨረሻም አዲስ አበባ ላይ የስልክ ማዕከልና ቢሮ በ1906 ዓ.ም. በፈረንሳዮች ሥራ አስኪያጅነት መከፈቱን ገልጸዋል ።[1]

ጸሐፌ ትእዛዙ ፡ "ባቡርም ሠረገላም ከፈረንጅ አገር አስመጥተው ካዲስ አበባ እስከ ገነት መመላለስ ተዠመረ" ያሉትንም ፡ የፈረንሳዩ ሚኒስትር ደኮፔ በተለመደ የማብራሪያ ማስታወሻቸው ይህ ባቡር የተባለው ሰርኪስ ተርዚያን የሚባሉት የአርመን ተወላጅ በሐዲድ ላይ ሳይሆን በተሠራ መንገድ ላይ በሎኮሞቲቭ ኃይል ሊሽከረከር የሚችል (እንደ አውቶሞቢል ያለ) መሆኑን ፡ ይኸንንም አስመጭው ሙሴ ሰርኪስ ተርዚያን ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ለማድረስ ብዙ ችግር እንደ ገጠማቸው ገልጸውታል ።[2]

በዚህ የባቡር አቶሞቢል ላይ ፡ ዐፄ ምኒልክ ለሙከራ በላዩ ላይ ተቀምጠው አዲስ በተሠራው ወደ ገነት ፡ ወደ አዲስ ዓለም በሚወስደው መንገድ ላይ ሲጓዙ ለሕይወታቸው የሚሳሱት መኳንንት ከኋላ ኋላ በፈረስ እየጋለቡ ፡ "እረ አቁም ምን ሊያደርጋቸው ነው" እያሉ ይጮሁ ነበር ይባላል ። ዳሩ ግን ፡ ይህም መኪና ትንሽ ጊዜ ከሠራ በኋላ ፡ በመጨረሻ ዛሬ ሰባራ ባቡር ከሚባለው መንገድ ተገትሮ እንደቀረ በዚህም ካንዲት ከዝንጉ ሴት ጠባይ ጋር በማዛመድ ፡

ቢነግሩሽ ፡ ቢነግሩሽ አታጠናቅሪ
እንደ ተርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ ።

ተብሎ ተገጥሟል ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ በዚህ ዐይነት የመንገድና የስልክ ፡ የመገናኛ መስመር በያለበት ሲዘረጉ ፡ ድልድዮች ሲያሠሩ ፡ የቤተ መንግሥታቸውን እልፍኝና አዳራሽ ባዳዲስ ሕንፃ ሲያሳንፁ ፡ ሥልጣኔ ወዳድ

1. Chronique du Regne de Menelik .... PP.484- 485, No. 2.
2. Idem

የሆነው ሁሉ በሥራቸው ተባባሪ ከመሆን ጋር ሥራቸውን ከማድነቅና ከማስደነቅ አልቦዘነም ። ግማሹም የደስታ ስሜቱን በግጥም እንደዚህ እያለ ገልጾላቸዋል ፤

ባቡርም ተጫነ ስልክም ተናገረ
ይኸ በማን ጊዜ ተደርጎ ነበረ
ምኒልክ ነቢይ ነው ሆዴ ጠረጠረ
የሐበሻው ንጉሥ ምኒልክ ነቢይ ነህ
ኃላፊውን ትተህ መጭውን ታውቃለህ ።

እንዳንድ የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት የዋሃን የሆኑት ባለሥልጣኖች የስልኩንም ፥ የመኪናውንም ሥራ የሰይጣን ሥራ ነው እያሉ ያጉረመረሙት እያደር የምኒልክን አያያዝ የተሠራውን ሁሉ የሚሰጠውን ጥቅም በመገምገም ፥ ሌላው ሲያደንቅ የነርሱ ክርፊያ ዋጋ እንደሌለው በመረዳት ፥ በግድም በውድም በመጨረሻ የሥልጣኔው እርምጃ አባሪ ተባባሪ ወደ መሆን አዘነበሉ ።





የዐፄ ምኒልክ አማካሪ እንጂኒዬር አልፍሬድ ኢ.ልግ

ከክሪስፒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ስድሳ ስምንት

## ያፄ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የቅርብ ግንኙነት

ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ያለ ምንም ማንገራገር በቅድሚያ መጥተው ላፄ ምኒልክ እንደ ገቡላቸው፣ ከዚያም የኢጣልያ ጦር በሰሜን ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ የመጨረሻው ጦርነት በዓድዋ በኢትዮጵያ አሸናፊነት በተፈጸመበት ሰዓት ሁለቱ እንደ ታላቅና ታናሽ ወንድማማች እየተመካከሩ ሁሉንም ይሠሩ እንደነበረ በየሰነዱ ላይ ይነበባል ።

ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው፣ ካባታቸው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተጣልተው አዲስ አበባ በነሩበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ እንደ አማላጅ ሆነው፣ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልሰው ለመላክና ከንጉሡ አባታቸው አንዳንድ ጉልት ተቀብለው እዚያው ጐጃም እንዲቀመጡ ባሳሰቡዋቸው ጊዜ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተሰጠው መልስ እንደዚህ የሚል ነበር ።

> "ይድረስ ኃበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ጃንሆይ የልጆቼንም ነገር የላኩብኝ ክቡር ማኅተምዎ ደረሰኝ ። ጃንሆይ፣ ራስ ደጃዝማች አሰኝቼ ያልሆነልኝን ዛሬ ጉልት ሰጥቼ በጥቂት ነገር እደሩ ብል ይሆናል? ትግሬም ዘምተን ሳለ እግዚአብሔር ደህና ቢመልሰን አንግዲህ እሰር እናሰርም ፤ የታሰረውንም እንፈታለን ብለን ብጽዓት(ስለት) አድርገን መነጋገራችን እውነት ነው ።. . . ለራሴ ብፈራ ነው እንጂ. . እኔ ስገዛ፣ ልጆቼ ታስረው ሊቀመጡ ወድጄ ነው?. . . አሁንም አንዱን ወደራስ መኰንን፣ አንዱን ወደ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ሰደው ባልደረባ ሰጥተው ያኖሩዋቸው እንደሆነ ነው እንጂ፣ ከኔ ጋራማ ተፈትተው መቀመጥ እንዴት ይሆናል?. . . ."

በሁለቱም መካከል፣ የሁለቱን ወዳጅነት የሚያጠብቁት፣ ለሁለቱም እንደ ሽማግሌ አባት ተቆጥረው በዚህ ዘመን የሚከበሩት ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ ነበሩ ። በዕድሜ የገፉ ባፄ ዮሐንስም ዘንድ በሁሉም የተከበሩ እንደነበሩ የሚታሰብ ነው ።

በዳኝነትና በፍርድ ረገድ የንጉሠ ነገሥቱና የንጉሡ ግንኙነት በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በፍትሐ ብሔርም ፤ በወንጀልም አንድ ተራ ሰው ወይም መኰንን የተከሰሰ እንደሆነ ራሱ ቀርቦ ፤ በደረጃ ተራምዶ አፈ ንጉሡ ላይ በይግባኝም እንደ ተለመደው ወደንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ይቀርባል ። ሆኖም ይህን ደንብ ጥሰው ከጐጃም አንዳንድ መኳንንት ወይም ተራ ሰዎች ወደ አዲስ አበባ እየመጡ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ ክስና ወቀሳ የሚያቀርቡ አልጠፉም ። ከነዚህም አንዱ ብዙ ዘመን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጠቅላይ የጦር አለቃ የነበሩት ራስ ደረሶ ናቸው ። እርሳቸውም ወደ መጨረሻው ዘመን ስላረጁ ሥልጣናቸው ወደራስ ወርቄ ስለሔደና ከንጉሡ ጋር ስምምነት ስላጡ ፤ በመልእክት ወደንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ልከው ኖሮ ዐፄ ምኒልክም ሁለታችሁም ቀርባችሁ ከኔ ፊት ተነጋገሩ በማለት ፈንታ ጉዳዩን እዚያው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንዲያዩላቸው ጽፈው ነበር ።

ለዚህም መልስ ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለንጉሠ ነገሥቱ በ1889 ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ ላይ ባንደኛው ፤

> "... ጃንሆዬ የራስ ደረሶን ነገር የላኩብኝ ክቡር ማኅተምዎ ደረሰኝ ። እርሱ ዘንድሮ የሚያደርገው ነገር ሁሉ የጤና አይደለም ። ራስ ደረሶ አባቴ ነው እንጂ ሎሌዬ አልነበረም ። እኔ አብሮ የተጠመደ አብሮ ይፈታል ፤ አብሮ የበላ አብሮ ይሞታል ብዬ ፤ እርሱም ያዝንልኛል ፤ እኔም እረዳዋለሁ መስሎኝ ነበር ። እንዲህ እየሆነ አስቸገረኝ ። አሁንስ ጃንሆዬ በምክር ተሆነ ደብረ መዊዕም ዘጌም ቢሆን እሺ ፤ ከወደደው ላይ ይሁን"...

የሚል ይገኛል ። በ1890 ዓ.ም. በጻፉት ላይ ደግሞ ፤ "...ከእግዚአብ አብሔርና ከጃንሆይ የሚሠወር የለም ። እየዋሉ እያደሩ ያገኙታል ። ሰይጣን አገብሮት* ነው እንጂ ፤ ምንም የሆነው ነገር የለም ነበር ። ዛሬም ይኸው ገባ ፤ ከልብ ታረቅን..." ብለው ደምድመዋል ።

ሌላው ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ፤ ማመልከቻም እየላኩ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ያስቸግሩ የነበሩት ፊታውራሪ ውድነህ የሚባሉ ናቸው ። እርሳቸውም ከፈረንጆች ጋር በመኖር ጥበብ የገበዩ መሆናቸው በደብዳቤው ላይ ተጠቅሶ ይነበባል ። እኚህ ሰው በደላቸውን በዝርዝር ላዔ ምኒልክ ቢያቀርቡ ፤ ጥበበኛና የትልቅ ወገንም ቢሆኑ ዐፄ ምኒልክ ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ተከሰሃል ናና መልስ ስጥ ማለት ቀርቶ ፤ እንደዚህ ብሎ ክስ አቅርቧልና ምክንያቱን እንኳ ጻፍልኝ ሳይሉ ክሳሹን የተደፈነ ደብዳቤ አሲይዘው ውድነህን ወደጐጃም

* አስቶት ለማለት ነው ።



መልሰው ላኩዋቸው ። ደብዳቤው የሚለውም እንደዚህ ብኋልና ቻለው ፤ እዚያው አንተ እንደ ዳኝነትህ አድርግለት የሚል መሆኑ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልስ ላይ ያስታውቃል ። በዚህም አያያዝ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ስለዚሁ ስለ ፊታውራሪ ውድነህ ጉዳይ መጋቢት 14 ቀን 1886 ዓ.ም. ላዔ ምኒልክ በጻፉት ደብዳቤ ላይ እንደዚህ ሲሉ መልሰዋል ። "ጃንሆዬ የላኩብኝ የፊታውራሪ ውድነህ ነገር ደረሰኝ ። ሁልጊዜ ይመቹኛልና እግዚአብሔር ያስመችዎ ። ጠላትዎን ዲያብሎስን አስሮ ከጻድቃን ከወዳጅዎ ጋር መንግሥተ ሰማይ ያግባዎ ፤ መንግሥትዎን ይባርክልዎ ፤ ከወዳጅዎ አይለይዎ" በማለት ከዠመሩ በኋላ ፤ ፊታውራሪው የበደሏቸውን በመዘርዘር መደምደሚያውን ፤ "እሺ ታርቄዋለሁ... ገንዘቡንም አልፈልገውም ...እሺ ጃንሆይ ፤ እንደ ላኩብኝ እችለዋለሁ" ብለዋል። ዐፄ ምኒልክ ፤ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ የተሰነዘሩትን ክሶች እየመለሱ ወደ ራሳቸው ስለላኩላቸው ንጉሡ ልባቸው ተነክቶ ፤ "ከምኒልክ በፊት እግዚአብሔር የኔን ሞት ያስቀድመው" ይሉ እንደ ነበር ይነገራል ።*

ያዔ ምኒልክ ያገዛዝ ዘዴ ፤ ከዚህ ዐይነቱ ዓላማ አኳያ ጭፍራ ከለቃው ፤ ባላባት ከሕዝቡ ተስማምቶ በሰላም አገሪቱ ዕድገትና ሥልጣኔ እንድታገኝ እንጂ ፤ የራሳቸውን የሥልጣን ዕድሜ ለማቆየት ሲሉ ሌሎችን ለማጣላት አለመሻታቸውን ይጠቁማል ። ይህ ዓይነቱ ያስተዳደር ዘዴ ፤ ለዐፄ ምኒልክ ብዙ ታላላቅ የጦርና ያስተዳደር መሳፍንትና መኳንንት አስገኝቶላቸዋል ። በነዚህም አማካይነት ከመረብ ሸገር ካለው በስተቀር የኢትዮጵያን ጥንታዊ ግዛት በአንድነት አደላድለው ለማስተዳደር በቅተዋል ።

* ከደጃዝማች የማነ ሐለን የቃል ንግግር የተገኘ ።



ንጉሥ ተክለሃይማኖት አዲስ አበባ መጥተው ዘውዳቸውን ባስመረቁበት ጊዜ

ከፊሊክስ ሮሴር (ዲኒስ ዠራልድ)

# ምዕራፍ ስድሳ ዘጠኝ

## የራስ ዳርጌ ፡ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የራስ መኰንን ሞት

### ሀ. የራስ ዳርጌ ሞት

ራስ ዳርጌ በ1892 ዓ.ም. መጋቢት 15 ቀን ዐረፉ ። ራስ ዳርጌ ዘራቸው ከዐፄ ልብነ ድንግል የወረደው የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ ወሪጌ (የስልጤ ጉራጌ) የወለዱዋቸው የቀጥታ ልጃቸው ናቸው ። ዳርጌ የልጅነት ጊዜያቸውን በአን ኮበርና በአንጐለላ ካሳለፉ በኋላ ፡ ሣህለ ሥላሴ በ1840 ዓ.ም. ሞተው ኃይለ መለኮት ሲነግሡ ፡ እርሳቸው ከታላቅ ወንድማቸው ከአ ቤቶ ሰይፉ ጋር ነበሩ ።ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ መጥተው ኃይለ መለ ኰትን አሸንፈው መርድ አዝማች ኃይሌን ሾመው ወደ ቤጌምድር እንደ ተመለሱ መርድ አዝማቹ ወንድማቸውን ሰይፉን ስላሰሩባቸው ዳርጌ ጐንደር ለአቤቱታ ወዳፄ ቴዎድሮስ ሔደው ነበር ። በመካከሉ ከመርዕድ አዝማች ኃይሌ በኋላ ለሸዋ ምስለኔ ሆነው በዛብህ ስለ ተሾሙ ፡ በዚሁም ሰይፉ "ከኛ ከመሳፍንቱ መካከል ሰው ጠፍቶ ነው ወይ በዛብህ የሚሾመው" ብለው አንኮበርን መውረራቸው ተሰማ ። ዳርጌም ለሰይፉ ልትሰልል ነው የመጣኸው ተብለው ታሰሩ ።

ዳርጌ ፡ ንጽሕናቸው ታውቆ ሲፈቱ ፍጹም ያፄ ቴዎድሮስ ባለሟል ሆኑ ። በጦርነት ላይ ዠግንነታቸው ፡ በጉግሥ ጨዋታ ጊዜ ዘንግ አወራወራቸው በቴዎድሮስና በመኳንንቱ ዘንድ ይደነቁ ነበር ። ዐፄ ቴዎድሮስም ከማፍቀር የተነሣ ዳርጌ በማለት ፈንታ ፡ "ዳሩ ወይም ዳርዬ" ይሉዋቸው ነበር ይባላል ።

መርድ አዝማች ኃይሌ በከዳት ተከሰው የታሰሩ ጊዜ ዳርጌን የሸዋን ግዛት ሰጥቸሃለሁ ብለዋቸው እጅ ከነሡና ከተዘጋጁ በኋላ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ የአቤቶ ዳርጌን የደመቀ ሠፈር ተመልክተው በነገሩ ስለሡጉበት አስጠርተው ፡ "ዳርጌ ፈራሁህ በጥንድ ጦር የሚስተውን ኃይሌን ሽሬ በነጠላ ጦር ደርበህ ሁለት ሰው የምትገድለውን አንተን በሸዋ ላይ አልሾምም" ብለው በሐቅና በግልጥ ከዱቸው ። ሥልጡኑ ዳርጌም "እንዴት ምነው" የሚል ሐተታ ሳያበዙ በዝምታ እሺ ብለው በትሕትና እጅ ነሡ ይባላል ።

በመጨረሻም ቴዎድሮስ ከዳተኛው በየጊዜው ቁጥሩ ስለበዛ ፤
ሰውን ሁሉ ጠርጥረው ፤ የትግሬን ፤ የቤጌምድርንና የጐጃምን ታላ
ላቅ መኳንንትና አማቻቸውን ምኒልክን ሳይተዉ በመቅደላ በግ
ዞት ያስቀመጡ ጊዜም ዳርጌንም የዚሁ የግዞት ዕድል አልማራቸውም ።
በመቅደላ በግዞት ከነበዓልጋዳ አርአያና ከነደጃች ብሩ ጐሹ ጋር እን
ዳሉ የእንግሊዝ ጦር በ1860 ዓ.ም. መጥቶ ዐፄ ቴዎድሮስን ካሸነፈ
በኋላ ፤ ሁሉም በየትውልድ አገሩ ሲገባ ዳርጌም ወደ ሸዋ ተመል
ሰው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተገናኙ ። በተገናኙ ጊዜ ምኒልክ ፤ "እር
ስዎ በቀጥታ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ስለሆኑ ንጉሥነቴን ለርስዎ
ልተውልዎ" ቢሏቸው ፤"የለም አባታችን ሣህለ ሥላሴ አልጋቸውን
አውርሰው የሞቱት ላንተ አባት ለንጉሥ ኃይለ መለኰት ስለሆነ ፤
የነጋሢነት መስመሩ በዚያው ባንተ በኩል መውረድ አለበት"
ብለው እምቢ አሏቸው ይባላል ።[1]

ከዚያ ወዲህ እንደ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ መሳፍንት በሥልጣን
አያያዝ ሳይጣሉ ዳርጌና ምኒልክ ከሠላሳ ዓመት በላይ እንደ አባትና
እንደ ልጅ ተማምነው ፤ ተደጋግፈው ጊዜያቸውን በሰላም አሳለፉ ።
ደጃች መሸሻ ሰይፉ በሸፈቱ ቁጥር ተቆጭና አስገቢ ፤ ዐፄ ዮሐንስና
ንጉሥ ምኒልክ በተቀያየሙ ጊዜ አማካሪ ፤ አወቃቃሽና አስማሚ
ነበሩ ።

ራስ ዳርጌ የደጃዝማች አስፋው ፤ የደጃዝማች ደስታ ፤ የፊታውራሪ
ሽዋረገድ ፤ የወይዘሮ ትሰሜ ፤ የወይዘሮ አስካለ ፤ የወይዘሮ ፀሐየ ወርቅና
የልጅ ጉግሣ አባት ናቸው ።[2] በዚህ ዐይነት ለንጉሠ ነገሥቱም
ለሁሉም እንደ አባት ሆነው አሩሲን አቅንተው ሰላሌንና አካባቢ
ውን በእስ ተዳደር ይዘው ሲኖሩ በ1892 ዓ.ም. በመጋቢት 15 ቀን
ዐርፈው ቤተሰቦቻቸው ፤ ንጉሠ ነገሥቱም ፤ እቴጌ ጣይቱም ሐዘ
ንተኛ ሆነው ሰነበቱ ። የዚህንም ወሬ ንጉሠ ነገሥቱ ለንጉሥ ተክለሃ
ይማኖት ጽፈውላቸው ስለነበረ ፤ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የመጣ
ላቸው የማጽናኛ ቃል እንዲህ የሚል ነው ።

ይድረስ ኃበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ . . . የራስ
ዳርጌን ማረፍ የላኩብኝ ክቡር ማኅተምዎ ደረሰኝ ። እጅግ አዘንሁ ።

1 የሕይወት ታሪክ ፤ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፤ ገጽ 86—87 ።
2 ትልቁ ትውልድ ዘንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፤ ብ.ጌ.ማኅተመ ሥላሴ የዘር ግንድ
ይመልከቱ ።



እኔስ ፊትም የሕማምዎን (የሕመማቸውን) ብርታት ሰምቼ እዛኙ
እምሩን ጠይቅልኝና ና ብዬ ሰድጀው ነበር ። ደርሶ መጥቶ ድካማ
ቸውን ነገረኝ ። እስጊዜ ነፍስ አትለይም እንጂ መሸነፋቸውንስ ከዚ
ህም ቀደም ሰማሁ እውነት ነው ። አሁንም ጃንሆይ ምንም የሁላችን
አባት ቢሆኑ የልማዱን እግዚአብሔር ያጥናዎ ። እኔስ ጃንሆይ አት
ምጣ ብሰው ቢልኩብኝ ነው እንጂ እንኳን እንዲህ ያለ ነገር ሲሆን
እንዲያውም ጃንሆይ ናፍቀውኝ እመጣለሁ ብዬ ነበር አሁንም የሐዘን
ዳርቻ ያድርግልን ። በመጋቢት 27 1892 ቀን ዓ.ም.[1]

ስለ ሥርዓተ ቀብሩ ዝርዝር ታሪክ አላገኘንም ። ዕድሜያቸው
ወደ ሰማንያ ሳይጠጋ አይቀርም ።

ለ. የንጉሥ ተክለ ሃማኖት ዕረፍት

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የቀድሞ ስማቸው አዳል ነው ። ዘራ
ቸው በአባት በኩል ሲዘረዘር እንደዚህ ይሆናል ። የጐንደሩ ዐፄ
ኢያሱ አድያም ሰገድ (1674—1699) ታላቅ ወለተ እስራኤልን ሲወ
ልዱ ፡ ወለተ እስራኤል ምልምል ኢያሱን ፤ ምልምል ኢያሱ ከንግሥ
ሥት ምንትዋብ ታናሽ ወለተ እስራኤልን ፤ ወለተ እስራኤል የጐጃ
ሙን ባላባት ደጃዝማች ዮሴዴቅን አግብተው ታላቅ ራስ ኃይሉን ፤
ኃይሉ ድንቅነሽን ፤ ድንቅነሽ ደጃዝማች ጐሹን ፤ ጐሹ ደጃዝማች
ተሰማን ፤ ተሰማ አዳልን (ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን)[2] ይወልዳሉ ።
ደጃች ተሰማ አዳልን የወለዱዋቸው ወይዘሮ ምዕላድ ከሚባሉ ከነ
ዐፄ እስክንድር ከሚወለዱ የነጋሢ ዘር መሆኑን አለቃ ተክለ ሥላሴ
መዝግበውት ይገኛል ።[3] የተወለዱበትን ዓመተ ምሕረት አልጠቀ
ሱትም ። ሁኔታው ሲታይ ዐፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው ቀደም ብሎ
ባለው ጊዜ (በ1830—ዓ.ም.) አካባቢ ይመስላል ።

አባታቸው ደጃች ተሰማ ፡ ባፄ ቴዎድሮስ ትእዛዝ ጭልጋ ዐርባ
እምባ ላይ ሲታሰሩ አዳልን ለደጃች ተድላ ጓሉ አደራ ሰጥተዋቸው
በዚያ ሲኖሩ ፤ በ15 ዓመት ዕድሜያቸው በዛብህን ከደጃች ተድላ ጓሉ
ቁባት ከወይዘሮ ጉዳዬ በድብቅ መውለዳቸው ስለ ተሰማ ወደ ደጋ
ዳሞ ጠለዛም ኮብልለው ሲኖሩ ፤ በኋላ ደጃች ተድላ ጓሉም ዐፄ ቴዎ
ድሮስም ሞተው ጐጃምን እነደጃች ንጉሤ ተድላ ፤ እነደጃዝማች
ደስታ ተድላ ሲገዙ ፤ አዳል በነዚሁ ውስጥ የጐልማሳነታቸውን

1 ከታላቁ ቤተ መንግሥት ከቀድሞ የጽሕፈት ሚኒስቴር ቤተ መዛግብት የተገኘ ።
2 የኢትዮጵያ ታሪክ ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ፤ ተ.ጸ.መ ገጽ 52
ያለውን የዘር ግንድ ተመልከት ።
3 የእጅ ጽሑፍ ፤ ገጽ 93

ጊዜ ባላምባራስ ተብለው አሳለፉ ። ከዚያ ደጃዝማች ደስታ ተድላ በቁራጭ አገርና በባላምባራስነት ስለ ወሰኑአቸው ፣ በዚሁ ተቀይመውና ሸፍተው ሲኖሩ ደጃች ደስታ ላዔ ተክለ ጊዮርጊስ አልገብርም ብለው የሸፈቱበት ሰዓት ነበርና ተክለ ጊዮርጊስ ለአዳል እህታቸውን ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅንን ድረው የራስነት ማዕረግ ጨምረው በጐጃም ሾሚቸው ። ይኸም ሹመታቸው ባዔ ዮሐንስ ዘመን ከመጽደቁ በቀር በጐጃም ስማቸውን ተክለሃይማኖት አሰኝተው እንዳነገሢቸው በእምባቦ ከምኒልክ ፣ በሣር ወሀ ከደርቡሾች ጋር ያደረጉት ጦርነት ሁሉ በየታሪኩ ስለተጻፈ እዚህ መድገም አላስፈለገም ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ እንደሞቱ ፣ ምንም ሳያንገራግሩ በ1881 ዓ.ም. ላዔ ምኒልክ ከገቡ ዠምሮ ፣ እስከሞቱ ድረስ በሁለቱ መካከል ምንም ዓይነት የቅያሜ ነቅዕ ሳይገባ ሁለቱ አዛዥና ታዛዥ ሆነው በስምምነት እንደ ወንድማማች በፍቅር ኖሩ ። ልጆቻቸው እነራስ በዛብህ ፣ እነ ደጃች በለው ከአባታቸው እየተጣሉ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ባባታቸው ላይ ክስና ወቀሳ ሲያቀርቡ ፣ በመጨረሻም እነራስ ደረሶም ፣ እነፊታውራሪ ውድነህ በጌታቸው ላይ ‘‘ተበደልን’’ እያሉ አቤቱታ ሲያቀርቡ በደብዳቤ ለማስማማትና ለማስታረቅ ከመሞከር አልፈው ምኒልክ በኃይላቸውና በንጉሠ ነገሥትነታቸው ተመክተው ፣ ‘‘ተክለሃል ቅረብና ተነጋገር’’ ብለዋቸው አያውቁም ።

ይኸን ሁሉ የሚያውቁት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ላዔ ምኒልክ በሚጽፉት ደብዳቤ ‘‘ጃንሆዬ ለኔ ሁልጊዜ እንደ ተመቹኝ ነው እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያስመችዎ. . .ጃንሆይ እንደ ፈጣሪዎ እንደ ክርስቶስ ሰው አለማስቀየም ልማድዎ ነው’’ እያሉ ከመጻፍ ጋር ከሳሾቹንና ወቃሾቻቸውን እየተበለጡም ቢሆን ጉዳያቸውን ይፈጽሙ ነበር ። በንጉሠ ነገሥቱና በእርሳቸው መካከል የሚደረገው ጥንቃቄና መፈቃቀር አስደናቂና ሌሎች ምሳሌ ሊያደርጉት የሚገባ መግባባት ነበር ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጥር 3 ቀን 1893 ዓ.ም. በዕለተ ዓርብ በ4 ሰዓት ደብረ ወርቅ ላይ ዐርፈው ባሰናዱት በመካነ ጐልጐታ በጳጳሱ በአቡነ ሉቃስ ጐን በታላቅ ሐዘን ተቀበሩ ።

ከልቅሶው ላይ ባለቤታቸው ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅን

ንጉሥ አይቆጡ የቀረች መስሎዎ ፤
ዕዳዬን ከፍዬ እስትከተልዎ ።

1 የኢትዮጵያ ታሪክ ካዔ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ. ፣ ገጽ 43—44 ፣59—60 ።



ብለው ሲገጥሙ ፣ ልጃቸው ደጃዝማች ሥዩም (ወደፊት ራስ ኃይሉ) እንደዚህ አሉ ።

በተድላ በጐሹ ያልነበረ ነገር ፤
በክርሠ መቃብር ከአቡን መነጋገር ። *

አለቃ እንግዳ የዳሞት ሠዓሊ እንዲህ አሉ ።

ምን ይጠጣ ይሆን የነገው እንግዳ ፤
ጠጁ በእየራሱ በየዐይኑ ተቀዳ ።**

ተክሌ (ተክለ ሥላሴ) ደግሞ በበኩላቸው

እንግዲህ የምኔ የጌታ ወዳጅ !
እወሀ (እንባ) ይሰጣል ወይ አስመስሎ ጠጅ ።[1]

ሐ. የራስ መኰንን ሞት

ባዔ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፣ በኢትዮጵያ የነበሩ መሳፍንትና መኳንንት በየራሳቸው የሕይወት ታሪካቸው ቢጻፍ ብዙ ነው ። በዚህ በ19ነኛው መቶ ዓመት መጨረሻ የሞቱትም ብዙ ናቸው ። በሸዋ በኩል እነደጃች ናደው ፣ እነደጃች ገርማሜ ፣ እነደጃች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን ፣ እነራስ ጐበና መሞታቸው ሲታወቅ የሕይወታቸውን ታሪክ በትክክል አናውቀውም ። በትግሬም እነራስ አሉላ ፣ እነራስ ሐጐስ ፣ እነራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን ፣ በቤገምድርም በላስታም ፣ በሰሜንም ፣ በአገው ምድርም እነራስ ወሌ ፣ እነራስ መንገሻ አቲከም ፣ እነዋግ ሥዩም ብሩ ፣ እነዋግ ሥዩም ጓንጉል ፣ እነራስ ወልደ ሥላሴ እንኳን ታሪካቸው የስማቸው ዝርዝር ብዙ ነው ።

በዚህ ምዕራፍ የታወቀውን የራስ መኰንንን አጭር የሕይወት ታሪክ እናወሳለን ። ባለፈው ከተጻፈው ከየታሪኩ ተለቅሞ ሲታይ እንደዚህ የሚል ነው ። አባታቸው የዶባው ባላባት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ፣ እናታቸው ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሣህለ ሥለሴ ናቸው ። የተወለዱት ያባታቸው ግዛት በሆነው በጐላ ከተማ በደረፎ ማርያም ግንቦት 1 ቀን 1844 ዓ.ም. ነው ። ክርስትናም የተነሡትና

* አቡነ ሉቃስ ጐን ስለተቀበሩ ነው ። ደጃች ተድላና ደጃች ጐሹ ያላደረጉትን ለማለት ነው ።

** ሰው ሁሉ በዐይኑ ብዙ እንባ ማፍሰሱን ለመጥቀስ ይመስላል ።

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፣ ገጽ 164

የመዝመሪያውን የወጣትነት ጊዜያቸውን ከወንድማቸው ከደጃዝማች ኃይለ ማርያም ጋር ያሳለፉት በዚሁ በጐላ ነው ።

ዐሥራ ስድስት ዓመት ሲሞላቸው አባታቸው ለንጉሥ ምኒልክ ሰጧቸው ። ከዚያ ጊዜ ዠምሮ የንጉሥ ምኒልክ የመዠመሪያ የእልፍኝ አሽከር ፤ ከዚያም የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ ፤ ከፍ ሲሉ በጅሮንድ ተብለው የንብረት ኃላፊና የክፍል ጦር ማዘዝ ዠመሩ ። ሐረርጌ እንደገና በማዕከላዊው መንግሥት ሥር በዋለበት ጊዜ እነቢቶደድ አጥናፌ ፤ እነፊታውራሪ ገበየሁ (ሻቃ አጥናፌ ፤ ሻቃ ገበየሁ) ተብለው ሲዘምቱ ፤ እርሳቸው የዘመቱት በባላምባራስነት ማዕረግ ነው ። ባላምባራስነት ከሻቃነት ብልጫ አለው ።

ንጉሡ ነገሥቱ ወደ ሐረር በሔዱበት ጊዜ አገሩን ለማስተዳደር ከዚህ በፊት ጨርጨርንም ያቀኑት ትልቁ ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል* ቢጠየቁ ፤ አለመፍቀዳቸው ታወቀ ። እርሳቸው አልፈቅድም ያሉት ለልጃቸው ለቀኛዝማች መኰንን እንደሚሰጡላቸው ተስፋ አድርገው ነበር ። በኋላ ግን ፤ ለባላምባራስ መኰንን የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው ሲሰጧቸው ፤ "የኔን መኰንን ትተው ለራሳቸው መኰንን ሰጡት ወይ ጉድ !" አሉ ይባላል ።

የመኰንን ዕድል በገሃድ እየጐላ የሔደው ከዚህ ቀን ዠምሮ ነው ። አገሩ ሰፊና ሀብታም ስለሆነ ከሸዋም ተወላጅ በቀር የትግሬ ፤ የጐጃምና የቤጌምድሩ ተወላጅ ሁሉ ቀድሞም የነበረው ከየአገሩም እየመጣ ገባላቸው ። ከዚህ በኋላ ለንጉሠ ነገሥቱ የወንድም አሽከር ሆነው ከልብ ማገልገላቸው ፤ ወደ ኢጣልያ አገር ለመዠመሪያ ጊዜ ተልከው መሔዳቸው ፤ ከዚያ ሲመለሱ በሐረር ላይ ጨርጨር ተጨምሮ ራስ መባላቸው ፤ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ባለው ግንኙነት በውጫሌው ውል ምክንያት ክርክር በተነሣበት ሰዓት እንደ አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው መሥራታቸው ፤ ክርክሩ ወደ ጦርነት በዞረበት ሰዓት በአላጌው ጦርነት ለአራት ራሶች የበላይ አዝማች ሆነው መዋጋታቸው ፤ በመቀሌው የክቢ ጦርነት ብዙ ጭፍራ አልቆባቸው ራሳቸው መቁሰላቸው ፤ ለመሞት ወደፊት ሲገፉ በራስ አሉላ ጉተታ መዳናቸው ይነገራል ።ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነበራቸው ቅራኔ ፤" ለኢጣልያኖች ያደላል ፤ ከነሱ ጋር መዋጋት አይፈልግም" የሚባለውን ክስና ወቀሳ ለማስተባበል መቀሌው ጦርነት ላይ

* ወልደ ገብርኤል አባ ስይጣን የነቀኛዝማች መኰንን አባት የራስ ብሩ (አባ ይስራው) አያት ናቸው ።



ሕይወታቸውን ለመሠዋት መቁረጣቸውን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያውቁላቸው ፈልገው ነበር ይባላል ።[1]

በመኰንን ልባዊ ታማኝነት ሳይሳካ ቀርቶ ነው እንጂ ፤ ኢጣልያኖች የምኒልክን ኃይል ለማዳከም ምኒልክን ብትከዱ በሐረር ራስ መኰንንን ፤ በትግሬ ራስ መንገሻን እናነግሣችኋለን በማለት ያላደረጉት ጥረት የለም ። ከዓድዋ በፊት ራስ ወልደ ሥላሴና ልጃቸው ደጃዝማች ነጋሽ ሸፍተው ሳለ ፤ ፊታውራሪ ዘውዴ ይዘው ወዳጄ ምኒልክ ከላኩዋቸው ወዲህ ራስ ወልደ ሥላሴ አዲስ አበባ ሲቀሩ ፤ ነጋሽ ለራስ መኰንን ተልከው በሐረር ይኖሩ ነበር ። ጧት ራስ መኰንን ከቤታቸው ሲወጡ ከፊትና ከኋላ በመኳንንት ታጅበው ቁጥሩ በበረከተ የጦር ሠራዊት መካከል በበቅሎ ላይ ሲሔዱ ደጃዝማች ነጋሽ አይተው ፤ "እኔ ነጋሽ ይኸን ያህል ጦር ይዤ ለምኒልክ አልታዘዝም ነበር" አሉ ።[2] ይኸን ቃል በኋላም የአጋሜው ባላባት ራስ ስብሐት ሐረር በ1896 ዓ. ም. በነበሩበት ሰዓት ደገሙት ይባላል ።[3]

በዚህ ዓይነት መተማመን ላይ እያሉ ንጉሠ ነገሥቱ የወለዱት ልጅ ደጃዝማች ወሰን ሰገድ የልጅ ልጃቸው ደጃዝማች አስፋ ወሰን ስለሞቱ ፤ ኢያሱም ሕፃን ስለሆኑ ራስ መኰንንን አልጋ ወራሽ ሊያደርጉዋቸው ወስነው ነበር ይባላል ። ነገር ግን የአምላክ ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ወራሹ መኰንን ከአውራሹ ከምኒልክ አስቀድመው ታመው በተወለዱ በ53 ዓመት ከ10 ወራት ከ12 ቀን በመጋቢት 9 ቀን በ1898 ዓ. ም. ሐሙስ በ3 ሰዓት ቁልቢ ላይ መሞታቸውንና ሐረር በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል መቀበራቸውን ግራዜታ ኃይለ ጊዮርጊስ አጣርተው ማስታወሻውን አቆይተውናል ።

ከዚያ በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ ልጃቸው ደጃዝማች ይልማ ሐረርጌን ሲሾሙ ፤ ሁለተኛው ትንሹ ልጃቸው ደጃዝማች ተፈሪና መኳንንቱ የወጉን ዕቃ ይዘው በሚያዝያ 3 ቀን 1898 ዓ.ም. ከሐረር ተነሥተው በዚሁ ወር 19 ቀን አዲስ አበባ ደረሱ ። ዐፄ ምኒልክም ፤ እቴጌም ፤ መኳንንትና መሳፍንቱ ሠራዊቱ በተገኙበት በፍል ውሃ ሜዳ ታላላቅ ድንኳን ተተክሎ ፤ ሥጋጃው ተነጥፎ ተቀምጠው ሲጠባበቁ ከራስ መኰንን መኳንንት አንዱ የራስ መኰንንን ሥዕል ይዘው እያለቀሱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን እየተራመዱ ሲጠጉ ፤ ዐፄ ምኒልክ

1 ዜናሁ ለራስ መኰንን ፤ ግራዜታ ኃይለ ጊዮርጊስ ፤ገጽ 53

2 የሕይወት ታሪክ ፤ ብላታ ኅሩይ ወ.ሥ. ፤ ገጽ 46

3 ዜናሁ ለራስ መኰንን ፤ ግራዜታ ኃይለ ጊዮርጊስ ፤ገጽ 70

ሳይታሰብ ከዙፋናቸው አፈፍ ብለው ተነሥተው የራስ መኰንንን ሥዕል ይዘው ከሚያለቅሱት ሰውዬ ወስደው "ወንድሜ ልጄ! ወንድሜ አገልጋዬ!" እያሉ አምርረው አለቀሱ ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ከተገጠሙት ግጥሞች ውስጥ ፤

ዋ ዐፄ ምኒልክ እግዚአብሔር ያጥናዎ
በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተብዎ ።[1]

ሲታሰር አየነው ብረቱ ሲመታ
ማን ዋስ አገኘና ሐረርጌ ተፈታ ።

ጃንሆይ ምኒልክ ጠጉራቸው ሳሳና በራ ገላጣቸው
እንግዲህ ምኒልክ ምን ራስ አላቸው ።

የሚሉ ይገኙባቸዋል ።[2]

1. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 324
2. የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ. ኃ. ሥ. (9ነኛ እትም) ፤ ገጽ 137



# ምዕራፍ ሰባ

## የዓድዋ የሰባተኛው ዓመት የድል በዓል አከባበር

ከዓድዋ በፊት በተለይ ንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ከመቀዳጀታቸው አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በ1881 ዓ. ም. ስመ ጥሩ የጦር አበጋዛቸው ራስ ጐበና ዐርፈዋል። እርሳቸውም የደቡብን ክፍለ ሀገር አብዛኛውን ያቀኑትና በ1870 ዓ.ም. የራስነት ማዕረግ ከራስ ዳርጌ ጋር የተቀዳጁት ናቸው ። ከልጅነት ዠምሮ ያገለገሉዋቸው እስከ ጐንደር እስከ መቅደላ ግዞት ድረስ ያልተለዩዋቸው እነደጃዝማች ናደው ፤ እነደጃዝማች ወልዴ ገብርኤል አባ ሰይጣን ፤ እነቢቶደድ አጥናፌና ሌሎችም በሞትና በእርጅና ተገልለዋል ። ግማሾቹንም የዓድዋ የጦርነት ሜዳ አስቀርቷቸዋል ።

ዐፄ ምኒልክ ልባቸው ከተንኮል ፤ ከቅናትና ከምቀኝነት ንጹሕ ስለሆነ ሰው ይዋጣላቸዋል ። አለቆችን በሙያና ባገልግሎት መምረጥ ፤ የተመረጡትን ያለ አድልዎ በሹመት ፤ በሽልማትና በማዕረግ ማሳደግ ልማዳቸው ነበረ ። ታላላቆቹ ቢሞቱ ወይም ቢያረጁ ሌሎች የሚተኩ ታላላቅ ባለሥልጣኖች በፍጹም አይገዳቸውም ። ስመ ጥሩው ራስ ጐበና ቢሞቱ ፊታውራሪ ገበየሁ ተተኩ ፤ ገበየሁ ዓድዋ ወድቀው ቢቀሩ ፤ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተተኩ ። ምክራቸው ጽኑ እነደጃዝማች ገርማሜ ፤ እነፊታውራሪ ሀብተ ማርያም (የዝቋላው) ቢሞቱ አገው ምድሬው ራስ መንገሻ አቲከም ተተኩ ። በየሥፍራው የሚተኩ የጐደለውን የሚሞሉ በየክፍሉ በየቅርንጫፉ በቁም ነገር በታማኝነት የሚያገለግሉ ግርማ ሞገስ የተዋሐዳቸው አገር አቀፍ ባለሥልጣኖች የሞሉበት ዘመን ነበር ። የሠለጠነው የአውሮፓ ኃይል በጦርነት የተንበረከከውና ኢትዮጵያ የጥንቱን ስፋቷንና ገናንነትዋን መልሳ የተቀዳጀችው ፤ እነዚህና ሌሎችም መሰሎቻቸው በሰጡት አመራር ፤ ኅብረትና ታዛዥነት ነው ።

ከዓድዋ ጦርነት (1888 ዓ.ም.) እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ሕመም (1900 ዓ.ም.) ድረስ ያለው የዐሥራ ሁለት ዓመት ጊዜ ኢትዮጵያ ከርስ በርስ ጦርነት የተላቀቀችበት ጊዜ ነበር ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱና ተባባሪዎቻቸው ጊዜው በሚጠይቀው አስተዳደርና ውጣ

ውረድ ዕረፍት ሳያደርጉ አሳባቸውን ሁሉ የአውሮፓን ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ወደ ማስገባት አዘነበሉ ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ የዓድዋን ስባተኛውን ዓመት የድል በዓል በ1895 ዓ. ም. በአዲስ አበባ በደመቀ አኳኋን ለማክበር ዝግጅት ሲያደርጉ አዲስ አበባ ላሉትም ፡ ከየአውራጃው ለተሰበሰቡትም ለየመኳንንቶቻቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መልእክት አስተላለፉ ።

> ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና እኔም ይኸንን በዓል እንዲህ አድርጌ ማክበሬ እናንተንም ማድከሜ እግዚአብሔር በቸርነቱ ስባት ዓመት *ሙሉ በዕረፍትና በጤና ስላኖረን ፣ ስለዚህ ነገር ማክበር ይገባናል ብዬ ነው እንጂ ለጥጋብና ለትእቢት ሠራዊት በዛ ነፍጥ (የጦር መሣሪያ) በረከተ ለማለት አይደለም ። ነገር ግን በዚህ በየሥራው ነገር በእንጨት ፣ በደንጋይ የማደክማችሁን አትመልከቱ ።** ይልቁንም እኔን ስታጡ (ስሞት) ብርቱ ኀዘን ያገኛችኋል ። አሁንም ወንድሞቼ ወዳጆቼ የማናቀው መከራ እንዳያገኘን እንዳይመጣብን በዚህ ነገር ደስ አይበላችሁ ።*** እግዚአብሔር እንዳይለየን አብሮ እንዲያስበን እኔም አዝናለሁ ፤ እናንተም እዘኑ ።[1]

የመታሰቢያው በዓል እንዲከበር የተወሰነው የዓድዋ ጦርነት በዋለበት ፡ ፈረሰኛው ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ለድሉ ረድቷል ተብሎ በሚታመንበትና የጊዮርጊስ በዓል በሚውልበት በየካቲት 23 ቀን 1895 ዓ. ም ነበር ። በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ባለው አደባባይ ለንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን መቀመጫ ፣ግራና ቀኝ ለእቴጌ ጣይቱ ላቡኑ ለአቡነ ማቴዎስና ለእጨጌው ለእጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ፡ ለውጭ አገር ዲፕሎማቶችና ቆንሲሎች መቀመጫ ፡ ለባለሟሎች መቆሚያ ሲደለደልና የተደለደለውም በልዩ ልዩ ሥጋጃና ምንጣፍ ሲለብስ ስነበተ ። ለመኳንንቱ መቀመጫና ለባለሟሎቹ መቆሚያ የተዘጋጀው ርዝመቱ ሁለት መቶ ክንድ ፣ ስፋቱ መቶ ሃምሳ ክንድ መሆኑን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ያወሳሉ ።

ዝግጅቱ ካለቀ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በወርቅ ያጌጠ ከፋይ ካባና ላንቃ ለብሰው ፣ በወርቅ የተከፈፈ ባርኔጣ እንዳደረጉ በዚሁ በየካቲት 23 ቀን የጊዮርጊስ ዕለት ከጧቱ በአንድ ሰዓት ደርሰው በተዘጋጀው ዙፋን ተቀመጡ ። የቀሩትም በእልፍኝ አስከልካዮችና በአጋፋሪዎች አስተናባሪነት ሥፍራ ሥፍራቸውን ያዙ ።

---

* 1888—1895 ልዩነት ስባት ዓመት

** ለሕንፃ ፣ ለመንገድ ፣ ለልማት ሥራ በማስጋዝና አቅርቡ በማለት

*** በዚህ ሰልፍ በመመካት ልባችሁ አይታበይ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 306



ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሰልፉን ቅደም ተከተል ሲጽፉ የጦሩን አለቃ ፣ የማዕረጉን ደረጃና የጦር ሠራዊቱን ቁጥር ከመጥቀስ በቀር የመሪዎቹን ስም አልጠቀሱም ። የጸሐፌ ትእዛዙን ጽሑፍ መሠረት ሳይለቁ ሌሎች የውጭ አገር ሰዎች የጠቀሱትን አሟልተው ሙሴ ሞሪስ ደኮፔ ያሰላለፉን ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበውታል ።

፩ኛ. የገሙና የቦረና የሰዶ ፣ ያማያና የጨቦ ገዥና ዋናው የጦር አበጋዝ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የፈረስ ስማቸው አባ መቻል 30,000 ባለጠበንጃ አሰልፈው እንዳማረባቸው አለፉ ።

፪ኛ በእናርያ (ሊሙ) እና በከፋ የተሾሙት የንጉሠ ነገሥቱ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽም ልጅ የራስ ወልደ ጊዮርጊስን አሰላለፍ ገብረ ሥላሴ እንደዚህ ሲሉ ገልጠውታል ። "እናርያንና ከፋን የሚገዛው ራስ የንጉሡ (የምኒልክ) ወንድም ፈረሱን ቀንድና ቀንድ አድርጎ (ፈረሰኛውን በሰልፍ አስተካክሎ) እምቢልታው መለከቱ ፣ ነጋሪቱ ሆኖ ከመኳንንቱና ከአደጉ (ጀሌ) በቀር 32,000 ነፍጥ (ጠበንጃ) ያስያዘው እጅግ አምሮ በዝቶ ታየ ። ባለብሩ ባለወርቅ ጣፋ ጋሻ በፀሐዩ ፀዳል (ብርሃን) ዐይን ለማየት ያስቸግራል ። የሱ ሰው በብር ካጌጠው በወርቅ ያጌጠው ይበልጣል ። "

፫ኛ. ጉማን የሚገዙት አፈ ንጉሥ ነሲቡ 15,000 ባለጠበንጃ አሲዘው አለፉ ።

፬ኛ. ያፈ ንጉሥ ነሲቡ ትልቁ ልጃቸው ደጃዝማች ደምሰው* የነቢቶደድ መኰንን አባት የወለጋና የጉድሩ ገዥ 30,000 ባለብረት እንዳሰለፉ አለፉ ።

---

* ደጃዝማች ደምስ (በኋላ ራስ) አሽከር ለማሳደግ ጦር ለማደራጀት ፡ ግብር ለማብላት ሽልማት ለመሸለም የራላቸው ገንዘብ እያነሣቸው ከሰው ይበደሩ ነበር ይባላል ። ከሞቱ በኋላ ላርባቸው ኑዛዜ ሲፈስ ባለዕዳዎች ቢቀርቡ መኳንንቶቻቸው ጌታችን ባለዕዳ የሆኑት ለኛ ያበሉትና ያጠጡት የሸለሙበት እኮ ነው ዝም ትላላችሁ ብለው ከሥጋጃው ላይ የወረወሩት ገንዘብና ወርቅ ቢቆጠር ከዕዳው እጥፍ ሆኖ ቤተሰብ ተከፋፈለው ይባላል ።

፭ኛ. ያሩሲና የባሌው ገዥ ደጃዝማች ሉል ሰገድ የፈረስ ስማ ቸው አባ በላይ ፣ ሉሉ መልከ መልካም ፣ ቁመናቸው ዠርጋዳ የእቴጌ መነን ሁለተኛ ባል ፣ በዚህ ጊዜ ባሌንና አሩሲን ሲያስተዳድሩ 15,000 ጦር አሰልፈው አለፉ ።

፮ኛ. የሉሜና የከምባታው ገዥ ደጃዝማች አባተ የፈረስ ስማ ቸው አባ ይትረፍ 20,000 ጦር ።

፯ኛ. የሲዳሞው ገዥ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ 10,000 ባለጠበንጃ ።

፰ኛ. የፋጅና የዲርማ ፣ የጃማ፣ የሚዳና የደራው ገዥ ራስ ወልዴ የፈረስ ስማቸው አባ ሥዩም 15,000 ጦረኛ ።

፱ኛ. የይፍራታና የግድም ፣ የቀወትና የጥሙጋ ገዥ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ (የራስ ወለዴ ልጅ) 9,000 ወታደር ።

፲ኛ. የጐላ አገረ ገዥ ደጃዝማች ውቤ የፈረስ ስማቸው አባ ታደግ የንግሥት ዘውዲቱ ባል የነበሩት 9,000 ጦር እንደያዙ ፡

፲፩ኛ. የንጉሠ ነገሥቱና የእቴጌይቱ አዛገሮች አዛዥ ዛማኔል (ዘአማኑኤል) እና አዛዥ በዛብህ ባንድነት 10,000 ባለጠበንጃ ።

፲፪ኛ. የወሎና የወረሂመኖ ፡ የሳይንት የቦረና ገዥ ራስ ሚካኤል 70,000 ወታደር ።

፲፫ኛ. የኢሉባቦርና ገባ ከሚባለው ወንዝ ማዶ ያለውን ሁሉ የሚያስተዳድሩት ራስ ተሰማ ናደው 30,000 ።

፲፬ኛ. የጐፋና የሸንጋማ አስተዳዳሪ ደጃዝማች ለማ አቦዬ (የራስ ወልደ ጊዮርጊስና የደጃዝማች በሻህ ወንድም) 12,000 ጦር አስከትለው አለፉ ።[1]

ጸሐፌ ትእዛዙ በዚህ ታላቅ የሰልፍ ትርዒት ዘየአውራጃው ርቀት የተነሣ የሐረርና የውጋዴን ፣ ከጨጨሆ በላይ የባምብሎ እስከ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ. 71 ገጽ 304—312. Chronique --- De Menelik 500—505



ወፍላ ፣ የትግራይ ፣ የጐጃም አስተዳዳሪዎችን አለመጨመራቸውን ካመለከቱ በኋላ ፣ በትርዒቱ ላይ የመድፍና የጠበንጃው ተኩስ ጢስ የፈረሱ አጐዳ (ኮቴ) አቧራው ባንድነት ሲነሣ ዠምበሯን እንደ ሐምሌ ጉም እንደ ሸፈናት ወታደሩም ጐራዴና ሰይፉን እየመዘዘ በፉከራ ሲጮህ በተኩስ ጢስ ጸዳል ጮራ ያረፈበት ባሕር መምሰሉን አብራርተዋል ። መደምደሚያውን ዐፄ ምኒልክ ዘበኞቸውን ይዘው በነፍጡና በመድፉ ተኩስ እጅግ በሚያስደንቅና በሚያስፈራ ግርማ ለሕዝብ ማሳየታቸው ፣ "እግዚአብሔር አያምጣብን እንጂ ፣ ሌላም ጠላት ቢመጣ እንደዚህ አድርጌ እረዳችኋለሁ አጠቃላችኋለሁ" ብለው ፣ ለሕዝባቸው ለማስረዳት መሆኑን ጠቅሰው አልፈውታል ።

# ክፍል ስድስት

## የንጉሠ ነገሥቱ መታመም

## ምዕራፍ ሰባ አንድ

### ዐፄ ምኒልክ በሕመም መውደቅ — የጀርመን ወኪሎችና ሐኪሞች ችግር መፍጠር

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከ1857 እስከ 1881 ዓ.ም. የሸዋ ንጉሥ በመሆን ፣ ከ1882 እስከ 1906 ዓ.ም በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት በገዙበት ዘመን፣ በውስጥም ፣ በውጭም አንድም ጊዜ የመሸነፍ ውርደት ሳይገጥማቸው በሕዝብና በወታደር ዘንድ እንደ ተወደዱ ኖረዋል ። የአውሮፓን ሥልጣኔ በየዘርፉ ላገራቸው ለማስጨበጥ ብዙ ድካምና ጥረት አድርገዋል ። እኚህ ገናና ንጉሠ ነገሥት በ1900 ዓ.ም. መጨረሻ በሚያዝያ ወር ላይ ሕመም አድሮባቸው በታመሙ ጊዜ ከሁሉ በፊት የመረመራቸው ዶክተር ቪታሊያ የሚባለው የሞሪሽስ ተወላጅ ፣ ከኩላሊት መበላሸት የተነሣ የደም እመታታቸው ልክ አለመሆኑን ተገነዘበ ። ሕመማቸው ስለጸና በዚሁ ዓመት በሰኔ ወር ላይ የሰውነታቸው አጋማሽ በድን ሆነ ። ከዶክተር ቪታሊያ ቀጥሎ ያከማቸው ዶክተር ተርሚኒዬ የሚባለው የፈረንሳይ ሐኪም ምንም የማዳን ውጤት ሳያሳይ ስለቀረ ፣ ይሻላቸው ይሆን በማለት ከግቢ ወደ እንጦጦ አዛውረው ከዚያም ወደ ደብረ ሊባኖስ ለጠበል ወስደው ቢያጠምቋቸው ፣ እንዲያውም ከቀድሞ መባሱን የተመለከተው ዶክተር ተርሚኒዬ ጠበሉን በግድ አስተወና ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በቤተ መንግሥታቸው ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱና ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱ እያስታመሟቸው ተቀመጡ ።

በዚህ ጊዜ ፣ አልፎ አልፎ ኢትዮጵያዊው ዶክተር ማርቲን (ሐኪም ወርቅነህ) ሲያክሙዋቸው ፦ ውጤት አልባ ስለሆነ ፣ አዲስ አበባ በሚቀመጠው በጀርመን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በዶክተር ፍሬዲሪክ ሮዘን አማካይነት ለዳግማዊ ውልሄልም የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ተጻጽፈው ፣ ዶክተር አልፍሬድ ሴንትግራፍ በሕክምና ላይ አማካሪ ለመሆን ፣ ዶክተር ማክስ ስቴንኩሀለር በተለይ ለሕክምና መጥተው ማከም ዠመሩ ።

ይኸው ስቴንኩሀለር የሚባለው ሐኪም ፥ "በንጉሠ ነገሥቱ ላይ
የሥራ ሥርና የጅማት መተሳሰርና የሰውነት መጨማደድ ይታይባቸ
ዋልና በሙቀትና በመታሸት ሊሻላቸው ይችላል" ብሎ በመዝመ
ሪያ በእጁ እያሸ ትንሽ የመሻል ምልክት እንዳሳዩ ፥ በመጨረሻም
የኤሌክትሪክ መታሻ መሣሪያ አስመጥቶ ዘዴውንም ላስታማሚዎች
አሳይቶ ሳለ ፥ "የበሽታው መነሾ ልዩ ሰበብ (መርዝ በመብላት?) አለ
ውና ያንኑ ብቻ ማከም ነው" ብለው እንደ ተቃወሙት ፥ እቴጌ ጣይ
ቱም ፥ "ዕድሜው ከ60 ወይም ከ40 ዓመት በላይ ለሆነ ሰው
የኤሌክትሪክ መታሸት እንደማይጠቅመው አንድ ሐኪም ነግሮኛል"
ብለው እንደ ተቃወሙትና በመካከሉም በአሠራር አለማወቅ የማሻው
ኤሌክትሪክ እንደ ተበላሸ ፤ ጥዋት በኤሌክትሪኩ መሣሪያ ታሽ
ተው ወደ ማታ ሲያዩዋቸው ደክመውና ዝለው ዐይናቸው ጨላልሞ
የደም እመታታቸው ሰንፎ ፥ እንዳገኛቸውና በጠቅላላው ሰውነታቸው
ተመርዞ ስላገኘው ፥ "በጥዋት ሽንታቸው ይላክልኝ" ቢል ወደ ማታ
አቆይተው እንደላኩለት ፥ ያንንም ቢመረምረው "ሲያንካሊ" በሚ
ባል ከሁሉ በከፋ መርዝ እንደተነደፉ ፥ ይኸም የመጣው ከመጠጥና
ከመብል መሆኑን በተወው ማስታወሻ ይገልጣል ። አሳቡም ወይ
በቸልታ አስዚያም ሆነ ተብሎ መርዝ ያለበት መብል አብልተዋቸዋል
ወደ ማለት ነው ።[1]

በዚህም ብዙ ውዝግብ በሐኪሙና በእቴጌ እንደዚሁም ፥ በአስ
ስታማሚዎቹ መካከል ከተፈጠረ በኋላ በመጨረሻ ዘንቲግራፍና
ሐኪሙ ስቴንኩሀለር ፥ "እኛ ለማዳን ስንደክም ሌሎች ሥራችንን
የሚያበላሹብን አሉ ። ከነዚህም መካከል የገንዘብ ሚኒስትሩን በኸ
ሮንድ ሙሉጌታንና የግቢ ሚኒስትሩን አዛዥ መታፈሪያን ጠርጥ
ረናቸዋልና ከግቢ ካልተወገዱ አንሠራም" የሚል ክርክር በከንቲባ
ገብሩ አስተርጓሚነት አቀረቡ ። ንጉሠ ነገሥቱም ፥ እቴጌ ጣይቱም
በኅብረት ፥ "እነዚህ ሁለት ባለሥልጣኖች ከልጅነት ዠምሮ በቤተ
መንግሥታችን አብረውን የኖሩ በፍጹም የማንጠረጥራቸው ታማኞ
ቻችን ናቸውና አይወጡም" የሚል መልስ ቢሰጡም ሐኪሞቹ እምቢ
አሉ ። እቴጌም "ጃንሆይ የሚመገቡት ከኔው ቤት በጥንቃቄ እየተዘጋጀ
እየመጣ ነውና እነዚህ ሰዎች መዳኒት ከመብል ጋር የሚወዷቸ
ውን ንጉሠ ነገሥት ያበላሉ ተብሎ አይጠረጠርም" ብለው ቢያባብ
ሏቸው ፥ "እነሱ ካልወጡልን እናከምም ወዳገራችንም እንመለሳለን"
ስላሉ ፥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ንጉሠ ነገሥቱም እቴጌም ለጀ
ርመኑ ንጉሠ ነገሥት ለመጻፍ ተገደዱ ።

---

1. ከትልቁ ቤተ መንግሥት መዝገብ ቤት የተገኘ ሰነድ



ሞዓ አንበሳ . . . ከዳግማዊ ዊልሄም የአልማንያ (አሌማኝ)ንጉሠ
ነገሥት ሰላምታ . . . የከበሩ ንጉሠ ነገሥት በቸርነትዎ ሐኪሙን ዶክ
ተር ስኪያንክለርን ፥ ለምክር የሚረዳንን ዶክተር ዲንትግራፍን ሰደ
ዱልን ። በመምጣታቸውም እኔንም ሠራዊቴንም ደስ ብሎን ነበር ። ነገር
ግን ሐኪሙ እንኳን መድኃኒት አድርጎ ሊያድነኝ በብዙ ሁከትና
በብዙ ድካም ከረምሁ ። እኔ የማምናቸውን እነሱ ካልወጡ ብለው
ዶክተር ዳንቴግራፍ እኔ አልኖርም አሰናብቱኝ አለ ። ሐኪሙም እነሱ
ካልወጡ መድኃኒት አላደርግም አልገባም ብሎ ሁለቱም ጻፉልኝ ።
እኔም የነዚህ ሰዎች ነውራቸው ሳይገለጥ ሳይረቱ እንዴት ይወጣሉ
አልኩ ። እነሱ ግን ካልወጡ አንኖርም አሉኝ ። እነዚህስ አይወጡም
ብዬ እሺ ብዬ አሰናበትኩ ።

ክቡር ወዳጁ መንግሥትዎ የውነተኛ ፈራጅ መሆኑን አምናለሁና
ይህ ነገር ተመርምሮ እንድሰማው ተስፋ አለኝ ። ይህነን ሁሉ ያረገና
ሁከት ነገር ያመጣ የኔ ዜጋ የጀርመንን ቋንቋ የሚያውቅ ሰው ነው *

እሱንም እኔ እንዳልመረምረው በባንዲራ ወስደው ከጀርመን ሌጋ
ሲዮን ቤት አስቀምጠውታል ። ሹሜ ነው ዜጋዬ ነው ወደኔ ስደድልኝ
ብለው የጀርመን መንግሥት ሚኒስቴር ደስዎ አላለው ። የግድም እንዳ
ላመጣው የጀርመንን መንግሥት ማስቀየም ይሆንብኛል ብዬ አሰብሁ ።
እሱም ከሰው ጋር ይምጣና ከዚያው ከመንግሥትዎ አብሮ ይመርመር ።
ይኸንን በብዙ ማፍቀርና ማመን ነገሩ ተገልጦ እንድንሰማው እለም
ንዎታለሁ ።

የሆነውን ነገር ሁሉ ገልጦ የሚያስረዳ ግን ፥ የእቴጌ (ጣይቱ) ደብ
ዳቤ ነውና ከዚያ ላይ ይገኛል ። ለስዎ (ለርስዎ) ዕድሜና ጤና ለሕ
ዝብዎ ሰላምና ዕረፍት እንዲሰጥ እግዚአብሔርን እለምናለሁ ። ነሐሴ
21 ቀን 1901 ዓ.ም. አዲስ አበባ ተጻፈ ።

እነዚህ ፤ አንደኛ ለተዠመረው የልማት ሥራ እንደ ቆንሲልም
ሆኖ በምክር ይረዳል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ዶክተር ሴንትግራፍ
በቀጥታ ለሕክምና ከመጣው ከስቴይንኩሀለር ጋር በመተባበር በጊ
ዜው የነበሩትን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሩንም ሚስተር ሮቤርቶ
ቬለር ሳይቀር ወደነሱ አሳብ በማስተባበር በሰው ቤት በማያገባ
ቸው ጉዳይ እየገቡ ፥ "እገሌና እገሌን እንጠራጠራቸዋለን ከቤተ መንግ
ሥት ይወገዱ ፤ እነሱም ካልተወገዱ አንሠራም ፤ እናክምም ፤ ወዳገራችን
እንመለሳለን" እያሉ በውቀታቸው በመመካት ማስቸገራቸው ሚኒስ
ትሩ ቬለርም ዜጎቹን በመግሠጽ ፈንታ መተባበሩ አሳዛኝ ነው ።

ለዚህ አድራጎት ንጉሠ ነገሥቱም ፥ እቴጌይቱም እጥፌ ያደረጉት
በጀርመን ሌጋሲዮን እንደ ወዳጅና እንደ አስተርጓሚ ሆነው የሚሠሩትን

---

* ከንቲባ ገብሩን ማለታቸው ነው ።

ከንቲባ ገብሩን ነው ። እርሳቸውም በኋለኛው ዘመን እንደ ተገነዘብነው ምሑር ፡ ላገር አሳቢና ኢትዮጵያም እንድትሠለጥን የሚደክሙ ሆነው ሳለ ፡ ምንም ከጀርመኖቹ ጋር አብሮ ብዙ ዘመን በመኖር ቢወዳጁም ፡ በዚያን ሰዓት ከወገኖቻቸው ተለይተው ከነዚያ ጋር ያስተባበራቸው ሰበቡ በግልጥ አይታወቅም ። ምናልባት ከበጅሮንድ ሙሉጌታና ከአዛዥ መታፈሪያ ጋር በግል ጉዳይ ተጣልተው ተቀያይመው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ፡ በሕመምተኛው ንጉሠ ነገሥትና በእቴጌይቱ ዘንድ አዲስ ከጀርመን ጋር የተወጠነው የወዳጅነትና የንግድ ግንኙነት እንዳይበላሽ ብዙ ጥንቃቄ እየተደረገ ጉዳዩ በራስ ቢቶደድ ተሰማና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ዘኩል እንዲመረመር ከታዘዘና ራስ ቢቶደዱም ፡ ቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስም በደብዳቤ ጥሪ ቢያደርጉላቸው ሴንትግራፍ ፡ "ስብሰባው ወዴት ነው? ሰብሳቢው ማነው? ሰዓቱ ስንት ነው?" እያለ ከማደናበር ጋር ፡ "ከጃንሆይ ሙሉ ችሎት ላይ ካልሆነ በቀር አልነጋገርም" ብሎ ገተረ።

ከዚህ ሁሉ ውዝግብ በኋላ ነው ንጉሠ ነገሥቱም ለጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት የጻፉት ። ከዚያም የበለጠ እቴጌይቱ አብራርተው ከዚህ እንደሚከተለው ጽፈው ላኩ ።

ይድረስ ለክቡር ወዳጃችን ከዳግማዊ ዊልያም የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ፤

የተላከ ከእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ።

ሰላምና ጤና ለእርስዎ ይሁን ።

በብዙ ማክበርና በትሕትና ይህንን ደብዳቤ ልጽፍልዎ አሰብሁ ። ስለዚህ ይህንን የደረሰብኝን የሚያሳዝን ነገር ደፍሬ ልጽፍልዎ የግድ ሆነብኝ ልታገሠው አልተቻለኝምና ። ስለ አጤ ምኒልክ ጤና መጉደል ጌታዬን ወዳጄን አጣቸው ይሆን ብዬ አጥብቄ ተጨንቄያለሁ ። ለሴቶች ካባት ካናት ከልጅ ከወንድምም የጮኛ (ባል ) ነገር ጭንቅ እንደሆነ የታወቀ ነው ። ስለዚህ የጀርመን መንግሥት ሐኪም የጥበብ ረቂቅ ብልሃት ሰመ ጥሩነቱ እስከኔ ደርሶ ንጉሠ ነገሥቱ ተፈውሰው እንደ ቀድሟቸው ሆነው ለማየት የተቃጠለ ምኞቴ እንዲፈጸምልኝና በብርቱ አጥብቆ ለሚወዳቸውም ሕዝባችን ንጉሡ በሕይወት እንዲቆዩለት ለመፈወስ የሚያስፈልግ ነገር ሳይደረግላቸው እንዳይቀር ብለን የጀርመንን ሰመ ጥሩን የጥበብ ረቂቅ ብልሃት ረዳትነት ለመንን ። ንጉሥም በቸርነትዎ ሐኪሙንም ምክር የሚረዳንንም ይስደዱልን ያልነውን ዶክተር ዲንትግራፍን ጨምረው ሰደዱልን ።

እነሱም በመምጣታቸው እኛንም ሠራዊታችንንም እጅግ ደስ አለን ። ነገር ግን እንደ ተመኘነው ሳይሆንልን ቀረ ። አለመሆኑንም ለማስረዳት ከዚህ ቀጥሎ በሚጻፈው ቃል አስታውቃለሁ ።



ሐኪም ዶክተር አስቴንኩለር በሚያዝያ በ2 ቀን ገቡ ። ከዚያም አንሥቶ እስከ ግንቦት 15 ቀን ጠዋት ማታ እየተመላለሱ ለንጉሥ መድኃኒቱን ሲያደርጉ ሰነበቱ ። በግንቦት በ15 ቀን ግን በንጉሠ ነገሥቱ ደም የመርዝ ፍሲጋ አገኘሁ ይጠንቀቁ ብለው ለእኔ ነገሩኝ ።

እኔም ዐፄ ምኒልክ መርዝ ማን ያደርግባቸዋል ፤ ይህ ነገር አይጠረጠርም አልሁ ።

ሐኪሙም ከወጥቤት ዕቃም ከምንም ከምን ዕድፍ መጠንቀቅ ነው አለ ። የከበሩም እጮኛዬ ሕመምዎ ከጀመረዎ ቀን አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ የዛሬው ሰዓት በኔ ዘንድ የተወደደ ስለሆነብኝ ያለእረፍት በብርቱ ትጋትና ጥንቃቄ ከብቤ ጌታዬን የማስታምም እኔ ራሴ ነኝና የሐኪምን ትእዛዝ ሁሉ መፈጸሙን ተደላድዬ ማስረዳት የሚቻለኝ ስለሆነ ፡ ይህንንስ እሺ የሚሰናዳውም ምግብ ሁሉ ከኔ ቤት ነው አልሁ ።

ከዚያም ወዲህ ዳግመኛ መርዝ አገኘሁ ብለው አልነገሩኝም ። እንደ ፊተኛው መድኃኒቱን ሲያደርጉ ቆዩ ። ዶክተር ዲንትግራፍም እሳቸው ያሉትን ሁሉ አድርገን ለሳቸው የሚያመቻቸውን ማለፊያ የተሰናዳ ቤት ሰጥተን አክብረን አስመችተን አኑረናቸው ነበር ። በሐምሌ በ5 ቀን ግን ዶክተር ዲንትግራፍ ሐኪሙን ይዘው መጥተው የኛ መኳንንቶችና ሠራዊት ከተሰበሰበበት በንጉሡ ክፉ ነገር ተደርጉባቸዋልና በብርቱ የታመኑትን አገልጋዮቻችንን እጃቸውን ተይዘው ይመርመሩ ፤ ይህ ካልሆነ ሐኪሙ ገብተው መድኃኒት አያደርጉም ብለው ከለከሉ ። በበነጋውም ዶክተር ዴንትግራፍ ከንጉሥ ልገናኝ ብለው ላኩ ። እኛም እሺ ብለንና ሁሉታችንም አንድ ላይ ሁነን ጠራናቸው ። እሳቸውም እነዚህ እጃቸው ተይዘው ይመርመሩ አሉ ። የታመኑ አሽከሮቻችን ናቸው አይጠረጠሩም እጃቸው ተይዘው የሚመረመሩት ምንድነው ብንላቸው ተይዘው ካልተመረመሩ ሐኪሙ አይገቡም አሉ ።

ደግሞ በበነጋው ምኒስትሩን ሙሴ ቮሴርን ጠርተን ንገሩን ብለን ብንጠይቃቸው ፤ በንጉሥ ምግብ ውስጥ መርዝ ተገኝቷል በመብልና በመጠጥ ውስጥ ሆኖ ንጉሡን አልጐዳቸውም እንጂ ሐኪሙ አግኝተዋል ብለው ነገሩን ።

እኔም ለምኒስትሩ ንጉሥ የሚመገቡት ሁሉ የሚሰናዳ ከኔ ቤት ነው ፤ የኔ ሹሞች ናቸው የሚያሰናዱ ። እነዚህ ሰዎች ግን ከእኔ ቤት በምንም በምን አይደርሱም ብዬ አስታወቅሁ ። ንጉሡም እነዚህ ሰዎች በዚህ ነገር አይጠረጠሩም ሥራቸው አይደለም ብለው ተናገሩ ።

ሕዝቡም ዐፄ ምኒልክን እንደነፍሱ እንዲያውም ከነፍሱ አልቆ እንዲያፈቅረዎ ንጉሥም በሕዝቡ አክብሮትና አፍቅሮት መካበብዎን ተደላድዬ ዐውቃለሁና ይህንን ሥራ በሕይወታቸው ላይ ሊሠራባቸው ማንም የሚችል ሰው የለም ።

ሚኒስትሩ ግን ፣ ምንም ቢሆን እነዚህ ሰዎች ካልወጡ አይሀንም ንጉሡን የሚጠብቅ ሐኪሙ ሌላ ሰው መርጠው ያግቡ አለ ።

ሐኪሙም እንደዚሁ እነዚህ ሰዎች ካልወጡ አልገባም ብለው ቀሩ ። እኔም በዚህ ነገር እኔን የሚጠብቅ ሌላ ሹም መቀበሉ ታላቅ ሸክም ሆነብኝ ።

በገዛ ሰውነቱ ላይ መርዝ በማድረግ መጠርጠር አይቻልምና ደግሞ የዚያኑ ለት ማታ ዶክተር ዲንትግራፍ እነዚህን ሰዎች ካልተሻሩና ካልወጡ እኔ አልቀመጥም ብሰው የሰጠናቸውን ቤት ለቀው ሔዱ ።

እዚያም ከሔዱ በኋላ ፣ እነዚህ ሰዎች ካልወጡ እኔን አሰናብቱኝ ብለው ወደ ንጉሥ ወረቀት ጻፉ ። ንጉሥም አንተም ልሰናበት ያልክበት እነዚህስ ሰዎች የሚወጡበት ብልሃት ካልተገለጠ እንዴት ይሆናል አንተው ይመርመሩ ባልክበት ነገር በ20 ሐምሌ ማክሰኞ እንድትመጡ ብለው ላኩባቸው ።

በዚያው ለነሱ ባስታወቅንበት ቀን አባታችን አቡነ ማቴዎስም በከተማም ያሉት ሐኪሞች ፣ የኛም መኳንንቶች ሁሉ ተሰብስበው ከ4 እስከ 6 ሰዓት ሲጠብቁ ውለው እነሱ ሳይመጡ ቀሩ ።

የተሰበሰበውም ሰው በየቤቱ ገባ ። ዶክተር ዲንትግራፍም ዳኛውስ ማነው ሥፍራውስ ወዴት ነው ብለው ሳይመጡ ቀሩ ። ሐኪሙም እነዚህ ሰዎች ፈጽመው ካልተከለከሉ እኔ አልገባም ። ደግሞም ስገባ እኔ የምወደውን አስተርጓሚ ይዤ ነው የምገባ ። ውሌ ይህ ነው ብለው ወረቀት ጻፉ ። በዚህ ምክንያት ወደፊትም እንዲያስታምሙልን እርዳታቸውን ለመፈለግ የማይመችን የማይመስለን ሆነብን ።

ደግሞ ሦስተኛ እነዚህ ሰዎች ከዚህ ተከልክለው ወደ ሌላ አገር ካልሔዱ እኔ አልኖርምና አሰናብቱኝ ብለው በራስ ቢቶደድ ተሰማ እጅ ወረቀት ላኩ ።

ንጉሡም እኔም በነዚህ ሰዎች በሹመት ነገር ሌላ የተመቀኛቸው ሰው ተነሥቶ አስወጡልን ያላቸው ሰው ይኖር ይሆን እነያዚም ከመጡ ጥቂት ቀን ነው አገሩን አያውቁት ፤ ሰዉን አለመዱት ፤ ከነሱም ጋር ጠብ የላቸው ፤ ይህ ነገር ምን ይሆን ብለን ገረመን ።

ከዚህ በኋላ ፤ ይህ ካልሆነ አሰናብቱኝ ብለው ሦስት ጊዜ ወረቀት ላኩ ። ከዚህማ ወዲያ አላሰናብትም አሉኝ ብለው ወደ መንግሥታቸው የላኩ እንደሆነ የከበሩ ንጉሠ ነገሥት ወዳጄ ይቀየሙኛል ብለው ለዶክተር ዲንትግራፍ ይመርመሩ ብትሉ እሺ ብለን ቀን ቆርጠን ብናስታውቃችሁ ሳትመጡ ቀራችሁ ።

እኔ የማምናቸውን ያሳደጉኋቸውን የሾሙኋቸውን ሹማምንቶቼን ከዚህ ወጥተው ወደ ሌላ አገር ካልሔዱ ከነሱ ጋር ለመኖር እይሆንልኝም ብለህ መሰናበትህን ከወደድህ እሺ አሰናብቼሃለሁ ብለው ጻፉለት ።



በዚህ በኛ ዘንድ ያሉት ምኒስትሩ ሙሴ ቮለር ግን መልካም ሰው ናቸው ። ዳሩ ግን ነገሩን መርምረው ለኛ ባለማስታወቃቸው አዘንን ። ስለሆነም ፣ የተመኘነውን ፈቃዳችንን ለመፈጸም ብለው በታላቅ ቸርነትዎ ላደረጉልን በጎ አድራጎት እኔው ራሴ በፍጹም ልቤ ግርማዊ ሰውነትዎን አመሰግናለሁ ። ይህንን ሁሉ ነገር መጻፋችን እነሱን ለማዋረድ ብለን አይደለም ። የንጉሡ ልቡና እንዳይቀየምብን ብለን ነው እንጂ ። ዳሩ ግን አንድነት የሚያዋህደንን ታላቁን ፍቅራችንን ለማሰናከል ይህ ትንሽ ነገር ምክንያት ይሆናል ተብሎ አለመጠርጠሩ ግልጥ ነገር ነው ። የንጉሡ ፈቃድም ቢሆን ከዚህ በኋላ ሁሉንም ነገር ለሚጠይቃቸው ምላሽ የሚናገሩ ከኛ ዘንድ መልክተኞች ለመስደድ እንመኛለን ።

ነገሩ ብዙ ስለሆነ በወረቀቱ አይጠቀስልምና ። ፊት ከሙሴ ሮዘን ጋር መጥተው የነበሩት ሐኪም ሐንስ ቮልብረሽት ለእኔም መድኃኒት አድርገውልኝ አድነውኝ ነበርና ዛሬም ለጥቂት ቀን እንዲመጡልን እንለምናለን ።

የከበሩም ንጉሠ ነገሥቱም በቸርነትዎ ይሰዱልናል በማለት ተስፋ እናደርጋለን ። ለእርስዎ ዕድሜና ጤና ለሕዝብዎም ሰላምና ዕረፍት እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ነሐሴ 15 ቀን 1901 ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ተጻፈ ።

መቼም በዘመኑ በንጉሠ ነገሥቱ ሕመም ላይ ግማሹ ፡ "በልጅ ኢያሱ የተገዙ ሰዎች ድመት አርደው ደንቃራ ጥለው አሳመሟቸው ፤ እቴጌ ጣይቱ ሥልጣን ለመጨበጥ ሲሉ መድኃኒት አደረጉባቸው" ሲሉ የቀረው ደግሞ ፡ "ሁሉም ውሸት ነው ንጉሠ ነገሥቱ ያገራችን መብልና መጠጥ እንዳይበሉ ሐኪሞች ከከለከሉ በኋላ ፣ ሕመምተኛው ለባለቤታቸው የዶሮ ወጥ በእንጀራ አማረኝ ስላሉ ፡ እቴጌይቱ በርኅራኄ የንጉሠ ነገሥቱን አምሮት ለመፈጸም በእቴጌይቱ ፈቃድና ትእዛዝ የተዘጋጀውን የዶሮውን ወጥ ከበሉ በኋላ ፣ በደም ሥራቸው ውስጥ መርዝ መስሎ የታያቸው ሐኪሞች በከንቱ እቴጌይቱንም የቅርብ አስታማሚዎቹንም ጠረጠሩ" ማለት ነው ።

## ምዕራፍ ሰባ ሁለት

### የንጉሠ ነገሥቱ ሥጋትና ዝርዝር ምክር — የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት የራስ ተሰማ ናደው እንደራሴነት

ንጉሠ ነገሥቱ ሕመም እንደ ጸናባቸና እርጅና እንደ ተጫናቸው በተረዱት ጊዜ፣ አሳባቸውና ሥጋታቸው "ያስተካከልሁት የኢትዮጵያ አንድነት ይፈርስ ይሆን? በዙሪያዬ በኔ ሰበብ በንጉሠ ነገሥትነቴም ምክንያት ባንድ ሥልጣን የተሳሰሩት መሳፍንትና መኳንንት እኔ ስሞት ተከፋፍለው በመዋጋት በኢትዮጵያ አንድነት ላይ አደጋ ይመጣ ይሆን?" የሚል ነው ። ይኽን ሥጋት የጣለባቸው ከዘመነ መሳፍንት ዠምሮ ሳያቋርጥ እስከ ዘመናቸው የደረሰው የርስ በርስ ጦርነት ነው ።

ለዚህ ሁሉ ሥጋታቸው መፍትሔ ብለው ያመኑበት፣ አንደኛ በጽሑፍ አዘጋጅተው ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ የሚያቀርቡት ዝርዝር ምክር ፤ ሁለተኛ ከርሳቸው ቀጥሎ በዙፋኑ የሚቀመጠው አልጋ ወራሻቸው ልጅ ኢያሱ መሆኑን በግልጽ ማስታወቅ ነው ። ኢያሱን የመረጡበት ምክንያት ግልጽ ነው ። ከወይዘሮ ጌጤ የተወለደ ደጃች ወሰን ሰገድ የሚባል ወንድ ልጅ ነበራቸው ። እንዲሁም ከልጃቸው ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከደጃዝማች ወዳጆ ጉበና የተወለደ በደጃዝማችነት ማዕረግ ያከበሩት አስፋ ወሰን የሚባል በእናት የልጅ ኢያሱ ታላቅ ወንድም ነበር ። ዳሩ ግን፣ ሁለቱም ቀደም ብለው ስለሞቱ አሁን በሕይወት ያሉት ኢያሱና ወይዘሮ ዘውዲቱ ናቸው ። ምንም እንኳን ዘውዲቱ ከወይዘሮ አብቺው የተወለዱ በቀጥታ ልጅ ቢሆኑም፣ በጾታ በኩል ሴት ስለሆኑና በተለይ ለነጋሢነት ለወንድ ልጅ ቅድሚያ ስለሚሰጥ፣ ዘውዲቱ ልጃቸው እያሉ ዘውዱ ለልጅ ልጃቸው ለኢያሱ እንዲተላለፍ ያደረጉት በጾታ ልዩነት ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ስለዚህ፣ አልጋ ወራሻቸውን ከማስታወቃቸው በፊት መሳፍንቱንና መኳንንቱን በግቢ ሰብበስው ሰፋ ያለ ታሪክ ጠቀስ ሐሳብ በጽሑፍ አድርገው እንደዚህ ሲሉ አስታወቁ ።

እኔ ዳግማዊ ምኒልክ . . . ይህንን ነገር ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ሕዝብና ሠራዊት አስታውቃለሁ ። ነገሩም ለሀገራችን ጥቅምና ትርፍ አገራችንን ነጻ የሚያወጣ ኃይላችንን የሚያበረታ ፤ ሀብታችንን የሚያበዛ ዕረፍትና ጤና የሚሰጠን ፣ ጠላቶቻችንን የሚያርቅ ነውና በውል ስሙት . . . የራሶችና የጭፍራ አለቆች ፍቅር ማጣት ሕዝብና ሠራዊት ክፍለ ሸዋ ትግሬ ጐንደር ጐጃም እየራሱ ሆነ . . .* ዐፄ ቴዎድሮስ ተነሱ አቀናለሁ ብለው ዠመሩት የሠራዊቱ ክፋት አበሳጫቸው ዠምረውት ሞቱ . . . ዐፄ ዮሐንስ ተነሱ መንፈሳዊነትን ዠመሩ ሊያቀኑም አሰቡ ። . . . ነገር ግን አሳባቸው አልተፈጸመም . . .

እኔም ዳግማዊ ምኒልክ በሸዋ 24 ዘመን (ዓመት) ነገሥሁ ከነገሥሁ እስካሁን አንድ ቀን አላረፍሁም ። ግራኝ ያጠፋውን ሁሉ አቀናሁ እንጂ . . . ሐረርን ሰበርሁ** ለሕዝቡና ለመንግሥቴ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማግኘት ወሰኔም የሕንድ ውቅያኖስ ሆነ . . . ውጋዴን ቆላ አሩሲ ቦረና ሲዳሞ ከምባታ ከፋ ገሙ ጅማ ጐማ ሌቃ ወለጋ ኢሉባቦር በዚህ ሁሉ ሠራዊቴ ሞላ ፤ አገሬም ነጻ ወጣ ። ችግርና መከራ ሽብርና ሁከት ጠፋለት . . . አሁንም ይኸውና በእግዚአብሔር ኃይል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆንሁ 17 ዘመኔ (ዓመቴ) ሆነ። ድምሩ 41 ነው። ይህ ሁሉ መሆኑ ኢትዮጵያ ባንድ ፈቃድ ብታድርና ባንድ ትእዛዝ (ሥልጣን) ብትሆን ነው ። አንድነት ክብረት ይጠናልና ተረቱም ከአንድ ብርቱ ሁለት ሰነፍ ይሻላል ነው የሚል ። አያቶቻችን (አክሱሞች) አንድነት ቢሆኑ ባሕርን ተሻግረው (ዓረብን) ገዙ ። ቢለያዩ ግን ግራኝ 15 ዓመት በእሳት አቃጠላቸው ። . . . ኢትዮጵያ አንድነት ሆና ከቶ ለጠላት ተሸንፋ አታውቅም ፤ በታሪክም የለ ።

ስለዚህ ምክር ነው የሰበሰብኳችሁ አንድነት እንዲጠና ብዬ ። ምናልባት ያ መለያየት ከኔ በኋላ ይመጣና አገር እንዳይጠፋ ጠላት ደስ እንዳይለው አገራችን እንዳይሔድ ሕዝባችን ወደ ግዞት (ወደ መገዛት) እንዳይገባ የሠራሁት እንዳይፈርስ ያቀናሁት መልሶ እንዳይጠፋ ብዬ ብፈራ ነው ። ዳዊት አስመ አልቦ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት ይላልና ። 1

ስለዚህ በኋላ (ከኔ ቀጥሎ) የሚነግሠውን ወራሼን ላስታውቃችሁ ከልጄ ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከራስ ሚካኤል የተወለደው ኢያሱ ነው የአልጋዬ ወራሽ ። እርሱን ዕወቁ ፤ እርሱን ተከተሉ ። 2

---

* ከዘመነ መሳፍንት ዠምሮ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ የደረሰውን ሲያወሱን ነው ።

** ሐረርን መልሼ በማዕከላዊው መንግሥት አስ ተዳደር ሥር አደረግሁ ማለታቸው ነው ።

1 የሰው ልጅ ሞትን ሳያይ የሚኖር የለም ፣ የዳዊት መዝሙር 89—49

2 የኢትዮጵያ ትእምርተ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማና ዘውዱን የጃንሆይንም ዐዋጅ የሚናገር መጽሐፍ ፣ ከኃይለማርያም ስራብዮን ፣



ይኸንኑ ቃል በስብሰባው ለባለሥልጣኖች ካስገነዘቡና በጽሑፍ ለውጭ መንግሥታት ወኪሎችም ካስተላለፉ በኋላ ፣ ጠቅላላው ሕዝብ ይኸንኑ እንዲሰማው ስለ አስፈለገ ፣ በግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ.ም. በጃንሆይ ሜዳ ታላቅ ስብሰባ ተደርጎ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ራሶች ፣ ደጃዝማቾች ፣ ሚኒስትሮችና የውጭ አገር መልክተኞች ባሉበት ከዚህ ቀጥሎ ያለው በይፋ ተነገረ ።

*ያገሬ የኢትዮጵያ ሰዎች ልጆቼ ወዳጆቼ እግዚአብሔር የገለጸልኝን ምክር ልምከራችሁ ። ዐፄ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከርሳቸው ጋር የነበረው ሰው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እደርበዋለሁ አንዱን ገድዬ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ሳይረባ ተላልቆ * ቀረ። ከዚህም በኋላ ያፄ ዮሐንስ ሰው የሆነውን የምታውቁት ነው ። ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ ጦርነት ሳይነሣበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደ ተላለቀ አይታችሁታል ።***

*አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ ፣ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር ያንዱን አገር አንዱ እደርበዋለሁ እንዳትባባሉ ። እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርኋችሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ ። እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ለሌላ ባዕድ አትሰጡትም ። ክፉ ነገር አገራችንን አያገኘውም ። ነፋስ (ጠላት) እንዳይገባባችሁ ። አገራችሁን በየአላችሁበት በርትታችሁ ጠብቁ፣ወንድሜ ወንድሜ ተባባሉ።*

*ይህን ምክር መጻፌ እኔም በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህን ያህል ዘመን ገዛሁ ። ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዲህ ምን ያህል ዘመን እኖራለሁ ስል ነው። አሁንም እኔ እንደ ተመኘሁት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ልጄን ኢያሱን ቢያቆይላችሁ ከልጄ ጋር ሆናችሁ አገራችሁን ጠብቁ፤ አደራ ብያችኋለሁ ። አደራ የሚባል ሰው የታመነ ነውና እኔም ሁላችሁንም አምናችኋለሁ። ከዚህም ከጻፍሁት ቃል የወጣ በሰማይም በምድርም የተረገመ ይሁን ። እኔም ሳለሁ ከፈቃዴ የወጣ ልጅ ረግሜአለሁ ። 1*

በሕይወታቸው እያሉ አልጋ ወራሻቸውን በይፋ አስቀድመው ማስታወቃቸው ፣ በኢትዮጵያ ያነጋገሥ ልማድ ንጉሥ በሕይወቱ እያለ አልጋ ወራሹን አያስታውቅም ፣ ያስታወቀ እንደሆነ ሌሎች ልጆቹ

---

* ካፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ዋግሹም ጐበዜ (ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ከጐጃሙ ባላባት ከደጃዝማች ደስታ ተድላ ከቤጌምድር ባላባት ከራስ ወልደ ማርያም ጋር ከየጁው ከዐሊ ፋሪስ እንደዚሁም ከደጃዝማች ካሣ (ዐፄ ዮሐንስ) ጋር ያደረጉትን ጦርነት በማስታወስ ፤

** ዐፄ ዮሐንስ መተማ ከሞቱ በኋላ ወራሼ ራስ መንገሻ ነው ብለው ፣ ቢናዘዙም የቀሩት ዘመዶቻቸው እነደጃች ቦጋለ እነደጃች ደብብ እነደጃች ሥዩም እባ ጐበዝ ያደረጉትን ጦርነት ሲያወሱ ነው ።

1 ታሪክ ዘመን ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 343—344

እኛ ለምን ቀረብን በማለት ተከታይ ይዘው ጦርነት ይቀሰቅሳሉ ። በዚህ ምክንያት የነገሥታት ልጅ ሁሉ በአምባ ግሼንና በወህኒ በግዞት እየተቀመጠ ነጋሢው ሲሞት ብቻ አለቆች ከዚያ አምጥተው ያነግሡታል ።[1] ዐፄ ዮሐንስ እንደ ቆሰሉ ወራሽ ለማድረግ የወንድማቸውን ልጅ ራስ ኃይለ ማርያምን ጥሩልኝ ቢሉ ሞተዋል አሏቸው ። "እንግዲያው ወራሼ ልጄ ራስ መንገሻ ነው" ብለው ተናዘው ወዲያው ስለሞቱ ፤ የትልቁ ራስ አርአያ ልጆች በቅርታ ከጦርነቱ ተመልሰው የርስ በርስ ውጊያ የተዠመረው ስለዚህ ነው ።

አሁን ዐፄ ምኒልክ ፤ በግልጽ ወራሻቸውን ማስታወቃቸው የዚህን ሁሉ ታሪክ በመገምገም መኳንንቱም ነገሩን ዐውቀው ከኢያሱ ጋር ተዋውቀው እንዲለማመዱና የቀረውም ሰው ሁሉ ፤ "ማንን ወራሽ ያደርጉ ይሆን ?" እያለ የአሳብ ጭንቀት እንዳይኖርበት ሲሉ ነው ። ከራስ ጉግሣ ወሌ ባለቤት ከወይዘሮ ዘውዲቱ በቀር ከማህለ ሥላሴ የሚወለዱ እነራስ ወልደ ጊዮርጊስና እነደጃች ታዬ በያለበት ስላሉ ፤ የመኳንንቱ አሳብ ወደነዚያ እንዳይበታተን ለማድረግ ነው ።

የልጅ ኢያሱን አልጋ ወራሽነት ባስታወቁበት በ1901 ዓ.ም. አልጋ ወራሹ ዕድሜያቸው 12 ዓመት ከመንፈቅ ነው ። በዚህ ዕድሜ ኢትዮጵያን ያህል አገር ብዙ ነገድ ፡ ልዩ ልዩ ሃይማኖትና ልማድ ያለበትን አገር ለማስተዳደር እንደ ማይቻል የታወቀ ነው ። ስለዚህ ለወጣቱ አልጋ ወራሽ እንደራሴ ሆኖ አገሪቱን በጊዜያዊነት የሚያስተዳድር ሲመከር ፤ ሲዘከር ምርጫው ራስ ተሰማ ላይ ወደቀ ። ከምርጫው ምክንያቶች አንዱ የራስ ተሰማ አባት ደጃች ናደው (ትልቁ ናደው) ላፄ ምኒልክ በወጣትነታቸው ጊዜ ሞግዚት ስለነበሩ ፤ አሁንም ልጅየው ራስ ተሰማ ለልጅ ኢያሱ ሞግዚት ሊሆኑ ይገባል ተብሎ ነው ይባላል ።

ስለዚህ ይኸንኑ የራስ ተሰማ ናደውን እንደራሴነት ሕጋዊ ለማድረግ ከዚህ ቀጥሎ ያለው በዐዋጅ መልክ በጽሑፍ ተነገረ ።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ። ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ያገሬ የኢትዮጵያ ሰዎች ልጆቼ ወንድሞቼ ወዳጆቼ ሆይ ። እስካሁን ድረስ ሳታስቀይሙኝ በእግዚአብሔር ቸርነት አገሬን ገዛሁ ።
>
> እኔን በውነት በመውደዳችሁና እናንተም አንድ ልብ በመሆናችሁ አገራችንን ኢትዮጵያን እስካሁን ጠላት አላጠቃትም ።

1 የግራኝ አህመድ ወረራ ፡ ፡ ምዕ 65 ፡ ገጽ 400—404



> አሁንም ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅኋችሁ ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ያልጋዬ ወራሽ ልጄ የወይዘሮ ሸዋረጋ ልጅ ከራስ ሚካኤል የተወለደው ኢያሱ ነውና ፤ ራስ ቢትወደድ ተሰማን ሞግዚት አድርጌ ሰጥቻችኋለሁ ። አልጋዬን የሚጠብቅ እሱ ነው ። ሌላ ወንድ ልጅ የለኝም ። ነገር ግን ይህንን ማድረጌ እኔ ከቤት ስውል ጊዜ እንዳትደነግጡ ብዬ ነው እንጂ ፤ እኔ ሳለሁ ልጄን ይዘን ወዲያ ወዲህ ብለን ክፉ ሥራ እንሠራለን የሚል ሰው እረግሜአለሁ ። የይሁዳ ርግመት የአርዮስ ግዝት ይድረስበት ። የኔን ቃል ያፈረሰ ሰው መሬት ይክዳው ፤ ጥቁር ውሻ ይውለድ ፤ ያሳደግኋችሁም የሾምኋችሁም መኳንንቶች ወታደሩም ትልቁም ትንሹም ከኔ ፈቃድ የወጣ ሰው ረግሜአለሁ ። ከኔም በኋላ ልጄን ያልተከተለ ሰው ረግሜአለሁ ። እሱም ከናንተ ከባቶቹ ከወንድሞቹ ፈቃድ እንዳይወጣ ያላግባብ ክፉ ነገር እንዳያደርግ ልጄንም ኢያሱን የሰጠሁትንም ሞግዚት ራስ ቢትወደድ ተሰማን ረግሜአለሁ ።[1]
>
> ጥቅምት 20 ቀን 1902 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

1 ዝክረ ነገር ፡ 2ኛ እትም 1962 ዓ. ም. ገጽ 509 ።



ልጅ ኢያሱ በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን

ከሞራስ ደኮፔ መጽሐፍ



ራስ ተሰማ ናደው
ከሞራስ ኦቦጌ

# ምዕራፍ ሰባ ሦስት

## የመለያየት ስሜት—የዋግሹም አባተና የደጃዝማች አብርሃ ጦርነት

"ወንድሜ ወንድሜ ተባባሉ ነፋስ በመካከላችሁ እንዳይገባ" ብለው ዐፄ ምኒልክ መሳፍንቱንና መኳንንቱን የተማጠኑት ፥ ከእርሳቸው ሕመምና ሞት በኋላ በኢትዮጵያ እንደ መጥፎ ዕድል ሆኖ የተለመደው የርስ በርስ ጦርነት እንደሚነሣ በመሥጋት ነው ። በእርግጥም ከእርሳቸው በሕመም መዳከምና ሞት ዠምሮ የቀጠለው የርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ሲታይ ግምታቸው ትክክል ነበር ማለት ይቻላል ።

ዐፄ ምኒልክ ፥ "አልጋ ወራሼ ኢያሱ ነው ። ለርሱም እንደራሴ ራስ ቢቶደድ ተሰማን አድርጌያለሁ" ብለው ሲያውጁ ፥ በርሳቸው የትዕግሥትና የመልካም አመራር መንግሥት ዙሪያ የተሰበሰበው ሁሉ ፥ "ወደፊት እኚህ ሰው ታመው እቤት ሲውሉ ጭራሹንም ሲሞቱ ምን ይደርስብን ይሆን? ከእርሳቸው በኋላ እንደ ርሳቸው የሚያስተዳድረን ማነው" የሚል የመንፈስ ሁከት በሁሉም ላይ እንደሚደርስ ይታወቃል ። የራስ ተሰማ እንደራሴነትና የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት በራስ ሚካኤል ዘንድ አለኝታንና መተማመንን ሲያሳድር ፥በሌሎች ዘንድ በተለይ በእቴጌ ጣይቱና በወገኖቻቸው በነራስ ወሌ ዘንድ ፥ በሸዋ መኳንንቶች ዘንድና በሰሜን በኩል በትግሬ መኳንንት ዘንድ የኢያሱ አልጋ ወራሽነት ልባዊ አቀባበል ማግኘቱ አጠያያቂ ጉዳይ ሆኖአል ።

በእርግጥም ራስ ቢቶደድ ተሰማ ፥ "እንደራሴነቱ በዐዋጅ ከተሰጠኝ ወጣቱን አልጋ ወራሽ ይዤ እሱን እየመከርሁና እያሠለጠንሁ ፥ የመንግሥቱን ሥራ እመራለሁ" ብለው ወገኖቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ይዘው ሲነሡ ፥ እቴጌ ጣይቱ ደግሞ ወገኖቻቸውን ይዘው፥ "ባለቤቴ ምንም ሕመም ቢዠምራቸውና አልጋ ወራሻቸውን ቢናገሩም ፥ እንደራሴም ቢሾም የንጉሠ ነገሥቱ ትንፋሽ እስከ አለ ድረስ ሥልጣናቸው አይሻርም ። በርሳቸውም ስም እኔ አስተዳድራለሁ፤ አልጋ ወራሹም ጊዜውን ይጠብቅ " የሚል አቋም ነበራቸው ። ሁለቱም ወገ

ኖች የየራሳቸው ደጋፊዎች አሏቸው ። የእቴጌ ወገኖች ዋነኞቹ ታናሽ ወንድማቸው ራስ ወሌና ልጃቸው ደጃዝማች ጉግሣ ፤ ሌሎችም የሩቅና የቅርብ ዘመዶች እነደጃዝማች አያሌው ብሩ ናቸው ። ሲያያዝ በመጣው አከብሮት የሸዋዎቹ ባለሥልጣኖች ንጉሠ ነገሥቱም ሕመሙ በ1901 እና በ1902 ዓ. ም. ላይ ስላልተሻላቸው የእቴጌይቱን ሥልጣን ለጊዜው ለመቃወም የደፈረ የለም ።

ከራስ ተሰማ ወገን አብዛኛው የሸዋ መኳንንት ፤ እቴጌን ማከበራቸውና መታዘዛቸው ባይቀርም ፤ በእንደራሴነት አገሪቱን ለመምራት ኃላፊነት ለራስ ተሰማ እንደተሰጠ በማመን ወደራስ ተሰማ ያዘነበሉ ይመስላል ። በትግሬም ተወላጆች እነራስ ስብሐት ፤ እነደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባሪያ ጋብር ፤ እነደጃዝማች አብርሃ አርአያ ይኸንኑ መስመር የተከተሉ ይመስላል ። ሌላው የዚህ ዘመን ቀንደኛው ባለሥልጣን የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፤ ደጃዝማች ባልቻን ጨምረው ከሁለቱም ወገን ነጻ ሆነው የዘብ አብራጅነትንና የገላጋይነትን መስመር በመያዝ እቴጌን አይዞዎ ፤ ከርስዎ ፈቃድ አንወጣም ተሰማን መታገሥ ይሻላል እያሉ የሚመከሩ ይመስላል ። በተለይ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የዚህ ዘመን ባለሥልጣንነታቸው በሁሉም ዘንድ ተፈሪነትና ተሰሚነት ያላቸው መሆኑ የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፤ በማናቸውም ረገድ ራስ ተሰማም እቴጌይቱን መግፋቱ እያሰቀቃቸው ፤ የቀሩትም በመፍራትና በማክበርም በንጉሠ ነገሥቱ አጠገብ ሚስትም ፤ አስታማሚም ሆነው ከሚገኙት ከእቴጌይቱ ፈቃድ የሚወጣ ለጊዜው አልተገኘም ። እቴጌይቱም በንጉሠ ነገሥቱ ስም እያደረጉ የራሳቸው ወገን የሆኑትንና ሌሎችንም ለመሳብ ሹም ሽር ማድረግን ይቀጥሉ ዠመር ። በዚሁ መሠረት ቀደም ብሎ ራስ መኰንን ስለሞቱ ልጃቸው ደጃዝማች ይልማ የሐረርን ግዛት ከያዙ በኋላ ፤ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆዩ ስለአረፉ ፤ ለደጃዝማች ባልቻ ተሰጥቶ ነበር ። በመጨረሻ በእቴጌዪቱ ፈቃድ የሐረር ግዛት በ1902 ዓ.ም ለደጃዝማች ተፈሪ ተሰጠ ። እንደዚሁም ቀደም ብሎ ራስ ስብሐትም በሐረር ከራስ ሙኰንን ዘንድ በግዞት ቆይተው ከተመለሱ ወዲህ አጋሜን አስመርቀው ወደ አገራቸው ተመልሰው የመንግሥቱ ታዛዥና ፈቃድ ፈጻሚ ሆነዋል ።

ቀጥሎም በትግሬ ራስ ወሌ ተሾመው እንደቆዩ ፤ አሁንም በእቴጌዪቱ ፈቃድ ቤጌምድር ለራስ ወሌ ተሰጠና ደጃዝማች አባተ ግንቦት 1 ቀን 1901 ዓ. ም. ዋግሹም ተብለው ላስታን በግዛት ፤ ትግሬን



በቆራጭነት* ተሾሙ ። በእርሳቸው ውስጥ ደጃዝማች አብርሃ አርአያ እንደርታን ተሾሙ ።

አብርሃ የትልቁ የራስ አርአያ ልጅ ፤ የደጃዝማች ደብብና የደጃዝማች ተድላ አባ ጉበን እንዲሁም የወይዘሮ አምለሱ** ወንድም ናቸው ። ታላቅ ወንድማቸው ደብብ ካፄ ዮሐንስ ከድተው ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር ባለሟል በነበሩበት ሰዓት ለኢጣልያኖች አመልክተው አብርሃ ወደ ኢጣልያ አገር ሔደው በቶሪኖ ከተማ የኢጣልያ ቋንቋ በጽሕፈትም ጭምር ሲማሩ ቆይተው እንደተመለሱና ። የዓድዋ ጦርነት እንዳለቀ በ1888—89 ዓ. ም. ወጣቱ አብርሃ አስተርጓሚ ሆነው ማገልገላቸው ይታወቃል ።

ከዚያ በኋላ ፤ አዲስ አበባ መጥተው ካፄ ምኒልክም ከተላመዱ ወዲህ ፤ የደጃዝማችነት ማዕረግ አግኝተው በራስ መንገሻ ሥር በትግሬ በአንዱ ክፍል በእንደርታ ቆይተዋል ። ባሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ሆነው ደጅ ሲጠኑ በዋግሹም አባተ ውስጥ የእንደርታ ግዛት ተሰጣቸው ። በዋግሹም አባተ ውስጥ መሆናቸው ቅርታ እንደ ፈጠረባቸው በዚህ ላይ ዋግሹም አባተ በዕድሜያቸው በሥልጣናቸውም ብልጫ ሰበብ "አንተ" እያሉ ሲያነጋግሩዋቸው ፤ "ለምን አንቱ አላሉኝም" በማለት በዚህም ቆጭቷቸው ነበር ይባላል ።

የሆነ ሆኖ ፤ ቁጭታቸውን በልባቸው እንደያዙ አባተም አብርሃም በ1901 ዓ. ም. ግንቦት 1 ቀን ቢሾሙም ክረምቱ ስለ ተቃረበ ፤ የክረምቱን ወራት አዲስ አበባ አሳልፈው አብረው ወደ ግዛት አገራቸው ጉዞ ዠመሩ ። በመንገድ ላይ እያሉ አብርሃ አስቀድመው ሔደው ላዲሱ ዋግሹም መስተንግዶ እንደሚያዘጋጁ አስመስለው በመሰናበት መቀሌ ከደረሱ በኋላ ፤ መሸፈታቸውንና ፤ ለመዋጋት ጦር ማዘጋጀታቸውን አባተ ሲሰሙ ወደ አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ለንጉሠ ነገሥቱም ፤ ለእቴጌይቱም የአብርሃን መሸፈት አስታወቁ ። ለትግሬም ሕዝብ "የአብርሃ በመንግሥት ላይ መሸፈት ከአሰል የሚገባው የጨው ግብር ገቢው የመንግሥት በመሆኑ ለኔ ለምን ቀረብኝ በማለት ነው ። አሁን በምኒልክ መንግሥት ላይ መሸፈቱ ንብረትህን ከብትህን ሚስትና ልጅህን ለማስጠፋት

* ይኸም ማለት በቀጥታ ትግሬን በበላይነት እንዲያስተዳድሩ ማለት ነው ።

** አምለሱ የራስ አሉላ ባለቤት ናቸው ።

ነው እንጂ የሚረባው ነገር የለም ። ለመንግሥት ታማኝ የሆንክ ወደኔ ና'' የሚል ዓዋጅ አናገሩ ።

ስለዚህም መልስ ደጃዝማች አብርሃ ፣ ''እኔ በምኒልክ መንግሥት ላይ አልሸፈትሁም ፤ እስከሁንም ድረስ 12 ዓመት (1888 1900 ዓ. ም.) ሙሉ በቅንነት እያገለገልሁ ከግዛቴም ያገባሁት ግብር 160,000 የማሪያ ትሬዛ ብር ይሆናል ። ባገልግሎቴም ሌላ ግዛት ይጨመርልኛል ስል የራሴ የሆነው ቀረ ። በዚህም ላይ እኔ አንተ መባልን አልለመድሁም'' የሚል መልስ ሰጥተው የጦር ዝግጅታቸውን ይቀጥሉ ዠመር ።

ካርሎ አናራቶሬ የሚባል የኢጣልያ ተወላጅ እንደ ቆንሲልም እንደ ሐኪምም ሆኖ በዚህ ወቅት በመቀሌም በዓድዋም በመቀመጥ ከነደጃዝማች ሥዩም መንገሻና ከነራስ ስብሐት ፣ ወደ ደሴም እየመጣ ከራስ ሚካኤል ጋር ተላምዶ ነበር ። በዚህ የመቃቃር ጊዜም እዚያው ነበርና ስለ ተቀሰቀሰው ጦርነት አዠማመርና ፍጻሜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በመጽሐፉ አስፍሯል ።

> . . . ከውጊያው በፊት የሁለቱ ወገን ጦር ሠራዊት ከተቀራረበ በኋላ አባተ ለአብርሃም ፣ በዚህ በትንሽ ነገር በሥላሴ ይገርሃለሁ የክርስቲያን ደም አይፍሰስ ፣ የሚገባህን እንድታገኝ እኔ ስለአንተ ለንጉሡ እነግርሃለሁ' ብለው ቢልኩ አብርሃ ፣ የነበረውን ሙሉውን ግዛቴን ይመልሱልኝ ፤ በግዛቴም ራሴ ለማስተዳደር ነጻነት ይሰጠኝ ፤ ቢፈልጉ አክሱምን ያስቀሩ ፤ ከዚህ በኋላ ምሕረት እንዲያደርጉልኝ ይሁን' የሚል መልስ ሰጡ ። አባተ ሁኔታውን ወደ አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ከእቴጌም ከንጉሠ ነገሥቱም ተነጋግረው ነበረ ። ከእቴጌዪቱም ፣ 'የጠየቅኸው ቀላል ነገር ነው የሚቸግር ነገር የለም' የሚል ቃል ለአብርሃ ቢመጣም ፣ እርስ በርስ ባለመተማመን ሁለቱ ወገኖች ለውጊያ ዝግጅታቸውን ቀጠሉ ። ከደጃች አብርሃ ወገን ሦስት የበታች ሹማምንት 200 ጭፍራ እንደያዙ ከድተው መጥተው ለዋግሹም አባተ ገቡላቸው ። በአብርሃ ጎን ወንድማቸው (ዘመዳቸው) ደጃች ረዳ ከሁለት መቶ ወታደር ጋር ሲገኙ ፣ ዋግሹም አባተን ለመርዳት የትግሬ መሆኔው ገኘ ደጃዝማች አበራና የራስ ወሌ የጦር መኰንን ፊታውራሪ አቦዬ ከየጁ የሁብልን ጦር ይዘው ገቡ ። ራስ ስብሐትም ከአጋሜ ወደ አባተ መደረባቸውን. . .

የኢጣልያኑ ጸሐፊ ካወሳ በኋላ ስለ ውጊያው እንደዚህ ሲል ይቀጥላል ።

> እ.ኤ.አ. በጥቅምት 8 ቀን 1909 (መስከረም 29 ቀን 1902 ዓ.ም.) አብርሃ ከነሰዋቸው ከእሽንጌ ሐይቅ በስተደቡብ ባለው ጉብታ ላይ እንደ ሰፈሩ አባተ በኮረምና በወፍላ ምሥራቅ መካከል እየመሸጉና እየተደራጁ ሲጠባበቁ ፣ አብርሃ ሉሲቱን ተጠግተው ሳይታሰብ በአባተ ጦር ላይ ሊነጋጋ ሲል ጦርነት ከፈቱ ። ከዚያ አባተ በጥድፊያ ወደ ጦሩ ግንባር ሔደው በ200 ሜትር ርቀት በመትረየስና በጠመንጃ ሲዋጉ ቆይተው ፣ በመጨረሻም የጨበጣ ጦርነት አድርገው ከተዋጉ በኋላ ፣ ደጃች አብርሃ ከመጀመሪያው ላይ ያሸነፉ መስሏቸው ምርኮኛ መቀበል ዠምረው

እንደነበረ ያመለክታል ።*

> ዳሩ ግን ፣ የራስ አባተ ወገኖች መልሰው በኃይል በማጥቃታቸው ከሦስት ሰዓት ውጊያ በኋላ የደጃች አብርሃ ጦር ተሸንፎ ወደ ራያና አዘቦ ሽሽት ሲጀምር የቀረውም ተማረከ ። አብርሃና መኳንንቶቻቸውም አብረው ተማረኩ ።

ጸሐፊው በሁለቱ መካከል የተደረገው የጠመንጃ ፣ የመትረየስና የጨበጣ ጦርነት ያስከተለው የሬሳና የቁስለኛ ብዛት ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የውስጥ ጦርነት መሰል የሌለው መሆኑን አውስቶአል ። በጸሐፊው ግምት ከጠቅላላው ተዋጊ ወታደር 31% እጦርነቱ ሜዳ ላይ መቅረቱን ያመለክታል ። ከዚሁ አያይዞ ጸሐፊው በራስ ሚካኤልና በራስ አባተ የችኮላ ልመና በቶሎ ወደ ጦርነቱ ሥፍራ ለሕክምና መሔዱንና ከመንግሥት ወገን የቆሰሉትን ወታደርና ሹማምንት ለማከም ከቁስለኛው ብዛትና ከመድኃኒቱ ማነስ የተነሣ መቸገሩን በዝርዝር ያወሳል ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ ዋግሹም አባተ ደጃዝማች አብርሃን ይዘው ወደ አዲስ አበባ እንደ መጡ ትንሽ ቆይተው የራስነት ማዕረግ አገኙ ። ደጃዝማች አብርሃም ሰላሌ በሸንኩርት ዋሻ ታስረው ተቀመጡ ።

አብርሃም በዋግሹም አባተ የበላይነት የትግሬ ግዛት ሲሰጣቸው ቅርታቸውን እንደያዙ እሺ ብለው በመሔድና በኋላ በመሸፈት ፈንታ ከጦርነቱ ትንሽ ቀደም ብለው ለአባተ የገለጡትን ቅርታ እዚሁ አዲስ አበባ ለእቴጌ ጣይቱ ወይም ለእንደራሴው ለራስ ተሰማ ገልጠው የማይለወጥም ሁኔታ ከገጠመ ፣ እዚሁ እቤተ መንግሥቱ ደጅ እየጠኑ ቢቆዩ ኖሮ ሰው ሳያልቅ ለችግሩ አንድ መፍትሔ ሊገኝ በቻለ ነበር ። መቼም በዕድሜም በሥልጣንም አባተ እንደ ሚበልጡ ቢታወቅም ፣ አባተ አንተ ብለው ሊያነጋግሩአቸው ከደፈሩ እሳቸውም አንተ ብለው ማነጋገር ነበር እንጂ ይኸ ሰበብ ሆኖ ለብዙ ሰው ሕይወት መጥፊያ ምክንያት ሊሆን ባልተገባ ነበር ።

---

* በዚሀ ጊዜ ከተማረኩት ውስጥ በኋላ ራስ የተባሉት አድፍርሰው ነበሩ ይባላል ።

1. In Abyssinia- Carlo Annaratore, PP.99-114.

በዚሁ ዘመን ደግሞ ፤ ይኸን በመሳሰለ ወይም በሌላ ምክንያት
አንዱ ቀንደኛ ሲሸፍት በርሱና በመንግሥቱ ወታደር መካከል ጦር
ነት ተደርጎ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወታደሮች ሕይወታቸው ሲጠ
ፋና አካላቸው ሲጐድል ፤ ጥፋተኛው አለቃ ይኸን በማድረጉ የሚገባ
ውን የሞት ቅጣት ወይም ረዘም ያለ የእስራት ዘመን አያገኘውም ።
ይኸም ሁኔታ ሌሎቹን በሸፍትነት እንደሚጋብዝ ግልጽ ነው ።

ዳሩ ግን ፤ በቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ዘንድ ከምኒልክ አቅ
ዋም የተወረሰው ያስተዳደር ዘዴ በኃይል ሳይሆን በትዕግሥት ችግ
ርን ማሳለፍ ስለሆነ ፤ በቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ዘንድ ፤ "እገሌ
አጠፋህ ብለን በሞት ብንቀጣው ወገኖቹ እነገሌ ይሸፍታሉ ። እነር
ሱን ለመቅጣት ጦር ሲላክ ሌላው ክፍለ ሀገር ይሸፍታል ። ይኸም
ሲሆን ፤ የአገሪቱ ጠቅላላ ጸጥታ ይናጋና የውጭ ጠላት ባገራችን
ይገባል " የሚለው ሥጋት በምኒልክና በመኳንንቱ ዘንድ እያንዣ
በበ ፤ በዳዩ ሁሉ የሚገባውን የሞት ወይም ለጥፋቱ ተመሳሳይ የሆነ
የረዥም ዘመን እስራት ሳያገኝ ይቀራል ። ምስኪን ባላገር በዘረፋ
ተጐድቶና የዋሁ ወታደር በውጊያ ላይ አልቆ ሳለ ፤ ሰውዬው ከጥ
ቂት የግዞት ዘመን በኋላ እንደ ሁኔታው በአጋጣሚ ሌላ ባለሥልጣን
ሲነሣ እሱም አብሮ ሊነሣና ሊሾም ፤የቀድሞ አጥቂውንም መልሶ
ሊያጠቃ ይችላል ።

ደጃዝማች አብርሃ ፤ ከላይ ዘራቸውን ከዓድዋው ከራስ ስሑል ሚካ
ኤል ፤ ከእንደርታው ከራስ ወልደ ሥላሴ ፤ ከተስፋ ኢየሱስና ከሹም
አጋሜ ወልዱ የሚቆጥሩ ናቸው ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከነበሩት
ካሤ ዮሐንስ ጋር የታናሽና የታላቅ ልጆች ናቸው ። ከዚህ የተነሣ በአ
ጋሜ ፤ በእንደርታና በተምቤን ባላባትነታቸው ግልጽ ነው ። ስለዚህ
እንደዚህ ያሉትን ባላባቶች በጥፋታቸው መጠን አግባብ የሆነ
ቅጣት መስጠት በዚህ ዘመን ላሉት አስተዳዳሪዎች አሥጊ ነው ።
" ሺ አውል ከሚሞት ፤ ሺ ይሙት " የሚባለውን ያስተዳደር ፍል
ስፍና ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ራስ ስሑል ሚካኤል ብቻ ሽረው ነፍስ
ቢገድሉ በልጆቻቸው ላይ የሞት ፍርድ ፈርደዋል የሚባለው ፤ ለዚያን
ዘመን ኢትዮጵያውያን ብዙ ነገድ የተደባለቀበትን ሰፋ አድርገው
ለያዙ አዲስ ያገር አስተዳደር ጐጆ ወጭዎች አያገለግልም ።

በዚህ ምክንያት ፤ አብርሃ ያን ሁሉ ሰው አስጨርሰው እጃ
ቸውን ለአባተ ከሰጡ ወዲህ ከፍ ያለ ቅጣት ሳያገኙቸው ሰላሌ
በሸንኩርት ዋሻ በግዞት ጥቂት ጊዜ ቆዩ ። በኋላም ንጉሠ ነገሥቱ
ፀርፈው በራስ አባተና በልጅ ኢያሱ መካከል በ1906 ዓ. ም. ጠብ
ተነሥቶ አባተ በራስ ሚካኤል እጅ ወደ አፍቀራ ተልከው ሲታሰሩ



አብርሃ ከሁለት ዓመት ግዞት በኋላ ተፈትተው ያገር ግዛት ሚኒስትር
ሆኑ ። ያንጊዜ ነው " ክትክት ብላ ሳቀች መሬት ጥርስ አውጥታ ፤
አባተ ሲታሰር አብርሃ ሲፈታ " የተባለው ። ከዚያ ደግሞ በ1909
ዓ.ም. በሰገሌ ጦርነት ኢያሱና ሚካኤል ሲወድቁ ለአብርሃ አዲስ
የመውደቂያ ፤ ለራስ አባተ የትንሣኤ ሁኔታ ተጠፈረ ።

# ምዕራፍ ሰባ አራት

## የራስ ቢትወደድ ተሰማና የእቴጌ ጣይቱ የሥልጣን ፍልሚያ
## የእቴጌይቱ ከሥልጣን መወገድና የራስ ተሰማ ዕረፍት

ጣይቱ በነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም. ሲወለዱ በነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም. የተወለዱትን ምኒልክን አራት ዓመት ይበልጧቸዋል ማለት ነው ። ምኒልክ የሸዋና የወሎ ንጉሥ ሆነው በነበሩበት ሰዓት ከአምባ ጫራ በጐጃም በኩል ሲያልፉ ደብረ መዊዕ ላይ ተገናኝተው ፣ ጣይቱ ወደ ሸዋ ከመጡ ወዲህ አንኮበር መድኃኔ ዓለም ቀርበው በ1875 ዓ.ም. ከምኒልክ ጋር ከተጋቡ በኋላ ፣ ንጉሥ ምኒልክ በ1882 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ ፣ ወይዘሮ ሲባሉ የቆዩት ጣይቱም ሥርዓተ መንግሥት ተደርጎላቸው እቴጌ መባላቸው ባለፈው ተጽፏል ።

ከዳኄ ምኒልክ ከተጋቡ ገሮምሮ በፖለቲካው ፣ ባስተዳደሩም እየገቡ ችግሩንም ፣ ደስታውንም አብረው እየተካፈሉ እስከዚህ ደርሰዋል ። ጣይቱ የቤት ጾታ ቢሆኑም ፣ የጦርነትም ፣ የፖለቲካም ፣ ያስተዳደርም አስተያየታቸው ከወንድ ቢበልጥ እንጂ አያንስም ።

ባልና ሚስቱ ተከባብረው ፣ ሥልጣን ተካፍለው ፣ በጭፍሮቻቸው ዘንድ ተፈርተው ፣ ተከብረውና ተወደው ሁለቱም የተሻለ እዱኛ አሳልፈው በደስታ ኖሩ ። አሁን ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም ተዳከመው ራስ ተሰማ እንደራሴ ከተባሉ በኋላ ፣ "የአገሪቱ አስተዳደር በኔ በእንደራሴው መመራት አለበት" በሚሉበት ሰዓት ፣ እቴጌይቱ ደግሞ "ባለቤቴ ምንም ሕመም ቢያድርባቸው ፣ አልጋ ወራሻቸውን ቢያስታውቁም ፣ እንደራሴ ቢሾሙም ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ትንፋሽ አለ ድረስ በርሳቸው ስም አስተዳዳሪነቱ ከኔ እጅ አይወጣም ፣ አልጋ ወራሹም ጊዜውን ይጠብቅ" የሚል ስሜት አደረባቸው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ቀድሞ ቤተ ዘመዶቻቸውን ከሸዋም ከሌላም መኳንንት ጋር እያጋቡ ወገን ከማበርከታቸው በቀር አሁንም ንጉሠ ነገሥቱ በታመሙበት ሰዓት ደጃዝማች ተፈሪ ሐረርን የተሾሙትና የወንድማቸው የራስ ወሌ ልጅ ደጃዝማች ጉግሣ ራስ ተብለው ቤጌምድርን የተሾሙት ፣ ዐዋጁ በታማሚው ንጉሠ ነገሥት ስም ቢሆንም ፣ ትክክለኛው አሻሿም ግን በእቴጌ ጣይቱ ፈቃድ ነው ። የጐጃሙን

የደጃዝማች ሥዩምንም ወገንነት ለማግኘት ሲሉ ሥዩም ሲመኙት የኖሩትን ዳሞትንና አገው ምድርን ከራስ መንገሻ አቲከም ላይ ወስደው የራስነት ማዕረግ ጨምረው ሰጡዋቸው ። ስማቸውም ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ሥዩም መሆኑ ቀርቶ ራስ ኃይሉ እየተባሉ ይጠሩ ዠመር። በዚህ ጊዜም እቴጌይቱን ለማስደሰት ራስ ኃይሉ የራስ ቢቶደድ መንገሻን ልጅ ወይዘሮ አስካለ ማርያምን ፈትተው የእቴጌ ጣይቱን ዘመድ ወይዘሮ አስለፈች ወንዴን አገቡ ።ራስ ቢቶደድ መንገሻ ባዬ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በሁሉም እየገቡ የሚሠሩና ምክራቸውም ተደማጭ ነበር ። በመጨረሻም በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ አገራቸውን አገው ምድርን ተሾመው ሔደው ነበር ።

ራስ ቢቶደድ መንገሻ ፡ በዚህ ጊዜ እርጅና ተጭኖአቸው በቤታቸው እንዳሉ ግዛታቸው ለራስ ኃይሉ የመሰጠቱን ወሬ ሲሰሙ ፡ "በውነት ጌታዬ ምኒልክ ነፍሱ እያለ እንደዚህ አይደረግም ሞቷል እንጂ "ብለው እንዳለቀሱ[1] ተክለ ሥላሴ መዝግበውታል ።

የሆነ ሆኖ ፡ እቴጌ ጣይቱ ይኸን ሁሉ ሹም ሽር ሲያደርጉ ፡ በ[illegible] ለበት ወገኖቻቸውን ሲያጠናክሩ ፡ ለጊዜው ራስ ተሰማም እነፊታውራሪ ሀብተ ጊርጊስም ከቀድሞ ዠምሮ በመጣው አክብሮትና [illegible] ሐት የተነሣ እቴጌይቱ የሚያደርጉትን በቅርታም ቢሆን ከመ[illegible] በቀር ፊት ለፊት ለመቃወም የደፈረ አልነበረም ። በኋላ ግን ፡ [illegible] አድሮ መቀያየማቸው አልቀረም ።በመካከሉ የእቴጌ ወንድም ራ[illegible] ወሌና የአልጋ ወራሹ አባት ራስ ሚካኤል ፡ አምባሰል ላይ ለ[illegible] ርነት በተሰለፉበት ሰዓት እቴጌይቱና ራስ ተሰማ የየራሳቸውን ጠብ ወደ ጎን አድርገው ፡ እቴጌም ራስ ወሌን እንዲቆጡ ራስ ተሰማም ራስ ሚካኤልን እንዲያስታግሡ ደብዳቤ ይጻጻፉ ዠመር ።

የራስ ወሌ ልጅ ራስ ጉግሣ ፡ ከአዲስ አበባ ወደ ቤጌምድር የተላከ አንድ ሰው ስለ ገደሉ ፡ "ባለ ደሞቹ ክስ አቅርበዋልና መጥተህ ተነጋገር" የሚል ከነራስ ተሰማ ቢላክ ፡ ጉግሣም አክስታቸውን በመተማመን "አልመጣም " ብለው እምቢ አሉ ። ይኸም ራሱ በእቴጌይቱና በነራስ ተሰማ መካከል ትልቅ ውዝግብ ፈጠረ ። ተሰማ "ተከሳሹ ጉግሣ ቀርቦ መልስ ይሰጥ " ሲሉ ፡ እቴጌይቱ "አይመጣም " በማለት የሁለቱ ልብ መሻከር ዠመረ ።

1. የእጅ ጽሑፍ ፡ ገጽ 196—197



በዚህ መካከል ደግሞ ፡ "እቴጌይቱ ወገኖቻቸውን ይዘው መንግሥት ከአዲስ አበባ ወደ ጐንደር አዛውረው ለመንገሥ ወጥነዋል ፤ በአዲስ አበባ ያሉትን የውጭ አገር መንግሥትታት ወኪሎች 'ደግፉኝ 'የሚል ደብዳቤ ጽፈዋል'' የሚለው ወሬ እየገነነ ሲሔድ ፡ ራስ ተሰማ በአሉበት በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት መጋቢት 11 ቀን 1902 ዓ.ም ስብሰባ ተደርጎ ብዙ ውይይትና የአሳብ መለዋወጥ ከተደረገ በኋላ ፡ በመጨረሻ እቴጌ ጣይቱ ከአስተዳደር ውጭ ሆነው በግቢ ተቀምጠው ጃንሆይን በማስታመም ይወሰኑ ተብሎ ተቆረጠ ።

ይኸንንም ውሳኔ ሔደው የሚነግሩ ራሳቸው ራስ ቢቶደድ ተሰማ ሆነው ሌሎችም ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባሪያ ጋብር ፡ ፊታውራሪ ወሰኔ ትርፌ (ደጃዝማች) ፡ ደጃዝማች ብርቄ ጫጫ ፡ ደጃዝማች መንገሻ ተደልድለው ወደ እቴጌ ተልከው ይኸንኑ ውሳኔ መጋቢት 12 ቀን በግልጽ ነገሩዋቸው ። በዚያን ጊዜ እቴጌይቱ በንዴት ፊታቸውን ወደ ራስ ቢቶደድ ተሰማ አዙረው ፡ "ይህን ነገር ሁሉ ያበብከውና ያደረግኸው አንተ ነህ . . .ሁሉንም ነገር በእርግጥ ሰምቸዋለሁ . . . ገና አስቀድሜ እኔ ጃንሆይን አስታምማለሁ ፤ የመንግሥቱ ሥራ ይቅርብኝ ብልህ . . የመንግሥቱን ሥራ እየሠሩ እርስዎ ካላሳመሩን እኛ ምኑን እናውቀዋለን . .ብትለኝ ሠርቼ የምጠቅም ከሆነ በሚቻለኝ እረዳለሁ አላልኩህም . . .ላንተስ ሳላማክር ምን የሠራሁት ሥራ አለ ?" ብለው ወረፉቸው ።አብረው የቆሙትንም መኳንንት ግማሹን በመልኩና በአለባበሱ ፡ የቀረውንም ባለፈው በጠባዩ ያሳየውንና የሠራውን እየጠቀሱ የስድብ ናዳ አወረዱባቸው ።

የሆነ ሆኖ ፡ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የእቴጌ ሥልጣን ቆሞ የራስ ተሰማ ሥልጣን ተረጋገጠ ። በዚያን ዘመን ያሉት ታላላቆቹ እነ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፡ እነራስ አባተ ፡ እነ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፡ ጳጳሱም ፡ እጨጌውም ከራስ ተሰማ ጋር ተባበሩ ። እቴጌይቱም ከግዛቸውም ሥልጣን ተወግደው ከእንጀራ ልጃቸው ከወይዘሮ ዘውዲቱ ጋር ሆነው ትርታና ቁጭታቸውን በልባቸው እንደያዙ ንጉሠ ነገሥቱን በማስታመም ተወሰኑ ።

ነገር ግን ፡ ራስ ቢቶደድ ተሰማ በዚህ ሁኔታ ጊዜያዊ ደስታ አግኝተው እንደ ልባቸው በመሾም በመሻር ሥልጣናቸው የተሟላ ቢሆንም ፡ ሙሉ ደስታ ለማግኘት አልቻሉም ።ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽ እንደ መሆናቸው መጠን ፡ በርሳቸው ሥልጣን ለመጠቀም የፈለጉ ብዙዎቹ በዙሪያቸው ተሰበሰቡ ።በዚህም ላይ ራስ ተሰማ ኢያሱን ፡ "ይኸን ልበስ ይኸኛው ባንተ ላይ አያምርም ፤ በፍርድ ሸንጎ ረግተህ ተቀመጥ ፡ ሥነ ሥርዓትና ፍርድ ተማር" በማለት ከኢያሱም

ከወገኖቻቸውም ጋር በየዕለቱ ጠብና ክርክር ሆነ ። "ወደፊት የሚነግሠውም ያው ኢያሱ ነው ። ተሰማም በዕድሜ ገፍተዋል ። እሳቸውም ሲሞቱ እኛ እንደራሴ እንሆናለን "በሚል ተስፋ ወደ ልጅ ኢያሱ እየተደረቡ ነገርና ተንኮል በመሥራት ራስ ተሰማን ጤና ነሷቸው ። በምኒልክና በጣይቱ የተገነባውም ጠንካራ መንግሥት በዚህ ጊዜ መዋዠቁ ስለተሰማ ተመልካችን ሁሉ ሁኔታው አሳዘነ ። ሁሉም "አዬ ጉድ ! የተወዳጁ ንጉሣችን የምኒልክ መንግሥት እንዲህ ይሁን" እያለ መጸጸት ዠመረ ።

ስለዚህ እቴጌ ጣይቱ ፣ በመጋቢት ወር 1902 ዓ.ም. ከሥልጣን እንደ ተወገዱ ራስ ተሰማም በሚቀጥለው ዓመት 1903 ዓ.ም. በመጋቢት ወር ሥጋቱም ፣ ብስጭቱም እንዳደረባቸው ታመው ባጭር ጊዜ ውስጥ በሚያዝያ 3 ቀን ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ተኩል ዐርፈው ደብረ ሊባኖስ ወስደው ቀበሩዋቸው ። [1] በርሳቸውም ሞት ኢያሱና ወገኖቻቸውም ፣ "ከሞግዚት ነጻ ሆነን የልባችንን እንሠራለን " በማለት ለብዙ ጊዜ የማይቆይ ደስታ አደረባቸው ። ለአማሚታቸውም ብዙ ትርጉም ተሰጠው ። ከዚህም መካከል አንዱ ፣ "በልጅ ኢያሱ ተገፍተው ባለቤታቸው ወይዘሮ በለጥሻቸው በመድኃኒት ገደሏቸው" የሚለው ሐሜት ይገኝበታል ።

1. መልካም ቤተሰቦች ቢቶደድ መኰንን እንዳልካቸው ምዕ 5—6 ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቀ.ኃ.ሥ. ገጽ 16—18



# ምዕራፍ ሰባ አምስት

## በየግዛታቸው ያሉት ባለሥልጣኖች — የወጣቱ የልጅ ኢያሱ ሥልጣን አያያዝ— የራስ አባተ ተቃውሞና እሰራት — ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ቀኛዝማች ደቻሳ

የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት እንደ ታወጀ ፣ ባፄ ምኒልክ የመጨረሻ ዘመነ መንግሥት በየአውራጃው ያሉትን አስተዳዳሪዎች ስንመለከት ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ከራስ መንገሻ እስራትና ከራስ መኰንን ሹመት ወዲህ ፣ በኮረም ዋግሹም አባተና ደጃዝማች አብርሃ ከተዋጉ በኋላ ፣ የደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ዕድገት እየጨመረ ሔደ ።

ገብረ ሥላሴ አባታቸው ደጃዝማች ባሪያ ጋብር ይባላሉ ። ገብረ ሥላሴ ምንም እንኳ ትውልዳቸው ከመረብ ወዲህ በትግራይ ቢሆንም ፣ ከዓድዋ ጦርነት ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ጣልያኖች ኤርትራ ብለው ወደ ያዙት ክፍል የኢጣልያ ቋንቋ ከነጽሕፈቱ ተምረው በወታደርነት ደረጃ እስከ ዩዝባሽነት ደርሰዋል ። ስለርሻቸውም በሰሜን ኢትዮጵያ ከመረብ ባሻገርና ከወዲህም ብዙ ዘመን ያሳለፈው አናራቶሬ እንደዚህ ይላል ።

. . ገብረ ሥላሴ የኛ ዩዝባሽ ነበረ ። በ1896 ዓ ም በተደረገው የጦርነት ዘመን 100 ወታደር እንደያዘ በደብረ ኃይላ ጦርነት በታማኝነት አገልግሎናል ። ከራስ መንገሻ በኩል ከኢጣልያ እንዲሸፍት የቀረበለትን ሐሳብ አልተቀበለም ። . . . በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ከራስ አሉላ ተቀበለ ። በራስ ወሌ ዘንድ ሲጠላ በራስ መኰንን ዘንድ በጣም የተወደደ ነበር ። ከትልቅ ጦርነት በኋላ ደጃዝማች አብርሃን ማርኮ ለንጉሡ አቅርቧል ። መልከ መልካም የ38 ዓመት ሰው ነው ።* ከሁሉም ጋር ስምምና በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ነው ። 1

በውነትም በራስ መኰንን አማካይነት ፣ ካፄ ምኒልክ ጋር ተዋውቀው በብዙ ረገድ ታማኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ ንጉሡ ነገሥቱ ባለሟል አድርገው በዓድዋ ሾሙዋቸዋል ። በአክሱም ንቡረዕድ

* በየትኛው ዓመተ ምሕረት መሆኑን አይገልጽም ። 1890—95 ዓመተ ምሕረት መካከል ይሆናል ።

1 In Abyssinia, C. Annaratore, PP.71-73.

ተብለው የራስ ወርቅ እስከ ማሰር ደርሰዋል ። ራስ መንገሻ እጃቸውን ለራስ መኰንን ሰጥተው ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ጊዜ የደጃዝማችነት ማዕረግ አግኝተዋል ። የራስ መንገሻ ልጅ ደጃዝማች ሥዩምና የወንድማቸው የራስ አርአያ ልጅ ደጃዝማች ጉግሣ ሸፍተው በዚያው በትግራይ የቆዩትን በማስፈራራትም ፤ በማባበልም በየተራ ወደ አዲስ አበባ አምጥተው ላፄ ምኒልክ ያስገቡ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ስለሆኑ ባፄ ምኒልክ ዘንድ ተወደው ራስ ሊባሉ ሲሉ ፤ በእቴጌዪቱ ተቃውሞ ቀረ ይባላል ።

ካፄ ምኒልክም ጋር ያላቸው ግንኙነት እየጠበቀ ሲሔድ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ የሚወለዱትን የቅርብ ዘመዳቸውን ወይዘሮ አማረች ዋለሉን ዳሩላቸው ። አሁንም ንጉሠ ነገሥቱ በታመሙበት ሰዓት የእቴጌይቱ ሥልጣን ባለቤታቸውን በማስታመም እንዲወሰን ሲደረግ ፤ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ከራስ ተሰማ ጐን በመቆም ከእቴጌይቱ ጋር ጠብ ከማብቀል ደርሰው ነበር ። በዚህ ምክንያት በአሁኑ ሰዓት በትግሬ መሆኔ ደጃዝማች አበራ ተድላ ፤ በአጋሜ ራስ ሰብሐት ፤ በዓድዋና በአካባቢው ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ አስተዳዳሪነት ሲሰጣቸው በተምቤን ደጃዝማች ሥዩም መንገሻ ፤ በሽሬ ደጃዝማች ጉግሣ አርአያ ያስተዳድራሉ ።

በሌላም በኩል ፤ ቤጌምድር ለራስ ጉግሣ ወሌ ፤ የጁ ለራስ ወሌ ፤ ጐጃም ከአገውና ከዳሞት ጋር ለራስ ኃይሉ ፤ ወሊቃይትና ስሜን ለፊታውራሪ ኪዳነ ማርያም ፤ በደቡብ በኩል ሐረርጌ ለደጃዝማች ተፈሪ ተሰጥቷል ። ከጨቦና ከአመያ ዠምሮ የጉራጌ አገርን ይዞ እስከ ቦረና ድረስ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዱ ፤ በከፋና በአካባቢው ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፤ በከምባታ ራስ አባተ ፤ በሲዳሞ ደጃዝማች ባልቻ ፤ በወሎ ራስ ሚካኤል ፤ በጅማ ራስ ልዑልሰገድ ፤ በሚዳና በይፋ ራስ ወልዴ ፤ በኤፍራታ ፤ በግድም ፤ በቀወትና በጥሙጋ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ፤ በጐላ ደጃዝማች ውቤ አጥናፍ ሰገድ በሰላሌ ፤ ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ ፤ አጋግሹ ወለጋ ደጃዝማች ደምሰው ነሲቡ ፤ አጋግሹ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርና ሌሎችም ይኖራሉ ። በመካከሉ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ቀደም ብለው ከፋን ተሽረው ወደ ጐንደር ተዛውረው ፤ በጌምድርንና ስሜንን ጠቅልለው በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ ። ከእቴጌ ጋር ያድማሉ ተብለው ወንድማቸው ራስ ወሌም በመጨረሻ በግዞት ወደ አንኮበር ሲላኩ ልጆቻቸው እነ ራስ ጉግሣ ደግሞ ታስረዋል ።

በ1903 ዓ.ም. የልጅ ኢያሱ ሞግዚት ራስ ተሰማ ናደው ሲሞቱ ፤ ለልጅ ኢያሱና ለወገኖቻቸው ትልቅ ልጓም እንደ ወለቀላቸው ተቆጠረ።



ባንድ ወገን ዋናዋ የሥልጣን ባላንጣ እቴጌይቱ ባለቤታቸውን በማስታመም ብቻ ስለ ተወሰኑ ፤ ለልጅ ኢያሱ ሰፊ የሥልጣን ሜዳ ተከፈተላቸው ። ታላላቆቹ መሳፍንትና መኳንንት ለጌታቸው ሕመም በማሰብ ፤ "ወደፊትስ ምን ይደርስ ይሆን በዚህ አገር" እያሉ በማሰላሰል ገርበብ ቢሉም ፤ ሹመትና ሽልማት ፈልጎ የወደፊት ትዳሩን ለማቃናት የተመኘውና በተለይ እንደ ወጣት ያለው በኢያሱ ዙሪያ ተሰበሰበ ።

ኢያሱ በዚህ ወቅት (በ1903 — 04 ዓ. ም.) ዕድሜአቸው 15 ዓመት ስለደረሰ ፡ ጊዜያቸውን በፈረስ ግልቢያና በጉግስ ጨዋታ ማሳለፋቸው ሌላም ሌላም የልጅነት ሥራ መሥራታቸው ፤ ያፄ ምኒልክንም ሽማግሌ መኳንንት እየነቀፉ ማንጓጠጣቸው ፤ የብዙ መኳንንት ሴቶችን ማማገጣቸው ወይም ለማማገጥ መሞከራቸው ውስጥ ውስጡን በርክቶ ይወራ ዠመር ።

በዚህ ምክንያት ፤ ራስ አባተ ቧያለው እነደጃዝማች ይገዙን ፤ እነንቡረዕድ ገብረ ሥላሴንና ሌሎቹንም ጨምረው በመሰብሰብ ፤ "ራስ ተሰማ ከሞቱ ወዲህ ልጅ ኢያሱ ልቅ ወጣ ። ብዙም የማይገባ ሥራ መሥራት ዠመረ ። ስለዚህ ይዘን በምክር በሥነ ሥርዓት በማስተማር እናሳድገው ። የመንግሥቱ ሥራ ግን ፤ በአንድ ሥርዓት ዐዋቂ ሞግዚት ይመራ" የሚል ሐሳብ አቀረቡ ። ልጅ ኢያሱም ነገሩን ሰምተው በመደንገጥ ወደ ስብሰባው ሔደው ፤ "ከፈቃዳችሁ አልወጣም" ብለው የመለማመጥ መልክ አሳይተው ነበር ።

በኋላ ግን ውሎ አድሮ ፤ "የራስ አባተ አሳብ ወይዘሮ ዘውዲቱን ለማንገሥና ራሱ የእንደራሴነት ሥልጣን ለመያዝ ነው" የሚለው ወሬ በርክቶ ስለተወራ ፤ የዚህን ሁኔታ ያልደገፉት እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፤ እነራስ ሉልሰገድ ኢያሱ ራሳቸውን ችለው እንደ ኑዛዜው ቃል ቢገዙ ይሻላል ብለው በመወሰን አቤቶ ኢያሱን ስለደገፉ የራስ አባተ ሐሳብ ውድቅ ሆነ ። ቢሆንም ግንቦት 21 ቀን 1903 ዓ.ም. "የራስ አባተና የልጅ ኢያሱ ጦር ሊዋጋ ነው ፤ ከተማውም ሊሸበር ነው" ተብሎ ሰው ሁሉ ሲሠጋ ውሎ ነበር ። ነገር ግን ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ወደ ሁለቱም ወገኖች ተመላልሰው ጦርነቱን ወደ ሰላም መለሱት ። ራስ አባተም በነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተጽዕኖ አዲስ አበባን ፤ ለቀው በግማሽ ግዞት ወደ ግዛታቸው ወደ ከምባታ ሔዱ ።

ከዚህ በኋላ፣ የልጅ ኢያሱ አባት ራስ ሚካኤል ፤ "ልጅዎን ከሥልጣን ሊገለብጡ እነራስ አባተ ተነሥተዋል" የማለትን ወሬ ሰምተው

ነበርና ሲገሠግሡ ከወሎ መጥተው አዲስ አበባ ገብተው ፣ ከነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋር ተገናኝተው ፣ የነራስ አባተ ሐሳብ መክሸፋንም ፣ ራስ አባተም ወደ ግዛታቸው ሔደው ነገሩ መረጋጋቱን ሰሙ ። ቢሆንም “አሁንስ ራስ አባተ ይኸን ምኞቱን ትቶ ሰላማዊ ሆኗል ወይ ? አንድ ሰላይ ሔዶ ሁኔታውን መርምሮ ይመለስ” ብለው ራስ ሚካኤል ስለተጫኑ ፣ አንድ ሰው ወደ ከንባታ ሔዶ ሁኔታውን መርምሮ እንዲመለስ ተላከ ። ሰውዬው ደርሶ ሲመለስ ፣ “ራስ አባተ ሥራዬ ብለው የያዙት ወታደር ማብላትና ማጠጣት ፣ ማስፎከር ነው አሳባቸው አልበረደም ”የሚል ሐሳብ አቀረበ ።

እንግዲያውስ ይጠሩ ተብሎ በ1904 ዓ. ም. በመስከረም ወር የጥሪ ወረቀት ቢደርሳቸው አባተ “አሞኛል” ብለው ሳይመጡ ቀሩ ። በዚህ ጊዜ አሁንም በራስ ሚካኤል ተጽዕኖ የከምባታ ግዛት ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በዐዋጅ መሰጠቱ ተነገረና ወዲያው የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ምስለኔ (እንደራሴ) ከምባታ ሲደርስ በራስ አባተ ውስጥ የነበረው የቁጥር* ጦርና ከአሽከሮችም ውስጥ እየከዱ ወደ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ እንደራሴ ዞሩና በራስ አባተ ውስጥ የቤት አሽከር ብቻ ቀረ ።

ከዚህ በኋላ ከሹማምንቶቻቸው አንዱ ፣ “የራሳችን ሰው ከድቶ እጃችንን ይዞ ሳይሰጠን እኛው በፈቃዳችን ወደ አዲስ አበባ ብንሔድ ይሻላል” ብሎ ስለመከረ ፣ አባተም “እውነትህ ነው” ብለው አሳቡን ተቀብለው በታኅሣሥ 19 ቀን ወደ አዲስ አበባ መጡ ። እንደመጡም ያለብዙ ማንገራገር ራስ ሚካኤል እጃቸውን ተረክበው ይዘዋቸው ወደ ወሎ ሲሔዱ አፍቀራ ላይ አሰሩዋቸው ።

ልጅ ኢያሱ ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ መቀመጫ ቤታቸው በራስ ተሰማ ቤት ነበር ። የራስ ተሰማ ባለቤት የነበሩት ወይዘሮ በለጥሻቸው አባጀቢርም ፣ በመልካም አያያዝ ወጣቱን መስፍን ያስተናግዳሉ ሲባል ፣ ሌላው የበለጠ ፍቅራቸውን እማውራት ደረሰ ። ኢያሱ ግን መቀመጫቸውን ከራስ ተሰማ ቤት አዛውረው በአባታቸው በራስ ሚካኤል ቤት አደረጉ ። አንዳንድ ጊዜም ወደ ደሴ እየሔዱ አባታቸው ዘንድ ይሰነብታሉ ። በዚህ መካከልም “የጊሚራ ሕዝብ ባገረ ገዥው

* የቁጥር ጦር ማለት አሽከር ሳይሆን በራስ አባተ ሥር ቢታዘዝም ደንበኛ የመንግሥት ወታደር ነው ።



በደጃዝማች ሙሉጌታ ላይ አምጿል” ስለተባለ ፣ በግንቦት ወር 1904 ዓ.ም. ከደሴ ተነሥተው ወደ ጊሚራ ሔደው አምጠዋል የተባሉትን ቀጥተው አገሩን ካረጋጉ በኋላ ፣ የከረምቱን ወራት በዚያው አሳልፈው በጥር ወር አዲስ አበባ ገብተው ሹም ሽር አደረጉ ።

በዚህ ጊዜ ፣ “ልጅ ኢያሱ አያታቸውን ዐፄ ምኒልክን ከቤተ መንግሥት አስወጥተው ወደ አንኮበር ሊሰዱዋቸውና እርሳቸው ቤተ መንግሥቱን መቀመጫ ሊያደርጉ ነው” የሚል ወሬ በከተማው ተነዛ ። መቼም አንዱ ሰው ምንም ስመጥር ንጉሥ ቢሆን ፣ በጣም በዘመኑ የተወደደና የሕዝብ አባት ቢባልም ፣ እርሱ በሕመም ወድቆ የመዳን ተስፋ ሲያጣ ፣ እንደ ኢያሱ ያለ አፍላ ወጣት እለሁ እለሁ ሲል ፣ “ይኸን አድርግ ፣ ይኸን አታድርግ አይዞህ እኛ አለንልህ” እያለ በዙሪያው በማነብነብ ርስትና ጉልት ፣ ሹመትና ማዕረግ ፈላጊው ብዙ ነው ። ስለዚህ ያፄ ምኒልክ ሕመምተኛነት ጊዜው ሲቀጥል ለሥልጣን የቸኰሉ ሰዎች ፣ “እርሳቸው አንኮበር ሔደው ይተኙ ፣ ቤተ መንግሥቱን ለኛ ይልቀቁልን ” የሚል መካር ይጠፋል ማለት አይቻልም ። በዚህ ጊዜ 17ኛውን ዓመት ዕድሜ የያዙት ኢያሱ ይኸን የመሰለው አሳብ ለወጣትነትና ለሥልጣን አምሮታቸው ሳይጥም አይቀርም ።

ነገር ግን ፣ የግቢ ዘበኞች አለቃ ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ምክትላቸው ቀኛዝማች ደቻሳ ፣ “ከንዳችንን ሳንንተራስ ጌታችንን ከቤቱ የሚያስወጣው የለም ” እያሉ ይፎክሩ ዠመር ። ከውጭም ወገን የልጅ ኢያሱ ወገኖች እነፊታውራሪ አሸናፊ ጥሰው ወደ ግቢ ለመግባት ተደራጅተው ምቹ ጊዜ ሲያማርጡ ፣ ከነርሱ ወገን የካቲት 1 ቀን 1905 ዓ.ም. ቅዳሜ ወደ ማታ ያንድ ጥይት ተኩስ ተሰማ ። በዚህ ጊዜ እነፊታውራሪ ገብረ ማርያም በቋፍ ነበሩና እየተፏከሩ ከሁለቱም ወገን ተኩሱ እስከ ሌሊቱ 5 ሰዓት ድረስ ከቆየ በኋላ በረደ ። የሆነ ሆኖ ፣ በዚህ ግጭትና በተባራሪ ጥይት ከዐሥር እስከ ዐሥራ አምስት ሰዎች ሞቱ ይባላል ።

በማግሥቱ እሑድ ጳጳሱና እጨጌው ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ ነገሩ በስምምነት አለቀና ልጅ ኢያሱን በመፍራት ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ቀኛዝማች ደቻሳ አቡኑ ቤት ሔደው እንደቆዩ በመጨረሻ ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ወደ ጎንደር ለራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ቀኛዝማች ደቻሳ ወደ ጐጃም ለራስ ኃይሉ በግዞት ተልከው እስከ ሰገሌ ዘመቻ ድረስ በዚያው ቆዩ ። የግቢውን የዘበኝነት እልቅና ፊታውራሪ ተሰማ ገዝሙ ደጃዝማች ተብለው ተሾሙ ። ወዲያውም ሕዝቡን ለማረጋጋት ሲባል ፣ “ንጉሠ ነገሥቱን ከግቢ ለማስወጣት በፍጹም

እልታሰበም" የሚል በሚኒስትሮች ስም አንድ መግለጫ ታትሞ ወጣ ። በረዥሙ ተጽፎና ታትሞ ከተበተነው ውስጥ እንደዚህ የሚል ይገኝበታል ።

> የሚኒስትሮች የምክር ቃል ...የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ከጥንት ዠምሮ ራሱን የቻለ ቢሆን ጭራሽ በዓለም ሁሉ የታወቀው በዳግማዊ ምኒልክ ነው ።...ዐፄ ምኒልክ ሕመማቸው በርትቶ እቤት በመዋላቸው አዝነን ሳለን እረኛ እንደ ሌለው በጐች እንዳንበተን ያልጋ ወራሽ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን በመስጠታቸው እጅግ ደስ አለን... እኛ ግን ...እየተስማማን መንግሥታችንን እየጠበቅን በፍቅር መኖራችንን ትተን እርስ በርሳችን እየተጣላን ለባእድ መሣለቂያ እንዳን ሆን ጃንሆይ የመከሩንን ምክር ጠንክረን ማጽናት ይገባናል ።... መንግሥቱን ወዶ በአንድነት ተስማምቶ የሚኖረውን ሕዝቡን አለያይቶ ለማፋጀት ደም ለማፍሰስ ጃንሆይን እንኮበር ሊያወርዷቸው ነው የሚል የሐሰት ወሬ ተወራ ። ጠላትን አጥፍተው ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉንም በየማዕረጉ ሹመው ፣ ሸልመው ኢትዮጵያን አልምተው ያቆዩንን አባታችንን ጌታችንን ጃንሆይን በዚህ በነቀስ አይውጡብን ብለን ስንጨነቅ እንዴት ያለ ክርስቲያን እንኮበር ይውረዱ ብሎ ይመክራል? ወይስ እንዴት ያለ ልጅ አባቱን አስወጥቶ እልጋ ይላል?...አሁንም ይኸ ሁሉ ክፉ አሳብ በልጅ ኢያሱም ፣ በእኛም ልብ እንዳልታሰበ ያው መሐላና ግዝት ይድረስብን ።...ይኸም የሐሰት ወሬ መንግሥቱና ሀገሩን ከሚወድ ሰው እንዳልወጣ የታወቀ ነው ። አሁንም ይህ ወሬ ከምቀኛ የወጣ ነውና ይህን ወሬ ያወራ ቢገኝ የመንግሥት በደለኛ መሆኑ ይታወቅ ። እሱ ግን ተሰውሮ ይኸን የእንክርዳድ ዘሩን እየዘራ ስንዴ ልባችንን በእረም ሊያበላሽ ያሰበ ነው ። ይኸንን ያወራ ምቀኛ ...ከመካከላችን ነው ። በመሐላ በግዝት እውጥተን እንለየው ...ወደፊት ጃንሆይ እንደመከሩን ነቀስ እንዳይገባብን አንድ ልብ ሁነን በፍቅር መንግሥታችንን ብንጠብቅ መልካም ነው ። ታኅሣሥ 11 ቀን 1905 ዓ ም. አዲስ አበባ ከተማ 1

በልጅ ኢያሱና በወገኖቻቸው ዘንድ ያፄ ምኒልክ ሞት መዘግየት ለሥልጣን እያያዝ በመጠኑ እንቅፋት በመሆኑ ፣ እንኮበር ይዛወሩ የሚባለው ሤራ ሳይጠነሰስ እንዳልቀረ የታወቀ ነው ።የነፊታውራሪ ኀብረ ማርያም ተቃውሞ ግርግር ባያስነሣና ሰሚውንም እንዴት ተደርጎ ባያሰኘው ኖሮ አሳቡ በቀላሉ ሊፈጸም በቻለ ነበር ። ነገር ግን ፣ ጉዳዩ እስከ መቃኮስ ከተማ እስከ ግምበር ሲያደርስ ወደኋላ አፈግፍጎ ፣ "እንዲያውም አልታሰበም" ማለት ዐውቆ የመሸነፍ ዘዴኛ ነት ነው ። በዚህ ዘመን ያሉት ሚኒስትሮችም ተሰብስበው ኃላፊነት በመስጠት የንጉሠ ነገሥቱን ምክር በመገምገም የሕዝቡንም ትረታ በማጤን ፣ ሕዝቡን ለማረጋጋት ይኸን ማስታወቂያ ማውጣታቸው የተገባ ነው ።

1. An Amharic Reader, Major J. I. Eadie, P. 79





ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዴ

ከሐድሰን መጽሐፍ

አልታሰበም'' የሚል በሚኒስትሮች ስም አንድ መግለጫ ታትሞ ወጣ ። በረዥሙ ተጽፎና ታትሞ ከተበተነው ውስጥ እንደዚህ የሚል ይገኝበታል ።

የሚኒስትሮች የምክር ቃል ． የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ከጥንት ዠምሮ ራሱን የቻለ ቢሆን ጭራሽ በዓለም ሁሉ የታወቀው ባፄ ምኒልክ ነው ።. . . ዐፄ ምኒልክ ሕመማቸው በርትቶ እቤት በመዋ ላቸው አዝነን ሳለን እረኛ እንደ ሌለው በጐች እንዳንበተን ያልጋ ወራሽ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን በመስጠታቸው እጅግ ደስ አለን. . . እኛ ግን . . . እየተስማማን መንግሥታችንን እየጠበቅን በፍቅር መኖ ራችንን ትተን እርስ በርሳችን እየተጣላን ለባእድ መሣለቂያ እንዳን ሆን ጃንሆይ የመከሩንን ምክር ጠንክረን ማጽናት ይገባናል ።. . . መንግሥቱን ወዶ በአንድነት ተስማምቶ የሚኖረውን ሕዝቡን አለያይቶ ለማፋጀት ደም ለማፍሰስ ጃንሆይን አንኮበር ሊያወርዷቸው ነው የሚል የሐሰት ወሬ ተወራ ። ጠላትን አጥፍተው ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉንም በየማዕረጉ ሹመው ፣ ሸልመው ኢትዮጵያን አልምተው ያቆዩንን አባታችንን ጌታችንን ጃንሆይን በዚህ በነፋስ አይውጡብን ብለን ስንጨነቅ እንዴት ያለ ክርስቲያን አንኮበር ይው ረዱ ብሎ ይመክራል? ወይስ እንዴት ያለ ልጅ አባቱን አስወጥቶ እኔ ልግባ ይላል? . . . አሁንም ይኸ ሁሉ ክፉ አሳብ በልጅ ኢያሱም ፣ በእ ኛም ልብ እንዳልታሰበ ያው መሐላና ግዝት ይድረስብን ።. . . ይኸም የሐሰት ወሬ መንግሥቱና ሀገሩን ከሚወድ ሰው እንዳልወጣ የታወቀ ነው ። አሁንም ይህ ወሬ ከምቀኛ የወጣ ነውና ይህን ወሬ ያወራ ቢገኝ የመንግሥት በደለኛ መሆኑ ይታወቅ ። እሱ ግን ተሰውሮ ይኸን የእን ክርዳድ ዘሩን እየዘራ ስንዴ ልባችንን በአረም ሊያበላሽ ያሰበ ነው ። ይኸንን ያወራ ምቀኛ . . . ከመካከላችን ነው ። በመሐላ በግዝት አው ጥተን እንለየው . . . ወደፊት ጃንሆይ እንደመከሩን ነፋስ እንዳይገባ ብን አንድ ልብ ሁነን በፍቅር መንግሥታችንን ብንጠብቅ መል ካም ነው ። ታኅሣሥ 11 ቀን 1905 ዓ ም. አዲስ አበባ ከተማ [1]

በልጅ ኢያሱና በወገኖቻቸው ዘንድ ያፄ ምኒልክ ሞት መዘ ግየት ለሥልጣን አያያዝ በመጡ እንቅፋት በመሆኑ ፣ አንኮበር ይዛወሩ የሚባለው ሤራ ሳይጠነሰስ እንዳልቀረ የታወቀ ነው ።የነፊ ታውራሪ ኀብረ ማርያም ተቃውሞ ግርግር ባያስነሣና ሰሚውንም እንዴት ተደርጎ ባያስኘው ኖሮ አሳቡ በቀላሉ ሊፈጸም በቻለ ነበር ። ነገር ግን ፤ ጉዳዩ እስከ መታኮስ ከተማ እስከ ማሸበር ሲያደርስ ወደኋላ አፈግፍጎ ፤ "እንዲያውም አልታሰበም'' ማለት ዐውቆ የመሸንፍ ዘዴኛ ነት ነው ። በዚህ ዘመን ያሉት ሚኒስትሮችም ተሰብስበው ኃላፊነት በመሰማት የንጉሡ ነገሥቱን ምክር በመገምገም የሕዝቡንም ቅሬታ በማጨን ፤ ሕዝቡን ለማረጋጋት ይኸን ማስታወቂያ ማውጣታቸው የተገባ ነው ።

1. An Amharic Reader, Major J. I. Eadie, P. 79





ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዴ
ከሐድሰን መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሰባ ስድስት

## የደጃዝማች ሥዩምና የራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ጠብ

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት ፣ በዚህ በሸዋ የንጉሠ ነገሥቱ ሕመም ብዙ ነገር እንዳናጋ በጐጃም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሞት ብዙ ጠብ ፣ ብዙ መለያየት ፈጥሯል ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በወጣትነታቸው ዘመን ራስ በዛብህን ፣ ቀጥሎም ደጃዝማች በለውን ከዚያም ወደፊት ራስ ኃይሉ የተባሉትን ደጃዝማች ሥዩምን ከተለያዩ ሴቶች ወልደዋል ። በመጽሐፍ ከምናውቀው ከአቤሴሎም ዝምድ ያደገ ልጅ ብዙ ምኞት ስለሚያደርበት ከወላጅ አባቱ ጋር አይስማማም ። ለም ሳሌ ደጃዝማች አስፋው ዙፋን እየተመኙ ስለ አስቸገሩ ፣ አባታቸው ራስ ዳርጌ አስረው ወደ ዐፄ ምኒልክ ላኩላቸው ።ምኒልክ ግን ፣ "ምንም እንኳን እርሳቸው ልጃቸውን አስረው ቢልኩልኝ አላስርም" ብለው አስፋውን ፈትተው ወደ ባሌ ልከዋቸው ነበር ። በቅርቡም ራስ ሥዩም መንገሻ ልጃቸውን ደጃች ካሣን በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ የላኩበት ሁኔታ ተመሳሳይ ነው ።

እንደዚሁም ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው ፣ በየምክንያቱ ካባታቸው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ስምምነት አጥተው አዲስ አበባ መጥተው ለነርሱ ለሰዋቸውም ድርጎ እየተቀበሉ በደጅ ጥናት መቀመጣቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ በ1893 ዓ. ም. ሲሞቱ የኑዛዜው ቃል ትክክል አለመሆኑ ፣ በሦስቱ ወንድማማቾችና በባለቤታቸው በወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅን መካከል ብዙ ውዝግብ ፈጥሮ ነበር ።

አለቃ ተክለ ሥላሴ የዚህን ሁኔታ ሲዘረዝሩ ፣ ከዐርባው በኋላ ራስ ወርቄና* ደጃች ሥዩም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ዘውድና መጣሪያ (የወግ ዕቃ) ይዘው ፣ አዲስ አበባ መጥተው ፣ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው ደጃዝማች ሥዩም እስከ ሙት ዓመት ድረስ ቁርባን እያስ ቆረቡ የመቆየትን ፣ ይኸውም ማለት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን

* ከራስ ደረሶ በኋላ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደራሴ የነበሩ ።

ንብረትና ቤት ይዘው ለጊዜው እንዲያስተዳድሩ መጠየቃቸውን አመልክተዋል ። ይኸም የሆነበት ምክንያት ሁለቱ ታላላቅ ወንድማማቾች ከአባታቸው ተጣልተው አዲስ አበባ በቆዩበት ሰዓት ፣ ትንሹ ደጃዝማች ሥዩም ከአባታቸው ሳይለዩ አስታመው በመቀበራቸው ነው ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ በሕመም በደከሙበት ሰዓት "የአልጋዬ ወራሽ ራስ በዛብህ ነው" የሚል በመልእክ ገንት አሥራት እጅ አጽፈው ማኅተም አሳትመው ላፄ ምኒልክ ሲልኩ ፣ ሚስትዮዋ ወይዘሮ ላቀች ደግሞ ከንስሐ አባትየው ጋር ተመሳጥረው ፣ "ልጆቼን ይዛ በአልጋዬ (በሥልጣኔ) ላቀች ትቀመጥ" የሚል ማኅተም አቀረቡ ። በበኩላቸው ደጃዝማች ሥዩም "ወራሼ እሱ ይሁን" የሚል ማኅተም አትመው ከጐጃም ላኩ ። ታላላቆቹ ልጆች ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው "የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጆች ትልልቆቹ እኛ ነንና ለእኛ ይሰጠን ኑዛዜውም ለኛ ነው የሚፈቅደው" የሚል አቤቱታ አቀረቡ ። ደጃዝማች ሥዩም ፣ "አባታችሁን በድላችሁ ፣ ተክዳችሁ አድራችኋል ፤ አይገባችሁም ። ኑዛዜውም ለኔ ነው" የሚል መልስ ስለ ሰጡ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በነገሩ ተቸግረውበት ቆይተው በመጨረሻ ፣ "ስለ ኑዛዜው ጉዳይ ንስሐ አባቱን እስክመረምርና የመጨረሻ ውሳኔ እስካደርስ ድረስ ደጃዝማች ሥዩም አባቱን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አስታሞ ስለ ቀበረና የሙት ዓመት ተዝካር ለማውጣት ስለሰመነ ሔዶ ያውጣ ። ወደፊት ክርስቶስ ለፈቀደለትና ለእኔ ለሚመቸው አስቤ መክሬ እሾማለሁ" ብለው መወሰናቸውን አለቃ ተክሌ ሥላሴ መዝግበዋል ።

ከዚህ በኋላ ፣ በዓመቱ በአዲስ አበባ ተመክሮ ተዘክሮ ንጉሠ ነገሥቱ ሰፊውን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግዛት የነበረውን ከሦስት ላይ ክፍለው ጐጃምን ለደጃዝማች ሥዩም ፣ ጉድሩንና የወለጋን ሰሜናዊውን ክፍል ለደጃዝማች ደምሰው ነሲቡ ፣ ከጐጃም ምዕራብ የሚገኘውን የዳሞትና የአገው ምድርን ግዛት ለራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ሰጡ ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ጠቅላላ ግዛት ላንዱ ልጅ ወይም ለሦስቱም ሳያከፋፍሉ በመቅረታቸው የጐጃም ሰው ቅሬታ ገብቶት ነበረ ። በዚህም ጊዜ አቅራሪ፦

እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጐበኘው ፤
የአባጠናን አገር ማነው የተመኘው ።

ምን ያለ ንጉሥ ነው ቂሙን የማይረሳ ፤
የአባ ጠናን አገር ሰጠው ለኮሳሳ ።



ጋሻውን ውሰዱት ጐራዴውን ውሰዱት ነፍጡንም ውሰዱት . . . እንዲሆን ለምስል ፤
የዚህ ቤት እዚያ ቤት አይገባ አይመስል ።

በስተቦረና በስተበላያ በስተደንገል በር ያቀናውን አገር ፤
እስረክቦት መጣ አወይ የልጅ ነገር ።

ተብሎ እንደ ተገጠመ ተክለ ሥላሴ ያስረዱናል ።*

ነገር ግን ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ጐጃምን ለሦስቱ ልጆች ቢያከፋፍሉ ከሦስት አንዱ በተለይ ትልቁ ቅር በመሰኘት የርስ በርሱ ጦርነት አይቀርም ነበር ። መቼም በሸዋም ፣ በጐንደርም ዘመነ መንግሥት (15—19 መቶ ዓመታት) ዳሞትና አገው ምድር ከጐጃም እየተለየ ይሾምበታል ። በነኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመነ መንግሥት ጐጃምን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የዘር አባቶች እነ ታላቅ ራስ ኃይሉ ፣ ያስተዳድሩት ነበር ። በዘመነ መሳፍንትም በዳሞት እነደጃዝማች ዘውዱ ሲገዙ በጐጃም እነራስ መርድ ነበሩ ። ነገር ግን አንዱ ኃይል ሲሰማው ሌላውን መደረቡ ፣ የዳሞት ባላባት የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟል ሲሆን ፣ ጐጃምን ወይም የጐጃሙ ዳሞትን በውስጡ ማድረጉ የተለመደ ነው ።

ራስ አዳል ፣ በፊት ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ቀጥሎም ያፄ ዮሐንስ ባለሟል በነበሩበት ሰዓት ፣ ዐፄ ዮሐንስ በጐጃም ላይ ዳሞትንና አገው ምድርን አክለው ስማቸውን ተክለ ሃይማኖት ብለው ሲያነግሷቸው ራስ ቢቶወደድ መንገሻ የዳሞትና የአገው ባላባትነት የኔ ነው በማለት ቅርተኛ ነበሩ ።

ይኸም ሲሆን ደጃዝማች ሥዩም ፣ ለራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ፍጹም ታማኝ በመምሰል ፣ " . . ዛሬ ከራስ መንገሻ ብንሆን ልባችን ካንተ ነው ፤ ናልን እንውጋው ያለው ጦር ያባትህ (የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት) ጦር ነው እያሉ ይልኩብኛል ። እኔ ግን አባቴን እርስዎን አልወጋም እያልሁ ዝም ብዬ ተቀምጫለሁ ። በነአፈንጉሥ ይግዛው ተንኮል ይንቁባቸው" የሚል ደብዳቤ ጽፈው ለራስ መንገሻ ላኩ ። ራስ መንገሻም ይኸ መልእክት ሲደርሳቸው ፣ "በውነት ይኸ ነገር መሆኑን የማውቀው ፣ ያንተንም ልጅነት የምረዳው እንውጋው ናልን

*አባ ጠና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የፈረስ ስም ነው ። ቂሙን የማይረሳ የተባሉት ንጉሠ ነገሥቱ ምኒልክ ናቸው ። ቂሙ የእምባቦ ጦርነት ይሆን ? እንደውነቱ በዚህ ምንም ዓይነት ቂም አልነበረም ። «የዚህ ቤት እዚያ ቤት አይገባ ይመስል» የተባለው በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ የደረሰው ሞት ባፄ ምኒልክም እንደሚደርስ ለማለት ነው ። አወይ የልጅ ነገር የተባሉት ሥዩም ናቸው ።

ብለው የላኩብህን ደብዳቤ ስታሳየኝ ነው ። ደብዳቤውን ካላሳየኸኝ
በውነትም ልትወጋኝ ከጅለሃል ማለት ነው'' ብለው መለሱ ።

በዚህ ጊዜ ፤ ደጃዝማች ሥዩም አለቃ ተክሌና አለቃ ተገኝ በሚ
ባሉ ሠዓሊዎችና ጥበበኞች አማካይነት በአፈ ንጉሥ ይግዛው ስም
አዲስ ማኅተም አመሳሰለው አስቀርፀው ፤ "ናልን መንገሻን እንውጋ''
ብለው እነርሱ እንደ ላኩባቸው አስመስለው አስተኛውን ማኅተም
አትመው ለራስ መንገሻ ላኩላቸው ። መንገሻም እውነተኛ ማኅተም
መስሏቸው ለካ ያለሁት የኔን ሞት ከሚፈልጉ ጠላቶቼ ጋር ነውና''
ብለው ሁሉንም አስረው ዝርዝር ሁኔታውን ጨምረው በ1894
ዓ. ም. አዲስ አበባ ወዳፄ ምኒልክ ላከዋቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፤ ደጃዝማች ሥዩምንና አዲስ ማኅተም አስመሰ
ለው ቀርፀዋል የተባሉትን አለቃ ተገኝንና አለቃ ተክሌን ወደ አዲስ
አበባ አስመጥተው ጉዳዩ በጉባዔ በሚታይበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ
አፈ ንጉሥ ይግዛውን ራስ መስፍንን ፤ ፊታውራሪ ኃሉንና ፊታውራሪ
መሸሻን እንደ ተያዙ ፤ "ይኸ የናንተ ደብዳቤና ማኅተም አይደለምን?''
ብለው አሳይተው ቢጠይቋቸው ፤ "ማኅተሙ ይመስላል ፤ እኛ ግን
እንደዚህ ያለውን ሥራ አልሠራነውም ። ነገር ግን ጠላትን አጥፍቶ
አገር አስፍቶ ያነገሠዎ የጃንሆይ አምላክ እውነተኛ ፍርዱን አይነሣዎ
ምና እንደ ገለጸልዎ ይመርምሩልን'' ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ
በጉባዔው ያለው መኳንንት ግማሹ ፤ "ከማኅተም ወዲያ ምን ምስክር
አለ ? ይቀጡ ?'' ሲል ፤ ሌላው "ማኅተም የያዘውን አሽከር በገንዘብ
ገዝቶ ቢያሳትመውስ ?'' ሲባባል ንጉሠ ነገሥቱ የተያዙትን የመኳ
ንንቱን እውነተኛ ማኅተምና ደጃዝማች ሥዩም ያሠሩትን ሐሰተኛ
ውን ማኅተም አቅርበው በማስተያየትና በመመርመር ፤ ትንሽ ልዩነት
ስለታየ ንጉሠ ነገሥቱ ፊታቸውን ወደ ደጃዝማች ሥዩም አዙረው
"እውነቱን ንገረኝ ። በኋላ ከደህ የተገለጸብህ እንደሆነ ቅጣቱ ይከፋ
ድብሃልና እውነቱን ብትነግረኝ ይሻልሃል'' ብለው ቢጠይቋቸው
" . . . እንዲህ ያለውን እግዚአብሔር ከገለጸልዎ በኋላ እንደ ምሕረ
ትዎና እንደ ቸርነትዎ ያድርጉ እንጂ ምን እሰውርዎ አለሁ'' ብለው
አመኑ ።

በዚህ ጊዜ ተይዘው የነበሩት መኳንንት ፤ ከእስራት ነጻ ሆነው
"ይቀጣልን'' ብለው ጮሁ ። በጉባዔው የተገኙት መሳፍንትና መኳ
ንንት ሁሉ ባንድ ቃል "ያስቀጣዋል'' ብለው ስለፈረዱ ፤ ደጃዝማች
ሥዩም እጃቸው ተይዞ ወደ እፍቀራ ለመላክ ከጉባዔ ሲወጡ ከጐጃም
"ደጃዝማች ሥዩም በድለውናል'' ብለው ወደ አዲስ አበባ ላቤቱታ
መጥተው የነበሩ የወንድ መኳንንትም ፤ የሴት ወይዛዝርትም ብዙ
ነበሩና ተይዘው ባጠገባቸው ሲያልፉ ዕልልታቸውን አቀለጡት ።



ደጃዝማች ሥዩም እንደተያዙ ፤ "ወንድሞቼ ይገዙሻል እንጂ አንቺ
አትገኘር'' የሚል ቃል ለሴቶቹ ወርውረው ወደ ግዞት ቦታቸው ወደ
አፍቀራ ሔዱ ።

እንደ ተባለውም ፤ ለታላቅ ወንድማቸው ለራስ በዛብህ በጐጃም
ላይ ሙሉ ሹልማት አድርገው ሾመው ወዲያውም ዝምድና እንዲጠ
ነክር በማለት ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ ሚካኤልና ከወይዘሮ ሸዋረጋ
የተወለደችውን ወይዘሮ ዘነበወርቅ የምትባለዋን የልጅ ልጃቸውን
ዳሩላቸው ። ዳሩ ግን አሁንም ራስ በዛብህ ፤ "በርሷ ሰበብ ዳሞትን አገ
ኛለሁ ፤ ራስ ቢቶደደ መንገሻም አርጅተው ይሞታሉ'' የሚል ምኞት
አድሮባቸው ሳለ በመካከሉ ሴትዮዋ ቀድማ ሞተች ። የሞተችውም
ተደብድባ ነው ይባላል ። ቀጥሎም ደጃዝማች ወዳጄ የሚባሉ ሚስ
ታቸውን በቅንዓት ደብድበው ገድለው ሸፍተው ሳለ ፤ የሚች ዘመዶች
"አዲስ አበባ መጥተው እንፋረዳለንና ይቅረቡልን'' ብለው አመለ
ከቱ ። እንዲቀርቡም ተደጋግሞ ለራስ በዛብህ ቢላክ ውስጠ ስምም
ነት ኖሮ ሳይልኳቸው ቀሩ ። በኋላ ግን ፤ በሌሎቹ በራስ በዛብህ መኳ
ንንቶች ግፊት ወዳጄን በወታደር አሲይዘው ወደ አዲስ አበባ ራሳ
ቸው ይዘዋቸው መጡ ። ሲመጡም ወዳጄ መንገድ ለመንገድ ፤ "ብቻ
ዬን አልሞትም'' ብለው ዝተው ነበርና አሁን በራስ በዛብህ አቅራ
ቢነት ሲፈረድባቸው ፤ "እኔና ራስ በዛብህ ጃንሆይን ከድተን ራስ መን
ገሻ አቲከምን ልንወጋ ተስማምተናል'' በማለት ራስ በዛብህ ስለ
ዚሁ በወዳጅነታቸው ጊዜ የጻፉላቸውን ደብዳቤ አቀረቡ ። ሰነዱም
የራስ በዛብህን ውስጠ ክዳት ስላጋለጠ ራስ በዛብህ ወዲያው ተይ
ዘው ወደአፍቀራ ሲላኩ ፤ ደጃዝማች ሥዩም ከአቀፍራ መጥተው ጐጃ
ምን ለሁለተኛ ጊዜ ተሾሙ ።[1]

እርስ በርስ መዋጋት በሁሉም አገር ይደርሳል ። ነገር ግን በኢትዮ
ጵያ ከደረሰው ጋር ሲያመዛዝኑት የኛው የከፋ ይመስላል ። ሕዝቡ
መሳፍንቱን ወዳድ ሲሆን ፤ መሳፍንቱ በየራሱ የሥልጣን ምኞት
እየተዋጠ በግድታ ካልሆነ በቀር ለሌላው መታዘዙን የማይወድ
ነው ። ለጊዜው ታማኝ ቢመስልም ጊዜና ወቅት አማርጦ የሚሸፍት ፤
እስራትም ግዞትም የማይበግረው ስለሆነ ፤ ጠቅላላው ሕዝብ የጸጥ
ጥታና የሰላም ጊዜ ያገኘበት ዘመን በጣም አጭር ነው ። የኢትዮጵያ
ንም ከጠቅላላ ታሪኩ ሰባ በመቶውን የያዘው የጦርነት ታሪክ መሆኑ
አሳዛኝ ነው ። አገራችንንም በልማት ወደኋላ ያስቀረ ይኸው
ሁኔታ ነው ።

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፤ ምዕራፍ 51—54 ፤ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ
ምኒልክ ፤ ምዕራፍ 70 ።

ብለው የላኩብህን ደብዳቤ ስታሳየኝ ነው ። ደብዳቤውን ካላሳየኸኝ በውነትም ልትወጋኝ ከጅለሃል ማለት ነው" ብለው መለሱ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ደጃዝማች ሥዩም አለቃ ተክሌና አለቃ ተገኝ በሚባሉ ሠዓሊዎችና ጥበበኞች አማካይነት በአፈ ንጉሥ ይግዛው ስም አዲስ ማኅተም አመሳስለው አስቀርፀው ፣ "ናልን መንገሻን እንውጋ" ብለው እነርሱ እንደ ላኩባቸው አስመስለው አስተኛውን ማኅተም አትመው ለራስ መንገሻ ላኩላቸው ። መንገሻም እውነተኛ ማኅተም መስሏቸው ለካ ያለሁት የኔን ሞት ከሚፈልጉ ጠላቶቹ ጋር ነውና" ብለው ሁሉንም አስረው ዝርዝር ሁኔታውን ጨምረው በ1894 ዓ. ም. አዲስ አበባ ወዳፄ ምኒልክ ላኩዋቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ደጃዝማች ሥዩምንና አዲስ ማኅተም አስመስለው ቀርፀዋል የተባሉትን አለቃ ቱገኝንና አለቃ ተክሌን ወደ አዲስ አበባ አስመጥተው ጉዳዩ በጉባዔ በሚታይበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ አፈ ንጉሥ ይግዛውን ራስ መስፍንን ፣ ፊታውራሪ ጓሉንና ፊታውራሪ መሸሻን እንደ ተያዙ ፣ "ይኸ የናንተ ደብዳቤና ማኅተም አይደለምን?" ብለው አሳይተው ቢጠይቋቸው ፣ "ማኅተሙ ይመስላል ፤ እኛ ግን እንደዚህ ያለውን ሥራ አልሠራነውም ። ነገር ግን ጠላትን አጥፍቶ አገር አስፍቶ ያነገሠዎ የጃንሆይ አምላክ እውነተኛ ፍርዱን አይነሣዎ ምና እንደ ገለጸልዎ ይመርምሩልን" ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ በጉባዔው ያለው መኳንንት ግማሹ ፣ "ከማኅተም ወዲያ ምን ምስክር አለ ? ይቀጡ ?" ሲል ፣ ሌላው "ማኅተም የያዘውን አሽከር በገንዘብ ገዝቶ ቢያሳትመውስ ?" ሲባባል ንጉሠ ነገሥቱ የተያዙትን የመኳንንቱን እውነተኛ ማኅተምና ደጃዝማች ሥዩም ያሠሩትን ሐሰተኛውን ማኅተም አቅርበው በማስተያየትና በመመርመር ፣ ትንሽ ልዩነት ስለታየ ንጉሠ ነገሥቱ ፊታቸውን ወደ ደጃዝማች ሥዩም አዙረው ፣ "እውነቱን ንገረኝ ። በኋላ ከደህ የተገለጸብህ እንደሆነ ቅጣቱ ይከብድብሃልና እውነቱን ብትነግረኝ ይሻልሃል" ብለው ቢጠይቋቸው ፣ " . . . እንዲህ ያለውን እግዚአብሔር ከገለጸልዎ በኋላ እንደ ምሕረትዎና እንደ ቸርነትዎ ያድርጉ እንጂ ምን እሰውርዎ አለሁ" ብለው አመኑ ።

በዚህ ጊዜ ተይዘው የነበሩት መኳንንት ፡ ከእስራት ነጻ ሆነው "ይቀጣልን" ብለው ጮሁ ። በጉባዔው የተገኙት መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ ባንድ ቃል "ያስቀጣዋል" ብለው ስለፈረዱ ፣ ደጃዝማች ሥዩም እጃቸው ተይዞ ወደ አፍቀራ ለመላክ ከጉባዔ ሲወጡ ከጐጃም "ደጃዝማች ሥዩም በድለውናል" ብለው ወደ አዲስ አበባ ላቤቱታ መጥተው የነበሩ የወንድ መኳንንትም ፣ የሴት ወይዛዝርትም ብዙ ነበሩና ተይዘው ባጠገባቸው ሲያልፉ ዕልልታቸውን አቀለጡት ።



ደጃዝማች ሥዩም እንደተያዙ ፣ "ወንድሞቼ ይገዙኛል እንጂ አንቺ አትገዥ" የሚል ቃል ለሴቶቹ ወርውረው ወደ ግዞት ቦታቸው ወደ አፍቀራ ሔዱ ።

እንደ ተባለውም ፣ ለታላቅ ወንድማቸው ለራስ በዛብህ በጐጃም ላይ ሙሉ ሽልማት አድርገው ሾመው ወዲያውም ዝምድና እንዲጠነክር በማለት ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ ሚካኤልና ከወይዘሮ ሸዋረጋ የተወለደችውን ወይዘሮ ዘነበወርቅ የምትባለዋን የልጅ ልጃቸውን ዳሩላቸው ። ዳሩ ግን አሁንም ራስ በዛብህ ፣ "በርሷ ሰበብ ዳሞትን አገኛለሁ ፤ ራስ ቤቶደድ መንገሻም አርጅተው ይሞታሉ" የሚል ምኞት አድሮባቸው ሳለ በመካከሉ ሲትዮዋ ቀድማ ሞተች ። የሞተችውም ተደብድባ ነው ይባላል ። ቀጥሎም ደጃዝማች ወዳጄ የሚባሉ ሚስታቸውን በቅንዓት ደብድበው ገድለው ሸፍተው ሳለ ፣ የሚች ዘመዶች "አዲስ አበባ መጥተው እንፋረዳለንና ይቅረቡልን" ብለው አመለከቱ ። እንዲቀርቡም ተደጋግሞ ለራስ በዛብህ ቢላክ ውስጥ ስምምነት ኖሮ ሳይልኳቸው ቀሩ ። በኋላ ግን ፣ በሌሎቹ በራስ በዛብህ መኳንንቶች ግፊት ወዳጄን ዘወታደር አሲይዘው ወደ አዲስ አበባ ራሳቸው ይዘዋቸው መጡ ። ሲመጡም ወዳጄ መንገድ ለመንገድ ፣ "ብቻ ን አልሞትም" ብለው ዝተው ነበርና አሁን በራስ በዛብህ አቅራቢነት ሲፈረድባቸው ፣ "እኔና ራስ በዛብህ ጃንሆይን ከድተን ራስ መንሻ አቲከምን ልንወጋ ተስማምተናል" በማለት ራስ በዛብህ ስለ ዚሁ በወዳጅነታቸው ጊዜ የጻፉላቸውን ደብዳቤ አቀረቡ ። ስነዱም ራስ በዛብህን ውስጠ ክዳት ስላጋለጠ ራስ በዛብህ ወዲያው ተይዘው ወደአፍቀራ ሲላኩ ፣ ደጃዝማች ሥዩም ከአቀፍራ መጥተው ጐጃምን ለሁለተኛ ጊዜ ተሾሙ ።[1]

እርስ በርስ መዋጋት በሁሉም አገር ይደርሳል ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ከደረሰው ጋር ሲያመዛዝኑት የኛው የከፋ ይመስላል ። ሕዝቡ መሳፍንቱን ወዳድ ሲሆን ፡ መሳፍንቱ በየራሱ የሥልጣን ምኞት የተዋጠ በግዴታ ካልሆነ በቀር ለሌላው መታዘዙን የማይወድ ው ። ለጊዜው ታማኝ ቢመስልም ጊዜና ወቅት አማርጦ የሚሸፍት ፡ ስራትም ግዞትም የማይበግረው ስለሆነ ፣ ጠቅላላው ሕዝብ የጸጥታና የሰላም ጊዜ ያገኘበት ዘመን በጣም አጭር ነው ። የኢትዮጵያም ከጠቅላላ ታሪኩ ሰባ በመቶውን የያዘው የጦርነት ታሪክ መሆኑ ሳዛኝ ነው ። አገራችንንም በልማት ወደኋላ ያስቀረ ይኸው ኔታ ነው ።

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፣ ምዕራፍ 51—54 ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕራፍ 70 ።

# ምዕራፍ ሰባ ሰባት

## የንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ምኒልክ ዕረፍት ።

ገናናው ንጉሠ ነገሥት ፣ በ1900 ዓ.ም. የጀመራቸው በሽታ እየጸና ሔዶ በመጨረሻ ሰውነታቸው ዝሎ አንደበታቸው ተዘግቶ እንደቆየ በታኅሣሥ 3 ቀን 1906 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። የሸዋ ንጉሥ ፣ በኋላም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ዘመን ሁሉ ክፉውን በክፉ ሳይሆን ፣ ክፉውን በደግነት እየመለሱ ፣ ጥፋትን ሁሉ በትዕግሥት እያሸነፉ ፣ አገር የሚሰፋበትን ፣ ልማት የሚዳብርበትን ፣ ሕዝብ ዕረፍትና ሰላም የሚያገኝበትን ከማሰብና ከመፈጸም አልተቆጠቡም ። የአውሮፓን ኃያል መንግሥት በጦር ሜዳ በማሸነፍ ኢትዮጵያን በዓለም እንድትደነቅ አድርገዋል ። ስለዚህ ሥርዓተ ቀብራቸው በታላቅ ሥነ በዓል መሳፍንትና መኳንንት ፣ የውጭ መላክተኞች በተሰበሰቡበት በወግ በማዕረግ ሊፈጸም በተገባ ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ ባልሠለጠኑና በሕገ መንግሥት መተዳደርን ባልለመዱ አገሮችና በኢትዮጵያ በወግ በማዕረግ የሚቀበር ንጉሥ ፣ በዙፋን በሰላም የሚተካ አልጋ ወራሽ ማግኘት ብርቅ ነው ። በዚህ ምክንያት ፣ የሞተን ንጉሥ ግርግር እንዳይነሣ አቻኩሎ በድብቅ መቅበርና ከዚያ ምቹ ወቅት ጠብቆ "የሞትንም እኛ ፣ ያለንም እኛ" ብሎ ዐውጆ ተወላጁን ማንገሥ የኢትዮጵያ ዓይነተኛ መልክ ነው ። አልፎ አልፎ ንጉሥ ታመመ ሲባል ፣ ሹክሹክታውና መታመሱ ወደ ግርግርታ ፣ ሲሞት ደግሞ ግርግታው ወደ ረብሻ ፣ ረብሻው ወደ ጦርነት ይለወጣል ። ባለፈው በኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ንጉሥ በታመመና ከሕመም ወደሞት በተሻገረ ቁጥር ወራሹ በዙፋኑ እስኪረጋጋ ድረስ ያለው የቤተ መንግሥታችን ደንበኛ ሁኔታው ይህ ነው ። በዚህም ሰበብ የሚሞተው ፣ የሚሰደደውና ንብረቱ የሚባክነው ብዙ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ሲሞቱ ፣ ተፋጦ የተቀመጠው የኢያሱ ወገን በአንድ በኩል ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ እስከ መጨረሻ የታመነው ፣ የእቴጌ ተከታይና የራስ አባተ እስራት የቆጨው ፣ በሌላው በኩል እያሉ ፣ ሁሉም

በአንድነት ተሰብስቦ የሚወዳቸውን ንጉሠ ነገሥት በወግና በሥርዓት ፣ በሰላምና በጸጥታ ለመቅበር አዳጋች መሆኑን ታላላቆቹ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተገንዝበዋል ። ሞታቸው ራሱ የተሰማ እንደሆነ ቀደም ብሎ የተቀያየመው በዚህ ጊዜ ገንፍሎ እርስ በርሱ ተዋግቶ አገር ይሸበራል በማለት ታላቁንና ስመ ጥሩውን ንጉሠ ነገሥት በዝምታና በሹልክታ እዚያው ቤተ መንግሥቱ ግቢ ባለው ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቀበሩዋቸው ። ወጣቱ ኢያሱም በዚህ ቀን ጃንሜዳ የፈረስ ጉግሥ ይጫወቱ ነበር ይባላል ። ይኸንንም ፣ "የሚወዳቸው ሕዝብ በንጉሠ ነገሥቱ ሞት እንዳይገነግን ሆነ ብለው ነው" ብሎ ግማሹ ሲያሳብብላቸው ፣ የቀረው ደግሞ "እሳድጎ ለዚህ መንግሥት ያበቃ አባትና አያት ሲሞት ጉግሥ መጫወት ውለታ ቢስነት ነው" ብሏል ። ይሁን እንጂ ፣ ምንም ለመደበቅ ቢሞከር ወሬው ካንዱ ወደሌላው እየተላለፈ ነገሩን የተረዳው ሁሉ "እምዬ ጌታዬ ! እምዬ አባቴ !" እያለ በየቤቱ ያለቅስ ነበር ። ከአልቃሾቹ አንዱ ፤

"ፈረስ በቅሎ ስጠኝ ብዬ አለምንህም
አምና ነበር እንጂ ዘንድሮ የለህም" አለ ይባላል ።

በንጉሠ ነገሥቱም ሞት ዋናዎቹ ሐዘንተኞች ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ፣ ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱና ብዙ መኳንንት ናቸው ። በልቅሶውም ጊዜ እቴጌ ጣይቱ እንደዚህ ብለው ገጠሙ ይባላል ።

ነጋሪት ማስመታት ፣ እምቢልታ ማስነፋት ነበረ ሥራችን ፣
ሰው መሆን አይቀርም ደረሰ ተራችን ።[1]

ወይዘሮ ዘውዲቱ በበኩላቸው ደግሞ እንደዚህ አሉ ።

አልፍ ነፍጥ በኋላው አልፍ ነፍጥ በፊት ፣ ባለወርቅ
መጣብር እያሌው ፈረስ ፤
ይመስለኝ ነበረ ይኸ የማይፈርስ ።

33 ዘመን የበላንበቱ የጠጣንበቱ ፣
የትሣሥ ባታ ለት ተፈታ ወይ ቤቱ ።

ብትታመም ልጅህ እጅግ ጨነቀኝ ፣
ብትሞትስ አልሞትም እኔ ብልጥ ነኝ ።

1 ጣይቱ ብጡል አጭር የሕይወት ታሪክ ፣ ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ ገጽ 59



ወልደውኛል እንጂ እኔ አልወለድሁዎ ፣
እንገሮቴን ተብትበው ምነው መሔድዎ ።

እሳዳጊ አላንተ አላውቅም እናት ፣
ምነዋ ሞግዚቴ እንዲህ ያል ክዳት ።

ቀድሞ የምናየው የለመድነው ቀርቶ ፣
እንግዳ ሞት አየሁ ካባቴ ቤት ገብቶ ።

እጅግ አዝኛለሁ አላቅሽኝ አገሬ ፣
የሁሉ አባት ሞቶ ተጐዳችሁ ዛሬ ።

ትንሽ ትልቅ አይል ለሁሉ መስጠት ፣
ከጢት እስከ ማታ ያለመሰልቸት ።

ድርቅ ሆኗል አሉ ዘንድሮ አገራችሁ ፣
ዝናሙ ሲጠፋ ምነው ዝም አላችሁ ።

አሻግሬ ሳየው እንዲያ በሰው ላይ ፣
መከራም እንደሰው ይለመዳል ወይ ።[1]

የገናናው ንጉሠ ነገሥት አስከሬን በሥረገላ ሆኖ ፣ ጉንጉን አበባ ተረብርቦ ፣ በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅቦ ፣ በነጋሪትና በእንቢልታ እየተሸኘ ፣ "እምዬ ጌታዬ" እየተባለ ፍትሐት እየተፈታ ፣ በይፋ በማልቀስ ወግና ሥርዓት ያለው አቀባበር አይደረግ እንጂ ፣ ብዙ መሳፍንትና መኳንንት በየቤታቸው አልቅሰዋል ።

ከነዚህም አንዱ ያፄ ምኒልክ ታማኝ አሽከር ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የሚባሉት ፣ "ሣህለ ማርያም የሚባል ወንድሜ ሞቶ መርዶው መጣልኝ" ብለው ምክንያት በመስጠት ፣ በሐዘን እያለቀሱ እቤታቸው ሰንብተው በኋላም ለዐርባው አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ድግስ ደግሰው ያፄ ምኒልክን ተዝካራቸውን አወጡ ። ሣህለ ማርያም ያፄ ምኒልክ የክርስትና ስማቸው ስለሆነ ፣ በወንድማቸው አመካኝተው ላፄ ምኒልክ ነው ሐዘኑም ተዝካሩም የተፈጸመው ።[2]

1. ያለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፣ ገጽ 202—203
2. አለቃ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ የጽሑፍ ማስታወሻ ፣ ገጽ 44



**ዳ፪ ምኒልክ**



ሞዋ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ
እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ከኮንት ፔትሮ አንቶኔሊ ከመጣህ እስከ
ዛሬ ድረስ ስለ ተነጋገርነው ነገር ሁሉ ሙሉ ሥል
ጣኔ በአ፡ ሠ፯ዘ፱ በ፲፫ የገበሬ በተጻፈ ውል
ኦይ ያለ ፲፯ኛ ክፍል ተስማምተን ይሰረዝ ፡ ስላ
ክኝ ነገር ግን ለኢትዮጵያ ለኢጣልያ መንግሥ
ት የሚያስማማ ምላሽ ይስጡን ብለህ ስለ ፡ ለመን
ኝ ፲፯ኛው ክፍል ባማርኛም በኢጣልያም
ተጻፈው ስር ዘነዋል ይቀርም ስላልነ የሁለ
ትን መንግሥት ዩስ ማሰነቆ ይገባልና ለን
ሥ ያምበርማ የዚህን ፲፯ተኛ ክፍል ምላሽ
ሉ ስዩ ፲ ልዋለሁና ከንጉሥ ያምበርማ ፊት
ዩሬስ በኋላ ቀር የሚላችሁ እንዲለ ምላሹን
ተብለህ ማሉ እንድትሐክብኝ ተስፋ አደርጋለሁ።
ጥር ፡ በሐቀን ፡ በ፲፰፻፹፫ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በዲስ ፡ አበባ ፡ ከ
ተማ ፡ ተጻፈ ።

ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

አርኪቪዮ ኤቲዮፒኮ

ሞዓ፡አንበሳ፡ዘእምነገደ፡ይሁዳ፡ዳግማዊ፡ምኒልክ፡ሥዩመ፡እግዚአብሔ
፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢትዮጵያ።
ይድረስ፡ወደ፡ክቡር፡ወደ፡ተቀዳሚ፡የሮም፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ሊዎን፡፲፫ኛ።
ሰላም፡ለርስዎ፡ይሁን።   የከበረው፡ያባትነትዎ፡ደብዳቤዎ፡በቡነ፡መቃር
ስ፡እጅ፡ደረሰልኝ። በዚህም፡ደብዳቤዎ፡የተጻፈውን፡መላላካችንን፡አሳምሮ፡
የሚያስታውስ፡እግዚአብሔር፡ከኔ፡እጅ፡የጣላቸውን፡ስለ፡ኢጣልያ፡ምርኮኞች፡
ርነት፡ሥራ፡እንድሰራ፡የሚያመለክት፡መሆኑን፡በጣም፡አየሁ። ደግሞም፡
በሬ፡ቅዱስነትዎ፡ከአቡነ፡መቃርስ፡የበለጠ፡መልክተኛ፡ነገሩን፡በጣም፡አስረ
፡እጣፍጦ፡ሀሳብዎን፡የሚናገር፡መላክ፡እንዳይቻልዎ፡አወቅን። የክርስ
ን፡ሁሉ፡አባት፡የላከው፡እጅግ፡የሚያስደንቅ፡ደብዳቤዎን፡ባነበብሁ፡ጊዜ፡
ን፡መታው። ደግመኛም፡የከበረውን፡የመልክተኛዎን፡የቃል፡ንግግር፡በሰ
፡ጊዜ፡ልቤ፡ቅዱስነትዎ፡በሚከብር፡ለለመኑኝ፡ጉዳይ፡ለመፈጸም፡ጨከነ፡ነበ
ረ፡ሣልፈልገው፡በዚህ፡በከፉ፡ጦር፡የሞቸው፡ለፈሰሰ፡በከንቱ፡ላለቀ፡
ደሮች፡እጅግ፡አለቀስሁ። ነገር፡ግን፡ቅዱስነትዎ፡የተመኙትን፡ለመፈጸም፡የኢ
፡መንግሥት፡ያልታሰበው፡የዛሬ፡ሥራቸው፡የማያስፈቅድ፡መኘ፡ሆነ። ይህ
፡ማለቱ፡የእርቅ፡ፈቃድና፡በደህና፡ለመላላክ፡መመኘታቸውን፡ካሳዩኝ፡በ
ሥራቸው፡በጦርነት፡እንዲለሰን፡አደረገው፡ይኼ፡ነው፡ነገር። አሁንም፡
በኔ፡ንጉሥነቴና፡የሕዝብ፡አባትነቴን፡ይህን፡አውቆ፡በእጄ፡ያለውን፡የ
፡ምርኮኛ፡መልቀቅ፡የማይቻለኝ፡ሆነ። ቅዱስነትዎ፡ያሰበውን፡ሀሳብ፡ዩለ፡

**ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**
**አርኪቪዮ ኢቲዮፒኮ**

ለማስኘት፡የኒኛም፡መልካሙን፡ሀሳብ፡ለመፈጸም፡ክለከለኝ። በክርስቲያንነቴና፡
በንጉሥነቴ፡ልብ፡አውጥቼ፡አውርጄ፡ሳበቃ፡የፍቅሬን፡ምልክትና፡ብዙ፡ማክበ
ሬን፡በሌላ፡ቀን፡እጽርገዋለሁ፡ማለት፡ስለሆነብኝ፡ዛሬ፡ሳይሆንልኝ፡በመቀረቱ፡አ
ዥኛ፡ያሳዝነኛል። እግዚአብሔር፡እዚሬ፡የሰጠኝ፡መንግሥቴን፡የሕዝቤን፡ነፃ
ነት፡የምፈልግ፡ስለሆንሁ፡በክርስቲያኖች፡ሁሉ፡በማክበር፡የሚሰማውን፡የቀ
ድስናም፡ቋምነ፡ለኛ፡ብለው፡እንዲያሰሙልኝ፡ተስፋ፡አለኝ። ይህ፡የሆነ፡እንዲሆ
፡ከዘመዶቻችሁም፡ለተለዩ፡ምርኮኞች፡በቀርቡ፡ለመመለስ፡እንዲመችን፡
ጽፌላዎ፡ነው። ነገር፡ግን፡ይህ፡ነገር፡እስኪጨረስ፡ድረስ፡ከኔ፡ዘንድ፡ያሉትን፡
ምርኮኞች፡እንደ፡ክርስቲያን፡ሥራ፡ከዚህ፡ቀድም፡ጠብቄ፡በመልካም፡አድ
ርጌ፡እንደምርኂቸው፡ይልቁንም፡ከእንግዲህ፡ወዲህ፡ስለር ሰዎ፡ፍቀር፡በ
ሙን፡ጠብቄ፡በደህና፡አሣምሬ፡እንደምራቸው፡በዚህ፡አይጠርጥሩኝ።
መስከረም፡በ፲፩ ቀን፡በዴስ፡አበባ፡ከተማ፡ተጻፈ።
፲፰፻፹፱ ዓመተ፡ምሕረት።

ከርማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቪዮ ኤቲዮፒኮ


የተላከ፡ ከእቴጌ፡ ጣይቱ፡ ብርሃን፡ ዘኢትዮጵያ።

ይድረስ፡ ከማጆር፡ ሲዝር፡ ኔራዚኒ፡ የኢጣሊያ፡ መንግሥት፡ በሙሉ፡ ሥልጣን፡ መልክተኛ።

ሰላም፡ ለንተ፡ ይሁን።

ስለፍቅር፡ የተደረገውን፡ ውል፡ የኢጣሊያ፡ ንጉሥ፡ ተቀብለው፡ እሶሙ፡ ብለዘ፡ የላኩሽው፡ ደብዳቤ፡ ደረሰልኝ፡ እጅግ፡ ደስ፡ አለኝ፡ ደግሞ፡ እግዚአብሔር፡ ፍቅራችንን፡ ለዘለዓለም፡ እንዲያጸና፡ እስከ፡ ምጽአቱ፡ ድረስ፡ የማይፈርስ፡ ያድርገው። በመጋቢት፡ በ፲፰ ቀን፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ተጻፈ።

በ፲፰፻፹፩ ዓመተ፡ ምሕረት።



ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

አርኪቭ ኢቲዮፒኮ

የተላከ፡ከራስ፡ዳርጌ፡ደጅ፡ረስ፡ከሐኪም፡ነራዚኒ፡እንደት፡አለ
ሁ፡እኒ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ።
ወረቀትህም፡ደረሰልኝ። እኒ፡ከዚህ፡ቀደም፡አላውቁህም፡ነበ
ረ። አሁን፡በወረቀትህ፡ነው፡ማወቄ። ከዚህ፡ቀደም፡ደህን፡
ደህል፡ቀን፡ሳላውቅህ፡መቅረቴ፡ምንኛ፡ተጎዳቻለሁ። አሁን
ም፡የልጅን፡የልጅ፡ጉዳዩን፡ነገር፡ወደ ኢጣልያኖች፡መግባ
ትን፡የላከህብኝን፡ሰማሁ። ደኅና፡ከሆነ፡መልካም፡ነው፡እን
ጂ፡ምን፡ነገር፡አለ፡ያጤ፡ምኒልክን፡አልጋ፡መቀበል፡ነው፡ሌ
ንጂ። እኔም፡አባቴ፡አደሳ በባን፡አልጋውን፡ደገር፡ተቀምጫ
ለሁ። ምን፡የሚቸግር፡ነገር፡አለ። ዳሩ፡ግን፡ያንተ፡ደብዳቤ፡
ብቻ፡ነው፡እንጂ፡የመጣው፡የሌላ፡ደብዳቤ፡አልመጣልኝ
ም። ደህ፡ነገር፡አሰት፡ውሸት፡የሆነ፡እንደሆነ፡እንተንም፡ነ
ራዚኒ፡የተባልከውን፡የዚፉ፡እባብ፡የለመርዝ፡ያስመስል
ሃል። ኢጣልያኖችንም፡ጉልበቱ፡ቢያንሣቸው፡የሃበሻን፡
ጉልበት፡የፈለጉ፡ያስመስላቸዋል። ያንተንም፡ሐኪምነት፡
የመልካም፡የዳ፡የነበርከውን፡የውሸትና፡የቀጥፈት፡
ሐኪም፡ያስመስልህ፡ደመሰላል። ዳሩ፡ግን፡ሐሰቱን
ም፡እውነቱንም፡የሚያውቅ፡መለኮት፡ደመልከት።
በጥር፡በ፳ ቀን፡ተጻፈ። ባደሰ፡አበባ፡ከተማ። በ፲ወ፰፻፹
ወ፰ ዓመተ፡ምሕረት።




ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቪዮ ኢቲዮፒኮ

ወተካከ፡ ነፌስ፡ መከዋግየ ዋሐሬየ ዮ
ውራ ዲዋ፡ ግዥ፡፡ ደዋሬስ፡ ከወዊን ነ
ዱክዋር፡ ኔሩ ዝኒ፡፡—

ሰላምታ የው፡ ሳገት፡ የሄዋ፡፡
በሰኒ፡ በጟዋኝ፡ የተዳሌ፡ ወረቀትህ ዷሬ
ሰሬኝ፡፡ የኔን፡ አዩ.ፔ፡ የጄፃዋይንጀህ ላ
ክሁ፡፡ ደሄ፡ ወረቀት፡ ወዋቁ፡ ምክንያ ኒ
ስኒመላ፡ ዴሬስ፡ አዚደው፡ ዘዲላ፡ ኢ
ንዷት ቀዩ፡ ዲሁኝ፡፡ ከፃኝዋዩ፡ ፍቀዷ
ካፌወጣ፡ እኔ፡ ፍቃዴ ልሰጥህ አይቻ
ለኝም፡፡ እኔም በዚያ፡ ኩበት፡ መዋገዴ
ኒዴ ጓ፡ ዷሌ፡ በሎሻ፡ ተጣዋት፡ አቢቴ፡
ነበሁ፡፡— ኒኽኒ፡ በፊር፡ ጫር፡ ዊሮ
ሁ፡፡ ተጻፈ፡ ስረር፡ ሰኔ፡ ሰማን፡ ፲፻ዩ...

**ከርግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**
**አርሺቭ ኢቲዮፒክ**

ይ.ያ·ረስ፡ ንብ·ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ፡ ምኒልክ
ንጉ·ሠ፡ነገሥት፡ ዘኢ·ት·ዮ·ጵ·ያ። ፬ንሆዩ·፡ የሬ·ስ·ዲ·ርጊ
ን፡ ለማረፍ፡ የላክ·ብኝ፡ ክ·ቡር፡ ለማሳተምዉ፡ ዲ.ሬስኝ
አ፬·ግ፡ አዘነሁ·፡ አኔ·ስ፡ ፈ·ት·ም፡ የሕማምምን፡ ብር ታ
ት፡ ስምቸ፡ አዛገር፡ እምቡ·ን፡ ጠይ·ቀሽልኝ፡ ነ፡ ብዬ·· ስ
ዩ·፮ው·፡ነበር። ዲ·ር ስ፡ ለሞ·ተ·፡ ይ·ካማቸ·ው·ን፡ ነገሩኝ፡
አለጊዜ·ው፡ ነፍ·ስ፡ አትለይምእን፩·፡ መጸነፋቸ·ው·ንአ·
ክዚ.ሳም፡ ቀዲ.ም፡ ሰማሁ·፡ አጠ·ነት·፡ ነው··አሁ·ንም፡
፯ንሆዩ·፡ ምስጉም የሁ·ሳች·ኝ፡ አባት በ·ሆኑ·፡ የል
ለማጊ·ን እግዚአብሔር ሮሞናም·ሕ·አኔ·ስ፡ ፭ንሆዩ··አ
ት·ምጣ፡ ብለው·፡ ቢ·ልኩ· ብኝ፡ ነው·፡ እን፮፡ ስንኳን፡
እንዲ·ሳ· ይለ፡ ነገር·ሊ·ሆን፡ እንዲያው·ም፡ ፯ንሆዩ·፡
የፍቀው·ኝ፡ እመጣለሁ· ብዬ··ነበር ሐ·አሁንም፡ የ
ኀዘን፡ ደርቻ፡ ደደ·ርጓልኝ። የተላከ፡ ክ·ቡ·ሥ፡ ተክ
ለ፡ ሃይማኖት፡ ርቱዕ፡ ሃይማኖት፡ ወልደ· ሰቀዩ·
ስ፡ ማርቆስ፡ ወንጌላዊ ሖሆው፡ አበ፡ ነጋሚ፡ መዩ·ኔ
ኔ፡ ኪሰም፡ ጠ·ነ፡ ዩ· ስጥልኝ፡ ዘዩ፲፲ ጊዜ፡ ኢ፮፡ ኢነሣ
ለሁ፡ በመጋቢት· በ፳፰ቀን፡ በ፲፰፻፺፱ ዓመተ፡ ምሕ
ሕረት፡ በጉድሩ፡ ሰፈር፡ ተጻፈ። ፨ ፩



ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቪዮ ኤቲዮፒኮ

# UMBERTO I.

Per grazia di Dio e per volontà della Nazione

# Re d'Italia

A tutti coloro che le presenti vedranno, salute.

Un Trattato di

Commercio essendo stato concluso fra il Regno

[illegible]

# Traité de Commerce.

Sa Majesté Humbert I Roi d'Italie et Sa Majesté Menilek II Roi des Rois d'Ethiopie, pris dans l'intention de régler les rapports commerciaux, de les développer et de les rendre de plus en plus avantageux aux deux puissances contractantes, Sa Majesté Humbert I ayant envoyé et choisi des pleins pouvoirs Monsieur le Major César Nerazzini, Grand officier de la Couronne d'Italie et chevalier des Saints Maurice et Lazare, S. M. Menilek II Roi des Rois d'Ethiopie en son propre nom et Monsieur le Major Nerazzini au nom de Sa Majesté le Roi Humbert I ont convenu et arrêté les articles suivants.

## Article I.

Les sujets de chacune des deux parties contractantes auront pleine liberté d'entrer, de sortir et d'exercer leur commerce dans les territoires de l'autre, jouissant de la protection du gouvernement sous la juridiction duquel ils se trouvent.

## Article II.

Il est convenu que les deux parties contractantes feront de leur mieux

pour

[illegible]

## ፫ተኛ፡ ክፍል

[illegible]

## ፬ተኛ፡ ክፍል

[illegible]

## ፭ተኛ፡ ክፍል

[illegible]

pour développer les routes de commerce entre leurs possessions et garantir aussi la sûreté des négociants et de leurs marchandises.

## Article III.

Les sujets éthiopiens dans les États de l'Italie et les sujets italiens dans les États éthiopiens jouiront en ce qui concerne les droits de douane, les impôts intérieurs et le traitement général dans les avantages qui seront accordés par les deux gouvernements aux sujets d'autres nations.

## Article IV.

Le transit des armes et munitions de guerre destinées à S. M. le Roi des Rois d'Éthiopie est autorisé à travers les territoires dépendants du gouvernement italien sur demande de Sa Majesté sous les conditions prescrites par l'acte général de la Conférence de Bruxelles, signé le 2 juillet 1890.

## Article V.

Tout matériel destiné au service de l'État éthiopien aura le droit de passer en Éthiopie par les ports et territoires italiens en franchise de douane sur demande de S. M. le Roi des Rois d'Éthiopie, de même

[illegible]

፮ ተኛ ፡ ክፍል ።

[illegible]

፯ ተኛ ፡ ክፍል ።

[illegible]

፰ ተኛ ፡ ክፍል ።

[illegible]

même tout le matériel destiné au service du gouvernement italien passera en franchise de douane par les portes et territoires éthiopiens.

## Article VI.

Dans le but de favoriser les rapports commerciaux entre les possessions italiennes du côté de l'Océan indien et le Sud de l'Empire d'Ethiopie, les deux gouvernements s'engagent d'étudier d'un commun accord l'établissement de routes commerciales nouvelles et sûres.

## Article VII.

Pour bien surveiller et garantir les rapports amicaux entre l'Italie et l'Ethiopie, les deux parties contractantes ont convenu de s'envoyer mutuellement des représentants agréés et choisis par chacun des deux gouvernements, et il est entendu qu'en cas qu'un représentant ne conviendrait pas, qu'il sera remplacé.

## Article VIII.

Le présent traité pourra être modifié et renouvelé d'un commun accord en tout ou en partie après trois ans à partir

[illegible]



partir de la date de sa signature. Dans ce cas les modifications doivent être notifiées par la partie contractante qui les propose à l'autre partie six mois avant ce délai de trois ans.

## Article II.

Le présent traité devra être ratifié par le gouvernement de S. Majesté le Roi Humbert dans le délai de six mois à partir d'aujourd'hui et entrera en vigueur dès que la Ratification sera notifiée à S. Majesté l'Empereur d'Éthiopie.

En foi de quoi S. M. Ménélek II Roi des Rois d'Éthiopie en son propre nom et Monsieur le Major Nerazzini au nom de S. M. Humbert, Roi d'Italie ont signé le présent traité, fait en deux exemplaires, écrit en amharique et en français identiquement, les deux textes étant considérés comme officiels et y ont apposé leurs sceaux.

Fait à Addis Abeba le 24 juin 1897.

[illegible]



# በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የነበሩ መሳፍንትና መኳንንት

## ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ

አቤቶ ዳርጌ ፡ የፈረስ ስማቸው አባ ግርሻ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴና ከወይዘሮ ወሪኔ (የሥልጤ ባላባት ልጅ) ይወለዳሉ ።

ከዐፄ ቴዎድሮስ ዕረፍት በኋላ በእንግሊዝ የጦር አለቆች ፈቃድ እንደሌሎቹ ተፈትተው ፤ ወደ ሸዋ እንደመጡ በደጃዝማችነት ማዕረግ ቆይተው ፤ በ1871 ዓ.ም የራስነት ማዕረግ አግኝተው የራስ ወርቅ አሰሩ ።

በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ (1888 ዓ.ም) ራስ ዳርጌ በአዲስ አበባ ተቀምጠው በእንደራሴነት ያገሪቱን ጸጥታ እየጠበቁ በደንብ አስተዳድረዋል ። ይኸም በዚያን ዘመን የምኒልክንና የእርሳቸውን መተማመን የሚያስረዳ ነው ።

ራስ ዳርጌ ፡ በጦርነትና በአስተዳደርም ኢትዮጵያን አገልግለው ዕድሜ ጠግበው ፡ ብዙ ዘር አትርፈው በ1892 ዓ.ም በመጋቢት 15 ቀን ዐርፈው ደብረ ሊባኖስ ገዳም በክብር ተቀበሩ ።

## ራስ ጐበና ዳጨ

ጐበና ያባታቸው ስም ዳጨ ፡ የእናታቸው ስም ጐራዲት ፡ የፈረስ ስማቸው አባ ጥጉ ፤ የትውልድ አገራቸው አብቹ ነው ።

ደጃዝማች ምኒልክ ፡ ከመቅደላ አምልጠው ከበዛብህ ጋር ጋዲሎ (ግድም) ላይ የተዋጉለት የሸዋ ተወላጅ ሁሉ ለምኒልክ ማድላቱን በመረዳት ፡ የበዛብህ አጋፋሪ የነበሩት ጐበናም የጋዲሎውን ጦርነት በበዛብህ ጋር ሆነው ሳይካፈሉ ወደ ምኒልክ ስለዞሩ ፡ ወዲያው የደጃዝማችነት ማዕረግ አገኙ ። ቀጥሎም በ1871 ዓ.ም ከደጃዝማች ዳርጌ ጋር ሁለቱ ራስ ወርቅ አስረው የራስነት ማዕረግ ተቀበሉ ። እነዚህም መጀመሪያዎቹ ያፄ ምኒልክ ራሶች መሆናቸው ነው ።

የደቡብ ክፍል አውራጃዎችን በማዕከላዊው መንግሥት ሥር ለማጽናት በተካሔደው ትግል ራስ ጐበና በአብዛኛው ዋና ተካፋይና ያፄ ምኒልክ ዋና የጦር መሪ ነበሩ ። በገዥግንነትም ስመጥር ናቸው ። በዚያም ዘመን የጀግንነት ነገር በተነሣ ቁጥር "በትግሬ አሉላ ፤ በሸዋ ጐበና ፤ በጐጃም ደረሶ" እየተባለ የሦስቱ ዝነኛነት ጐልቶ ሲወራ ይኖራል ። ባፄ ምኒልክ መንግሥት ተከብረው

ተፈርተው ሲኖሩ ሰኔ 27 ቀን 1881 ዓ.ም. ሞተው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ ።

## ደጃዝማች ናደው

ደጃዝማች ናደው ፡ የፈረስ ስማቸው አባ ባሕር ከንጉሥ ኃይለ መለኮት መኳንንት አንዱ ናቸው ። በዚህ ምክንያት ለምኒልክ ከልጅነት ጀምሮ ሞግዚት ነበሩ ።

ዐፄ ዮሐንስ ፡ ከእንግሊዞች በስጦታ ፡ ከግብጾችም በጦርነት ማር ከው ባገኙት በብዙ የጦር መሣሪያ ወታደራቸውን አስታጥቀው ወደ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ ፡ እርሳቸውንና ምኒልክን ፡ ለማስማማት በተደረገው ግልግል ደጃዝማች ናደው ዋንኛው መላክተኛና ገላጋይ እንደነበሩ ይታወሳል ። እርሳቸውም የራስ ተሰማ አባት መሆናቸው ነው ። የሞቱበት ጊዜ አይታወቅም ።

## ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ

ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ ፡ የፈረስ ስማቸው አባ ጉራች የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሣህለ ሥላሴ ባለቤት ፡ የራስ መኰንን ፡ የደጃ ዝማች ኃይለማርያምና የወይዘሮ እህተ ማርያም አባት ናቸው ። ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፡ ከንጉሥ ኃይለ መለኮትና ከንጉሥ ምኒልክ ታላ ላቅ መኳንንት አንዱ ናቸው ። ግዛታቸው አንኮበር አጠገብ ጎላ የሚባለው ነበር ።

## ደጃዝማች ገርማሜ

ደጃዝማች ገርማሜ ወልደ ሐዋርያት ፡ የፈረስ ስማቸው አባ መላ የንጉሥ ኃይለመለኮት አሽከር ነበሩ ። ኃይለ መለኮት ከሞቱ ወዲህ ወጣቱን ምኒልክን ተከትለው አብረው ጐንደር ሔደው በዚያው ተቀ መጡ ። ወይዘሮ ቀጠሮን በሚስትነት አግብተው ታላቅ የወዳጅነት ግብዣ በማድረግ የምኒልክን ጠባቂዎች በመጠጥ አስክረው ምኒልክን ከመቅደላ እንዲያመልጡ ያደረጉ ገርማሜ ናቸው ።

ምኒልክ ሸዋ ገብተው ከነገሡ ወዲህ ፡ ከምኒልክ መኳንንት ከዋ ነኞቹ አንዱ ናቸው ። ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ምኒልክ ከሸዋና ከወሎ አልፈው ቤጌምድርንና ጐጃምን አስገብራለሁ ብለው በ1869 ዓ.ም የዘመቱ ጊዜ በሸዋ የንጉሡ እንደራሴ የነበሩት ደጃዝማች ገርማሜ ነበሩ ።



ደጃዝማች ገርማሜ ምክር ዐዋቂና ለሞኝ ዘር ሁሉ እንደ በላይ አባት ሆነው ላፄ ምኒልክ ዋና አማካሪ ነበሩ ።

## ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን

ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል ፡ ከመዠመሪያዎቹ ያፄ ምኒልክ ታላላቅ መኳንንት አንዱ ናቸው ። በጐንደሩም የግዞት ዘመን ከምኒልክ አል ተለዩም ።

ምኒልክ ወደሸዋ ተመልሰው ከነገሡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የሐረርጌን ዙሪያ ኢቱንና ጨርጨርን ያስተደደሩ ናቸው ። ዐፄ ምኒልክ ራሳቸው ወደ ሐረርጌ በዘመቱበት ጊዜ የሐረርን ግዛት ልሹምህ ቢሏቸው ለልጃቸው ለቀኛዝማች መኰንን ይሰጡልኛል ብለው እምቢ አሉ ። ዐፄ ምኒልክ ለባላምባራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው ሐረርን ሰጧቸው ።

ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የዚህን ወሬ ሲሰሙ ፡ "እዩጉድ ለኔ መኰንን ቀርቶ ለራሳቸው መኰንን ሰጡት" ብለው በጸጸት ተናገሩ ይባላል ። እርሳቸውም የራስ ብሩ አያት መሆናቸው ነው ። ብሩ በአባ ታቸው በሀብተ ማርያም በመጠራት ፈንታ በአያታቸው ብሩ ወልደ ገብርኤል ይባሉ ነበር ።

## ራስ መንገሻ አቲከም

መንገሻ አቲከም ፡ በአገው ምድር የባላባቱ የከንቲባ አቲከም ልጅ ናቸው ። በጐንደር ኑሮ ከምኒልክ ጋር ተዋውቀውና ተላምደው ነበ ርና ከቤጌምድር መጥተው ላፄ ምኒልክ አደሩ ። ጥቂት ጊዜ እንደቆዩ ደጃዝማች ተብለው ኤፍራታን ይገዙ ነበር ። ዐፄ ምኒልክ በዋሉበት በአብዛኛው አገር የማቅናት ጉዳይ በጦርነቱም በምክሩም አልተለዩም።

ዐፄ ዮሐንስ ፡ በ1881 ዓ.ም. ዐርፈው ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነቱን ሥልጣን እንደያዙ ፡ የራስነት ማዕረግ አግኝተው ዋና አማካሪ ሆነው የግል ጦራቸውን ይዘው የዓድዋን ዘመቻ ተካፍለዋል ። በመጨረሻም ራስ ቢትወደድ መንገሻ እየተባሉ እንደ ሙሉ እንደራሴ ሆነው ያፄ ምኒልክ ዋና አማካሪና ባለሟል ነበሩ ። እርሳቸውም የራስ ከበደና የወይዘሮ ወሰንየለሽ አባት ፡ መሆናቸው ነው ።

## ራስ ወሌ ብጡል

ራስ ወሌ ብጡል ፡ ወሌ አባ ጠጣው ፡ በጐንደር ከደጃዝማች ምኒልክ ጋር ተዋውቀው በዚያው ሰበብ ወደሸዋ ከወንድማቸው ከአሉላ ጋር መጥተው ስለነበረ ወሌ የደጃዝማችነት ፡ አሉላ የፊታውራሪነት ማዕረግ አገኙ ። ቀጥሎም ታላቅ እህታቸው ወይዘሮ ጣይቱ ብጡል ከንጉሥ ምኒልክ ከተጋቡ ወዲህ ወሌ በአገልግሎትም ፡ በአማችነትም ስለ አስደሰቱ ፡ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ወዲህ የራስነት ማዕረግ አግኝተው ባለሟል ሆኑ ። የዓድዋንም ጦርነት ተካፍለዋል ። በግዛትም ቤጌምድርን ፡ ከዚያም ለብዙ ጊዜያት የጁን እየተሾሙ በግዛት ወሰን ብዙ ጊዜ ከወሎው ከራስ ሚካኤል ጋር ይጣሉ ነበር ።

ራስ ወሌ በገርግንነትም ስመጥር ከመሆን የተነሣ ፡ "ዐሥር ፊታውራሪ ሰባት ደጃዝማች የጠመቀውን ፡ የወሌ ፈረስ ጠጣው ብቻውን " ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።

ወሌ የንግሥት ዘውዲቱን ባል ራስ ጉግሣን ፡ የራስ መንገሻ ዮሐንስን ባለቤት ወይዘሮ ከፈይንና ደጃች ዓመዴን ይወልዳሉ ።

## ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል

ራስ መኰንን አባቃኘው ፡ የንጉሥ ሣህለሥላሴ የልጅ ልጅ ፡ የወዘሮ ተናኘ ወርቅና የደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ልጅ ናቸው ።

ከልጅነታቸው ጀምሮ ያፄ ምኒልክ የእልፍኝ አሽከር ሆነው ሲያገለግሉ ኖረው በብዙ የጦርነት ቦታም ውለው የራስነት ማዕርግ አገኝቶ ዋል ።

እንደ በኩር ልጅ የሚያዩዋቸው ምኒልክ አልጋ ወራሽ ሊያደርጉዋቸው ነው እየተባለ ሲወራ ፡ ወራሹ ከአውራሹ ቀድመው በ1898 ዓ. ም. መጋቢት 9 ቀን ዐርፈው ሐረርጌ በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል ተቀበሩ ።

## እፈ ንጉሥ ነሲቡ

እፈ ንጉሥ ነሲቡ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ዳማ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴና በንጉሥ ኃይለ መለኮት ጊዜ ባገራቸው በአልዩ አምባ ጠበቃ ሆነው እንኮበር ይሟገቱ ነበር ይባላል ። በ1890 ዓ . ም. በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚኒስትሮች ካቢኔ ሲቋቋም ፡ አፈንጉሥ ነሲቡ የፍርድ ሚኒስትር ሆነው እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሁሉም ተቀዳሚ ፣ በሁሉም ዘንድ ተፈሪና ተከባሪ እንደ ነበሩ ይነገራል ።



## ራስ ወልዴ አባ ሥዩም

የግድምና የኤፍራታ ባላባት ናቸው ። ላፄ ምኒልክ በፊት ደጃዝማች ወልዴ እየተባሉ ለረጅም ዘመን በወታደርነትም በአስተዳደርም አገልግለዋል ። በኋላም የራስነት ማዕረግ አግኝተዋል ። ወደ መስኮብና ወደ ፈረንሳይ አገር በመልእክት ሔደው የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማየት ችለዋል ።

## ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ

ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ሰጉድ ነው ። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ፣ ያፄ ምኒልክ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽም ልጅ ናቸው ።

በደቡብ ኢትዮጵያ አውራጃዎችን በማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማጽናት በተደረገው ጥረት የከፋውን ንጉሥ አሳምነው ላፄ ምኒልክ ያቀረቡ እርሳቸው ናቸው ። ቀጥሎም ወደ ጐንደር ተዛውረው ቤጌምድርንና ስሜንን አንድ አድርገው በራስነት ማዕረግ ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል ። ንግሥት ዘውዲቱ በ1909 ዓ . ም የነገሡ ጊዜ ፣ እርሳቸውንም በየካቲት ወር የጐንደር ንጉሥ ብለው ሾሟቸው ። ከዚያ ምንም ያህል ሳይቆዩ በየካቲት 24 ቀን 1910 ዓ . ም ሞተው በደብረ ታቦር ተቀበሩ ።

## ራስ ቢቶደድ ተሰማ ናደው

ራስ ተሰማ አባ ቀማው ፣ ያፄ ምኒልክ ሞግዚት የነበሩት የደጃዝማች ናደው ልጅ ናቸው ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንዳሉት በኢሉባቦር (ጐሬ) እስከ ነጭ አባይ ድረስ ያለውን አገር አቅንተዋል ።

ዐፄ ምኒልክ ከ1901 ዓ.ም. ጀምሮ ሕመም በተሰማቸውና ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሻቸው መሆኑን ባወጁ ጊዜ ለወጣቱ ለልጅ ኢያሱ ሞግዚትና የመንግሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል ። ነገር ግን ሳይታሰብ በድንገት ታመው በ1903 ዓ.ም. ሞተው በደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ ።

## ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ

መሸሻ ወርቄ ፣ የቤጌምድሩ ያፈ ንጉሥ ወርቄ ልጅ ናቸው ። ከቤጌምድር ወደ ሸዋ መጥተው ካፄ ምኒልክ መኳንንት አንዱ በመሆን አገልግለዋል ።

ሁለት ጊዜ በመልእክት ወደ አውሮፓ ሔደው ተመልሰዋል ። ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ እርጅናም ሕመምም ተጭኗቸው ሞቱ ።

## አዛዥ ወልደ ጻድቅ

አዛዥ ወልደ ጻድቅ የፈረስ ስማቸው አባ መንዝር ፣ በጐንደር ዐሥር ዓመት ለምኒልክ ሲያገለግሉ ኖረው ምኒልክ ካፄ ቴዎድሮስ አምልጠው ሲመጡ ባንድነት መጡ ። ከዚህ በኋላ የወሀኒ አዛዥ ተብለው የሣህለ ሥላሴንና የኃይለ መለኮትን ከተማ አንኮበርን ተሾመዋል ። ዳግማዊ ምኒልክ የታመኑና በቤተመንግሥቱም የታፈሩ ሆነው ሲኖሩ እዚያው አንኮበር ዐረፉ ።

## ነጋድራስ እግደው

ከጐንደር መጥተው ያፄ ምኒልክ ባለሟል ሆኑ ። በአዲስ አበባ ነጋድራስ እግደው እየተባሉ የከተማውን ፣ የገበያውን ሥርዓትና ንግዱን በመዠመሪያ ጊዜ ያስፋፉ ፤ መንግሥቱን በቀረጥ ያከበሩ እርሳቸው ናቸው ። የመንግሥት ጉምሩክ በአዲስ አበባ በርሳቸው ጊዜ በደንብ መቋቋሙን በቸርነትና በጌትነት የታወቁም እንደነበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ይጠቁማሉ ።

እርሳቸውም ከኢጣልያ ወረራ ከ1928ዓ.ም በፊት ባለው ጊዜ የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት የበጅሮንድ ዘለቀ አባት መሆናቸው ነው ።

## ቢቶደድ አጥናፌ

ግብጾች ከሐረርጌ ሲባረሩ እርሳቸውና ፊታውራሪ ገበየሁ የሻቃነት ማዕረግ ነበራቸው ። ገበየሁ የጦር አበጋዝ ከሆኑ በኋላ ፣ አጥናፌ ወደ ቢቶደድነት ማዕረግ ከፍ ብለዋል ።

ቢቶደድ አጥናፌ ፣ በጣም የታወቁና በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ እርሳቸው መደበኛ መሥሪያ ቤታቸውን ወረይሉ ከተማ አድርገው ከሸዋም ከያለበትም የሚመጣውን ስንቅ ተቀብለው እያደራጁ ለዘማች ወደ መቀሌ ፡ ወደ ዓድዋ በመላክ በጣም ተመስግነዋል ። በዚህም ከዓድዋ በኋላ ከምስጋና ጋር ከንጉሠ ነገሥቱ ኒሻን ተሸልመዋል ።

## ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዴ

ሀብተ ጊዮርጊስ ፡ የፈረስ ስማቸው አባ መቻል ነው ። በወሊሶና በአምቦ መካከል ባለው ጥቁር በሚባል ስፍራ ተወላጅ የሆኑት ሀብተ



ጊዮርጊስ ምኒልክ አካባቢውን ባቀኑበት ጊዜ አንድ ወታደር ማርኮ በኋላ በትእዛዝ ለመንግሥት አስረከባቸው ።

ባፄ ምኒልክ ፈቃድ አንኮበር ሔደው ባዛዥ ወልደ ጻድቅ ውስጥ ሆነው የመንግሥት ሥነ ሥርዓት እያጠኑ ቆዩ ። በኋላ ወደ ቤተመንግሥት መጥተው ባሽከርነት ሁሉንም እየተማሩ በማደግ የታወቁ ሆኑ ። ከዚያም ላፄ ምኒልክ ዕቁባት ለደጃዝማች አስፋወሰን እናት ለወ ይዘሮ ጌጤ እንደ እንደራሴ ሆነው የወሊሶንና የአመያ አውራጃን ያስተዳድሩ ነበር ። በመካከሉ የዓድዋ ጦርነት ስለ ተነሣ ሀብተ ጊዮርጊስ በዚያ አውራጃ ያለውን ጦር ይዘው ዘመቱ ።

በዓድዋ ጦርነት ላይ የጦር አበጋዝ የነበሩት ፊታውራሪ ገበየሁ በውጊያው ላይ በዠግንነት እንደሞቱ ወደ አዲስ አበባ መልስ ሆኖ የርሳቸውን የጦር አበጋዝ አዛዥነት ብዙ የጦር አለቆች በተለይ እነሊቀ መኳስ አባተ ሲመኙት ፣ ባፄ ምኒልክ ፈቃድ የራስ ወርቅ ጨምረው የጦር አበጋዝነቱን ሥልጣን ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሰጧቸው ። የተሾሙለት ባፄ ምኒልክ የጭን በቅሎ በቡሊት እንደ ተቀመጡና ንጉሠ ነገሥቱም እቤታቸው ድረስ ሔደው ግብር አብልተው እንዳ ከሩዋቸው ይነገራል ።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በታኅሣሥ 3 ቀን 1919 ዓ.ም. ሞተው በታላቅ ክብር በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀበሩ ።

## ራስ ናደው

ራስ ናደው ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ሙብረቅ ነው ። አባ ወሎ የሚሉዋቸውም አሉ ። ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ሊቀመኳስ ናደው እየተባሉ ዓድዋም ዘምተዋል ።

ከዚህ ወዲህ የራስነት ማዕረግ ይዘው ኢሉባቦርን ያስተዳድሩ ነበር ። በመልክት ወደ አውሮፓም ፣ ወደ አሜሪካም ፣ ወደ ኢየሩሳሌምም እየተላኩ የውጭ አገርን ሥልጣኔ ተመልክተዋል ።

## ራስ አባተ ቧ ያለው

ራስ አባተ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ይትረፍ ሲሆን በሸዋ የቤዛ ዘር ናቸው ። አባታቸው ደጃዝማች ቧያለው ይባላሉ ። ከልጅነታቸው ዠምሮ ባፄ ምኒልክ ቤተ መንግግሥት ያደጉ ናቸው ።

በዓድዋ ጦርነት በዠግንነት ተዋግተው አዲስ አበባ እንደተ መለሱ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተቀብለዋል ። ቀጥሎም ዋግሹም

ተብለው በዋግ ላይ የትግሬን የበላይነት ተሾሙ ። በኋላም ራስ ተብለው የንጉሥ ሚካኤልን ግዛት ወሎን ተሾመው እንደቆዩ ሞተው ደብረ ሊባኖስ በታላቅ ክብር ተቀበሩ ።

## ደጃዝማች ባልቻ

ባልቻ ፤ የፈረስ ስማቸው አባ ነፍሶ ነው ። በልጅነታቸው ከጦርነት ላይ ተማርከው ባፄ ምኒልክ ቤት ያደጉ ታማኝ የጦር መኰንን ነበሩ ። ብዙ ጊዜ በጅሮንድ ተብለው የንብረት ኃላፊ ሆነው ሠርተዋል ። አዲስ ዓለም ማርያም ስትሠራ ኃላፊው እርሳቸው ነበሩ ይባላል ።

የበለጠ እንደራስ አባተ የሚታወቁት በወታደራዊ መስክ ነው። በመቀሌውና በዓድዋው ጦርነት በዠግንነት ተዋግተው ስመጥርነት አግኝተዋል ።

ከዓድዋ መልስ በደጃዝማችነት ማዕረግ ሲዳሞን ሌላ ጊዜ ሐረርጌን ተሾመው አስተዳድረዋል ። በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን በክብርና በታላቅ ማዕረግ ሲኖሩ ፤ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር ስምምነት ስለ አልነበራቸው ፤ ብዙውን ጊዜያቸውን በግዞት አሳልፈዋል ።

በ1928 ዓ .ም የኢጣልያ ፋሺስት የዓድዋውን ብድር ለመመለስ በተዋጋበትና አዲስ አበባን በያዘበት ጊዜ በ80 ዓመት ዕድሜያቸው በአርበኝነት ዘመቱ ። "ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያልቻሉትን ጠላት እርስዎ ሊመልሱት አይችሉምና ለጣልያን ቢገቡ ይሻላል" ብለው ቢመክሩዋቸው ፤ "ሽምግያለሁ መሞት እንደሆን አይቀር ፤ በሰማይ ላይ ጌታዬ ምኒልክ በኢትዮጵያ ዙፋኔ ላይ ማነው የተቀመጠው ብለው ቢጠይቁኝ ምን ብዬ እመልሳለሁ" የሚል ቃል ወርውረው ሽማግሌው እንደ ወጣት በወጨጫ ከጠላት ጋር ተዋግተው ሞቱ ።

## ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ

ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ፤ የደጃዝማች ባርያ ጋብር ልጅ ናቸው። ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ በራስ አሉላ ውስጥ ሆነው ሠርተዋል ። መዠመሪያ የደጃዝማችነት ማዕረግ እንደያዙ ዓድዋን ቀጥሎ ፤ በንቡረ ዕድነት የራስ ወርቅ አስረው አክሱምን ጭምር ያስተዳድሩ ነበር ።

ዐፄ ምኒልክ ከሞቱ ወዲህ ፤ ደጃዝማች ገብረሥላሴ ከልጅ ኢያሱም ሆነ በርሳቸው ፈቃድ የወሎና የትግራይ ንጉሥ ከተባሉት አባታቸው ከራስ ሚካኤል ጋር ስምምነት ስለ አልነበራቸው ፤ ንጉሥ ሚካኤልን



ከደገፉት ከራስ ስብሐት እንደዚሁም ከራስ ሥዩም ጋር ጦርነት ገጥመው ራስ ስብሐት በጦርነት ሞቱ ።

ከዚህ በኋላ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከቤጌምድር ጦር ይዘው ወደ ዓድዋ ሲዘምቱ ገብረ ሥላሴ እሥመራ ሔደው ተቀመጡ ። የልጅ ኢያሱ መንግሥት ወድቆ ንግሥት ዘውዲቱ ሲነግሡ ከእሥመራ በመልእክት ተላልከው ይቅርታ ተደርጎላቸው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከንግሥት ባለሟሎች አንዱ ነበሩ ።

በኋላ ግን ፤ ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ጋር ብዙም ስምምነት ስላልነበራቸው በሜጫ ተግዘው እንዳሉ ለጠበል ሚጣቅ አማኑኤል ሔደው በዚያው ዐርፈው ሬሳቸው አክሱም ሔዶ ተቀበረ ።

## ሌሎች መኳንንት

ባፄ ምኒልክ ዘመን ፤ በወጣትነታቸው ጊዜ የእልፍኝ አሽከር በመሆን ወደ መጨረሻው እስከ ሚኒስትርነት ወይም እስከ ከፍተኛ የሹመት ደረጃ የደረሱት ብዙ ናቸው ። ታሪካቸውን በዝርዝር የማናውቀው ስለሆነና በጣም የበረከቱ ስለሆኑ ፤ ስማቸውን ብቻ ከነማዕርጋቸው ከዚህ ቀጥሎ እናመለከታለን ።

ቱርክ ባሻ ታምሬ ፤ ደጃዝማች አስፋው ዳርጌ ፤ ደጃዝማች ገሠሠ ብጡል ፤ ራስ ሉል ሰገድ ፤ ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል ፤ራስ ጌታቸው አባተ ፤ ቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደሚካኤል ፤ ቢቶደድ ወልደ ጻድቅ ጐሹ ፤ ቢቶደድ ወልደ ገብርኤል ፤ ራስ ሙሉ ጌታ ፤ ደጃዝማች መኰንን ተወንድ በላይ ፤ ሊጋባ ሠራዊቱ ፤ ቀኛዝማች በየነ ይመር ፤ ደጃዝማች ብሩ ኃይለ ማርያም ፤ ደጃዝማች ለማ አቦዬ ፤ ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ ፤ አዛዥ ደግፌ ፤ አዛዥ ወሰኔ ፤ አዛዥ ግዛው ፤ ደጃዝማች መታፈሪያ መልከጼዴቅ ፤ ፊታውራሪ ወልደ ገብርኤል ከተሬ ፤ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፤ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ ፤ አፈንጉሥ እስጢፋኖስ አፈንጉሥ ከተማ ፤ ደጃዝማች ገነሜ ፤ አዛዥ አባ ተምሳስ አዛዥ ስንቄ አዛዥ በዛበህ አዛዥ ኃይለ ሥላሴ ፊታውራሪ ገብረማርያም ቀኛዝማች ደቻሳ ሌሎችም የማናውቃቸው ወይም የዘነጋናቸው ሊኖሩ ይችላሉ ። ከዚህም በተ ጨማሪ ደጃዝማች ጫጫ ፤ ፊታውራሪ ገበየሁ ፤ ፊታውራሪ ዳምጠውና ቀኛዝማች ታፈሰ ዓባይነህ የተባሉት ስመጥር መኳንንት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ ታሪካቸው የተወሳ ስለሆነ ፤ ከዚህ እንደገና መዘርዘሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም ።

# ዋቢ መጻሕፍት

## ካገር ውስጥ


መንግሥቱ ለማ

መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፥ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተ ሚያ ቤት ፥ 1959 ዓ. ም.

መሠረት ስብሐት ለአብ

ትውፊታዊ ኃሳብ ዘመንና ታሪኩ ንግድ ማተሚያ ቤት 1981

ማኀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (ብላቴንጌታ)

ዝክረ ነገር ፥ 2ኛ እትም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1962 ዓ.ም.

መኰንን እንዳልካቸው (ቢቶወደድ)

መልካም ቤተሰቦች ፥ አሥመራ ፥ ኮሬዮሬ ኤሪትሪዮ ፥ ማህበር ማተሚያ ቤት ፥ 1949 ዓ.ም.

ተክለ ሥላሴ ዋቅጅራ (አለቃ)

ታሪካዊ የእጅ ጽሑፍ (ያልታተመ)

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ

የኢትዮጵያ ታሪክ ፥ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፥ አዲስ አበባ ፥ መርኃ ጥበብ ማተሚያ ቤት ፥ 1938 ዓ.ም.

———

የኢትዮጵያ ታሪክ ፥ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ (5ኛ እትም) አዲስ አበባ ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፥ 1965 ዓ. ም.

———

የግራኝ አህመድ ወረራ ፤ አዲስ አበባ ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፥ 1966 ዓ.ም.

ቶደስ ዘወልዴ (ቀኛዝማች)

ማይቱ ብሎል አዲስ አበባ ፥ ንግድ ማተሚያ ቤት 1979 ዓ.ም.

ታዬ ገብረ ማርያም (አለቃ)

የኢትዮጵያሕዝብ ታሪክ ፤ አዲስ አበባ ፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፥1964 ዓ.ም.

**ኃይለ ጊዮርጊስ ዘሐረር (ግራጌታ)**

ዜናሁ ለልዑል ራስ መኰንን ፤ አዲስ አበባ ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፣ 1965 ዓ.ም.

**ኃይለ ማርያም ሰራብዮን**

የኢትዮጵያ ትእምርተ መንግሥት ፣ ስንደቅ ዓላማና ዘውዱን የጃንሆይንም ዐዋጅ የሚናገር ፣ አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ፣ 1906 ዓ ም

**ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ)**

የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዓድዋ ጦርነት (ያልታተመ)

---

የሕይወት ታሪክ

መጽሐፈ ቅኔ በኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በ1981 ዓ.ም

**ዐጥሜ (ዐጽመ ጊዮርጊስ)**

የጋላ ታሪክ (ያልታተመ)

**አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (ነጋድራስ)**

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ፤ ሮማ ፣ 1901 ዓ ም

**ከበደ ተሰማ (ደጃዝማች)**

የታሪክ ማስታወሻ ፤ አዲስ አበባ ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፣ 1962 ዓ ም

**ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (ጸሐፊ ትእዛዝ)**

ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ አዲስ አበባ ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት ፣ 1959 ዓ ም



## ከውጭ አገር

Annaratore, C., **In Abyssinia.**
Bairu Tafla, **Ethiopia and Germany.**
Baratieri, O. Gen., **Memoire d' Afrique.**
Battaglia, R., **La Prima Guerra d'Africa.**
Bellavita, E., **Adua.**
Bureau, J., **Ethiopie: Un Drame Imperial Et Rouge.**
Cane Vari, E. & Comisso, E.H., **le Generale Tomaso Salsa.**
Crispi, F. & Palamenghi ,T., **La Prima Guerra d' Africa.**
Coulbeaux, J.B., **Histoire Politique et Religlenese d' Abyssinie, 2 tomes .**
De Coppet, M., **Chronique du Regne de Menelik il.**
Del Boca, A., **Gli Italiani in Afrca Orlentale.**
Giglio, C., **L'Italia In Africa: Ethiopla—Mar Rosso.**
Jones, A.H.M. e Monroe, **Histnire del' Abyssinie.**
Le Roux, H. **Menellk et Nous—**
Martini, F., **Diario Eritreo, Cose Africane.**
Mazzucconi, R., **La Giornata di Adua.**
Merab, P Dr., **Impressions d' Ethiople.**
Milano, C.T.I., **Guida dell' Africa Orientale.**
Pankhurst, R. The Ethiopian Royal Chronicle.
Pantano, G.Gen., **Ventitre Anni di Vita Africana.**
Pierre—Alype, **L'Ethiopie et les Convoitises Allemandes.**
————————'**L'Empire des Negus.**
Prouty, C., **Empress Taytu and Menelik II.**
Rossini, C.C., **Italia ed Ethiopla,DAL Trattato d'Uccialli alla Battaglia di Adua.**
Rossetti, C., **Storia Diplomatica Durante il Regno dl Menelik II.**
Sapelli, A., **Memorie d' Africa.**
Tedone, G., **Anghera.**
Vigneras, S., **Une Mission en Abyssinie .**
Ximenes, (ed.), **Sul Compo di Adua.**
Zaghi, C., **I Russi in Ethiopla,** 2Volume.
————————,**Crispi e Menelich nel Dlario Inedito del Conte A. Sallmbeni.**

## ያልታተሙ ሰነዶች
## UNPUBLISHED MATERIALS.

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ቤተመጽሐፍት ወመዘክር (ባሕል ሚኒስቴር)**

Public Records Office,
F.O. 40116 4249—F.0.403 (LONDON)

Archivio Storico del Sopresso Ministero dell'Africa Italiana.
Etiopia ,Posizione ,36—2—19—36 3—37—36 3—39... (ROMA)

Ministere des Affaires Etrangeres; **Memoires e Documentsl Afrique**
**II. 106—107. Mer Rouge, V—VI**
(1886—1887), 136—137, **Mer Rouge, VII—Ix** (1887—1895)
Collection de M.Mondon Vidaillet... VII,Manuscrips... B.M.
Mss Ethiopie 269 Mondon 82. (PARIS)